

@OLDBOOOKSPDF

ኬክዕ በምህረት

ምህረት ደበበ ገብረጻድቅ

ሰኔ 2007 ዓ.ም.

@OLDBOOOKSPDF

©መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

የመጀመሪያ ዕትም ሰኔ 2007
First Published June 2015
Addis Ababa, Ethiopia
ሁለተኛ እትም ሐምሌ 2007 ዓ.ም
Second Published July 2015
Addis Ababa, Ethiopia
ሶስተኛ እትም ነሐሴ 2007 ዓ.ም
Third Published August 2015
አራተኛ እትም ጥቅምት 2008 ዓ.ም
Fourth Published October 2015
አምስተኛ እትም ታህሳስ 2008 ዓ.ም
Fifth Published December 2015

ለአስተያየት

Email: mirumercy@gmail.com
Facebook: LelaSew ሌላሠው-በምህረት

@OLDBOOOKSPDF

ስሞታኑቱ …

ኣላረፈድኽ … ስተስመረኽ
መጣሁ እያለኽ … ብዙ ለቀየኽ

ይሁን …

@OLDBOOOKSPDF

መታሰቢያነቱ

ለዶክተር አብዱልረሺድ አብዱላሂ (በአ.ሲ.ዩ. የአእምሮ ሕክምና ተባባሪ ፕሮፌሰር) - ቀደምትና አንጋፋ የአእምሮ ሐኪም ስነበሩት፥ እኔና ብዙ የሀገራችንን ዶክተሮች ላስተማሩና ላሠለጠኑ ድንቱ መምህራችን መታሰቢያ ይሁን። ስተማሪዎችዎና ስሕመምተኞችዎ የሠጡትን ጊዜ የማይሽረው ልባዊ አገልግሎት በመዘከር ዘወትር እናስብዎታለን።

ለየኔታ ነበበ - የ'ህሁ' ገበታንና የአራቱን የሒሳብ መደቦች ተአምር ላስተማሩኝ የልጅነት አስተማሪዬ። የየኔታ ጭራና ምክር፥ አስንጋና ፍቅር በእኔና በብዙ የሞጆ ልጆች ልብ ውስጥ ህያው ሆኖ ይኖራል። ላታላቁ መምህር ከጥልቅ አክብሮት ጋር ውስታቸውን በመዘከር።

ለደን አያቴ ሰረፍየስሽ ባዩ - ያለ ገደብ ስለሰጠሽኝና በሕይወትሽም ስላስተማርሽኝ ፍቅርና ደግነት። አምዬ፥ ዛሬም ከብዙ አመታት በኋላ ትገዘታሽ በልቤ ህያው ሆኖ ይኖራል።

@OLDBOOOKSPDF

ምስጋና

ከሁሉ በፊትና በላይ ፈቃዱ ሆኖ ይህንን ሥራ ለመሥራት ጤናና ጉልበትን ለሰጠኝ፣ የፈጠራ ሰራ ሁሉ ጀማሪና ባለቤት፣ የሁላችን ፈጣሪ አምላክ ሀያው እግዚአብሔር ውዳሴና ምስጋና በሰማይ በምድር ይሁን ።

እኔ ከሥራዬ በፊትና በላይ ስሙ እንደመሆኔ መጠን በእውነተኛ ወዳጅነት የደገፉኝንና ያበረታቱኝን ወዳጆቼንና ቤተሰቦቼን ከልብ አመሰግናለሁ ። በርግጥ የሁሉንም ስም መጥራት አልችልም ። የተመሰኑትን በስም እየጠራሁ ማመስገኑ ግን ተገቢ ነው ። ዶክተር ለዓለም ጥላሁን (ላሊ) እና ባለቤቱ ሰላማዊት አሰራት (ሻፒ) ከነልጆቻቸው በእመታት መካከል ያልተቀየረና ያው የሆነ ጓደኝነታቸው ለምሠራው ሥራ ብቻ ሳይሆን ለማንኒውም ሞነኛ ድጋፍ ሆኖኛልና የተለየ ምስጋናዬ ይድረሳቸው ። ለወላጆቼና ለወንድም እህቶቼ በምሠራው ሥራ ስለምታምኑና በሁሉ ስለምትደግፉኝ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ ።

በሲይንት ሊውስ ውስጥ ያላቸው ሌሎች ብዙ ወዳጆቼንም ከዚህ ጋር እጅግ ላመሰግን እወዳለሁ ። አማንና ኤዱ፣ ዘሪሁንና ሚርሲ፣ ሄኖክና እጸደ፣ ሚሪ የጋሽ ፍስሀጽዮን ልጅ፣ ኑሬና መስኪ፣ መጋቢ ተስፋዬና ቭዬ መልካም እንዲሁም የሁል ጊዜ አበረታቼ ብርሃኔ፣ ታላቅ ምስጋናዬን ውሰዱና የራሳችሁን ካስቀራችሁ በኋላ የቀረውን ለሌሎቹ እድርሱልኝ ። አምላኩ (ሴቾ) እና ኤዱ፣ ዝኒኩና ፊሽ እንዲሁም መዓዚና ሲስ ደግሞ በረጅም አመታት ተፈትኖ ነጥሮ ለወጣ ጓደኝነታችሁና መልካምነታችሁ ምስጋና አቀርባለሁ ።

በዚህ 'ሌላሠው' በተሰኘ ሥራ ላይ ቁትራቸው የበዛ ወዳጆቼና ባለሙያዎች ያደረጉልኝ እገዛና አስተዋጽኦ ታላቅ ከሚገልጹት በላይ ነው ። ጋሽ ዘሪሁን አስፋው በመጽሐፉ እርማትና አርትኦት ላይ በከፍተኛ መስዋዕትነትና መሰጠት ስለሠሩት ሥራ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ ። በመጽሐፉ እርማትና አርትኦት ላይ ሌላው ትልቁን ሥራ የሠራው ጋሽ ንጉሴ ቡልቻ በጽሁፉ ላይ ያጠፋኸውን ጊዜና ጉልበት ብቻ ሳይሆን ለሥራው ያሳየኸውን ትልቅ መሰጠት ከልባዊ ምስጋና ጋር አውቅና ለመስጠት እፈልጋለሁ ። ወዳጄ ቴዲ ታደሰ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ለሰጠኸኝ ጠንካራ አስተያየቶችና ጠቃሚ ሃሳቦች ታላቅ ምስጋናዬ ይድረስህ ።

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጽሁፍ ላይ አስተያየትንና እርማትን በመስጠት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰዎችን ስም ሁሉ መዘርዘር ባልችልም የተመሰኑትን ግን በስም ጠርቶ

@OLDBOOOKSPDF

ማመስገኑ ተገቢ ይመስለኛል። ዶክተር መስፍን አርአያ፣ የሲቢንወርት መልደኒዮርጊስ፣ ዶክተር ግሩም ለማ፣ ሃና ሁሴን፣ ብሌን ሳህሉ፣ ዘራቱ ከበደ፣ ናሁሰናይ አፈወርቅ፣ ናርዲና መንዴ፣ ያሬድና ጎብረት፣ ታልኪዳን ፣ መንግላዊት ለገሰ፣ ዘላለምና ሜሪ፣ የጋሽ ንጉሌምቄ ማዜና ኤፌ፣ መገበረና ሳባ፣ የፅሁራን ግርድፍ ከማንበብ ጀምሮ ጊዚያችሁን ብቻ ሳይሆን ልባችሁንና እውቀታችሁንም ስላካፈላችሁኝ በአንባብያን ስም እመሰግናለሁ። ከመጀመሪያው መጽሐፍ በኋላ በኢሜይልም ሆነ በአካል ያበረታቱኝን አንባብያን ሁሉ አመሰግናለሁ።

በእኔና በምሰራው ሥራ ላይ ባለው ጠንካራ መተማመን ሁልጊዜም የሚያስገርመኝን ዶክተር ቤተ መንግስቱን ከልብ ላመሰግነው እወዳለሁ። በዚህ መጽሐፉ በህትመት ላይ ባለበት ወር ላይ ጋሽ ቤተ የስባኛ አመት ልደቱን ያከብራል። 'መልካም ልደት ... የተባረኩ ብዙ አመታትን እመኝልሃለሁ' ብል የሚዘገይ አይመስለኝም። አንተ ብዬ መጥራቴ የርሱ የስብእና ወጣትነትና በመካከላችን ያለው መቀራረብ የፈጠረው ነው።

የመጽሐፉን ግሩም የገጽ ሽፋን የሰራችው ብሌን ዮሐንስ ደግሞ የተለየ ምስጋና ይገባታል። ያላት የሙያ ብቃትና የባሀርይ መልካምነት ብቻ ሳይሆን በመጽሐፉ ውስጥ የተቀመጠውን ሐሳብ የገለጠችበት ምስላዊ መንገድ ከፍ ያለ አድናቆትን እንዳቀርብላት ያደርገኛል። ከቪ ጋር ያገናኘንና በዚህ ሥራ ላይ ትልቅ ማበረታቻ ሲሰጠኝ የቀየው አማን መንግስቱንም ከልብ አመሰግናለሁ። ይህ መጽሐፍ ለንባብ እንዲመችና አይን የማይገረብየ እድርገ የገጹን ቅንብርና ውስጠ መልኩን ለሠራልኝ ለካሌብ ያለኝን ልባዊ ምስጋና እገልጻለሁ። ካሌብ ጥሩ አስተማሪና አብሮ ለመሥራት ደስ የሚል በሙያው የተካነ ወጣት የጥበብ ሰው ነው።

የመጽሐፍ የመጨረሻ ውበትና የተንባቢነት ልኩ ከሕትመቱ ጥራት ሊበልየ አይችልም። የተቀለፈበት ቁልፍንም ሆነ ይዛንን መጽሐፍ በጥራትና ልብን በሚያረካ መንገድ እትመው ያቀረቡልን የርሆቦት ማተሚያ ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ጋሽ በፍቃዱንና የማተሚያ ቤቱን ሠራተኞች በሙሉ በአንባብያን ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።

@OLDBOOOKSPDF

ክፍል ፪

የመዳረሻው መንሻ

@OLDBOOOKSPDF

"ስማ ሴላ፣ በማዬ ምት እኔ ያንተን የማያልቅ የፍስናና ዲስኩር መሰማት ሰልችቶኛል። ደግሞ ... እድሜ ልክህን ስትሰታደ እንደናርዘ አላውትም ነበር" አለች፣ ብስጭት፣ ምጸትና ትዕግስት ማጣት በተሸከመ ድምጽ። የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ሆኖ ወደ አሜሪካ ሲሄድ ተቀብላ ያስተናገደቸውና ያስተማረችው አሰ፡ ናት። በመካከላቸው የአስራ አምስት ዓመት ልዩነት በመኖሩ እንደ ሁለተኛ እናቱ ነው የሚያያት።

"እሺ ቀይ ምን አድርግ ነው የምትፈኝ? እዚህ የጀመርኩትን ነገር ሁሉ በትኜ፣ ብድግ ብዬ እንድመጣ ነው የምትፈልጊው? ብመጣስ ለምኑ ነው? ከዚህ በኋላ ሁሉም ነገር ተበላሽቷል። ስለዚህ ወደ እዚህ ያመጣኝን ጉዳይ ከሜሩፍ ሳላደርስ መመለስ አልችልም አለ፣ ቁርጥ ባለ ድምጽ። ሊገባቡ እንደማይችሉ ቢገባውም ተስፋ ሳይቀርጥ የንግግሩን አቅጣጫ ቀይሮ ሁኔታውን ሊያሰረሳት ያደረገው ሙከራ ሊሳካለት አልቻለም።

"ስማ ሴላ ... ሚስትህንና ልጆችህን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጣት ካልፈለግህ ይሄ ብቸኛ ዕድልህ ነው። ቀይ አንተ ግን ... ምንድነው የነካህ ነገር? ቢያንስ ልጆቹ አያሳዝኑህም? እሷስ ብትሆን በዚህ አገር ኑሮ ሁለት ልጆች ይዛ ላይ ታች ስትሯሯጥ ምንድነው ልብህን እንዲህ ያደነደነው?" አለች።

የልጆቹና የሚስቱ ነገር ሲነሣ ስውነቱ ሲግል ተሰማው። ውስጡ ማልቀስ ቢፈልግም ስሜቱን እገደምንም ተቆጣጠረው። ሰው በሌለበት ሣቂ መሃል ወይም በተራራ ላይ ቆሞ እሪ ብሎ መጮህ አማረው። ሳያስበው የውጪው በር ጋ ሲደርስ፣ ጥበታው ስላልነበሩ በሩን ከፍቶ አገሩ ወጸመራው አቅጣጫ ወጥቶ ሄደ። እህቱ ስታወራ ያሮው ቢለማትም በጭንቅላቱ ውስጥ ባለው የሀሳብ ሣጣታ ተውጦ በተሞኗ የጠጠር መንገድ ቁልቁል ወረደ። ስልኩ ድንገት ሲጮረጥ እየት እደረገውና ከእጁ ላይ አሽቀንጥሮ ሊወረውረው ፈለገ። እጆቹን እሱረው ኪስ ውስጥ ከትቶ በጸጥታ ቁልቁለቱን መራመዱን ቀጠለ።

ከዋናው አስፋልት ከመግባቱ በፊት ካለች እንዲት ሱቅ ገብቶ ፓኮ ሮዝማን ሲጋራ ገዛ። ከአስራ አምስት አመት በኋላ ሲጋራ በእጁ ሲነካ የመጀመሪያ ጊዜው ነው። ወዲያው ወደ ዋናው መንገድ እንደታጠፈ እንዲት ትንሽ ካፈ በረንዳ ላይ ተቀመጠ። ከፓኮው ያወጣትን ሲጋራ እያፍተለተለ አመነታ። ሲጋራዋን እያነደደ በሚወጣው የሚትነለነል ጭስ ውስጥ ታፍኖ ... የውስጥ ስታዩን ሊደብቅ ፈለገ። ቡና እንደመረደ አዘዘና ደጋግሞ በረጅሙ ተንፈሰ። መራራውን ጥቁር ቡና በትኩሱ ፉት ፉት ብሎ ጨለጠው። ከብዙ ትግል በኋላ ያወጣትን ሲጋራ እያመነታ ወደ መጣጥበት መለሳት። ሙሉ ፓኮው ጨመጻጮ ከባዶው ስኒ ውስጥ ጨምሮ ጠቀጠቀው። ሒሳቡን ከስኒው ማስቀመጫ ስር አስቀመጠና ወደ ዋናው መንገድ ገብቶ እግሩን ተከትሎ ተጓዘ።

ዐሐያማ ሆኖ የዋለው የአዲስ አባባ ሰማይ ከወደ ሰሜን ምሥራቅ በመጣው ጥቁር ደመና ሲሸፈን ከተማይቱ ፈዙቶ የዋለ ፊቷን ባንዴ አጨፈገገችው። ሰማዩን ያጨለመው ዶፍ ያረገዘው ደመና የተሸከመውን ውኃ ከተማይቱ ላይ ስመዝገፍ አዮብቁበ፣ ልጣን በሚሰነዋቀው መብረቀ ነኮድንዱ እያምበረቀ በማን አለብኝነት

@OLDBOOOKSPDF

1

"ግራጫ ... ነጭ የሚጠቁርበትና ጥቁርም የሚነጣበት ሰፊ ግዛት ነው። የሕይወት መልክ አስር እጁ ጥቁርና ነጭ ... የቀረው ደግሞ ግራጫ ነው ሊባል ይችላል። ግራጫ ... የብርሃን ኩርፊያ ወይም የጨለማ ፈገግታ ሆኖ ይታያል ... ወደ አንደኛው የወገ ... ግን ደግሞ ሁለቱንም አጣምሮ የያዘ ቀለምም ይመስላል። በርግጥ ግራጫ ቀለም አይደለም ... የራሱም መልክ የለውም ... ብሎ መከራከርም ይቻላል። በሌላ በኩል ሁሉም ቀለማት በየመልካቸው የየራሳቸው ሰፊ የግራጫ ድርሻ አላቸው። ሰው የመሆን ሌላነትና ያውነትም ... በራሱ ሰፊ ግራጫነት ውስጥ ተሰውሮ ተገልጧል። እያንዳንዱ ሰው ሌላ ሰው ... ሌላውም ሰው ያው እንደ እኛው ሰው መሆኑን መረዳት እንዱ ግራጫ የሕይወት አተያይ ነው።"

ዶክተር ሌላሠው ከገባበት የግራጫ ሃሳብ ውስጥ የእሀቱ ስልክ መንጭቀ አወጣው። እያወራ ማሰብና እያሰበ ማውራት፤ ከሥራው የተማረው የዘወትር ልማዱ ሆኗል። ነጭና ጥቁር እይታዋ እየጋረዳት የርሱን ግራጫ ዓለም መረዳት እንደ ተሳናት ከሚያስባት እሀቱ ጋር መነጋገርና መግባባት እየተሳነው መጥቷል።

"እቴቴ ... ምንም ብልሽ የኔ ሃሳብ ሊገባሽም ሆነ ሊስማማሽ አይችልም" አለ፤ እጁን እያወናጨፈ ከበረንዳው ወርዶ፤ ከሊኒኩ ግቢ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያለ። የስልኩ ጮገድ ከቢሮው ውስጥ እየተቆራረጠ ስላስቸገረው ነው ወደ ውጪ የወጣው።

ከታላት እሀቱ ጋር ቀዝቀዝ ብለው የጀመሩት የስልክ ወሬ ወደ ጋለ ንትርክ ተቀየረ። "የማይገባኝ ከሆነ ታዲያ ለምን አታስረዳኝም?" ብላ፤ በደረቱ ስትስቅ የበለጠ ተበሳጨ። ሁልጊዜም እንደ ልጅ የምታየው ይመስለዋል።

"እሺ ... አንድ ጊዜ በደንብ ስሚኝ። ለእኔ፤ ስኬትና ምኞት ስትኖሪ የምታገኚያቸው የሥራ ፍሬዎች ናቸው እንጂ የምትኖሪላቸው የሕይወት ጥሪና አላማዎች አይደሉም። የመኖር ትርጉምን ሊሰጥ የሚችል ኃይል በውስጣቸው የለም። እኔ ወደ ሀገር ቤት የተመለስኩት የሕይወቴን ጥሪ ለመፈጸምና አድሜ ልኬን ሲያሰቃዩኝ ለኖሩ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ነው። ይህንን ደግሞ ለንጹህም ላስረዳት ..." ብሎ ሳይጨርስ አቋረጠችው።

@OLDBOOOKSPDF

መጣሁ መጣሁ ይላል። ሳር ቅጠሱን እያነሳና እየጣለ የሚያቃጨው ነፋስ ደግሞ የደመናውን ከምር ከሰማዩ ገጽ ላይ ሊያባርር ይመሰል በምታ ነጋሪት ዓይነት ጥድፊያ ከወጺያ መጺህ ይራወጣል። የኃያላኑ አሰጥ አገባ ያስጨነቃቸው ሕያዋን ፍጥረት ከመጠለያቸው ገብተው ሊሸሸጉ በያቅጣጫው ይጣደፋሉ። የውሾች ጩኸትና የሰዎች ሩጫ ... የታዘሲዎች ውክቢያና የዛፎች ኧሻታ ... የፈጠረው ድብልቅልት ትርምስ ብረሩ ብረሩ የሚያሰኝ ልብ የሚያባባ ስሜትን ያጭራል።

የአየሩ ቅዝቃዜና የሰማዩ ጥቁረት ሲጨምር መገነቡ ቁርዮ እየሆነ መጣ። ሁኔታው ያሳሳረው ሊላሠውም ፍጥነቱን ጨምሮ ወደ ክሊኒኩ አቅጣጫ ተመለሰ። ወደ ተጭኗ መንገድ ሲደርስ መንጠባጠብ የጀመረው ዝናብ ባንድ ጊዜ መአት ያፍን በረገፈው። እግሬ አውጪኝ ሮጦ የውጪው ደጅ ጋ ሲደርስ በሩ ከውስጥ ተቆልፎ ስለ ነበር መግባት አልቻለም። ባለ በሊስ አትሙ እያንኳኳ ከበሩ ስር ለመጠለል ጮከረ። ጥበቃው ሰምቶው እስኪከፍትለት ድረስ ሁለንተናው በውሃ ተጠመቀ። እስክ ቤቱ ሊሸኙት ዣንጥላቸውን ቢያጠልሉትም "የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም" ዓይነት ትቷቸው ሮጠ።

በረንዳው ላይ ደርሶ ከላይ እስከ ታች በልብሱ የተሸከመውን ውኃ ሲጨምቀው "ትንሽ ጎርፍ" ፈጠረ። ሰው ሁሉ በየቢሮው ተወሽቆ ስለነበር ማንም አላየውም። በነን ባለው በር ወደ ራሱ ቢሮ እንደገባ በፍጥነት ልብሱን ቀየረ። ጠጥት ለሰፖርት መበሪያ ከያዘው ቦርሳ ውስጥ ያለውን ልብስ ሲለውጥ እጥንቱ ውስጥ የገባው ብርድ ትንሽ ጋብ አለለት። ስእቱን ሲያይ ሰአሰራ አንድ ሰአት ሩብ ጉዳይ ይላል። ከውሃ ማጣሪያው ውስጥ የፈላ ውሃ ቀድቶ ሻይ ቅጠል ጨመረና ራሱን ለማሞቅ ሞከረ።

ተጠቅሞበት የማያውተውን ከወደ ጥግ ያለውን የእሳት ማንደጃ ቀረብ ብሎ አየው። ውሰጡ የተረበረበው ፍልጥ እንጨት የአንዳጅ ያለህ ይመስል ደረቱን ገልብሞ ተጋድሟል። ወደ ካርድ ክፍል ደውሎ የጽዳት ሠራተኛዋን እንዲልኩለት ነገራቸው። በሩን አንኳኩታ አንገቷን ብት ሰታደርግ ሰላም ካሳት በኋላ፣ "ደጅ ወጥቼ ዝናቡ መርዶብኝ፣ በብርድ መሞቴ ነው ባክሽ። እዚህ ምድጃ ውስጥ ያለውን እንጨት እሳት ብታያይዝልኝ ብዬ ነው፣ ክብሬትና ጋዝ ነገር ካለ በቂ ነው" አሳት።

"ውይ በሞትኩት ... ብርዱ እኮ እንዲህም አጥንት ይሰብራል። መጣሁ አስኪ" ብላ፣ በሩን መልሳ ዘጋችው። ብዙም ሳትቆይ እሳቱን አያያዛለት ስትወጣ ሶፋውን ሳብ አድርጎ ወደ እሳቱ ተጠግቶ ተቀመጠ። የበለጠ እንዲነድ እየቀሰቀሰ ብርዱ ያቀረፈጵቸውን እጅና እግሩን ጠጋ አድርጎ ለማሞቅ ሞከረ።

ከተቀመጠበት ተነሥቶ ትንሽ ወጺያ ወጺህ ሲል ቀየ። ወደ ሳሮ ከሚያሳየው ሰፊ መስኮት እንጻር ሄዶ እጁን ጨበጥ ላላ እያደረገ ጥቂት ቆመ። እውን ዝናቡ ሙሉ ሰሙሉ ተሚል። በየሀቃ ቅጠል ላይ የተኩማቹው ውሃ ወደ መሬት ይንጠባጠባል። ለመጥለት ጥቂት የተራት ጅምበር የመጨረሻውን መሞት አልብ ቀይ ብርቱካንማ ቀለሚን ፈንጥቃ በወረደው ዶፍ ለተወገሩ ፍጡራን ሃዘኔታዋን የምትገልጽ ትመስላለች። ሁሉም ነገር ፈጭና ሄዋ ብሏል፣ ከሊላሠው ውስጠ ነፍስ በቀር። ወደ ሥራ ጠረጴዛው ሀረና

@OLDBOOOKSPDF

ተጀምረው የተከፈቱ ጥቂት መጻሕፍቱን እየዘጋ ጥሰላቸው ።

ከሁለት ዓመት በፊት ከሚሰቱና ከሁለቱ መንትያ ልጆቹ ጋር የተነሡትን ርቶ ከጠረጴዛው ላይ እንሰቶ በጥንታቱ ማጤን ጀመረ ። ወንበሩን አሽከርክሮ ወደ መስኮቱ አስጠግቶ ተቀመጠ ። ደጅ ደጁን እያየ ፈዘዘ ። አሁን ዐሐይዋ ሙሉ ለሙሉ ጠልታለች ። ድንግዝግዝ ያለ የአመሻሽ ብርሃን ባካባቢው ላይ ተንሰራፍቷል ። ዓይኖቹ በእንባ ግጥም ሲሉ የሚተናነቀውን ሳግ ለመቀባጠር ምራቁን ዋጥ አደረገ ። ፎቶውን ቀስ ብሎ ወደ ነበረበት መለሰው ። ጠረጴዛው ላይ ባፍጢሙ የተደፋ ሲላ ፎቶ እነሳና ለትጽበት አይኖ አስተካክሎ አስቀመጠው ። በልጅነቱ ከእባቱ ጋር ሲላፉ የተነሡት ነው ።

እባቱ ጥንቱት ፣ ጽዱና ትጉህ ሠራተኛ እንደነበሩ ትዝ ይለዋል ። ሰው ሁሉ እንዴት ይፈራቸው እንደ ነበር አውንም ዓይኑ ላይ አለ ። በፖሊስ ኮሚሽንና በማዕከላዊ ምርመራ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሠርተዋል ። አብሮቱ ሲፈነዳ የመኖ አለታ ነበሩ ። በአጭር ጊዜ ወደ ከፍተኛ ማዕረግ ከተሸጋገሩ ጥቂት መኮንኖች አንዱ ናቸው ። በደጅ እንደ አንበሳ አስፈሪ ፣ እንደ መብረት አስደንጋጭ ቢሆኑም ፣ እቤት ውስጥ ግን ተጨዋች ፣ ደስተኛና ቤተሰባቸውን አፍቃሪ ነበሩ ። የሁለትነታቸው ነገር ዛሬም ለርሱ ምስጢር ነው ።

በደርግ ምትክ ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝ ነገሮች በፍጥነት ተለዋወጡ ። መታሰራቸውን ሲሰማ ድንጋጤው ለረጅም ጊዜ አለቀቀውም ነበር ። ከአሥራ ሦስት ዓመታት እስራት በኋላ ነበር በጤና መታወክ ምክንያት የተፈቱት ። ከእስር ቤት ወጥተው ብዙም ሳይቆዩ ከጥቂት ወራት ሕመም በኋላ አረፉ ። ከመሞታቸው በፊት ለተወሰኑ ሳምንታት ቢሆንም ጥሩ ጊዜ አብሯቸው አሳልፏል ። ሰምቶ የማያውቀውን በደም የተቀባ ታሪካቸውን ያጫወቱት ያኔ ነበር ። አስር ቤት እያሉ የጸፉለትን ረጅም የማስታወሻ ደብዳቤ የሰጡት ያኔ ነበር ። አሳዛኝና ዘግናኝ የኑዛዜ ትረካቸውን ባነበበ ቁጥር የሲላ ሰው ታሪክ እንጂ የደግ ተጫዋች አባቱን ታሪክ የሚያነብ አይመስለውም ።

በሕመምና በእርጅና የወጸደቀ ሰውነታቸውና በሐዘንና በጸጸት የተሰበረ መንፈሳቸው ከፊቱ አይጠፋም ። በነዚያ የመጨረሻ ቀናት ውሃ ቀድቶ ለመጠጣትና የገዛ ሰውነታቸውን ያግፈው ለመቀመጥ እንኳን አቅም አጥተው ነበር ። በስለለ ድምፃቸው ሲያወሩ ፣ የዛሉ እጆቻቸውን ለማንቀሳቀስ ሲሞክሩ ያሳዩት የነበረው ሥቃይ ዓይኑ ላይ ድቅን አለበት ። በደከሙ እጆቻቸው ጠንካራ እጅቹን ይዘው ከጎደንዱ ዓይኖቻቸው ውስጥ የመጨረሻ እንባቸው በተሸበሸበ የፊት ቀዳቸው ላይ ዘብልል እያለ የነገሩት የመጨረሻ ታሪ እያረሳውም ። በእንባ የተሞሉ የራሱን ዓይኖች ጠረግ ጠረግ አድርግ ጠቃሚ ፋይሎችን ቀልፎ ከሚያስቀምጥበት መሳቢያ ውስጥ የርሳቸውን ማስታወሻ አውጥቶ እሳቱ አጠገብ ሄዶ ተቀመጠ ።

ድንገት የሆነ ሃሳብ በአእምሮው ውስጥ ሽው ሲል ደነገጠ ። ሃሳቡን እህቱ ናት ከሳምንት በፊት በልቡ ውስጥ የዘራችበት ። "በአባታችን ጸጸትና በትዝዝል ያልተሞረ ህይወት አዙሪት ውስጥ ራስህን አትዝፈት ። የሁሉም ሰው የአደራ ሃላፊነት የራሱን ህይወት መኖር እንጂ በወላጆቹ ቀጻ ውስጥ ገብቶ የነርሱን ውድቀትና ጸጸት ማከም

@OLDBOOOKSPDF

እይዶለም' የሚለው ቃሏ ትዝ አለው። ለመጀመሪያ ጊዜ በአባቱ የአደራ ቃል የታሰረ መስሎ ተሰማው። ስጌትን አልወደደውም። ይብዛቤውን ማንበብ ሲጀምር በሚቀጥለው ገጽ ታየው።

አባቱ ያደረጓቸውን ስህተቶችና ብዙ ጸጸቶች የሚገልጹትን የመጀመሪያ ገጽ አንድ ባንድ ያነብና ሞምድድ አድርጎ ይይዛቸዋል። ከዚያም እሹ ውስጥ እንደ ካስ የተደበቁለየለትን ወረቀት ከሚነደው እሳት ውስጥ ሲወረውረው ቦግ ብሎ ይነዳል። ወረቀቱ ወደ አመድ ሲቀየር እንደገና የሚተዋሰውን ከፍል ማንበብ ይጀምራል። ወደ መጨረሻው ገጽ አካባቢ ሲደርስ የያዘውን ገጽ ሮክ ብሎ ለራሱ ማንበብ ጀመረ።

''ልጄ ሲሳ፣ እኔ አባቱን አይደለሁም፣ ብፈልግም መሆን አልችልም። አንተም እኔን አባትህን ሳትሆን ሲሳ ሰው ነህ። አባቱ ሞቶናን ሰማ ፈንታው አድርገ የተቀበለ ገስጽላ ሞሰኛ ገበራ ነበር። ትሮውን ካምላክ የተሰጠ ያርባ ቀን ዕድሉ ብሉና ተቀብሎ ኖረ። መወለዱም ሳይታወቅ በልጅነቱ አርጅቶ በድንነት እንደማቀቀ ሞተና በተወለደበት ሰፈር ተቀብሮ ተረሳ። እኔ ደግሞ የሱን ፈለግ አልተከተልኩም። ገና በልጅነቴ ዕጣ ፈንታዬን በእጄ አደረግኋት። 'የሕይወቴን ድርሻ ከማንም አልለምንም፣ ሊከለክለኝ የሚችልም አንዳች ሰው የለም' የሚል ጠንካራ እምነት ነበረኝ። 'የማንም አሽከር አይደለሁም፣ ለማንም ጌታ መሆን አልፈልግም' ብዬ ለራሴ ማልኩ።

'በወትሮ አገር የተንቀጠቀጠችላቸውን የዳሽዝማች መከቴን ብቸኛ ልጅ የነበረችውን ያንተን እናት ያገባኋት ያለማንም እርዳታ፣ ያለምንም ልመናና እቤቱታ ነበር። ፈተናው ቀላል አልነበረም፣ ያጋጠሙኝ መሰናክሎች ሁሉ ወደላይ ያወጡኝ መሰላሎቹና ችው። መሰላል ያላደረከው ችግር ብቻ ነው። መጥበራያ ገደል የሚሆንብህ። መፈተርና መከበር ለምች የሚሰጠህ ሳይሆን ላተረብከላቸው ማንነትህ የምታገኘው ምላሽ ነው። የፈለግሁትን አገኘሁ፣ ያሰብኩትን ሆንኩኝ።

'በዚሁ ትኩስ የወጣትነትና የስኬት ዕድሜዬ ላይ እኔና አብሮቱ አከል ፈንዳን ብል ማጋነን አይሆንም። አብሮቱ የቸገረውን ሁሉ ነጻ የሚያወጣ የድነት ማዘተሚያና የጭቆና ማብቂያ ብቸኛ ጉዳና ለመሆኑ ጥርጣሬ አልነበረኝም። የኛ ትውልድ የለሻሊዝምን ትርጉም ለማወቅና የኮሚኒዝምን ፋይዳ ለመረዳትም ሆነ ለመጠየቅ ደንታውም ጊዜውም አልነበረውም። አሮጌውን ማፍረሱ ላይ ስንረባረብ አዲሱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ጥያቄና ሐሳብ አላስጨነቀንም ነበር። የተፈጠረው እንደ ኤሊዘትሪክ የሚነዝር የለውጥ ማዕበል ከንጭሉ ውብቱና ግለቱ ለእኛ አዲስ የሃይማኖት ጎራ፣ የንጹህ ሥራ፣ የብልጽግና ጮኅናና የሞቱት ሕዝባችን ብቸኛ ብራሃ ተስፋ ሆኖ ታየን።

'መጪያው ከሙጪ መረራና ከሙስጥ ተታለውም ሲተለተለብንና ከሻራ ከቀኝ ሲያጣድፈን፣ የማያባራ 'መታደራዊና ኢብዮታዊ' ሩጫ በውስጡ

@OLDBOOOKSPDF

ተተሰተሰ። እየሀ ቱጣ ደግሞ ጨካኝና አብድ ያደርገሃል። የአብዮቱን ጠላቶች የደመሰሰን መሰሉን የአገራቷን ምርጥ ልጆች ጨረስናቸው። ነጭ ሽብር አወጀብን ያልነውን ጸረ ሕዝብ ኃይል በተደ ሽብር አጋይተን ያሸነፍን መሰለን። ነገር ግን በድርብ የሽብር እሳት አንድ ትውልድ ፈጅተን ባዶ ቀር ታትፈን ቀረን። አብዮት ለሚባል ሐሳብ ከቡር ሰሙ እንደ ቅጠል ረገፈ። አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት በሚል መፈክር፣ ራሷን እናት አገርን በዐመፅ ገመድ አንቀን ገደልናት። የልጆቿን ፈሳ በያደባበዩ ጥለን የድል ሥክ እየረገጥን ተሰድገባት።

የያዛትን ገጽ መጨምደድም እሳት ውስጥ ለመጣልም አትም አጣ። ማንበቡን አድርሞ የቀሩትን ጥቂት ገጾች ከነኩ ሶፋው ላይ አስቀመጠና ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደ። ፊቱን ለሰስ ባለ ውሃ ታጥቦ ከመለተዋቱ ውስጥ ባለው የራሱ ምስል ላይ አፈጠጠበት። ጸጉሩና ጢሙ ማደግ ጀምሮ ሌላ ሰው ሳያስመስለው አልቀረም። በግሡ ፈገግ እያለ አገጩን አሻሸ። የለበሰውን የስፖርት ቱታ ጃኬት ሙሉ ለሙሉ ዘጋው። መስኮቱ አጠገብ እንደገና ቀሞ ይሄንን ያብጸቤ ማታጠሴ ልዘ ነው አይደለም እያለ ወደ ቢሮው ተመለሰ። ወደ ግር ከሚያሳየው ትልት መስኮት አንጻር ቀሞ ደጅ ደጁን እያየ እየጨሳለመ ያለው ደጅ ላይ መልሶ አፈጠጠበት።

በዚህ መሃል አንድ ነገር ከራቱ ካለው የመስኮቱ መስታወት ጋር ሲላተም ከሐሳቡ ነታ። በዚያው ቅጽበት ከመስኮቱ ላይ ተንሸራታ ወደ ታች ስትወድት ወፍ መሆኗን ገመተ። በመስታወቱ በኩል ወደ ታች ሲያያት ቢሞክርም አልቻለም። የደጁ ብርሃን በመደብዘዙ ወይም በውሃ ልኩ አንጻር ካሉት አበበች መሃል ወድታ ተሸጉጣ ሊሆን ይችላል ብሎ አሰበ። መስኮቱን ሲከፍተው ከደጅ ያለው ተገታላ የነፋስ ሽውታ ፊቱን ሲገርፈው፣ የወርቹና የነፍሳቱ ሚጣታ ደምቶ ከጆሮው ሲዘልት ከገባበት ሐሳብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ነታ። ሳያይ እንዳይረግጣት እየተጠነቀቀ በመስኮቱ ዘልሎ ወጣ። ላርና አበቦቹን እየገላለጠ ቢፈልጋትም ሊያገኛት አልቻለም።

በመጨረሻ ከአንድ ጥግ ላይ የሚንቀሳቀስ ነገር አይቶ ጠጋ ሲል በጀርባዋ ከንብል ብላ አገኛት። የሞተች መሰሉት አዘነ። ብድግ አድርጎ ሲይዛት ትንሽ ተንፈራገጠችና እግሮቿን ሰብሰባ የሞተች ይመስል ጸጥ አለች። ዙሪያ ገባውን ቃኘና በጠጣበት መስኮት ተመልሶ ገባ። በእጁ እንደ ያዛት ባንድ ጣቱ እያባበሰ የቁሰለች ወይም የደማች መሆንዋን ለማየት ሞከረ። የክንፏ ላባ ከመዘበራረቱ በቀር ምንም አላገኘም። እየደከመ ካለው እሳት ፊት ለፊት ተቀመጠና የበለጠ አገላብጦ መረመራት። የነሱ ቁስለትም ሆነ ተስፋ ሰጪ የሕይወት ምልክት ሰላላየባት የሚያደርገውን እጥፉ ከፊት ለፊቱ ወደ መሬቱ ጠጋ አድርጎ አስቀመጣት። ከሶፋው ላይ ያስቀመጠውን የተጀመረ የአባቱን ደብዳቤ አንስቶ ማንበብ ቀጠለ።

'አሁን ልቦናዬ ተመልሶ ሳስበው፣ ሕዝቦቿን ካልሆነ በእውነት አገር እንል የነበረው ምኑን እንደሆነ አይገባኝም። ልጆቿ ካለቱና ከተሰደዱ እናትነታ ምኑ ላይ ይሆን ብዬ እንገበገባለሁ። ዛሬ ያለፈውን ዘር ብዬ ሳየው የሚሰማኝ ባዶ ጨኸት ነው። የመፈክር፣ የሰብሰባ፣ የዘመቻና የጋርዲ

@OLDBOOOKSPDF

ጨዝት። የወላድ እናትች ለቅሶ፣ የሕጻናት እሪታ፣ የወጣቶች ሰቀቃ፣ የሀንብ ፍንዳታ፣ የጥይት እሩምታ፣ የታንክ ጓጓታ አውንም በልቤ ውስጥ ያስተጋባል። የሚታዩኝን በደም የተጨማለቁ አስር ቤቶች፣ በራሳ የተሞሉ ጉድባዶች፣ በሞስለኛ የተጨናነቁ ሆስፒታሎች፣ በነፍስ ገዳይ የተሞሉ መንገዶችና በእብራተኛ ዛፎራዎች የታጨቱ አዳራሾች ከዓይነ ኅሊናዬ ላወጣቸው አልችልም።

"ጉስቁላ አገር ወስደን በሳእረ ሞት የምትንፈራገጥ ምድር አስረከብናችሁ። ኩሩ ሕዝብ ተተብለን ፈሪ መንጋ አስተረገላችሁ። ሰለሙጥ የተራበና ለመሥዋዕትነት ራሱን የሰጠ ምርጥ ትውልድ ይዘን ተነሥተን ትስሙ የተበበረና ለጥቅም የነሆለለ ጨካኝ ትውልድ ትተንላችሁ ሄድን። ሀብታምን ማጥፋት ድኅን እንደማያበለጽግ፣ የተማረን መጨረስ ማይማንን ምሁር እንደማያደርግ የገባን እጅግ ዘግይቶ ነበር፣ ለዛውም ዛሬም በትጡ ከገባን። የተታመንንን ሁሉ አስወግደን ያለ ደጋፌ ስንቀር ግራ ገባን። በትውልድ ደምና በሕዝብ አምባ ላይ የነገባነው የአብዮት ጣልት ሲፈረካከስ ማመን አቃተን። ምሬትና ብሶት የወለደው በጥላቻና በበቀል የተሞላ ተተኪ ኃይል በስፍራችን ሲተካ ፍዳችን ገና ተጀመረ እንጂ እንዳላለቀ ተረዳሁ።

"ባለቆት አሥራ ሃስት ዓመታት ሙሉ ወሀኒ በነበርኩበት ጊዜ ይህንን ሁሉ እያሰቡ ከመንገብገብ በቀር ምን ሥራ ዝረኛ ብለህ ነው ልጄ? የኖን ስሕተትና የሆነውን ነገር ከሆነልኝ በዓይነ ሥጋ ላሟውትህ፣ ካልሆነም በጽሑፍ ላስቀርልህ ሳልችል እንዳልሞት በየቀኑ ጸሎት አድርሻለሁ። ከወር በኋላ እንደምትመጣ ባውቅም፣ ነገ የሚሆነው አይታወቅምና ሕመሜ ታገሥ ሲልልኝ ነው በየመሃሉ የጻፍኩት።

"በዚህ ሁሉ ጸጸትና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ የሚታየኝን ሚላንሚል የተስፋ ብርሃን ላወራህ ነው ዋናው ፍላጎቴ። በተለይ የሥነ ልቦናና የአእምሮ ሕዝምና ማጥናትህን ከተረዳሁ ወዲህ አንድ ምኞት ውስጤ ይነድ ጀምሯል። ምኞት ብቻ ሳይሆን የአባትነት አደራም ማለተላለፍ ኃላፊነቱ እንደ ሆነ ይሰማኛል። የምሰጥህ አደራ ምንም የገዘፈ መስሎ ቢታይህም፣ የማይቻል ግን አንዳይመስልህ። አኒ ባንተና እንዳንተ ባሉ ልጆቻችን ላይ ትልት አምነት አለኝ። በርግጥ ብዙ እንደማልኖር አውቀዋለሁ፣ የሚቆጨኝ ያንተን ልጆች ሳሳይ መሞቴ ነው። ግን የሕይወት ግዴታ ነውና አንዱ ትውልድ ሲሄድ ሌላ ትውልድ ይተካል። ባንተና በልጆችህ ውስጥ እኔም እኖራለሁ። አሁን ይልቁን ጊዜህን ሳላባዘን ወደ አደራ ንባቤዬ ልግባ። በረጅሙ ደብዳቤዬ እንዳላታክትህ አምናለሁ።

አንብቦ የጨረሳቸውን ገጾች ላለማታጠል አስበና ከግኑ መርመር አደረገው። ከፊት ለፊቱ ያለችውን ወፍ እንደገና አንሰተ ማናሸት ጀመረ። ጠረጲዛው ላይ ካለው የጠዘሙስ ውሃ ውስጥ እ[illegible] ሞከረ። ትንሽ ስትንፈራገጥ

በያሰታ ብድግ አለና ወደ መታጠቢያ ቤት ይዚት ሄደ። በቀስታ ተዝታዛውን የቧንቧ ውሃ ላይዋ ላይ ሲለቀው ከእኛ ለመጠጣት እየታገለች ከንፈርቿን ማንቀሳቀስ ጀመረች።

መደ ቢሮው ይዚት ተመለሰና እጁን ከፍ አድርጎ ሲያዝላት አንድ ሁለት ጊዜ ለመብረር ሞከራ እትቷት ወደቀች። ጥቂት ቀይታ ቢሮው ውስጥ ወዲያ ወዲህ በረረችና በዚያው አጋጥቶ በጣላት መስኮት በኩል ተመንትሳ በረረች። ክፍያም ምስጋናም ሳትሰጥ መሄዲ ቅያሜ አልፈጠረብትም። መልካሙን ተመኝቱላት በመስኮቱ የሚገባውን ቀዝቃዛ ንፋስ እየተቀበለ ትንሽ ቀየና የቀረውን የአባቱን ማስታወሻ ለመጨረስ ወደ መቀመጫው ተመለሰ።

''አገራቱ የደማች የቁሰለች ብዙ ሕዝምና የሚያስፈልጋት ናት። ትውልዱ በሥቃይና በሣንት፣ በፍርሃትና በሽብር ሥነልቦናው የተሰለበና ማንነቱ የተዘረፈ ሆኗል። ኢትዮጵያችን ያለፉት ከፍለ ዘመናት ቍስልና የገፍ እበሳ ላይሽርላት፣ የዘፋውን ሰቀቃ በእኛ እጅ በግድ ተጋቶች። እኛ ሰልሀ የቍንም ሁድንና ገራ ላይሆን፣ የእኖን ትውልድ ማለቱነው። መደፎም ጠላ፣ አወቅም አላወቅም፣ ሁሉም ሰው ይህንን ጠባሳ ይዞ ይዞራል። በውጪ በስደት የምትኖሩትም ሆን እዚህ በሀገር ቤትም ያለነው። አሸንር ሥልጣን የያዘውም፣ ተሸንር የሸሸውም። መግቱም፣ ንልግሳውም። ወንዱም፣ ሴቱም። ገጠሬውም፣ ከተሜውም። በድርቅ በሣንት፣ በድንነት በቂሞኖና፣ በሲጋት በፍርሃት ማንነቱን የተዘረፈ ሀልውናውን የተገፈፈ ሕዝብ ነውና የሚይታይ የጎሊና ቍስሉንና የልባና ጠባሳውን ተሸክሞ ይዞራል።

'ልጀ ሙያህን የፈረንጅ አገር ሐኪም ሆነህ ያሜራካንን ምቹ ኑሮ ለማጣጣም ብቻ ብትጠቀምበት ትልቅ ክስረት ነው። እትም ላይከፍህ፣ ፕልበትህ ሳያልቅ ወደ ሕዝብህ ተመለስ፣ ወደ አገርህ ግባ። የቁስለውን የአገራቱን ነፍስ እያከማችሁ የተፈረካከሰውን የኢትዮጵያዊነት ክብርና ማንነት ፈልጋችሁ ከመድኀበት አንሥት። የዚህን ምስኪን ሕዝብ ፍርሃቱንና ድንጋጤውን አርግዙለት። ፕላቻና አለመተማመን፣ ሟኅኔና ስግብግብነት፣ የበሽታ ምልክቶች ናቸው እንጂ የሔነኛ ሰው የሥለጠነ ንብረተሰብ ባሕርያት አይደሉም። አለመደማመጥ፣ ልዩነትን መፍራት፣ በሠራት ተወጥሮ በዚታችንት ስሜት መሠቃየት፣ ሴላውን ሞሎ ትልቅ ለመሆን መምዘር ሁሉ የተሸንፈ ማንነት፣ የዘቀጠና የተቀጠቀጠ ሰብእና መገለጫዎች ናቸው። ለንፍሩ ላንተ ምኑን እነግርሃለሁ። ያለፈው ይበቃል፣ አሁን ግን ፈረንጅቹ የእኖን ማንነትና ምንነት እንዲያስተምሩን የምንጠብትበት ጊዜ አይደለም።

'ትልቅነትን ከውስጣችን፣ ታላትንትንም በመካከላችን ፈልገን ልናገኘ ያስፈልጋል። አፍሪታን ሲመራና የጥቁር ሕዝብ አርአያ ሲሆን የሚችል ሕዝብ፣ በሞር መሣሪያ ሞንዛራ ወይም ባለፈ ታሪክ ላይ የሙጢኝ በማለት አይፈጠርም። በኅብረተሰብ የጅምላ ሥነሥታ ውስጥ የጠፋውን ግለሰባዊ የሰብእና ማንነትና ድምጽ ፈልጋችሁ አግኙት። ስታገኙት ደግሞ

@OLDBOOOKSPDF

በራስ ወዳድነትና ስግብግብነት፣ በተጠላለፈ ግለ ፍቅር ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር፣ በመናናትና በመናቁር እንዳይጠፋ፣ ያንድነቱን ገመድ የጎብረ-ማንነት መለያ ሀገራዊ ነፍሱን አስጨብጡት። ሥልጣኔ የሚፈጠረው በግለሰብ ነጻነትና በማኅበረሰባዊ ኃላፊነት መካከል ባለው ሚዛን ላይ ነው። ግለሰብን እየገደሉ ሀገር ሀገር ማለት ቀልድ ነው። ሀገራዊ ኃላፊነትና ማንነትን እንደ ኳስ እየሰጉ ነጻነትና መብት እያሉ ማላዘንም ትርጉም የለውም።

'የኢትዮጵያንና የልጆቿን ፈውስና እድገት፣ ብልጽግናዋንና ከፍታዋን በሰው ሕይወት ዘቡርነትና እኩልነት ላይ መሥርቱት። ሰው መሆን በራሱ እጅግ የከበረ ምስጢርና ድንቅ የጥበብ መደምደሚያ ነው። ሰውነት ከጾታና ከዕድሜ በላይ ነው፣ ከብሔርና ቋንቋ ይረታል፣ ከቁሳዊ ሀብትና ሃይማኖታዊ ቀኖናም ይገዝፋል። ያንተ ሥራ ይህንን በየልቦናውና በየቤቱ እንደገና መፍጠር ነው።

የአባቱን ማስታወሻ አንብቦ ሲጨርስ ከእሳት የተረፉትን ገጾች እንደያዘ ባደረገው ነገር ተደናግሞና ተጸጽቶ ከእሳቱ አካባቢ ዞር አለ። በግራ እጁ አጣጥፎ በያዛቸው ከእሳት የተረፉ ጥቂት ገጾች ከንፈሮቹን እየጠበጠበ በተደበላለቀ ሃሳብ ውስጥ ገብቶ ተናጠ። የትናንትን ጸጸትና ጥፋት በነገ ተስፋና ሕልም ማከም ይቻላል ብሎ ለማመን ከራሱ ጋር ግብግብ ገጠመ። የብዙ ትውልድን መከራና አበሳ ለመፈወስና ለማዳን እባቱ እንደ ጻራሊት መልሱ በእርሱ እጅ ላይ አለ ብሎ ማመን ከበደው። ተስፋ መቁረጥና መሸነፍን አማራጭ አድርጎ ማየት ግን አልፈለገም። እንደወጣ ከፊቱ የተጉበረውን ወኒማ ሰንጥቀ ለመብረር ተመኘ።

@OLDBOOOKSPDF

2

ሉላሠው አርብ ከሰአት በኋላው ከመቼው ፈጥኖ እንዳለቀ አልታወቀውም። ከወትሮው ቁጥራቸው የበዛና ችግራቸው ውስብስብ የሆኑ ባለተጠሮዎችን ሲያይ ዋለ። እስከናካቴው ካልቀረች ቢያንስ ማርፈዷ የተለመደው የዕለተ አርብ የመጨረሻ ሀመም‘ኖው እንኳ ሳትቀር ዛሬ በሰዓቷ ተደም ብላ ደርሳለች። ከጥቂት ወራት በፊት ባለቤቷ በማይወጣው የእዳ ማጥ ውስጥ ገብቶ በብስጭት ራሱን ካጠፋ በኋላ የገባችበት ጥልቅ ድብርትና የሐዘን አረንቋ ነበር ወዶ ከሲኒኩ ያመጣት። ብዙ ጊዜ ሞልቶላት በተጠሮዋ ባትገኝም እሱን ማየት ከጀመረች ወዲህ ጥሩ ለውጥ አሳይታለች።

ከእርሷ የማይለየው የሦስት አመት የመጨረሻ ልጇም አብሯት ይመጣል። ከሉላሠው ጋር መጫወትና መላፋት ስለሚወድ ከርሷ ይልቅ ሳምንታዊውን ተጠሮ በናፍቶት የሚጠብቀው እሱ ሆኗል። ከፍለ ጊዜው አልቶ ከመሰናበታቸው በፊት ፒያኖ ስለሚያጫውተው ‘ዶክተር ፒያኖ’ የሚል ስም አውጥቶለታል። እነርሱ ሲነጋገሩ እርሱም በፊናው አልፎ አልፎ ከራሱ ጋር እያወራ፣ በሰጠው ባለ ቀለም እርሳስ ወረቀቱ ላይ እንጉቻቀባ የሰጠው ስዕል ላይ ይቸከችካል።

ዋናው ክሊኒክ በሚገኝበት ቪላ ውስጥ ካሉት ሁለት ሰፋፊ ሳሎኖች አንዱ የርሱ ቢሮ ነው። በጥሩ ሁኔታ የተሠራው የድሮ ቤት በተንጣለለው ግቢ ውስጥ በዛፎች ተከቦ ሊወጣ የተዘጋጀ ሙሽራ ይመስላል። ሰፊውን ክፍል መሃል አጋማሹ ላይ ያለው ከፊል ግድግዳ ቢሮውን ለሁለት ይከፍለዋል። ባንድ በኩል የግል ሥራውን የሚሠራበትና አልፎ አልፎም እንግዳ ተቀብሎ የሚያናግርበት ቦታ አለው። ከወደ ጥግ አካባቢ አነስተኛ ፍሪጅ፣ የቡና ማፍያና የውሃ ማጣሪያ ይታያሉ። ከሥራ ጠረጴዛው በስተግራ ባለው ሰፋ ያለ ቦታ ደግሞ መጻሕፍት የተገጠገጡበት መደርደሪያ ግድግዳውን ሞልቶታል። በአንጻሩ ደግሞ ተመሳሳኝ ወንበር ከትንሽ የገን ጠረጴዛ ጋር ተሠይሟል። መተከሻና የሃላብ ጣቢያዬ ነው ብሎ ሰይሞታል።

በዚሮው ሌላ አጋማሽ ደግሞ ህመምተኞቹን የሚያይበት ከብ ሠርተው የተደረደሩ ምቹ ሶፋዎች አሉ። ከፊት የተቀመጠችው ተመካሪ ስታወራለት ሚንትላቱን እየነቀነቀ

@OLDBOOOKSPDF

በጸጥታ ያዳምጣታል። ከሚች ባሷ ቤተሰቦች የደረሰባትን ችግር እያወራች ማልቀስ ጀመረች። ጸጥ ብሎ ሲሟገት የነበረው ልጅ ወረቀቱን ወለሉ ላይ በትኖ እየበረረ ወደ እነርሱ መጣ። አንድ እጁን ጉልበቷ ላይ አድርጎ በድንጋጤ ከፊቷ ቀሞ ሲያያት እጁን ሰባ አቀፈችው። እሷ እንደምታደርግለት በትንሽ እጁ እምባዋን ከጉንጯ ላይ ሲጠርግላት ፈገግ ብላ እንቅ አድርጋ ሳመችውና ሞኗ ላይ አስቀመጠችው። የእለቱን የምክክር ክፍለ ጊዜ ሲጨርሱ ልጇን እንደ ታቀፈች ከወንበሩ ተነሳች። ተንሸራቶ ከላዩዋ ላይ ወረደና በሩጫ ሄዶ የበታተነውን ወረቀት ሰብስቦ አመጣና

"የውልዘ ዶክተል ፒያኖ ..." ብሎ፣ ወረቀቱን ከፍ አድርጎ አንጋጦ ሲያየው በርሱ ቁመት ደረጃ ለመሆን ባንድ ጉልበቱ በርከክ አለና የሳለውን እያየለት

"ዋው ... በጣም ቀንጆ ነው ... ማናቸው እነዚህ?" አለው፣ በደማቅ ቀይ፣ በጥቁርና በቢጫ ቀለም የተሳሉትን የተለያየ መጠን ያላቸው ሰዎች እያየ። በቀይ የተሳለችው ትልቋ የሴት ምስል እናቱ ስትሆን፣ በቢጫ የተቀቡት ትንንሾቹ ምስሎች ደግሞ እህቶቹና ራሱ እንደሆኑ ነገረው።

"ይሄስ ማነው?" አለው፣ ራት ብሎ በጥቁር ቀለም የተሳለውን ቀብ ያደረገ ትልቅ ወንድ የሚመስል ሰው እየጠቆመው።

"እሱ አጎቱ ነው ... ዝም ብሎ ጾሎ ይቀናጠጣል እኮ እሱ" አለ፣ ፊቱን ጭምድድ አድርጎ።

በሰእሉ ላይ ከቢጫዎቹ ትናንሽ ምስሎች ያንዱን ጆሮ በረጅም እጁ የያዘ መሆኑን አይቶ ፈገግ አለና፣ "ምን እያደረገ ነው?" ሲለው፣

"እንዴ ጾሎ እየተቀናጠጠ ነዋ ... የሚጡን ጾሎ እኮ ነው የሚቀናጠጠው። እነ ሮዉ ነው የማመልጠው" አለ፣ ግንባሩን ቅጭም አድርጎ።

"ይሄኛው ስ?" አለው፣ በሰማያዊ ቀለም ከወረቀቱ እናት ላይ የተሳለውን ባለ ከንፉ የመሰለ ሰው እየጠቆመ።

"እንዴ ... እሱማ አባቢ ነው ... ወደ ሰማይ ቤት ሲበርር ነው። ሉሊት ሉሊት ሰው ሁሉ ሲተኛለት ደግሞ ... ተሰ ብሎ ይመጣና አይት አይት አድርጎን ... በመ... ሞ...ት ብን ብሎ ይጠፋል እኮ..." አለ፣ አይኑን አቡዝዞና አፉን እሹሉ እጆቹን እንደ መብረር ወደ ላይ እያደረገ። በወፈው የተገረመችው እናቱ አንዴ ሰዕሉን አንዴ ልጇን እያየች ታዳምጣለች። "በላ ዶክተል ፒያኖ... አሟጨሁኛ ..." ብሎ፣ ወደ ፒያኖው ሮጠ። አጠገቡ ተቀምጦ አብሮት ቁልፎቹን እየነካካ አሟጨተው። ጊዜው እየመሸ ስለ ነበረ በሌላ ጊዜ እንደሚተዋለ ታልሳ ገባለትና ታትሮት ተነሳ። የቢሮውን በር ከፍተው ሲወጡ ግንባሩ ላይ ሳም አደረገውና ተስ ብሎ እያወረደው፣

"አንተ በጣም ገበዝ ልጅ ነህ እኮ ... አይደል? ማሚን አታስቸገር እሺ አለና አንዲት ቸኮሌት አውጥቶ ሊሰጠው ሲዘረጋ፣ ከእጁ ላይ መንሜቶ ወደ ቀጠሮ ማስያዣው ቦታ ከእናቱ ቀድሞ ሮጠ።

@OLDBOOOKSPDF

እንርሱን አስናብቶ ወደ ቢሮው ሲመለስ ቢሮው ውስጥ የንግስው የጸጥታ ድባብ ተቀበለው። በስተቀኝ ካለው መስኮት አንጻር ያለው ጥቁር ፒያኖ ላይ ዓይኑ አረፈ። ወንዘሩን ላብ አድርጎ ተቀመጠና ስለ ራሱ ልጅነት ማሰብ ጀመረ። ደግሞ ስለ ባለቤቱ። አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ይላል። በመስኮት በሚገባው ደብዛዛ ያመሻሽ ብርሃን ለማናት እየሞከረ በረጋታ የፒያኖውን ቁልፎችና የፊት ገላ ማጽዳት ጀመረ። ባለቤቱ ንጹሕ ሁል ጊዜም ከመጫወቷ በፊት ፒያኖውን ልትም አድርጋ ማጽዳት ታዘወትር ነበር።

ድጁ በፍጥነት እየጨለመ ስለ መጣ ከፒያኖው አጠገብ ያለውን ደብዛዛ መብራት አበራው። ቁልፎቹ አንጸባርተው ታዩት። እያንዳንዷን ቁልፍ ቀስ ብሎ በጥንቃቄ እየወለወለ በውስጡ በሚፈሰው የሐሳብ ወንዝ መሐል ላይ ቁሞ የመጣውን ሲሸኝ አዲሱን ሲቀበል ደቂቃዎች ነጎዱ። ማጽዳቱን ሲጨርስ ጣቶቹን ወዲያ ወዲህ እያያደረገና ቁልፎቹን እየነካካ፣ ለስለስ ያለ ሙዚቃ መጫወት ጀመረ። በተመስጦ ውስጥ እየገባ ሲሄድ እንዴ ከፍ እንዴ ዝቅ፣ እንዴ ፈጠን እንዴ ረገብ እያደረገ የጥልት ስሜቱን ዜማ እየተጫወተ ግማሽ ልቡ ከክፍሉ ርቆ ሄደ።

ከቢሮዋ ሆና የፒያኖውን ድምጽ የሰማችው ምስጢር በሩን ደጋግማ ስታንኳኳ አልሰማትም። የበሩን እጅታ ቀስ ብላ ጫን ስትለው ተከፈተላት። በቀስታ ገባችና ከጀርባው ቀጣ በጸጥታ ስታዳምጠው ቀየች። መጫወቱን ድንገት ሲያቆም ጨለማ የነገሠበት ክፍል ቀዝቃዛ ጸጥታ ወረረው። ሠኖሯን ለማሳወቅ ያህል ጉሮሮዋን ጠራረገችና እያጨበጨበች ከኮመችበት ወደ እርሱ ቀረብ አለች።

"ዎው! በ-ጣ-ም ... በ-ጣ-ም አሪፍ ነው። ወይኔ ... ታድለህ ዶክተር ሌላ ... ግን ምነው ከጨለመ ... ወርቹ ተመስጠው እ-ን-ዳ-ይ-ረ-ግ-ፉ ነው እ-ን-ዴ ጨልሞ ከተ-ኛ በኋላ ..." አለች፣ ለስለስና ሞልቀቅ ባለ ድምጽዋ። ከፍሉ ውስጥ ሌላ ሰው ይኖራል ብሎ ስላልጠበቀና መኖሯን ስላላወቀ ድንግጥ ብሎ፣

"እንዴ ... መጣሁም የለም እንዴ? አስደነገጥሽኝ እኮ። መቼ ነው የገባሽው ልጄ?" አለና ግማሽ ሰውነቱን ወደ እርሷ አዙሮ ሊጨብጣት እጁን ዘረጋላት።

ጠጋ ብላ ጉንጩን በትንሿ አጋጭታ ሰላም እያለችው፣ "ባንኳኳ ባንኳኳ ... አንተ ለራስህ በሙዚቃው ተመስጠህ ምንም አትሰማም። ከምረብሽህ ትንሽ ላዳምጥ ብዬ በቀምኩበት ... በቃ ... ሙዚቃው እኔንም ይዞኝ ሄደ። ያለሁበትንም አስረሳኸኝ እኮ"

"እቤት እቤት ... እንዲያው አሁን ይሄ ምኑ ነው? ... እንኳን ያሉበትን ሊያስረሳ" አለ፣ የጨበጠውን እጇን እየሰቶ።

"የምር ዶክተር ሌላ ... በጣም አሪፍ ነው። ምነው ትንሽ አልጨለመብህም? ... ወይስ ፈልገኸው ነው? ቢሮው እኮ የተወረረ መስሏል። በእርብ ምድር ደግሞ እስካሁን እንዴት አልወጣህም?"

@OLDBOOOKSPDF

"ኧረ ገና እሱን መጨለሙ ነው። ድግሞ ... ዩ ኖው ... ደብዘዝ ባለ ብርሃን ቤት ሆኖ ወይም ጨለም ሲል መሣሄት ደስ ይለኛል። የሆነ ሙድ ይፈጥራል። አሪፉ መብራቱን ከፈለግሽ። አነቺስ ዛሬ እንኴት ገባሽ?" በግራ እጁ ጭቁት የፒያኖውን ቁልፎች መነካካቱን ቀጠለ። ግድግዳው ላይ የተለጠፉት መብራቶች ከየማእዘኑ ሳቢ፣ ቢሮው በብርሃን ፈላሽ ተሞላ።

"ምን ባክህ ለረጅም ጊዜ ጠፍተሙብኝ የነበሩ ስምንር የማያቸው ቤተሰቤ ነበሩ። ያስ ዛሬ አይመቸንም ስላሉኝ እነሱን ለማየት ብዬ ነበር መጄ አሥር ፅግት ላይ የገባሁት። የባልና ሚስቱ ጠብ ልጆቹን መከራቸውን አበላቸው። አንተስ እንዴት ነር ቸንህ?" አለችና ከጥግ አካባቢ አንድ ወንበር ሳበችና ወደሱ ዞራ ተቀመጠች።

"ደህና ... ምንም አይል፣ ዛሬ ትንሽ ቢዚ ነገር ነበር። ሴላው ... ያው እሱ ሁሉም ነገር ባለበት አለ። ምን ይሆናል ብለሽ ነው" አለ፣ ትንሽ ትክት ባለው ድምጽ። ጀርባውን ለጊያኖው ሰጥቶ እጆቹን አቀላልፎ ባንባበራቸው አግሮቹ ላይ ጫናቸው፣ ለጥቂት ጊዜ ሁለቱም ጸጥ ብለው ቆዩ። ያለበት ሁኔታ ቢያሳስባትም እንዴት እድርጎ ልታወራውና ልትረዳው እንደምትችል ግራ ገባት።

"ይክተር ሴላ ... እይ ኖው ...የራስህን ጉዳይ ለለው ማውራት ላንተ ምን ያህል በጣም ከባድ ሊሆን እንደሚችል። ግን ደግሞ ... አለ አይደል ... ዝም ብዬ ሳሰበው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደሆንክ ይገባኛል። ራስህን እየገዳህ እየመለስኝ ምንም ልናደርግልህ አለመቻላችን በጣም ያስጨንቀኛል። ግን እንዲያው ቢያንስ የምታወራው ሰው አለን" አለች፣ ፊቷን ጽጠር ፈታ እያደረገች። በቀኝ መዳፏ እንዚን ደግፋ የውስጥ ስሜቱንና ሃሳቡን ለመረዳት ይመስል ባደገ ጢሙ ውስጥ የተደበቀ ፊቱን ሀዘኔታ በተሞሉ አይኖቿ ልትበረብር ሞከረች።

በረጅሙ ተነፈሰና፣ "አይ ደህና ነኝ እኮ፣ ያው ትንሽ ማሰብና ... አለ አይደል... አንዳንድ ነገሮች መልክ እስኪይዙ ጊዜ ይፈልጋሉ መሰለኝ። እኔ አንቺ... ምንየሚወራ ነገር አለ ብለሽ ነው?" ብሎ በማመንታት አይነት ዝም አለ።

"እኔማ ወደ ቤት ለመሄድ ልወጣ ሰል ጂያኖውን ሰምቼ ሰላም ልልህ ነበር አመጣጤ። መዚታውን ስሰማ ሳላሰበው እዚሁ ተልጡ ተረሁ እንጂ" አለች፣ ምን ማለት እንዳለባት ግራ ስለገባትና ጸጥታው ስለ ነበጻት። እንደ ምንም ፈገግ ብላ እየት እደረገችውና ደጁን የሞጠውን ጨለማ አልፋ በመስኮቱ አሻግራ ለማየት ሞከረች። ትክሻዋ ላይ ጣል ያደረገችው የሙዚታ ማዳመጫ ገመድ ብዙ ጊዜ ወይ ከጆሮዋ ወይ ዛንገቷ ላይ አይጠፋም። የገመዱን እንድ ጫፍ ጣቷ ላይ እየጠመጠመች ስትፈታ እጅ እጇን ሲያያት ቀየ።

"ታውቲያለሽ፣ ይሄ ከለኒክ ባያከፈት ወይም ሞራሽ አኔ ወደ እዚህ እዝ ባልመጣ እነ ይሄ ሁሉ ችግር አይፈጠረም ነበር። እኔም ..." አለ፣ የራሱን ችግር ሰሙናገር የፈራ ይመስል ጥርሱን ነክሶ እጁን ጨበጥ ለተቅ አድርጎ ዝም አለ። ናቢ እጆች ላይ ተተክለው የቀዩ ዓይኖቹን ማሳረፊያ እንደጣጣቸው ሁሉ መሰድ የራሱ ጫማ ላይ ጣላቸው።

@OLDBOOOKSPDF

"የሆነው ነገር ሁሉ እነ አንተ ስለ መጣህ ወይም ይሄ ከሊኒክ ስለ ተከፈተ አይደለም የሆነው። መሆን ካለበት በሌላ መንገድም ሊሆን ይችላል። እንዲያውም ከዚህ የባሰ ነገርስ ቢሆን? የተፈጠረውን ችግር ሳይሆን ምንም ባትሠራ ኖሮ ሊሆን የሚችለውን የባሰ ነገር ማሰብ ያለብህ ይመስለኛል። እዚህ በመምጣትህና ከሊኒኩ በመከፈቱ የሆነውን ጥሩ ነገርና የተረዱትንም ሰዎች መርሳት የለብህም" የተናገረችው ባያሳምነውም ለመከራከር ምንም አትምና ፍላጎት ስላልነበረው ዝም አለ። "ምን አስብክ ታዲያ ... ወደ ቤት ለመሄድ ወይስ?"

"እኔ እንኳ፣ የጀመርኩት መጽሐፍ አለ፣ ወይ እሱን እጨርሳለሁ። አስበስዚያም ድክም ስላለኝ ወደ ቤት ገብቼ አረፍ እላለሁ" አለ፣ በተሰላቸና የስሜቱን መውረድ በሚያሳብቅ ድምፅ።

"ውይ ውኃ እንዴት እንደ ጠማኝ ... ሁለት ሰአት ሙሉ ያለ ማቋረጥ ስንዳሪቅ ነው ያለተው ... ብታይ ሙሉ ሲሸት ንትርክ ነበር። ውኃ ትፈልጋለህ?" ብላ ፀልሱንም ሳትጠብቅ ቦርሳዋን መነበሩላይ ጣል አድርጋ ተነሳች። ከባሻገር ካለው ማጣሪያ በሁለት ብርጭቆ ይዛ መጥታ እያቀበለችው፣ "እሺ ቢያንስ እዚህ አታምሽ በናትህ። ከመጣህ ጀምሮ እኮ ... በቃ፣ ይሄ ቢሮ ኦልሞስት ቤትህ ሆኗል። አይ አም ሹር ... እናትህም ብዙ እንደሚጨነቁ" አለችና የያዘችውን ውኃ ባንድ ትንፋሽ ጨለጠችው።

"እም ... ችግር መኖሩን ሳትጠረጥር አትቀርም። የሲ ፍላጎት ሁልጊዜም ወደዛው ተመልሼ እንድሄድ ነው። ያለሁበት አጣብቂኝ ፈጽሞ ስለማይገባት ዝም ብዬ እሺ እሺ ከማለት በቀር ምንም ማድረግ አልችልም። አንቺ ግን የምትሄጂበት ቦታ ካለ እንዳይመሽብሽ" አለ፣ አብራው መቀየድን በልቡ ቢመኝም። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከሩብ ሆኗል። ጥሰቱልቱል ያለውን ፊቱን ስታይ ይበልጥ አሳዘናት።

አሲም ሰዓቷን እየት አድርጋ፣ "ውይ ግና ነው ጊዜው። እዚህ ብቻህን ከምትሆን ለምን እኔ ራት አልጋብዝህም? በናትህ የዛሬን እሺ በለኝ። ግድ የለህም ዶክተር ሌላ ... እዚህ ብቻህን ከምትሆን ይሻላል" አለች፣ ያላትን ድፍረት ሁሉ አሰባስባ።

ትንሽ ካመነታ በኋላ "ጥሩ ... አሪፍ ራት ከጋበሽኝ ምናለ" ብሎ የደከመ ፊቱን ፈገግና ዘና ለማድረግ ሞከረ። በትርብ ከአሜሪካ ከተመለሰ ወዲህ ከማንም ጋር ወጥቶ አያውቅም። ገብሃዋን ድንገት እሺ ሲል ማመን አቅቷት አሳቡን እንዳይቀይር ይመስል ከመቀመጫዋ በፍጥነት ብድግ አለች።

ከፒያኖው በላይ ያለውን መስኮት መጋረጃ ዘጋግታ ወደ እርሱ ጠጋ ብላ እጁን ትከሻው ላይ ጣል አደረገችና፣ "የፈለከውን እራት ... የፈለከው ቦታ" አለች፣ ፊቷ ባንዴ ፈክቶ። መብራቱን አጠፋፍተው እየወጡ፣ "ተከታትለን እንሂድ ወይስ ባንድ መኪና?" አለች፣ አብሮ መሄዱን ብትፈልገውም የርሱን ፍላጎት ለማወቅ።

"ከመሸ በኋላ እዚህ ድረስ ተመልሰን መምጣት ይሆናል እንጂ ጥሩ ነበር። ግድ የለም እንከታተልና ባይሆን የእራቱ ቦታ ሩቅ ከሆነ አማካይ ስፍራ አቋመን ባንድ መኪና እንሂዳለን።"

@OLDBOOOKSPDF

መኪናው ውስጥ ገብቶ ሲያስነሣው ቢሞክር ሞተሩ አልነሣ አለው። ችግሩ ከ ባራ ሲል ያላስተየረው ባትሪ እንደሆነ ገብቶታል። ወደ እሷ ሲመጣ አየችና መስኮቷን ዝት አድርጋ፣ "ምነው? ... ስላም ነው?" አለች፣ ሃሳቡን ለውጦ ሲተር እንደማያሆን ተስፋ እያደረገች።

"አይ ቲንክ ... ባትሪው መሰለኝ፣ አልነሳ አለ ሞተሩ። ባትሪ ማንቂያ ገመድ አለሽ እንዴ?"

"አዩ ... አይታይህም፣ ኧረ ምንም የለኝም። ታዲያ ምን ተሻለ? ለምን በቃ በኔ መኪና አብረን ሄደን ... ከራት በኋላ ወደ ቤት እኔ ላደርስህ እችላለሁ" አለች፣ ለመውረድ እይነት በሯን ከፍታ አንድ እግሯን በከፊል እያወጣች።

"አይ ገስ ... እሱ ይሻላል መሰል" ብሎ፣ በረጅሙ ተነፈሰና ዞር ገባ። የምትነዳት ውስጧም ውጪዋም ብርማ የሆነ ቢ ኤም ደቢሊው ኤክስ ሩይፍ ስትሆን ሁልጊዜም ንጹህና በመልካም መዓዛ የታወደች ናት። ጣጣ በሚያጣት በርሱ እርጌ ተዮታ ሃይላክስ ሰርፍ መቀለድ ትወዳለች። ሂልተን ለመሄድ ስለወሰኑ ለመድረስ ብዙም አልወሰደባቸውም። ከወደ ጥግ አካባቢ ተቀመጡና የቤቱን ፒዛ እዘው ወደ ወሬያቸው ገቡ።

ያዘዙት ፒዛ ሲመጣ ከመቀመጫው ተነሳና "እስኪ ... ጀምሪ አንቺ ... እኔ በእሺ ስለምበላ ታጥቤ መጣሁ" ሲል፣

"ግዴለም ... ደርስህ ና ጠብቅሃለሁ። እንዲያውም እስክዛ ማሚ ጋ ልደውል፣ ቢመሽ እንዳታስብ" አለችና፣ ስልኳን ፍለጋ ቦርሳዋን መበርበር ጀመረች። ሒልተን በስው ተሞልቶና ደምቀ ምግብ ቤቱም በበላተኛ ተጣቧል። ዓርብ ማታ በመሆኑም ይመስላል በየሰዉ ፊት ላይ ከፍ ያለ መንፈስና የጋለ ስሜት ይንሸራሸራል። እየበሉ የሆ ያልሆነውን እያወሩ ሲሣሣቁ ቀዩ። በውስጧ ስለ አርሱ ልትጠይቀው ያሰበችውን ጉዳይ እንዴት አድርጋ መጀመር እንዳለባት ስታስብ ቀየችና፣

"እኔ የምልህ ዶክተር ሉላ፣ ካሚሪካ ተመልሰህ ከመጣህ እኮ በሥን ሥርዓቱም ቁሞ ብለን አላወራንም። እንዴት ናቸው እነ ንጹሕ? ጨጨዎቹማ እንዴት እንዶ ናፈቁኝ ... ቀይ አንተ ግን ናፍቀቱን እንዴት ነው የምትችለው?" አለች፣ ፊቱን እያጠናች።

ያነሳውን የፒዛ ቁራጭ መልሶ አስቀመጠና እምቦ ውሃውን ጎንጨት አድርገ "እንዴት ነው የምችለው? እውነቱን ልንገርሽ? ...አልችለውም። ግን ደግሞ ምን ይደረጋል? ሁለት መደ አይሆንም። አንድ ነገር ለማድረግ ስትፈልጊ ሌላ ነገር መሥዋዕት መሆኑ አይቀርም። የተከፋፈለ ሕይወት ስትኖሪ ደግሞ አንዳንድ ነገሮች አንቺ እንዳሰብሻቸው ሳይሆን እነሱ እንደ ፈለጉት ስለሚሄዱ ጣጣው ብዙ ነው። "ማድረግም አለማድረግም ኪሳራ ሲሆን' እንደሚሉት አባባል" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ። ጭላጭ እምቦ ውሃ የያዘውን ብርጭቆ በጣቶቹ እያሽከረከረ የሐሳብ አዙሪት ውስጥ ገባ።

@OLDBOOOKSPDF

እምቦ ውሃውን እየሞላችለት፣ "ኮይ እኔ የምልህ ... በአሁኑ የሄድክ ጊዜ ንጹሕ ባስቸኳይ ጠርታህ ነበረ የሄድከው አይደል? ... ወዲያው ደግሞ ኦልሞስት በሁለት ሳምንቱ ተመልሰህ መጣህ። ከመጣህ ጀምሮ ደግሞ በፍጹም የቀድሞውን አንተ አይደለህም። አዲስ የሆነ ነገር ወይም የተፈጠረ ችግር አለ? ማለቱ ልትነግረኝ የምትችል ከሆነ" ብላ፣ ጠረጴዛውን በክርኖቿ ተደግፋ መልሱን መጠበቅ ተጠለች።

"ኡፍ...ፍፍ...ፍ ... ዩ ... ኖው ... ቀይ ምን ልንገርሽ? ነገሩ ራሱ እኮ ለወሬ አይመችም። እኔይ ... አንዱ ባጠቃላይ ወደ እዚህ አገር መምጣቴንም ሆነ የህክምና ማእከል መክፈቴን ... በዚህም የተነሳ አብዛኛውን ጊዜዬን እዚህ ማጥፋቴ ልክ ነው ወይስ ልክ አይደለም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ትልቅ ትግል ላይ ነኝ። ንጹሕ ሁልጊዜም እዚህ መምጣቴንም ሆነ ክሊኒክ ከፍቼ መሥራቴን ከመጀመሪያውም ተቃዋሚ ነበረች። ሌላው አስቸጋሪ ነገር ደግሞ ... አሁን ሀሳቤን ልለውጥ ብል እንኳን እዛ ያለው ነገርም ተበለሻሽቷል። ስለዚህ እዚህ ብቀይም ተመልሼ ብሄድም ለውጥ የለውም። እስኪ እየበላሽ" አለ፣ በወሬው ተጠምዳ መብላቷን አቁማ ስለነበር።

"በጣም በላሁ እኮ፣ እንደዚህ እንደ ራበኝ አላወቅሁም ነበር። እሺ ግን ቀይ በመጀመሪያ ... በአሁኑ እዛ የሄድክ ጊዜ ምን ሆነ?" አለች፣ ግራ መጋባቷ ጨምሮ።

"እኪይ ... በመጀመሪያ ነገሩን ሌላ ሰው እንዲያውቅ ስለማልፈልግ ሰራስሽ ጠብቂው። ትዝ ይልሻል ... የዛሬ ሰባት ወር ገደማ ከክሊኒኩ ምረቃ በኋላ የሄድኩ ጊዜ? ሁለት ቦታ መኖር እንደማንችልና በምንም መንገድ እቢ እዚህ ኢትዮጵያ መጥቃ መኖርም ሆነ ልጆቹ እዚህ እንዲያድጉ እንደማትፈልግ ነግራኝ ነበር። ያው የተወሰነ ተጨቃጭቀን መጨረሻ ላይ አማካይ የሆነ ነገር ለመፈለግ ተስማምተን ነበር ነገሩን የዘጋነው። በመሃል ጥሩ የተግባባንና ልዩነታችንን ቀስ በቀስ የምንፈታው መስሎኝ ነበር። ማመን እኮ ነው የሚያቅተው" አለና ትንፋሹን ያገ አደረገ።

ሁሌም ወጥረት ሲሰማው እንደሚያደርገው እጁን ጨበጥ ፈታ አድርጎ ንግግሩን ቀጠለ። "ያው ባሁኑ ባስቸኳይ እንድትመጣ ስትለኝ ለእኔ የመለሰኝ ወይ ልጆቹ ታመው ወይ የሆነ ነገር ተፈጥሮ ነበር" ሲል፣ ቀጥል በሚል ዓይነት ዓይኖቿን እሱ ላይ እንደ ተከለች ሞንትላቷን ነቀነቀች። "እና ገና ስደርስ በጣም ነበር የደነገጥኩት። መኝታ ቤት ለይታ፣ ምን ልበልሽ ሁሉም ነገር አልቀ ነበር የጠበቀኝ። ባጭሩ የፍቺ ወረቀት አዘጋጅታ እንድፈርም ጠየቀችኝ።"

"እኔ አላ...ም...ንም እኮ" አለች ድንግጥ ብላ። አፏ የደረቀ ስለመሰላት ትንሽ ውሃ ተገነጨች።

"ያ ... እኔም ሰማይ ምድሩ ነበር የዞረብኝ። ኤኒ ዌይስ፣ ምን አዲስ ችግር ተፈጠረ ሰሳት ያው በፊት የተነጋገርናቸውን ነገሮች እንሥታ 'አንተም አባትህ የሰጡህን አደራ ተወጣ፣ ደግሞም የልጅነት ፍቅረኛህን መፈለጉን ተዮል። እኔም የራሴን ሕይወት እቅጣጫ ማስያዝ አለብኝ' ምናምን ስትል የሆነ ነገር ካሰብኩት በላይ ከመሰመር መውጣቱ በድንብ የገባኝ ያኔ ነበር" አለና ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ ተተመጠ።

@OLDBOOOKSPDF

"ቀይ ቀይ አልገባኝም ፣ ማለቴ ያባትህ አደራ እና የልጅነት ፍትረኛ ምን ማለት ነው?" አለች ፣ ፊቷን አጨማትራ ።

"የወ·ልሽ ሚስጥር ... ለዚህ እኮ ነው ነገሩን ማውራት የማልፈልገው· ። ብዙ የማታውቂው ነገር አለ ። "

"ላንተ የማይከብድህ ከሆነ ... ብትነግረኝ..." ስትለው ፣ ትንሽ ካመነታ በኋላ ስለ አስተዳደጉ ፣ ስለ አባቱና በመጨረሻም ከመሞታቸው በፊት ስለሰጡት እደራና ስለጻፉለት ማስታወሻ ዋና ዋና ነገሩን አጫወታት ።

"አይገርምም ... አባትህ ምን አይነት ሰው· ሊሆኑ እንደሚችሉ እስከዛሬ አስቢው·ም አላው·ትም ነበር" ብላ ጥቂት ዝም ብላ ቀየችና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ስትጠይቀው· ቀየች ። "እሺ ሌላው·ስ?" አለች ፣ 'የልጅነት ፍትረኛ ፍለጋ' የሚለውን ሃሳብ የማወቅ ፍላጎቷ ንሮ ።

"ቂ...ል እሱም ራሱን የቻለ ረጅም ታሪክ ነው· ። አሁን ሁሉንም ነገር ልነግርሽ አልችልም ። ሐሳቡ ግን ... እም ... ም እንዴት ልንገርሽ? ግድ የለሽም እሱን ሌላ ጊዜ ልንገርሽ ። " ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ ተቀመጠና እጆቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ዝም አለ ።

"ለምን? ጊዜ አለን እኮ ። ፕ...ሊ...ስ..." ብላ ተቁለጨለጨች ።

"እኩ ...አይ ቲንክ ..." አለና ጥቂት እንደገና አመነታ ። "የቱ ጋ ልጀምርልሽ ... እም...ም ... እሺ ... ባጭሩ ምን መሰለሽ ፤ ገነት የምትባል ከሰባተኛ እስከ አሥራ አንደኛ ክፍል ድረስ ጓደኛዬ የነበረች ልጅ ነበረች ። የመጀመሪያ የልጅነት ፍትረኛዬም ነበረች ። እናቷ የሥጋ ደዌ ሕመም ለመታከም መጥተው· በዛው· እዚሁ አዲሳባ የቀሩ ሲሆኑ ብቸኛ ልጃቸው· ነበረች ። አባቷ ከመወለዷ በፊት ነበር የሞቱት ። ደስ የምትል ቀንጅዬና በትምህርቷም ጐበዝ ልጅ ነበረች ።

"ታዲያ በእናቷ የሥጋ ደዌ ሕመም ሳቢያ ልጆች እያገለሉና እያበሽቁ በትምህርት ቤት· ው·ስጥ መከራዋን ያሳዩዋት ነበር ። አሁን ሲገባኝ ቀንጅና ጎበዝ መሆኗም መሰለኝ ጠላቷን ያበዛው· ። ኤኒ ሃው ... አንድ ቀን ሰባተኛ ክፍል እያለን የሆኑ ልጆች ከበዋት፣ ይብተሯን ሚዳ ላይ በታትነው· ሲቀልዱባት ከጓደኞቹ ጋር ድንገት ደረስን ። የእኛ ግሩፕ በዚያን ጊዜ በለፈሩና በትምህርት ቤቱ ሁሉ የተፈራን ተደባዳቢዎች ነበርን" ብሎ ሳት አለ ።

"ጉልቤነት ከድሮው·ም ነው· በለኛ?" ብላ እሷም ሳቀች ።

"ወይ ጉልቤነት ...አይገርምሽም ... ገና እኮ ትናንሽ ልጆች ነበርን ። አሁን ሳሰበው· የኔን አባት ሰው· ሁሉ እንደ ሥር ነበር የሚፈራው· ። ለዚያ ይመስለኛል ፣ ደፍሮ የሚናገረኝ ሰው· ያልነበረው· ። ብቻ የዚያን እለት ልጆቹን አንበርክከን እየገረፍን ይቅርታ እንዲጠይቁት አደረግናቸው· ። ከዚያ እኔና አንድ ጓደኛዬ ቤቷ ድረስ ሸኘናት ። ግቷ ላይ ለአባቱ ያደረግነው·ን ሰነገረው· ፊቱ ላይ ያየሁት ደስታ አይረሳኝም ። በህይወቱ እንደዛ ኮርቶብኝ የሚያው·ትም አያመስለኝም ። የራሱን የድህነት ታሪክና በልጅነቱ

@OLDBOOOKSPDF

የደረሰበትን ነገሮች ሁሉ ያጫወተኝም የዛን እለት ነበር ። በማግስቱ እቤት እንዳመጣት ነገረኝ ።

"በታ ምን ልበልሽ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንዶ ልጁ አድርጎ ነበር የሚያያት ። ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጋትን ነገሮችና ልብስ ፣ ሁሉንም ነገር ለኔም ሰፂም እንድ ላይ ነበር የሚገዛልን ። ከእኔ ጋር ጥሩ ጓደኛሞች ሆንን ። ብዙ ጊዜ እንደኛና ሁለተኛ ስለምንወጣ ብርቱ ተፎካካሪዎችም ነበርን ። አባቴ ትምህርት በጣም ስለሚወድ ፣ ንበገ ተማሪ መሆኗ ደግሞ የበለጠ እንዲወዳት ሳያደርገው አልቀረም ። ዓመት በአል ሲሆን የሚያስፈልገውን ነገር ለናቷም ይልክላቸው ነበር" ሲል ፣

"ወይኔ ምን አይነት አሪፍ አባት ናቸው?" አለች ፣ ከሚች አባቷ ጋር እነጻጽራቸው ። ጥሩ አባቶችን ባየችና ደስ የሚል ታሪክ በሰማች ቁጥር የአባት ረሃቧ ይቀሰቀስባታል ።

"አባቴ በጣም ብዙ የሚገርሙ ባህርያት ነበሩት ። ኤኒ ዌይስ ... ወዶ ታሪኩ ልመለስ ። እንዳልኩሽ አብረን ነበር የምናጠናው ። በዛ ላይ በአገር ኳስም ጉበዝ ስለ ነበረች ሰፈር ውስጥ ከእኛ አትሰይም ነበር ። ብዙ ጊዜ የምናጠናው እኛ ቤት ነበረ ። እናቷ ልክ እንዶ ልጃቸው ነበር የሚወዱኝ ። እኔም እንደላቸው ሽሮ ፣ የምወደው ምግብ አልነበረም ። እናቴ ለወጥ ብታዝንላትም አብረን ብዙ ጊዜ ማጥፋታችንን አትወደውም ነበር ። አባቴ በጣም እንደሚወዳት ስለምታውቅ ምንም ማድረግ አልፈለገችም ። የእናቷን ሕምም ስለምታውቅ ብዙም እነሱ ቤት እንድሄድና እንድንቀራረብ አትፈልግም ነበር"

"ይቅርታ አቋረጥኩህ ። ስሟ ማነው?"

"ገነት"

"ደስ የሚል ስም ... እሺ ... ቀጥልልኝ" አለችና ተመቻችታ ተቀመጠች ።

"አሥረኛ ክፍል እካባቢ ስንደረስ ግን መዋደዳችን መልኩን ቀየረና ሌላ አይነት ፍቅር ውስጥ ገባን ። ለሁለታችንም የዛ አይነት ፍቅር የመጀመሪያ ስለሆነ ምን ማድረግና መሆን እንዳለብን እንኳን እናውቅም ነበር ። በታ እጅ ለእጅ መያያዝ ፣ መተቃቀፍና መሳሳም ፣ ሲተያዩ መዋል ሆነ ሥራችን ። እንድ ቀን አይ ቲንክ ለአሥራ አንደኛ ክፍል የመጨረሻ ፈተና እያጠናን ይመስለኛል ኃይለኛ ገነናብ ይዘንብ ነበር ። ማንም ሰው ቤት ውስጥ አልነበረም ። እንዶ ነገሩ አጥንተን እንዶ ቀልድ ልፊያ ነገር ጀመርንና ሳናስበው ..." አለና የቀረችውን እምቦ ውሃ ብርጭቆ ውስጥ ጨምሮ እንድ ሁለቴ ተጮነጨ ።

ልባ ትር ትር ማለት የጀመረው ምስጢር ሳታስበው ፣ "እሺ ... ከዛስ?" ስትል ሳት አለ ።

"እንዴት ነው ልብ ሰተላ ባዘሽ ፣ የሚተዋለውን ነገ ብንገርሽስ?"

"ውይ በናትህ ... ዶክተር ሴላ ደግሞ ..." አለች ፣ ትዕግስቷ አልቀ በመቄነጥነጥ ።

"በታ እንቺ ይሄንን ዶክተር ተይ ብትባይ እምቢ አልሽ አይደል?"

@OLDBOOOKSPDF

"ውይ በናትህ፣ እኔ ዶክተር ሌላ ተስማምቶኛል። ይልት ቀጥልልኝ ከዛስ" አለች፣ እየተቁነጠነጠች።

"ከዛማ ... አንዳችን በሌላችን እትፍ ውስጥ ወደቅን። እንዳልኩሽ ከዚያ በፊት የተወሰኑ ቀናቶች ተሳስመን ...ተቃቅፈን እናውቃለን። ከዚያ ያለፈ ግን ሄደን አናውቅም ነበር። የዛን ለታው የተለየ ነበር። የውስባችን እሳተ ገሞራ ከቁጥር ውጪ ሆኖ ፈነዳ..." ሲል፣ ስሜቷ ነትቶ ራቷ በርቶና የልቧ ምት እየጋለበ ቀጥል በሚል ዓይነት ባይኖቿ ተማጸነችው። ከፊቷ ካለው ውሃ እንዲት ብርጭቆ ተጭነጪችና በገራ ጣቶቿ ጸጉሯን እንደማስተካከል አድርጋ እይን አይኑን ስታየው፣

"በቃ እዛችው የምናጠናበት ክፍል ውስጥ የተቀመጡትን ኬላዎች ሁሉ ጥበን ሄድን። ወይ አሷ ጮሃ ይሁን አላውቅም፣ ብቻ በዛ መሃል ገነትን የማይወዷት የረጅም ጊዜ የቤት ሠራተኞችን ከተፍ አይሉ መሰለሽ። ደግነቱ የሳሎኑ በር ገባ ሰሰ ነበር መግባት የቻሉት እኔ ክፍቼላቸው ነው። ግን ... ዩ ካን ኢማጂን፣ ሲሰርቅ እንደ ተያዘ ሌባ እኔም እሷም አንገታችንን አቀርቅረን ገባም አልን። ምን እንዳሉን አገሩም ታል ትገ አይለኝም።

"በኋላ ትንሽ ስንረጋጋ፣ እንደ ምንም ሽኝቼያት ተመለስኩ። ሰራተኞችን ያደረግነውን ያወቁብኝ ሰለ መሰለኝ ለእናቴ እንዳይነግሯት እንዴት እንደ ተማጸንኳቸው አትጠይቂኝ። በሕይወቴ እንደዛ ቀን ሰው ሰምኜ የማውቅ አይመስለኝም። ያለ ፕርፐር ለእናቴ ነግረዋታል። በጊዜው እናቴ እኔን ምንም ባትለኝም ገነት ለአንድ ወር ከኖ ቤት ስትጠፉ የት ጠፉች ወይ ምን ሆነች ብላ እንኳ አልጠየቀችኝም ነበር" ብሎ ከባሻገር የሚያውቋት ሰዎች ሰላም ስላሉት፣ ፈገግ ብሎ እጁን እወ.ለብልቦ እጸፉውን መለሰ። ፊቱን አሻሽቶ ወሬውን ሊቀጥል ሲል፣

"አባትህስ ምን አሉ?" አለች።

"ኦህ ሶሪ ... አልነገርኩሽም ለካ፣ እሱማ ገና አስረኛ ክፍል ስንገባ አካባቢ በሥራ ተቀይሮ አስመራ ሄዶ ነበር። እሱ ቢኖር ኖሮ ብዙ ነገር ሌላ መልክ ይይዝ ነበር። ኤኒ ዌይስ..." ብሎ ትንሽ ተከዘና ቀጠለ። "እንደ ነገርኩሽ፣ የሁለታችን መቀራረብ እናቴን በጣም ሳያሳስባት አልቀረም። ከዚያ በኋላ ገነት እኛ ቤት ለመምጣት ፈጽሞ እሻፈረኝ አለች። በደጅ ግን መገናኘታችንን ቀጥለን ነበር። በዚህ መሃል እኔን ከዛ ዘወር ማድረጉ እንደሚሻል እናቴና አሜሪካ ያለችው ታላት አጎቴ ሳይደልቁብኝ አልቀሩም።

"ትምህርት ቤት እንደተዘጋ ከረምቱ ሲጀምር ወደ አሜሪካ ለመሄድ የሚያስፈልገው ወረቀት ሁሉ ማለቁን ሲነገሩኝ ማመን አልቻልኩም። ሐምሌ አጋማሽ ላይ ወደ አሜሪካ እንደምሄድ ሲነገረኝ እኔም ገነትም ሰማይ የተደፋብን መሰለን። የመለያየት ፍርሃታችን ደግሞ የፍቅራችንን እሳት የባሰ እጋለው። ወደ አሜሪካ መሄጃው ጥቂት ቀን ሲቀረው ገነት ደብዘዋ ጠፋ።

"ውይ ... ምነው?" አለች ምስጢር ሳታስበው ድንግጥ ብላ።

"አላውቅም ... ደጋግሚ ቢታትው ብሄድም የሚያናግረኝ አላገኘሁም።

@OLDBOOOKSPDF

ለወትሮ እንደ ልሸቸው የሚወዱኝ እናቷ ባሎሩ የለችም ይሉኝና በደጅ ይመልሱኝ ጀመር። ሞንትላቱ ሊፈነዳብኝ ሆነ። ጠዋት ማታ እያለተስኩ ሳስቸግራቸው ከሳምንት በኋላ እንዲት ደብዳቤ ሰጡኝ። እሳቸውም እያስቀሱ ሁለተኛ ቢታቸው እገዘልመጣ ለምነው ሸኙኝ" አለና ጸጥ አለ። ፊቱን በግራ እጁ ደጋግሞ አሻሸና በረጅሙ ተነፈሰ።

"ምን ይላል ደብዳቤው?" ስትለው፣ የገንዘብ መያዣ ቦርሳውን እውጥቶ እንዲት ያረጀችና የተጣጠፈች ወረቀት እውጥቶ ሰጣት። በጥንቃቄና በፍጥነት ዘረጋጋቻትና ማንበብ ጀመረች። እሲ ሲትንብ እሱ ያስተናገዱቻቸውን ልጅ ጠርቶ ሻይ አዘዘ። በምልክት ሲጠይቃት ይቅርብኝ ብላ ደብዳቤውን ማንበቧን ተጠለች።

"ሌላነት ያለሁበት ሥቃይና ሕመም ካቅሜ በላይ ሰለ ሆነብኝ ላገኝህ አልችልም። ለምን ተገናኘን ብዙ አላማረርም። ለምን ጓደኛ ሆንን ብዙም አልኖሯም። መፋቀራችንም ስሕተት ነው ብዬ አላስብም። ምን ብዬ እንደምነግርህ ግን አላውቅም። ባንተ መሄድ ነፍሲ ስትሠቃይና የሚያጽናናኝ ነገር ሰፈልግ ልሸከማቸው ይቅርና ለመናገርና ሰማስብም የማልችላቸው ሁለት ከባድ ነገሮች ደረሱብኝ። አንተ ጸጸትም ሐዘንም እንዲደርስብህ አልፈልግም። እነሱ እንዳመጣብኝ እችለዋለሁ። ሁለቱንም ነገሮች በፍጹም ልነግርህ አልችልም። እንደምንም ብዬ ብችልም እንኳን አልፈልግም። መንገድህን በሰላም እንድትሄድ። እኔ ግን ሁልጊዜም ለምን? ለምን? ለምን? እንዳልኩ እኖራለሁ። ልትፈልገኝ አትምከር፣ ብትምከርም ልታገኘኝ አትችልም።

ግን እደራህን ቶሎ አትርሳኝ፣ እሺ ሌላነት። ከሁሉም ከሁሉም እንደምትረሳኝ ሳስብ ልቤን ያመኛል። እኔማ ልርሳህም ብል አልችልም። ሁልጊዜም እንተን ተሸክሚ እሠራለሁ፣ በየቀኑ አስብሃለሁ።

የኔንም ያንተንም ፋንታ እኔ አለቅሳለሁ። በቂ እምባ ስላለኝ አትጨነት፣ አታልቅስ። አልታሻ እንደሆንክ ስለማውቅ ታሳዝነኛለህ። የኔንም ያንተንም መክራ እኔ እሸከማለሁ። ከሁሉ ከባዱ ነገር ግን ለምን የሚለውን ጥያቄ መመለሱ ነው።

ግን ለምን?

መልካም ጉዞ። ደህና ሁን።

ያንተው ገኒት"

"የኔ እናት" አለች ባዘነ ድምጽ። ከደብዳቤው ላይ አይኗን ሳትነቅል እንባዋ አመለጣትና ባንድ እጇ ፊቷን ሸፈነች።

"እንዴ፣ ሼረ በፈጣሪ እስኪ ..." አለ፣ ነገሩ ቢያሳዝናትም እንደዚህ ትሆናለች ብሎ ፈጽሞ ሰላልጠበቀ።

"እሺ ... ከዛስ?" አለች፣ እንባዋን እየጠራረገች።

@OLDBOOOKSPDF

"ከዛማ አላስችል ብሎኝ በማግስቱ ተመልሼ ስሄድ ቤታቸው ተቀልፎ ደረሰኩኝ። ብጠይቅ ባስጠይቅ የሄዱበትን የሚነግረኝ እንኳ ሳላገኝ እንዲሁ ልቤ ተንጠልጥላ የተቀለፈ በራቸውም ሳይከፈት፣ በጥያቄ እንደ ተሞላሁ ወደ አሜሪካ ሄድኩ። ይሄው ደብዳቤዋ ብቻ እስከ ዛሬም ሳትለየኝ ከኔ ጋር አለች። እልፍ ጊዜ ደጋግሜ ባነባትም ዛሬም እንቀቅልሽ እንደ ሆነችብኝ አለች። እዚህ በመጣሁ ቀጥር ገንትን ለማገኘት ያላደረኩት ጥረት የለም። እስካሁን ግን ምንም ፍንጭ አላገኘሁም" ብሎ፣ በረጅሙ ተንፍሶ ዝም አለ።

"በጣም ይገርማል ... ደብዳቤዋ ግን በነዚህ ሁሉ ዓመታት ውስጥ እንዴት አልጠፉብህም ወይም ተቀዳዳ አላለቀችም? ሁልጊዜም ቦርሳህ ውስጥ ይዘሃት ነው የምትዞረው?" አለች፣ ሀዘንና መገረም ድብልቅልቅ ካለ ስሜት ጋር ውስጧን እያተራመሰው።

"ኮፒና ስካን አድርጌ ቀሪ አስቀምጫለሁ። በታ ኦሪጂናሉ ግን ከእኔ እንዲለየኝ አልፈለግሁም። አይ ዶኖ ለምን እንደሆነ ..." አሰና መረቀቷን ተቀበላት። በጥንቃቄ አጣጥፎ ከፊት ለፊቱ አስቀመጣት።

"ወይኔ ... ግን ምን ሆና ይሆን? የኔ ናት ስታሳዝን" አለች። ሌላው ያልጠበቀችው አይነት ሴላ ሰው መስሎ ታያት። ጠንካራውና ለሰው ሁሉ መልስ ያለው ሳይኪያትሪስት ሳይሆን ምስኪን በራሱ ጥያቄ የተሞላ ሆኖ አየችው። "ቆይ ግን ብታገኛትስ ... ማለቴ አሁን ብታገኛት ምን ታድርጋለህ?"

"ምን አደርጋለሁ ... ሁ...ህ ፍ...ፍ... ዚሊዮን ጥያቄዎች አሉኝ። እኔ እገኛ ሳገኛት ብቻ ይመስለኛል የማውቀው። መገመት አይቻልም" አለ፣ ሁለንተናው ግራ ገብቶት።

"እሺ እስከ ዛሬ እየጠበቀችህ ቢሆንስ ... ማለቴ ሳታገባ አንድ ቀን እገኛሃለሁ ብላ ተስፋ አድርጋ?"

ያላሰበው ጥያቄ ስለነበር፣ "እንዴ ... አብዶሻል እንዴ፣ የምናወራው እኮ ስለ ብዙ ዓመታት ታሪክ ነው። የታይታኒክ ታሪክ በይው። አይመስለኝም። ከሆነም ... ያው ያለሁበትን ሁኔታ እንግራታለሁዋ። ጥሩ ወንድምና እኅት የምንሆን ይመስለኛል" አለ፣ ከዓይነ ሥጋው ውጪ ያለውን ነገር በዓይነልቦናው ለማየት እየሞከረ።

"እኔ ግን ሳስበው ሳስበው ... የምታገኛት ይመስለኛል" ብላ፣ ጠረጴዛው ላይ ተጣጥፎ ወደ ተቀመጠው ደብዳቤ እያየች ፈገግ አለች።

"አይ አንቺ ... እስኪ እንዳፍሽ ያድርገው። ኤኒ ዌይስ ... ይሄንን ሁሉ የነገርኩሽ ሳስለትሰሽ አልነበረም። ላንቺ የነገርኩሽን ነገር ለንጹሕ ስነግራት ነገሩ ቢያሳዝናትም ገንትን ፍለጋ መነሣቴን በበጎ አላየችውም ነበር። በኋላ ላይ ሐሳቤ እንደማያስወጣና ይህንን ነገር ካልጀመሁ ሰላም እንደማያገኘኝ ስታውት እያንገራገረች ተስማማች።

"ባሁኑ የሄድኩ ጊዜ ያለችኝ ነገር ግን ውስጤን አውኮት ነበር። 'አንተ የልጅነት ፍቅረኛህን ፍለጋ ላይ ታች ስትል የኔ ሕይወት ተንጠልጥላ ልትቀር አትችልም። እኔም

@OLDBOOOKSPDF

ፍትሩን የሚያጋራኝን ቢጤዬን ያገኘሁ ይመስለኛል ። ደግሞ የልጅነት ፍትረኛህን ሳያሠን ልጅ እገር ፍትረኛ እንዳገኘህም ሰምቻለሁ ... ምናምን' ስትለኝ መጀመሪያ ተልጂን ነበር የመሰለኝ ። ምክንያቱም ንጹሕ እንደዛ በእሽሙር የምታስብና የምትናገር ልጅ አያያለችም ። እየቀየ ሳየው ግን ሁሉም ነገር የምሯን ነበር ። ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ መሆናቸው ቀደኖ ነበር የገባኝ" አለና ፊቱን በሁለት እጁ ሸፍኖ ጸጥ አለ ።

የምትለው ሰለ ጠፋባት "አልገባኝም" አለችና ፊቷ ሁሉ የጥያቄ ምልክት መሰለ ።

"ልክ ነሽ ፣ ምኑም አይገባም ። ለማንኛውም እንዳልኩሽ ባሁኑ የሄድኩ ጊዜ ያጋጠመኝን ነገር ፈጽሞ አልጠበቅሁትም ነበር ። ምን ማድረግ እንደ ነበረበኝ እንኳን አሳወትሁም ። ስለዚህ ያለችውን ሁሉ አድርጊላት ፣ የጠየቀችውን ፈጽሚላት ፣ ከፉም በነም ሳልናገር ቶሎ ወደ እዚህ ተመልሼ መምጣት ነበረብኝ ። አይ ገስ ... እሱም ይመስለኛል ያሰበችውና ያለችው ነገር ሁሉ እውነት እንዲመስላት ያደረገው ። እኔ የባሰ ብጥብጥ እንዳይፈጠር መሸሼ ነበር ። በሰንት ልመና መሰለሽ ፍቺውን ለጊዜው ለማዘግየት የተሰማማችው ። "

የሐሳብ ደረሰኙን ሊያነሳ እጁን ሲዘረጋ በፍጥነት ያዘችና ፣ "እስኪ እጅዎት ይረፍ ዶክተር ፣ ተጋባሃ ነህ ዛሬ ረሳኸው?" አለች በፈገግታ ።

ንጹሕ 'ልጅ እገር ፍትረኛ አግኝተሃል' ያለችው እሷን መሆኑን ሊነግራት አልፈለገም ። እንድም ትን ልቦናዋን ሊያቀሽሸው ስላልፈለገ ፣ ደግሞም ለንጹሕ ያላትን ትልቅ ፍቅር ስለሚያውቅ ። አብዛኞቹ ተስተናጋጆች ወጥተው ቤቱ ጭር እያለ ነው ። ሰዓቱ አራት ከሩብ ይላል ።

"ልጆቹስ ግን በናትህ?" አለች ፣ ፊቷ እንደገና በሐዘን እየጨለመ ።

"እም...ም ልጆቹን ...ምንም ማድረግ አልችልም ለጊዜው ። ያው ፍርድ ቤት ብንሄድም ለሷ ነው የሚሰጡት ። በዛ ላይ አትመም ልቡም የለኝም ከንጹሕ ጋር ፍርድ ቤት ለመቆም ። ለነርሱም ከሷው ጋር ቢቀዩ ነው የሚሻለው ። በቃ ራሴን ብቻ ነው ይገር የወጣሁት ። ለዛውም የእኔም ግማሹ የት እንዳለ አላወቅም ። የሆነ የማላውቀው ሌላ ሰው የሆንኩ ያህል ነው የሚሰማኝ"

"ሌላሠውማ ነህ ፣ ተጠራጠርክ እንዴ?" አለች ላት ብላ እይን አይኑን እያየች ። ጠረጴዛው ላይ ያለውን እጁን በእጇ መታ መታ እያረገችና ከሰልኳ ላይ ሰዓቷን እየት እያረገች ።

"ያውን እሰኪ" አለ ያዩገ ጢሙን እያሻሸ ። "እይ ቲንክ ፣ መንቀሳቀስ ሳይኖርብን እያተርም ። እንዳያመሽብሽ እንቺም ። " ለአስተናጋጇ የምትሰጠውን ጉርሻ አስቀርታ መልሷን ወሰደች ። የገንዘብ ቦርሳዋን ከዋናው ቦርሳ ከተተችና ተነሡ ።

"ሌላሠው አሉ ... ያለ ምክንያትም አልመሰለኝ ይዜንን ግራ የሚያጋባ ስም ያወጡልኝ"

@OLDBOOOKSPDF

"ስምን መላእክት ናቸው የሚያወጡት በሚለው ትስማማለህ ማለት ነው መላእክት ደግሞ አይሳሳቱም" ብላ ሳቱኝ አፏን ጠመም አድርጋ። ከንዴን ይዛ ሣግቶን እያስተካከለች ተና ብላ "ግን ማነው ስምህን ያወጣልህ?"

"የሻምቡው መልአክ ኮሎኔል ዲንሳ ናቸው። ከኔ የተለየ ታሪክ እንዲኖርህ ስለምፈልግ ነው ይሉኝ ነበር። እኔ እንጃ፣ ምን ዓይነት ሲላ ሰው ሆኜ እንደ ተገኘሁ በሆቴሉ ሰፊ ሶቢ መሀል አቋርጠው ወደ ውጪ ለመውጣት በገሞታ መራመድ ቀጠሉ። የሰውን ስም መልአክ ነው የሚያወጣው የሚለውን አባባል እያሰበ ያንዳንድ ሰዎችስም ትገ ሲለው ፈገግ አለ።

መኪናው ጋ ሲደርሱ በሩን ከፍታለት እንዲገባ ስትይገለት ሣት ብሎ፣ "እህኖት ኤ ጀንትል ሌዲይ! ራቱ ሳያንስኝ ደግሞ በር ተከፍቶልኝ ... ታንክ ዩ" ሲል፣ እየሣቀች ሠራ ገባችና ሞተሩን አስነሣች።

"ታው ታለህ፣ ብዙ ወንዶች ሴት በር ከፍታ ልታስገባቸው ብትሞክር ዘራፍነው የሚሉት። ኢቫን ተጋብዘው ሴት ስትከፍል የማይመቻቸው ወንዶች ብዙ ናቸው አለች፣ ዞር ብላ እያየችው።

"ለምን ልጄ ... በተከበሩ አካኪ ዘራፍ ማለት ...? ግን ደግሞ መቼም ታውቂያለሽ፣ አንዳንድ ሴቶችም ለነገር ብለው ከደረጉት ተሳልሳይሆን ይችላል። ለእኛ አገር ወንድ ደግሞ ነገሩ ለምን እንደሚከብድ መረዳት የሚያቅትሽ አይመስለኝም"

"አይ ባክህ ... የኛ አገር ወንድ፣ የሌላ አገር ወንድ የሚባለው አይገባኝም። ሴት ልጅ እጁ እስክትገባ የመኪና አይደለም የሰማይ በር ለመክፈት አይመለስም። ማስሪያ የሌለውን ጫማ ተፈታብሽ ካላሰርኩልሽ እያለ ሲያሸረግድ ይቀይና ልክ የፈለገውን ሲያገኝ ደግሞ ውኃ ተጠን አየር ወፈረ እያለ መላደብ ማመናጨት ይጀምራል። ላስበው ሴት ስትጋብዘው ወይም የሆነ ትንሽ ትዕቢቱን ነካ የምታደርግ ነገር ስታደርግለት በደስታ ወይ ቢያንስ በጸጋ የማይቀበል ወንድ ውስ አድሮ ያከብራታል ብዬ አላምንም"

"ነጥብሽ ይገባኛል። ግን ደግሞ ገና ነን፣ እንደ ማኅበረሰብ ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል። ከልጅነታቸው ወንድና ሴት ልጆቻችንን ከምናሳድግበት መንገድ ጀምሮ፣ ባህሉና ልማዱ የተጠላለፈበትን ማኅበራዊና ሥነልቦናዊ ገመድ መፍታት ቀላል አይመስለኝም" አለ፣ የተደመለ ስልክ መኖሩን ለማየት ስልኩን እያወጣ።

"ባለፈው፣ ከሲራክ ጋር ለቡና ስንወጣ እኔ ነበርኩ የነዳሁት። ልክ አሁን ላንተ እንዳደረኩት ከፍቼ ይገደለት ግባ ብለው፣ ዘራፍ አሻፈረኝ 'ምን መስዬ ታየሁሽ ብሎ እጣ-ፍ ት-ሙ-ት እምቢ አሻፈረኝ አለ። እኔማ ሥቱም አላባራሁ። እሱ ደግሞ የባስ አናደደው። ብቻ እንዲያው ትገ ሰላለኝ ነው" ብላ ሣቀች። ሲራክ አብሯቸው የሚሠራ ወጣት የአእምሮ ሕክምና ዶክተር ነው።

"ምን መስለሽ፣ ባህልና ልማድን መቀየር ቀላል አይደለም። ሁላችንም በጋራ ለገነባነው ልማድና የቀደመው ትውልድ ፈልሰር ሰጫንብን ወግ ባሮችና እስረኞች ነን"

@OLDBOOOKSPDF

አለ ፡ የመኪናውን ቁቢቶ እያጠበቀ ። በንገሩ ላይ ትንሽ ካወሩ በኋላ ከብሔራዊ እስከ ሚከሲኮ ድረስ ሁለቱም በየራሳቸው ሐሳብ ውስጥ ገብተው በጸጥታ ተዋጡ ።

" ስለዚህ ...ታዲያ ምን እያሰብክ ነው?" አለችው ድንገት ዞር ብላ ።

" ምን እያሰብኩ ነው? ምን የማላስበው ነገር አለ ብለሽ ነው ። ብዙ ነገሮች እኔን እየጠበቁ እንደሆነ እውቃለሁ ። አይ ዶኖ ፡ ምናልባት የመጨረሻ ውሳኔ ከማድረጌ በፊት ሁሉንም ነገር እንደገና ማየት ሳይኖርብኝ አይቀርም" አለ ከኪሱ ውስጥ የሚጮኸውን ስልክ እያወጣ ። "ኦህ እናቴ ናት መሰለኝ ... ቀይ አንጄ ልመልስላት" አለና ፡ በአሥር ደቂቃ ውስጥ ቤት እንደሚደርስ ነግሯቸው ዘጋው ። እናቱ እርሱ ቤት ካልገባ አይተኙም ። ዝርዝር ጉዳዩን ባያውቁም ትዳሩ ላይ ያለውን ችግር ከእህቱ ሰሰ ስሙ በሚኮቀት ተወጥረዋል ።

"ቀይ ግን ዶክተር ሌላ ... ነገትን ፈልገ ለማግኘት ንጹህንና ልጆችህን ማጣቱ ተገቢ ይመስልሃል? ማለቱ ... በንጹህም ቦታ ሆኜ ሳስበው ነገሩ ቀላል አይመስለኝም ። ይቅርታ ግን ... ያለህበት አጣብቂኝ ስለማይገባኝ አይደለም" ብላ ነዳጁን ስጠት አድርጋ ፍጥነቷን ጨመረች ።

"እኔ ኮ ነገትን አገኛለሁ ብዬ ስነሳ ንጹሕን አጣለሁ ብዬ አይደለም" ሲል ዞር ብላ ግራ በገባው ፊት በታየው ዝም አለ ። 'እውነት ታዲያ ምን ፈልጊ ነው?' አለ በውስጡ ። "እኔ የምፈልገው ነገትን በተመለከተ አንድ የሆነ ፍጻሜ ማግኘት ነው ... ይሄ ደግሞ ለምን ንጹሕን ሊያሳጣኝ እንደሚገባ ነው ያልተረዳሁት ። "

"እሺ ነገት ካልተገኘችስ? ወይም ብትገኝስ? ደግሞ ያባትህ እደራ ያለበትና በውስጥህ ታምቆ የኖረ ሀልምህና እዚህ ማድረግ የምትፈልገው ነገር ከነባሽው የግልህ ሀይወትና የኑሮህ አቅጣጫ ጋር ሲጋጭ ምርጫህ ምንድነው?" ስትለው ። ትክሻውን ሰብቶ እጁን ጨበጥ ለቀቅ እያደረገ ዝም አለ ።

"ዩ ኖው ሚስጥር ... አውን የኔ ሀይወት በሚገፋፉና በሚሳሳቡ ኃይለኛ ማግኔቶች መካከል እንዳለች ቁራጭ ብረት ግራና ቀኝ እየተንተቀተች ነው ። ለየትኛውም ጥያቄሽ መልሰም ሆነ ስሚት የሚሰጥ ማብራሪያ ማቅረብ አልችልም ። አውን ለምጓጓወተው የሕይወቴ መዚታ የተጻፈ ፍታና የተስተካከለ ትኝት የለኝም ። በታ ምን ልበልሽ ... አሰ አይደል ... ቀለም ባለቀበት ብዕር የምጽፍ ያህል ነው የሚሰማኝ ። " የምትመልስለት ስላልነበራት ዝም አለች ። የሌላሠው እናት ቤት ደጃፍ ሲደርሱ መኪናውን ዳር ላይ አቀመች ።

"በይ እስኪ ... በጣም መሽቷል ፡ ግቢም እትባይ ። በጣም በጣም ነው የማመሰግነው ። እንዴት ቅልል እንዳለኝ ... ያው የቴራፒ ሒሳቡን እዛው በክሊኒኩ በኩል እናወራርዳለን" ብሎ ቀለደና ወረደ ። እሷም ወርዳ ጥምጥም ብላ አቅሩ ተሰናበተችው ።

@OLDBOOOKSPDF

"እኔም በጣም ደስ ብሎኛል። አይዞህ ... ሁሉም ነገር በጊዜው ይፈታል፡ ለሁሉም የራሱ መንገድ አለው። 'ጊዜ የማይፈታው ቋጠሮና የማያስረሳው እርር የለም' ትል የለ ራስህ" አለች። ወደ መኪናዋ ገብታ አዞረችውና መብራቱን ወደ ፊ አብርታ ቀመች። በሩ ሲከፈትለት እጁን አውለብልባ ወደ ሻከርስ ተፈተለከች።

@OLDBOOOKSPDF

ክፍል ፪

ድልድይ

@OLDBOOOKSPDF

3

ሴላሠው በእውሮላኑ ውስጥ ሰውነቱን እያፍታታ ወዲያ ወዲህ ሲል ቶየ፣ እንቅልፍ እንዲወስደው ፊቱን ሸፋፍኖ ደገፍ ብሎ ተቀመጠ። ረዳት አብራሪው "አዲስ አበባ ለመድረስ የቀረን አምስት ሰአታት ሲሆኑ የምንደርስውም ጠዋት እንደ ሰዓት ከሩብ አካባቢ ነው። የአዲስ አበባ የአየር ሁኔታ ..." እያለ የጉዞ መግለጫ ሲሰኖ 'ኡፍ ... ገና ...' አለ ለራሱ። አብዛኛው መገደኛ በየወንበሩ ላይ ያሸለበው ይመስላል። ባለቤቱ ንጹህና ሁለቱ መንትያ ልጆቹ ግን ለሽ ብለዋል።

አምስቱን ሰዓት ቶሎ ለመጪረስ ጊዜም እንደ ቦታ በወደዱት አቅጣጫ ሰንጥቀው የሚሄዱት አውነታ ቢሆን ብሎ ተመኘ። የጊዜ ላይ ጉዞ በተወሰነ ፍጥነትያንድኾነ የወደፊት ብቻ መሆኑን ሲያስብ ሰው መሆን፣ የጊዜ እስረኛ መሆን ነው ብሎ ደመደመ። በጊዜ ጉዳይ ያለውን ሃሳብ እያሰፋና እያጠበበ ሲያወጣ ሲያወርድ ቀየ።

'ጊዜ የዘላለም አሽከር ሲሆን፣ ሰው ደግሞ የጊዜ ባሪያ ነው። ሰው ጊዜን በደቂቃና በሰዓት፣ በወራትና በዓመታት ሸንሽኖ፣ ከግድግዳው ላይ ሰቅሎ በአጹ ላይ ጠፍሮ ሊገዛው ሲቀጣጠረው ይሞክራል። ጊዜ ደግሞ ሰውን ከልጅነት ወደ ወጣትነት፣ ከጉልምስና ወደ እርጅና እያስለፈለፈ ከሞት ደጃፍ ያደርስና መቃብር ይጨምረዋል። በዘረፍትና በበጋ፣ በጸደይና በመጸው እየተመሰለ መልኩን እየቀያየረ ሲመጣና ሲሄድ፣ ሲዞርና ሲፈራረቅ፣ ... የጊዜ ጉዞ ያዙሪት እንጂ የወደፊት አይመስልም። በድል ፈረስ ላይ ተቀናጦ በስኬትና በውድቀት፣ በቁጠሮና በድንገት፣ በጥበቃና በጥድፊያ ተጠቅኖ የሰውን ዕጣ ፈንታ የሚወስን ጊዜ መሆኑን በቀላሉ እንዘነጋለን። ጊዜን መግዛት ሲባል ራሰን እንጂ ጊዜን ማሰገዛት አይደለም።

'በጊዜ ውስጥ ትናንት የትዝታ፣ ነገ ደግሞ የተስፋ ጎተራ ናቸው። ከመለስ ትናንት ... ያልመጣ ነገ ይሻላል። በእጅ ያለ ዛሬ ግን ከሁሉም ይበልጣል። ዛሬ ሁሉም ያለ እየመሰለ የማይያገም ... ተመልሶም የማይመጣ ... ላንድ አፍታ ለትጽበት ታይቶ ጸርቃ ከሌለው የዘላለም ጠራር ገብቶ የሚሰወር ... በትናንትና በነገ መሃል የተሸነቆረ

@OLDBOOOKSPDF

እንቶ ነው ። የዛሬ ምስጢሩና ጥልቁ ያለው ደግሞ 'አሁን' ላይ ነው ። 'ትድም' እና 'በኋላ' ግን ያለቦታቸው ዛሬ ውስጥ የተደነቱሩ የትናንትናና የነገ ሽርፍራፊዎች ናቸው ።

'የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑ ጨቅላ ሕፃናት ካልተነካ ቁጣ ዕድሚያቸው ሳይ ብዙ ዛሬዎች መና ከሞሉ በስተመጨረሻ በአጸት የተሞላ እርጅና ኩሲ መሆናቸው አይቀርም ። የልጅነት ጨዋታ ፣ የመጣትነት ፍትር ፣ የጥልምስና ስኬትና የእርጅና ሞገስ በዋናነት የዛሬ ዕድል ፍሬዎች እንጂ የነገ ተስፋ ወይም የትናንት ትዝታ ውጤቶች አይደሉም ። '

ከተሳፈረበት ሃሳብ ሲወጣ 'ጊዜም እንደቦታ ደርዘ ብዙ የህይወት እውነታ ነው' የሚል ባንድ መጽሀፍ ላይ ያነበበው ድንት አረፍተ ነገር ትዝ አለው ። ሃሳብ እንዱ በጊዜ ውስጥ ወዲያ ወዲህ የሚያሳጥዘን እውሮፕላን መሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ በራለት ። ቀና ብሎ ትንሽ ተንጠራራ ። አሁንም በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ያሉትን ሚስቱንና ልጆቹን አየና 'አሃ ... ሁለተኛው በጊዜ ውስጥ መንሸራሸሪያ እውሮፕላን ደግሞ እንቅልፍ መሆኑ ነው' ብሎ ፈገግ አለ ። ሰው በምናቡና በራእዩ በጊዜ ውስጥ ወደ ፊት ይጓዛል ። በትዝታውና በትውስታው ደግሞ ወደ ኋላ ሊንጉድ ይችላል ።

ከብዙ ማግባባትና ማሳመን በኋላ ነበር ባለቤቱ ንጹሕ ልጆቹን ይዘው ወደ ሀገር ቤት ለሦስት ወር እረፍት በመምጣታቸው የተስማማችው ። በልጅነቷ ከሃገር ቤት ከወጣች በኋላ ላጭር ጊዜ ከወላጆቿ ጋር ካልሆነ መጥታም አታውቅም ። የመጨረሻ ጉዞዋ ከአስራ አምስት አመት በፊት ነበር ። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ይሰሩ ከነበሩ አባታቸው ጋር ካገር አገር ሲጓዙ ስላደጉ ፣ ምንም አይነት ረጅም ጉዞ አትወድም ። ወደ አዲስ አበባ ለመድረስ ሲታሪቡ የአውሮፕላኑ የውስጥ መብራት ሲበራ ነቃች ።

"ደረስን እንዴ ሌላዬ?" አለች አይኗን እያሻሸች ፊቷ ላይ ጣል ያደረገችውን ያንገት ልብስ አጣጥፋ ከጎኗ እያስተመጠች ።

"ኦልሞስት ... አንድ ሰዓት ነው የቀረን ፣ ትንሽ ተኛሽ?"

"ያ ... እንዴ ነገሩ ... ያውሮፕላን ውስጥ እንቅልፍና ምግብ እኮ ..." ብላ ሳት ስትል ፣ እጁን እያሻሸ ፈገግ አለ ። ብዙም ሳይቆይ ልጆቹም ነቁ ። ለፊት ማጽጃ የሞቀ ርጣ ሲሰር እሷ ልጆቹን ይዛ ወደ መጸዳጃ ክፍሉ አመራች ። አውሮፕላኑ መሬት ሲነካ መንገደኛው ጭብጨባና እልልታውን አቀለጠው ። ነገሩ ባይገባቸውም ልጆቹም አብረው እያጨበጨቡ ሥሁ ። ነገሩ ግራ ያጋባት ንጹህ 'ምንድነው በሚል' ጥያቄ የተሞላው ፊት ስታየው

"ከሰማይ መውረድ ቀላል ነገር ነው እንዴ?" ብሎ ሲስቅ ፣ ቀልዱን እንደሆነ ገብቷት ፣

"የምር ..." አለችው ።

"የእርይታ ይሁን የደስታ ... የምስጋና ይሁን የአድናቆት እኔም አይገባኝም ። ስሜቱን ግን አልጠላውም" አለ ፣ የልጆቹን ልብስ እያስተካከለና የእጅ ሻንጣዎቻቸውን ከራስ በላይ ማስተመጫዎቹ ውስጥ እያወጣ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ነጋ ማለት ነው?"

"ያመሰላል" አላት ፣ በረጅሙ እያዛጋ ።

"ወይኔ ... ካሁኑ አሜሪካ ናፈቀችኝ" ስትል ፣ ከጆርባዋ ያሉ ሽምገሌ ያሉ ሰውዬ ሽንቀጥ በሚያደርግ እይታ ገረመሚትና ቁንጥላታቸውን አወላወሰ ።

"ከሶስት ወር በኋላ ስንመለስ ደግሞ 'መቹ ነው ኢትዮጵያ የምንመለሰው ... ገና ሳልሄድ ናፈቀችኝ' ማለትሽ አይቀርም ።" የኢሚግሬሽን መስከቶቹንና የገምሩክ ፍተሻውን አልፈው ሲወጡ ድካምና ግራ መጋባቷ ፊቷ ላይ ይነበብ ነበር ። የሁለቱን ልጆች እጅ ይዞ ከፊቷ የሚሄደውን ሊላሠውን እያየች ከጎኗ አቃቸውን የሚገፋውን ወጣት በተስላቸ ድምጽ ፣ "ሊላም ፍተሻ አለ እንዴ?" ስትለው ፣

"እሩ በቃ ... የሚመስጻችሁ መኪና አላችሁ?" አለ ፣ ዞር ብሎ ከሳይ እሰከቃች እያጤናት ። ካነጋገሯና ከጥያቄዋ ለረጅም ጊዜ ውጪ የኖረች መሆኗ ገብቶታል ።

አሮጌ አየር ማረፊያ ሰፈር የሚገኘው የሊላሠው እናት ቤት ነው ያረፉት ። ቤቱ ሰፊና ሁሉም ነገሩ የተሟላ ስለሆነ በቲ ምኞት አለው ። ንጹሕ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት ምንም ሳትደሰት ጊዜው እንደዋዛ አለፈ ። የእንቅልፍ መዛባቱ ፣ የምግቡ ለውጥ ፣ የልጆቹ ጤና ማጣትና መሰላቸትን ጨምሮ ብዙ ነገር አታከታታል ። ሊላሠው ደግሞ ብዙም ሳይቆይ ጳውሎስ ሆስፒታል ገብቶ መስራት ስለጀመረ ብቸኝነቱም አልገፋ ብሳታል ። ቀስ በቀስ ጓደኞች ስታፈራና ወጣ ወጣ ማለት ስትጀምር ትንሽ ቀለል አላት ። ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ እንኳን ለኖርባት የሚመጣባት ሀገርም ሆና አልተዋጠችላትም ። የሊላሠውና የልጆቹ ደስተኛነት ለምስጢር ፈጽሞ ሊገባት አልቻለም ።

'ደስታ በሁሉም ቦታና ጊዜ ሊፈጥሩ የሚችሉት ነገር ነው ወይስ ቦታና ጊዜ እየመረጠ የሚነሰት እድል? ሰው በምርጫው ደስተኛ የመሆን ነጻነት አለው ወይስ ደስታ እንዳሻው የሚነሰት የእድለኞች እጣ ፈንታ ነው?' ለሚሉና መሰል በውስዉ ለተፈጠሩ ጥያቄዎች መልስ አላገኘችም ። 'በቀላሉ የሚደሰቱ ... በሁሉም ቦታና ሁኔታ ደስተኛ መሆን የሚችሉ የተባረኩና የሚተናገቸው ሰዎች ናቸው' ብላ አሰበች ። 'ደስታ የኑሮ ምኞት ውጤት ነው ወይስ የሕይወት የትርጉም ፍሬ? ለመደሰት የፈለግነውን ሁሉ ማግኘት ያስፈልገናል ወይስ የሚያስፈልገንን ነገር መረዳትና ያለንበትን ሁኔታ የመቀበል ጸጋ ይበቃል? ደስተኛ ለመሆን ፈለገች ።

@OLDBOOOKSPDF

ክፍል ፫

ሰዎቹ

@OLDBOOOKSPDF

፡ 4 ፡

የጠዋቱ ጫጫታ ጋብ ያለለት ክሊኒክ፣ ድንገት አንዳች መለት እንደ መጣበት ድብልቅልቁ ወጣ። በደማቁ የምትጮህ አንዲት ሴትና በዛ ያሉ አሻቢ ድምፆች የፈጠሩት ሁከት የሁሉንም ቀልብ ሰቢል። የጳውሎስ ሆስፒታል የአእምሮ ሕክምና ክሊኒክ ዕለ የውስጥ ግድግዳ አንኳን አንባርቀው በት ወትሮውንም ድምፅ የመከላከል አቅሙ እገዛ ነገሩ ነው። ክሊኒኩ ከዋናው ሆስፒታል በስተጥዋሮ ወሽት ብሎ ይገኛል። እንጻያለር ያህል ከተራረፈ ዕታ የተሠራ ይመስላል። ዓይንና ጥርስ፣ ጆሮና ጉሮሮን ጨምሮ አእምሮና ካንገት በላይ ያሉ አካላት መታከሚያ ክፍሎች የሚገኙት በዚችው እንስቶኝ የሆስፒሊታሉ ምራቂ ቤት ውስጥ ነው። ካንገት በላይ ላለ ስውር ሕመም ሽገጥ ያልቸ ቦታ መች አነሰችው ስማለት ይመስላል።

ጠዋት ረፋዱ ላይ ከሰው ብዛት የተነሳ በቢሮዎቹ መካከል ባለችው ጠባቧ ኮሪደር መተላለፉም ሞንት ነው። ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሰው ተስተናጋጅ እስታግሚና አሻቢ ነው። እንዳንዴ ጥቂት በከፍተኛ ደረጃ የታመመው የአእምሮ ሕመምተኞች ካሉ፣ አካባቢው በእሪታና በሁካታ ቀውጢ ይሆናል። ከቀኑ ስድስት ሰዓት ከመሆ በፊት አብዛኛው ሕመምተኛ ታክሞ ወደ የቤቱ ስለሚሄድ ሁሉም ነገር እንደገና ያ ረጭ ይላል። በዚያ ሰአት ወዲያ ወዲህ ውር ውር የሚሉት የጽዳትና የካርድ ክፍል ሠራተኞች ካልሆኑ እምብዛም ሰው አይኖርም።

ሌላው ቢሮው ውስጥ ሲያያቸው የቆዩትን በዕድሜ ጠና ያሉ ሕመምተኛ ለማሰናበት በሩን ሲከፍት፣ ከደጅ የቀለጠው የጨነት ወላፈን ጆሮ ግንዱን ገረፈው፣ የክሊኒኩ ጋላፊ ነርስ ወደ እርሱ እየመጣች ስለ ነበር ተከታትለው ወደ ቢሮው ገቡ።

"ምንድነው ጫጫታው፣ ሲስተር?" አለ፣ በሩን እየዘጋ ፊቱን ወደ እርሷ መለስ።

"ምን ሰላም አለ ብለህ ነው፣ ዶክተር። ፖሊሶች አንዲት አስቸጋሪ ሳይኮቲክ ህመምተኛ አምጥተው ከቀጥጥር ውጪ ሆናብናለች። ሐኪሞቹ ሁሉ ስብሰባ ብለው ቀደም ብለው ወጥተዋል። ነፍሰ ጡር ስለ ሆነች ሳትታይ መድኃኒት ለሰጣት

@OLDBOOOKSPDF

አለፈለጉም ። እንዲያው ባዘዘ ብታይለን ብዬ ነበር " አለች ፣ ተልፃ ከውጭ ባለው ሚጫታ እንደ ተሰረቀ ።

"ምንም ችግር የለም ፣ አያታለው ። ከዚህ በፊት እዚህ የታየች ሕመምተኛ ናት እንዴ? " አለ ፣ ጠረጴዛው ላይ የተበታተኑትን የሀመምተኛ ካርዶች ለማበተካከል እየሰበሰበ ።

"አዩ ... እኔ እንኳ ፣ እዚህ እንኳ ታይታ የምታውቅ አይመስለኝም ። ግን ከርኒከ ነገር ናት ። የለየላት ጨርቂን ጥላ ጉዳና ላይ የወጣች ዓይነት ትመስላለች ። መንገድ ላይ የቀሙ መኪናች መስተዋት ሰባብራ መሰለኝ ፖሊስ ጣቢያ አሳድረዋት ሲያት ታቸው ወደዚህ ያመጧት ። በዛ ላይ ደግሞ ድርስ ነፍሰ ጡር ናት ። አይ ዘንድሮ እንዲያው ሴት መሆን ። አሁን እንዲያው በፈጣሪ ... ካልጠፋ ሴት ይቺን ምን ብለው ነው? ዘንድሮ ወንዱም እንሰሳ ሆነ መሰል ልጄ ። ምን ዓይነት ዘመን ላይ ደረስን አውንስ ፣" አለች ፣ በመንገሽገሽ ራቷን አጨራምታ ።

ዕድሜዋ ለሰድሳ ብዙም ያልቀረው ሲስተር ዘሪባ ለብዙ ዓመታት በአማኑኤል ከባም በጻውሎስ ሆስፒታል ሠርታለች ። በልምድም በእውቀትም ከያረጹና ሙያውን አውንም በፍትር ከሚሠሩ ጥቂት የቀዩ ነርሶች አንዷ ናት ። የምታደርጋት ጥቁር ባላሰግያዊ ፍራም ተሜን የእይታ መነጽርና ሁል ጊዜም የማይለያት ነጭ ሂጃብ ከጠይም ከብ ራቷ ጋር የተጣጣመ ነው ። የምትነግረውን እያጻመጠ ያያቸውን ካርዶች ባንድ ላይ ቸለላቸው ።

"ምን ታደርጊዋለሽ ... ሰጪ ብቻ ሳይሆን ጊዜውም ነው ያበደ የሚመስለው ። መንገድ ላይ ለሚኖር ሰው ደግሞ መቼም ቢሆን ሕይወት እብድት ናት ። ቀይ ፖሊሶቹስ ቢሆኑ አያስቡም እንዴ? እንደዚህ የተረበሸች ከሆነች መጀመሪያውንስ እንዴት ወደ ፖሊስ ጣቢያ መሰደው ያሳድሯታል? ምንም ቤተሰብ የላትም ማለት ነው!" አለ ፣ በውሰጡ ሀመምተኛዋን እንዴት ብሎ እንደሚያናግራት እያሰበ ።

"አይ ዶክተር ... አንተ ባሜሪካው እያስብክ ነው ። እዚህ አገር እኮ ብዙም ሙላ ያለው ነገር የለም ። በቤተሰብም መፍረድ ይከብዳል ። ያንንም ይሄንንም ብሎ ብሎ ሲያትተው በታ በየመንገዱ ወድቀው ይቀራሉ ። ፖሊሶቹስ ቢሆኑ ከሌላው ሰው በምን ይሰያሉ ብለህ ነው ። የተለየ ትምህርት ካልተሰጣቸው ምኑን ያውቁታል! እንዲያው ተወኝ ባክህ ፣ ሁሉም በያመ ነፍስ ነው" ብላ ፣ ውጪ ያለው ሚጫታ ሲካሪር ተከታትለው ወጡ ።

ካልሄድኩ እያለች ከፖሊሶቹ ጋር ከምትጥሞተተው ረጅም ቀጭን ቴት ጋር ራት ለራት ተጋፍጠው ባሰብት ቀሙ ። ሆኗ ተቀብትቶ ነፍሰ ጡርነቷን ያሳብቃል ። ተሸራርቦ ወደ ብዙ አቅጣጫ እንደ ቀንድ የተገጨበረረው ጸጉሯና እንቅልፍ ሳይዞርባቸው የከረሙ በርበሬ የመሰሉ ሕያወት አልባ ዓይኖቿ ጋኔናች ሰከረው ሲጨፍሩባት ያዩሪች አስመስሏታል ። ብዙ ከመሥውጥ የተነሣ የተዘጋው ድምፅዋ ጉሮንና በፍጥነት ሲታወራ የምትሰውን ለመረዳት አሰቸጋሪ ነው ። የሆነ ነገር ትለፈለፍ ትለፈለፍና ደግሞ ዝም ብላ አየሩ ላይ እፍጥጣ ከቀየች በውዋላ ድንገት ትሙሃለች ።

@OLDBOOOKSPDF

"ብር ያለው ደደብ ... ደደብ ሁላ ... ብር ብቻ ... ደደብ የያዘው ብር! የደደብ ብር... ገሞ ብሎ መብረር ... ብር ብርት መስሎሻል ... ብ-ር ማለት የዱ-ብ ከ-ብር ነው" ትልና እጁን ከፖሊሶቹ ለማስለቀቅ ጮትታ ጮትታ ሲያቅታት "ኡ ኡ ኡ!" ብላ፣ እሪታዋን ታስነካዋለች። ይዘዋት ከመጡት ፖሊሶች አንደኛው ትዝት ባለው ድምፅ፣

"ኧረ ጮበሻ እስኪ አንድ በሉን፣ ነትማችን በላይ ሆናለች" አለና ትከሻው ላይ ልትነክሰው በትሞክር የተወችውን በምራት የራስ የአፍ ምልክት አሳያቸው። ከአእምሮዋ መታወክ የተነሣ ሊያነጋግራት እንደማይችል የተገነዘበው ሌላው ድምፁን ከፍ አድርጎ፣

"ኪስተር መመርመሪያ አልጋ ያለበት ክፍል ብናስገባትስ? መድኃኒት ከተሰጣት በኋላ መተኛቷአይተርም። በዚህ ሁኔታዋ ምንም ልናናግራት የምንችል አይመስለኝም። የኦክተር ምስክር ቢሮ ክፍት ነው እንዴ?" አለ፣ አውንም ዓይኖቹን ከሕመምተኛዋ ላይ ሳያነሳ።

"እውነትህን ነው ልጄ፣ ትንሽ ሰፋ ስለሚልም እዛ ይሻላል መሰል። ታዲያ ምን አስብዘ? ኢንጄክሽን ላዘጋጅ እንዴ?" አለች፣ ፖሊሶቹን ወደ ቢሮው እየመራቻቸውና በሩን ለመክፈት ከቁልፎቿ መሃል ለመምረጥ እየሞከረች።

"ጥሩ ... እኔ እስከማያት ለምን 100 ሚሊግራም ሳሮጋከቲል አታዘጋጂላትም" አለ፣ አልሄድ ብላ መለሰ ላይ የምትንፏቀቀውን ሕመምተኛ ወደ ክፍሉ ለማስገባት የሚገትቷትን ፖሊሶች ለማገዝ እየሞከረ። ሌሎች ሁለት የጽዳት ሠራተኞች ተጨምረው ከግራና ከቀኝ ይዘዋት ክፍሉ መሀል ካለው አንዱ መቀመጫ ላይ ሊያስቀምጧት ሞከሩ። እንዴት ብሎ የምርመራ ጥያቄውን እንደሚጅምር እያሰበ ከሕመምተኛዋ ፊት ለፊት ካለው የጠረጴዛ ጠርዝ ላይ ድግፍ ብሎ እንደ መቀመጥ አለ። የተበጫጨቀ ራቷ ግርጣቱና እድፉ ተደራርበበት በደሀና ቀን የፊቷ ቀለም ምን ይመስል እንደ ነበር ለመገመት አዳጋች አድርጎታል።

እግሮቿን አመናጭራ ስትቀመጥ እርቃኗ በክፈል ተገለጠ። አጠገቧ ከቀሙት የጽዳት ሠራተኞች አንዲ ተሚሲን ልታለብሳት ስትሞክር ዓይኖቿን እያጥረገረገች ስትሥሀበት ደንግጣ እጇን አሳት እንደ ነካ ሀጻን ሰበሰበች። ወደ ሌላው ትዝ ብላ ስታየው ቀየችና ድንገት "ብር ያለው ደደብ" ብላ ስትረጭሀበት እሱም ከው አለ። ቀኝ እግሯን አመናጭሩ ልትረግጠው ስትል በፍጥንት ዞር ብሎ ስትነሽ ሳተችው። ሜማ ከገባቸው የቀዩ እግሮቿ እስከ ቁርጭምጭሚቷ በላይ ድረስ አፏራ ጠገቦዋል። በእንቅሩት የተወለጋገዱት የእግር ጣቶቿ ጥፍሮች ያለ ቅጥ እድገው የጹር እሾህ መስለዋል። አሀና እዚህ የተበጫጨቀው ቀሚሷ እድፍ ጠገቦ የፋብሪካ ቀለሙን ለመገመት እንኳ አይቻልም።

ድንገት ብድግ ብላ ወደ በሩ ለመሮጥ ስትንደረደር ጥቂት ጸጥ ብሎ የነበረው ክፍል እንደገና ተረበሸ። አሲን መደ በታዋ ለመመሰስ በተፈጠረው ርብርብና ትግል የረፋዱ ዐሐይ ያሞቃት ቢሮ የባስ ታመቀች። በግብግቡ ሳቢያ ከየሰጪ ሰውነትና ሥጋ እየተነ የወጣው ጠንካራ ጠረን ሉ[illegible]ሚስተር ዘቢባ ያዘጋጀችውን

መርፈ ባንድ እጁ ይባ በሩን ከፍታ ስትገባ የታመቀው ክፍል ሽታ ገፍትሮ ሊጥላት ነበር ። ፊቷን ሞምድድ አድርጋ ፣

"ውይ ውይ ምነው? እንዴት ታፍኗል ከፍሉ ልጄ ... ኧረ መስኮቱን ክፈቺው እስኪ ዘነብ" አለች ፣ በመስኮቱ በኩል ያለችውን የጽዳት ሠራተኛ ። የተዘጋጀውን መርፈ በሊስተር ዘቢባ እጅ ስታይ በጨከትና በመወራጨት ሊያሳር ለክልካይ አስቸገረች ። እንደ ምንም ተባብረው ይዘዋት ረጋ ስትልላቸው ከቀኝ ታፋዋ ላይ ተወጋች ። እንድ አምስት አሥር ደቂቃ እየተወራጨች ፣ የሆነ ያልሆነውን መቀባጠሯን ቀጠለች ። ከዋቂት ደቂቃ በኋላ መድኃኒቱ መሥራት ሲጀምር ፣ ትንሽ ቅዝዝ ብላ ቀይታ እንደ ማንቀላፋት ስትል ተጋገዘው የመመርመሪያ አልጋው ላይ በትክክል አስተኟት ። ፖሊሶቹም አጠገባቸው ባገኙት መንበር ላይ ቁጭ ቁጭ ብለው በረጅሙ ተነፈሱ ። የጽዳት ሠራተኞቹ ደግሞ የሆነ ነገር እያጉተመተሙ ሹልክ ሹልክ እያሉ ወጡ ። ሲስተር ዘቢባ እንዴ ፖሊሶቹን እንዴ ሌላውን እያየች ፣

"ዶክተር ፣ ካርዴ እስኪመጣልህ ከፖሊሶቹም ቢሆን የቻልከውን ያህል ሂስትሪ ውሰዳ ። አልጋ ከተገኘ አማኑኤል ማስተኛት ሳይኖርብን ይቀራል ብሰህ ነው? እንዲህ ሆኖ መቼም ወደ እስር ቤት ወይ እንደገና ወደ ጦዳና መመለስ የምትችል አይመስለኝም ። ተመልሳ ሳትነቃብን ቶሎ ብለን የሚደረገውን ማድረግ አለብን" ብላ ፣ ለመውጣት በሩ ላይ ከደረሰች በኋላ መለስ ብላ ፣ "ውይ የኔ ነገር ረስቼው ፣ የሚጠብቁህ ሰዎች አሉና ፣ ለሰው ልትጠራቸው ወይስ? ከትትል ናቸው መሰለኝ ፣ የምሳ ሰዓትህም እዚሁ መቃጠሉ ነው እኮ" ስትል ፣ ሰዓቱን እየት እያደረገና ፣

" ኧረ ግድየለም ፣ አለኝ ትንሽ ሰዓት ፣ እስካሁን ጠብቀው'ኝማ እያቸዋለሁ ። ብቻ ትንሽ ይታገሱኝ ፣ ንገረያቸው" አላት ። ለሽ ብላ ወደምታንዘራፋዋ ሕመምተኛ እያየ ።

"ኧ...ረ እነሱማ በደስታ ይጠብቁሃል ። ያው የሚሆነውን እያዩ አይደል? ውይ አላምድሊላሂ ... እ...ን...ዴ ሰላም ወረዱ እኮ ። እንዲያው ላርጋዘቲልን የፈጠረ እጅ! በእውነት አላህ ዘርማንዘሩን ይባርክ" አለች ። መድሃኒቱ ባይኖር ምን ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ፣ ተንፈስ ብላ ከዘፍሉ ወጣች ።

በሚቀጥሉት አሥር ደቂቃዎች ፖሊሶቹ የሚያውቁትን ሁሉ ነገሩት ። ካርዱ ላይ ማስታወሻውን ሣር ሣር እደረገና ሕመሚ 'ስኪዞፍሬኒያ' መሆኑን አሰፍሮ መጥሯት እንዳሰባት ውሳኔውን ጻፈ ። ወደ አማኑኤል የምትተላለፍበትን መሸኛ ቅጽ ሞልቶ ካርዴ ውስጥ አስቀመጠ ። ፖሊሶቹ እንደ ነገሩት ከሆነ ኦሊምፒያ አካባቢ ሁሌም የማትጠፉ 'ኡብድ' ስትሆን ሰሞኑን ግን ሕመሚ ብዶባት ነበር የከረመችው ።

ከአንድ ቀን በፊት ወደ ፖሰት የሚጠጉ የቅሙ መኪኖች መስተዋት ሰባብራ ነው ፖሊስ ማቢያ ወስደው ያሳድሯት ። አስር ቤቱ ውስጥ ከሁዋዋር ውጪ ሆና የሚያደርጉት ሲጠፋባቸው እንጸመፀት ነገሩት ። ያነባቢው ሰዎች ዝናሽ ብለው እንደሚጠሯት ብቻ እንኺ ስለ አርሷም ሆነ ስለ ቤተሰቧ ሌላ ምንም እንደማያውቁ አስረዱት ። ተኝታ

@OLDBOOOKSPDF

መታከም እንዳለባት ነግሯቸው ወደ አማኑኤል የሚወስዳት ትራንስፖርት እስኪመቻች እነርሱ እየጠበቋት ሊቀየ ተስማሙ ።

ዝናሽን ከፖሊሶቹ ጋር ትቶ ወደ ራሱ ቢሮ ሄደና የቀሩትን ሕመምተኞች ማየቱን ቀጠለ ። የመጪረሻ ሕመምተኛውን አስናብቶ ሲቀመጥ ፣ ባለቤቱ ጎኡሕ ደጋግማ መደወሏን ተመለከተ ። አገቷ ጋ የነበራቸው የምሳ ቀጠሮ ገና አሁን ትዝ አለው ። አጭር የሃኪም ማስታወሻውን ካርዱ ላይ እየጻፈ ሲደውልላት ወዲያው አነሳችና "ሴላ ... በሰላም ነው? ሥራ በዛ እንዴ?" አለች ፣ ረጋ ባለ ለስላሳ ድምፅዋ ።

"ሰላም ነው ፍቅር ፣ ያው ታውቂው የለ ። የሚገርምሽ ምሳውን ኦልምስት ረስቼው ነበር ። አንድ በጣም የተረበሸች ሕመምተኛ ባለቀ ሰዓት ፖሊሶች አምጥተዋት እሷን ስናይ ብዙ ጊዜ ወሰደብኝ ። አሁን ግን ኦልምስት ጨርሻለሁ ፣ ትንሽነው የቀረኝ ። ብዙም አልቀይ እወጣለሁ" አለ ፣ አስክርቢቶውን በጣቶቹ መሃል እያሽከረከረ ።

"ታዲያ የምትዶርስ ይመስልሃል? አገቴ ደጋግሞ እየደወለ ነው ። ታውቀው የለ እሱን ። ብዙ ሰው ሳይጠራ አይቀርም ። ትንሹ ልጁም ዛሬ ማታ ወደ ለንደን ትመለሳለች መሰለኝ" ሰትል ፣ ከወንበሩ ተነሥቶ ወደ መስኮቱ እየሄደ

"እሰኪ ቀይ ፣ ሲስተርን እንዴ ላናግራት ። ያልኩሽን ሕመምተኛ ወደ አማኑኤል ልመላክ እየሞከርን ነው ። ግን እኔ ገና ቤት መጥቼ እንደገና ሰሜን ማዘጋጃ ተያይዘን ስንሄድ የባሰ እንዳናረፍድ ። ለምን እናንተ ቀድማችሁኝ አትሄዱም? እኔ እዛው በቀጥታ መምጣት እችላለሁ" አለ ፣ የተሻለ ሐሳብ ሰለ መሰለው ።

"ሳይሻል አይቀርም ፣ እንዶርሱ እናዳርጋለን ። አንተ ግን ሳትጠዳደፍ በቻልከው ሰአት ድረስ ። ለእነርሱ እኔ እነግራቸዋለሁ"

"ግን መኪናስ ... ምን ታደርጋላችሁ ታድያ? አታቲም ለምሳው ትመጣለች እንዴ? እሷ ልታደርሳችሁ ከቻለች ብዬ ነበር" አለ ፣ በመስኮት ውጪ ውጪውን እያየ ። እናቱን ወይዘሮ አታለምን ከልጅነቱ ጀምሮ አታቲ ነው የሚላቸው ።

"እንዴ ምን ማለትህ ነው? አገቴ እንዳትተር ደጋግሞ ነው የነገራት ። እሷም ተዘጋጅታ እየጠበቅንህ ነበር እኮ ። በታ አልያዝህ የኔ ፍቅር ። ታድያ ... ረፈደ ብለህ በሃው እንዳትቀር ደግሞ ፣ እሺ?" ብላ ስታስጠነቅቀው ፣

"አ-ይ-ዶ-ራ-ግ-ም ... በቻልኩት ፍጥነት እመጣለሁ" አለ ሳቅ ብሎ ። ስልኩን ዘግቶ ትንሽ ተረጋጋቶ በአጥታ ደጅ ደጁን እያየ ማሰብ ጀመረ ። ወዲያው 'ብር ያለው ደደብ' የሚለው የዝናሽ ስድብ ቀመስ ቁጣ ትዝ ሲለው ፈገግ አለ ።

'ብር ያለው ደደብ! ሀም ... ድንት ስድብ ነው ። ደደብ ከሆኑ ፣ ብር የሌለውስ ቢኮን ምን ለውጥ አለው?' አለ ለራሱ ድምፁን አሰምቶ ። እንደዚህ ዓይነት ስድብ ሰምተም ስለማያውቅ ግርም ብሎታል ። ምናልባትም የተያያዘ ታሪክ ሊኖረው እንደሚችል ገመተ ። ቢሮውን ዘጋግቶ ሲስተር ዘቢባ ወዳለችበት ቢሮ ሊደርስ ስልክ እየደዋወለች ነበር ። ከራት ለራቷ ከሉ ማንበሪያ ላይ ተቀመጠ ። የያዘችውን ስልክ ዘግታ ወደ እርሱ ቀና አለችና ፣

@OLDBOOKSPDF

"ዶክተርዬ ጉድ ኒውስ፣ አማኑኤል ሲተበሏት ተሰማምተዋል። ችግሩ አምቡላንስ ማግኘት አልቻልኩም። ፖሊሶቹ ደግሞ የነሱን መኪና እንዲመሰዳት ለመጠየቅ እንደማይችሉ ነው የነገሩኝ። እዚሁ ከዋየች ደግሞ አምቡላንስ እስክናገኝ መከራችንን ማየታችን ነው" አለች፣ ግራ ግብት ብሏት ጠረጴዛውን በያዘችው እስክርቢቶ እየቀረቀረች። ቢሮው የጠዋቱ ግርግር ቀለል ብሎት ባዶ ሆኗል። እቢራ በለበሰው ወለል ላይ የወዳደቁ ወረቀቶችንና የጫማ ኩቴዎች እያየ ቀየና ቀና ብሎ፣

"ባስፈው እንደዚሁ አምቡላንስ ማግኘት አትቷቸው በራሱ መኪና እንድ ህመምተኛ አማኑኤል አድርሶ እንደ ነበር ዶክተር ምስክር ነግሮኝ ነበር። አማራጭ ከሌለ እንድ ቀጠሮ ስላለኝ እገረ መንገዴን አድርሺያት በላው ልሂዳ ታድያ" አለ፣ ውስው ቢጣደፍም ነገሩን እዕ ላይ ትቶ መሄዱ እየከበደው።

"እረ ምን በወጣህ ዶክተርዬ፣ ይህን ያህል ያቀየሁህ መች እነስ። በል ተነሳ፣ ሂድ ልጁ። ቀጠሮህ ይረፍድብሃል። እኖው እንጻመጣብን የሆነ መፍትሔ ፈልገን እንልካታለን" አለች። ሐሳቡን ባትጠላውም ዝግ በላይ እርሱን ማስቸገሩ ከበዳት።

"ግዴለሽም ሲስተር፣ ሁሉም ነገር ገዝጁ ከሆነ ምንም አይደለም። እኔ መኪናዬን ቀረብ ላድርጋትና አንጻፍታ በህው ጥያት ላልፍእችላለሁ። ብቻእንዳታስቸግረን ጸሎት አድርሽልን።" ብሎ መግደርደሩ እንደማያዋጣ በመረዳት እያቅማማች ተስማማች። የምሳ ግብዣ ቀጠሮው ምን ያህል እንደ ረፈደ እያወቀ ህመምተኛ አማኑኤል ካላደረስኩ ብሎ የመግደርደሩ ምክንያት አልገባውም። ትከሻውን በውስጡ ሰበቅ አድርጎ ነገሩን ለመርሳት ሞከረ። በራቱ ላይ ትንሽ ቀም አለና "እምም ... ለማንኛውም መንገድ ላይ እንጻታስቸግረን 10 ሚሊግራም ቫልዩም ብትጨምሪላት ጥሩ ነው መሰለኝ ሲስተርዬ?" ብሎ መኪናውን ለማቅረብ ወጣ።

በርግጥም የመድኃኒቱ ጉልበት እየደከመ ስለ መጣ ዝናሽ በክፈል ንቅታ መለፍለፍ ጀምራለች። ተጨማሪ መርፈውን ከሰጪት በኋላ ተጋግዘው መኪና ውስዋ አስገቧት። የኋላው ወንበር ላይ እሷን ከመሃል አድርገው ፖሊሶቹ ግራና ቀኝ ተቀመጡና ወደ አማኑኤል ተንቀሳቀሱ። ውስዋ ለውስዋ ያለውን መንገድ በትክክል ስለማያውቀው፣ ርቀቱ ቢጨምርበትም በቀለበት መንገዱ መሄዱን ነው የመረጠው። የሚነዳት ቶዮታ ሰርፍ እሮጌ ብትሆነም፣ ጥሩ ጉልበት ስላላት ባዶው የቀለበት መንገድ ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም። ከፖሊሶቹ ጋር ጥቂት ታላትን ከመለዋወጥ በቀር ባብዛኛው በጸዋታ ነበር የሄዱት። ወደ ጦር ኃይሎች አካባቢ ሲደርሱ በክፈል የነታችው ዝናሽ ጥቂት መወራጨት ጀመረች።

"እኔ እዛች ቤት አልሄድም" እያለችና የማይገባቸውን ሴሎች ነገሮች እየዘበራረቀች መጮህ ጀመረች። የጦር ኃይሎች አደባባይን ዞረው ተመልሰው ወደ አማኑኤል አትጣጫ ሲያቀኑ ደግሞ ትንሽ የተረጋጋች መሰለች።

'ጦር ኃይሎች አካባቢ ምን ዓይነት ነገር አጋጥሟት ይሆንን ደግሞስ የት ቤት ይሆን?' ብሎ አሰበ።

@OLDBOOOKSPDF

ከዋናው መንገድ ወጥተው የውስጥ ለውስጥ መንገዱን አገባደው ወደ ሆስፒታሉ አካባቢ የሚወስደው ቅጥን አስፋልት ውስጥ ገቡ ። ወደ አማኑኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ እየቀረቡ ሲመጡ ፣ እንደገና አራታዋንና ያዙኝ ልቀቁኝ ብላ መወራጨቷን ጀመረች ። የሆስፒታሉ በር ጋ ሲደርሱ ጭራሽ የፊት ወንበሩን በእግሯ እየረገጠች ለያዥ ለገናዥ አስቸገረች ። ሕመምተኛ እንደ ያዙ ያዩት ጥበቃዎች ፈጠን ብለው በሩን ከፍተው የድንገተኛ ክፍሉን ጠቀሙዋቸው ። በሳምንት አንድ ቀን ለግማሽ ቀን ብቻ ስለሚመጣ ሌላሠውን ብዙዎቹ የሆስፒታሉ ጥበቃዎች አያውቱትም ።

የድንገተኛ ክፍሉ አካባቢ ሲደርሱ እንደ ምንም ተጋግዘው ከመኪናው አውርደው በብዙ ትግል ወደ ውስጥ ይዘዋት ገቡ ። የክፍሉ የቀን ተረኛ ነርስ ፣ አቶ ሐዲስ ከጥቂት ሠልጣኝ ነርሶች ጋር በረንዳው ላይ ተቀምጠው ሲያወሩ ነበር የደረሱት ። የተፈጠረውን ግርግር ሲያዩ ተረባርበው አገዟቸው ። አቶ ሐዲስ ዝናሽን ገና እንዳዩዋት አወጽት ። ጭንቅላታቸውን በሐዘን እየነቀነቁ

"ዋእይ ... ምን የመሰለች ልጅ ፣ እንዲያው አሁንማ ከሰውነት ተራ ሁሉ ወጥታ ፣ ማን ያውቃታል" አሉና ካስታወሰችኝ ብለው ስሟን ጠሯት ። ትንሽ አፈጠጠችባቸውና ከት ብላ መሣቅ ጀመረች ። ወዲያው ደግሞ ተነስታ ለመውጣት ብድግ ስትል ተረባርበው ይዘው አስቀመጧት ።

" እ እ ... መጡ ...መጡ ... ሊገሉኝ እኮ ነው ...እ እ" እያለች ላንቃዋ እስኪሰነጠቅ ጮኸች ። ወዲያው ደግሞ ራቷ ተለዋውጦ አርጩሜ እንዳየ ሀዳን ሰቅቅ ብላ ራቷን በእጆቿ ሸፍና በጸጥታ ከግድግዳው ማእዘን ጥግ ላይ ኩርምት ብላ ስትቀመጥ ዘፍሱ አረጭ አለ ። የመጣችበትን ሁኔታ አስረድቷቸው ራሱ የጻፈውን የመሸኛ ደብዳቤ እየሰጣቸው ፣

"እዚህ ብዙ ጊዜ ትመጣ ነበር እንዴ?" ብሎ ጠየቃቸው ።

"እንዴ ዋ... ቤቷ ነበር አማኑኤልማ ፣ ባመት ሁለት ሦስቴ እዚህ ሳትተኛ አትቀርም ። ክትትሏም እዚሁ ነበር እኮ ። እናቷ ከሞቱ ወዲህ ግን ይኸው ሦስት አራት ዓመት መሰለኝ አይቼያትም አላውቅ ። እንዴት ያለች ልጅ ነበረች መሰለህ ዶክተር ። እንግዲህ እኔ እንኩዋ ሳውት ይኸ ሁለተኛ ወይ ሦስተኛ እርግዝናዋ ነው መሰለኝ ። ሰውነት ከፉ ባዳ ነው ፣ አሁንማ ሌላ ሰው መሰላ ዝናሽ መሆኗንስ ማን ያውቃል ። አይ ፈጣሪ! እንዴኛዋን ገዳና ላይ ወጥታለች ማለት ነው?" አሉ ፣ እጃቸውን ከነጩ የሥራ ልብሳቸው ኪሶች ውስጥ እንደጨመሩ ። ሁለቱም ፖሊሶች ባንድነት የአዎንታ መልሳቸውን በሚንቅላታቸው ነቅናቁ ሰጡ ። የቀጠሮው ጥድፊያ ውስጡን ቢቆጠቁጠውም ስለ ዝናሽ ለማወት ያለው ፍላጉቱን መግታት አልቻለም ።

"እና ቤተሰቦቿ ይታወቃሉ ማለቱ ከእናቷ ሌላ የሚታወት ዘመድ ይኖራል?" አለ ፣ ከራቷ የሚጠብቃት ፈተና እየታየው በሃዘኔታ ወደ እርሷ እያየ ። ዝናሽ ግን ከክፍሉ ውስጥ የሌለች ያህል በማጉተምተምና በሰመመን መሃል ጠፍታ አሁንም ከክፍሉ ጥግ መሬት ላይ ኩርምት ብላ ታታሮጣለች ።

@OLDBOOKSPDF

"አዎን ፣ የድሮ ካርዲም ላይ ስልክ ቁጥር አያጠፋም ። ኧረ እንደውም ማናት ያቺ አማረች ፣ እዚሁ ከርድ ክፍል የምትሠራ የሰፈራቸው ሰው አለች ። እዚህ ታች ዘበ ወርቅ አካባቢ እኮ ነው የሚኖሩት ዘመዶቿ ። አባቷም በሕይወት ያሉ መሰለኝ ። አይ አለመታደል ፣ ሰው መሆን አበሳ ነው ። ኧረ ኤዲያልኝ!" አሉ ፣ አቶ ሐዲስ አደፍ ያለ ነጭ የሥራ ልብሳቸውን ቀልፈው አሻቸውን ኪሳቸው ውስጥ እንደከተቱ ቀርጠጥ ቀርጠጥ እያሉ ። ዶታታ ሰውነታቸውና ሽበቶ ጠጉራቸው አትመ ቢሰ ቢያስመስሳቸውም ንቁ ቁመናቸውና ሰል አነጋገራቸው የሰውን ቀልብ ይገዛል ። ዘንበወርቅ ሲባል ሴላሙ ድንግጥ ብሎ ውስጡ ይበልጥ ነቃ ። ፖሊሶቹ መሄድ እንዳለባቸውና በሴላ ጊዜ እንደሚመለሱ ተናግረው ሲወጡ እሱም

" ሐሙስ ሐሙስ እዚህ ሰለምሠራ መጥቼ እያታለሁ እስኪ ። ታውታታለች ያሏትን ልጅም ባገኛት ደስ ይለኛል" ብሎ አቶ ሐዲስን አመሰገኖ ከከፍሉ ሲወጣ በሩ ላይ ሲደርስ ቀም ብሎ ፣ "ይቅርታ ፣ እንደው ካወቁ ብዬ ነው ፣ ደጋግማ 'ብር ያለው ደደብ' ብላ በቁጣ ስትሳደብ ነበር ። አዲስ ነገር ነው መይሰ በፊትም የምትሰው ነገር ነው? እንደው ትርጉም ያለው ነገር ከሆነ ብዬ ነው" አለ ፣ ወዲ እርሳቸው ዞሮ ።

"እዩ ፣ ሁሉም ሲያማት ወይ ስትናደድ ያው ነው ። መጀመሪያ ታማ የመጣችው አረብ አገር ለሥራ ሄዳ ነበር ። ከአሠሪዋ መሰለኝ አርግዛ የመጣችው ። እና 'ብር ያለው ደደብ' የሚለው ከዛው የተያያዘ ይመስለኛል ። እንዴ ጠይቂያት - 'ብር ያለው ደደብማ አረብ ነው' እንጂለችኝ ትገ ይለኛል ። በጣም ከተናደዱች ትልቁ ሲድቢ 'ብር ያለው ደደብ' ነው ። ሲያማት ግን ያው ሁሉም ሰው ሰርቢ 'ብር ያለው ደደብ' ነው" አሱት ፣ ይበዛሃ ምስጢራዊ ፈገግታቸውን በወርቅ ጥርሳቸው አስጊጠው ።

ነገሩ ድብልቅልቅ ስሜትን እንደ ፈጠረበት በሐሳብ ተውጦ ተሰናብቷቸው ጠጣ ። መጀመሪያ ጳውሎስ ሲያያት ከገዳና ላይ የቀሙ መኪናች መስተዋት ሰባብራ ፖሊሶች ያመጧት እንድ ከሊኪኩን የረበሸች 'አብድ' ነበረች ። አሁን ደግሞ ባለ ብዙ ታሪክና ምስጢር ፣ ምናልባትም ውስብስብ ሀይወት ያላት ሴላ ሰው መሰላ ታየቻው ። ውስጢም ያልተኖረ ሕይወትና ያልተጀመረ ታሪክ ያለው ያልተመለደ ሴላ ሰው መኖሩን ሰማስብ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገደደ ።

በመርካቶ መሃል አጽርጦ በጊዮርጊስ አላብር ሽትብ ወደ ሰሜን ማዘጋሻ ሲሄድ በየመንገዱና በየሱቱ ፣ በየመኪናውና በየጥጋጥጉ የሚያያቸው ወንድና ሴት ፣ ልጅና አዋቂ ፣ የኔቢጡና ከበርቴ ፣ ተሽካሚና አሽካሚ ፣ ንጹና ተነጹዎች ሁሉ ለወትሮ ከሆኑት ተለያበት ። ሴላ ሰው ... ሴላ ፍጥረት መስለው ታዩት ። ከመሃል መርካቶ እስከ አዲስ አበባ ጥግ ከተማይቱን ያጨናነቱው ሰው ሁሉ ፣ ውጪው በሥጋ ተለብጦ ፣ በውስጡ ምስጢራዊ ሪቲት ንፍሱን ሰውሮ የሚንከላወስ ሴላ ሰው ሆኖ ታየው ።

'ሰው ሁሉ ሴላ ሰው ነው ። ውጪው ሴላ ውስጡ ሴላ ፣ ኑሮው ሴላ ሀልሙ ሴላ ፣ ልቡ ሴላ አፉ ሴላ' አለ ለራሱ ። ሃሳቡ ሲመስድ ሲመልሰው ፣ ሲመዘመዝ ሲንጣው ፣ ከመጀመሪያ እንደ ደረሰም ላያውቀው የባለቤቱ አንት ሰፈር ደርሶ ራሱን አገኘው ። ለመኪናው ማቆሚያ ከሚሆን ሰፊ ቦታ ላይ በልኩ ሥፍ ። ንጹሕ

©OLDBOOKSPDF

ነበረች ። መድረሱን ነገራት ። ልብሱን አስተካክሎ ኮሎኙን አወጣና የቀኝ እጁ መዳፍ ላይ ነስነስ አድርገ ካንገቱ ገን ላይ በስሱ ቀባ ቀባ አደርገው ። ከመኪናው ሲወርድ ትንሽ ዘና የማለት ሰሚት ተሰማው ። የጠዋት የሆስፒታል ውሎውንና ገናናሽን ከአሳቡ ለማውጣት እየታገለ ወደ ሰፊው ግቢ ዘለቀ ።

ወደ ቤት ሲገባ 'ብር ያለው ደደብ' የሚለው የገናናሽ ጩኸት አሁንም ጆሮው ላይ አንቃጨለበት ። እዚህ ደግሞ ብዙ ብር ያላቸው ሰዎች ሳሎን ቤቱን ሞልተውት ስለ ነበር ነገሩ ላይወድ ትንሽ ፈገግ አደረገው ። በየወንበራቸው የተኮፈሱትን ብዙ ባለ ብሮች እየሳመና እየጨበጠ ሰላምታ ሲሰጥ ሣቁን በአሳር ነበር የተቀጣጠረው ። 'ብር ያለው ደደብ' ብሎ ስድብ አለ በሆዱ ። ያማኑኤል ሕመምተኞችን ፣ የመርካቶ ገብያተኞችንና የሚስቱ አባት ቤት ድግስ ታዳሚዎችን በትጽበት በማንጻጸር አሰበና ሁሉም ሰው 'እብድ' ፣ ሁሉም ነገር ስም ያልተሰጠው 'እብደት' መሰለው ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 5 ፡

ሌላው ከእንቅልፉ እንደነቃ ሰዓቱን ሲመለከት ከሌሊቱ ለአሥራ አንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ይላል ። ከአጠገቡ የተኛችው ንጹሕ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ራሷን ጥላለች ። ደረቱ ላይ ያደረገችውን እጇን ቀስ አድርጎ እንሣና ከአልጋው ውስጥ ሹልክ ብሎ ወጣ ። የሆነ ነገር እጉተምትማ ስትገላበጥ ሰውነቷ በከፊል ስለ ተገለጠ ፣ የአልጋ ልብሱን አልብሷት ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደ ።

ራቁን በቀዝቃዛ ውሃ ሲታጠብ የበለጠ ነቃ ። ፎጣውን ካልጋው ጠርዝ ላይ ጣል አድርጎ ከመልበሻው ሬት እንደቀመ ሰራሱ ፈገግ አለ ። ከወዲያ ወዲህ እማተረና ከወደ ጥግ ካለው ሶፋ ላይ ዘና ብሎ ጥቂት ተቀመጠ ። የመስኮቱን መጋረጃ በከፊል ሰብስቦ ውጭውን ሲያይ ገና እንደ ጨለመ ነው ። ለጭንቅላቱ የቀረበውን ሃሳብ ሲያሰላስል ቀየ ። ባለ ሙሉ ቀይ ቀለም የስፖርት ቱታውን ለብሶ ኮሽታም ሳያሰማ በቀስታ በሩን ዘጋና ወደ ታች መረደ ። ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ከፍሪጁ ውስጥ ያለውን የውኃ ጮማ አውጥቶ ሁለት ሙሉ ብርጭቆ እከታትሎ በባዶ ሆዱ ሲያንደቀድቅበት እንጀቱ በትዝታዚው ተላወሰ ። የላሎኑን በር ከፍቶ ሲወጣ ፍጥረተ ዓለም በጥብቅ የእንቅልፍ መዳፍ ውስጥ ወድቀ ጸጥ ረጭ እንዳለ ነው ።

የቀት ያህል ንቁ የሆኑት ዘበኛቸው ጉሮሯቸውን እየጠራረጉ ከማደሪያ ቤታቸው ያረጀ ጋቢያቸውን ተከናንበው በትራቸውን ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ወጡ ። "ደህና እደርክ ሌላንስም?" አሉ የመኪናውን በር ሲከፍት ወደ እርሱ እየቀረቡ ። እርሳቸውም ከእናቱ ተከትለው ሌላንስም ብለው ነው የሚጠሩት ። "ወዴት ነው በውድቅቱ ልሄ?" ሲሉት ፣

"ትንሽ ሮጥ ሮጥ ልበል ብዬ ነው ሳይሞት በማለዳው ። እንዴት ይቀዘቅዛል ባክዎ ... እፍ...ፍ...ፍ ... ብርዱ እንዴት እያደረግዎ ነው?" አለ ፣ ከውስጥ የጠጣው ውኃ ትዝታዚ ከውጭ ከሚነፍሰው ስስ ንፋስ ጋር ተባብሮ ሽንቱጥ ሲያደረገው ።

"እዬ...ዬ ምናላት ይቺ? ኧረ ይሄ ደህና ነው ፣ ባለፈው ሰሞን የነበረ ቁር

@OLDBOOOKSPDF

አይጣል፣ አጥንት ይሰብር ነበር። ግን እንዲያው በየህ በወድትት ... ስመሆኑ የት ነዉ ስቦርት የምትሠራ ልጅ" አሉ፣ ማለጻነቱ አይሎባቸው።

"እብዮት አደባባይ አካባቢ ነው። በጣም ብዙ ሰው በሌሊት እዛ ይሂዳል። ምን እሱ አሁን ገና ሳልደርስ ነው የሚነጋው" አለ፣ ብርዱን ሽሽት ወደ መኪናው ውስጥ እየገባ። ከደርግ መውደቅ በፊት ከሀገር ስለ ወጣ አሁንም እብዮት አደባባይ የሚሰው ስም ነው አፉ ላይ የሚቀለው። የውጭ በሩን ከፍተውለት ወጣ። መንገዱ ባዶ ሰላ ነበር ከአሮጌው አየር ማረፊያ አካባቢ መስቀል አደባባይ ለመድረስ አሥር ደቂቃም አልወሰደበትም። ከተዶረደሩ መኪናዎች ተርታ አቅመና የመገለያ ገመዱን ይዞ ወጣ። ቀድመው የደረሱ ሰዎች ከወዲህ ወዲያ እየተሯሯጡ በግልና በቡድን የተሰያዩ እንቅስቃሴዎችን ወደሚሰሩበት ደረጃዎች ፈጠን እያለ ወጣ።

ዐሐይ የምሥራቁን አድማስ ቀድዳ ገና ባትወጣም፣ ደስ የሚል የንጋት ጸዳል አካባቢውን አጥለቅልቀታል። ውር ውር የሚሉ በተለያዩ የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎች ለስፍራው የበለጠ ድምቀት ስጥተውታል። የልብሳቸው ጎብረ ቀለማትና ድብልቅልቅ የስፖርተኞች ድምፅ ከእንቅስቃሴያቸው ትርምስ ጋር ተሰባጥሮ በአደባባዩ ላይ በጥድፊያ የተወጠረ ርጋታን ፈጥሮበታል። ከባሻገር የሚሰማው የእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ቅዳሴ ደግሞ ከመኪኖችና ከሰዎች ከሚወጣው ድምፅ ሁሉ ገንኖ ከፍ ዝቅ እያለ ይንቀረቀራል።

ቅዳሜ ማለዳ በ 'እብዮት አደባባይ' ለሌላሠው ከስፖርትነቱ በላይ የማይረሳ የልጅነት ትዝታነቱ ያመዝናል። ኢትዮጵያ መጥቶ አዲስ አበባ ካለ፣ ካቅም በላይ ችግር ካልገጠመው በቀር አይቀርም። በልጅነቱ ከአባቱ ጋር በየቅዳሜው ማለዳ እዚህ መጥተው መሮጥ ወይም በግቦን ሆቴል መዋኘት ሳምንታዊ ልማዳቸው ነበር። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከገባ በኋላ አባቱ በስራ ምክንያት ወደ አስመራ ስለ ተዛወሩ፣ ብዙም ሳይቀይ ደግሞ እሱ ራሱ ወደ አሜሪካ ስለ ሄደ የቅዳሜ ማለዳ አዘውትሯቸው ተጽርሶ ቀረ።

የልጅነት ትዝታ ከልብ የማይጠፉ የስሜት ለዛን ተላብሶ ናፍቆትን የሚያጭር ምስጢራዊ አቅም አለው። ዛሬም ከብዙ አመታት በኋላ ልቡ እስኪጠፋ በስጢ መሃል እየሮጠ ላቡ በግንባሩ ላይ ሲንቀረቀር፣ ንፁሁን አየር በጥልቅ ሲስብ፣ አባቱ አጠገቡ ያሉ ያህል ይሰማዋል። በቅጽበቲቱ ላይ የነገሠውን የጊዜን አገዛዝ ረስቶ እንዴ የኋልዮሽ፣ እንዴ የአሁንዮሽ፣ የትዝታና የመኖር መነግብቱን እያጣቀሰ ዛሬ ያኔ የሆነ ያህል የውስጥ ናፍቆቱን የሚቀሰቀስ ደስታ ይሰማዋል። እዚህ መጥቶ ሲሮጥ የአባቱ አብሮነት ይታደስለታል፣ እንደገና ልጅ የሆነ ይመስለዋል።

ላንድ ግማሽ ሰዓት ያህል በየመሃሉ የራሱን እንቅስቃሴ እያደረገ፣ እንዴ ፈጠን እንዴ ረጋ እያለ ሲሮጥ ቆየ። የማለጻጥ ጸሃይ ጨረሯን በአካባቢው ላይ ስትዘራው የሰጢ ሁሉ መልክ ፈካ ብሎ ታየው። ከዚያም ወደ ታች ወርዶ በዛ ብለው በቡድን ሆነው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ከሚሠሩ ወጣቶች ጋር ተቀላቅሎ የነሱን የድግግሞሽ እንቅስቃሴ መስመር ገብቶ መሥራት ጀመረ።

@OLDBOOKSPDF

በድንጋይ መቀመጫዎቹ ላይ እግራቸውን በማፈራረቅ በማውጣትና በማውረድ የሚሠሩት እንቅስቃሴ፣ ፈጣንና አድካሚ ነው። 'አንድ ... ሁለት ... ሦስት'... እስከ አሥር ... ከዚያ ደግሞ 'አሥር ... ዘጠኝ ...ስምንት' ... እስከ አንድ ... ዙሩ ቶሎ አያልቅም፣ ሲያልቅም ትንፋሽ አያስቀርም። ስፖርት ለገራው የሌላሠው ሠውነት ከድካም ይልቅ ጡንቻ የሚኩረኩር ደስታ ፈጠረለት። የወጣቶቹ ጠረን፣ ላቅና መተራረብ፣ አንዱ ከሌላው ቀድሞ ላለማቆም የሚያሳዩት የእልህ ሲቃ እሱም ተጋብቶበት ተቀላቅሏቸው እነርሱኑ መሰለ።

ብዙዎቹ በስም ስለሚጠራሩ የሚተዋወቁ ጓደኛሞች ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ጠርጥሯል። ከአጠገቡ ያለው ልጅ እግር፣ ደልዳላ ወጣት በየመሃሉ የሆነ ቀልድ ነገር ጣል ሲያደርግ ሁሉም ካ...ካ... ብለው ይሥቃሉ። መጀመሪያ ላይ ብዙም ስላልገባው ላለመለየት ብሎ ፈገግ ሲል ቀየና የቀልዱ ይዘት እየገባው ሲመጣ እሱም አብሮ መሣቅ ጀመረ። ከሌላው ቀድሞ ያቀመ ስለሚሳቅበት ሁሉም ጥርሱን ነክሶ ዙሩን ለመጨረስ ይጥራል። እርስ በርስ መተራረቡና መበሻሸቁ የተለመደ ነው። በመሃል አረፍ ብለው ሰውነታቸውን ሲያፍታቱ አንዳንዱ ንግግራቸው ቢያስቀውም ሳይስደነግጠው አልቀረም።

"ቀይ ግን በረሮ፣ እንቺ መቼ ነው ጡንቻ የምታበቅዪው፣ ወይ ስፖርቱን ተይውና ቦይንግ ሄደሽ ክንፍ አስገጥሚ" አለ፣ ሰውነቱ የገዘፈ ከፊት አካባቢ ያለ ወጣት ከአጠገቡ ያለውን አሞርና ቀሞን ልጅ። ዝሆንና ጉንቸል ይመስላሉ ጉን ለጉን ሲያዩዋቸው። በተረቡ የተሣቀበት ቀሞን ልጅ ከእርሱ የወጣ በማይመስል ጉርናና ድምጽ

"ለማኩብኩቢያ መላጣህን ከፈቀድክልኝ፣ በደስታ" ሲል፣ ሁሉም እንደገና ሣቁ።

"ችግሩ እኮ፣ በዚች አቅምሽ ብፈቅድልሽስ የኔ ጭንቅላት ላይ እንዴት ብለሽ ትወጫለሽ?" ለእሱም ተሣቀለት። ከመላጣው ላይ የሚንቀረቀረውን ላብ በካናቴራው ሲጠርግ በጸጉር የተሸፈነ ቦርጫም ሆዱና ለጥ ያለ ደረቱ በከፊል ታየ።

"ምን ችግር አለ፣ ተንደርድሬ ቦርጭህ ላይ ነጥሬ፣ ትከሻህ ላይ እቀምና፣ በቀጥታ ከመላጣህ ላይ እኩብኩቢ መብረር ነዋ" አለ፣ ወደ ታላቅ ቦርጩ እየጠቀመ። "እንደምታውቀው ይሄ ስፖርት ያላቸለጠው ጉተራ ቦርጭህ፣ እንኳን እኔን ጉማሬ ያዘልላል። ለምን ግን ለኤሮቢክ መስሪያ ወይም ለቦክስ መለማመጃ አታከራየውም በናትህ? የምር፣ በዛውም እኮ እንደ ካናዳ በረዶ ሲቀልጥልህ ይችላል" ሲል፣ ሁሉም ከትከት ብለው በረጅሙ ሲሥቁ ንዴቱን መደበቅ አልቻለም። ደም በሩ በግንባሩ ላይ መታየት ጀመረ።

"በቃ ይሄን ጥሙጋ አፍሽን ዝጊ እሺ፣ ፊት ሲሰጡሽ ኮ፣ ከልጅ አትጫወት አሉ። ተባይ ፊት ..." ብሎ፣ ምራቁን ወደ ቀጫጫው ልጅ አቅጣጫ ተፋ።

@OLDBOOOKSPDF

"ኧረ ምን ይላል ይሄ ... ራስህ ነህ የጀመርከው። ኧረ በናታችሁ ሬት በሉ ይቺችሁ እንዳይሄድ ... ይሄ ገርፍ ነው ምራት?" አለ ተጫጫነው ልጅ፣ አይኑን ሌላ አድርጎ በማሾፍ አይነት አጠገቡ ካረፈው ምራት እንደ መሸሽ ብሎ። ሁሉም እነሱ ከትከት ብለው ሣቁ። በዚህ ጊዜ ግሙፉ ልጅ ተንደርድሮ፣ ለጥፊ እጁን ሲሰነዝር በፍጥነት ሲያጮነብስበት ስዮት ተንገዳገደ። እንደምንም ዘሮ ከኋላ ግጅራቱ ሄ የቲሸርቱን ኮሌታ ይዞ ወዘወዘው።

በመሃል ሌላሠው አጠገብ የነበረው ደልዳላ ወጣት ዘሎ ጣልቃ ገባ። "ይቅቀው ... ራስህ ነህ ብሽሽቁን የጀመርከው አይደል? እሺ፣ ልቀቀው እንገቱን እ እንዳይመታው እየተከላከለለት።

ወፍራሙ ወጣት ጠጉንጮ የያዘውን ኮሌታ እንደ ጨመደደ እያለከለከ፣ "ሳ ሳንቾ፣ ይሄ አንተን አይመለከትህም እሺ" ብሎ፣ ባንድ እጁ ጨምቶ የያዘውን ልጅ ደጋግሞ በቦክስ ሚንትላቱ ላይ ሲመታው፣ ከምቱ ለማምለጥ ጉያው ስር የተወሸቀ ልጅ እየተሳደበ መንፈራገጡን ቀጠለ። ሳንቾ የትልቁን ልጅ እጅ ጨምድዶ ያዘው፣ "ልባድርግ ሳንቾ ከኔ ጋር እንዳትጣላ፣ ልቀቅ እጁን" ብሎ አከታትሎ የብልግና ስደቱ ሲሰድበው፣ የበለጠ ጠበቅ አድርጎ ጠመዘዘው። የባስ ንዴቱ ከቁጥጥር ውጪ ሆነ በጩኸት "የማነው ጮማ ፊት ይሄ! ይሄንን ጥፍጥፍ ፊትህን እንዳልደለድልህ አትለቀኝም ሳንቾ?" አለ፣ ሙሉ ለሙሉ ፊቱን ወደ እርሱ አዙሮ።

የጨመደደውን ልጅ ለቅቆ ሁለቱ ግብግብ ገጠሙ። ሳንቾ በቅጽበት ሁለቱንም እጆቹን ጠመጋዘ ወደ ጀርባው አዙሮ ያዘው። ለማስለቀቅ ሲታገል የራሱን የሰለ ተጠቅሞ መሬት ላይ አጋደመው። እሣው ባለበት እንደ ያዘው በንዴት መወራጨቱን ቀጠለ። ተጫጫው ልጅ ደግሞ ፈንጠር ብሎ ፊቱን እያሻሸ በከፊል ከደማ አፉ ውስጥ ምራቁን ደጋግሞ ይተፋል።

"እጄን ልቀቅ አንተ የወሻ ልጅ። ትከሻዬ ውልቃት አለው፣ ሰበብ እንዳትሆን በኋላ" አለ፣ አውንም ባልሸነፍ ባይነት ከላይ ከላይ እያለከለከ። ሌላሠው ቀረብ ብሎ የሳንቾን ትከሻ ሞታ ሞታ አድርጎ እንዲለቀው ነገረው። ሌሎቹም ልጆች ተረባርበው ሲነጣጥሏቸው ደረቱ ላይ የጫነውን ቀኝ ጉልበቱን አላላና ቀስ ብሎ ከላዩ ላይ ተነሣ ከወደቀበት ተነስቶ እየተሳደበ እንደገና ለድብድብ ሲጋበዝ ጓደኞቹ ይዘውት ሄዱ፣ ሌላሠውም ሳንቾን ይዞት በሌላ አቅጣጫ ከደረጃዎቹ ወረዱ። ሌሎቹም ሙገቶች ወዲያው ተበታተኑ። ሳንቾ ከተረጋጋ በኋላ ትንሽ ፈንጠር ብለው ሄዱና በሌላሠው ገመድ እየተፈራረቁ እየዘለሉ ማውራት ጀመሩ።

"እዚህ አካባቢ ነው እንዴ የምትኖረው?" አለ ሌላሠው፣ ገላዩ ከሰረቀው ትንፋሽ እንደምንም ሰብሰቦ።

"እም ... ራት አይባልም ... አዟራ አካባቢ ነው" ላመል ያህል ጉብ ጉብ እያለ እግሩን እያንቀሳቀሰና ሙንቻዎቹን እያጥታታ መለሰለት።

@OLDBOOOKSPDF

የለበሰውን ካናቴራ ወጥሮ የያዙትን የደረትና የትከሻ ጡንቻዎች ባድናቆት እያየ፣ "ኦ እዚሁ ነዋ ... ቤተሰብም እባው ነው የሚኖረው?"

"እም...ም ... ማለት ይቻላል ... እሱ የተባሉት እዚሁ ነው ያሉት" አለ ነገሩን ባጭር መገጋቱ ወይ ዘርዘር አድርጎ መናገሩ የተሻለ መሆኑን መወሰን አቅቶት ይመስል በማመንታት አይነት።

"እሀ ... ስለዚህ የዚሁ ያዲሳባ ልጅ ነሃ?"

"አይ ... ውልዶቴና እድገቴ እንኳ ደሴ አካባቢ ነው። ወላጆቼ በልጅነቴ ስለሞቱ አላውቃቸውም። የማውቀው ወንድምና እህትም የለኝም፣ ማለቴ ቢኖረኝም አላውቅም። እስከ አሰራ አምስት አመቴ ድረስ ለብቻዬ ነው የኖርኩት ማለት ይቻላል። ከዛም እዲሳባ ከመጣሁ በኋላ አንድ አክስቴን ባጋጣሚ አግኝቼ እዚሁ እባራ ከሷ ጋር መኖር ጀመርኩ። ሳይታሰብ የዛሬ ሁለት አመት ድንገት ታማ ሞተች። እሁን የምኖረው ትታቸው ከሄዱቻቸው ሁለት ትንንሽ ልጆቿ ጋር ነው" አለና ወሬው እንዳለቀበት ድንገት ዝም አለ።

ሌላሠው ሳያስበው የልጠበቀውን የታመቀ አሽንዳ የከፈተ ስለመሰለው ቁጥሎ ምን ማለት እንዳለበት አላወቀም። መገለሉን አቀመና ገመዱን አቀብሎት እያለከለከ ጉልበቱን በእጆቹ እንደያዘ ጎንበስ ብሎ ቀየ። ሳንቾም በተራው ዝም ብሎ በፍጥነት ረዘም ላሉ ደቂቃዎች ላቡ እስኪንጠፈጠፍ ሲዘልል ቀየ። ድክም ሲለው ዝላዩን አቀመና ገመዱን በአንድ እጁ እንደያዘ ከላይ ከላይ መተንፈሱን ቀጠለ።

"በጣም ትልቅ ሃላፊነት ነው የተሸከምከው። ሥራስ?" የነገረው ታሪክና ልጁን መጀመሪያ ሲያየው የገመተው አይነት ሰው የተለያዩ ሆኑበት።

"ለመኖር ላዳ ታክሲ እይዛለሁ። እዛ ጋ የምታያት የኔ ታክሲ ናት" ብሎ በጁ ጠቀመው። "ከባለቤቱ በኮንትራት ወሰጄ ነው የምሰራባት። የማታም ምንም እያልኩ ዩኒቨርስቲም እየተማርኩ ነው። በዚህ አመት ዲግሪዬን እጨርሳለሁ። አልሰራሁበትም እንጂ አካውንቲንግም የማታ ጨርሼ ዲፕሎማም ነበረኝ" አለና ገመዱን ከፊት ለፊቱ ጣል አደረገው። ጎንበስ ቀና እያለ ትንፋሹን በረጅሙ እያወጣ እያስገባ የደከመ ሰውነቱን ማፍታታት ጀመረ።

"እው ሪሊይ? ... በጣም ጥሩ ነው። በአካውንቲንግ ነው ዲግሪህንም እየሰራህ ያለኸው?"

"አይ ... ሶሺዮሎጂ ነው። ስረጅም ጊዜ መማር የምፈልገው ነገር ነበር። የመጨረሻ አመት ተማሪ ስለሆንኩኝ የተግባር ልምምድ ለመጀመር እየተዘጋጀሁ ነው። ብችል የሆስፒታል ስራ ነው መስራት የምፈልገው። ከበረታሁና ነገሮች ከተጎኙ በዚህ አመት የምጨርስ ይመስለኛል።"

የገመድ ዝላዩ ስለደከማቸው ከደረጃዎቹ ጠርዝ ላይ አረፍ አረፍ አሉ። እንደ ተቀመጡ ሌሎች ነገሮችን ሲያወሩ ቆዩ። ሌላሠው ሰዓቱን ሲያይ ድንገጥ ብሎ "እህ ግይ ጋድ ... ጊዜው እንዴት ፈጁ ላዘህ። እሁን ወደ ቤት መሄድ አለብኝ። እንደገና

©OLDBOOKSPDF

በሌላ ጊዜ ተገናኝተን ቡና ብንጠጣና ብንጫወት ደስ ይለኛል ። በመሬ ተመኖ በሚገባም እንኳ አልተዋወቅንም ። እኔ ሌላሠው እባላለሁ" አለ ፣ የጫማውን ማሰሪያ አጠባብቆ ቀና ብሎ እያየው ።

"እኔም ሰኢድ ነኝ ። ሰው ሁሉ የሚያውቀኝ ግን ሳንቾ በሚለው የቤት ስሜ" አለ ፣ መዝለያ ገመዱን አንስቶ እየጠቀለለ ።

"ኦ እሺ ... ቅድም እኮ ሳንቾ ብሎ ሲጠራህ ዋና ስምህ መስሎኝ ነበር ። ብዙ ጊዜ ትመጣለህ እንዴ እዚህ?"

"በሳምንት ሁለት ሦስቴ እመጣለሁ ። ቅዳሜ ጠዋት ግን ችግር ካልገጠመኝ በቀር አልቀርም ። "

"እህ ናይስ ... ስለዚህ የስፖርት ጓደኛ አገኘሁ ማለት ነዋ?"

"አሪፍ ነው ... ስልክ ብንለዋወጥም ደስ ይለኛል ። የታክሲ አገልግሎት ካስፈልገህም ያለህበት ቦታ ልመጣልህ እችላለሁ ፣ ደውልልኝ" ብሎ ስልኩን እወጣ፣ ቁጥራቸውን እየተለዋወጡ ወደየመኪናቸው ሄዱ ።

ከሳንቾ ተለይቶ መኪናው ውስጥ እንደ ገባ የቱታ ሻኪቱን አውልቆ ወደ ኋላ መረመረው ። ሞተሩን ሲያስነሳ የሬዲዮኑ ድምጽ ከልክ በላይ ተለቆ ናሮ እንባረቀበት፣ ድንግጥ ብሎ ጆሮዎቹን ያዘና በፍጥነት ድምፁን ቀነሰው ። መስኮቱን ወደ ታች አውርዶ ወደ ቤቱ አቅጣጫ አቀና ። ሬዲዮኑ ውስጥ ቅየት ያለ የአለማየሁ እሸቴ ሙዚቃ ይጫወታል ። እባቱ የአለማየሁ እሸቴ ጥብቅ አድናቂ ነበሩ ። እርሱም ልክ እንሶ እርሳቸው ሚንቅላቱን ከትከሻው ጋር እየመዘመዘ፣ መሪውን ላመል ያህል መታ መታ እያደረገ፣ አብሮ ማንጎራጎር ጀመረ ። ድምጹን ከሬድዮኑ በላይ አድርጎ እየዘፈነ ግራ ቀኝ እማትሮ ወደ አስፋልቱ ገባ ።

ሚክሲኮ እደባባይ አካባቢ ሲደርስ መንገዱ ተዘጋግቶ ስለነበር እንደ ኤሊ ጉዞ ማዝገም ግድ ሆነበት ። ወደ ጉኑ ዞር ሲል አጠገቡ የነበረ መኪና ውስጥ ከነበረች ቀንጅዮ ሴት ጋር አይን ላይን ተጋጨ ። ፊቱን ከስክሶ አጠገቧ ከተቀመጠው ሰውዬ ማን በላኝ እይት እይኗ ወዲያ ወዲህ ይንከራተታል ። ጉንጮ ሙሉ ፈገግታ ተለዋወጡና ሁለቱም ለትጽበት እይናቸውን ሰበሩ ። ጮክ ብሎ በመዝፈኑ ትንሽ እንደ ማፈር ቢልም ውስጡ ያለው ትዝታ እየናጠው መዝፈኑን ቀጠለ ። ትራፊኩ ለቀቅ ሲያደርጋቸው ደመቅ ባለ ፈገግታ ተሰናብቷት ከግርግሩ አመለጠ ።

ከመኪናው ወርዶ ግቢው ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያለ ከዘበኛቸው ጋር ትንሽ ሲያወሩ ቆዩ ። እናቱ በጠዋት ለሰልስት እንደ ወጡ አለመመለሳቸውን ነገሩት ። ከሰዓት ሽቅብ ወደ መኝታ ቤቱ የሚወስደውን ደረጃ በፍጥነት ወጣ ። በሩን በቀስታ ሲከፍተው ንጹሕ አሁንም እንደ ተኛች ናት ። ከመሸ በኋላ መንትያ አህቷ አርሴማ ከአሜሪካ ደውላ ሲያወሩ ብዙ እንደቀዩ ገምታ ሞባይሏ ያረፈው የጠዋት ቡሐይ መኝታ ቤቱን ሞቅና ፈካ አድርጎታል ።

@OLDBOOKSPDF

ንጹሕ ትራሱን እንዳቀፈች በደረቷ ቢ ብላ ተኝታለች ። ለረጅም ሰአት በደረቷ ሙተኛት መቻሏ ሁሌም ይገርመዋል ። እርሱ ደግሞ ወዲያው ድዘም ስሊትት ይለዋል ። ተጋጭተው የተኳረፉ ቀን እርሱ በጀርባው እጁን ማጅራቱ ሥር አድርጎ እሷም በደረቷ ትራቢን አትፋ ይተኛሉ ። ፍቅር የነገሠ ቀን ደግሞ እሷ በጀርባዋ እሱ በደረቱ ለረጅም ጊዜ ሳይገላበጡ የመተኛት ውድድር ያደርጋሉ ። ሁለቱም ከጥቂት ደቂቃ በሁዋላ ስለሚሰልቻቸው እንዱ ወደ አንዱ ዞረው ነገሩ ወደ ልፊያ ይቀየራል ።

መኝታ ቤቱ ወስጥ የናንወጉን ደስ የሚል መዓዛ በስፊው ማገው ። ሲጋራ እንዱ ጠማው ሰው እየሩን ሳምባው ውስጥ ብዙ አቀየው ። ቀስ እያለ ደረጃ በደረጃ ሲለቀው ሚስ አልባ አተነፋፈሱ ደስ የሚል ስሜት ፈጠረበት ። ከተመሰቃቀለው ያልጋ ልብስ እምልጠው የወጡት የንጹህ እግሮች የህጻን ገላ መስለው ታዩት ። ውስጥ እግሯን እከክ ሊያደርጋት እጁን ከዘረጋ በኋላ ደንግጣ ልትነቃ እንደምትችል አሰቦ አሳዘነችውና ተወው ። ቀስ ብሎ የአልጋ ልብሱን ሳብ አድርጎ አሰበላትና ወደ ቁም ሳጥኑ ሄደ ። የሚተይረውን ልብስ መርጦ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባ ። አንዴ እያኗኋ ሲለውም አያንገራገረ የውሃውን ሙቀትና ኃይል እየጨመረና እየቀነሰ ዘለግ ላለ ጊዜ ቆየ ። ሰውነቱን አደራርቶ ፎጣውን አሽረጠና ሲቀይር የያዘውን ልብስ ትነሻው ላይ ጣል አድርጎ ከመታጠቢያ ቤቱ ወጣ ።

ከመልበሻ መስተዋቱ ፊት ለፊት ሆኖ ሰውነቱን ዞር ዞር ብሎ እያየ ለራሱ ፈገግ አለ ። ጨበጥ ለቀቅ እያደረገ እንደሚሸጥ በግ የገዛ ገላውን ገመተው ። ወደ ጥቁረት የሚያደላው ጠይም ቀዳው ያብረቀርቃል ። በሱንቻ የተሞላው ሰውነቱ በረጅም ቁመቱ ተውጦ ከሆነው በላይ ቁሜን ያስመስለዋል ። ቦርቂ እልባ ሱንቻማ ሆዱን ፐሽፈነው ጸጉር የተቀረ ሰውነቱን ከሆነው በላይ ቀይ አስመስሎታል ። ሚኑና ቀኝ ትከሻው ላይ ያሉት ትላልት ጠባሳዎች ከጉርምስና እድሜ የድብድብ ዘመኑ የቀሩ ምልክቶች ናቸው ። ከኢትዮጵያ ከመውጣቱ በፊት ከባደሮቹ ጋር በየሰፈሩ እየዞሩ ቡድን መደባደብና ሳስ ጨዋታ ያዘወትሩ ነበር ።

ከዳርና ከዳር ትንሽ ገባ ያለው ጸጉሩ ብዛቱና ልስላስሊው ተዳምሮ ገና ከፍ ሲል ሙስተላስል ይጀምራል ። ሚስቱ ንጹሕ ሙልሞ አድርጉ ሲላጨው ደስ ይላታል ። ቁሚ ጸጉር አስተካክየም እሷው ናት ። ወጣ ገባ የሌለው ከብ ሚጉትላቱና ሞለል ያለ ቴልካ ራቁ ጸጉሩ ሲንሳለት ከእድሜው በታች ልጅ ያስመስለዋል ። ቀለል ያለ ቁምጣና ነጥቂ አደረገና አንሶላውን ገለጥ አድርጎ ቀስ ብሎ አልጋው ውስጥ ገባ ።

ወዴ እርፊ ጠጋ ብሎ ሲጉነጉትላት በከፊል የነቃችው ንጹሕ ፣ "እ ደ ደይይ ... ምነው ሌላ ... አንተ ልጅ ሁ ... ነካ ያደርገሃል አይደል? እስኪ ተነስ ዞር በልልኝ ... ልተኛበት ... በናትህ አትጋዘጠ! " ብላ ፣ እንዲነሳላት ልትገፋው ስትሞክር በቀዘቀዙ እግሮቹ እግሮቿን ቁልፍ አድርጎ ያዛት ። ሙሉ ስሙሉ ያልደረቀውን ጸጉሩን ፊቷና አንገቷ ላይ እያሻሸ ሊላፋት ሲሞክር "እን... ዴ አንተ ሞ.ዛ.ዛ ... ልጅ ... ኧረ በናትህ አስፈረድክኝ እነ ። ከፈለግህ ደጅ ውጣና ፀሐይ ሙቅ ... በናትህ አሁን ካልጋ ውስጥ ውጣልኝ ... " ብላ ፣ ራቢን ለማስለቀቅ ሞከረች ። በድጋሚ በርጥብ ጸጉሩ እንገቷን ሲያሻሽት ቱግቶ ጠፍቶ ሳጽ

@OLDBOOKSPDF

ንቷን በጥርሱ ሲነክት ሁሌም

እትችልም ። ለዚህም ይሆናል ከሰር ከሰሩ የምትላጭበት ። ደረቱ ላይ ልትከሰ
ስትሞክር አልያዝ አላት ። የመጨረሻ አማራጯን በመጠቀም እንደምንም ብላ ትኩ
ገብታ ስትኮረኩረው ከልጋው ውስጥ ተፈትልኮ ወጣ ። ጮኮን ከኮረኮሩት ፈረ ከ
እትሙ ሁሉ ይከላሞል ።

"እሰይ ዋጋህ ነው ። ምን አይነቱ ጨካኝ ነህ አንተ ግን ። እውነግ እኔ
አሞላቀቁህ በታ ... ያለ መሚዘገ ስራም አጣህ እኮ ። እስኪ በናትህ ቁርስህ ናናቶና
ሌላዬ... ዛሬ ..." እጇን በልመና አይነት እየዘረጋች ትራሱን ከፍ አድርጋ ራስጌ
ላይ ደገፍ ብላ ተቀመጠች ። የወደቀውን ትራስ አንስቶ ሲወረውርባት ቦር ሳ
አመለጠችው ። የተገረበረበውን የአልጋ ልብስ ለመስብሰብ ስትሞክር እንደ ገአቱ
ውስጥ አስገባት ። ጠበቅ አድርጎ ያዛትና እንገቷን በጸጉሩ ሲያሻሻት እየተንፈራፈረ
ስትንከተከት እሱም ተጋብቶበት መሳት ጀመረ ። እጁን ላላ ሲያድርግላት ባለ በሳ
ጋይሷ ጮኮን ስትኮረኩረው አትም አጥቶ ሙሉ ለሙሉ ለቀቃት ። በጀርባው ተጋድ
ሲሰት በፍጥነት እላዩ ላይ ፊጥ አለችበት ። "አሁን ሄደህ ቁርስ ትሰራለህ አትከራም
አለች በድል አድራጊነት ።

እንደምንም ትንፋሹን ለመያዝ እየሞከረ፣ "እንዴ ... ምን ማለትሽነው... በስድ
ቤትማ አይሆንም ... እኛ እኮ እዚህ እንግዶች ነን ። በሰው ቤትና ... በሰው እገር ያ
እንዳረጉሽ ... መሆን ነው እንጂ ..." አለ፣ በየመሃሉ ሳቁን መቆጣጠር እያቃተው፣

"እቤት እቤት ... ይሄው በሰው ቤት እኔን አላስተኛ እያልክ አይደል ። ቆይ
ብቻ እታቲ ትምጣልህ ባልናገርልህ...ዛሬ" ስትለው፣ ወገቧ ላይ በጠመጠመው እጁ
ጀርባዋን እያሻሸ ወደ ራሱ ሳብ አድርጎ ያዛት ።

"ከነገርሽማ አይቀር..." ብሎ ጠበቅ አድርጎ ሲስማት የተበታተነው ጸጉሯ ፊቷን
ሸፈነው ። በጆሯ ፊቷን እያባበሰች "ሌላ-ዬ!" ብላ፣ አይን አይኑን ስታየው እጅግ
በወገቧ ዙሪያ እንዳደረገ እንደገና ዘለግ አድርጎ ሳማት ። ጠጉሩን እያሻሸች እሺ
በጥልቅ ስሜት አጸፋውን መለሰችለት ። ከነጋ መኝታ ቤት የነሱን የልፊያ ድምጽ
የሰማችው ትንሿ አርሴማ በሩን ብርግድ አድርጋ ስትበርር መጣችና አልጋው ላይ ፊኖ
አለች ። አባቷ ከታች፣ እናቷ ከላይ ሆና ስታይ እንደ ለመደቻው ለአባቷ ለመርዳት
የናቷን አንገት ይዛ ለማውረድ ስትሞክር ሌላውም እንደ ተጎዳ አስመሰሎ

"ዝልፐ ዝልፐ ... እርሲ ... ኡህ ... ኡህ..." ሲል፣ በበለጠ ሞራል ጎኡሀን
ከሌላው ላይ ለማውረድ ትግሏን ተጠለች ። ሁለቱ ተጠቃቅሱና ጎኡሕ ወደ ገ
እንደ ተሸነፈ ሆና ዘንብል አለችላት ። በድል አድራጊነት እየፈነደቀች እናቷ ደረት ላይ
ተቀመጠችና ያባቷን እጅ ይዛ፣

"ተነስ አባቢ ... ተነስ ..." ስትለው፣ ገልበጥ ብሎ ጎኡሀን ከታች አድርገው
ባሸናፊነት እየኮረኮሩ ይተልዱባት ጀመር ። ዘግይቶ የደረሰው የእርሴማ መንታ
ወንድም ዲንሳ ተንደርድሮ አልጋው ላይ ወጣና በተራው ለእናቱ እርዳታ ያባቱን
እንገት ይዞ ለመጣል ትግል ውስጥ ገባ ። ከጥቂት መጣተት በኋላ ኩርፍ ብሎ ለማልቀስ

@OLDBOOOKSPDF

ሲጸጸው ንጹህ ሲላሠውን በቱጣ ገረመመችው። ወዲያው እንዴ ተሸነፈ ሆኖ ወደ ጮን ከብለል ሲልለት በአሸናፊነት ፍንደታ አባቱ ሆድ ላይ ወጥቶ ተከመረ።

"ማሚ ማሚ ... አልሺን እንቺ አሸንፊያት ..." ብሎ፣ ሳቅ በሞላው ፊት የናቱን እይን እያየ ማበረታታቱን ቀጠለ። ከጥቂት ትግል በኋላ ትንሺን አርሴማን ከላዩዋ ላይ እንከባላ አባቷ ደረት ላይ አስተኝታ ስትይዛት ድሉ የንጹህና የዲንሳ ሆነ። ዲንሳን ታቅፋው ካልጋው ላይ እየወረዱ፣

"በታ አሁን ጨዋታው አልቋል። እኔና ዲንሳ አሸንፈናል" ስትል አልከኛዋ አርሴማ ያባቷን ጉንጮች በትንሽ እጆቿ ወደ ራሷ ለማዞር እየታገለች፣

"ባቢ ተነሳ ... እናሸንፋቸው" እያለች ስትወተውተው፣ እንትልፍ እንደያዘው ሰው አይኖቹን ጨፍኖ ልፍስፍስ ብሎ ዝም አለ። ብዙ ታግላ ታግላ ዝም ሲሳት ድምጿ ወደ ለቅሶ መቀየር ጀመረ። ድንገት ብድግ አለና ታቅፏት ሲቀም አይኖቿ በደስታ አበሩ። በተደጋጋሚ ወደ ላይ እየወረወረና እየቀለበ ሲያጫውታት ቆየና

"ዝም በያቸው በታ፣ አርሲዬ፣ እኛ ደግሞ ነገ እናሸንፋቸዋለን" ብሎ፣ በቀልድ አረላሳት። ተመልሶ አልጋው ላይ ከነንጹሕ ጮን በጀርባው ሲንጋለል ትንሺ አርሴማ እንደ ልማዷ ደረቱ ላይ ወጥታ አንገቱን አቅፋ ጋደም አለች። የናቱን ጸጉር እየበታተነና እየነነነ መጫወት የሚወደው ዲንሳ ደግሞ ፊቷ ምራቅ በምራቅ እስኪሆን ድረስ እየሳማት በጨዋታ ተጠምደዋል።

"ተው ምራትህን አትቀባኝ" ስትለው፣ የባስ አውቶ ይለቀልታታል። የዋህነቱን ታይና ልቧ በፍቅር ቡሙቡሟ ይልና ምጥምጥ እድርጋ ትስመዋለች። አርሴማ አባቷ ጣት ላይ ያለውን ቀለበት ለማውለቅ ያቅሟን ታገላ ሲያቅታት፣

"ባቢ ይሄ ምንድነው? ማነው የገዛልህ?" አለችው። ጥያቄ ከጀመረች አታቀምም።

"ይሄ ቀለበት ይባላል። ማሚ ናት የሰጠችኝ። እኔና እሷ ባልና ሚስት ስንሆን ነው የገዛችልኝ። እኔም እርሷ ያደረገችውን ገዛሁላት። አየሽ እሷ እጅ ላይ እኔ የሰጠሁዋት ቀለበት አለ።"

"ለኔስ መቼ ነው የምትገዛልኝ ታዲያ?" ስትለው፣ ሳቅ ብሎ ትንሽ እጇን ሳም እያደረገ፣

"አርሲ ... እንቺ የኔ ልጄ ነሽ። እንደዚህ አይነት ቀለበት ለሚስትና ለባል ብቻ ነው የሚሰጠው። ሌላ አይነት ቀለበት ግን ወደ ፊት ትምህርት ስትጨርሺ እኔና ማሚ እንሰጥሻለን።"

"አይ ... እኔ የማገባው አንተን ነው። ማሚ ከፈለገች ዲንሻን ታግባ ... በታ የማሚን ልውሰድባት?" ስትለው። ማምረሯን አወቀ፣

"አይ እሱማ የማሚ ነው። የውልሽ እኔ የማሚ ባል ነኝ። እንቺ ደግሞ ስታድጊ ሌላ ሰው ታገቢያለሽ እሺ? ያኔ እሱ ሰውዬ ደግሞ ላንቺ ቀለበት ይገዛልሻል" አለ።

@OLDBOOOKSPDF

"እንዴ ባብቢ ደግሞ ... አንተ አነ ነክ ሴላሠው ... እኔ የማገባው ሰውዬ አንቱነ ነው" ስትለው ሥክ ብሎ ሳቀ። ነገሩን እንዴት ማስረዳት እንዳለበት ሲያስብ ዲንላ ጣልቃ ገብቶ፣

"እኔ የማገባው ማሚን ነው። ባቢ ዘፈልግክ አልሺን አግባ" ብሎ፣ እናቱን እንት አድርጎ ሲይዝ ሴላሠውና ንጹሕ ተያይተው ፈገግ አሉ።

"እስኪ ሂዱ ግራንድማን እዩ ... ተነስታለች እንዴ?" አለች፣ ንጹሕ ራቢዮ መነሳት ስለፈለገች። ወደ አያታቸው መኝታ ቤት ተሯሩጠው ሲሄዱ "ልጆቼ ምን መሆናቸው ነው፣ ሰው ሊያፋቱ ነው እንዴ?" አለች፣ ወደ ሴላ ሰው ጠጋ ብላ ጣሪ ጣሪውን እያየች። የግራ እጅጋን ጣቶች ይዞ እያፍተለተለ

"አይገርምሽም ... ይሄ እነሱ ያሉበት ሰነልቦናዊ የአድገት ደረጃ በደንብ የተጠና በብዙ ሀጻናት ላይ የሚታይ ነገር ነው። በዚህ እድሜያቸው እንደዚህ ማሰባቸው የሰነልቦና ጤንነት ምልክትም ነው ማለት ይቻላል። ምናልባትም ቤት ልጅ አባቷን ወንድ ልጅም እናቱን ማግባት የመፈለጉ ስሜት እሁን መኖሩ ጤነኛ የማፍቀር መሰረት በሰብእናችን ላይ የሚጣልበት የአድገት ደረጃ ስለሆነ ሊሆን ይችላል። ሲግመን ፍሩይድ 'ዘ ኤዲፐስ ኮምፐሌክስ' የሚለውን ጽንሰ አሳብ ያመጣውም ከዚሁ አዛምዶ ነው። ትንሽ ከፍ ሲሉና ነገሩ እየገባቸው ሲመጣ ግን ሴት ልጅ ወደ እናቷ ወንዱም ወደ አባቱ ማዘንበል ይጀምራል። ይህም የማይጋፉትን ጣውንት ወዳጅ በማድረግ በሰላም ለመኖር የሚያደርጉት ሰነልቦናዊ የአድገት ሽግግር ነው ይላሉ የፍሩይድ ደቀመዛሙርት።"

"አቤት አቤት፣ መቼም የማታመጡት የለም።"

የያዘውን እጁን ያገ ለቀቅ እያደረገ የጀመረውን አሳብ በመቀጥል፣ "እና ... ይህ የአድገት ደረጃ ሲባባ፣ ማለት ነገሩ በጊዜ ካልረገበ ልክ በግሪክ አፈ ታሪክ አባቱን ገድሎ እናቱን እንዳገባው ንጉስ ኤዲፐስ ሊሆን ይችላል ወንዱ ልጅ። ከዚህ ነው 'ዘ ኤዲፐስ ኮምፐሌክስ' የሚለው ሃሳብም የመጣው። ያባቷን ገዳዮች፣ እናቷንና የእንጆራ አባቷን በበቀል ለመግደል በዶለተችው ኤላክትራ ስም ደግሞ 'ዘ ኤላክትራ ኮምፐሌክስ' የሚባል በሴቶች ላይ የሚከሰት ተጓዳኝ ክስተትም አለ" አለ።

"እናንተ ልጄ ... እሀ ብሎ የሚለማችሁ ካገኛችሁ እኮ መሚዘዛችሁ እያልትኖ ... እሺ ሴላስ" አለች፣ ፊቷን ጨምዶድ አድርጋ። ልጇ ዲንላ ሴላሠውን ገድሎ እሷን ሲያገባት ታይቷት ዘገነናት።

"የምልሽ ነገሩ በጣም የተጋነነ ነገር ሊመስል ይችላል። ምክንያቱም አፈታሪክ ደገፍ ስለሆነ። አፈታሪክ ደግሞ አንድም ግንት ነው፣ ግን ደግሞ የእውነት ትንጣቢም ነው። በዶንብ ካሰብሽው አርሲም ሆነች ዲንላ ውስጣቸው ባለው የስሜት ጥንካሬ አንጻር የአትም ማጣታቸው ይሏቸው ካልሆነ በአሁኑ የስሜታቸው ጉልበት እንዳችንን አስወግደው ሊያገቡን ቢችሉ ኖሮ ይመለሳሉ ብለሽ አታስቢ" ብሎ ሲስቅ፣ ቁንጥጥ አደረገችው። እጁን ያገ አድኖ በሱ እያቀፍኩ ደግሞ በተታራኒው በዚህ እይነት ስሜት ውስጥ ማለፍ ያልቻሉ ልጆች ሲያድጉ የማፍቀር አትማቸው የተዛባ

ሊሆን ይችላል የሚልም እይታ አለ ። እስኪ አሰቢው ግን ... አሁን ማን አስተማራቸው ይባላል ታዲያ? ይሄ ሁሉ ነገር ተፈጥሯዊ የስነልቦናዊ እድገት ደረጃ ካልሆነ ምን ልትይው ትችያለሽ?"

ራሱን ደረቷ ላይ ደገፍ ሲያደርግ ያደገ ጸጉሩን እያባበለች፣ "ነገሩማ ... የሚገርምም የሚያስፈራም ነው ። ሆ... ሆ እንዲያው የኮምፕሌክሱ አበዛሽ" አለችና ከፊት ለፊት ግድግዳው ላይ ያለውን ሰአት አየት አድርጋ፣ "እንዴ ኧረ እንተ ልጅ እዚሁ ተኝተን እኮ አራት ሰአት ሊሆን ነው ... አታቲየለችም እንዴ ዛሬ?" አለች፣ ያደገጸጉሩን ለመቁረጥ እንደ ቋመጠች ሁሉ ጣቶቿን ጸጉሩ መሃል አስገብታ አያፍተለተለች ።

"ከስፖርት ስመለስ አባባ ሰልስት ብላ በጠዋት ወጥታለች ብለውኝ ነበር? እንግዲህ አረፋፍዳ ይሆናላ የምትመጣው ። የዚህ አገር ለትሶ እኮ፣ ሚች ወዴ ሰማይ ቤት በሰላም መድረሱን የጻፈው ደብዳቤ እስኪደርስ ይመስል ማለቂያም የለው?" አለ ። ለትንሽ ጊዜ ጸጥ ብለው ቆዩ ።

"ሌላዩ ያቺ ባለፈው ሳምንት ሆስፒታል ያደረስካት እርጉዝ በሽተኛህስ እንዴት ሆነች? ደጋግሚ ሳስባት ነበር ። የገባንላትን ልብስ ወስድክላት እንዴ?" አለች፣ በጨነቀው ፊት ወዶ እርሱ ዘንበል ብላ ፊቱን ለማየት እየሞከረች ።

"መታወኩ ትንሽ ጋብ ያለላት ይመስላል ... ማለቴ እንደበፊቱ ብዙ አትጮህም ። ትልቁ ችግር በደንብ ሳይሻላት የወለደች እንደሆነ ነው ። እሳው የምትሰራ ቤተሰቦቿን የምታውቅ እንዲት ሴት አግኝቼ ትንሽ አወራቹያት ነበር ። እናቷ ከሞቱ ነው አሉ እንደዚህ የባሰባት ። እስኪ አባቷን ለማገኘት እንዲቸጥሩልኝ ነግሬያቸው እየጠበቅሁ ነው ። አማኑኤል ሆስፒታል ደጋግማ ስለ ተኛች ብዙው ሰው ያውቃታል ።"

"እኔ ምልህ ካሁን በኋላ ሙሉ ለሙሉ ተሸሏት ልጇን ማሳደግ የምትችል ይመስልሃል?" አለች፣ እጁን ከከንፈራው ሰር አስገብታ በሆዱ ላይ ጣቶቿን ፔያኖ እንደምትጫወት ሂድ መጣ ነካ መታ እያደረገች ።

"እኔ እንጃ፣ ምን ያህል ሊሻላት እንደሚችል ከባድ ነው ለመገመት ። ቢሻላትስ የት እየኖረችና በምን መተዳደሪያ ህክምናዋን እየተከታተለች ነው ልጇን የምታሳድገው የሚለው ጥያቄም ቀላል አይደለም ። በርግጥ አንዳንድ ሀመምተኞች በሚገርም ሁኔታ መድሃኒት ሲወስዱ ይሻላቸዋል ። ለርሷም ተስፋ የማደርገው ያንን ነው"

በዚህ መሃል ልጆቹ ከታች እየተንጫጩና እየሮጡ መጡ ። "ግራንድማ መጣች ... ለትሶ ቤቶች ነው የሄደውት አሉት ። አባቢ ግን ለትሶ ቤቶች ምንድነው?" አሉት ትንሿ እርሷማ፣ ያባቷን አንገት ወደ ራሷ ለማዞር እየሞከረች ። ንጹሀና መንትያ እህቷ እርሷማ የመጀመሪያ ልጃቸውን ሲወልዱ ሴት ከሆነች እንዳቸው በሌላቸው ስም ለመሰየም የልጅነት ቃል ስለተገባቡ ነው እርሷማ የተባለቸው ። ዲንሳ ደግሞ የሌላሠውን አባት ኮሎኔል ዲንሳን ለማስታወስ ነው ዲንሳ ሌላሠው ዲንሳ የተባለው ።

"እርሷዬ ... ለትሶ ቤት ማለት ምን መሰለሽ ...እምም ... ሰው ሲሞት ቤተሰቦቹ ሁሉ ያገኙና በጣም ያለቅሳሉ ። ከዚ ደግሞ ቤተ ዘመድ እንሱ ቤት ሄደው አይሏችሁ

@OLDBOOKSPDF

ብለው ያባብሏቸዋል ። ጎረቤቶቹ ተሰብስበው ቤታቸው አይዟችሁ ለማለት ሲሄዱ የለትሶ ቤት ይባላል ። ገባሽ?" ብሎ፣ ፊቷን ሲያየው የበለጠ ጥያቄ እንደተጭነች በሚያሳይ ፊት

"መሞት ምንድነው? ለምን ያስቅሳሉ?" ስትለው፣ ዞር ብሎ ጉዱን አየት ሲያደርግ አንተው እንደ ገባህበት ራስህ ተወጣው በሚል ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ፣ ዲንሳን እንዳቀፈች ማዳመጥ ቀጠለች ።

"ሞት ማለት ... እ...ም ..." አሰና፣ እጁን ልቡ ላይ አድርጎ "እዚህ ውስጥ ያለችው ነፍሳችን ወጥታ ብር ብላ ወደ ሰማይ ትሄድና ... በታ ሰውነታችን ሁሉ ዝም ጭጭ ይልና መስራት ያቆማል ። ትገዘ ይልሻል ... የኛ ድመት እንኳ ... ማጊ ... የሞተች ጊዜ? ... በታ መሞት ማለት እንደሱ ነው ። ሰው ሲሞት ማውራት፣ መሄድ፣ መብላት፣ በታ ምንም ማድረግ አይችልም ። ከዛ ዘመዶቹ ያለቅሱና በታ ወስደው መሬቱን ቆፍረው ውስጡ ቅብር ያደርጉታል ። ከዛ በኋላ እንደገና ሰለማያዩት ያገኙና ሁሉም ሰዎች ያለቅሳሉ" አለና ምን ያህል እንደገባት ሲያጤናት የባስ ግራ የገባት ስለመሰለው ተጨንቆ እንዴት እንደሚያስረዳት ማሰቡን ቀጠለ ።

"ቶይ እሺ ... ለምን ታዲያ ባውሎፒላን ብልልል ብለው ነፍሹን ያገ አድልገው አምጥተው ልቡ ውስጥ እንደገና ክትት አያደልጉለትም ታዲያ?" ስትለው፣ ሃሳቡ ትንሽ የገባት መስሎት ደስ አለው፣ና

"ነፍሱ ወ...ደ ሰማይ ሩቅቅቅ ቦታ ... ወደ እግዚአብሔር ቤት ስለምትሄድ እዛ ድረስ አውሮፕላን አይደርስማ" አላት ።

"እሺ እግሥቢልን ... ፕሊስ ነፍሹን ስጠን ቢሉትስ?" ብላ፣ ካፉ ነጥታ ጠየቀቸው ። የሷን ጥያቄ ሰመመለስ ሲሰናዳ እናቱ መይዘሮ እታለም ደረጃው እየወጡ ናሮ

"ልጆች አልተነሳችሁም እንዴ? ወዴት ሄዱ ልጄ ሀጻናቱ?" ሲሉ፣ ጉዱ ዘላ ካልጋው ላይ ወረደችና ወደ መታጠቢያ ቤት ስትገባ ዲንሳና አርሴማ ደግሞ ወደ አርሳቸው እየተንጫጩ ሮጡ ። ሌላውም እናቱ በሩን ከፍተው ሲገቡ ብድግ አሰና

"ኧረ ተነስተናል አታቲ ... ወደ እዚህ ነይ" ብሎ፣ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለ ።

"ሌላ ሰላሜ ይህና አደርክ? ... ንጹሕወርቅስ የት ሄደች?" አሉ፣ ንጹሕን ከፍት ውስጥ ሰላላይዋት ። ለሰርጋቸው ባመጡላት የዳቦ ስም ነው የሚጠሯት ።

"መታጠቢያ ቤት ገብታ ነው ። እንዴት ነው ... ሰዎቹ ተጽናኑ?" አለ፣ በውስጡ የአርሴማ ጥያቄ እንደገና እንዳይቀሰቅስ እየፈራ ።

እንደፈራውም አልቀረ አርሴማ፣ ነፍሹ ሰማይ ቤት ሄዳበት ነው የሞተው እንዴ?" አለች ።

@OLDBOOKSPDF

"ምኑ የኔ ሚጥሚጣ?" ብለው ግንባሯን ሳም አደረጓት ።

ጥያቄውን ለማረሳሳት በማሰብ እይነት እንደ ቀመ ዲንሳን አንስቶ ወደ ጣራው እያመጣና እያወረደ ሲያጫውተው ቀንታ ጥያቄዋን ትታ ፣ "እኔንም አባቢ እኔንም ..." ብላ ፣ እግሩን ይዛ ስትማጸን ዲንሳን አስቀምጦ እሷን ልጇ እስኪጠፋ እየወረወረ እየቀለበ አጫወታት ።

መሬት ሆኖ የሚስተው ዲንሳ ያባቱን ቁታ ሱሪ እየጎተተ ፣ "ግራማንም ግራማንም" ሲለው አርሴማን አልጋ ላይ አስቀምጦ እናቱን አንከብክቦ አነሳቸው ።

"እንዴ አረ አንተ ልጅ ...እንዲያው በመቤቱ ይሁንብህ ... እንዳትጥለኝ ..." እያሉ ፣ እንደ ተሸከማቸው መኝታ ቤቱ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሠረ ። ልጆቹ እየጮሁ ከኋላ ሲከተሉዋቸው ፣ እሷቸውን ሞንትላቱ ላይ አድርገው ከመሳት ውጪ ምንም ማድረግ አልቻሉም ።

ጫጫታው ሰምታ የመጣችው ንጹሕ ያየችውን ማመን አቅቷት ፣ "እንዴ አንተ ልጅ ዛሬ ግን ነካ ሳያደርግህም አልቀረም መሰል ። ኧረ በፈጣሪ ባክህ" አለች እንደምንም ሳቋን ተቆጣጥራ ።

ልጆቹ ወደ እርሷ ሠረው ፣ "ማሚንም ማሚንም ..." ሲሉ እናቱን ቀስ ብሎ አልጋው ላይ አስቀመጣቸውና ወደ እርሷ ሠረ ።

"ኧረ የምን መሚዘገ ነው ፣ ዋ ብዬሃለሁ ሌላ" ብላ ፣ በያዘችው ፎጣ ለመከላከል ስትሞክር ገፅ ብሎ ከታች እንከብክቦ አነሳት ። እንደ ታቀፋት ክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲሠር ፣ ልጆቹ ከኋላ ኋላ እየጮሁና እየሳቁ ተከተሏቸው ። ድክም ሲለው ቀስ ብሎ አልጋው ላይ ከእናቱ ጐን አስቀመጣት ።

ሁለቱም ሀጻናት ድጋሚ ዙር እንዲያጫውታቸው እሷቸውን ወደ ላይ ሲያርገበግቡ ፣ "በታ ፣ በታ ፣ ኑ እንሂድ ፣ አሁንቁርስእንብላ ። ደግሞ ነገ ትጫወታላችሁ" ብለው ፣ የሌላሠው እናት ሲነሱ ፣ ሁሉም ተከታትለው ወደ ታች ወረዱ ።

@OLDBOOOKSPDF

6

ምስጢር የአባቷ ስባተኛ ሙት አመት የሚዘከረው ቅዳሜ ቢሆንም የሳምንቱ መጨረሻውን አዲስ አበባ ላለመቀየት ወሰናለች። እናቷን ብቻቸውን ትታ መሄዷ ቅር ቢላትም፣ የሚሰበሰቡትን ያባቷን ዘመዶች ማየት ስላልፈለገች ሌላ አማራጭ አልታያትም። እናቷም ብትኖርላቸው ደስ ቢላቸውም፣ ችግሩን ስለሚያውቁ የግድ ሊሏት አልፈለጉም። አርብ ማታ ላይ ከአብሮ አደግ የቅርብ ጓደኛዋ ጋር ወደ ደብረዘይት ኩሪፍቱ ተያይዘው ወጡ።

ቅድሚን ናዝሬት ላይ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር አላልፈው ከመሸ ወደ ደብረዘይት ተመለሱ። ደከሚቸው ስለነበር እንደገቡ ነበር የተኙት። ድምጽ በቀላሉ የሚቀሰቅሳት ምስጢር ሌሊት ላይ ስትነቃ ጓደኛዋ አልጋዋ ጫፍ ላይ ተቀምጣ እየተንሾካሾከች ታወራለች። ስልኩን እስክትዘጋ ጠበቀችና "ው.ይ ምን ይሻልሻል ማርቲ ... ቀይ በቃ አንቺ ከው.ቂያኖስ ማዶ የሚንተከተክ ፍቅር ይዞሻልና ሰው አይተኛበትም እንዴ? አይደክምሽም እንዴ ደግሞ?" አለች፣ ሙሉ ለሙሉ ያልነቃ ፊቷን እያሻሸችና እየተንጠራራች።

"በኔ የደረሰው ይድረስብሽ ብዬ ልመርቅሽ?" አለች፣ ስልኩን መልሳ ኃይል መሙያው ላይ እየሰካች።

"ኡሁሁ ... ባትሪ እስኪንጠፈጠፍ የሚያስወራ የርቀት ፍቅርስ ይቅርብኝ ... ምርቃቱ ላንቺው ይሁን። ለመሆኑ ደህና ነው? መቼ ነው የሚመጣው ግን እሱ?" አለች፣ አልጋው ውስጥ እንዳለች ትራሷን ደራርባ ለመቀመጥ እየተመቻቸች።

"ምኑ ይታመታል ብለሽ ነው አሁንስ ... ማስተርሱ ተጠናቀቀ ብዬ ተንፈስ ስል ለፒኤችዲ ስኮላርሺፕ ሰጡኝ ነው የሚለኝ። እሱን ሳያመቻች ወደ እዚህ ከመጣ ደግሞ ቪዛ ሊከለክሉኝ ይችላል ብሎ ፈራ። ... እኛ ዲሞ እንዴት እንደናፈቀኝ፣ ኡፍ ...ፍ ... አሁንስ ትምህርት ሚኒስቴር ንግር ቢጠሩ ምናለ" ብላ፣ ትራሷን እቅፍ አድርጋ ኩርምት ብላ ተቀመጠች።

@OLDBOOKSPDF

"አይ ኖው፣ አይዞሽ የኔ ናት። ግን ታዲያ መቼ ነው የሚመጣው? ቀይ ግን እኔ የምልሽ ፒኤችዲውንም የሚሰራው በፊሎሶፊ ነው?"

"መሰለኝ ... ሌላ ምን ይሆናል ብለሽ ነው? አንዴ በርሱ ተለክፏል።" ሳራ ጣራውን እያየች ጣቶቿን ማንቋቋት ጀመረች።

"ከዛስ እዚህ መጥቶ ሰማስተማር ነው? ምንድነው ዓላማው?" በጣም ራስ ወዳድ የሆነ ስለመስላት የበለጠ አናደዳት። ብዙ ተርባ ባታውቀውም ድሮውንም የፍትር ኃላፊነትን መሸከም የሚችል ቁም ነገረኛ ነው ብላ አታስብም ነበር። 'ከቀሰም የተጋባ፣ በላምባው ሳይሆን በትምህርት የሚተነፍስ የአድሚ ልክ ተማሪ' አለች በልቧ።

"ወፈላሰፍ ነዋ ... እኔ አንትሮፖሎጂ፣ እሱ ፍልስፍና አጥንተን፣ ልጆቹ ምን እንደሚበሉ ማን ያውቃል?" ብላ፣ እምባዋን ዋጥ አድርጋ የግዷን ሳቀች።

"የምር ግን ማርቲ ለምን የሆነ ሥራ የሚያስገኝ፣ አለ አይደል፣ የሆነ ሙያ ነገር እያጠናም መጀመሪያ? ፍልስፍናው እንደሆነ የት ይሄድበታል? ሲሪየስሊ፣ ምንድነው ግን ፊዩቸራችሁ?" አለች፣ ሙሉ ስሙሉ ወደ ማርታ ዘራ ለመቀመጥ ትራቪን እያመቻቸች።

"እሱስ ችግር አልነበረውም። ሰርሱ ደስ ካለው ይሁን፣ ግን ደግሞ በቃ ... ሁሉም ነገር ሞልም ብሎብኛል። ናፍቀቱም ነው መሰለኝ ..." ብላ፣ ካልጋዋ ላይ ፍንጥር ብላ ተነበታ በባዶ እግሯ ቀንጠር ቀንጠር እያለች ሄዳ የመስኮቱን መጋረጃ ከፈተችው። ሰማዩ ገና መላቀቅ እየጀመረ ነው። "እስኪ እዩው ... ሌሊቱ ይነጋል፣ ደመናውም ዞሮ ዞሮ ሲበታው ያዘለውን ትነት አተዝትዞ ውሃ ያደርገውና ይዘንባል። አበባው ውበቱን እርግፎ ፍሬ ይሆናል። የኔ ህይወት ብቻ ሁሌም ባለህበት እርገጥ ... እንቄሞ እንደሆነ የሚኖረው እስከመቼ ነው?" አለች። መስኮቱን ሙሉ ለሙሉ ስትከፍተው ቀዝቀዝ የማለጻ አየር የጋለ ፊቷን በረድ አደረገላት። ምስጢርም ከአልጋዋ ወርዳ በስስ ፒጃማዋ ላይ የማታ ጋወኗን ደርባ በገሞታ ካጠገቧ ቀመች።

"ይሄም ደግሞ ያልፍና ... እንደገና አብራችሁ ትሆኑና መሳቃችሁ አይቀርም። አይዞሽ" ስትላት፣ ዞር ብላ አተፈቻትና አንገቷ ስር ገብታ ማልቀስ ጀመረች። "እንዴ! ምነው ማርቲ? ኧረ አይዞሽ" ብላ፣ ጀርባዋን መታ መታ ስታደርጋት ይባስ እየተንሰቀሰቀች

"ትናንትና ማታና ቅድም በጣም ተጨቃጭቀን ነው ስልኩን የዘጋነው። እሱ ሁሉ ነገር ላይ ይፈላሰፋል። ምን ያህል እንደምወደውና እንደምናፍቀው እንኳ የሚገባው አይመስለኝም። ኡፍፍ ... ሰውንም እንደ እታ ነውስጥሽ አሽቀንጥሮ መወርወርና ትውት ማድረግ ቢቻል እንዴት ጥሩ ነበር" ብላ፣ ስፍራውን ለቀኑ እየለቀቀ ባለው ጨለማ ውስጥ አሻገራ ማየት ጀመረች። እንደ ቀመሙ ሲያወሩ ቀዩና የጠቁ ብርድ ትዝታዘሉ ሲጠነዠርባቸው በሩን ዘግተው በየአልጋቸው ውስጥ ገቡና ወሬያቸውን ቀጠሉ።

@OLDBOOOKSPDF

"ጥይ የኔስ አንደ አዞብኝ ነው ... አንቺ ግን በታ አሻፈረኝ ማለትሽ ነውኮ ስትላት ፣ ሰለምን እንደምታመራ ብታውቅም እንዳልገባት ሆና

"ምኑን ነው አሻፈረኝ የምለው ማርቲ?"

"ምን እንዳላወቀ ትሆኛለሽ ... ቀይ መልኩ ብትዩ ... ቁም ነገረኛነቱ ፣ ምን አነሰው ብለሽ ነው? በዚያ ላይ እሱም ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሳይኪያትሪስት ይሆንና አብራችሁ አገሩን እያሳበዳችሁና እያስተባበዳችሁ አሪፍ ኑሮ ትኖሩ ነበር ... ደስ አይልም?" ስትላት ፣ ከት ብላ በረጅሙ ሳቀች ። ምስጢር ከጥቂት ወራት በፊት ጳውሎስ ሆስፒታል የካውንሰሊንግ ሰይኮሎጂ ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋትን የልምምድ ሥራ ለመሥራት ሂዳ ነበር ። በዛው አጋጣሚ የአእምሮ ሕክምና ጥናት ሠልጣኝ ከሆነው ዶክተር ሲራክ ስር ትሰራ ነበር ። እንዳፈተራት የነገራትን አሟሙታት ነበር ። ካላስተዋወቅሽኝ ብላ ካየችው በኋላ እሺ እንድትለው መጐትጐቷን ተጥላለች ።

"ቀይ ግን አንቺ እሱ ላይ ምን አይተሻል? ተላክሽ ወይስ ሚስጥር ለእሱ እሺ ካላለች ባል አታገኝም ... ምናምን ተብልሽ?" አለቻት ፣ የታች ከንፈሯን ጠመም ረዘም አድርጋ ትከሻዋን እየሰበቀች ።

"እኔ ሰራለሽ ብዬ ነው ... እንደሱ አይነት ቀሽት ወንዶች ከገቢያው ላይ እንደ ሞልያ ተመናምነዋል ። ያሉትም ተይዘው በየሴቱ የፍቅር ሙዚየም ገብተው ሳያልቁ አይቀርም ይባላል" ስትል ፣ ሁለቱም እንደ ሞኝ ትራሳቸውን ይዘው በረጅሙ ሳቁ ።

ትንሽ ጋብ ሲልላቸው ፣ "የኔ እህት ... እኔ ካገኘው ሴት ጋር የሚጓተት ወንድ ደስ አይለኝም ። በዛ ላይ ልጁ ትንሽ በራሱ የተሞላ ልብ አድርቅ ነገር ነው ። ይልቅስ ማሚ አንድ ከወጪ የመጣ ሳይኪያትሪስት በቲቪ አይታ ወትውታ ልትገድለኝ ነው ። እሱም ላሞር ጊዜ አዛው ጳውሎስ ነው የሚሠራው መሰለኝ ። አሱን ካላየሁ ብላ ልትሞት ነው ። ያንቺ ሲራክ ጋ ደውዬለት እንግባባለን ሊያያቸው ይችላል ብሎኝ ነበር ባለፈው ሳምንት" አለች ፣ አይኗን በዘገዘ አድርጋ ባርምሞ እያየቻት ።

"እኔም ኮ ጠርጥሬያለሁ ሚሲ ... በማሚ እያሳበብሽ እንዲህ ነው እንጂ ልጂት ። ዳያስፖራው ይሻላል ብለሽ ነው? ግን አሪፍ አትችኩልም ትዪ የለ ... ሁሉም ነገር ቀስ ቀስ እያሉ ነው ። የምር ቀልጠፍ ነው ... ካልሆነ ደግሞ ይቀራል ... እንኳን ስው ኩላሊትስ ይቀየር የለ እንዴ?" ስትል ፣ የያዘችውን ትራስ ወረወርችባት ። በትራሷ መክታ በተራዋ የሷን ትራስ ስትመርመርባት አፍና ያዘችው ። እሁዱ ሙሉ ቀኑን የባጥ የቆጡን እያወሩ ማሳሸና ሳውና ፣ ዋናና የጀልባ ጉዞ ሲሉ ቀኑ ሳይታወቃቸው አለቀ ።

በማግስቱ ሰኞ ከሰዓት በኋላ ላይ ዘግየት ብለው ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመሩ ። መንገዱ እንደ ወትሮው የተጨናነቀ አልነበረም ። የመቅደም አባዜ የያዛቸው ቀሽቃሻ ሚኒባሶችና ሽክም ከብዷቸው እየቃተቱ የሚጉተቱ ከባድ መኪኖች የሚፈጥሩት መላ ያጣ አነዳድ ብቻ አልፎ አልፎ ሞጉንጉን ይፈጥራል ። አንድ ጊዜ ቀለበት መንገዱ ውስጥ ከገቡ በኋላ በበለጠ በፍጥነት መንዳት ቻሉ ። ጉርዱ ሾላ አካባቢ ሲደርሱ ያለ

@OLDBOOOKSPDF

ወትሮው ጸጥ ብሎ የዋለውን ስልኳን አወጥታ ስታየው ባትሪው አልቶ ጠፍቷል። የመኪናው የባትሪ ሃይል መሙያ ላይ እየሰካችው፣

"እይገርምሽም ማታ ቻርጅ ሳላደርገው ባትሪው አልቶ ነው ለካ። ስልኩ መጥፋቱንም ልብ አላልኩትም ነበር። እኔኮ ያለወትሮ ዝምታው ገርሞኛል። ማሚ ይሄኔ ነፍሲ ሊወጣ ደርሷል። አይ አም ሹር እስካሁን ሠላቶ ጊዜ ደውላለች።"

"ግን ምን አስጨነቀሽ እንቺ? ዝም ብለሽ እኮ ነው። እንደ እኔ እንደ እኔ ... ቢያንስ ትናንትን ብትገኚላቸው ምንም አልነበረም" ስትላት፣ ነሰተርተር አለችና በታ በሚል አይነት እጇን ነፍ አድርጋ፣

"እዪ ማርቲ ... እያወቅሽ አታሰለፍልፊኝ" አለች፣ ማወራትም እንዳልፈለገች። እነ ማርታ ቤት ሲደርሱ አስራ ሁለት ሰአት አካባቢ ነበር። ግቢ ውስጥ ቆመው እያወሩ የምሰጪር ስልክ ደጋግሞ ጮኸ። የማታውቀው ቁጥር ስለነበር እያመነታች አነሳችውና፣

"ማነው በናትሽ ዝም ብሎ ደጋግሞ የሚደውልልኝ" ብላ "ሃ...ሎ" ስትል፣

"እ-ን-ዴ---ት ነሽ የኔ ልእልት ... ደብረዘይት ጥሩ ነበር? በጣም አምሮብሽ ነበር" አለ ጉርጋን ያለ የሚገተትና የምታውቀው ድምጽ።

በድንጋጤ ስልኩን ከእጇ ላይ የመወርወር ያህል ጣለችውና፣ "እሱ ነው፣ እሱ ነው፣ ወይኔ ማሚዬ፣ ደብረዘይት እንደ ነበርኩ ሁሉ ያውቃል። ቁጥሬን ደግሞ ከየት አግኝቶት ነው ይባላል?" አለች፣ የጓደኛዋን ትከሻ ጭምድድ አድርጋ።

ማርታም ግራ ገብቷት፣ "ምንድነው እሱ? ማነው? ምን ሆነሻል?" ስትላት፣

"ማስረሻ ነው፣ ማስረሻ ነው የደወለው። ይሀን ታግሶለት ጠፍቶ ነበር። ደግሞ ሊነሳበት ነው መሰለኝ" አለች፣ መርበትበቷ ሳይቀንስ።

"ቀይ ተረጋጊ እስኪ። በመጀመሪያ፣ እርግጠኛ ነሽ እሱ ነው? ቀይ ውጪ ሄዷል ተብሎ አልነበረም እንዴ? ምን አይነት ጣጣ ነው ባካቹ። ግን እርግጠኛ ነሽ እሱ ነው?" አሰኝ፣ ስልኩን ከወደቀበት አንስታ ቁጥሩን እያየች።

"እም ሪሉ ነው ማርቲ። ደብረዘይትም ተከትሎን መጥቶ ነበር ማለት ነው። በቃ አሁን ሳያመሽ በገዚ ልሂድ፣ ማሚም ታስባለች" አለች፣ በመርበትበት ድፎ ዶጁን እያናች።

"ቀይ ብሪዘርን ልጥራውና፣ ለማንኛውም ተከታትሎን እንሸኘሽ። ዩ ነቨር ኖው፣ ይሄ አብድ የሆነ ሰውዬ እንዲያው ምን ይሻለዋል? ምን እይነት አበሳ ነው በናታቹ። አያሳሽ ቀንጅዩ" አለች፣ ተንጠራርታ እያቀፈቻት። ወንድሟን ከቤት ለመጥራት ስትዶልል፣ ምሰጪርም ለእናቷ 'እየመጣሁ ነው፣ መንገድ ላይ ነኝ' ብላ ነገረቻቸው። ማስረሻ ከየኒቨርሲቲ ተማሪነቷ ጀምሮ እየተከታተለ መከራዋን ሲያሳያት የኖረ እወድሻለሁ ባይ እያደባ ያሸበታተላት ሰው ነው። እንዲተኛት ያላደረገችውና

@OLDBOOOKSPDF

ያልሞከረችው ነገር ባይኖርም ትኮ ሊተዋት አልቻለም ። ሳለፉት ዘጠኝ ወራት ፕሩት ብሎ ከርሞ አሁን ደግሞ ድንገት መነሰቱ ነው ። ብዙ ጊዜ ሲገድላት ዝቷል ።

ማርታ ለወንድሟ ከነምስጢር ቤት እቃ ይዘን እንምጣ ብላው፣ እሱ እየተከተላቸው ወደ የረር ጽዘሮስ አመሩ ። ስአቱ ማታ አንድ ተኩል ሊሆን ነው ። እቢት ሲደርሱ በመጠኑ መረጋጋት ችላ ነበር ። ማርታ የምስጢርን እናት በቁሟ ሰላም ብላ፣ እራት ብዪ ብትባልም ሰው አቁሚያለሁ ብላ ፈጥና ወጣች ። ሳሎን ውስጥ ለብቻቸው ተቀምጠው ቲቪ ሲያዩ የነበሩት እናቷ ልጃቸውን ሲያዩ ከሜንቀታቸው ተንፈስ አሉ ። ቁጣቸው እንደማይሰራ ስለገባቸው ለማኩረፍ ሞከሩ ። ልታጥራቸው በሞከረች ቁጥር ወይ አጭር መልስ ይሰጧታል ወይ ደግሞ ትከሻቸውን እየነቀነቁ አይናቸውን ቴሌቪዥኑ ላይ ሰክተው ዝም አሏት ።

"በናትሽ ማሚዬ ተቀየተሳል አውቃለሁ ... ይገባኛል እኮ... እሺ በቃ ...ሶሪ በጣም... ካሰብኩት በላይ ፕሮግራሜ እቀየኝና በጊዜ መምጣትም አልቻልኩም ። ፕሊ--ስ" አለች፣ ግድግዳውን ደገፍ ብላ ጫማዎቿን ከእግሯ አውልቃ ወዲያና ወዲህ እያሸቀነጠረቻቸው ። የለበሰችውን ስስ ጃኬት አንዱ ሶፋ ላይ መረመረችና የናቷን ጉንጭ በግድ ስባ በስሱ ሳመቻቸው ። አጠገባቸው እንዘጭ ብላ ተቀመጠችና በረጅሙ ተነፈሰች ። ቁጣቸው የማይቀየው እናቷም ስሜታቸው ትንሽ በረድ ሲልላቸው በግርምት አይን የነሪጥ እያዩዋት

"ምነው ልጄ እንዲያው ሰው ያስባልም አትይም እንዴ? እንግዳው ሁሉ ሚሚስ ሚሚስ ሲል፣ አኔንም እኮ አሳጣሽኝ ። ደጅ ደጁን እንዳዩ ነው ያሄዱት፣ ያባትሽ ዘመዶችማ በቃ ላይተየሙም አይቀር ። ቢያንስ ማለቂያው ላይ ብቅ ብለሽ ፊትሽን ብታስመቺ ምናለ ። ደግሞ ስልክሽን አንኳ ብትመልሽስ ልጄ? ስልክ መዝጋት ደግሞ ከመቼ ወዲህ ያመጣሽው ጸባይ ነው? " ሲሉ፣ የበለጠ ተጠጋቻቸውና እጇን አንገታቸው ላይ ጠምጥማ ዓይን ዓይናቸውን እያየች ።

"ስልኩ ባትሪ ምቶብኝ ነው አኮ ። ማሚዬ ሙች፣ አታምኚኝም? ደግሞ ማሚዬ ያው ታውቂው የለ፣ እዚህ ተሰብስበው እኮ ሰው መቦጪት እንጂ ሌላ ምን ሥራ አላቸው ብለሽ ነው ። በቃ ድከም እኮ ነው የሚያደርጉኝ ። ትዩ ዘሚስ ... መቼ ሄደች? በጣም ነው የናፈቀችኝ" አለች፣ በዛውም የነገሩን አቅጣጫ ለማስቀየር ።

"ባሏ ድንገት ታምባት ሆስፒታል ስለ ገባ መምጣት አልቻለችም ። ደውላ ግን ሰላም ብላኛለች ። ሻል ካለው ለሚቀጥለው እሁድ እመጣለሁ ብላለች ። " ከሟች ባለቤታቸው ዘመዶች ወይዘሮ ዘምዘም ብቸኛ የቅርብ ጓደኛቸውና የረጅም ጊዜ ምስጢረኛቸው ናት ። ሚስጥርም ከአባቷ ዘመዶች የምትቀርበው እርሷን ብቻ ነው ።

"ውይ ምን ሆነ?" አለች፣ ደንገጥ ብላ ።

"ያንጀት ሙታጠፍ ነው መሰለኝ ያሉኝ ። "

"የኔ ናት አሁን እሱ ለራሱ ምን አንጀት አለውና ነው በጎትሽ ። እስኪ ነገ ደውዬላት እሄዳለሁ" ብላ፣ አጠገቧ ተመቻችታ ተመለጠች ።

@OLDBOOKSPDF

የምስጢር አባት ገና በህይወት እያሉ ንብረት ያላቸውን ንብረት ሁሉ በስማቸው ሙሉ መራሽ ያደረጓት ። ይህም ሆኖ ከአባቷ ሞት በኋላ እናቷንና እሷን ከንብረታቸው ለማፈናቀልና ለመቀራመት ቢተሰቡ ያልፈነቀሉው ድንጋይ አልነበረም ። በተጨማሪም አባቷ በጠና በታመሙ ጊዜ መይዘር ዘምዘም ብቻ ነበረች ከጎናቸው የቀመቻቸው ። ድንገት ብድግ አለችና ከቴሌቭዥኑ አንጻር ከፍ ብሎ የተቀመጠውን ትልቅ ያባቷን ፎቶግራፍ አንስታ በፊቱ ደፍታ ከታችኛው መደርደሪያ ላይ ስታስቀምጠው

"እንዴ! ምነው ልጄ፣ ደግሞ እሱ ምን አደረገሽ? ለዛሬ እንኳን ይሁን እስኪ" እሱ እያመነቱ ።

ወደ እርሳቸው ዞር ብላ ቀጣ ባለ ድምጽ፣ "ይበቃዋል ... ይበቃዋል ። በህይወት እያለ ያፈጠጠብን ይበቃዋል ። ቤቱ ሀያዋን የሚኖሩበት እንጂ ሙታን በመንፈሳቸው የሚዝበት አይደለም ። እንዲያውም ነገ የሆነ ቦታ ካላስገባሽው ወደ ጓሮ ሊጣልም ይችላል ። ሁሉም ያው ናቸው ። ያሉትም ከሞቱት አይሻሉም ። የራሳቸውን ሙት ህይወት ለማረሳሳት፣ ሌላ ሟች ለማኖር ይንገዳገዳሉ" አለች፣ ሰሚቷ እየጋለ ። እነጋገሯ ድንገጥ ቢያደርጋቸውም የውስጥ ሰሚቷን ስለሚረዱ፣ ደግሞም በዚያ ሰዓት ከርሷ ጋር ለመሟገት ምንም ፍላጎት ስላልነበራቸው መሬያቸውን ወደ ሌላ ሃሳብ ቀየሩት ።

"እስኪ ቴሌቪዥኑን ዘፈቺው ሚሚዬ ሰአቱም ደርሷል መሰል እኮ ። "

"የምኑ ነው ሠዓት ነው የደረሰው?" አለች፣ ሠዓቷን እያየች ። ትንሽ እንደ መቁነጥነጥ እያደርጋቸው

"ረሳሽው እንዴ ልጄ? ያ ዶክተሩ፣ ማን ነበር? ዶክተር ሌላው ነዋ ። ጓው-ሎስ ነው የሚሰራው ብለዋል ብዬሽ ነበር ። ጎደኞችሽን ጠይቂሽ ቀጠሮ ልታስይዝልኝ አልነበር እንዴ? ያንቺ ነገር፣ ይሄኔ ረስተሽዋል እኮ ። የቴሌቪዥኑ ኢንተርቪው የመጨረሻው ክፍል ዛሬ ነው ። አስራ ምስት ደቂቃ ነው የቀረው ሊጀምር"

"እይ አልረሳሁትም ማሚ ። እንዲያውም እዛ የሚሰራ አንድ የማውቀው ዶክተር አለ ። ሰሱ በቀደም ደውዬለት ነግሬው ነበር ። ቀይ እንዲያውም አሁን ልጠይቀው እስኪ" አለችና፣ ትንሽ ተንጠራርታ፣ "አ...ፍ... ፍ ... ድክም ብሎኛል ። እስኪ በዛውም ልብሴንም ቀያይሬ መጣሁ ። ውሃም ጥምት ነው ያለኝ፣ መጣሁ እሺ ማሚዬ..." ብላ፣ ቦርሳዋን እንደነገሩ እንጠልጥላ ወደ መኝታ ቤቷ ሄደች ።

"እንዳያመልጥሽ ቶሎ ነይ ታዲያ ..." ሲሉ፣ ዞር ብላ በፈገግታ እየት አድርጋቸው

"እደርሳለሁ ማሚዬ ። ካልደነግቸው ልጅቱ ቡና ቢያፈሉልን እንዴት ጥሩ ነበር ። " መኝታ ቤቷ እንደ ገባች ከቦርሳዋ ውስጥ ስልኳን አወጣችና ወለሉ ላይ ጣል አደረገችው ። አልጋዋ ላይ የመጠረመር ያህል ተዘረረችና በጀርባዋ ተንጋላ ጣራ ጣራውን እያየች ጥቂት ቀየች ። ከዚያም ከቁጥሮቹ መሃል ዶክተር ሲራክ የሚለውን መርጣ ደወለች ።

እንዴ እንደ ሙነ አነሳው ። "ሃሎ ... ሃሎ ... ሚ-ስ-ጥ-ር? ታዲያስ ... ሰላም ነው?" አለ በሹቀጥቀጥ አነጋገር ።

@OLDBOOOKSPDF

"ሄ...ይ ዶክተ-ሩ እንደ-ት ነሀ" አለች ፣ ትላጺው ሞልቶት ባለና ሙዚቃዊ ሳ
በተሞላ ድምጽ ።

"አለን ደሀና ፣ ያው ሥራ ምናምን ትንሽ ይበዛል ። ደው-ዬልሽ እኮ ሰልክሽ
እምቢ አለኝ ። አሁን አንደገና ልሞክር ስል ነው የደወልሽው ። የናትሽን ጉዳይ፣
ዶክተር ሌላው ነገ ጠዋት ይምጡ ብሏል ። ብታይ በጣም የተመቸው ቀሽት ሴ
ነው ። አለ አይደል ... የገባው ነገር ... አሪፍ ሳይኪያትሪስት ነው" አለ ፣ ፈጠን ባ
ድምጽ ። ግዳዩን መጣሉ ነጥብ እንደሚያሰጠው ተስፋ አድርጓል ።

"ሪሊይ? እንተ ይሀንን ያህል ካደነቅኸው ፣ እውነትም አሪፍ መሆን አለበት።
እናቴ ደግሞ እንዴት እንደምትመርቅህ ልነግርህ አልችልም ። ታዲያ ስንት ሰአት
ብንደርስ ጥሩ ነው?" አለች ። ሲራክ እንኳን እንዲህ ለማድነት ቀርቶ ለብዙ ሰዎች
ያለው ንቀት ሰማይ የነካ እንደሆነ ስለምታውቅ ገርሟታል ።

"በቃ ሦስት ሰአት አካባቢ ብትደርሱ ፣ ከጠዋት ሰብስባ እንደወጣ ሰው ሳይበ
መጀመሪያ ሊያያቸው ይችላል ። ከቻላችሁ ለምን እዛ ... በገን በር በኩል ያለችው ካፌ
አንገናኝም ። እኔም ከቀደምኳችሁ እዛው እጠብቃችኋለሁ"

"ባጣም ... አሪፍ ነው ። እዛው አይሃለኋ እንግዲየው ። ታንክ ዩ ሶ ማች እሺ
ሪ...ሊ....ይ ..." አለች ፣ ደስ ብሏት ።

"ኧረ ምንም አይደል ፣ ሌላስ ነገር ቢሆን"

"እኔ የምልህ አንተ ግን በዚህ ወር ጻውሎስ አይደለሁም ያልከኝ መስሎኝ
ባለፈው ። ለኛ ብለህ ነው እዛ ድረስ የምትመጣው?" አለች ፣ አማኑኤል ነኝ ያላትን ነ
ብሏት ።

"እ-ዎ-ን አማኑኤል ነኝ ። ነገ ግን ብዙም የሚያስቸኩል ነገር ስለሌለኝ አንዳፍታ
ከርሱ ጋር አገናኝቼያችሁ መሄድ እችላለሁ" አለ ፣ ነገሩን ቀለል እያደረገ ።

"ኦ-ህ ታንክ ዩ ኤጊይን ... ሪ-ሊ-ይ ... ዛት ኢዝ ሶ ናይስ ኦፍ ዩ " አለች ። ወሬየ
ብዙ ጊዜ እንግሊዝኛ ይበዛዋል ። ሪሊይ የምትልበት የራሷ ሙዚቃዊ ቃናም አላት ።

"ኧረ ምንም አይደለም ... ኢት ኢዝ ማይ ፕሌዠር ..." ብሎ ፣ እሱም ንግግሩ
ውስጥ ለማርከሻ ያህል እንግሊዝኛ ጣል አደረገበት ። ሌላ ወሬ ያለቀባቸው ይመስል
ጥቂት ጸጥ አሉ ።

"በቃ ነገ አገኝሃለሁኝ ። አሁን ማሚም እየጠበቀችኝ ስለሆነ ልሂድና ልንገራት፣
እንዴት ደስ እንደሚላት ... ቻዎ እሺ" ብላው ተሰናበቱ ። ስልኩን ከዘጋች በኋላ እንደ
ተጋደመች ውል የሌለው ሃሳብ ስትፈታ ስትቋጥር ትንሽ ቆየች ።

እንዴ ምንም እትሚን ሰብስባ ከተጋደመችበት ብድግ አለችና ከቱም ሳጥኑ ውስጥ
የምትተይረውን ፒጃማና ፎጣ አወጣች ። ልብሶቿን አወላልቃ አልጋው ላይ እንደነገሩ
ወርውራ ሻወር ውስጥ ዘላ ገባች ። ከሻወር እየተቀባባች ከመስታዎቱ
ራት እንደቀመች ተነስ ስትሰማ የሞለችውን አዲስ ሙዚቃ ለራሷ ማንባራገር ጀመረች ፣

የቀጻጥ መልክ ጥይምና ወደ ቅላት ያዘነብላል ። ሰውነቷ ሞላ ያለ ቢሆንም ደስ የሚል የሴትነት ቅርጿ በቀላሉ ዓይን ይገባል ። በመካከለኛ ቁመቷ ላይ ሁሌም ከፍ ያለ ሜማ ስለምታደርግ ከሆነችው በላይ ረጅም ትመስላለች ። አይኖቿ ትልልቅ የሚባሉ ባይሆኑም በስሜት የተሞሉና ጥቅጥቅ ባለ ሽፋል የተከበቡ ናቸው ። ከማየት ተግባራቸው በላይ እንደሚያበሩ ባለፈርጥ ጌሞች ታይተው አይጠገቡም ። በተለይ ስታስባቸውና ስትስቅባቸው የበለጠ ያምራሉ ። ጸጉሯ ሁሌም አጭር ነው ። ከብዛቱ ጋር ፍሪዝ ስታደርገው ፊቷን በጥቁር ጫካ የተከበበ ውብ መስክ ያስመስለዋል ። ፒኟማዋን ለባብሳ እንደ ልማዷ እየተጎዶረዶረችና ደረጃው እያንደዛደዘች ወደ ሳሎን ስትደርስ ፕሮግራሙ ተጀምሮ ነበር ።

"ብዙ አመለጠኝ እንዴ ማሚዬ?" አለች ፣ አጠገባቸው ተቀምጣ ጋቢያቸውን ለመጋራት እየሞከረች ።

"አይ ብዙም አይደል ፣ ስጠራሽ እኮ ሻወር ውስጥ ነበርሽ መሰል አልሰማሽኝም ። ደወልሽ እንዴ ጓደኞችሽ ጋ?" አሉ ፣ መጓጓታቸው በሚያስታውቅ ድምጽ ጋቢውን የበለጠ እንድትጋራ እያስተካከሉላት ።

"እምን ለነገ ጠዋት ቀጠሮ አስይዘውልሻል ። መጀመሪያ እንዲያይሽ ሶስት ሰአት መድረስ ይኖርብናል" አለች ፣ ሙሉ ለሙሉ ሶፋው ላይ እግሮቿን አውጥታ በጋቢው ተሸፋፍና እየተቀመጠች ። እውነት እንዳልመሰላቸው ሁሉ ድንግጥ ብለው

"ነገ? ... ከዶክተር ሌላሠው ከሱ ጋር?" አሉ ፣ ዓይናቸውን ሚስጢር ላይ እንደ ተከሉ ወደ ቴሌቪዥኑ ጣታቸውን እየጠቆሙ ። የናቷ አባባል የገረማት በሚመስል አይታ አፏን ጠመም አድርጋ

"እምና ፣ ማሚ ደግሞ ዝም ብለሽ ነው እኮ የምታካብጂው ። እሱ የሆነ እንደሆነ ምንድነው? ምን የተለየ ነገር አለው ብለሽ ነው" አለች ፣ ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ ። ምናልባት ብዙ ነገር ጠብቀው ተስፋ እንዳይቆርጡም ሰግታለች ።

"አይ ልጄ ... እንቺ የማታውቂው ስንት ጉድ ... ስንት ህመም አለኝ መሰለሽ ። ይሄን ዶክተር ፈጣሪ ለኔ ብሎ ፣ መድሐኒያለም የነገሩትን የማይረሳ የጠየቁትን የማይነሳ በጥበቡ የላከልኝ መፍትሄ ነው ። በጣም ነው የማመሰግንሽ" ብለው ፣ ራሷን እያሻሹ ትከዝ ሲሉ ፣

"እንዴ ማሚ ደግሞ ምንድነው እንደዚህ መሆን ። ደግሞ እኔን የምታመሰግኚው ምን አድርጊልሽ ነው? ምንድነው እኔ ማላውቀው ችግር አለ እንዴ?"

"አይ ተዪው ፣ እንዲያው ዝም ብዬ ነው ። እስኪ ድምጹን ጨመር አድርጊው ። ሰባሬ ያለውን ውይይት ሊጀምሩ ነው መሰል" አሉና ተመቻችተው ተቀመጡ ። ጋዜጠኛዋ አስቀድማ የመግቢያ ማስተዋቂያዋንና ስላለፈው ሳምንት ንግግራቸው አጠቃላይ የክለሳ መግለጫ ሰጠች ። አሰከትላ በሚጎትትና በፍርሃት ዙሪያ ላቀረበችለት የመጀመሪያ አጠቃላይ ጥያቄ መልስ በመስጠት ላይ ነበር

@OLDBOOOKSPDF

"ባጠቃላይ ሞንቶት የሚለው ያማርኛ ቃል ለብዙ ነገር ስለምንጠቀምበት የሚወክለውን ትክክለኛ የስሜት ስቃይና ሀሙም ለመለየት አዳጋች ነው። ለድብርትም፣ ለእእምሮ መታወክም፣ እንዲሁም ለሌሎች ድብልብስ ስሜቶች ሁሉ ሞንቶት የሚለውን ቃል ስለምንጠቀምበት እሱን ትንሽ ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል። ዛሬ ከምናወራው ሃሳብ እንጻር ሞንቶት የምንለው ውጥረት ያየለበት በጊዜው በእውኑ አለም ከተፈጠረ ክስተት ጋር ተዋተኛ ዝምድና የሌለው ወይም ከእውነታው ጋር ያልተመጣጠነና የተጋነነ የፍርሃት ስሜትን ነው።

"ፍርሃት በምንልበት ጊዜ ግን በየዕለቱ ኑሮአችን ላሉ በእውኑ አለም አስፈሪ ለሆኑ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች የምናሳየው ስሜት ስለሆነ ብዙ አሻሚ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ ብቻሽን ሆነሽ እውሬ ቢመጣብሽ፣ ፎቅ ላይ ሆነሽ እሳት ቢነሳ፣ የታጠቁ ሌቦች ባላሰብሽው ሰአት ድንገት ቢያግቱሽ ... ይሄ የሚፈጥረው የፍርሃት ስሜት የጤና እንጂ የበሽታ ሊባል አይችልም።

"ነገር ግን አንድ ሰው ባለፈ ጊዜ ውስጥ ያጋጠመው አሰቃቂና አስፈሪ ሁኔታ ልክ ዛሬ እንደሆነ በፍርሃት ጠፍሮ ሲይዘው ... ወይም ... ገና ለገና መደፈት ይደርስብኛል አልያም ይሆናል ብሎ ውስጡ በሚፈጠረው ስጋት ከልክ ባለፈ ፍርሃት ሕይወቱ ቢመሰቃቀል ሀሙም ሊሆን ይችላል።

"እ ም...ም ... ወይም ደግሞ ለምሳሌ እንደ ሽረሪትና የመሳሰሉ ሌሎች በአብዛኛው ሰዎች ከምንም የማይቀጥሯቸውንና አደጋ የማይፈጥሩ ነገሮችን፣ ማየቱም ሆነ በአካባቢው መኖራቸውን በማሰብ ብቻ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ፍርሃት ሲርበደበድ ... 'እንዛይቲ' ብለን በምንጠራቸው የተለያዩ ከፍተኛ የሞንቶትና የመረበሽ ስሜት ያዘሉ የእእምሮ ሀሙም አይነቶች እየተሰቃየ ሊሆን ይችላል።

"ሁሉንም በያምሳላው የሞንቶት ሀሙም ወይም 'እንዛይቲ' ብንላቸውም የተለያዩ ሀሙሞችን በስሩ አቅፎ የያዘ ጥቅል የሀሙም አይነት ነው" ብሎ መለሰ።

ምስጢር አፏን ጠመም አድርጋ፣ "ሽረ ... ሽረ ... ሰውዬው ከሜሪካ ነው ከጎንደር የመጣው? አማርኛው እንዴት አረጉ ነው ባክሽ። ደግሞ ዘናሞ ቢጤ ነገር ይመስላል። እኔ እኮ በጣም ትልቅ ሰው መስሎኝ ነበር" አለች።

"እኔም ባለፈው ሳምንት ከየሁት በኋላ ቀልቤ በጣም ነው የወደደው" አሉና የሚቀጥለውን ጥያቄ ለመስማት ዝም አሉ።

ጋዜጠኛዋ ጥያቄዋን ቀጠለች። "እሺ ዶክተር ነገሩን እንዳልከው ለጊዜው የሞንቶት ወይም የፍርሃት ሀሙም እንበለው። አይነቱም መንስኤውም ብዙ ነው ብለኸናል። እኛ አገር ደግሞ እንዚህ ሀሙሞች ገና ሀሙም እንደሆኑ እንኳ ግልጽ የሆነ ስም ተሰጥቷቸው እውቅናንም ያገኙ አይመስሉም። ለምሳሌ ብዙ ሰው ቅድም እንዳልከው ሽረሪት፣ አይጥ፣ ድልድይ፣ ዉለማ ምን ልበልህ ብዙ ነገር ይፈራል ... ለምሳሌ እኔ አንድ ጓደኛ አለኝ ፍየል በጣም ነው የሚፈራው ... የፍየል ፎቶ እንኳ ሲያይ ይቀፈጥል። ይሄንንስ የአእምሮ ሀሙም ነው ልንል እንችላለን ማለት ነው? መፍትሔስ አለው?" ስትለው

@OLDBOOOKSPDF

"እዎን ሀመም ሊሆን ይችላል። አንድ ነገር የአእምሮ ሀመም ሊባል የሚችለው፣ የተፈጠረው የስሜትና የአስተሳሰብ ስቃይ ዘፍተኛ ሆኖ የተለመደውን ዕለታዊ የግንኙነት፣ የስራና ማህበራዊ ህይወትን ሲያዛባ ብቻ ነው። ስለዚህ እንዚህ ጥቃትን የሚመስሉ ፍርሃቶችም የአንድን ሰው ህይወት በመቆጣጠር ከባድ በሽታ ሊሆኑ ይችላሉ።

"በጣም የሚገርምሽ ነገሉት የሞንቲቃዊ ፍርሃት ሀመሞች (አንዛይቲ) ውስጥ ብዙ ሰዎችን በማስቃየት ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው የዚህ ዓይነቱ ችግር ነው። በህክምናው 'ርቢያ' እንለዋለን። በዋናነት በተለያዩ የምክር ዘዬዎች፣ በተወሰነ መጠን ደግሞ በመድሃኒት የህክምና መፍትሄ ሊኖረው ይችላል። በርግጥ አውን ካለን ስእትና ከፓሮግራሙ ይዘት አንጻር ሁሉንም ለመዘርዘር ያጻግታል" ሲል፣ ጋዜጠኛዋ ተበለ አድርጋ፣

"ዋሩ ዶክተር ... ያው እንጸልከው ከጊዜም አንጻር ዝርዝር ውስጥ ለመግባት አስቸጋሪ ነው በርግጥ። ግን በተለይ ዛሬ ትንሽ ገለጥለጥ አድርገን እንድንወያይ የምፈልገው የሞንቲት-ፍርሃት ሀመም ዓይነት አለ። ምናልባትም ባገራችን በጣም በከፍተኛ ደረጃ ብዙ ሰው የሚሰቃይበት ጉዳይ ሊሆን ቢችልም ገና ሀመምነቱ እንኳ በቅጥ መታወቁንም አጠራጠራለው። በናንተ የህዘምና ሂንጂ 'ፖስት ትራውማቲክ ስትረስ ዲስኦርደር' የሚባለውን ማለቱ ነው። በአማርኛ ስመተርገም ያስቸግራል ... ምን እንበለው?" አለችና የያዘችውን መረቀት ከራት ለፊቷ ያለው ጠረጴዛ ላይ አስተመጠች።

"እ... ም ...ም ያው እንጸልሽው በቅጥታ ወደ አማርኛ መተርገሙ ከባድ ነው። ሃሳቡ ግን ሰው ከደረሰበት ከባድ የሆነ አሰቃቂ እደጋ ወይም ዘስተት በመከተል የሚፈጠር በሞንቲት የተመላ የፍርሃት ሀመም ነው። ይሄ አሰቃቂ ክስተት በሀመምተኛው ላይ የደረሰ ወይም ሀመምተኛው በቅጥታ ባይኑ ያየው፣ የተሳተፈበት ከፍተኛ እደጋ ወይም ጉዳት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የቅርብሽ የሆነ ሰው ያለፈበት አሰቃቂ ነገርም ሊሆን ይችላል።

"ለምሳሌ አንዲት ሴት ተገዳ ብትደፈር ወይም ሌላ ሴት ስትደፈር ብታይ ... እም ...ም ወይም በጦር ሜዳ ላይ በሚደርሱ አሰቃቂ ግድያዎች ላይ የተሳተፉ ወይም የቅርብ አጋሮቻቸው በሚዘገንን ሁኔታ ሲገደሉና ስቃይ ሲደርሰባቸው ማየት ሊሆን ይችላል። ሌላው ሕፃናትና አዳጊዎች ላይ የሚደርስ የአካል፣ የወሲብና የስሜት ጥቃቶች በብዛት የሚታዩ መንስኤዎች ናቸው።

"እነዚህ ሁሉ እንግዲህ ወዲያው ከሚፈጥሩት ሜሪና ስቃይ በተጨማሪ በአእምሯችን የትዝታ ማህደር ውስጥ ለመፋትና ፈጽሞ ለማጥፋት በማይቻል ሁኔታ ይመዘገባሉ። ከጊዜ በኋላ በተለያየ ምክንያት አእምሮሽ እነዚህን ያለፉ ክስተቶች ለተወሰነ ጊዜ ቀልር ያሸገበት ካገና ላልቶ ሲከፈት ትዝታዎቹ እየሾለኩ ይወጡና እንደ አዲስ ክስተት መሆን ይጀምራሉ። ሞንትላትሽ ልክ እንደ ካሴት እየደጋገመ ሲያጫውታቸው የሚፈጠረው ስቃይ እንዳንድ ጊዜ ነገሩ በተፈጸመበት ጊዜ ከሆነው

@OLDBOOOKSPDF

የነፋ ሊሆን ይችላል ። በኔ ግምት በሀገራችንም በጣም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሕፃናትና አዋቂ ሰዎች በዚህ ስታይ ውስጥ ማንም ሳያውቅላቸው የሚኖሩ ይመስለኛል" ብሎ ራቱ ካለው ውሃ ገንጪት አለ ። ምስጢርና እናቷ ሄኖ ብሰው ማሻመጥ ተያይዘዋል ። ከፊታቸው የተረበውን ራትም ልብ ያሉት አይመስልም ።

"ወደ ተጨማሪ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት ዶክተር ለምሳሌ የዚህ አይነት ችግር ያለበት ሰው ምን አይነት ምልክቶች ሊታዩበት እንደሚችሉ ብታብራራልን" ብላ ፣ የተቀመጠችበት ሶፋ ላይ ለመመቻቸት ሞከረች ጋዜጠኛዋ ።

"እንግዲህ ያው ከሰው ሰው ቢለያይም አጠቃላይ የሆኑ ምልክቶች አሉ ። በተለይ ሕፃናት ላይ ምልክቶቹ ለየት ሊሉ ይችላሉ ። በወንድና በሴት መካከልም መጠነኛ ልዩነት ሊኖር ይችላል ። እንዴ ጉዳቱ ልክ ፣ እንዴ የሰጪ የሰብእና እመቃቀርና ነገሮችን የመቋቋም ችሎታ ምልክቱ መለያየቱ አይቀርም ። በአጠቃላይ ግን ሁል ጊዜ በእደጋ ተጠና ውስጥ እንደሚኖር ሰው በስጋት መሞላት ፣ ከፍ ያለ ድምጽና ጩኸት ሲሰሙ መደንበርና ድንጉጥ መሆን ፣ ሌሊት በእንቅልፍ ትዝቦትና ቀንም በንቃት ለእት ላይ የደረሰባቸውን ወይም የችግሩ መንስኤ የሆነውን ሰዎታ ደጋግሞ ደጋግሞ በዓይነ ህሊና ማየትና ልክ አሁን እንደሆነ ያህል መሰቃየት ፣ በዚህም የተነሳ በቀላሉ ብስጩና ሆድ ቡቡ መሆንንም ያጠቃልላል ።

"በተጨማሪም ሌሎችን ማመንና ዘና ብሎ መኖር አለመቻል ፣ እንዳንዴም በተለያዩ ሱሶች በመጠመድ ስታይን የመሸፈን ዝንባሌ ይታያል ። የደረሰውን ሰቆታ ሊያስታውሱ ከሚችሉ ሰዎችና ሁኔታዎች መሸሽና እንዳንዴም ከፍተኛ የሆነ የስሜት መዋዠቅና ብሎም ከባድ ድባቴ ውስጥ መግባትም በብዛት ይታያል ። ብቸኝነትና ከሰው አለመግባባት ፣ እንቅልፍ ማጣት ፣ ጸጸትና በማይገባ ደረጃ ራስን መወቀስም አለ ። ግን እንዳልኩሽ ነገሩ ከሰው ሰው ይለያያል ፣ ደግሞም ሁሉም ምልክት ሁሉም ሰው ላይ ላይታይ ይችላል" ብሎ ፣ ራሱን እያነቃነቀ እጁን እጣምሮ ወደ ኋላ ደገፍ ብሎ ተቀመጠና ዝም አለ ።

"ጥሩ ... በጣም ግልጽ ነው ዶክተር ። ግን ቅድም እንዳልከው ችግሩ እዚህ አገራችን ውስጥም ትንሽ የሚባል አይመስልኝም ። በሃገራችን ላለው ችግር እንደ መንስኤ ብለን የምንዘረዝራቸው ዋነኛ ነገሮች ይኖራሉ? ይሆን ያህል ችግሩ ብዙ ከሆነስ ለምንድነው ችግሩ ያደባባይ ሚስጥር ሆኖ እያለ ሰው ሁሉ በየቤቱ የሚሰቃየው ትላለህ?" አለችና ማስታወሻዋ ላይ የሆነ ነገር ሚር ሚር አድርጋ ቀና አለች ።

"መንስኤው ብዙ ነው ። ለምሳሌ ከአብዮቱ በኋላ በተቀሰቀሰው ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካና የርእዮተ አለም ግጭት ተይኖ ነጭ ሽብር ውስጥ ብዙ አስታቲ ግድያ ባደባባይ ተፈጽሟል ። በየአስር ቤቱ የተፈጸመውት ግርፋትና ሲንገሩ የማይችሉ ስቃዮችና የሰብአዊ ክብር መደፈር ሰቀታ ሁሉ ባብዛኛው ላይታዘዝም በየሰዉ ልቦና ታፍኖና በየቤቱ ታሽጎ ቀርቷል ። ሕፃናት በጠራራ ጸሃይ የወደቁ ሬሳዎችንና ሊሞቱ የሚያጣጥሩ ወጣቶችን አይተዋል ። እናቶች የልጆቻቸውን ሬሳ በገዝዝ ገዝቷል ።

@OLDBOOOKSPDF

"ባለፉት አርባ አመታት ብቻ የእርስ በርስና ከጎረቤት አገሮች ጋር የተደረጉ ጦርነቶች የፈጠሩት ጥፋት፣ የህይወትና የአካል ጉዳት ሁሉ ምንም ታሪ ሊገልጸው አይችልም። ይህ ደግሞ ምንም ዓይነት ህዝምና ያላገኘ የሰሚት ጠባሳ ብቻ ሳይሆን ያላጠገጉት ቁስሎች ዛሬም በየቤቱና በሰዎች አእምሮ ውስጥ የማይታመን ስቃይን እያመጡ እንዲኖሩ አድርጓል። በድርቅና በሌሎች ተፈጥሮአዊ አደጋ ሰበብ በደረሰባቸው መፈናቀልና መከራም በዚህ ሀመም የሚሰቃዩ ብዙ ሰዎች አሉ።

"ሴላሙ ብዙ ጊዜ አትኩሮት የማይሰጠው ... ለምሳሌ በቤት ሰራተኞች ላይ በየቀኑ የሚደርሰው የወሲብና የአካል ጥቃት ነው። በህጻናት ላይ በቤተሰብና በጎረቤት ባሉ አዋቂዎች የሚደረገው ወሲባዊም ሆነ አካላዊ ጥቃትና መደፈር ያልተነገረ ሥነልቦናዊ እዳ ነው። ሴላሙ ቀርቶ ተጋብተው በሚኖሩ ሴቶች ላይ በባሎቻቸው የሚደርሱ አካላዊ ጥቃቶችና አስገድዶ መድፈሮች ሁሉ ተላል እንዳይመስሉሽ። ባህላችን ብዙ ነገሮችን ከድኖ እንዳላየ የሚያልፍና ድብቅ ስለሆነ ይሄ ነው የማይባል ቁስል በየቤቱ እያመረቀዘ ይኖራል።"

የቡና እቃውን አቀራርባ ወጣ ገባ ስትል የነበረችው ልጅ ስትፈራ ስትቸር "ትዬ ቡናው ይፈላ ወይስ እስክትጨርሱ ..." አሰች፣ እጇን አፏ ላይ አድርጋ።

"አይ ትንሽ ይቀየን ... እንዴ ይሆቺን እንጨርስና ይደርሳል..." አሏት፣ አይናቸውና ግማሽ ልባቸው ቲቪው ላይ እንደ ተሰካ። የዶክተሩ ታሪ ምልልስ እንደቀጠለ ነበር።

"እና ... እንዳንዴ የድብትነት ባህላችንን ከምን ጋር ይመሳሰልብሻል መሰለሽ? ... አስቢው ከደጅ የሚታዩትን በረንዳችንንና አጥራችንን እንዴት እንደምናሳምር። ደግሞ የበለጠ የሚጠቅሙንንና የምንጠቀምባቸውን ኩሽናዎቻችንና የሽንት ቤቶቻችን ደግሞ በየቤቱ፣ በየመስሪያ ቤቱና ሆቴሉ ምን እንደሚመስሉ እስኪ አስቢያቸው። እንዳንዴ እንኳን ለማየትና ለመጠቀም ቀርቶ ስማሰብም ይዘገንናሉ። ይሄ ደግሞ ለብዙዎቻችን እንግዳ ነገር አይመስልሽም። ልክ እንደዚሁ መዴ ሰጪ የውስጥ ሕይወትና ያለፈ ታሪክ ስትገቢም 'ገመና መደበት' በሚለው የአስተሳሰብ ሥስ ብዙ ሰቆቃና የስሜት ስቃይ ትገታዎች ምስጢር ሆነውና ተቀብረው እንደታፈኑ ይኖራሉ። ሙዚቃን ስቃዬው ብዙ ሰው ሳቂታና ደስተኛ ቢመስልም" አለ። በተመሰጦ ስትሰማው የነበረችው ጋዜጠኛ ሴሎች ጥያቄዎችንም አዘታትላ ጠየቀችው። ምስጢርና እናቷም በጸጥታ ሲያዳምጡ ቀዩ።

"ማሚዬ የሚለው ሁሉ ኮ ልክ ነው። ግን ደግሞ በቃ ምን ያደርጋል ችግሩ ተራራ መፍትሄው ግን ጠጠር ነው። ማንው ይህን ሁሉ ጉድ ከየቤቱ ለትሞ እያወጣ የሚያከመው። ሆስፒታልስ ልሂድ ቢባል የት ነው የሚኬደው! አዩ ቲንክ እሱን ማየትሽ ጥሩ ይመስለኛል" ብላ፣ ተንጠራርታ ተነሳች። ማስታወቂያዎች እስኪታዩ ልጆቹን ጠርታ ወሰቹንና ቡናውን እንደገና አሙላው እንዲያመጡት ነገረቻቸው። ማስታወቂያው በማስከተልም፣ ስለ ችግሮቹ መፍትሔዎችና ያሉትን የህክምና

@OLDBOOOKSPDF

አማራጮች በተመለከተ ሃሳብ ሠጥቶ፣ በሌላ ጊዜ ተመልሶ በተያያዥ ችግሮች ላይ ውይይቱን ለመቀጠል ቃል ገብቶላት ፕሮግራሙ ተጠናቀቀ።

እራት እየበሉም በጉዳዩ ሲጨዋወቱ ቆዩ። ቡናው አልቆ ሲነሳሳ ሰልክ ሲመጣባት ጉንጮቿውን ሳም አድርጋቸው ወደ መኝታ ቤቷ ሄደች። እናቷ ግን በተቀመጡበት በአሳብ ሟልዋ ብለው ሄዱ። አንዴ በራሳቸው የህይወት ምህዋር ሲዞሩ፣ ደግሞ ስለ ምስጢር ሲጨነቁና ሲብሰለሰሉ፣ ከዛም ስለሟች ባላቸው በትዝታ ሰረገላ ተጭነው ሲማስኑ ቆዩ። ድካሙና እንቅልፉ ሲጫጫናቸው፣ እንደ ምንም ከሶፋው ላይ ተነስና ለብቻው የሚጮኸውን ቲቪ አጥፍተው ወደ መኝታቸው ሄደው ጋደም አሉ። አብሯቸው ሌሊት እንቅልፍ አልባና ትዝት የሞላበት ሆኖ ሲባንናና ሲያሸልቡ ነበር የተገባደደው። እንዳይተር ያህል ወደ ማነጋገያው ላይ ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰዳቸው።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 7 ፡

ወይዘሮ አደን ጠዋት ላይ ምስጢር ስትተሰትሳቸው፣ ሰውነታቸው ከብት ሲሄድበት እንደሞሰ ማሳ ተደቅድቀ፣ ድቅት ብለው ካሊጋቸው በግድ ወጡ። ትንሽ ቀለል ቢለኝ ብለው ቁርስ ቢጤ ከአንድ ስኒ ጥቁር ቡና ጋር አፋቸው አደረጉ። እሷ ግን ለምዶባት ቁኑ ሞቅ ካላለ ምንም ነገር ወዳሷ አይገባላትም። ብቻ ቀዝቀዛ ውሃ ውስዋ ሎሚ ጨምታ በባዶ ሆዷ መጠጣት የሁል ጊዜም ልማዷ ነው። ከሰፈራቸው እስከ ጳውሎስ ሆስፒታል ድረስ የጪት መንገዱ ብዙ ውጣ ውረድ ስላለው፣ ላለማርፈድ በጊዜ ወጡ። መንገዱ ክፍት ስለ ነበረ ሁለት ሰአት ተኩል ላይ ደረሱ። መኪናቸውን ሲያቆሙ ካፈው አካባቢ ሲጠብቃቸው የነበረው ሲራክ ምስጢርን ከሩት አይቶ ወደ እነርሱ መጣ።

ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣ "በጣም ነው የምናመሰግነው ... በጠዋት አደከምነህ አይደል?"

"ምን መንገዱ እኮ ደህና ነው ስትዪው አቁሞ ያውልሻል፣ ይዘጋጋል ብለሽ ስትፈሪ ደግሞ ባዶ ይሆናል ..." አለ።

ፈገግ አንዳለች ወደ እናቷ ዞር ብላ፣ "ማሚዬ ዶክተር ሲራክ ይባላል። ከዶክተር ሌላው ጋር ተጠሮ ያስያዘልሽ እሱ ነው። የአእምሮ ህክምና ስፔሻሊስት ለመሆን እያጠና ነው። ዘንድሮ ነው አይደል የምትጨርሰው ዶክተር?"

"ልክ ነው፣ እግዚር ካለ ዘንድሮ ያልቃል" አለ፣ ካንገቱ ሰበር ብሎ እናቷን በሁለት እጁ እየጨበጠ።

"በጣም ነው የማመሰግነው ዶክተር። መቼም ጥሩ ሰው እያጥሩ። እንተም እዚህ ሆስፒታል ነው የምትሠራው እንዴ ታዲያ?" አሉ፣ አይናቸውን ከርሱ ላይ ሳይነቅሉ እንደ ግጥናት ዓይነት እየታዩት።

@OLDBOOOKSPDF

"እይ እሱ በዚህ ወር አማኑኤል ነው ያለው። ላንቺ ብሎ ነው ከዶክተር ሌላው ጋር ሊያገናኝሽ እዚህ ድረስ መጥቶ የጠበቀን" አለች ፈጠን ብላ፣ ሙሉ ውለታዉ እንዲታወቅለት ይመስል።

"ውይ በጥቅሁት የኔ ጊታ። እሱ ከሥራህ አስተጓጉልንሃ። በጣም ነው የማመሰግነው" አሉ፣ የምርም ነገሩ ከብዷቸው።

"ኧረ ምንም አይደለም። እደርሳለሁ፣ ዛሬ ብዙም ከባድ ነገር የለኝም። ወደፊ ወደ ካፈው ጋ ሄደን ሻይ እየጠጣን ብንጠብት ይሽላል መሰለኝ። ዶክተር ሌላው የጠየት ስብስባውን ጨርሶ የሚወጣው ሦስት ሰአት አካባቢ ስለሆነ ብዬ ነው" አለ። ተከታትለው ከሆፒታሉ የጮን መግቢያ አንጻር ከፊት ለፊት ከመንገዱ ዳር ወዳለችው ካፈ አመሩ።

ነጫጭ የለበሱ ሃኪሞችና ነርሶች ቤቷን ሞልተዋታል። ሁሉም በየፊናቸው እያወካከኑ በሻይ ቡናው ዙሪያ ተጠምደው ገቢና ወጪውን ልብ የሚልም የለም። በረንዳው ላይ ያልተያዘ ወንበር አገኙና ተቀመጡ። አስተናጋጇን ዶጋሞ ምልክት ቢያሳያትም ችላ ያለችው ስለመሰለው በስጨት ብሎ አጨብጭቦ ጠራት። የሰበሰበችውን ስኒዎችና ሰሃኖች እንደ ያዘች ፈንጠር ብላ ስትቆም ቀጣ ብሎ

"ቆይ ሁሉ መለመን አለባችሁ ማለት ነው? እስኪ ፈጠን ብለሽ ሦስት ማኪያቶ ... ኖርማል ... አውሪልን" ብሎ ከመጨረሱ ሬቲን አዙራ ልትሄድ ስትል "እንዴ ... ምንድነው ነገሩ ዛሬ? ምን ያንቀለቅልሻል ... ምን ዓይነት ..." አለና፣ ሊል ያሰበውን ዋጥ አደረገው።

ራቅ ብላ የቀመችው አስተናጋጅ ደንታም እንዳልሰጣት፣ "በቃ ... አዘዛችሁ አይደል? ..." አለችና ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች።

"እንዲየውም ተዪው ... ተዪው በቃ ሂጂ። ይቅርታ ስትክፍስፈለፍብኝ እኮ ምን እንደምትፈልጉም ሳልጠይቃችሁ። ምን ይምጣላችሁ?" አለ፣ በልጅቷ ሁኔታ በስጨት ብሎ። ሁለቱም ማኪያቶው እንዲሆንላቸው ሲስማሙ፣ በንዴት ፈገፍገ ብሎ ተነሳና ገባ ብሎ አልፏት ወደ ውስጥ ገብቶ ተመለሰ።

"እንጀት አድብን ብቻ እኮ ነው የተሰበሰበው። ከየት እንደሚለቃትኟቹ አላውትም። ትንሽ ከተሻለ ብዬ፣ ውስጥ ራሴ ለባራስታው ነገሬው መጣሁ። ያው መቻል ነው እንግዲህ፣ የዚህ ቤት ማኪያቶ እንደ ካልዲስና ጥሞካ አይሆንም አለ፣ ወደ ወንበሩ ተመልሶ ተቀመጠና ሳት ለማለት እየሞከረ።

"ሻያቸው ግን ጥሩ ነው መሰለኝ ..." አለች፣ ምስጢር የቡናው መራራ ጣእም ትገ እያላት።

አንዴ አካባቢውን አንዴ ሲራመን ሲያጤኑ የነበሩት የምስጢር እናት፣ "እሷ እንግዲህ ቤት ያፈራውን ነው። አትጥገር፣ ችግር የለም" አሉ። የለበሰው ጥቁር ቡኒ ሙሉ ልብስ ከፈዛዛ ብርቱካንማ ሽሚዙ ጋር ጠይም መልኩን ፈካ አድርጎታል። የሲራክ ትልት ወጪው ተበራና ሚዛናዊ ነው። ጥቁር ተበቶና ደከማ ጫማ የወንድ

@OLDBOOKSPDF

ልጅን ቱመና በገማሽ ይተንሳል የሚል አባባል አለው። በረጅም ቀጭን ቱመቱ ላይ ሁልጊዜም ጢሙን ሙልጭ አድርጎ ተላጭቶ ጸጉሩን አጎፍሮ ዘንከት ዘንከት ሲል ገና የኮሌጅ ተማሪ ይመስላል። ለደረሰበት የትምህርት ደረጃ ልጅ እግር መስሎ ታያቸው። ሁሌም ቀልባቸው የወደደውን ሰው ሲያዩ ለልጃቸው ማሰብ መስለላቸው አይተርም። በወሬ በወሬ ስለ ዶክተር ሌላሠው ኢንተርቪው አንስተው ሲጫወቱ ቀዩና ሲራዘም ስለርሱ ስለሚያውቀው አንዳንድ ነገሮች አድንቶ ነገራቸው።

ብዙም ሳይቆይ የጠዋት ስብሰባቸውን ጨርሰው ዶክተር ሌላሠው ከሌሎች ሁለት ሳይካትሪስቶች ጋር ወደ ካፈው ሲገባ ከሲራክ ጋር ተያዩ። አብረው ያሉትን ሃኪሞች ይቅርታ ጠይቆ ሰላም ሊላቸው ወደ እነርሱ ጠርጌያ መጣ። ምስጢርና እናቷም ደንገጥ ብለው ብድግ ብድግ ሲሉ፣ "እንዴ ኧረ አይገባም። ተቀመጡ ... ተቀመጡ። ይህና እደራችሁ? ዶክተር ሲራክ፣ እነሱ ናቸው ዘመዶችህ?" ብሎ በመሉ ፈገግታ አንዴ እርሱን አንዴ እነርሱን እያየ እጁን ለሰላምታ ዘረጋ።

"አዎን እነሱ ናቸው። እላቸው እናቷ ናቸው። እቢ ናት እዚህ እኛ ጋ ለፐራክቲክም ባለፈው መጥታ ነበር ያልኩህ። የነገውስሊንግ ሳይኮሎጂ ማስተርስ ተማሪ ናት" ብሎ፣ የቻለውን ያህል የማስተዋወቅ ሥራውን ለመሥራት ሞከረ። የምስጢርን እናት ለሳም ካለ በኋላ እቢን ሰላም ሊል እጁን ዘረጋ። "ሚስጥር" ስትለው ሰሟን እንደነገረችው የተረዳው ተለይቷቸው ከሄዱ በኋላ ነበር።

ሌላሠው ከካፈው ሲወጣ ሊመጡ እንደሚችሉ ለሲራክ በምልክት ስለ ነገረው ተከታትለው ወደ ከሊኒኩ አቀኑ። ካርድ እስኪያወጡ እንዲጠብቁ እናቷን ከቢሮው ራት ለራት ካለ አግዳሚ ወንበር ላይ ትተዋቸው ምስጢርና ሲራክ ወደ ካርድ ክፍል ሄዱ። የከሊኒኩ ኮሪደር ቀስ ቀስ እያለ በሰው መጨናነቅ ጀምሯል። በየቢሮው በራፍ ላይ የተኮለኮሉ ህመምተኞች፣ የቀጠሮ ክፍሎችን በራፍ ያጨናነቡ ተመዝጋቢዎችና የከሊኒኩ ሰራተኞች ሁሉም በየራሱ ጉዳይ ተጠምደዋል።

ሌላሠው እንዴ ለመያዙ ከሲስተር ዘቢባ ጋር ትንሽ ተጨዋውቶ ከነርሶቹ ቢሮ ሲመጣ የምስጢርን እናት በመረፋ መጠበቂያ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጠው አየና፣ "ብቻዎትን ትተዎት የት ጠፉ?" አለ፣ ከአጠገባቸው ቁም ብሎ።

ተርበትብተው ከተቀመጡበት ብድግ እንዴ ማለት ብለው፣ "ካርድ ሊያወጡ መሰለኝ፣ አውን ነው የሄዱት ዶክተሮዬ" አሉ፣ ውጪ ውጪውን እያዩ።

"ታዲያ እነርሱ እስኪመጡ ለምን እኔ ቢሮ ገብተን እየተጫወትን አንጠብቃቸውም? እንደሱ ይሻላል መሰለኝ" ብሎ፣ ቢሮውን ከፍቶ ቀድሞ ገባና ወንበሮችን አስተካክሎ እንዲቀመጡ ከፊት ለፊት ያለውን ወንበር ጠቆማቸው። ከጠረጴዛው ጀርባ ባለው ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጦ የተበታተኑ ወረቀቶችን እያስተካከለ፣ "ይቅርታ፣ ስምዎን ማን ነበር ያሉኝ? ትድም እኮ ግርግር ሆኖ በድንብም አልሰማሁዎትም" አለ፣ ቀና ብሎ ፊታቸውን በጥልቀት እየታኝ።

@OLDBOOOKSPDF

"እደ ዶክተር እናንተማ የሰንቱን ሰው ሰም ይዛችሁ ትችሉታላችሁ። እኔን እባላለሁ። በጣም ነው የማመሰግንው መቼም ዶክተር ሲያዩኝ ፈታይኖ ሰለሆኑ እውታለሁ ሰራ በጣም እንደሚበዛብም" አሉ ፣ እጃቸውን እያፍተለተሉ።

"ኧረ ደስታዬ ነው። ምንም አይደል ፣ ደግሞ አንተ ይበሉኝ። አንቱታው አይገባም" አለ ፣ በደማቁ ፈገግ ብሎ።

"ያው ዶክተርንና ቂስን አንቱ ማለት የተለመደ ሆኖ ነው። እሺ ፣ አንተ በጸኝ ክልክ። ሰሞኑን በቴሌቪሽን የነበረህን ታለ መጠይቅ ሁሉ ተከታትያለሁ። መቼም ታል የለኝም ፣ በጣም አስተማሪ ነበር። በጣም ጥሩ ነው። ሰብዙ ሰው የሚጠቅም ነገር ነው አሉና ብዙ እንዳያወሩ ለመቀጠብ ይመስል ከጎናቸው ያለው ወንበር ላይ ያስተመጡትን ቸይ ቦርሳ አንስተው ታቀፉና ሳይታወታቸው ሙምድድ አድርገው ያዙት።

"ኦህ እውነት ፣ ተከታትለውት ነበር? እንዴት ነው ... አሳቡ ግን ግልጽ ነበር፣ አንዳንዴ የሕክምናና የሥነ ልቦናን ጉዳይ ባማርኛ ማብራራት በጣም ይከብዳል" አለ፣ ፊቱ የበለጠ በርቶ።

"ኧረ በጣም ግልጽ ነው። እንዲያውም ልጄ ካአሜሪካ ነው ከጎንደር የመጣው ብላ ስትተልድብህ ነበር ፣ ባማርኛህ እየተደነቀች" አሉ ፣ ፈገግታቸውን አስተድመውና አንጋገራቸው መዳፈር እንዳይሆንባቸው በመፍራት ሰተት እያሉ። ሰተት ብሎ በደግፋ ሳቀና

"አ...ይ የጎንደሬ ያህል አማርኛ ማውራት ከቻልኩማ ፣ ጎበዝ ሆኛለሁ ማለት ነው። እርሷ ብቻ ናት ወይስ ሌሎችም ልጆች አለዎት"

"አይ አሷው ናት። እንዴት ዓይነት የተባረከች ልጅ መስለችህ። ለሰው አባኝ፣ በዛ ላይ ስማርት የሆነች ልጅ ናት። ይሄው አባቷ ከሞተ አሁን ሰባት አመቱ ሊሆን ነው፣ አሷው ናት ቢዝነሱን ሁሉ ተጥ አድርጋ የምታስተዳድረው። በዛ ላይ ትምህርቷም ጥሩ ይዛለች። እንደ እናንተው ለመሆን ነበር ምኞቷ ፣ ማስትሬቷን በማማከር ከስድስት ኪሎ አሁን ሰኒ ላይ ትጨርሳለች። ከተባረከ አንድ ልጅም መድሃኒት ነው" አሉ፣ ፊታቸው ባንዴ አየፈካ።

"ልክ ነው። የተባረከ ልጅ እንድም ቢሆን በምንም አይለካ ፣ አድለኛ ነፆ አለና ጉሮሮውን ጠረግ ጠረግ አድርጉ "በጣም አዝናለሁ ስለ ባለቤትዎ። ብዙ ታመው ነበር?"

"አዎን ፣ ለረጅም ጊዜ ታሞ ነበር ፣ ከሁለት አመት በላይ ካልጋም ሳይወርድ ብቻ ሰታይ ውሰጥ ነበር። ጉበቱ ከጥቅም ውጪ ሆኗል ነበር ያሉት ሐኪሞቹ። ታሪኩ ረጅም ነው። እንዴት ያለ ገበዝ የቢዝነስ ሰው ነበር መሰለህ" ሲሉ ፣ እንዲቀጥሉ በማደፋፈር አይነት ሙንትላቱን እየነቀነቀ ዝም አለ።

"እና የመጨረሻው የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት እስኪቀሰቀስ አስመራ ነበር የምንኖረው። ታውቅ እንደሁ እንጃ ያኔ እዚህም እዛም ያሉ ብዙ ሰዎች ንብረታቸው መና ሆኖ ቀርቶ ነበር። እኛ ደግሞ ምጽዋና አስመራ ላይ ብዙ ንብረት ነበረን። ሁሉም

@OLDBOOOKSPDF

ተልኮ መኖ ቀረ ። እሱም በዛ ብስጭት መጠጣት ሆነ ሥራው ። ስንገሩ ባይልለት ነው እንጂ ገንዘብስ አልነበረም ችግሩ ። እዚህም የተሳካ ቢዝነስ ነበረው ። ግን በታ ልቡም ነፍሱም እዛ የነበረው ሥራው ላይ ስለነበረ ፣ ነገሩ ሲበለሻሽበት ህልሙም አብሮ ጦተ መሰለኝ ። እያደር ብስጭቱም መጠጡም ተጨምሮ ጉበቱ በጣም ተገፋ ። በኋላማ ሆዱ ውሃ እያጠራተመ መንተሳቀስም አቃተው ። ካልጋም ሳይወርድ ነው በዛው የቀረው" አሉ ፣ ቀስ በቀስ የሃዘን ድባብ ሲያጠላበት የነበረው ፊታቸው በእንባ እየራጠበ ።

ከፊት ለፊቱ ያለውን ናፕኪን ሲያስጠጋላቸው ፣ "ኧረ እዚህ ቦርሳዬ ውስጥ ሳይኖረኝ አይቀርም ። ይቅርታ ፣ እንግዲህ ገና ከመግባቱ እንቸገርኩህ" አሉ ፣ እንባቸውን ከቦርሳቸው ባወጡት ነጭ መሃረብ ጠረግ ጠረግ እያደረጉ ።

"ኧረ በፍጹም አይጨነቁ ። አዝናለሁ ..." ብሎ ፣ ስሚታቸው ተረጋግቶ ለመመለስ እስኪዘጋጁ ትንሽ ዝም ብሎ ቀየና "አስመራ ብዙ ኖራችሁ ነበር?" አለ ረጋ ባለ ድምጽ ።

"እኔ ያስመራ ልጅ ነኝ ። ከሱ ጋራም የተገናኘነው ደርግ ከመውደቁ አስር አመት በፊት እዛው ነበር ። በመ.ያዬ አነከውንታት ስለ ነበርኩ አንዳንድ ሥራ እሠራለት ነበር ። ያው መቼም የፈጣሪ ፈቃድ ከማን እንደሚያጣምርህ አታውቀውም ። ሚሰጥርዬም እዛው ነው የተወለደችው ። ደርግ ሲመጣት የነበረው ግርግርና ችግር መቼም ካትም በላይ ነበር ። ብዙ ሰው ተበተነ ፣ ስንቱ ተፈናቀለ መሰለህ ።

"ባለቤቴ ግን በታ ከሰዎቹ ጋር በጣም ይግባባ ስለነበር ምንም አልተቸገረንም ። ደርግ ሳይመጣት በፊትም በየንዘብ ይደገፋቸው ስለ ነበር ፣ በንጹነት ማግስት ማንም አልነካውም ። ከወደዱህ እንዴት ጥሩ ሰዎች መሰሉህ ። ይገርምሃል እሱ የመሃል አገር ጉራጌው ከኔ ከአስመራዊቷ ይልቅ የአገሬው ሰው ሆኖ ነበር ። በኋላ ግን ይሄ የመጨረሻው የድንበር ግጭት ሲነሳ ነገር ሁሉ ተቀያየረ ። የሚጠሉት ሰዎች ጥሩ አጋጣሚ አገኙ ። የሆነ ያልሆነ ነገር አስወርተው ችግር ውስጥ ከተቱት ። ደግነቱ ሰው ስለሚወደውና ብዙ ሰው ስለሚያውቅ ንብረት ቢጠፋም እኛን ግን ምንም ሳንሆን በሰላም ወደዚህ ሸኙን" ብሎው ፣ የሃሳባቸው ውል የጠፋቸው ይመስል ዝም አሉ ።

"እዚህ ከመጣችሁ በኋላ ያጋጠማችሁ የተለየ ችግር ነበር? ማለቴ ከነገሩኝ ነገር ሌላ የባለቤትዎን ጸባይ እንዲቀየር ያደረገው ነገር ካለ ብዬ ነው?" አለ ፣ አሁንም እርሱን ለማየት ያመጣቸውን ችግር ከመጠየቁ በፊት ቀደምት ታሪካቸውን ማጣራቱን መርጦ ።

ትንሽ ዝም ብለው ሲያስቡ ቀየና ፣ "ያው የሱ ዘመዶች መወል ምንም ሰላም የለም ። እንዴት መሰለህ ... አባቱም በጊዜያቸው የተሳካላቸው ነጋዴ ነበሩ ። ከልጆቻቸው ሁሉ እሱን ነበር በጣም የሚወዱት ። እናቱ ቀድመው ሞተው ስለ ነበር ትልቅ ግቢ ያለውን ዋናውን መኖሪያ ቤታቸውንና አብላጫውን ንብረታቸውን ለሱ ነበር ያወረሱት ። በዚያ የተነሳ ቤተሰቡ ውስጥ ብዙ ብጥብጥ ተፈጠረ ፣ ሁሉም ተባብረው እደመበት ። ያ በጣም ያበሳጨው ነበር ። ብታ መጀ እዚህ ከመ.ነ በኋላ ከሰዉ ሁሉ ጋር መስማማት አቃተው

@OLDBOOOKSPDF

"እንደ መሰለኝ ብዙ ያመናቸው ጓደኞቹም ገንዘብ እየተበደሩት ሳይከፍሉት አልተሩም። ብቻ መጨረሻ ላይ ብስጭትና መጠጣት ሆነ ሥራው። እያደርግ ጥሬ ኑሮውን በየቡና ቤቱ አደረገ። ሰዘር ወደ ቤት ሲመጣ ደግሞ እኛንም ሰላም ይነሳን ጀመር። መጀመሪያ ላይ ስድብና ጩኸት ነበር። እያደር ግን ጩሳና አምባጓሮ ሁሉ አመጣ። እኔም ሲያቅተኝ ቤቱን ጥዬ ወጥቼ ነበር ለተመሰነ ጊዜ ..." አሉና ለትንሽ ብለው ሲያለቅሱ፣ የሚያደርገው ስለ ጠፋው ለትንሽ ጊዜ በዝምታ ጠበቁ።

በየመሀሉ "በጣም አዝናለሁ ..." ብቻ እያለ፣ ስሚታቸው እስኪረግብ ድረስ በዝምታ ጠበቃቸው።

የለቅሶው ሳግ ትንሽ ተንፈስ ሲሉላቸው፣ "ንገሩ በጣም ምርር ሲለኝ ቤቱን ጥዬ ወጣሁ። ያኔ ታዲያ ሚስጥርዬን ከሱው ጋር ነበር ትቻት የሄድኩ። ከእኔ ጋር እንዳትንገላታ ነበር የኔ አሳብ። እንደው እግሬን በስበረው ያኔ ..." አሉና አሁንም ሌላ ዙር ለቅሶ ማልቀስ ሲጀምሩ ይበልጥ ግራ ገባው።

ከመቀመጫዬ ተነስቶ አጠገባቸው ተቀመጠና እጁን ትከሻቸው ላይ ጣለ አድርጎ ዶጋግሞ፣ "እይዝምት ..." እያለ ከወሰጣቸው እየፈነቀለ የሚፈልቀው ትኩስ እምባ ጋብ እስኪልላቸው ጠበቃ።

"መጀመሪያ ላይ ሰክሮ ይመጣና እኔን ሲሰድበኝ ወይ ሲደበድበኝ እሪ ብላ ስታለቅስ ይሥሀባታል ወይ በጥፊ ብሎ ከአጠገቡ ያባርራታል። እንዳንዴ ደግሞ ጥንብዝ ብሎ ይመጣና አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ሲሥሀ ይቀይና ተነስቶ ሳሎን ሶፋ ላይ ተጋድሞ ያድራል። እኔ ቤቱን ጥዬ ስሄድ እሷ ከርሱ ጋር ለመኖየት መርጣ ስለነበር ትቼያት ነበር የሄድኩት። ምን እንደሆነችም አላወቅም፣ ብዙም ሳይቀይ እሷም ቤቱን ጥላ እከሰቷ ቤት ገባች። ከዛ በኋላ ታሞ አልጋ ላይ ሲወድት ታረቅንና ተመልሼ ገባሁ። እሷ ግን ሲሞት ጥቂት ቀን እስኪቀረው ድረስ ፊቱንም አላየችውም።

"በጥፋቱ ጸጸት ይሁን የዘመዶቹን ዘለፋት ስለሚያውቅ እንኳ፣ ያለውን ሃብት ሁሉ ገና በህይወት እያለ ነበር በስሟ ያዞረው። ሊሞት ሳምንት ሲቀረው ብቻ በስንት አማላጅ መጥታ አየችው። 'ልጄ ምነው ስታዩን እይተሽ እንኳ ይቅር ብትይኝ...' ሲላት 'እንተ አውራ ነህ ... ይቅርታ አይገባህም፣ የሚገባህን ነው ያገኘኸው' ብላ ጥላው ሄደች። ላዩጥን ስታየው ገርና ሳቂታ ትመስልሃለች እንጂ ውስጢ ያልበረደቱግ አዝላ ነው የምትዞረው" ብለው፣ በሚማቸው መሬቱን እየቀረቀሩ አቀረቀሩ።

በግራ እጁ መላ ፊቱን አሻሸና የእጅቱን ጣቶች እርስ በርስ አቀላልፎ፣ "በሣኖ ከባድ ነገር ነው ..." ብሎ ዘለግ ላለ ትጽበት ሁለቱም ዝም ብለው ቀዩ። ጸጥታው የጨነቃቸው ይመስል ትንሽ ትንፋሻቸውን ሞት አደረጉ። የተነሰበትን ሃሳብ ለቀው ብዙ እንደ ሄዱ ሲገባቸው አፈር ብለው ዝም አሉ። የልጃቸውን የግል ጉዳይ ገና በመጀመሪያ ቀን ማውራታቸውም ሀሊናቸውን ሸንቆጠጥ እንደገና እግር እግራቸውን እያዩ አቀርቅረው ቀሩ። ነገሩ የገባው ይመስል ትንሽ ሃሳባቸውን መሰብሰብ እንዲችሉና ስሚታቸው እንዲረጋጋ ቀለል ያሉ ጉዳዮችን ሲያወራቸው ቀየ። ሙሉ ለሙሉ ሲረጋጉ እሱን ሲያዩ ስለ መጡበት ጉዳይ [illegible] ወደ ወንበሩ ተመለሰ።

"ምኑን ነግሬሀ ምኑን ልተወው ዶክተር?" ብለው፣ መነሻና መድረሻው እንደ ጠፋባቸው መራት መራቱን ሲያዩ ቀዩና የተከፈተ ቦርሳቸውን ዘግተው አጠገባቸው አስቀመጡት። "ትልቁ ችግር ... ስንት ጊዜዬ መሰለህ ዶክተርዬ፣ የረባ እንቅልፍ ባይኔ ከሠረ። ደግሞ በቃ በሆነ ባልሆነው ሆድ ይብሰኛል። ሰው ማግኘትማ ገና ሳስበው ያደክመኛል። ጨለም ያለ ቦታ ሆኜ ስተክዝና ስቀዝም ለብቻዬ ቁጭ ብዬ መዋል ነው የምመርጠው። ጠዋት ሲነጋ ካልጋ መውጣት ስቃይ ነው። ልክ በቃ ሌሊቱን ሁሉ ከባድ ሥራ ሲሠራ እንዳደረ ሰውነቴ ሁሉ ባል ብሎ ጉልበቱ ፍስስ ብሎ ነው የምንሣው። የሌሊቱ መላ ቅጥ የሌለው ቅዠት ሳያንስ ቀኑን መሉ ደግሞ የሆነ ያልሆነው ነገር አንደፈልም ፊቴ ደንቅሮ ሲያጫውተው ይውላል። በር ሲዘጋ ወይ የሆነ ነገር ወድቆ ኳ ያለ እንደሆነ ፈንጂ የፈነዳ ያህል መገለል መደንበር ነው።

"ምንም የገደለ ነገር ሳይኖር በሆነ ባልሆነው ነገር መጨነቅ መጠበብ ነው። አንዳንዴማ በቃ ልቤ ድንገት ተነስታ በጉሮሮዬ ልውጣ ትላለች። ትንፋሽ አጥሮኝ ከላይ ከላዩ ስተነፍስ ያስሰመልመኝና ያለሀበትንም አላውቅ። ከዛ ሰውነቴን ቁምድድ አድርገኝ ይቀይና ድንገት ተገታህ ውሃውን ጀርባዬ ላይ ይከልሰዋል። ሰውነቴ ሁሉ በድን ይሆንብኝና የኔም አይመስለኝም። ኧረ ስንቱን ልንገርህ ዶክተር" ብለው፣ ቁንት እንደላቸው በመስኮቱ አሻግረው እያዩ ዝም አሉ።

"ከዚህ በፊት ሃኪም ወይም አማካሪ ጋ ታይተው ያውቃሉ?" ብሎ፣ የነገሩትን ስራ የስሚት ስቃይ ገርገር ማሰብ ተጠለ። በእንቅልፍ እጦት የጠቀረው የዓይናቸው ሁሪያና ድርብርብ ቁንጥት የረበበበት ፊታቸውን ሲያይ የዘረዘሩት የውስጥ ስቃይ ገጻቸው ላይ የተጻፈ መሰለው።

"አንድ ሁለቴ ታይቼ ነበር፣ እዚህ ምንድነው ስሙ እቱ? የግል ክሊኒክ ነው። ምንም አልረባኝም እንጂ፣ አንድ ሁለት የሚሆን መድሃኒትም ሰጥተውኝ ነበር። ይሄው ልህ በቃ ትንሽ ትልቁን ሁሉ መርሳት ነው። እንዲየው ምን ይሻልኝ ይሆን? የሰጡኝ መድሃኒትም ቢሆን ማጥዘዝ ማስተኛት ካልሆነ ምንም አልፈየደልኝም። አንድ ሰድስት ወር ሞክሬ ተውኩት። ከዚያም ጠበሉንም፣ የባህሉንም መድሃኒት፣ ሁሉንም ሞክሬ ነበር። ጊዜ ለጥቶ የሚያዋራ ሁነኛ አማካሪ ማግኘቱ ደግሞ ከባድ ነው" ብለው፣ በረጅሙ ተነፈሱ።

"ቅድም በእንቅልፍ ተኝተው በቅዠትና ቀንም ነቅተው እያሉ ትዝታው ፊቴ ላይ እየመጣ ያስቸግረኛል ያሉኝ ነገር ነበር። ነገሩ ከዚህ ቀደም በህይወትዎ ከደረሰ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው?" ሲል፣ ጥቂት ጸጥ ብለው ቀዩ። ድንገት ኩልል ብሎ በጉንጫቸው ላይ መፍሰስ የጀመረውን እምባ በመዳፋቸው ጠረግ አደረጉና፣

"እ-ባ-ቴንና ወን-ድ-ሜን ዓይኔ እያየ ነው የገደሏቸው። ሻእቢያ ናችሁ ብለው ደጃፋችን ላይ ደፍተዋቸው ሄዱ። እኔ ያኔ ወጣት የክሊጅ ተማሪ ነበርኩ። ታናሽ ወንድሜ ብቻ ሸሽቶ ወደ ጫካ ገባ። እኔም ብዙም ሳይቀይ እሰር ቤት ተወሰድኩ። ወንድምሽ የት እንዳለ ምሪ፣ የክተማ ሰላይ ነሽ ተብዬ የደረሰብኝን ግፍና ስቃይ በቃላት

@OLDBOOOKSPDF

ልነግርህ አልችልም። እናታችን ብቻዋን ቀርታ እንዲሁ በሃዘን እንደተቀረመደች በዓመቱ ሞተች። ከሁለት ዓመት በኋላ ከእስር ቤት ስወጣ ህይወቱ ሁሉ እንዳልነበር ሆኖ ነበር።

"ይሄንን ሁሉ ጉድ ደህና የረሳሁት መስሎኝ ነበር። የጠሩ የመሰለኝ ነገር ሁሉ አሁን እንደ ተቀበረ ፈንጂ መፈንዳት ሲጀምር ውስጤን እያፈራረሰው ነው። አሁን ከስንት ዓመት በኋላ እንደ አዲስ ነጋ ጠባ እነሱ ናቸው ፊቴ ላይ የሚመጡት። ልክ ትናንት የሆነ ነው የሚመስለኝ። በቃ መተኛትም ብቻዬን መሆንም እንዴት እንደሚያስፈራኝ አትጠይቀኝ። በተለይ ያባቴና የወንድሜ ፊታቸው ላይ የነበረው ስቃይ ፊቴ ድቅን ይልብኛል። እስር ቤት የደረሰብኝ ግፍ ...ግርፋቱ ... መደፈሩ ... እህ...ሀ...ሀ" ብለው፣ ልክ አሁን የሆነ ያህል ስሜታቸው ተንዘፈዘፈ። በዚህ ጊዜ አባቱ የጻፉለት የኑዛዜ ደብዳቤ ትዝ አለው። ምንም የሚለው አልነበረውም።

"እንዳንዴ ሴሊት በትዝታ ስሙህ ሰምታ ልጄ ትመጣና ስትቀስቅሰኝ ላብ በላብ ሆኜ ታገኘኛለች። ከዛ በኋላ ተመልሼ መተኛትም ስለምፈራ ቁልሟ እንዳልኩ ይነጋል። ቀኑን ደግሞ በእንቅልፍና በንቃት መካከል ሆኜ ወይ ሲያንገላጅጀኝ ያልፋል፣ አለበለዛም በቃ ሶፋው ላይ ደገፍ ባልኩበት ትንሽ ያሸልበኛል። ሜንትላቲ ያንኑ መልሶ መላልሶ እንደ ፊልም ሲያጫውትብኝ ይውላል። ዶክተርዬ እንዲህ ስታየኝ ደህና እመስልሃለሁ እንጂ፣ ተሸክሜ የምዞረው ጉድ እኮ ማለቂያም የለውም። ሰው በቀን አረፍት፣ በማታ እንቅልፍ ሳይኖረው እንዴት ይኖራል?" ብለው፣ ዓይናቸውን በያዙት መሃረብ አደራረቁ።

"በጣም አዝናለሁ ወይዘሮ ኤደን፣ በጣም ከባድ ነገር ነው።"

እጁ ላይ ያለውን እስክርቢቶ በጣቶቹ እያፈተለተለና ፊታቸውን እያጠና "እንዴት አንድ ሰው ይሄንን ሁሉ መከራ ይቀበላል፣ እንዴትስ ይሄንን ሁሉ ጉድ ተሸክሞ ሊኖርና ቀሞ ሊሄድ ይችላል?" የሚሉ ጥያቄዎችን ሲያስብ ቆየ። ምናልባትም ረጅም ጊዜ የሚወስድ የምክክርና የመድሃኒት ህክምና እንደሚያስፈልጋቸው ገመተ። የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜም ስለሆነ ስላፊ እስካሁን ከነገሩት ታሪክ በላይ መሄድ አልፈለገም።

ጥቂት የቀሩ መሰረታዊ ነገሮችን ከጠየቃቸው በኋላ ሰአቱን አየት አድርጎ ከፍቶ ውስጥ የሰፈነውን ከባድ የሃዘን ስሜት ለማርገብ፣ "እነዚህ ልጆች ካርድ ለማውጣት ተቸግረው ይሆን እንዴ?" ብሎ፣ ስልክ ለመደወል ከኪሱ ሲያወጣ በሩ ተንኳኳ። ሲስተር ዘሪባ ነበረች።

እንግድን በክፉል አስገብታ፣ "ይቅርታ ዶክተር ካርዱ ወጥቷል። እነ ዶክተር ሲራክ እኩ ከመጡ ቆይተዋል። እንዳያጋርጧችሁ ብለው እኔ ቢሮ ነው ያሉት። ድንገት ካርዱን ከፈለግኸው ብዬ ነው" አለች።

"አይገርምሽም እኛም ካርዱን ለማውጣት አስቸግሯቸው ይሆን ብለን ልክ ልደው ልልሽ ስለ ነው የመጣሁት። ታንኩ ሲስተር።" ካርዱን እየተቀበላት ወደ

@ETHIOBOOKSPDF

ምስጢር እናት ዞር ብሎ ፣ "ልጅዎት እሁን ብትገባስ? እኛ ለባሬው ምናልባት ላይበቃን አይቀርም" አለ ።

ወይዘሮ ኤደንም ፈጠን ብለው ፣ "አዎን ፣ ጥሩ ነው ። ጥሩ ነው ፣ ትግባ" አሉ ፣ ሽቱዋቱዋ ባለ ድምጽ ።

"ቢቃ ልጃቸውም ትግባ ፣ ንገሪያት ሲስተር ዴ" አለ ፣ የተቀበላትን ባዶ ካርድ ከፍቶ ከራቱ እየዘረጋ ። ሲስተር ዘቢባ በሩን ዘግታ ስትሄድ ወደ እርሳቸው ዞር ብሎ ፣

"ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ ያህል የምክርና የመድሃኒት ህክምና ማድረግ ያስፈልግዎ ይሆናል ። ያለፉበት ነገርና አሁንም የሚሰማዎ የስሜት ስቃይ ከፍተኛ ስለሆነ ሙሉ ለሙሉ እስኪሻልዎ ረዘም ያለ ጊዜ ቢወስድም መታገስ ያስፈልግዎታል ። እኔም እንግዲህ ከእግዜር ጋር የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ ። መርሳት የሌለብዎ ነገር ግን ይህንን ሁሉ ፈተና አልፈው ዛሬ ላይ መቀምዎ ራሱ የሚያሳየው ፣ ምን ያህል ከባዱን ሥራ በራስዎ እንዳለፉት ነው ። ስለዚህ በፍጹም ተስፋ መቁረጥ የለብዎትም " ሲል ፣ ጥንቅላታቸውን በእምንታ በመነቅነቅ መስማማታቸውን ገለጡ ። ወዲያው በሩ ተንኳኳና ምስጢርና ሲራክ ተከታትለው ገቡ ።

"እኛ ኮ ካርድ አልቀ ለፍለጋ ወደ ከተማ ሄደው ይሆን ብለን አሳብ ገብቶን ነበር" ሲል ፣ ሁሉም ሳቁ ።

"ኧረ ወዲያው ነበር እኮ የመጣነው ። ላለመረበሽ ብለን እነ ሲስተር ዘቢባ ቢሮ ተቀምጠን ነው" አለ ፣ ሲራክ እንደ ቀሙ እጁን እያሻሸ ።

"እይ ቀልዴን ነው ፣ ሲስተር ነገረችን እኮ ። ቁሜ እትሉም ታዲያ?" አለ ፣ ወደ ባዶ ወንበሮቹ እየጠቀመ ሁለቱንም በመጋበዝ ፣

"እይ ዶክተር ፣ እኔ እንኳ ብሄድ ይሻላል ። አማኑኤል ከምሳ በፊት የምደርስበት ጉዳይ አለኝ ። የሚስጥርን እናት ሳልሰናበታቸው እንዳልሄድ ብዬ ነው የቆየሁት" አለ ፣ ወደ እሳቸው ጠጋ እያለ ።

"በጣም ነው የማመሰግነው የኔ ጌታ ፣ አደከምኩህ ግን" አሉ ፣ እየተሽቀጠቀጡ በሁለት እጃቸው እጁን እንደጨበጡ ፣

"ዶክተር ሲራክ በጣም ገበገ ሐኪም ነው ። ትልቅ ተስፋ ከሚጣልባቸው ወጣት ዶክተሮቻችን አንዱ እሱ ነው" ብሎ ፣ እርሱም ጨበጠውና "ነገ ጥቁር አንበሳ እንገናኝ የለ?" አለው ።

"ልክ ነው ፣ የከሰአት በኋላውን ሴሚናር አንተ ነህ አይደል የምትሰጠን?" አለ ። ከመውጣቱ በፊት ዞር ብሎ ከናቷ ጉን የተቀመጠችውን ምስጢርን በእደውላለሁ ምልክት እጁን አሳይቷት በሩን ዘግቶ ወጣ ። እሱ ከወጣ በኋላ ለጥቂት ደቂቃ ክፍሉ እንደገና ጸጥ ብሎ ቀየ ። ሌላሠው አይኖቹን ምስጢር ላይ ጣል አድርጎ ረጋ ባለ አነጋገር ፣

"ያው ከእናትሽ ጋር የተወሰኑ ነገሮችን ለማውራት ሞክረናል ። ወዳሜሪካ ከመመለሴ በፊት የተወሰኑ ሳምንታት ብቻ ስለሚቀረኝ በሳምንት ሁለት ቀን ላያቸው

@OLDBOOOKSPDF

ነው፡ የተስማማንው ። በቂ እንቅልፍ እንዲተኙና የሚሰማቸውን የጭንቀትና የውጥረት ስሜት ቶሎ ለማርገብ መድሃኒት ለተወሰነ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል ። አንቺም በቻልሽው መጠን ሥራዬ ብለሽ አብረሻቸው ብታሳልፊ ጥሩ ይመስለኛል" ሲል ፣ በመስማማት ራሷን ነቀነቀች ። እናቷ ተበል አድርገው

"እሷማ መች ካጠገቤ ትለይና" አሉ ፣ በስስት አይን እያዩዋት ።

"ልክ ነው ። እሱ እንዶ እናትና ልጅ ሲሆን ይችላል ፣ ግን ደግሞ ችግሩን እነደ ሀመም አይቶ በማስታመምና በመደገፍ አንጻር ማለቴ ነው" አለና ሁለቱንም በተራ በተራ እያየ "ይሄ ካርዴ ነው ፣ ምንም ችግር ካለ ደውሉልኝ ። ወዲያው እንኳ ማገላት ባልችል በቻልኩት ፍጥነት እመልሳለሁ" ብሎ ፣ ሁለት ካርድ አወጣ ። ምስጢር ልትቀበለው እጇን ስትዘረጋ በጣቶቿ መሃል ሾልኮ መሬት ወደቀባት ።

"ኡፐስ ... ይ-ቅ-ር-ታ" ብላ ፣ ከወደቀበት አንስታ ቀና ስትል ፈገግ ብሎ በምንም አይደለም አይን ሲያያት እንደ ማፈር ብላ አይኗን ሰበረች ። ስለ መድሃኒቱ አወላለድና ዋና ዋና የጉን ጉዳቶች አሰረድቷቸው ማዘገፖውን ሰጣቸው ።

ያቀረቡለትን ጥቂት ጥያቄዎች ከመለሰላቸው በኋላ ሲያሰናብታቸው ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ በሩ እያመራ ፣ "ስለዚህ በታ ሲስተር ዘቢባ ጋ ሂዱና ለሐሙስ ተጠሮ ውሰዱ ። ማክሰኞና ሐሙስ ጠዋት ከሶስት እስከ አራት ሰአት ጥሩ ነው?" አለ ፣ በየተራ እያያቸው ።

"በጣም ጥሩ ነው ። ዶክተር መቼም ታል የለኝም ፣ እጅግ በጣም ነው የማመሰግነው" አሉ ፣ እናቷ ። ምስጢርም መስማማቷን ገለጸች ።

እርሳቸውን ከተሰናበተ በኋላ ሲጨበጣት ፣ "ሚስጥር ... ቀንጆ ስም ነው" አላት ።

ፈገግታ ተሞልታ የስሟን ቃል ገተት አድርጋ ፣ "አመሰግናለሁ ። ትክክለኛው ስሜ 'ሚስ-ጥ-ረ' ነው ።" አለች ።

የበለጠ ፈገግ ብሎ ፣ " ኦህ! ኢቫን ቢተር" አለና በሩን ከፍቶ ያዘላቸው ። የእናቷ ትከሻ ላይ እጇን ጣል አድርጋ ተከታትለው ወጡ ።

የቀረውን ሙሉ ጠዋት አልፎ አልፎ 'ምስጢረ' የሚለውን ስም ትዝ ሲለው ሞለ ። ያላለቀ ፣ የተንጠለጠለና ያልረገበ በጅምር ተንጠልጥሎ የቀመ መዚቃ መስሎ ተሰማው ። የወይዘሮ ኤደንን ስቃዮች ሲያስብ ደግሞ ፣ ያለፉበት የሕይወት መራራና ጠመዝማዛ መንገድ የስንት ሰው ታሪክ ሲሆን እንደሚችል አሰበ ። አባቱ የጸፉለት የትዝታ ማስታወሻ ከነሙሉ ግዝፈቱ ለመጀመሪያ አፍጥጦ ታየው ።

ከርሱ ቢሮ ሲወጡ ምስጢር እናቷን ከሲስተር ዘቢባ ጋ አስተዋወቃቸው ፣ የሚተጥለውን ቀጠሯቸውን አስመዝግበው ወደ መኪናቸው ሄዱ ። "እንዴት ነበር ማሚ? ምነው ብዙ አስለቀሰሽ እንዴ ፣ ፈትሽና ዓይንሽ?" ብላ ፣ የለበሱትን ጥቁር ያንገት ልብስ አስተካከለችላቸው ።

@OLDBOOOKSPDF

"ው·ይ ቢለቀስስ ደግሞ፣ ብታዪ በጣም እንዴት አይነት ሩሀሩህ ሰው መሰለሽ። ከማንም ጋር አው·ርቼው·የማላው·ቀው·ንጉድ ሁሉ·ነው·ማው·ራት የቻልኩት። እንደ ሌሎቹ ዶክተሮች ተዋክቦ አያዋክብሽም። ገዛ ብሎ ሲያጻምጥሽ የሆነ ነገር ከው·ስጥሽ እው·ሪ እው·ሪ ያስኝሻል። ዘኔ በቀር ሌላ ታካሚ ያለው·ም አይመስልም። መናገር ራሱ ለካ መድሃኒት ነው·። ኡፍፍ ... እንዴት ቅልል እንዳለኝ።"

"እምን፣ ሥርዓት ያለው· ሰው· ይመስላል። በሳምንት ሁለት ጊዜ ሲያይሽ መፍቀዱም ደስ ነው· ያለኝ። እኔ ምለው· ግን ወላጆቹ ሌላሠው· ያሉት፣ የምር ሌላ ስም አጥተው· ነው·?" ብላ ሳቀች።

"ምን ታው·ቂያለሽ? ያገራችን ሰው· እንዲህ አይነት ስም ያለ ምክንያት አያወጣ። ደግሞስ ጥሩ ስም ነው፣ ምን ወጣው·?" አሉ። ነገር ስትፈላልጋቸው· መሆኑን አው·ቀው·ታል።

"እሱማ መጥፎ ስም ነው· አላልኩም እኮ፣ እንዲያው· ገርሞኝ ነው·። ማለቴ ሲወለድ ምን አይነት ሰው· ጠብቀው· ቢሆን ነው·? የምልሽ አይ አም ሹር እሱ ሲወለድ አልትራሳው·ንድ ምናምን አልነበረም። ምን ያህል ከጠበቁት የተለየ ሀጻን ቢሆንባቸው· ነው· ሌላሠው· ያሉት ብዬ ገርሞኝ ነሞ" ብላ፣ አሁንም እንደ ሞኝ ስትስቅ ትንሽ እንደመናደድ አሉ።

"ጀመረሽ ደግሞ ይሄ ቂልነትሽ፣ ይልቁን ያ ያንቺ ጓደኛ ትንሹ ዶክተር ማነው· ስሙ·እቴ፣ ጥ...ሩ ልጅ ይመስላል። ቁም ነገረኛ ነው·፣ እዚህ ድረስ ለኛ ብሎ መምጣቱ። ብዙ ትተዋወቃላችሁ·?" አሉ፣ ነገሩን ለመቀየርም ትንሽም የማወቅ ፍላጐታቸው· ተጨምሮበት።

"ሲራክን ነው·? ረሳሽው· እንዴ ... ነግሬሽ ነበር እኮ። ያኔ እዚህ ለፐራክቲከም የመጣሁ· ጊዜ ጓው·ሎስ ነበር የሚሰራው·። ትንሽ ችክ ያለ ቀበጥ ቢጤ ነው·። ስለ ራሱ ያለው· አመለካከትም ቁልል ተራራ ነው· የሚያክለው·። አለ አይደል፣ አፍታራ·ሲራክ ነገር ... ገባሽ አይደል?" አለች።

"አቤት አቤት አንቺ ልጅ፣ ኧረ እንዲያው· ለሰው·ም ጡር አለው·። እንዲያው·ላንቺ ማን ይሆን ጥሩ ሰው·? እንዲያው· እሱ ብቻ ያሳየኝ ያንቺን ነገር" ብለው·፣ ቦርሳቸው·ን ወደ ጎለኛው· ወንበር ወርወር አድርገው· ተመቻችትው· ተቀመጡ።

የጉዞ ቀበቶው·ን እያጠበቁ በጐን አየት ሲያደርጓት፣ "ለኔ ጥሩ ሰው· ይጠፋል ብለሽ ነው· ማሚዬ፣ አንድ ቀን ይመጣል። አሁን ያሉት ግን ሁሉም ያው· ሰው· ነገር ናቸው·። ሰው· ነገር ደግሞ መች ጠፋ፣ በተለይ ወንድ። አታይው·ም መንገዱን፣ የታዘሲ ው·ይይቱን፣ ቀበሌና ሱቁን፣ ቢሮው·ና እስር ቤቱን የሞላው· ሁሉ ወንድ ነኝ ባይ ነው· እኮ" ብላ፣ የመኪናው·ን የጣሪ መስኮት ከፈተችው·። "እገሩ ሁሉ ሰው· ነው· ... ሰው· መች ጠፋ። እስካሁን ሊገኝ ያልቻለው· ... ሉ...ላ... ሰ...ው· ነው· ማሚዬ" ብላ፣ የው·ሽት ስትስቅ በትግብት ዓይነት ፈገግ ብለው· የጐሪጥ አዩዋት። "ዶክተሩን ሌላሠው· ማለቴ መለሎሽ ነው· አይዬል? አይ ማሚ ... እሱንስ ማን አየው· ብለሽ

@OLDBOOKSPDF

ነው። እኔ በጠቅላላው ሌላ ሰው ማለቱ ነው። ደግሞ ... ሰዚህ እኮ ነው ለምንድነው ሌላሠው ብለው ስም ያወጡለት ያልኩሽ" ብላ እንዶገና ሳቀች። "ወደው አደለቱ አሱና እላቸውም ከት ብለው ሳቁ።

"ይልቁን ሚስጥሬ ሙች ያንን ትንሹን ዶክተር ቀልቤ አልጠላውም። ው፥ ደግሞ እንዴት ሽር ሽቁጥቁጥ እንደሚልልሽ" ብለው ከዓይኗ ውስጥ አሳቢን ለመበርበር ይመስል አጥልቀው ሲያዩዋት፣

"አይ ማሚዬ ነገርኩሽ እኮ፣ ልጹ ብልጣብልጥ ነገር ነው። ሽቁጥቁጥነትና እሱ አብረውም አልተፈጠሩ። እዛ ካፌ ቅድም አስተናጋጇን እንዴት እንዳመናጨቃት አላየሽውም እንዴ? ከኔ የሆነ ነገር ባይፈልግ እንኳን በጠዋት ሰራ ትዮ እዚህ ሲመጣ፣ አዩ ተይው ባክሽ፣ ተበልቶበታል። ትገ አይልሽም እንዴ? ነግሬሽ ነበር እኮ። ያ እዚህ ስሰራ አላስቀም አላስቀምጥ ያለኝ እኮ እሱ ነበር። ደግሞ ከተማሪውም ከነርሱም ጋር ስለሚጓተት አይመስጠኝም" ብላ፣ መሪውን መታ አድረገች።

ሳታስበው ፍጥነቷን ጨምራ ኖሮ፣ "ኧረ ልጄ ቀስ በይ... የት ለመድረስ ነው፣ ግን ደግሞ ዶክተር ሌላሠውስ ቢሆን እንዴት አድንቀት እንደተናገረ አልሰማሽም፣ አሱ ተስፋ ባለመቁረጥ።

ትንሽ በስጪት ብላ፣ "ማ-ሚ ደግሞ፣ እሱ የዶክተር ሌላሠው ምርጫ ነው። ካሜሪካ የመጡ ሰዎች ደግሞ የለበጣ ማቅላጸስ የማልወደው ጸባያቸው ነው። የምሩንም ላይሆን ይችላል። ይልቁን ሲራክን እንርሳውና እስኪ ኢንሪኮ ጎራ እገበል፣ እኔ ኪካቸው አምሮኛል" አለች ድንገት ፊቷ በርቶ። የጣፋጭ ነገር ጠር ናት።

"ጥሩ ነሞ... ካላስቀ... አራት ሰአት ተኩል ሆኗል ግን" አሱ ሰአታቸውን እያዩ።

"እንሞክር ዕድላችንን" አለችና ወደዛው አመሩ።

ሲደርሱ ኢንሪኮ እንደ ልማዱ ገና በረፋዱ በሩን ዘግቶ ጠበቃቸው። በአራት ኪሎ ውስጥ ለውስጥ አጽርጠው በፍጥነት ወደ ቤት ነዱ። እንደ ደረሱ ምስጢር ደህና ሰላሳት ቁርስ ቢጤ ተማመስችና ትንሽ ለማረፍ ስለፈለገች አልጋዋ ላይ ጋደም አለች፣ በተከፈተው መስኮት አሻግራ፣ በጠራው ሰማይ ላይ የሚንከራተተውን እንደ ባዘቶ ጥጥ የተከመረና ብትንትን ያለ ነጭ ደመና እየተከተለች በራሷ የሃሳብ ጉም ላይ ተሳፍራ ከነፈች።

ከቦርሳዋ ውስጥ ያስቀመጠችውን የዶክተር ሌላሠውን ካርድ እውጥታ በጠርዙ ከንፈሯን መታ መታ እያደረገች ትኩር ብላ ስሙን ስታይ ቀይታ 'ዶክተር ሌላሠው ዲንሳ' አለች ድምጿን አሰምታ። ጣቱ ላይ ያየቻትን የጋብቻ ተለበት ባይነ ህሊናዋ አሰበች። ሚስቱ ምን ትመስል ይሆን? ... ልጆችስ ይኖሩት ይሆን? ... ለቤተሰቦቹስ ምን አይነት ሰው ይሆን? መጀመሪያና ማለቂያ በሌለው ሀሳብ ስትናጥ ሰውነቷ ዛል አለ፣ ዓይኖቿም ቀስ በቀስ እየተከደኑ፣ ጥቅጥቅ ካለው የእንቅልፍ ደመና ውስጥ ላታውቀው ገባች። የሌላሠው የቢዝነስ ካርድም እንቅልፍ በፈታቸው ጣቶቿ መሃል ተንሸራታ ግራ ዶረቷ ላይ ወደቀች።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 8 ፡

ሌላው ቱኑ በቀጠሮ የተጣላና በሥራ የተጨናነቀ ሊሆን እንደሚችል አያሰበ በጠዋት ከቤት ወጣ። መንገዶቹ ገና በሰውና በመኪና ስላልተሞሉ ዘና ብሎ ለመንዳት ይመቻሉ። ፍንትው ባለው ጠዋት ፀሐይዋ፣ ወርቃማ ጨረሯን በለስላሳ ሙቀት አስጊጣ ማልዶ ከቤቱ ለወጣው ሁሉ ያለስስት ትቸራለች። ቀየት ሲል ደግሞ አርፍዶ የወጣውን በግለቷ መቅጣቷ አይቀርም። ዕለቱ ሐሙስ ነው ... ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ከሩብ ይላል የመኪናው ሰዓት። አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ ከለው የአናቱ ቤት ተነሥቶ ከርስ አደባባይ ላይ ወደ ግራ አላበረና ውስጥ ውስጡን ጠመዝማዛውን መንገድ ሲጨርስ፣ ቀለበት መንገዱ ከመግባቱ በፊት ካለው ካልዲስ ገራ አለ። ማኪያቷቸውን ይወደዋል ... አሜሪካ የለመደውን ስታርባዘስን ተክዮለታል። በተለይ ጠዋት ጠዋት ግቢው ሞር ስለሚል፣ ቱኑን በሰረፍት እንደመጀመር ያህል ይሰማዋል።

ደብል ማኪያቶ እገዛ ከቤት ከመውጣቱ በፊት ሲያንብ ስለ ነበረው መጽሐፍ ማሰብ ጀመረ። ሌሊት ላይ ያለ ወትሮው እንቅልፍ እምቢ ብሎት ረዘም ያለ ሰዓት በማንበብ ነበር ያሳለፈው። ለረጅም ጊዜ መጨረስ ያቃተውን 'ዘ ሳይኮሎጂ ኦፍ ዲሲት' (የሐሰት ሥነልቦናዊ ሐተታ) የሚለውን መጽሐፍ አንብቦ መጨረሱ ደስ ብሎታል። መጽሐፉ ብዙ ጥናቶችን ተንተርሶ የተጻፈ በአስቂኝ ምሳሌዎችና በታዋቂ ሰዎች አባባሎች የተሞላ በውሸት ሥነልቦና ዙሪያ ለሁሉም እንባቢ እንዲሆን ተደርጎ የተጻፈ ነው።

ውሸት በሁሉም ባህሎችና ሰዎች ዘንድ የተጠላና የተወገዘ ድርጊት ቢሆንም፣ በባው ልክ በስፋት የሚዘወተር ተግባር ነው ይላል። አፍታሪ ከፍተረኛው ... ነጋዴ ከደንበኛው ... የሃይማኖት መሪዎች ከምእመናኑ ጋር ይወሻሻሉ። ወላጅና ልጅ ... ሐኪምና ሕመምተኛ በየቱኑ ሊካድ በማይቻል ነጭና ጥቁር ውሸት የእውነትን መራራ ሥቃይ ሊያስታግሱ ይሞክራሉ። ውሸት እየረገመ የሚያቅፏት፣ በሰው ላይ እየጠሏት የራስ ጉዳይ ሲሆን ግን የሚታገሥዋት ለማጸ አውሬ መስላ ታየችው። የቀረችውን ማኪያቶ ጨልጦ ሒሳብ ለመክፈል ዘላዘስ አደረገ። በመጽሐፉ የፊት ገጽ ላይ በተንሻፈፈ ጽሑፍ የተጻፈው ' ውሸት ... ውሸት ...ውሸት' የሚለው ከመጽሐፉ

@OLDBOOOKSPDF

ሞና ርእስ ሥር ያለው ጽሑፍ ፊቱ ላይ ድቅን አለበት። በራሱና ለራሱ ማቅ አለና 'እስኪ ደግሞ ወዶ ሆስፒታሉ ሄዶን ... ብዙ የታመሙ ውሸቶችን እንስማ...' ብሎ መኪናውን አስነሥቶ ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ገሰገሰ።

ወዶ ሆስፒታሉ እየተረበበ ሲመጣ፣ ዕታ የሚኑ አይሱዙምችና አሀዮች፣ ሚኒባስ ታክሲዎችና ወደ የት እንደሚሄዱ እንኳ ለማወቅ የሚያስቸግሩ በሐሳብና በችግር የተዋጡ እግረኞች መንገዱን ሞልተውታል። እንዱ አንዱን ለመቅደም ሲሞክር በሚፈጠረው መዘጋጋት ሳቢያ 'ጊዜ' ሁሉንም ቀድሞ ያመልጣል። አንድ ወላጁ ከብዙ ጊዜ በፊት 'ኋላ ቀር ሕዝብ እርስ በርሱ ሲሽቀዳደም ጊዜ ራሱ ቀድሞ ያመልጠዋል። ጊዜ ያመለጠው ህዝብ ደግሞ ከኋላው ሌላ ሕዝብ ሊኖር አይችልምና ኋላ ቀርነቱን ማንም ሊወስድበትም ሆን ሊወስድለት አይችልም' ያለው አባባል ትዝ አለው። ከሆስፒታሉ ጋር ድንበርተኛ የሆነው አማኑኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ሲደርስ ዳገታማዋ ቀጭን መንገድ በሰውና በመኪና ተዘጋግታ እሱም ረዘም ያለ ጊዜ ቀመ።

የቤተክርስቲያኑ ሃይማኖታዊ ድባብና በዙሪያው ያለው የመርካቶ ሸቀጡ ገንዘባዊ ጥድፊያ በመሃል በተሸነቀረው ሆስፒታል ላይ የጣሉት ተጽእኖ ገዝፎ ይታያል። የቤተክርስቲያኑ ተጽእኖ በሆስፒታሉ ስም ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በአጥሩ ላይ በቀይ ቀለም በተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችም ተከትቦ ይታያል። ከፊት ለፊት ያሉት የንግድ ቤቶችና የሚያባራው የገበያ ትርዘመዘም ሁካታ ደግሞ የመርካቶን የሚጫታ ማኅተም በሆስፒታሉ የፊት ገጽ ላይ በማያሳስት ሁኔታ አኑሯል። እንደ ምንም ወደ ሆስፒታሉ መግቢያ ታጠፈና በሩ ሲከፈትለት ፈጠን ብሎ ከግቢው ጥልቅ አለ።

ከቀመት መኪኖች መሃል ወደ አንድ ጥግ አካባቢ አቁሞ ወደ ሐኪሞች ቢሮ አቀና። በቅርብ ጊዜ በተሠሩት ሁለት ሕንጻዎች መካከል እየተራመደ እዚህና እዚያ በየውሃ ልኩና መፈቱ ላይ የተኙና የተቀመጡ ሕመምተኞችን እያለፈ ሄደ። ሁሉም በራሳቸው ዓለም የተጠመዱና ለግላቸው የሚያልንመጉዎ ምናልባትም በሚወስዱት መድኃኒት የደነዘዙ መስለው ይታያሉ። ጠዋት ሲሆን ደግሞ ዐሐይ ለመጥቅም ይመስላል በቀጥር በዛ ብለው ውር ውር ይላሉ። በሰተቀኙ በኩል ያለው ሕንጻ የሴቶች መኝታ ክፍሎች የሚገኝበት ስለ ሆነም ይሆናል የሚታዩት አብዛኞቹ ሴት ሕመምተኞች ናቸው። የቀሸሸው ፒጃማቸው ገላቸውን እጅግም አለመሸፈኑ የረበሻቸውም አይመስሉም። የብዙዎቹ ጸጥር ተንጨባሮ ... ባዶ እግራቸውን ያለሟማ ወዲያ ወዲህ ሲንከላወሱ አማኑኤል የሌላ ዓለምና የሌላ ዘመን የአእምሮ ታማሚዎች ማጮሪያ እንጂ የሃያ አንደኛው ዘመን ሆስፒታል አይመስልም።

የሕመምተኞች ስም እንደ ወረፋቸው የሚጠራበትን መተላለፊያ ደሸፍ አለና ደረሻውን ከወጣ በኋላ፣ በሰው የተምላችውን ጠባብ ኮሪደር 'ይቅርታ... ይቅርታ... አንድ ጊዜ...' እያለ በሰጪ መሃል አቋራርጦ አለፈ። ወደ ዩኒቨርስቲው የአእምሮ ሕክምና መምህራን ቢሮ ከመድረሱ በፊት፣ ሁሌም ያናንጫን አትም የሚፈታተነውን 'ሽንት ቤት' ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ፣ እንደ ተቀየመ ሰው ፊቱን አዙሮ አለፈ። በግራና በቀኝ የተለያዩ ተመላላሽ ሕመምተኞች የሚታከሙበትን ክፍሎች እንዳለፈ በስተግራ ያለው ቢሮ ገርበብ ብሎ ስለነበር ሳያቆሙ ደህና አትክልቱ ገባ።

@OLDBOOOKSPDF

በየጠዋቱ ከሁሉ ቀድሞ የሚገባው ዶክተር ካሊድ ኮምፕዩተሩ ላይ ተጠምዷል። ሰላምታ ተለዋውጠው ትንሽ ከወሩ በኋላ ሰዉ እስኪመጣ ሻይ ለመጠጣት ከጮን በኩል ወዳለችው ካፊቴሪያ ሄዱ። በሆስፒታሉ ሠራተኞች የተጨናነቀችው ካፌ ውስጥ መቀመጫ ስላላገኙ ወጥተው በረንዳ ላይ ተቀመጡ። ከጣራው ላይ ካለው በረንዳ ላይ ዙርያ ገባው ሁሉ እስከ አጥር ግዶ ድረስ በግልጽ ይታያል። ያለ ምንም ከልካይ የፀሐይዋን ሙቀት ማጣጣም ስለሚቻል ሌላው ብዙ ጊዜ ውጪ መቀመጡን ይመርጣል።

ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን፣ ለጠዋት ስብሰባው ወደ ቢሮ ተመለሱ። ጠባቧ ቢሮ በሕክምና ተማሪዎችና የአእምሮ ሕክምና ሠልጣኝ ዶክተሮች ታጭቃ ደረሱ። አንድ ሦስት የሚሆኑ አስተማሪ ስፔሻሊስት ሐኪሞችም በየወንበራቸው ተሠይመው የሪፖርቱን መጀመር ይጠባበቃሉ። ከፍሏ ሾጣጣና ጠባብ ዓይነት ስትሆን፣ የሐኪሞቹ የሥራ ጠረጴዛ፣ ቅርጽና ቀለማቸው የተዘበራረቀ ወንበሮች፣ የፋይል መደርደሪያ ቁም ሣጥኖችን፣ ካለፈ የምርምር ሥራ በተራረቀ የተበላሹ ኮምፒዩተሮችና በሴሎች ዕቃዎች ተጭበራ እንዶ ጠገበ የድሃ ሆድ ተቀዝራለች።

በዶክተር ካሊድ መሪነት ስብሰባው ሲጀመር፣ አዳሪ የነበረው ሠልጣኝ ዶክተር በተረኝነቱ ሰዓት ሰላያቸው አዳዲስ ሕመምተኞችና ሌሎች አዝሎች ሪፖርቱን ባጭሩ አቀረበ። አንዳንድ ጥያቄዎች ከተሰነዘሩለት በኋላ ተማሪዎቹን ለማስተማር በማሰብ ባንዱ ሕመምተኛ ጉዳይ ላይ ገርገር ውይይት ተደረገ። በሕመሙ ምክንያት ያደረገው ነገር እስደንጋጭና እስፈሪ ስለ ነበረ ሁሉም የቀረበውን ሪፖርት ጮሮአቸውን እቁመው ነበር የሰሙት። ሰልጣኙ ዶክተር ሪፖርቱን ቀጥሎ፣

"ሰውዬው ሕመሙ ሲጀምረው 'መሥሪያ ቤቴ ውስጥ ይከታተሉኛል ... ጎረቤቶቼንም ሲ አይ ኤ ቀጥሮአቸው ካሜራ ገጥመው ቀንና ሌሊት ያዩኛል' በማለት ነበር። ከዚህም የተነሣ እንቅልፍ መተኛት ጭራሽ አቁሞ እቤት መዋል ጀመረ። እየባሰበት ሲመጣ ደግሞ የውሻዬ ጮሮ ላይ ጨረር የሚረጭ መሣሪያ ተገጥሟል በማለት የሚወደውን ውሻ በመርዝ ገደሉ እጓሮው ቀበረው። ቤተሰቦቹ ተደናግጠው ወደ ጠበል ቢወስዱትም 'ደህና ነኝ ... አሻፈረኝ' ብሎ፣ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

"ትንሽ ለነባብቶ ደግሞ ነገሩ እየባሰ ሲመጣ ሚስቱንና ሁለት ሕጻናት ልጆቹን መርዝ የሚረጭ መሣሪያ የእስራኤል የስለላ ድርጅት ደረታቸው ውስጥ ቀብሯል ማለት ጀመረ። በትናንትናው ዕለት ጠዋት ቤተሰቡን በጠቅላላ በገመድ አስሮና አንድ ክፍል ውስጥ ዘግቶባቸው ግቢ ውስጥ ሊቀብራቸው ጉድጓድ ሲቆፍር የተጠራጠሩ ጎረቤቶች ደረሱበት። ይግባቱ ባንዳቸውም ላይ አካላዊ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ደረሱበት እንጂ አሰቃቂ ነገር ነበር የሚሆነው። በመጀመሪያ ያካባቢው ሰዎችና ዘመዶቹ ተረባርበው ወደ ጳውሎስ ሆስፒታል ወስደውት፣ ከዚያ ነው ተኝቶ እንዲታከም ወደዚህ የተላለፈው" ብሎ ሪፖርቱን ጨረሰ። ጥቂት ጥያቄዎችን ከጠየቁት በኋላ በሕመሙ ምንነትና ሊደረግለት ስለሚገቡ የሕክምና አማራጮች ዘግማሽ ሰዓት በላይ ውይይት ተካሄደ።

@OLDBOOOKSPDF

የጠዋት ሪፖርቱ ሲያልቅ የሕመምተኞች ጉብኝት ጊዜ እስኪደርስ ሁሉም በየፊናው ከቢጤው ጋር ተበታተነ። አስተማሪ ሐኪሞቹ እባው ቀርተው በዩኒቨርስቲው ውስጥ ሰምኑን ስለተደረጉ ለውጦች አንሥተው ሲያወሩ ቀዩ። ለአንድ ወር የበጎ ፈቃደኝነት ሥራ ለመሥራት ከአውስትራሊያ የመጣች አንዲት አበሻ የአእምሮ ሐኪም የመጀመሪያ ቀኗ ስለነበር ሰፉ ሆስፒታሉ ውኔታ ጥቂት አስረዷት። በሆስፒታሉ ውስጥ ቀደምት ከሆኑ ሳይኪያትሪስቶች አንዱ የሆነው ዶክተር ሰቦታ ነው። ከሕመምተኛ የጉብኝት ሰዓት በፊት ሆስፒታሉን እያዞረ ሲያሳያቸው አሲንና ዶክተር ሌላሠውን ይዟቸው ወጣ።

እያንዳንዱን ክፍል እያዞረ ሆስፒታሉ ሲከፈት ከነበረው ታሪክ ጋር እያዋሃና እያጣቀሰ በመንገር አስጐብኛቸው። በመጨረሻም ቀድሞ የሠራተኞች ካፊቴርያ ከነበረውና ወደ ጥግ አካባቢ ካለ ጨለም ያለ ክፍል ገቡ።

"ቅድም የነበርንበት አዲሱ ሕንጻ ከመሠራቱ በፊት እንግዲህ ይኼ ነበር ካፈያችን። አውን ላየው የከተማ ዋሻ ነው የሚመስለኝ። ብዙ ታሪክ ያላት ቤት ናት- አለና እየሣቀ አስከትሏቸው ወደ ውስጥ ገባ። ጨለምና ቅዝቅዝ ያለ ክፍል ሲሆን፣ ዝቅ ያለ ጣራው የበለጠ ወደ ታች ይጫናል።

"እና አውንም ይሠራበታል?" አለች፣ አዲሲ ዶክተር።

"እ...ም ሥራ ይጠፋለታል ብለሽነው ዶክተር?...የሕመምተኞችና የጠያቂዎች ካፌ ሆኗል። በየጠዋቱ ምን የመሰለ ቡና መሰለሽ የሚፈላው! አንዳንዴ እዚህ መጥቶ ቁጭ ማለት ደስ ይለኛል። ቅድም እንዳየሽው ሕመምተኛውና አስታማሚው ገቢው ውስጥ ነጻ ሆኖ ነው የሚኖረው። እንደ እናንተ አገር ባንድ ጠባብ ክፍል ተቀልፎባቸው አይውሉም። ቤተሰብም፣ ሕመምተኛም ሠራተኛውም ተረዳድቶና ተያይዞ ነው ሳይኪያትሪን የሚሠራው እዚህ እኛ አገር። ደሞዝ የሚከፈለው ለኛ ሆነ እንጂ...ቱፓሬ ደሞዝ ከተባለ" ብሎ ሣቀ። ዶክተር ሰቦታ ሲሥቅ ቦርጩና ጉንጩ አብሮ ስለሚናነዝ ሣቁ በራሱ አብሮት ያለን ሰው ሳይወድ በግድ ያሥቃል። ቡና እንዲጠጡ ስለ ተጋበዙ ከወደ ጥግ ቁጭ አሉ። የድሮ ትዝታዎቹን ሲያወራላቸው ቀየና አንድ አንድ ስኒ ቡና ጠጥተው ወጡ።

ዶክተር ሌላሠው የሕመምተኛ መጐብኛ ሰዓቱ ስለ ደረሰ ይቅርታ ጠይቶ ወደሚሠራበት የሕመምተኞች ክፍል ሲሄድ ሁለቱ ተያይዘው ወደ ሐኪሞቹ ቢሮ ተመለሱ። ጠጋ እያሉ ገንዘብና ሲጋራ የሚለምኑትን ሀመምተኞች ሰላም እያለና እያሞራ ወደ ሕመምተኞች ክፍል ደረሰ። አማኑኤል በሳምንት አንድ ቀን ይመጣል፣ ከፍተኛ በሆነ የአእምሮ መታወስ የታመሙ ሕመምተኞች ተኝተው ከሚታከሙበት ክፍል ውስጥ ነው የሚሠራው። ብዙ ሕመምተኞች በየጥጋ ጥጉና በየክፍሉ መግቢያ ደጃፍ ላይ ተቀምጠው እያወሩ ዐሐይ ይሞቃሉ። አንዳንዶቹ ሰብሰብ ብለው እድግም የማይገባ ነገር እያወሩ ይሣሣቃሉ። ሌሎቹ ደግሞ ለብቻቸው ፈገጠር ብለው ከማይታዩ አጋሮቻቸው ጋር ይሟገታሉ፣ ወይ ያወጋሉ።

@OLDBOOOKSPDF

ሌላሠው በራፉ ላይ ቀም ብሎ "እንደምን አላችሁ?" ሲል ብዙዎቹ ሕመምተኞች ብድግ ብድግ እያሉ አጸፋ ሰላምታ ሰጡት። የተወሰኑት ከኋላ ተከትለውት ወደ ውስጥ ገብተው የነርሶቹ የሥራ ኪላ አካባቢ ትንሽ እንገፓበቡና ወደ የመኝታቸው ሄደው ጋደም ጋደም አሉ። አልጋዎቹ እንደ ወታደር ካምፕ ተቀራርበው የተዘረጉ ናቸው። ባለው የበታ ጥበት የተነሳ የሕመምተኞችን ደህንነትና የግል ነጻነት ያገናዘቡ አይደሉም።

ሕመምተኞች ወደ ሚታዩበት ክፍል ሲገባ ተማሪዎችና ሠልጣኝ ዶክተሮቹ በረድፍ ተደርድረው ሲጠብቁት ደረሰ። ተማሪዎቹ ቶሎ ቶሎ ስለሚለዋወጡ ስማቸውን ብቻ ሳይሆን መልካቸውንም ለማጥናት ያስቸግራል። ዛሬም አዲስ ዙር ተማሪዎች ናቸው ያሉት። የሕክምና፣ የነርሲንግ፣ የማማከርና የጤና መኩንንነት ተማሪዎች እየተፈራረቁ ስለሚመጡ ማን ማን መሆኑም ለማወቅ ይከብዳል። ሁሉም የአእምሮ ሕክምና ሠልጣኝ ዶክተሮችንና የክፍሉን ጽሚ ነርሶች በስማቸው እየጠራ ሰላም ብሎ በተዘጋጀለት ወንበር ላይ ተሠየመ።

"እሺ ሰላም ነው... ታዲያስ? ዛሬም አዳዲስ ተማሪዎች ያሉን ይመስላል ... ሁላችሁም የሕክምና ተማሪዎች ናችሁ መይስ?" ብሎ፣ ተራ በተራ ወደ ተማሪዎቹ ሲያማትር ሁሉም በአምንታ ራሳቸው ነቀነቁ። ሁሉም የመጪረሻ ዓመት የጥቁር አንበሳ ተማሪዎች መሆናቸውን ነገሩት። ለመተዋወቅ ያህል የያንዳንዳቸውን ስምና ሲጨርሱ ምን የሕክምና ዘርፍ ማጥናት እንደሚያስቡ ጠይቀ ትንሽ ካወራቸው በኋላ የቡድኑ መሪ ወደ ሆነችው ሠልጣኝ ዶክተር ዘወር ብሎ፣ "ዛሬ ብዙ የሚታዩ ሕመምተኞች አሉን እንዴ ዶክተር ምዕራፍ?" አለ፣ ከፊት ለፊቷ ወደ ተከመሩት ቻርቶች እያየ።

"እዚህ ወንዶቹ ክፍል ሦስት አዳዲስ ሕመምተኞችና ሁለት ደግሞ አስቸጋሪ የቀዩ ኪዞች አሉን። የምንችለውን ሁሉ ብናደርግም እየባሰባቸው ነው። እንዱ በተለይ ሌላ ሕመምተኛና ስታፍ ካልደበደብኩ ብሎ እያስቸገረ ነው። ትናንት ሌሊት መስኮት ሰብሮ በግድ ነው መርፈም የተወጋላቸው። ሌላው አዲስ ሕመምተኛ ግን ያጠዋት የተወያየንበት ኬዝ ነው" ብላ፣ እምታገላብጣቸው ቻርቶች ላይ ዓይኗን ተክላ ዝም አለች።

"ኦኬ ... ጥሩ፣ በሌቶች በኩልስ ምን ያህል ሕመምተኞች አሉን?" አለ፣ የሚኖረውን ጊዜና መታየት ያለባቸውን ሕመምተኞች ቁጥር ለማመጣጠን በማሰብ።

"አዲስ ሕመምተኛ የለንም፣ ግን ሁለት ኬዞች አሉ አብረን ብናያቸው ብለን ያሰብናቸው። አንዷ ዝናሽ ናት" አለች፣ የሚታዩትን ቻርቶች ከሌላኛው የአንደኛ ዓመት ሠልጣኝ ዶክተር ጋር እየተከፋፈሉ። የአእምሮ ሕክምና ስፔሻላይዘሽን ሥልጠናው በአጠቃላይ የሚወስደው ሦስት ዓመት ነው።

"ኦው ... ዝናሽን አይተኻት ነበር? እንዴት ናት? እንደውም ካባቷ ጋር ዛሬ ቀን ሰዎንት ሰዓት ላይ ቀጠሮ አለን አይደል ሲስተር?" አለ፣ ዓይኑን በዶክተር ምዕራፍና በኃላፊ ነርቧ መካከል እያመላለሰ።

"እምን ... እንግዲህ አልቀርም እመጣለሁ ብለውኛል ከትናንት ወዲያ። አቧም ብዙ ሰወጥ አላት። አሁንማ ወሯም እየገባ ነው መሰለኝ፣ አልትራሳውንዱ

@OLDBOOOKSPDF

የሚያሳየው እንደዛ ነው። ሌላው ሞንቱት ግን እንግዲህ ድንገት ምጥ የመጣ እንደሆነ ነው። በየሆስፒታሉ የኛን ሕመምተኞች ለመቀበል ያለው ችግር ሥታይ ነው።" አለች፣ ሃላፊ ነርሲ ትንሽ በስጨት ባለ ድምጽ።

"እኔም እሱን ሳስብ ነበር። በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው ...ምን ማድረግ ይሻል ይሆን ታዲያ? ለመሆኑ የቤተሰቦቿ የኑሮ ሁኔታ እንዴት ነው?" አለ፣ ፊቱ ላይ ግልጽ ያልሆነ ሞንቱት እየተነበበት። ኃላፊ ነርሲ አሁንም ተበል አድርጋ፣

"አዱ ዶክተር ሌላሠው ... አባቷ ድክም ያሉ ሽማግሌ ናቸው። ለራሳቸውም በልመና ነው የሚተዳደሩት። እንደ ሰማሁት ከሆነ የርሲንም ሁለት ሕፃናት ልጆችም የሚያሳድጉት እሳቸው ናቸው። እንጃ ... የሆነ ነገር ካልተገኘ፣ እንዲያው ምንም ተስፋ ያለውም አይመስለኝም" ስትል፣ ከፍሉ በጨለምተኛ ድባብ ተሞላ።

"የሆነ ነገርማ መደረግ መቻል አለበት። ለማንኛውም እስኪ እሳቸውንም በኋላ አናግራቸዋለሁ። እስኪ እዚህ ያሉንን ሕመምተኞች እንይና ወደ ሴቶች ክፍል ስንሄድ ስለርሲ እናወራለን" አለና ወደ ተማሪዎቹ ዘረ። "ያው ለዛሬ አዲስ በለሆናችሁ የሚደረገውን እዩ። ጥያቄ ካላችሁ በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ትችላላችሁ። ከዚያ እነ ዶክተር ምዕራፍ ሁለት ሁለት ኪዞች ይሰጧችኋል። በዚህ ሳምንት እነርሱን ኢንተርቪው አድርጋችሁ በሚቀጥለው ታተርባላችሁ። ምን ያህል ጊዜ ነው ከኛ ጋር የምትቆዩት?"

"ሁለት ሳምንት" አለ፣ አንደኛው ተማሪ ፈጠን ብሎ።

"ጥሩ ... በታ የተቻለውን እናደርጋለና። ያው እንደምታውቁት እዚህ ክፍል በተለይ የአእምሮ መታወስና መረበሽ የደረሰባቸው የስኪዞፍሬንያ ሀመምተኞች ናቸው ያሉን። ስለዚህ ቢያንስ ያንን በደንብ ማወቅ ይጠበቅባችኋል። አስቸጋሪና አደገ የታመሙ ሕመምተኞችን ስታዩ ግን ከነ ዶክተር ምዕራፍ ጋር መሆን አለባችሁ፣ ቢያንስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለብቻችሁ ሕመምተኛ እንዳታዩ። ሁሉም ነገር ቀስ ተብሎ ነው፣ ብዙ አትዳፈሩ። ኦኬ ... ታዲያ የመጀመሪያውን ኬዝ ማነው የሚያቀርብልገ"

ያሉትን ሕመምተኞች ጉዳይና ሕክምናቸውን እየተወያዩ መደረግ ያለበትን ነገር ወስነው ሲጨርሱ፣ ሴሎች ጉዳዮችን ሲያወሩና የተነሡ ጥያቄዎችን ሲመለሰ ቆዩ። ከተረበሹና በከፍተኛ ደረጃ ከታመሙ ሕመምተኞች ጋር እንዴት ማውራት እንዳለባቸው በተግባር እያሳየና በገለጻ እያብራራ አስተማራቸው። ውይይቱን ሲጨርሱ የክፍሉን ነርሶች እመስግኖና ተሰናብቶ ወደ ሴቶቹ ክፍል ለመሄድ ተነሡ፣ ወደ እዛው እየሄዱ ከዶክተር ሲራክ ጋር የምሳ ቀጠሮ ስለ ነበራቸው ቦታና ሰዓቱን ለማረጋገጥ ደወለለት።

ወደ ሴቶቹ ክፍል ሲደርሱ፣ ዝናሽ ከአንዲ ነርስ ጋር ቀማ ስታወራ አይቶ ባሳየችው ለውጥ ውስጡ ደስ አለው። ሰውነቷ መለስ ያለ ይመስላል። ጸጉሯ ታጥቦና ተስተካክሎ ሻሽ ጣል አድርጋበት ሌላ ሰው አስመስሏታል። ባለቤቱ ንጹሕ የላከችላት የንፍሰ ጡር ተሚሰም ተስማምቷታል። ሌላሠውን ስታይ ፈገግ ብላ ከበሩ ላይ ቦር

@OLDBOOOKSPDF

አለችና ዓይኗን ሰበር አደረገች ። በደህናው ቀን ምን ዓይነት ሴት ትሆን ይሆን የሚል ጥያቄ በውስጡ አለፈ ።

"ታድያስ ዝናሽ ... እንዴት አለሽ?" አላት ፣ አጠገቧ ሲደርስ ።

"ደህና ነው ... ደህና... እየተሻለኝ ነው" አለች ፣ እንዳቀረቀረች ። የመድኃኒቱ የጮን ጉዳት ይመስላል ትንሽ እንትስታሴዋ ዘገም ፣ ሰሜቷም ደብዘዝ ያለ መስሎ ታየው ። ከህመሙ እንጻር ሰጊዘው የጮን ጉዳቱን መታገሡ የግድ መሆኑን አወቋል ።

"እንዴት ነው እንትልፍስ ትተኛለሽ?" አላት ፣ አሁንም ሁኔታዋን ለማጥናት እየሞከረ ።

"አዎን ... ምንም አይል ..." አለች ፣ ጣቶቿን እያፍተለተለች ። ረጃጅምና ቀንጅዬ ጣቶች እንዳሏት አስተዋለ ።

"እሺ ጥሩ ነው ፣ በቃ ወደ ውስጥ ገብተን ፣ ተራሽ ሲደርስ እናይሻለን" ብሎ ፣ ትከሻዋን በማደፋፈር አይነት መታ መታ አደረገና ከሕክምና ቡድኑ ጋር ተከታትለው ገቡ ። ሌሎቹን ሕመምተኞች አይተው ሲጨርሱ ነበር ዝናሽን ያዩዋት ።

ሻሿን ፊትታ እንደ እንገት ልብስ ጣል አድርጋ ከራት ሰፊት ያለው ወንበር ላይ ተቀመጠች ። የእግር ጣት ጥፍሮቿ ተቁርጠው ፣ ቀለል ያለ ጫማ ተጫምታ ስትታይ በባዶ እግሯ ስትዳክር የከረመች አትመስልም ። ጠቁሮና ገርጥቶ የነበረው መልኳ መመለስ ሲጀምር ፣ የሚያምር የጥቁር ጠይም ቀለሟ መውጣት ጀምሯል ። የስሜቷ መስከንና የአስተሳሰቧ መረጋጋት ፣ መልኳንና የሴትነት ወዘናዋን መልሶት ደርባባ ነፍሰ ጡር አስመስሏታል ። በጫማዋ መሬቱን እየጠበጠበች ፣ አገዟን ባስደገፈችበት እጇ ጭንቅላቷን እንደ ተሸከመች ሰውነቷን አስቀምጣላቸው በሐሳብ ጭልጥ ብላ ሩቅ ሄዳለች ።

የተጋገረውን የጸጥታ በረዶ ለመስበር በማሰብ ፣ "እንዴት ነው ... መድኃኒቱ ተስማማሽ ዝናሽ?"

ከእንቅልፏ እንደባነነ ደንገጥ ብላ ፣ "እ ... ጥ...ጥሩ ነው መሰለኝ ፣ ያው ነው ። ድከም ይለኛል ግን ፣ መድኃኒቱ ነው መሰል ፍዝዝ ያደርገኛል ። እነርሱም ደግሞ ተይ ኪኒኑን አትውሰጂ ይትርብሽ ሊገድሉሽ ነው ይሉኛል ። እስኪ ተዉ ... ኡፍ" አለችና በስጪት በማለት እጇን ስታወናጭፍ ፣

"እነማናቸው እነሱ?" አለ ፣ ፊቱን ትጭም አድርጎ ።

"ያው የልጁ ባለቤቶች ናቸዋ ። ልጁን ሊገድሉብን ነው ኪኒንና መርፌ የሚሰጡሽ ይላሉ ። ሌሊት ፀጥተው ደግሞ ... ኡፍ ...ፍ ... እይሰማችሁም ሲያንሾካሽኩ ። ግን መድኃኒቱ ሰው ይገድላል እንዴ?" ትክ ብላ ስታየው መረበሿን በመረዳት እንዴት ሊያስረዳት እንደሚችል ትንሽ አሰበ ።

@OLDBOOOKSPDF

"እየውልሽ ዝናሽ የምንሰጥሽ መድኃኒት ላንቺም ሆነ ለጽጌሉ ጤዝት በጣም አስፈላጊ ነው። አሁን ሚንትላትሽ ውስጥ እየሰማሽ ያለው ድምፅና ሐሳቧ እንደሚረብሽሽ ይገባኛል። ዶግሞ ብዙ ጊዜ ጥሩ ምክርም አይሰጥሽም አይደል?"

"ኡፍ...ፍ ምን ጥሩ ምክር አለ ብለሀ ነው። ቶይ ዝም እንጂሉ ማድረጊያ ነገር የለም እንዴ? ምነው አሁንስ ... እነርሱ ያለ እኔም ሰው አላዩም እንዴ? ተውኝ ካልኳቸውማ በቃ የባስ ጆሮዬ እስኪደነቁር ይጮሁብኛል፣ ዶግሞ ያስፈራሉኛል። ትንሽም ጋብ የሚልልኝ ወይ ስተኛ ወይ መድኃኒቱን እንደ ወሰድኩ አካባቢ ብቻ ነው ብላ፣ ርብሽ ያለ ፊቷን በጆሯ ሸፍና ዝም አለች።

"እስኪ መድኃኒቱንም እናስተካክልልሻለን። ድምፁ ሲረብሽሽ ደግሞ ለነሲስተር ንገሪያቸው። ድምፁን ከጆሮሽ ላይ የሚያጠፋ መድኃኒት ይሰጡሻል። ሁለት ሳምንት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ብዙ ለውጥ ነው ያላየሽው። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ዶግሞ የበለጠ ደህና ትሆኛለሽ። ስለዚህ አይዞሽ። ሌላስ ምን ችግር አለ?" አለ፣ ሥቃዩዋ እያሳዘነው።

"እኔ እንኳ፣ በቃ ድምፁን ካጠፉችሁልኝ ሌላው ደህና ነው መሰለኝ። የማያደክምና የማያፈዝ መድኃኒትስ የለም እንዴ? በፊትም እኮ ሻል ሲለኝ መድኃኒቱን የማቆመው ለዚህ ነው" አለች፣ በከፊል ቀና ብላ ሁሉንም በወይኗ ገረፍ እያደረገች።

"እስኪ ከነዶክተር ምዕራፍ ጋር ተነጋግረን የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለና። ቤተሰብስ ይመጣሉ ሊያዩሽ?" አለ፣ ርዕሱን መቀየር ስለፈለገ። እግረ መንገዱንም ከቤተሰብ ጋር ያለውን ሁኔታ ለመቃኘትና ከአባቷ ጋር ያለውን የከሰዓት በኋላ ቀጠሮውንም ታውቅ አታውቅ መሆኑን ለማወቅ ፈልጎ።

"ምን ቤተሰብ አለና ... አባቱ ነው ያለው ... እሱም አርጅቷል ... ልመና ነው የሚውለው .... አንድ ሁለት ጊዜ መጥቶ ነበር መሰለኝ ..." ብላ፣ ትከዝ አለች።

"አባትሽ ዛሬ በኋላ ይመጣሉ መሰለኝ። አይዞሽ እኛም የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን። እስኪ የቀረውን ዶግሞ ከሰዓት በኋላ እናወራለን" ሲላት፣ ምንም እንጻልሰማ ዝም ብላ መራቱን መቀርቀሯን ቀጠለች።

"ዕንሱስ እንዴት ነው? ወርሽም እየገባ ነው አይደል?" ሲል፣ ትዝሻዋን ሰበት አድርጋ አሁንም ዝም አለች። ወደ በሩ ደጋግማ ስታይ በለጪ ብዛት ተጨንቃ ሊሆን እንድሚችል ገምቶ፣ "በቃ እሺ ከሰዓት በኋላ አባትሽን ካዋራው በኋላ እናገርሻለሁ፣ ጥያቄ ከሌለሽ አሁን መሄድ ትችያለሽ። ችግር ካለ ግን ለነሲስተር ንገሪያቸው እሺ?" ብሎ፣ እጁን ሲዘረጋላት ላመል ያህል ጨብጣው እንዳገነበለች ወጣች። እሷ እንደ ወጣች ሠልጣኝ ዶክተሮችን ጨምሮ ከተማሪዎቹ ጀምሮ በተራና በየደረጃው ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለ ዝናሽ ሕመም ትምህርታዊ ውይይት ጀመሩ።

"እሺ ስለ ዝናሽ ዶክተር በነገረችን ታሪክና ከራሷም በሰማነው መሠረት ሕመሟ ምን ይመስላችኋል?" አለ፣ ወደ ተማሪዎቹ እያየ። አጠር ቀጠን ያለች ከፊት ለፊት የተቀመጠች ተማሪ ፈጠን ብላ፣

"ዘሮኒክ ፓራኖይድ ስኪዞፍሬንያ ..." አለች፣ ድግሞ በሆነ ቁርጥ ያለ ድምፅ

@OLDBOOKSPDF

"ስኪዞፍሬንያ ምን እንደሆነና ያንን ለማለት ያስቻሉሽን ፣ ዝናሽ ላይ ያሉትን የሕመም ምልክቶች ልትነግሪን ትችያለሽ?" ሲላት ፣ ጥያቄውን ስላልጠበቀች ትላልት ዓይናቿ ከገሬያቸው በዝፊል ወጥተው በፊቷ ላይ ተንከባለሉ ። ጥቂት ካሰበች በኋላ ፣

"እ...ም ዘርኒዝ የምንለው ያው ካንድ ዓመት በላይ በመታመሚ ሲሆን ... እም... ያው ከፍተኛ የመጠራጠርና ያለማመን ስሜት ስላላት ፓራኖይድ ዓይነቱ ነው ሊባል ይችላል ። ድምፅ መስማቷ ፣ የተለያዩ ከእውነታ የወጡ አስተሳሰቦችና እምነቶችም ስላሉዋት ስኪዞፍሬንያ ይመስለኛል ሕመሚ" ስትል ፣ የእንግሊዝኛ አነጋገር ችሎታዋ ብቻ ሳይሆን ስለ ሕመሙም ያላት ግልጽ መረዳት ደስ ብሎት ፣

"በጣም ጥሩ ... ሌላስ ..." አለ ፣ ወደ ሌሎቹ ተማሪዎች ዞሮ ። ሁሉም ዝም ሲሉ ወደ አንደኛ ዓመት ሠልጣኝ ሐኪሙ ዞር አለ ።

"ከዛ በተጨማሪም የባሕርይ መረበሽና የንግግር መዘበራረትን ማላየትንም ይጨምራል ። የአእምሮ መረበሽን የሚያመጡ እንደ አደንዛዥ ዕፆችና የተለያዩ አካላዊ ሕመሞች እንደ መንስኤ ካሉ ግን ሕመሙን በርግጠኝነት ስኪዞፍሬንያ ማለት አይቻልም ። ዝናሽ ግን ሱስ ቢኖርባትም ፣ ከሕመሙ በኋላ የጀመረቻቸው ስለሆኑ ሕመሙን ሊያባብሱት ይችላሉ እንጂ እንደ መንስኤ ልናያቸው እንችልም ። ሌላ ይህ ነው የሚባል የአእምሮ መረበሽን ሊያመጣ የሚችል አካላዊ የሆነ ሜዲካል ችግር ያላት አይመስለኝም" አለና ተስተካክሎ ተቀመጠ ።

ሌላሠው ከሱ ቀበል አድርገ ፣ "ልክ ነው ... በንግራችን ላይ ስኪዞፍሬንያ የምንለው በአብዛኛው በተለምዶ 'እብዶት' የምንለውን ችግር ነው ። ብዙ ጊዜ በየመንገዱ የምናያቸው ጨርቃቸውን የጣሉ 'እብዶች' የዚህ ሕመም ተጠቂዎች ናቸው ። የቃሉ ጥሬ ትርጉም 'የተከፋፈለ አእምሮ' እንደ ማለት ነው ። ይህም ሕመሙ የውጭውን ነባራዊ እውነታና በውስጣችን የሚገኘውን የሐሳብ ዓለም አጣጥሞና አስማምቶ ለመኖር አለመቻልን ስለሚፈጥር ነው ። ያልሆኑ ነገሮችን ማመንና የሆኑትን መካድ ... ያልተፈጠሩ ነገሮችን ማየትና መስማትን ... በዚህም የውስጥ መረበሽ የተነሣ ... የንግግር ፣ የባሕርይና የስሜት መዛባቶችም ይፈጠራሉ ። እሺ ጥሩ ... መንስኤውስ ምንድነው?" በማለት ፣ ተማሪዎቹን ሲያይ ሁሉም ዝም ዝም ብለው ዓይናቸውን ሲያሸሹ ወደ ዶክተር ምዕራፍ ዞር አለ ።

የያዘችውን የሕመምተኛ ካርድ እየዘጋች ጉሮሮዋን ጠረግረግ አድርጋ ፣ "እርግጠኛ የሆነ አንድ መንስኤ ተብሎ የሚባል ነገር እስካሁን አልተገኘም ። ግን ብዙ መላምቶች አሉ ። ዋና ዋናዎቹን ከሕመሙ መነሰት ጋር የሚያያዙ ነገሮች በአጠቃላይ በሦስት ልንከፍላቸው እንችላለን" አለችና ያሰበችው የጠፋባት ይመስል የያዘችውን አሰከርቢቶ እያፍተለተለች ትንሽ አሰብ አድርጋ ፣ "ይህም ለሕመሙ የሚያጋልጡ ፣ ሕመሙን የሚቀሰትሱና የሚያባብሱ ነገሮች ብለን እንከፋፍላቸዋለን ። ማንም ሰው ለሕመሙ መቶ በመቶ ያልተጋለጠ ነው ማለት ባይቻልም አንዳንድ ሰዎች ግን በትርብ ዘመዶቻቸው ወይም በቤተሰብ ውስጥ ሕመሙ ያለበት ሰው ካለ ከሌላው ሰው የበለጠ

@OLDBOOOKSPDF

የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ ። እም...ም በተጨማሪም አንዳንድ የሰብአና አወቃቀርችው የትድሙ ስኪዞፍሬንያ ምልክት ሊሆኑ ይችላሉ ። ከዚያ ውጪ ያሉት ቲዎሪዎች ግንኙ የሩቅ መላምቶች ይመስሉኛል ።

"በሌላ በኩል ደግሞ ከእትም በላይ የሆነ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ጫና ሲኖር፣ በለጋ ዕድሜ ሱስ በሚያሲዙ እደገኛ ዕፆች መጠመድ፣ ከፍተኛ በሆነ አካላዊ እደጋ ላቢያ የጭንቅላት መጮዳት ሲደርስና የመሳሰሉት ደግሞ ሕመሙ እንዲከሰት አስተዋጽኦ ሊኖራቸው ይችላል ። በተጨማሪም ሌሎች ማኅበራዊና የግል ሕይወት ጫናዎችና መድኃኒቱን በትክክል አለመከታተልና የመሳሰሉ ነገሮች ደግሞ ሕመሙ ለመባባሱና ላለመሻሉ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ..." ብላ ፣ ሐሳብ እንዳለቀባት ድንገት ዝም አትል፣

"በጣም ጥሩ ነው ። ሌላው እይታ ደግሞ በአንጎላችን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ኬሚካሎች መዛባት ይሆናል የሚለው ነው ። ለምሳሌ ዶፓሚን የሚባለው ኬሚካል ተዛብቶ ባንዳንድ ያንጎላችን ክፍሎች ከሚገባው በላይ ሊበዛ ወይም ሊያገስ ይችላል የሚለው መላ ምት አለ ። የምንሰጣቸው መድኃኒቶች በአብዛኛው ይህንን መዛባት ነው የሚያስተካክሉት ። ሌሎች ቲዎሪዎች ደግሞ እንደ ሴሮቶኒንና ግሉታሚት የመሳሰሉ በአንጎል ውስጥ ያሉ ሌሎች ጠቃሚ ንጥረ ነገሮች መዛባት ነው ይላሉ ። ለዚህ ነው ለምሳሌ የተለያዩ እደንዛዥ ዕፆችን በከፍተኛ ደረጃ የሚወስዱ ሰዎች የአንጎላቸው ውስጥ ኬሚካሎች ሲዛቡ ፍጹም ስኪዞፍሬንያ ብለን ከምንጠራው የአእምሮ መረበሽ ሕመም ተመሳሳይ ምልክቶችን የሚያሳዩት" ብሎ፣ የተለያዩ ቲዎሪዎችን ከነመገፃ ሐሳባቸው ጋር በስፊው ካሰረዳቸው በኋላ፣ ጥያቄዎቻቸውን ሲመልስ ቆየ ። ሰዓቱን እይቶ ለመውጣት ሲል አንደኛዋ ተማሪ እጇን አውጥታ ጥያቄ አቀረበች ።

"ብዙ ጊዜ ባጠቃላይ የአእምሮ ሕመሞች በተለይ ደግሞ ስኪዞፍረኒያ የምንለው የአእምሮ መታወስ ሲፈጠር መንፈሳዊ መንስኤ አለው ተብሎ ነው የሚታመነው ... በተለይ በእኛ ባህል ውስጥ ። ከአእምሮ ሕክምና ሳይንስ አንጻር ስለ መንፈሳዊ ነገር ያለው እይታ ምንድን ነው?" ብላ፣ ባንሣችው ሐሳብ ዙሪያ የተነሳ የጋለ ውይይትና ክርክር ሊያደርጉ ቆዩ ።

በመጨረሻም እሱ ነገሩን ሲያጠቃልለው፣ "እ ...ም እንግዲህ ምን ያህሉ መንፈሳዊ ነው፣ ምን ያህሉ አካላዊ ነው፣ የሚለው ሁሌም አከራካሪ ነገር ነው ። ባገኘው በኩል የጉበትና የጨጓራን ህመም እንደ ተፈጥሮአዊና አካላዊ ሕመም አድርጎ መቀበል ለብዙ ሰው ቀላል ነው ። የአእምሮ ሕመም ሲሆን ግን አንጎልም የሰውነት አካል ስለሆነ በተመሳሳይ መንገድ ሊታመም ይችላል ብሎ ማመን የሚቸግራቸው ብዙ ሰዎች አሉ ። ብዙ ጊዜ በሃይማኖት አካባቢ ያሉ ሰዎች አካላዊ ገጽታውን ለመተበል ይቸገራሉ ።

"በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው የአእምሮ ሕክምናና የሥነልቦና ሳይንሶችን ጥልቀ ያለው የሕይወት እይታ ወይም ንጽረተ ዓለም የመንፈሳዊውን ዓለም መኖር አይቀበልም ። በዚህ ቁሳዊ በሆነ የፍልስፍና እይታ የፈጣሪን መኖር ጨምሮ ሰይጣንና ጋኔን የሚባል ነገር አለ ብሎ ማመንም እንደ ሞኝነት ነው የሚታየው ። ሰዎች በርኩስ መንፈስ ተይዘው ባሕርያቸውና ማንነታቸው ይቀየራል የሚለውን እይታ እንደ ከንቱ

@OLDBOOOKSPDF

ያረጀ ያፈጀ ልማድ ነው የሚወስዱት ። የሰውን መንፈሳዊነት የሚቀበሉበት ሁኔታ ቢኖርም ሰው ውስጥ ተጀምሮ ሰው ውስጥ እንደሚያልቅ እውነታ ወይም አንድ የማንነት መገለጫ አድርገው ብቻ ነው የሚወስዱት ። መንፈሳዊውን ዓለምና እውነታ መቀበል በማይቻልበት ሁኔታ ደግሞ ችግሩንም ሆነ መፍትሔውን መንፈሳዊ አድርገ መውሰድ ራሱ ኢሳይንሳዊ ተደርገ ነው የሚገመተው ።

"በእኔ እይታ ግን ... ሰው ሁለቱም ካምፖች ከሚሉት በላይ የተወሳሰበና ምስጢራዊ የሆነ ፍጥረት ይመስለኛል ። እኔ ባለኝ ልምድ በመንፈሳዊ እገዛ ፈጽመው የተረዱም የተገዱም ሰዎች አውቃለሁ ። በተመሳሳይ ሁኔታ በዘመናዊው ቁስ መር ሕክምናም የተረዱም የተገዱም ሰዎች አሉ ። አሁን የደረስኩበት መረዳት ፣ ሰው አንድ ስለሆነ ሳናከፋፍልም ሳናበላልጥም በሁለቱም እውነታዎች ሊታይና ሊረዳ ይገባል ነው ። በመንፈሳዊውም ሆነ በአካላዊው መፍትሔዎች በኩል ያሉትን ጥሩ ነገሮች ክፍት በሆነ ልቦና መጠቀም ያስፈልጋል ባይ ነኝ ። በመካከል በተፈጠረው ገደል ላይ ድልድይ መሥራት የሚሻል ይመስለኛል ። አለበለዚያ ከሁሉም በላይ የሚጐዳው ሕመምተኛው ነው" አለ ፣ በረጅሙ ተንፍሶ ሰዓቱን እያየ ።

"ኦህ ማይ ... ሰዓቱ እንዴት ሄዷል ባካችሁ ። ለምሳ ቀጠሮዬ ሳላረፍድም አልቀረሁ ። ለማንኛውም ይሄ ብዙ አነጋጋሪም እከራካሪም ጉዳይ ነው ። ስለዚህ በሚቀጥለው ሳምንት እንቀጥለዋለን ።" አለና ወደ ሃላፊ ነርሷ እያየ ፣ "ሲስተርዬ ፣ ያው ስምንት ሰዓት ላይ እመጣለሁ ። በሉ ቻው" አለና እጁን ለሰላምታ አውለብልቦ እየተጣደፈ ትቷቸው ወጣ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 9 ፡

ሌላሠው፡ የቀጠሮው ሰዓት ስለረፈደበት ልቡ ተሰቅሏል። ከሆስፒታል ወጥቶ ውስጥ ለውስጥ እየነዳ፣ ወደ ዋናው መንገድ ከመግባቱ በፊት ከተቃራኒ አቅጣጫ የመጡ መኪኖች ዘግተውበት ቆመ። የሁለቱ መኪኖች ሾፈሮች ወርደው በጋለ ስሜት ሲነጋገሩ እንደሚረፍድበት ስለገመተ ሲራከ ጋ ደውሎ ይቅርታ ጠይቀው።

የባለ መኪናቹ ንግግር ወደ ስድብና ሚኮትሚኮት ሲቀየር እሱም ከመኪናው ወረደ። አጠገባቸው ሲደርስ፣ ከፊትና ከኋላ መንገዱ ተጨናንቆ በሰው ተከበቡ። "ቀይ እና ምን ይጠበስ ነው የምትለው? እኔ ላይ ስለዘጋህ በለዓት ደረስክ እንዴ? ... የሰው መንገድ ስለዘጋህ እኮ ያንተ እይከፈትልህም" አለ፣ ሰውነቱ ደልደል ያለ ሃይሉክስ ቶዮታ መኪና የያዘው ረጅም ሰውዬ።

"እቦ ዝም ብልህ ሰው ላይ አትደንፋ ... በትክክል መንዳት የማትችል ከሆነ ... አስተማሪ ቀጥረህ መማር ትችላለህ። ምን ... ሰሞኑን የገዛኸው መኪና ነው እንዴ? ራስህ ከጮን ገብተህ ጥልቅ ካልክ በኋላ ... ደግሞ ካንተ ብሶ ... የማነው ባካችሁ?" አለና ተጠጋው፣ ጠቀር ቀጠን ያለው ባለ አይሱዙው ሾፈር። የባለ አይሱዙው ረዳት ለጥል አቀብቱቦ ከሌላኛው ሾፈር አጠገብ ቀሚል።

"እሺ ... አሁን መንገዱን ትለቅልኛለህ ... ወይስ?" አለ፣ ረጅሙ ሰውዬ፣ እጆቹን ጨብጦ እየተጠጋው።

"ባለቅልህ ምን ታመጣለህ? ... ከፈለግህ ወደ ኋላ ወጥተህ ..." ብሎ ሳይጨርስ፣ የሃይላክሱ ባለመኪና በቦክስ ነረተው። ሁለቱ ተናንቀው ሲቀራቀሱ የአይሱዙው ረዳት ዝየት መጣ ሳይባል፣ በያዘው የሌባ ጉማ ሌላኛውን ሾፈር ሙንቅላቱ ላይ ሲዝለጠው ሙኽ ወደቀ። ሌላሠው ተንደርድሮ ረዳቱን ሲይዘው፣ ሌሎቹ የከበቢቸው ሰዎች ደግሞ ሁለቱን ለማለያየት ተረባረቡ። የተፈጠረውን ጠብ ማብረድ ካትም በላይ ሆነ፣ በዘህም ምክንያት ፖሊስ እስኪመጣ ድረስ ያዙኝ ልቀቁኝ ተጠለ።

ሌላሠው መኪናውን እንደ ሾፈር አላልፎ መንገዱን ቀጠለ፣ ሁለት በምክንያትና በመረዳዳት ሊነጋገሩ የሚችሉ ሰዎች፣ በጡጫና በርግማ

@OLDBOOKSPDF

ለመግባባት መሞከራቸው ይገርማል ። ስሜት ፣ ማሰብን ሲገዛና ሲክልል ትልቅ ሰው ትንሽ ይሆናል ። ሰሜቱ ያሸነፈው ሰውና ፍራት ተበጥሶ መሪው የማይሰራ በፍጥነት የሚገሰግስ መኪና እንድ ናቸው' ብሎ አሰበ ።

ከመኪናው በጥድፊያ ወርዶ ከሲራክ ጋር ለምላ እተቃጠሩበት ቤት ገባ ። ቀድሞት ደርሶ ኖሮ ቦታ ይዞ በተመስጦ ሲያነብ ደረሰ ። ትከሻውን ነካ አደረገና እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ ፣ "ሄይ ፣ ወጣቱ ዶክተር ... በጣም ይቅርታ ... ከተማሪዎቹ ጋር አንላቀቅ ብለን ... ሳላሰበው ጊዜው እንደ ሄደም ሳላው ት አረፈድኩ ። ታዲያስ ... ብዙ አስጠበቅሁህ እንዴ?" አለው ።

"እይ ፣ ኧረ አሁን ነው የመጣሁት ። አንዳንዴ መንገዱም እኮ ያላሰብክበት ቦታ ይዘጋጋል ። እንዴት ነው ... አማኑኤል ሰላም ነው?" አለ ፣ ፈገግ ብሎ ።

"አማኑኤልና ሰላም ... በሽበሽ ነው" አለና ኮቱን አወልቆ ወንበሩ መደገፊያ ላይ ሰቀለና ተቀመጠ ። ቤቱ ብዙ ብርሃን የሚገባበትና መቀመጫዎቹም ዘርዘር ብለው የተሰናዱ ስለ ሆነ ቅልል ይላል ። የበግ ጥብስና ሽሮአቸው ታዋቂ ነው ።

ሲራክ ሁሌም መጽሐፍ ከእጁ አይለየውም ። ሴላሠው ጥቁር እንበሳ ሊያስተምር በሄደበት ጊዜ ተዋውቀው በቀላሉ ነበር የተግባቡት ። በሳምንት እንዴም ሁለቴም ለምላ ወይ ለቡና መገናኘት ልማዳቸው ሆኗል ።

"ምን እያነበብክ ነው?" አለ ፣ ሴላሠው ከፊት ለፊቱ ዘግቶ ያስቀመጠውን መጽሐፍ ለማንሣት እጁን እየዘረጋ ። መጽሐፉን ወዶ እርሱ እየገፋለት ፣

"የሲግመን ፍሩይድ ... ዘ ኢንተርፕሪቴሽን ኦፍ ድሪምስ (የህልም አተረጓጐም) ነው ። ሰውዬው ነገሮችን የሚያይበት መንገድ ይገርማል ። ችግሩ ... እዚህ አገር እንኳን የሚተረጐም ሕልም ይቅርና ገና የሚተኛበትም ደህና አልጋ አለመኖሩ ሆነ እንጂ" ሲል ፣ ሁለቱም ሣቁ ። ንግግሩን ቀጥሎ ፣ "ሲርየስሊይ ግን እንዲያው እነ ፍሩይድና ዩንግ የፈጠሩት ሳይኮአናልይሲስ ምናምን የሚሉት ነገር እዚህ እኛ አገር ይሠራል ብለህ ታምናለህ? ማለቴ ፣ ቲዎሪው አሪፍ ነው ፣ ግን እንዳንዴ በልቶ ባልጠገበ ጎብረተሰብ ውስጥ እየኖርክ ... አሰ አይደል ... ትንሽ ትብጠት አይመስልብንም?" አለና ባቀላለፋቸው እጆቹ ማጅራቱን ደግፎ ወዶ ኋላ ለጠጥ ብሎ ተቀመጠ ።

"ባንድ በኩል ልክ ነህ ... ግን ደግሞ በመጀመሪያ ሁሉም ያገራችን ሰው እኮ በልቶ የማያድር ወይም ሕልም የለሽ አይደለም ። ደግሞ ደሃስ ሕልም የለውም ያለው ማነው? እንዲያውም 'ደሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ' ሲባል አልሰማህም?" ሲል ፣ ሁለቱም እንደገና ሳቁ ። ሴላሠው ትንሽ አሰበና ንግግሩን ቀጠለ ። "ግን በቁም ነገር ምናልባት እነ ፍሩይድ ወይም ዩንግ ከነበሩበት የዛሬ መቶ ዓመት አካባቢ ከነበረው አውሮጳ ይልቅ ዛሬ እኛ ያለንበት የኑሮ ደረጃ እኮ በብዙ መልኩ ቢሻል እንጂ አያንስም ። ሳይኮአናሊሲስ ደግሞ እነርሱ በራሳቸው መንገድ በጊዜው የነበረውን የጎብረተሰባቸውን ስሜትና ጭንቀት ... አላብና ጥልቅ የእስምሮ ጓዳ ለማየት የፈጠሩትና የምከሩበት መንገድ ነው ። ለምሳሌ ፣ ፍሩይድ ሕልምና የምላስ ወለምታ ወደ ጥልቁና ስውሩ የአእምሮአችን

@OLDBOOOKSPDF

ጳጳ የሚያደርሱ አውራ ጐዳናዎች ናቸው ብሎ ያምን ነበር ። ይህ የእርሱ አይታ ነው ... ብዙ የማይስማሙ ሰዎችም አሉ ።

"በሌላ በኩል ስታየው ደግሞ ምናልባትም የዓለምን አስተሳሰብ በከፍተኛ ደረጃ ከቀረጹ ፍልስፍናዎች መካከል ማለት ትችላለህ የነፍሩይድ ሥራ ሊጠቀስ ይችላል ። እስከ አሁንም ቢሆን ኪነጥበብ ብትል ፍልስፍና ፣ ሳይኮሎጂ ብትል ሥነመለኮት እነርሱ በቀረቡት ሥነልቦናዊ መላ ምቶች ብዙ ተቀርጸዋል ። ከዛ በኋላ የመጡ ብዙ ሥነልቦናዊ መላ ምቶችና የተለያዩ የሰዎችን የስሜትና የነፍስ ሥቃይ ለማከም የተፈጠሩ ዘዴዎች ሁሉ ቢያንስ በከፊል ከዛው የተቀዱ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም ። ግን ደግሞ እንዳልኩህ አንደ ማንኛውም ቲዎሪ የራሱ ግድፈትና ጉድለት ይኖረዋል ። ከዘመን ጋር የሚያረጁ ነገሮችም ያሉት ይመስለኛል" አለ ። የሚታዘዘው ልጅ ሰለ መጣ የሚበሉትን መርጠው ወሬያቸውን ቀጠሉ ።

"እሱማ ልክ ነው ... ይገባኛል ። ግን እዚህ አገር እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ሳስበው ተስፋ ስለሚያስቈርጠኝ ነው ። ማለቴ የበሽተኛው ብዛት ፋታ አይሰጥህም ። ከሲኒክ ከፍቼ ጥቂት ሰው ብቻ እያየሁ አንዴ መጽሐፉ እኖራለሁ ካልክ ደግሞ ምን በልተህ ልትኖር ነው? ማለቴ ማን ይከፍልሃል? ጨከኖስ ነፍሴን መርምርልኝ... የልጅነት ውልግድግዴን አስተካክልኝ ብሎ ከፍሎ ስመታየት የሚመጣ ሰው እኛ ሀገር ይኖራል ብለህ ታምናለህ? የነፍሱን ጉዳይ ለማስመርመር ከሆነ አብዛኛው ሰው የነፍስ አባት አለው" አለ ሲራክ ።

ጠረጴዛ ላይ ያለውን መጽሐፍ እንስቶ እያገላበጠ ወሬውን ቀጠለ ። "እማኑኤልን ብትወስድ ለምሳሌ ... እዛ ቤት ያለው ችግር እንኳን ለሳይኮአናሊሲስ ለመድኃኒትም የሚበገር አይደለም ። ገዘም ብዬ ሳስበው እነዚህን መጽሐፎች እንደ ሥነጽሁፍ እያነበቡና እየተደሰቱ ከሰሞ እስከ ዓርብ ግን ብዙሃኑን ሕዝብ ባለው ነገር ማነሙ ነው የሚሻለው" ብሎ ፣ በረጅሙ ተንፈሰና የሚሰጠውን መልስ ለመስማት ገዘም አለ ። ሲናገር እሹን የሚያወናጭፈው ሲራክ ፣ ሰሜት ውስጥ ገብቶ ሲያወራ ድምፁም ሳያስበው ይግላል ።

"እንዴ እንደ እሱማ ባጭሩ ተስፋ መቊረጥ የለም ወጣቱ ይከተር..." አለና መጽሐፉን ከሲራክ እጅ ተቀብሎ ማውጫውን በፍጥነት እየት እየት አደረገው ። "ፍሩይድና የሱ ዘመን እኩዮቹ የሠሩትን ታላላቅ ሥራ የሠሩት ... ሁሉ ነገር ተመቻችቶላቸው አይመስለኝም ። እንዲያውም በነርሱ ዘመን የመድኃኒትም ሆነ የሥነልቦና ዕውቀት የነበረበት ደረጃ ... ባጠቃላይ ሕክምና የነበረበት ሁኔታ አውን እኛ ካለንበት በጣም ያነስ ነበር ። በርግጥ ከኛ ጎብረተሰብ እንጻር የሆነ ዘመኑ አውሮጳ በብዙ የነቃና የሚያነብ ማኅበረሰብ ነበረ ሊባል ይቻላል ። ምናልባትም ደግሞ እንደ ግለሰብ ስለ ኑሮና ስለ ገንዘብ ጉዳይ እንደኛ ብዙ ጭንቀት አልነበረባቸውም ይሆናል ። ግን እንዱ ፈር ቀዳጅ የሆነ ሰው የሚጠበቅበት ነገር ... በአዲሱ መንገድ ላይ መጣገ ብቻ ሳይሆን ... ራሱ የሚሄድበትን አዲስ መንገድም መንጥሮ ማዘጋጀት ነው ።

"የህገባችን ሥነልቦናና የውስጥ ሰብእና አመቃቀር ገና ያልተጠናና በግልጽ ያልተብራራ ጉዳይ ነው ። በባህል ፣ በእምነት ፣ በአስተዳደጋችንና በኋላ ታሪካችን ላይ

@OLDBOOKSPDF

ተቀብረን ፣ ድብት ሆነን እንኖራለን ። ሁሉም ነገራችን መጥፎ ነው ማለቴ አይደለም ። ግን ብዙ ነገሮች በሰሜትና በአስተሳሰብ መሞቅራችን ላይ የጣሉት አሻራና የፈጠሩት ተጽእኖ ምን እንደሆነ እንኳ ገና በቅጡም አናወቀውም ።

"የሚገርምህ እነ እንኳን ለእኛና ለራሳቸው በዚህ ዘመን ላሉት ላውሮጳው ያኑና ላሜሪካኖቹም እኮ ፍሩይድ ያሉት ነገር ሙሉ ለሙሉ አይሠራም ። በሲላ በዙል ግን ለምሳሌ ስለ ሰው የስብእና አወቃቀር ፣ የውስጥ ግሎቶቻችንን ስለምናቻቸልባቸው የማስታረቂያ ብልሃቶች (ዲፈንስ ሚካኒዝምስ) ... ስለ ንቱውና ስውሩ የአእምሮአችን ጓዳዎች (ኮንሺየስና አንኮንሺየስ ማይንድ) ... እንዲሁም የኋላ ኋለ ታሪካችንና አስተዳደጋችን በዘንድሮ ኑሮአችን ላይ ሊያሳድር ስለሚችለው ተጽዕኖ ... የሰውትን ፅላ ምቶች ፣ ባብዛኛው ዘመንና ድንበር የማይከለላቸው ሁለገብ ሰዋዊ እውነቶች ናቸው ።

"እሁን ባብዛኛው አውሮጳና አሜሪካም ብትሄድ ሳይኮአናሊሲስ ለሌሎች የማማከርና የቲራፒ ዘዴዎች ከማገገሽ በዘለለ በዋናነት እጅግም አይሠራበትም ። ከጊዜ ጋራ አብሮ የሰጪም የሥነልቦና አወቃቀርና የንፍሱ ሕመም ትሁረት ይቀያየራል ። ስለዚህ ያንዱ ዘመን ሥራ ለሌላ ዘመን ... ያንዱንም ባህል አተረጓጎም ለሌላው ባህል ... በቀጥታ እንጠቀምበት ብንል አይሠራም ። እኛ አገርም በየሃይማኖቱና በባህሉ ውስጥ የተተበሩ ብዙ ሥነልቦናዊ ሀብቶች ቢኖሩንም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተጠንተውና ተጽፈው ስላልተቀመጡ ብዙም አልጠቀሙንም" አለና ፣ ለረጅም ጊዜ ሲያሽሞነሙን የቀየውን ጥርሻ ገረሰ ። የጀመረውን ሐሳብ ባይጨርስም ሲራክ የሚለውን ለመስማት ስለፈለገ ሌላ ጥርሻ ማሰናዳት ጀመረ ።

"ይገባኛል እሱ ... ግን እስኪ እየው... ለምሳሌ ፣ እሁን እኛ የአእምሮ ሐኪም ስመሆን የምንሰለጥንበት መንገድ ራሱ ለዚያ ዓይነት አስተሳሰብም ሆነ አኗኗር እያዘጋጀህም ። እኔን ብትመስድ ፣ ለምሳሌ ፣ እሁን የግንደር ዩኒቨርስቲ ነው የሚያሰተምረኝ ። ስለዚህ ልክ ሥልጠናዬን ስጨርስ ወይ ሂጄ እዛ አምስት ዓመት እሠራለሁ ። ለስበለዚያ ደግሞ ብዙ መቶ ሺህ ብር መክፈል አለብኝ ። እሺ ፣ እዛ ሂጄ ምን ማድረግ እችላለሁ?

"ከጠበል የተረፈ ወይም ለጸሎት ያታተ ውስብስብ እብዶት ባሮጊ መድኃኒት ለማዘም ከመሞከር በቀር ። ምን ልበልህ ... በቲ መጻሕፍት የሉም ... አብረኸው እንደዚህ የምታወራው እኮያ አስተሳሰብ ያለው ሰው አይኖርም ። ያው እንዳልኩህ ጥቂት ያረጁ መድኃኒቶችን እየሰጠህና ጊዜ ያለፈባቸውን መጻሕፍት እንደ ጻዊት እየደገምክ የሚያብደውን እያስተባበድክ ከመኖር ውጪ ። ለዚያውም አንተ ተድመግቸው ካላበድክ ማለት ነው ። አንዳንዴ የእአምሮ ሕክምናውን በቃ ለራሴ ዕውቀት ያህል ከተማርኩት ለምን ሌላ ነገር ሠርቼ አልኖርም ብዬ ሁሉ አስባለሁ ..." አለና ፣ ከፊቱ የተቀመጠውን ግማሽ ብርጭቆ አምቦ ውሃ ባንድ ትንፋሽ ጨለጠው ።

"ሲራክ ... ምንም ጥያቄ የለውም ፣ ነገሩ ከባድና አስቸጋሪ ነው ። በምንም መንገድ እነ ቀላል ይሆናል አንልም ። ከባድ ስለሆነም ነው ሁሉም ሰው የማይሠራው ።

@OLDBOOOKSPDF

ግን ደግሞ የማይቻለው ነገር ላይ ከተኩርክ ወይም ጉድለቱ ብቻ ጮልቶ ከታየህ ምንድነው ፋይዳው? ለምሳሌ ግንዶርን ብትመስድ፣ ብዙ ሰዉ በኩሮው ችግረኛ ሊሆን ይችላል። የሰዉ ስብእናና የሥነልቦና መሰብሰቢያው ግን የፈለገ ሠለጠነ ከሚባለዉ ፈረንጅ ቢበልጥ እንጂ እይተናነስም። አዲስ የሥነልቦና ቲዎሪና የአእምሮ ሕክምና ጮጸና መፍጠር ከፈለግህ ... እንደኛ አገር ሕዝብ በሥነልቦናውም ሆነ ባስተሳሰብ ደረጃው የበለጸገና የተወሳሰበ፣ ያልተነካ ጥሬ የአእምሮ ሀብት ያለው ማኅበረሰብ የትም አታገኝም። የተዘጋጅ ነገር ከጠበቅን ግን ምንም ሳንሠራ ልንሞት እንችላለን" አለ ሌላሠው፣ ከባሻገር የሚያውቃቸው ሰዎችን ስላየ እጁን ለሰላምታ እያወዛበሰበ።

"እሺ ቀይ ለምሳሌ አንተ እዚህ ለመኖር ብትችል ወይም ቢኖርብህ ... ምን ታደርጋለህ? ማለቱ አሁን ከምናወራው አንጻር?" አለ ሲራክ፣ በያዘው ናፕኪን እጁን እየጠራረገ።

"ቀላል አይደለም። ህም ... በመጀመሪያ የማደርገው ... ህም ... እኔ በምፈልገው ዓይነት የራሴን ክሊኒክ መክፈቴ የግድ ይመስለኛል። ማዕከሉ በተቻለ መጠን ሌሎች ሳይካትሪስቶችን፣ ሳይኮሎጂስቶችንና የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችን ያካተተ እንዲሆን አደርጋለሁ። የሥራ ትዝመረቴንም በተለይ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውና አሁን እንዲሆን አደርጋለሁ። የሥራ ትዝመረቴንም በተለይ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውና አሁን ሠሰጡ ያሉ ጥያቄዎችን የሚመልሱ ጥናቶችን ማድረግ ላይ ይሆናል። የብዙ ሰዎችን ችግሮች በሚወክሉና የሕዝቡን ሥነልቦናዊ እንቅስቃሴ ለመረዳት ቁልፍ በሆኑ የተመረጡ ኬሶች ላይ ብዙ ጊዜ ለማጥፋት እስበለሁ።

"ከዛ ቡተጨማሪ ደግሞ፣ መጻፍና ምናልባትም ሚድያ ወስጥ ገብቶ የሰፊን ስነልቦናዊ ንቃት መኮርኮርና ማሳደግ ይመስለኛል ዋና የትኩረት አቅጣጫዬ። እኔ እንደማምነው ያበሻ ነፍስና ሥነልቦና ለረጅም ዘመናት ከምናስበው በላይ የቁስለና መከራ የተሸከመ ነው። ያለፈውን አርባና አምሳ ዓመት እንኳን ብታስበው ይዘግንንሃል። ያ ሁሉ ያልታከመ ሕመም ያልተከፈለ የሥነልቦና ዕዳ ነው ማለት ይቻላል። ነገሩ ያንድ ቀን ሥራ አይደለም በርግጥ።

"ሌላ የማደርገው ደግሞ ከጠጣት የሥነልቦና ባለሙያዎችና ተማሪዎች ጋር የቻልኩትን ያህል ጊዜ ማጥፋት ነው። ምክንያቱም አሁን የምናወራውን ነገር እኛ ብንጀምረውም የሚሠሩት እነሱ ናቸው ብዬ ከልቤ ስለማምን ነው። ግን ያው ሸ ብዙ ነገር መልክ ስላልያዘልኝ ነገሩ ከምኞት ያለፈ ላይሆን ይችላል ..." አለና ከባሻገር ከሚሰማው መዚቃ ምት ጋራ ሞንትላሉን እያነቃነቀ ሲራክን አጥልቀ ለማየት ሞከረ።

"ዶክተር ሌላ ... ያልከው ነገር ሁሉ አሪፍ ነበር፣ ችግሩ በጣም ቅልት ኢንነበትመንትና ሰፊ ጊዜ ይጠይቃል። ደግሞስ የት ጋ ጀምረህ የት ትዉርሰዋለህ? አብዛኛው ሰው እነ ተንተሳቃሽ ችግር ነው። ድብቅነታችን በጀ እንጂ እንደ እናንተ አገር ሰዎች ግልጽ ብንሆን ምን ሊፈጠር እንደሚችል አስበው ..." አለና ዝም አለ። ባጠገባቸው የሚያልፈውን አስተናጋጅ ጠርቶ የቱይ ጢፍ እንጀራ እንዲጨምርለቸው ጠየቀና በግራ እጁ ከሽኮ የያዘችን ጉርሻ እንጀራ ያዘቦሸሩን በመቀጠል "እሺ ያስብሙ

@OLDBOOKSPDF

ሁሉ ተሳክቶና እዚህ መኖር ብትችል ... ትኩረት የምትሰጣቸው ዋነኛ ሐበሻዊ የሥነልቦናና የአእምሮ ችግሮች አሉ ወይስ ገና በሱ አትጣጫ አልወሰንክምን?"

ሲራክ በጉጓዩ ላይ ይሄንን ያህል ጠልቀ ሰምጧል ብሎ ያልገመተው ሌላው ውስጡ ደስታም አድናቂትም እየተሰማው ፣ "በርግጥ ብዙ ነገር ጥያቂና የማወቅ ፍላጎት አጭሮብኛል ። ለኔ ግን ጥቂት ነገሮች ሁሌም ዋና ናቸው ። አንደኛ በጦርነትና በግጭት ብዙ እንደኖርን ሕዝቦች ይህ የፈጠረብን የሥነልቦና ጫናና የተቀበረ ሥቃይ ማጥናትና መረዳት ነው ። ለምሳሌ ፣ ባለፈው አርባና አምሳ ዓመት ብቻ የእርስ በርስ ጦርነቱ ... የቀይና ነጭ ሽብር እልቂቱና ያለፍንበት ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ሰቀቃ ... በሕፃናትና በሴቶች ላይ የተጫነው ጥቃትና ሥቃይ የፈጠረው ሥነልቦናዊና ሰብእናዊ ጫናን ማወቅ በራሱ የዕድሜ ልክ ሥራ የሚፈልግ ይመስለኛል ። በተጨማሪም የድኽነትና የአቦት ተጽእኖው የሥጋ ብቻ ሳይሆን የነፍስ መቁሮቴዝና መጨራመት ሳይፈጥርብን የቀረ አይመስለኝም ። ከወሲብና ከጾታ ግንኙነት አንጻር ታፍኖና ተሸፋፍኖ ስላለው አስተሳሰባችንና ስሜታችን ሳስብ ደግሞ ሌላ ያልተነካ ትልቅ ችግር ይታየኛል ።

"በተጨማሪም በማኅበረሰባዊና ጋርዮሻዊ አስተሳሰባችን ውስጥ ተቀብሮና ተረስቶ ስለሚኖረው የእያንዳንዱ ሰው ግለሰባዊ ማንነት ብዙ ሥራ መሥራት ያለብን ይመስለኛል ። እንደ አንድ ሰው የየሰዉ የማንነትና የሰብእና አረዳድ ጉዳይ ። ደግሞም ... መራቱ ውስጥ ካለው ሀብት ይልቅ በየሰዉ ውስጥ ተደብቀው ያሉ መልካም እሴቶች ይበለጣሉ ባይ ነኝ ። ሰዉ ከችግሩ በላይና ከነችግሩ ደስተኛ ሆኖ መኖር የመቻሉ ምስጢር ... በእምነቱና በሃይማኖቱ ያገኘው ሥነልቦናዊ ጥንካሬ ... እንደ ቡና መጣጣት ያሉ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ተሰባጥረው ስላሉ ደጋፊ ልምዶቹ ... ብዙ ነገር አለ ... ተቀፍሮም የሚያልቅ አይመስለኝም ፣ ብዙ ሥራ ነው የሚታየኝ" አለና ትንሽ ተንጠራራ ።

"ዶክተር ሌላ ... እኔ ግን ይኼን ሁሉ ሳስበው ከቅሚ በላይ ይሆንብኛል ። ስጊዚው የሬዝደንሲ ሥልጠናዬን መጨረስ ነው የሚታየኝ ። ሌላው ከዛ በኋላ ይታያል ባይ ነኝ ። ግን በጣም ታንክ ዩ ... ብዙ ነገሮችን ባሳየሁባቸው አትጣጫዎች ነው ያሳየሽኝ" አለ ። ከማኪያቶው ውስጥ የጨመረውን ስኳር እማሰለና ማንኪያውን በሙቢታዊ ምት ከስኒው ጠርዝ ጋ በቀስታ እያጋጨ ፣ "በታ ፣ እናንተም መሄጃችሁ እየደረሰ ነው አይደል? ከዚህ በኋላ ምን ያህል ትቀያላችሁ?"

"እኔ እንኳ ትንሽ ብቀይም ደስ ይለኝ ነበር ። ንጹሕ ግን ፈጽሞ አገሩን አትወደውም ። ይሄንንም ያህል የቀየችው በስንት ልመና ለእኔ ብላ ነው ። ደግሞ የልጅቷም ትምህርት ቤት ስለሚከፈት ከሦስት ሳምንት በኋላ የግድ መሄድ አለባቸው ። እሷ ከፈቀደችልኝ እኔ እንድ ወር ምናምን ብጨምር ደስ ይለኛል ። እዛ ያለው የሥራ ውኒታ ከፈቀደልኝ ማለት ነው" አለ ፣ ሐሳቡ ብትንትን ያለበት በሚመስል ድምፅ ።

"ኦህ ... ከቤተሰብ ጋር ተላል አይደለም ። አንተ እንዲያውም በጣም ጎበዝ ነህ ። ሳስበው እኔ ውጭ የምኖር ብሆን እዚህ ሀገር መጥቼ እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ

@OLDBOOOKSPDF

የምጸከርም አይመስለኝም ። አላውቅም ... ግን አይመስለኝም ። በነገራችን ላይ የምር ንጹሕ እሺ ብትልህ እዚህ መኖር ታስባለህ?" አለ ፣ ፊቱን ጭምድድ አድርጎ ።

"እድርገልኝ ነው ። ለኔ እዚህ መኖር ልገልጸው የማልችለው የሚሰጠኝ ደስታና ርካታ አለ ። ምናልባትም አባቴ ከልጅነቱ ጀምሮ የፈጠረብኝ ተጽእኖ ሊሆን ይችላል ። እዚህ ብኖር ምን ዓይነት የሕክምና ማዕከል ልከፍት እንደምችል ሁሉ ይታየኛል ። የረጅም ጊዜ ሕልሜም ስለሆነ ሊሆን ይችላል ። ደግሞ ግን እንዳልከው ይሄ ሁሉ ከቤተሰቤ በላይ ሊሆን አይችልም" አለ ። ወደ ኋላ ደገፍ ብሎ ከሩቅ የሚመጣውን ሙዚቃ እያዳመጠ ጣራ ጣራውን እያየ ፣ እንዴ ወደኋላ ደግሞ ወደፊት ርቀ እየሄደ በጊዜ ዥዋዥዌ ላይ ተመላለሰ ። ሲራክም ከራሱ ሐሳብ ጋር እየታገለ ደጅ ደጁን እያየ በራሱ መንገድ ነጐደ ።

"አንተ ግን እንዴት ነው ስለ ማግባት ምንም እቅድ ምናምን የለህም እንዴ?" አለ ፣ ከገባበት የራሱ ሐሳብ ሲወጣ የሚያወሩበትን ርእስ በመቀየር ።

"ም...ን ...ባክህ ... ብታስብ ምን ፋይዳ አለው ። ሴቱ ሁሉ እኮ የማይጨበጥ ጉም ሆነብን ። ትንሽ ደህና ናቸው ያልካቸው ፣ ጥቂት አብረሃቸው እንደ ቀየህ የሚፈልጉትንም የሚያውቁ እይመስሉም ። አለ አይደል ... በቃ ልክ እንደገዙህ ዕቃ እንደገና ጠፍጥፈው ሊሠሩህ ይፈልጋሉ ። እኔ እንኳ ... ግራ ይገባኛል ...አለ አይደል ... ደግሞ ገና ሠላሳም አልደፈንኩም እኮ... ለምኑ ነው ጭንቀቱ..." ብሎ ፣ እጁን እርስ በርሳቸው አሻሸ ።

የሚጠራ ስልኩን እየት አድርጎ ኪሱ ውስጥ መልሶ ከተተውና ንግግሩን በመቀጠል ፣ "ሳስበው ሳስበው ግን እግብቶ መታሰርና የማልወጣበት ወጥመድ ውስጥ መግባት አልፈልግም መሰለኝ ። እግብተው የተደሰቱ ብዙም ሰዎች አላውቅም ... ከራሴ ወንድም ጀምሮ ... ስለዚህ ማግባቱ ያንንም ያህል አያጓጓኝም ። ብረር ... ከነፍ ... ሞክር ... ያገ ... ልቀቅ ... ነው የሚለኝ ታስሮ የተለቀቀው ልቤ" አለ ፣ ከመቀመጫው እየተቁነጠነጠ ።

ሌላው ሜንትላቱን እየወዘወዘ በእንከሮ ሲያጻምጠው ቀየና ፣ "ያው እንደ ሁሉም ጥሩ ነገሮች ማግባትም የራሱ ችግሮች ሊኖሩት ይችላል ። ሁላችንም የምናልፍበት ግራ መጋባትና መፍራት አለ ። ግን ዋናው ማወቅ ያለብህ ... ሁሉንም ሴቶች ሳይሆን እንተ የምታገባው እንዲት ሴት ብቻ ነው ። ያገሩን ሴቶች ሁሉ ችግር የራስህ ማድረጉ ፍራቻህን ያበዛል እንጂ ብዙም ጥቅም የለውም ። አንተ እንዳልከቸው ዓይነት ብዙ ሴቶች ሊኖሩ ይችላሉ ... እንዳልኩህ ግን ሁሉም ያንተ ሚስቶች አይደሉም ። ወጥመድ ሳልከው ... ዩ ኖው ... እኔም እንዳንተ ነበር የማስበው ። መጨፈር ... መደሰት ... ደስ ካሰችኝ ልጅ ጋር ሁሉ መዝነጥ ...መብረር ነበር ሕይወት የሚመስለኝ ።

"ንጹሕ ባላሰብኩበት ጊዜ ወደ ሕይወቱ ስትመጣ ግን ... በሷ መታሰርን ነጻነት ሆኖ አገኘሁት ። የእኔ የተሻለ ማንነት በርሷ ሰብዕና ውስጥ አብቦ ታየኝ ። የመስጠትን ትርጉምና ለሌላ ሰው በመኖር ውስጥ ያለውን ደስታ ከእሷ ተማርኩ ። በመዘንና

@OLDBOOOKSPDF

በመቀበል ካለው ደስታ ይልቅ በመስከንና በመስጠት የሚገኘው እርካታ በጣም እንደሚበልጥ ያወቅሁት ከሷ ጋር ስሆን ነው። ለኔም ያኔ እሷን ሳላገኝ ይህንን ሁሉ ብትነገረኝ ስቁብህ ነበር የምሄደው። ያው ይገባሃል፣ ማግባት ምንም ችግር የለውም እያልኩህ እንዳልሆነ። ግን ደግሞ ደስታው ይበልጣል ለማለት ነው። በዛ ላይ ልጅ ሲመጣ ደግሞ ለራስህ ከመኖር ባርነት ነጻ ያወጡሃል ... አለ አይደል ... ቀምሰህ ከላየኸው ምንም ቃል አይገልጸውም።"

"ዶክተር ሌላ ... ምናልባት እንተ ዕድለኛ ሆነህ ነው፤ ጎጹህን የመሰለች ሴት ያገኘኸው። እስኪ እኛም የሚጥልልን እንጠብቃለና እንግዲህ" አለ። ዝም ብሎ የያዛትን ስንጥር እንጨት እየሰባበረና እየሰነጣጠቀ የማኪያቶው ስኒ ውስጥ እየወረወረ ሊጫወት ጥቂት ቀየና፣ "እኔ የምልህ የሚስጥር እናት እንዴት ናቸው?" ብሎ የጨዋታቸውን አቅጣጫ ቀየረው።

በሆቸው ሰዓት ሌላሠውም ስለ ምስጢር ሲያስብ ስለ ነበር ድንገጥና ግርም ብሎት፣ "ደህና ናቸው ... አይ ቲንክ ... ብዙ ለውጥ አላቸው። ያው ነገሩ ጊዜ መውሰዱ አይቀርም" አለ በደፈናው ሲራክ ስለ ችግራቸው ምን ያህል እንደሚያውቅና ከምስጢርም ጋር ያላቸውን ቀረቤታና ጓደኝነት ዮቱን ያህል እንደሆነ እርግጠኛ ስላልሆነ።

"እሷ ደግሞ ትገርመኛለች፣ የሆነች በጣም ውስብስብ ያለች ልጅ ትመስላለች" አለ ሲራክ፣ ፊቱን በግዴለሽነት እንዳጨማደደው በማስመሰል።

"ለምን እንደዛ አልክ? ያን ያህል ታውቃታለህ?" አለ፣ ሌላሠው ከወገቡ ስበር በማለት ወደ ሲራክ ቀረብ ብሎ። ለሁለት ወር አቁማ የነበረውን የተግባር ልምምድ ከአንድ ሳምንት ወዲህ ከሌላሠው ሥር በመሆን እንደገና መጀመሯን ሲራክም ያውቃል። ከጥቂት ቀን በፊት በወሬ በወሬ ተነሥቶ እሷም ስለ ሲራክ ያለችው ትዝ አለው።

"እም ... ብዙም አላውቃትም፣ ግን የተግባር ልምምድ ለማድረግ ከጥቂት ወራት በፊት ጻውሎስ ትመጣ ነበር። አንድ ሦስት ሳምንት ከኔ ሥር ነበር የምትሠራው። በርግጥ በጣም ጐበዝ ልጅ ናት ... ግን በቃ እንዳንዴ ሕመምተኛዬ ብትሆን ብዬ አስብና ምን ያህል ከባድ የእጅ ሥራ እንደምትሆን ይታየኛል። ብዙ ያልተፈቱና የተቀበሩ ሥነልቦናዊ ጉዞች ያላት ይመስለኛል። ብቻ ዝም ብዬ ሳያት ከወንዶችም ጋር ብዙ ችግር ያለባት ትመስላለች። ያ የኔ አስተያየት ሊሆን ይችላል" አለ። ሳያስበው ያወራው ነገር በሌላሠው የምርመራ ወንበር ላይ ያስቀመጠው መስሎ ተሰማው። ጣራ ጣራውን እያየ የኮርኒሱን አራት ማእዘኖች መቁጠሩ ላይ አተኮረ።

"እንግዲህ እኔ ለጊዜው ያን ያህል ብዙም ያወቅኳት አይመስለኝም። ከናቷ ጋር ግን ጥሩ ግንኙነት ያላቸው ይመስላሉ" ብሎ፣ በማጨን ዓይን ትኮር ብሎ ሲያየው ነገሩ ይበልጥ ያልተመቸው ሲራክ፣ "እስኪ መታጠቢያ ቤት ደርሼ ልምጣ" ብሎ፣ ድንገት ብድግ አለ።

@OLDBOOOKSPDF

ሌላው ደግሞ ለምን ስለ ጋብቻ ካወሩት ወሬ ጋር አያይዞ ሲራክ ያን ሁሉ ስለ ምስጢር እንዳለ ማሰላለል ጀመረ። በተለይ 'በሽተኛዬ ብትሆን' የሚለው ሐሳብ ያዘለው ትርጉም ምን ሊሆን እንደሚችል የተለያዩ አማራጮችን ለመገመት ሞከረ። ሒሳቡን ከፍሎና ለመውጣት ተዘጋጅቶ ስለነበር ሲራክ ከመታጠቢያ ቤት እንደተመለሰ ወዲያው ተከታትሎ ወጡ።

@OLDBOOOKSPDF

፡10፡

ሴላሠው፡ ከምሳ ተመልሶ አማኑኤል ሆስፒታል ሲደርስ ስምንት ከሩብ አልፎ ነበር። ከመኪናው ወጥቶ ወደ ሴቶች መኝታ ክፍል እየተጣደፈ ሄደ። ከነርሶች ጣቢያ ሲደርስ የዝናሽ አባት ገና እንዳልደረሱ ኃላፊ ነርሲ ነገረችው። ከእርሲ ጋር ሴቶች ሕመምተኞች በሚተኙበት ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያሉና እንዳንድ ሕመምተኞችን እያወሩ ጥቂት ቀዩ። ከፍሉ እንደ ጠዋቱ ብዙም ግርግር አይታይበትም። አብዛኞቹ ሕመምተኞች በያልጋቸው ላይ ተኝተዋል፣ ሌሎቹ ደግሞ ሰብሰብ ብለው፡ ያወ፡ካካሉ።

ስምንት ተኩል ሲሆን አለመድረሳቸው፡ ትንሽ ስላሳሰበው፣ "ሲስተርዬ ምናልባት ቀጠሮውን ረስተውት እንዳይሆን ..." አለ፣ ምንም እንኳን ግማሽ ሰዓት ማርፈድን ሁሉም የለመደውና የተቀበለው፣ ሲራክ እንደሚለው 'ያገሩ ደምብና ያበሻ መብት' መሆኑን እየጠላ የተቀበለው፡ የቀጠሮ እውነታ ቢሆንም።

"ምን እኮ ... ሰዒም ሰዓት እያከብር። ደግሞ ማን ያው፡ቃል በዚህ በዐሐይ ይሄኔ ከዛ ድረስ በእግራቸው፡ ይሆናል የሚመጡት። እስኪ ለማንኛውም በር ላይ ዘበኞቹ አሳስገባ ብለዋቸው፡ እንዳይሆን። እዚህ ቤት ስንት ሞከና አለ መሰለህ። ቆይ እስኪ እኔ ራሴ ልሂድና ስለ ማው፡ቃቸው በር ላይ ቼክ ላድርግ ..." ብላ፣ ፊቷ የበታተነችውን ወረቀት ሰብሰብ አድርጋ ጣደፍ ጣደፍ እያለች ወጣች። እሱ ደግሞ ወደ ቢሮ ገብቶ ቀን ያልመለሳቸውን ስልኮች መደዋወል ጀመረ።

ብዙም ሳይቆይ ኃላፊ ነርሲ እንኳኳታ ገባችና "እይገርምህም ዶክተርዬ፣ ልክ እንዳልኩት ሰውዬው በጊዜ ደርሰው ነበር። በር ላይ ጥበቃዎቹ አሳስገባ ብለዋቸው፡ነው። እንዲያው፡ አሁንስ ይሄ አገር ምን ይሻለን ይሆን? ው፡ይ እኔ አይገባኝም፣ ደሃ ለምን በደሃ እንደሚጨክን።"

"የሕመምተኛ መጠየቂያ ሰአት ስላልሆነ ነው፡ የከለከሉዋቸው፡?" አለ፣ ነገሩን መ፡ሉ ለመ፡ሉ ስላልተረዳ።

@OLDBOOOKSPDF

"የምን የበሽተኛ መጠየቂያ ሰዓት ዶክተር? ሰውዬው ዶክተሮቹ ቁጥሬን እ
ልጄ ጉዳይ ሊያናግሩኝ ነው ቢሏቸውም ከቱቦም አልቱጠሯቸውም። ያው የኒ ቢጫ
የሥጋ ደዌ ሕመምተኛ በለሆኑ ነዋ። ድንነት ወንጀል የሆነበት ሀገር ... እንዲያውቁ
ባከሀ። ለማንኛውም እዛኛው ቢሮ አስገብቻቸው እየጠበቁህ ነው። ገናሽን አባረ
ነው የምታያት ወይስ ለብቻቸው ልታናግራቸው ነው ያሰብከው?" አለች፣ ነገሩ ግርም
እንዳደረጋት በሚያሳውቅ ፊትና ድምፅ። የዐሐይዋ ግለት ጭንቅላት ይበጠብጣል።

"እይ መጀመሪያ እስኪ እሳቸውን ለብቻ እናናግራቸው። ከዚያ በኋላ እሷንም
እንጠራታለን" አለና ተከታትለው ወደ ቢሮው ሄዱ።

በከፊል የተዘጋውን በር ከፍተው ሲገቡ የገናሽ አባት በትራቸውን ደገፍ ብለው፣
ቁጭም እንዳሉ ከእንዱ ወንበር ጫፍ ላይ ተቀምጠዋል። እነርሱ ሲገቡ ደንገጥ ብለው
የግዳቸውን ከመቅመጫው ብድግ እንደማለት አሉና፣ "ኖር ...ኖር" አሉ ድክም ባለ
ድምፅ።

"ኧረ አይገባም አባት ... እንደምን አሉ?" ብሎ፣ ለመጨበጥ እጁን ሲዘረጋላቸው
እንደ መሳቀቅ ብለው እጃቸውን ከፍ አደረጉ። ከሁለት ጣቶቻቸው በቀር በሥጋ ደዌ
ሕመሙ የተነሣ ሌሎቹ ጣቶቻቸው ከግማሽ በላይ የሉም።

ከጨበጣቸው በኋላ ተቀመጠና፣ "በጣም ይቅርታ አቶ በድሉ ... በር ላይ
ጥበቃዎቹ እላስገባ ብለው እንዳንገላቱዎ ሲስተር ነገረችኝ። ደግሞ በዚህ በዐፊዲ
እዚህ ድረስ ስለመጡ በጣም ነው የማመሰግንው" አለ፣ ቀስ እያለ ከላይ እስከታች
እያጤናቸው።

"አዬ ምናለ ... እነሱም ሥራቸው እይደል። ወረኧት ካላመጣህ ብለው ነው
እላስገባ ያሉኝ። እኔ ደግሞ ምንም ወረኧት የለኝ ብላቸው ሊያምኑኝም አልቻሉም፣
ስጪ እኮ ዘንድሮ ተጨካክኗል" አሉ፣ ስማቸውን እንዴት እንዳወቀ ገርሟቸው፣ ምን
እንደሚሉ ጭንቅ ብሏቸው መሬት መሬት እያዩ ብትራቸውን እንደተደገፉ ጸኖ አሉ፣

ዕድሜያቸው ከሰልሳ ብዙ ባይዘልም ችግሩ ተደራርቦ ግርጅፍፍፍ ብለየል፣
በሕመሙ የተነሣ ነርቮቻቸው ከጥቅም ውጪ ስለሆኑ፣ በጊዜ ብዛት በደረሰባቸው
ትንንሽ ቁስለቶችና እደጋዎች አብዛኞቹ የእጅና የእግር ጣቶቻቸው ተቀራርሙ
አልቀዋል። ያደረጉት ጫማ እግራቸውን ከተጪማሪ ጉዳት እንዲጠብቅና የማይሙ
ጡንቻዎቻቸውን እንዲደግፍ ተብሎ በተለይ የተሠራ ነው። የጫማው ለየት ያለ
ቅርጽ ደግሞ ሕመሙ በሰውነታቸው ላይ የፈጠረውን ጉዳት እጉልቶት ይበልጥ ከሃ፣
አስመስሏቸዋል።

እድገ ያልተቈረጠው ሽበቶ ሪዛቸው ... ዐሐይና ጭር የተፈራረቀበት ፊታቸው
ላይ የተጋደመት ብዙ መስመሮች፣ የለምን ድካማቸውን ብቻ ላይሆን የሳመታት
መከራቸውን ያስነብባሉ። በሴላ በኩል ደግሞ ስልከከ ያለ ፊታቸው፣ ዘለግ ያለ
ቁመታቸውና ሰፋ ያለ ትከሻቸው ተጸምረው ጽናትንና ትእግሥትን የተላበሰ ፐሰናሊቲ
ያልሰበረውን የውስጥ ማንነታቸውን ጥንካሬ ያሣያሉ።

@OLDBOOOKSPDF

"እኔ ዶክተር ሌላሠው እባላለሁ። የገናኘሽ ሐኪም ነኝ። ሲስተርን ያው አግኝተዋታል ብዬ ነው። የርስዎ ስም እቶ በድሉ ነው አይደል?" ሲል ከመቀመጫቸው ብድግ እንደማለት ብለው "ልክ ነው ዶክተር ... ልክ ነው፣ በድሉ ሜኔ ነው ስሚ" አሉና ወደ ኃላፊ ነርሲ ሁለት እጆቻቸውን ዘርግተው፣ "አይ እሳቸውማ እመብርሃን የባረከቻቸው ብሩክ መላክተኛ ናቸው። እሳቸው ባይመጡልኝ ኖሮማ እዛ ጠሐዩ ቲከካኝ መዋሌም አልነበር" አሉ። ሰውነታቸው ትንሽ ዘና ሲል፣ ተስተካክለው ተቀመጡ። በትራቸውን በእግራቸው መሃል ሸጉጠው፣ በሁለት እጆቸው ደገፍ አሉና ጉንጫቸውን አሳረፉበት።

"እንግዲህ እርስዎን ለማግኘት የፈለግነው አንጻንድ ነገርችን ስለ ገናኘ ለማወቅና ከዚህም በኋላ ስላለው ሕክምናዋ ለማቀድ ነው። እዚህ ከመምጣቷ በፊት እርስዎ ለመጪረሻ ጊዜ ያዩዋት መቼ ነበር?"

"ቀየ ልጄ ... ዓመት ተሁለት ወሯ አልሆነም ብለው ነው ድንገት ብን ብላ ተጠፋች። ፈልገን አስፈልገን ትናጣት በቃ እርማችንን ለማውጣት ምንም አልቀረን ነበር። መቼም እሷ ወላዲት አምላክ አያልቅባት ... ቸሯ እናቴ..." አሉ።

"ሰሞኑን መጥተው አይተዋት ነበር እንዴ?" አላቸው፣ ወደ ሌሎቹ ጥያቄዎች ከመግባቱ በፊት።

"መች ነበር ልጄ ... በእደም ለታ ... ሦስት አራት ቀን ቢሆነው ነው መሰል። ይመስገነው ታምሩ እያልት አሉ፣ ብዙ ለውጥ አላት። የገባች ሰሞን ተነበረችው፣ ተመጀመሪያው ረገብ ሰከን ብላ ነበር። ሰለ ልጆቿም ሁሉ ጠየቀችኝ። እሷ እኮ መድኃኒቷን ትትወስድና ይሄን ሜት ማመንዠሀና መጠጡን ትትተው እንዴት ዓይነት ልጅ መሰልችም። ግን በቃ ኻል ቲላት የሆነ እሚጠራት ጋኔን አለ መሰል ብን አድርጎ ያጠፋታል" አሉ፣ እንዴ ሌላሠውን፣ እንዴ ነርሲን እያዩ።

"ልጆቿ ከእርስዎ ጋር ነው የሚኖሩት? ስንት ልጆች አሏት?" አለ፣ ስለ ልጆቿ መጠየቁ የመኻል ምልክት መሆኑን በማሰብ።

"ሁለት ናቸው። እንዱ መጀመሪያ የዛሬ ስምንት ዓመት እመመ ቲጀምራት ተአረብ አገር ትሪት ሁናው የመጣችው ነው። እሱ ያረብ ዘልስ ቁርጥ አረቦቹን ነው እሚመስል። ሁለተኛዋ ደግሞ አራት ዓመት ሊሆናት ነው መሰል እንዲሁ ብን ብላ ጠፍታ ከርማ ተመንገድ እርግዝ መጥታ ነው የወለደቻት። ልጆቹም እበላቸው በዛ እኮ ... ያለ እናት ያላባት። እናቷ ታትሞት በፊት እሷ ነበረች ስንቱን ጉድ የተሸከመች። ይኸው ገናኘም ጉዳና ወጥታ የተረች እሷ ተምተች ወዲያ ነው። እናቲቱ ነበረች የቤተሰቡ ማገር ምሰሶ።

"አሁንማ ማንም ሃይ ባይ ቢጠፋ ጊዜ ቤቱም ሊበተን አፋፍ ላይ ነው ያለ። እኔም ይኸው በልመና ቀኑን ሁሉ ትዋትር ይመሻል። ልጆቹንም አንድ የሚሲዮን ርዳታ ድርጅት እየረዳልኝ ነው ተማሪ ቤትም መሄድ የቻሉት። "እንደ እሳት የሚፋጅ ብሶታቸውን በረጅመ እየተነፈሱ ዘከዘኩት። ሳያስቡት፣ ትኩስ እንባቸው በጉንጫቸው ላይ ከብልል ሲል ድምፃቸው[illegible]።

ሌላሠው የሚለው አጥቶ በሐዘን ሲያያቸው ከጐናቸው የተቀመጠችዉ ኃላፊ ነርስ፣ "አይዝሎ አባባ ... መቻል ነው እንግዲህ ምን ይደረጋል፣ እሰኪ እሮኦ የቻልነውን እናደርጋለን። ሌሎች ልጆች የሉዎትም?" አለች።

ያነቃቸውን ሳግ ለመሞጥ ትንሽ ዝም ብለው ቀዩ። "የዝናሽ ታናሽ አለች፣ እሷም ሦስት እምቦቀቅላዎች አሏት። አረቂና ጠላ ቸርችራ ነው እምትተዳደር፣ ባሏም እማይረባ ሰካራም ቢጤ ነበር። እሷን ጥሎ ታንዲት ኮማሪት ቤት ጠቅልሎ ገብቷል አሉ። ሌላ አንድ ወንድ ልጅም ነበረኝ። አሱም ያኔ በጦርነቱ ገዢ መታደርኩ ገብቶ ይመትም ይኑርም አይታወቅ። መቼም በሕይወት ቢኖር እስታሁን አይጨክንም ብዬ እርሜን አውጥቻለሁ። እናቱንም የገደላት እንድም የሱ ሐዘን ነው። እገሊህ እንዳለቀሰች፣ ደጅ ደጁን እንዳየች ወደ መቃብሯ ወረደች" ብለው፣ በሻኪታቸዉ ጫፍ እንባቸውን ጠራረጉ።

"እርስዎ እዚህ እዲሳባ ምን ያህል ኖሩ?" አለ፣ ሌላሠው የተፈጠረውን ጠንካራ ስሜት ለማርገብ በማሰብ የጥያቄውን መሰመር እያዘረና ግለቱን እየቀነሰ።

"ኧይ ዲየሁ... አሁንማ እርባ ዓመት ሲሆነኝ ነው። ተገፍም ነበር የመጣሁ፣ መጀመሪያ ይሄን ቁምጥና እታከማለሁ ብዬ ነበር የመጣሁ። ኋላ ተከምናው በኋላ አገሬ ልመለስ ነበር። ወዲያው ለውጡ ቲመጣ አገር ሁሉ ተመሳቀለ። ብዙም ታይቶ በሽታውም እንደገና አገረሸብኝና እዚሁ ትታከም ቀየሁ። ያኔ ሰውም እንዲህ አልበዛ መንደሩም ሁሉ ጫካ ነበር። እዚያው ዘነበመርቅ አካባቢ ተሰው ተጠግቼ ያገኘሁትን እየሠራሁ መኖር ጀመርሁ። ተሦስት ዓመት በኋላ እንደኔው ልትታከም መጥታ ቢጋጣ ተዋወቅንና ተልጆቹ እናት ጋር እህል ውሃ አጣመረን። ይሽው መከራህ አይለቅ ብሉኝ እስታሁን እዚሁ እንከላወሳለሁ ... ለጉድ የፈጠረኝ ..." አሉ፣ ከሕመሙ ተርፎ የቀረ እጃቸውን አንዴ ወደ አነርሱ አንዴ ወደ እግዚሩ በአቤቱታ አይነት ከፍ ዝቅ እያደረጉ፣

"ዝናሽ የመጀመሪያ ልጅዎ ናት?" አለች ነርሲ፣ እርሲም ስሜት ካዘሉ ጥያቄዎች ለመሸሽ ይመስል።

"አይ ወንዱ ነበር የመጀመሪያስ ... እሷ ተከታይ ናት።"

"እንዲያው ዝናሽ ወደ አረብ አገር ከመሄዱ በፊት ምንም እንዲህ ያለ ነገር አሟትም አያውቅ? ሌላስ በዘመድ አዝማድ በቤተሰብ እንደሷ ያለ የአእምሮ ሕመም የሚያመው ሰው አለ?" ዓይኑን ከሳቸው ላይ ሳይነቅል የጥያቄውን መልስ መጠበቅ ጀመረ።

"ኧረ ምንም ... እኔ አስተማውቅ እብደት በኔም በናቷም ወገን እንዳለ አልሰማሁም። እንግዲህ አገር ቤት ያለውን ማን ያውኣል። ልጅቱ እንዴት ያለች ጐበዝ ተማሪ ነበረች መሰለህ። ሁሌ አንደኛ ነበር እምትወጣ። ደግሞ ሁሌ ጉዞ፣ ዓይነገሉ ቀንጆ ተጫዋች ነበረች። ወደ ዓሥራአንድ ክፍል ትትደርስ ግን በታ ጐረምሳው ሁሉ አሳስወጣ አሳስገባ አሳት። በኋላ ታቅማ በላይ ቲሆን መሰለኝ ተማይሆኑ ልጆች ጋር ገጠመች። ትምርቷንም ችላ ብላ ተሰፈር ኮልኮሌ ጋር ሆነ ውሎሞ። ኋላ ያ ምንደነው

@OLDBOOOKSPDF

እሱ ቱ ... ማትሪካ ነው? ያስራሁለተኛ ክፍሉ ፈተና ... እሱን በትወድቅ ጊዜማ በታ ... ተያ በኋላ ለይቶላት እንዳይን ጠፋች ።

"ኋላ ፈጣሪ የኛንም ልመና የሰማን መሰለን ። በዚህም በዛም ብላ አረብ አገር ሄደችና እኛም ትንሽ እርይ አልን ። ምን ያደርጋል ገና ትንፋሻችንን ሳንይዝ፣ ያልታደለች ... ዓመትም ታይሞላት አትሏን በታ ያን የመጀመሪያ ልጇን ቅሪት ሁና መጣች ። ተያ ወዲህ ይሄው ሰውም ሆና ሰው አልሆነች" አሉ፣ ወደ ታች የተገለበጠ አሮጌ ጋቢያቸውን አጥፈው ከትከሻቸው ላይ እየደረቡ ። ሌሎች ጥያቄዎችን ከጠየቁዋቸው በኋላ ገና ንሽ ተጠርታ ከአባቷ አጠገብ ተቀመጠች ።

ወደርሷ ዞር ብለው፣ ቀስ ባለ ድምፅ፣ "እንዴት ዋልሽ የኔ አበባ?" አሉና እጇን ሳብ አድርገው ሲስሟት፣

"ደህና ነኝ አባዬ" ብላ፣ እንዳቀረቀረች በጨረፍታ አየቻቸው ።

"አቡሻና ሚጢ ናቸው የላኩልሽ ..." ብለው፣ ከኪሳቸው አንድ ወረቀት አውጥተው እንደተጣጠፈ ሰጧት ። ፈጠን ብላ ተቀበለችና ከፍታ ለረጅም ጊዜ ፍዝዝ ብላ ሰታይ ቀየችና፣ ድንገት እንባዋ ወረቀቱ ላይ ጠብ ጠብ አለ ። በዝምታ ሲያዩዋት የነበሩት ሌላሠውና ኃላፊ ነርሲም ሳያስቡት አይኖቻቸው ረጠቡ ።

"ምነው አበባዬ ... ምነው?" አሉ፣ አባቷ በተለያየ ቀለም የተሳሉ አበባዎችና ቀይ የልብ ቅርጽ የተሳለበት ወረቀት አይተው በትልልቅ ጽሑፍ የተጻፈውን የልጆቿን ደብዳቤ ማንበብ ስላልቻሉ ።

እንጆት በሚበላ በተሰባበረ ድምፅ፣ "ልጆቼ ... ልጆቼ ..." አለችና አሁንም ዝም እንዳለች እንባዋ መፍሰሱ ቀጠለ ።

ሌላሠው ዓይኑን ጨመቅ አድርጎ ፊቱን ጠረግ ጠረግ አድርጎ፣ "ማየት ይቻላል?" አለ፣ ንሽ ወስጥ እያለፈ ያለውን ከባድ ስሜት ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ገብቶት ። ዝም ብላ እጇን ዘርግታ ወረቀቱን ሰጠችውና አገጯን በሁለት እጇ እንደ ደገፈች አቀርቅራ ትክዝ ብላ ቀረች ።

"እማሚዬ በጣም እንወድሻለን ። ሁልጊዜ እግዛቤል እማዬን ጠብታት እያልን እንጸልያለን ። መቼ ትመጫለሽ ። ሚጡ ላመትባል የተሰጣትን ቸኮሌት ላንቺ አስቀምጣልሻለች ። እኔም ቀንጆ ስጦታ አስቀምጨልሻለሁ ። ልንመጣ ነበረ ። ልጆች አያስገቡም አለን አባባ ። እማሚዬ ሚጡና እኔ በጣም ናፍቀሽናል እሺ ። ቶሎ ቶሎ ነይ ።"

ይላል፣ ትልቁ ልጇ የጻፈላት ደብዳቤ ። በልብ ቅርጽ ባሸበረቀው ወረቀት ላይ የማይነበብ ሙንሜርሜር ጽሑፍም አለ ። እሱ ደግሞ የትንሿ ደብዳቤ መሆኑ ነው ። ውስጡ የተሰማውን ስሜት እንደ ምንም ታግሎ ወረቀቱን ለኃላፊ ነርሲ ሰጠና ዝም አለ ። ኃላፊ ነርሲ ካነበበችው በኋላ ስላላስቻላት ወረቀቱን ከሌላሠው ፊት አስቀምጣ ከፍሉን ለታ ወጣች ።

@OLDBOOOKSPDF

ውይይታቸውን ሲጨርሱ፣ ገናሽን አበረታቱና የሚቻለውን እድርገው ተሌ ወደ ቤት እንደሚልኳት ነግሯት ከለባቷ ጋር እንዲያወሩ ጊዜ ሰጧቸው። ወርሰቄ ሲለያዩ ሌላው እግሬ መንገዱን ይዟቸው ሊሄድ እንደሚችል ሲነግራቸው እምቢ አሻፈረኝ አሉ። ከብዙ መግደርደር በኋላ እሺ ብለው ይዟቸው ከግቢ ወጡ። የመኪናው ንጽህናና ፍጥነት ... የዶክተር ሌላው ደግነትና የልጃቸው ጤና እየተመለሰ መሆን፣ ተደማምረው የተፈጠረባቸው የተደበላለቀ ስሜት በሌላ ዓለም ውስጥ እየተንሳፈፉ፣ በሕልማቸው ወዳልታወቀ ስፍራ የሚወሰዱ መሰሎ ተሰማቸው። እሱም በራሱ ሐሳብ ውስጥ ገብቶ ሲዋልል የሰልኩ ጩኸት አነቃው።

"ሃሎ ... ሳንች እንዴት ነህ?" አለ፣ የመኪናውን ፍጥነት እየቀነሰ።

"ደህና ነኝ ዶክተር ... ማውራት የምትችልበት ሁኔታ ላይ ነህ እንዴ ያለኸው?"

"አረ እንዲያው በፈጠረህ ... ይሄንን ዶክተር የምትለውን ነገር ተው። እውነ እየነዳሁ ስለሆነ እጭር ነገር ከሆነ ሰፒከር ላይ አድርጌህ ማውራት እንችላለን።" ሂያ ዶክተር እይባልም ቢለውም፣ አሻፈረኝ ብሎ አሁንም ዶክተር ብሎ ነው የሚጠራው፣ በሶሻል ዎርክ የጀመረውን ትምህርት እየጨረሰ ስለሆነ ለተግባራዊ ልምምድ ቦታ እየፈለገ ነው ያለው።

"እስኪ መጀ ፊት ቀስ እያልን እንለምዳለን። ለአሁን ግን ዶክተሩ ይሻለሃል ብሎ ሣቀ አለና "በቃ አሁን ጊዜህን አልውሰድብህ። እንዴ የፐራክቲከሙን ነገር እንዴት አደረክልኝ ልልህ ነበር። ሌላው ግን ቅዳሜ ሳንድ ጉዳይ ወደ ሐዋሳ ስለምሄድ፣ ምናልባት ጠዋት ካልኖርኩ ብዬ ልነግርህ ነበር።"

"እንግዲህ ምን ይደረጋል ብቻዬን እሮጣለኋ ..." አለና፣ "አይ ስቀልደህ ነው ... ጓደኞቼ እንጦጦን ካልወጣን እያሉኝ ስለ ነበር እሱን ማድረግ እችላለሁ ... ስለሆነ እትጨነቅ። የተግባር ልምምዱን በተመለከተ ግን ጳውሎስ ተፈቅዷል። ሐሙስእና እኖራለሁ። የክሊኒኩ ኃላፊ ነርስ ሲስተር ዘቢባ ትባላለች ... ከሷ ጋር ተነጋገረናል፣ ጠዋት ሁለት ሰዓት ተኩል የአእምሮ ሕክምና ክሊኒክ ከደረስክ ጥሩ ነው" አለ፣ ሰሞ ላለ ጊዜ መንገዱን ዘግቶ እላሳልፍ ብሎ ከፊቱ የተጋረጠውን ከባድ መኪና እየቀደመ፣ ከሳንች ጋር የበለጠ ተቀራርበው በየላምንቱ ቅዳሜ ላይ እብረው ይሮጣሉ። በየመሃሉ ተገናኝተው ሻይ ቡና ማለት ጀምረዋል ... ከንጹሕና ከልጆቹ ጋርም አስተዋውቋታል፣ ንጹሕ ታክሲ በምትፈልግበት ጊዜ ቋሚ ሾፌሯ ሆኗል።

በቀለበት መንገዱ በኩል ከአለርት ሆስፒታል በፊት ያለው አደባባይ ጋሲደረሱ ወደ አቶ በድሉ ዞር አለና፣ "ወደ የት በኩል ነው የሚሄዱት አቶ በድሉ?" ሲላቸው፣ እንደ መባነን ብለው፣

"ወደ ቤት ነው ... ብዙም አይርቅ ኧረ ... እዚህ ተደረሰሁ ይበለኛል - የቀረውን በግሬ አዘግማለሁ። እመቤቴ የማታ እንጀራን ትሰጥዎ ዶክተር" ብለው እየተርበተበቱ አጉተመተሙ።

@OLDBOOOKSPDF

"ኧረ ግድየለም ሰፈርዎ አደርሰዎታለሁ። እኔም እዛው አካባቢ ኗሪ ስለሆንኩ አይጨነቁ..." ሲላቸው፣ ትንሽ ተግደርድረው ዝም አሉ። አቅጣጫውን እየመሩት ወደ ቀሬ አቅጣጫ መሄድ ጀመሩ። ልጠይቃቸው አልጠይቃቸው እያለ ልቡ ውስጥ ሲብላላ የነበረውን ጥያቄ እንደምንም ብሎ አወጣና፣ "ይቅርታ አቶ በድሉ፣ እዚህ አካባቢ ብዙ ከኖሩ ምናልባት ሰው ብጠይቅዎ ያውቁ ይሆን?" አላቸው።

ደንገጥ ብለው ወደ እርሱ ዞር አሉና፣ "ማንን ልጄ? እንዳልኩህ እርባ ዓመት ሊሆነኝ ነው እንግዲህ እዚሁ ሰፈር" አሉ፣ ትንሽ እንደ መርበትበትም እያላቸው።

"ወይዘሮ ተዋበች ቸኮል። ጊዜው ቀየ በጣም ... ሠላሳ ዓመት አካባቢ ላይሆን ይቀራል ብለው ነው። እሳቸውም የሥጋ ደዌ ለመታከም ከጎጃም መጥተው ነበር እዚሁ የቀሩት። እንዲያው ምናልባት ብዬ ነው" አለ፣ ፊታቸው ላይ ያለውን ስሜት ለማንበብ እየሞከረና የሚሉትን በጉጉት እየጠበቀ። የሥጋ ደዌ ሕመም እንዱ ጦስ በፊት ላይ ያሉ ጡንቻዎቻችንን የሚቆጣጥሩትን ነርቮች ሁሉ ከጥቅም ውጪ ስለሚያደርግ ፊትን ስሜት አልባ ግድግዳ ማስመሰሉ ነው።

"እንጃ ልጄ ... ተዋበች ... ተዋበች ቸኮል ... እስቲ ላጠያይቃ ... እንጃ ልጄ ... ሰሙ አዲስ አይዶለም ... ምን ሰፈሩ እኮ ባህር ሁኗል" አሉ፣ ግራ እንደ ገባቸው። ከሙቀቱ ጋር ተደማምሮ የመኪናዋ ጠረን ስለ ታመቀ በርሱ በኩል ያለውን መስኮት እስከ መጨረሻ ከፈተው።

"በቃ እስኪ ያጠያይቁልኝ ... ከሰሙ ደግሞ ይነግሩኛል። ለዝናሽም የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን አይዝዎ እንግዲህ። አሁን ምንም አትልም። ይቺ ደግሞ ላንዳንድ ነገር ትሁንዎ፣ ትንሽ ትረዳዎታለች" ብሎ፣ ሁለት መቶ ብር በእጃቸው ሲያስጨብጣቸው፣

"ኧረ ባዛኙቱ ይኼ ሁሉ ምንድነው? ኧረ ባክዎ ዶክተር ... ኧረ አያስፈልግም" ብለው፣ በመግደርደር እየተርበተበቱ የሚያደርጉትን አጡ።

"ግድ የለም አባባ ... ለዝናሽ ልጆችም የሚያስፈልጋቸውን ይግዙላቸው። ምንም አይደለም" ብሎ፣ ገንዘቡን እጃቸው ውስጥ እንዲቀይ አጥብቆ ያዘቸው።

ወዲያው ቀና ብለው ወደ ውጪ ግራና ቀኝ አዩና፣ ፊታቸው ላይ ያለው ድንጋጤ እየጨመረ፣ "በቃ በቃ ዶክተር ... እየህ ድረስ በቂ ነው. ...እይሄች ጋ ልውረድ። ተየህ በላይ ተተጠጉ ደግሞ የመንደሩ ሰው ያይና በመሂና ተሞኛ ጋር መጣ ብሎ መከራዬን ነው እሚያበላኝ። ቤት ኪራይም ይጨምሩብኛል ... ሌባውም ፍጻ ነው። እዚሁ ያውርዱኝ" ብለው፣ በፍጥነት የለጣቸውን ብር ከደረት ኪሳቸው ውስጥ ለመወሸቅ ሲንደፋደፉ አሳዝነው መኪናውን አቀመ። ነገሩ ሙሉ ለሙሉ ባይገባውም በሩን ከፍቶላቸው ወርደው እየተገላመጡ ካንድ ሰላች መንገድ ገብተው እስኪሰወሩ ድረስ ባይኑ ሸኛቸው። በቅጡ እንኳ አልተሰናበቱትም ነበር።

@OLDBOOOKSPDF

ለርሳቸው ግይነት ሰው ከርሱ ጋር መታየቱ ይህንን ያህል መዘገ ያለው መሆኑ እንዴ ገረመው፣ መኪናውን አዙሮ ተመለሰ። አራቱንም መስኮቶች ከፍቶ ነፋሱ በሁሉም አትጣጫ በጥድፊያ እየገባ ሲወጣ አብዛኛውን የታመቀ አየር ጠራርጎ ቢያወጣውም ጠንከር ያለው የገናና አባት ጠረን ግን ከመኪናው ውስጥ ሲንቀዋለል ቀየ። ብዙ አሳቦችን ሲያወጣና ሲያወርድ ወደ ቤቱ የመጨረሻ መታጠፊያ መድረሱ እንኳ አልታወቀውም ነበር።

"ልጆቼ ... ልጆቼ!" የሚለው የገናና እናታዊ የሰቀቀን ድምፅና ወረቀቱ ላይ የተንጠባጠበው እንባዋ ደጋግሞ ፊቱ ላይ ድቅን አለበት። ከብዙ ዓመታት በፊት እዚሁ ሰፈር ውስጥ ገንትና እናቷ ወይዘሮ ተዋበችም ይኖሩ እንደ ነበር ትዝ አለው። ያጋጣሚው ነገር እንቀቅልሽ ሆነበት። 'ሌላ ዘመን ... ሌላ አጋጣሚ ... ሌላ ሰው ... ሌላ ሁኔታ ... እንቀቅልሹ ተፈትቶ፣ ውስጠ ነገሩ ተከፍቶ ቢታይ፣ ሁሉም ነገር የቀደመው ነገር ግልባጭ ... ያለፈው ክስተት ድግግሞሽ ... 'ውሃ ቅዳ' መስሎ ተሰማው። ሕይወት ራሷ ... የታቀደች አጋጣሚ... ሌላና ያው ... አዲስና ድጋሚ ... በግጭት ወስጥ ያለች ስምምነት ሳትሆን አትቀርም' አለ ለራሱ ... በሐሳቡም በድምፁም።

@OLDBOOOKSPDF

፲፩

ሳንቾ ገና በጠዋት ነው ከእንቅልፉ የነቃው። በማያውቀው ደስታ ተሞልቶ ከመኝታው ላይ ፍንጠር ብሎ ወረደ። የአልጋ ልብሱን እንደ ነገሩ ለበስበስ እድርጎ፣ እየተንጠራራ መስኮቱን ወለል እድርጎ ከፈተው። ከአልጋው ፊት ለፊት ካለው ወለል ላይ ቁጥሩ ያልታወቀ 'ፑሽ አፕ' ሰርቶ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባ። ቧንቧው ውኃ ስላልነበረው፣ በጀሪካን ተሞልቶ ከተጠራቀመው ወደ ሳፋው ውስጥ ገለበጠ። ሰውነቱን በቀዝቃዛ ውኃ በጠዋት መታጠብ ልማዱ ነው። ሌሊቱን ሞቶ ያደረው ገላው በረድ ሲልለት ሰውነቱ የበለጠ ቀለለው። ፎጣውን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ እየተንቀጠቀጠ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ። ብርዱ ጋብ እስኪልለት በፎጣው ተጥቅልሎ፣ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠና ማታ ይዞ የገባቸውን የስፖርት ጋዜጦች ሲያገላብጥ ቀየ።

ሰዓቱ አንድ ከሩብ ሲል ተነስቶ ለመውጣት ዝግጅት ጀመረ። ባለፈው ሳምንት ላይ የቅርብ ጓደኛው ከፈረንሳይ ይባለት የመጣችውን ሹራብና ጂንስ ለብሶ፣ ወዲያ ወዲህ እያለ ሞከረው። ከቁም ሳጥኑ መስተዋት ፊት ቆመ። ከፊት ለፊቱ ከሚያየው ፈርጣማ ጕፈራ ወጣት ጋር እንዳማረባቸው ተስማሙ። ነጫጭ ጥርሶቹን ፈልቀቅ አድርጎ ፈገግ ሲል፣ ሰፋ ባለ ሻካራ ፊቱ ላይ ፀሐይ የወጣች መሰለ።

ወደ ኩሽና ገብቶ ትንሿ ባለ ሦስት ጕልቻ የጋዝ ምድጃው ላይ የሻይ ውኃ ጣደ። ተመላላሽ ሰራተኛው ከፍሪጁ ውስጥ በሰሃን ሰርተው ያስቀመጡትን የፍርፍር ቁሌት አውጥቶ ቀነሰና ከሻዩ ገን ጣደው። ደርቀሽ ዉምሮ ፈጣን ፍርፍር ሰራ። ቁርሱን በቁመ- ቀማምሶ ለልጆቹም በሰሃን በሰሃን ድርሻቸውን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦላቸው እያኝዉ በሩን ዘግቶ ወጣ።

ከፈረንሳይ ከመጣችው ጓደኛው ጋር የያዘው የምሳ ቀጠሮ እስኪደርስ ልቡ ተንጠልጥሏል። የሁለተኛ ዶረኛ ትምህርቷን በሊሴ ገብረማርያም ስትማር ጠዋትና ማታ በታክሲ ሲያመላልሳት ነው የተዋራረቡት። ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ ፈረንሳይ ሀገር ከሄደች በኋላ፣ ብዙ ጊዜ በመር አንድ ሁለት ጊዜ ሳትደውልለት አትቀርም። ማታ ላይ ደግሞ ሲስተር ዘቢባ ቤት የእራት ግብዣ ስላለው፣ ዛሬ ቀኑን ሙሉ መሥራት

@OLDBOOOKSPDF

አይችልም። በለስ ቀንቶት በጠዋት ያገኛቸውን ሁለት የኮንትራት ሥራዎች ረፋዱ ላይ ጨረሶ፣ ጠቀም ያለ ብር ኪሱ አስገባ። ከዚያም እስከ አኩለ ቀን አካባቢ መስመር ገብቶ ሲሠራ ቀየ።

ከአትላስ ጆርባ ከሚገኘው የጓደኛው ወላጆች ቤት በሰዓቱ ደረሰ። ዘበኛው በሩን ከፍተው ለት ገብቶ መኪናውን ግቢው ውስጥ አቆመና እያመነታ ወረደ። ሁሌም እዚህ ቤት ሲመጣ የቤቱ ግዝፈትና ግርማ ሞገስ፣ በርሱና በላዳ ታክሲው ላይ ትከሻውን ቀልሱ የሚያሸፍባቸው ይመስለዋል። ተወልውለው እያብረቀረቁ ግቢው ውስጥ የተደረደሩት ሌሎች መኪኖች ደግሞ ያንን እየሰሙ የሚያላግጡበት። በረንዳ ላይ ሆና ስትቁነጠነጥ የነበረችው ጓደኛው ከሩጫ ባልተናነሰ ፍጥነት ወደ እርሱ መጣች። አጠገቡ ደርሳ እንኳ ሰላም ስትለው፣ 'ይሄን የመሰለ ግቢ ውስጥ የተፈጠረች ይቺን የመሰለች ቁንጅ ልጅ አሁን እኔ ላይ ምን ያንጠላጥላታል?' አለ ለራሱ።

የተቀባችው ሽቶ መዓዛ እንኳንስ በሕይወት ያለን መታንን የመቀስቀስ ኃይል አለው። "ሳንች ... ጊዜው እንዴት ነው የሚንቀራፈፈው። ደጋግሜ ደውዬልህ ዝር እኮ። ኡፍ ያቺ ስልክህ ላይ ያለችው ደረቅ ሴትዮ ... ምን አቃጥል የሆነችው ናት በናትህ ... 'ደንበኛዬ ባካባቢው የለምና አትጨቅጭቂው' ምናምን ስትል እንዴት እንዳናደደችኝ ብታይ" ስትል ፈገግ አለና፣

"ኧር ዝም በያት ... ከጠዋት ጆምሮ እኮ አብራኝ ነበረች። ሰው ሲደውልልኝ በጣም ነው የምትቀናው" ሲላት፣ ንዴቷ ሁሉ ባንዴ ጠፍቶ መስቅ ጀመረች። እኝነ እንደ ያዘቸው ሽቅብ እያየች ስታወራው፣ 'ላጭርም አጭር አለው ለካ' ብሎ ውሰው ደስ አለው። ወዲያው ደግሞ 'አይ ሰው መሆን ... አሁን ይህቺም የቁመት ልዩነ ብልጫ ሆኖ ነው' ብሎ፣ የራሱን ደስታ ታዘበ። ልጅቱ በቅጭን ሚጢጢዬ ሰውነቷ የሶስት ሰው ውበት ያንቀጠቀጣት፣ የእናቷ ግልባጭ ትመስላለች።

"በቁምህ ጹስ ነገር ቅመስ በናትህ ... በዛውም እነ ባቢም ስላሉ ሰላም ብለሃቸው እንወጣለን" ስትለው፣ ዘብድ ብሎት እያመነታ፣

"ይሻላል ብለሽ ነው...?" ሲል፣ እጁን እንደ መጮተት በለንድ እጁ ሳብ እያደረገችው፣

"በጣም እኮ ነው የሚወዱህ ... ደበረህ እንዴ መግባቱ?" አለች፣ በሌላ እጁ ከሹራቡ ስር ያለውን የሽሚዙን ኮሌታ እያስተካከለችለት። 'እንኳን አነርሱ እንቺም ለምን እንደምትወጂኝ ሊገባኝ አይችልም' የሚል የውስጥ አሳቡን ገሞ ለማስመል እየታገለና እያመነታ ተከተላት። የሳሎኑ በር ሲከፈት አይን የሚያጭበረብር ውብ ከተሳበሱ የቤት እቃዎችና የግድግዳ ስዕሎች ጋር ፊት ለፊት ተጋፈጠ። በርሱ የኮንዶሚንየም ሰፈር የርቀት አለካክ ሀግ 'ከማዶ ያለው ብሎክ' በሚባል ርቀት ላይ ወላጆቿ ተቀምጠዋል። የተቀመጡባቸው ሶፋዎች እያንዳንዳቸው አንድ ጥሩ ላይ ታክሲ ሊገዙ የሚችል ዋጋ አላቸው። ወደ ወላጆቿ አማተረና ቀም አለ። ከፊቱ ያለው ምንጣፍ ላይ መረማመድ የሰው ፊት የመርገጥ ያህል ስለ ዘገነነው ጫማውን ሊያወልቅ

@OLDBOOOKSPDF

ጎንበስ ሲል፣ አሻፈረኝ ብላ እጁን ያዘችው።

አባቷን ከጨበጠ በኋላ እናትዬው በጉንጭ ለጉንጭ ግጭት ሳሙትና፣ "ሳንችዬ ... በቃ ሰሚር ከሌለች እኛ እንጠየቅም እንዴ?" አሉ፣ እጁን ሳይለቁ አይን አይኑን እያዩ ሳቅ ብለው።

"ምን ... ሁል ጊዜም ለመምጣት አስባለሁ እኮ፣ አልሞላ ብሎኝ ነው እንጂ። እናንተም በጣም ቢዚ ትሆናላችሁ ብዬ ስለማስብ ..." ብሎ፣ ራሱን እከክ እከክ አድርጎ እጮነበሰ። ከጫካው ወጥቶ በከተማ መሃል እንደተገኘ የጉር አውራ እጅና እግሩ ረገሞ ተሳሰረበት። እንደቁሙ ትንሽ አውርተው እንዲቀመጥ ቢጋብዙት አሻፈረኝ አለ። ሰሚራ ለመውጣት ተዘጋጅታ ቦርሳዋን ይዛ ከላይ ስትወርድ ውሰጡ ተንፈስ አለለት። ሴላ ጊዜ ለመምጣት ቃል ገብቶ ተከታትለው ሲወጡ፣ ወላጆቿም የሳሎኑን በር አስወጥተዋቸው በረንዳው ላይ ጐን ለጐን ቆሙ።

የሳንቾ አሮጌ ላዳ መኪናም መስላ የማትታያቸው አባቷ፣ "እንቺ ሰሚር ... ወይ ባይሆን ለምን የኔን ወይም የጥትሽን መኪና አትይዙም?" አሉ በኀርናና ድምጻቸው። በፒጃማቸው ላይ የደረቡትን የቤት ቤት ካባቸውን ሰብሰብ አድርገው የምድር ወገብ ከመሰለ ወገባቸው ላይ በማሰሪያው ሸብ አደረጉት። የሰውነታቸው ግዝፈት አስገምጋሚ ድምጻቸው የሚሰራበት ፋብሪካ ይመስላል።

"ኖ ... ባብ ... ዋናው ቁም ነገሩ ያለው እኮ ... በላዳ መሄዱ የሚለጥህ የልጅነት ትዝታና ነጻነት ላይ ነው። ከፈለግህ አንተ ና ና ተሳፈር" ብላ ስትስቅ፣ ጭንቅላታቸውን ወዘወዙ። "በሉ መልካም ቀን ... ደህና ዋሉ" ብላ ቦርሳዋን የኋላ ወንበሩ ላይ ጣል አድርጋ እጁን አውለብልባ ገባች። ሚስታቸው ትከሻ ላይ የጫኑትን እጃቸውን አንስተው አጸፋውን መለሱላት።

"ደግሞ ቀስ ብላችሁ ንዱ" ሲሉ እናቷ፣ በፈገግታ እጁን ላም አድርጋ ወደ እርሳቸው መልሳ ዘርጋችላቸው።

ከግቢ እንደወጡ፣ "ምንድነው ምላ ያሰኘሽ?" አለ ትንሽ ዘና ብሎ።

"የገል ጥብስ ... ያ ቤት ምን ነበረ ስሙ ... ያኔ የምንበላበት ቦታ ..."

"ጊርጊሮ?"

"አዎ ... በናትህ እሱ ቤት አለ አሁንም?"

"ቦታ ቀይረዋል ... ቀይ እንደውም ሴላ ቦታ ላሳይሽ። ጥሬ ሥጋ መሞከር ትፈልጊያለሽ?"

"በልቼ አላውቅም እኮ ... ቢያመኝስ?" ብላ ስታመነታ፣

"ትታከሚያለሽ ... ደግሞ ምንም ጣጣ የለውም የታከመ ሲጋ ነው። እንዲያውም አዲስ ሰው ሲበላው ሥጋው ነው የሚታመመው ..."

@OLDBOOOKSPDF

"ኧረ ባኮ ..." ብላ ሳቀችና፣ "እንሞክረዋ ... አይገድለን። ለነሚ ነገ አንናገርም እሺ" ስትለው፣ 'እንቺው ነልተናገርሽ እኔማ በምን አትሚ' አለ በሆዱ።

"እንዲያውም ላባትሽ ነው የምንገራቸው። ልጅዎ አንድ የበሬ ሽንጥ ጨርሳ እያ ውስጥ ከተተችኝ ብዬ"

"እሱማ እንድበላለት ነው የሚፈልገው እኮ። እንዶሱ ብለህ ብትነግረው የወርቅ ሚዳሊያ ነው የሚሸልመኝ። እሱ ራሱ እኮ አንድ ቁጥር ቀራጭ ነው። ደግሞ ጋባሹ እኔ ነኝ እሺ ..."

"እሱን እናያለን ... አበላልሽ ታይቶ" አለ። በተጋጨ መኪኖች ምክንያት መንገዱ ስለተዘጋጋ መንገድ ቀይሮ ውስጥ ውስጡን አሳብሮ ከምሳ ቦታው ደረሱ። ምሳ ቡና ሲሉ፣ ከሰዓት በኋላው ሳይታወቃቸው ነበር ያለቀው። የማታ የእራት ቀጠሮው እየደረሰ ስለነበረ፣ እንዳበቡት አብረው ቀይተው ፊልም ለማየት አልቻሉም። ወደ ቤቷ አድርሷት ሲመለስ፣ ለረጅም ጊዜ በልቡ ውስጥ አፍኖ ያቀየው ስሜት እንደኸ ሲያገረሽበት ተሰማው። ከሁሉም ጋር ተግባቢና ጓደኛ ስለሆነች ለርሱ ያላት ስሜትም እንደሆነ በትክክል ሊያውቅ አልቻለም። ስለዚህ ከውስጡ ልውጣ ልውጣ ለሚለው ፍላጎቱ ፊት ሊሰጠው አልፈለገም። እሷ እንኳን ብትወደው ቤተሰቦቿ የማይዙ ተራሮች መስለው ታዩት።

እሷን አድርሶ ሲመለስ፣ ማታ ሲስተር ዘቢባ ቤት ይዞ የሚሄደውን ኬክ ገዝቶ አፓራ አካባቢ ወደሚገኘው ኮንዶሚኒየሙ በቀጥታ ነዳ። ሲገባ ልጆቹ ጉን ለጉን ተቀምጠው እያጠኑ ነበር። ይዞ የሚሄደውን ኬክ ፍሪጅ ውስጥ ከተተና ያመጣላቸውን ጥብስ አካፍሎ አቀረበላቸውና ግንባራቸውን ሳም ሳም አድርጎ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ፣ ትንሽ ማረፍ ስለ ፈለገ፣ በሩን መለስ አድርጎ ጫማውን ብቻ ወለቅ ወለቅ አደርጎ አልጋው ላይ ጋደም አለ። ሰለ ሙሎው እያሰበ ሽለብ እንዳደረገው፣ የጥልና የለሾ ድምጽ ሰምቶ ወደ ሳሎን ሲሄድ፣ ያከሰቱ ልጆች እንገት ላንገት ተናንቀው ይደባደቡ፣

"እንዴ ምንድነው እሱ? አቁሙ ብያለሁ፣ ሁለታችሁም ቁጭ በሉ እዛ ሶፋላይ" ብሎ ሲያንባርቅባቸው፣ በመካከላቸው መብረቅ ገብቶ የለያያቸው ያህል ተነጣጠሉ፣ ፈንጠር ፈንጠር ብለው በእልህ እያለከለኩ ቁጭ ቁጭ አሉ።

ታናሽዬው ከድር ገና ሳይጠየቅ እንባው ዱብ ዱብ እያለ፣ "ራሺ ናት መጀመሪያ የተማታችው ... እኔ ምንም ሳለደርጋት" ሲል፣

ታላቅ እህቱ ሃሊማ ደግሞ፣ "የበላበትን ሣህን እንሳና አጥበህ አስቀምጥ ስለው፣ የሴት ሥራ አልሠራም ብሎ እንደ ልማዱ ሊሮጥ ሲል ... እዚህ ገረድ የለህም እንሣት ስለው ... አላትልሽም ከፈለግሽ ራስሽ እጠቢ ብሎ ሣህኑን መሬት ላይ ወርውሮ፣ ሊሮጥ ሲል ነው ይገር የመታህት" ብላ፣ እልህ እየተናነቃት የራሺን ታሪክ አቀረበች፣ ዕድሜያቸው ሰባትና ዘጠኝ ነው።

"አንተ ለምንድን ነው የበላህበትን የማታጥበው?" አለ ሳንኦ፣ ወደ ከድር፣

"እኔ ጥናት አለብኝ ስሞ ያልቤ ሳ ሳ ብ ሞ ሰ ሰ ተረተረ።

"ዝም በለው የሴት ሥራ ነው ... ራስሽ አጠቢ ነው ያለው ። ደግሞ መኝታ ቤቱን ሁሉ እያቀሸሸና እያዝረከረከ ተው ስለው ይላደባል ። አልጋ ማንጠፍ ... እም ... ቤት ማጽዳትና ዕቃ ማጠብ የሴት ሥራ ነው ... እያለ ... ደግሞ በቀደም 'ገረድ' ብሎ ተሳድቦ ወደ ውጭ ሮጧል" ብላ ፣ ሳግ እየተናነቃት አስቀሰች ።

"እሺ በቃ ዝም በይ ... ይሄስ ውሽት ነው?" አለ ሳንቾ ፣ ቀጣው እየጨመረ ። እንባቱን አቀርቅሮ ዝም አለ ። "ተናገር እንጂ ... በመጀመሪያ አቢ ታላቅህ እንደሆነች አታውቅም? የምን መወጣጠር ነው ። ማነው ደግሞ እቃ ማጠብና ቤት ማጽዳት የሴት ስራ ነው ብሎ ያስተማረህ ። በል አሁን ተነሳና ይቅርታ ጠይቅ ..."

ጎንበስ ብሎ ቀየና ፣ "ራሲ ናት ጥፋተኛ ... ምን አድርጌ ነው ይቅርታ የምጠይቃት?" ሲለው ፣ ሳንቾ የንዴት ሳቅ ሳቀ ።

"እሺ አሁን ሁለታችሁም ኑ" ብሎ ፣ ጠረጴዛ ላይ ያለውንና መሬት የወደቀውን ሣህን እንስቶ ፣ ወደ ጓዳ አስከትሏቸው ገባ ። ሁለቱም ካጠገቡ ዐጥ ብለው ቀሙ ። ሣህኖቹን አጣጥቦ ማድረቂያው ላይ ደረደረና ኩሽናውን እያጸዳዳ ሻይ ጣደ ። "ከድር ... እኔ ወንድ ነኝ ሴት?" አለው ጠጋ ብሎ ።

"ወንድ" ብሎ አትተመተመ እንዳቀረቀረ ።

"እና ዕቃ ስላጠብኩ ምን ሆንኩኝ? ወንድ ስለሆንኩኝ ዕቃው አልታጠብም አለኝ?" ሲለው ቀና ብሎ አይቶት በእፍረት ዝም አለ ። "እየህ ሥራ ጾታ የለውም ። ከዛሬ ጀምሮ እዚህ ቤት የሴት የወንድ የሚባል ነገር የለም ። እንዲያውም ሁሉንም ሥራ በየተራ ነው የምትሰሩት ። ልክ እንደ አንተ ሃሊማም መጫወትና ማጥናት ትፈልጋለች ። እማማ ሲመጡ የሚሠሩት እኛ የማንችለውን ሥራ ብቻ ነው ። እሺ ... አሁን ጊዜ የለኝም ፣ የቀረውን ግቻ ስመለስ ወይም ነገ እናወራለን ። አሁንስ እህትህን ይቅርታ መጠየቅ ትፈልጋለህ?" ሲለው

"ይቅ...ር...ታ" አለ በሃፍረት ድምፅ ፣ ፊቱን ከመሬቱ ላይ ሳይነቅል ።

እንዲተቃቀፉ ካደረገ በኋላ "በሉ አሁን ወደ ጥናት ። ከዛ በፊት ሂድ ስልኬን ከታክሲ ውስጥ አምጣልኝ" ብሎ ላከው ። ትንሽ ቀየት ብሎ ሻዩን ቀድቶ ካመጣላቸው ኬክ ጋር ከፊት ከፊታቸው ሲያስቀምጥላቸው በደስታ ተፍነከነኩ ። ወደ ጓዳ ተመለሰና የራሱ ሻይ ውስጥ ትንሽ ፈጣን ዱቄት ቡና ጨምሮ እያማሰለ ምስጢር ጋ ደወለ ።

"ሄይ ሰኢዶ ... አልተነሣሁም እንዳትለኝ ብቻ ... እየመሸ ኮ ነው?" ሳንቾ የሚለው ሰም ብዙም ስለማይጥማት ፣ ሰኢዶ ብላ ነው የምትጠራው ። ሚች እከስቱ ብቻ ነበረች ሰኢዶ የምትለው ። ከምስጢር ጋር ከተዋወቁ ጥቂት ሳምንታት ቢሆንም በፍጥነት ነው ተግባብተው የተቀራረቡት ።

"ይቅርታ በናትሽ ... እዚህ ስንሞዳሞድ እኮ ጊዜው ከነፈ ። አሁን ልወጣ ነው በቃ ... የት እንገናኝ?" አለ ፣ ወደ መኝታ ክፍሉ እየሄደ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ለምን እኛ ሰፈር ሮቤራ ቡና አንገናኝም? ሁለታችንም ከምንነዳ ካልደከመህ ያንተን መኪና ይዘን እንሂድ?"

"ጥሩ ... በቃ እንድ ሠላሳ ደቂቃ ከሰጠሽኝ ደርሳለሁ። እነ ዶክተር ጋ ደውለሽላቸው ነበር እንዴ?"

"አይ አልደወልኩም ... ለምን አንተ እትደውልላቸውም? በቃ አታርፍድ ኸ እሺ?"

"እየመጣሁ ነው ... አሁን እደርሳለሁ" ብሎ፣ ስልኩን ዘጋ። "በሉ እኔ አንድ ቦታ እራት ስላለኝ መሄዴ ነው። ድንገት ከቀየሁ ግን ራታችሁን በልታችሁ መተኛት ትችላላችሁ ... እሺ?" ሲል፣ ሁለቱም ባንድ ድምፅ "እ-ሺ" አሉ። መጣላታቸውን ረስተው እየተሣሣቁ ኪካቸውን ለመጪረስ እየተጣደፉ ነው። በመገረም ጭንቅላቱን ነቅንቆ 'አይ የልጅ ጥል' ብሎ፣ ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰ።

በችኮላ ልብሱን ለውጦ፣ ፍሪጅ ውስጥ ያስቀመጠውን ኬክ ይዞ ወጣ። ሌላው ጋ ሲደውል ከቤት ወጥተው ሚክሲኮ አካባቢ መድረሳቸውን ንጹሕ ነገረችው። ሮቤራ ሲደርስ ታክሲውን አቆመና ምስጢር ላታየው ከጮኺ ቀስ ብሎ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ በወፍራም ድምፅ፣ "እዚህ ቤት አትምጭ አላልኩም ነበር" ሲላት፣

"ማሚዬ ..." ብላ፣ በድንጋጤ ተስፈንጥራ ብድግ ሰትል ማቁን ለቀቀው።

"ሂ ...ዛ ... ምንድነው አንተ እንደዚህ ሰው ማስደንገጥ። ቀልቤን ገፈፍከኝ እኮ። ደግሞ ማርፈድህ እንሶህ ነው ..." ብላ ፈርጣማ ትከሻው ላይ በጨበጠችው እጇ መታችው። ጆሮዋ ላይ ያደረገችውን የሙዚቃ ማዳመጫ አውጥታ ቦርሳዋ ውስጥ ጨምራ ሰላም ተባባሉ።

"ው ይይይይ በናትሽ ... አንቺ ግን ምንድነው እንደዚህ ማማር ... ወላሂ ... ለኛም ሞራል መጠንቀቅ አለብሽ እኮ ... ደሞ ቁመታችንን እንዴት ነው የጨመርነው? ... ማንን ለማሳጣት ነው?" አለ፣ እጇን እንደ ያዘ ካጠገቧ ቀሞ ቁመቱን ከሆነው በላይ አሳጥሮ እየቀለደ።

"አቤት አቤት ... የምን ማጋነንነው ... የምር የምር ግን ... ቁመቱን ግን አስብበት ... እስኪ እስኪ" ብላ ጮኦ ቀሞ ሰትል፣ ካደረገችው ረጅም ታኮ ጫማ ጋር በደንብ በልጣዋለች። በትከሻዋ ገፋ እያደረገችው፣ "አይ ሰኢዶ ዛሬስ የምር ተበልጠሻል ... እንግዲህ መከባበር ያስፈልጋል። ዛሬ አለባበስህ አልተቻልክም ... የ.ም.ር፣ ሽቶው ደግሞ የላቀ ነው ... ማን እንበለው?" አለች ዓይኖቿን ዘጋ አድርጋ ሽታውን እንደሚያጣጣም በረጅሙ ወደ ውስጥ እየሳበች። ለሽታና ለሽቶ፣ ለድምፅና ለሙዚቃ ስል ስሜት አላት።

"እኔ እንኳ ... ስሙን ለናንተ ትተነዋል ... የኛ ሥራ ከብልታሙ እስኪያልፅ መነስነስ ነው። አንዱ ጓደኛዬ ነው፣ ባለፈው ከጣሊያን ያመጣልኝ ... አዛሮ ነው አሸራራ ያለኝ ባክሽ ... ምን ለውጥ አለው ብለሽ ነው" ሲል ትከሻውን ደገፍ ብላ ሣቋን ለቀቀችው።

@OLDBOOOKSPDF

"ሁሉም ሰው እንዳንተ የማያከብድ ቀለል ያለው ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር" አለችና ኮሌታውን ትንሽ አስተካክላለት፣ "በል በል አሁን እንሂድ ... ሰአቱ በጣም ሄዷል..." ብላ ወጡ።

"ምንድነው ደግሞ የተሸከምሽው?" አለ፣ በፈስታል የያዘችውን ነገር እየተቀበላት።

"እይ ትንሽ የተቀላ ቡና ... ያው ቤቱ እንዳይለምድብን።"

"እንዲያውም ሙች ... ቡና ይዘሽ ከሄድሽ በጣም ነው የሚለምድብሽ ... ካሁን በኋላ ከዛ ቤት ላትጠፊ ትችያለሽ። እንዳይለምድብሽ ከፈለግሽ ኪስ ነው መድኃኒቱ" ሲል፣

"ምን እዚህ ሰፈር ... ኪስ ከየት ይመጣል? እንዲያውም ካልከሰ ይልመድብኝ ... ቢስተርዱ እኮ ነፍሴ ናት። እናት ነገር የሆነች ሰው ..." አለች፣ በሩን ከፍቶላት ስትገባ። ከኋላ ወንበር ላይ ያስቀመጠውን ኪስ እየችና እየሣቀች፣ "አጅሬው ተንቃብህ ... ለካ የሚንከውን ሚነህ ነው ኪስ ምናምን የምትለው። ጉበዝ ልጅ ነህ ግን ... ማሰብህ ይበቃል" አለች፣ ትከሻውን መታ መታ እያደረገች። ለመሣቅ ትንሽ ነገር ይበቃታል።

የለበሰችው ጥልቅ ድምቀት ያለው ጥቁር ሞሚስና ፍንትው ያለ ውሃ ሰማያዊ ጃኬት ተፈርፍሮ ከተበተነው አጭር ጸጉሯ ጋር የቀይ ጠይም መልኳን ይበልጥ አስውቦታል። ፍልቅልቅ ብላ ስትሥቅ ደግሞ የብርሃን ፈሳሽ የተደፋባት ትመስላለች። ውበትን ለመካብ ታላትአጥሮት የማያውቀው ሳንቾ ደግግሞ ሲያደንቃት አፈር ብላ፣ "ውይ በቃ የምን ችክክ ማለት ነው" አለችና ቆንጠጥ አደረገችው።

"የምር የምር ግን ... እኔና ፉንጋ ታክሲዬ እንቺን ሞኑን ለእራት ስንሄድ የሚሰማንን ዘብር ብንገልጽ ችክ ማለት ይባላል? ... አላህ ቁንጅ ሰውና ምርጥ የጉራጌ ከትፎ ባይፈጥር ኖሮ ሕይወት ምንሞ አሰልች ትሆን ነበር" ብሎ፣ ዓይኑን ቦዘገ አድርጎ፣ ጉንጩን በሣት ሞልቶ በጮን አየት ሲያደርጋት፣

"መንቻካ ሆነሃል እኮ ሰኢዶ ... እስኪ በቃ አሁን አፍህን ዘግተህ አርፈህ ትነዳ" አለች ፊቷን በመኪናው መስተዋት እያየች። እቤት ባከሰቱ ልጆች መካከል ሰለ ተፈጠረው ጥልና ምን እንዳደረገ ነገራት። በሴት ልጆች ላይ ካስተዳደጉ ጀምሮ ስለሚደርሰው ጫናና ሚዛን ያጣ ኃላፊነት፣ በትምህርት ቤትና በውጪም ስለሚደርሰው ተዉማሪ አድልዎና ፈተና በዚያው አንስተው አወሩ። ትንሽ ከመነታች በኋላ ከነሴጅ ጀምሮ እየተከታተለ መድጂሻለሁ እያለ ስለሚከታተላት ልጅ የተመሰነ ነገር ነገረችው።

"እና ምን ሆነ መዉረሻ ላይ ... አቀመ መነከታተሉን?"

"አዪ ምን ያቀማል ... ባለበት እንጂ ..."

"ሰመነሰስ ምናምን አልሞከርሽም?"

"ወይ መነሰስ ... ያልደረስንበት ቦታ አልነበረም ... ትምህርት ቤትም ላራሳቸውም እየፈሩት ይሁን አላወቅም ገዘ ብለው ማስጠንቀቂያ እየሰጡ እንደ

@OLDBOOOKSPDF

ቀለደብኝ ጨርሶ ወጣ። እኔ ሁለቱኛ ዓመት ስደርስ ነበር እሱ የተመረቀው። ከዚያ በኋላ እንኳ ግቢ እየገባ ሲያስፈራራኝ ... እስከ ቤት እየተከተለ ሲነዘንዘኝ ምንም ላደርግ አልቻልኩም። በኋላ ከእናቴ ጋር ሆነን ብንከስም ፍርድ ቤቱም ምንም ሊያደርግ አልቻለም። አንድ እንደ እሱው ማን አለብኝ ባይ ባለስልጣን እገት አለው፣ ፖሊሶቹም የማን ዘመድ መሆኑን ሲያውቁ፣ በቃ አይተው እንዳላየ ነው የሚሆኑት።"

"እናስ መጨረሻ ምን ሆነ?" አለ፣ የነገሩ ፍጻሜ እያሳሳው፣

"በሊሚልና በስልክ እያስፈራራኝ የሱ ብቻ መሆኔንና በፈለገ ቀን የራሱ እንደሚያደርገኝ ይነግረኛል። በቃ እንዴት እንደሆነ አላውቅም የምወጣበትና የምገባበትን ሁሉ ያውቃል ነው የምልህ። ሲለው አንድ ቀን ጠልፎኝ ስለሚወስደኝ እንድዘጋጅበት ይነግረኛል። ማሰብ ትችላለህ ... የገዛ ጥላዬን እንደ ሽሽው ነበር የምኖረው። ማታ ላይማ በተአምር ስብቻዬ አልወጣም። ከዛ ላስፈው ዓመት ከሸጠኝ ወር ጠፍቶ ነበር። ውጪ ሀገር ሄዷል ሲሉ ሰምቼ እርይ ብዬ ነበር" አለችና ካለፈው አንድ ወር ጀምሮ እየደወለ እንዳስቸገራትና እገዳሚከታተላት ልንገረው አልንገረው ብላ አመነታች።

"እና ... አልሄደም?" አለ ፊቱን ወደቢ ዞር እድርጎ እያያት

"እኔ ምን አውቃለሁ ... ካለፈው ወር ጀምሮ ደሞ መደወል ጀምሯል። ስልክ ቁጥሬን ቀይሬ ነበር። ግን እንደሚሰጠው አላውቅም። አንዳንዴ የትና ከማን ጋር ምን ስሠራ እንደ ዋልኩ ሁሉ ዝርዝሩን ጨምሮ ቲከሰት ያደርግልኛል። በቃ ያየጠፋው ፍርሀቴ ሁሉ እንደገና አገርሽቶብኛል ... ለማሚ ደግሞ ልነግራት አልፈልኩም፣ ብታይ እንዴት እንደምትፈራው" አለች፣ ፍርሃት በተሞላ ፊት ሰውነቷን ስብስብ፣ ፊቷን ሞምትርትር አድርጋ።

"ምናይነቱ ሳይኮ ነው በናትሽ ... ጤነኛ ነው ግን? ለመሆኑ ሥራ ይሠራል ... ስለርሱ ምን ያህል ታውቂያለሽ?" አለ፣ እነ ሲስተር ዘቢባ ሰፈር ስለ ደረሱ መገዛነ በጥንቃቄ እያየ። ልቡ በወሬው እንዲ ተያዘ ስላወቀች፣

"ታሪኩ ብዙ ነው፣ ሌላ ጊዜ እጨርስልሃለሁ። ቀይ ሲስተር ጋ ልደውልላት መሰለኝ ... ደርሰናል ... በዛኛው መንገድ ጋ ይመስለኛል ..." ብላ፣ ስልኳን አውየታ መደወል ጀመረች።

መኪናቸውን እጥር ሥር አቶሙና ከንዱን ያዝ እድርጋ፣ የውጭ በሩ ጋሊያደሱ፣ ከሲስተር ዘቢባ ጋር ተከታትለው ገቡ። በአንድ ሺህ ካሬ ሜትር ግቢ ውስጥ የተሠራ ትልቅ ቤት፣ በአበቦችና በተለያዩ ዛፎች ተከቦ፣ ትንሽ ቤተ መንግሥት ይመስላል።

"ሲስተርዬ ... ውይኔ እንዴት ያምራል ግቢያችሁ ... አረፈድን እንዴ" ብላ ተቃቀፉ።

"የኔ ቀንጆ ታንክ ዩ ... ደግሞ እንዴት እንዳማረብሽ ... ትፍ ትፍ ... ከይነ ያውጣሽ ልጄ ... ምንድነው ደግሞ ይሄ የተሸከማችሁት?" ብላ፣ የያዙትን ዕቃ ተቀብላ ተከታትለው ገቡ። ወደ ሳሎኑ ሲገቡ ከፍ ያለ ጣራውና ሰፋፊ መስኮቶቹ፣ በተለመ

@OLDBOOOKSPDF

በመጠን ከቤቱ ጋር ተዋሕደው፣ በጥራትና በዓይነት የተሰካኩት የቤት ዕቃዎች ቦታ ቦታቸውን ይዘው ቀልብን ይስባሉ። ቀድሞ የደረሰውን ሲራክንና የሲስተር ዘሪባን ባል ሰላም ብለው፣ ሳንቾ ፈንጠር ብሎ ሲቀመጥ፣ ምስጢር ደግሞ ከሲስተር ዘሪባ ጋር ተያይዛ ምግቡ ወደ ተደረደረበት ጠረጴዛ ሄደች።

"ሲስተርዬ ወይኔ ... ቤታችሁ ... በጣም ነው የሚያምረው ... እኔ አልሄድም እዚሁ ነው የምኖረው ..." ብላ ስትሥቅ፣ ጉንጯን ያገ አድርጋ፣

"እግኝቼ ነው አንቺን የመሰለች ልጅ ... የኔ ቀንጮ ... ወደድሽው? ታንክ ዩ" አለች፣ የሲም ፊት በፈገግታ ተሞልቅቀ። የምግቡ ሽታ ቤቱን አውዶታል። በቀስታ የተከፈተው በመሃሪያ ብቻ የተቀነበበረው ሙዚቃ ደግሞ ቤቱ ውስጥ ደስ የሚል ሞት ያለ ድባብ ፈጥሯል። ከባሻገር የዶክተር ሲራክና የአቶ ሲራጅ ወሬ ጮልቶ ይሰማል። አልፎ አልፎ ሰረቅ እያደርግ ምስጢርን ቢያያትም፣ እሷ ግን ቀልቧ ሁሉ ሌላ ቦታ ነበር። ሳንቾ ደግሞ ከገባ ጀምሮ አገጉበሶ ስልክ ያወራል።

እነ ሌላሠው ከሲስተር ዘሪባ ቤት ሲደርሱ ላንድ ሩብ ጉዳይ አካባቢ ነበር። ሕየናቱ አርሴማና ዲንሳ ያመጡትን ቾኮሌትና ስጦታ ካልያዝን ብለው ሰላስቸገሩ ንጹሕ እየረዳቻቸው የበረንዳ ደረጃውን ወጡ። የቤቱ በራፍ ላይ ሲደርሱ ሲስተር ዘሪባ እስገባቻቸው። ንጹሕ እንደ ገባች ከአንድ ጥግ ላይ ከተሠየመው ጥቁር ፒያኖ ላይ ዓይኗ አረፈ።

"እሰኪ ወዶ እዛ እስቶ ... እዛች ሶፋዋ ላይ አረፍ በሉ። ሲራጄ ... ተሞወታቸው ... ሁሌ የማወራልህ ዶክተር ሌላሠው ማለት እሱ ነው። ያው በቲለቫሽ'ንም እይተኸዋል አይደል?" አለችና ልጆቹ የተሸከሙትን ስጦታ ተቀብላ፣ እቅፍ አድርጋ ሰማ ስታመሰግናቸው፣ በደስታ እየቦረቁ ወደ እናታቸው ሮጡ።

"ሙኒር ... የት ሄደች ልጄ ... አንቺ ሙኒራ ..." ብላ ተጣራች ሲስተር ዘሪባ። ከላይ አንዲት ቀንጅዬ ልጅ እየተንደረደረች ስትወርድ "ይሄው ዶክተር ሌላሠው ..." ስትላት፣ እንደ ማፈር ብላ ስትሽኮረመም አንገቷን እቅፍ አድርጋት "እ--ን--ዴ የምን መሽኮርመም ነው። ይሄው ቤትሽ ድረስ መጣልሽ ... በይ ሰላም በያቸው አንጂ" አሰቻት። ወደ ሌላሠው ዞራ፣ "እድናቺህ ናት ... እሷም ሳይካትሪስት ነው መሆን የምትፈልገው። ሙኒራ ማለት እሷ ናት" ስትለው፣

"እህ ታዲያስ ... ብዙ ነገር ነው ስላንቺ የሰማሁት ..." አለና፣ እንደሞሙ ትንሽ አወራት። ሁሉንም ሰላም ካለች በኋላ፣ የእናቷን አንገት አቅፋ እግሯን እያወዛወዘች ቀመች። ዕድሜዋ አሥራ ስድስት ሲሆን የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ናት።

"ዛሬ ብዙ ጥያቄ መመለስ ላይኖርባችሁ አይቀርም። እንዴት ዓይነት ጂኒየስ ልጅ መሰለቻችሁ። ብዙ ጥያቄዎቿን እኛ እንኳን ልንመልሳቸው አንደርስታንድ ለማድረግም አልቻልንም" አለ፣ አባቷ አቶ ሲራጅ፣ አንዴ ሲራክን አንዴ ሌላሠውን እያየ።

"አ-ባ-ቢ ..." ብላ ቁጣ ስትል፣ ስቶ ዝም አለ።

@OLDBOOOKSPDF

"በጣም ደስ ይላል ...ብራቮ ሙኒራ" አለ ሲራክ ።

ምስጢርና ንጹሕም አጠገብ ላጠገብ ተተምጠው የሞቱ ወሬ ይዘዋል ። ሳኝ ሁለቱን ሕፃናት ባንድ ላይ ታቅፎ ተራ በተራ እየኰረኰሪ እያሣቃቸው ከወደ ኀላ ይጓሚሉ ። እነርሱም ፊቱን በእጃቸው እየሸፈኑና እየኰረኰሩት ሲሣቁ፣ እጃቸውን በአፉ ለመነከስ አሰፈሰሉ፣ "አሀም... አሀም..." እያለ፣ ሲያስጮኻቸው የሴሎቹንም ቀልብ ሳቡ ።

ሲስተር ዘቢባ ከባቫገር ካለው ጠረጴዛ ላይ የተዘጋጀውን ምግብ ቃኘት ቃኘት አድርጋ፣ ወደ ተሰበሰቡት እንግዶች መጣችና፣ "ኦልሬዲ በጣም መሽቷል ፣ ሳይርባችሁም አይቀርም ... በሉ እንግዲህ ተነሡና እየበላን እንጫወት ። ከዛ በሊት ግን ይሄ ራት የተዘጋጀው አንድም እርሰ በርሰ በደንብ አንድንተዋወቅ ነው ። በተለይ ሳናስበው ተጀምሮ እያደገ የመጣውን የጳውሎስ ከሊኢክ ቡድናችንን ስማጠናከር ስትል፣ ሁሉም በደማቁ አጨበጨቡ ። "ደግሞ በጣም የምንወደው ዶክተር ሴላሠዬ እም...ም ባለቤቱም ንጹሕዬና ልጆቻቸው፣ አገራቸውን ሲያገለግሉ መኖተው አሁን መሄጃቸው ስለደረሰ፣ እነሱንም እመስግንን ለመሸኘትም ነው ።

"እኔ መቼም ስለ ዶክተር ሴላሠው ተናግሬም አልጨርስም ... ለሕመምተኞች ... ለተማሪዎችና ለሰታፍ ሁሉ ያሳየኽውን ምሳሌነትና ፍቅር፣ ምን ያህል እንደምናደንቅህና እንደምንወድህ እንድታውት እፈልጋለሁ ። የኛ ምኞት እሺ ጠቅልላቸሁ እንድትመጡና እንድትኖሩልን ነው" ስትል፣ አሁንም ሁሉም እየጮሁ አጨበጨቡ ። "በሉ እንግዲህ ከነንጹሕ እንጀምራለን ዶክተር አንተም ተነሥ ...እናንተ ጀምሩልን..." ብላ፣ አስነሥታቸው፣ ወደ እጅ መታጠቢያ ክፍሉ መራቻቸው ።

ምግቡን እየበሉ የተለያዩ ወሬዎችን በተናጠልና በእንድነት ሲጫወቱ ቀየ፣ ሴላሠው ከሲስተር ዘቢባ ልጅ ከሙኒራ ጋር የደመቀ ወሬ ይሂል ። ንጹሕና ምስጢር ደግሞ አንድ ጥግ ይዘው ብዙ እንደሚተዋወቁ ወሬያቸውን ቀጥለዋል ። ሲራክ ከመጣ ጀምሮ ከአቶ ሲራጅ ጋር የያዙትን ፖለቲካዊ ሙግት ቀጥለው ሞት ያለ ክርክር ውስኖ ገብተዋል ።

ሲስተር ዘቢባ እንዴ አንዱ ጋ ደግሞ ሴላው ጋ እየሄደች ጨዋታ አድማቂ ጅክር ሆና፣ እንዲበሉ ባናት ባናቱ ምግቡን ትጨምራለች ። የተዋጣለት ራት ነበር ። ምግቡ ጋብ ብሎ ትነሰስ ነገርና ጣፋጮች ሲቀርቡ፣ ሲስተር ዘቢባ እንደገና አጨበጨበችና፣ "እኔ ግን አንድ ጥያቄ አለኝ፣ በናንተም በኩል ተቀባይነት ካገኘ ... በሚብጨባ ትደግፉኛላችሁ" ስትል፣ የሁሉም ዓይኖች ወደሷ ተሰበሰቡ ።

"በመካከላችንበጣምጉበዝሙዚቀኛእንዳለምተናል ። እንደምታይትየሙቪታ መሣሪያው ደግሞ ተጫዋች እየጠበቀ ስንት ጊዜው ። በርግጥ ኳንድ በላይ ሙዚቀኖች እንዳሉ እናውታለን ። ግን ፒያኒስት ንጹሕ አንድ ሙዚቃ እንድትጫወትልን ለምን በሚብጨባ አንጋብዛትም" ስትል፣ ሁሉም እየሥሁ ሲያጨበጭቡ አፍሬ አጮንበች ። ሲስተር ዘቢባ አጠገቧ መጥታ እጇን ይዛ ወደ ፒያኖው ስትመስዳት ሚብጨባው ቀጠለ ። ቀስ እያለች ጀምራ እየደመቀ የሚሄድ ለስለስ ያለ ሙዚቃ ተጫወታ ስትጨርስ ሚብጨባው ቀለጠ ።

@OLDBOOOKSPDF

ሙኒራ አጠገቢ ቀማ አጨዋወቷን እያየች ስታዳምጥ ቀየችና፣ "ወይኔ ታድለሽ ... እንደዚህ አራፍ ሊጫወት ግንጉም አይቼ አላውቅም። በጣም ጉበዝ ነሽ" አለችና አቀፈቻት።

ለእናቷ የተረበውን ጭብጨባ የሰማችው ትንሿ አርሴማ እኔም ካልተጫወትኩ ብላ በትንንሽ ጣቶቿ አባቷ ያስተማራትን ሙዚቃ ባጭሩ ተጫወተች። ሁሉም በደማቁ ሲያጨበጭቡላት ሮጣ አባቷ ላይ ተጠመጠመች። "ጉበዝ የኔ ልጅ ... በጣም ጉበዝ" ብሎ፣ ግንባሯን ሳም ሲያደርጋት የበለጠ ፈነጠዘች።

ሲስተር ዘቢባም ብድግ አድርጋ ታቀፈቻትና፣ "የኔ ቀንጆ ማነው ያስተማረሽ? በጣም ግሩም ሙዚቃ ነው" አለቻት፣ በእንግሊዝኛ።

"አባባና እማሚ" ብላ፣ በደስታ እየተፍነከነከች ሲስተር ዘቢባን ግምጥ አድርጋ ሳመቻት። አጸፋውን ሰማ ስታወርዳት ሮጣ ወደ ሳንቶ ሄደች። ከዛ ቡና እየተቀዳ፣ ሁሉም ተስብሰበው የጋራ ወሬ ተጀመረ።

"በጣም በጣም ግሩም ራት ነው። መቼም ለማመስገን ታል የለንም ..." ሲል ሴላሙ፣ ሁሉም መስማማታቸውን በየራሳቸው ታል እከታተለው ገለጹ።

"ቢታችሁን በጣም ነው የወደድኩት፣ ታላት ከሚገልጸው በላይ ያምራል" ሲል ሲራክ፣ እቶ ሲራጅ ተበል አድርጎ፣

"ይኼ ሁሉ የዘቢባ ሥራ ነው ... ይሄው ሠላሳ አንድ ዓመታችን ከተጋባን። ሁል ቀን እንዳስገረመችኝ ነው። እዚህ ቤት ውስጥ የምታዩትም ሆነ ደጅ ያለው ሁሉ የሷ የእጅ ሥራ ነው። ሆስፒታል ለሚያውታት ነርስ ብቻ ትመስለዋለች። እንደሷ ዓይነት ሁለ ገብ የሆነ ሰው እኔ በበኩሌ አይቼም አላውቅም። አላህ እንዴት ቢወደኝ ነው እንደሷ ዓይነት ሚስት የሰጠኝ ብዬ ሁልጊዜ እደነቃለሁ" ሲል፣ እንደ ማፈር ብላ ተሽኮረመመችና፣

"እይ ሲራጅ አንተ መቼም በጣም ታበዛዋለህ ..." ስትል፣ ምስጢር አጠገቢ ያለችውን ሲስተር ዘቢባን እቅፍ አደረገቻት።

"ወይኔ ... በጣም ነው ደስ የምትሉት። ለኔ ከሁሉም ይልቅ ከዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላም እንደናንተ የሚዋደድና የሚከባበር ሰው መኖሩን ማየቱ ራሱ ካይምሮዬ በላይ ነው። በጣም ነው ደስ የምትሉት ... በውነት ... ታድላችሁ" አለች፣ ዓይኗ እምባ እያቀረረ።

ሲስተርም በተራዋ እቅፍ አድርጋት፣ "የኔ ቀንጆ ... ታንክ ዩ ..." አለች።

ለጥቂት ጊዜ ሁሉም ነገር ጸጥ አለ። ድንገት ከተፈጠረው ዝምታ በኋላ እቶ ሲራጅ፣ "ቀይ እኔ ምለው ታዲያ ለምን አንድ ነገር አትጀምሩም አብራችሁ? ዶክተሮች አላችሁ ... ነርስ አለ ... ሳይኮሎጂስት ... ሶሻል ወርከር ... መድሃኒትና የህክምና መገልገያ አስመጪ ብትፈልጉ እኔ አለሁ። ምን ያህል ሰው እኮ በናንተ ሙያ የሚረዳው አጥቶ እየተቸገረ እንዳለ ብታውቁ። ግን ቢያንስ አስቡበት። ይህን የመሰለ ወዳጅነት

@OLDBOOOKSPDF

ወደ ሥራ ቢቀየርና የሆነ እናንተን ሰብስቦ አንድ ላይ የሚቋጥር ሐሳብ ቢገኝ ምን ዓይነት ትልቅ ሥራ መሥራት እንደምትችሉ ይታየኛል" አለ ።

ሁሌም ዕድሎች በቀላሉ የሚታየውና የቢዝነስ ራእዮችና ሐሳቦች የማያልቁለው ነው ። ከተወሰኑ አመታት በፊት በትንሽ የጀመረው የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች አስመጪ ድርጅቱ ዛሬ በሚሊዮን የሚቋጠር ብር የሚያንቀሳቅስ ሆኗል ።

"ጥሩ ሐሳብ ነው ፣ ግን መጀመሪያ ዶክተር ሌላና ንጹሕዬ ... ምን ያስቢሉኔ ጥያቄው" አለች ፣ ሲስተር ዘቢባ ።

ሌላሠው ወደ ንጹሕ ዞር አለና ፣ "ዋና አለቃዋ እሳቸው ናቸው እንግዲህ ..." ብሎ ፣ እያያት ሲሥቅ ፣

"ምን ወደኔ ትገፋለህ ... ራስህ ነህ እንጂ ..." አለች ፣ ባይኗ ቁጣ ብላ ።

"ሐሳቡ ጥሩ ነው ። እስኪ ዛሬ ሐሳቡ ተወልዷል ... ትንሽ እንተኛበት" አለ ፣ ነገሩን ለማርገብ የሚሰቱን ዓይን አንብቦ ። ነገሩን ይበልጥ እንዲያስቡበት የፈለገ አቶ ሲራጅ ፣

"ካሜሪካ ጋር ሲነጻጸር በርግጥ እዚህ አገር ብዙ የማይመቹ ነገር ሊኖር ይችላል ... ግን ደግሞ እናንተ እዚህ ብትሠሩ የምትፈጥሩት ልዩነት ቀላል አይመስለኝም ፣ ትንሽ ከተሠራ ደግሞ ምንም ያልተሠራበት ሀገር ስለሆነ ፣ እንደ ቢዝነስ ራሱ በጣም ትልቅ ዕድል ያለው ነገር ይመስለኛል" አለና ፣ እጁ ላይ የቀረችውን ኩኪስ ጮረሰ ።

በጉዳዩላይ ትንሽ ካወሩና ከተጨዋወቱበኋላ ሲስተር ዘቢባ ፣ "ታዲያ የመሄጃው ቀን ተቁረጠ እንዴ?" አለች ።

"እኔና ልጆቹ የዛሬ ሳምንት አካባቢ ነው ለመሄድ ያቀድነው ። ሌላ ግን እንናንደ መጪረስ ያለበት ነገር ስላለ ምናልባት እንድ ወር ለመጪመር እያሰበ ነው ።"

"ውይ ብቻሽን ሁለት ልጆች ይዘሽ አይከብድም ያን ሁሉ መንገድ" አለች ምስጢር ፣ የታቀፈችውን ዲንላን ግንባሩ ላይ ሳም እያደረገች ።

ንጹሕም ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን ስለገለጸ ፣ "ምን ይደረግእንግዲህ የልጆቹም ትምህርት ቤትና የኔም ሥራ ስላለ መሄዱ ግድነው" አለች ፣ በዚህ መሃል ልጆቹም እንቅልፋቸው እየመጣ ስለ ሄደ ፣ ሌላሠው ሰዓቱ ምሽት ሰዓት ከሩብ መሆኑን አይቶ ፣ "ሲስተርዬ እንሂድ መሰል ... ልጆቹም እንቅልፋቸው ሳይመጣ አልቀረም ። እኛ ብዙ ብንቀይም ደስ ባለን ነበር" አለ ፣ አርሲማን ከሳንቲ ተቀብሎ እየታቀፉት ።

ከሙኒራ ጋር በሌላ ጊዜ በደንብ ሊገናኙ ተነጋገረው ፣ እንድትደውልለትስልክ ሰጣት ። ዲንሳም ምስጢር ላይ ተኝቶ ስለነበር እንደ ታቀፈችው እነ ሌላሠው ሾልኮ ውስጥ አስገብታላቸው ፣ ከንጹሕ ጋር ከተቻለ ከመሄዷ በፊት ሊገናኙ ተስማምተው ስልክ ተለዋወጡ ።

@OLDBOOOKSPDF

ሲራክ ያለ ወትሮው ብዙም ሳያወራ ዝም ብሎ ነበር ያመሸው። ነገሩን ልብ ያለችው ሲስተር ዘቢባ ከሁሉም ቀድሞ ተሰናብቶ ሲወጣ፣ "ዶክተር ሲራክ፣ ምነው ዛሬ ድምፅህም አልተሰማም። እኔም ከሲራጅ ጋር ጨዋታ የያዛችሁ መሰሎኝ ዝም አልኩህ። ለመሆኑ ራት በደንብ በላህ? ትንሽ አገልግል ነገር ልሰርልህ ባክህ?" አለች፣ ፃይን ፃይኑን እያየች።

"እም ሲስተርዬ፣ በደንብ ነው የበላሁት። ግሩም እራት ነበር። አገልግሉ ይትርብኝ ግዴለሽም። ትንሽ ደክሞኸም ስላለኝ ነው እንጂ፣ በጣም ነው ኢንጆይ ያደርኩት። ከጋሽ ሲራጅም ጋር ብዙ ተጫወትን እኮ" አለ፣ ጫኪቱን እያስተካከለና የግዱን ፈገግ ለማለት እየሞከረ።

የምስጢር ከሳንቾ ጋር ባንዴ ይህን ያህል መቀራረብ ከንክኖታል። ሰላም ካለችው በኋላ ዞር ብላም እንኳን ስላላየችው፣ ነገሩን አውቃ እንደምታደርገው ነው የወሰደው። 'እኔን ለማስቀናት ሊሆን ይችላል' የሚል ሐሳብ ልቡን አውኮታል። 'ምኗ ነኝና ነው ልታስቀናኝ የምትሞክረው?' ብሎ ሐሳቡን መለስ ለማድረግ ቢሞክርም፣ ውስጡ የተፈጠረውን ቀዝቃዛ ንዴት፣ ሰርጉ ከገባበት የልቡ ንቃቃት ውስጥ ጠራርጎ ሊያወጣው አልቻለም። በተለይ መኖሩን እንኳ ከቁም ነገርም የቁጠረችው ስላልመሰለው፣ ልቡ ከፊል በንዴት ከፊል በቅናት ሲጨስ ተሰማው።

@OLDBOOOKSPDF

12

ሲራክ ከሲስተር ዘቢባ ቤት ከወጣ በኋላ፣ ከአያት ሰፈር እስከ ካዛንቺስ ድረስ ያለው መንገድ ባዶ ስለ ነበር ፍጥነቱን ጨምሮ ከነፈ። ከውስጡ ያለውን ሚሜታ ለማርገብ፣ መስኮቶቹን አውርዶ ሙዚቃውን ከፍ አድርጎ ለቀቀው። አልፎ አልፎ መሪውን በእጆቹ ይመታና፣ 'ሺት ... መምጣት አልነበረብህም ሲራክ ... ቀይ እኔ አይደለሁም ብቻ' ይልና ደግሞ ተመልሶ ከት ብሎ በራሱ ይሥቃል። ደግሞ እንደገና "እና፣ ምን እንድታደርግህ ፈልገህ ነው? ሲራክዬ የኔ ፍቅር ብላ ዓይን ዓይንህን እያየች አጠገብህ ትቀመጥልህ?' ይልና ራሱ ላይ እንዳጠፋ የቤት አሽከር ይጮህበታል።

መገናኛ አካባቢ ሲደርስ፣ ባዶ ቤት ገብቶ ከመደበር በዚያው ወዴ ክለብ ሄዶ ሲያመሽ አሰበና መልሶ ተወው። ጎሊናን ወይንም ወዳሴን ደውሎ ካንዳቸው ጋር ለመቆየት አሰበ። ሰዓቱን ሲያይ የመሸ መስለው። ሌላ ምንም ሐሳብ ስላልመጣለት ገዛም ብሎ ወዴ ቤቱ መንዳቱን ቀጠለ። ግቢ ሲደርስ መኪናውን እቀመና ከኋላ ወንበር ላይ ኮቱንና ቀን የጀመረውን ጋዜጣ ይዞ ወደ አፓርታማው አመራ። የሚኖርበት አፓርትመንት ከካዛንቺስ ወደ አራት ኪሎ መታጠፊያ ላይ ይገኛል። ጨለማና ጸናታ እዋጠው ባዶ ቤት ሲገባ መጮህ አማረው። መብራቶቹን አበራርቶ ቲቪውን ከፈተና ሶፋው ላይ እንዘጭ ብሎ ተቀመጠ።

ቲቪውን በግማሽ ልቡ እያየ ማምሻውን ሁሉ ተዘግቶ የቀየውን ስልክ ከፈተው፣ ብዙ የጽሑፍ መልእክቶች ተግተልትለው ወጡ። አብዛኞቹ ከጎሊናና ከወዳሴ የተላኩ ናቸው። ጎሊና ደግ፣ የዋህና ለስላሳ ልጅ ናት። ሲራክ ከፍቅረኝነት ይልቅ በሕይወት የማያውቀውን የእናት ፍቅር ይዛ የመጣችለት ተንከባካቢው ስለምትመስለው፣ እንድትርቀው አይፈልግም። ወደ ሁለት ዓመት ያህል አብረው ቢሆኑም፣ ጓደኝነታቸው ሲገል ሲቀዘቅዝ፣ አቅጣጫና መድረሻው ለሁለቱም እንቶትልሽ ሆኗል። ሲራክ ሙሉ ተስፋዋን የጣለችበትና ሁለንተናዋን የሰጠችለት የመጀመሪያ ፍቅሯ ነው። ከእርሱ በቀር በዓለም ላይ ሌላ ወንድ ያለም አይመስላትም።

@OLDBOOOKSPDF

ውጻሌ በታመቀ የሕገ አግካሪ ቢሮ ውስጥ ጠበቃ ሆና የምትሠራ በአንድ የሽኝት ፓርቲላይ የተዋወቃት ወጣት ናት ። ከጎሲና ጋር ተጋጭተው ለሦስት ወር በተኮራረፉበት ወቅት ነበር ከውጻሌ ጋር ተቀራርበው ወዳጅ የሆኑት ። ከጎሲና ጋር መልሰው ከታረቁ ወዲህ ውስቱን አቻችሎና አራርቆ መኖሩ ራሱ ከባድ ሥራ ሆኖበታል ።

በዚህ መሃል ምስጢር ጳውሎስ ሆስፒታል ለተግባር ሥልጠና መጥታ ካያት ወዲህ ደግሞ ልቡ ወደ እርሷ ሸፍቷል ። የምታሳየው ቸልታ የንቀት ስለሚመስለው እልህ ውስጥ ገብቷል ። ሰብቻው ሲሆን ብዙ ያቅድ ይፎክርና አጠገቧ ሲደርስ ፣ ለምን ጊታውን እንዳየ ውሻ ጭራውን እንደሚቁላ አይገባውም ። ነገሩ የሚፈጥርበትን ብስጭት ለማርገብ ለራሱ የሚያቀርበው ምክንያት ፣ ለምስጢር ያለው ስሜት የእውነተኛ ፍቅር ምልክት ስለሆነ የርሱ እጣ ፋንታ እሷ መሆኗን ለራሱ እየተናገረ ውስጡን በተስፋ ይሞላል ።

ፒሾግውን ቀይሮ ከፍራኝ ውስጥ ያላበው ቢራ አውጥቶ ሲጉነጭ ውስጡ ረገብ ያለለት መሰለው ። አዛው ሶፋ ላይ ጋደም እንዳለ ካጠገቡ ያለውን ጋዜጣ እንደነገሩ ማገላበጥ ጀመረ ። ዓይነ ሥጋው ጋዜጣው ላይ ያፍጥጥ እንጂ ልቦናው ግን አሁንም ጥቁር ቀሚስና ብሩህ መሃ ለማያዊ ሻኬት ለብሳ ከሳንቾ ጋር እየተፍለቀለቀች ስትሥት የነበረችውን ምስጢርን ደጋግሞ እመጣበት ። "ኡ ፍፍፍፍ ..." ብሎ ምስሏን ከራሱ ለማስወገድ ይመስል ፊቱን በቀኝ እጁ ከላይ እስከ ታች ሞገለቀና በትናት የተቃጠለ ጪራው ላይ ተዝታባ ቢራውን ችለበበት ። ጋዜጣውን ከራቱ ወርወር አድርጎ ቲቪው ላይ ላይ አፍጥጦ ልቡ እዛና እዚህ ሲረግጥ ቀየ ።

ብዙም ሳይቀይ ስልኩ ጮኸ ። ጎሲና ነበረች ። ትንሽ አመንትቶ አነሣው ። "ሃይ ሂሉ ... አም ሶሪይ ... እንድ ሰብስባ ስለ ነበረኝ ስልኬን ዘግቼው ነበር ... የመሸ ስለ መስልኝ ነገ ልደውልልሽ ነበርኮ ..." ብሎ ፣ ቀበጣጠረ ። በመደወሏ ውስጡ ደስ ብሎታል ።

"እንዴ እኔ ኮ በጭንቀት ልፈነጻ ነበር ። ትናንትም እኮ እደውላለሁ ብለህ ቴክስት አድርገህ በዛው ጠፋህ ... በደህና ነው? ዛሬ ደግሞ እከሰቱ ጋ እራት እንሂዳለን ተባብለን አልነበረም? ... ረሳኸው እንዴ?" አለች ፣ ናፍቃትና ጭንቀትን በሚያሳይ ድምፅ ።

"ኦህ ማይ ጋድ ... በናትሽ በጣም ይቅርታ ... ኮምፕሊትሊይ ነው የረሳሁት ። ለምኑን በታ በጣም ቢዚ ሆኜ ቀልቤ ሁሉ ጠፍቷል ። በጣም ብዙ ነገር እየረሳሁ ተቸገራያለሁ ። እሺ የት ነሽ አሁን?" አለ ፣ ትንሽ ጸጸት እየተሰማው ።

"እኔማ አሁን ካክስቱ ቤት ወጥቼ ወደ ቤት እየሄድኩ ፣ ካዘንቺስ አካባቢ ነኝ ። ድንገት ቤት ገብተህ ከሆነ ብዬ በዛው ላልፍ ነበር ። ሰላም ብለውሃል ደግሞ ... ያው በሥራ አላብቤልሃለሁ ። መኪና ሰላልያዝኩ ከሣራ ጋር ነኝ ። ትዝ ትልሃለች ከገዜ ናት?"

"ኦህ ያ ... ደህና ናት?" አለ ፣ በትክክል ባያስታውሳትም ። "በታ እከሳለሁ የኔ ፍትር ... እዚህ አካባቢ ከሆንሽማ ጥሩ ነው ፣ ጮራ በይ ። እኔም ገና መግባቴ ነው ። እንዲያውም ወደ ቤትም ለምን እኔ አላደርስሽም?" አለ ፣ ድብርቱ ሁሉ ባንዴ እየጠፋ ።

@OLDBOOOKSPDF

"መጣሁ በታ ... አምስት ደቂቃም አይወስድብኝ" አለች፣ እየተናነቀባቀት።

ጎሊና በአንድ ትልቅ የውጭ ድርጅት ውስጥ አካውንታት ናት። ለመላጀ ብቸኛ ልጅ ናት። ከሳሙን እስከ ዙሽና ያለው ዕቃ የተሟላው በጎሊና እገዛ ነው። በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ እየመጣች ፍሪጁን ሞልታ፣ ቤቱን መልክ መልክ አስይዛለት መሄድ ደስ ይላታል። ሲራዘ ደግነቷንና የዋህነቷን ቢወደውም 'ፕልት የሆነ ፍልስፍናና የሕይወት አተያይ የላትም ... አግብቶ ከመውለድ የዘለለ የሕይወት ዓላማ አይታያትም' ብሎ ስለሚያስብ ትንሽ አብረው ሲቆዩ ስልችት ይለዋል። ለርሱ ደግሞ አግብቶ መውለድ እስራት እንጂ የሕይወት ጥሪ ወይም ትልት ተግባር መሰሉ አይታየውም።

ውጸቤ ይህንን ሁሉ ከሚያስበው በላይ የምታሚላ መስላ ትታየዋለች፣ ተከራካሪ፣ አገባቢ፣ ማንኛውም ወቅታዊ የሆነ የዓለም ሁኔታ የሚያመልጣትና ስለ ብዙ ነገር ከማንም ጋር ማውራት የምትችል ልጅ ናት። ማሽነፍ በሐሳብ ብቻ ነው ብላ ስለምታምን ተከራክረው ሳይጣሉ የሚለያዩበት ጊዜ ጥቂት ነው። ሁለቱም እልከኛና መበለጥ የማይወዱ ስለሆኑ አንድ ቤት ውስጥ ለመኖር እንደማይችሉ ልቡ ያውቀዋል። ተርካካሪ ጓደኛ እንጂ ተንከባካቢ ሚስት ልትሆነኝ አትችልም ብሎ ስለሚፈራ ሩቅ መንገድ አብረው ሲሄዱ አይታየውም።

ጎሊና ደርሳ በሩን ሲከፍትላት ፊቷ ሁሉ ጥርስ በጥርስ ሆኖ የያዘችውን ዕቃ መሬቱ ላይ አስቀምጣ ተጠመጠመችበት። እንቅ አድርጋ ሳመችው፣ "እንተ ግን ጨካኝ ነህ ... ሰው ይናፍቀኛል እንኳን አትልም? ሲሩ ግን ልክ አይደለህም ..." አለችው፣ እንደ ማኩረፍ ብላ።

"ሂሉ ሙች፣ ስለማላስብ እኮ አይደለም። ያው ምን ታውቂው የለ ... እኛ ወንዶች ባንዴ ካንድ በላይ ነገር ማሰብም ማድረግም አልፈጠረብንም። ሄይ፣ ደግሞ... ዩሱክ ገርጂያስ ... ኧረ ኧረ ... በጣም ነው ያማረብሽ" ብሎ፣ እንደገና እቅፍ አደረጋት። "ደግሞ ይሄ ሁሉ የያዝሽው ጓዝ ምንድነው? ማራ ሄደች እንዴ?" አለ፣ በፈስታል ያለውን ዕቃ ከመሬት እያነሣ።

"እም ... ይመሽብኛል ብላ ሄደች። ሰላም ብላሃለች። ድንገት እቤት ካገኘሁህ ብዬ ካከሰቴ ቤት አገልግል አላሰርኩልህ። ብታይ በጣም አሪፍ ድግስ ነበር። ቶሌ አምጣው ፍሪጁ ውስጥ ላድርግልህ። ትንሽ ትቀምሳለህ?" አለችና፣ ጃኬትና ያንገት ልብሷን ሶፋው ላይ ጣል አድርጋ እንደ ልማዷ ፍሪጁንና ሳሎኑን ማስተካከል ጀመረች።

"ውይ በትርብ ነው ራት የበላሁት ሂሉ" አለና፣ መደጓዳ ገብቶ የሻይ ውኃ ጣደና ለራሱ ሌላ ቢራ ይዞ መጣ። "ቢራ ለምን አትሞክሪም? ግሪን ቢራ ነው ... አንድ እኮ ምንም አይልሽም ... የሚከሊኮው ቅዱሱ ነው።"

"ውይ ጀመረህ ደግሞ ... በናትህ ያበቃሃል እንተም ... ስንተኛህ ነው ግን" አለች። ብላው ብላው ልታቆመው ስላልቻለች ተሰላቹ ቁጭ ጣለች።

@OLDBOOOKSPDF

"ግና መገባቱ እኮ ነው ... በታ በጣም ተታጥዬ ስለነበር አንድ ለጥም ... ይችኛዋ ደግሞ ለጨዋታ ..." አለ ። ሶፋው ላይ ከአጠገቧ ቁጭ አለና ጉንጯ ላይ ሳም አደረጋት ። የሆነ ያልሆነውን እያወራና እየተላፉ ትንሽ ቀዩ ። እጆቹን በወገቧ ዙሪያ አድርጎ ወደ እርሱ ሰቦ ጠበቅ አድርጎ ሲስማት ፣ እርሷም እጆቿን በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥማ እጸፋውን ሳትስስት መለሰችለት ።

ትንፋሻቸው እየጋለ ሲሄድ ለስለስ ባለ ድምፅ ፣ "በናትሽ ካሁን በኋላ በጣም መሽቷል ... ለምን እዚሁ አታድሪም? ...ፐሊስ ..." አለ ፣ መልሱ ምን እንደሆን ቢያውቀውም ። ደረቱ ላይ ልጥፍ እንዳለች ጸጉሯን ደጋግሞ እየሳመ ።

ካንገቷ ቀና ብላ ዓይን ዓይኑን እያየች ፣ "እንተ...!" አለች ፣ እጇን በሸሚዙ ቁልፎች መሃል አስገብታ ደረቱ ላይ እያንሸራሸረችና ቀንጠጥ እያደረገችው ።

"ምና...ለበት? በታ መሽ ጓደኞቹ ጋ ነኝ ምናምን በያቸው" አለና ፣ የአፍንጫዋን ጫፍ ከዛም ዓይኖቿን ሳም ሳም አደረጋቸው ። እንደ ምንም ከእቅፉ ውስጥ ወጥታ ብድግ አለች ። ጸጉሯን አስተካክለችና ሰዓቷን አየት አደረገች ።

"የምርህን ነው እንዴ አንተ ልጅ ... እንዲያውም በጣም መሽቷል አሁን ልሂድ ፣ በል ሽኘኝ" ብላ ፣ ቁልቁል ስታየው ዓይኖቹን እንዴ ጨፈነ ዝም አለ ። ልብሷን አስተካክለችና ጃኬቷን ደርባ እንደገና አጠገቡ ቁጭ አለች ።

"አይ ፕሮሚስ ... ሰሞኑን በሰፈው እንጫወታለን ... ዛሬ ግን መሄድ አለብኝ ። ደበረህ እንዴ?" አለች ፣ ትንሽ ጨነቅ እያላትና ፊቱን ወደ እርሷ ልታዞር እየሞከረች ።

"ዛት ኢዝ ፋይን ... ኢት ኢዝ ኦኬይ ... በታ እንዳይመሽብሽ እንግዲያውስ ..." ብሎ ፣ ብድግ አለ ። የቀረችውን ቢራ ጨለጠና ጂንስና ቲሸርት ቀየረ ። የቀዳ ጃኬቱን ጣል አደረገና ሽቶውን ላመል ያህል ነስነስ አደረጎ "እንንቀሣቀስ?" ሲላት ፣

"ለሽኝት ነው ለአዳር? ዘንጥክሳ?" ስትለው ፣

"የሚሆነው አይታወቅም ፣ የሚጠልፈን ከተገኘ ... የእኩለ ሌሊት ሲሳይ" አለና ሣቀ ።

"ደረቅ ነገር እኮ ነህ ... ይሄን ሽቶ እንዴት እንደምወደው ... ውይ...ይ..." ብላ ፣ ደረቱ ላይ ልጥፍ አለች ። እሷን ቁራ አካባቢ ካለው የወላጆቿ ቤት ጥሎ ፣ ወሎ ሰፈር አካባቢ ሲደርስ ሰዓቱን ሲያይ አምስት ሰዓት ከሩብ ይላል ። ከመንገዱ ዳር ሰዎች ወጣ ገባ የሚሉበት ላውንጅ ባር አይቶ ፣ መኪናውን አቁሞ ገባ ። በሙዚቃና በመጠጥ የተሰጠው ቤት በደብዛዛ ተለዋዋጭ ባለ ቀስም ብርሃኖች ተሞልቶ ፣ ይምሽ ይንጋ እያስታወቅም ። አይኖቹን ጨፈን ከፈት አድርጎ ካንድ ጥግ አካባቢ ካገኘው ባዶ ወንበር ላይ ተቀመጠ ።

ያዘዘውን ቀዝቃዛ ቢራ ሁለት ጊዜ እንደተጮነጨ ፣ ከፊት ለፊቱ ካለው ጠረጴዛ ላይ ከተቀመጡ ልጆች መሃል አንዲት ወጣት ወዳለበት መጥታ ፣ "ከመተከዝ መደነስ አይሻልም ብለህ ነው?" ብላ ፣ ለዳንስ ስትጋብዘው ሳይግደረደር ተነሳ ። የለበሰችው ጥቁር ተሚሰና ሰማያዊ ጃኬት መሆኑን ያስተዋለው ተመልሰው ሲቀመጡ ነበር ።

@OLDBOOOKSPDF

"ህም ... ይገርማል" ሲል

"ምኑ...?" አለችው ፈጠን ብላ ።

"አለባበስሽ በጣም ያምራል" ሲላት ፣

"እንተ ግን ከቤት ርርፈህ የወጣህ የሃይ ስኩል ተማሪ ነው የምትመስለው፣ ስትለው ፣ ሞንቅላቱን ወዘወዘና ፣

"እንዴት አወቅሽ?" አላት ሳት ብሎ ።

"ልብስህ ... ቢራ አጠጣጥህ ... አደናነስህ ... ወዘወዙ ነገር ትመስላለህ" ብላ በሹፈት አይነት ሳቀችበት ።

"እንቺ! በጣም ... ደፋር ቢጤ ነሽ" ብሎ ፣ ቢራውን ወደ አርቧ እያስጠጋ ፣ "እሺ የተከበሩ መምህርት ... ተማሪዎችዎ ከኮሌጅ የተመረቁ ሥልጡን ከተሚ እንዲመስሉ፣ የቢራ አጠጣጥ ያስተምሯቸው" አለ ፣ ድምጹን እንደ ራድዮ ትምህርት አደርጉ፣ ቢራውን ወደሱ መልሳ ገፋችው ። ከኪሱ ውስጥ ሲጋራ አውጥቶ ሊለኩስ መለኮሻውን ሲፈልግ ፣ እንደገና ከት ብላ ስትስቅ ፣ ምነው በሚል አይነት የሲጋራውን ፓኮ እንደያዘ ቀና ብሎ አያት ።

"ቀይ ..." ብላ ፣ ከቦርሳዋ ውስጥ ፓኮ ሲጋራ አወጣችና "ይሄንን ሞክረው ..." ብላ ስጠችውና የያዘውን ኒያላ ተቀብላ ጠረጴዛው ላይ አስተመጠችው ። ጠጋ አደርጎ ሲያነበው 'ፊሊፕ ሞሪስ' ይላል ። ሳት ብሎ ከውስጡ አንዲት ሲጋራ አወጣና መለኮሻ ፍለጋ ኪሱ ውስጥ ሲገባ ፣ እሳቱን ከፊቱ ገጭ አደረገችለት ።

"ታንክ ዩ ... ምን ... ለነርሱ ነው የምትሰሪው? ይሄም ኒኮቲን ያም ኒኮቲን... ምንድነው ልዩነቱ?" አላት ። የለኮሰውን ሲጋራ ፊቷ ላይ አቦንነውና የሲጋራውን ፓኮ መለሰላት ።

"እይ ሊጠፉ የተቃረቡ የዱር አራዊቶቻችንን ከምታጨስ ብዬ ነው" ብላ ፣ ሞሱን በእጇ ከፊቷ ላይ አራገበች ፈዘዝ ፈገግታ እያሳየችው ።

"ሆ ሆ ... ምን ልጋብዝሽ?" አለ ፣ እሱም ፈገግ ብሎ ። ነገረ ሥራዋ ደስ ብሎታል ፣

"እኔንኛ ... ለጊዜው ቶኒክ ነገር ..." ስትለው ፣ የባስ ግራ ገባችው ። ከትንሿ መጠጣቷን አውቋል ። ትንሽ እንዳወሩ ካጠገባቸው የነበሩ ብዙ ጐረምሶች መኻከል ብጥብጥ ተነስቶ ሜዳው በዛ ።

"ቦታ ብንቀይርስ?" ሲላት ትክሻዋን ሰበቅ አድርጋ ፣

"ደስ እንዳለህ ... ያው አውቀሃል ... አይደል?" አለችው ፈገግ ብላ ።

"ያ ያ ..." ብሎ ፣ ተያይዘው ወጡ ። ግልጥ ነፍልስዋገን መኪናው ውስጥ ገብተው ፍጥነቱን ጨምሮ እየነዳ ፣ "እሺ ... ታዲያስ ... ሥራ እንዴት ነው?" አላት ፣ ዙር ብሎ በጨረፍታ እየት እያደረጋት ። ለመኪናው ደስገጭሳት ሰፊ ሞስ ማውጫ የሚፈጥረው

@OLDBOOOKSPDF

ነጮድጓዳማ ድምፅና አካባቢውን ሁሉ በነሜ የብርሃን ጸዳል የሚሞላ መብራቷ በውስጡ ጥንካሬና ጉልበትን ይሰጠዋል ።

"ሥራ ምን ይሆናል ብለህ ነው ... ሠሪ ካልደከመውና አሰሪው ካልደኸየ በቀር" ብላ፣ ፈገግ አለች ። "ይቅርታ ... ቅድም የሃይ ስኩል ተማሪ ትመስላለህ ስላልኩህ" ስትለው፣ ሣቅ አለና ፣

"ተገኝቶ ነው" ሲላት ፣ እሷም ሳቀች ።

"መኪናህን በጣም ነው የወደድኳት"

"እኔንስ?" አለ ፣ ሙዚቃውን እየቀየረው ።

"ግና ፀባይህ ታይቶ ነዋ ... እት ሲሰት ... በጣም አሪፍ ኮሎኝ ነው የተቀባኸው" ስትለው፣ ዞር ብሎ አያትና ፈገግ አለ ።

"ግን ለሆነ ሚሽን የተጣደፍክ ትመስላለህ" አለች ፣ ሞልቀት ባለ ድምፅ ።

"ምን ሚሽን አለ ብለሽ ነው ... ሽሽት ነው ። የምሬን ነው ... አለባበስሽ ምርጥ ነው ... ተመችቶኛል" ብሎ ፣ በእጹ ቂኗን መታ እደረገና ፣ "ትንሽ ከለብ መቀየት እፈልጋለሁ ... ራት ነገር መብላት ትፈልጊያለሽ?" አለ ፣ ፍጥነቱን ቀነስ እያደረገ ።

"በቅርብ ነው የቀማምስኩት ... አሁን ምንም አላሰኘኝም ። ታንክ ዩ ግን" አለችው ። ቦታ መረጡና የሙዚቃ ማጫወቻውን ድም-ደላቂ 'ሳብዉፈር' እስክ መጨረሻ ለቅቀት በባዶው አስፋልት ላይ በረሩ ።

"ሲራክ እባላለሁ ... ያንቺስ?" አላት ፣ ከሙዚቃው ጋራ ባንገቱ ለመደነስ እየሞከረ ።

እሷም ከሙዚቃው ምት ጋር ቂንቅላቷን እያወዛወዘች ፣ "ሉሲ" ስትለው ፣ ፊቱን ወደሷ አዞረ ።

"ካም'ኦን ... ባልጠፋ ስም የስንት ሚልዮን ዓመት አሮጊት ዐፅም ምን ያደርግልሻል? ... ሌላ ሞክሪ ... አንቺን የመሰለች ቶንሺት ሉሲ ልትሆን አትችልም" ሲላት ከሙዚቃው ጋር የበለጠ እየተወዛወዘች ፣

"እ-ና-ቱ-ን- ሉሲ ነው" አለች ፣ ግድም ሳይሰጣት ድምጿን እየነተተች ።

"ወይ ጉ—ድ ... ሌላ ሞክሪ ስልሽ ... አለበለዚያ ... እኔ ሻል ያለ ስም ላወጣልሽ ነው ። ሉሲ ብሎ ስም አፍ ላይም ይቀፋል ። በናትሽ ... ሙዚየም ያለሁ መሰለኝ" ሲል ሣቋን ለቀቀችው ።

"እሰኪ ሞክር ..."

"በቃ 'ሚስጥር' ብዬሻለሁ መብቱ ከተሰጠኝ ... 'ሚስጥር' እንዴት ነው?"

"ይደብራል" ስትለው ያልጠበቀው ስለ ነበር ዞር ብሎ ፣

@OLDBOOOKSPDF

"ለምን?" አላት በመገረም እያያት ።

" ሚስጥር አልወድም ..."

"ኡሁሁ ...ሁ፣ እኔ ግን ሳይሽ ... ስምሽም ፣ ኑሮሽም ፣ ሁለመናሽ ሚስጥር ነው የሚመስለው ። ሰው የሆነውን የሚጠላ ... ላልሆነው የሚንጠራራ አሰቸጋሪ እንስሳ ነው ያላሉ ሳይንስ ያልተማሩ የባህል ምሁራን ..." አለ ፣ ሙዚቃውን ቀነስ እያደረገ፣

"ጀማሪ ሳይኮሎጂስት ነገር ነህ መሰለኝ ። እሰኪ መርምረኝ በናትህ" ስትለው በውስጡ 'ይቺን ይወጻል ሲራክ' አለና ዝት ብሎ ሣቀ ።

"ለምርመራውም ለምንም እኮ መጀመሪያ በስሙ ላይ መስማማት ያስፈልጋል፣ ወይ ሚስጥር ሁኚ ወይ ደግሞ ... ሚስጥራዊ ስምሽን ንገሪኝ ... ሱሲ ግን አትበይኝ ዘፈን ነገር ይመስለኛል ... የሆነ የማንም ነሥጥባ ሰካራም አርክዮሎጂስት ያወጣው ስም ..." ብሎ ፣ ለራሱም ያልገባውን ነገር ቀበጣጠረ ።

"እሺ ደስ ይበልህ ... 'ሚስጥር' ሆኜልሃለሁ ለጊዜው ... አንተስ ሲራክ የሌሊት ስምህ ነው?" አለች ፣ በውስጧ 'ይቺ ጩጩ የዋሣ አይደለችም ... ወይ የመጽሐፍ መሸጎጫ ናት ወይ የምር የገባት ሳትሆን አትቀርም' ብላ እያሰበች ።

"ሲራክ ... የዘወትር ስሜ ነው ... እኔ ቀንና ሌሊት አልቀያየርም ... ሲራክ ሁሌም ሲራክ ነው" ሲላት ፣ ቀጭን ሣቋን ለቀቀችው ።

"አቤት አቤት ... አልተስማም ... ይሄኔ ...ገረመው ... ወርቅነህ ... ወይ ደጋ ምናምን ይሆናል እውነተኛው ስምህ ። ሲያዩህ ምንም ሲራክ አትመስልም" ስትለው፣ የመንጃ ፈቃዱን አውጥቶ ለጣት ። ገርሟት አየት እደረገችውና ተቀበለችው።

"ዶክተር ሲራክ ...አይላ-ይክኢት ...ዶክተር ለመሆን ጩጩ ነገር ትመስላለህ፣ የምን ዶክተር ነህ ግን? ... በናትህ የከብት እንዳትለኝ ። ወይስ ያባትህን ዱክትና ነው ከመኪናቸው ጋር ሌሊት ሌሊት ሲተኙልህ ሰርቀሃቸው ይዘህ የምትዞረው" ብላ ስትሥቅበት ፣ መንጃ ፈቃዱን ተቀበላትና ትከሻዋ ላይ ላመል ያህል በካርዱ ፆታ እደረጋትና ኪሱ ውስጥ መለሰው ።

"ብራቮ ሚስጥር እንዴት አወቅሽ?" ብሎ በፉጨት ከሙዚቃው ጋር ለግጨየ ሞከሮ ሲያቅተው ፣ "ዱክትርናውስ የራሱ ነው ። ከጠዋት እስከ ማታ በሁለት እጁ የሚሄዱ ከብቶች ሳክም ነው የምውለው ። "

"ዶሮ ስታባርር ነዋ የምትውለው ። የዶሮም ሐኪም እንዳለ አላውቅም ነበር፣ የምር የዶሮ ዶክተር ነህ?"

"ብሆን ይሻለኝ ነበር ... የኛን ሰው ከማከም እነሱን ማከም ሳይሻል አይቀርም፣ ከብዙ ሰው እኩ ዶሮቹ ይሻላሉ ። ሰው ማለት ታክሞ የማይድን በሽታውን በመደበቅ የተካነ ሥልጡን ከብት ነው ። ሁለት እግር ያለው ከብት ደግሞ ዶሮ ብቻ አይደለም፣ ሁሉንም ነገር አታምርር እሺ። ዶክተር ነህ?"

@GEDBOOKS

ከዘለቡ ፊት ለፊት ማቀሚያ እየፈለገ፣ "የሰው ... የሰው ሚንትላት ...እንዳንቺ ነክ ያደረጋቸውን ሰዎች ሳይ ነው የምውለው" አሰና፣ መኪናውን አቆመ። "ስለዚህ ሚስጥር በሚለው ተስማማንን?" አለ፣ ለመውረድ በሩን እየከፈተ፣

"ይሁንልህ ... እና፣ የአብድ ሐኪም ነኝ ነው የምትለኝ? እኔ ግን እናንተም ጤነኛ እትመስሉኝም። እዘህቱ ለብዙ ጊዜ አማኑኤል ተኝታ ነበር።" ያደረገችው ረጅም ታኮ ያለው ሚማ እንዳያደናቅፋት ከንዱን ይዛው ወደ ውስጥ ገቡ። ከአንድ ጥግ አካባቢ ቁጭ ብለው የሚጠጡትን አዘው ትንሽ በነገር ሲቀራቀሱ ቀዩ። ከዛም መጠጡን በላይ በላዩ እየጨመሩ፣ ሲጨፍሩ ቀይተው ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ እየተወለካከሱ ተደጋግፈው ወጡ። መኪናውን እንዴት ነድቶ እቤት እንደ ደረሱና ከዛ በኋላ ያደረጉት ሁሉ ትዝ አይለውም።

ጠዋት ላይ ሚንቅላት የሚከፍል ራስ ምታት ሲቀሰቅሰው አዲሷ 'ምስጢር' ጉኑ አልነበረችም። ደንገጥ አለና እሷ በተኛችበት አቅጣጫ ሲያይ ጥቁሩ ተሚሷና ሰማያዊ ጃኬቷ ወንበሩ ላይ ተዝረክርኮ ተበትኗል። ሌላኛዋ የሆስፒታሏ ምስጢር ትዝ ስትለው ፊቱን በሁለት እጹ ሸፍኖ፣

"ኡፍፍፍ ... ወይዛ... ሲረሷት አታውቅም እንዴ ይቺ? ምን በጠዋቱ ትነጅሰኛለች" አለ ሥክ ብሎ፣ እዛው በጆርባው እንደ ተኛ ጣራ ጣራውን እያየ። እጹ ላይ ያለውን ሰዓት ሲያየው አንድ ተኩል ይላል። ከመታጠቢያ ቤት የሚወርደውን የውሃ ድምፅ ሲሰማ 'ይቺ ደግሞ ምን በሴሲት ያንተገፐቅገፐታል?' አለና ገልበጥ ብሎ ፊቱን ትራሱ ውስጥ ተብሮ ራስ ምታቱ እንዲሄድለት እየተመኘ በደረቱ ለጥ አለ። ትንሽ ቀየት ብሎ ድንገት ጆርባው ላይ ቀዝቃዛ እጅ ሲያርፍበት ደነገጠ።

"ኡፍፍፍ ... እሰኪ ግንባሬ ላይ በፈጠረሽ ... ራስ ምታቱ ሊገድለኝ እኮ ነው" አለ፣ ዓይኖቹን እያጨናበሰ በርጣ ተጠቅልላ ከፊል ርቃኗን ያለችውን ልጅ እያየ። በሁለት እጇ ግንባሩን ከዛም ፊቱን ስትይዝለት "ኡፍ ይስ ሲል ... አንቺ ግን ምን ብሪቷ ነሽ ... አይደክምሽም ... ምንም ራስ ምታት ምናምን የለም?"

"ሥራችን ነው ለምደነዋል ... ይሄ ለኔ ገንቶ ነው። ስንት ዓይነት ሰው እንደሚያጋጥመን እኮ አንተ አታውቅም። እንዳንዱ ትውከታም ... ካልተደባደብኩ የሚለው ብትል፣ ስንት ዝተታም የወንድ አውሬ አለ መሰለህ። የፈለገውን አድርጎ እንደ ቀሻሻ ዕቃ ዞር ብሎ የሚያይህ ... የገዛህ የሚመስለው ... ባለ ትዳሮቹማ በቃ የሰው ምራቂ ... ቅል ሚንትላቶች ናቸው ... ኧረ ስንቱ" አለች፣ ግንባሩን በቀስታ እያሻሸችለት። ማታ ካያትም የበለጠ ቀንጆ ሆና ታየችው። መከራ በጠገበ ፊቷ ላይ የሐዘን ድባብ ይነበባል። ስትሥቅ ደግሞ ፊቷ ላይ የተከመረው ሐዘን እንደ ምትሐት ብን ብሎ ይጠፋል። "አውን ሽር ፍትፍት ነገር በበረዶ፣ ቂ ካለ ቀንጆ አቦል ቡና ጋር ብታገኝ እኮ ... አ-ዲ-ስ ራስ ምታት ነበር" ስትለው፣ ማታ ጎሊና ያመጣችለት ምግብ ትዝ አለውና ግንባሯ ላይ ሳም አድርጓት ሩንዮር ብሎ ተነሣ። ያገኘውን ልብስ ጠለቅ ጠለቅ አደረገ፣

@OLDBOOOKSPDF

"ላይሻል አይተርም ... እስኪ ምን እንዳለ እንይ" አሰና ወደ ፍሪጁ ተንደረደረ። ተከትላው ወደ ኩሽና ገባች። ዱቄቱን በዛ አድርጎ ቡናውን ጣደና የምግቡን ሚስጣ ከፍሪጅ አውጥቶ ሲከፍተው ግድግዳውን ደገፍ ብላ በገሞታ ስታየው ቀይታ፣

"ማናት ልጁ እንደዚህ ከሽና አገልግል የምትጽጥርልህ?" አለችው፣ በኩፋት ዓይነት ወደ እርሱ ጠጋ እያለች።

"ምን ባክሽ ማታ ያክስቱ ልጅ ናት ይዛልኝ የመጣችው። ቤታቸው ድግስ ነበር ... መሄድ ስላልቻልኩ ልከውልኝ እግሪ መንገዴን ጥላልኝ አሰፈች" አለ። ለምን መዋሸት እንዳስፈለገው አስቦ በራሱ ተናደደ።

"ያክስት ልጅ አያላጣህ። ብዙ ያክስት ልጆች አሉህ?"

የገረጥ አየት አደረጋትና፣ "እሺ ከገርል ፍሬንዶቼ አንዷ ናት ... ስሟ ትዝ አይለኝም። ለው መዋሸት አይችልም ማለት ነው በቃ?" አለ፣ ትከሻውን ካንገቱ በላይ ከፍ አድርጎ።

"እንደሱ ይሻላል። የሷን ፍትፍት ለኔ ቁርስ እንዴ ጋበገከኝ ትነግራታለህ ወይስ ... ከነ ዶክተር ምንትሱ ጋር በላነው ... እንዴት ይጣፍጣል ነው የምትላት?"

"የሆነ ደረቅ ነገር ነሽ ግን ... እስኪ ወሬውን ተይና ቡናውን ቅጂልን ... የሴት ወጥን ሞከሪ ... በጠዋት የተፈረካከሰ ጭንቅላቴን አትነርቺው በናትሽ ..."

"አይ ወንዶች ..." ብላ፣ በጨበጠችው እጇ እንደ ቀልድ ጀርባውን ደለቅ አደረገችው። ስኒው የት እንዳለ ጠይቃው ወተት አሙቃ ቡናውን ቀዳችና ቀዝቃዛ ፍትፍቱ ላይ ዘመቱበት።

"ለምን ግን ሚስጥር አልከኝ?" አለች፣ ረሃቡ ጋብ ሲልላቸው ቡናውን ፉት እያለች፣

"በቃ ... ሚስጥር ሚስጥር ስለምትሸቺ ... ሚስጥር ነገር ስለመሰልሽኝ ... ለምን ይመሰልሻል አንቺ?" አለ፣ እውነቱን ልንገራት አልንገራት ብሎ እያመነታ።

"ያው ወንዶች እኮ ያው ናችሁ ... ምን የተለየ ነገር አላችሁ ... ወይ ሚስጥር የምትባል በጣም የምትወዳት ጓደኛህ ሳፈር ብላሃለች ... ወይ ደግሞ በፍቅሯ የምትንገበገብላት ሚስጥር ተብዬ ሚስጥራዊ ልጅ ትኖራለች። እሷን ካላገኘህ ... ሞደሪክ ነገር ፈልገህ ... የራስህን ሚስጥር ፈጥረህ ... ከሸሌ ጋር ማደር ነዋ። ማታ በስካር ነፍስህ ጠፍቶ እሷ መስዬህነው መሰል ሚስጥርዬ ... ማሬ ወተቱ ... ቅብጥርጥርሉ ... አንድ ዕድል ስጪኝ ... እኔ ኮ ነፍሴ እስኪወጣ ነው የምወድሽ ምናምን እያልክ የሆነ ያልሆነ ነገር ሰትዘበዝብ ነበር" ብላ፣ በትዝብት ዓይነት እያሾፈች ስታየው፣ እንደ ማሬር ብሎ ለራሱ ያዘጋጀውን ፍትፍት አጉረሳትና ቡናውን ፉት አለ።

"ልክ ነኝ?"

@OLDBOOOKSPDF

"ልክ ሁኚም እትሁኚም ... እኔ ማታ ስወጣ አንቺን የመሰለች ልጅ አገኛለሁ ብዬ አላሰብኩም። የኔን ተይው አንቺ ግን ለምን ..." ብሎ፣ የጀመረውን ዐረፍተ ነገር ሳይጨርስ፣

"እኔ ምን ዓይነት ልጅ ነኝ?" ብላ፣ አቋረጠችውና እጁ ውስጥ የገባውን እንቍላል ገምሳ አገረሰችው። " ገብቶኛል ... ለምን ወደዚህ ህይወት ገባሽ ... መውጣት አትፈልጊም ወይ ... ብ-ላ-ብ-ላ ... ለማለት ከሆነ ብዙ ጊዜ የሰማሁት፣ የለለቸኝና የሚያስጠላኝ ዘፈን ነው። እሱንም እንገለለው" አለችው፣ የቀረውን እንቁላል የመሃሉን አውጥታ ነጩን ትንሽ ትንሹን በጥርሷ ሸራርፋ እየበላች።

"ኦኪይ፣ ኦኪይ ... እሺ ... ግን ቢያንስ እውነተኛ ስምሽን ማወቅ እችላለሁ?" አለ፣ ይቅር በሚል አይነት ሁለት እጆቹን እያነሳ።

"ምን ለውጥ አለው? ... እውነተኛ ስሜ እውነት ሊወራ በማይችልበት ሁኔታ ትርጉም አይኖረውም። በለጡ ... አልማዝ ... ሰብለ ወንጌል ... ብልሀ ምን ይጠቅምሃል። ስጊዜው እንተ የሰጠኸኝ ተስማምቶኛል ... ሚ-ስ-ጥ-ር ሆኜ ልቀይ"

የበሉበትን ካነሣሡ በኋላ፣ ሁለተኛ ቡና ቀድቶ ቲቪውን ከፈተና ሶፋው ላይ ቁጭ አለ። እሷ ደግሞ ወደ መኝታ ቤት ገብታ ልብሷን ለባብሳ መጣች። አዲሷ 'ሚስጢር' ተስናብታው ከወጣች በኋላ በመስኮቱ በኩል ቀሞ ግቢውን ለታ እስክትወጣ ባይኑ ሸኛት። ስልክ ቁጥር አለመለዋወጣቸው ትዝ ሲለው ትንሽ ቁጨው። እዛው እንደቆመ ከውዳሴ ጋር ጠዋት አራት ሰዓት ላይ ያለውን ቀጠሮ አስታወሰና 'ኡፍፍፍ ምን ጣጣ ነው ባካቹ ... ማረፍ አልተቻለም እኮ" ብሎ ትንሽ ለመተኛት ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰ። ከራስጌው ከመዲኖ ላይ ስልኩን ብድግ ሲያደርገው ከሥሩ የታጠፈ ብጣሽ ወረቀትና የተጠቀለለ ገንዘብ አገኘና ደንገጥ ብሎ ወረቀቱን ከፈተው

"በጣም አመሰግናለሁ ትንሹ ዶክተር። ጨዋና ደግ ሰው ትመስላለህ። ፍትፍቱና ቡናው ይበቃኛል፣ ገንዘቡ ይቅር። እውነተኛ ስሜን ማወቅ ከፈለግህ ደውል 0912 ... ኤሰ ኤስ"

ይላል። የጅ ጽሑፏም እንዳነጋገሯ ሞልቶቅ ያለ ሲሆን ጥርት ባለ እንግሊዘኛ ነው የጻፈችው። "አሞበርባሪ ...እንኳን ሌላ ልንጨምር ... ያሉትንም መቀነስ አትቶናል" አለ። እንድ ሲጋራ አውጥቶ ለኩሶና በተረፈችው የክብሪት እሳት ወረቀቷን አቃጠላት። የቀረችውን የክብሪት እንጨት ይዞ ሲጋራውን እያቦለለ ፈገግ አለ። አልጋው ላይ በጀርባው እንደ ተንጋለለ ጣራ ጣራውን እያየ፣ ከውስጡ ጋር ሲናጆስ ብዙ ደቂቃዎች እንደ ጥላ ወደ ኋላ ፈሰሱ።

@OLDBOOOKSPDF

፡13፡

ሌላው ሰኞ ቀኑን ሙሉ ባለቤቱ ንጹሕ ወደ አሜሪካ ይዛ የምትሄዳቸውን ዕቃዎች ሲገዙ ዋሉ። ማታ ላይ ደግሞ እናቱ የመሸኛ እራት አዘጋጅተው ስለነበር ቱኒ ሳይታወቅ አለቀ። እንድ ወር ከነርሱ ተለይቶ መቅረቱን መቀበል አቅቷት ከብዙ ከርከር በኋላ ነው በመቀየቱ የተስማማችው። ማክሰኞ በጠዋት ከቤት ወጥቶ እንደ ልማዱ ትንሽ ለማሰብና ለማኪያቶ ካልዲስ ሄዶ ቁጭ አለ። የሲስተር ዘቢባ ባል አቶ ሲራጅ ያነሣው የክሊኒክ ሐሳብ ከአእምሮው ሊጠፋ አልቻለም። ንጹሕ የማትስማማበት ሐሳብ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለክሊኒክ የሚሆን ሁነኛ ቦታ ማግኘትና የፈቃድ ማውጣት ሂደቱ ተራራ መስሎ ታየውና ነገሩን ከሜንቅላቱ ለማውጣት ሞከረ።

ጳውሎስ እንደ ደረሰ የሐኪሞች የጠዋት ስብሰባ ስላልነበረ በቀጥታ ወደ ክሊኒኩ ገባ። ከርሱ ቢሮ ፊት ለፊት ካለው የነርሶች ቢሮ ሲደርስ፣ ሲስተር ዘቢባ ከምስጢርና ከእናታ ጋር የደራ ወሬ ይዘው ደረሰ። ጨዋታቸውን ገታ አድርገው፣ ሲስተር ዘቢባ የርሱን አለባበስ በማድነቅ የጀመረችው ወሬ መንደርደሪያ ሆኖ መሣሣቅ ጀመሩ፣ ወዲያው ሳንቾም ሲቀላቀላቸው ጨዋታው የበለጠ ደመቀ። በሳምንት ሁለት ቀን ጠዋት ለሶሻል ወርክ ዲግሪ የልምምድ ስራ ለማድረግ ጳውሎስ መምጣት ከጀመረ ወር አለፈው።

"ዛሬ ትንሽ በጊዜ መመጣት ሳይኖርብኝ አይቀርም፣ ሲስተርዬ። የንጹሕ ንየ እሑድ ስለሆነ አንዳንድ የማጣቱት ነገር አለኝ" አለ።

"አይምንም አይደል ...ዛሬ በቲ ሬዚደንት ዶክተሮች ስላሉን እነሱ ያዩዋቸዋል፣ ዶክተር ሲራክም እኮ በዚህ ወር እዚህ ነኝ ሲል ነበር። ለካ ከነገ ወዲያ ነው ወሩ የሚጀምረው የኔ ነገር ..." ስትል፣

"ጥሩ ... እንግዲያው እኔና ወይዘሮ ኤደን መጀመር እንችላለን ... በሩ ተከፍቶ ይሆን እንዴ?" አለ፣ እንዴ ወደ ሲስተር ዘቢባ፣ እንዴ ወደ ወይዘሮ ኤደን እያየ።

@OLDBOOOKSPDF

"የምንረዳህ ነገር ካለ ... ለጉዞ የሚገዙ ዕቃዎች መግዛት ምናምን ..." አለች ፣ ቁልፎቿን ከኪሷ ውስጥ እየፈላለገች ።

"ኧረ ምንም ... ብዙም እኮ አይደለም ... ያው ከዚህ ሲኬድ አለ አይደል አንዳንድ ለወዳጅ ቤተሰብ ምናምን የሚሆን ስጦታ" አለ ፣ ነገሩን ቀለል እያደረገ ።

"ግን ፣ ኤኒ ታይም ንገረን ... ቀይ ልከፈትልህ በሩን " አለችና ፣ ብዙ ቁልፎች ያነገተውን የቁልፍ መያዣ እያቅጨለጨለች ተነሣች ። ተከታትለዋት ወይዘሮ ኤደንና ዶክተር ሌላሠው ሲወጡ ምስጢር ከጓላው ነካ አድርጋው ፣

"ዶክተር ሌላ ... አንድ ጊዜ " ስትለው ፣

"እ...ሺ " ብሎ ወደርሷ ዞረ ።

"ማሚና እኔ አንድ ልናወራህ የምንፈልገው ጉዳይ ነበር ። ከማሚ ጋር አንድ ግማሽ ሰዓት ካወራችሁ በኋላ ጆይን ላደርጋችሁ እችላለሁ?" አለች ፣ እጁን እያፍተለተለች ።

"ሹ--ር ... ወዶ ሦስት ተኩል ላይ ግቢያ ... ምን በለላም ነው?" አለ ፣ ፈገግ ብሎ እጁን ዚሉ ውስጥ እንደከተተ ።

"ኧረ በጣም ሰላም ነው ...በጣም በሰላም ነው... በታ አልያገህ" ብላ ፣ ተመልሳ ከሳንቾ ጋር ወሬ ጀመረች ።

ወይዘሮ ኤደን ፍክት ያለ ባለ ጎብረ ቀለም ተሚሳቸውና የያዙት ቀይ ቦርሳ ደስተኛ አስመስሏቸዋል ። ጸጉራቸውን ቀይ ቡኒ ቀለም ተቀብተው ከባለ ታኮ ቀይ ሚማቸው ጋር የበለጠ አድምጽቸዋል ። ተጭኗቸው የኖረው ድብርት እየተነሣና የሚንቀታቸው መጠን እየረገበ በመጣ ቁጥር የሰብእናቸው መልክ እየተመለሰ ነው ። ተከታትለው ሲገቡ ፣ ባዶ ወና ያደረውን ክፍል የተቀበት ሽቶ ናኘበት ። ያደሩና የተራረፉ ካርዶችን አንድ ላይ አስተካክሎ ከሞን ወዳለው ጠረጴዛ ላይ እያስቀመጠ ፣

"እንዴት ዘረመሙ ታዲያ? በጣም አምሮብዎታል" አለ ፣ ከልብ የሆነ ፈገግታ እያሳያቸው ።

"አመሰግናለሁ ... አመሰግናለሁ ዶክተርዬ" አሉ ፣ እጅ እንደ መንሳት ብለው ።

"መጀመሪያ ሳይዎት ከነበረው ብዙ ለውጥ ያለ ይመስለኛል ... ለእርስዎ እንዴት ነው?" አለ ፣ ሁኔታቸውን እያጠና ።

"ው-ይ ዶክተርዬ እሱማ ምን ታል አለው? የቀንና የማታ ያህል ነው ለውጡማ ... ቢያንስ እንትልረ ደህና መሆኑ ራሱ አይበታም እንዴ? ደግሞ ወጣ ወጣ ማለትም ጀመራያለው እኮ ። እላዬ ላይ እንደ ከምር የተጫነብኝ ጨለማ እኮ ነው ብድግ ያለልኝ ። አንተን ላከለኝ እሱ ... መቼም አያልትበት" አሉ ፣ ዓይን ዓይኑን እያዩ ።

"በጣም ጥሩ ነው ። የማታገኙትና እንዳንድ ያለፉ ነገሮች ደጋግመው ራትዎ ላይ ድትን ማለታቸውስ?"

@OLDBOOOKSPDF

"በጣም ቀንሏል።"

"እም...ም ... በጣም ጥሩ ነው፣ ከፍ ያለ ድምፅ ሲሰሙ ተደናግጠ የመጀንሲ ነገርስ ትንሽ ቀነስ?" አለ፣ ካርዳቸውን ወደ ፊትና ወደኋላ እያገላበጠ።

"እ...ሱ ሙሉ ለሙሉ አልጠፋም ... ግን እንደ ፊቱ ግልቀስ የለም ... ስብቻዬ ሞብኖ ብዬ ጨለማ ክፍል አልቀመጥም። ምግብም ቢሆን በጣም ተሻሽያለሁ ... ትንሽ ኪሎስ ሳልጨምር ቀረሁ ብለህ ነው" አሉ፣ ሰውነታቸውን አየት እያደረጉ።

"በጣም ጥሩ ነው። መድኃኒቶቹስ ... ምንም ችግር አልፈጠሩብዎ?" ቢሉ፣ ቀበል አድርገው፣

"እኔ ድሮም ኪኒን ምናምን ብዙም አልወድ ስነገሩ። ግን ከጤና የሚበልጥ የለም። በርግጥ ትንሽ ማድከሙ አለ ... አሁን ግን ሰውነቴም ለመደው መሰል ብዙም አይረብሸኝ። ትንሽ ችግር የሆነብኝ ድንገት ሳላሰበው ልቤ ትር ትር ትልና ካልወጣው ብላ ደረቴን እንዳንድ ነገር ተሰር ይይዘኛል። ከዛ ከላይ ከላይ እያስተነፈሰ ላብ በላብ ዘፍቶ የሚያሩነኝ ነገር ነው ... መላው የጠሩብኝ። በታ እኮ ሰማይና ምድሩ ላይ ሊደፋብኝ የደረሰ ነው የሚመስለኝ" አሉ፣ ነገሩን በትክክል ለመግለጽ እየተቸገሩ።

"የዚያ አይነት ስሜትን የሚፈጥረው፣ ባብዛኛው ፓኒክ የምንለው የጥንቱ ስሜት ሊሆን ይችላል። እርስዎ ግን ስኳር ሕመምም ስላለብዎ የስኳሩ መጠንም ዝቅ ሲልም የዛ ዓይነት ስሜት ሊፈጠር ይችላል። ስለዚህ እሱንም ማሰብና መጠኑት አይርሱ። ቶሎ ቶሎ መተንፈሱ ደግሞ ደምዎ ውስጥ ያለውን የኦክሲጅንና ካርቦን ዳይኦክሳይድ መጠን ስለሚያዛባው ነው ሌሎቹ ምልክቶችም የሚታዩት።

"ይቺ ሰስ ፈስታል አለች አይደል? ... ልክ ሲጀምርዎ ትንፋሽዎን ያዝ አድርገው ተስ እያሉ ... በረጅሙ ... ፊስታሏ ውስጥ ... ወደ ውስጥና ወደ ውጪ መተንፈስዎን ይረዳል። እስኪ ይሞክሩትና ይንገሩኝ። ሲተነፍሱ አፍና አፍንጫዎን ሙሉ ለሙሉ ፈስታሉ ውስጥ አድርገው፣ የሚተነፍሱት አየር ከላስቲኩ ውስጥ ሳይወጣ ላንድደቂቃ እሱን ወደ ውጪና ወደ ውስጥ እየተነፈሱ ይሞክሩት። ልክ እንደዚህ ..." ብለው፣ እተነፈሱን ሲያሳያቸው እንደ ተረዱት ሞንትላታቸውን በመወዝወዝ አሰረገሙ፣ "አሁ ከልሠራ ግን የመድኃኒቱን መጠን ላስተካክልልዎ እችላለሁ" አሉና፣ ዋቂት አያሰበ ዝም አሉ።

"በታ ዶክተር ... መሬቻህ ደረሰ ማለት ነው?" አሉ፣ እዝን ባለ ድምፅ።

"አዎን፣ እግግዲህ ኑሮ አስቸጋሪ ነው ... ቢተስቢም እዛው ስለሆነ፣ ቀየ ብሮ ደግሞ ብት እሉ ይሆናል" አለ፣ ለሚቀጥለው ወር የሚሆን መድኃኒት ማዘዣ እየጻፈላቸው።

"አም ... እሱስ ልክ ነው ... ግን ለኛ እዚህ ብትሆንልን በማለት ነው እንጂ ... ስው መቼም ራስ ወዳድ ነውና። ሚሚዬም ስትነግረኝ ነበር ... ስለ ሚስትህና ስለ ልጆችህ መቼም እውርታም አትጠግብ። በቀድም ለእራት ተገናኝታችሁ ነበር መሰል ሲስተር ቤት" ሲሉ፣ በሩ ከ@ALEBOOKSPDF

"ይግቡ..." አለ፣ ሌላሠው ፊቱን ወደ በሩ ዞር አድርጎ።

"ይቅርታ፣ አሁን መግባት ይቻላል?" አለች፣ ምስጢር እንገቷን አስገብታ።

"ኦህ ... ያ ...ያ ... ግቢ ግቢ ..." አለ፣ መንበሩ ላይ ወደ ኋላ ደገፍ ብሎ። ገብታ ከእናቷ አጠገብ ተቀመጠችና ዓይን ዓይናቸውን እያየች፣

"እንዴት ነው ... ፒስ ነው ማሚዬ ..." ስትል፣

"ሁሉ ጥሩ ..." አሉ፣ ግንባሯ ላይ የተበታተነውን ጸጉሯን በጃቸው እያስተካከሉላት።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ፣ "ይቅርታ አቋረጥኳችሁ እንዴ?" ብላ፣ ግራና ቀኝ ሁለቱንም አየት አደረገች።

"አይ ጨርሰናል ...እንዲያው ዶክተርና ቤተሰቡ ስለ መሄጻቸው እንሰተን ... ስናወራ ነው የመጣሽው" አሉ።

ተበል አድርጋ፣ "ዶክተር ሌላ ... ትንሽ ልናግራህ የፈለግነው ጥንኛው ምክንያት ለናቱ ስላደረክላት ሁሉ አብረን ልናመሰግንህ ነው። ምናልባት መጀመሪያ ልታይህ ስትመጣና በዛው መካከል ያለውን ለውጥ አንተም ታየዋለህ። ሌላው ደግሞ እኔንም አብራህ ሆኜ ለፐራክቲክሚ የሚያስፈልገኝን ልምምድ እንዳገኝ ስለ ፈቀድክልኝ ለሱም ለማመሰገን ነው። በትርብ ባለቤትህና ልጅቸህ እንደሚሄዱና አንተም ጥቂት ጊዜ ነው የቀረህ ስላት ነው እናቱ እንዲያው በትው እንኳ ሳናመሰግነው ..." ብላ፣ እናቷን እየት አደረገቻቸው።

"ልክ ነው ዶክተር ...እንዳንተ ዓይነት ራኅሩኅና ሰውን ሁሉ በኩል ዓይን የሚያይ ... ደግሞም የሚሠራውን የሚያውት ብዙ ሰው ቢኖር ይሄ ሕዝብ አገሱ የሚሀረውን መከራ ገና ድሮ በጣለ ነበር። በውነት መድኃኒዓለም እሱ የሥራህን ፍሬ እንደሚለዋህ አውቃለሁ ... አሁንም ሰዋቶሃል። ግን በቃ እንድታውቀው ነው ... መቼም እኛ አገር ሰው ካልሄደና ካልሞተ አይመሰገንም እያደለ?" አሉ።

"እሺ ... እኔም በጣም አመሰግናለሁ ... ደግሞም እናንተን ማወትና ከናንተም ጋር መሥራት ለኔ ትልት ደስታ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ እርስዎ ተሽሉዎት ማየቱ ነው የኔ ትልቱ ፍሬ ..." አለና ሌላ ምን ማለት እንዳለበት ስላላወቀ ዝም አለ፣ የያዘውን እስክሪብቶ ካንድ እጁ ወደ ሌላው እያሸጋገረ።

"ሌላው ግን በተደም የሲስተር ባል ያነሣው ሐሳብ ትገ ይልሃል? ስለ ክሊኒክ ምናምን ..." ስትል፣ በእፎንታ ራሱን ነቀነቀ። "እና፣ ነገሩን ከማሚ ጋር እቤት ሰናወራ አንድ ሐሳብ መጣልን። ማለቱ ሐሳብ ነው፣ ግን ለማንኛውም አንተም ንጹሕም ከመሄጻችሁ በፊት ብንነግርህ ማን ያውታል ብለን ነው።" ብላ ትንሽ ዝም አለች። ወደ እናቷ አየት አደረገችና፣ "ሌላው አንድ አባቱ በውርስ ያገኘነው ትልቅ ግቢ ያለው ቪላ አለ። እምልህ ግቢው ብቻ ከሦስት ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ነው። በብዛት ሣሬካና ባና ነው። አዘራይተነው የሆኑ ፈረንጆች ናቸው የሚኖሩበት። ወደ ፈረንሳይ አካባቢ

@OLDBOOOKSPDF

ሲሆን፣ በጣም ጸጥ ያለ ሰፈር ነው። የእእምሮ ሕክምና ማዕከል ቢሆን ብዙ ሥረ
ሊሠራበት ይችላል ብለን አሰብን። ምናልባት እንተም ሐሳቡ ጥሩ ከመሰለህ ...” ብላ
የሚለውን ስትጠብቅ፣ እናቷ ቀበል አድርገው፣

“እኔ መቼም ከዚህም ለተሻለ ቅዱስ ተግባር ያ ቦታ ይመሳል ብዬ አላስብም።
ደግሞ ካንተም የተሻለ ሰው ሊሰራበት ይችላል ብዬ አላምንም። ሰምቼም በዚህ ወር
ስለሚለቁት ቦታውም ክፍት ይሆናል። ግን ያው ሰው ይመኝ የለ ... እንዲየው ይሄ የሻ
ምኮት ነው...” ብለው፣ እላቸውም ገም አሉ።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ፣ “በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው ... የኔም አንዱ ሕልሜ፣ ብዙ
ሰው ሊረዳና ሊማር የሚችልበትን የሕክምና ማዕከል መክፈት ነው። ቦታው ደግሞ
ለዚህ የተመቸ ይመስላል። እስኪ ስለ ጉዳዩ ከንጹሕ ጋር ልመካከር፣ እኔም የበለጠ
ላስብበት” አለ። ውሳኔ ደስ ቢለውም፣ ብዙ ሊታዩና ሊታሰቡባቸው የሚገቡ ነገሮች
መኖራቸውን አሰበ።

“እርግጠኛ ነኝ ዶክተር ሌላ ... ቦታውን ስታየው ዋ...ው፣ ነው የምትለው።
እንተም ንጹሕም እስክምታዩት አይ ካንት ዊይት ... እነ አርሲማ እንኳን ሳይቀሩ ነው
አሜሪካ አንሄድም የሚሉት...” ብላ፣ ስትሥት እናቷና ሌላውም አብረዋት ሣቁ።

እነርሱ ከሄዱ በኋላ ሊጠብቁት የነበሩትን ጥቂት ሌሎች ሕመምተኞች እያቶ
ሲመጣ፣ በቀጥታ ፖስታ ቤት አካባቢ ሄዶ ንጹሕ እንዲገባ የነገረችውን የስሞታ ዕቃዎች
ገዛዝቶ ወደ ቤት አመራ። ቤት እንደ ደረሰ የነበራቸው የምሳ ቀጠሮ ስለደረሰ ወዲያው
ተያይዘው ወጡ። ወደ አሜሪካ ከመመለሳቸው በፊት ልጆቹን ይዘው ወደ እየላ
ለመውጣት ቢያስቡም ባለቀ ሰዓት እንዳይታመመሙባቸው ስለፈሩ ሐሳባቸውን ቀይረው
ሁለቱ ለብቻቸው ለመውጣት ነው ያቀዱት። እነ ምስጢር የነገሩትን የክሊኒክ ጉዳይም
እዛው ሊያነጣጥት እቅዷል። ንጹሕ ዝናሽን ለመጠየቅ ብታስብም፣ ቀኑ ሳያስቡት
አለቀ። ጠዋት ከከተማ ከመውጣታቸው በፊት እግረ መንገዳቸውን እይተዋት ሊያልፉ
ወሰኑ።

ጠዋት ላይ ልጆቹ ከእንቅልፍ ሳይነሱ ቀደም ብለው ከቤት ወጡ። የንጹሕን
በልጆቿ ጉዳይ መጨነቅ ያወቁት የሌላው እናት፣ “ንጹሕ ወርቅዬ ... ካጠገቤም
አይለዩም። ያክስታቸው ልጆችም እዚሁ ስለሚሆኑ ምንም አሳብ አይግባሽ፣
አትጨነቂ። ደግሞ ስትደርሱ ደጢሱ” አሉ፣ ከግቢ ሲወጡ። ሆስፒታል እንደ ደረሱ
መኪናቸውን ግቢ ውስጥ አቁመው ወደ ሴቶቹ መኝታ ቤት እየሄዱ፣

“እኔ ምልህ ሌላዬ ... ስንት ሰዓት ይወስድብናል ከእዚህ ሀዋሳ?”

“እሪ ኮርተን እንደርሳለን፣ ቢበዛ አራት ሰዓት ቢፈጅብን ነው። ይልቅ
ሆስፒታልም ስራ ተጀምሮ ግርግር ሳይበዛ አይተናት መመለሳት ይኖርብናል። “የማይገባ
ነገር እየሰፈሰፈች በምትሥት ታማሚ አጠገብ ሲያልፉ፣ ንጹሕ በፍርሃት ክንዱን
ጨምድዶ ያዘችው።

@OLDBOOOKSPDF

ወደ ሴቶች ክፍል ሲደርሱ ኃላፊ ነርሲን በር ላይ አገኟት። ከንጹሕ ጋር ከሰተሞቃቸው በኋላ አብረው ወደ ዝናሽ መኝታ አካባቢ ሄዱ። አልጋዋ ሜዳ ላይ ተቀምጣ ከጮኗ ከለችው ሕመምተኛ ጋር ስታወራ ደረሱ። ስታያቸው ብድግ አለች።

"ታዲያስ ዝናሽ ... እንዴ ነፍሰ ጡር እኮ አይነሣም፣ ቁጭ በይ ... ቁጭ በይ። እንዴት ዘረምሽ?" አላት፣ ፈገግ ብሎ።

"በጣም ይሀና ... ጥሩ ነው ..." አለች፣ አንገቷን እየደፋች።

"እሲ ባለቤቱ ናት ... ሁል ጊዜ ነው ስላንቺ የምትጠይቀኝ ..." ብሎ፣ ወደ ባለቤቱ ዞር አለና ፈገግ አለ።

ንጹሕ ልትጨብጣት እጁን በትዝረጋላት ልስልስ ባለ ድምፅ፣ "አመሰግናለሁ" አለችና ጨበጠቻት።

"ይህችን ደግሞ ለመተየሪያና ስትወልጂ ላንቺና ለልጅሽ እንድትሆንሽ ነው" ብላ፣ የተጠቀለለ ነገር ሰጠቻት።

እናፈትና ፈገግታ በተሞላ ፊት፣ "እሪ ይሄ ሁሉ ምን ያደርጋል ... ደክማችሁ እኮ። በጣም ነው የማመሰግነው" ብላ፣ አልጋው ላይ አስተመጠችው። ትንሽ ዝምታ ከሰፈነ በኋላ ድንገት ፊቷ ብርት ብሎ፣ "ቀይ ላሳያችሁ ... ሲስተር እኮ ልጅቼን አስገብታልኝ እሑድ መጥተው ነበር" አለችና፣ ከትራሷ ሥር የሁለት ልጆቿን ፎቶ አውጥታ ለሌላው ሰጠችው። ወደ ኃላፊ ነርሲ ጠጋ ብላ እጁን እየያዘች "ሲስተርዬ ... በጣም ነው ውለታሽ ለኔ ... እሷ እመቤቱ ትስጥሽ ..." አለች ከራስጌዋ በላይ ወደ ተሰቀለው የማርያም ምስል ዞር ብላ።

ኃላፊ ነርሲም የዝናሽ ትክሻ ላይ እጁን ጣል አድርጋ፣ "ውይ ዶክተርዬ፣ እንዴት እኮ የሚያማምሩ ማር የሆኑ ልጆች መሰሉህ ..." አለች።

"በጣም ቀንጅዬ ልጆች ናቸው ያሉሽ..." አለ፣ ፎቶውን ለንጹሕ እያቀበላት።

"እምን ... ትልቁ እኮ አባቱን ቁጭ ነው፣ ምን ያደርጋል ብር ብቻ ... ደደብ አረብ ሆነ እንጂ ..." አለች፣ ፊቷ ልውጥውጥ ብሎ።

"እይዞሽ ዝናሽዬ፣ ዋናው ጤና ይሁኑልሽ ... እንቺ ደህና ከሆንሽ ሁሉም ይደርሳል ..." አለቻት፣ ኃላፊ ነርሲ ትከሻዋን እያባባሰች።

"ትንሿ ስንት ዓመቷ ነው?" አለች፣ ንጹሕም ወደ ዝናሽ እያየች።

"አራት ዓመት ሆናት መሰለኝ። ውይ ብታዩ እንዴት ዓይነት ሚጥሚጣ ሆናለች መሰለሽ ..." አለችና፣ ከንጹሕ የተቀበለችውን ፎቶ ሁለት ጊዜ ሳም ሳም አድርጋ ወደ ልቧ አስጠግታ ያዘችው።

ትንሽ አውርተዋት ከነርሲ ጋር ተከታትለው ሲወጡ፣ እንባ ባቀረሩ አይኖቿ ተከተሉቻቸው። ሌሎቹንም ሕመምተኞች በጅምላው ሰላም እያሉ ሲወጡ፣

@OLDBOOOKSPDF

እንዳንዶቹ እየመጡ ሰጥ ብለው እጅ እየነሡ ሰላም አሉት ። ንጹሕም ፈራ ተባ እያለት እየጨበጠቻቸው ከክፍሉ ወጥተው ወደ ቢሮ ሲገቡ ነፍሷ ትንሽ መለስ አለችላት፥ ኃላፊ ነርሷን አመስግነው በሳው ጥሏቸውን ወደ ሐዋሳ ጀመሩ ። ያየችው ነገር ስሜቷን የነካው ንጹሕ ሰረጅም ደቂቃ ዝም ብላ ቀየች ።

"ሌላዬ ... በየቀኑ እዚህ ውስጥ ነው የምትሠሩት? በጣም ነው እኮ የሚያሳዝኑት፥ እናንተ ግን እንዴት አትፈሩም? ሲሰቱርን እንዴት እንዳደነቷት ። አቤት የሰው ሕይወት ፈተናው ብዛቱ ..." አለች ፥ ሞንቅ ባለው ፊት ።

"ይሄ እንዲያውም ያን ያህል ከባድ አይደለም ... አንዳንዴ ራስሽን ነው የሚያዞርሽ ። እዚህ አገር በሚከፈላቸው ደሞዝና የሥራ ሁኔታ ይኼንን ሥራ የሚሰሩትን በተለይ ነርሶቹን በጣም ነው የማደንቃቸውና የማከብራቸው ። እስቪ መመታት ሊኖር ይችላል ... መሰደብማ ተይው ። በዛ ላይ አብዛኛው በጣም ደሃና ቤተሰቡም ምርር ብሎ የተወው ስለሆነ ሕመማቸውን ብቻ ሳይሆን ሥቃያቸውንና ተስፋ ቢስነታቸውንም ችለው ነው የሚሠሩት ..." ብሎ ፥ መሪውን የያዘባቸውን ጣቶቹን ጠበት ላላ እያደረገ በረጅሙ ተነፈሰ ። የትራፊክ ሞንትንቱን እስኪ ወጡ ደረሰ ጥቂት ዝም ብለው ነዱ ።

"በናትህ የዝናሽ ልጆች እንዴት ያምራሉ ... የድሃ ልጅም አይመስሉ ፥ ቤ እናት ፥ ደግሞ አሁን ሌላ ልጅ ሊመጣ ነው ። አባቷ በልመና ነው የሚተዳደሩት ኮ ያልከኝ?"

"አምን ... በዚያ ላይ ድከም ያሉ አባወንት ናቸው ። ምን ታደርጊዋለሽ እንግዲህ ... ስንት ሰው አለ መሰለሽ እንደሳቸው ። "

"ቶይ ግን አሁን የሷ ሀመም ወደ ልጆቿ አይተላለፍም? ላይክ ... እንደ ስኳር ... ደም ግፊት ፥ ማለቱ ነው ። "

"እ ...ም የአእምሮ ሕመም ላይ ሰትመጪ ነገሩ ትንሽ ውስብስብ ያለ ነው፥ ባጠቃላይ ከሌላው ሰው ይልት የበለጠ በሕመሙ የመያዝ ዕድሉ ሊኖራቸው ይችላል ... ግን ያን ያህል ሳይሆን ይችላል ። በተለይ ብዙ ሚና የሌለው ኑሮ ከኖሩና ከሰሰ ምናምን ከራቁ ዕድሉ የጠበበ ነው ። "

"እሷስ አሁን ከተሻላት በኋላ የመዳን ተስፋ አላት? ወይስ በቃ እንዴ ከታመመች ምንም ተስፋ የለውም?"

"ባጠቃላይ ሁሉም ሰው ላይ የመዳን ዕድሉና ደረጃው አንድ አይደለም ። ዋናቶች የሚያሳዩት አንድ ሦስተኛ አካባቢ የሚሆኑት ባደጉትም እንኳ በጊዜ ብዛት ተሽሏቸው ያሠሩ ሊሆኑ ይችላሉ ። ሌላው አንድ ሦስተኛ ግድሙ ደግሞ በመታከም ብቻ ሳይሆን ሊረዱና ሊሻላቸው የሚችሉው ። የቀረው ግን መታከሙ ለራሳቸውም ለቤተሰባቸው ያለውን ሚና ከመቀነስ አንጻር ጥቅም ቢኖረው እንጂ ፥ ብዙ እገዛ የሚያስፈልጋቸው የዕድሜ ልክ ሕመምተኛ መሆናቸውን አይቀይረውም ። አንዳንድ ጠጭ ነገሮች

@OLDBOOOKSPDF

ቢኖሩም ... ችግሩ ባጠቃላይ የትኛው ሰው በየቱ ምድብ ውስጥ ሊሆን እንደሚችል በትክክል ማወቅ አይቻልም" አለና ፣ በረጅሙ ተነፈሰ ።

በወሬው ተመስጦ ከሙቶ ኪሎሜትር በሰዓት በላይ እየፈጠነ ስለነበር ፣ "ቀስ ሌላዬ ... አውሮፕላን አደረክው እኮ ..." አለች ፣ እጁን በጂ ላመል ያህል ያዝ አድርጋ ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፣ "የዕለ እንዴት ይመስልሃል?" ስትለው ፣ በየመንገዱ ጸር ቀመው ለሰላምታ እጃቸውን የሚያውለበልቡላቸውን ልጆች እጁን አውጥቶ ሰላም እያለ ፣

"ደጋግማ ሆስፒታል መግባቷና ህመመሙም ብዙ ስለቆየባት ምናልባት ዕድሜ ልኳን መድኃኒት መውሰድ ይኖርባታል ። ግን እሁን በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ያሳየችው ከፍተኛ ለውጥና ሌሎችም ሁኔታዎች የሚጠቁሙት መድሃኒቷን በትክክል ከወሰደች ጤነኛ ኑሮ ለመኖር ጥሩ እድል እንዳላት ነው ። ሴትነቷ ፣ ስሜቷን የመግለጥ ችሎታዋ ሙሉ ለሙሉ አለመጥፋቱ ፣ ከመታመሟ በፊት የነበራት ጥሩ የሰብእና ሁኔታ ሁሉ ተደማምሮ ጥሩ ተስፋ እንዳላት ነው የሚያሳየው" አለና ፣ ከአጠገቡ ያለውን የላስቲክ ውሃ እንድትከፍትለት አተበላት ።

በዚህ መሃል በዛ ያሉ አሰፋልቱን በቀስታ የሚያጽርሙ ዘብቶች መንገዱን ስለዘጉት መኪናውን በረድ አድርጎ ቆመ ። የከፈተችውን ውሃ ለራሷ ገንጨት ብላ ሰትሰጠው ተቀብሎ ገማሹን ባንድ ትንፋሽ አንደቀደቀውና "ኡፍይይይይ ... እንዴ በጥያቄ አድርተሽኝ እኮ ... ማይ ጋድ ... ልትገድይኝ ..." ብሎ ሲሥቅ ፣

"ዝም በል ... ሞዛዛ ... አሁን እንተ በእንቅልፍ ልብህስ ቢሆን ውሃ ካገኘህ ... ማን ይመልስሃል ..." ብላ አሷም ሣቀች ።

የውኃ ጠርሙሱን ተቀብላው እንደገና ጮንጨት ብላ አስቀመጠችውና ፣ "ቀይ ደግሞ ሌላ ትዝ ያለኝ ... እዛ ጠደ መው-ጫው ጥግ አካባቢ የነበረችው ዓይኗን እጮረጥርጣ ስትሥሀና ስትሳደብ ... ዕቃ ስትወረውር የነበረችው-ስ? ... አሁን አሷምም ይሻላታል? ቀይ ግን ... ሰይጣን ይሁን የአእምሮ በሽታ መሆኑንስ እንዴት ነው የምታውቂት? ወይስ በአናንተ ላይንስ ሰይጣን ምናምን የለም ፣ ሁሉም በሽታ ነው ብላችሁ ነው የምታምኑት? ምክንያቱም አይ አም ሹር በተሰብ ቢሆን ጠበል ወይም ጸሎት ነበር የሚወስዷት ፣ ወይም እስካሁንም መስደዋታል ርግጠኛ ነኝ ። "

በዚህ ደረጃ ተመስጣና ፍላጎት አድሮባት ስለ ሥራውም ሆነ በአእምሮ ሕመሞች ዙሪያ ጠይቃው ስለማታውት መገረምም ደስታም ተሰማው ። "በታ ኮ የአእምሮ ሐኪም መሆንሽ ነው ። ምን ተረሽ?" ብሎ ፣ በስሱ ፈገግ ብሎ በጮን አየት አደረጋትና ፣ "የትኛውን እንዳልሽ ገብቶኛል ። የሚገርምሽ ነገር ዝናሽን መጀመሪያ ከጻውሎስ ጠደ አማኑኤል ሳመጣት ትዝ ይልሻል እንኳን አጎትሽ ቤት ምሳ ግብግ የነበረ ጊዜ ። እሁን ካልሻት ሴት በብዙ እጥፍ የባሰች ነበረች ። አንዳንዴ በሚገርምሽ ፍጥነትና ሁኔታ ሊሻላቸው ይችላል ። ደግሞ የፈለግሽውን ብታደርጊም ብዙም ለውጥ ላያሳዩ ይችላሉ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ሰይጣን ላልሽኝ ግን ... በጣም አነራላሪ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ መንፈሳዊ ዓለም አለ ወይ? ሰውስ መንፈሳዊ ፍጥረት ነው ወይ? ሰይጣን ወይም ጋኔን አለ ወይ? ያዘው ስንልስ ምን ማለታችን ነው? በምንስ እናውቃለን? መንፈሳዊ ባልሆኑ ምክንያቶች የሰው አእምሮ ሊታመም አይችልም ወይ? ለምሳሌ፣ የተለያዩ ዕፆችና በአእምሮ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ በሚችሉ ንጥረ ነገሮች ቁጥጥር ውስጥ ያለ አእምሮ ልዘ ጋኔን እንዳደረበት ሰው ያለ ባሕርይ ሊያሳይ ይችላል። በግዚርም ሆነ በመንፈሳዊ ዓለም መኖር በማያምነው ጮራ እንደሆኑ ራሳቸውን የሚፈርጁ ሰዎች፣ መንፈሳዊ እውነታን እንደምታምኚ ሲያውቁ እንደ ምኝ ነው የሚሥቁብሽ ወይም እንደ ምስኪን ነው የሚያዩሽ። በእነርሱ አይታ ሁሉም ነገር ከአንጐልና ከሰው አእምሮ መገባት አንጻር ብቻ ነው የሚታየው።

"በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውም የባሕሪይና የሥነልቦና ቀውስ የሚታይበትን ሰው ሁሉ በርኩስ መንፈስ እንደ ተያዘና በሰይጣን እንደ ተለከፈ የሚያምኑ ብዙ ሰዎች አሉ። በተለይ እዚህ አኖ አገርና ባጠቃላይ አፍሪካውያን መደዚህኛው ምድብ ሳናደላ አንቀርም። ለእኔ ግን ሰው ማለት በመንፈሳዊው አለምና እውነታ ውስጥ የሚኖር አካላዊና አእምሯዊ ማንነት ያለው ፍጥረት ነው። ስለዚህም የመንፈሳዊ ቀውስም ሆነ የአካላዊና አእምሯዊ ችግሮች በጥንታቱ ከላይዋቸው ሊያምታቱ የሚችሉ ተመሳሳይ ባህርያት አላቸው።

"መፈሳዊው አለም ስለካድነው የለም ማለት አይደለም። ሳይንስ ደግሞ መንፈሳዊውን እውነታ እንደቱሳዊው ነገር መለካትና ማረጋገጥ የሚችል መሣሪያ አትምም አለው ብዬ አላምንም። ደግሞ ሁሉንም ነገር በማመናፈስና ያልገባንን ነገር ሁሉ በሠይጣን በማላከክ ችግሩን መፍታት ሳይሆን፣ ትርፉ ይባስ ማወሳሰብ ሊሆን ይችላል። ሚዛናዊነት አስፈላጊ ነው" አለና፣ እሷ ምላሽ በመጠበቅ የመንገዱን ግራና ቀኝ እያየ ዝም አለ።

በዚህና በመሰል ጉዳዮች ላይ ስትጠይቀውና ሲያወሩ ሳይሰለቻቸው ነበር ቡታጅራ መታጠፊያ ላይ ደረሱ። "ቡታጅራ አካባቢ ደረስን ማለት ነው። ማኪያቶ ነገር ... አንዴት ነው?" አላት፣ ለማኪያቶ ያላትን ፍትር ስለሚያውቅ።

"ያ ... ጊዜ ካለን ነጻ ነጻ እያደረግንም ከተማው ብናየው ደስ ይለኛል። ማኪያቶም ሁሌም ጥሩ ሐሳብ ነው።" ተቀምጠው ማኪያቶ ካዘዙ በኋላ፣ "ሌላዬ ... ልጆቹ አታቲን አስቸግረዋት እንዳይሆን፣ አስኒ ቤት ደውል" ብላ፣ ተንጠራራች፣ ልጆቹንና እናቱን አሞርተው መንገዳቸውን ስመተጠል ተነሱ። አስፋልቱን ተከትለው ከተማይቱን አየት አየት አደረጉና ከተማይቱ መግቢያ ከመንገድ ዳር ካለ ትልቅ ሆቴል ገቡና ማኪያቶ አዘው ቁጭ አሉ።

@OLDBOOOKSPDF

፡14፡

ንውሕ ክኢትዮጵያ በልጅነቷ ስለወጣች ፣ ሁሉም ነገር አዲስ ፣ ሁሉም ነገር ብርቅ ሆኖባታል ። ከቡታጅራ እንደ ወጡ ወደ ዋናው የሀዋሳ መንገድ ከመግባታቸው በፊት እስከ ዝዋይ ያለው መንገድ ላይ ዘና ብለው መንዳት ቻሉ ። በየመሃሉ ጥቂት ትናንሽ ከተሞች ካልሆኑ በስተቀር ጸጥ ያለና ጥቂት መኪናዎች የሚታዩበት መንገድ ነው ። የመሬቱ አቀማመጥና ዙሪያውን ሰፊ ክፍት ሜዳ መኖሩ መንፈስን ዘና ያደርጋል ።

"ሌላዬ እንዴት ደስ ይላል በናትህ? ጸጥታው ... ደግሞ የአየሩ ንጹሕነት ... ኦህ ማይ ጋድ ... እዚህ መኖር ደስ የሚል ይመስለኛል" አለች ፣ መስኮቱን ከፍታ ነፋሱን በእጇ እየቀዘፈች ።

"እዚህ እንኑራ ታዲያ ..." ብሎ ሣቅ ሲል ፣

"ቀልዴን መሰለህ እንዴ? ... አዲሳባ አልፈልግም ። እዚህ ግን በደስታ ... ገበሬ ለመሆን ፈቃደኛ ከሆንክ?"

"በትርፍ ጊዜዬ እያከምኩ ... ገበሬ ብሆን አልጠላም ። ቀሮና ክትፎ ሠርተሽ እስካበላሽኝ ድረስ" ብሎ ፣ ጀርባዋን አሸት አሸት አደረጋት ።

"መንገዱ ደግሞ እንዴት ጭር ያለ ነው ... መኪናም የለም እንዴ?"

"እምብዛም ነው ... ለፍጥነቱ ብለው ያኛውን መንገድ ነው የሚመርጡት መሰለኝ ... ይሄ ትንሽ ራቅ ይላል ። ግን የምር ኢትዮጵያ የመመለስ ጉዳይ እንዴት ነው?" አለ ፣ ዕድሉን ተጠቅሞ ትንሽ ለማውራት አሰበ ።

"እንተ ቀልድም አታውቅም እንዴ ... እኔ እዚህ ለሚኖሩትም አዝናለሁ ። ሁሉም ነገር እኩ ገና ... ገና ነው ። እኔ አሜሪካዬ ምናለኝ ልጄ" ብላ ፣ የቀልዷን ኮስተር አለችበት ።

"ቆይ እስኪ ... አሰቢው ... በርግጥ አይመችም ልክ ነሽ ። ግን ልናመጣ የምንችለውን ልዩነትና ሰጪ ያለበትን ይኖሮ ሁኔታ አስቢው ። አለ አይደል ምኾት ጥሩ

@OLDBOOOKSPDF

ነው፣ ግን እኛ ካልሆንን ይሄ ደሃ ሕዝብስ ማን አለው? ለምሳሌ፣ እንዴ ዝናሽና አባቷ ዓይነት ስንት ሰው አለ መሰለሽ? ደግሞ ደስታ ሁሌም እኮ ከምጮት አይደለም የሚገኘው ... መስጠትና ለሌላው መኖር የሚሰጠው እርካታ የሚበልጥ አይመስልሽም?" ብሎ፣ ልቡ ውስጥ ያረገዘውን ፍላጐት ማፍሰስ ጀመረ።

"ውይሌላዬ ደግሞ ... ይሄንንእኮ ብዙ ጊዜአወራነው። እሺእኔን ተወኝለልጆችስ ቢሆን? በታ ... አትማችን የፈቀደውን ያህል፣ የምንችለውን ሁሉ እንረዳለን። ከዛ በላይ ግን እኔንሽ ... ለእኔ መጀመሪያ ቤተሰቤ ነው ... የኔ ፍቅር። እዚህ ልኑር ብል እኔ ራሴ በድብርት የምሞት ይመስለኛል።" ብላ፣ ፊቷን ጨምዶድ አደረገች።

"ምን ችግር አለ ታዲያ ባልሽ ሳይከትሪስት ... ትታከሚያለሽ።"

"አለመታመም እያለ መታከምን ምን እመጣው ልጄ። አይ ኖው ሌላዬ ... አንተ ያለህ ፍላጎት ይገባኛል። ግን እኔ እንሽ የሆነ መንገድ እንፈልግለታለን እንጂ ኑሯችንን አፈራርሰን እዚህ መምጣቱ አይታየኝም" ብላ፣ ሐሳቡን ስትዘጋበት ነገሩን ባለበት ተወው።

"እኔ ምልሽ ፍቅር ... ለዚች አጭር ጊዜ አዋላ ድረስ ከምንሄድ ለምን ላንጋና አንቀይም? ሳባና ወይ ቫኪሽን ከለብ መሞከር እንችላለን" አለ፣ ከመንገዱ ጸር ተሰልፈው የሚሄዱትን ዝንጆሮዎች እንድታያቸው መኪናውን ቀም አደረገ።

"ጥሩ ነው ... አንተ የመረጥከው ሁሉ ይስማማኛል" ብላ፣ ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች።

"እንዴት ቀድሚ እንጸላሰብኩት ይገርማል። ቀይ እንግዲያው ስለቴ ጋ ልደው ልላት መሰል ... ባለፈው ታይም ሼር አባል ነን ስትል ነበር" አለ፣ ቁጥሯን ከሰልኩ ላይ ለማውጣት እየሞከረ።

እጎቱ ብዙም ሳትቀይ መልሳ ደወለችለት። ክፍል እንዳገኘችላቸውና በደረሱበት ሰዓት መግባት እንደሚችሉ ነገረችው። ቫኪሽን ከለብ ሲደርሱ ወደ ምሳ ሰዓት ላይ ነበር። ክፍላቸው ወደ ሐይቁ አትጣጣፊ ከፊል አይታ ያለው ሲሆን፣ ለሙሉ ቤተሰብ የሚበቃ ራሱን የቻለ ጎጆ ነው። ትልቁ አልጋ ካለበት መኝታ ክፍል ዕቃቸውን አስገብተው ለትንሽ ደቂቃ ጋደም ጋደም አሉ። ከዛም ተለል ያለ ልብስ ቀያይረው መጡና ከመዋኛው ፊት ለፊት ካለው ባር ተቀመጡ። ብዙም ሰው ስላልነበረ አካባቢው ደስ በሚል የጸጥታ ድባብ ተውጧል። ከባሻገር ካለው ሐይቅ እየተነሣ የሚመጣው ቀዝቀዝ ያለ ስስ ንፋስ እየዳሰመረ የመጣውን የፀሐይ ግለት ለስስ አድርጎታል። ባካባቢው ያሉ ወርቅ ዝማሬ ... ለሰለሰ ያለው ሙዚቃ ... የቡና ማሽኑ ድምፅና የምግቡ ሽታ ተስናስሎና ተሰባጥሮ ውስጥን እያባባ ዘና የሚያደርግ ሰሚት አካባቢው ላይ ፈጥሯል።

"ውይ እንኳን እዚህ መጣን ... በጣም ነው ደስ የሚለው። ሐይቁ ቢች አለው እንዴ?" አለች፣ ቀኝ እጁን በእጇ ይዛ የጣቶቿን ቁመት ከርሱ ጣቶች ጋራ እያወዳደረች።

@OLDBOOOKSPDF

"ይመስለኛል ... እዚህ መጥቼ አላውትም። የሳባናውና የበቱለ ሞላ ሆቴሎቹ እንዳላቸው አውቃለሁ"

"ወይኔ ... ሰዓቱ ግን እንዴት ይሄዳል ... ከመቼው ነው ዘጠኝ ሰአት የሆነው" አለች፣ እንደ መገበራራት እያለች።

"ሪሊ? ... ለመዋኘት ካልፈለግሽ በቀር ... መደ ሐይቁ ሞላ በረድ ሲል ብንሄድ የሚሻል ይመስለኛል። ምን አሰብሽ?"

"ወረድ ብለን እንየውና ... ወይ ወደ ከፍላችን ሄደን አረፍ ብለን እንዳልከው በረድ ሲል እንምጣ። አሁን ግን ከመዋኘት ይልቅ ማረፍ ነው ያሰኘኝ ... ምሳውም ነው መሰል ዛል ብያለሁ። አንተ ማረፍ አትፈልግም?" አለች፣ ፊቷ ላይ ድካም እየተነበበ።

"ጥሩ ... መሽት ሲል ሐይቁ ዳር ካምፕ ፋየር አስደርገን ማምሸትም እንችላለን" ብሎ፣ ይረሰኙ ላይ ከፈረመ በኋላ ተነሥተው እጅ ለእጅ እንደ ተያያዙ መደ ሐይቁ ዳር ሄዱ። መቀቱ ከፍተኛ ስለነበረ ብዙም ሳይቆዩ ወደ ከፍላቸው ተመለሱ። እንደገቡ እሷ አልጋው ላይ ጋደም ስትል፣ እሱ ደግሞ ከሻንጣው ውስጥ የጀመረውን መጽሐፍ ፍለጋ መበርበር ጀመረ።

"ምን ጠፋብህ ሌላዬ ..." አለች፣ በደረቷ እንደተኛች ፊቷን ወደርሱ መልላ።

"አይ ምንም ... አንድ የጀመርኩት መጽሐፍ ነበር ... አንቺ ከተኛሽ ትንሽ ባነብ ብዬ ነው።"

"እይ በናትህ ... እዚህ መጽሐፍ አይነበብም ... ና በናትህ አረፍ በል። መንዳቱ አላደከመህም እንዴ?" አለች፣ እጆቿን እየዘረጋችለት።

"አይ ቡናው መሰለኝ ንቅት ብያለሁ። ለነገሩ እሱም ጠፋ መሰል ... እዚህ ያደረኩት መስሎኝ ነበር" አለና፣ ሻንጣውን በግሩ ገፋ አድርጎ አልጋው ላይ እጁን እያሻሸ ቁሞ አለ። እጆን ገትታ ልታስተኛው ስትሞክር አውቀ አጠገቧ ውድት አለላትና ልፊያ ነገር ጀመሩ። ሁለት እጆቿን ይዞ አገጩን እንገቷ ሥር እያስገባ ሆዷን እስኪደክማት ድረስ ሲያስታት ቆየ።

"አውነስ እንቅልፍ አልሄደም ..." አለ፣ እጆን እያላላላት። ሁለት እጆቿን እንደ ምንም አስለቅታ ከቱፐዋሩ መጣችና ከላዩ ላይ ፊጥ ብላ ተራዋን ስትኮርኮረው ቆየች። እንደ ምንም ብሎ ከላዩ ላይ እንዳለች ሁለት እጆቿን ከጀርባዋ ላይ ጠፍሮ ሲይዛት ትግሉን አቁማ ላዩ ላይ ገዘም ብላ ለጥ አለች። በቀስታ እጆቿን ለቅቆ ጀርባዋን ማሻሸት ሲጀምር፣ እሷም ሞንትላቱን እያሻሸች በለውነቷ ውስጥ ስሜቷ በፍጥነት መርመስመስ ጀመረ። ወደ ጆሮው ጠጋ አለችና በሚፋጅ ትንፋሽ በታጀበ ለስላሳ ድምፅ፣ "ሌላዬ የኔ ፍቅር ..." ብላ፣ ሁለንተናዋን ላዩ ላይ ጣለች። ከንፈሮቻቸው ሳይፈላለጉ ተገናኙ።

ጥላ በረድ ሲል የሞና ልብሳቸውን ቀይረው ፎጣቸውን ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው መደ ሐይቁ ወረዱ። አልፎ አልፎ በሐይቁ ዳር ሰብሰብ ብለው የሚያወሩ ሰዎችና ከዳር እየተንበሳበረ የሚጫወቱ ልጆች ይታያሉ።

@OLDBOOOKSPDF

ወደ ሐይቁ ዳር ሲደርሱ ውሃውን በእግሯ ነካ እያደረገች፣ "ውይ በጣም ቀዝቃ ይመስላል መልኩ ... እዚህ ውስጥ ነው የሚዋኘው?" አለች፣ ፊቷን ጨምደድ አድርጋ፣

"መልኩ ነው እንጂ በጣም ንጹህ ውሃ ነው። አፈር እዘል እሸዋ ላይ ስላረፈ መሰለኝ ..." አለ፣ ውሃውን በእጁ ዝቶ መልሶ እያፈሰሰ።

"ግን እይመስልም ... አንተ ዋኝተህ ታውቃለህ እዚህ ውስጥ?"

"ባለፈው አመት የመጣሁ ጊዜ ከእህቴ ቤተሰቦች ጋር ሳባና ነበርን። ንጹህ ነው ግዬለሽም ... ደግሞ ብዙም አይቀዘቅዝም። እንግባ ..."

"ውይ እኔ ይቅርብኝ ..." አለች፣ ቀስ እያለ እግሯን እየመታ የሚመለሰውን ውሃ እያንቦጫረቀች ገንበስ አጎዳለች። ቀስ ብሎ ውሃውን በሁለት እጁ አፈሰና ሲረጫት፣ "ውይይ እማሚ ... ምነው ባትሚዘዝ በናትህ ..." ብላ፣ ሰትንዘፈዘፍ እየሣቀ በሩጫ ውሃው ውስጥ ገባ።

ትንሽ ተግደርድራ እሺም ገብታ ሲዋኙ ቀዩ። ከውሃው ወጥተው ሰውነታቸውን አደራረቁና እዛው ውሃው ዳር ተቀመጡ። እግሩን እስከ ቁርጭምጭሚቷ ድረስ ውሃው ውስጥ አድርጎ ጭንቅላቱን ጭኗ ላይ አንተርሶ በጀርባው እንደ ተጋጋለ የባጥ የቆጡን ሲያወሩ ቀዩ። ቁጭ ባለችበት ባንድ እጇ መፈቱን እንደ ተደገፈች በሌላኛው እጇ ደረቱ ላይ ያለውን ጸጉር እንደመንጨት ሳብ ለቀቅ እያደረገች፣ "ቀይ እንተ ግን ጨክነህ ጥለኸን ላንድ ወር እዚሁ ልትቀይ ነው?" አለች፣ ሲያብሰለስላት የቀየውን ጉዳይ እንደገና እያነሳች።

"ምን ላድርግ ፍቅር ... እኔም እኮ እየደበረኝ ነው ... ግን ደግሞ ምንም ጥሩ ነገር ላድርግ ካልሽ ትንሽ ሀሙም መፍጠሩ አይቀርም።"

"ቀይ እሺ ... አሁን እንተ እዛ ሠርተህና ሌሎች ሰዎችን አስተባብረህ ገንዘቡን መላክ ብትችል ወይም እዛ ካሉ ሳይካትሪስቶች ጋር አንድ ላይ ሆናችሁ ፈንድ ምናምን አሰባስባችሁ ... አለ አይደል እኔ እንኳ ተለቅ ያለ ነገር ካልተደረገ ሩይጻው ምንድነው እዚህ የምታደርገው አይጠቅምም ማለቴ ሳይሆን ..." አለችና፣ የጀመረችውን ሐሳብ ሳትጨርስ ከሐይቁ ባሻገር ወደ ማዶ እያየች ዝም አለች። ከነርሱ ብዙም ሳይርቅ እያጓራ ውሃውን ሰንጥቆ የሚሄደውን ጀልባ ድምፅ ሰምቶ ቀና ብሎ ቁጭ አለ።

"ፍቅር ምን መሰለሽ ... እኔ ላደርግ የምችለውንና ያለብኝን ሌላ ሰው ሊያደርገው ይችላል ብዬ አላምንም። እኔም ደስተኛ አልሆንም። በደንብ ሳስበው እሁን የሚያስፈልገው የዘመቻ እርዳታ ሳይሆን ሥር ነቀል ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ዘላቂ ሥራ የሚሠራ ሰው ነው።"

"እሱ እኮ ይገባኛል ... ግን ከቤተሰብ ጋር እንዴት ሊሆን ነው? ማለት እዚህና እዛ መኖር መቼም የማይታሰብ ነው። እዚህ መኖርን በተመለከተ የተነጋገርን መሰለኝ ... አልገባኝም እንዴት ሊሆን እንደሚችል ... እንተ ኮ ራስህን ማሰብ ያለብህ ቤተሰብ እንዳለው ሰው ነው" አለች፣ ንግግሯን ረገጥ አድርጋ።

@OLDBOOOKSPDF

"ልክ ነው ... በርግጥ መመላለሱ የማይቻል ነው ፣ ምንም ጥያቄ የለውም ። ቀይ መዶ እዚህ መጥተን ብንኖር ችግሩ ምንድነው? ማለቴ በዓላማው ነመንንበት ..." አለ ፣ ብዙ ጊዜ የተከራከሩበት ጉዳይ ቢሆንም የመጨረሻ ፅድሉን ለመሞከር ።

"የምርህን አይደለም መቼም ... እንዴ ... ቀይ የልጅቱስ ጉዳይ? ... እኔስ ብሆን ምን ላደርግ ነው እዚህ? ... እዛ የጀመርናቸው ነገሮችስ? ... እንዴት ነው ምን ችግር አለው ማለት?" አለች ፣ ድምፅዋ የበለጠ ገላ እያለ ።

"ቀይ ሲርየስሊይ ግን ፣ እዚህ ልንሠራ በምንችለውና ልናመጣ በምንችለው ልዩነት ታምኖለሽ? ምንድነው የምትፈሪው እዚህ ጠቅልለን ብንገባ?" አለ ፣ እጇን ይዞ እያሻሸ ።

"ብዙ ጊዜ የተነጋገርን እኮ መሰለኝ ሌላ ... ቀይ እኔ ብድግ ብዬ ሩዋንዳ ሄደን እንኑር ምክንያቱም ብዙ ችግር አለ ... ምናምን ብዬ ላሳምንህ እችላለሁ? ምንም ጥያቄ የለውም ... እዛም ብንሄድ እኮ ጠቃሚ ሥራ እንሠራለን ። አይደለም?"

"ካም'ኦን ፍትር ... ኢትዮጵያና ሩዋንዳንማ እታወዳድራብኝም ... ማለቴ እኛ ኮ አሜሪካ ብንኖርም ሐበሾች ነን ። በርግጥ ሰው ስለሆንን ለሰው ልጆች ሁሉ መልካም ማድረግ ምንም ከፋት የለውም ። አሁን ግን እያወራን ያለነው ... ሀገርም እኮ ቤተሰብ ነው ። አሜሪካ ብንኖር ምኾቱ ጥሩ ነው ... ግን ጥሩ ቤት ኖሮ ፣ ልጅ ወልዶ አላድግ ... ሙሪታ ወጥቶ በምኾት ከመኖር ያለፈ ማሰብስ አያስፈልግም? ከራሳችን ሕይወት የበለጠና ያለፈ የምንኖርለት ነገርስ አያስፈልገንም?" አለ ፣ ባይኗ ዘልቀ ጭንቅላቷ ውስጥ ገብቶ ሐሳቧን ያስቀይር ይመስል አጥልቀ እያያት ።

"እንደሱ ለማድረግ የገድ እዚህ መምጣት አለብን? ልጅን ወልዶ በሥን ሥርዓት ማሳደግና ሃላፊነት ያለው ኑሮ መኖርስ ከራስ ያለፈ ህይወት መኖር ሊባል አይችልም? ፕሲስ ሌላ ... እና ይሄ ሁሉ ካገሩ ወጥቶ የሚኖር ሐበሻ ለራሱ የሚኖር አላማ ቢስ ስግብግብ እንደሆነ ነው የምታስበው?" አለች ፣ ትንሽ በስጨት ብላ ።

"እንደሱ ማለቴ አይደለም ። የሁሉም ሰው የመኖር ዓላማ እንደ ሙልኩ የተለያየ ነው ... እሱን እወ ታለሁ ። ግን ደግሞ የኛስ ምንድነው ብለን መጠየት ያስፈልጋል ። ታሪካዊ በሆነ ጊዜ ላይ ነው ያለነው ... ከሌላው ሰው ይልቅ ከእኛ ብዙ ይጠበቅብናል ። ትዝ ይልሻል ፣ አባቴ ከመሞቱ በፊት ጽሮ የሰጠኝ ደብዳቤ ... እንብቤልሽ ነበር" አለ ፣ ከተጋደመበት ብድግ እያለ ሊያወራት መዳሰበው ጉዳይ መግቢያ ሊሆነው እንደሚችል አሰበ ።

"ያ በሳም ትዝ ይለኛል" አለች ፣ ቀጥሎ የሚለውን በመጠበቅ ዓይነት ።

"በዚህ ጉዞዬ የተረዳሁት እሱ ያለው ነገር ምን ያህል እውነት እንደሆነ ነው ። ዝናሽንና አባቷን ስታዩ ሕዝባችን ተሸክሞ የሚዞረውን ሰቀቃ ታያለሽ ... የምስጢር እናት ያሳለፋትንና በውስጥዋ እምቱው የሚኖሩትን የሥቃይ ፍም ብትሰሚ ... በታ ደሃ የኔ ቢጤው ብቻ ሳይሆን ፣ ያለው የሌላው የሚመስለውም ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሊሆን እንደሚችል ያሳይሻል ። በሳም ብዙ ምሳሌዎች ልንገርሽ እችላለሁ ። ጨርቱን

@OLDBOOKSPDF

ያልጣለውና ጤናማ የሚመስለው ሰው እንኳን ምን ያህል ርዳታ የሚያስፈልገው መሰለሽ ። ግን የት ይዘዳል? ... ችግሩን በትክክለኛ ሰው ለመጥራትና ለመረዳት እንኳን እኮ ገና መሠረታዊ ሥራውም አልተሠራም ..." አለ ።

"ታዲያ ይሄ ካባትህ ይብዳቤ ጋር ምን ያገናኘዋል?" አለች፣ ፊቷ ላይ ገረመጋባት እየታየባት ።

"በደንብ ነው እንጂ ... እሱ እንዳለው ያለነው በቱሰሰች ሃገር ... ኑሯ በተሰበረች ሕዝብ ... በድህነት ... በእስተዳደግ ... በተፈራራቂ ሮርነትና ግጭት ውስጥ ልቦናው በተጉሳቁለችበት ሕዝብ መካከል ነው ። የተፈራረቀበትን ሰቀቃ ሰታስቢው፣ ብዙ ሥራ ይጠብቀናል ። አባቱ ደግሞ ባለፈው የለውጥ ጊዜ ዋነኛ ተዋናይ ስለነበረ ራሱ ካየውና ከተሳተፈበት ተነሥቶ በሕዝቡ ላይ የደረሰውን ሰቀቃና መከራ ምን ያህል እንደሆነ የጻፈው ትዝ አይልሽም? ሳስበው እሱ የሳለብንንም እደራ ለመፈጸም ከዚህ የተሻለ ጊዜ ያለ አይመስለኝም" ብሎ፣ በጁ የያዘውን አሸዋ ጭምት አድርጎ መልሶ በተነው ።

"እውነቱን ንገረኝ ካልከኝ ... እኔ ይሄ ሁሉ ብዙም አይገባኝም ። በሐሳቡ ላይ ምንም ተቃውሞ የለኝም፣ ግን ትልቁ ጥያቄ እንዴት የሚለው ነው ። እሱን ልታስረዳኝ ትችላለህ?" ብላ፣ አቀማመጧን አስተካከለች ።

"እሺ ልሞክር ... በመጀመሪያ ባንድ ጊዜ ጠቅልለን እንሥጣ አይደለም የምለው ። እውነቱን ንገረኝ ካልሽኝ እሱም ቢሆን ለኔ ደስ ይለኛል ። በመጀመሪያ ባሁት የተወሰነ ጊዜ መመላለስ ያስፈልገኝ ይሆናል ። የማስበው አንድ ማዕከል መክፈት ነው፣ የሕክምና የሥልጠናና የጥናት ማዕከል ። ዋናው ትኩረቱ ሐበሻዊ የሆነ የሥነልቦናና የአእምሮ ሕክምና መንገዶችን እሁን ከተደረሰበት ሳይንሳዊ መንገድ ጋር አዋሕዶ የሚሠራና የሚያጠና ።

"በሕዝባችን ውስጥ ያለውን ስቃይና ሕመም ማጥናትና ማስተማር ... ደግሞ ሚዲያውን በተቻለ መጠን በመጠቀም ብዙኀኑን ማንቃትና ማስተማር ሊሆን ይችላል ... የተዘነጋውን ሥነልቦናዊ ሕይወቱን፣ በአጠቃላይ በፖለቲካው፣ በማህበራዊ ኑሮውና በእምነቱ ላይ ያለውን ተጽዕኖ እንዲረዳ ማገዝ ... ብዙ ነው" ሲል፣ እንደ አንድ ሰባኪ ስትሰማው ቀይታ መልሰ መስጠት ስላልፈለገች ገዘም ብላ ታየው ጀመር ።

ያበጠው ይፈንዳ በሚል ዓይነት ንግግሩን ቀጠለ ። "ከትናንት ወዲያ ሚስጥርና እናቷ እናገረውኝ ነበር ። አንድ ለኪራይ ክፍት የሆነ በጣም ትልቅ ቤት ወዴ አራት ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ያለው ግቢ አላቸው ። ከሊኒክ መክፈት ካሰብኩ ልጠቀምበት እንደምችል ነግረውኛል ። ያው ከንቺ ጋር ተማክረን ቦታውን ባየው ደስ እንደሚለኝ ነግሬያቸዋለሁ ። ስለ ቦታው ሲነግሩኝ በቀደም ሲሰተር ዘቢባ ቤት ባሷ ያለው ነው ትዝ ያለኝ ። የሆነ ነገር ለመጀመር ጊዜው ይመስለኛል ... ምን ታስቢያለሽ አንቺ?" አለ፣ ዓይን ዓይኗን እያየ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ምንስቢመስለኝ ምን ለውጥ ያመጣል ሌላ? ይሄ ውሳኔ በቤተሰባችንና በኑሯችን ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥና ሚና ግን አሰበኸዋል? ይገጥሞ ከሕመምተኞች ጋር ፕሬብ ነክ በሆነ ጉዳይ መነካካቱ ከሕዝቦና ሥነምግባር አንጻርስ ጥሩ ነው? ... እሱንስ እስቢላታል" አለች ፣ ከምስጢር ጋር ያለው ትርርብ መጨመር አንዳች ያለ የማይል ስጋት እየፈጠረባት ።

"እንዴት ነው ለውጥ የሌለው? ታዲያ ይሄንን ሁሉ የግግክርሽና ምንጨቃጨቃው ለውጥ ስላለው አይደል እንዴ?" አለ ፣ በስጪት ብሎ ። ትዝትዝ ሲላት ቀጥል በሚል አይነት ዝም አለች ። "በቤተሰባችን ላይ ለውጥ እንደሚያመጣ ሳላሰበው አልቀረሁም ። ግን እኔና አንቺ ከተስማማንና ካመንበት ሁሉም ነገር ጥሩ ይሆናል ። ችግሩ እኛ መስማማት ካልቻልን ነው ። ስለ ቦታው ጉዳይ ያልሽውን እኔም እስቢኖለሁ ። ግን ሚስጥርም አሁን ማስተርሲን ስትጨርስ የክሊኒኩ ስታፍ መሆን ትችላለች ። እናቷም ከተሻላቸው እኔን ማየት ላያስፈልጋቸው ይችላል" አለና ፣ ነገሩን ለማትለል ሞከረ ።

"እንድ ጊዜ ሕመምተኛህ የሆነ ሁሌም ሕመምተኛህ ነው' የሚለውን በሕመምተኛና በሐኪም መሃል ያለውን የግንኙነትን ድንበር የሚወስነው የሞራል ደንብ ትዝ ሲለው ደግሞ እናቷ ናቸው እንጂ ምስጢር ሀመምተኛዬ አይደለችም ብሎ በውስጡ ራሱን ለማሳመን ሞከረ ።

"ገንዘቡንስ አሰበኸዋል? እርግጠኛ ነኝ አንተ ያሰብከውን ዓይነት ማዕከል መክፈት ቀላል አይደለም" አለች ፣ በታከተ ድምጽ ።

"አዎን ... ትልቁ መሰናክል እሱ ነው ። ያሰብኩት ወይ እንደ ሼር ካምፓኒ አድርጎ መጀመር ነው ... ብቻ እኛ ከተስማማን መንገድ ይጠፋለታል ብዬ አላስብም ። ቦታውን ከመሄድሽ በፊት ብናየውስ?" አለ ፣ የሚጠብቀውን ተግዳሮትና መሰናክል አሰበና ውስጡ ያንሰራራው ተስፋ ሲገዘገዝ ተሰማው ።

"ይሰ እንዳለህ ፣ በፈለከው ጊዜ ማየት እንችላለን" አለች ፣ ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ ። በመካከላቸው ጸጥታ ሰፍኖ ይቂታዎች አለፉ ።

ፀሐይዋ የቀን ዙረቷን ጨርሳ ለማታው ተረኛ ለማስረከብ ማዘትዘት ጀምራለች ። ሐይቁ ላይ ያረፈው ጨረር በወርቃማ ነጸብራቁ አካባቢውን ያበልጥ አድምቀታል ። ከሐይቁ እየተነሣ ሽው የሚለው ነፋስ ቀዝቀዝ ማለት ጀምሯል ። በሐይቁ ጸር ጥቂት ጎጆች ውሃውን እያንቦጫረቁና እየተጫወቱ ሲያዘግሙ ይታያሉ ። በውሃው ላይ ወዲያ ወዲህ ብር ብር የሚሉት ወፎችም በራሳቸው ዓለም ይባትላሉ ። ራት ብለው ደንም በዛ ያሉ ልጆች እየተንጫጩ ይዋኛሉ ። ሰሞኑን ምንም ስላልዘበ ከእጂስ አክፍ ሽብና ጭቃ ሸሸተ የመጣ ተገናኝ ላያደሰት አይተርም ። አንድ ሶስት ቢት ደፕም ቁማታ አሳት ለማዘጋጀት የድርጅቱ ሠራተኞች ላይ ታች ይላሉ ።

ነገሩ ከተጀመረ አይተር ውስንም ሃላቡን አውርት መነላገል የፈለገው ሌላሙ ጥቂት በሃሳብ ሲናጥ ቀየና ፣ "ሌላሙ ትዝ ይልሽ ዘሆን ሌላውቅም ... አንድ ሃይ ሰ ል

@OLDBOOOKSPDF

እያለሁ ገነት የምትባል ባደኖ ነበረችኝ ብዙሽ ነበር። የመጀመሪያ ገርል ፍሬንዴ" ብሎ፣ ዝም ሲል ከገባችበት የራሷ የሐሳብ ባሕር ጠላች።

"ያ ... ትገ ይለኛል። ምን ተገኘ?" አለች፣ የማወት ፍላጎቷ ቢገርም ነገ እንደሌላት በመምሰል።

"እይ ምንም አልተገኘም ... ግን ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ከደምሮዬ አልወጣ ብላኛለች። ምን ያህል ገርገሩን እንደ ነገርኩሽ ትገ አይለኝም። በተለይ እውነ ገናሽን ማዘም ከጀመርኩ ወዲህና አባቷም የሥጋ ደዌ ታማሚ መሆናቸውን ምኑን ሳውቅ ... የበለጠ ማሰብ ጀመርኩ መሰለኝ" አለና፣ ፊቷን እያጠና ዝም አለ።

"ብዙም ገርገሩ ትገ አይለኝም ... እንተ መዳሚሪካ ልትመጣ ሰትል ድንገት ብድግ ብላ እንደ ጠፋች ምናምን እንደ ነገርከኝ ትገ ይለኛል" አለች፣ በእጅጉ መሬቱን ተደግፋ ወደ ኋላ ሰጠጥ ብላ እንደ ተቀመጠች።

"ለናቷ ብቸኛ ልጅ ነበረች። አባቷ ከሞቱ በኋላ እናቷ ነበሩ እንጀራና ጣላ እየሸጡ ያሳደጓት። ሰባተኛ ክፍል ሆነን ተቀራረብንና በዛው በአድሜ ከፍ እያልን በጓሄድ ግንኙነታችን ወደ ፍቅር ባደገንበት ተለመጠ። በመሃላችን የተፈጠረውን የናቱ ግንኙነት ያልወደደችው እናቴ፣ ከእህቴ ጋር ተመካክረው አሰራ እንደኛ ክፍል ላይ ወዳሚሪካ እንድመጣ አደረገች። የመሄዴን ነገር ለነገት ስነግራት በጣም ነበር ያዘነችው ... አልቅሳ ልትፈነዳ ነበር። ድንገት ስትጠፋብኝ ጊዜ ቢታችው ሄድኩኝ። እናቷ ልታናግረኝ እንደማትፈልግ ደጋግመው ነገሩኝ። የሳቸውም ፊት ተሰሞውሞብኝነበር፣

"በቅን አሥር ጊዜ እየተመላለስኩ ላስቸግራቸው የጻፈችልኝን አጭር ደብዳቤ ሰጡኝና ሁለተኛ እየመጣሁ እንዳላስቸግራቸው እያለቀሱ ነገሩኝ። ደብዳቤው ሲገባኝ ስላልቻለ ከሦስት ቀን በኋላ አላስችል ብሎኝ ተመልሼ ስሄድ፣ ቤታቸው ከውጭ ተቀልፎ አገኘሁ። ተመላልሼ ጎረቤቶቻቸውን ብጠይቅም ማንም ምንም እንደማያውቅ ነገሩኝ። በዛው ወዳሚሪካ መጣሁ። ነገሩን ለመርሳትና ለመረጋጋት ብዙ ጊዜ ነበር የወሰደብኝ። ከብዙ ዓመታት በኋላ የመጣሁ ጊዜ፣ ሰፈራቸው ብሄድ ሁሉም ነገር ተቀያይሮ ማንነታቸውን የሚያውቅ ሰው እንኳን ስላላገኘሁ ተስፋ ቁርጬ ተውኩት" አለና፣ በእግሩ ውሃውን መልሶ እየመታ፣ በሁለት ክርኑ አሸዋው ላይ ደኽ ብሎ ዓይን ዓይኗን እያየ ዝም አለ። ጸጥ ብላ ስታዳምጠው ቆየችና፣

"ታዲያ ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ አሁንም ተገኘ? ማለቴ የት ብለህ ልትፈልጋት ነው?" አለች፣ ግራ በመጋባትና የነገሩ አካሄድ ስላልገባት።

"የሷም እናት እንደ ገናሽ አባት የሥጋ ደዌ ታማሚ ነበሩ። ለሕክምና መጥተው ነው እዚሁ አዲስ አባባ የቀሩት። የሚኖሩትም አሁን የገናሽ አባት የሚኖሩበት አከባቢ ነበር። የገናሽን አባት ጠይቂያቸው ሊያወጧቸው አልቻሉም። ግን ደግሞ የሆነ ተአምር ነገር አደረብኝ። ምናልባት ወይ እሷን ወይ እናቷን ባገኛቸው ይሆንን ሁሉ ዓመት ያልተመለሰልኝ ጥያቄ ድምጻሚ ያገኝልኝ ይሆን ብዬ አሰብኩ"

@OLDBOOOKSPDF

"ብታገኛት ምን ታደርጋለህ?" ስትለው ፣ ያላሰበው ጥያቄ ስለነበር ፣ ትንሽ ጸጥ ብሎ ቆየና ፣

"ምንም ... ያው እንዳልኩሽ ሲያስታየኝ ለኖረው ጥያቄ መልስ የሚገኝ ይመስለኛል ... በቃ" አለ ። የጥያቄዋ ዓላማ ምን እንደሆነ አልገባውም ።

"ያኔ ስትጠፋ አርግዛ ሊሆን ይችላል?" ፈጽሞ አስቦት የማያውቅ ጉዳይ ስለሆነ ተምታታበት ።

"እኔንሽ ... ብታረግዝ ኖሮ ለምን ትዘጋኛለች ... በሰላም ተለያይተን ነው በሚተዋለው ቀን በግታኝ በሃው የጠፋችው ... አይመስለኝም" አለ ። ነገሩ ሊሆን ይችላል ብሎ ሃሙን አልፈለገም ። ሃሳብ ውስጥ ገብቶ ሙልጥ አለ ።

"ልጅህን ይዛ ... በተሰፋ ይሄንን ሁሉ ዓመት እንተን እየጠበቅሁህ ነው ብትልህስ?" አለች ፣ እንቅትልሻዊ የሆነ ፈገግታ እያሳየችው ።

"ታኘፊያለሽ እይደል...? የምናወራው እኮ ... ከብዙ ዓመታት በፊት ስለሆነ ታሪክ ነው ..." አለ ። ሰምን ንጹሕ ቁጣ ቁጣ እንደምትልና የሱ ሙንትት ሊገባት እንዳልቻለ ግራ ገብቶታል ።

"የልጅነት ፍትረኛህን መፈለግ ... ያባትህን አደራ መወጣት ... አገሪቱን ማዘም ... ጥሩ ነው ። " ለረጅም ደቂቃ ተጠንቅቃ ስትገነባ የቀየችው የሚያምር የአሸዋ ቤት ባንዴ አፈራረሰችው ። "እሺ ፣ በዚህ ሁሉ ውስጥ ታዲያ የኔ ድርሻ ምንድነው? እቤት ወጥ ሰተቅል እየሞልኩ ማታ ስትመጣ 'ገነትን አገኘሃት... አገሪቱ ተሻላት...' ማለት ነው ... ወይስ?" ብላ ፣ ነፈራረሰችው ያሸዋ ቤት ላይ እጇ የቻለውን ያህል አሸዋ ዛቀች ። ቀስ ቀስ እያደረገች መልሳ ፍርስራሹ ላይ አፈሰሰችው ።

"አልገባኝም ... ምን ማለት ነው? የኔ ሕይወት ያንቺ ነው ... ያንቺም የኔ ነው ። እኔ ውስጤ ያለውን ሁሉ አወጥቼ የማካፍልሽ ... ሁሉም ነገር አንቺንም ስለሚመለከትሽና ያንቺም ስለሆነ ነው ። " እጇን ለመያዝ ሲሞክር አሸሸችበት ። ሊያቅፋት ጠጋ ሲላት ከተቀመጠችበት ብድግ ስትል እጇን ይዞ ወደ ራሱ እየሳባት "ምነው ... ገና ኮ ነው ..." ሲል ፣ እጁን በሌላኛው እጇ ፈልቅቃ አስለቀቀችው ።

"ለብቻችን እዚህ እንድንመጣ የፈለግኸው ይህንን ልትነግረኝ ነበር ፣ እይደል? ሌላስ የምትነግረኝ ነገር አለህ ...መይስ? ... በናትህ አሁን ትንሽ ከራሴ ጋር መሆን እፈልጋለሁ ። አትቸገር ... ሁሉም ነገር ገበቶኛል" ብላ ፣ መራመድ ስትጀምር ሊከተላት ብድግ አለ ። "ፕሊስ ሌላ ... ትንሽ ጊዜ ለብቻዬ መሆን ነው የምፈልገው ... በናትህ አትከተለኝ" ስትለው ግራ ገብቶት በተቀመጠበት ቀረ ።

ፊቷን አዙራ ነጠላ ጫማዋን በጇ እንደያዘች ፣ ወደ ፀሐይ መጥለቂያ አቅጣጫ በሐይቁ ዳር ዳር ስትሄድ ፣ እርሱ ደግሞ ግማሽ እግሩን ውሃው ውስጥ እንደነከረ በጀርባው ተጋደመ ። ውሃው እትመውን እየተያየረ እንዴ ቪ ... ደግሞ ቄ እያለ ይመጣና እስከ ጉልበቱ ድረስ እያረሰው ተመልሶ ወደ ኋላ ያፈገፍጋል ።

@OLDBOOOKSPDF

ቀና ብሎ ሲያይ ንጹሕ ብዙ ርቃ ሄዳለች። በሐዩቱ ኃይለ ጽድ መኖ እርሷ ስትመጣ ከሩት የምትታየው እቢ ስለ መሰለችው፣ እሳው ሊጠቂት ጠነ። ዶሊየ እንደጠለቀች ስማዩም በፍጥነት ዝናብ ባረገዘ ደመና ተጋረደ። ጨለምለም ብሎ ጓደኛ ያገዛማድረግ ሲጀምር ተነስቶ ተቅመጠና ዙሪያ ገባውን አማተረ። መጣሁ መጣሁ ሲል የቀየው ዝናብ መንጠባጠብ ሲጀምር፣ ዘተቅመጠበት ተነስቶ ንጹሕ ወደ ሄደችበት አቅጣጫ መሮጥ ጀመረ። ከሩት ያያት ሴት እቢ አለመሆኗን ሲያውቅ ደነገጠ። በልቡ ዳርቻ እስከ ጫፍ ድረስ ቢፈልጋትም ሊያገኛት አልቻለም።

ምሽቱን ሁሉ ዝናቡ ሲያላዝንበት ስለቆየ ደጅ እባት ለማንደድ ሳይችሉ ቀሩ። ራታቸውን እንደነገሩ ቀማምሰው ምንም ሳይነጋገሩ ወደ ዘፍላቸው ሄዱ። ከሊጅኗ ትገሽ እውርታ ስትጨርስ፣ ስልኩን ለርሱ ሰጥታው ጥቅልል ብላ ተኛች። ሊያናግራት ቢሞክርም፣ ለማስብ ጊዜና ጸጥታ እንደምትፈልግ በአጭሩ ነገረችው። በየራሳቸው ዓለም ገብተው፣ እሱ በጀርባው እቢም በደረቷ ተኝተው እንድም ቃል ሳይለዋወጡ ሌሊቱ ነጋ።

ቁርስ ላይ ላንጋኖ መቀየት እንደማትፈልግና የምትሠራቸው ነገሮች ስላሏት፣ አዲስ አበባ መመለስ እንደምትፈልግ ነገረችው። መንገዱን ሁሉ ያለ መትጅቸው ደኖ ብለው፣ በየራሳቸው ሃሳብ ሲዳክሩ ቀዩ። ሐሳቡን እንደገና ለማስረዳት መሞከሩ ዋጅነ ሊያባብስ ይችላል ብሎ ስለፈራ፣ እሱም ዝምታን መረጠ። ሐሳቡን ላይቀያር ነገር ከርሱ ጋር ምን አዳረቀኝ በማለት፣ የተነጋገሩት ነገር በርሊም ልብ ስጥታ ሲብሰለሰልና ሲንተከተክ አዲስ አባባ ገቡ።

የቀሩትን ሁለት ቀኖት ምንም እንዳልተፈጠረ ካንገት በላይ እየተነጋገሩ ግሜታቸውን በውስጣቸው ቀብረው ያላለቁ ነገሮችን ለመጨረስ ላይ ታች ሲሉ ቀኑ ለዘሊኒክ የታሰበውን ቦታም አብረው ሄደው አይተው ምንም መናገር ስላልፈለገች 'ጥሩ ነው' ብላ ዝም አለች። ቦታውን ውስጢ ቢመደውም ሐሳቡን አውጭ አልተቀበለችውም። በሌላውና በምስጢር መካከል ቅርርብ ሊፈጠር ይችል ይሆናል የሚል ሀሳብ በእእምሮዋ ሲጸነስ፣ የማትፈልገው ስሜት ውስጢ ተፈጠረ። ቢታውን ለማየት ሲሄዱ ልጆቹን ይዘው ነበር። ምስጢርና ሕፃናቱ እየተጋጋጠ በሚከው ውዝግ ድብብቆሽ ሲጫወቱ እያየች ልጅቷን በማታውቀው ነገር በመጠርጠሯ፣ ብርቅ ደነት ተሰማት።

በማግስቱ ንጹሕና ልጆቹ የሚሄዱበት ቀን ስለነበር ሁሉም ቅፍፍ ብሊቾ ሞሉ። ማታ ላይ እየር ማረፊያ እስኪደርሱ ሕፃናቱ የሌላውው አለመሄድ እውነት አልመሰላቸውም ነበር። እንደማይሄድ ቁርጡን ሲያውቁ እያለቀሱ አስቸገሩ። በብዙ ማባበያ ተለምነው እሱ ራሱ ይዟቸው ወደ ውስጥ ገቡ። ብዙ ነገር ታል ገብቶላቸውና ለትቢቸውን ያቀመጡት። በተለይ እርሲማን ማሳመኑ ከለበው በላይ ከባድ ነበር።

@OLDBOOOKSPDF

ከንጹሕ ጋር ሲለነባበቱ እቅፍ አድርጓት ፣ "የኔ ቀንጆ ... ይቅርታ ስለ ሁሉም ነገር ... በጣም እንደምወድሽ እወቂ ... በምችለው ጥያነት እመጣለሁ ... ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል" ብሎ ሲስማት ፣ እንባዋ ግጥም አለና ደረቱ ላይ ልጥፍ አለች ። ከንፈሩ ላይ ሳም አድርጋው ያጉተመተመችው ነገር ሳይሰማው በለቅሶዋ ውስጥ ተዋጠ ። መለስ ቀለስ እያሉ እጃቸውን የሚያወለበልቡትን ሁለቱን ልጆች ግራና ቀኝ ይዛ የሺዛ ኬላውን አልፈው ወደ ውስጥ ገቡ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡15፡

ሌላሠው፡ በየቀኑ ንጹሕንና ልጆቹን በስልክ ቢያገኛቸውም፣ ገና በላምነቱ ናፍቅታቸው፡ ጠንቶበታል። ከአውሮጳ ከመጡ ሁለት የልጅነት ጓደኞቹ ጋር ናዝሬት ው·ሎ፣ ከመሸ ነበር ወደ ቤት የገባው፡። እናቱም አዲስ የገዙትን ጋቢ እየጻጩ ልባቸው ስቅል ብሎ ሲጠብቁት ደረሰ። ራት በልቼያለሁ ስላለ በቴርሙስ ጠረጴዛው ላይ ከተቀመጠው ሻይ ላይ ቁጨስትና ትንሽ አሜው·ቷቸው፣ ው·ልቅልቅ ያለ ሰውነቱን እየጮተተ ወደ መኝታ ቤቱ ገብቶ የቀዘቀዘ አልጋው· ውስጥ ተጠቅልሎ ተኛ፣ አብባኛው·ን ሌሊት ወዲያ ወዲህ ሲገላበጥ የረባም እንቅልፍ እንቅልፍ አልወሰደውም፣

ማለዳ ላይ ከራስጌው· ኃይል እየተሞላ ያለው· የእጅ ስልኩ ሲጮህ ብንን ብሎ ነቃ። መንጋቱን ለማሳበቅ ይመስል ደብዘዝ ያለው· የጠዋት ብርሃን በመስኩተቹ ገብቶ ክፍሉን ፈካ አድርጐታል። ዓይኖቹን አሻሽና ስልኩን እንሥቶ መለሠ። ከአግኦል ሆስፒታል የገናኘ ነርስ መሆኗን ሲያው·ቅ፣ ተነስቶ ተቀመጠ።

"ይሰማኛል ሲስተር ... ሰላም ነው?" አለ፣ ችግር ባይኖር በዚህ ሰዓት እንደማትደው·ልለት ስላወቀ።

"ይቅርታ ዶክተር በጠዋት ደወልኩብህ። ትንሽ ካቅም በላይ የሆነ ችግር አጋጥሞን ነው·። ሌሊት ላይ ገናኘ ምጥ መጥቶባት ጥቁር አንበሳ መሰደናት ነበር ..."

"እሺ በሰላም ተገላገለች?" አለ፣ በጥድፊያ።

"ምን ባክህ ድንገተኛ ክፍል ካማኑኤል ሆስፒታል መሆኗን ሲያው·ቁ፣ በደንብ ሳያዩዋት ገና ናት ብለው· መለሲት። ተመልሳ ግቢ ገብታ ካንቡላንሱ እንደ ወረደች እሷን ላይ እንኳን ሳትደርስ ኮሪደር ላይ ወለደችብን። እንግዴ ልጅ አልወጣ ብሎን፣ ብዙ ደም ፈሰሰላት። መጨረሻ ላይ እንግዴ ልጁ ሲወጣ፣ ማኅፀኗ ወደ ቦታው ሊመለስ አልቻለም። ደሟን ማቆም ስላልቻልን፣ አምቡላንስ ጠርተን ጉሉኮስ ቀጥለንላት ወደ ጳው·ሎስ በድንገተኛ ላክናት" ብላ፣ ትንፋሽ ለመሳብ ገዘም አለች።

@OLDBOOOKSPDF

"እና አሁን እንዴት ናት?" አለ፣ የበለጠ ነቅቶና ወደ መስኮቱ ተጠግቶ ውጭ ውጪውን እያየ፣ በስጋት እንደተወጠረ።

"ይዛት የሄዶችው ስታፍ አሁን ነው ደውላ እንደምትነግረኝ ... ይኼው አንድ ሰዓት ሙሉ ማንም ዞር ብሎ አላያትም። ድከምከም ብላለች ነው የምትለኝ። እባ የምታውቀው ሐኪም ካለ ብዬ እኮ ነው። በቃ የኛ ሕመምተኞች ለነርሱ ለውም አይመስሏቸውም ..." አለች ብስጭት ብላ።

"እሺ እኔ ራሴ አሁን በቻልኩት ፍጥነት ወደዛው እሄዳለሁ። እስኪ እየሄድኩም ለመደወል እሞክራለሁ ... በጣም ነው የሚያሳዝነው።" ስልኩን እንደያዘ ፊቱን ለመታጠብ ወደ መታጠቢያ ቤት ተጣደፈ። ስልኩን ከዘጋ በኋላ በጥቂት ደቂቃዎች ከቤት ወጥቶ ወደ ጳውሎስ ሲከንፍ ሄደ። ስልኩን ያነሳለት ሰው ሰላልነበረ ውስጡ የነበረው ጭንቀት የበለጠ ናረ። ጠዋት እንድ ሰዓት አካባቢ ስለነበረ በቀለበት መንገዱ በኩል ገብቶ ካሰበው ፍጥነት በላይ ደረሰ። መኪናውን እንደ ነገሩ አቁሞ በሩጫ ዋናውን የሆስፒታል በር አልፎ ባይውን ኮሪደር እየቀዘፈ ከማጎዐንና ጽንስ ድንገተኛ ክፍል ዘውብሎ ገባ። ሰአቱ ጠዋት እንድ ሰዓት ተኩል ዕለተ ሰኞ።

በክፍሉ የፊተኛ ክፍል ውስጥ ካሉ ሁለት ዴስኮች ላይ አንድ በስልክ ተጠምዳ እየሚቀሯ የምታወራ ነርስና ሌላ ካርዶች እያገላበጠ ለጠዋት ስብሰባ የሚዘጋጅ ልጅ እግር ቀጠን ያለ ኢንተርን ሐኪም ነበሩ ያሉት። ትንፋሹ ከላይ ከላይ ቁርጥ ቁርጥ እያለ፣

"አንድ እዚህ አሁን ጠዋት ላይ ያመጧት ዘመድ ነበረችኝ ... አሲን ለማየት ነበር" ሲል፣ ሁለቱም ከቁም ነገርም ሳይቆጥሩት የጀመሩትን ቀጠሉ። አሁንም ድምፁን ጮሳ አድርጎ "አሁን ጠዋት ላይ የመጣች ዘመድ ነበረችኝ ... ዝናሽ ትባላለች። የትና እንዴት እንደ ሆነች ሊነግረኝ የሚችል ማነው?" ሲል፣ ሁለቱም ቀና ብለው አዩት።

ሴቷ ነርስ ስልኳን ከጉንጯ ላይ ዞር አድርጋ ዙሪ እንዳለች "ካማኑኤል ያመጧት ናት?" አለች፣ እሱን ጠይቀው በሚል ዓይነት አገጯን ከካርዶቹ ውስጥ ተቀብሮ የጠዋት ሪፖርቱን ከሚያጠናቅረው ዶክተር ላይ እየጠቀመች።

"እምን ... ዝናሽ በድሉ ነው ስሟ። እንዴት ናት?"

እትረብሸኝ በሚል የተሰላቸ አይታ ገረመመውና፣ "አሁን በቅርብ ሰዓት ነው የመጣችው መሰለኝ። ሌላ አጣዳፊ ኪዝ ስለነበረን አሁን ገና ነው ከኦፕሬሽን ክፍል የመጣሁት። የጠዋት ገቢዎቹ ያዩዋታል። ትንሽ ሳይኮቲክ ነገር ስለነበረች በትክክል ላናያትም አልቻልንም። ሲስተር እንዴት ናት አሁን?" ኳሱን መልሶ ወደሷ ሚዳ አሻግሮ ያላለቀ ሪፖርቱ ላይ ተጠመደ።

ሌላሠው ነገሩ ቢያናድደውም ሰሚቱን እንደምንም ተቆጣጥሮ ፊቱን ወደ ነርሲ መለሰ። "የት ናት ያለችው አሁን?" አለ፣ ረጋ ባለ ግን ደግሞ ቆጣ ባለ ድምፅ።

"በዛ በኩል ወደ ጓዳ አሊችልህ። አብራት የመጣችው ጤና ሪዳትም አጠገቧ ናት መሰለኝ" ስትለው፣ በፍጥነት ችኮት ወደ ውስጥ ሄደ።

@OLDBOOKSPDF

መኝዳው'ን በተደረደሩት የድንገተኛ አልጋዎች ላይ ወዳለችው ብቸኛ ሕመምተኛ በፍጥነት ሄደ። አጠገቧ ሲደርስ ሰስ የሆስፒታል አንሶላ ጣል ተደርጎላት ደረቅ የማኅፀን አልጋ ላይ በጀርባዋ ተጋድማለች። እጁ ላይ የተተከለ የጉሉኮስ መስመር ቢኖርም፣ ውስጡ ያለው ፈሳሽ አልቆ ባዶ ከረጢቱ ተንጠልጥሏል። ጠጋ ብሎ ሲያያት ግባር ላይ ላብ አቸፍቸፍና ከንፈሮቿ ድርቅ ብለው፣ ጉንጮቿ ሰርጉደው ዓይኖቿ እኒ ተከደኑ፣ ሌላኛው እጁ ወደ መሬት ተጠንጠልጥሏል።

የጽዳት ኬሚካሉ ጠንካራ ሽታ፣ ከትኩስና የቆየ ደም ጋራ የፈጠረው ጠንካራ ጠረን፣ በዘፍሉ ውስጥ ያለው ቅዝቃዜና ዝብርገዝርት ያለው የዕቃዎቹ አቀማመጥ ተደበላልቆ ለጥቂት ደቂቃ ማሰብ ተሳነው። የተንጠለጠለውን እጁን ብድግ እድርገ ሲይዘው በረዶ ሆኗል። የልብ ምቷን ለማግኘት ሞከሮ ሲያትተው ሙክ ብሎ፣

"ዝናሽ ... ዝናሽ ... ትሰሚኛለሽ? ... ሌላሠው ነኝ" ብሎ፣ ደጋግሞ ጠራት፣ ዓይኖቿን በግድ ከፈት አድርጋ የሆነ ነገር ለማለት ከንፈሯን እንቀሳቅሳ ሲያትታት ደካማ ፈገግታ አሳይታው አይኖቿን መልሳ ከደነቻቸው። ላይዋ ላይ ጣል የተደረገውን አንሶላ ገለጥ ሲያደርገው በራሷ ደም ተነከራለች። ለትንሽ ጊዜ ያለበት ሁሉ ዞረበት፣ አልጋውን ደገፍ ብሎ ቆመ። ዞር ሲል በቁጣ የተሞላችውን ነርስ፣

"ሲስተር ምንድነው እያደረጋችሁ ያላችሁት? ይኼ ድንገተኛ ክፍል መስሎኝ አለ፣ እንዴ ወደ ጉሉኮሱ፣ እንዴ በደም ወደ ራሰው የገነና ሰውነት እያየ። የጉሉኮስን መስመር ለመክፈት ይመስል ነካ ነካ ስታደርግ ጎዴቱን መቆጣጠር አቅቶት፣ "ምንድነው የምታደርጊው? ...ከረጢቱ አይታይሽም እንዴ ተሟሞ ያርቀ? ልጅቷ እኮ ሾክ ውስጥ ናት" ሲላት፣ ከባሻገር ካለው መደርደሪያ ውስጥ ሁለት ጓንት አውጥታ እያጠለቀች፣

"እስኪ እንድ ጊዜ ... ቤተሰብ ወደ ደጅ ቀድን ባስቸኳይ ... እዚህ የምንሠራው ሥራ አለ ..." ስትል የንዴት ሣቁን ለቀቀው።

"የኔ እመቤት ይልቅ መጀመሪያ ... ተረኛ ዶክተር ካለሽ ባስቸኳይ ጥሪ ... ከሷ የሄንን ባዶ ከረጢት ቀይሪና ባስቸኳይ ሌላ ፍሉድ ቀይሪላት" ሲላት፣ ደንገጥ ብትልም የመጨረሻ ሙከራ ይመስል፣

"ሥራዬን አንተ አትነግረኝም ... ውጣልኝ አሁን እንሥራበት" ብላ ተመነጫጨቀች። ዝም ብሎ ጥሏት ሐኪሙ ወዳለበት ክፍል ሲሄድ፣ አውንም ቦነ ነገር እየሞነጫጨረ ከነርዶቹ ጋር ግብግብ ገጥሟል።

"ዶክተር ቅድም ያልኩህን ሕመምተኛ ያየኻት አንተ ነህ ወይስ..?"

በግማሽ ልቡ ቀና ብሎ፣ "ምን ... ችግር አለ?" አለና ተመልሶ ሲያተረማ ተንደርድሮ ሄዶ የሚጽፍበትን ወረቀት በትልት እጁ ሸፈነበት።

"የማናግርህ እኮ በሕያወትና በሞት መካከል ስላለች ሕይወት ነው። ስመሆ ምንድነህ አንተ ... ኢንተርን ነህ ረዚደንት?" ሲለው፣ ደንግሞ ቀና አለ። ፍርሃትና ግራ መጋባት በሞላበት ፊት ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ወደ ኋላ አፈገፈገ።

@OLDBOOOKSPDF

"ኢንተርን ልሁን ሬዚደንት እሱ ያንተ ጉዳይ አይደለም ... ምንድነው ችግርህ?" አለ፣ ያለ የሌለ የዶክተርነት ወኔውን አሰባስቦ። ንዴቱ ከቁጥጥር ውጪ እየሆነ የመጣው ሌላሠው የዝናሽ ሁኔታ በምታልፈው በያንዳንዱ ደቂቃ በቀጭን ክር ላይ ያለች ሕይወቷ እያንቀጠቀጠው፣

"እሺ ቻርቷን ማየት እችላለሁ? ታይታለች ወይ? ምን እያደረጋችሁላት ነው እኮ ነው የምልህ?" አለው።

"የኔ ወንድም ... ማንም ተነስቶ የበሽተኛ ቻርት ማየት አይችልም። ደግሞ በመጀመሪያ እንተ ራስህ ማነህና ነው የበሽተኛ ኢንፎርሜሽን የምሰጠህ?" ሲለው፣ ከፊቱ ያለውን ካርድ ገፍቶ አነሣና ማገላበጥ ጀመረ። የዝናሽ ስም ያለበትን ካርድ ሲያገኝ ሌላውን ጠረጴዛ ላይ በትኖ ገላልጦ አየው። ውሰጡ ከተቀመጠው ከአማኑኤል ከተላከችበት ሪፈራል ወረቀት በቀር ምንም የተጻፈ ነገር አልነበረም። "ሰውዬ በህግ እምላክ የበሽተኛ ካርድ ብታስቀምጥ ይሻልሃል። ጥበቃ መጥራቴ ነው።"

ካርዱን ራቱ ላይ ወረወረውና ተንደርድሮ ሄዶ የሽሚዙንና የነጭ ኮቱን ከሌታ ባንድ ላይ ጨምድዶ ከግድግዳው ጋር አጣብቆ ባየር ላይ አንጠልጥሎ ይዘት፣ ጥርሱን እንደ ነከሰ "እንተ ቀርቀሮ ራስ ... አሁን አንተም ሐኪም ትባላለህ። ሾክ ውስጥ ሆና ለሞት ስታጣጥር ... እዚህ ተጎልተህ ... የበሽተኛ ኢንፎርሜሽን ምናምን ትለኛለህ? ምንድነው የሚያስተምሯችሁ? ... ቢያንስ ብለድ ታይፕ ... ክሮስ ማች እንኳን መቼ አስርተህ ነው? እንዴት አይቪ ፍሉድ እንኳን አትሰጪትም... ባታውቀው ነው እንጂ የሶስት ሕፃናት እናት ናት። ደግሞ ሳይኮቲክ ናት ትለኛለህ እንዴ ... ለመሆኑ ከመጣች አይተሃታል? ... ሀሊና ቢስ ... ካንተ ይሄ ግድግዳው ላይ ሲንቀዋለል የሚውለው በረሮ ይሻላል። እየው ይሄንን ነጭ ልብስ ለብሰህ ባይሆን ኖሮ ጨመዳድጄ እንደ ቀሻሻ ወረቀት በመስኮት ነበር የምወረውርህ ..." ብሎ ከግድግዳው ጋር የበለጠ አጣብቀት ሲለቀው ተንሸራቶ ወረደና ጸጥ ብሎ እንደቀመ ቀረ። "ምን ይገትርሃል ቢያንስ ለነፍስህ ይሆንሃል። ልጅቷ ኮ ደሟ እየፈሰሰ ነው ... እስኪ ፍሉድ እንኳን እንድትሰጣት ለነርስህ ንገራት..." ብሎ አፈጠጠበት። ስልኩን አውጥቶ የማጎፀንና ጽንስ ከፍል ሃላፊዋ ዶክተር ሜሮን ጋ ሲደውል ወዲያው አነሳችው።

"ይትርታ ሜሮን ሌላሠው ነኝ። እዚሁ ጳውሎስ ከናንተው ድንገተኛ ክፍል ሆኜ ነው የምደውልልሽ። ባክሽ እንድ ዘመዴ ከወሊድ በኋላ ደም አለቀም ብሎ አምጥተዋት፣ ምንም ሳያደርጉላት ሾክ ውስጥ ገብታለች። ሩቅ ነው ኦንዴ ያለሽው?" ሲላት የሰማው ኢንተርን ሐኪም ዶክተር ሜሮን ባልሆነች ብሎ በልቡ እየጸለየ መሯሯጥ ጀመረ። ባዶውን ካርዷን ከሌላሠው እጅ እንዴት አውጥቶ የሐኪም ማስታወሻውን እንደሚጽፍ ቢያስብም ተላል መንገድ አልታየውም።

"እምን እዚሁ ቢሮ ነኝ። ወዶጠሞት ስብሰባ ለመሄድ እየተዘጋጀሁ ነበር። አሁኑኑ መጣሁ ... ሁለት ደቂቃ ... ኢንተርኖች ወይም ሬዚደንቶች አላዩዋትም እንዴ?"

"ኧረ፣ በጣም ነው የሚያሳዝነው ... ሌላ ቦታ ይሁን እሺ ... ሰው እንዴት እዚህ ሪፈራል ሆስፒታል ድረስ መጥቶ ሳይታይ ይሞታል" አለ ባዘነ ድምጽ

@OLDBOOOKSPDF

"እጠብህ ያለ ሐኪም አለ?" ስትለው ፣ ስልኩን ለኢንተርኮ አተበለው ።

ሲፈራ ሲቸር "ሃሎ..." ሲል አሷ ሆና ተገኘች ። ዶክተር ሚሮንን ሁሉ እንደ ጦር ነው የሚፈሯት ። ትንሽ አሠር ታው ፣ "በል እሳው ጠብቂኝ" ብላ ፣ ስልኩን ጾሮው ላይ ዘጋችው ።

ፊቱ ላብ በላብ እንደሆነ ስልኩን መለሰለት ። ዶክተር ሚሮን ስትመጣ የያዘውን ባዶ ቻርት ሲሰጣት ንዴቷ የባስ ሆፈ ። ተሯሩጠው በሁለቱም እጆቿ ግሉኮስ ከተከሉ በኋላ ማጎዳኟን መርምራ ስትጨርስ ፣ "ባስቸኳይ ... ደም የተቻለውን ያህል አዘጋጂ ... ኦፐሬሽን ክፍል ንገሩልኝ ... አሁኑኑ ይዘናት መሄድ አለብን ... ሲስተር እስኪ በረዶ ካለ በላስቲክ ቱሎ ..." አለችና ቀስ ቀስ እያለች ሆዱ ላይ አንድ እጇን ጥና ያልተለበለበውን ማጎዳን ማሸት ጀመረች ... በራሱ ተንሣሥቶ ቢሰበሰብ ብላ ። ካጠገቧ ተፍ ተፍ የሚለውን ኢንተርን ቀጣ ብላ "ማነው ለመሆኑ ተረኛ ሬዚደንት?" ስትል አንገቱን ደፋ አድርጎ ፣

"ዶክተር ላባና ዶክተር ገነነ ናቸው" አለ ጣቱን እያፍተለተለ ። እነደዚህ ኩምሽሽ ብሎ ሲያየው ያናደደውን ያህል መልሶ አሳዘነው ።

"ነግረሃቸው ነበር? እንተስ አይተሃት ነበር?" ስትለው

"ኦ አር ነን ብለው ሊመጡ አልቻሉም ። እኔ አይቻት ነበር" አለ የውሸቱኮ ቢሆን ፣ የሚጋረፈውን ራቷን ስለፈራ ።

"እና እንደዚህ ሆና ... ይህንን ሁሉ ሰዓት ምን ስትሠራ ነበር? እነሱ ካልቻሉ ቺፍ ሬዚደንቱ ጋ አትደውልም ወይም ተረኛ ሲንየሩ ጋ ። ደግሞ ቢያንስ መሠረታዊ የሆ ላብራቶሪዎችንስ መች አሠራህና ነው አይቻታለሁ የምትለኝ ። ማስታወሻህንስ ካርዱ ላይ መች ጻፍክ? እንተ ራስህ ያየሃት አይመስለኝም" ስትለው ጸጥ አለ ። ስልኩ ደጋግሞ ሲጠራ አንስቶ ፣

"ዶክተር ገነነ ነው ... ለሞርኒንግ ሰብሰባ እየጠበቁኝ ነው መሰለኝ ... የትናንትናና የሌሊቱን እኔ ነኝ የማቀርበው" አለ ፣ እየተሸማቀቀ ።

"እንዲያውም እዚህ ኖረህም እትጠቅምም ። አንተ ሄደህ ሪፖርትህን አቅርብ። እሱን ንገረውና እሁኑኑ ይምጣ" ስትለው ፣ ከድመት ሸሽታ ጎሬ እንዳየች አይጥ ሹልክልክ ብሎ ካካባቢው ጠፋ ።

"የምትተርፍ ይመስልሻል?" አለ ሌላው ፣ ሞንቀቱ ሰማይ እየነካ ።

"እኔንኛ ... እስኪ የቻልነውን እናደርጋለን ... በቂ ደም ከገኘንና ኦፐሬሽን ክፍሉ ከተዘጋጀ ... አይ ሆፕ ... ደግሞ ማነው ለኦፐሬሽኑ የሚፈርምልን?" አለች ለሷ ጥልጥል ብሎ ። አንዴ ግንባሯን ፣ አንዴ አንገቷ ላይ ያለ ደም ሥሯን እየነካ ሲቁነጠነጥ ቀየና ወደ ውጪኛው ክፍል ወጣ አለ ። የዝናሽ አባት ለመግባት ፈርተው በራፉ ላይ ሲያጮልቁ ናሮ ልክ ሲያዩት ተንደርድረው ገቡ ።

@OLDBOOOKSPDF

ከፊት ለፊት የነበሩ በዕድሜ ገፉ ያሉ የጽዳት ሠራተኛ "እንዴ የት ነው የሚወላከፉት ... ይሄ ማዋለኛ ክፍል ነው። እስኪ ወደ ደጅ ... ምነው አሁንስ የማንም ግሳንግስ ሁሉ ... ደግሞ ኮ ቤቱን አጨቀዩት " ሲሉ፣ የሰማው ሌላው፣ ስድባቸው ዘገንኖት ዞር ሲል፣ የገነናሽ አባት መሆናቸውን ሲያይ ቁጣውን በትግል ተቆጣጠሮ፣

"የሕመምተኛዋ አባት ናቸው" አለ፣ ረጋ ባለ ድምፅ።

"ቢሆንስ ታድያ ... እዚህ ቤተሰብ መግባት አይፈቀድም ... እዛው ይጠብቁ ..." ሲሉ፣ ብልጭ አለበት።

"ሰሙ እርሶ ሴት ልጅ የለዎትም ... ልጅዎ በሞትና በሕይወት መሃል ሆና ... ሚማዎ ጭቃ አለው ብዬ እንዳይገቡ ብከለክልዎ ምን ይሰማዎታል?" ሲል፣ ቀበል አድርገው፣

"እሱ ሌላ ጉዳይ ነው ... ይሄ የሆስፒታሉ ሕግ ነው ... ሰውዬ በሕግ እዛው ይጠብቁ ..." ሲሉ በንዴት ከላይ እስከ ታች በንቀት እየት አደረጋቸውና፣

"ኑ አባባ በዚህ በኩል። የርሶ ሥራ ማጽዳት ነው፣ ሌላ ወሬ አያብዙ" አለና፣ ይዟቸው ሲገባ፣ እያጉተመተሙ ወጥተው ሄዱ። ዶክተር ሚሮንም ስታያቸው አሳዘኗት።

"አባባ ... ልጅዎ በጣም በከፍተኛ ደረጃ ታማለች ... አሁኑኑ ወደ ኦፕሬሽን ይዘናት ልንገባ ይገባል ... ልናተርፋት የምንችለው በዛ መንገድ ብቻ ነው" ስትል፣

"ልጄ እናንት እንዳላችሁ ... የሦስት እምቦቀቅላዎች እናት ናት ... አባከዎ እንዲየው በመብርሃን ይገርዎታለሁ የዛሬን ይማሩኝ ... ያትርፉልኝ ... የሙት ልጅ ናት" ብለው ሲያለቅሱባት፣ የራሷን እምባ በግድ አቀመችው።

"የሚቻለንን ሁሉ እያደረግን ነው አባባ ... እርሶ ኦፕሬሽኑን እንድናደርግ የሚፈቅደው ወረቀት ላይ ከፈረሙልን አሁኑኑ ይዘናት ልንገባ እንችላለን።"

"ውይ ምን ገዶኝ ... እፈርማለሁ። እመብርሃን ትከተላችሁ ብቻ ..." ሲፈሩ ሲቸሩ ጠጋ ብለው የልጃቸውን ግንባር ሳም አድርገው የሆነ ነገር አጉተመተሙ። እማትበው ጸሎት ካደረሱ በኋላ እምባቸውን ባደፈ ጋቢያቸው እየጠራረጉና መፈረሚያ እስኪርቢቶውን ለመጪበጥ እየታገሉ፣ ወረቀቱን ፈርመው ወጡ። እስኪወጡ የሚጠብቁበት ቦታ ወስዶ አስቀመጣቸውና በጥድፊያ ወደ ኦፕሬሽን ክፍሉ ሮጠ።

በቀዶ ማከሚያው ክፍል ውስጥ የሚያስፈልገውን ነገር በተቻለ ፍጥነት ተዘጋጅቶ ዶክተር ሚሮንና ጥና ቀዳጅ ሃኪም፣ ሬዚደንቱ ዶክተር ገነነ ረዳት፣ ሌላውም ተጨማሪ ሆነው ከበቡዋት።

ማደንዘዣውን የሚሰጣት የአንስቲዥያ ዶክተር ያለውን ሁኔታ ከገመገመ በኋላ፣ "ዶክተር ሚሮን ... ልጅቷ በጣም ጥልቅ ሾክ ውስጥ እኮ ነው ያለችው ... ማደንዘዣ ልሰጣት የምችል አይመስለኝም ... በዛው ነው የምትሄድብን" አለ ረጋ ባለ ድምፅ፣ በልመና ዓይነት።

@OLDBOOOKSPDF

"አራት ዩኒት ደምና አምስት ከረጢት ጉሉኮስ ነው የሰጠናት ... የገባው ሁሉ እየወጣ ነው። ገብቶን ማጎዳኗን ከማውጣት ሌላ ምንም አማራጭ የለንም። ያለዉ ተስፋ እሱ ብቻ ነው" አለች፣ ቁርጥ ባለ ድምፅ።

እርሱም እጅመንን ሳይለቅ፣ "እኔ ግን አይ ዶኖ ... ዓይኔ እያየ ማይንዘባ ልሰግት አልችልም" አለ፣ ሞኒትላቱን እያወዛወዘ።

"ዶክተር ጊዜ የለንም ... ነገርኩህ እኮ ... ባትሰጣትም እዚሁ ጠረጴዛ ላይ ትሞታለች ... ቢያንስ ዕድል እንስጣት ነው የምልህ" ብላ፣ ስትሰምነው አልሰማ ሲላት፣ በስጨት ብላ "ቢቃ እምቢ ካልክ ፈርምልንና ... እንውጣ እኛም ..." ብላ፣ ጓንቷን ማወላለቅ ስትጀምር፣ አያትሞማ ማያንዘባውን ለመስጠት ተስማማና ሥራ ጀመሩ። በፍጥነት ወደ ውስጥ ገብታ የሚያማውን የማጎዳኗን ክፍል ቆርጠው አወጡና ሁም ሥሮቹን ሁሉ ተቀጣጥረውና ቀጣጥረው መገጋት ሲጀምሩ ሲሉ የማይንዘባ ሃኪሙ፣

"ዶክተር ምንም ደም ግፊት የላትም ... የልቧ ምትም በጣም የተዛባ ነው..." ሲል ከግራና ከቀኝ ዝናሽን ለማትረፍ መረባረብ ጀመሩ። ልቧ ቀጥ ብሎ ሲቀም የሁሉም ተስፋ ነፋስ እንዳጠፋው ሻማ ድርግም አለ። ከብዙ ልፋት በኋላ እንደ ሲመጣ እንዲ ሲጠፋ የቀየው ልቧ ቆሞ ቀረ። ተስፋ በቁረጠ ድምፅ፣ "ቢቃ ምንም ማድረግ አንችልም ... የለችም ... እምልጣናስች" አለ፣ ግንባሩ ላይ ያቸፈፈውን ላብ እየጠረገና ራሱን እያወዛወዘ።

የመጪረሻውን ቃል ሲሰማ የሉላሠውም ወሽመጥ ብጥስ አለ። "አምላኬ ... ምናለ ..." ብሎ ጓንት ባጠለቁ እጆቹ ራሱን እንደ ያዘ የሆነውን ማመን እቅቶት በተቀላቀለ ንዴትና ጸጸት ውስጡ ሲጨስ ተሰማው። ወደ መስኮቱ ሄዶ አላፊ አግዳሚ መኪኖችንና ሙር ሙር የሚሉ ሰዎችን በደመ ነፍስ እያየ በቆመበት ቀረ። አባቷ ትዝ ሲሉት "አሁን ምን ይባላል ..." ብሎ ዓይኖቹን ጨፈነ። የደረቀ ከንፈሩን በምላሱ ሲያርስ ከሠላት ዓይኖቹ እንባው በጉንጮቹ ላይ ያለ ከልካይ ወረደ።

ውስቢ ድብን ያለው ዶክተር ሚሮንም የማይንዘባ ሃኪሙን እመስግና፣ አብሯት የነበረውን ረዚደንት ዶክተር ላይ ሕይወት አልባ ተዝቃዛ ዓይኖቿን ተክላ፣ "ዶክተር ሳባና ኢንተርኑን ጨምሮ አራት ሰዓት ላይ እኔ ቢሮ እንገናኝ" አለችና፣ ወደ ሉላሠው አጠገብ ሄዳ፣ ጸጥ ብላ ጥቂት ቆመች። ከንዴን ይዛው ከኦፕሬሽን ከፍሉ ወጡ። ቢሮዋ ሲደርሱ ሰውነቱ ሁሉ ከድቶት አንዱ ሶፋ ላይ ዘሙ ብሎ ተቀመጠ።

ስለ ዝናሽ ታሪክ ጻውሷስ ሆስፒታል እንዴት እንዳገኛት ከመጀመሪያ ጀምሮ አጫወታት። ስለ ልጅነቷና ስላባቷ ሲንግራት የቧም እምባ መፍሰስ ጀመረ። ከጥቂት አገበ የሆነውን ነገር ሁሉ ሲንግራት ሃዘኗ ወደ ንዴት ተቀይሮ ከፍሉ ውስጥ ተንቀራጠቀች፣ ምን ማድረግ እንደምትችል አያስበች ተመልሳ ተቀመጠች።

"መከሰስ አይቻልም እንዴ? ... ይሄ ኮ ነፍስ ማጥፋት ነው ... እንዴት ዝም ተብሎ ይታያል?" አለ፣ ውስጧ የሞላውን ሲቃ እያቀቀጣጠረ።

@OLDBOOOKSPDF

"ማንን ትከሳለህ ሴላሙ? ሆስፒታሉን ... ሐኪሞቹን ... ነርሶቹን ... ዘበኞቹን የድኗት ሰራተኖቹን ... ጤና ጥበታን ... ማንን? የተሰከፈ ሀዘ ውሰጥ እኮ ነው የምንኖረው። ደግና ሰው አከባሪ ባሕል እየተባለ ቢለፈፍም እውነቱ ግን ጎሊና የሌለው ጨካኝና ለሰው ዋጋ ደንታ የማይሰጠው ሰው ነው የሚበዛው። ማንን ትከሳለህ? ደፍሮ ያስረገጠህ ማንን? ዶግሞ የሚከሰስ ተገኝቶ ብትከስስ? ... ፍርድ ቤቱም ያው እኮ ነው? የት ሄደህ ለማን አቤት ትላለህ? ማንስ ምስክር ሆኖ ይቀምልሃል? የምትተናነቀው ከሰው ጋር እንዳይመስልህ ... ከሕግ ጋርም አይደለም። ሀሊናው ከጠፋበት፣ የሰው ዋጋ ከተሰወረበት የታመመ ጥቅል አስተሳሰብ ጋር ነው። ይሄንን ሁሉ ዓመት ተምሮ በሰውና በእግዚር ፊት በመሃላ ከታሰረ ባለሙያ ያላገኘኸውን ሞራል ከየት ታገኘዋለህ?" ብላው፣ ተንሰታ ከመስኮቱ አጠገብ ሄዳ ራሷን ይዛ ቀመች።

ተመልሳ እንደገና ዞር ብላ ወደ አርሱ መጥታ እጆቿን እያወናጨፈች "ግን ደግሞ እንደዚህ ሰል ዝም የምል እንዳይመስልህ ... እስከ መጨረሻው ድረስ ... ስዚች ልጅ ሞት ቢያንስ በሕክምናው በኩል ያጠፉ ሰዎች ... የጥፋታቸውን ዋጋ ይከፍላሉ። ቢለወጡም ባይለወጡም የራሳቸው ጉዳይ ነው። እዚህ ነፍሰ ገዳዮችን አናሠለጥንም" ብላ፣ ነጭ የሥራ ኮታን አውልቃ ከአጠገቡ ተቀመጠች።

"እውን ምን ተብሎ ነው ሳባታ የሚነገራቸው? ልጆቿንማ ሳስብ ... አይ ዶኖ ..." ብሎ ዝም አለ። እንዲ ምንም ሳንቾ ጋ ሲደውል፣ እዛው ጻውሎስ የአእምሮ ሕክምና ክሊኒክ እንዳለ ነገረው። የሆነውን ነገር ባጭሩ አሰረዳውና የዝናሽን አባት የቀጠረበት ቦታ እንዲመጣ ነገረው። ከዶክተር ሚሮን ጋር ትንሽ አውርተው፣ አመሰግኗት ክቢሮዋ ወጣ። የዝናሽ አባት ደግሞ አንዳች ነገር የልጃቸውን ዜና ሞት ሹክ ያላቸው ይመስል እያለቀሱና እየተንቀራጠሱ ሲጠብቁት ደረሰ። ሳንቾ ከምስጢር ጋር ነበር የመጣው። ሁለቱም ስለ ዝናሽ ስለሚያውቁ እዝን ብለዋል። የዝናሽ አባት ሴላሙን ሲያዩት አንከሰ አንከሰ እያሉ በፍጥነት መጼ ርሱ ተጠጉ።

"እንዴት ሆነች ልጄ ... ተረፈችው?" ሲሉ፣ ጥቂት ዝም ብሎ ቀየና ትክሻቸውን ደገፍ አድርጎ፣

"የምንችለውን ሁሉ አድርገን ነበር አባባ። ብዙ ደም ስለፈሰላት ልናተርፋት አልቻልንም ... አመለጠችን" አለ፣ የማደንዘዣ ሐኪሙን ሂንቲ በመጠቀም ስብር ባለ ድምፅ። ዝልፍልፍ ብለው ሊወድቁበት ሲሉ ከሳንቾ ጋር እንደምንም ደጋግፈው ከጀርባቸው ካለ ባለ ድጋፍ እግዳሚ መንበር ላይ አስቀመጧቸው። ድርት እንዳሉ ሰጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ቀዩ።

"አዬ ልጄ ... የኔ አበባ ... የኔ ዝና ... እኔ አፈር ልብላልሽ ... እኔ ልትደምሽ" እያሉ፣ እዛው ባሉበት ሆነው ልብ በሚሰብር ዜማ እያንጉራጉሩ ቀዩ። ድንገት ከእንቅልፉ እንደ ነቃ ሰው ከመሶዕላው ላይ ብድግ አሉ። "ልጄ ... ዝናዬ ... ምን ልበላቸው ለማናቱ ... ቲጠብቁሽ ነበር እኮ ለንቲጣማሽ ... እወይ ምነው ባውዳ መቂ ... ያቺ እናትሽ ምን ትል ነበር ... ዝናዬ ..." እያሉ፣ ደረታቸውን ላመል ያህል እየደቁና ጉንበስ ቀና እያሉ ሲያለቅሱ፣ የሁሉም ልብ አብሮ ደማ። የልጅን ሞት ህመም

@OLDBOOOKSPDF

የሚያውቀው ልጁን በሞት ያጣ ብቻ ነው ። ሐኪሞች በቸልታም ይሁን በድካም በማን አለብኝነትም ይሁን በችሎታ ማነስ የሚሰሩት ስህተት የሚፈጥረውን የስቀታ ልዘ ምን ያህል ያውቁ ይሆን? ብሎ አሰበ ሌላሠው ። ሐኪም ቢሆንም ሐኪም ባልሆነ የወላጅ ልቡ ለማሰብ ሞከረ ።

ለሳንቶና ምስጢር ከዝናሽ አባት ጋር እንዲሆኑና የተረውን የሆስፒታል ሂደት እንዲያግዟቸው አደራ ሰጣቸው ። የሚያስፈልገውን ገንዘብ እሱ እንደሚከፍል ነግሯቸው ፣ ለጊዜው ኪሱ ውስጥ ያለውን ሰባት መቶ ብር በሙሉ ለሳንቶ ሰጠው ፣ "ይቅርታ ፣ እኔ አሁን እዚህ መቀየት አልችልም ... አንድ መሄድ ያለብኝ ቦታ አለ ። እንደ ጨረስኩ እደውልላችኋለሁ ። አባባ እነርሱ ይረዱዎታል ። አይዝሎ ... እኔም ቶ...ሎ እ...መለሳለሁ ..." ብሎ ፣ ትከሻቸውን ሙታ መታ አድርጎ ትንሽ አጽናንቷቸው ወደ መኪናው በፍጥነት ሄደ ። መጨረሻ ላይ እንደ ሕልም የሰማው የምስጢርን ፣

"ቀስ ብለህ ንዳ ዶክተር ሌላ ..." የሚል የተጨነቀ ድምፅ ነበር ። የሚሄድበት ቦታ ኖሮ ሳይሆን ለብቻው መሄድ ... ከከተማው መውጣት ... ከለው ሁሉ ራቅ ማለት ፈልጎ ነበር ። ከሁሉም ነገር ለመሸሽ ... ከምንም ነገር ላይሸሽ ።

አሁንም ውስጡ በሥጋ ይነዳል ። በማን ላይ እንደተቁጣ ወይም መቆጣት እንዳለበትም አላወቀም "ማንን ትከሳለህ? ለማንስ አቤት ትላለህ?" የሚለው የዶክተር ሚሮን ታል ደጋግሞ እያታጨለበት ከሆስፒታሉ ውልቅ ብሎ ወጣ ። ልቦናው ላይ በሚጋልበው ስሜት እየተነዳ መኪናውን እየረገጠ ከነፈ ። ለመጨረሻ ጊዜ ዓይናቸን ገለጥ እድርጋ ያተተመተመችውን ነገርና የደብዛዛ ፈገግታዋን ትርጉም ለማወቅ ፈለገ ።

የዝናሽ ነፍስ ወደ ሰማይ ቤት ለመጨረሻ ጊዜ ከመሰናበቷ በፊት በፍጥነት የሚነዳትን መኪና ተከትላ ከበላዩ እየበረረች የምትከተለው መሰለው ። አነዳዱ ከዝናሽ ነፍስ ጋር እሽቅድድም ይመስል ነበር ። ከሐሳቡ ሲነቃ ራሱን ከከተማው ወጥቶ ፣ ወደ ደብረሊባኖስ ገዳም በሚወስደው መንገድ ላይ በተንጣለለ ሰፊ ሜዳ አቋርጦ በሚሄደው አስፋልት ላይ ነበር ። መኪናውን አቁሞ ወደ ማሳው ውስጥ ገብቶ ገዘም ብሎ ወደ እንዱ አቅጣጫ እግሩ እንደ መራው ሄደ ።

'ርግጥ ነው ማን ይከሰሳል?' አለ በውስጡ ... 'ደፍሮ ያስረገዛት ገረምላ ... ከጥቁር አንበሳ ሳያይ የሸኘች ሐኪም ...የጸውሎስ ድንገተኛ ክፍል ሠራተኞች ... ወይስ ማን? ደግሞስ አእምሮዋ ባይታመም ለዚህ ትበቃ ነበር? ለሱስ ተጠያቂው ማነው? ሁሉም ቢከሰሱ ... እጃቸውን የሚጠቁመውበት ከእነሱ ሌላ ሰው አያጡም ። ጥፋቱ የኔ ነው የሚል እንድም ሰው አይገኝም ... ጥፋተኛውን መርምሮ ተገቢውን እርምጃ መውሰድስ የማን ሥራ ነው? ...እሱም የሌላ ሰው ተግባር እንደሆነ የሚያስብ እንጂ የኔ ኃላፊነት ነው የሚል የት ይገኛል? ... ዶክተር ሚሮንስ ብቻዋን ምን ልታደርግ ትችላለች? ... እዕ.ም ሌላ አቤቱታ ሰሚ ... ለመትጣትና ለመሸለም ጥልበት ያለው ... ሌላ ሰው ትፈልጋለች ። እንዳለችው 'ለማን አቤት ይባላል?'

የሚጸኝ ጥፋተኛንና ... የሚጸኝ ጻዲን ማን ሊያገናኛቸው ይችላል? ... የውስጥ የኅሊና ጻዲ ያልጻፍውን ... @OLDBOOKSFROM ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ... ብይን

ሊሰጥበት፣ ፍትህ ሊያወርድበት ይችላል? የገና'ሽን ጉዳይ ከታላቁ የጎሲና ፍርድ ቤት አቅርቦ የሚሞግትላት ታዲያ ማነው?' እያለ ሲያስብ፣ ምን ያህል ርቀ አንደ ተጓዘ አልታወቀውም ነበር ።

ወደ መኪናው እየተመለሰ ዝና'ሽ ያሳለፈችው መንገላታት ... የልጆቿ ናፍቀትና ስቃን ... ያባቷ ጉስቋላና መከራ የጠገበ ፊት እየተራራረቁ ሲመጡበት ውስጡ ተረበሸ ።

'ልጆቿስ አሁን ምንድነው የሚሆኑት? አዲስ የተመለደችውግ ሕፃን ማን ያሳድጋታል? የሴት ልጇስ ዕጣ ፈንታ ምን ይሆን?'

'ሞታቸውም መኖራቸውም የማንም ጉዳይ ሳይሆን ... እንደ እንሩሱት ተነው ... እንደ ጤዛ ረግፈው በየስርቻው የሚቀሩ ስንት ዝና'ሾች ይኖሩ ይሆን?'

'እእምሮአቸው በታመመ ሰዎች ላይ የጤና ባላሙያዎች እንኳን ሳይቀሩ ለምንድነው እንደዚህ የሚጨክኑት? ሰው አይመስሏቸውም ማለት ነው? ልብና ጉበቱ ለታመመ ሰው የሚራሩ ሰዎችስ፣ ለምንድነው አእምሮቸው በታመመ ሰዎች ላይ የሚጨክኑት? ጋኔን ተሸክመው፣ እርግማን አዝለው የሚዞሩ ስለሚመስላቸው ይሆን?

'አሁን ዝና'ሽ የአእምሮ ሕመተኛ ባትሆንና ገንዘብ ያላት የተማረች ነፍሰ ጡር ብትሆን የጥቁር አንበሳ ተረኛው ዶክተር ላያይት በገጼለሽነት ይመልሳት ነበር? ጳው'ሎስ ሆስፒታልስ ያን ያህል ጊዜ እንደወደቀ ዕቃ ተጥላ በደሟ እንደተነከረች ትረሳ ነበር? የለው ዋጋ የሰው ያህል እንዲሆን ገንዘብ ... ዘመድ ... ሥልጣን ...ታዋቂነት የመሳሰሉ ኮተቶች ያስፈልጋሉ ማለት ነው? እነዚህስ ጠፊና መጪ ቅጥያዎች ለምንድነው ሰው ከመሆን በላይ ተከብረው፣ የሰው'ን ዋጋ ሊወስኑ የቻሉት?' የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንጂ መመለስ አልቻለም ።

እንዲህ ባሉ ማለቂያ በሌላቸው የጥያቄ ሰንሰለት የተጠፈረው'ን ሚንትላቱን ቢያረገብልኝ ብሎ ጸጥ ወዳለ ስፍራ ሲደርስ እንደገና መኪናው'ን አቁሞ ወረደ ። አሁንም በእግሩ ረጅም መንገድ እየተጓዘ 'ዝና'ሽን የገደላት ማነው?' ለሚለው ጥያቄ መልስ ፍለጋ ይመስል በእግሩም በሐሳቡም እስኪደክመው ተጓዘ ። በመጨረሻ መልስ ብሎ የደረሰበት፣ ተጠያቂው የዝና'ሽ ገዳይ 'ሌላ ሰው' የሚባል ሰው መሆኑን ነው ። ወዲያው ግን 'ሌላ ሰው' ማነው? የሚለው ጥያቄ፣ መልስ የለሽ ሆነበት ።

መኪናው'ን በቀስታ እየነዳ ከጠመገ'ማዛና ዳገታማ የአዲስ አበባ መግቢያ አፋፍ ላይ ደረሰ ። ከተማይቱን ቁልቁል አይቶ አዘነላት ። ካትማቸው'ና ከቁመታቸው በላይ ቁልል የግቢ እንጨት ተሸክመው ሽትብ እየወጡ ቁልቁል የሚወርዱ ሴቶችን ቢመገማቸው እያለፈ ሄደ ። ያንዳቸው'ንም ሸክም ሊያቀልላቸው ወይም ሊሸከምላቸው ዝግጁ አልነበረም ። 'እኔ ሌላሙ ነኝ፣ እኔ ሌላ ሰው መሆኔን መካድ አልችልም' ብሎ ላልተመለሰው ጥያቄ መልሱን ከመ'ስጡ አገኘው ።

@OLDBOOOKSPDF

16

ሳንቾና ምስጢር የገናናሽን አባት ምን እንደሚያደርጓቸው ግራ ገብቷቸዋል። ምስጢር ልትቀርባቸው ፈርታ እያመነታች ራቅ ብላ ቀማለች። ህመሙ እጅና እግራቸውን ብቻ ሳይሆን የፊታቸውንም ቅርጽ ቀይሮት፣ እውነተኛ መልካቸው ከጠፋ ቆይቷል። ማንንም ከቁብ ሳይቀጥሩ፣ እያንገራገሩና ደረታቸውን እየደቁ፣ ገበጥ ያለ ሰውነታቸውን በያዙት በትር ደገፍ አድርገው፣ "ገናዬ ... ገናዬ ... የኔ ገር ... ሆደ ቡቡ ... የናትሽ ልጅ ... ምነው በጨለማው ...ለማን ጥለሽኝ ..." ይሉና፣ በየመሃሉ ጭንቅላታቸውን ይዘው ዝም ብለው ይወዛወዛሉ። በሊሊት ተነሥተው ከዘነበ ወርቅ ድረስ አብዛኛውን መንገድ በእግራቸው ስለመጡ መቀመጡም አቅቷቸዋል።

"አባባ እስኪ በርታ ይበሉ ... መቼስ ምን ይደረጋል እንግዲህ። አሁን ማድረግ ያለብንን ነገር ትንሽ ብንነጋገር። ዶክተር ሌላው ነው እንድናግዝዎ የነገረን" አለ፣ ሳንቾ ፊራ ተባ እያለ ተጠግቷቸው።

"ምናልሽኝ ልጄ ... ጆሮዬም እኮ በቅጡ አይሰማ" አሉ፣ ወደ እርሱ ዞር ብለው ግንኙቱን ለማጣራት ይመስል፣ አይናቸውን ባዳፋ ኮታቸው ጠረግ ጠረግ እያደረጉ።

"ዶክተር ሌላው ነው እንድናግዝዎ የላከን" አለ፣ ጮክ ብሎ የበለጠ ቀረብ ብሎ።

"እዬ የተባረክ ሰው ... እሱማ ያቅሙን ጥሮላት ነበር ... አትትረፊ ብሏት ... የእሳት ራት ሆና ቀረች እንጂ ... የኔ አበባ ... እኔን ይትጠፈኝ ..." ብለው፣ እንባቸውን እየጠራረጉ የሚለውን ለመስማት ትንሽ ጋብ አሉ።

"አባባ... እንግዲህ ምን ይደረጋል? አይዝዎ ... ፈጣሪ ያመጣውን መቀበል ነው እንጂ። አሁን እስኪ ምን መደረግ እንዳለበት እንነጋገር ... እኛም የምንረዳዎ ነገር ከለ ብለን ነው..." ሲል፣

@OLDBOOOKSPDF

"አዬ ልጄ እኔ ምኑን አውቀውና ብለህ ... እናንተው ንገሩኝ እንጂ ... እንደምታየው ቤቱም ባህር ነው ..." አሉ፣ በሆስፒታሉ መሃል እንዳቆሙ ሐዘናቸው ላይ ግራ መጋባታቸውም ተጨምሮ ።

"እስኪ እዛች አግዳሚ ወንበሯ ላይ አረፍ እንበልና ምን ማድረግ እንዳለብን እንግለር" ብሎ፣ ዶገፍ አድርጓቸው በሆስፒታሉ መሃል ካለው ክፍት ቦታ ሄደው ተቀመጡ ። ገዛ ብላ ስታዳምጥ የነበረችው ምስጢርም ከኋላ ተከትላቸው አጠገባቸው ቀመች ። ሳንቾን በልቧ እያደነቀች ነገሩን እንደ ታዛቢ መከታተል ቀጠለች ። ሰፈራቸው የት እንደ ሆነና ቀብሩ የት እንደሚፈጸም ጠየቃቸው ። ፊሳውን ከየትና መቼ ማውጣት እንደሚችሉ አረጋግጦ እስኪመጣ ድረስ ከሚሰጥር ጋር እንዲጠብቁት ትቷቸው ወደ ውስጥ ገባ ። በትራቸውን እንደተደገፉ ሲቀዝሙ ከላይ እስከታች በጥንቃቄ ስታጠናቸው ቀየች ።

"አውን የተወለደውስ ሀጻን የት እንዳለ ያውቃሉ?" አለች፣ ስትፈራ ስትቸር ዝምታውን ለመስበር ። ፊታቸውን ላመል ወደሷ ዞር አድርገው፣

"እኔ ምናባቱ አውቂ ልጄ ... ተዚያ ታማኑኤል ነው የተገላገለችው ነበር ያሉት ... መገላገል ተተባለ ። ዕድለ ከልብ መከረኛ ጨቅላ ... ምናባቴንስ ነው አውን የማደርገው ... አይ አንተ ፈጣሪ ምነው ብትወስደኝ ። እንዲህ ለጉድ ጎልተኸኝ ... መጫወቻ ተምሆንብህ ..."ብለው፣ ሲንሰቀሰቁ የምታደርገውን አጣች ። የበለጠ ጠጋ ብላቸው ትከሻቸውን መታ መታ እያደረገች፣

"አይዞት አባባ ... አይገዎ ..." ሌላ ጥያቄ ለመጠየቅ ፈርታ ጥቂት ዝም ብላ ቀመች ። እጇን ትከሻቸው ላይ አድርጋ ስታጽናናቸው የሚያዩ አላፊ አግዳሚዎች ቀም ብለው ያዩዋቸዋል ። የቸኮለው ሲያልፍ ሌላው አንድ አንድ እያለ ሲቀም፣ ሳይታወቅ በሰው ተከበቡ ። ነገሩን ለማወቅ ከግራና ከቀኝ የሚመረመረውን ጥያቄ ምን ብላ መመለስ እንዳለባት ግራ ገብቷት ጨነቃት ። በመሃል ሳንቾ ደርሶ ገላገላት ።

"እንዴ ምንድነው እሱ? ምንድነው የምትፈልጉት?" ብሎ፣ እጁን ሲያወናጭፍ፣ አንድ በሰል ያሉ ሰው፣

"አሳቸው እያለቀሱ አሲም ልትረዳቸው ስትሞክር አይተን ነው ። የምንረዳቸውም ነገር ካለ ብለን ነው" አሉ ኩስትር ባለ ፊት ።

"እሺ ... አሳቸው ልጃቸው በድንገተኛ ለመሊድ መሞታ ሞታባቸው ነው ። እኛ ልናግዛቸው እየሞከርን ነው" ብሎ ወደ ዝናሽ አባት ዞረ ። አንዳንዱ 'እናቲ እኔ አፈር ልብላ' ብሎ እንትፍትፍ ብሎ መንገዱን ሲቀጥል፣ ሌላው 'እቤት የደሃ ዕድል ... ሕፃኑስ ተርፎ ይሆን?' ይልና፣ መልሱንም ሳይጠብቅ በራሱ ችግር እየተነዳ ጉዞውን ይቀጥላል ። ሳንቾ ደግፏቸው ሲነሡ የቀረውም ሰው በዛው ተበታተነ ።

"አባባ ከዚህ ያለውን ጉዳይ አናግራያለሁ ... ችግር የለውም ። ሳጥን ያስፈልጋል ብለዋል ... እሱን እኛ ገዝተን እናመጣና ወደ ከሰዓት ወይም ቢገሉ ነገ ጠዋት ፊሳውን እንረከባለን ። አውን እርሶ ነገሩን ለዘመድ ለጐረቤት መንገር ያስፈልግዎታል አይደል?" ሲላቸው፣ ድርቅ እንዳሉ ትንሽ ሲያስቡ ቆይና

@OLDBOOKSPDF

"አምድ ልጄ ... እህታ አለች እባው ተኛ ቤት በታች ... ደግሞ ዕድር ቢጠፋ የናቷም ባልትና አለ መሰል" ብለው፣ እንዳቀረቀሩ ዝም አሉ።

"ዘቃ አሁን ወደ እርስዎ ቤት እንሂድ ... እኛ መኪና ስለያዝን ልናደርስዎ እንችላለን ... አይሻልም?" አለ፣ አንዱ ወደ እሳቸው አንዱ ወደ ምስጢር እያየ።

"እንቱ እንዳልሀ ልጄ ..." አሉ፣ የእርጅናቸው ሽብሽብና የሐዘኑ ሞምትር አንድ ላይ ተባብሮ ፊታቸውን ጉርባማ ሰፈድ አስመስሎት።

"በኔ መኪና እንሂድ ... እዚህ ከቆያችሁኝ ቶሎ ይገርው ልመጣ እችላለሁ ... እሳቸውን እዛ ድረስ ከምናደክማቸው" አለች፣ ምስጢር የመኪና ቁልፏን ከቦርሳዋ ውስጥ እያወጣች።

"ገቢ ውስጥ ከምትገቢ እኛ በታችኛው በር ወጥተን መንገዱ ዳር እንጠብቅሻለን ... እዛ ድረስ ከመጣሽ ይበቃል" አሉና፣ በርሳቸው አረማመድ እያዘገመ ወደ በሩ አመሩ። ከኋላ መቀመጫዉ ላይ ደጋግፈው ካስቀመጧቸው በኋላ ትንሽ እንደነዱ፣

"አባባ ሰፈርዎ ወዴት ነው?" አለ፣ የት አካባቢ እንደሚኖሩም እንዳልጠየቃቸው ትዝ ብሎት። ጉሮሯቸውን ጠረግ ጠረግ አደረጉና፣

"እዬሀ ታች ... ከዘነበወርቅ ማዶ ... ቀሺ ሳይደርስ ... አሮጌው ቤተስኪያን ሰፈር ነው።" ዘነበወርቅ የሚለውን ጨምሮ የጠሩት ሥም አንዱም ስላልገባት ዞር ብላ ሳንቾን አየት አደረገችው። 'እንደዚህ የሚባል ሰፈር አዲስ አበባ ውስጥ አለ ወይ?' በሚል አስተያየት።

"እሺ አባባ ... ዘነበ ወርቅ ሆስፒታሉ አካባቢ ስንደርስ ይመሩናል" አለና፣ ሰፈሩ ወደ የት እንደሆነ አሰረዳት። ሳንቾ ታክሲ ረዳት፣ ከዚያም ሾፈር ሆኖ ሲሠራ ያልገባበት ሰፈር የለም።

እየቀረቡ ሲመጡ፣ "በመካኒሳ በኩል ብንገባ ይሻላል ወይስ?" ሲላቸው፣ ግራ ተጋቡ።

"ይሻላል መሰል ... እኔ ምናባቴንስ አውቂው ብለህ ልጄ ..." አሉ፣ እንደተኮራመቱ ቁጭ ካሉበት ቀና ብለው። ዝናብ ካራሰው ያደፈ ልብሳቸውና ሰውነታቸው የሚወጣው የታመቀ ጠረን መኪናውን አፍኖታል። መስኮቱን በከፊል ብትከፍተውም ብዙም ለውጥ አልነበረውም። በአቦ ማዞሪያ ወደ መካኒሳ እድርገው፣ ቀራን አለፉ። ትንሽ እንደነዱ በውስጥ ለውስጥ ኮረኮንች መንገድ እየመሯቸው በእንጨት የታጠረች አነስተኛ ቤተክርስቲያን ጋ ደረሱ።

"እዬሀ ጋ ታቀምሽ ይበቃል የኔ ልጅ ... እዚሁ ሰፈር ስለሆነ ካየሀ በኋላ አያስገባሽም" አሉ፣ ጨርቃቸውን እየሰበሰቡ። ፈጠን ብሎ ወረደና ደገፍ አድርጓቸው በትራቸውን ተመርኩዘው ወረዱ። በሩን ዘጋግተው ሲወጡ፣ ከየት መጡ ሳይባል የሰፈሩ ልጆች ወረሯቸው። ሁለቱን ከፍ ከፍ ያሉ ልጆች መኪናውን እንዲጠብቁ ነግረው፣ የዝናሽን አባት ቤት ውስጥ ሠርገው ገቡ። ሰፈሩ

@ETHIOBOOKS

ሙጨትናቱም በላይ ግለቷን የጨመረችው ዘሐይ፣ ከመራት ጋር ተሞሀዶ የተቀበረውን ያህል ምድርና ሌላ ቀሻሻ ተስትሳው፣ አካባቢው ሁሉ ሞንትላት በሚበዙበዋ ጠረን ትሞላቷል። ምስጢር ሞታውን አመልጣለሁ ብላ ካንድ ድንጋይ ላይ ለመጫማት ስትሞክር አዳልዛት ልትወድት ስትንገዳገድ፣ ሳንቾ እጇን ይዞ ለትንሽ ባያተርፋት ኖሮ ከመራቱ መቃሳቱ አይቀርም ነበር። ከዛ በኋላ ከንዱን ጥብት አድርጋ ይዛ፣ ቀስ ብለው መራመድ ጀመሩ።

ምስትልትልና ግጥግጥ ብለው በተሰሩት የሞታ ቤቶች መካከል ያሉት መንገዶች በጣም ጠባብና ወጣ ገባ ናቸው። ባንድ ግቢ ውስጥ ስንት ቤትና ቤተሰብ እንዳለ ለማወቅም የሚቻል አይመስልም። በያጥሩ ላይ የጠላ ጣሳ፣ 'ጥሩ አንጀራ አለ' የሚሉ ምልክቶች፣ አንዳንዱ ግቢ ውስጥ ደግሞ ተዝረክረከው የተጣሉ ቢጫ ያረቁ ጀሪካኖች ይታያሉ። የተለያዩ የመጠጥ ጠርሙሶች፣ የቀርቀሮ ጣሳዎችና የወሃ ሳስቲኮች የተዘመራባቸው ግቢዎችን አለፉ። በየደጃፉ ላይ ከስድስት እስከ ሰምንት የሚሆኑ ነረምሶች ቀጠው ያወራሉ። በየበራፉና ግቢ ውስጥ ውር ውር የሚሉ እዛና እዚህ እኽብ ብሰው የሚጫወቱት ህጻናት ቁጥር ቀላል አይደለም። ወዲያ ወዲህ የሚሮጡ ውሾች፣ ጥቂት የማይባሉ ዶሮች፣ አህዮችና ድመቶችም በለፉሩ ውስጥ መኖራችን ይታወቅልን የሚሉ ይመስላሉ።

በሌላ ፕላኔት ላይ ወይም በሕልሟ እንዳለች ድንግርግር ያላት ምስጢር፣ በደመ ነፍስ ጥታውን እየሸሸች የሳንቾን ጃኬት ከኋላው ይዛ ትከተለዋለች።

"ሰኢዶ ... አር ዊ ኢን አዲስ?" አለች፣ ጃኬቱን ጎተት አድርጋ የዝናሽ አባት እንዳይሰሟት ይመስል።

ድንገት ካንድ ግቢ ውስጥ አንዲት ሕፃን ልጅ እየበረረች ሠዋታ የዝናሽ አባት እግር ላይ ተጠመጠመችና ትንፋሿ እየተቆራረጠ፣ "አባባ ... አባባ ... እየው ላዲሱ ግሙሽ የሠራው ለት መጫወቻ አሻንጉሊት። እማዬስ ... ማሙሽን አላመጣከውም እንዴ?" ስትላቸው፣ እንድ እጃቸውን ራሳቸው ላይ አድርገው ባለ በሌለ ድምጻቸው እሪታቸውን ለቀቁት። ከየግቢው ውስጥ ሰዉ ሁሉ ተሰበሰበና አካባቢው ባንድ ጊዜ በእስደንጋጭ ድራማ ተሞላ።

"ወየው ዝናዬ ጉድ አረግሽኝ ... ምን ልበላቸው ለልጆቹ ... ምን ልበላት ለሚው ... አዬ ዝናዬ ... እኔን ባስቀደመኝ ... አይሂሂሂ ... ልጄ ..." በማለት፣ እንከስ እንከስ እያሉ ወደ ግቢ ገቡ። ነገሩን ልከ ተንጋግረው በት እንደተዘጋጁ ግቢው ባንዴ በለቀሰተኛ ተሞላ። ሁኔታው ያሰደነገጣት የዝናሽ ልጅ አይኖቿን እያቁለጨለጨች ሰዉን ሁሉ ስታይ ቀየችና በፍርሃት ተወጣ ከአጥሩ ስር ተወሸቀች። በቀጸባ አያቷንና የሚጫሁትን ሰዎች እያየች የምታደርገው እንደ ጠፉት ታስታውታለች። እጇ ላይ ያለውን ሚጠጪዬ የጨርት አሻንጉሊት በትንሽ እጆቿ ሞብጥ አድርጋ አይኗ ግራና ቀኝ ተቁለጨለጨች። አይኖቿን ከሷ ላይ ያልነቱለችው ምስጢር ሁኔታው ከምትችለው በላይ ሆኖባት እንባዋ ፍልት ፍልት ማለት ጀመረ።

@OLDBOOOKSPDF

እንዴ ምንም ተስ ብላ ወዴ አጥሩ ጠጋ አለችና ልጅቷን ከጆርባዋ ነካ አድርጋ፣ "ሚሚዬ" ስትላት ፣ በደፍ የነበረችው ልጅ እሪታዋን ለቀቀችውና ወዴ ግቢው ውስጥ ሮጣ ገባች ። እሷም በድንጋጤ ድርቅ ብላ ለዮቂት ጊዜ ባለችበት ቀረች ። ግቢ ውስጥ ምንም መፈናፈኛ ቦታ ስላልነበረ ሁለቱም ከውጪ ቀመው ነገሩን መከታተል ጀመሩ። ብዙም ሳይቀይ ያችው ልጅ ባጠገባቸው ብን ብላ ስትሮጥ ምስጢር ተከትላት ለመሮጥ ዳዳት ።

ሳንቾን ግሽም አድርጋ ስታሳየው ፣ ወዴ ጆሮዋ ጠጋ ብሎ "ስው ልትጠራ ተልካ ይሆናል?" አላትና አይኑን እያሻሸ "ወይ ፈጣሪ" አለ ። እንዳለውም ብዙም ሳይቆይ አንዲት ወጣት ሴትዮ ሦስት ሕፃናት ልጆችን ከኋላዋ አስከትላ እየተወራጨች መዳሉበት ቀረበች ። ትንሿ የዝናሽ ልጅ ከሴትዮዋ ጮን ድክ ድክ እያለች ወዴ ሴትዮዋ እያየች የሆነ ነገር ታወራለች ። በሩ ጋ ስትደርስ ሴትዮዋ ሰዉን ሁሉ ጥሳ ገብታ ግቢውን ባዲስ ጩኸት አደባለቀችው ።

ትንሿ ልጅና ሌሎቹ ሕፃናት የሴትዮዋን ጩኸት ሲሰሙ በፍርሃት ሮጠው ወጡና ተደናግጠው እደጅ ቀሙ ። የዝናሽ ልጅ ሉሳዊ ጸጉሯ ሞብርር ብሎ ፣ በጠይም ከብ ፊቷ ላይ ትልልት አይኖቿ ሲንከባለሉ አንጀት ትበላለች ። ባጠለቀችው ያደፈ ቀይ ቀሚስ ላይ እጇና አንገቱ ላይ የተተዳደደ አረንጓዴ ሹራብ ደርባለች ። አንገቷ ላይ ያሰረችውን የክር ማተብ እየነካካች ፊቷን የወረሩትን ዝንቦች በሌላ እጇ ለማባረር ትሞክራለች ። ቁዝር ሆዷና በሞቷ የላቀጡ ድብልብል ባዶ እግሮቿ ድኽነትን ገና በጠዋቱ ተጫምታ ስታዩካው አንዳረፈዶች ምስክር ይመስላሉ ። ከሩቅ ቀማ ሰረቅ እያደረገች ስታያት ቀይታ ፊራ ተባ እያለች ወዴ ምስጢር ተጠጋች ።

ቀልቧን ከሷ ላይ ማንሳት ያልቻለችው ምስጢርም ቀስ ብላ ተጠጋቻትና ለስለስ ባለ ድምፅ ፣ "ሚሚዬ የኔ ቀንጆ ... ማነው ስምሽ?" ስትላት ፣ አፈር እንዴ ማለት ብላ ወዴ ኋላ ሸሸት አለች ። አሁንም ሪጋ ባለ ድምፅ ፣ "እስኪ ሚሚዬ ... የሠራሽውን አሻንጉሊት ልይልሽ ..." ስትላት ፣

ወዴ ዶረቷ አሰጠግታ በሁለት እጆቿ ጥብቅ አድርጋ ያዘችውና ፣ "እምቢየው ... ለማሙሽ ነው ...የሰላሁለት" ብላ ፣ ገረመመቻት ።

"ሌላ ወንድምና እህት አለሽ?"

"አዎና ... ሻምሾን ... አሁን ቅሺ ለቀማ ሂዱ ነዋ ..."

"ምንድነው ቅሺ ለቀማ?"

"እንዴዬ ልጅቷ ቅሺ ለቀማም አታቅም እንዴ...?" አለች ፣ ትንሽ ፊቷን ቀማ አድርጋ ።

"ምንድነው የሚለትመት ሚሚዬ?"

"እንዴዛ ... ጠልሙስ ... ኮንጆ ምግብ... እምም ... በቃ ኮንጆ ነገል ሁሉ ነዋ አለች ፣ ትንሽ ዘና እያለች ።

@OLDBOOOKSPDF

"ከየት ነው የሚለትሙትን?"

"ተገር ተቀሺ ነሞ ... ሙአት ከምል ኮ ነው ። አንቺ ቀሺ ሄድሽ አታቲም እንዴ?" ብላ፣ ፊቷን ቁጥር አድርጋ አየቻት ።

"አላውቅም የኔ ቀንጮ ። ማነው ያንቺ ስም ግን?"

"እዮ ቤቱ ቤቴ ሚጡ ... ትምልት ቤት ግን ሽምረት ነው ..." አለች፣ ኮራ ብላ ። ወዲያው ስሚ ሲጠራ ሰምታ ብር ብላ ወደ ውስጥ ገባች ። የተሰበሰበው ሰው ቁጥር ባይቀንስም ፈሚዜታውና ለትሶው ጋብ ሲልላቸው ሳንቾና ምሰጢር ወደ ውስጥ ገብተው የዝናሽን አባት ከልጃቸው ጋራ ሊያናግሯቸው ሞከሩ ። ሌሎች አንድ ሁለት ትልልቅ ያካባቢው ሰዎች ተጨምረው፣ ስለ አስከሬኑ አመጣጥና የቀብር ጉዳይ ተነጋገሩ ። የዝናሽን እህት ስልክ መሰዱና ሳንቾም የራሱን ቁጥር ሰጥቷቸው ወጡ ። ከሩቁ ተደብቃ ስትከታተላቸው የነበረችው የዝናሽ ልጅ ከግቢ ሲወጡ ሮጣ ተከትላቸው ምስጢርን ከኋላ ነካ አደረገቻት ። ዞር ስትል "አንቺ ልጅ ...ሽምሽ ማነው?" አለቻት ።

"የኔ ቀንጮ ..." ብላ ጮንበስ ብላ እቅፍ አድርጋ ሳመቻት ። "የኔ ስም ሚስጥር ነው ። ጓደኛዬ ትሆኚኛለሽ?" አለች ፊቷ ጥርስ በጥርስ ሆኖ ።

"እንዴሄ ... የሰው ስም ደሞ ሚሸጥል ነው እንዴ ..." ብላ፣ ፊቷን ኮስተር አደረገች ።

"እምን የኔ ስም ሚስጥር ነው የሚባለው፣ ስምረትዬ የኔ ቀንጮ ። አሁን መሄድ አለብን፣ ተመልሰን እንመጣለን እሺ? ምን ላምጣልሽ?"

"እም...ም ... መቻወቻ ..." አለች፣ ፊቷ ፍንድትድቅ ብሎ ።

"እሺ አመጣልሻለሁ፣ የኔ ቀንጮ"

"እሱ ያንቺ ወንድም ነው? ማነው ሽሙ?" አለች፣ ወደ ሳንቾ እያየች ።

"እሱ ሰኢድ ይባላል ። የኔ ጓደኛዬ ነው ። አንቺስ የኔ ጓደኛ ትሆኚኛለሽ?"

"እንዴሄ ... ትንሽ ልጅ ደግሞ የትልቅ ሰው ጓደኛ ይሆናል ደሞ እንዴ..."

"ለምን አይሆንም?" አለቻት እየሳቀች ።

"አይ ትልክ ሰው የትልክ ሰው ጓደኛ ብቻ ነው የሚሆነው ። "

ምስጢር ደግማ ሳም አደረገቻትና፣ "እሺ በቃ የኔ ቀንጮ ... እመጣለሁ እሺ"

"እማዬን ይዘሻት ትመጪለሽ? አሁን የት ነው ያለችው?" አለች፣ ትንሽ ፊቷ ላይ ጭንቀቷ እየተነበበ ።

"ስምረትዬ ...እሱን ስመጣ እናወራለን እሺ ..." አለች፣ በድንጋጤ የምትለው ጠፍቷት ።

"እሺ ... ማመሺን ይገዛሽ ቶሎ ነይ በያት እማዬን እሺ ..."

@OLDBOOOKSPDF

"እሺ ..." ብላ፣ ፊቷን አዞረች ሳታስበው እምባዋ እንዳያመልጣት ፈርታ፣ ምስጢር ተሰናብታት ስትሄድ፣ ሳንቾም ጎንበስ ብሎ ግንባሯ ላይ ሳም አድርጓት ወደ ቤት እንድትገባ ነገራት። ዞር ሲል ምስጢር ታለትሳለች። በዝምታ ወደ መኪናው አመሩ። ሰዓቱ ከቀኑ አምስት ሰዓት ተኩል አካባቢ ሲሆን በጠራው ሰማይ ላይ የዐሐያ ግለት አይሏል። ቀኑ ብራ ሊውል ይመስላል። ሞቷው ጠገግ ብሎ ለመረመድ ብዙም እገር አይገሙም። ዘባኻገር ካለው አጥር ጥግ አንድ ትልት ሰውዬ ቁሚ ብለው ሲጸዳዱ ሳንቾ አይቶ አፈረና ፊቱን አዞረ። የግድ ባጠገባቸው ማለፍ ስለ ነበረባቸው፣ ቀረብ ሲሉ ሰውዬው ኮራ ብለው ሰላምታ ሲሰጧቸው አጸፋውን ሰመመለስ ተገደዱ።

"አሁን ለዚች ሕፃን ልጅ ስለ እናቷ ምት እንዴት አድርገህ ነው የምታስረጻት፣ ኡፍፍፍ ... ወይኔ ... እዚሁ አዲሳባ ውስጥ እንደዚህ አይነት ሕይወት እንዳለ በውነም በሕልሜም አስቤም አላውቅም" ብላ፣ ፊቷ እንዲ ጨፈገገ ከሰፈሩ ፈጥና ለመውጣት እንደ ፈለገች ሁሉ የመኪናውን ፍጥነት ጨምሬ ወጣች።

"ሽረ ቀስ ... ወዴት ለማምለጥ ነው? ከዚህ የባሰ ስንት ነገር አለ መሰለሽ። እዲስ አባባ ኮ አበባዋ ቦሌ መንገድ ... ጃክሮስ ... ሲኤምሲ አካባቢና አስፋልት አስፋልቱን ተከትሎ ነው። ውስጥ ውስጡን ስትገቢ እዲስም የለም አበባም የለም ... ዕድሜ የጠገበ አሮጊ መከራ ብቻ ነው። ለቀብር ስንመጣ ደግሞ የባስውን ገና ታያለሽ።" መላ የሌለው ዝብርቅርት ፋጨት ማፏጨት ጀመረ።

"አንተ ግን ምንም የገረመህ አትመስልም ... ዘግናኝ ነገር አኮ ነው። ባንድ ከተማ እየኖርን ... ኦህ ማይ ጋድ" ብላ፣ መሪውን በቡጢ ስትጠልዘው ከላክሱ አምባረቀ።

"ሚስጥር ... እኔ ኮ ሰምረትን ሳክል ነው ጮዳና ላይ የወጣሁት። ደሴ በየቱቦውና በየበረንዳው ላይ ስድስት ዓመት ኖሬያለሁ። እጣቢ ብትይ የቦይ ውኃ፣ ሰው ሲያስበው የሚችለው ፈላሽነገር ... እኔ ያልጠጣሁት የለም። ከውሻ ጋር ተሻምተንየተበላሸምገብ በልተናል። ሌሊቱን መሉ ላዬ ላይ ዝናብ ዘንቦብኝ ሳልበላ ወዬ አድሬ አውቃለሁ። ሥጋማ ማድረግ ምን እንደሆነ ያወቅሁት መቼ እንደሆነ ታውቂያለሽ? አዲሳባ መጥቼ ታክሲ ረዳት ሆኜ መሥራት ስጀምር ነው። ስላውም ሁለት አይነት እሮጌ ሥጋ።

"ጮዳና ላይ ስኖር፣ ተደብድቤና ደም በደም ሆኜ እንደ ሰው በሐኪም ርዳታ ሆስፒታል ገብቼ ሳይሆን፣ በአላህ ፈቃድ ብቻ ነው ትረፍ ስላለኝ በተአምሩ የዳንኩት። ገና ባስራ ሁለት ዓመቴ ሶስት ጮሪምሶች ሌሊት ላይ በግድ እንቀውኝ እያስሠሙ ..." አለና ፊቱ ተለዋወጠ። የእጁን ጣቶች ደጋግሞ እያንቋቋ በረጅሙ ተነፈሰና ዝም አለ። "ከፈለግሽ ሌላም ልነግርሽ እችላለሁ ከዚህ የባሰ ... አይበቃም ...? ይሄ ላንቺ አስደንጋጭ የሆነ አዲስ የሕይወት ዕይታ ሊሆን ይችላል። ለኔ ግን ተዘፍቄ የኖርኩበት ያረጀ የኑሮ ትዝታ ነው። አያስደንግጠኝም ማለት ግን አይሰማኝም ወይም አያመኝም ማለት አይደለም። ከማንም በላይ ውስጤን ያመሸል... ልቤን ያደማዋል" ሲል፣ አያንዳንዱ አረፍተ ነገር በድንጋጤ እድርቀ አስቀራት። ይሄኛው የሳንቾ ታሪክ ፈጽሞ የማታውቀው ነው።

"ይቅርታ ... ይቅርታ ... በራሴ አፈርኩ" አለች፣ ምንም የምትለው ቢጠፋት።

@OLDBOOOKSPDF

"ለምን? ... ያንቺ ጥፋት አይደለም ። እኔም ብሆን ያለፍኩበትን ሕይወት እንኳን ለራሴ፣ ለጠላቴም ልጅ አልመኘውም ። የእውነታውን ጥልቀት እንድታውቂውና የዚህ ዓይነት ሕይወት ለመረዳት ሩቅ መሄድ እንደማያስፈልግሽ እንድታውቂው ብዬ ነው ። የግቢያችሁን ዘበኛ ወይም የቤት ሠራተኞችሁን ጊዜ ወስደሽ አዋሪያቸው ። ብዙዎቹ ተመሳሳይ ታሪክ ተሸክመው ነው የሚዞሩት ። ሀብታም ቤት ተቀጠረው ሰለሠሩ ሀብታም ቤት ያድጉ እንዳይመስልሽ ። እንዲያውም ቀሺ ከሚናሩት ይልቅ በየቦሌው በየኒላው ያሉ ዘበኞችና የቤት ሠራተኞች ናቸው የሚያሳዝኑኝ ።" ግንባሩ ላይ ያለውን ላብ ከኪሱ ናፕኪን አውጥቶ ጠራረገ ።

"ዓይናችን ታውሮ፣ ልባችን ተዘግቶ ነው ... ልክ ነህ ... እንደ ዝናሽ ያሉ መንገዱን የሞሉ የአእምሮ ሀመም*ተኞች ... ሳንቲም ወርውረንላቸው የምንሄደው የኔ ቤጤዎች ሁሉ ታሪክና ኑሮ ያላቸው ሰዎች መሆናቸውን እንረሳለን ። ስምረት የዝናሽ ልጅ መሆኗን ብቻ ሳይሆን ዝናሽ የስምረት ሕይወትና ዓለም መሆኗን መች እናስባለን ። ...ኦህ ማይ ጋድ ... ምን አይነት ስግብግቦች ሆነናል?"

"ካስብንበት አውንም ብዙ ጊዜ አለ ... ከዛሬ የተሻለ ቀን ከአውንም የተመቸ ስእት ናሮ አያውትም" ብሎ፣ በረጂሙ ተነፈሰ ። በሱ በኩል ያለውን መስኮት ሲከፍተው ተዝታዛው ነፋስ የደጁን ብርድ ሽሽት ይመስል በጥድፊያ ከመኪናው ውስጥ ገብቶ ተጠቀጠቀ ።

"ውይይ በናትህ ሰኢድ ዝጋው ... አይበርድህም እንዴ?" ብላ፣ ስካርፏን አንገቷ ላይ አስተካክላ ። "ቆይ አንተ ግን እንዴት ይሆንን ሁሉ ነገር ተሸዘመህ እንድ ነገር እንኳን ሳትነግረኝ?"

"ሚስጥር ... የምትሰሚው የጠየቅሽውን ብቻ ነው ። የምትጠይቂው ደግሞ የፈለግሽውን ነው" ሲላት፣ ዞር ብላ አየት አደረገችው ።

"ዛሬ ግን ትንሽ ፈልሰፍሰፍ አድርገሃል ሰኢድ ... ጠለት ያለ ነገር ሆኗል ንግግርህ ሁሉ ... ምነድነው ንገሩ? " ብላ፣ ትከሻውን መታ አደረገችው ። ሁለቱም ሰረጅም ዶቂቃዎች በየራሳቸው ሐሳብ ውስጥ ተውጠው ቆዩ ። "እንዴ በዛው ጠፍቶ ቀረ እኮ ዶክተር ሴላ... ወይ እስኪ ደውልለት ። ሲሄድ በጣም የተረበሸ ይመስል ነበር ..." አለች፣ ሃሳብ ገብቷት ።

ሰልኩን ከኪሱ ውስጥ አውጥቶ ደወለ ። "አይገርምም ... እኔም ልክ እሱን ሳስብ ነበር ... ምናልባት ብቻውን መሆን ፈልጎ ይሆናል ብዬ ነው የተውኩት ። በዝናሽ ጉዳይ በጣም ኢንቮልቭድ ሆኖ ሰለነበር በጣም ሳይገዳ አይተርም ። ትዝ ይለኛል ትንሽ ሲሻላት እንዴት ደስ ብሎት እንደነበር ። ንዴሕ ከመሄዱ በፊት ሄደው ጠይቀዋት ነበር" አለ ። ወዲያው ሰልኩ ሲነሣ፣ "ዶክተር እኛ ነን ... እማን ነህ? ቺክ እናድርግህ ብለን ነው"

"ምን ይህንነት አለ ብለህ ነው ሳንች ... የለው ሕይወት በረከሰበት ሀገር ውስጥ ጾሀኖ መሆን መታመም፣ መ*ሞ*ሞሞሞ መሆኑ ነው ። ሙስጠ በጣም ተረብሾ ሰለነበር ሳብቻዪ መሆን ፈለግሁኝ ። በጣም ይቅርታ በማታውቂት ችግር፣ እናንተ ላይ

@OLDBOOKSPDF

ጥይቱችሁ ጠፋው አይደል?" አለው፣ ሐዘንና ተስፋ መቁረጡን በሚገልጥ የታከተ ድምፅ።

"ኧረ በፍጹም እትጨነት ... እኛ ላንተ ነው ያሰብነው።" ያዩረትትን ነገር ባጭሩ ንግሮት ሰምንት ሰዓት ላይ ሊገናኙ ተቀጣጠሩ። የተቀጣጠሩበት ሰዓት እስኪደርስ ምላ እየበሉ የጀመሩትን ጨዋታ ተጠሉ። የሕይወት ታሪኩን በሙሉ ከሥር መሠረቱ ጀምሮ አጫወታት። ከተቀጣጠሩበት ኢትዮጵያ ሆቴል ቀድሟቸው ካንድ ጥገኛ ተቀምጦ ጋዜጣ ሲያገላብጥ ደረሱ። ወንበር ስበው ተቀመጡና ስለ ዝናሽ ግውረት ጀመሩ።

"ታዲያ የቀብሩን ሰዓት ወሰኑ እንዴ?" አለ፣ ሌላሠው ውኃው ውስጥ ተዘርሮ የተረሳው ሻይ ዘመቅላት ወደ መጥቁር መቀየሩን እያየ። አስተናጋጁን ጠርቶ ቀዋነ ያለቀለት ሻይ አዘዘ።

"ለነገ ጠዋት ነው የታሰበው። ቀብሩ የሚፈጸምበት ቤተክርስቲያንም እዛው ሰፈር ነው መሰለኝ። የእህቷ ቤት ትንሽ ሰፋ ስለሚል ነው መሰለኝ። የአባቷ ነገር ስላለ ከዛ ነው ሬሳውም እንዲወጣ ያሰቡት" ሲል፣ ምስጢር ቀበል አድርጋ፣

"በሕይወቱ እንደዛ ዓይነት ሰው የሚኖርበት ቦታ ይኖራል ብዬ ... በተለይ እዚህ አዲሳባ ውስጥ ... አስቤም አላውቅም ... ው-ይ-ኔ ... ደግሞ ብታይ የዝናሽ ትንሿ ልጄ ... የኔ እናት ለሕፃኑ መሥዧወቻ አሻንጉሊት ሠርታ አያቷ ...ን ..." ብላ እንባዋ ቀደማትና መቀጠል አቃታት። ከቦርሳዋ ውስጥ ናፕኪን አውጥታ ዓይኗን ጠራረገች። "እቡ ግን አውን የት እንዳለ ይታወቃል እንዴ ለመሆኑ? የት ነው ግን የወለዷችው?" አለች፣ አውንም ካልወጣው እያለ የሚተናነቃትን እምባ እየገታች በተቀራረጠ ድምፅ።

"ገና አልደረሰችም ብለው ከጥቁር አንበሳ መልሰዋት አማኑኤል ኮረደር ላይ ነው የወለደችው፣ ብላ ነው ነርሷ የነገረችኝ ጠዋት። ስትነግረኝ በጣም ደንግጬ ነበር። ስለ ሕፃኑ ምንም አልጠየኳትም ... አሷም ምንም አልነገረችኝም መሰለኝ።" ጭንግላ ያለ ፊቱን ፈታ ቋጠር እያደረገ ለማሰብ ሞከረ።

"የሷን መሞት ከሰሙ ቢያንስ በተሰብ ሳያማክሩ ለአንዱ ሕፃናት ማሳደጊያ ወይም ጉዲፈቻ ድርጅት እንዳይሰጡት ደግሞ። አውንማ ኮ የልጅ ገዘያውም ደርጅቶ አሉ ... በተለይ አዲስ የተወለደ ሕፃን በጣም ነው የሚፈለገው ይላሉ" አለ፣ ሳነ አንዳንድ የሰማቸው ታሪኮች ትዝ እያሉት።

"ለምንድነው አዲስ የተወለደ ሕፃን የበለጠ የሚፈለገው?" አለች፣ ምስጢር ንገሩ ከሞታሰበው የተገላቢጦሽ እየሆነባት።

"አዲስ ሕፃን ከሆነ ያው ያለ ብዙ ኮተትና የኋላ ታሪክ የራሳቸው ልጅ አድርገው ስለሚያሳድጉት መሰለኝ። አዲስ ልጅ ሲሆን አይ ቲንክ የበለጠ ወላጅነትም እንዲሰማ ሳያደርግ አይቀርም። በተለይ ተጥለው የተገኙ ልጆች ከሆኑ ደግሞ ተቀናቃኝ ስለማይኖር የበለጠ ይመ[illegible]ማ ማዋለጃ ክፍሎችና የወሊ

ሕፃናት የዘትባትና ክትትል ከሲኒኮች ሰለ ተሰረቁ ልጆች ብዙ ሰምቻለሁ" ሲል ፣ ነገሩ ሁለቱንም ዘገነናቸው ።

"እውነትህን ነው? ... የማይሰማ ነገር የለም ። እስኪ ለማንኛውም ሲስተር ጋ አማኑኤል ልደውልላት ..." ብሎ ፣ ስልኩን አውጥቶ ጠዋት የደወለችለት ነርስ ጋ ደወለ ። ሕፃኗ ሴት መሆኗንና ትንሽ የመተንፈስ ችግር ስለነበረባት ጥቁር አንበሳ በድስተኛ ፎቅ እንዳስተኟት ነገረችው ። ብዙም ሳይቆዩ በእርሱ መኪና ተያይዘው ሕፃኗን ለማየት ወደ ጥቁር አንበሳ ሄዱ ። ገና የተወለዱ ጨቅላ ሕፃናት ወደሚተኙበት ክፍል ደርሰው መረጃ ለመጠየቅ ቢሞክሩም ምንም የሚረዳቸው ሰው አላገኙም ። አንዲት እድሜዋ ገፋ ያለ ነርስ ወደ ውስጥ ለመግባት በሩን ስትከፍት ጠጋ ብሎ

"ደህና ዋልሽ ሲስተር ... እባክሽ ላስቸግርሽ ..." ሲላት ፣ በሩን በእጇ እንደ ተደገፈች ዞር ብላ ስታየው "ዶክተር ሴላሠው እባላለሁ ። ጠዋት ላይ አንድ ህመምተኛዬ ከአማኑኤል ሆስፒታል ወልዳ ነበር ። ሕፃኗ ትንሽ የመተንፈስ ችግር አጋጥሟት እዚህ ተኝታለች ብለውኝ እሷን ለማየት ነበር" ሲል ፈጠን ብላ

"ማነው ስሟ?"

"የናቷ ስም ዝናሽ በድሉ ነው ። "

"እስኪ ልይልህ ... እናቷም እዚህ እኛው ጋ ናት ወይስ?" አለች ፣ ሴላሠውን ከላይ እስከታች እያጠናች ። ብዙ ሐኪሞች ለሕመምተኛ ያን ያህል ተጨንቀው እንደዚህ ሲያደርጉ ስለማታይ ትንሽ ገርሟት ።

"አይ አይደለም ... በጣም ነው የሚያሳዝነኝ ጳውሎስ ልከዋት ከወለደች በኋላ ብዙ ደም ፈሷት በለአቱ ሳይደርሱላት እዛው አርፋለች ..."

"ውይ ውይ ... እኔ አፈር ልብላ ... እስኪ ውስጥ እንግባና ቺክ ላድርግልሃ ... ቀን ላይ እንደሱ ዓይነት ነገር ሲያወሩ የሰማሁ መሰለኝ" አለች ፣ በሩን ከፍታ እየያዘችለት ።

"ከነርሱም ጋር አብረን ነው የምንሠራው ... መግባት ይችሉ ይሆን?" ሲላት ፣ ፈቀደችላቸውና ተከተለዋት ወደ ውስጥ ዘለቁ ። ገና ሲገቡ የከፍሉ ሙቀትና አዲስ የተወለዱ ሕፃናት ጠረን ተቀበላቸው ። ወደ አንድ ቢሮ አስገባቻቸውና ለማረጋገጥ ሕፃናቱ ወደሚተኙበት ክፍል ሄደች ። ብዙም ሳትቀይ ተመለሰች ።

"አምን አለች ... ምንም አትልም ፤ አተነፋፈሷም ብዙ ለውጥ አለው ። ውይ ደግሞ እንዴት ቀንጅዬ ልጅ ናት መሰላችሁ ... ታዲያ ቤተሰብ አለ ወይስ ምንድነው የሚደረገው?" ስትል ፣ እርስ በርስ ተያዩ ።

"የናቷ እህትና አባት አሉ ። ሌሎች ሁለት ታላላቅ እህትና ወንድሟም ከእያትዬው ጋር ነው የሚኖሩት ። ግን ያው ችግረኛ ቤተሰብ ነው" አለ ፣ ሴላሠው ጠረጴዛው ላይ በከፊል ደገፍ ብሎ እንደ ተቀመጠ ።

"አባቷስ?"

@OLDBOOOKSPDF

"አባቷ እንኳ የሚታወት አይመስለኝም" አለና የዝናሽን ታሪክ ባጭሩ ሲነግረት በነገሩ የበለጠ አዘነች ።

"አይ ሰው መሆን ... መፈጠር የሚያስጠላበት ዘመን ... ታዲያ ምንድ የምትደረገው?" በመስታወት ግድግዳው ውስጥ አሙልቀው በተርታ ተደርድረ የተኙትን ሕፃናት ለማየት ሞከሩ ።

"እስኪ እንግዲህ የእናቷ ቀብርም ነገ ነው መሰለኝ ። ቤተሰቡን አናገረ የሚደረገውን እናያለና ። እዚህ ብዙ የሚያቀፍዋት ይመስልሻል? ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ምንድነው የሚያደርጉት?"

"አይ ዶክተርዬ ... ብዙ የጉዲፈቻ ድርጅቶችና የሕፃናት ማሳደጊያዎች አሉ፣ ተረካቢ ቤተሰብ ከሌለ ለፖሊስ አስታውቀን እነርሱ ይወስዷታል ። ከዛም ... ወደ እንዱ ፈረንጅ ይወሰዳታላ ... ምን መላ አለው ብለህ ነው የድሀ ነገር" ብላ፣ ሰላቷን አየት አደረገች ።

"ሲስተርዬ ... የትኖዋ እንደ ሆነችም እኮ አላወቅሁም ... ባክሽን ተረብ ብለን ልናያት እንችላለን?" አለች፣ ምስጢር ፈራ ተባ እያለች ።

"ቀይ እስኪ ትንሽ ደህና ከሆንች ወደዚህ ላምጣላችሁ? እስከዛው እዛች ጋ እጃችሁን መታጠብ ትችላለችሁ" ብላ፣ ወደ ውስጥ ገባች ። ይዛት ስትመጣ ምስጢር ተሽቀዳድማ ታቀፈቻት ። ሚጢጢዬ እጆቿን አቆ ላይ እያሻሸች ዓይኗን በክፈል ከፈት አድርጋ ትንሽ ድምፅ አሰማች ። ከላይ ከላይ ስለምትተነፈስ ትንሽዋ አፍንጫና ያንገቷ ጡንቻዎች ሥራ በዝቶባቸዋል ። ከሦስት ኪሎ የማታንስ ድንቡሽቡሽና ቀላ ያለች ስትሆን፣ ጥቁር ሱሟ ጸጉሯ የበለጠ የምታምር ሕፃን መልእክ አስመስሏታል ።

"የኔ ቀንጆ ... እንዴት ታምራለች?" ብላ፣ ወዲ ደረቷ ጠጋ አድርጋ ያዘቻት ። እህቷ ስፆሪት ጠዋት መሣፈቻ እሻንጉሊት ይዛ ሮጣ ስትመጣ የነበረው ሁኔታ ትዝ ሲላት፣ እንባዋ ገባኦም አለባትና ሕፃኗን ለሌላው ሰጠችው ። ገም ብላ ዓይን ዓይኗን ማየት ጀመረች ።

"እህቷን አትመሰልም?" አለ፣ ገም ብሎ የነበረው ሳንቶ ትንሽ እጇን እየነካካ ።

"እኔም እሱን ነበር ሳስብ የነበረው" አለች፣ ምስጢር መልሳ ከሌላው ላይ እየተቀበለችው ። ነርሷ ተመልሳ ስትመጣ ቤተሰቡን አነጋግረውና ከቻሉ ያዘዋቸው ከቀብር በኋላ እንደሚመጡና ከዛ ወዲህ ግን ከሆስፒታል መውጣት ከለባት እንድትያውሏቸው ሰልካቸውን ሰጧት ። ሕፃኗን ከተቀበለች በኋላ ሌላውን ትኮ ብላ አየት አደረገችው፣

"ላሰፈው በቴሌ ኢንተርኒው ሲያደርጉህ የነበረው ከሜሪካ የመጣችው ሳይኪያትሪስት ነህ?" ስትለው፣ ትከክል እንደሆነ ነገራት ። ታለ መጠይቁን በጣም እንደ ወደዱትውና ፕሮግራሙ ቢተኮል ብዙ ሰው እንደሚጠቅም ነግራውና ተመልሶበት ሄዱ ። የምስጢር ልብ ግን @ebcbooks ከሕፃኗ ጋር ተጣብቆ ቀረ ።

ከሆስፒታል ከወጡ በኋላ ወዶ ዝናሽ ቤተሰብ ቤት ሄደው ስለ ሕባኗና ስለቀብሩ ጉዳይ ከአሀቷና ካባቷ ጋር ተመካከረው አስከሬኑን ለማጓጓዣና ላንዳንድ ወጪ የሚሆን ገንዘብም ሰጪቸው። ምስጢር ከስምረት ጋር መጻጅንቷን አጠናክራ ካንድ ጥግ ተቀምጠው ያወራሉ። ከመኪናዋ ውስጥ ያገኘችውን ትንሽዬ የጥንቸል አሻንጉሊት ለጥቃት ተፍነክንካለች። ስጊዚው እናቷንም ሕባኑንም ረስታ ዓለሟ ሁሉ በምስጢርና በአዲሱ አሻንጉሊቷ ሙሪያ ሆኗል። በመሀል ብር ብላ ሮጣ ወጣችና ወንድሟን ከባሮ አስከትላው መጣች።

ምስጢር ጋ ሲደርሱ ትንፋሿ እጥር እጥር እያለ "እሺ የማዬና የኔ ጓደኛ ናት ... አሻንኩሊቷን የሸተችኝ እሺ ነች..." ብላ፣ እትፏ ውስጥ ስትገባ፣ ጸጉሯን እያሻሸች ሳመቻት። አፈር ብሎ ራት ብሎ ወዶ ቀመው የስምረት ወንድም እጇን ዘርግታ፣

"ና እስኪ ... ጨብጠኛ ... ምነው ፈራህ እንዴ?" ስትለው፣ እያመነታ ቀረብ ብሎ ቀመ። እዚህ ሰፈር ሕባኑም አጥቂውም ተጠራጣሪ ይመስላል። ትልልቁም ሰው እነሱን እያየ ያንሾካሹካል። ጠጉረ ልውጦቹ እነሱ ብቻ ናቸው። ቀስ ብሎ እጁን ከሩቁ ዘርግቶ ሲጨብጣት፣ "ማንው ስምህ የኔ ቀንጆ? ና እስኪ ጠጋ ብል ..." ስትለው፣

"ሳምሶን" አለ፣ ድምፁን ዝግ አድርጎ በጨረፍታ እያያት። ዕድሜው ሰባት አካባቢ ሲሆን ዓይናፋር ነገር ይመስላል። የአረብ ክልስ ስለሆነ፣ ሠፈር ውስጥ አረቦ ነው የሚሉት። ብዙ ልጆች በተለያየ ስም እየጠሩ ስለሚያበሽቁት ሁሌ እንደ ተደበደበና እንደ ተደባደበ ነው። ከዕድሜው በላይ ረጅም ሲሆን፣ የሚያምር የክልስ መልክ አለው። ምስጢርን ያስቸገሯት ስለ መሰላት የዝናሽ እህት ድንገት አንባረቀችባቸው። "ዝሉ ወዶ ጓዳ ሂዱ ... ምን ዓይነት ዓይናውጣዎቹ ናቸው ባካቹ ... ገፊዎች" ስትል፣ ደንብረው ተሯሩጠው ሂዱ። ምስጢርም በድንጋጤ ከው ብላ መልስ ለመስጠት እንኳ ጥቂት ጊዜ ወሰደባት።

ሰዓቱ እየሄደ ስለነበረ በማግስቱ ለቀብሩ እንመጣለን ብለው ተሰናብተው ወጡ። ሳንቾን ቤቱ አድርሳው ለብቻዋ ወዶ ቤቷ ስትነዳ የዝናሽ ልጆች ሁኔታ ሞንትላሷን ወጥሮት እላሷ ብቻ ነበር መኪና ውስጥ የነበረው። ልቧ እንዴ ሆስፒታል ያለችው አዲሷ የዝናሽ ልጅ ጋ ደግሞ ዘነበወርቅ ቀሺ ሰፈር ስታወራቸው የዋለችው ስምረትና ሳምሶን ጋ ሲመላለስ ነበር። ዋናው መግቢያ በር ላይ ስትደርስ ዝማታ ተረኛ ዘበኛው ጋር እንደልማዷ ትንሽ እወርታ

"ይሀና ይደሩ" አለችና አልፎ አልፎ እንደምታደርገው ለቡና መጠጫ ብላ ትንሽ ገንዘብ ስታሰጪብጣቸው ወዶ ታች ለጥ ብለው ወደ ላይ የተለጠጠ ምስጋናቸውን አዘንቡባት። ወዶ ግቢ ስትገባ የግቢው ሰፋትና ማማር፣ እሷና እናቷ ብቻ የሚኖሩበትን ባለ ስድስት መኝታ ቤቱን ትልቅ ነፈላና ባለ ብዙ ክፍል ሰርቪስ ቤት እይታ ለመጀመሪያ ጊዜ ኃፍረት ተሰማት። ቤት እንደገባች እንደለመዱት ጫማዋን ወርወር ወረወር አድርጋ የናቷን ትንሿ ሣም አድርጋ ወዶ መኝታ ቤቷ ለመሄድ ስትነሣ፣

"ሚሚዬ ትንሽ ቁጭ በይ እንጂ ዶት ትሂጅ" አሉ።

@OLDBOOKSPDF

"ውይ ማሚዬ ዛሬ እንዴት እንዴ ደከመኝ ... ዩ ሃቭ ኖ አይዲያ ... የት እንደ ዋልኩ ብታቂ ... መጀመሪያ ግን ሻወር መውሰድ አለብኝ ... ቁሽሽ ነው ያልኩት፥ ልጆቹ የሉም እንዴ?" አለች ፥ ፊቷን በድካም እንደጨፈገገ ።

"ኧረ ነበሩ ..." ብለው ተጣሩ ። "የት ስትሆሪ ውለሽ ነው ልጄ ፥ እንደዚህ ጥቃ በጭቃ የሆንሽው? ራትሰ በልተሻል?" አሉ ፥ ከግር እስከ ራሷ እያጤኗት ።

"አይ ይቅርብኝ ... ቆይ አሁን ልብሴንም ልቀይር ማሚዬ ... ሽሮ ነገር ካለ ትንሽ እቀምሳለሁ ... እና ቡና ካለ ...ራስ ምታቱም ሊገድለኝ ነው" ብላ ፥ መልሳቸውን ሳትጠብቅ ወደ ላይ ወጣች ። መኝታ ቤቷ ስትገባ የክፍሉ ስፋትና ያልጋው ትልቅነት ... ቁም ሳጥኗ ውስጥ ያለው ልብስ ብዛትና መልበሻ ጠረጴዛዋ ላይ የተደረደረው የሽቶና የቅባት አጓኑት ሁሉ በዘንበወርቅ ድሆች ላይ የሚቀልዱ አሽሟጣጮች መሰለው ታዩዋት ።

በፍጥነት ልብሷን ውልቅልቅ አድርጋ ፥ ፎጣዋን እንደያዘች ከውሃው ውሰየ ገባች ። ውሃውን ለታ ጸጥ ብላ ቀመች ። ለሰስ ያለው ውሃ ዛል ያለውን የጋለ ሠውነቷን ተገዛተገና ዘና አደረገላት ። ከጠዋት ጀምሮ ስታየው የዋለችውን አላባኝ ትዕይንት ግ ከውስጢ አዮዐ ሊያስወጣላት አልቻለም ። የዝናሽ አባት ጉስቁልና ... የልጆቿ ዕጣ ፈንታና በዘንበወርቅ ውስጥ የታጨቀው የሰው ልጅ ስቃይ ባንዴ በውስጢ ተገተልትለው አለፉ ። ትንሿ የዝናሽ ልጅ ገና በልጅነቷ ያረፈባት የመከራ ዱላ ያላጠፋው የዋህ ፊቷ ድቅን አለባት ። ባንድ አዲስ አበባ ውስጥ ስንት ዓይነት ሰው አለ ። ድምፅዋን ባታውጣም ውስጢ ግን እየለፈለፈ ነበር ።

አዲሳባ የማታውታቸውና አሷን የማይመስሉ ሌላ ዓይነት ሰዎች በሌላ ሰፈር እንደሚኖሩ እስከ አሁን አለማወቋ አስደንግጢታል ። ጐረምሶቹና ሕፃናቱ ፥ ቤቶቹና ወንዶቹ ፥ አዛውንቶቹና አትሙ ደካሞቹ ሁሉ ታዩዋት ። ቀሺና ዘንበወርቅ ያንድ ሰፈር ሁለት ሰሞች ። ቢያንስ ዝናሽን ለማዳን ጊዚው ያለፈ ቢሆነም የዝናሽ ልጆች ዕጣ ፈንታ ግን በሌላ ሰው ሊሳበብ የማይችል የሷ ኃላፊነት እንደ ሆነ አሰበች ። ትንሽ ቀለለ ብሷት ፥ ስውነቷን አደራርታ ከመታጠቢያ ቤት ወጣች ።

ዘንበወርቅ ፥ ካፈሩ ወርቅ ባይታፈስም ከወርቅ ይልቅ የክበሩት እንደ ከየከብት የሚያበሩት የዝናሽ ልጆችና ሰፈሩ ውስጥ የሚርመሰመሱት ሌሎች ሕፃናት ታዩዋት ፥ ሰው ሚሊዮን ዶላር አፍስሶ ከድንጋይ መሀል ወርቅ ያስላል ። እዚሁ ከተማ መሀል የፈሰሱት ሕያዋን ወርቆች ላይ ግን የቢትና የሠቱሉን ቁሻሻ ይደፋባቸዋል ። ይህን እያሰበች እንገቷ ላይ ያለውን የወርቅ ሀብል እውልታ በጥንቃቄ አስቀመጠች ፥ የዝናሽ ልጆች በጭቃ ጸዝረውና በረሀብ ጠውልገው ፥ በእናታቸው ሞት ቅስማቸው ተሰብሮ አልጋ በሌለበት ሜዳ ላይ መጻድተው ታዩዋት ። በሚያምር ሙጸይ ውስዋ የጨመረችው የሚያብለጨልጭ ወርቅ በምጸት የሣቀባት መሰላት ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 17 ፡

ሌላው የረባ እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር እንዲሁ ሲገላበጥ ነጋ ። ከነምስጢር ጋር ቀብር ለመድረስ ላፍቶ ሞል ፊት ለፊት ተገናኝተው በሱ መኪና ተሰባስበው ሄዱ ። መኪናውን አሮጌው ቤተክርስቲያን ጋ አቆማት ። በቀጭኗ መንገድ ውስጥ ውስጡን ተከታትለው ሲሄዱ ፣ ያካባቢው ሰው ዞርና ቀም እያለ አያቸው ። የዝናሽ አባት የሚኖሩበት ግቢ ሲደርሱ ሜር ብሎ ማንም ሰው አልነበረም ። እስከፊት የሚወጣው ከዝናሽ እህት ቤት ሰለሆነ አንድ ከፍ ያለች የሰፈሩ ልጅ ቤቱን እሳየቻቸው ።

ጠቅር ያለው ደመና ከበላዩ ያለውን ሰማይ ለመሸፈን በጥድፊያ ከወዲያ ወዲህ እያለ ፣ ገባ ወጣ ከምትለው ፀሐይ ጋር እሰጥ እገባ የያዘ ይመስላል ። ፀሐይዋም የሰማዩ እመቤትና የምድሪቱ አድማቂነቷን ለማስረገጥ ይመስል ፣ በሰማያዊ ጥለት ያጌጠውን ደመና እንደ ሀገር ልብስ ተጉናጽፋ ፣ አልፎ አልፎ ብቅ ጥልቅ ትላለች ።

ግቢው በሰው ግጥም ብሎ ለቀስተኛው ሲንጫጫ ደረሱ ። ወደ ውስጥ ሲገቡ ያገር መሪ እንደ መጣ ያህል ሰዉ ሁሉ መንገዱን ክፍትፍት እያደረገ ዞር ዞር አሰላቸው ። ማንነታቸውን ያላወቀው እየጠየቀ ያወቀውም ላላወቀው ባድናቆት እያንሾካሾከ ዝናቸው በለቀስተኞቹ ዘንድ ባንዴ ናኘ ። መምጣታቸው ሲጠበቅ የነበረ ይመስል ወዲያው አስከሬኑ ከቤት ወጥቶ ጉዞ ወደ ቤተክርስቲያን ሆነ ። ምስጢር እነስምረትን ፍለጋ ዓይኗ ግራ ቀኝ ቢንከራተትም አንዳቸውም በአካባቢው አልነበሩም ።

ሌላው በበኩሉ ገነትን ወይም እናቷን የሚመስል ሰው ካገኘው ብሎ ወዲያ ወዲህ ማማተሩን ቀጠለ ። ሥርዓተ ፍትሃቱ እስኪያልቅ ድረስ በዕድሜ ገፋ ወዳሉ ሰዎች በቀስታ እየቀረበ ማጠያየቁን ቀጠለ ። እንድም ፍንጭ የሚሰጠው ሰው አላገኘም ። ጸሎቱ አልቆ አስከሬኑ ሲያዘቀዝቅ ፣ የዝናሽ እህት ለያዥ ለገናዥ አስቸገረች ። ወደ ጉድጓዱ ካልወደቅህ ብላ ሰትዝለፈለፍ ተረባርበው ዘመር አደረጓት ። በትራቸውን ደገፍ ብለው የሐዘን እንጉርጉሮቻቸውን የሚያንቀረቅሩት አባቷ ትስማቸው ተሰብሮና አቅማቸው ተሟጦ የሚሉት ሰው ጠፍቶ

@ETHIOBOOKSPDF

በቱብሩ ላይ የተገጉት አብዛኞቹ ዕድሚያቸው የገፋ አሳው·ንቶች ናቸው። እድና እግራቸው ላይ ከሚታየው ጉዳት ባሻገር የሥጋ ደዌው ሶስ በፊታቸውና በድምፃቸው ላይ የፈጠረው ጉዳት ሁሰንተናቸው·ን ለመ·ሶታል። በነርቭ ጉዳት የደከመው·ና ሰሚት አልባ የሆነው እግራቸው·ን እንዲደግፍ ተብሎ የተሠራው ቅርጹ ለየት ያለ ሜማ የሌላ ዓለም ሰው አስመስሏቸዋል። መጣቶቹና ልጆቹ ከሕመሙ ነጻ በመሆናቸው ወይም በጊዜ ሕክምናው·ን ስላገኙ፣ ምንም አካላዊ ጉዳት አይታይባቸው·ም። ከሕመሙ ጋር ተያያዘ የሚያጋጥማቸው መገለል የፈጠረባቸው ሥነልቦናዊ ሜና·ና የኑሮ ጉስቁልና ከአካላዊው ጉዳት ቢከፋ እንጂ አያንስም። ከዚህም የተነሣ ብዙዎቹ እንግዳ ሊያዩ የመደናገጥና የመጠራጠር ስሜት ይታይባቸዋል።

ጥቂት ቀይተው ተሰናብተው ወጡ። የዝና·ሽ አባት ብርድ ብርድ ስላላቸው ከቀብር እንደገቡ ጥቅልል ብለው ተኙ። ልጆቹ እስከ መኪና·ው ድረስ እንዲሸኟቸው ተፈቅዶላቸው የሳንቾንና የምስጢርን እጅ ይዘው ወጡ።

በአራተኛው ቀን የዝና·ሽ እህት ለሳንቾ ደወ·ላ፣ አባቷ መታመማቸው·ንና ሕፃኗን ከሆስፒታል አወ·ጥታ ወደ ቤት መወ·ሰዷ·ን ነገረች·ው። እነሲላሠው በዚያው ዕለት ከጳው·ሎስ ሥራ ጨርሰው ሲመ·ጡ፣ ምሣቸው·ን መንገዳቸው ላይ በልተው ሊጠይቋቸው ወደዚያው አመሩ። እው·ቢው በር ሲደርሱ ማንንም ስላላዩ ዝም ብለው ወደ ው·ስጥ ገቡ። የተሰጣ ብቅል፣ ገመድ ላይ የተሰቀሉ ጥቂት ልብሶች፣ የተከመሩ ቅራቅንቦ የፕላስቲክ ጠርሙሶችና የምግብ ጣሳዎች ግቢው·ን ሞልተው·ታል። እንዲት በጭ·ታ የላቀጠች ወጣት አዝላው·ን የሚያለቅሰው·ን ሕፃን እያባበለች፣ 'በዋናው ቤት ላይ ተቀጥሎ የተሠራው·ን ትንሽ ክፍል ግድግዳ፣ የከብት አሣባ ከኖራ ጋር ቀላቅላ ትቀባለች። ሳንቾ ትንሽ ወደርሷ ጠጋ ብሎ ሰላም ካላት በኋላ፣

"እባክሽን አቶ በድሉ ይኖሩ ይሆን?" ሲል፣ ሁሉ·ንም ተራ በተራ ትኩር ብላ አጤነቻቸው·።

"ትንሽ አመም አድርጓቸዋል መሰል ከለቅሶው በኋላ እንደተኙ ነው። ያ በሩ ገርበብ ያለው ቤት ነው" ብላ፣ በእበት በላቀጠው እጇ ጠቀመቻቸው·። በራፉ ላይ ሲደርሱ ትንሽ እንኳኩና "ግቡ" የሚል ደካማ ድምጽ የሰሙ ስለመሰላቸው በሩን ገፋ አደረጉት። ወደ ው·ስጥ ሲገቡ ጨለማው·ና የታፈነው እምቅ አየር ተቀበላቸው·።

"ጤና ይስጥልን ... ደህና ከረሙ አባባ ..." አለ፣ ቀድሞ የገባው ሳንቾ።

"ደህ·ና ... ይመስገነው ... ኡህ·ኡህ·ኡህ ..." ሳላቸው አቋረጣቸው·። "ምነው ልጆቹ በዚህ በጭ·ታ እዚህ ድረስ መድከማችሁ·" አሉ፣ ከተኙበት መኝታ ላይ ተነስተው ለመቀመጥ እየሞከሩ። መኝታቸው ከሚድግዳው ተጣብቀ የተሰራ ከፍ ያለ መደብ ሲሆን፣ በላዩ ላይ በጆንያ ከረጢት የተገሰረ የጭድ ፍራሽና ድራቶ ተደራርቦበታል።

ከራስጌያቸው ሻጥ ያደረጉትን ከዘራ ላቡና ተደግፈው ለመቀመጥ እየሞከሩ "ኡሁ·ሁ ... ው·ይ ... እናት ዓለሜ ..." ብለው፣ ሞንትላታቸው·ን በሌላኛው እጃቸው ደግፈው ሌላ ዙር አሳሉ። ከቀጣ·ም ው·ጪ ያለውን እግራቸው·ን አንጠልጥለው

@OLDBOOKSPDF

እንደምንም ተቀመጡ ። ተቀራርጠው ያለቁ ጣቶቻቸውና ሰልል ያሰ በጠባሳ የተሸነረገረ እግራቸው ከርሳቸው ሰውነት ጋር የተያያዘ አይመስልም ። ምስጢር ዝግንን ብሏት ፊቷን ወዱ በሩ ዞር አደረገች ። ባደረገችው ነገር እፍረት ተሰማትና ፊቷን ወደ እርሳቸው የግዷን መለሰችና ፣

"እንደግፍዎ አባባ?" አለች ፣ ወደ ተቀመጡበት ቀረብ ብላ ።

"አዩ ልጄ ግዴለ ... በሰንቱ ትግድፉኝ ... እመ ብርሃን እሷ ብድራታችሁን ትስጣችሁ እይ ... እስቲ እንዲየው ንጡህም አዶል ... እግራችሁን አጠፍ አርጉ እስኪ እዚያች ላይ ። ልጆቹም የሱ መሰል ..." አሉ ፣ ስቅቅ ብሏቸው ። ከፊት ለፊት ወዳለው ረጅም የእንጨት ሳጥን እየጠቆሙ "እስቲ ልጄ ... እሱን ላስቲክ ወዲያ ወደ መሬት ላይ ገፋ አድርገውና ተቀመጡ ..." አሉት ሳንቾን ፣ ሞንቅላታቸው ላይ ያሰሩትን ጨርቅ ጠበቅ እያደረጉ ።

"ግድ የለም ...አይጨነቁ አባባ ። እርስዎ ጋደም ይበሱ ፤ እኛ እንቀመጣለን ። ምነው ሕመሙ ባሰብዎ እንዴ?" አለ ፣ ሌላሠው ጠጋ ብሎ ጆሮ ግንዳቸው ላይ እጁን ጣል አድርጎ ። ትኩሳት እንዳላቸው እየና የልባቸውን አመታት ለማየት ካንገታቸው ስር ያለውን ደም ስር ትንሽ ጫን ብሎ ያዘ ። ከድካሙ ጋር የተደራረበ ጉንፋን ነገር ይሆናል ብሎ ሰላሰበ ፣ ጥቂት ጥያቄዎችን ከጠያየቃቸው በኋላ ተጠጋግተው ተቀመጡ ።

ዓይናቸው በጨለማ የተዋጠውን ጠባብ ክፍል ሲለምደው ፣ ግራና ቀኝ እየቃኙ ቤቱ ውስጥ ባሉት ነገሮች ግራ ተጋቡ ። እዚህና እዛ በቡትቶ ጨርቆች የተወታተፈው ግድግዳ ንፋስና ብርድ ሰለሚያስገባ ፣ አልፎ አልፎ ንፋሱ ሲበረታ ዚማ የሌለው ፉጨት ያሰማል ። "ልጆቹ ትምህርት ቤት ሄደው ነው?" አለች ምስጢር ፣ ጸጥታውን መታገስ ሲያቅታት ።

"አይ ተማሪ ቤትስ አዶለም ... አሁን እዚህ ነበሩ ... ወይ ቶሼ ወርደው ይሆናል አሊያም እዚሁ ሰፈር ውስጥ እየተጫወቱ ነው" አሉ ፣ ከእንግዶቻቸው ጋር በደረቁ መፋጠጡ እያሳቀቃቸው ።

"ሁለቱም የዝናሽ ልጆች ከርስዎ ጋር ነው የሚኖሩት?"

"አዎድ ... ሌላ ምን መድረሻ አላቸው ብለሽ ... እናታቸው እንደሁ ... እንዲሁ ጉዳና ቢቱ እንዳለች ፣ መቅኖ ቢስ ሆና ፣ እንደወጣች ቀረች ። ሆነም ቀረ ያችው እናታ ነበረች የቤቱ ምሰሶ ... ይህ ያልበቃኝ ይመስል ... እሷንም ፈጣሪ ቀማኝ ... እሱ ታመጣዉ ማን ተው ይለዋል?" ብለው ፣ አይናቸውን ወደ ላይ ሲያቱኑ እንባቸው ኩልል ብሎ በጉንጫቸው ላይ ወረደ ። ድምጻቸውም ተሰባበረ ። ሁሉም የሚሉት ስለጠፋቸው ጥቂት ዝም አሉ ።

"ቤቱ ለሁላችሁም ለመተኛት እንዴት ይበቃችኋል?" አለች ምስጢር ፣ በዚች ጠባብ ክፍል ውስጥ ይሄ ሁሉ ሰው የት እንደሚገባ ስታስብ ። ግራ በመጋባት ዓይነት አየት አደረጓት ።

@OLDBOOKSPDF

"እይ ልጄ ተተዛዘኑ አንድ እንጀራ ለስንት ያጠግባል ይሉ የለ ... አንዳንዴ እዚው ተጠጋግተን ተኔው ጋር እንተኛለን ... ትልቀኛው ታሻው እሱ ሳጥን ላይ ምናምን እነጣጥፎ ይተኛል። እሱ ሚዳው ላይ ደግሞ ... ያን እያ ጋ ያለውን የተጠቀለለ ምንጣፍ ዘረጋግቶ የሚተኛ ተከራይ የኔ ቢጤ አለ። ኪራይዋ ትንሽም ብትሆን ትደጉመናለች" ሲሉ፣ ሁሉም በድንጋጤ ዓይናቸው ፈጠጠ።

"ምግብስ ማነው የሚያበስልላችሁ?" አለች፣ ወደ በራፉ ላይ የተከነበለ የከሰል ምድጃ አይታ።

"እየሀ ደጁ ላይ አከራዮቹ የሚጠቀሙበትን ቦታ ይፈቅዱልናል። ያው ትንሽ ወጥ ብጤ ተሰራን ነው ለያውም። አልያ ይህን የተለመነ ድርቀሽ በውሃ ፈርፈር አድርገን ነው የምንበላ። እንዳንዴ ልጄ ተሞላላት ትኩስ እንጀራ ታቀብለናለች ... ወጥም ሰርታልን ትሄዳለች። በተቀር ትልቁ ልጅ ነው አብስሎ የሚያበላን። አውነግ ... እዚያ ተማሪ ቤት ምሳ ይሰጧቸው ጀምረዋል መሰለኝ፣ ይሄን እቤት ያለውን ድርቀሽ ነፍሳቸው ተጠይፋው ሊሞቱ ነው። ችጋሩ ታልቀላቸው በቀር ንክችም አያደርጉትም። ሁሌ እንጀራ ተገዝቶ ደግሞ አይቻል" አሉ። የሁሉም አይን በትልቅ የላስቲክ ከረጢት ተጠቅጥቆ ግድግዳው ላይ የተሰቀለ መልኩ የተሻሸገረገረ ከረጢትላይ አረፈ።

"ይሄንን ሁሉ እርሶ ለምነው ያመጡት ነው?" አለ ሌላሠው፣ ወደ ከረጢቱ በእጁ እየጠቀመ።

"አዎድ ... ያ ግድግዳ ላይ በከረጢት ጥግ የተቀመጠውም እሱ ነው። ብቸ ሰለሚተርፍ ይሸጣል። የዳቦውን ድርቀሽ ለብቻ የጎጀራውን ለብቻ አድርገ እንሸጠዋለን። ባብዛኛው በወጥ የራሰ ስለሆነ ትንሽ ውሃ አድርገህ ትታበስለው ግለሰብ ፍርፍር ነው የሚሆን" አሉ።

"እዚህ ሰፈር ብዙ ኖሩ እንዴ?"

"ምን ቁጥር አለው ብለሽ ልጄ ... እንግዲህ በጅንሆይ ጊዜ ነው ወደህ የመጣሁ። መጀመሪያ ታገር ቤት ትመጣ ገና የሰድስት ወር መሸራ ነበርሁ። በሽታውም እንዴ ዝመረኝ ነበር። ህክምናውን ጨርሼ ሁለት አመት ተመንፈቅ ቀይቼ ትመለስ ምሽቴን ቤተሰቦቿ ለሌላ ድረዋት ደረስኩ። በዛው ብስጭት ትንገበገብ ብዙም ሳይቀይ ሀመመ ቲያገረሽብኝ ዘንዳ ተመልሼ መጣሁ። ተያ ወዲያ እኔም ወደ ሀገሬ አልተመለስኩ። ሀመመውም እየጠናብኝ ይሄው እንደምታዪው ቀስ ቀስ ብሎ መልክና ቅርጼን አጠፋው። የዝናሽ እናትም ተግንደር እንደኔው ለክምናው መጥታ እዚሁ ተገናኘተን እህል ውሃ አቀራኘን" አሉ፣ ትክዝ ብለው ያረጀ ጋቢያቸውን ባንገታቸው ዙሪያ እየጠመጠመ። ትንሽ ጉሮሯቸውን ጠራረጉና፣

"እየሀ ሰፈር ተመምጣታችን በፊት ወደ ላይ ዘው ዴ ሚዳ የሚሉት ሰፈር አለ፣ ከፍ ብሎ ተመንገዱ ብዙም ሳይገባ ነበር የምንኖር። ኋላ ግን ሰዉም ቲበዛ ቦታው ለንግድ ሲፈለግ ኪራይም ሰማይ ነካ። ይሄ ያኔ ማታ ብቻ ነበር። ኋላ አዲሱ ቤተክርስቲያን

@OLDBOOKSTORE

ቲሰራ ጊዜ እንደ እኛ ኑሮ የከበደውና መድረሻ ያጣው ሁሉ ገጾ እየቀለሰ እዚሁ መስፈር ጀመረ። አሁን ይሄ የምንተኛበት መደብ ተበታትኖ የመቃብር ቦታ ነው፣ እዛ መደርደሪያ ስርም ሌላ መቃብር ነው። አንዳንዴ ቅዠቱና መጫጫኑም መከራ ነው። ግን ምን ይደረግ እንግዲህ ሕያዋኑ ቲሸሹን ጊዜ ተሙታኑ ተጠግተን እንኖራለን" ብለው፣ ቁሠማቸውን ሲቀጥሉ ሁሉም ጸጥ አሉ።

"እና ይሄ ሰፈር ሁሉ ባብዛኛው የመቃብር ቦታ ነበር ማለት ነው?" አለ፣ ሴላሠው የለማውን ማመን እያቃተውና 'ሕያዋን ሲሸሹን ከሙታን ተጠግተን እንኖራለን' ያሉት ደጋግሞ በውስጡ እያስተጋባ።

"አዎድ ... እዚህ ሰፈር ያለ ቤት ሁሉ ተበታትኖ መቃብር ነው። እሱስ ቢሆን መች ረጋልን። እንዴ ሆስቢታሉ የኔ ነው ለማስፋፊያ እወስደዋለሁ ብሎ ቲያስፈራራን ደግሞ ቀበሌውና ማዘጋጃው የለም የኔ ነው ትለቃላችሁ ቲሉ ስጋቱ ጠዋትና ማታ ነፍሳችንን በቁሚ አስለሰላት። በያ ላይ ያሳያችሁ እኔ ይችን ጠባብ ክፍል በወር ሁለት መቶ ነው የምከፍልባት። አሁን ደግሞ እናንተ እየሀ ትትመላለሱ ታዩ፣ ሞጃ ዘመድ ያገኘሁና ርዳታ የምቀበል ስለሚመስላቸው ሦስት መቶ ያገቡብኛል ብዬ ስጋቱ ስጋዬን በቁሚ ጨረሰው። እነሱ ምናስባቸው ገንዘብ የሚታጨድ ነው የሚመስላቸው። ሌላ የትም መድረሻ የለን፣ ያሉንን መክፈል አልያም ደጅ ወድቶ ያውራ ሲሳይ መሆን ነው እንጅ" ብለው፣ ጫማቸውን ለማጥለቅ መታገል ጀመሩ።

"አባባ ... ሰዉ ግን ምን ሠርቶ ነው የሚያድረው?" አለች፣ ምስጢር የእግራቸውንና የጫማቸውን መዋደድ ባግራሞት እያየች።

"ምን ይሠራል ብለሽ ነው? ... ቢሠራስ በየትኛው አቅም ልጄ ... ብዙው የኔ ቢጤው መቼም በልመና ነው የሚኖረው ... ደግሞ እየሀ ታች ቀሺ የሚሉት ያገሩን ሁሉ ቀሻሻ አምጥተው የሚደፉበት ቦታ አለ። ተዚያ ላይ የተገኘውን እየለቃቀሙ በመሸጥ የሚተዳደሩም አሉ። ተያ ውጭ እንግዲህ መሸታ ቤት፣ የቀን ሥራ፣ ችርቻሮ ምናምን ነዋ ... ሌላ ምናለ ብለሽ? ፈጣሪ ፊቱን ያዞረላቸው ደግሞ ... ልጆቻቸው ውጭ ሃገር ሄደው ተቀናቸው ተገላገሉ ማለት ነው። የኔዋም ዝናሽ ለኛ አሳልፋለሁ ብላ አረብ አገር ሒዳ ነው ከንቱ ተቀጭታ እንደዋዛ የቀረች" አሉና በትካዜ ተዋጡ።

ሴላሠው ለመጀመሪያ ጊዜ ገነት አረብ አገር ሄዳ ይሆን እንዴ ብሎ አሰበ። "አካባቢው ቀሺ የተባለው ከከተማ እየመጣ በሚደፋው ቀሻሻ ምክንያት ነው እንዴ?" አላቸው፣ የሰፈሩ ሥም በአካባቢው ከሚጣለው ቀሻሻ ጋር መዛመዱ ለመጀመሪያ ጊዜ ታይቶት።

ትንሽ ፈገግ እንደ ማለት አሉና፣ "ቀሺ ... ጎላሳ ልጄ... እዚህ እኛ ሰፈር ቀሻሻም ይቀላመጣል። የከተማው ሰው ሁሉ ያለ የሌለ ቀሻሻውን አምጥቶ እዚህ ይደፋዋል። እኛም ተያገራችን ይህንን ቀሻሻ የቁምጥና በሽታ እናራግፋለን ብለን መጥተን እንደ ቀሻሻው እዚህ ተጥለንና ተረስተን ቀረን። መልከ ጥፉን በሰም ይገድፉ እንዳሉ ነው። እኛም ቀሻሻውን ቀሺ ... መቃብር ላይ የተሰራውን ቤት ከንደር አሮጌው ቤተሰኪያን ሰፈር

@OLDBOOKSPDF

እያልን እንኖራለን ። የሚያሳገኙኝ የኛን አበሣና ርግማን ተሸክመው የሚወለዱ እኒህ እጣናት ናቸው"

ምስጢር መቸመጫው ስለቁረቁራት አቀማመጧን እያስተካከለች፣ "እርስዎ ምን ይሠራሉ? በምንድነው የሚተዳደሩት?" አለች ። ሳንቾ በጥያቄዋ ትገሽ ሰቀቀ ብሉ ጮሽም አደረጋት ። ከበስተ ራስጌያቸው ሽር ብላ ያለፈችውን አይጥ አይተው በበትራቸው ሊመቷት ሞክረው ሳቷት ።

"ይቺ መናጢ ሰላቢ ... በታ ኮ እዚህ መታብር ውስጥ ይራባሉ ማን ይቻላቸው፤ ምን ድመቱም እኮ አታተው ። " የገባችበትን ቀዳዳ እያዩ ዓይናቸው ወዲያ ወዲህ ተንከራተተ ። "እንግዲህ ሴት በሌለበት ባዶ ቤት መጥታችሁ እንዲሁ በወሬ አደርቅኋችሁ ... እንዲያው አሁን እዚህ ድረስ ምን አደከማችሁ?"

ምስጢር ብድግ አለችና ይዘው የመጡትን ኑኪስ ከፈተችና፣ "በወሬ ጠምደነዎ እርስት አደረኩት ። እስኪ ከዚች ላይ ያዙ አባባ ... ምንም አትልምም" ስትላቸው፣ ምን እንደሆነ ጠጋ ብለው ለማየት ሞከሩ ።

"ምንድነው ልጄ?" አሉና አንዲት ፍሬ አንስተው ወዳፋቸው ሰደዱ፣ እያላመጡና ጉሮሯቸውን እየጠራረጉ፣ "እንዴት ትጣፍጥማለች ልጄ? ይችን እሚጡሻ ታገኙ እንጃ ... እሷማ ኮ ያላንቺም ወራ የላት" አሉ ። እንዲጨምሩ ቀረሽ ስታደርግላቸው፣ ትንሽ ተግደርድረው ጨመሩ ። የጠየቀቻቸው ጥያቄ ትዝ ሲላቸው ጉሮሯቸውን ጠረግ ጠረግ አደረጉና፣ "አትም እያለኝ በደህናው ቀን ምን ያልሰራውት አለ ብለሽ ነው ። ጥሩ ግንበኛ ነበርሁ ። ኋላ ግን በሽታው እጅና እግሬን ቀማምሮ ቲጨርሰው ምንም መሥራት አልቻልሁም ። ልመናው እንዴት ያሳፍራል መለሽ - የሰው ፊት ማየቱ ... ስድቡ ... ጠሃዩ ... ተሰው ተውሽ ጋር ተናጥቀ መኖሩ ... ኧረ ተዪኝ ... ያኔ ባቡሩ ታይጽረጥ ፊት ደግሞ በልብስ አጥላቂነት ትንሽ ሰርቼ ነበር" ሲሉ፣ ስላልገባቸው እርስ በርሳቸው ተያዩ ።

"ምንድነው አባባ ልብስ አጥላቂ?" አለች፣ ምስጢር ቀበል አድርጋ ።

"ነጋዴውና ፊናስ ቦሊሱ አይጥና ድመት ነበር የሚጫወቱ ። ታዲያ ምን ያደርጋል መለሽ እንደኔ ያለ አንድ አራት ቀማጣ ይዘው ታዲሳባ ይሂዱና ልብሱን ስአቱን ምን ይቀራል ብለሽ ነው ደራርበው ደራርበው ተራራ ያሳክሉንና ባቡሩ ወይ አውቶቡሱ ውስጥ እንገለታልን ። ታዲያ ፈታሹ ቦሊስ ሲመጣ ይሄንን እጃችንን እናንዘረናና ፊታችንን አጨፍግገን ከላይ የተደረበውን ቡትቶ ስናሳያቸው ተጠይፈውን ትተውን ያልፋሉ ። አንድ ሁለት ዓመት እሱን ሠራሁኝ ። ኋላ ግን ጤናውም ጠፋ ... ወሬ በረሃው ላይ ያለ መሠቅቅማ ተይኝ ። እንዳንዴ እዛው ልብስ ውስጥ ቀልዉ የማለያ ይመስለኛል ወይም ታፍኜ ልሞት እደርሳለሁ ። ተያ ኋላ ግን አትሜም ተለሙና ተልመና በቀር ምንም መሥራት አልቻልሁም" አሉና እግሯቸውን በሁለት እጃቸው ደገፈው ገለም አሉ ።

@OLDBOOOKSPDF

"እኔልጅሆኜ ከማወ·ተው· ሰፈሩ በጣም ተቀያይሯል ። ሰው·ም የበዛ ይ፡፡ሰላል ። ፃራ ሮሚባለው·ም ይሄው· ሰፈር ነው· ወይስ...?" አለ ሌላሠው· ። ከዚሁ ሰፈር ው·ስጥ ሁልጅነቱ፣ በነገነት ይሳሳ ጎጆ ው·ስጥ የበላው· ያረቱ ቂጣና ትኩስ ሽሮ ትዝ እያለው· ።

"አዩ ያፍተር ... እሱማ ማ ምኑ ትው ... ሰው·ው·ማ ምን ልክ አለው? እንኳን ላንተ ለኛም ችግር ነው· ። ሰዉም ተዋልዶም ተሰዶም ያለ ቅጥ እየበዛ ነው· ። የድሮው· ሰው·ማ ደግሞ ረገፈ እንዴ ትጠል ... ድኽነቱም ... ይህ የዘመኑ በሽታም በንቱን ቀጠፈው· መሰለህ ... ደግሞ መጠ፡ው· በዛ ... እ፡፡ም·ተኛው·ም ... ችግርም ያሳደደው· ... ደግሞ ሰወንጀለኛው·ም ቢሆን ሁነኛ ጎራ ነ ነው· ... ማ ማን እንደሆነ ማን ያው·ቃል ብለህ ነው· ። እኛ ትንመጣ ሰፈሩ ... በተለይ ተየህ በታች ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነበር ። ኸቦ ብትል ምኑ ... አሁንማ ዛፉ ሁሉ አልቶ አገሩ የሰው· ጫካ ሆኗል ።" ለረጅም ጊዜ በላይ በላዩ ቢያስላቸው· ቶየና ትንሽ ጋብ ሲልላቸው፣ ከላይ ከላይ እየተነፈሱ ገም አሉ ።

የምታደርገው· ግራ የገባት ምስጢር ተንሰታ ትከሻቸው·ን ደግፋ ካጠገባቸው· ቀመች ። "አይገዞ እሰኪ በቃ አረፍ ይበሉ ... ገም ብለን እደረቅንም አይደል?" አለች እንደቀመች ።

"እዩ እዶለም ... አይዞሽ ልጄ ደህና ነኝ ... ሂጂ አረፍ በይ ... ቅዝቃዜው·ም የሰሞኑ ድካም·ም ተደራርቦ ነው· መሰል ... ደግሞ ይቺ አሰሚ አረፍ ብላ ነበር ልትነላብኝ ነው· መሰል..." አሉ፣ ላብ ያቸፈቸፈ ፊታቸው·ን ራሳቸው· ላይ በጠመ፡ጠመ·ት አሮጌ ዉቦት እየጠረጉ ። ከዚያም አፋቸው· ው·ስጥ ያጠራቀመ·ትን አክታ የሚተፉበት ቦታ ሰላጡ መልሰው· ዋጡትና ወሬያቸው·ን ቀጠሉ "ምንድን ነበር ያልከኝ ልጄ ... የኔ ነገር ...በቃ ሸጀሁ መሰል ... ነገር ታይም·ሮዬ ይሰልበኝ ጀም·ሯል ..." አሉ፣ ወደ ሌላሠው· እያዩ ።

"እይ ኸረ በፍጹም ... እርስዎ እንዲያው·ም በጣም ጎበዝ ነዎት ...ስለ ቀራ ነበር የጠየቅሁዎ ..."

"እሁንማ የሰፈሩ ስም አበሳዙ አይጣል ነው· ... አገር ከተ·ማ ኮ ሆኗል ... ተላይ ተመካኒላ እሰተዚህ ...ደግሞ ቁልቁል ገደሉ እስተዋሽ ... ታች ተሆስፒታሉ ማዶ ታስፋልቱ ባሻገር ... ብዙ ሰፈር ነው· ያለው· ። ቀሬ የሚሉት ግን ወዲያ ወደ መካኒሳ አቅጣጫ ስትሄድ ያለው·ነው· ። እሁን ሰፈሩ ተለው·ሮ ገነት መስሏል ። ደርግ እንደ ወደቀ የተፈናቀለና በምርነት እጅ እግሩን ያጣ ጉዳተኛ መጠለያ ሰርተው· እዚያ ነበር የሚኖሩ ። ጎላ የእኖን የቶማሶች ሰፈር ሲሉ፣ እዚህ ያለው· ሰው· ደግሞ እነሱን ቀሪሶች እያለ መጥራት ጀ፡፡ረ ። ታዲያ እንርሱ ነገሩ አናዷቸው· ነብር ሆኑ ። እቅመም ስለነበራቸው· ያጠቂን ጀ፡፡ር ። ታዲያ ጎላ ቀሪዋ የሚለው·ን ትኖ ሰጪ እንደ ተልድ ቀሬ ቲል ሰፈሩም ያው· ቀሬ ሆኖ ቀረ ። ቀሺም ቀሬም የተቀላ፡፡ጠ ችግር ነው·" ብለው፣ ሲስቁ ሁሉም አብረዋቸው· ሳቁ ። የታሪኩንና የስሙን አመጣጥ እው·ነተኛነት ግን እርግጠኛ መሆን አልቻሉም ።

"እና እነሱ አሁንም አሣው· ሰፈር ነው· ያሉ·ት ወይስ?" አለች ምስጢር ።

@OLDBOOOKSPDF

"እዩ የመጥሽን ... ስንቱ እየመጣ ቡቶ ቲያንሳ ቢዲዮ ሲተርጥ ... በነሱ ስም ርዳታ ቲሰበስብ ... የጠገበ ቲሄድ የራበው ቲመጣ ... ኋላ አንደኛው ይሄ ምንድነው እሱቲ ኒንዶሚኖ መጣና ጠራርጎው አንቢቸው። ሰፈሩን ሁሉ መንግሥት ሰወጠው። የቱሪውን ቦታ የከተማው ቲሻር መጥቶ አሳር ሶሳር የሚያህል ቤት ሰርቶ ሰፈረበት። የሃም ዕጣ ተንሱ የተለየ አይመስለኝም ... አሁን ነጋ ጠባ አንዴ ተበሴው፣ አንዴ ሆስቢታሉ ያስፈራሩናል ... እንኛ ብቻ ቀሼም ተጥሬ የተለየ ጣጉንታ ያለው አይመስለኝም፣ ተምን የተጠጋ ምን ቲያለትስ ይኖራል አይዶል የሚሉ።" ከወዶ ደጅ የልጆች ጫጫታ ሰምተው ጆሮአቸውን አሰሉ።

ወዲያው ስምረትና ወንድሟ እየተሯሯጡ በሩን ብርግድ አድርገው ገቡ። ቤቱ በእንግዳ ተሞልቶ ሲያገኙ ድንግጥ ብለው ባሉበት ቁጥ አሉ። "ኧረ እስቲ ቀስ በሉ... ምን አሳዴችሁ ነው?" ሲሉ ስምረት አያቷ ላይ ተጠምጥማ በትንሽ እጇ አገጣቸውንና ጉንጯቸውን ወደ እሷ ለማዞር እየሞከረች ወንድሟና ጓደኞቹ ያደረጉትን ወገደል አብራራች። እሱም በበኩሉ ካጠገባቸው ቀሞ ወሽቷን መሆኑን ለማስረዳት የራሱን ማስተባበያ በጮላ ድምጽ አቀረበ።

"አቢት ወሽታሞ ... እስቲ እነ ስንታየው ይተየቱ ከፈለክ ..." ስትል፣ እሱም "ይጠየቋ ታዲያ ... አባባ ዝም በላት እሷ አታጣሪ ወሽታም ናት ... ከኛ ጋር ቀሼ እትሄጂም ስላልናት ነው" አለ። በተራዋ የራሷን ማስረጃ ስታቀርብ ነገሩ ተካረረ። ሁሉም ነገሩን በፈገግታ ሲከታተሉ ቀዩ። ምስጢር ነገሩን ለማብረድ ሃሳብ መጣላት፣ ካመጡት ኩዚስ ለሁሉቱም አፈሰ አፈሰ አድርጋ ስትሰጣቸው ጥሉ ተረሳና ተከታትለው ወደ ደጅ በረሩ።

እንሌላሠው ተሰናብተው ሊወጡ ሲሉ፣ ልጆቹ ሄደው ነግረዋት ኖሮ የዝናሽ እህት ሀጻኗን አዝላ ... ስምረትና ወንድሟን አስከትላ ደረሰች። ትንሽ ከተጫወቱ በኋላ ስለ ዝናሽ ልጆች የመደፈት ዕጣ አንስተው አወሩ። እሷም ሆኑ አባቷ ልትሞ እንደሌላቸውና ከተቻለ ላይነጣጠሉ በአንድ ላይ የሚያሳድግላቸው ድርጅት ወይም ቤተሰብ እንዲፈልጉላቸው እያለቀሰች ለመነቻቸው።

ከቤት ወጥተው ሲሰናበቱ "ይሄ ቀሺ የሚባለው ቦታ ከዚህ ሩቅ ነው እንዴ...! ሂዶ ማየት ይቻል ይሆን?" አለ፣ ሴላሠው ወደ ዝናሽ እህት ዞር ብሎ።

"እዩዩ ... ኧረ ምኑ ይታያል እሱ ... ሽታው ሞቷው እያስገባችሁም ትንሽ ብራ ካልሆነ በቀር ..." አለች፣ ፊቷን ሞርምትምት አድርጋ።

"ጥሩ ነበር ማየት ከተቻለ ..." አለች፣ ምስጢር የስምረትን እጅ እንደያዘች፣

"እኔና ሻምሾን ... እናሳያቹ?" አለች፣ ስምረት በደስታ እየዘለለች። አከቷ አፏን ጠመም አድርጋ በማሾፍ አያጎት ቁልቁል እያየ ቻት።

"አቢት ...አቢት ... ሚኮሚጣ! ... አሁን እንቺን ብሎ አሳዬ ... ልብሽ መቼም ታትምሽ በላይ ነው" አለችና "ሳሚ ... አንተ ሳምሶን ... አሁን እዚህ አልነበረም እንዴ ... የት ገባ ልጁ" በትል፣ ስምረት ሮጣ ጠጣች።

@OLDBOOOKSPDF

ወዲያው እያሰከለከች ተከታትለው ሲገቡ ፣ "እነ ዶክተርን ቀሺ ጋ ይዘሃቸው ሂድ ... ሞቃው እንዴት ነው?" አለች ፣ የገናስ እህት ።

"መግቢያው ጋ ግን በጣም ያስቸግራል" አለ ።

"እኔም እኪዳለሁ ኮ" አለች ፣ ስምረት የአክሲጅን ፈቃድ በመለማመጥ ዓይነት ።

"አይ ...ይ ... እንቺ እዚሁ ካባዬ ጋር ቀዪ ... እሞት የለ እሱ ... ምንድነው ብቻውን ጥላችሁት የምትጠፉት" ሰትል ፣ ከየት መጣ ሳይባል እንባዋ ባንዴ መንታ መንታ እየሆነ መርገፍ ጀመረ ። ምስጢር እንባዋን እየጠራረገች አባበለቻት ።

"አይ ልጄ ... ትሂድ ተያት ... እኔ ትንሽ አረፍ እላለሁ ገብቼ ። አውንማ ቀለል ብሎኛል ። አንቺም ባዶ ቤት ትተሽ ነው የመጣሽ ... ተስተኛጅ ከመጣ ያጣሻል ሂጂ ... አናንተም ቅዱስ ሚካኤሉ ተገናችሁ ይቂም ። በቃ ተሄዳችሁ በጊዜ ሂዱ ። እንዳይተናነሷ ችሁ ደግሞ ጠንቀቅ ብሉ ... የዛሬ ጊዜ መላም የለው" አሉ ፣ ተነስተው ለመቆም እየሞከሩ ። ሞቃው አያሳልፈንም ብለው ስለፈሩ በሌላ ቀን ሊያዩት መስነው ልጆቹን ተሰናብተው ወደ መኪናቸው ሄዱ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡18፡

ሌላሠው ለሚከፍተው የአእምሮ ሕዘምናና የምርምር ማዕከል የሠራውን መነሻ ዕቅድ በተዘረጋው ወረቀት ላይ ሲፃፍው፣ ሰዓቱ ምን ያህል እንደሄደ አልታወቀውም። በቴርሙዝ ተዘጋጅቶ ከቀረበለት ቡና ላይ እየቀዳ ራት ይልና ተመልሶ በሥራው ይጠመዳል ... በምናቡ አዲሱን ማዕከል ያይና ፈገግ ይላል። ድግሞ የተበታተኑ ወረቀቶቹ ላይ ሐሳቡን ለማስፈር ይሞክርና ሲያቅተው ወዲያ ወዲህ ይላል። ቀኑን ሙሉ ከያቅጣጫው ተሰባስቦ የአዲስ አበባን ሰማይ የሸፈነው ደመና የተሸከመውን ውሃ ለመዘርገፍ በቋፍ ነው። ከመብረቱ ብልጭታና ከነጎድጓዱ ማስገመግም ጋር ተቀላቅሎ የንፋሱ ፉጨት ጉተት ያዘለ ናፍቆት በልቡ ውስጥ አሚረበት።

የዝናሽ ልጆችና አባቷ ትዝ አሉትና ይህንን ከረምት በዚያች ደሳሳ ቤት ውስጥ እንዴት ይሆን የሚያሳልፉት ብሎ አሰበ። ሃ'ስቱንም ልጆች በአንድ ላይ ለማሳደግ ፈታኝና የሚሆን ጥሩ ቤተሰብ ቢያስብም ሊመጣለት አልቻለም። በየጉዲፈቻ ድርጅቱ ከነሳንቾ ጋር እየሄዱ ብዙ ነገር ቢሞክሩም፣ የረባ መፍትሄ አላገኙም። ድንገት እንደ መብረቅ የሆነ ሐሳብ በአእምሮው ብልጭ አለለት። አስካሁን እንዴት እንዳላሰበው ገረመው።

"ይሄ ነው ... ከዚህ የተሻለ ሌላ ምንም የለም ..." ብሎ፣ ወደ ጠረጴዛው ተመልሶ ስልኩን ከሃይል መሙያ ገመዱ ላይ ነቀለና ወዲያው ለንጹሕ ደወለ።

"እንዴት ፈጽሞ እንዳላሰብኩት ይገርማል ... ያን ሁሉ ነገር ስናወራ እንዴት እንዳልመጣልን ..." አለ፣ ደስታው ከድምፁ ሞልቶ እየፈሰሰ።

"ምን ተገኘ?"

"የዝናሽን ልጆች ነሞ ... ስለ ጉዲፈቻ ስናወራ አልነበረም ... የሆነ ሰው መጥቶልኝ እኮ ነው የደወልኩልሽ ... እስኪ ገምች ..." ብሎ፣ ከፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ተንገራደደ።

@OLDBOOOKSPDF

"እ ም ... እኔ እንጃ ... ምን አስብክ? አንተ እንደ ሆንክ ሐሳብ አያልቅብህ ..." ብላ፣ ላት አለች ።

"እይገርምሽም ... አርሲና ንዋይ ... ከተጋቡ ይሄው አስር ዓመታቸው ... ልጅ አለኩን የለም ... ባለፈው በወሬ መኃል እሱ ትንሽ ፍንጭ የሰጠኝ መስሎኝ ነበር ። ምን ይመስልሻል?" አለ፣ የሲን መልስ በጉጉት እየጠበቀ ። የአርሴማ ባል ንዋይ ከሕክምና ትምህርት ቤት ጀምሮ የሌላሠው የረጅም ጊዜ ጓደኛው ነው ። ንጹሕና ሌላሠውም የተዋወቁት በነአርሴማ ሠርግ ላይ ሚዜ ሆነው ነው ። ንዋይ የልብ ሐኪም ሲሆን አርሴማ ደግሞ የራሷን ቢዝነስ ትሠራለች ።

"ኦህ ማይ ጋድ ... እኔም ፈጽሞ አላሰብኩትም ነበር ... ግን ..." ብላ አመነታች ።

"ግን ምን...?"

"አለ አይደል አርሲ በጣም ስሜቷ ስስ ሆኗል ... ናዊ ራሱ በጣም ተቸግሮ ሲነግረኝ ነበር ። እንዴት አድርገን ... ማለቱ ማን ሊነግራት ይችላል?" አለች ። አርሴማ ልጅ የመውደዷንና የመፈለጓን ያህል ያልሞከሩት ነገር ባይኖርም ፈጽሞ ሊላከላቸው አልቻለም ። አሁን አሁን ገና ጉዳዩ ሲነሣባት ቁጣ ቁጣ ስለሚላት፣ ንጹሕ ትፈራት ጀምራለች ።

"ምንም ችግር የለም ... በመጀመሪያ ነገሩን ከንዋይ ጋር ላውራው ። እነርሱ ነገሩን አስበውት ከሆነ ቀላል ነው ። ካልሆነም እርሱ እንዲያነሳበት ምናምን አድርገን ... የሚሆነውን እናያለን ። በዚህኛው ነው በሚቶጥለው ዓርብ እንቺ ጋ የሚመጡት?" አለ፣ በውሰጡ ነገሩን እንዴት ሊነግራቸው እንደሚችል እያሰበ ።

"ከነገ ወዲያ ማታ ነው የሚመጡት ። ከሆነማ ጥሩ ነበር ... ታዲያ ለምን እንተ አሁኑ ደውለህ ከናዊ ጋር አታወሩም?" አለች፣ እሷም ነገሩ እንዲሆን በልቧ እየተመኘች ።

"እስኪ ምናልባት ሥራ ካልገባ እሞክርለታለሁ ። በይ አንቺ ሥራ ላይ ነው አይደል ያለሽው ። እንዳልይዝሽ?"

"እምን ወጣ ብዬ ነው የማወራህ ። ፎቷቸው አለህ እንዴ ... እኔም እኮ ላያቸው ናፈቅሁ ። የሁለቱን ፎቶ እንኳ ያኔ ሆስፒታል አይቼዋለሁ ። ዕድሚያቸው ስንት ነበር?" አለች፣ ጉጉቷን በሚገልጽ ድምፅ ።

"ትናንት ዝናሽ እህት ቤት ከሳንቾ ጋር ሄደን ነበር ። ትልልቆቹ አራትና ሰባት ናቸው ። ቀንጮ ፎቶ ነው ያነሳናቸው ... ኢሜይል አደርግልሻለሁ ። በቃ ፍቅርዬ አልያዝሽ ... ቀንጮዎቹን ሳሚልኝ"

"እትርሳ ደግሞ አሁኑኑ ላክልኝ ... አይ ላቭ ዩ ...ቻው ። ሄይ ደግሞ ልጅህ ዛራ ግቷ ደውል ብላሃለች ... ሚስጥር የምንገረው አለ ስትል ነበር ። ቃል ገብቼላታለሁ እንደምነግርህ ። እንዳትረሳ" ብላ ጉሻሉቱን በልታ ሰጠችው ። በደመለ ቁጥር ትንሿ

@OLDBOOKSPDF

እርሷማ ነገ ምስጢር ስለምነግርህ ደውል፡ ስለም"ትሰው ነው የሳቁት ። ቢያንስ በየሦስት ቀኑ ስካይፒ አድርጉ ያወራቸዋል ።

ከጉሕ ጋር ተሰነባብተው ስልኩን ዘጋና ጉዋይ ጋ ደጋግሞ ደወለ ። ስልኩን አያነሳም ። ኢንተርኔቱም እምቢ ስላለው ፎቶውን ለጉሕ ሊልከላት አልቻለም ። ድክም ብሎት ወረቀቱ ሁሉ ጠረጴዛው ላይ እንደተበታተነ አልጋው ላይ ጋደም እንዳለ እንትልፍ መሰደው ። ሌሊት ላይ የጉዋይ ስልክ ተሰተሰው ።

ጥቂት ካወሩ በኋላ ፣ "ምን መሰለህ ናዊ ... እንድ የሆነ ሐሳብ መጣልኝና ... ላዋይህ ፈልጌ ነበር ማታ ያን ያህል ደጋግሚ የደወልኩልህ "

"ሌልሽ ... እንተ ሃሳብ ታጣለህ ብዬ ሃሳብ ገብቶኝም አያውቅ ... ምን ተገኘ"

"ሲርየስ ነገር ነው ... እንተ ሁሉን ተልድ አታድርግ ... ስለ ልጅ ምን እያሰባችሁ ነው? ማለቴ አንተና አርሲ?" ፊጽሞ ያልጠበቀው ነገር ስለነበር ትንሽ ግራ ገባው ።

"ምን እናስባለን ብለህ ነው ። ያው የምንችለውን ሁሉ አድርገን ፈጣሪም ሐኪምም የከለከለን ይመስላል ። አዲስ የባሕል ሞድኃኒት ተገኘ እንዳትሰኝ ብቻ ..." ብሎ ፣ አሁንም ንግግሩን በሣቅ ዘጋው ። ሲሥቅ ከልቡ ስለሆነ ደስ የሚል ለዛ አለው ፣

ከአልጋው ላይ ወርዶ ጠርዙ ላይ ቁጭ አለና ፊቱን እያሻሸ ተንጠራራ ። "ልጅ ስለ ማሳደግ አስባችሁ ወይም አውርታችሁ አታውቁምን? ማለቴ ያው እንደምታውቀው ሜናውም ቀላል አይደለም በተለይ አርሲ ላይ ... በተለይ በሷ ልጅ መውደድ"

ጥቂት ዝም ብሎ ቀየና ፣ "ብዙ ጊዜ ላንሣባት ስሞክር ፣ ነብር ነው የምትሆነው ፣ በታ በእኔ መውለድ ተስፋ ቀረጥክ ማለት ነው ትላለች ። ከዛ እሷን ማባበሉም መከራ ነው ። ልጅ ብናሳድግ ሜናውን ከኛ ላይ ስለሚያነሳልን ፣ ለመውለድም እንኳን የምንችል ከሆን ፣ የበለጠ ዕድል ይኖረናል ብዬ ላግባባት ሞክሬ ነበር ። ግን ታውቃታለህ አርሲን ... ራሷ ካላመነችበት ማንም ፍንክች አያደርጋትም" ብሎ ፣ በረጅሙ ተነፈሰ ፣

"እኔማ እኮ እንድ የማያት ሕመምተኛ ነበረችኝ ። በጣም ችግረኛ ቤተሰብ ነው ። በተደም በመሲድ ላይ በሚያሳዝን ሁኔታ ሞተችብን ። አዲስ ከተወለደችው ሕፃን በተጨማሪ ሌሎች ሁለት የሚያማምሩ የአራትና የሰባት አመት ልጆች አሉዋት ። ትልቁ ወንድ ነው ። ቤተሰቡ ሁሉንም እንድ ላይ ወስዶ የሚያሳድጋቸው ጥሩ ሰው ከተገኘ ፣ ለጉዲፈቻ ለመስጠት ተስማምተዋል ። አታምንም ምን አይነት ልጆች እንደሆኑ ... ምን ይመስልሃል?"

"ሌልሽ ... እኔማ ምንእንደማሰብ ታው ታለህ ... ከኔ ይልት አርሲ ምን ታስባለች ነው ጥሩው ነገር ... ሌላው አላሳበ ነገር ፕሮሰሱ ነው ... በጣም ረጅምና አታካች ነው ይባላል? አይ ዶኖ ..." አለ ፣ ምን ማለት እንዳለበት ግራ እየገባው ።

"እኔ መቼም በጣም አራፍ ዕድል ይመስለኛል ... ለልጆቹም ከናንተ የተሻለ ወላጅ ይገኛል ብዬ ማሰብ አልችልም ። እንዴት ዓይነት የሚደሳሱ ልጆች እንደ ሆኑ ልነግርህ አልችልም ። ርቷቸው አለ እኔ ጋ ከመጣ ገና ... ሁለት ሳምንት ብቻ ነው ። ግን ...

©OLDBOOKSPDF

"እስኪ በናትህ ላከው ... ኦልራዲ ጓጓሁ እኮ ... ለአርሲ ግን እንዴት እንደሚነገር እገኛ ... ለማንኛውም ፎቶውን ኢሜይል አድርግልኝና ... እም ...ም ... እንዴያውም ዛርብ እኮ ንጹሕ ጋ እንሄዳለን ... አይ አም ሹር ከሲ ጋር አወርታችኋል ... ምን አለች?"

"ልክ እንዳንተው ነው የሲም ሐሳብ ... እኔማ ያሰብኩት ፎቶውን ላንተና ለርሲ ልላክላችሁና እናንተ ትንሽ ካወራችሁት በኋላ... አንተ ቀስ ብለህ ለአርሲ ሐሳቡን ጀማምረህላት ... ሙሉ ሃሳቡን ኦስትን ስትሄዱ፣ እኔም ከዚህ ደውዬ አብረን ብናወራው ምን ይመስልሃል?"

"ጥሩ ነው። ግን ደግሞ ሁላችንም አወርተነው አርሲን መጨረሻ ካደረግናት ይደብራታል ብዬ ፈራሁ። ከማንም ይልቅ አንተን ነው የምትሰማው። በዛ ላይ ታውቃለህ የሲ ጥያቄ ማለቂያ የለውም። ስለዚህ ያለችውን ብትልም ለእኔ የነገርከኝን ይውለህ አሁኑ ንገራት። ውጤቱ ምንም ይሁን ምን፣ ቅዳሜ ከዛው ሆነን፣ ለምን ሁላችንም አንድ ላይ አናወራውም"

ወዲ መበኩቱ ሄዶ መጋረጃውን ሙሉ ለሙሉ ሰብስቦ ሲከፍተው፡ ፀሐይዋ ፍንትው ብላ ወጥታለች። ቀዝቀዝ ያለ ንጹህ አየር ተቀበለው። "እንዲያውም እሱም ጥሩ ሃሳብነው ... ስለዚህ ከአርሲ ጋር ካወራሁ በኋላ፣ ለሦስታችሁምአንድ የጋራ ኢሜይል ከፎቶው ጋር አልካለሁ ... ሃው አባውት ዛት?"

"አሪፍ ሐሳብ ነው ... ታዲያ ቶሎ ላከው ፎቶውን ..." ትንሽ ተሳሰቀው፣ ስለ እርሱም ሥራ ተጨዋወተው ሰልኩን ዘጋው።

ወዲያው አርሴማ ጋ ደወለ። አርሴማ ሃሳቡን ሲያነሳላት መጀመሪያ ላይ እንዳልገባው ሆነች። ከዚያም ቁጣ ቁጣ እያላት ለምን ጥሩ ሃሳብ እንዳልሆነ ልታሳምነው ሞከረች። ስሜታዊ ሆና ማልቀስ ስትጀምርና ለማባበል ሲከብደው ነው፣ በነገሩ ምን ያህል እንደ ተጐዳች የተረዳው። በመጨረሻም ለንጹህና ለንዋይም ደውሎ ሐሳቡን እንደ ነገራቸውና የግድ አሁን ምንም ነገር መወሰን እንደሌለባትና ምናልባት ከንዋይና ከንጹህ ጋር ቢወያዩበት ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ነገራት።

"በናትህ ሴላዬ ... ምኑን ነው የምንወያይበት? ... ከኢትዮጵያ... ልጅ... ስላውም ፖሰት ልጅ ... እንዴ ... በፍጹም የሚታሰብ አይደለም። ደግሞ ... እኔ..." ብላ እምባዋ ቀደማት። "በቃ ብዙ አታስወራኝ ... ይበቃሃል ... ልቤ አስከትፈርጥ አስለቀስከኝ ደግሞ ... ቀይ ላግኝህ ብቻ" ብላ ሳቀች።

"አርሲ በቃ ተከራክሮ አንቺን የሚያሸንፍ ይጥፋ ... አልትሰሽም እኮ ቢሆን አትሸነፊም። ግን ሲርየስ ... ለሦስታችሁም የልጆቹን ፎቶ ኢሜይል አደርግላችኋለሁ ... አስትን ስትሄዱ ተነጋገሩበት ... ከፈለጋችሁ ደውሉልኝ ... አርሲ ሙች ... የማይጸጽትሽ ውሳኔ ነው የሚሆነው"

"ምንም ለውጥ አያመጣም ... ይሲ እንጸልይ። አንተ ግን ሙቹ ነው የምትመጣው? ደግሞ ትንሽ ቀየት ብለህ ጠቅልላችሁ አገር ቤት ገብ አንዳትለን ..." አለች፣ አሁንም

@OLDBOOKSPDF

እየሣቀች ። ስለኩን እንደ ዘፕ ከእጅ ኮምፕዩተሩ ላይ ፖስት ፎቶዎችን የልጆቹን ሥዕ
ጨምሮ በለገድ ኢሜይል ለሁሉም ላከላቸው ።

በሚቀጥሉት ቀናት ሌላሠው ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ ተወጣጥሮ ለምገብ
መብያ እንኳን ትንፋሽ አጣ ። ከነምስጢር ጋ የዐታውን ውል መፈራረም ... ሳጎችን ዋና
መኪልና ጉዳይ አስፈጻሚ አድርጉ መወከልና መቅጠር ... ከሲራክና ከሲስተር ዘቢባ ጋር
ወደፊት አብረው የሚሰሩበትን ሁኔታ መስመር ማስያዝ ... የክሊኒክ ፈቃድ ከሚሰጡ
ቢሮዎች የሥራውን መሠረታዊ ሂደት በተመለከተ መረጃዎችን መሰብሰቡ አባክነው ።
በወትሮ የሥራ ሰዓቱ ሆስፒታል ሊገባ ስላልቻለ የሕክምና ሥራውን ለጊዜው
አቁሞታል ። ወደ አሜሪካ ለመመለስ የቀረው አስር ቀን ብቻ ስለሆነ፣ የጀመራቸውን
ነገሮች ለመጨራረስ ቀንና ሌሊት ይሠራል ።

ቅዳሜ ጠዋት ከቁርስ በኋላ የወረቀት ሥራውን ሲሠራ አረፋፈደ ። ወደ አራት
ሰዓት ላይ እነ ንጹሕ ከአሜሪካ ደወሉለት ። በጉጉዩ ብዙ ውይይትና ክርክር አደረጉ ።
አርሴማ ጥያቄዎቿ ከሞላ ጎደል ስለ ተመለሱላት ነገሩን የበለጠ ልታብብትና ሊማክሩበት
ተስማች ። የልጆቹን ፎቶ ካየች በኋላ የሁሉቱም ልብ በፍጥነት መቀየር ጀምሯል ።
ልጆቹን ለማሣደግ ከወሰኑ እርሱ ወደ አሜሪካ ከመመለሱ በፊት ቢመጡ እንደሚሻል
መከራቸው ። ከዝናሽ ቤተሰቦች ጋር ለመተዋወቅና ሂደቱን በቶሎ ለመጀመር ነገሩን
እንደሚያቀልላቸው አስረዳቸው ። በአርሴማና በንዋይ ድምጽ ውስጥ ተስፋና የደስታ
ፍንጣቂ ያየ ስለ መለሰው ውስጡ የበለጠ አትም አገኘ ።

ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ከአዲሱ የወደፊቱ የክሊኒክ ቦታ ሲደርስ፣ ከሲስተር ዘቢባ
በቀር ሁሉም ደርሰው ነበር ። ወደ ዋናው ቪላ ቤት ሲገባ ቤቱ በምግብ ሽታ ታውዷል ።
በብርሃን የተሞላው ሰፊ ሳሎን ከፍ ያለው ነጭ ኮርኒሱ ግርማ ሞገስ ሰጥቶታል ።
የምስጢር እናት ከሠራተኞቹ ጋር ጓዳ ውስጥ ጉድ ጉድ ይላሉ ። የቡና ዕቃው ተደርድሮ
ዙሪያውን ከበው የደመቀ ጨዋታ ይዘዋል ። በአንድ አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ የተለያዩ
ያበሻ ምግቦች ተደርድረዋል ። ሲስተር ዘቢባ ከባሏና ልጇ ጋር ሌላ የምግብ መሰናዶ
ይዘው መጡና ተቀላቀሉ ።

"እንዴ እኔ ኮ እንዲህ የደመቀ ድግስ መሆኑን አላወቅሁም እንጂ ... ያውቆ
ቢሆን ሰርቼ አመጣ ነበር ..." ሲል ፣

"አይ ዶክተር ሌላ ... ያንተ ወጥ ለዋናው ምረቃ ይቀይልን ። እንዲያው በባዶ
ቤት እንዳይሆን ብለን ነው" አሉ ፣ የምስጢር እናት ወይዘሮ ኤደን ። ሲስተር ዘቢባ እንደ
ለመደችው ሁሉንም እትፍ እያደረገች ሰማ ከምስጢር እናት ጋር ምግቡን እየደረደሩ
ወሬ ጀመሩ ። የሲስተር ዘቢባ ልጅ ሙኒራ ከሌላው ጋር ቁም ነገር ወሬ ይዘለች ፣
ምግቡ ለመበላት ተሰናድቶ ሲያልቅ፣ በምስጢር መሪነት ቤቱን ጎበኙ ። በጎን በኩል
ያሉትን ተጨማሪ ሰርቪስ ቤቶች ካዩ በኋላ ከዋናው ቤት ጀርባ ወዳለው ጫካ ወረዱ ።

ከግቢው መሃል የተሰየመው ቪላ ቤት ስድስት ለቢሮ የሚሆኑ ሰፋፊ መኝታ
ክፍሎችና ሁለት ትልልቅ ሳሎኖች አሉት ። ያሳሳሙ ሐሳብ፣ ዋናው ክሊኒክ ቪላው
ውስጥ እንዲሆንና ከበስተጀርባ ያሉትን ክፍሎች ለተለያዩ ቢሮዎች ለማድረግ ነው ።

@OLDBOOKSPDF

ጉብኝታቸውን ሲጨርሱ ወደ ቤት ገብተው እየበሉ ጪዋታቸውን ቀጠሉ። ሴላሠው በለ ሥራው ያለበውን ከነገራቸው በኋላ ያላቸውን ሐሳብ እየጨመሩ ከሊኒኩ አልቀ ሲዘፈት ምን ሊመስል እንደሚችል በምናባቸው ለመሳል ሞከሩ። በሁሉም ላይ ከፍተኛ ደስታና መነሣሣት ይነበባል።

ወደ አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን ሲራክ ከወዳሴ ጋር ቀጠሮ ስለነበረው ይቅርታ ጠይቆ ቀድሞ ወጣ። እነ ሲስተር ዘቢባም የታመመ ዘመድ መጠየቅ አለብን ብለው ብዙም ሳይቀዩ ሄዱ። የገናሽን ልጆች ምናልባት የንፁህ እህትና ባሷ ሊያሳድጓቸው እንደሚችሉ ከነንፁህ ጋር ያወሩትን ለሳንቾና ለምስጢር ሲነግራቸው፣

"እ-ም-ቢ-የ-ው ስምረትን እኔ ነኝ የምወስዳት ..." አለች፣ ምስጢር ሳታስበው ልቧ እገን ብሎ። ነገሩ ደስ ቢላትም ባጭር ጊዜ ከስምረት ጋር የፈጠረችው ጓደኝነት ሆዷን እባባው።

"እሱማ ቢሆን እንዴት በጣም አሪፍ ነበር ... እኔ በዚህ ፍጥነት ይላካል ብዬ በፍጹም አላሰብኩም ነበር። ደግሞ የሚታወቅ ቤተሰብ መሆኑ በጣም ደስ ይላል። ሦስቱንም ለመውሰድ ፈቃደኞች ናቸው ማለት ነው?" አለ፣ ባለማመን ዓይነት።

"እንግዲህ ነገሩን ገና ዛሬ ጠዋት ነው በሰፊው ያወራነው። መጀመሪያ ላይ የንጹሕ እህት አንገራግራ ነበር። ባጠቃላይ ልጅ ስለ ማሳደግም ሆነ በተለይ ከኢትዮጵያ ሦስት ልጅ ስለ መውሰድ ... አለ አይደል ቤተሰብንም የማላመኑ ነገር ከባድ ነው። ርቷቸውን ልኪላቸው ካዩ በኋላ ዛሬ ጠዋት ላይ ስናወራ ልባቸው በጣም የተለሳለሰ ይመስላል" አለ፣ ፊቱ ከቀረበው ዳቦ ቁሌ ላይ ቀንጠር አድርጎ እየቃመ።

"እነርሱ ምንም ልጅ የላቸውም እንዴ?" አለች፣ ምስጢር አሁንም ስለ ስምረት እያሰበች።

"ከተጋቡ አስር አመት ቢያልፋቸውም እስካሁን አልቀናቸውም። ደግሞ ልጅ እንዴት መሰለሽ የሚወዱትና የሚፈልጉት። ከወሰኑ እኔ ከመመለሴ በፊት ሳይመጡ የሚቀሩ አይመስለኝም። አይ ሆፕ ... እንደሚላካ"

"የገናሽ አባትና እህቷስ የሚስማሙ ይመስልሃል? ሃሳባቸውን እንዳይለውጡ ደግሞ ..." አለ ሳንቾ።

"እንግዲህ ባለፈው እንደ ሰማኸው ተስማምተዋል። ነገሩ እውነት ሆኖ ሲመጣ የሁሉም እጽምና አትም ይለያል። እስከዛ ግን ማን ያውቃል?" የሚቀጥለው ቀጠሮው ስለደረሰበት ቀድሟቸው ወጣ።

@OLDBOOOKSPDF

፡19፡

ንጹሕና ንዋይ አርሲማን ለማሳመን ያደረጉት ጥረት በመጨረሻ ትንሽ የእሺታ ፍንጭ ሰጠ። ከብዙ ውትወታና ማደፋፈር በኋላ ልጆቹን በአካል ለማየት ተስማማች። ቢሆንም ባይሆንም ለጉዲፇቻ አስፈላጊ የሆኑ መረቀቶችን ሁሉ አሟልተው ያዙ። ሌላው ወደ አሜሪካ ከመመለሱ በፊት በተቻላቸው ፍጥነት ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ አቀዱ።

የገዛናሽ እህትና አባት ደግሞ ነገሩን ሲነግራቸው ማቅማማት ጀምሩ። ሌላው ነገሩ የጠበቀው ቢሆንም የተወሰነ ብስጭት ፈጥሮበታል። ከቤተሰብ ጋር ተነጋግረን ውሳኔያችንን እናሳውቃችኋለን ብለዋቸው ቀጠሮ ይዘዋል። ገንዘብ እንደፈለጉ ስለገባው ነገሩ አናዶታል። ከገዛናሽ ሞት ጀምሮ የረዷቸው ልጆቹን ለመውሰድ አስበው ያደረጉት ስለመሰለው ነገሩን እርግፍ አድርገ ሊተወው‌ም አሰበ። የአርሲማን መነሣሣትና የሕፃናቱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ አሰቦ ንዴቱን ዋጥ አድርጎ ዝም አለ።

በቀጠሮው ቀን ረፋዱ ላይ ከሳንቾ ጋር ወደ ገዛናሽ እህት ቤት ሄዱ። አባቷና ሌሎች ሁለት ጠና ጠና ያሉ የሠፈር ሽማግሌች ተቀምጠው ሲጠብቋቸው ደረሱ። እርሷም ቡና እያጣጠበች ወዲያ ወዲህ ጉድ ጉድ እያለች ቤቱ ደማምቋል። ስፋ ያለ ሳሎንና አንድ መኝታ ክፍል ያለው ቤት ውስጥ የገዛናሽን ሕፃን ልጅ ጨምሮ አራት ልጆቿ፣ ሌሎች ሁለት ዘመዶቻቸውና ባልና ሚስቱ ይኖሩበታል። ግድግዳው በጭቃ ተለስኖ እስከ አጋማሹ በከብት አዛባ ተለትልቋል። ጥግ ላይ ዳንቱል ከለበሰው ቴሌቭሽን አጠገብ ጣሳ የተያረያረበት አሮጌ መደርደሪያ ይታያል። ከባሻገር ደግሞ ባሮጌ በርሚል ላይ ያረጀ ሌማት ላመል ገርበብ ብሎ ይታያል። ትንሿ መስኮት እስከ ጥግ ብትከፈትም ቤቱ ሞልምልምና ትዝትዝ እንዳለ ነው።

የነሌላሠውን መምጣት ያጅ በቅመው መኪና ያወቱት ልጆች ግር ብለው ሊገቡ የቤቱ ጸጥታ ባንዴ ደፈረሰ። ስምረትና ሰምሳን ሳቋቸው ላይ ተጠመጠሙበት። ሌሎቹ ልጆችም ዙሪያውን ከበቡት። የገዛናሽ እህት ወደ ደጅ ወጥተው እንዲመጡ ሥፃ

@OLDBOOKSPDF

ለታመራቸው እንዳመጣጣቸው ተሯሩጠው ወጡ። ስምረት ብቻ ሳንቶ ላይ ልጥፍ ቀለቀረች። እናቷን እምጡ ብላ እያለቀሰች ስታስቸግር ስለሰነበተች ተመቻት።

ወደ ዶሮው ጠጋ ብላ "ሚስጥልስ?" አለችው።

ጉንጩ ላይ ሳም አደረጋትና፣ "ስራ ላይ ናት ሚስጥር ... ሰላም ብላሻለች ... ለላጊዜ ትመጣለች" ብሎ፣ ከኪሱ ውስጥ ማስቲካ አውጥቶ ሲሰጣት፣ ከእትፋ ውስጥ ወቶታ ወደ ደጅ ሮጠች። የዝናሽ እህት ቡናውን ስትቀላላ ትልጁ ልጇ ደግሞ ዕቃ ቤግቶራረብ ትረዳት ነበር። ለመንደርደሪያ ያህል የሆነ ያልሆነውን ሲያወሩ ቆዩ።

ሌላሠው ሀሳቡን ሰበሰብ አድርጎ፣ "ያው እንግዲህ ባሰፈው እንደ ተነጋገርነው ሦስቱንም ልጆች መስዶ ለማሳደግ የባለቤቴ እህትና ባሏ በደስታ ፈቃደኞች እንደ ሆኑ ነግረውኛል። በቀደም እንጻላችሁኝ አስባችሁበት ከቤተሰብ ተማክራችሁበት ከሆነ ..." ብሎ፣ ተራ በተራ እያያቸው ዝም አለ።

የዝናሽ እህት ፈጠን ብላ "ነገሩ እኮ ከማንም በላይ ደስ የሚያሰኘንም የሚጠቅመንም እኛን ነው። ደግሞ እንዚህ የሙት ልጆችስ ቢሆኑ ማን አላቸው። ግን በቃ ለዚ ሁሉ ገና አርባዋ እንኳ ሳይወጣ ልጅቷን ሊሸጡ ነው፣ እያሉ ቁም ስቅላችንን አሳዩን። እኛስ ብንሆን በሰንቱ እንጠበስ ...ቢሳቢስቲን ላናገኝ። ከዚህ ሁሉ እበላ፣ እዚሁ እንደሆኑ ሆነው እኛ የበላነውን በልተው ያድጋሉ" አለች፣ እምባዋ እየቀደማት።

ከዝናሽ አባት አጠገብ ያሉ ቢጫ ቀብ ያዶሬጉ ጠና ያሉ ሰውዬ ጉሮሯቸውን ጠረግ ጠረግ አደረጉና፣ "እዬ አንቺ ደግሞ ... የሰው ምላስ ተፈርቶማ የሚሆን ነገር የለም። ሰውምንም ብታደርጊ የሚለው አያጣም። ሰውና ጉም አይታመንም። ይልቁን ለነዚህ ልጆች የሚበጅና የሚጠቅመውን ማሰብ ነው የሚበጅ። እግዜር የናታቸውን ጸሎት ሰምቶ የሰጣቸውን ሲሳይ መንሳት ጡር አለው" አሉ፣ ከፊታቸው የቀረበውን ቅራሪ አንስተው ተንከዱ።

ንግግራቸውን በመቀጠል፣ "ሆኖም ግን የኛ ሰው አፉ እሳት ነው። በርግጥ መቼም ገና ተቀብራ አካሏም ሳይፈርስ ልጆቹን መበታተኑም ደግ አይደለም። እኅህስ አሳውንት ቢሆኑ ላይናቸው ምን ተስፋ አላቸው? ተማክረው ምን ያደረጉት እንደሚሉት ነው። እነዚህም ጣድቃን እግዜር ቢላቸው እንጂ በዛሬ ጊዜ ማነው የሰው ልጅ ወስጄ ላሳድግ የሚል ...እንኳን የደሃን ልጅ ... ሰጪ ተጨካክኗል እኮ ... እግዝያሀር የመረቃቸው ..." አሉ፣ ወደነሌላሠው ጭራቸውን እየጠቀሙ።

"እሱማ ገቡ ከታመመች ጀምሮ እንርሱው አይደል ሲረዷት የቆዩት። የማዬ አምላክ ብድራቸውን ይክፈላቸው እንጂ እነሱ ባይኖሩ ምን ይውጠን ነበር። ግን በቃ አሁን አባዬም እትሙ እየደከመና እየታመመ ነው ... እኛም በቃ እበላችን በዛ። ምንም ጠብ የሚል ነገር የለም። ጉረቤቱ ሁሉ ... ልጆቹ ለጉዲፈቻ ድርጅት ቢሰጡ፣ ቤትሰብንም ይረዳሉ ... ምን እንዲህ አስቸነላችሁ እያሉ ነፍሴን ሊያወጧት ነው" ሰትል፣ የነገሩ አካሄድ ቢገባውም ዝም ማለት መረጠ ሌላሠው።

@OLDBOOOKSPDF

"ኧረ ልጆቹን ታይለያዩ ተንከባክቦ የሚያሳድጋቸው ይገኝ እንጂ፣ እኔ ደግሞ ለየትኛው እድሜዬ ነው። እሱ የከፈታትን ይቺን ጉሮሮ ታይዘጋ አያድር።"

ሌላኛው እንግዳ ከገናናሽ አባት ቀበል አድርገው፣ "እኔ ትንሽ ያላሰበኝ ... እንዲያው ከናካቴው ከዘመዶቻቸው ይቀራረጣሉ ወይስ እንዴት ነው? አሳዳጊዎቹ ተውሜ ሃገር ኗሪ ናቸው ወይስ?" አሉ።

ሌላሠው፣ ነገሩን ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ስለመሰለው፣ "ልክ ነው እባባ አሳዳጊዎቹ ውጪ ሃገር ነው የሚኖሩት። ሴትየዋ የባለቤቴ እህት ስለ ሆነች የቅርብ ሰዎች ናቸው። ጥሩ ኑሮ ያላቸው መልካም ሰዎች ናቸው። የራሳቸው ልጆች ስለሌላቸው እንደ ልጆቻቸው አድርገው ነው የሚያሳድጓቸው። ከቤተሰብ ጋር ሳይቀራረጡና ታሪካቸውንም ሳይረሱ የሚኖሩበትን ሁኔታም ማመቻቸት የሚፈልጉ ናቸው። ከዛ ውጪ ግን ልጆቹን በማደጎ ሲወስዱ ለዘመድ ገንዘብ መክፈል ወይም የማደጎ ድርጅቶቹ ያደርጋሉ የተባለውን ነገር በክፍያ መልክ ማድረግ እንደማይፈልጉ እርግጠኛ ነኝ..." አለ።

"ኧረ እኔ ኮ ገንዘብ ይከፈለን ማለቱ አይደለም" አለች፣ የገናናሽ እህት ደንገጥ ብላ።

"እንግዲህ ስለተዛመድንና ቤተሰብ ስለሆንን ልባችን የፈቀደውን ለልባቸው ይሁን ለናንተ ማድረጋችን አይቀርም። ስትቸገሩ እያየን እኛስ እንዴት ዝም እንላለን። ልጆቹን እንድትሰጧቸው በማለት ግን በልዋጭ ወይም በክፍያ መልክ የሚደረግ ነገር ሊኖር አይችልም። እንግዲህ እኔም ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ውጭ አገር ስለምመለስ ውሳኔያችሁን ንገሩኝ" አለ ሌላሠው፣ ቁርጥ ባለ ድምጽ።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ መጀመሪያ የተናገሩት አዛውንት፣ "እኔ መቼም ለነዚህ ልጆች የመጣላቸውን ሲሳይ በሰው ወሬ ተገፍተን ባናከላክል ይሻላል ባይ ነኝ። ሰዉዛሬ የፈለገውን ቢል፣ ነገ ቀን ሲከፋ እንዲት ጣላ ውሃ አይሰጥ ...ለምኑ ነው? ሁሉ ስወሬ ነው የሚበረታ። እቤታችሁ ድረስ የመጣ ሲሳይ ባትመልሱ ... እነርሱንም ባታስቀይሙ ደግ ነው። ደግሞ ልጆቹን ተቤተሰብ አንለይም ታሉ ... ለምን እነሱ ህሊናቸው የፈቀደውን እንዲያደርጉ ዝም አትሉም?" ብለው፣ ነገሩን ደመደሙት።

የገናናሽ እህት የተወቀጠውን ቡና ከጀበና ውስጥ እየጨመረች ያባቷን ዓይነ ዓይን ስታይ፣ "እኔም ልቦናዬ የሚለው ያው ነው። ዶክተር መቼም ለገናናዬ ታደረጉላት ከብካቤ አንጣር እኔ የልጆቹንም ነገር በላቸው ላይ ነው አደራ የምጥለው። ለኛ ተሆነ እስታውን ያደረጉልንንስ ውለታ ቢሆን፣ በምን አትም ነው የምንመልስ" ሲሉ፣ የገናናሽ እህትም ትር እያላትም ቢሆን፣ ነገሩን መቀበሏን ገለጸች። ቡናው ተጠጥቶና ትንሽ ተጨዋውተው አሳዳጊዎቹ ሲመጡ፣ ለመገናኘት ተስማምተው ተለያዩ።

@OLDBOOKSPDF

ከሳምንት በኋላ አርሴማና ንዋይ አዲስ አበባ ገቡ። ከንጹሕ ጋር ተነጋግረው እንአርሴማን ሊያገባቸው፣ ሌላው የመመለሻ ጊዜውን በአስር ቀን አስረዘመ። በመሆኑ በሦስተኛው ቀን የገናናሽን ቤተሰብ ሊተዋወቁ ወደ ዘነበ ወርቅ ይዘዋቸው ሄዱ። አርሴማ ከሳንቶ፣ ንዋይ ደግሞ ከሌላው ጋር በየፊናቸው የሞቀ ወሬ ይዘው ስለታወቃቸው ደረሱ። ከመኒና እስኪወርዱ በወሬ ተጠምደው የሰፈሩን ሁኔታ ልብ አላሉትም። በእግራቸው ውስጥ ለውስጥ እየሄዱ ወደ ሰፈሩ ጉራንጉር ሲገቡ አርሴማና ንዋይ ድንጋጤያቸው ጨመረ። የገናናሽ እህት ቤት በር እስኪደርሱ ድረስ ያለም አልተነፈሱም።

ቤት ሲገቡ የፈላ ቡና ላይ ደረሱ። ልጆቹ ተጣጥበውና ተሽሞንሙነው እንግዳ ይመጣል ተብለው ጸባያቸውን እንዲያሳምሩ ብዙ ሥልጠናና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። ስምረት ገና ሳንቾን ስታየው የተባለችውን ረስታ እግሩ ላይ ተጠመጠመችበት። መጀመሪያ ላይ እንግዶቹን ለመቅረብ ቢያንገራግሩም ይዘውላቸው የመጡትን ልብስና መጫወቻ ከተሰጣቸው በኋላ ግን ስምረት የንዋይ ወዳጅ ሆነች። አርሴማ አዲሲን ልጅ ታቅፋ አይን አይኗን እያየች ስታጫውታት የተሰየ ስሜት ውስጧ ተፈጠረ።

በጨዋታ መሃል ስለቀሺ ተነስቶ ሲወራ አርሴማ ማየት ስለፈለገች ተያይዘው ወጡ። ከግቢው ወጣ እንዳሉ የገናናሽ እህት ገረቢት የሚኖር ጎረምሳ ልጅ ከአጥራቸው ስር ያለ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ አየችና፣ "ስማ አንተ ዳርጌ ... እስኪ ባክህ ቀሺን ለማየት ፈልገው ነበር። አብረህ ወስደህ አሳያቸው። ሰዎች እንዳይተናኮሏቸው ... እዶራ ... እዚሁ መኪናቸው ጋ እስኪመለሱ ድረስ አብረሃቸው ሁን እሺ" አለች፣ የገናናሽ እህት በግዘዝ ድምጽ። እሱም ከመቀመጫው ተነስቶ ራሱን እያከከ ትዛዙን ተቀብሎ ቀመ።

በዚያው ለመሄድ ስለፈለጉ የገናናሽን እህትና አባት አመስግነውና ሰሞኑን እንደሚያገኟቸው ነገረዋቸው ተለያዩ። ስምረት ግራና ቀኝ የሳንቾንና የንዋይን እጅ ይዛ እየዘፈነችላቸው ታስታቸዋለች። ሳምሶን ደግሞ ከአርሴማ አጠገብ እየሄደ ስለ ሰፈሩ የምትጠይቀውን ጥያቄ እየመለሰላትና የሚያውቁን ያህል ሲነገራት በብስለቱ ተደነቀች።

"ያመጣችሁልኝ ሚማ በጣም ነው ደስ ያለኝ። ትምህርት ቤት ልጆች አድርገውት አይቼ ..." ብሎ, እንደ ማፈር ብሎ ሲያገነብስ ጠጋ ብላ አቀፈችው። ቀና ብሎ "አመሰግናለሁ" ሲላት, እንባዋ መጣ። ለስላሳ ጸጉሩን እያሻሸች "በጣም ደስ የምትል ልጅ ነህ" ስትለው, ሳቅ ብሎ እንገቱን ሰበረ።

በሰፈሩ ውስጥ ውስጡን አሳብረው አስፋልቱን እስኪሻገሩ ጥቂት የሰፈሩ ልጆች ተከትለው ሲያጅቧቸው ዳርጌ ተቆጥቶ አባረራቸው። ምንም ማድረግ ስላልቻሉ እየተንጫነጩ ተመለሱ። የተከመሩ ላስቲክችንና ጣሳዎች ያሉባቸውን ገቢዎችን እያዩ ጠመዝማዛ በሆኑ ጻገት ቁልቁለታማ ቁጫጭን መንገዶች አለፉ። አልፎ አልፎም በግዳበሪያ ከረጢት ሙሉ ቅራቅንቦ እቃዎችን የተሸከሙ ሴቶችና ልጆች ቀም እያሉ

@OLDBOOOKSPDF

እያዩዋቸው የሆነ ነገር ተንሾካሹከው ያልፋሉ ። ከሩት ሲያዩት ካሰቡት በላይ ትልቅና ሰፊ ቦታ የያዘ የቀሻሻ ክምር መሆኑ ሁሉንም አስደንግጣቸው ።

መጸረጓው ላይ ቆመው ከጸር እስከጸር ለማየት ሞከሩ ። በተከመረው የከተማይቱ ቀሻሻ ላይ ሰዎችና ውሾች ከወዲያ ወዲህ ይራኮታሉ ። ሁሉም የሚፈልገው'ን ለማግኘት ይማስናል ፤ ይሞራል ደግሞ በያዘው እንጨት ይሞነጫጭራል ። በአንድ ጥግ ደግሞ ተመርጠው የተለቀሙ እቃዎች ተከምረዋል ። በቡድን በቡድን እየሆኑ የሚለቅሙና ተቀምጠው የሚያወሩ ወጣቶች አልፎ አልፎ ይታያሉ ። ሞኑቱን ለማራገፍ በመጣ መኪና ዙሪያ አያሌ ሰዎች አሰፍስፈው ይጠብቃሉ ። ከማዶ ደግሞ ተከምሮ በቀየው ቀሻሻ ላይ ቁራዎችና አሞራዎች ስፍረውና በላዩ ሲያንሣብሱ ይታያሉ ።

በመሃል ባለችው ተሞን መንገድ ላይ ወደ ውስጥ ሲገቡ ካንድ ጥግ ላይ በፈስታል ውስጥ ያለ ነገር ከበው የሚቀራመቱ ልጆች ጋ ደረሱ ። ጠጋ ብለው ሲያዩ የተራረፈ ምግብ መሆኑን አዩ ። ቀሺ ሰው ፣ ውሻና ቁራ ተዛዝኖና ተሻምቶ የሚኖርበት ምስጢራዊ ቦታ ።

"ጸርጌ ... እንተም እዚህ አካባቢ ነው ያደግኸው?" አለ ፣ ሴላሠው አብሮ ያለውን ወጣት ልጅ ። ንዋይም አርሴማም የልጁን መልስ ለመስማት ዞር አሉ ።

"እምን ... እዚሁ ቀሺ ሰፈር ነው ያደግነው ። ከትምህርት ቤት መልስ ኑሯችን ሁሉ እዚህ ነበር" አለ ፣ አፈር ብሎ ።

"አሁን እዛ ከምር ቀሻሻው ላይ ያሉት ሰዎች ምንድነው የሚፈልጉት?"

"የተገኘውን ... እንዳንዴ እሽጉ ያልተከፈተ ምግብ ... አሮጌ ልብስ ... መጠጥ ... ቀርቀሮና ፕላስቲክ የሃይላንድ ጠርሙስ ... በቃ የተገኘውን ..."

"ከዚህ ላይ የተሰበሰበው ምግብ ስትበሉት አያማችሁም እንዴ?" አለች፣ አርሴማ ነገሩ ከአእምሮዋ በላይ ሰለሆነ ጣልቃ ገብታ ።

"ምግቡ ይመመው እንጂ ... ባክቴሪያዎቹም በድሃ ሆድ አይጨክኑም ... እኛ የትም እንደማንሄድባቸው ስለሚያውቁ ብዙም አይተናኮሉንም" ብሎ ሲስቅ፣ ሁሉም ሳይወዱ በግዳቸው ፈገግ አሉ ።

"እንተ ቤተሰቦችህ እዚህ ሰፈር ናቸው?" ስትለው ፣

"እናቴ በልጅነቴ ነው የሞተችው ... አውሬው ነው የገደላት ... አባቴን አላውቀውም" አለ ።

"የምን አውሬ?" አለ ፣ ንዋይ ግራ ገብቶትና ደንግጦ ።

"አይ ጅብ ምናምን መስሎህ ነው ። ቫይረሱ ነው ... አውሬው የምንለው" አለ፣ በሐዘን የተሸረበ ፈገግታው ብልጭ ብሎ እየጠፋ ።

"ዘመድ ጋ ነው ያደግኸወ?" አለ ድንጋጤው ያለቀተው ንዋይ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ቀሺ ነው ያላደገኝ ... እዚሁ ያገኘሁትን እየለታተምኩ ነው ያደግሁት ። ሲመሽ ከቻልኩ ከጎዱ ቤት ጥጋ ጥግ ካልሆነም ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ አድራለሁ ። በዛ ላይ የሸሌ ልጅ ... ኤይድስ አለበት እያሉ ... ያገኘኝ ሁሉ እንደ ሰባራ የቀሺ ጠርሙስ ይጠልዝሃል" አለ ።

"ትምህርት ቤትስ?" አጠገባቸው ያለው መጥፎ ጠረን ሲጠነክርባቸው ፈጠን ብለው አለፉት ።

"የሆኑ ሰዎች እየረዱኝ ... እስከ ሰባት እንደምንም ተማርኩና ... በኋላ ግን ረሃቡና የልጆቹ ስድብ ሲብስብኝ ትቼው እዚሁ ቀሺ መዋል ጀመርኩ ። ታክሲ ወያላነትም ሞክሬ ነበር ... አሁን ሲገኝ የግንበኛ ረዳት ሆኜ እሰራለሁ ። "ጸጥ ብሎ ቀየና ድገት ቁጭ ብሎ ስትስቅ ብሎ ሲያለቅስ የሚይዙ የሚጨብጡትን አጡ ። እንደ ምንም ተጋግዘው አባበሉት ። ለቅሶው ጋብ ሲልለት ከሥራ ተባርሮ የቤት ኪራይ የሚከፍለው እንደሌለውና ሁለት ቀን ሙሉ ከትንሽ ዱረቅ ቂጣ በቀር ምንም እንዳልቀመሰ ሲነግራቸው የሚሉት አጥተው ጸጥ አሉ ። ተመልሰው ወደ መኪናቸው ሲመጡ ለቤት ኪራይና ለአንዳንድ ወጪ የሚሆን ገንዘብ ሰጥተው ፣ ተስፋ እንዳይቆርጥ አበረታቱት ።

ስምረትና ሳምሶንን ወደ ቤት አስገብተው ከሰፈሩ አስኪወጡ ሁሉም በዝምታ ተዋጡ ። አርሴማና ንዋይ ያዩት ያካባቢውና የሰዎቹ ሁኔታ ፣ በእውናቸውም በህልማቸውም አዲስ አበባ ውስጥ ይኖራል ብለው ያልጠበቁት ነገር ነበር ።

"እንዴት አገኛችኋቸው ታዲያ?" አለ ፣ ሴላሠው ወደ ዋናው መንገድ ሲገቡ ።

"ምን እንደሚሰማኝ በትክክል አላውቅም ... ድብልቅልት ነው ያለብኝ ። ሳምሶን በጣም ነው ያሳዘነኝ" አለች አርሴማ የንዋይ ትከሻ ላይ ደገፍ ብላ ። አየት አታደርገው "ባይኔ ባላይ ኖሮ ፣ እንደዚህ አይነት ቦታ አዲሳባ ውስጥ ይኖራል ብዬ ማመን መቻሌንም እጠራጠራለሁ ። " አሁንም በፊቱ ላይ የምትሄደው ስምረት ናት ። "ስምረት ገና ካሁኑ እየናፈቀችኝ ነው ፣ እንመለስ እንዴ?" ሲል ፣ ሁሉም ሳቁ ።

መንገድ ላይ ለቡና ቀሙና ብዙ አወሩ ። ልባቸው በልጆቹ ፍቅር መነደፉ ከንጋራቸው ያስታውቃል ። ባልና ሚስቱ ቤት ተከራይተው ላቸው ቤተሰቡን እንዳለ ከዛ አካባቢ አውጥተው ሊያስቀምጧቸው ቢያስቡም ሴላሠው በሐሳቡ አልተስማም ። ኑሯቸውን ለማሻሻል ሕይወታቸውን ማፍረስ የባሰ ጉዳት ነው ብሎ ሊያስረዳቸው ሞከረ ። ሰፋ ያለና የተሻለ ፣ የራሱ ግቢ ያለው ቤት እዛው አካባቢ ቢከራዩላቸው እንደሚሻል ተስማሙ ።

ከልጆቹ ጋር ከተዋወቁ ጀምሮ የተወሰነ ጊዜ አብረው ማጥፋት ጀምረዋል ። እስካሁን ሁለቱም ሐሳቡን ለቤተሰቦቻቸው እንዴት እንደሚነግሩ ጨንቋቸዋል ። የጉዲፈቻውን ሀጋዊ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት ከቤተሰብ ጋር መማከር እንዳለባቸውና ሴላሠው ከመሄዱ በፊት ሊያደርጉት ወሰኑ ። ከቤተሰብ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደሚያጋጥማቸው ስለጠበቁ ምን ማድረግና መናገር እንዳለባቸው በጥንቃቄ ተዘጋጅተዋል ።

@OLDBOOOKSPDF

የቤተሰብ ስብሰባው በንጥይ ጠላጅች ቤት ተደረገ። በአጋጣሚ የእርሷግ ወላጆችም ለረጅም እረፍት አዲስ አበባ ስለነበሩ መገናኘት ቻሉ። ሀጋቢ ሂደቱን ለመጨረስ ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ ስላወቁ ሌላውና ንጥይ ከሰብሰባው በኋላ በሚቀጥለው ሳምንት ወደ አሜሪካ ለመመለስ አቀዱ።

ከዮቂት የቤተሰብ አባላት በተር አብሳኛው ቤተ ዘመድ የግበሣውን ዓላማ አላወቀም ነበር። ለረጅም ጊዜ ተራርቀ የቀየን ቤተሰብ አጋጣሚውን ተጠቅመው ለማገናኘት የተደረገ ነው የመሰላቸው። የምሳ ድግሱ ተገባዶ ቡና መጠጣት ሲጀመር አርሴማ ወደ መሃል አካባቢ ቀማ አጨበጨበች። ሁላታው ጋብ ሲልላት ንዋይን አብሯት እንዲሆን በምልክት ጠራችው። ከጮኗ ሲቀም እጁን ያዝ አድርጋ ወደ ንዋይ እያየች

"በመጀመሪያ ማሚና ጳዲ በጣም ነው የምናመሰግነው ስለዚህ ግሩም ምሳ" ስትል ለጪ ሁሉ አጨበጭበ። "በመቀጠልም ይሄ ምሳ የተጠራበት አንዱ ምክንያት እኔና ናዩ ልንነግራችሁ የፈለግነው ትልቅ ዜና ስላለን ነው" ብላ፣ ወደሱ ዞር ስትል ሁሉም ለው አርግዝ መሆኑን አርግጠኛ ሆኖ በድጋሚ በጭብጨባ ቤቱን አቀለጠው።

ከዛ እሱ ትንሽ ጉሮሮውን ጠራረገና፣ "እንግዲህ እናንተ ከጠበቃችሁት ዜና ጋር ምን ያህል እንደሚመሳሰል አላውቅም። ያው እንደምታውቁት እኔና አርሲ ከተጋባን አሥር አመት አለፈን። ያምላክ ፈቃዱ ሆኖ እስካሁን ልጅ ሊኖረን አልቻለም። ድንገት በተፈጠረ አስገራሚና አጋጣሚ በሚመስል ከስተት ሳናቅደው አዲሳባ ተገኝተናል። ይኸውም ከዚህ አገር በጉዲፈቻ ልጅ ለማሳደግ ስለወሰንንና ዕድሉም ስለተገኘ ነው" ሲል፣ የነበረው የተጋጋለ ስሜት ባንድ ጊዜ ውርድ ብሎ ጥቂት ሰዎች ሲያጨበጭቡ በይሉኝታ ሌሎቹም እንደ ነገሩ አጨበጨቡ።

ነገሩ ብዙም ያላስገረማት አርሴማ ቀበል አድርጋ፣ "ሁላችሁም የራሳችንን ልጆች ብንወልድ ምን ያህል ደስ እንደሚላችሁ እናውቃለን። ግን አልሆነም። አሁን የመጣነው እዚህ ያንድ እናት ልጆች የሆኑ፣ እናታቸውን በቅርብ በሞት የተነጠቁ ሦስት ሕፃናትን ልጆቻችን አድርገን ለማሳደግ ስለወሰንን ነው። ሂደቱን በተወሰነ ደረጃ የጀመርን ሲሆን፣ አንዶ እግዚአብሔር ፈቃድ በቶሎ ሁሉም ነገር አልቆ ከኛ ጋር እንደሚሆኑ እናስባለን" ስትል፣ ሁሉም በድንጋጤ ጸጥ ሲሉ ክፍሉ ረጭ አለ።

ንግግሯን በመቀጠል፣ "ያው ያልተለመደ ስለሆነ ሊያስደንግጣችሁና ግራ ሊያጋባችሁ እንደሚችል ገምተናል። ሁላችን ጠላጅ አልባ ልጆችን መሰዶ ማሳደግ የፈረንጅና የትዲፈቻ ድርጅቶች ስራ እንጂ የኛ ኃላፊነት አድርገን እንደማናስብ የታወቀ ነው። እኛም እዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የቻልነው ብዙ አስበንበትና ከፍተኛ ውስጣዊ ትግል አድርገን ነው።

"ግን ነገሩን ከናንተ ጋር ልንወያይና ልናካፍላችሁ የፈለግንበት ምክንያት ደግሞ አለ። የመጀመሪያው የናንተን ሐሳብና ምክር ለመስማት ሲሆን፣ ጥያቄ ከላችሁም ለመመለስ ነው። በተለይ ግን ልጆቹ ቢኖሩ ተፈጥሯዊ ልጅ ቢኖሩ ከሆኑ በኋላ ልጆቻን ስለሆኑ

@OLDBOOOKSPDF

እናንተም በሙሉ ልብ እንደ ወለድናቸው ልጆቻችን እንደትተቡዋቸው ለመጠየቅ ነው። ይህ ጊዜ ለኛ ከእርግዝናና ከምጥ ያላነሰ ከባድ ጊዜ ነው ... ስለዚህ በተቻላችሁ መጠን አብራችሁን ከኮናችን ብትቀሙ ደስ ይለናል" አለች።

"ምናልባትም እኔ ወደ ሥራ መመለስ ስለሚያስፈልገኝና ሌላም በሚተዋሰው ሳምንት ስለሚሄድ ያው እገዛችሁ ከአርሲ እንዳይለይ ..." አለ ንዋይ፣ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ ዙሪያውን እየቃኘ።

ቤተሰቡ ሁሉ የሚፈራቸው የንዋይ አባት የሆኑ ሰው፣ "እንዴ እንዴት ነው ነገሩ? እገዳ ዱብዳ ነ ነው ያወረዳችሁብን ... ተማክረ ማድረጉ አይሻልም ነበር? ጉዲፈቻ እኮ ስንት ጣጣ አለው። ለመሆኑ ዕድሚያቸው ስንት ነው? ደግሞስ የጤናቸው ጉዳይ ተጣርቷል? እንዴት ነው የልጅ ነገር እኮ አደረጋችሁት" አሉ፣ ገና ብዙ ጥያቄ እንዳላቸው በሚመስል አነጋገር።

"ዕድሚያቸው አንድ ወር፣ አራት ዓመትና ሰባት አመት ሲሆኑ ትልቁ ወንድ ነው። እናታቸው በወሊድ ምክንያት የዛሬ ወር ግድም ነው የሞተችባቸው። እሁን ያሉት ወንድ አያታቸው ጋ ሲሆን እሳቸውም የሥጋ ደዌ ታማሚ ስለነበሩ አሁን በልመና የሚተዳደሩ በጣም ችግረኛ ቤተሰብ ናቸው" ስትል፣ አርሲማ የተሰበሰቡት ዘመዶች የበለጠ ማጉተምተም ጀመሩ።

አባትዬው እጃቸውን እያጨበጨቡ፣ "እንዴ ኧረ ባዘኔቱ ...ይሀን እኮ ነው የምለው። እናቲቱ ለኤይድስ ተመርምራ ነበር? ደግሞ ቁምጥናውም እኮ በዘር የሚሄድ ነገር ነው። ልጆቹስ ቁምጥና እንደ ሌለባቸው አስመርምራችኋል? ምንድነው እንዲህ ያጣደፋችሁ ... ባልጠፋ ባገሩ ላይ በፈሰሰ ሕፃን ... ደግሞ ባንዴ ሦስት ልጅስ አልበዛም?" ሲሉ፣ አብዛኞቹ ተሰብሳቢዎች በመስማማት ሞንትላታቸውን ነቀነቁ።

አርሲማና ንዋይ ነገሩ ከጠበቁት በላይ ስለሆነባቸው ዝም ሲሉ ሌላው ጣልቃ ገባና፣ "ጋሽ ጸምጤ እንዳሉት ነገሩ ቀላል አይደለም። ያነሷቸው ነጥቦች ሁሉ በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል። እዚች ላይ ትንሽ ለመጨመር ግን ... የሥጋ ደዌ ህመም በንክኪም ሆነ በዘር እንደማይተላለፍ በህክምና የተረጋገጠ ነገር ነው። ልጆቹም ፍጹም ጤነኛ ናቸው።" ሲል እናቱ አቋረጡት።

"ልጅ ማሳደጉ ጥሩ ነው ግን ሳይጣደፉ ተጠንቅቀ አይሻልም? ልጅ ቀላል ነገር አይደለም። ስንት የጉዲፈቻ ድርጅቶች አይደል እንዴ ከተማው ያጣበቡት። እኔም በጋሽ ጸምጤ ሐሳብ ነው የምስማማው" አሉ፣ መደ ንዋይ አባት አየት እያደረጉና ነገሩ እንዳልተዋጠላቸው በሚያሳይ ፊት። ነገሩ ሳይታሰብ መደ ተለጠ ክርክር ተሰመጠ።

"እናንተ የምትሉት እኮ ገብቶናል ... እንዚህን ሌላ ሰው ያሳድጋቸው ወይም እንደሆኑ ይሁኑ ... በዘራችን የሌለ በሽታ እንዴት ቤታችን ይገባል ነው አይደል? ቀይ ሰው አርግዞ ቢወልድም እኮ ሁሌ የመረጠውን ነገር አያገኝም። ... ያው የተሰጠውን አይደል የሚተበለው። እነዚህ ልጆች ደግሞ ለኛ የተዘጋጁልንናቸው። የኛ ልጆች ከሆኑ ደግሞ ሰሌላ ሰው ልንለጣቸው ወይም ልንተዋቸው አንችልም። እኛ የምንጠይቃችሁ

@OLDBOOOKSPDF

አሁንም ልጅቻችን ስለሆኑ እንደ ወለድናቸው ልጆች ወዶ ቤተሰቡ በፍትርና በሙሉ ልብ እንድትቀበሏቸው ነው። ይህንን ማድረግ ይከብዳችኋል" አለች፣ አርሲማ ስሜቷ ገሎ። ሁሉም እንደገና ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ።

የአርሲማ እናት ትንሽ ነገሩን አለሳልሰው፣ "ቀይ እኔ የምለው ከምትቸኩሉ ለምን ሌሎች አማራጮችንም እታዩም? ደግሞ መጀመሪያ አንድ ልጅ ውሰዱና ከዛ ብትጨምሩ አይሻልም? ጸምጤ እንዳለው ... ልጅ ማሳደግ እኮ እንዲህ ቀላል ነገር አይደለም። በዛ ላይ በችግርና በስቃይ ያደገን ልጅ ማሪቱም ቀላል እንዳይመስላችሁ" ብለው፣ የራሳቸውን ሲጋት ገለጹ። አንድ ሁለት ሰው ያንኑ አያጠነክረ ሲቀመጥ ብዙኃኑ በሳቸው ሃሳብ የተስማማ መሰለ።

ነገሩ እንደገና ወደ ቦፈ ክርክር ሲለወጥ ትንሽ ልባቸው ቢራራ ብሎ ንዋያ የያዛቸውን ፎቶዎች እንዲያዩት ለሁሉም አሰራጨና ረጋ ባለ ድምፅ፣ "እስኪ እነዚህን ልጆች እዩዋቸው። እኔ ደግሞ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ። ለመሆኑ ከአለርት ሆስፒታል ጀርባ ባለው ቀሺ በሚባለው ሰፈር የሚኖሩትን ሰዎች ሄዶ ያየ ከዚህ መሃል አለ? እኛ ከመጣን ጀምሮ ብዙ ጊዜ ሄደናል። እንሱስ ያለኛ ማናላቸው?" ብሎ ግራና ቀኝ አያቸው።

"ቀይ ... አልገባኝም እኮ ንዋዬ ... የሰበሰባችሁን የርዳታ ድርጅት ለማቋቋም ነው ወይስ ልጅ ስለ ማሳደግ ነው። ይሄን ሁሉ ዓመት ውጪ ከርማችሁ ... አሁን ለኛ ምኑን ነው የምትሰብከን። ልጅ ለናቷ ሆንከብኝ እኮ። ማን አትርዷቸው አላችሁ? ልጅ ወስዶ ማሳደግ ግን ሌላ ጉዳይ ነው። ደግሞ እያደር ይገባችኋል ... የሰው ልጅ እንደሁ የሰው ነው። ሰንት የተቸገረ የዘመድ ልጅ በየገጠሩ ሞልቶ የለም እንዴ? ሦስት እይደለም ሠላሳ ወስዳችሁ ማሳደግ ትችላላችሁ" አሉ፣ ሌላኛው አጎቱ በቁጣ ድምፅ።

ሚትሚቱ እየተካረረ ሲሄድ አርሲማ ተነሥታ፣ "እስኪ ልጆቹንም ቤተሰቦቻቸውንም ስለሚያውቃቸው ሌላሠው ትንሽ ታሪካቸውን ይንገረን። ከዛ ደግሞ የምትሉትን እንሰማለን" ብላ፣ እንዲናገር በዓይኗ ጋብዛው ተቀመጠች።

እጁ ላይ ያለውን ፎቶ አየት አደረገና ንግግሩን በጥያቄ ጀመረ። "በሥጋ ደዌ ታሞ የታከመ አንድ የምታውቁትና ወዳጃችሁ የሆነ ሰው አለ? ምን ውስጥ እንደሚኖሩ ምን እንደሚበሉና ሲያማቸው የት እንደሚታከሙ የሚያውቅ አለ? እዛ ሰፈር ስንት ሕፃናት በቀላሉ ሊድኑ በሚችሉ ህመሞች እንደሚረግፉ ታውቃላችሁ? እነርሱ የኛ አካል አይደሉም? ከድህነትና አንዳንዶቻችሁ እንደምትሉት 'ከቱምጥናው' በስተጀርባ ያለው ከቡር የሆነ ሌላ ሰው አይታያችሁም?

"የነዚህን ልጆች እናት ያገኘኋት ድንገተኛ ከፍል ፖሊሶች ይዘዋት መጥተው አእምሮዋ ተረብሾ ታማ ነው። ረጅም ቁንጅ ወጣት ሴት። ግን ህመሙ ከጥቃም ውጪ ያደረጋት አሰፈሪና ማንም የማይፈልጋት እኛ እንደምንለው 'አብድ' ናት። በጥቂት ሳምንት ውስጥ እማኑኤል ሆስፒታል ንብታ ታክማ ደህና ሆና ነበር። ታማ በነበረችበት ጊዜ ገዳና ላይ ስትኖር በዚያ ሁኔታ ተደፍራ አርግዛ ስለነበር ያንንም መሸከም የቷ ዕዳ

@OLDBOOOKSPDF

ነበር ። ዘመድ የሌላት የአእምሮ ታማሚ ብቻ ስለሆነች በሃኪሞች ደንታ ቢስነትና ሙከኒ ባሞር ተተጨች ። አንዴ ጥቁር አንበሳ አንዴ ጻውሎስ ስትንከራተት የወለደችውን ሀጻን እንኳን ለመሳም ሳትበቃ ደሟ እንደውሃ ፈሶ በሆስፒታል ጠረጴዛ ላይ እያየኋት ሞተች" አለና ፣ የረጠቡ ዓይኖቹን ጠራረገ ። ከፍሉን ሞልቶት የነበረው ትኩስ ስሜት መርገብ ጀመረ ።

"የመጀመሪያ ልጇን የወለዱችው የቤተሰቦቿን ድኽነት ለመቅረፍ አረብ አገር ሄዳ ሰው ቤት ስትሣሰን ጌታዋ አስገድዶ ደፍሯት ነው ። ምን የመሰለች ልጅ እእምሮዋን ስታ ሀመም*ተኛ ሆና መጣች ። የም*ታዩት ትልቁ ልጅ የዛ እርግዝና ውጤት ነው ። መላጆቿ በድሃ አቅማቸው ለምነውና ማሰነው እሷን ለማስታመም ሞክረው ነበር ። ሲብሳበት አገር ጥላ እየጠፋች ሁለተኛዋን ልጅ እርግዝ ስትመጣም ተተብለው ባቅማቸው አረሷት ። በስተርጅና ሁለት ልጆቿን ማሳደግ ጀመሩ ። በዚህ መሃል እናቷ በሷ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ለወትድርና ዘምቶ እንደጠፋ በቀረ ልጃቸው ሐዘን እንደ ባዘኑ ድገት ሞቱ ። ከዛ ወዲህ መድሃኒቷን አቁማ ጨርቋን ጥላ ሙሉ ለሙሉ የጮዳና ኗሪ ሆና ቀረች" ብሎ ፣ ጸጥ ብለው የሚሰሙትን ሰዎች አየት አየት አድርጎ ንግግሩን ቀጠለ ።

"በዚህ ውስጥ ነው የም*ታዩዋት ሕፃን የተረገዘችው ። አሁን እናቲቱ ሞታለች... እያትዬውም በሕመምና በእርጅና ደቀው ለመለመን እንኳን አትም አጥተው ካልጋም አይወርዱም ። የሚኖሩበትን ቤትና የሚበሉትን ምግብ ብታዩ መፈጠራችሁን ነው የምትጠሉት ። ሕፃናቱ ሚዳ ላይ ነው የሚተኙት ። ከከተማ በሚጣል ቁሻሻ ነው ረሃባቸውን የሚያስታግሱት ። ቢታመሙ በሕክምና ሳይሆን ባምላክ ምህረት ብቻ ነው የሚተርፉት ።

"እስኪ አስቡት ... እነሱ ማለት እኛ አይደለንም? የሌላ ዓለም የሌላ ፕላኔት ሌላ ሰዎች ናቸው ማለት ነው? እኛስ ካልሆንን እነርሱን የሚረዳና የሚያግዝ ሌላ ሰው ከየት እንዲመጣ ነው የምንጠብቀው? እነርሱን ማሳደግ የፈረንጅና የጉዲፈቻ ድርጅቶች ሃላፊነት ነው ያለው ማነው? ለመሆኑ አርሲና ንዋይ ይህንን ሃሳብ ሲያካፍሉን መከራከርና ልባቸውን ማዛል ይገባናል?

"ለሁላችሁም የምጋብዛችሁ እዛ ሰፈር ሄዳችሁ አንድ ቀን ከለምቹ ጋር አብራችሁ እንድትውሉ ነው ። አሁን እዚህ የምትሉትን ያኔ መድገም የምትችሉ ከሆነ የም*ቀርቡትን ሐሳብ ለመቀበል ችግር የለብኝም ። እነርሱም ያሉት አዲሳባ እኛም ያለነው አዲሳባ ... ልብ ከተራራቀ ... አገር ቢቀርብ ምን ያደርጋል? መተዛዘን ከጠፋ ... ሰፈር እንድ ቢሆን ... ቢገራበቱና ባንድ ቋንቋ ቢያወሩ ምን ፋይዳ አለው ። ምክንያቱም ለእሷ እነሱ ሌላ ሰው ናቸው ... የማንነካቸው ፣ የማናገባቸው ፣ የማናውቃቸው ... አብረናቸው የማንበላ ...ልጆቻቸውን የማናሳድግ ..." አለና የጀመረውን ሳይጨርስ በረጅሙ ተንፍሶ ዝም አለ ። ሁሉንም ግራና ቀኝ ታኝቶ በጸጥታ ወደ ወንበሩ ሄዶ ተቀመጠ ። አርሲማ አዲስ የአምቦ ውሃ ከፍታ ብርጭቆውን ሞላችለት ።

@OLDBOOOKSPDF

ለጥቂት ጊዜ ቤቱ ረጭ ብሎ ዝም ነሰ በኋላ የንዋይ አባት ተንሰተው ሚዛናዊ የሆነ ንግግር አድርገው የልጆቻቸውን ፍላጎት እንደሚያነብሩና የሚችሉትን ሁሉ እንደሚያደርጉ ውሳኔያቸውን ገልጸው ቁሙ አሉ። የንዋይ አጎት እንደተናደዱ ወጥተው ሄዱ። የሉላሠው እናትም በነገሩ አልተደሰቱም። አርሲማና ንዋይ በጉዲፈቻ አርገዘው የወለዷቸውን ልጆች ለማሳደግ ውስጣቸው ጨክኗል። የገዛ ሽን ልጆች ከዘነጠረች አውጥቶ ከማሳደግ በላይ፣ ዘመዶቻቸውን ከገቡበት የተቸገረ አመለካከትና እምነት አውጥቶ በአዲስ አመለካከት ማሳደግ ሊከብድ እንደሚችል ተረዱ።

@OLDBOOOKSPDF

፡20፡

ሌላሠው ወደ አሜሪካ ከመመለሱ አንድ ቀን በፊት እናቱ ባዘጋጁት የእራት ግብዣ ላይ ከጠበቁት በላይ ሰው ስለመጣ ቤቱ በሰው ተጨናንቆ ነበር ያመሸው። አብዛኛው ሰው ከወጣ በኋላ የቀሩት ወደ ሶፋው እካባቢ ተሰባስበው ስለ ውጭ አገር ኑሮ ጨዋታ ተጀመረና እንዳንድ እየተባለ ገራ ከፍለው መከራከር ጀመሩ።

"እኔ ኮ አንዱ የማይገባኝ ነገር ዳያስፖራ የሚለው ቃል ልክ እንደ አንድ ማዕረግና የትልቅነት መለያ መወሰዱ ነው። ለእኔ አገሩን ጥሎ የተሰደደና የተበተነ ሕዝብ ከማለት የተለየ ትርጉም የለውም። አውሮጳና አሜሪካ መኖራቸውን ለማሳየትና ልክ እንደ አንድ ያዋቂነት መታወቂያ ካርድ መጠቀሙ ጉራ ብቻ ነው" አለ፣ ሲራክ በሞቀ ስሜት ንዋይ ያለውን በማጣጣል።

"ቃሉ ምንም ትርጉም ይኑረው ምን፣ በውጪ ያሉ ሐበሾች ሃገር ውስጥ የሌለ ነገር፣ ለሀገር ጥቅም ሊያመጡ ይችላሉ። እነርሱን ወደ ሀገራቸው ለመሳብና ተመልሰው ባላቸው ሃብትም ሆነ እውቀት ላገራቸው የሆነ ነገር እንዲያደርጉ ማበረታቱ አስፈላጊ ይመስለኛል። ወደድንም ጠላንም እዚህ ያለው ሐበሻ የሌለውና የማይችለውን ብዙ ነገር በውጭ ያለው ዳያስፖራ ሊያደርግ ይችላል ባይ ነኝ" አለ፣ አሁንም ንዋይ አቋሙን ሳይለቅ።

"ቀይ በመጀመሪያ ማነው ዳያስፖራ በሚለው እንስማማ ... ለምሳሌ ጅቡቲ ሃያ አመት የኖረ ስደተኛና ባንድ አረብ አገር በሰው ቤት ውስጥ ለብዙ አመታት ተቀጥራ የምትኖር ሴት ... እም ደግሞ ... አውሮጳ ውስጥ ምንም ሳይሰራ ከመንግስት በሚያገኘው ችሮታና ድጎማ ምናምን በስደተኛ ካምፕ የኖረ ሰው ... ደግሞ ... አሜሪካን አገር ባንድ የመኪና ማቀሚያ ጋራጅ ውስጥ መኪና ሲያስገባና ሲያስወጣ እድሜ ልኩን የኖረ አበሻ እንዳለ የታወቀ ነው። አብዛኛውን አበሻ ደግሞ የሚወክሉት እነዚህ ይመስሉኛል። እነዚህም ዳያስፖራ ናቸው አይደል?" አለች፣ ምስጢር የሲራክን ነጥብ እያጠናከረች።

"ልክ ነው ..." አለ ንዋይ፣ ወደ የት እየሄደች እንደሆነ የሀሳቧ ፍሰት በመጠኑ ስለገባው።

@OLDBOOOKSPDF

"እዚህ አገር ሠሰጥ ደግሞ በከፍተኛ ዶረሻየተማሩ ወይም ከመሬት ተንስተው ብዙ ትልት ቦታ ቦታ የደረሱ ... ደግሞም በላቸው ችሎታና አትም አገራቸውን ሲያገለግሉ የኖሩ ብዙ ሐበሾች እንዳሉ የታወቀ ነው። ማለቱ ካገር ወጥተው የማያውቁ ወይም ቢወጡም ወዲያው ተመልሰው ያለውን ችግር ሁሉ ተቋቁመው ባገራቸው የሚኖሩ... እምም ... እነዚህን 'ዳያስፖራ' ያልሆኑትን ምን እንበላቸው...?" አለች ምስጢር።

ሲራክ ጣልቃ ገብቶ፣ "የኛስፖራ ... ብንላቸውስ?" ሲል፣ ሁሉም ሳቁ።

ሳንቾ ደግሞ ቀበል አድርጎ፣ "እኔ ላሚቦራ ሲሉን ነው የሰማሁት ..." አለ። ሁሉም እያጨበጨቡ ሳቁ።

"እሺ እይ ላይክ ዛት ... ላሚቦራ ... ግን ሚስጥር ነጥብሽ አልገባኝም ..." አለ፣ ንዋይ ወደሷ ፊቱን አዙሮ።

"ነጥቤማ ... ዳያስፖራም ቢሆን ላሚቦራ ... ሁሉም ላገሩ ያስፈልጋል። ግን ደግሞ ልክ ላገር ብለው አገር ጥለው እንደሄዱና ከሌላው የተሻለ ላገር እዋቂና ያለ እነሱ በገ ፈቃድና ብጣቂ ዶላር፣ አገራቱ ውላ እንደማታድር ጉራቸውን እይቸርችሩብን ነው። የተለየ ጥቅማ ጥቅምና ማባበያ ድገማ ልክ እንደ ልዩ 'የዳያስፖራ' መብታቸው ከዚች ደሃ አገር አይጠይቁ ባይ ነኝ" ስትል፣ ሁሉም እንደገና ሳቁ።

ገዛም ብላ ስትሰማ የነበረችው አርሲማ፣ "ግን አንድ ከሃገሩ በምንም ምክንያት ለረጅም ጊዜ ተለይቶ በባእድ አገር ሲኖር ቆይቶ ለመጣ ሰው፣ ቀና አቀባበልና በቀላሉ ተጽኖም፣ ያለውን እውቀትና ጥሪት አገሩ ላይ እንዲያውል ነገሮችን ማመቻቸት ምንድነው ስሀተቱን እንዳልሽው ሁሉም ሰው ወጪ ስለኖረ ባለጸጋና የተማረ ላይሆን ይችላል። ግን ደግሞ ውጪ መኖሩ በራሱ እዚህ አገር የማታገኚው የሚያስተምርሽ ነገር አለ። ትልቁ ነገር ገንዘብና ችሎታ ብቻ ሳይሆን ሥልጣኔንና ዕድገትን የሚያመጣ ባህልና አስተሳሰብን ማስተላለፍ መቻሉ ላይ ነው። በሌላ ሀገር ኑሮ ብዙ ነገር ስለመደ ሰው፣ እዚህ መጥቶ ባለው ሲስተም ውስጥ ተመልሶ መግባቱ ራሱ በጣም የሚከብድ ይመስለኛል" አለች።

አሁንም ነገሩ ለሲራክ የተዋጠለት አይመስልም። "የኔ ችግር፣ በጅምላ ዳያስፖራ በሚል ገፆንጥላ ተመሳሳይ የሆነ ጥቃማ ጥቅምና ማቋቋሚያ ይደረግለት የሚለው ነው። የትም አገር ደግሞ እንደሱ አይደረግም። ለምሳሌ መኪና ከታክስ ነጻ ያስገቡ ተብሎ የተፈቀደ ጊዜ የምር ስንቱ ዳይስፖራ ነው በትክክል የተጠቀመበት። ለዘመዱ መኪና ያስገባውና ለነጋዴ ፈቃዱን የሸጠው አይበዛም? ደግሞስ አገሬ ተመልሻለሁ እያሉ መሬት በነፃ ወስደው ቸብችበው የተመለሱትስ? ቀይ እኔስ ብሆን ከታክስ ነጻ መኪናና መሬት አይወድልኝም እንዴ? ወይስ አገሬን ጥዬ መሄድ አለብኝ ከታክስ ነጻ ዕድል ለማግኘት? እንዲያውም ዕድሉ ባንገብጋቢ ሁኔታ የሚያስፈልገው፣ ለኛ በወር ሁለት መቶ ዶላር ለማትሞላ ደሞዝ ለሚከፈለን ነው እንጂ ማን ይመኝ ለዳያስፖራው ምን ያደርግለታል? የኛ የወር ደሞዝ እኮ ለናንተ የምላ ወጪ ናት ... ለዛውም ቲኮን ሳይጨምር ..." ሲል፣ ብዙዎቹ ሳቁ።

@ZEBOOOKSPDF

"የውልህ የታክስም ሆነ ሌላ ጥቅማጥቅም የሚሰጣቸው እኮ ለመጦሪያ ወይም እንደ ሽልማት አይደለም። ተመሳሳይ ወይም ከዛ በላይ ማበረታቻ ለሌሎች የውጪ ባለሀብቶችና ዜጎች ይሰጣል እኮ። ለምንድነው ፅድሉ ለወገናችን ሲሰጥ የሚያንገበግበን?" አለች፣ ዝም ብላ ስታዳምጥ የነበረች የአርሴማ ጓደኛ።

"ለኢንቨስተሮቹማ ይሰጣቸው ... ግን ተታወመ እሱን? ግን ዳያስፖራ ሁሉ ኢንቨስተር አይደለም ነው ነጥቡ" አለች ምስጢር።

ሃሳቡን ያልጨረሰው ሲራክ መግቢያ ተዳብ ሲጠብት ቁየና፣ "ሲላመ ትልት ችግር ደግሞ እዛ ቁጭ ብለው ስለ ዲሞክራሲ ስለ ነጻነት ምናምን የሚደሰኩሩት ነው። አብዛኛው ዳያስፖራ ሳስበው ካገር በመጣበት ዘመን ላይ ተንጠልጥሎ የሚኖር ሀልመኛ ይመስለኛል። የዳያስፖራ ካላንደር እንኳን ከአውሮጳ ካላንደር፣ ከኢትዮጵያውም ከአስር አስከ አርባ አመት ወደ ኋላ የቀረ ይመስለኛል። ብዙ ሰው በወጣበት ዘመን ላይ ሆኖ እንደቆመ ሰዓት ነው የሚኖረው። ለሁሉ ነገር መለኪያቸው ከዚህ አገር የሄዱበት ጊዜ ነው።

"እርስ በርሱ እንኳን ቁጭ ብሎ ተስማምቶ ማውራት የማይችል እዚህ ያለውን ሕዝብ...በፈጣሪ ...ሊያስተምሩን እንዴት ይችላሉ? እንዲያውም ሳስበው ዳያስፖራው ለሃገሪቱ ባጠቃላይ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ይመስለኛል። ባብዛኛው የማይሆን ተራርካሽ ባህልና አኗኗር አምጥተው እዚህ ምስኪን ሕዝብ ላይ የሚያራግፉት እንርሱ አይደሉም? ... አለበለዚያም በወጡበት ዘመን የነበረውን የፖለቲካ አውማቸውን ሊያራግቡ ነው የሚገቡት።

"እነሱ ያልባረኩትና ያላጸደቁት ነገር ሁሉ አገር የሚያጠፋ ያልተማሩ ሰዎች ጨዋታነው የሚመስላቸው። ከዚህ ሄደው ለሀገር ልማትና ለሕዝብ ብልጽግና ሌት ከቀን ሲማስኑ እንደኖሩ ሲመጻደቁ አያፍሩም። አገር ከወደዱ መጥተው እንጻገራው ይኑሩ። መጀመሪያ ምን ጥሩ ነገር ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ሞርተው ያሳዩን። እንጂ ኪሳቸውን ተበድረው ባመጡት ጥቂት ሽህ ዶላር አሳብጠው፣ ሳንድ ወር የትም በየቡና ቤቱ ሲዘሩ ቀይተው ... ገንዘባቸው ሲያልቅባቸው ... እዚህ አገር ቢሮክራሲው ... ዲሞክራሲው ... ቅብጥርሲው ምንትሲው ... መንግሥት አያሰራም ... ሕዝቡ ቢነግሩት አይገባውም ...ምናምን እያሉ አይደሰኩሩ። ለእኔ አብዛኛው ዳያስፖራ ጎጂ ዜጋ ስለሆነ ማበረታቻ ሳይሆን ከፍ ያለ ታክስ ሊጣልበት ነው የሚገባው።"

የሲራክ ንግግር ከማሳቅ ይልቅ ያናደዳት አርሴማ ብስጭቷን ዋጥ አድርጋ፣ "የውልህ ሲራክ የምትለው የተወሰነ እውነት ሊኖረው ይችላል። በነገራቸን ላይ ሳይህ ስዳያስፖራው የከረረ ጥላቻና መራራ ስሜት ያለህ ይመስላል። ዳያስፖራ ማለት እኮ ሌላ ሰው አይደለም ... እዚህ ከተሰበሰብነው ግማሽ ቻችን ማለት ነው። ልክ አገራቱን ለመውረር የተዘጋጁ ሽብርተኞች አስመሰልካቸው" ስትል፣ ሀሉም ሳቁ።

ንግግሯንበመቀጠል፣ "ለምሳሌአንደአሰራኤልሀንድና ቻይና ያሉትንሌሎቹንም ሃገሮች ብታያቸው ለእድገታቸውና ለህልውናቸው የዳያስፖራው አስተዋጽኦ የጀርባ አጥንት እንደሆነ የታወቀ ነው። [illegible] አልተባለም። ግን ደግሞ

አስኪ ትንሽ ወጣ ብለህ ለማሰብ ሞክር እንጂ ... ስንት ዳያስፖራ ነው ብዙ መስዋዕትነት እየከፈለ በራሱ ገንዘብ ስንት ነገር ለሃገሩ የሚያደርገው ። ዳያስፖራውን ለምን ጥቅም ፈላጊ ጉረኛና ከእውነታው የራቀ ብቻ አድርገህ ታስባለህ ። የፈለከውን ብትል እዚህ አገር የሌሉ ብዙ ችሎታዎችና ቴክኖሎጂዎች ከማንም በላይ ዳያስፖራው ነው ሊያመጣ የሚችለው ።

"እያልኩ ያለሁት የተለየ ጥቅም ሳይሆን ቢያንስ ለሌላ አገር ዜጎች የሚሰጡ መብቶችና ማበረታቻዎች፣ ጠቃሚ ሥራ ሊሠሩ ለሚችሉ ከወጭ ለሚመጡ ሐበሾች ቢደረግስ ነው ። ለምሳሌ አንድ ፎርመናዊ ወይም ጃፓናዊ ኢክስፐርት ላገኙ ሥራ ሲመጣ የሚከፈለውን ደሞዝ ያክል፣ በዚያው ወይም በተሻለ ደረጃ ሥራውን ሊሠራ የሚችል ሐበሻ ከወጭ መጥቶ ሲከፈለው ለምን እንናደዳለን? አረብ ሃገር ብትሄድ የሚጠቅማቸው አስክሆነ ድረስ፣ ለሌላ ሃገር ዜጋ የሚሰጡት ማበረታቻና ጥቅማ ጥቅም ምን ያህል እንደሆነ ታውቃለህ? አሁን ናዊ ወይም ሌላ እዛ ቢሄዱ አሜሪካን አገር የተማሩ ዶክተሮች ስለሆኑ ብቻ ምን ያህል እንደሚከፍሏቸውና ምን ያህል ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅም እንደሚያገኙ ብነግርህ አታምንም? አገሬ ስለመጣሁ ግን ለምን እንደ ጠላትና ጉረኛ እታያለሁ? ነው የኔ ጥያቄ" አሉች ።

ሲራክ፣ ያነሳችው ነጥብ እውነትነቱ ቢታየውም ሃሳቡን ዞር በማድረግ፣ "እሺ ታዲያ ዳያስፖራ የሚለውን ማዕረግ መያዝ ያለበት ማነው? ወይስ ነገሩ ማእረግ ሳይሆን በቃ ውጪ ተሰደው ሰኖሩ ወገኖቻችን የመለያ ስም ብቻ ይሁን ነው? ይሄ ከሁሉም በፊት መመለስ አለበት ። አሁን እርሷማ ባነሳሽው ሃሳብ በተወሰነ መጠን እስማማለሁ ... ግን " አለና፣ ሌሎቹም እንዲያወሩ ይመስል ሁሉንም ዞር ዞር ብሎ እያየ ።

ሉላሠው ገዘም ብሎ ሲያጸምጥ ቀየና፣ "እኔ ... በመጀመሪያ ደረጃ ዳያስፖራ የሚለው ስም ማዕረግ ስለመሆኑ የማውቀው ነገር የለም ። ሰዎችን በችሎታቸውና ላገር ሊያበረክቱ በሚችሉት አስተዋጽኦ መጠን ማበረታት መሰረታዊ የእድገት ህግ ይመስለኛል ። ብዙ ሰው ካገር የወጣው አገሩን ጠልቶ ሳይሆን የተሻለ ዕድል ፍለጋ ወይም በተለያዩ ችግሮች ተማሮና ህይወቱን ለማዳንም ሊሆን ይችላል ። ደግሞ እዚህ የቀረውም ሃበሻ እኮ ውጪ ያልሄደው ያገሩ ፍቅር አንገብግቦት ወይም ዕድሉን አግኝቶ እምዬ አገሬን ለማን ጥዬ ... እምቢ ላገሬ... አልፈልግም ብሎ አይመስለኝም ፣ የትም እንሁን የትም ሀገሪቱ የሁላችንም ናት ። እኛና እነሱ ከመባባል ይልቅ 'ለድሃው ሕዝባችንና ለምስኪኗ አገራችን ምን ብናደርግ ነው የሚጠቅመው?' ብሎ፣ መጠየቁ ይሻላል ።

"ዳያስፖራውም ሆነ ሳንቾ እንዳለው ላሚበራው ..." ብሎ ሳት አለና፣ "ግልፅ ያለበት ለሌላው የሚደረገው ነገር ዞሮ ዞሮ የሚጠቅመው ሁላችንንም ነው ። ብዙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ በውጭ ያሉ ያገራችንን ልጆች የተከፈለው ዋጋ ቢከፈለም እንዲመጡ ማባበሉ ሠዉረኛ ላይ ማንን ነው የሚጠቅመው? በርግጥ የጅምላ ማበረታቻ በምንም መልኩ ቢሆን አሞበርባሪውን እንጂ ትክክለኛውን ሰው አይጠቅምም ። እዚህ ላለው ፕሮፌሽናልና አዳጊ የቢዝነስ ማኅበረሰብም የተቻለውንና አስፈላጊውን ማበረታቻና ጥቅማጥቅም መስጠቱ ጥሩ ነገር ነው ። ስዳያስፖራው

@OLDBOOOKSPDF

የተፈቀዱ ጥቅማ ጥቅሞች ሲከለከሉ የሚደሰት ያገር ቤት ፎረ ግን ምቀኝነት እንጂ ላገር መቆርቆር ነው ብዬ አላምንም ።"

"እንደሱማ አትበል ዶክተር ሌላ ... ሁሉም ዳያስፖራ እንዳንተ ቢሆን እኮ ምንም ቢደረግላቸው ማንም የሚከፋው አይመስለኝም ። የትም ሀገር ሄዶ መኖር ቢችልም ፣ ሀገሩን ስለሚወድ ብቻ እዚህ የሚኖር ብዙ ሰው በደንብ አለ ። ባብዛኛው ዳያስፖራ በስደት እዚህ ካለው የተለየ ለሀገር ሊያደርግ የሚችለው ነገር ስለሌለ ከፈለገ እንደኛው መጥተው ይኑሩ ። ያልሆኑትን ነገር አይሁኑብን ነው ሀሳቡ" አለች ፣ ምስጢር ሌላሠው ባለው የተወሰነ ሐሳብ ስላልተስማማች ።

"ዳያስፖራው ነው አገርና ባህል ያጠፋው የሚለው ብዙም አያስኪደንም ። የተወሰነ ሃላፊነት መውሰዱ ተገቢ ቢሆንም ግን አሁን በኢንተርኔትና በሶሻል ሚድያ ዘመን ለመበላሸት የትም መሄድ አያስፈልግም ። እኛን የማይመስለው ሌላ ሰው ሁሉ ችግርና የማይረባ ጥቅም ፈላጊ ነው ብለን ጣት ከምንጠቋቀም አብረን ሃላፊነትን ብንወስድ ብዙ ማድረግ የምንችል ይመስለኛል ። መረዳት ያለብን ዳያስፖራ የምንለው የሌላ ዓለም ፍጡር አይደለም ። ስለ ሌላ ሰው አይደለም የምናወራው ። የኛው እህቶችና ወንድሞች ናቸው ። ለምሳሌ እኔ ... ንዋይ ወይም አርሴማን ማለት ነው ። ምናልባትም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ደግሞ እናንተም ልትሆኑ ትችላላችሁ" ብሎ የጀመረውን ሀሳብ ሲቋጭ ሌላ ክርክር ተቀሰቀሰ ። ለሚቀጥሉት ሃያ ደቂቃዎች ቢከራከሩም ወደ አንድ ድምዳሜ ሊደርሱ አልቻሉም ። ጊዜው መሽቶ ስለ ነበር እንርሱም ወደ የማደሪያቸው 'መቦታቸን' ነበረባቸው ።

'መቦተን መሰብሰብ ... መሄድ መምጣት ... መዋደድ መጣላት ... መነሳት መተኛት ... ከወልደት እስከ ሞት ... ይሄው ነው የሰው ሕይወት ።' ሲራክ በዚህ ሀሳብ ውስጥ እየተናጠ ፣ ግልጥ መኪናውን እያስንራ ወደ ቤቱ ነጐደ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 21 ፡

ሲራክ ነገሮች እየተላኩለትና እንዳሰበው እየሄዱት ስለሆነ ሰሞኑን ባየር ላይ ነው፡ የከረመው። የአእምሮ ሕክምና ጥናቱን ከጨረሰ ጥቂት ወራት ቢሆነውም ወደ ገንደር አልተመለሰም። ቢያንስ ለሁለት ዓመት አብሮት ሊሠራ ከተስማማ፣ ለመንግሥት መክፈል ካለበት ዕዳ ግማሹን ከሊኒኩ እንደሚከፍልለት ሌላው ቃል ገብቶለታል። አዲስ አበባ በመቅረቱ የተደሰተው ታላቅ ወንድሙ፣ መ፡ሉ ዕዳውን እኔ እከፍልልሃለሁ ስላለው፣ የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቷል።

ትምህርቱን ከጨረሰም በኋላ ከሲስተር ዘቢባና ከባሏ ጋር አልፎ አልፎ ይገናኛሉ። ዛሬም ከርሷ ጋር ቀጠሮ ስላለው ወደ ጳው፡ሎስ እያመራ ነው። ቀኑ ከወትሮው የበለጠ ፀሐያማና ሞቃት ሆኖ ነው የዋለው። ሲስተር ዘቢባ ሥራዋን ጨርሳ ከሌሎቹ የክሊኒክ ሠራተኞች ጋር እያወራች ስትጠብቀው ደረሰ። ሁሉንም ሰላም ብሎ ከሆስፒታሉ ውጪ ወዳለችው ካፌ ጌዱና በረንዳው ላይ ተቀምጠው ቡና አዘዙ። መ፡ቀቱን መቋቋም ሰላልቻለ ጃኬቱን አወለቀ።

"ው፡ይ ... አንተ ልጅ ከሳህ ልበል? ምንድነው፡ አሁን ደግሞ ትምህርቱ አልጻል ወይስ መብላት ተው፡ክ?" ብላ፣ ክንዱን በጆቿ እንደ መለካት ያዘች።

"ምን ባክሽ ... ሐሳብ ማለቂያ አለው፡ ብለሽ ነው ሲስተርዬ ... አሁን ደግሞ ቀጥሎ የት ነው፡ የሚኬደው ምናምን ... እያልን ስንተክዝ ... ሰው፡ነታችንም አለቀ" ብሎ፣ እሱም የጆቱን ጡንቻዎች እያሻሸ ፈገግ አለ።

"አይ ግዴለህም ... እኔ እው፡ቃለሁ መድሃኒቱን ... አሁን ጥሩ ሚስት ነው የሚያስፈልግህ። ከዚህ ወዲያ ምን ቀረህ? ... ደግሞ አንተን የመሰለ ዘንካታ ሽበላ ... ባይሆን መም፡ረጡ እንዳያስቸግርህ እንጂ" አለች፣ ፊቱን እያጠናችና እየሳቀች።

"አዪ ነው፡ ብለሽ ነው ሲስተርዬ ... ወይ ቤ፡ቱ አልቀሞል ... ወይ ደግሞ ወንዶቹ ሞራል አጥተናል ... እኔም እኮ አንዳንዴ ብቸኝነቱ እንዴት ነው፡ መሰለሽ የሚያስጠላኝ

@OLDBOOOKSPDF

... ግን እስኪ ለጊዜው ... ዝንጅሮዋ እንዳለችው መጀመሪያ መቀመጫዬን ነው" ብሎ፣ በቀረበለት ጥቁር ቡና ውስጥ የሞጂረውን ሦስት ማንኪያ ስኳር አማሰለ።

ከኪሱ ውስጥ ተንሸራቶ የወደቀውን መጽሐፍ አንሥታ ጠረጴዛ ላይ እያስቀመጠች፣ "ደግሞ ቀንና ሲሊት ማንበቡንም ቀነስ አድርግ። ሕይወት እኮ መጽሐፍ ብቻ አይደለም ዶክተር። ሁሌ ንባብ ምንድነው። አሁን ቀንጅዬ ልጅ ጭንህ ሽጥጠህ ማየት ነው ጸሎቴ" አለች፣ መጽሐፉን አንስታ ወደ ጭኗ ሽጦጥ አድርጋ እያሳየችው። "እንዲያው እስኪ መች በለኝ ዶክተር አሁን በቁም ነገር የምታስባት ልጅ የለችም?" አለች፣ በየጊዜው ሲራከን እያሉ ሆስፒታል ይመጡ የነበሩትን ቀነጻጅት እያሰበች።

"ምንም ሲስተርዬ ... ያው እኮ እንዳንዴ ብዙ ሰው ሲቀርብሽ ራሱ ችግር ነው። እኔ የምወደው ዓይነት ሴት አላገኘሁም። አለ አይደል ...ምን ልበልሽ? አንዷን ባንድ ነገሯ ስትወጂያት፣ ሌላዋ በሌላ ነገር ትበልጥብሻለች። ዞሮ ዞሮ ሁሉም ላይ የሆነ ነገር ፈልገሽ ስታጪባቸው ... እርግፍ አድርገሽ ትተይዋለሽ ... ደግሞ ቀይተሽ እንደገና ወደ ገበያው ትመለሺያለሽ ..." ብሎ፣ ዓይኑ ላይ ያለችውን ቀጭን ፍሬም አልባ መነጽሩን አስተካከለ። በሰልካካ ጠይም ፊቱ ላይ ችምችም ያለ ጸጉሩ፣ ከእይታ መነጽሩ ጋር የበለጠ ጥልቅ አሳቢ ያስመስሉታል።

"እይ ዶክተርዬ ... አላህ ሁሉንም ጎዶሎና የሌላውን ጉድለት መሙያ አድርጎ ነው የፈጠረው። ሁሉን ያሟላች ስትፈልግ ጊዜው ሞልጥ እንዳይል ..." አለች፣ ሃሳቧን መጪረስ እንዳልፈለገች።

"መራሞ ይወድቃል ከምራሞ እንደሚሉት እንዳልሆን ፈራሽልኝ ..."

"ሆሆ አንተ ተረቱን ማነው ያስተማረህ ልጄ? አንተን የመሰለ ልጅ ምን በውጣህ፣ ከምራሞማ አትወድቅም። ደግሞ ለወንድ ልጅ በሀገራችን ዐሐዩዋም ቀስ ብላ ነው የምትጠልቀው፣ እንኳን ዶክተር ሆነህ። ግን ደግሞ ሁሉም ነገር በልጅነት ነው የሚያምረው ብዬ ነው። ግን እንዲያው ..." ብላ፣ ያሰበችውን ሳትናገር ተወችው።

ፈገግ ብሎ ዓይን ዓይኗን እያየ፣ "ግን ምን ሲስተር ..." አለ፣ እሱም በልቡ ያለውን ያወቀችበት እየመሰለው።

"እይ ተወው ... የኔው ሃሳብ ሊሆን ይችላል" አለች፣ የጠጣችበትን የቡና ስኒ ቀስ አድርጋ በማስቀመጫው ላይ እያሽከረከረች።

"ምናለ ንገሪኝ ... ያንቺን ሃሳብ እኮ በጣም ነው መስማት የምፈልገው ..." አለ፣ የበለጠ ፍላጎቱ እየናረና ምን እንዳሰበች እየጠረጠረ።

"እይ ዝም ብዬ ሳይህ ከሚስጥር ጋር ትንሽ ልብህ ..." ብላ፣ ስትሥቅ እርሱም ከት ብሎ ሣቀ።

"ያን ያህል ሲስተር ... ምን ... የወደድኳት እመስላለሁ? ... አንቺ ብቻ ነሽ ወይስ ሰዉ ሁሉ ነው የሚያወራው?" ብሎ፣ ሐሳብ ገባው።

@OLDBOOOKSPDF

"ያው ፍትርና ሳልን መደበት አይቻልም ይባል የለ ... ደግሞ ምን ጨነቅህ ማንስ ቢያወራ" አለች፣ አምልጦ የወጣ ጸጉሯን ወደ ሻሿ እየመለሰችና ፊቱን እያጠናች።

"በርግጥ ደስ ትለኛለች ... ግን ደግሞ በጣም ውስብስብና ጉረኛ ነገር ትመስለኛለች። ከሳንቶ ጋር ብዙ ጊዜ አብረው ስለሚሆኑ አውን አውን ነገሩንም ትቹዋለሁ። ደጋግሚ ለሻይ ቡና እንድንገናኝ ብጠይቃትም፣ የሆነ ያልሆነ ሰበብ እየፈጠረች እንደማትችል ስለነገረችኝ ... አለ አይደል ..."

"አይ ... ከሳንችዬ ጋር እንኳ ምንም ያላቸው አይመስለኝም። እሱ እኮ የሁሉ ወዳጅ የሞሀ ነው። ጨዋታ ብቻ ነው እሱ። ከሱ ጋር ከሆንክ እኮ አፍህን መግጠም የለም። ደግሞ በዛው ልክ በጣም ቁም ነገረኛና ደግ ልጅ ነው። እንደ መስለኝ ዶክተር ሌላሠው የሰጣቸው ስራ ነው ያቀራረባቸው እንጂ፣ እመነኝ ምንም ነገር በመካከላቸው የለም ስትለው፣ ትንሽ ተስፋው እንሰራራ።

"አይ ሲስተር ... የሞሆች ናቸው እኮ አገሩን የጨረሱት ..."

"ይልቅስ አንድ ልጅ ያለ ይመስለኛል ... በጣም አስቸጋሪ ቢጤ ነው፣ ከትምህርት ቤት ጀምሮ እየደወለ በታ አበሳዋን ነው የሚያሳያት። አውንም ይከታተላታል መሰለኝ። እናቷ ደግሞ አግብታላቸው ከዚህ ሁሉ ጭንቅ መገላገል እንደሚፈልጉ ነግረውኛል። ያለቻቸው አንድ ልጅ እሷ ብቻ ስለሆነች አያት መሆንም ሳይጓጉ ይቀራሉ ብለህ ነው። ብዙ ጊዜ ስላንተ እያደነቁና እያመሰግኑ ነገረውኛል። እስኪ አስበው ማን ያውቃል የፈጣሪን ሥራ" አለች፣ መራት የነካውን የኸኬቱን ሜዳ እየሰበሰበችለት።

የተዳከመ ተስፋውን ቀሰቀሰችበት። "እስኪ እንግዲህ እናያለን ሲስተርዬ። ከሊኒኩም ሲጀመር አብረን መሥራታችን አይቀርም። ኧረ ዋናውን ነገር ሳልነግርሽ ... በጣም ደስ የሚል ዜና። ወንድሜን አናግረዋለሁ ብዬሽ አልነበረም? እርሱም እዚህ አዲሳባ መቅረቴን በጣም ወዶታል። እና ለገንደር ዩኒቨርስቲ የሚከፈለውን ሙሉውን ገንዘብ እንደሚከፍልልኝ ነገረኝ። ስለዚህ ዶክተር ሌላሠው ቃል በገባልኝ ገንዘብ አክሲዮን ልገዛበት ነው ያሰብኩት" ሲል፣ ሁለት እጆቿን ወደ እርሱ ዘርግታ፣

"ውይ ዶክተር ሲራክዬ ... እንኳን ደስ ያለህ። በጣም ደስ ይላል። ምናለች በለኝ ሌላውንም ነገር እንደዚሁ አላህ ስክትክት ነው የሚያደርግልህ" ብላ አቀፈችው፣ የምር ደስታዋ እየፈነቱላት። ብዙ የክሊኒኩ ነርሶችና ሐኪሞች ጉረኛና ራስ ወዳድነው ብለው ስለሚያስቡ አይወዱትም። ሲስተር ዘቢባ ግን ጉብዝናውንና ስለ ራሱ ያለውን ከፍተኛ አመለካከት እንደ ትልቅነት ስለምትቀጥረው የምሯን ትወደዋለች ... ሽንቧን ይዛ ትሟገትለታለች።

"እንቺስ ምን እያሰብሽ ነው?"

"እኔማ ምን አስባለሁ ... በታ ከዚህ ቤት ለመሰናበት አንድ ወር ናት የቀረችኝ፣ ከዛማ ጡረታዬን አስከብራ፣ ከናንተ ጋር ሽር ነጥ። እየታደሰ ያለውን ክሊኒኩን አይተኸው የለ? እንዴት እንደሚያምር ... ሌላ ሃገር ያለህ እኮ ነው የሚመስለው፣ በታ ምነው እንደናንተ በልጅ ቢሆን ኖሮ ..." ደክተር ሌላሠው የክሊኒኩ

ETHIOPIANBOOKSPDF

አስተዳዳሪና ሃላፊ ነርስ እንድሆን ነው ዕቅዱ። ከሲራጅ ጋር ተነጋግረን ከተቻለ አንድ አስር ፐርሰንት አዝሲዮንም ለመግዛት አስበናል።"

"ሚስጥርስ ... አዝሲዮን ለመግዛት አላሰበችም? አርባ ፐርሰንት አካባቢ ነው አይደል ለአዝሲዮን ሽያጭ ሲያቀርብ ያሰበው ዶክተር?" አለ፣ በውስጡ የራሱ አክስዮን በንቱ እጅ እንደሚሆን እያሰላ።

"ምናውቁ ልጄ ... ምን ቦታውስ የሷ አይደል ... ከፈለገች በገንዘብም ለመግዛት ዕቅዱ ያላቸው ይመስለኛል። እንደ ነገረኝ ስራው ካለሁ በኋላ የክሊኒኩ ሙሉ ዋጋ ሲታወቅ ነው ያክስዮኑን መጠን ለመወሰን ያሰበው። እኛ ለመግዛት ከፈለግንና ከቻልን እስከ ሃምሳ ፐርሰንትም ብንወስድ ደስ እንደሚለው ነው የነገረኝ። ምን አይነት ጥሩ ሰው ነው እንዲያው?"

"እንደሱ አይነት ጮበዝና ደግ ሰዎች ብዙ የሉም" አለ፣ ሰዓቱን እያየ። ሌሎች ነገሮችን እያነሡና እየጣሉ ሲያወሩ ከቀዩ በኋላ፣ እርሷን እባሷ ቢሮ አድርሷት በቀጥታ ወደ ወንድሙ ቤት ሄደ።

ወንድሙና ባለቤቱ ከታይላንድ ገና መግባታቸው ስለነበረ ቡና ተፈልቶ ቤቱ ደመቅመቅ ብሎ ደረሰ። ሌሎች እንግዶችም ስለ ነበሩ ሲራክ ተሞው ቋቸው ወደ ጓዳ ልጆቹ ጋ ገባ። እንግዶቹ ሲወጡ ተመልሶ ወደ ሳሎን መጣ። ታይላንድ ሰላዩዋቸው ነገሮች እየነገሩት ቀዩና ያመጡለትን ስጦታ የወንድሙ ሚስት ሰጠችው። ከረባቶች ነበሩ። የከረባት ፍቅሩ ልክ የለውም።

በመሃል ሁለቱ የወንድሙ ልጆች ተጣልተው እየተላቀሱ ወዳ አባታቸው መጡ። ለመዳኘት ብሎ መጀመሪያ ትልቋን ልጁን የተጣሉበትን ምክንያት ጠየቃት። "ቸኮሌታችን አሲይዘን ማዘር ቴሬዛ የምን ሃገር ተወላጅ ናቸው ብለን እሱ የጣሊያን ሲል እኔ ደግሞ ያልባኒያ አልኩኝ። ከዛ ሲሸነፍ እፍርታም ሆኖ ቸኮሌቱን ሊመስድ ሲታገለኝ ወደቀ ... ከዛ እያለቀሰ መጣ"

"እሺ አንተስ ምንድነው የሆናችሁት?"

"ዝም በላት ውሸታን ነው" ብሎ እምባው እየቀደመ ማውራት አቃተው።

"ወንድ እይደለህም? ምን ያስነፈርቅሃል? እኮ ለምንድነው የተጣላችሁት?" አለ አባቱ ቀጣ ብሎ።

"አላቅላችሁም ሁላችሁም ለሷ ነው የምታገዙት..." ብሎ፣ እየተንሰቀሰቀ ፊቱን አዙሮ ሄደ።

"ና ነው እኮ የምልህ ... ምን ይሄ ... የገረድ ልጅ ይመስል ..." ብሎ፣ ተናዶ ሲነሳ፣ ባለቤቱ ይዛ አስቀመጠችው። ወደ ሴት ልጁ ዞር ብሎ፣ "በቃ ሂጂ አንቺም ... ወደዛ ስዉው ቸኮሌቱን ... እኔ ላንቺ ሌላ አስጥሻለሁ" ሲል፣ ባሸናፊነት እየዘለለች ሮጣ ወጣች። ልጆቹ ሲወጡ የወንድሙ ባለቤት ልጆቹን ለመዳኘት ተከትላቸው ስትሄድ ከፍሉ ፀጥታ ወረሰው። ወንድሙም ሳሎኑን ተዘዋወረ ጣራ ጣራውን እያየ

@OLDBOOKSPDF

በረጅሙ ሲተነፍስ ቀየና "ምን ኩታራ ሁሉ ... ስው ይነጅሳሉ ..." አለ ። የቲሲቪሽኑን ጣቢያ መቀያየሩን ቀጠለ ።

ውስጡ ስም ሲሰጠው ባልቻለ ስሜት የተወጣጠረው ሲራክ አቀርቅሮ ቀየ። ቀና ብሎ ወንድሙን ሲያየው ንዴቱ ብልጭ አለበት ። ወደ መታጠቢያ ሄዶ ራሱን ለማረጋጋት ሞከረ ። ፊቱን በቀዝቃዛ ውኃ ታጥቦ ተመለሰ ። ድንገት ብድግ ብሎ፣ "ይሀና እዶሩ ... ቀጠሮ አለኝ እኔ" ሲል ፣

"አሁን ቲማቲም ይሰራልኝ አላልከም እንዴ ... ምን ያንቀገፍቅሽሃል?" አለው፣ አሁንም ንዴቱ ያልበረደው ወንድሙ ።

የወንድሙ ሚስት ተመልሳ መጥታ ፣ "ውይ ሲራክዬ ቁጭ በል እንጂ ፣ ደርሷል እኮ ... እምስት ደቂቃም አይቆይም?" አለች ።

መልስ ሳይሰጣት እንደቀመ ወደ ወንድሙ በቁጣ እያየ ነበር ። "ቀይ ግን እስኪ ልጠይቅህ ጋሼ ... የገረድ ልጅ ምን ዓይነት ነው?"

"ምን ማለት ፈልገህ ነው? ... ምን ይመስላል እንድልህ ነው?" በልጁ እንደ ተናደደ ስለነበረ ለጥያቄው ትኩረትም አልሰጠውም ።

"ማለቴ ... ባቢን ስትቀጣው እንደ ሰማሁት ከሆነ የገረድ ልጅ ምን ዓይነት እንደ ሆነ የም ታውቅ ትመስላለህ ... የገረድ ልጅ ምን እንደሚመስል ማወቅ ፈልጌ ነው" አለ አሁንም ፣ ውስጡ የሚንተከተከው ስሜት ልውጣ ልውጣ እያለ ።

"በፈጣሪ ይሁንብህ ሲራክ ፣ እኔ አሁን ካንተ ጋር ለመፈላሰፍ አልችልም ... በጣም ደክሞኛል ። በቃ የገረድ ልጅ የገረድ ልጅ ነዋ ... ምን አዲስ ነገር አለ?" አለ፣ እግሩን አነባብሮ ትከሻውን ከፍ ዝቅ አድርጎ ።

"ስለዚህ ላንተ የገረድ ልጅ ማለት ስድብ ብቻ ነው?"

"እቦ አትጨቅጭቀኝ ሲራክ ... ደክሞኛል ነው እኮ የምልህ" ብሎ፣ ዓይናቹን ጨፈኖ በጀርባው ተንጋሎ ተቀመጠ ።

"ቀይ ... እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ... ሌሎች እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ሁሉ ችግረኞች ናቸው ... እናታችንም ሜምር ... ለነርሱ አንዲት ሰጥተኸቸው አታውቅም ። ለምንድነው ለኔ ይህንን ሁሉ ነገር የምታደርግልኝ? መኪና ገዝተህ ሰጠኸኝ ... አፓርትመንት ተከራየህልኝ ...እ..."

"ችግር የለም ... ካልፈለግህ ሊቀር ይችላል ። አንድ የተማርክና ያባታችንና የቤተሰባችንን ስም ለማስጠራት የቻልክ አንተ ስለ መሰልከኝ ነው ። ካሁን በኋላ ራስህን ችለሃል ... እንደ ፈለግህ መሆን ትችላለህ ። ካልፈለከው ደግሞ የሰጠሁህንም መመለስ ትችላለህ" ብሎ ፣ የቲሲቪሽኑን መቀጣጠሪያ አሽቀንጥሮት ተነሳ ። በእጠጅ አልፎ ትከሻ ለትከሻ ተነካክ

@OLDBOOOKSPDF

"እንጂ ይህን ሁሉ ያደረክልኝ የገረድ ልጅ ስለሆንኩ አይደለም ነው የምትለኝ?" ሲል ወንድሙ ባለበት ቀጥ ብሎ ቀመና ከባለቤቱ ጋር ተያዩ። "ጣጣም ጥሩ ነው... ጥሩ ነው ... ግን ሁሉንም ነገር አውቃለሁኝ። ከነገ ዛሬ ራስህ ታነሣዋለህ ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር። የሃይ ስኩል ተማሪ ሆነህ የቤት ለራተኛችሁን አስረግዘህ፣ ሳልፈለግ የተወለድኩ የገረድ ልጅ መሆኔን፣ ዛሬ ላይሆን ገና በልጅነቴ ነው ያወቅሁት። አባታችን ከሞተ በኋላ ... ያቺ ክፉ የእንጀራ አያቴ ልበላት እንጂ፣ እሷ እናቴ ልትሆን አትችልም ... ያላየችኝን ስቃይ ሳስበው እናቴ ባለ መሆኗ ደስ ይለኛል።

"ለማንኛውም አባቴ መሆንህን እንድ ቀን ወኔ አግኝተህ ትነግረኛለህ ብዬ ተስፋ አደርግ ነበር። ይህንን ያህል የሚያሳፍርህ ከሆነ ግን ... ቢቀር ይሻላል። ካሁን በኋላ ምንም ለውጥ የለውም። ምናልባት እንዳልከው 'የገረድ ልጅ ያው የገረድ ልጅ ነው' ብለህ አስበህ ይሆናል። ለማንኛውም ይህና ሁኑ ..." አለና፣ ሊያመልጠው የሚተናነቀው እምባ ሳይዘረገፍ እንደምንም ተቆጣጥሮ ... ተንደርድሮ ወጣ። ወንድሙ በድንጋጤ ድርቅ እንዳለ በቀመበት ቀረ። ባለቤቱ ተከትላው ወጣች። ደጋግማ ስትጠራው፣ ሩቱንም ማዞር አልፈለገም።

"እትዬ ፐሊስ አሁን መሄድ አለብኝ ... ለብቻዬ መሆን ነው የምፈልገው" ብቻ ብሏት፣ እየተጣደፈ ከግቢው ወጣ። መኪና ውስጥ ሊገባ እምባው ጠፍቶ በንዴት ተንጨረጨረ። "የገረድ ልጅ ... ሲራክ ... የገረድ ልጅ ..." ብሎ በረጅሙ ሳቀ። ውስጡ ግን ማልቀስ ነው የፈለገው። "የገረድ ልጅ ምን እንደሆነና ምን ማድረግ እንደሚችል እናያለን ... ብቻ ዕድሜ ይስጠን" አለ፣ ጮክ ብሎ። የሙዚቃውን ድምፅ ያለ ልክ ለቀቀው። መስኮቶቹን እስከመጨረሻ ከፋፈታቸው። ቀዝቃዛውን ንፋስ በግራ እጁ እየቀዘፈ ካካባቢው በፍጥነት ተሹለክልኮ ወጣ። ወደ ዋናው መንገዱ ሲገባ ተዘጋግቶ ስለነበር፣ ብዙ ደቂቃ መቆም ነበረበት። ሰዓቱን ሲያይ ከውዳሴ ጋር ያለው ቀጠሮ እንደሚረፍድ አሰበ።

"የገረድ ልጅ ቢያረፍድ በሰዓት ቢደርስ ... ምን ለውጥ አለው?" ብሎ ወደኋላ ለጠጥ ብሎ ተቀመጠ። ከሚሰማው የሙዚቃ ዜማ ጋራ እየተወዛወዘ

"የገረድ ልጅ ... የገረድ ልጅ ... ሃሃሃ ... ኡህ

የማይጠብቅ ከማንም እጅ ...ሁሁሁሁ ... አህ

ሲራክዬ የተመቸው እሃሃሃ

ቢረፍድ ባይረፍድ ምን ጨነቀው ... ሆሆሆሆ

የገረድ ልጅ ቀብራራ ነው ..." ራሱ በደረሰው ግጥምና ዜማ ባልተገራ ድምፁ ሊያንገራገር ሞከረ። ቀጠሮው ቦታ ሲደርስ ውዳሴ አኩርፋ ጣበቀችው።

@OLDBOOOKSPDF

"ሂይ ቀንጂት ... በጣም ሶሪ ... መንገድ ተዘጋግቶ... ካትም በላይ ሆኖብኝ ነው" አለ፣ ከንገት በላይ በሚመስል ግድየለሽ ድምፅ ።

"ላንተ ብቻ ነው መንገዱ የሚዘጋጋው ... ቢያንስ ስልክ አትደውልም ታዲያ? ደግሞ ስልክህንስ ብታነሳ ... በጣም ታሳዝናለህ" አለች፣ ሊስማት ሲል ፊቷን እያዞረችበት ።

"ነገርኩሽ እኮ መንገዱ ተዘጋግቶ ነው ። ምን የገረድ ልጅ ይመስል ..." ሲላት፣

"ምናልክ ... ማነው የገረድ ልጅ እንተ? ተሳደብልኛ ደግሞ ባንተው ብሶ ..." ብላ፣ ነብር ሆነች ።

"ምን ... የገረድ ልጅ መሆን ነውር ነው እንዴ...?" አላት ። 'እንቺ ተባልኩ ብለሽ ነው ግስላ የምትሆኚው ... እኛ የሆነው ምን እንበል ታዲያ' ብሎ አስበና የለበጣ ሳቁን በረጅሙ ሳቀ ።

"ምን የሚያስቅ ነገር ተገኘ ... ቀይ ግን ትንሽ ያበሳኸው አልመሰለህም?" ብላ፣ ቦርሳዋን መሰብሰብ ጀመረች ።

አጠገቧ በርከክ እንደ ማለት ብሎ፣ "ይቅርታ ይቅርታ ውዲ ... በቃ እኔ ልሁንልሽ የገረድ ልጅ ... የኔ ቀንጆ ..." አላት ። ትንሽ መለስ ስትል፣ ቦርሳዋን ባንድ እጁ ያዝ አድርገና "እዚህ እንቀይ ወይስ ..." ሲላት ፣ በቀመችበት አፍጥጣ እያየቸው፣

"ምን በጤናህ ነው ዛሬ ... ምን ሆነሃል? ደግሞ የት ነበርክ?" አለችው፣ ፊቱን እያጠናች የሚለው ሁሉ ስላልገባት ።

"እዪ በጤና ነው ... ወንድሜ ቤት ነበርኩ ... ዛሬ ነው ከታይላንድ የመጡት ... እነሱ ይዘውኝ ነው ። በጊዜ ነበር የተነሳሁት ... ሲሪየስሊይ መንገድ ተዘጋግቶ ነው ያዘገየኝ ... አይ እም ሶሪይ ... ምን አሰብሽ ታዲያ? እዚህ እንቀይ ወይስ?" ሲላት፣ ትንሽ በረድ አለች ።

"አይ ዶንት ኬር ...ደስ እንዳለህ" ብላ ተመልሳ ተቀመጠች ። ኩርፊያዋ ሙሉ ለሙሉ አለቀቃትም ። የሽቶዋ መአዛና ልቅቅ አድርጋ የተሰራችው ረጅም ጸጉሯ ቀልብ ይስባል ። የለበሰችው ቢጫ ሹራብና አጠር ያለ ጥቁር አረጓዴ ጉርድ ቀሚሷ የፈዛች እደይ አበባ አስመስሏታል ።

"በጣም ነው የዘነጥሽው ደግሞ ... ጸጉርሽን እንደዚህ ስትሰሪው በጣም ነው የሚያምርብሽ ..." በከፊል ዓይኗን የሸፈነውን ጸጉር ገለጥ አድርገ ግንባሯን ሲስማት ፈገግ አለች ። እዛው ለመቆየት ወስነው ራት እዘዙ ። ምንም እንዳልተፈጠረ እየተሳሳቁና እየተጎራረሱ ቀን ፍርድ ቤት ያጋጠማትን አስቂኝ ገጠመኝ ነገረችው ፣ የጠቀለለውን እንጀራ እጉርሷት ፣ ከጎኑ የቀመውን ሰው ለማየት ቀና ሲል ግይኑን ማመን አልቻለም ።

"ዶ...ክተር ሊ-ራ-ክ ... ታ...ዲ...ያስ ...በና...ትህ በዛው ጥፍት ትላለህ እን...ዴ ..." አለች፣ አጠገቡ የቀመችው ልጅ፣ እጁን ለሰላምታ እየዘረጋችለት ፣

©OLDBOOKSPDF

ድንጋጤውን ለመደበቅ እየሞከረ ፣ በወጥ የተነከካ እጁን አጠፍ አድርጎ ከፍ ብላ እንድትጨብጠው እጁን ሰጣት ።

"ሄደ ... ታዲያስ ... እንዴት ነሽ" አለና ነገሩን ተራ ትውውት ለማስመሰል ሞከረ ።

"ረሳሽኝ እንዴ" ይትርታ ከራት ላይ አድረሞኳችሁ ... "ሚ-ስ-ጥ-ር" እባላለሁ" ብላ ፣ ወዳሴንም ጨበጠቻት ።

ነገሩ ግራ የገባት ወዳሴ በደመነፍስ ዓይነት ፣ "ወዳሴ ..." አለች ።

እንግዳዋ ልጅ ሲጋራዋን ወደ ላይ አቦነነችው ። "ትደ...ው.ል...ል...ኖለህ ብዬ ጠብቁ ነበር ... ምነው በሰላም ነው?" የነገሩ አካሄድ አላማረውም ።

"እም ም ... ቁጥርሽ የት እንዳስቀመጥኩት ጠፋብኝ ... ደግሞ ሥራም በጣም በዛና ..." አለ ፣ አጭር ቀሚስ ከረጅም ባለ ተረከዝ ጫማ ጋር ያደረገችውን ልጅ ሽቅብ እያየ ። ሌላ ነገር ሳትል ፣ ዞር አድርጎ ሊያመራት በማሰብ ከመቀመጫዉ ተነሳ ።

"እይዝምህም እኔም ጠርጥሬያለሁ ... ይትርታ ... እንዳልረብሻችሁ ... በቃ ቁጥርህን ስጠኝና ሰሞኑን እደውልልሃለሁ ..." ብላ ፣ ስልኳን አወጣች ። ቶሎ እንድትሄድለት ቁጥሩን ሲሰጣት መዝገባ ወዲያው ደመለችለት ። ስልኩ ሲሥሀ ፣ ድምፁን አጥፍቶ ኪሱ ውስጥ መለሰው ። ዛሬ እንደ መጀመሪያው ቀን ቀንጮ መስላ አልታየችውም ። ሰላናደደችውም ይሆናል ምስጢርን የሚመስል ምንም ነገር አላየባትም ።

"የመጨረሻው ዘጠና ሰባት ከሆነ የኔ ነው ... ፕሊስ ደውል ደግሞ ... እኔም ደውልልሃለሁ ... ይቅርታ የኔ ቀንጮ ረበሽኳችሁ ..." እጇን አውለበለባ ወዳሴን ተሰናብታት ስትሄድ ተቀመጠ ። ከባሻዝር ያሉ ጥቂት ሴቶች መካከል ተቀላቅላ እየተሳሳቁ ሲንጫጩ ፣ እሱና ወዳሴም ተፋጠጡ ። ማናት በሚል አስተያየት አየችው ።

"ምን ባዘሽ ባለፈው እናቷን አክሚላት ... ቁጭሪን ሰጥታኝ ነበር መስለኝ ... የት እንደ ጣልኩትም ትዝ አይለኝም ። እዚህ አገር ሐኪም መሆን እኮ ጣጣ ነው ... አንድ ቀን ቢተሰባቸውን ካየሽላቸው ፣ በቃ ጓደኞቸው የሆንሽ ይመስላቸዋል"

"እናቷን አከመህላት ከሆነ ... ምን እንዲህ አሽቀጠጮጠህ ታዲያ? ... አንተን ለማርከትበት ከቻለች ... ነገሩ ከዛ በላይ ነው የሚመስለው ... ወይም..." ትኩር ብላ ስታየው መጠጡን የሚቀዳ መስሎ ዓይኑን ሰበረ ። ከዚያም እንደተበሳጨ ሆኖ ንጭንጭ ባለ ድምፅ ፣

"እና ታዲያ ልክ ረጅም ጊዜ እንደምታውቀኝ ሲጋራዋን እያቦነነች ... ስትመጣ ... ምን ልታስቢ እንደምትችይ ገምቼ የተርበተበትኩ ብመስል ... ይገርምሻል?" በረጅሙ ተንፍሶ ፣ ወደ ኋላው ተንጋለለና አይኖቹን ጨፍኖ ዝም አለ ።

"ለማንኛውም ከሕመምተኞችህና ካስታማሚዎች ጋር በልክ መለሞወጡ የሚጠቅምህ አያመስለኝም ። @[illegible]ቱ ያስፈልጋል ። "

"በናትሽ አሁን እሱን ትተን ራታችንን በሰላም መብላት እንችላለን?" አለ ቀጣ ብሎ።

"እይሲራክ ... ችግርህ እኮ ካንተ ሌላ ... ሰው ምንም የሚያውቅ አይመስልህም። አሁን ይቺ ልጅ ምን እንደ ሆነች የማላውቅ ይመስልሃል። ደግሞ ... አንተም እኔም እናቷን አዘመህላት እንዳልተዋወቃችሁ እናውቃለን። እንደሱ ከሆነ ምነው ታዲያ ስለ እናቷ ጤንነት አንድ ጊዜ እንኳን አላነሳችሁም? ... ሞተዋል እንዴ?"

"ደስ ያለሽን ማሰብ ትችያለሽ። ሰው ማሰብ የፈለገውን ከመሰነ በኋላ አላቡን ማሰለወጥ ከንቱ ድካም መሆኑን አውቃለሁ"

"ልክ ነህ ... ሰው መሞሸት ከፈለገም ጎደኑ ስር ያፈጠጠውን ዝሆን ጥንቸል ነው ብሎ ለመከራከር አይመለስም። ሲራክ ... አሁን አሁን ግን በጣም ግራ እየገባኸኝ ነው። ቀድ አንተ ግን ከኔ ምንድነው የምትፈልገው ... ሲርየስሊይ?"

"ምን የምፈልግ ይመስልሻል?" አለ፣ አቶን ጠመም አድርጎ።

"አንተ ንገረኛ ... ሳይህ የምትፈልገውንም የምታውት አትመስለኝም" አለች፣ ቱግሞን እየተቀጣጠረች።

"እኔ የምፈልገው ... ካልተሳሳትኩ አንቺ የምትፈልጊውን ይመስለኛል። አንቺ ከኔ የምትፈልጊው ምንድነው?" ጎይኗ ድም ነርሶ ከንፈሮቿን በምራጭ እንደግራሰና እንደ መንከስ አድርጋ አገጯን አሻሸች።

"እኔ ካንተ? ... ምንም አልፈልግም ... ምንም አልፈልግም ... ለማንኛውም በል ደህና እደር ..." ብላው፣ ዕቃዋን በፍጥነት ሰብስባ ብድግ አለች። "ካንተ ምንም አልፈልግም እሺ ... ምክንያቱም ... ለኔ የሚሆን ምንም የለህም። ገባህ?" አለችው፣ ድምጿን ከፍ አድርጋ። መልሱን ሳትጠብቅ፣ በሹል ሣጣግጥ መለሱን እያንጸቃች በዘፍሱ መሀል ሰንጥቃ ስትወጣ፣ ሰው ሁሉ ዞር ዞር እያለ አያት። ሲራክ ሊከተላትም አልሞከረም፣ ፍላጐቱም አልነበረውም። እሳው ቁጭ እንዳለ ፊቱ ያለውን ቢራ ጨለጠና አስተናጋጁ ሌላ እንዲያመጣለት ምልክት ሰጥቶት በረጅሙ ተነፈሰ።

"ይቺ የገረድ ልጅ ... ደግሞ 'ምን ትፈልጋለህ?' ... ምናምን ትላለች እንዴ... ኮተታም ... 'ምንም የለህ...ም?' ... መናጢ ... ተፈላስፈሽ ሞተሻል። እስኪ እናያለን ... ማን ያለው ... ማን የሌለው እንደሆነ ... እኔ ሲራክ አይደለሁም ... ባሻጅ ራሰ አለ ድምጹን አውጥቶ። ሦስተኛ ቢራውን በፍጥነት ጨልጦ ለመውጣት ሂሳቡን ሲያስቀምጥ 'ሉሲ' ከአጠገቡ ቀማ ቁልቁል ታየዋለች።

"መቀመጥ ይቻላል?" ስትለው፣ ትከሻውን ሰብቆ ወዳቤ ተቀምጣ የነበረበትን ቦታ ባንጨ አሳያት። ሳታቅማማ ተቀመጠችና ከኪሷ ውስጥ የሲጋራ ፓኮውን ስታቀብለው በግራ እጁ እንዲት ሲጋራ መዘዘና የርሷን ወስዶ ለኮሰ። ባለ በሌለ ጋይድ ምጥጥ አድርጎ ሲያቦነው፣ አካባቢውን አሮጌ ትሬንታ ኳትሮ ባጠገባቸው ያለፉ አስመሰለው።

@OLDBOOOKSPDF

"ምነው ... ምን ተፈጠረ? ልጂቱን ምን አደረካት?" አለችው፣ አፏን ጠመም አድርጋ።

"እድሜ ላንቺ ..." ሌላ ቢራ እንዲያመጣለት ላስተናጋጁ ምልክት ሰጠው።

"ደግሞ እኔ ምን አደረኩ ... ጠፋሀ ... በጣም ላስብህ ነበር ... ድንገት ላይህ መጣሁ ... በታ ስልህህን ነው የወሰድኩት፣ ሌላ ምን አደረኩ?" ያደረገችውን ሁሉ አስባ ያደረገችው ስለ መሰለው፣ አላመናትም።

"አይ ዶንት ኒር ... ማናት ምናምን ስትለኝ ... እናቷን አክሚላት ነው ... ገለመሌ ብላትም ልታምነኝ አልቻለችም ... የሆነች የገረድ ልጅ ነገር ናት ... ተያት በከሽ ... አንቺ የገረድ ልጅ ታውቂያለሽ?" ብሎ፣ አይኖቹን ቦዘዝ አድርጎ ሲያያት ሳቋን ለቀቀችው።

"የገረድ ልጅ? እም...ም ... የሳይኮሎጂ ጥያቄ ነው?"

"ካም ኦን ... ሱሲ ...አይደል ስምሽን ያልሽኝ? ምን 'የገረድ ልጅ' ብለው ሲላይቡ ስምተሽ አታውቂም? የምር የገረድ ልጅ ምን አይነት ነው? አይ ኖው ዩ አር ስማርት ..." ሞቅ እያለው ስለሆነ፣ ድምፁም ጋል እያለ ነው።

"ምናልባት የበታችነት ስሜት ስለሚሰማቸውና ያለ አባት ስለሚያድጉ ... አይ ዶኖ ... አስቢው አላውቅም ... አዙራፊ ናቸው? ... አንተ ንገረኛ ... ሳይኮሎጂስቱ አንተ ነህ" ስትለው፣ ከት ከት ብሎ እያጨበጨበ ከጣራ በላይ ሳቀ። ሰው ሁሉ ዞር ዞር ብሎ ሲያየው ከቁብም አልቆጠራቸውም።

"ኖ ... ኖ ኖ ኖ ... በተቃራኒው ... የገረድ ልጆች ለጌቶችና ለመቤቲቱ የተሰራውን እፍታ እየበሉ ስለሚያድጉና ... ገና በትንሽነታቸው ከእመቤቲቱ ልጆች ጋር ስለሚፋለሙ ... ጠንካራና ጀግና፣ በራስ የመተማመን መንፈሳቸው የጸበረ ሊሆኑስ አይችሉም?"

"እንደሱ ከሆነ ታዲያ ለምን የገረድ ልጅ ነገር አልካት?"

"ጠብ ትወጻለች ... መሸነፍ ግን በፍጹም አትወድም። ሁሉን የምታውቅ ይመስላታል ...ግን ምንም አታውቅም። ግልፍተኛ ነገር ናት ... ግን ምንም አቅም የላትም ... ገም ብላ እምቡር እምቡር ታበሳለች ... ገባሽ? አዲዮስ የራቢ ጉዳይ ... አሁን ከዚህ ቤት መውጣት እፈልጋለሁ ... አንቺ ትቀያለሽ?"

"አብረን ማምሸት እንችላለን ... ከፈለግህ"

"ጥሩ ... ኡፍፍፍ ... ትንሽ ጸጥ ያለ ቦታ ብሄድ ደስ ይለኛል" ሒላብ አስኪመጣላቸው ሁለቱም በራሳቸው ዓለም ውስጥ ተዘፈቁ ... ድንገት ተመልሳ የመጣችው ወጻሌ ጸጥታውን አስከታደፈርሰው።

"ዶክተር ... አሁንስ ስለ እናታ ጤንነት በቢራ ዙሪያ እየተመካከራችሁ ነው?" ብላ ስታፈጥበት 'ሱሲ' ደንግጣ ሽምቅቅ አለች።

@OLDBOOOKSPDF

ሞት ብሎት ስለነበር ግንባሩን እያሻሸ ተኛ ብሎ "እናቲ ደህና ናቸው እንዲያውም ስላንቺ ጤንነት እየተጠያየን ... ያገረድ ልጅ ይመስል ጠባይሽ ግራ እንደገባኝ ሳስረዳት ..." ብሎ ሳይጨርስ ድንገት ጉንጩ ላይ ያረፈውን ጥፊ ጨክኝት ከሰጪ እኩል ነበር የሰማው። ሰጪ ሁሉ ወደ እነርሱ ዞር ዞር ሲል፣ 'ሱስ' ላይ የሚጋረፋ ግድፍን አጉረጥርጣ "ራሱን ማከም ያልቻለ ... ገና ራሱን የማያውቅ፣ የዘረበት ዶክተርነው አዝለሽው ዙሪ ...እሺ ..." ብላ፣ በመጣችበት ጥግንት ተመልሳ ጠ፣ች።

ጥፊው ያረፈበትን ጉንጩን እያሻሸ፣ "ንግራሻለሁ አኮ ልጅቱ የተፈጠረችው ለጥፊና ለመግት ነው። አላት የላስች ጠበቃናት። አየሽ ... የገረድ ልጆች ከተነሳሳቸው ... አንበሶች ናቸው። ኡፍ...ፍ ..ኑ ... ጥፊያቸውማ አይጣል ነው። ሙያ ውደ እንዴት አንደሚለበልብ አትጠይቂኝ። እኔ ኮ ላንቺም አንድ የሚደርስሽ መስሎኝነበር ...' አለና ዝት ብሎ ሳቀ። የሆነው ሁሉ በትጽበት ሰለሆነ ማመን አልቻለም። 'ዋጋህ ነው ... የገረድ ልጅ ... ጥፊ ሲያንስህ ነው ...' አለ፣ በሆዱ እየተንጨረጨረ።

"እኔን ብትመታኝ! ... ያሄን የፈረሰ ጭራ የመሰለ ጸጉሯን ይገፍ ... ፊቷ የጥፊ ማሳ እስኪመስል ... አሮጌ ታለሁኮ ... ላንተም ደሜ ፈልቷል'

ዙሪያ ገባውን ሲያይ ሰጪ ሁሉ ወደነሱ እያየ ሲያንሾካሹክ አይቶ ተበሳጨ። "ወፈፍ የገረድ ልጅ ሁሉ .. አሁን እዚህ ሲያዩዋቸው የጨዋ ልጆች ይመስላሉ ... እንኳን እናንተ እኔም ዶክተሩ የገረድ ልጅ ነኝ። ከወጪ በልብስ ተደርቸ ሲያዩት ሌላ ሰው ይመስላል። ውስጡ ግን ያው ሁሉም የገረድ ልጅ ነው። ወንድሜ የራሱን ልጅ ... የገረድ ልጅ የሚለው ወዶ አይደለም ለካ። እያንዳንዱ ሰው የሌላ ሰው ገረድ ነው'

ምንም ስላልገባት ፈገግ ብላ ስታየው ድንገት በሞቅታ ብድግ አለና ሙዝ ብሎ "ላለም የገረዶችና የገረድ ልጆች ትሆናለች! ... ከገረድ ልጆች ጋር ወደፊት!' አለ የቀኝ ክንዱን ዘና አደረገ። ሁሉም ሰው ደንገጥ ብሎ ወደ እነርሱ ዞር ዞር አለ። ግድም አልሰጠውም። 'ባደባባይ ከተመሰከኩት ጥፊ በላይ ውርደት ... አይደርስብኝ' አለ ለራሱ።

"ነይ ባክሽ ከዚህ እንወጣ ... ሉዘር ብቻ ተሰብስቦ ... ከርሱን እየሞላ፣ ቢራውን ይቸልስ ... በሚንቅላቱ ላይሆን በቢራ ሃይል የሚነዳ ... ባጀጅ ራስ ሁላ ..." ክ'ሉሲ' ጋር እጅ ለጅ ተያይዘው ወጡ። የመኪናውን ሞተር እያስነሳ ሰዓቱን ሲያይ ከምሽቱ ሦስት ተኩል ይላል። "ሌላ ፕሮግራም ከሌለሽ ወደ ቤት ቀጥታ ብንሄድስ?"

"ውጪ የማምሽቱን ሃሳብ ተመከወ?" አለች፣ መስኮቱን ከፍታ የሲጋራ አላቂዋን እየወረወረች።

"ምናስ ... ሚጻ ላይ ከምትወረውሪው እዚህ መከስተሪያ ውስጥ ብትጥፊው ብሎ እየተንጫነጨ ከመኪናው ወርዶ፣ የጣለቻትን የሲጋራ አላቂ ፊልግ መተከሽ ውስጥ በሥርዓቱ ሲያስተምጣት ገርሟት ዝም ብላ እየችው። "በታ ስለ መሽ አይ ቲገስ ለዛሬ ይበቃኛል መሰለኝ ..." ብሎ ጉንጩን እያሻሸ አለና፣ "ሌላ ፕሮግራም ከሌለሽ

@OLDBOOOKSPDF

...አብረን ብናድር ያስ ያለኛል ... ፖሊስ ..." አሰ ፣ በመለማመጥ ዓይን ዓይኗን እያየ ። ብቻውን መሆን አልፈለገም ።

"እሺ ..." አለች ፣ ትዝሻዋን ስበት እያደረጋ ። ቤት እንደደረሱ ቲቪውን ከፍቶ ፣ ዚፑ ውስጥ የሞለውን መጽሐፍ ሶፋ ጠረጴዛው ላይ አሽቀንጥሮ ጣለው ።

"ያው ፍረጁም እዛ ጋ ነው ያለው ... ያስ ያለሽንና ቤት ያፈራውን ። እኔ ግን ቶለል እንዲለኝ ሻወር መስጄ ልብስ መቀየር አለብኝ" ብሎ ወደ ጎዳ ገባ ። ለስስ ያለ ውሃ እላዩ ላይ ሲለቅ ቀለል አለው ። ከሰአት በኋላ ጀምሮ በፍጥነት የሆኑትን ነገሮች ለማሰብ ሞከረ ። ቢስተር ዘሪባ ስለ ምስጢር የነገረችው ... ከወንድሙ ጋር ያደረገው ጭቅጭቅ ... ከውዳሴ ጋር የነበረው ፍልሚያና የ'ሉሲ' በድንገት እንደገና መነሰት ሁሉ ከሙንቱላቱ ተርፎ ፈሰሰ ። ከሁሉም በላይ ግን 'የገረድ ልጅ' የሚለው የወንድሙ ቃልና የውዳሴ ድንገተኛ ጥፉ ፣ በሳሙናና በውሃ የማያለቅ ሆነበት ።

ውሃው ከአርቱ እየተፈተለከ ሰውነቱ ላይ ሲያርፍ ፣ በቀጨት እያንገራገረ ስለ እናቱ ማሰብ ጀመረ ። ከዛ ስለ ምስጢር ደግሞ ስለ ጎሊና አሰበ ። ከውሃው መጮቶ እያንገራገረ የሴሊት ልብሱን ቀያይሮ ጸጉሩን በፎጣው እያደራረቀ መደ ሳሎን ተመለሰ ።

"ቶየሁ እንዴ?" አለ ጋደም ካለችበት ሶፋ ፊት ለፊት ተቀምጦ በልታ ካሰቀረችው ፒዛ ላይ አንድ ቁራጭ አንስቶ እየገመጠ ።

"እደርክ እንጂ .. ልጅት ያቀመስችሃን ጥፉ ስታስለቅቅ ነው?"

"እይዝምም ... ደፋር .. መደ ጥፉ ... ለቀቀችብኝ እኮ ... ለጥቂት ጊዜ ማሰቢያዬን ነው የዘጋችው . ደቅ ጠዘቃ ሳደሆን ... ቂጣ ጋጋራ ነበር መሆን የነበረባት ።"

"ሻደ ነገር ትፈልጋለህ?" አለች ፣ ለራሷ የቀዳችውን ሻይ ፉት እያለች ።

"ከተዳሰልኝ?" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ ። "ሻወር ምናምን መውሰድ ከፈለግሽ . ርጣና የሰ ን ጊጄ አለጋው ላይ አድርጌልሻለሁ ። ሌላ ላንቺ የሚሆን ልብስ ያለ አይመስለኝም .."

"አንተ ... እንኳን ፒጃማሃን ለብሽ ... ካንተም ጋር ስላመራሁ የቀመስከውን ረሳኸው እንዴ?" ብላ ፣ እየሳቀች ሻዩን ቀዳችለት ።

"ስቀልድሽ ነው ባክሽ .. ከሆነሽ የኔን ቁምጣና ቲ ሸርት ነው ያስቀመጥኩልሽ ... ፕርስ ብሩሽ መታጠቢያ ቤት አለልሽ ።" የሰጠችውን ሻይ እንደያዘ ቀሞ የቲቪ ሜዚያውን በፍጥነት ቀያየረው ።

"እሺ በቃ መጣሁ ... እኔም ትንሽ ቀለል ይበለኝ" ብላ ፣ ወደ ውስጥ ገባች ። የሲጋራኤን ዚና ትንሽ ሲስጣ ቆየ ። ከዚያም ቲቪውን አጠፋፍቶ መደ መኝታ ቤቱ ሄደ ። አልጋ ውስጥ ገብቶ ሰሞኑን የጀመረውን መጽሐፍ ለማንበብ ሞከረ ። የአልጋ ውስጥ ንባብ ደስ ይለዋል ። መብራቱን ሁሉ አጠፋፍቶ ፣ የራስጌው መብራት ብቻ ነበር የሚበራው ።

@OLDBOOOKSPDF

የሱን ቁምጣና ቲሸርት አድርጋ ስትመጣ፣ "እንዴ ልከሽ ሆኖ የለም እንዴ?" አለ፣ የሹፈት ሳቁን እየሳቀ።

ዞር ዞር እያለች በመስታዋት እየችና፣ "ምን ልኬ ይሆናል ... እንደዚህ ተንዘላገለሎ ... ትቀልድብኛለህ አይደል?" ብላ ትራሱን አንስታ ፊቱ ላይ ወርውራ አልጋው ገልጣ ገባች። "ምንድነው ደግሞ በዚህ በጨለማ የምታነበው? ማንን ለማሳሳት ነው ... ወይኔ መጽሐፍ ካነበብኩ ስንትና ስንት ጊዜ ሆነኝ ..." ብላ፣ የያዘውን መጽሐፍ ተቀብላ መገላለጥ ጀመረች።

"ልቦለድ ነው 'ዘ ፖርትሬይት ኦፍ ኤ ሌዲይ' ... ስላንዲት ቅብጥብጥ ቀንጆዬ ወጣት የሕይወትና ስንክላ የፍቅር ታሪክ ነው የሚያወራው። ጄምስ ሄንሪ የተባለ ታዋቂ አሜሪካዊ ደራሲ የጻፈው አሪፍ መጽሐፍ ነው"

"ደስ ሲል ቅብጥብጥ ቀንጆዬ ወጣት መሆን ... ሁላችንም እንደዛ ነበርን ... ክንፋችን ተሰበረና የትም ቀረን እንጂ" ብላ፣ የፊት ገጹ ላይ ያለውን ስእል እያየች ጭልጥ ያለ ትካዜ ውስጥ ገባች።

"እሷም የራሷ አሳዛኝ ታሪክ አላት ባክሽ። በጣም ብሩህ ሞንትላትና ሰው ሁሉ በቀላሉ የሚወደው ብርቅርብቅ ሰብእና ከተንዛዛ ውበት ጋር ያደላት ወጣት ታሪክ ነው። ከፈለግሽ ስጪርሰው ማንበብ ትችያለሽ" መጽሐፉን ተቀብሎ ወደ ኮመዲናው ላይ ወርወር አድርጎ፣ በጀርባው ተጋደመና በረጅሙ ተነፈሰ።

ትንሽ በራሷ ሐሳብ ውስጥ ወጣ ገባ ስትል ቀየች። "ቅድም የሰጠሽኝ መልስ አላረካኝም ... የምር ለምን አልደወልክልኝም?" አለችው፣ ቀና ብላ ዓይን ዓይኑን እያየች፣ እጁን ደረቱ ላይ ጣል አድርጋ።

እንዴትና ምን እንደሚላት ግራ ገብቶት አንገቷ ስር ሳም አደረጋት። "እም ... በቃ አሪፍ ጊዜ ነበር ያሳለፍነው ... ግን ከዛ በላይ መሄድ ያንን ማበላሸት ... ዝም ብሎ ኩተት መሰለኝ። በቃ እዛው ጋ እንደ ጣፈጠ እንዲቀር ፈለግሁ ... ወንጀል ነው?" አለ፣ ዓይኗን ለመሸሽ ይመስል ጣራ ጣራውን እያየ።

"አይ አይደለም ... ግን በቃ ዝም ብዬ ... ትደውልልኛለህ የሚል እምነት አድሮብኝ ነበር መሰለኝ ... በቃ በጣም ጠብቂህ ነበር። ከማውቃቸው ሰዎች ሁሉ ሌላ አይነት ሰው ስለ መሰልከኝ ... ሳትደውል ስትቀር ደግሞ የበለጠ ላገኝህ ፈለግሁ። ብዙ ጊዜ ቤትህ ልመጣ አስቤ ነበር ... ደጅ ላይ ደርሼ የተመለስኩበትም ቀን ነበር። ምንሆነ ነው ግን?"

"እንግዲህ ጥሩ ሰው ስለ ሆንሽ ይሆናላ ..."

"አቤት አቤት ... ሞኝህን ፈልግ ... ተወው እሺ ... ግን ሥራ ጥሩ ነው?"

"ጥሩ ነው ... ያው የተለመደው ነው ... ቀይ ግን አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ ... እውነቱን ንገሪኝ ... የገረድ[illegible] ነው እንዴ?" አለ፣ እንደ መቀለድ ብሎ በተረጋ ትኩር ብሎ እያያት።

"ምንድነው አንተ ልጅ ... የገረድ ልጅ ... የገረድ ልጅ የምትለው ከትድም ጀምሮ? አልገባኝም።" እሷም ትራሷን አቃናችና ደገፍ ብላ ተቀመጠች።

ከወንድሙ ጋር ያደረጉትን ሙቅሙቅትና ለማንም ነግሮ የማያውቀውን የራሱን ታሪክ ከልጅነቱ ጀምሮ አጫወታት። "ቅይ ግን ለምድነው የገረድ ልጅ መሆን የሚያሳፍረው? ገረዶች እናት የመሆን መብት የላቸውም?" አለ፣ አሁንም መልሱ እሷ ጋ ያለ ይመስል።

"እኔንጃ ሲራክ ... ለኔ ሰው ሁሉ ሰው ነው። ልዩነቱ ልብሱና ልቡ ብቻ ይመስለኛል። አንተ የገረድ ልጅ ስለሆንክ ታፍራለህ?" አለችው፣ ምን ማለት እንዳለባት ስላላወቀች።

"እፍ ኮርስ ... በጣም እንጂ ... 'የገረድ ልጅ' ብሎ የገዛ አባቱ ልበል ወይም ወንድሜ ሲላደብ እየሰማሁ እንዴት ነው የማላፍረው። የገረድ ልጅ መሆኔንና እሱም አባቴ መሆኑን እንደማውቅ ስነግረው በድንጋጤ እንጪት ሆኖ የቀረው ስለሚያሳፍር አይመስልሽም? እሱ ሠራተኞቹን በጉርምስናው አስገድዶ ወይም በፍቃዷ ተስማምተው አላውቅም ... ስታረግዝበት ወላጆቹ እርሱን መደ አዲሳባ ላኩት።

"እሷን ራቅ ያለ ቦታ ልከው እኔን ከመለዶች በኋላ፣ ልጇን ከነጠቋት በኋላ ሁለተኛ ድርሽ እንዳትል አስፈራርተው እንዳባረሯት ነው የሰማሁት። ማንነቴን ደብቀውኝ ኖረው ኖረው ... ዕድሜ እናቴ ላልሆነችው ክፉ 'እንጆራ እያቴ' በተበሳጨች ቁጥር 'የገረድ ልጅ' እያለች ስትሰድበኝ 'የገረድ ልጅ' ምን ይሆን እያልኩ ገና በልጅነቴ ግራ ይገባኝ ነበር። አሁንም አይገባኝም። ቅይ ግን የገረድ ልጅና የሌላው ሰው ልጅ ምንድነው ልዩነቱ?" አለ፣ ከሚያውቀው ሌላ መልስ ቢኖር ብሎ ተስፋ ያደረገ ይመስል።

"ሲራክ ... የምትለው ለኔ አይገባኝም። ለኔ የገረድ ልጅም ሆነ የለማኝ ልጅ ከሌላ ሰው ልጅ የተለየ ነው ብዬ አላስብም። ችግሩ የሕዝባችን ግብዝነትና በሌቦች ላይ የሚነው ከተት ... በልጆች ላይ የፈጠረው ተቀጥላ ቀንበር ነው። ለምሳሌ ሲትኛ አዳሪዎችን ውሰድ ... አየኸኝ እኔን ... እኔ ለምሳሌ ምንድነኝ ... ሽሌ ነኝ አይደል? ግን ላንተ ልጅ ብወልድልህ ሕፃኑ ምን እንደሚባል ታውቃለህ? የዶክተር ልጅ አይባልም። 'አባቱ የማይታወቅ ዲቃላ የሽርሙጣ ('ሽ---') ልጅ' ነው የሚባለው። ካሁን በፊትስ ሲባል አልሰማህም? ታዲያ ለምን ይገርምሃል?

"አንተ አሁን ዶክተሩ ከኔ ጋር እዚህ የልብህን እያወራህ የልብህን እየሰራህ አንድ አልጋ ላይ ትተኛለህ ... ትጫወታለህ። ነገ ግን ሥራ ሆስፒታል ስትሄድ ይዤ ሁሉ እንዲታወቅብህ ትፈልጋለህ? በሌላ ቋንቋ የሽ--- ጓደኛ መባል ትፈልጋለህ? ከኔ ጋር ማደርህ እንኳን እንዲታወቅብህ አትፈልግም። ልጅ ብወልድልህስ ... ኮራ ብለህ ባደባባይ ልጅህን ይዘኸው ትዞራለህ? አታደርገውም። ልጁ ምንም ችግር ስላለው ሳይሆን እኔ እናቱ ሽ--- ስለሆንኩ ነው ...ገባህ? ..."

@OLDBOOOKSPDF

"ከናትሽ ሽርሙጣ የሚለውን ታል አትጠቀሚ ... በጣም ነው የሚያበሳጨኝ አለ ፊቱን ሞናገግ አድርጎ።

"እኔን አትፈሀ እየተኛህ ... ታሉ ለምን እንደዚህ ቀፈፈህ? ምን ልበልልህ ታጂያ? ቺዝ ወይስ ሽሉ ይሻልሃል? ነው እንደ ሰለጠኑት አገሮች 'ኮል ዝርል' ... 'ኢስኮርት' እንባልላችሁ? ... ጋለሞታ ወይም ሽ... ከመባል ወደ 'ሴትኛ አዳሪ' ወይም 'የመሊቭ ጎሚድ ሠራተኞች' ተብሎ ስሙ ስለ ተቀየረልን ሥራውን የሚቀይረው ይመስልሃል? ስሙ የተቀየረው ለሴቶቹ ክብር ተብሎ ሳይሆን ወንዶቹ ያለ ምንም ጸጸት ልክ እንደ ጤፍና ያጣት በአል ዘግ ... እንደ ሽቀጥ እየቸበቸቡት እንዲጠቀሙ ተብሎ ነው።

"ስንት እንቱ የተባሉ የከተማው ታዋቂ አባወራዎች ሚስቶቻቸውን አጋድመው፣ መሊቭ እንደ ሽቀጥ ሲቸበችቡ እንደሚያድሩ ብንገርህ አታምንም። ስንቱ የሽ--- ልጆች እንቱ የተባሉ አባቶች እንዳሏቸው ታውቃለህ? ደግሞስ ገረዶች ከማን የሚወልዱ ይመስልሃል? ወይ ከጌቶቻቸው ወይ ከጌቶቻቸው ልጆች ነው። የገረድ ልጆች አባቶቻቸው ጌቶች ናቸው። የሽ-- ልጆችም ... ያንተና ካንተም የሚበላልጡ የምሁራንና የባለጠጎች ልጆች ናቸው። ግን የሽ--- ልጆች ነው የሚባሉት። እና ምንድነው የሚገርምህ? ለምንድነው የምትናደደው? አንተም ያው ነህ ... የገረድም ... የጌታም ልጅ ነህ ... ምን ለውጥ አለው?"

ጸጥ ብሎ ሲሰማት ቀየና ሞንትላቱን እየወዘወዘ፥ "ኦህ ማይ ጋድ ...አንቺ ... ምን እያነበ ጠምዛዛ ሞ ንትላት ነው ያለሽ?" ብሎ፥ ራሱን እያሻሸ ገሙ አለ።

"እና ሽሌ ስለሆንኩ የማላስብ ይመስልሃል? ያቺ ቀንጅዬ ዝርል ፍሬንድህ የገረድ ልጅ ስትላት ለምን ይመስልሃል በጥፊ ያተመሰችህ? ደግሞስ ከኔ ጋር ስትይህ ለምን ይመስልሃል እንዴት ተናቅው በሚል ስሜት እየተንጨረጨረች የተውረገረገችው? እየህ ግርድናና ሴትኛ አዳሪነት ማንም ወይ የሚገባበት ሥራ አይደለም። ግን ገረድና ሽ--- ለመሆን የተፈጠረ የለም። የእያንዳንዷ ሴት ልጅ ምኞት ... የተከበረች እመቤትና የተወደደች የፍትር ንግሥት መሆን ነው ... ለዛም ነው የተፈጠረችው። ግን ገረድ ሳለመሆን ስትሞክር ሽ--- ለመሆን ትገደዳለች። ሽ -- ሳለመሆን ከመሰነች ደግሞ ገረድ መሆን ያላት ብቸኛ አማራጯ ነው። የቱ እንደሚሻል አላውቅም። እንተ ቦቶ የሚሻል ይመስልሃል?" ዝም፥ ብሎ ሞንትላቱን ወዘወዘ።

"ለእኔ ግን ከሁለቱም የሚከፋው በህሊና ሽ---ጥና ነፍስን እየሸጡና ያልሆኑትን ለመምሰል እያሽቃበጡ የዘቀጠ ኑሮ መኖር ነው። አሳፋሪው ግርድና ... በግዝትህ እያፈርክ ያልሆንከው ለመባልና የህሊናህን ከርሰ ለመወላት ስማታምነዝት ነው አሽከር ሆነህ የምትኖረው የሚበመስል ኑሮ ነው"

"ስለዚህ ..."

"ስለዚህማ ... ይፈርሽን ካላልክ ...እስኪ በድንብ አስበው። እኔስ ያው አንሱ ሽ--- ነው የምባለው። አንተስ ምንድነህ? ... የተከበሩ የአእምሮ ህዝምና ስፔሺያሊስት ዶክተር ሲራክ ... አይደል? ©EHDBOOKSPDF ...ምት የም ታደርገውን ነገር ... እ

ደግሞ ኑሮዬን ለመግፋት ስለምሠራው ነው ። ዘገባ ገንዘቤ ስለገባሁት ካላልክ በተር ... አንተም እኔም ሽ---ምች ነን ። አንተ ገዢ ሽ--- ስትሆን ፣ እኔ ደግሞ ሻሞ ሽ--- ልባል እችላለሁ" ብላ ፣ ከት ብላ ሳቀች ። በጅረባው ተንጋለለና ፊቱን በጆቹ ሸፈነ ።

"አፈርኩ እንዳትለኝ ብቻ ... ቀጣፊ" ብላ ፣ እጆቹን ከፊቱ ላይ አንስታ ሳመችው ።

"ለዚህ ነው ባለፈው ገንዘቡን ያልወሰድሽው?"

"አይደለም ..." ጉንጩን ቀንጠጥ አደረገችው ።

"እና ..."

"የገረድ ልጅ ስለሆንክ አላገኝሽኝ ነው" ስትል

"አንቺ ..." ብሎ ፣ በትራሱ ደጋግሞ ሲመታት ፣ ትራሱን ነጥቃ ፊቱን ሸፈነችው ።

ተነስታ ሁለት ብርጭቆ ውኃ ይዛ መጣች ። አንዳንድ ያጋጠሟትን ታሪኮች እያነሳች ስትነግረው ቀየችና ፣ "ሲርየስሊ ግን ... ምን እንደማስብ ታውቃለህ? ብላ ፣ ትንሽ ጸጥ አለች ። የራሱን እናት ማንነት በዚያች ደቂቃና ሰዓት የት ልትሆን እንደምትችል አሰበ ።

"እኔን በከተማው የታወቀና አንቱ የተባለ ሃብታም ነጋዴ ልጅ መሆኔ ሽ--- ከመሆን አላዳነኝም ። አንተንም ያንድ ያልታወቀች የገረድ ልጅ መሆንህ ዶክተር ከመሆን አልከለከለህም ። አስበው እስኪ ... አንተ የገረድ ልጅ በመሆንህ ካፈርክና ከተደብቅህ ሌሎች ትናንሽ ሕፃናት የገረድ ልጆች እንዴት ባህሉ ያጠለቀባቸውን የህሊናና የማንነት ሰንሰለት በጥሰው ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ? ገረድ ስለሆኑ ብቻ ልክ ያንተ እናት የደረሰባትን መከራ የሚያዩ ሴቶችስ ምን አይነት ተስፋ የሚኖራቸው ይመስልሃል?" ብላ ፣ እንደገና ጸጥ አለች ። እምባዋ በጉንጮቿ ላይ መፍሰስ ሲጀምር የሚያደርገው ጠፍቶት ዝም አለ ። ድብልቅልቅ ስሜት ውስጥ ገባ ።

"እስኪ አስብ ስንት ገረዶች እዚህ አገር እንዳሉ ... ምን ያህል ግፍ እንደሚፈጸምባቸው ታውቃለህ? ደግሞስ በየአረብ አገሩ ስንት ልጆች በግርድና እንደሚኖሩ አስበኸዋል? ቤተሰቦቻቸው እነርሱ በግርድና ደም ተፍተው በሚልኩት ብር እየኖሩ ፣ ከነርሱ የተወለዱትን ንጹሕ ሕፃናት ግን 'የገረድ ልጅ' ሲሉ አያፍሩም ። አንተ የገረድ ልጅ የሆንከው ይሄ ካልገባህ ማን ሊገባው ይችላል?

"ሽ---ጥናውም ያው ነው ። ለምን ይመስልሃል የሽ---ጥና ሥራ ከጥንት እስከ ዛሬ ሳይጠፋና ሳይቀንስ የሚኖር የሥራ ዘርፍ የሆነው? ዋናው ምክንያት የማይነጥፍ ከወንድ ሽ---ጮች ኪስ የሚዘንብ ብር ስለሚገኝበት ነው ። በሴላ በኩል ደግሞ በኦሮ ምራትና በሕይወት አዘል ጦስ ፣ ሥራውን ለመሥራት የሚገደዱ ሴቶች ሁሌም የሚጮርፉበት የመከረኛ ሴቶች የስድት ጉሬ ስለሆነ ነው ። አንተ ከገረድ የተወለድከውና ሽ...ጣ አትፈህ የምታድረው ይህ ነው ። ከየት ሊመጣ ነው?"

@OLDBOOKSPDF

በረጅሙ ተንፍሳ ጉንፏ ላይ ያለውን እንባ በእጇ ጠራርጋ ወደ አንሶላው ውስጥ ሸርተት ብላ ገባች ። እጆቿን ማጅራቷ ላይ በትራሱ ስር አነባብራ ጸጥ ብላ ተኛች ። ምንም የሚናገረው ነገር ስላልነበረ ፣ "አንተ ዶክተሩ ካፈርክና ከፈራህ ሌላ ሰው ከየት ሊመጣ ነው? ... አንተ ሸርሙጣ አትፈሀ የምታድረው የገረድ ልጅ ..." ያለችውን እያሰበ ፣ ወደሷ ጠጋ ብሎ እንባዋን በጆቹ ጠራረገላት ። ያለቀሱ አይኖቿን ደጋግሞ ሳመና በወጥታ ተታቅፈው ብዙ ቆዩ ።

"አንቺ ግን ማነሽ? ስለ ራስሽ እነ ምንም አልነገርሽኝም?" ልቡን ከፍቶ ሲናዘዝላት የነበረችው ልጅ ግራ አጋባችው ። ያስተሳሰቧ ደረጃና ጥልቀት ውስጡ አንዳች ፍርሃት ፈጠረበት ።

"ለጊዜው ከመንገድ ያመጣኸኝ አንዲት ሴትኛ አዳሪ ነኝ ። ለዛሬ አንተን ካወቅን ይበቃል ። ሌላ ጊዜ ደውለህ ካገኘኸኝ ስለኔ የማወቅ ዕድል ይኖርህ ይሆናል ። ለጊዜው ግን እንተው፡ የሰጠኸኝ 'ሚስጥር' የሚለው ስም በጣም ተስማምቶኛል ። ከፈለግህም 'ሉሲ' ብሆንም አይ ይንት ኪር ። አይሻልም ትንሹ ዶክተር?"

"ወይ ጉድ ... አለችን በሰባራ ሽጥጥ አሉ ..." ብሎ ፣ ፊቱን እያሻሸ ዝም አለ ።

"አንተ ልጅ በጣም ቀጣፊ ነህ እነ ... የምር የደረትና የጡንቻ ስፖርት መሥራት ያስፈልግሃል ። ለወንድ ልጅ ጭንትላት ብቻ አይበቃም ። ብረት መዝኚያ ሲባል አልሰማህም?" ብላ እየሳቀች አይኖቿን ስትጨፍን በሁለት እጆቹ ወደ ራሱ ሰቦ ጥብቅ አድርጎ አቀፋት ። "ብቀጥንም ጠጅ ነኝ ሲባል አልሰማሽም?" አለ ።

ብዙም ሳይቆይ እንቅልፍ ወሰዳት ። እርሱ ግን ወጥታ ከነገሰበት ደብዛዛ ጨለማ ጋር ተፋጠጠ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 22 ፡

ሌላው ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ በአዲስ አበባና በአሜሪካ መካከል እራት ጊዜ ተመላልሷል ። አርሴማና ንጥያም የዝናሽን ልጆች የጉዲፈቻ ሂደት ጨርሰው ወደ አሜሪካ ከገቡ ሦስት ወራት አለፉ ። ልጆቹ ባሜሪ ጊዜ ፈጽመው አፈ ልውጥ አሜሪካዊ ሆነዋል ። የጀመረው የአእምሮ ሀክምና ማዕከል የዝግጅት ስራም እየተጠናቀቀ ነው ። የሚያስፈልጉ እቃዎችን ማስገባትና የማሰማመር ስራ ብቻ ነው የቀረው ። በአሜሪካ አገር ያሉ የርሱና የንጹህ ጓደኞች ፣ አብረውት የሚሰሩ የስራ ባልደረቦቹና የሚሠራበት ሆስፒታል ከፍተኛ ድጋፍ ስላደረጉለት ከገንዘብ አንጻር ችግር አልገጠመውም ።

ሳንቾና ምስጢር በክሊኒኩና በሌሎች ሥራዎች የተጎሳበሳምንት የማይገናኙባቸው ቀናቶች የሉም ። እሷም ለንግድ ድርጅቶቻቸው ጉዳይ የማስፈጸምና ሌሎች ሥራዎች ሲኖሯት ለሱ ሆኗል የምትሰጠው ። ቤቱ ከቢሮዋ ሩቅ አይደለም ። ብዙ ጊዜ እሱ ቤት ስለምትሄድ የአክስቱ ልጆችም ለምደዋታል ። እርሱም ከናታ ጋር ሽርክ ሆኖ ቤተኛ ሆኗል ። ሰሞኑን በሥራ ምክንያት ዱባይ ስለከረሙች አልተገናኙም ነበር ። ሲስተር ዘሪባ ደግሞ ሙሪታ ከወጣች ጀምሮ ክሊኒኩን በማዋቀርና አጋዥ ሠራተኞችን ለትዮር የመመልመል ሥራውን ከሳንቾና ከምስጢር ጋር በመሆን እያጣደፉት ነው ።

ምስጢርን ከአየር ማረፊያ ለመቀበል ሌሊት ላይ ወጥቶ ዘግይቶ ነው የተኛው ። ከእንቅልፉ ቢነቃም ሰውነቱ ድትት ስላለ ፣ ካልጋው መውጣት አልፈለገም ። ቅዳሜ ጠዋት ሦስት ሰዓት ከሃያ ይላል ፣ ከፊት ለፊቱ ያለው የግድግዳ ሠዓት ። በመኝታ ቤቱ መስኮት እኳያ የጠዋቷ ፀሐይ ጨረር ከገን ካለው ኮንዶሚኒየም ቢጫ ግድግዳ ላይ አርፎ ነጸብራቁ ክፍሉን ሷ አድርጎታል ። ባንደኛ ፎቅ ላይ የሚገኘው ባለ ሁለት መኝታ ቤት ኮንዶሚኒየሙ ከኮቲት እመታት በፊት በዕጣ የደረሰው ነው ። በፊት የሚኖሩባት ጠባብ የቀበሌ ቤት ፣ ባካባቢው ካሉ ሌሎች የቀዩ ቤቶች ጋር ከፈረሰች ወዲህ ፣ ከሚች እክስቱ ልጅች ጋር እዚህ ነው የሚኖረው ።

@OLDBOOOKSPDF

ሉሊት ሲገባ ገዚው ውስጥ ምንም ቦታ ስላላገኝ መኪናውን ደጅ ከመንገድ ዳር አቁሞ ነው የገባው። ተነስቶ ወደ ውስጥ አስገብቶ ጥላ ላይ ማቆሙ የተሻለ መሆኑን ቢያስብም ድካሙ ስለተሟጠጠ ከአልጋው ውስጥ መውጣት አልፈለገም። ሬዲዮ ከፍቶ እያዳመጠና በስልኩ ጌም እየተጫወተ እንደ ተጋደመ ቀየ። የረሃብ ሰሚት ቢሰማውም ወደ ኩሽና ገብቶ የሚበላ ለማምጣት ሰነፈ። ከራስጌው የነበረውን የተጀመረ ነካ ተነነጨና በጆሮባው ተንጋሎ፣ በእጆቹ የእግሮቹን ሓሩ ለመንካት ሲሞክር በደረቱና በሆዱ ላይ ያሉ ጡንቻዎች ተከፋፍለው አፈጠጡ። የማርሻል አርት ባለ ጥቁር ቀበቶ መሆኑን ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው የሚያውቁት።

መልሶ እንቅልፍ ሊወስደው ሲል፣ የሳሎኑ በር በሃይል ስለተንኳኳ ዘሎ ተነሣ። በሩን ሲከፍት ሰረጅም ጊዜ የሚያውታቸው የነጎንዮሚኒየሙ ዘበኛ ደንገጥ ብሎው ቆመዋል። በሩን ከፍቶ እየተጨናበሰ ሰላም አላቸውና ጥያቄ በተሞላው ፊት ሲያያቸው በቀኝ እጃቸው በያዙት ብትር ደገፍ ብለው

"ይሀና አደርክ ሳንችዬ ... የሆነ ትንሽ ልጅ ነው ይሀን መረቀት ስጥተኝ እዛ መንገድ ዳር ለቆሙችው ባለ ታክሲ ስጡት ብሎ የሄደው። መኪናዋን ሳያት ያንተ መስለችኝ። ደጅ ነው እንዴ ያቆምክ መኪናህን?" አሉ፣ በግራ እጃቸው የያዙትን የተጣጠፈ ወረቀት እየሰጡት።

"ይሀና አደሩ አባባ ... ምን ማታ ነ በጣም ከመሸ ነበር የገባሁትና ግዚው በጠላላ ሞልቶ ስለነበር፣ እዛ መንገድ ዳር አቁሚያት ነበር የገባሁት። የምን ወረቀት ነው?" አለ፣ ወረቀቱን ለመክፈት እየሞከረ።

"እዬ እንጃ ስመለስ ልጁም ባካባቢው የለም። የመኪናህን አራቱንም ጎማዎች አተንፍሰውታል። የኋላ ጎማው እንዲየውም ሳይቀደድ አይቀርም። የምን ጉድ ነው?" አሉ፣ ፊታቸው ላይ ግራ መጋባት እየተነበበ።

"የኔን መኪና? ..." አሰና ወረቀቱን ፊቱን አቀጭሞ ማንበብ ጀመረ። ንዴቱ በተስእየጋመ "ሺት ..." አለና ወረቀቱን ጨመደደው። "መጣው እስኪ ሜማ እድርጊ..." ብሎ ወደ ውስጥ ገባ። ልጅቹ ትምህርት ቤት ስለሄዱ ቤት ውስጥ ማንም አልነበረም፣ መኪናው ጋ ሲደርስ እንዳሉትም ጎማዎቹ ሁሉ ተንፍሰዋል። የቀኝ ኋላ ጎማው ተቀዳዷል። በተጨማሪም የኋላ መስተዋቱ ላይ በቀይ የስፕሬይ ቀለም በልብ ቅርጽ ላይ የተሰካ ቦርና መሃሉ ላይ 'ኤም' ነጥብ 'ጂ' የሚል ጽሁፍ አለ። እንደተናደደ የሰጡትን ወረቀት እንደገና አነበበው። ውልግድግድ ባለ የእጅ ጽሁፍ የተጻፈ አጭር መልእክት ነው። ተመሳሳይ በቦር የተመጋ ልብና ፊደሎቹ በቀይ ብዕር ተከትበውበታል። "ይሄን የሰጠዎትን ልጅ ያውቁታል?" ሲላቸው፣

"በፍጹም ያለ ዛሬም አላየሁት ልጄ። እኔ ወደ መኪናው ስመጣ የት እንደ ተሰለበም አላጠት። ልጆች ብጠይትም ማንም አየሁት የሚል ሰው አላገኘሁም፣ አንዲት ጥርኝ የማይሞላ ልጅ እነ ነው" አሉ፣ ግራና ቀኝ እያዩ።

@OLDBOOOKSPDF

በረጅሙ ተነፈስና ፡ "አባባ እንግዲህ ምን ይደረጋል ... እግዚር ይሰዋልኝ ... መሊናዋን ጋራጅ ማስመጣን ይኖርብኛልና እስኪ ከቻሉ ወይ አርስዎ ወይ ሉላ ሰው ፈልገው ያስጠብቁልኝ ። ልብስ ልተያረና ... መሣሁ" አለ ፡ ንጹቱና ግራ መጋባት ተቀላቅለውበት ። እቤት እንደ ገባ ተጥሎ ምን ማድረግ እንዳለበት ለማወቅ ትንሽ ጊዜ ወሰደበት ። ወረቀቱን ደጋግሞ እያነበበ ጥቂት ቆየ ። ማን እንደሆነ ቢያውቅም ፡ ሊያምነ ግን አልቻለም ። ልብሱን ከተያየረ በኋላ መጀመሪያ ፖሊስ መጥራት እንዳለበት አሰበና ትንሽ አመነታ ። ለማንኛውም ብሎ ምስጢር ጋ ደወለ ።

"እንዴ አንተ ሰው እደተኛበትም እንዴ ምንድነው በጠዋት ... አንተ አይደክምህም እንዴ?" አለች ፡ ካሊጋ ባልወጣ ድምጽ ።

"መኖ ለሁሉ ይደላል ብለሽ ... ይልቅስ እንዳትደነግጪ ... ገስ ዋት?"

"በናትህ ስኢዶ ... አትቀልድ ... እንትልፈን እንዳታጠፋብኝ ... ወየው·ልህ ግን?"

"ቀልድ ቢሆን በምን ዕድሉ ... መቀለጃ ሆኜ ነው እንጂ ። ሰው·ዬሽ ወደ እኔ ሳይዞር አይተርም" አለ ፡ የምጸት ሳቅ እየሳቀ ።

"የው እንግዲህ ... የምን ሰው·ዬ ነው በናትህ ... በማይቀለድበት አትቀልድ እሺ ... ኤፐሪል እንዳልሆነ ታቃለህ አይደል?" አለች ፡ ልቧ የሆነ ነገር እየፈራ ።

"እሺ ብዙ አላድክምሽ ... ከጥቂት ደቂቃ በፊት ዘበኛችን አንኳኩተው· ቀሰቀሱኝና ..." ብሎ ፡ የሆነውን ነገር ሁሉ ሲነግራት ጸጥ ብላ ቀረች ።

"ምነው· ዝም አልሽ?"

"በናትህ ... ደግሞ አንተን እዚህ ጉድ ው·ስጥ መጪመራ ነዋ ... የኔ ሳያንስ ... ምን አይነት ነገር ነው· ባካቹ ... ለፖሊስ ማመልከት አይሻልም መጀመሪያ? "

"እንቺ እይደለሽም ። እንቺማ ምን አደረግሽ? ፈሪና ደደብ ሰው· ብቻ ነው· እንደዚህ የሚያደርገው· ። ለዚህ ፖሊስ ምናምን አያስፈልግም ። የተማመነው·ን ተማምኖ አይደል ። እኔ ራሴ ነኝ ጉሮሮው·ን እንቲ የማናገዘው·"

"እሺ ... ረጋ በል ... ለመሆኑ ምንድነው· የሚለው· ወረቀቱ?" አለች ፡ ግራ እንደ ገባት ። ድምጹን ተየር አድርጎ አነበበላት ።

"አዲሱ የሚስጥር ቦዲ ጋርድ ... ይህ የመጀመሪያም የመጨረሻም ማስጠንቀቂያ ነው· ። ከሰው· አበባ ላይ ማር ለመቅሰም የሚሞክሩ ንቦች መጀመሪያ እግራቸው· እምቢ ካሉ· ደግሞ አንገታቸው· ይቀረጣል ። ማን መሆኔን የምታው·ቅ ይመስለኛል ። ካሁን በኋላ አጠገቢ እንዳት·ደርስ ተናተኛ በሆነው· የፍቅር አምላክ ስም አዝሃለሁ·"

ይሄው· ነው· የልቡ·ስ መልእክት ብሎ ሲሥት ፡ "በናትህ ሠኢዶ አት·ሣቅ ... ምን የሚያሥቅ ነገር አለ ። እሺ ምን ማድረግ ነው· የምትፈልገው? ለማንኛው·ም

@OLDBOOOKSPDF

ልምላልህና መኪናውን ቢያንስ ወደ ጋራጅ እንላክው። የኔ ድንበኛ አለ ... ልምጣና ደውልንላቸው ትተህው ጋራጅ ሊያደርስልህ ይችላሉ። አርግጠኛ ነህ ለፖሊስ ማመልከት አትፈልግም?"

"ያማ የፍርሃት ምልክት ነው ... ተዪው ምናልባት የሆነ ዐታ ሆኖ እየተከታተለኝ ነው። ምማ ማስቀየር ነው አይደል ... ከዛ እናያለን። በታ አቤት እጠበቅሻለሁ ከመጣሽ።" ትንሽ ካወሩ በኋላ፣ ነገሩን ለናቷ እንዳትንገር ተስማምተው ስልኩን ዘጉት። ማረፋፈጃው ላይ መኖታ መኪናውን ጋራጅ አስመስያው፣ ለምሳ አብረው ቀይና ተከታትለው አዲስ የሚገዙ ዕቃዎችን ለመረከብ ወደ ክሊኒኩ ሄዱ። ስለሚከታተላት ስው የምታውቀውን ሁሉ ነገረችው። ከክሊኒኩ ጆርባ መዳለው ሜካ ቀስ ብሎ እየተራመዱ

"ቀይ አንቺ በትክክል አይተሽው ታውቂያለሽ? አሁን መንገድ ላይ ብታዩው ታውቂዋለሽ?"

"አብረን ተምረናል ስልህ ... ለኔ የየቀኑ ትገቡ ነበር። እሱን የማላይበት የት ልድረስ እስክል የሰለቸኝ ስው ነው" አለች፣ ጠበቅ ባለ ድምጽ።

"እስኪ ምን ይመስላል ... ማለቴ መልኩ ምናምን?" አለ፣ ሲሰለው ምክር ስላልቻለ።

"በታ ምንም የተለየ ነገር የለውም ... አማካይ አበሻ ነው። ግን ደግሞ የሆነ የማይሰሞች ነገር አለው። ጠይም ... ዘርዛራ ቢጫ ጥርስ ... ሰፊ አፍንጫና ትንንሽ አይኖች ... ረጅም ቁመት ... ሲራመድ ሀይሙት የከበደችው ይመስል ገበጥ ያለ ድምፁ በየመሃሉ የሚሰልል ጉርናና ነገር ... ብቸኛ ... የወየበች ቀይ ቀብና በኢትዮጵያ የቀጸ ጽኪት መስራት ሲጀመር የተገዛች፣ አሮጌ ጨምዳዳ ሌዘር ጃኬት ዘወትር የሚለብስ ... ብዙ ጊዜ ደማቅ ቀለም ያላቸው ቀበቶና ጫማ ማድረግ የሚወድ ... አይበቃም?"

"ኦሆሆሆ ... ሳልሽው እኮ ... ቀይ እኔ የምለው ... አንቺን ብቻ ነው ወይስ እዛ ክሊጅ እያላችሁ ሌላም ስው ያስቸገር ነበር?" አለና ከኪሱ ውስጥ ሶፍት ወረቶት አወጣ። ጎንበስ ብሎ ጠረግ ጠረግ አደርጎ ካንድ ድንጋይ ላይ ቁጭ አለ።

"ሁለት ልጆች በሱ ምክንያት ትምህርት አቋርጠው ወጥተዋል። ሲገባ ሲወጣ እዛ ግቢ ውስጥ ሰባት ስምንት አመት አይሆንም ብለህ ነው የኖረው። ያው ባለስልጣን ዘመድ ስላለው ይሁን አላውቅም፣ ማንም ጠንካራ ርምጃ ሊወስድበት የደፈረ ሰው የለም። አንዷንማ ከግቢ ውጪ ከጓደኞቿ መሃል ገትሮ አንዴት እንደ ደበደባት አትጠይቀኝ። የክፍለ ሃገር ልጅ ስለ ነበረች ጥላ ከመሄድ ውጪ ምንም አማራጭ አልነበራትም። እኔም አንድ ሁለት ጊዜ ጥሬ ተምሻለሁ" አለችና፣ ሀሞሙ እስኪወጣ ያለ ያህል ጉንጯን አባበለች።

"እና ምንም አልተደረገም?" አለ፣ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ።

"እይ ሰኢዶ ... እዚህ አገር ሰት ልጅን ባይባባይ መደብደብ ምን ነውር አለው

@OLDBOOOKSPDF

ብለሀ ነው? የጠላት ብቻ ሳይሆን ወዳጅኳት ያለ ሁሉ ደብዳቢ ነው ... ከባ ስትከስ ደግሞ ስለሚወድሽ ነው ትባላለህ። ነገሩ ከቤት ይጀምራል። ባል ደብዳቢ ነው ...ወንድም ደብዳቢ ነው ... አባት ደብዳቢ ነው። ተወኝ ባክህ ... የዚህ የለየለት ስለሆነ ነው እንጂ ሁሉም ያው ነው። ወንዶች ግን ለምንድ ነው በዱላ የምታምኑት?"

"የምትዪው ይገባኛል ... መልሱን ግን አላውትም። እኔ የማውተው ስደበደብና ስደበደብ ማደጌን ብቻ ነው። ምናልባት ... እኔንጃ..." እጅቹን ከፍ ዝቅ እያደረገ ጥያቄውን ለመጀመሪያ ጊዜ የምር እያሰበ ጥቂት ጸጥ አለ። "ቀይ ሰውዬው ግን ጤነኛ ነው? ሰው እንዴት ይሄንን ሁሉ ዓመት ... መዝገዝ ይላል?"

"አላውትም ... ማወትም አልፈልግም። የሚታየኝ በታ ከዚህ አገር ለቀ መሄድ ብቻ ነው። ካሁን በኋላ ከሱ ጋ አይጥና ድመት መጫወት አልችልም" ብላ ፣ ድንገት ማልቀስ ስትጀምር የሚያደርገው ጠፋው።

"እንዴ ... ኧረ በናትሽ ... በታ በታ እሺ ... እሱን እንተወውና ሌላ ነገር እናውራ ..." ብሎ ፣ አቀፋትና ጀርባዋን መታ መታ እያደረገ ሊያባብላት ሞከረ።

ለቅሶዋ ሲበርድላት ድንገት ዘት ብላ ሳቀች። "ቀይ እስኪ ... እሺ ብለው ግን ምን ሊያደርገኝ ነው? አይ ቲንክ እሺ ብዬው የሆነ የሚያስተኛ መድሃኒት ሰጥቼው ... እስር አድርጌ አርባ ከገርፈኩት በኋላ ... እየተንፋረቀ ሲናዘዝ ቪዲዮ ተርፀጽ ከዚህ በኋላ ብታስቸግረኝ ..." አለችና ሃሳቧ ስላላረካት ጥቂት አሰበ ፣ "ወይ በታ ሚኒካ ውስጥ እስር ጅብ እንዲበላው መተው ነው ..."

"ጅቦቹ ፈርተው ቢተጢት ወይም አይጣፍጥም ብለው ፈተውት ተመልሶ ቢመጣስ?"

"ሂድዛ ... እይለቱትም ፣ አግኝተው ነው" አለችና ትከሻውን ቁንጥጥ አደረገችው።

"አይ ጅቦች የራሳቸውን ዘር አይበሉም ብዬ ነዋ" ሲል ፣ ሁለቱም እንደ ሞኝ ሳቁ። "ስውዬው እኮ ግን የምር ታሞ ሊሆን ይችላል። ለዶክተር ሌላ አማዘረሽው ታውቂያለሽ?" አለ ፣ የተለየ አማራጭ ስላልታየው።

"ምን ብዬ ነው የምነግረው? እኔ እናቱ አይደለሁ ... በሽታ ቢሆንስ ምን ላደርግ እችላለሁ?"

"አይ ... ዩ ነቨር ናው ... የሆነ ከሳይኮሎጂ አንጻር ... ከልምዱም ጥሩ ሃሳብ ሊሰጥሽ ይችላል።"

"በዚ ጉዳይ እኮ ያላነበብኩት ጽሑፍ የለም። አይ ዶኖ ምናልባት በለው ላይ ከሚደርሱ በታዮች ከፍተኛ ከሆኑት ውስጥ ነው ባይ ነኝ። የገዛ ጥላህን እየፈራህ ነው የምትኖረው። ውስጥህ ከሚፈጠረው ፍርሃት ሊያድንህ የሚችል ምንም ነገር የለም። የቀን ሕይወትህን ብቻ ሳይሆን የማታ እንቅልፍህን ሁሉ ነው የሚመርዘው። ነፍስህ ከውስጥህ በስጋት ስትመነምን እንተ ብቻ ነህ የምታውቀው።

@OLDBOOOKSPDF

"ነብሰይ እንደኛ ባለ ህብረተሰብ ውስጥ ሰብ ልጅ ሰትሆን ፣ ልክ የራሳ ፍላጎትና ፈቃድ እንደሌለህ ፣ ደስ ያለው ሁሉ ተነስቶ በፍትር ስም አዘላህን ሲያሳይህና ሲያስፈራራህ አስዘሙ ። በዛ ላይ የምትሰማቸው ታሪኮች አሉ ። "እንትናን ወጂት እንዚ ስላለችው ዘጠዜ ውጣ ሃደላት" የመሳሰሉ ታሪኮች የሚፈጥሩብህን ፍርሃት አስዘሙ ።

"በዛ ላይ ቤት መናገር አትችል ፣ ምክንያቱን ራሳቸውም ሰለሚፈሩ ይሁን አላውቅም እንተኑ ነው መልስው የሚወንጅሉህ ። አለበለዚያ ደግሞ በግለፍተኝነት የማይሆን ርምጃ ወስደው የበለጠ ስቃይ ዘውስጥ ይከቱሃል ። ይሄ ሃሰተኛዪ መሰለኝ ፣ ዘሃይ ሰኩል ጀምሮ ... ምን ማሳዜት አሳዬ ላይ እንዳለ አላወቅም ...በሽተኛ በሽተኛውን የሚሰብ ..." ብላ ፣ በንዴት የተደገፈችውን ዛፍ በካልኮ አተመሰችው ።

"ምናልባት ቁንጅና የሚባል ምትሃትና ደግነት የተባለ ማሜኔት ይሆን ያለብሽ"

"ሂድባ ... እናንተማ ምን አለባችሁ ..." ብላ ፣ በጂ የምትቀነጣጥበውን ቅጠል ወረወረችበት ።

"እንዴት ምን አለብን? ... ይሄው ባንድ ጠዋት አራት ገማ አጣን ... እርፈን ከልተቀመጥን ደግሞ ዛቻውን አይተሸው የለ...?"

"ቀልድ ... ብቻ ምን ልበልህ ፣ አንድ ለሞን በዚህ ዙሪያ የተሰሩትን ሙሺቃች ብትል ... ምን ልበልህ ያላነበብኩት መጽሐፍ አልነበረም ። ኢክስፐርት ሆኜልህ ነበር ፣ የሚያላዝነው ነገር ግን ፣ የራሴ ሰውዬ ሊገባኝም ሊተወኝም አልቻለም ። የትስ እቤት ትላለህ ። በተለይ እበጀህ የሚለው ደንዝ ቤተሰብ ከሆነ ያለው ... ምን ታደርጋለህ አለች ፣ ስሜቷ እየጋለ ።

"እና ጥናቶቹ የሚሉት በሽታ ነው ወይስ?"

"ዊል ብዙ ዓይነት ነው ከፍፍሉ ... እሱማ የጤና ሲሆን አይችልም ... ከሁሉ ግን የፍቅር ልባስ የተጠናወተውና የበቀልና እንዴት ተናቅሁ የሚል የበታችነት ስሜትን የተላበሰ ከሆነ አደገኛ ሲሆን ይችላል ። ብዙ ጊዜ ደግሞ መሰረቱ ቢስ በሆነ ተስፋና እምነት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ተደራድረህም ተከራክረህም የምታመጣው ለውጥ የለም ። የምር የእእምሮ ህመም ታማሚ ሲባሉ የሚችሉ ግን ብዙ አይደሉም ፣ በአብዛኛው ቀስ ቀስ እያለ የተዛባ የሰብእና እድገታቸው በተንሻፈፈ ምኞት ሲመረዝ የሚፈጠር ወልጋዳ ስሜት ነው ። የጎብረተሰብን ሞራን እስተሳሰብና የህግ ደዘኖት የሚጠቀሙ የማፍቀርና የመፈተር ሃላፊነትን መሸከም የማይችሉ ሉዘሮች ባህሪ ነው ስትል ፣ አይኑን ፍጥጥ አድርጎ ፣

"እስኪ እሰኪ ድገሚው ... ሆ ሆ ... ሚስጥር የተጻፈ ነገር የምታዚ ነሮ የሚመስለው ..." ብሎ ፣ በሁለት እጁ ተከሻዎቿን ነቀነቃት ።

"አቢት ማጋነን ስትወድ ... በል ይልቅስ አሁን ሳይመሽ እንሂድ ። ማሚ ስለ ቦታ ራት ስላላት አብረን እንሂድ ብላኛለች ። ታዙ ታለህ ከሁሉ ማነ እንደሚያሰጨነ የሚሰማቸውና የሚያምናቸው ልጅዋ ነህ ። ሃይ ስኩል ውስጥ ያለውን ፈተና

@HARBOOKSPDF

መከራ እኮ አታምንም ። የማንም ለሀጫም ሁሉ ኮ ነው ... ልክ እንደገባህ አታ 'እንቺ ነይ' ... ምናምን ብሎ ከፈለገ ከጓላህ መጥቶ የፈለገውን የሰውነትህን ክፍል ልክ እንዳስቀመጠው እታ የሚይዘው ። መቼ ከዚህ ደነገ አስተሳሰብ እንደምንላቀቅ አላውቅም " ብላ ፣ ወደ መኪናቸው ተመለሱ ። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለ ያያቸው ነገሮች ትዝ አሉት ።

"በርግጥ በጣም ብዙ እንደምታውቂ አውታለሁ ... ግን ለማንኛውም ዶክተር ሌላ ሲመጣ ብናወራው ፣ መመካከሩ ጥሩ ሊሆን ይችላል ። ደግሞ አይዞሽ ... ዝም ብሎ ቡፋውን ሲነፋ ነው" አለ ፣ ውስጡ ያለውን ስጋት እንደ ምንም ደብቆ ፣ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ ።

"ታንክ ዩ ..." ብላ ጆርባውን መታ መታ አደረገችው ። ሁል ጊዜም ቢኖረኝ ብላ የምትመኘውን ወንድም እንዳገኘች ተሰማትና ፍርሃቷ በመጠኑም ቢሆን ረገብ አለ ። የጓሮውን በር ከፍተው ወደ ክሊኒኩ ሲገቡ "ኦ ማይ ጋድ ... እኔ ኮ አላምንም ... የዛሬ ወር እኮ ይሄን ጊዜ ክሊኒኩ ሥራ ጀምሯል ። ይታየኛል ..." ብላ ፣ ፊቷ ተስፋና ደስታ ተቀላቅሎበት ፍክት አለ ።

ወደ ዋናው ሳሎን ሲገቡ የህመምተኛ መቀያ ወንበሮቹ ላይ ቁጭ ብሎ ድምጹን እንደ ትልቅ ሴት ወይዘሮ ቀየረና ፣ "ምንድነው ከመጣሁ እኮ ይሄው ሦስት ደቂቃ ሊሆነኝ ነው ። ዶክተሩ የሉም እንዴ?" ሲል ፣

ድምጿንና አካሄዷን እንደ ሌላው አድርጋ ፣ "ይቅርታ ወይዘሮ ሳንችነት ... አስቸኳይ ጉዳይ ይዞኝ ነው ። በዚህ በኩል ይምጡ ..." ብላ ፣ እጇን ስትዘረጋለት ተከታትለው እየተሳሳቁ በሩን ቀልፈው ወጡ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 23 ፡

ከእናቷ ጋር የተጋበዙበት ራት ላይ አምሽተው ወደ ቤት ሲመለሱ አምስት ሰአት ሊሆን ምን አልቀረውም ነበር ። ወደ ሰፈራቸው ሲደርሱ መብራት ጠፍቶ ስለነበር አካባቢው አልፎ አልፎ ውርውር ከሚሉ መኪኖች ብርሃን በስተቀር ጨለማ ነግሦበታል ። ከዋናው መግቢያ ሲደርሱ እንደ ልማዷ መስኮቱን ገቅ አድርጋ ዘበኛውን ሰላም ስትላቸው ፣ "የኔ ልጅ ... ቀዪኝማ አንዴ ..." ብለው ፣ ከትንሿ ቤት የሆነ ነገር በእጃቸው ይዘው ጠጋ አሉ ። "ይችን ላንቺ ይስጡልኝ ብለውኝ ነው አንድ ልጅ እገር ሰውዬ" ብለው የታሸገች ፖስታ ሰጧት ። ውጭው ላይ ምንም የተጻፈ ነገር የለውም ፥ ነገሩን በዝምታ ሲከታተሉ የነበሩት እናቷ

"ደግሞ የምን ፖስታ ነው በዚህ በጨለማ ልጄ?" አሉ ፣ መኪናው ዳሽ ቦርድ ላይ ጣል ስታደርገው ባይናቸው እየተከታተሏት ።

"እኔ እንጃ ማሚ ... ወይ የቢሮ ሰዎች ይሆናሏ ... ምን ይታወቃል ብለሽ ነው?" አለች ፣ ስለደከማት አልጋዋ ብቻ እየታያት ። ቤት ገብተው ትንሽ እውርተው ሁለቱም ደክሟቸው ስለነበር ጉንጯቸውን ሳም አድርጋቸው ወደ የመኝታ ክፍላቸው ገቡ ። ለመተኛት ተዘገጃጅታ ስትጨርስ አልጋዋ ላይ ከውጪ ጋደም ብላ የቀን ውሎን እያሰበች ትንሽ እንደ ቀየች ጥበቃው የሰጧት ደብዳቤ ትዝ አላት ። ከልጋዋ ላይ ተስፈንጥራ ወረደችና ደብዳቤውን ከመኪናው አውጥታ እግረ መንገዷን በብርጭቆ ተዝቃዛ ውሃ ይዛ ወደ መኝታ ቤቷ ተመለሰች ። ውኃውን ከራስጌዋ አስቀምጣ ትራሷን ተደግፋ አልጋዋ ላይ ተቀመጠች ። ፖስታውን ቀዳ የተጣጠፈውን ወረቀት ስትከፍተው ፣ "ኦ ማይ ጋድ ..." ብላ መልሳ ዘጋችው ። የምታውቀው የጅ ጽሁፍ ነው ፥ ድንጋጤው ሰቀቅ ሲያደርጋት ፣ እንደ ምንም ጨክና ከፈተችውና ማንበብ ጀመረች ፥

"ምንም እንኳን ፍቅርን የፈጠረ የትናት አምላክን የሚያበሳጭ ድርጊት ብትፈጽሚም ዛሬም የኔ ልዕልት ብዬ ስጠራሽ ልቤ በደስታ

@OLDBOOOKSPDF

ይሰክራል። ግን ምን ያህል እኔን ለማስቀናት ብታስቢ መይንም ደግሞ ለሚንቀልቀል ፍቅሬ ንቀት ቢያድርብሽ ነው ካልጠፋ ሰው ከታክሲ ሾፈር ጋር፣ ለዛውም እዚህ ግባ የማይባል ድፍንድፍ ጎረምሳ ጋር የምትማግጪው። በተቻለኝ አቅም ልተውሽ የምችለውን ሁሉ ሞክሬ፣ ከአንድ ለመት በላይ ለረሳሽ ሞዘራ ነበር። ደግሞስ ከናት አባትሽ ሃይማኖት ውጪ የምትሄጂው ለኔ ያለሽን ንቀት ለማሳየት ካልሆነ ሌላ ምን ትርጉም ሊኖረው ይችላል።

"ቀይ በመልክ ብትዪ በትምህርት ደረሻ፣ በእምነት ብትዪ በጨዋ ልጅነት ከእኔ በምን ተሽለሽ ነው? ድሮም ሴቶች ስትባሉ እንደ አሀያ በጋ ከብር አይወድላችሁም። ከዱርዬ መዋል ከዋልጊ መባለግ ገና ስትፈጠሩ ደማችሁ ውስጥ ነው ያሰው። ይሄ ሁሉ የሚያረጋግጥልኝ ምን ያህል ፈጣሪ አንቺን በኪነ ጥበቡ ሲከይንሽ፣ አሳምሮ ሲፈጥርሽ ለኔና ለኔ ብቻ እንድትሆኚ፣ አለም ከመፈጠሩ በፊት መወጠኑን ነው።

ስለዚህም ላለፉት ሁለት ወራት የሚቻለኝን ሁሉ አድርጊ ዝግጅቱን ጨርሻለሁ። በትርቡ ከእውነተኛ አፍቃሪሽ አቅፍ ውስጥ ትገቢያለሽ። ለዚያ ድቡልቡል ታክሲ ነጂ ባሬ ጠዋት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ብስጠውም አብራችሁ መዋላችሁን አወ·ታለሁ። እሱም የሚገባውን ቅጣት ይቀበላል። አንቺና እኔ ግን ፈጣሪ በመጠነልን መሰረት፣ በትርቡ በፍቅር ደሴት ላይ አለማችንን ስለምንተሟሙ ተዘጋጂ። የቀረውን ለኔ ተይልኝ። ያንቺው።"

ይልና በቀይ ብዕር በሳንኾ ታክሲ ላይ በስፕሬይ ከተሳለው በጦር የተወጋ ልብ ቅርጽ ስር ፊርማው ሰፍሯል። ደብዳቤውን ስትጨርስ የማታውቀው ፍርሃት ወረራት። ሳንቾ ጋ ለመደወል እስባ ሰአቱ በጣም ስለሄደ እመንትታ ተወችው። እናቷ ጋሄዳ ለመተኛት ብትፈልግም፣ ነገሩን ከጠረጠሩ ወይ ደግሞ ሳታስበው ብትነግራቸው ሊረበሹ ይችላሉ ብላ ስላሰበች የምታደርገውን እጥታ ቀየች። ጸጥታው ስለ ረበሻት ከስልኳ ላይ ሙዚቃ ከፈተችና ቁጭ ብላ ለብዙ ደቂቃዎች ደብዳቤውን እንደ ያዘች ቀየች። ማልቀስ ቢያሰኛትም ፍርሃቷ ንሮ እላስለቅስ አላት። ፊቷን በቀዝቃዛ ውሃ ታጥባ በጀርባዋ ጋለል ብላ እንደ ተኛች ደከሟት ኖሮ ብዙም ሳይቆይ ደብዳቤውን እንደ ያዘች እንቅልፍ ይሏት ሄደ።

ሌሊት ላይ የተንኳኳ ነገር ሰምታ ብንን ስትል የመኝታ ቤቷ መስኮት ተከፍቶ ንፋሱ መጋረጃውን ከመስኮቱ ጋር ወዲያ ወዲህ ሲያደርገው እየችና ዘላ ተነሳች። ፍዝዝ ባለው የራስጊ መብራት ስታይ ምንም ነገር ማየት ስላልቻለች ተንፈስ ብላ ዋናውን መብራት አብርታ ዙሪያ ገባዋን አይታ ወደ መስኮቱ ሄዳ ጥብቅ አድርጋ ዘጋችው። መጋረጃውን በትክክል ግጥም አድርጋ ሸፍና፣ ዋናውን መብራት እጥፍታ ወደ አልጋዋ ዞር ስትል ትልቅ ስለት የያዘ ሰው ከራቷ ተገትሮ ስታይ ደርቃ ቀረች። ልትጮህ ስትል ይደባለቃው ብርሃን የሚብለጨለጨውን ቢላዋ እያወዛወዘ ትልቅ ጣቱን ወፍራም ከንፈሩ ላይ አስቀምጦ፣ "ስስስስስ" ብሎ ሲጠይቃት እንድትቀመጥ ጠቆማት። ከአጠገቧ ተቀመጠና ሳቅ አለ። እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል ሲያደርገው በፍርሀት ሽምቅት

@OLDBOOKSPDF

አለች ። የምታውታቸው ዘርዛራ ጥርሶቹ ከፊት ይልት ተዘርገረው የሰነፍ አዮር መስለው ታዩዋት ።

"በትርብ እንነናኖለን ስልሽ አላመንሽኝም ነበር እይዶል?" አለና አልጋው ላይ ተዘርግቶ የወደቀውን ደብዳቤ እንሰቶ "የኔ ልዕልት ... ምን ያህል ብናፍቅሽ ነው ደብዳቤዬን አቅፈሽ የተኛሽው?" ብሎ ሊስማት ጠጋ ሲል ፊቷን አዞረች ። እንዲን በትልት መዳፉ ይዞ ጉንጯ ላይ ሳም ሲያደርጋት ፣ የከንፈሩ ትዝትዚ እስከ እጥንቷ ተሰማት ። "አውን ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል ። ከዚህ ቶሎ ወጥተን መሄድ አለብን ሲላት ፣ በፍርሃት በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ፣

"እኔ ከዚህ የትም አልሄድም" ስትለው ፣ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ እንገቱን ዘንበል ፣ አፉን ጠምም አድርጎ ፣

"መሄዳችንማ የግድ ነው ፣ የኔ ፍቅር ። ምናልባት የማይሆን ነገር እንዳትሞክሪ እንዳንድ ነገሮችን ልንገርሽ ። አዲሷ ሠራተኛችሁ የኔ ቅጥር ናት ... እሷን አትቁጠሪያት ። እንዴት እንደገባሁ ለማወቅ አያዳግትሽም ብዬ አስባለሁ ። ዘበኛችሁና ሌላዋ ሠራተኛም እስከ ነገ ማታ እንቅልፋቸውን እንዲለጥጡ ፣ ከቢራ ጋር የሚቀመም ነገር ተስጥቷቸው እያንኮራፉ ነው ። ለእናትሽም ከመኝታ በፊት የለመዱትን አረገባኗ ሻይ ፣ ከእንቅልፍ መድሃኒት ጋር ቀምማ ስለሰጠቻቸው ፣ ለሽ ብለው እንደተኙ አረጋግጬ ነው እንቺ ጋ የመጣሁት ። ስለዚህ ብዙ የማይገባ አምባጓሮ ሳንፈጥር ፣ እነዚ ተከባበርንና እንደ ተዋደድን ቀሰ ብለን እንውጣ" ብሎ ፣ ካልጋው ላይ የወደቀውን ደብዳቤ በጥንቃቄ አጣጥፎ ኪሱ ውስጥ ከተተው ። ወደ ራሷጌዋ ሄዶ የልጅነት ፎቶዋን እንስቶ ሳም አድርጎ መልሶ አስቀመጠው ። ከዛም ስልኳን ከሃይል መሙያ ሽቦው ላይ ነቅሎ ወደ ኪሱ ከተተው ።

ቀን ከሳንቾ ጋር ያወሩት ሁሉ አንድ ባንድ በውስጢ አለፈ ። ደብዳቤውን እንዳነበበኩት ምነው በደወልኩለት ወይም እናቴ ጋር ሄጄ በተኛሁ ብላ ተጸጸተች ፣ ዘመዶቻቸው ቤት እደሩ ሲባሉ ቢያድሩ ኖሮ ፣ ከዚህ ሁሉ ጉድ ታመልጥ እንደነበር አሰበች ። ከእንቅልፋቸው ሲነቁ እናቷስ ምን ይላሉ ? እነ ሳንቾና ሌላው ሁሉ ለትጽበት ትዝ አሏት ። ከንጹን ይዞ ሲያስነሳት ከሐሳቧ ባነነች ። በደመ ነፍሷ እየተከተለችው ሰመጨረሻ ጊዜ መኝታ ቤቷን ዞር ብላ ተሰናብታ ወጣች ። የናቷ መኝታ ቤት ጋስትደርስ ቀም ስትል በሩን ከፈተና ዋናውን መብራት አብርቶ "ካላመንሽኝ እዩ ... እንደዛሬውም ተኝተው አያውቁ ..." ብሎ ጠጋ አድርጎ የሚያንኮራፉ እናቷን ሲያሳያት ሁሉም ነገር ያሰቱ ጉዳይ መሆኑን አመነች ። መብራቱን አጥፍቶ ከንጹን እንደ ያዘ ደረሻውን ወርደው ፣ በሳሎኑ በኩል ዋናውን የበረንዳ በር ከፍቶ ወጡ ።

የውጪው በር ላይ ሲደርሱ ገርበብ ያለውን የዘበኛውን ቤት በር በእግሩ በረገደው ። በጀርባቸው ጋለል ብለው ወደሚያንኮራፉት ሽማግሌ በአገዉ ጠቀሳት ፣ ሳቅ ብሎ በትልቅ ብርሌቅ ተቁድቶ ያላለቀውን ቢራ ብድግ አድርጎ አሸተተው ፣ የውጪውን በር ከፍተው ወጡ ። ከውጪ ቀልፎት ቁልፉን በላይ ወረወረው ። እሱ

@OLDBOOOKSPDF

አስቀድሞ የኋላ መንበር ላይ ተቀመጡ። መኪናዋ ስትንቀሳቀስ ወዶ ኋላ ሀር ብላ ገቢያቸውን ባይኗ ተሰናበተች። መኪናውን የምትሸፍረው ሴት መሆኗን አይታ ገረማት። ከገኗ የተቀመጠችው በትርብ የቀጠሯት የቤት ሠራተኞቸው ነበረች። እሁን ያላት ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን ይበልጥ አመነች። የመጪረሻውን የዘብ ኬላ አልፈው ሲወጡ ውስጧ የቀረው ተስፋ ሁሉ ተሟጦ ጠፋ።

ወዶ ሲ ኡም ሲ አትጣጫ እዙሪው ፍጥነታቸውን ጨምረው ሲገሰግሱ ከኪሱ ውስጥ ጥቁር ሻሽ አወጣ። "ከዚህ በኋላ ወዴት እንደምንሄድ ማወቁ ስለማይጠቅምሽ አይነሽን ማሰር ይኖርብኛል። ከዛ ውጪ የማይሆን ነገር እደርጋለሁ ብለሽ እስካልሞከርሽ ድረስ ሴፍ ነሽ" ብሎ አይኗን በሻሹ ሸብ አደረገና አጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ ጸጥ እንዳሉ ጉዟቸውን ቀጠሉ።

ግማሽ ሰአት ያህል ከነዱ በኋላ ለሌላ ግማሽ ሰአት አካባቢ ኮርኮንች በሚመስል መንገድ ላይ እየነጠሩና እየተንገጫገጩ ነዱ። ፍጥነታቸውን እየጨመሩና እየቀነሱ ... እየተጣጠፉ ሲሄዱ ቆይተው ድንገት ቀጥ አሉ። ከመኪናው ሲወርዱ ዓይኗ ላይ ያሰረውን ሻሽ ሲያወርድላት የት እንዳለችም ለማወቅ አልቻለችም። ለመጥለት አፋፍ ላይ ባለችው ዶብዛዛ ጨረቃ ብርሃን በአካባቢው የሚታይ ሌላ ቤት እንደሌለና ከቤቱ ጀርባ ያለውን ሜካ ለማየት ብቻ ችላለች።

ቤት ከገቡ በኋላ ከመደርደሪያ ላይ ያለውን ትልቅ ፋኖስ ለኮሰው። ሁለቱ ሴቶች ከወደ ጥግ ያሉ በርጩማዎች ላይ ቁጭ ቁጭ አሉ። ባይናቸው የሆነ ነገር ተነጋገሩ። አገዲት ሻማ ለኩሶ መደርቢ ተጠጋ። ባንድ እጁ ከንጁን አፈፍ አድርጎ ወደ ጓዳ ከለ እንድ ከፍል ይዟት ገባ። "እዚህ ጠብቂኝ። የሞኝ ሥራ ለመሥራት እንዳትሞክሪ" ብሎ በሩን ዘግቶባት ተመልሶ ወጣ።

ክፍሏ መስኮት የላትም። ጣራው በሞስ የጠቀረና ከፍ ያለ ነው። ክፍሉ ውስጥ ከሰው የሰፖንጅ ፍራሽና አግዳሚ ወንበር በቀር ምንም ነገር የለም። ትንሽ እንደ ቆየ ሳሱን ቤት ውስጥ የጋለ ከርከር ሰማች። ምን እንደሚያወሩ ለመስማት በሩ ላይ ጆሮዋን ለጠፈች። የሚሉትን ልትረዳ አልቻለችም። በሩን ለመክፈት ሜን ሜን ስትለው ከውጪ መቆለፉን አወቀች። 'የሞኝ ሥራ ለመሥራት እንዳትሞክሪ' ያላት ትዝ አላት። ተመልላ አግዳሚ ወንበሩ ላይ ተቀመጠች።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከውጪ ያሰው በር በሃይል ተዘጋ። ብዙም ሳይቆይ መኪናዋ ጮሃ ስትሄድ ተሰማት። በከፍተኛ ድምጽ እየተሳደበ ወዳለችበት ክፍል ሲመጣ፣ ኮቲውን ሰምታ ውስጧ በፍርሃት ራደ። በሩን ከፍቶ ሲገባ አስና መልሶ በሃይል ደርግሞት ወደ ሳሎኑ ተመለሰ። ወደ በሩ ጠጋ ብላ ቢታየው በሩ አስመቀለፉን አረጋገጠች። ወደ መደርደሪያው ተጠግቶ ፋኖሱን ሲያጠፋ ሲታገል የመውጫ በሩን አትጣላ በጥንታቱ ሳማየት ሞከረች። ልክ ፋኖሱን ሲያጠፋው እሷም ሻማውን አጠፋችው። በሩን ከፍቶ ሲገባ ከፍሉ በጨለማ ተውጧል።

"ሻማው'ን ምን አጠፋው" ብሎ ሲያንባርቅ፣

@OLDBOOOKSPDF

"እ...ኔ ምናው ታስሁ" አለች ፣ ድምፅዋን በፍርሃት እንደሚንቀጠቀጥ አድርጋ።

በሩን እንደ ተከፈተ ትቶ ወደ ሳሎኑ ተመለሰ። ተከትላው ቀስ ብላ ከከፍሉ ወጣችና ከጥግ አካባቢ ልጥፍ ብላ ቆየች። የበራውን ፋኖስ ይዘ "ጨለመብሽ ቤ ልዕልት ..." እያለ ወደ ነበረችበት ክፍል ገባ። ኮቴዋን ቀስ አድርጋ ወደ ዋናው በር ፈጠነች። "የው የሞኝ ሰራ እሠራለሁ ብለሽ ፍቅሬን ወደ ቱጣ እንዳትቀይሪው" ሲል የመውጫ በሩን ለመክፈት ታገለች።

ፋኖሱን እንደያዘ ወደ በሩ ሮጠ። የፋኖሱ ብርሃን ወገግታ በሩን ለመክፈት ረዳት። እየሮጠች ስትሮጥ ተከትሏት ወጣ። የያዘውን ፋኖስ ሜዳው ላይ አሽቀንጥር "ብትቀሚ ይሻልሻል ... ዛሬ" እያለ ተከተላት። ከዋናው መንገድ ወጥታ ወደ ጫካው ገባች። ከኋላ የሱ የስድብ ጩኸት ፣ ከፊቷ ደግሞ ከሩት የሚሰማ የጅቦች ጩኸት ሆዷን በፍርሃት አገላበጠው። ነፍሷን ለማዳንና ለመኖር የሚደረግ የሞት ሽረት ተጋድሎዋ አይሉ ፣ ወደ ፊት ጥላው ገሰገሰች።

የሱ ድምጽ እየራቀ መጣ። የጨለማውና የጫካው አስፈሪነት ውስጧን አራደው። ዛፍ ላይ ወጥታ ሌሊቱን ለማሳለፍ አሰበች። ለመውጣት የማይመቹ ችፍግ ያሉ ቁጥቋጦዎች ሆኑባት። ከፊትና ከኋላ አስፈሪ በሆኑ የማታውቃቸው ድምጾች ተከበበች። እየተንቀጠቀጠች ቀጥ ብላ ቆመች። እየቀርቧት ያሉት ድምጾች የተቆጡና የተራቡ መሆናቸውን ውስጠ ልቦናዋ ነገራት። ከፊት ለፊቷ በቅርብ የሚታያት ጥላ እየቀረባት መጣ። ጩኸቷን ስትለቀው ዘሎ ተከመረባት። ከላዩዋ ላይ ገፍትራ ለማንሳት አንገቱን ጨምድዳ እየታገለች ሳንቃዋ እስኪሰነጠቅ ጮኸች።

ከመኝታ ቤታቸው ጩኸቷን ሰምተው የመጡት እናቷ ትከሻዋን እየነቀነቁ ሲቀሰቅሷት በላብ ተዘፍቃ ነበር። እቅፋቸው ውስጥ ሆና ፣ ለረጅም ደቂቃዎች ያለማቋረጥ እየተርገፈገፈች እንደ ሕፃን ልጅ አለቀሰች። ነፋሱ እያላጋው በመጋረጃው የተጠላለፈውን የመኝታ ቤቷን መስኮት ተነስተው ዘጉት። ወደ ራሳቸው መኝታ ቤት ደግፈዋት ሲሄዱ ህልምና እውኑ ተደባልቀባት ነበረ። ከአስፈሪ ህልም እንደነቃች ለማወቅ ረጅም ደቂቃዎች ወሰደባት። በየመሃሉ ስትንቀጠቀጥና ስትደነበር ፣ እንቅልፍ ባይናቸውም ሳይዘር ነጋ። ጠዋት ላይ የደብዳቤውን ጉዳይና ቀን የሆነውን ሁሉ ነገረቻቸው። በዚሁ የተነሳ ቁጉን ሁሉ ተረብሻ ከቤትም ሳትወጣ ዋለች። ማታ ላይ ሳንቾ ቤታቸው መጥቶ የሆነውን ነገረችው።

ስሚቷን መቀጣጥር እያቃታት ፣ "ይሄንን አብድ ወይ ፈልጌ ራሴ ነኝ የምገድለው ወይ ደግሞ የሰው መበትና ክብር የማይከበርበትን ሃገር ጥዬ መሄድ አለብኝ። ያልተከሰሁ ... እሱ ኮ ስለሚወድሽ ነው ... አያሳዝንሽም ወይ ቅብርጥሴ ... ምናምን ይላሉ እሱን ነበር በቁሙ ለጅብ መስጠት። ጅብ የመሰለ ፍጥረት" ብላ ተቁነጠነጠች። እስከ እኩለ ሌሊት አካባቢ ቀይቶ ወጣ። ሜር ባለው መንገድ ላይ እየነዳ ሊመልሳቸውም ሲያስቀማቸውም ያልቻሉ ብዙ ጥያቄዎች ከግራና ከቀኝ አዋከቡት።

'እንደ ምስጢር ያሉ ... አፍቃሪ ነን ባይ አድብቶ አሳዳጆቻቸው መከራቸውን የሚያሳዩዋቸው ስጉት ይሆኑ?

በስሜታቸውና በህልውናቸው ላይ የሚፈራረቅባቸውን ስቃይ ማን ይረዳላቸዋል? የወጣትነታቸውን ዕድሜ የደስታ ሳይሆን የሽብር፣ የእንቅልፋቸውንም ሰዓት የእረፍት ሳይሆን የቅዠትና የሰቀቃ ከማድረግ የከፋ፣ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ሊፈጸም የሚችል ምን ግፍ አለ? በሌላ ሰው ወይም በሌላ ሰው ልጅ ላይ የሚደርሰው አበሣ ቤታችን እስኪገባ ዝም ካልን ... ችግሩ እኛ ቤትስ የገባ ቀን ለኛስ የሚደርስልን ማነው? ከተንሻፈፈ ፍቅር ቀጥተኛ ጥላቻን መሸከም፣ ከበሽተኛ አፍቃሪም ከጤነኛ ጠላት ጋር መኖር እንደሚሻል የሚያውቁ ስንት ይሆኑ?'

እንደ ምንም ግቢ ውስጥ ቦታ ፈልጎ መኪናውን አቆመና አስራ እየተገላመጠ ወደ ቤቱ ገባ። 'ጥቃት በሌላ ሰው ሲደርስ ተረት ነው በራስ ሲደርስ ግን ከሞት የከፋ መከራ ነው። ጥቃት የሚፈጽሙት ከሰው ያልተፈጠሩ አውሬዎች ናቸው ብለን ስለምናምን፣ የኛ ልጆችና የቅርብ ሰዎች በሌላ ሰው ላይ ለሚያደርሱት ስቃይ አይናችን በቀላሉ ሊታወር፣ ሽንጣችንን ይዘን ልንሟገትላቸውም እንችላለን። ተጠቂዎች የሌላ ሰው ልጆች እስከሆኑ በኛ ላይ የማይደርስ ይመስለናል። መፍትሄው ... ጥቃትን ማንም ይፈጽመው፣ በማንም ላይ ይፈጸም፣ በእኛ ላይ እንደ ተፈጸመ እድርገ መውሰድ ብቻ ነው' ከተኛ በኋላም ነገሩን ለረጅም ደቂቃዎች ከአእምሮው ሊያወጣው አልቻለም።

@OLDBOOOKSPDF

ክፍል ፬

ሌሎቹ ሰዎች

@OLDBOOOKSPDF

፡ 24 ፡

ሌላው፡ ከመስተዋቱ ፊት ለፊት ሆኖ እያሻሸጨ ከራሳቱን ሲያስተካክል ንጹህ ከአንቅልፏ ነቃች። "ወይኔ ድካም ... ነጋ ማለት ነው? ... አንተ አይደክምህም እንዴ? አይኗን እያሻሸች ተንጠራራች።

"ድካምን ይድከመው፡ እንጂ እኔ በምን ጥዳዬ ..." አለ፡ ወደርሷ ዞሮ። "እንዴት ነኝ ... ይሄ ከረባት ብዙም የሄደ አልመሰለኝም ...የቱ ይሻላል?" ከመልበሻው ላይ ያስቀመጠውን ጥቃቅን መርቅማ ነጠብጣብ ያለውን ጥቁር ሰማያዊ ከረባት መረጠች፡ እንድታስርለት ወረወረላትና ያጠለቀውን ካንገቱ ላይ ማውለቅ ጀመረ።

"ዛሬም ሥራ መግባት አለብህ እንዴ? አውቀሃል አይደል ለመሄድ ሦስት ቀን እንደቀረን?" ፊቷ ላይ የረበበውን ቅሬታ ለመደበቅ አልቻለችም።

"ብናትሽ እሱን አታስታውሺኝ ... ምን ላድርግ ገና ብዙ ያልተያያዘ ነገር ስላለ እኮ ነው። ቶሎ ጨርሼ ከምላ ሰአት በፊት እመለሳለሁ።" ጸጉሯን እያሸሸ ካልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለ።

"እኔ ግን ማለቂያው ... ዓላማውም አይገባኝም ..." እጁን ከራሷ ላይ አንስታ ውስጢ ያለውን ብሶት እንደምንም አፍና ለማስቀረት ሞከረች። ስሞኑን ሁሉ ንጭንጭ ሲያደርጋትና በሆነው፡ ባልሆነው፡ ስትበሳጭ ነው፡ የነረመችው። "ለምን ገዜ ትላለህ፡ ቢያንስ ይቺን ሦስት ቀን ምናለ አብረን ብናሳልፍ። አንተማ የፈለከውን አግኝተሃል ... ምን አለብህ"

ካልጋው ውስጥ ወጥታ ወደ መታጠቢያ ቤት ልትሄድ ስትል እጁን ያዝ አድርጎ አቆማት። "ፍቅር ... ከናንተ ለወራት አይደለም ላንድ ቀንም መለየት ምን ያህል ለእኔ እንደሚሆንብኝ የምታውቂ ይመስለኛል። ጥሩ ነገር መሥራት ከበፈለግ ያለ ሲሆን አይችልም" ሲል፡ እጇን አስለቀቃችው።

@OLDBOOOKSPDF

እኔ አንተ ደስ እንዲልህና ህልምህ እንዲሳካ የሚቻለኝን ሁሉ ሰማድረግና ለመሆን ምዘራያለው። ግን ማለቂያው እይታየኝም። ምኑ ነው ጥሩ ነገሩ... ልጅነትህንና ዜጥሰብዝን የትም በትነህ የምትሰራው ሥራ? ቆይ እስኪ ከዚህ በኋላ ... በነመት ስንት ገዜ ነው ከሲኒከሀን ጥለህ ከኛ ጋር መሆን የምትችለው? መቼም ወደ እዚህ ጠቅልለን ገብተን እንኖራለን የሚል ተስፋ ይዘህ እንደማይሆን አስባለሁ"

"እሺ ... አሁን ምን እድርግ ነው የምትዪኝ? ይሄ ሁሉ ስራ ከተጀመረ በኋላ ጥዬ ልሂድ! ወይስ ... ዛሬ ጠዋት ሰራ ሙግባቴና መቅረቴ የሚያመጣው ልዩነት አለ? እንደሱ ከሆነ ደውዬላቸው ልተር እችላለሁ" አለ፣ በስሜት ባለ ድምፅ።

"ሌላ ... እኔ የምለው ነገር አኮ የገባህ አልመሰለኝም። ራስህ አስበህ የማታደርገው ነገር ምንም አይጠቅመኝም። ጉዳዩ ዛሬ ጠዋት ሥራ መግባት አለመግባትህ ላይ አይደለም። ቤተሰቡ ላይ አየፈጠርክ ያለውን ሜና የተረዳኸው አልመሰለኝም። አትሜንም ፍቅራን እየገዘገዘከው ነው። ቢያንስ ያለችውን ትንሽ ጊዜ ሥራ ስብሰባ ትብጥርስ እያልክ የምትጠፋ ከሆነ ... ተልያይተን በምንቀይባቸው መራት በምን አትም ነው አንዱ ቤተሰብ ተያይዘን የምንቀየው?" ተመልሳ ራሷን በሁለት እጇ ይዛ ተቀመጠች። የሚይሆን ዘርዝር ሙሰቂ ገብቶ ነገሩን ማባባስ ሰላልፈለገ ዝም አለ። ከትንሽ ጸጥታ በኋላ፣ "የማትተርበት ጉዳይ ከሆነ ሂድ። ቢያንስ ግን ቅሎ ተመለስና ከሰንት በኋላውን ከልጅቱም ጋር የሆነ ነገር እያደረግን አብረን እናሳልፍ።" ወደ መታጠቢያ ቤት ለመግባት ሰትነሳ አቀፍ አድርጎ ሳማት።

ልቡ ግን ሊገባው ባልቻለ ምክንያት እየደማ ወጣ። መንገዱን ሁሉ ስሜቱ ኮረብኖ ... ሐሳቡ ተደበላልቀበት ነበር ከሲኒክ የደረሰው። የመጀመሪያ የማኔጅመንት ሰብሰባቸውን የሚያደርጉት ዛሬ ነው። የስብሰባውን አጅንዳ እየት እየት አድርገ፣ ስለ ከሲኒኩ የአመራር መዋቅር ያወጣውን ዝርዝር ዕትድ ሲያስብ ቀየ። አሁንም ሙስሙ አልረገብ ስላለው፣ ትንሽ ዘና ቢያደርገኝ ብሎ የተዳሙን ቡና ፉት እያለ ፒያኖው ሪጋ እድርገ መጫወት ጀመረ። ፒያኖው በከሲኒኩ ምረቃ ላይ ባለቤቱ ንጹህና ጓደኞቹ በሰጦታ ያበረከቱለት ነው። በዚሮው ሙስዋ ፒያኖ እንዲኖረው የሁልጊዜ ምኞቱ ነበረ።

የከሲኒኩ ምረቃ ቀን ንጹሕ ያደረገችውን ንግግርና ለርሱም አበርክቶት የተጫወተችው ሙዚቃ አሁንም አይረሳውም። የምታሳየው ብስጭትና ሰለ ከሲኒኩም ያላት ምሬት ግራ አያጋባው ነው። ይኼ ዓመት በስምንት አመት የትዳር ጊዜያቸው ሙስዋ ፈታኝ ሆኖበታል። ጠደ አንድ አትጣጫ የሚመራ የጋራ ዓላማ የሌላቸው ተጋቢዎች፣ ያስተሳሰራቸው ፍቅር እንኳን ሳይኖር ደስታ ሳይሆን እሰር ቤት ሊሆንባቸው ይችላል። ፍቅር አጣማሪ ኃይል ቢሆንም የሕይወትን ትርጉምና አቅጣጫ ሰጪ፣ አጣጣሚ ኃይል ግን የጋራ የሕይወት አላማ መሆኑ ገና አሁን ነው የተገለጠለት። ከዚህም በኋላ አንዳቸው ወይም ሁለቱም አቻችለውና አመቻምተው ወደ ጋራ የጉሮ አላማ ካልመጡ ንጹሕ እንዳልችው ቀላ ፍቅራቸው ተገዝግዞ መበጠሱ እንደማይቀር ስስ ሰጋት ገብቶታል።

@OLDBOOKSPDF

ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ለስብሰባው ከክሊኒኩ ጀርባ ወዳለችው የሰራተኞች ካፌ ሄደ። ካፈሞ ዘብ ገጮ ስትሆን፣ በአብዛኛው ግድግዳዋ በመስተዋት የተሞላ ስለሆነ ውስጢ ፍክት ብሎ፣ ቅልልና ዘና ያደርጋል። የቀረበውን ሻይ ቡና እንደፈቃዳቸው እየቀዱ ትንሽ ከተጨሞወቱ በኋላ፣ በዞና ዋና ጉዳዮች ላይ ተነጋገሩ። በመጨረሻም የክሊኒኩን የኃላፊነት መዋቅር እንዲወያዩበት፣ በስእል ቡተደገፈ ማብራሪያ አቀረበላቸው።

"ያው እንግዲህ እንደ ክሊኒኩ ጀማሪ ስታፍና መስራች አባልነታችን፣ የአመራር ቦርዶቹም እኛው አምስታችን ነን። የተለያዩ ሃላፊነቶችን የምንከፋፈል ሲሆን፣ ዶክተር ሲራክ ሜዲካል ዳይሬክተር፣ ሲስተር ዘቢባ ያስተዳደር ሃላፊና የነርሲንግ ዳይሬክተር፣ ሚስባር - የስነልቦና፣ የምክርና የማህበራዊ አገልግሎቶች ዳይሬክተር እንዲሁም ሳንቾ የክሊኒኩ ክሊኒካልና ጠቅላላ አገልግሎት ዋና አስተባባሪ ይሆናል።

"የሉሎቻችሁ ግልጽ ይመስለኛል። የሳንቾ ተጠሪነት በቀጥታ ለኔ ሲሆን የማዕከሉ መዋቅርም ሆነ አጠቃላይ ሥራ ያው በሂደት ነው የሚጸብረው። በማንኛውም ዘርፍ ክፍተት እንዳይኖር ሁላችንንም የሚያያይዘንና ሁሉም ነገር በትክክል እንዲሄድ የሚያደርገው ሳንቾ ይሆናል። ነገሮች በታቸውን ይዘው ሲስተካከሉ እንዴ ፍላጎቱ ወደ ማህበራዊ አገልግሎት ወይም ወዴ አስተዳደራዊ አቅጣጫ ማተኮር ይችላል" ብሎ ዝም አለ።

"የፋይናንስ ስራውንስ ምን አሰብክ? ምክንያቱም ከአገልግሎት ከሚሰበሰበው ገንዘብም ሆነ ካሉት የግንባታና የማስፋፋት ሥራ አንጻር የራሱ ባለሙያ የሚያስፈልገው ይመስለኛል" ስትል ሲስተር ዘቢባ፣ ሁሉም በመስማማት ራሳቸውን ነቀነቁ።

"እስካሁን በትርፍ ጊዜ የሂሳብ ሠራተኞችና በሳንቾም ተቆጣጣሪነት ነበር አብዛኛው ሥራ የተሠራው። እሁን ግን እንዳልሽው በሙያው በቂ ልምድና ስልጠና ያላቸው፣ የሙሉ ጊዜ ገንዘብ ያዥና የሂሳብ ሰራተኛ መቅጠር ይኖርብናል። ተጠሪነታቸው በቀጥታ ላንቺ ይሆናል ማለት ነው ሲስተርዬ ..." ራሷን ነቅንቃ መለማማጯን ገለጠች። ሉሎች ዝርዝር ጉዳዮችንና ያጋጠሟቸውን ችግሮች ተወያይተው፣ ቋሚ ስብሰባቸው ለጊዜው በየሳምንቱ ሃሙስ ጠዋት እንዲሆን ተስማሙ። ስብሰባቸው ሲያልቅ ወዴ ሲስተር ዘቢባ ዘወር ብሎ፣ "ሲስተር የጋሽሲራጅ ጓደኛ ያልሽኝ ሰውዬ ልጆቸውን ይዘው ዛሬ ነው የሚመጡት? ደውለሽላቸው ነበር እንዴ?" አለ፣ መረተቦቹን እየሰበሰበና የጀመረውን ጠሃ እየተነነጨ።

"መጥተው መኪናቸው ውስጥ ናቸው መሰለኝ። ሊረብሽ ይችላል ብለው ስለፈሩ ተራቸው እስኪደርስ እዚያው ብንቶይ ይሻላል ብለው ነው። በጣም ሚኒ ... ነገር ሰለሆነ አርፎ አይቀመጥም" ስትል፣ ሉሎቹም እነርሱን እየሰሙ እሳው ቀሙ።

"እህ ሪሲይ ... ኤድሚው ምን ያህል አንዴሆነ ታውቂያለሽ?"

"አይ አንሽብኝ ... ኮሲጅም የጨረሰ ነው። በጣም ገበዝ ልጅ ነበር ... ምን እንደ ነካው አንጃ ... እናቱ እንደነገሯችኝ ሰብ ሙናሚን ሙስሙም ላይገባ አልተራም።"

@OLDBOOKSPDF

"አይ ጥሩ በቃ ... ያው እነ ንጹሕ መሄጃቸው ስለ ደረሰ ... እኔ ቶሎ መውጣት አለብኝ ዛሬ ። ነገም መግባት የምችል አይመስለኝም ። ችግር ካለ ዶክተር ሲራክ በላለ ወደሱ ይመራልኝ እንግዲህ ..." አለ ሲራክን እያየ ።

"አለን የደጅን ሃይል ...ተማመን ነው" ብሎ ሳቀ ። ሁሉም ወደየቢሯቸው ሊበታተኑ ሳንቾና ምስጢር ብቻ እባው ቀሩ ።

ወደ ጥናው ክሊኒክ እየገቡ "ሲስተርዬ ... እኔ ቢሮ እጠብቃቸዋለሁ ... ለምን ቶሎ ካርድ አውጥተው እንዳያቸው አታስገቢልኝም?" አለ ።

"ቦሩ ዶክተርዬ ... በቃ ትንሽ ደቂቃ ስጠኝ ..." ብላ ፣ ተፍ ተፍ እያለች ሄደች ። ቢሮው ገብቶ የሚመስሉ ስልኮችን መላለስና ንጹህ ጋ ሲደውል አላንላችም ። "የኔ ፍትር ...እወድሻለሁ ... ጠዋት ስላላዘንኩሽ አዝናለሁ ... ቶሎ እደርሳለሁ" ብሎ ፣ የጽሁፍ መልእክት አስቀመጠላት ። ብዙም ሳይቆይ ሲስተር ዘሪባ ሀመምተኛውንና እባቱን እስከትላ ቢሮው ስትገባ ተነስቶ ተቀበላቸው ። እየጨበጣቸው "ሌላሠው..." ሲል እባትዬው

"ዘግል እባላለሁ ... ዶክተሬ ... አላህ ይስጥልኝ ... በጣም ትልቅ ውለታ ነው" አሉ በጨነቀው ፊታቸው እንደ ምንም ፈገግ ለማለት እየሞከሩ ። ቁመተ ረጅም ግዙፍ ሰው ናቸው ። ልጃቸው ከመዲያ ወዲህ እይናቹ ይቅበዘበዛሉ ። የሌላሠውን መኖር ልብም ሳይል ላመል እንደነገሩ ጨበጠው ። ወደ ፒያኖው ሄዶ ነካ ነካ አድርጎ ከራሱ ጋር እየላቀ ከፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲል ቀየ ።

"እንዴ ... ይሄ መኖሪያ ቤትህ ነው ወይስ ... ወላሂ እዚህ መታከም ላይሆን መኖር ነው የምፈልገው ። ... ፍሪጁ ... ቡናው ... ፒያኖው .... ምን ቀረ ... ኮካ ነገር አለ እንዴ ነፍሱ ..." ብሎ ፣ ወደ ፍሪጁ ሲሄድ እባቱ እጁን ይዘው አስቀመጡት ።

"ኧረባክህ ስርዓት አንተ ልጅ... እስኪ ..." ሌላሠው እንዳይጨነቁ አረጋግቷቸው ነርሱን ችላ ብለው እንዲቀመጡ ወደ ሶፋዎቹ ጠቀማቸው ። ወደ ፍሪጁ ሄዶ ኮካ ከፍቶ አመጣና ሰኑሪዲን ለጥቶት ከፊት ለፊታቸው ካለው ሶፋ ላይ ተቀመጠ ። ኮካውን ባንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርገ ጠጥቶ ጣራ ጣራውን እያየ ከት ብሎ መሳቅ ጀመረ ። በቢጫ ሸሚዝ ላይ ያደረገውን ወይን ጠጅማ ሹራብ አውልቆ አጠገቡ ጣል አደረገው ። ከራሱ ጋር እያጉተመተመ ሲያወራ ሌላሠው አጠገቡ ወደ ተቀመጡት አባቱ እያየ ፣

"ይቅርታ ... ስብሰባ ላይ ሆነን ብዙ አስጠበቅናችሁ? ... ቀያችሁ እንዴ ከመጣችሁ?" አለ ወሬ ለመጀመር ያህል ። ትንሽ ከተጫወቱ በኋላ ወደ ልጃቸው ዞር ብሎ "ኑረዲን ... ምን እያሰብክ ነው ... ችግር አለ እንዴ?" ሲለው ፣ ድንገት ቀጥ ብሎ ቀመ ። በደማቁ ከትከት ብሎ ሲስቅ ቀየና ተመልሶ ተቀመጠ ።

ግይናቹን እንደማጉረጥረጥ አድርገ ፣ "ታው ታለህ አገሪቱ ለምን ደሃ እንደሆነችገ ... ፈሪ በቅጂ ታ ሠው በዛ ... ቢዝነስ የገባው እንድ ሰው እንኳ የለም ... ሰባት በቢሊዮን የሚቆጠር ገቢ የሚያመጡ ፕሮጀክቶች ተርፈው ኢንቨስትመንት ቢሮ አስገባሁ ... እነሱ ሲንከረፈፉ ቻይናዎቹ ለሲት ቤት ድረስ መጥተው ብዙ ሰዓት አማላጅ ለምነውኝ መሰዱት

@OLDBOOKSPDF

ሀንዶቹ ራሳቸው አውን ውጪ እየጠበቁኝ ነው ... አባቱ ደግሞ ... ተመታላህ ... ሁለት የወደድኳቸው ሴቶች አሉ ... ግንዘብ ከሚባሀን ሁለቱንም ባንድ ቀን አጋጭን ብለው ... ግን ቀደ አንተ እንዴ ነህ ይህተር። ከሐሳብ ሐሳብ እንደ ፈንጣላ ሲዘል ቀየኝ ትክ ብሎ አፈጠጠበት።

"ምን እመስልሃለሁ?" አለው፣ ፈጋ ባለ ድምጽ ወደ ኋላ እንደ መደገፍ ብሉ።

"አሞበርባራ ንገር ነሽ ... በሙዚቃና በኮካ እያታለልሽ ... ሳሜሪካ እንግሊዘኛ ባ ደሄን ፋራ ህዝብ ፊዚ እየከተትሽ ... በይላር ትከትፊዋለሽ አይደል? የሰጪን ብር ማለብ ነው አይደል ሥራሽ? አይ አም ሹር ... ቺኮቹማ ... በቃ ፒያኖው'ን ገና ተረም ተረረም ስታድርጊላቸው ... ሠሞተው አንገትሽ ላይ ጥምጥም ሲሉ ይታየኛል ... ከነ መድገም እችላለሁ?" ብሎ ባደውን ጠርሙስ ሲጨልጥ፣ አባቱ ስትት ብሷቸው እጁን ጭምት አደረጉት። "እንዴ አባ ምነው? አባ በናትህ ... ሹፈው እስኪ ሣኒከውን ..." ብሎ መልሳቸውን ሳይጠብቅ ወዲያው ወደ ኮን ዞር አለና፣ "ፒያኖው ላይ ያለችው ቀያፈ ናት? ቀሽት ዝርል ነው ያፈስከው ዶክ" ብሎ፣ እየሳቀ የሆነ ነገር እንደ ጠፋበት ኪሱን ሲበረብር ቀየ። እርሱ ያወጣውን የተጨረማመተ መረቀት ሲያገላብጥ ሌላው ወደ አባቱ ዞረ።

"እስኪ እርሶ ይንገሩኝ ... እንኤት ጀመረው ... ቀየበት እንኤ?" ሲል በረጅሙ ተንፈሱ።

"እንግዲህ ይቅርታ ... መቼም ያገባሃል ላንተ ዶክተር። አውን ያሄው ዕድሜውም ሃያ አምስት ዓመት ሆነው አይደል? የመጀመሪያ ጊዜ ሲያመው ነሊጅ እንደገባ አካባቢ ... አስራ ዘጠኝ አመቱ ነበር። እንዲሁ አቅሉንና ጨርቁን ጥሎ ... አንዴ የአላህ መላክተኛ ነኝ ... አንዴ የሚቀጥለው ጠቅላይ ሚኒስትር እኔ ነኝ ... በማለት ነበረ። ደግሞ ምን ልበልህ እንትልፍ የለ ... አረፍት የለ ... መስፈስፍ ነው ... ኋላ እንደተረዳሁት፣ ያኔ ሣጌት ሲጋራ ምናምንም ሳይጀምር አልቀረም። በስንት መከራ አማኑኤል አስገብተን ሻል ብሎት ወጣ ... ደሄ እንግዲህ አራተኛው ነው፣ እንዲህ ሲመሩና ... ሻል ሲለው መድሃኒቱን ያቀማል ... ወይ ሽንት ቤት ይጨምረዋል ወይ ጠፋ ይለናል።

"የሆነ ያልሆነ ነገር ሲጀምር ሲያቅም ... ልቦናውን ሁሉ ይሰልበዋል። እያደር መተኛት ይከለክለዋል ... በቃ ጉልበቱን ከየት እንደሚያገኘው አላውቅ ... ንግግሩና አስተሳሰቡ ሁሉ አውሎ ነፋስ ይሆናል ... ይህን ሰያገባ ነው፣ ያንን መልቶ ነው ... ያያትን ሁሉ ካላገባሁ ነው ... ያችንም ይችንም መኮንተል ነው ... ምን እደነመሀ ምንም የማይችለው ነገር ያለ አይመስለውም። ሦስት ጊዜ የሥራና የቤት መኪኖቻችንን እየወሰደ እያጋጨ ከጥቅም ውጪ አደረጋቸው። እሱ ግን ይሄው እላህ ምን እንዳየለት አላውቅም ... ሞራት እንኳ ሳያገኘው አለ" ብድግ ሲል፣ እጁን ንቱሙ ሰልሰው አበቀመጠት።

"ታዲያ ችግሩ ... ልክ ውሩፍና ውስ እያለ ሲከሰም ... ያገሩን ጨሰማ አምሃ ይያፋበታል ... ካልጋ አይወጣ ... አይበላ ...ሰው ሚገናት አይፈልግ ... ሽም ብሎ

@OLDBOOOKSPDF

ማልቀስ ነው ... ኒጋ ጠባ ሞት ነው ወራው ... ስንቱ መሰለህ ነፋሩ የተረፈው ... ራሱን ሊያጠፋ እየሞከረ ። እና ይሄው እሁንም ... አስር ቀኑ እንዲህ መያገ መላው ከጠፋ" ብለው ፣ እንደገና በረጅሙ ተንፈሱ ።

በጥሞና ሲያዳምጣቸው ቀየ ። "ስለዚህ በተደጋጋሚም ሆስፒታል ተኝቶ ነበር ማለት ነው ። መጨረሻ ላይ ይመስድ የነበረውን መድሃኒት ያስታውሳሉ?"

"ሊቲየም ነው ... ሊቲየም የሚባል ነገር ግን ባይኒም ማየት አልፈግም ። ዴፓኩት ... ላሪጋዘቲል ... ቶራዚን ... ሜላራል ... ሁሉንም ሞክረው ብኖል ... ጊኒ ፒጋችው እያደለሁ? ስማ ዶክተር ... እኔ እብድ እያደለሁም ... ሄዳችሁ እብዳችሁን ፈልጋችሁ ማከም ትችላላችሁ ። እኔ ዓለምን የማዳንና ... ይቺን ደሃ መናጢ አገር እንደገና ጠፍጥፎ የመስራት ሚሽን ተሰጥቶኝ ... ማርስ ላይ የነበረኝን ሥልጠና ጨርሼ በቅርብ ነው ላንድ ያደረኩት ። ሀገራቱን በፍትር ሥራ ከፈረንሳይ ... በሀንጻና በኪነ ጥበብ ከጣሊያን እኩል የማድረግ ስፒሺያል ሚሽን ተሰጥቶኝ ነው የመጣሁት ። እንግሊዝና ጀርመንን ካላጣላው ግን ስራው ሊከብደኝ ይችላል" አሰና ከት ከት ብሎ ሳቀ ።

ድምጹን ጮክ አድርጎ ንግግሩን ቀጠለ ። "... ደግሞ የዚህን ደንቀሮ ህዝብ ኖሮ በፒንሳም ቢሆን ግርጉሬ መከፈት ይኖርብኖል ... አለበለዚያ የምለው ሊገባው አያችልም" ብሎ ፣ ያወለቀውን ሹራብ እንደገና ለማጥለቅ መታገል ጀመረ ።

"ያው እንዳልህ ነው ... ያልሞከረው መድሃኒት የለም ... ይገርምሃል ሊቲየም ላይ ሲሆን ነው ፣ ከሁሉም መድሃኖች በትክክል ለሱ የሚሰራለት ።"

"ኖ ኖ ...አባባ? ... ሊቲየም የሚባል ነገር ... አንባል ቋንጣ የሚያደርግ ጨው ነው እኮ ... እኔ ሜጎንትላቱን እፈልገዋለሁ ... ልክ እኮ ፖዝ እንደተደረገ ቲቪ ... ወይም ... አንባልህ ላይ እንደ እግር ኳስ ስሎው ሞሽን ነው የሚሠራወት ብሀ ... ዕድሜ ራሲ አሞር ናት ... ዶክተር ... ቀይ ሲላ አዲስ ዲስከቨሪ የለም? ... ምንድነው ... የዛሬ ሰባ አመት በተገኘ ጨው የምትለጠልጡን ... ሊቲየም ቀምሰህ ታቃለህ እንተ?" ሲለው እንደማያውቅ በሜንትላቱ ነገረው ። "ለዚህ ነዋ ሊቲየም ነው ደፐኩት ነው ቶራዚን ነው የምትሉት ... ደግሞ ቶራዚን ከመውሰድ ... በናትህ ያበሻ ወፍዶ ተሸክመህ መዘር ይሻላል ... ፈረስ በቁልቁለት የማይጎትተው ... ዞምቢዝም ማለት ቶራዚን ነው"

"ለመሆኑ በቤተሰብ ወይም በቅርብ ዘመድ ተመሳሳይ ህመም ያለው ሰው ነበር?" አለና ጥያቄውን ወዳባቱ አዞረ ።

"እንድ የኔ ታናሽ ወንድም ነበር ... እንዲሁ ላይ ታች እያለ እንዴ ሲወፍፍ እንዴ ሲያበት ... ጓላ ካገር እንደ ጠፋ ቀረ ። ያው መቼም በዛ ጊዜ እንደ ህመም የሚያየው የለ እንጂ ... አባታችንም ሰው መድሃኒት አርገበት ነው እየተባለ ... ንክ ቢጤ ነበር ። በናቱ ዘመዶች እንኳ ሁሉ ደህና ናቸው"

"እሁንም ይትማል? መጠጥስ?"

@OLDBOOOKSPDF

"ያው መታመን አቁሞም አያውምም ... መጠጥ እንግዲህ እኛ በሃይማኖታችን እንጠጣም ... እሱ ግን ሲነሳበት ከጓደኞቹ ጋር ... ከምንም ከምን ብሎ የት ይቀራል ... እሁን በቀድም ጥንብዝ ብሎ ነበር እቤት ሲመጣ" አሉ ፣ ትንሽ አፈር ብለው ።

"ድምፅ መስማት ወይ እንዲያው ለሌላ ለው የማይታይ ነገር ... ራእይ ምናምን ይታይሃል እንዴ ኑረዲን?" ሲለው ነት ብሎ ሳቀ ።

"ምን ነካህ ዶክተር ... እንኳን እኔ ... ለጪ ሁሉ ኑ ባለራእይ ሆኗል እዚህ አገር ... ዶክተር ... አይ ለምሳሌ እዛ ግድግዳ ላይ የሚሯሯጡ ልጆች ይታዩሃል? ... እነሱ ማለት ... የሚቀጥሉት የሀገራችን ሃይሌና አበበ ቢቂላ ናቸው ። ሎክ እዛ ጣራው ላይ ደግሞ ..." ብሎ ሲቀጥል ፣ እሱን ተወት አድርገው ወሬያቸውን ቀጠሉ ።

"ኑረዲን ምን ማድረግ ትወዳለህ በትርፍ ጊዜህ?" ሲለው

"ለኔ ሁሉም ጊዜ ትርፍ ነው ... በዋና ጊዜ ማለትህ ከሆነ ... ንባብ ... ሙዚቃም እጫወታለሁ ... እም ም ..." ሲል

"እውነት ሙዚቃ ትጫወታለህ ... ምን መሳሪያ ነው የምትጫወተው?"

"መሳሪያ ተጫው ቹ አላውቅም ... ግን ካገኘሁ ክላሽንኮቭ ብጫወት ደስ ይለኛል ... ይሄ ሀገብ እኮ በመሳሪያ ካልተጫወትክበት ምንም አይገባውም" ብሎ ሳቀ ። "ፒያኖ እችላለሁ ...ከፈለክ ልጫወትልህ" ሲል ፣ ወደ አባቱ አየት አደረገ ሌላው ።

"ንበገ ሙዚቃ ተጫዋች ነው ... የሚሰለው ን ስእል ብታይ አታምንም ... የሞከረውን ነገር ሁሉ ይችላል ... ኢኮኖሚክስ ነው የጨረሰው ከዩኒቨርሰቲ ... ከሰራ ንግድም የሚደርስበት የለም ። ችግሩ የሰራውን ሥራ መልሶ በአጥፍ ያፈርሰዋል ። ደግሞ ሰልቹ ነው ... ወረት ያጠቃዋል" አሉ አባትዬው ።

"እስኪ ታዲያ ለምን ፒያኖ አትጫወትልንም?" ሲለው ተንሰቶ ፒያኖው አጠገብ ተቀመጠ ። መጀመሪያ ላይ የግርማ ይፍራሸዋን አልልታ/ሙሽራዬ አላምሮ መጫወት ጀመረና ወዲያው ድብልቅልቅ ያለ ነገር መጫወት ሲጀምር አስቀሙት ። የሙዚቃ ችሎታውን አድንቀለት ወደ ፊት እንዲጫወትለት እንደሚጋብዘው ቃል ገባለት ።

ሃሳቡን ሰብሰብ አደረገና ፣ "ኑረዲን ... ላንተ ላይመስልህ ይችላል ። ግን እየሁ ... ሞንቅላትህ በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ነው ያለው ። በህክምና ቋንቋ ማኒያ የምንለው የባይፖላር ህመም ከፍል ነው ። በፍጥነትና በትክክል ካልታከምክ አንገልህንም ሆነ ላ የሰውነት ክፍሎችህን ይገዳል ። በተጨማሪም የመወሰንና ከፉ ድቡን የመለየት አቅምህ ትክክል ሰላልሆነ ፣ ለተለያዩ አደጋዎችና ችግሮች ልትጋለጥ ትችላለህ ። ስለዚህ መድሃኒቱን እንደገና መጀመር ይኖርብሃል" ሲለው ፣ ከመቀመጫው እየተነሳ ሁለት ጊዜ ቁጭ ብድግ አለና ፣

"አልገባህም እኮ ... ዶክተር ...ምንም ህመም የለብኝም ነው ኮ የምልህ አዝጋሚና ዶል በሆነ ህገብ መካከል እየኖርን ፣ ኖ ደስታና የላቀ ያስተሳሰብ ደረጃ ለእናንተ ስለማይገባችሁ እኮ ነው ። እኔና አንተ ፕሮግራም አውጥተን ... የሚፈጸ

@OLDBOOOKSPDF

ቱራፒ ... በጣም ለባሰባቸው ዶግሞ ስፖርት ቱራፒ እየሰጠናቸው፣ ይሄንን ሕዝብ አብረን ብናዘመው ደስ ይለኛል። እኔና አንተ አብረን ከሰራን የኢትዮጵያን አይደለም ያፍሪካን ህዝብ ጤንነት በቀላሉ ልናስተካክለው እንችላለን። አንዳንድ በሚስጥር የያዝኳቸው ዲስከቨሪዎችም አሉ ... አነሱንም ላስተምርህ እችላለሁ" ሲል ሁለቱ ተያዩ።

ያንድ እግር ሱሪውን ወደ ላይ ሰብስቦ ወደላይ ከፍ አድርጎ አቶየና ከኪሱ ውስጥ አስዘርቢቶ አወጣቶ በፍጥነት መጻፍ ጀመረ።

ሌላሠው ወደ አባቱ አንገቱን ዘመም አድርጎ፣ "ያው መቼም አብዛኛው ነገር አዲስ እንደማይሆንብዎ ነው። ሀመመው 'ባይፖላር ዲስኦርደር' የምንለው ሲሆን ባጠቃላይ የስሜት እንደ ሻሾዋሾዊ በፈረቃ መናጥና ከዛው ጋር የሚፈጠር የአስተሳሰብና ሌሎች የአእምሮ አንኳር ተግባራት መዛባትን ይጨምራል። ኑረዲን አሁን ከፍተኛ የሆነ የስሜት ግለት ውስጥ ነው ያለው። እንገለ ውስጥ በተፈጠረው የኬሚካሎች መዛባት የተነሳ መተኛትም ሆነ ረጋ ብሎ ማሰብ፣ ማመዛዘንም ሆነ እውነታንና ከእውነታ ውጪ ያለውን ነገር በትክክል መለየት አይችልም።

"መድሃኒቱን ማቋረጡ ... ጫትና መጠጡም የተወሰነ የማባባስ አስተዋጽኦ ሳያደርግበት አይቀርም። ከዚህ ሁኔታ በራሱ ቢወጣ እንኳ ቅድም እንዳሉት ከባዱ ነገር ወደ ድባቴ ተንደርድሮ የገባ እንደሆነ ነው። አሁኑኑ የስሜቱን ሁኔታ ማረጋጋትና እንገሉን አሁን ካለበት ውጥረት ማሳረፍ ያስፈልጋል። ምናልባት ሆስፒታል ለመተኛት እምቢ ማለቱ አይቀርም። ግን ምንም አማራጭ ያለን አይመስለኝም ... ወደ ቤት ብንልከውም መድሃኒቱን እሺ ብሎ የሚወስድላችሁ አይመስለኝም"

"እሪ በቁሙ ... መተኛቱ ነው የሚሻለው። እናንተ እዚህ አስተኝታችሁ ታክማላችሁ እንዴ?" አሉ፣ ሞንቀታቸው ከፊታቸው ላይ ተከምሮ።

"እዚህ አስተኝተን እናክምም። ሁለት አማራጭ ነው ያለው። ከፍያውን ከቻላችሁ የግል ሆስፒታሎች አሉ የተሻለ አገልግሎትና ምቾት ያላቸው። ካልሆነ ደግሞ አማኑኤል ላሉ ሃኪሞች ነገሬላችሁ ወደዛው መውሰድ ነው ያለው አማራጭ" ብሎ፣ አስዘርቢቶውን እያፍተለተለ የሚሉትን መጠበቅ ጀመረ።

"ክፍያው ምንም ችግር የለውም። እንዲያው ግን አንተ ብትከታተለው ደስ ይለኝ ነበር። እንዱም የዶክተር ለውጥ ነው መድሃኒቱን እንዲያቀም የሚያደርገው"

"እንግዲያው እኔ በላምንት ሁለት ቀን ከዚህ እንዲተኙ የምንልካቸውን ሕመምተኞች የምከታተልበት የግል ሆስፒታል አለ። እዛ እንላከው ታዲያ?"

"በጣም ጥሩ ነው። ችግሩ እንደኔት እሺ ብሎ ይሄድልናል ነው። ዶክተር ይሄ ነገር ግን ይድናል ወይስ እድሜ ልክ እንደዚህ አበሳ እያዩ መኖር ነው?" አሉ፣ ጢማቸውን እያሻሹ።

"አንዳንድ ሰዎች ላይ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሀመመው ደረጃ በመጠኑ እየቀነሰ

@OLDBOOOKSPDF

ይመጣል። የተመሰኑት ላይ ደግሞ ለረጅም ጊዜ ከሀመሙ ነጻ ሆነው ይቀያሉ። ባጠቃላይ ግን የሀመሙ ጥሩ ገጽታ ልንል የምንችለው ነገር፣ ህክምናውን በትክክል ከተከታተሉት እንደ ማንኛውም ሰው ጥርማል ህይወት መኖር ይችላል። እርስዎ ምናልባት በኮረዲን ላይ እንደሚያውቁት፣ ብዙ የዚህ ህመም ታማሚ ሰዎች በማግ ብሩህ አእምሮና ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ናቸው" አለ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ በእጅቱና በትክሻው እየደነሰ የሚያንገራገጥረውን ኑረዲንን እያየ።

"እሱ ኮ ነው የሚገርመኝ ... ያ ታናሽ ወንድሜም እንዴት ያለ ጂኒየስ ነበር መሰለህ። የነካው ሁሉ ወርቅ ነው የሚሆነው ... ቀልደኛነቱስ ቢሆን። ይሄም ልጅ ታዲያ እሱን ነው የሚያስታውሰኝ። እኔ እኮ አታምነኝም ዶክተር ... ከሦስት ሰው ጋር የምኖር ነው የሚመስለኝ። ሲደብተው ሌላ ሰው ነው ... ቤቱን ሁሉ በጨለማ ይሞላዋል። ከክፍሉ አይወጣ፣ የገዛ ጥላውን ፈርቶና ጠልቶ ነው የሚኖረው። ደግሞ እንዲህ ወፈፍ ያደርገው ጊዜ ደግሞ ፈጽሞ ሌላ ሰው ይሆናል። ፍርሃትና ይሉኝታው ሁሉ ይጠፋና የሚያቅተው የሌለ፣ ሰው ጠፉ ይሆናል። ከሁለቱም ደህና የሆነ እንደሆን ደግሞ ... ለሰው አሳቢ፣ ስሪውን አክባሪ፣ ሃይማኖቱን ጠባቂ ምን ልበልህ የማታውቀው ሌላ ሰው ነው። እንዴት አንድ ሰው እንዲህ እንዶ ሻርዋሻዊ ላይና ታች እያለ እንዶ ሚለዋወጥ ነው የማይገባኝ።"

"ምን መሰልዎ ... እሁን እዚህ ክፍል ውስጥ ከፍተኛ ሙቀት ወይ ከፍተኛ ቅዝቅዜ ቢሆን ወይም ድርግም ያለ ጨለማና አይን የሚያጥበረብር ብርሃን ቢፈራረቅ የሚታየውን ልዩነት ማለት ነው። ሚዛኑን ሲያጣ ሁሉም ነገር አጥፊ ነው። የሰው ህይወት ሚዛን ነው። ሁሉም ነገር ሲያንስም ሲበዛም በሽታ ነው። ህክምናውም ያንን ለማስተካከል ነው የሚሞክረው" ብሎ ካርዱ ላይ የሆነ ነገር ጫር ጫር ማድረግ ጀምረ።

"ያንኑ ሊቲየሙን ነው ወይስ ሌላ ነገር ልትጀምርለት ነው ያሰብከው ታዲያ?"

"ሌሎች የተመሰኑ አማራጮች አሉን። ግን ብዙዎቹ መድሃኒቶች እዚህ እገር አይገኙም ... ዋጋቸውም ወደድ ይላል። ከዚህ በፊት ሊትየም ላይ ሆኖ ጥሩ ከነበረ ግ ምናልባት ለሱ ዓይነቱ ባይፖላር ሊቲየሙ ከሁሉ የተሻለ ሊሆን ይችላል። ሊቲየ የሚወስድ ከሆነ ግን የተመሰኑ የደም ምርመራዎችን በየሦስትና ስድስት ወራቶች ማድረግ ያስፈልገናል" አለ፣ ቀና ብሎ እያያቸው። ኑረዲንም ሲስተር ዘቢባ ተከትላው ወደ መታጠቢያ ቤት ሄዶ ስለነበር የሆነ ነገር እያጉተመተመ መጣና ከባሻገር መደርደሪያው አጠገብ ቁሞ መጻሕፍት ሲያገላብጥ ቀየ።

"እህቱ ካታር ስላለች ከዛ የሚመጣ መድሃኒት ከሆነ ችግር የለም። አንተ ያ ነው ያልከው መድሃኒት ጀምርለት" አሉ፣ ወደ ጓላቸው ለጠጥ ብለው ጀርባቸውን እያሳረፉ።

"ጥሩ እስኪ መጀመሪያ ላይ ወይ በሌላ መድሃኒት ጀምረን በኋላ ካስፈለገ እስኖ ፈታደሻ ከሆነልን ወደ ሊቲየም እንቀይረዋለን። እስኪ ለማንኛውም እሁን መኖሪ እንጻሰበት ልናሳምነው እንሞክር። እምቢ ካለም ትንሽ የሚያረጋጋው መድሃ ሰጥተነው እንልከዋለን" ብሎ ተነስ ሲያላምጦት ቢሞክሩም አሻፈረኝ

@OLDBOOKS

ልጄ፣ ተረዳድተው ወደ መድሃኒት መስሪያ ክፍል መሰዱት ። መርፌ ከተሰጠው በኋላ ትንሽ ረጋ ሲል ወደ ሆስፒታል አስተላለፉት ።

እዝሱን አሰናብቶ ሥራውን ጨራርሶ ወደ ቤት ሲሄድም የኑሪዲን ነገር ከመሳሱ አልጠፋም ። አንዳንዴ ሀመምተኛን ተሸክሞ ወደ ቤት መጓዝና ወደ ገል ኑሮ መተላለፍ በሐኪሞች ዘንድ የተለመደ ነው ። ሌላው ሁልጊዜም በ'ባይፖላር' ሀመም እንደተገረመ ነው ። ሕይወት ዝቅዝቅዊ መሆኗን ያስታውሰዋል ... ያሳስበዋል ።

'ወደ ላይ ሲሮዙ ... ወዶታች ሲዘቅጡ ... በስሜት ማእበል ሲናጡ ... ሁሰንተናን ሚዛን አሳጥቶ ... በፈላ ውሃና በበረዶ እየተፈራረቀ እንደሚነክር እገር... በታማሚውና በቤተሰብ ላይ ድርብ ስቃይ ይፈጥራል ።

'ዝቅዝቅዊው ከተወሰነ ገደብ ሲያልፍ ኑሮ ይዛባል ፣ ይምታታል ፣ ይታመማል ። ደስተኛ ኑሮ በተቃራኒ ነገሮች መካከል የተሰወረን መካከለኛና ረቂት ሚዛን ፈልገ ማግኘት ነው ። ብርሃንና ጨለማ ... ሞትና ህይወት ... መሞትና ቅዝቃዜ ... ደስታና ሐዘን ... ነጭና ጥቁር ... አንድነትና ልዩነት ... ሁሉ ሚዛን የሚፈልጉ ጽንሮች ናቸው ። አንዱን ሣሩ አጥፍቶ በሌላው ላይ መጣበቅ የብዙ ጽንፈኝነትና አክራሪነት ምንጭ መሆኑንም አስበ ። የዝቅዝቅዊ ጨዋታ ከሚሰጠው ደስታ ባሻገር በግራም በቀኝም በኩል ከወደቁ ... አደገኛ ገደል እንዳለ ብዙ ጊዜ ይረሳል ። '

በአሜሪካና በኢትዮጵያ ባላቸው ኑሮና ስራ ላይ የርሱና የንጹሕ አለመግባባትም የዚሁ ዝቅዝቅዊ ውጤት መስሎ ተሰማው ። 'በቤተሰብ ምቾትና በሕይወት እላማ ... በባልና በሚስት ምርጫ ... በዛሬ ደስታና በነገ ስኬት ... በተረዳነው እውነትና በመገናርበት እውነታ ... መካከል በሚፈጠረው ውጥረትና ጡዘት ሸሽተው የማያመልጡት ዝቅዝቅዊ ይፈጠራል ። ሚዛን ሲያጡ ተሸቀንጥሮ መውደቅ ወይም ተነትሮ መቅረት ይመጣል ። ' ሚዛንን ጠብቆ በሁለቱ ሣሩ ላይ እየተጓዘው ለመኖር ደግሞ የልብ ስፋትና የአእምሮ ብልሀነት እንደሚጠይቅ የበለጠ ታየው ።

የራሱ ዝቅዝቅዊ ሁዘም እንዳይበጠስ ረግቦም እንዳይቀም ለማድረግ ብልሃቱ እውንም አልተገለጠለትም ። ቤት ደርሶ ገና ከመኪናው ሲወርድ ዲንሳና እርሴማ ሮጠው ተቀበሉት ። ቀኝና ግራ እጁ ላይ ተንጠላጥለው የለመዱትን ዝቅዝቅዊ እንዲያጫውታቸው ለመኑት ። ከነርሱ ጋር ሲጫወት ፣ ሞንትላቱ ውስጥ ሰፍሮ ሲፈነጥብት የነበረው ሐሳብ ለቀት በረረ ። ከንዱ እስኪገል ድረስ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ሠደፈትና ወደ ኋላ እያፈራረቀ ልባቸው እስኪጠፋ አጫወታቸው ። ዝቅዝቅዊ ... ላንዱ ዝሙም ... ላንዱ ጨዋታ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 25 ፡

ምስጢረ ሰኞ፣ ረቡዕና አርብ ለግማሽ ቀን ብቻ ነው ክሊኒክ የምትገባው። በቀሩት ቀናት ሌሎች የቤተሰብ ቢዝነሶችን ትከታተላለች ። በጥቂት ወራት ውስጥ ያላት ጊዜ ሁሉ በምክር ፊላጊ ደንበኞች የተሞላ ስለሆነ፣ አንዳንድ ጊዜ ለግምሽትም ትገደዳለች ። በጠዋት ቢሮዋ ገብታ ሰዕሉቱ የምታያቸውን ሰዎች የግል መዝገብ ማገላበጥ ጀመረች ። እንደ ለመደችው ጆሮዋ ላይ ማዳመጫዋን ሰክታ ከምትሰማው ሙዚቃ ጋር ሟኝትላታንና ትከሻዋን እያወዛወዘች፣ አልፎ አለፎም በመስኮት ወደ ወጭ እያየች በሐሳብ ወጣ ገባ ስትል ቀየች ።

የመዝገብ ቤትና የቀጠሮ ክፍል ሠራተኛዋ ደወለችላትና፣ "ሃሎ ... ሠናይት ነኝ ሚስርጥዬ ... ረበሽኩሽ" ስትል፣

"ኧረ ምንም ... ዝም ብዬ ቻርቶች እያገላበጥኩ ነበር ... ሰላም ነው?" ብላ ፊቷን ወደ ጠረጴዛው አዙራ ተቀመጠች ።

"እይ ያሉሽ ሁለት ሰዎች ቀጠሯቸውን ሰርዘው ስላስተላለፉ አንድ አዲስ ሰው ልተካ አስቤ ነበር ..."

"ማነው የሰረዘው? ... ታዲያ ምናለ ሰአቱ በዶ ከሆነ አዲስ ባለ ቀጠሮ አስገቢበታ" አለች፣ ቀጠሯቸውን የሰረዙት እንማን እንደሆኑ ለመገመት እየሞከረች ።

"እንደኛዋ ወይዘሮ ፋሲካ ናት ... የቤተሰብ ችግር አጋጠመኝ አለች ። ሌላው ደግሞ ባልና ሚስቶቹ ... እም ...ም ... ማናቸው ልጄ ..." ስትል

"እሺ አወቅኋቸው ... ምናሉ እነሱ ደግሞ?" አለች ባለፉት ሳምንታት ጥሩ የተሻሻሉና ከምክራም የተጠቀሙ መስሏት ስለነበር መቅረታቸው እያሳዘናት ፣ ወይዘሮ ፋሲካ ባለፈው ሳምንት ክፍለ ጊዜያቸው ላይ ብዙ ዳር ዳር ስትል የቀየቻቸውን ነገሮች አፍረጥርጣ ስላወራቻት አልትሳና ተበሳጭታ ስለሄደች ዛሬ መቅረቷ ብዙም አልገረማትም ።

@OLDBOOOKSPDF

ሚስትዬው ባሬ መምጣት እንችልም ብላ ብዙም ዝርዝር ሳትሰጠኝ እያለቀሰች ነው ስልኩን የዘጋችው።"

"እይ በታ እስኪ እኔ እደውልላታለሁ። አዲስ ያልሽውን ሰው በነሱ ቦታ እስገቢኖ። ወንድ ነው ሴት?" አለች፣ ሃሳቧን ለመሰብሰብ እየሞከረች።

"ወንድ ነው ... ግን በታ ምኑም ደስ አላለኝም ... እንደኛ አንቺ ብቻ እንድታዪው ነው የሚፈልገው ... ደግሞ ስካርዱ የመለያ ፎቶ እንዲነሳ ሲጠየት በብዙ ትግል ነው እሺ ያለው። ብቻ ቀልቤ ብዙም ሰላልወደደው ልንገርሽ ብዬ ነው። ካርዱን ላምጣልሽ ለማንኖውም?" ስትላት

"ጥሩ ... ሰኢዶ ገብቷል እንዴ?" አለች የሆነ ሃሳብ መጥቶ ፍርሃት ነገር ሰለ ተሰማት።

"አዎን ... አሁን ገባ ... በረንዳው ላይ ከጽጌ ጋር እያወራ ነው። ፈለግሽው?"

"አዎን ... ንገሪው አሁኑኑ እንድምፈልገው ... ካርዱንም ቶሎ አምጪልኝ። ታንክ ዩ የኔ ቸንጅ" ብላ ስልኩን ከዘጋችው በኋላ ማዳመጫውን ከጆሮዋ ላይ ነቅላ እያስቀመጠች ያዲሱን ሀመምተኛ ስም አለመጠየቋ ትዝ አላት። ካርዱን እስከታመጣላት ሜንቶት በተሞላበት ጉጉት መጠበቅ ጀመረች። ብዙም ሳትቆይ ካርዱን ይዛላት ስትመጣ ተጣድፋ ተቀበለቻትና ስሙን ስታየው የምታውቀው አይደለም። የመጀመሪያ ገጽ ላይ ገልጣ ፎቶውን ስታየው "ምን...!" ብላ ካርዱን ዘጋችው።

ድንጋጤዋን ፊቷ ላይ ያየችው የመዝገብ ቤት ሠራተኛ፣ "ምነው ሚስጥርዬ ... ችግር አለ እንዴ?" ስትላት ራሷን እያረጋጋች የደረቀ አፏን ለማርጠብ ሞከረች።

"አይ ... ምንም ... ምንም አይደለም ... ሰውዬውን ስለማውቀው ነው... ስኢዶን ነገርሽው እንደምፈልገው?" አለች ካርዱ ጠረጴዛዋ ላይ አስቀምጣ።

"አምን መጣሁ ብሎ ተከትሎኝ ነበር እኮ ... እንዱ ይሆት ይሆናላ የላንችዬ ነገር ... እስኪ ልየው" ብላ፣ በሩን ከፍታ ልትወጣ ስትል፣ እሱም ደርሶ ኖሮ በደማች ፈገታው ከፍሉን አጥለቅልቀት ገባ።

"ሄይይ ... ፒስ ነው ..." ብሎ ሊጨብጣት እጁን እየዘረጋ ፊቷ ደሀና ሰላልመሰለው፣ "ችግር አለ? ... ምን ሆነሻል?" አለ።

ከፊቷ ያለውን ቻርት ፎቶው ባለበት ገጽ አድርጋ እየሰጠችው ንዴት በተቀላቀለበት የሚንቀጠቀጥ ድምፅ፣ "ሉክ ... ደግሞ በዚህ መጣ ... ታካሚ ምክር ፈላጊ መሰሉ ...ያረፈት የሆነ ነገር ... እሷን ካላየው ብሎ ነበር አሉ ... እሺ እንዴት ነው ሊገባው የሚችለው ... ልጁ ሜንትላቱ ውስጥ የተጠቀጠቀው ጥጥ ነው እንዴ...?" ካርዱላይ ያለውን ስምና ፎቶ ካየ በኋላ ማን ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬ ቢያድርበትም፣ ርግጠኛ ለመሆን፣ "ማነው ይሄኮ አለ

@OLDBOOOKSPDF

"ስሙን ቀይሮ ተመዝግቦ እኮ ነው ... አቶ ማስረሻ" ድንጋጤዋ ወደ ንዴት ሊቀየር ፣ ቢሮዋ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ተንጎራደደች ። ተመልሳ ጠረጴዛዋ ጠርዝ ላይ ተቀመጠች ።

"ከካርድ ከፍል እንዴት አመቱት? ... ነው ወይስ አንቺም አየሽው እዚህ ግቢ" አለ ፣ ገራ እንደገባው ።

"ፎቶ ለመነሳት ብዙ እንገራገር በግድ ነው እሺ ያላቸው ። እዕን ካላየሁ ብሎ ሊያስቸግራት ... ነገረ ስራው ብዙም ስላላማራት ... ሰናይት ናት ቀጠሮውን ከመያዟ በፊት የነገረችኝ ። እኔ ኮ ይሄንን አውራ ... ሞርን የሆነ ለብር ... አውንስ እሱን የማላይበትና ስለርሱ የማልሰማበት ቦታ የት እንደምሄድ ግራ ነው የገባኝ ..." አለች ። ቁጣዋ ከሞንቶት ጋር ተቀላቅሎ አይኖቿ በእንባ ሞሉ ።

"እንዴ ... ሚስጥርዬ ... ምንድነው አሱ? አለቀስሽለት ማለት እኮ በርሱ ቁጥር ስር ራስሽን አስገባሽ ማለት ነው ። ቀይ ምንም ነገር ለማድረግ ከመቸኮላችን በፊት ለምን ዶክተር ሌላን አናማክረውም ። በዚህ ጉዳይ ላይ አሞርተሽው ታውቂያለሽ" አለ ትክሻዋ ላይ ጣል ባደረገው እጁ እሽት እሽት እያደረጋት ።

"ምኑን እነግረዋለሁ ስሊዶ ... ምን ለውጥ ያመጣል ለርሱ ማማከሩ? እሱ የራሱ ብዙ ችግር አለው ... ለሆነው ላልሆነው እሱን ማስቸገሩ አይታየኝም ። በቃ እዚህ ከሊኒክ ልትታይ አትችልም ... ሌላ ቦታ መታየት ትችላለህ ብሎ ማሰናበት ነው" አለች አይኖቿን እየጠራረገች ።

"እሱንማ በፈለግሽው ጊዜ ማድረግ ትችያለሽ ... ምናልባትም ደግሞ የማይክ አታካሪ ውስጥ መግባትም ሊሆን ይችላል ። እሱም የሚፈልገው ያንነው ሊሆን ይችላል ። አሁን ዶክተር ሌላ ገብቶ ከሆነ ሥራ ከመጀመሩ በፊት እሱ ጋ እንሂድ ። ገዴለሽም እናማክረው ... ሚይ ቢ ... ምንም ያላሰብነውን አትጣጫ ሊያሳየን ይችላል ። ገዴለሽም ... በኔ ይሁንብሽ" ብሎ ቻርቱን እንደያዘ ባንድ እጁ የመኮተት ያህል እየሳባት ሊሄድ ሞከረ ።

"እሺ ቀይ ... አት ሊስት ፊቴን ልታጠብ ... እሺ ደግሞ ምንድነው የምንለው?"

"እዚው እጠብትሻለሁ ደርሰሽ ነይ ... ሁሉንም ነገር ከመጀመሪያ ጀምረሽ በዝርዝር ብትነግሪው ጥሩ ይመስለኛል ... ስራ ጀምሮ ሌላ ሀመም ተኛ ማየት ሳይጀምር ቶሎ እንሂድ ለማንኛውም ..." ብሎ ተቀመጠ ።

ፊቷን ታጥባ ትንሽ ተረጋግታ ስትመጣ ፣ "ለው እንዴት ነው እንደዚህ እንደ መሸገር ተጣብቀ አልላቀቅ የሚለው ። ፓራላይት የሆነ ነገር ... እዚህ አስገብቶ መለጥለጥ ነበር ... ለሱ ሌላ መድሃኒት አይታየኝም" ተከታትለው ወደ ሌላው ቢሮ ሲዶርሱ ቢሮው ገብቶ ከከምፒዩተሩ ፊት ለፊት ቁጭ ብሎ ኢሜይል እየመላለሰ ስለ ይዞ ደረሱ ። በትርብ ያፈላው ቡና መጣ ቢሮውን እውዱታል ። ቀና ብሎ አያቸውና እንዲቀመጡ በእጁ ምልክት አሳያቸው ።

@OLDBOOOKSPDF

ስልኩን ጨርሶ ወደ እነርሱ እየሄደ ፣ "ይትርታ ... ደህና አደራችሁ ... የሚገርም እኮነው ... በጠዋቱ ... ስልክ አውርተሃል ብሎ አንዱ ፖሊስ ከመራት ተንሰቶ አስቲሞኝ ... ኧረ እኔ ከሙዚቃ ጋራ አብሬ ነው የዘፈንኩት ... ከፈለገህ ስልኩን አይ ብለው ... ሊሰማኝ ነው ። ... ለካ ይፈለገውን ፈልጎ ኖሯል ... መንገላታት ካልፈለግህ እዚህ ልቀጣህ እችላለሁ ... ዶክተር እርሶን የሚያክል ሰው ስሌላው ሰው አርአያ መሆን ሊችሉ ቅብጥርሴ ምናምን ሲል ብልሞ ብሎብኝ ነበር ..." ብሎ እየሳቀ ጨብጧቸው ከለመደው ሶፋ ላይ ተቀመጠ ።

"ታዲያ እሳው ተቀጣህ ... ወይስ ምህረት አደረገልህ?" አለ ሳንቾም እየሳቀ

"ወይ እሳው መቀጣት ... ምንም እኮ በቃ ... ተንጋግሮ መግባባት እንኳ አስቸጋሪ ነው ። መንሻ ፈቃዱ ላይ ዶክተር ... የሚለውን ሲያይማ በቃ አስተምሮ ሊገድለኝ ነበር ። ኤኒ ዊይስ መንሻ ፈቃዱን ወሰዶ ቲኬት ጽፎ ሰጠኝ" ብሎ ወደ ምስጢር እየ ። "ሰላም ነው? ሚስጥር ምነው ፊትሽ የተረበሸ ይመስላል?" ሲላት ጸጥ ብላ ቀይታ ድንገት ማልቀስ ስትጀምር ተደናግሞ ከጮኗ ተቀመጠ ።

"እንዴ ... ምነው ... ምን ሆንሽ?" ቢላትም ሳግ ይዟት መናገር ስላልቻለች ትከሻዋን እያሻሸ ወደ ሳንቾ ሲመለከት ቻርቱን ሰጠውና የሆነውን ሁሉ ከሚያውቀው ታሪክ ጀምሮ ባጭሩ አስረዳው ። እሱ ባጠራ ቁጥር ሳታቀም የምታስትሰው ምስጢርን በማባባል አይነት ጀርባዋን እያሻሸ "እይ አም ሶሪይ ... አይዞሽ ..." እያለ ሳንቾን ሲያጽምጥ ቀየ ። "እንዴት አልነገርሽኝም ይሄ ሁሉ ሲሆን ..." አለ ገንበስ ብሎ ተጨማሪ ናፕኪን እያቀበላት ረጋ ባለ ድምጽ ።

እንባዋን በጥንታቱ ካይኗ ላይ እየጠረገች ፣ ለቅሷን ለመግታት ሞክረች ። "ምን ብዬ ልንገርህ ... ደግሞ በስንቱ እናስቸግርህ ... በቃ ጋብ ያለለት መስሎኝ ነበር ደግሞ ..."

"ኖ ኖ ... ሚስጥር ... እንዴት እንደዚህ ታስቢያለሽ ... ደግሞ ምን አስቸገረሽኝ ታውቂና ነው? ... ይሄ ደግሞ ቀላል ጉዳይ አይደለም ... ይሄንን ያህል አፈክት እያደረገሽ ... ለመሆኑ መቼ ነው መጨረሻ ያየሽው ወይም ከሱ የሰማሽው?" አለ ትንሽ እስክትረጋጋ ጠብቆ ።

"እኔንጃ ... ሁለት ወር ወይም ሦስት ወር ... እንተ አሜሪካ እያለህ ከሊኒኩ ከመለፈቅ በፊት ብሶበት ቁየና ደግሞ ለሁለት ወር ያህል ደብዛው ጠፋ ። ችግሩ ኮ ... ልጁ ጠፋ ስትሰው ይመጣል ። ሩት አገር ይሂድ ፣ ከጀርባዬ እየተከታተለኝ ይሁን እንኳ ሰግቶት አልችልም ። እርግጠኛ ነኝ የምሠራውን ስራ ... መቼ መቼ ቀን እንደምገባ ሁሉ ሲከታተል ነበርሞ ነው እንጂ ፣ ድንገት አልመጣም" አለች ፣ በታከተው ድምጽ ።

"ይትርታ ... እኔ እንድ ተጠሮ ሰላለኝ ልሂድ ... ብዙ አልዮይም ... እመለሳለሁ ... በቃ እናንተ አውሩ ። እኔ ግድሬግ ያለብኝ ነገር ካለ ... እይዞሽ እሺ ..." አለና ሳንቾ ፣ ባንድ እጁ ማጅራቷን ሳጫን ሳጫን አድርጎ ወጣ ። ሌላሠውም ፣ "እንድ ጊዜ ሁለት ደቂቃ ጠብቂኝ" ብሎ ፣ ወደ ካርድ ክፍል ሄደ ። ለጠዋት የያዛቸውን ሁለት ተጠሮዎች

@OLDBOOOKSPDF

ወደ ከሰዓት በኋላ እንዲያዞሩለት ነግሮ ተመለሰ። "ጠጣ ብለን ብናወራ ይሻላል ... እንሂድ?" ሲላት፣

"ቀጠሮ የለህም ከህመምተኞች ጋር?" አለች ደንገጥ ብላ።

"ከዚህ የሚበልጥ ነገር የለም። ወደ ከሠዓት በኋላ እንዲያዛውሯቸው ነግራያቸዋለው"

"ኦህ እሺ ... በታ ቢሮ ደረስ ብዬ ቦርሳዬን ልያዝ?" ብላ ተነሳች።

"መኪና ውስጥ ጠብቅሻለሁ" አለ። ቻርቱ ላይ የተቀመጠውን ምስል እያጠና። እያንዳንዱን ህመምተኛ በትክክል ለመለየትና አንዳንድ ማጭበርበሮችንና ስህተቶችን ለመከላከል ሁሉም ህመምተኛና ምክር ፈላጊ ፎቶግራፉ ከግል ማህደሩ ሬት ለሬት ገጽ በውስጥ በኩል ይደረጋል። ካርዱን ጠረጴዛው ላይ ወርወር አድርጎ፣ ስልኩንና ቁልፉን ይዞ ወጣ።

ጸጥ ያለ ቦታ መርጠው ወደዚያው እያመሩ፣ "ቅይ እሁን ስላለው ስለ ገል ሕይወቱ ... ማለት የትና ከማን ጋር እንደሚኖር ... ምን እንደሚሰራ ምናምን የምታውቂው ነገር አለ?"

"ምንም አላውቅም ዶክተር ሌላ ... ዩኒቨርስቲ እኔ የሁለተኛ አመት ተማሪ ሆኜ ስድስት ኪሎ ግቢ ውስጥ ነበር። ሰባት ሰምንት ዓመት አልኖረም ብለህ ነው? ... መቼም ነዋሪ እንጂ ተማሪ ሊባል አይችልም። እኔ ከወጣሁ በኋላ ስንት ጊዜ እንደቀየ አላውቅም። ወይ አያባርሩት ወይ አያስመርቁት ... ስንት ልጆች እንዳስታየ ኮ ልነግርህ አልችልም። አንድ የሱ ቢጤ ዘልዛላ ባለ ስልጣን አጮት አለው ... ማን ደፍሮ ይንካው።

"ተካስሰን ፍርድ ቤት ሁሉ ሄደን ነበር። ተስማሙ፣ ቅብርጥሴ፣ ስለሚወደሽ ነው ምናምን ይሉና አድበስብሰው ይለቁታል። ሁለት ልጆች በሱ ምክንያት ትምህርታቸውን ጥለው ወጥተዋል። አንዷን ልጅማ እንዴት ባደባባይ፣ ለዛውም በቀን መሬት ጥሎ ሲረግጣት በስንት ምስክር እየታየ ... በታ ምንም ... ጥበቃዎቹ ብትል አስተዳደር ..."

ስለርሱ አንዳንድ ነገሮችን እየጠየቃት ሲደረሱ መኪናውን አቁመው ወደ ውስጥ ገቡ። ጸጥ ያለ ቦታ መርጠው ወደ ጥግ ላይ ተቀመጡ። ካፈው ውስጥ ብዙም ሰው አልነበረም። "ለመሆኑ እናትሽ ምን ያህል ያውቃሉ?" አለ፣ የሰማው ነገር ከአእምሮው በላይ ሆኖበት።

"እሷማ ገና ስሙ ሲነሳባት ነው የምትይዘው የምትለቀውን የምታውቅ። አንድ ቀን የሚገድለኝ ወይ ጠልፎ ይሠኝ የሚጠፋ ነው የሚመስላት። ያልደረሰችበት ቦታ የለም። ውጭ ሀገር ብሄድላት ሁሉ እርይ የምትል ይመስለኛል። አሁንማ እኔም ከዛ ሌላ ምንም ተስፋ ያለኝም አይመስለኝም። ባለፈው የዛሬ ሦስት ወር ግድም አሁንም እንደገና እንደሚከታተሉኝ ስታውቅ ደህና የተሻላት ነገር ሁሉ ተቀስቅሶ እንደሽ ርብሽብሽ አለች። እኔ ኮ የማይገባኝ ... እላዬ ላይ ሉዘር ሉዘሩን የሚሰብ ማጌት

@OLDBOOOKSPDF

ተጥሚል እንዴ" ... ይሄ ኮ ሦስተኛ መሆኑ ነው ... ከሁሉ የባስ መንቻካ ሆነ እንጂ ..." ብላ፣ እንድገና ሣልቀስ ጀመረች ። ከኪሱ ሠስኖ ናፕኪን አውጥቶ ሰጣት ።

"አሀ ሌላም ተመሳሳይ ዓይነት ነገር አጋጥሞሽ ነበር?"

"ሃይ ስነኑል እያሰው እንድ መላ ቢስ የሆነ አስተማሪ ... በታ አላስገባ አላስወጣ ብሎ ቢያስቸገረኝ ... የምታደርገው ብታጣ እናቴ ሌላ ትምህርት ቤት አስገባችኝ ። ከዛ ደግሞ ፍራሽ ማን ይር ላይ የሆኑ ትልቅ ሰውዬ ... ለሳውም ባለ ትዳርና ከኔ የሚበላልጡ ልጆች ያላቸው ሰውዬ ... እየመጡ በር ላይ ይጣዱ ነበር ። በኋላማ ግቢ ለመግባት ብለው የማታ ትምህርት ተመዘገቡ ። እፍረት የሌላቸው ሰውዬ ... ሌላም ሰራ ያላቸው እየመሰሉሀም እኮ ። መኪና እየቀያየሩ ... ባልጠብኩት ሰዓት አጠገቤ ይቀማሉ ። በኋላ ሰው አስቀጥረን ማንነታቸውን ካጠናን በኋላ ሰባለቤትም ነው የምንነግረው አልናቸው ። የባሰ 'ብሞን እድሉ ... ላንቺ ሰል እንኳን ትዳሬን ሀይወቴን እሰጣለሁ' እይሉኝ መስለሀ" ብላ ፣ ስትሥቅ እሱም ገርሞት

"ወይ ጉድ . ." አለ ።

"በኋላ ቢቸግረን እኔም መንዳት ጀመርኩ ። ሽማግሌው ም ምን እንደሆኑ እንጃ ጠፉ ጠፉ ። ከዛ መሸገር የሆነ ይሄኛው መከረኛ ጉድ መጣልኛ ... ይሄው ስድስት ግመቱ ።

"እም ረስቼው ... አንዱ ጉድ ደግሞ ማስተርሴን ጀምሬ በስድስት ወሩ አካባቢ ነበር የሆነው ። እንድ ከውጪ መ-ቸ እድርጎ የመጣ ዳያስፖራ ተብዬ ነበረ ። በስግም ሰው እንደዚህ ይጃሻላል ። መጀመሪያ እንዴ ጤንኛ ስልሙን ሰው ነበር የቀረበኝ ። ከዛ ሁኔታውን አይቼ ፊት ስነሳው አመጣሁ ። እንዴ እንዴ ልጅ ያለትሳል ... የሚስማው ሲያጣ ደግሞ እንዴ ጦረምሳ ለማስፈራራት ይሞክራል ።

"በታ እንዴት እንደሆን አላወቅም ... እኔ ካለሁ እሱን እዛ ሥፍራ አታጣውም ። ... አንዳንዴ እላዬ ላይ መከታተያ መሣሪያ እኔ ሳላወቀው ያስገጠመል ኝ ሁሉ ነበረ የሚመስለኝ ። በኋላማ ለይቶለት ጅዝብ ብሎ እኔን መከታተል የሙሉ ጊዜ ስራው ሆነ ። መዉረሻ ላይ ... ታሞ አማኑኤል ገባ አሉ ። ከዛ ወዲህ አላየሁትም ። ስንት ቀን በድንጋጤ ነፍሴን እንዳወጣት አትጠይቂኝ ..." የመጣላቸው ማኪያቶ ቀዝቅዞ ስለነበር ልጁን በምልክት ጠርቶ እንዲያስሞቅላቸው ነገረው ።

አቀርቅራ መሬቱን በእግሯ ስትጠበጠብ ቀየችና ፣ "ቀይ ግን እኔ ... ምንድነው ችግሬ ... መቼም የሆነ ችግር ባይኖርብኝ ይሄ ሁሉ ሲሆን አይችልም ። ያላነበብኩት መጽሐፍ የለም ። ይዤው ሳይኮሎጂም አጠናው ። ነገሩ እንኳን ሊገባኝ የባስ ነው ግራ የገባኝ ። ቀይ ግን ምንድነው ችግሬ?"

ጠረጴዛ ላይ ያለውን እጁን መታ መታ አደረገና ፣ "የመጀመሪያው ነገር ... ችግሩ እንዲፈጠር በምክንያትነት ራስሽን ለመውቀስም ሆነ ለመወንጀል ማሰብ የለብሽም ። እንቺ ተጠቂና የችግሩ ገፈት ቀማሽ ነሽ እንጂ ፣ የነገሩ ጠንሳሽና ጠያቂሽ በራስሽ ላይ ያመጠሽው ነገር አይደለም ። እንግዲህ ለምን ከሌላ ሰዎች በላይ ነገሩ እንቺ ላይ ጠና

@OLDBOOOKSPDF

ወይም ተደጋግሞ ያረሰ ... ምናልባት ብዙ አስተዋጽኦ ያደረጉ የሰብአናና የሀያ ጫት አጋጣሚዎች የፈጠሩት ነገር ሊሆን ይችላል ።

"ለምሳሌ ቀንጮ መልዘሽና ተግባቢ ሰብአናሽ በቀላሉ የሰዎችን ቀልብ ሊስብ ይችላል ። በባህሪሽም ሰዎችን መርዳትና ተርቦ ስሜታቸውን መረዳት ላታስቢው የምታሳዪው ዝንባሌ መሆኑ ፣ ደካማና የተዛባ የስሜት ብስለት ያላቸው ሰዎች በቀላሉ አንሻፈው ሊያነቡት ይችላሉ ። ለማገዝና ደግ ለመሆን ያደረግሽው ነገርም ይሁን ለመቅረብ የምትቀዪ አይነት ሰው መሆንሽ ፣ የያዙንታ ፈታኝ መሰሏቸው ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ሊረዱሽ ይችላሉ"

"እኔ እንጃ .. እኔ ግን እሱ ብቻ አያመስለኝም ። ለምሳሌ ... ሲርየስ ሊባል የሚችል ግንኙነት የነበረን ሶስት ቦያፍራንዶች ነበሩኝ ። ሁሉም ግን ለሴት ከብር የሌላቸው ፣ እምነቶችና ጠጪዎች ነበሩ ። መጀመሪያ ላይ ሲቀርቡኝ ... ምን ልበልህ ቀልደኞች ... ፍቅር የሚያዘንቡ የፍቅር አማልክት ያመስላሉ ። ለጥቂት ወራት ልቢ እስኪጠፉ ያክንፉኝና . ከትዝቴ ስባንን ... ሉዘርስ ሆነው ያገኛሉ ። ከጸባያ ጸባይ የላቸው ... ሚራሽ እኔ አሽከራቸውና የእነሱን ችግርና ህብት ተሸካሚ ሆኜ ቁጭ እላለሁ ።

" ሳስበው ሳስበው .. ሁሉም የምሽሽው ከአባቴ ጥላ ነው ። ራሴን የማገኘው ደግሞ ቁጭ እሱን ከሆኑ አውራዎች ጋር ያሆናል ። መቼም ይሄ አጋጣሚ አያመስለኝም ... በቃ አንዳንዴ ራሴን ሁሉ እፈራዋለሁ ። የማያሆን ሰው ላይ መድቴ እድሜዬን ሁሉ ስማትት እንዳልኖር" አለች ፣ ትንሽ እንደማፈር ብላ ። በመስክቱ አሻግራ ወደ ጠጭ እያየች ጣቶቿን ተራ በተራ እንቋቋች ።

ቀስ በቀስ እየጠየቃት ፣ ከልጅነት ጀምሮ ያላትን ሕያወት ከዛ በፊት ለማንም ነግራው በማታውቀው ዝርዝር ነገረችው ። ከአባቲ ጋር ስለነበራት ግንኙነትና ለምን እንደምትጠላቸው ሲጠይቃት ዝም ብላ ቀየችና ድንገት ፊቲ ተለዋወጠ ። እምባዋ ዱብ ዱብ እያለ መውረድ ሲጀምር ፣ ተደናግጦ ወነበሩን ወደ እርሷ ተርቦ እድረን ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠችውን ናፕኪን እያቀበላት ፣

"በቃ በቃ ... ተዪው ... ያትርታ ..." ብሎ ሊያባብላት ሞከረ ። ፊቷን በሁለት እጆቿ ሸፍና ጸጥ ብላ ትቀያና በመሃል አልሀና ላግ እየተናነታት ስትሰት ብላ ታለትሳለች ።

"ያትርታ ... ስለ አርሱ ገና ላስብ ውስጤ ሁሉ ነው የሚገለባበጠው ። ያዩንን ካክስቲ በቀር ለማንም ነግረው አላውትም ። እማሚ እንኳንየም ታውቅ እያመስለኝም ። ልትጠረጥር ትችላለች ፣ ግን በቃ ብታውቅ ልቧ በሐዘን ሊሰበር ይችላል ብዬ ስለምፈራ አልነገርኳትም ። በውስጤ የተዘጋ ፋይል ነው ።

"ካስመራ እስክንመጣ ድረስ በቃ ባቢ በጣም ጥሩ አባት ነበረ ። ምን ልበልህ ... ያለኔ ልሱ ሰው የለም ። የሱ አለም በስራውና በኔ ዙሪያ ነበር ። እዚህ ከመጣን በኋላ ቀስ በቀስ ጸባዩ እየተለመጠ በጣም ሰካራምና ቁጡ ሰው ሆነ ። ማሚን መዝራዋን ሲያሳያት

@OLDBOOOKSPDF

...ምን ላድርግ እኔ ... ልጅ ስለሆንኩ በምንም መንገድ ልረዳት አልችልም ነበር። በኋላ ላይማ ስድስትና ድብድቡ እየባሰ መጣ። እያስተወከ ሲያንራራ ማደር ሆነ ስራው። የሚመጣው ደግሞ ሴሊት ስምንት ሰአት ምናምን ነው።

ሲያናፋው ደግሞ የተዘጋጀውን ራት ከጠረጴዛው ላይ አሽተንጥሮ ያደፋዋል። መጀመሪያ ላይ ሳሎን ቤት ሶፋ ላይ ማደር ጀመረ። አንድ ቀን ጥንብዝ ብሎ በተጥ-ሞጥ አደ ጋ መጥቶ አጥ ብሎ ተኛ። በቃ ማሚንም ያላረፍኳት ስለመሰለኝ ደስ አለኝ። ከዛ በኋላ ከኔ ጋር መተኛት ልማዱ ሆነ። እንዴት ቀንጅ እንደሆንኩና ጥሩ ልጅ ከሆንኩ ደግሞ የፈለኩትን እንድሚያደርግልኝ ... መሰከሩንም እንድሚያቀም ሲነግረኝ የበለጠ ደስ አለኝ።

"ያኔ አስራ ሁለት አመቴ አካባቢ ነበር መሰለኝ። ከዛ የማያውን ቦታ ሊነካካኝና ሲተሻሸኝ እየቀፈፈኝ ተው ሰለው ... አንዴ ያስትሳል ወደ ደግሞ ማሚ, እንደሚገድላትና ራሱንም እንድሚያጠፋ ሲነግረኝ እየፈራው ዝም ማለት ጀመርኩ፣ አንዳንድ ቀን ራቁቱን አልጋ ውስጥ ይገባና በቃ ምን ልበልህ ... በመሸ ቁጥር ስቃያ ሆነ። ስቃዩ ጋብ ሲልላት መሰለኝ ማሚም ምንም እንዳልሆነ እሷም ዝም አለች። ትወት አትወት ርግጠኛ አልነበርኩም። ለሷ እንዳትጨነት ያገባኛት ስለመሰለኝ መንገሩንም ፈራው።" ብላ እንደገና ስትስት ብላ ስታለቅስ እጁን እያባበለ ሊያባብላት ሞከረ።

"የተፈጠረውን ሰላም የሚበጠብጠው ወይም የሚፋቱብኝ ስለሚመስለኝ ዝምታን መረጥኩ። በቃ ሰማን ልናገር ... ነጋ ጠባ ራሴን መውቀስ ... ቀሻሻ እንደ ነገው ዕቃ ራሴን መጸየፍ ጀመርኩ። ባጠቃላይ የሱ ማስፈራራት፣ የሚሰማኝ የሆነ ፍርሃት፣ ሃፍረትና አቅመ ቢስነት ተደራርቦ አፈን ለጉመው። አንድ ቀን ድብልቅልቅ ያለ ሞል ተባለና ልብሷን ጠቅልላ ብድግ ብላ ስትሄድ እኔን ይዛ እንዳትሄድ ከለከላት። እኔም ከሄድሽ ራሴን አጠፋለሁ ብሎ ነገሮኝ ስለነበር፣ ከርሱ ጋር አቀያለሁ አልኩኝ። በሁለተኛው ቀን ስነር ብሎ መጥቶ ..." ብላ፣ እንደገና መንታ መንታ እንባዋ ዱብ ዱብ እያለ ማልቀስ ስትጀምር ሲያባብላት ረጅም ደቂቃ ወሰደበት።

ያዛን ሴሊት በግድ ከደፈራት በኋላ ህይወቷ ሁሉ እንዴት እንደ ኮመስታወትና ከሌት ጠፍታ አከስቲ ጋ እንደገባች በዝርዝር ነገረችው። ይህም ወንዶችን ለማመንም ሆነ ራሷን ያለ መከልከል ለሌላ ለው ለመስጠት የፈጠረባትን ችግር ልታስረዳው ሞከረች። በነበድት ግንኙነቶች ውስጥ ሁሉ ከማያውን ወንዶች ጋር እንድትሆን ከውስጥ የሚገፋፋት ከዚህ ጋር የተያያዘ ችግር ይሆን ብላ እንደምትጠረጥርም ነገረችው። ለረዥም ጊዜ በጽጥታ ሲያጸምጣት ቀየ።

"ሚስጥርዬ ... አይ አም ሶ ሶሪይ" ብሎ እጁን ጨመቅ አድርጎ ያዛት። ፕያረስብሽ ነገርና ያሳለፍሽው ስቃይ ሁሉ ሊሆን የማይገባ ነገር ነው። ማወቅ ያለብሽ አንዱም ነገር ያንቺ ምርጫ ሳይሆን አንቺን ሊገልባበሁና ሊጠብቁ የሚገባቸው አባትሽ የፈጸሙት ከፋ ጥፋት ነው። በልጅ አእምሮ ራስን መውቀስና በደለኛ አድርጎ መቁጠር፣ ከደረስብሽ ነገር ድግሞ እንደ ገሥሉና የገፃ ሰውነትሽን እንደ ቀሻሻ ዕቃ መቁጠር በዚህ

@OLDBOOOKSPDF

እይነት ስንክላ የሕይወት ዕድል ሙሰኞ የሚያልፉ ልጆች ሁሉ የሚሰማቸው ተመሳሳይ ስሜት ነው ። ነገሩ ከባድ የሙሰኞ ቁስለትን የሚያደርስ ነው ።

"ስሙን የማመን አትምሽነና ለራስሽ የምትሰጪውን ዋጋ ከመሸርሸሩም በላይ፣ እንዳንዴም ለማይሆኑ ሳይነት ግንኙነቶች ሊያጋልጥሽ ይችላል ። በግንኙነቶችሽ ሙሰኞ ጥቃቶችና በደሎች ሲፈጠሩ እንደ ትዝከል የማየትና መብትሽ ሲጣስ እያወቅሽም ለረጅም ጊዜ ዝም ብሎ የማየትን የተዛባ አስተሳሰብን ሊፈጥርብሽ ይችላል ። እንዳንድ ልምች ስብእዊ ክብራቸውን የሚነፈጉበትና እንደፈለጉ የሚጫወቱባቸውን ሰዎች እንኳ እንደ አፍቃሪ የማየትና በስቃይ ሙሰኞ የመኖር ዝንባሌም ሊያሳዩ ይችላሉ ።

"ብቱላሉ በጸጸትና በፍርሃት የመወረስ ሁኔታ ስላለ ፣ ሌሎች በቱላሉ በስሜትሽ ስሰንትና በራስሽ ላይ በምትፈጥሪው አላስፈላጊ ግፊታ የግል ፍላጎታቸውን በቱላሉ ሊፈጽሙብሽ ይችላሉ ። እንዲያውም እንደ መጠኞ ባሉ የቱለያዩ ሱሶች የቱጠመደ፣ በሚስትና በልጆቹ ላይ ጥቃትንና ግፍን የሚያደርስ አባት ያላቸው ሴት ልጆች የሚታይ ተደጋጋሚ ባህርይ አለ ። እነዚህ ልጆች ሲያድጉ በተራቸው ያንን በልጅነታቸው ባባታቸው ላይ ሊፈቱት ያልቻሉትን ችግር ፣ የሚፈቱበት መንገድ ሲፈልጉ ዕድሜ ልካቸውን ሲማስኑ ይኖራሉ የሚል ግምትም አለ ።

"ስለዚህም ነገሩን ባለ መረዳት ... ከስካራም ወደ ስካራም ... አነላላጭና ሥነልቦናዊ ስቃይን ከሚያደርስባቸው አንድ ግንኙነት ወደ ሌላው ሲዘሉ ይኖራሉ ። ይህንን የሚያደርጉት እመቱመትና ተረድተውት ሳይሆን የሙሰኞ ገፈታቸው እየነዳቸው ነው ። ትልቁ ነገር ከሙሰኞ ያለሙን ቁስልና ተጋላጭነት በመረዳት ፣ ባለፉ ጊዜያት የደረሱ ነገሮችን በትክክል ማሰረያ እየሰጡና ወደ ዕሙትና እያመጡ ማለፉ ላይ ነው ። ይሄ ሰፉ ነገር ስለሆነ ጊዜ መስደን መንጋገርና የበለጠ መረዳት ያስፈልግሽ ይሆናል" ብሎ ዝም አለ ። ከሙሰኞ ካንጀቱ አላዘነችው ... ስቃይኞ ተሰማው ።

"እሺ ..." ብላ በረጅሙ ተንፈሰች ። ትክዝ ብላ ሜንትላቷን በግራ እጇ ላይ ደገፍ አደረገች ።

"አሁን ግን ... ይህንን ሰሙ በተመለከተ ምን እናድርግ የሚለው ላይ ማተኩሩ መትይም አለበት"

ድንገት ግንፍል አለች ። "የፈለገበት ሄዶ ይታከም ወይም ይመክር ... ለእሱ እስር ቤት እንጂ ምክር አይደለም የሚገባው" ሀዘኗ ሁሉ ድንገት ወደ ቁጣ ተቀያየር ።

"ልክነሽ ሚስጥርዩ ... ግን ደግሞ ... እሱ የሚያስበው ስማወትም ሆነ ምናልባት ከታቻለም ለማስቀየር ... ይሄ ሚስ ማድረግ የሌለብን ትልት ዕድል ሊሆንም ይችላል" አለ ፣ ፈራ ተባ እያለ ።

"እኔ እንደሆንኩ እንኳን ላየው ይትርና ... እዚህ ከሊኒክ የሚታዩ ዘቦን ... እዚህ መስራት የምትጥል አይመስለኝም" አለች ፣ ቁርጥ ቁርጥ በሚል ድምጽ ።

"እህ ኖ ኖ... አንቺማ በምንም መንገድ ልታዪው አትችይም ... እኔም እሱን ማለቱ አይደለም ። ግን እዚህ አትታይም ስላልነው እንቺን እያደባ መከታተሉን

@OLDBOOOKSPDF

እያቀምም ። እንዲያውም የባስ ሊመናችህና ሊያጠቃሽ ይችላል ። ያስብኩት እኔ ራሴ ላለው ነው ... ፈታኙኛ ከሆነ ። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ከሚያሰፈሪ ሩት በላይ ፈሪዎችና በውስጣቸው በብዙ ዝብርቅርቅ ጨነነት የተሞሉ ናቸው ። እንዴት እንደሚያስብና ምን እንደሚያስብ ማወቁ የሚረዳን ከሆነ እሱን ለመርዳት ብቻ ላያሆን እንቺም ምን ማድረግ እንዳለብሽ የበለጠ ማወቅ እንድትችይ ይጠቅመናል ብዬ አስባለሁ"

"እንደሱ አላስብኩትም ነበር ... ግን እሱ እኔ ያለሁበት መሆ ነና በትር በ ለመጥየት የሚያደርገው ጥረት ከሆነስ?"

"ኦህ እሱማ የታመቀ ነገር ነው ። መጀመሪያ ላይ የማቀርብለት ትድመ ሁኔታ ይኖራል ። እንደኛ የማየው አንቺ ከለኒክ በማትገቢ ቀን ነው ። ሀ ለተኛ በምንም መንገድ አንቺን ሊያገኝሽ መሞከሬ ማድረግ አይችልም ። በተጨማሪም የማየው እኔ ብቻ ነኝ። በዚህ ከተሰማማ አየሞለሁ ... አለበለዚያ ሴላ ቦታ እንዲሄድ እንመክረዋለን ። ምን ይመስልሻል?" ሲላት ተንፈስ አለች ።

"ጥሩ ነው እንሞክረው ...ይሻላል መሰለኝ ..." ብላ ሰዓቷን እያየች "ወይኔ ... ሰዓቱ እንዴት ይሄዳል? በጣም ይቅርታ ግን ጊዚህን አታጠልኩብህ ... ፕሮግራምህን ሳላዛባብህም አልቀር" ስትለው ፥

"ምን ማለትሽ ነው? ከዚህ የተሻለም ሆነ የሚቀድም ምንም ነገር የለም ። እወን እንዴት ነሽ?"

ከወንበሯ ተነስታ በተቀመጠበት አንገቱን አቀፍ አድረገችው ። "ታንክ ዩ ሶ ማች ... እሁን በጣም አረፍ ነኝ ... ቶለል ብሎኛል" ብላ ሂሳቡን ለመክፈል ቦርሳዋን ስታወጣ ተሸቀዳድሞ ቢሉን ያዘና

"አልታሻ አይከፍልም ... አንድ ላይ ከቱራፒ ቢሉ ጋር ..." ብሎ ሲስት ፥

"ራስህ ነህ ያስለቀስከኝ ..." አለች ልብሷን እያስተካከለች ። መታ ጠቢያ ቤት ደርሼ መጣሁ ብላ ስትሄድ ለመሄድ ተዘጋጅቶ ጠበቃት ።

"ታዲያ ዛሬ ታየሞለህ ወይስ?" ብላ ከፊት ለፊቱ ቁመች ። ፊቷ አንጓራዊ ሰላም ሰፍኖበት ተረጋግታለች ።

"ሹር ... አንቺ ከሰዓት የምታደርጊው ነገር ከሌለሽ መውጣት ትችያለሽ ። ከቻለ ሰዛሬ ስምንት ሰዓት ቀጠሮ እንዲሰጡት እናደርጋለን" አለ ትንሽ ፈገግ ብሎ ።

እንደደረሱ ደውለው ማስረሻን ለስምንት ሰዓት እሱ ጋ እንዲቀጥሩት ነገሯቸው ወደ ቢሮው ገባ ። የተነጋገሩትን ሁሉ እያሰበ ጥቂት ጸጥ ብሎ ተቀመጠ ። ከመሄዱ ስትታይ ደስተኛ ፥ ቀንጆና ፍልቅልቅ ሰብእና ያላት ልጅ ናት ። በመስቢ ይዛ የምትሠራውን ሚስጥራዊ ስታያና ስጋት ግን ...ማንም ሊያየው አይገ ልም ። አይ ሰው መሆን ... ሰው አንድ ... ሰው ሁለት ... ወዚው ሴላ ሰው ... መስሙ ደግሞ ሴላ ...' አለ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 26 ፡

ሌላው የጊዚው ሙዚር ሳያው ቀው የምሳ ሰዓት ደረስ ። እዛው የክሊኒክ ፡ ካፌ ሽር ነዚ ተማመስና ቡናውን ቢሮ እንዲያመጡለት ነግሯቸው የቀረውን ፊዚ ከንጹሕና ከልጆቹ ጋር በስልክ ሲያወራ ቀየ ። ልጆቹም እንደ ልማዳቸው ሳያስትሰ ወነ ለረጅም ደቂቃዎች አወሩት ። ከሦስት ሳምንት በኋላ ወደ አሜሪካ ስለሚሄድ ሀሉም ደስ ብሏቸዋል ።

ለስም ነት አምስት ጉዳይ ሲሆን ከካርድ ክፍል ደውለው ·ማስረሻ· መድረሱን ነገሩት ። ቻርቱ ላይ የተጻፈውን ስሙን እየት አደረገና ባለ ተጠሮዎች ወደ ሚጠባበቁበት ሰፊ የእንግዳ መቀበያ ክፉል ሲደርስ ··ፍትሩ ታደሰ ' ብሎ ተጣራ ። ከወደ ጥግ ያለ ፕቁር ቀብና መነጽር ያደረገ ሰው ብድግ ሲል ወደ እርሱ ተረመደና ጠበቅ አድርጎ ጨበጠውና ·ዶክተር ሌላው·· ብሎ ሲተዋወቀው እንዳንበሰ ··ፍ·ት·ሩ·· አለ እርገጠኛ ባልሆነ ድምጽ ።

··የመጀመሪያ ጊዚህ ነው መሰለኝ·· ብሎ ፣ ፊቱን በማዮናት ዓይነት ሲያየው መጪነቱ ያስታወት ነበር ። ለካርድ ክፍሎቹ ምስጢር እንደማታየው እነዳንገሩት ስላዘዛቸው ቀጠሮው እንደ ተያዘለት ብቻ ነበር የነገሩት ።

··እሥን ... ግን እኔኮ ለማየት የጠየኩት ..·· ሲል ሃሳቡ ገባው ።

··እውታለው ... ያው ስለሱም እንድንነ ንገር ነው ። ፕሊስ በዚህ በኩል ·· ብሎ በሩን ከፍቶ ያዘለትና ተከታትለው ገቡ ። የቢሮው ትልትንትና የዕታዎቹ አቀማመጥ ሁሉም ነገር ከጠበቀው በላይና ውጪ ስለሆነበት ግራ ተጋብቶ እንደቆመ ቀረ ። በዘብ ወደ ተቀመጡት ሶፋዎች እያሳየው ··የሚመችህ ላይ ተቀመጥ·· ብሎት ፣ በመስኮቱ አንጻር ካለው የሁሉ መቀመጫው ቡኒ ሶፋ ላይ አረፍ አለ ። ቻርቱን ሲየገላበ ዮ ቀየና ፣ ተዳያስ እንዴት ነህ·· ብሎ ከላይ እስከታች ያጠናው ጀመረ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ደህና ፈጣሪ ይመስገንው ... ያው አንዳንድ ችግር መቼ ይጠፋል ..." ብሎ በስሱ ፈገግ ሲል ዘርዛራ ጥርሱና ቀይ ድዱ በነፈሰል ታየ። ትንፋሹ ላይ ተበታትኖ የበቀለው ቀናርፒ ያለው ጢሙ ጥቃትን የጠገቸ ኳሶች ከፊቱ ላይ የተረፈቱበት ይመስላል።

"ቀጠሮ ስታስይዝ ሚስጥር እንድታይህ እንኑ ጠየቅህ ነግረውኛል። በአንዳንድ ምክንያቶች እሷ ልታይህ አልቻለችም። ፈታይኛ ከሆንክ እኔ ላይህ እችላለሁ። ያዝተር ሴላሙ እባላለሁ። የአእምሮ ሃኪም ነኝ። የምክር አገልግሎትም ከሆን የምትፈልገው፣ እሱንም ማድረግ እችላለሁ" ሲለው፣ ፊቱን ቲምትርትር አድርጎ፣

"አመታለሁ በቴሌቭዥን የሰጠኸውን ኢንተርቪውም አያ ቻለሁ። ግን ማወቅ እችላለሁ ... እሷ ለምን ልታየኝ ፈታይኛ እንዳልሆነች?" ሲል

"እህ የቴሌቭዥኑን ታለመጠይቅ ተከታትለኽው ነበረ!" አለው ወደ ጥናው ድጋፍ ከመግባቱ በፊት ትንሽ ወዳጅነትንና መተማመንን እንዴት መመስረት እንደሚችል ዕድል እየፈለገ።

"ሁሉንም በደንብ ነው የተከታተልኩት ... በጣም ጥሩ ነው ... ለኛ ሳይኮሎጂ ለተማርነው ሰዎች እንኳን ጠቃሚ ነበር። ከሁሉም በላይ ሰው ሁሉ በተላሉ በሚገባው ደንቋለሆነ የምትናገረው ... በጣም ደስ ይል ነበር። ወደ ፊትም ተጨማሪ ኢንተርቪው ብትሰጥ ጥሩ ይመስለኛል" አለ ትንሽ ዘና ብሎ።

"እሀ ታንክ ዩ ... እ...ም ውሃ ለስላሳ ምናምን ከፈለግህ ..." አለ ለራሱ ውሃ ለማምጣት እየተነሳ። ከፀሐይ ላይ ስለመጣም ይሆናል የሚገመተና የሰውነቱ ጠረን የንባሬ ከሩቅ ይገፈትራል።

"ተዝቃዛ ኮካ ካለ ... ጉሮሮዬ ድርቅ ብሎብኛል" አለ፣ ጉሮሮውን እየጠራረገ።

ለስላሳውን ፊቱ አደረገለትና ተቀመጠ። "ከሚስጥር ጋር ካው ነበረ ፊት ትተዋወቃላችሁ?"

ያላሰበው ጥያቄ ስለነበር ድንግርግር አለው። "እም ... ም ... መተዋወቅ ከተባለ የኒቨርስቲ ውስጥ ባንድ ጊዜ ላይ ነበርን መሰለኝ ... እኔም ማይንሪ ሳይኮሎጂ ስለ ክር አንድ ሁለት ኮርስም አብረን ሳንወስድ አልቀረንም" አለ ጣራ ጣራውን እያየ።

"እህ ... ቀይቷላ ... ከዛ ወዲህስ ተገናኝታችሁ ታው ታላችሁ?" እንዴት መመለስ እንዳለበት ግራ ገብቶት ጥቂት ዝም ብሎ ቀየ።

"እይ መገናኘት ሳይሆን ... አልፎ አልፎ መንገድ ላይ ምናምን እየቻት አው ቃለሁ። እሷ ትየኝ አትየኝ አላወቅም።"

"ከዛ ያለፈ ወይም የተለየ ግን ምንም ትውውቅ የላችሁም?"

"ማለት?" አለ፣ ቀጣ ብሎ።

@OLDBOOOKSPDF

"አይ አብራችሁ ቡና መጠጣት ... ወይ በነርስ ወርክም ቢሆን ማህበረሰቧ ጓደኝነት ... ምክንያቱም ለምን እሷ እንድታይህ እንደፈለግህ ብዙም ሰላልገባኝ ነው" አለው ነገሩን ተለል አያያረገ ።

"እዩዩ ...ኛ ... ኛ ... አልር አልር ያንንት ሰላምታ ... ምናልባት እሷ ገቢ ውሰጥም ታዋቂ ስለሆነች ... ስልህ ባለመኪና ነበረች ... የሁሉ ሰው ጓደኛ ናት ... በትምህርቷም ገበዝ ቢጤ ስለነበረች ... ምናልባት እኔ ስለሷ ብዙ ሳላውት አልቀርም ። እንድታየኝም የፈለግሁት ለዚያው ነው"

የነገሩን አትባሜ በመቀየር፣ "ያትርታ ስምህ ማን ነበር?" ሲለው ሳያሰበው አመለጠውና "ማሰረሻ ..." አለ ።

"ኦህ ... ቻርትህ ላይ እንደሱ ነው የሚለው?" ግራ እንደ ገባው ሆኖ ቻርቱን ገልበጥ አድርጎ ሲያይ ግንባሩ ላይ ያቸፈፈውን ላብ በመዳፉ ጠረገና ፣

"ፍቅሩ ታደሰ የቤት ስሜ ነው ... እንዳንደ እሱንም አጠቀማለሁ" አለ፣ ለመረጋጋት እየሞከረ ።

ያለውን እንዳልሰማ በመሆን "የውልህ ማሰረሻ ... ሚስጥር ሁሉንም ነገር ነግራኛለች ። የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ከነበረች ጊዜ ጀምሮ ስለሆኑት ነገሮች ... እስከ ፍርድ ቤት ተዳርሳችሁ እንደ ነበረ ... በጥፊ ሁሉ መተሃት እንደምታውቅ ... ደግሞም ... የባሬ ሦስት ወር እካባቢም ስለሆኑት ነገሮች ። ስለዚህ አሁን ዳር ዳር ብንል ብዙም አይጠቅመንም ። ሚስጥር ልታደህ የማትችለው ለምን እንደሆነ የሚገባህ ይመስለኛል ።

"እንተ ደግሞ የምትፈልገው መታከምና ትክክለኛ የምክር አገልግሎት ከሆነ ... የምትረዳህ እሷ ልትሆን አትችልም ። በትክክል እገሳና ምክር ከፈለግህ እኔ ላይህ እችላለሁ ። እዚህ ክሊኒክ መታየት ከፈለግህ እኔ ብቻ ነኝ ላይህ የምችለው" መጀመሪያ ላይ ብዙ የማይሆን ከርክርና የተባለው ነገር ሁሉ ልክ እንዳልሆነ ሲያሳምነው ሞከረ። በመጨረሻ ያለውን ሁኔታና ውሳኔ ቁርጥ አድርጎ ሲነግረው ፣

"እሺ ግን ... እኔ ላንተ የምነግርህ ነገሮች ሁሉ በሚስጥር እንዲያዙልኝ እፈልጋለሁ ። ታዲያ ሰርጲም ቢሆን ለማንም ሚስጥሬን እንደማታካፍልብኝ በምን አውታለሁ?" አለ ጥርጣሬ በተሞላ አይነ ።

"ይሄ የመጀ ግዴታዬ ስለሆነ በርሱ ጉዳይ ልትሰጋ አያስፈልግህም ። ሚስጥርህ ማንም ሊደርስበት የማይችል የክሊኒኩ ሚስጥር ነው ። እዚህ የምታወራው ሁሉ እዚህ ታሽጎ ይቀራል ። ሆኖም ግን ራስህን ወይንም ሌላን ሰው ሊገዳ የሚችል ነገር ስታትድ ወይም ስትፈጽም ካየሁ፣ ሌላውን ሰው የማስጠንቀቅና አስፈላጊም ከሆነ ለሚመለከተው የሕግ ክፍል የማሳወቅ ግዴታ አለብኝ" ሲለው ፣

"እሱ ግልጽ ነው ... ምንም ችግር የለም ...እስማማለሁ" ብሎ፣ አሁንም እያመነታ ፣ "ታዲያ መቼ ነው ቴራፒውን ልንጀምር የምንችለው?" አለ ፣ የእድሰልኩን እያፈተለተለ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ባሪ መጀመር እንችላለን። በነገራችን ላይ እንድ ተጨማሪ ነገር ... እኔ የማይህ ሚስጥር በማትገለበት ቀን ሲሆን ያለቀጠሮህ ቢሮ መምጣትም ሆነ በምንም መንገድ እሷን ለማግኘት መሞከር በፍጹም ከህክምናውና ከምክር አገልግሎቱ ዓላማ እንጻር ተቀባይነት ስለሌለው ይሆንንም ልታውቅ ይገባል" ሲለው፣

"ያከተር አልበዛም ... ነጻነቴን ሁሉ ገፈፍከኝ እኮ ... ታዲያ ምኑን መከርከኝ ... ምኑን አከምከኝ?" አለ፣ ድምጹ ብስጭቱንና ተስፋ መቁረጡን እያሳበቀበት።

"ያው ሁሉንም ነገር አሁኑ ግልጽ ላድርግልህ ብዬ ነው። ይሄ ነጻነትህን ለመውሰድ ላይሆን ያንተንም ሆነ የሌሎች ሰዎችን መብትና ኃላፊነትን አመጣጥኖ ማስኬዱ የግድ ስለሆነ ነው።"

ነገሩን ከልቡ ባይቀበለውም አማራጭ እንደሌለው በማሰብ "እሺ ... ወደ ባሪው ክፍለ ጊዜ መግባት እንችላለን?" አለ ትንሽ እየተቁነጠነጠ።

"ኦህ ... አሱን እኮ ነው እየሰራን ያለነው። አሁን እያደረግን ያለነው ... ሲከበሩ ስለሚገባቸው የምክር መመሪያዎች፣ የኔና ያንተን ኃላፊነት መረዳት እንዲሁም ለምንሰራው ስራ ግልጽ ዓላማና ግብ ማስቀመጣችን ሁሉ የቴራፒው ክፍል ነው። አሁን አሱን ስለጨረስን ... ለምን ለባሪ ታሪክህን ከልጅነትህ ጀምሮ ዋና ዋና ነገሮቹን አትነግረኝም?" ብሎ፣ ወደ ኋላው ልጥጥ ብሎ ተቀመጠ። ያላሰበው ነገር ሰለነበረ ለትንሽ ጊዜ ሁሉም ነገር ድብልቅልቅ አለበትና በሁለት እጅቹ ፊቱን እያሻሸ ቀየ። የጅቹ ትልትነት የሁለት ሰው ፊት መሸፈን የሚችል መሰሎ ታየው።

"የኔ ታሪክ ... ምን ... ከየት ልጀምርልህ? ... ከባድና አስቸጋሪ የልጅነት ጊዜ ነው ያሳለፍኩት። እናቴ ገና የሃይ ስኩል ተማሪ ሆና ነው የወለደችኝ። አባቴ ከናቴ ፍቅር ተጠናወቶት ነገር ዓለሙን ትቶ፣ ስትጠጣ ስትገባ ለምስት አመት ያህል እሷን መከታተል ነበር ሥራው። እናቴ እንደ ነገረችኝ እሷ ደግሞ እንደሱ የምትጠላው ሰው በምድር ላይ አልነበረም። በፅድሚም ብዙ ይበልጣት ነበር መሰለኝ። በኋላ አንድ ቀን አላናገር ስትለው ከፉኛ ደበደባትና ነገሩ ወደ ቤተሰብ ደረሰ" አለና ለመቀጠል ያመነታ ይመስል ከካውን ተገንጭቶ መፊት መፊቱን እያየ ዝም አለ። እንዲቀጥል በአይኑ እያያሉፈረው "እሺ ..." ሲለው የቀረውን ታሪኩን ያለማቋረጥ ዘከዘከ ነገረው።

"አሁን አብራው የምኖረው አኅቴ፣ ያባቴ ታላት ወንድም ነው። በሁለቱ መሃል ግልቃ ገብቶ አባቴን ወደ ክፍለ ሀገር ሥራ አስይዘው ሲያርቁት ነገሩ ትንሽ ቆታ አገኘ። በዚህ መሀል አኅቴ ከእናቴ ጋር ቀስ በቀስ ተቀራርበው እኔ ተረገገዝኩ። እሱ ባለ ትዳርና የልጆች አባት ነበር። እሷም ከቢተሰቦቿ ጋር ነበር የምትኖረው። እርጉዝ መሆኗን ሲያውቁ እንዴት እንዳሳመናት አላውቅም፣ የሆነ የሆነ ነገር ተደርጎና ተሸፋፍኖ ከአባቴ ጋር ተጋብተው እኔም የሱ ልጅ ተብዬ ተወለድኩ።

"ትንሽ አብረው እንደኖሩ ያ የምትጠላውንና እንዴ ሥር የምትፈራውን ሰው በፍቅር አበደችለት። እናቴ ... ላባቴ ያላትን ፍቅር ልነግርህ አልችልም። እንደ ነገረችኝ ከሆነ ... እንደዛ አይ[illegible]ት ኖሮ፣ እንደዛ በሷ ፍቅር

ሲስታደኝ እሷም ለማደሪያ ስሙ ሲላኝ አትሆንም ነበር። ለምንድነው ግን ሴቶች የወንዶች ስታደኝ የማያገባቸው ... የወደፍቸውን መኖላት የሴቶች እርግማን ነው፣ እኔ እውን ጨካኝና መጥፎ ሰው እመስላለሁ! መቼም ቢሆን ግን ፍትር እንድሚያሸንፍ እርገጠኛ ነኝ። ለነገሩ ፍትር መጠበቅና መሰየሱ ትንት እንደሆነ አውታለሁ።"

ነገሩን ወዴት እየመራው እንደሆነና የአስተሳሰቡ መመሊጋኤድ የት ጋ እንደጀመረ በዘፈል ቢገባውም፣ ነገሩን ሙሉ ለሙሉ መሰማት ስለፈለገ ጥያቄውን ተጠለ። "አንተ ይሄንን ሁሉ ያወቅኸው መቼ ነው?"

"አባቱ ከሞተ በኋላ ነው እናቱ የነገረችኝ። ባስራስድስት ዓመቱ ነው እሱ የሞተው። አባቱና እሞቱ ብዙም አይሰማሙም ነበር። እንደመሰለኝ ... ያኮቱ ልጅ መሆኔን ሙሰጥ ሙስጡን አባቱ ሳያጠረጥር አልቀረም። ብቻ እያደር በመካከላቸው ትልቅ ግጭት ነበር። እናቱ ባባቱ ሞት ጠስጥም ያኮቱ እጅ ሳይኖርበት አይተርም ባይ ናት። አሞቱ ለኔ ሊያደርግ የማይሞክረው ነገር የለም። አባትህ ነኝ ብሎ አፋን አሙጥቶ ነግሮኝ ግን አያውቅም።

"የምር ግን ... ቀደ አውን የኔ አባት ማነው? ... የሚገርምህ እነ ስሙን ብነግርህ ታጠቀዋለህ ... የታወቀ ባለስልጣን ነው። ማንም እንዲነካኝ ተርቶ እንዲናገረኝም አይፈቅድም። እናቱ ግን ... በጣም ስለምትጠላው ... እንደ ሰውም አታየውም ... የኔ ነገር እየሆነባት ነው እንጂ። ያቅርታ ደብተር ከነጠሙ ነው መሰለኝ ... መታጠቢያ ቤት መጠቀም እችላለሁ?" ሲለው አትጣመጨውን አሳየው። የራሱን መታጠቢያ ቤት ለሀመመተኛ ባያጋራም፣ በደኅና ያለ ስሜቱን ለመጠበቅ ሲል ፈቀደለት።

ተመልሶ ሲመጣ ዘና ብሎ ነበር። "ዶክተር እንደዚህ የሚያምር ቢሮ አያቹም አላጠቅም ... ዝም ብለህ ብትተመጥበት እንኳን እነ ያድንሃል ... ጊያኖ ትጣጠለህ እንዴ?"

"ትንሽ ..."

"እኔም ወደ ፊት እንደዚህ አይነት ቢሮ ነው እንዲጥረኝ የምፈልገው"

ራሱን ከሱ ጋር ማመሳሰሉ ጥሩ ምልክት እንደሆነ በማሰብ ወደ ጥና ምዙ ተመለሰ። "እህ ጥሩ ነው። እና አውን ከናትህ ጋር ነው የምትኖረው? በትምህርትስ ምን ደርሰሃል?"

"አይ ብዙ ጊዜዬን እሞቱ ቤት ነው የምሆነው። በላይኮሎጂ ማጅር አድርጌ በታሪክ አራተኛ አመት ላይ ደርሻ ልጨርስ አልቻልኩም። ያኔ ነበር ከሚስጥሩ ጋር በፍትር የሰከርኩት። ከተወሰኑ አመታት በኋላ፣ አባቱ ሀገር ለቀኝ አንድ ዓመት ተምሬ ትቼው መጣሁ። አገሩን አልወደድኩትም ...ከዚያ በላይ የሀገሬ ናፍቆት ሲጠናብኝ የዛሬ አመት አካባቢ ተመለስኩ። በዚያን ጊዜ ... እሷን ልረሳት እነ ያልሞከርኩትና ያላደረኩት ጥረት የለም።

"ግን በታ ይገባሃል መቼም ... እውነተኛ ፍትር ... አንዴ በል ብሀ ውስጥ ከጠለ ምንም አይነት መከራና [illegible] ።" እኔ ኮ ትንሽ ጊዜ ፅድል

ብትሰሽኝ ምን ያህል ልትመደኝ እንደምገችል አውቃለሁ። እናቲም የምትለው ይኽንኑ ነው። እሷ ናት ተስፋ አትቁረጥ .. አባትህ ተስፋ ስላልቆረጠ ነው እኔን ያገኘው ብላ ነገሩን ተስፋ አስቆርጦኝ በፍትር ሀሙም ሳቃስት የምታበረታታኝ አስ ሳይት እየረዘመ።

"በቃ ኑ እንዳንደሜማ እሷ ከሴላ ሰው ጋር ሆና ማየት የምችልም አይመስለኝም። እሷም ራሷንም የፍትር መስዋዕት ማድረግ ብቻ ይመስለኛል ብቸኛው መንገድ። ያኔም ምስኪን እናቱ ታሳዝነኛለች። ግን ዶክተር ምንም ተስፋ ያለው አይመስልህም? ምናለ አንድ ጊዜ ሁሉታችንንም አብረህ አስቀምጠህ ብትመክረን ... ቢያንስ ቱርጥ ያለውን ነገር ካቆ ብሰማ እኮ፤ በቃ ለኔም የራሴን መንገድ መሄድ እችላለሁ" አለ፤ ድምጹ ገላ ብሎ እምቅ እየተንተባተበ።

"ምን መለስለህ ማስረሻ ... ቅድም እንደተነጋገርነው ይሄ ከፍለ ጊዜ በምንም መንገድ ሚስጥር ሊጨምር አይችልም። ዋናው አላማችን ያንተን አስተሳሰብና ስሜት በመረዳት የምትለመጥበትን መንገድ መፈለግ ነው። ያ ደግሞ ባንድ ቀን የሚሆን ነገር አይደለም። ስለዚህ እኔና አንተ በየሳምንቱ በዚህ ሰዓት ለአንድ ሰዓት እንገናኛለን። ምናልባት በማቀዋለው ሳምንት ደግሞ ከሚስጥር ሌላ እንደዚው በፍትር ስሜት ገብተህ ስለነበርካቸው ለሱት ሁኔታዎችና ... አንተም መነጋገር በምትፈልጋቸው ነጥቦች ላይ እናወራለን። አውን ሌላ ባለ ተጠሮ ሰላለኝ የዛሬውን እዚህ ላይ እናብቃ"

በሃላው ተስማምቶ እስከ መውጫው ድረስ ሸኘው። "እደራ ዶክተር የነገርኩህ ውስጤን ነና ባንተ መካከል ይቅር ... በ ሶስይ ለሷ ነግረህ መሳቂያ እንዳታደርገኝ"

"በፍጹም እትጨነቅ። በሱ ጉዳይ ሀሳብ አይግባህ።" ጠበቅ አድርጎ ጨበጠውና ወደ ቢሮው ተመለሰ። ማስታወሻውን እየጻፈ እንዴ ያ"ስጪርን እንዴ ማስረሻን ... ከዛም የማስረሻን እናት ... ባይነ ህሊናው እያየ ሚስሳስሉን ቀጠለ። "እያንዳንዱ በሴላ ሰው የተበላሸ ሰው ያድግና በተራው ሌላ የባሰ የማበላሸት ስራ በሴላ ሰው ላይ ይፈጽማል። በያንዳንዱ ሰው ውስጥ ተሰውሮ ያለው የስብእና ማንነት አካላዊ መልክ ይዞ ቢታይ ... ስንት ጠባሳ ... ስንት ጨርማታ .. ስንት ስንኩልነት በየስጪ ላይ ይታይ ነበር።"

"የማስረሻ የተመለጋገደ "ፍትር" እና የምስጪር ያልጸነ የልጅነት "ሽንቁር" መፈወሻው ቀላል እንዳልሆነ እያሰበ ቀየ። ማስረሻ የናትና ያባቱን ታሪክ የህመሙ መንስኤና የተንሻፈፈ ስብእናው መነሻ አድርጎ ሳይሆን ከምስጪር ጋር ስያዘው "ፍትር" የግበረታቻ ምሳሌ አድርጎ ነው የሚየየው። በምስጪር ላይ የሚፈጥረውን ሕመምና ስቃይ የሚያይብኑ ዓይን የለውም። ለማስረሻ ፍትር የፈቃድና የመፈታቱድ ጉዳይ ሳይሆን ልብ የፈቱደውን የገበበት ገብቶ አድኖ የማንበርከክ ... የሪሱን ሽፋፋ ህልም የግላነት ሥራ ነው።

"የሴላውን ሰው ፈቃድ፣ ስሜትና ፍላጎትን የሚያይ ዓይን የሌለው ነገር ፍትር ላባል እንዴት ይችላል! በተፈታሪው ላይ ስቃይና ፍርሃትን .. ስጋትና ጥላቻን የሚፈጥር ነገር ... ፍትሪ ተብሎ [illegible] ፍትር በሁለት ፈቃዶችና

ስሜቶች የመፈላለግ ውህደት ላይ የሚፈጠር ውብ ሀብረ-ሰብዕና እያደለምን፣ ባንድ ጉልበተኛ ፈቃድና ራስ ወዳድነት በሚፈጠር የስሜት ማእበል ... የሉላውን ሰው ፈቃድ ዝርስሶ ... በሉላው ስውነት ላይ ሰፍሮ ... የጦዘ ስሜትን የማርከት አባዜ ... ፍቅር ሊባል እንዴት ይችላል?

'ፍቅር ስለ ሉላው እንጂ ስለ ራስ ማሰብ አይደለም ። ራስን ስሉላሰው ደስታ ስለ መስጠት እንጂ ሉላውን ሰው በግድ የራስ ስለ ማድረግ ሊሆን አይችልም ። ፍቅር ሲታመም ሁሉም ነገር ይታመማል ... ሰብአናም ... አሰተሳሰብም ... ስሜትም ... የራስም ... የሉላው ሰውም ። የታመመ ፍቅር ከሁሉ የተመሳሰለ የነፍስ ደዌ ነውና ማዳኑም የዛኑ ያህል ይከብዳል ።'

ሉላዊው ይህን ሁሉ አሰቦ የከፈተውን የማስረሻን የጤና ማህደር ስገሸው ዘንግ የሚቀጥለውን ሀመምተኛ ለማስገባት ከመተመጫው ተነሳ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 27 ፡

ሲራክ ቱኑን ሙሉ ሲያንገላጅጀው ነው የሞለው ። ለጓደኛው ሽኝት በተዘጋጀ ፓርቲ ላይ ቀይቶ ሲንጋጋ ሲል ነበር ወደ ቤት የገባው ። ለማፈስ እንዲመቸው ከሊኒክ ውጪ ምላ በልቶ ቢሮ ሲገባ እንትልፋ አዳፋው ። ከወትሮው የበለጠ ስለጠጣ ሆዱም ጤና አልሰጠውም ። ጠረጴዛው ላይ ደገፍ እንዳለ እንትልፍ ያዘት ሄደ ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሲነቃ ራስ ምታቱ ሞንትላቱን እየፈለጠው ነበር ። ከዶክተር ሌላም ጋር የቡድን ምክክር አገልግሎት የሚጅምሩበት ቀን ስለሆነ እንዲያመልጠው አልፈለገም ። ቡና ብጠጣበት ይሻለኛል ብሎ ስላሰበ ወደ ካፈው ሄዶ ፣ እንደመረደ ቡና አገዘ ው-ጪ ተቀመጠ ።

አርብ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው ። በዛፍ በተከበበው ጎጆ ካፈያቸው እንደ ሁሌውም አልፎ አልፎ ሽው የሚለው ቀዝቀዝ ያለ ነፋስ ዘና ያለ ስሜትን ያፈጥራል ። ቡናውን በትኩሱ ቶሎ ቶሎ ጨለጠና ሌላ አዘዘ ። ትንሽ ቀለል ያለው መሰለው ። ወዲያው ሲስተር ዘቢባና ምስጢር መሞተው ወንበር ስበው አጠገቡ ተቀመጡ ።

"ዶሀና አይደለሀም እንጂ ዶክተር ሲራክ? ፊትህ ክብድ ያለህ ትመስላለህ" አለች ሲስተር ዘቢባ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ።

"ምን ባክሽ ... አንድ ጓደኞችን ወደ ው-ጪ ሊሄድ ... መሸኛ ብለው ... የረባም እንትልፍ አልተኛሁም ። ራስ ምታቱ ሊገድለኝ ነው" አለ ግንባሩን መዳፉ ላይ አስደግፎ ።

"ታዲያ ለምን ወደ ቤት ሄደህ አረፍ አትልም?" አለች ምስጢር ሻዩዋ ው-ስጥ የጨመረችውን ስኳር እያማሰለች ።

"ከዶክተር ሌላ ጋር የሱስ ችግር ላለባቸው ግሩፕ ቴራፒ የምንጅምረው ዛሬ ነው ። እንዲያመልጠኝ አልፈለኩም ። ካንድ ግማሽ ሰዓት በኋላ ይጅምራል" አለ ሁለተኛ ስኒ ቡናውን ያለ ስኳር ፉት አለና [illegible] ።

"እህ እንደራሱ ከሆነስ መቻል ነው። ስታያቸውን ነገር በላይ ሲረዳቸው የሚችል የለም" ብላ ስትስት፣

"ምን ለማለት ነው?" አለ፣ ተረፈ ቢገባውም።

"እይ ስታያቸው ስታይህ ነው ብዬ ነዋ ..."

"መጽሐፍ እንብዛ ... በማያውቱት ጉዳይ ለመምከር ከመምከር ይሻላል ማለትኳ ነው?"

"ልክ ብለሃል ... በዚያውም እየመከሩ ተመካሪ ለመሆንም ዕድሉ ጥሩ ነው ... ያው ብዙዎቹ በጎደኛ ሽኝት ምናምን ነው የጀመሯቸው ብዬ ነው" ስትለው፣ በመስኮቱ ያቺ ደረቅ ልጅ ዛሬ ደግሞ ማነው አሰታዋቂ የላካት' ብሎ በስጨት ብሎ፣

"ለቡድን ምክሩ የተመዘገቡት ብዙዎቹ ሴቶች ናቸው። ትናንት ሪቡ መጠጡን እያተጋቡ ሲንዘባረሩ የነበሩት ሴቶቹ ናቸው። ምንድነው ነገሩ? ይሄም የእኩልነት መድረክ መሆኑ ነው?" አለ፣ ሊረታ የሚችልበትን የዘርዘር አትጣጫ ለመቀየስ እየሞከረ።

"እናንተን ወንዶቹን ካልገደላችሁ ሴቶቹን ምን ያደርጋናል ብለህ ነው?"

"በጣም ነው የሚያስጠላባቸው። ሴት ልጅ ስነሪ ስትለፋደድ ... ሞንቅላት የሌላት ዝንጀሮ ነው የምትመስለኝ" አለ። መጀመሪያ ላይ ያለችው ነገር ስላናደደው፣ እንዴት ሊያናድዳት እንደሚችል ሰበብ እየፈለገ መሆኑ ገብቷታል።

"ወንዶቹ ጠንብዘው ... ሊያላዝኑስ?"

"ሴት ልጅ የሚጠመቀውን ጠምቃ ጌታዬ ጠላልኝ ብላ ... አስተካክላ አትርባ ... እም ... ወደ ጓዳ ገብታ ጥጥ ስትፈትል ... ምናምን ነው የሚያምርባት። ወንድ ልጅ ቢጠጣ ... ቢስነር ... ቢንገዳገድ ... ቢጨፍር ... የተፈጠረለት ነገር ነውና ያምርበታል ... ድግሞ ልኩን ያውቃል። አትክልትና ሴት ውሃ ከጠጣ በቃ ..." ብሎ ሲስት ትንሽ በስጨት አለች።

"ልክ ነህ ... ጋንና ወንድ ሞንትላት ስለሌለው ... ወይ ለመጥመቂያ ... ወይ የተጠመቀውን ለመገልበጫ ካልሆነ ሌላ ምን ሊያደርግ ይችላል?" ስትል ሊስተር ዘርዓ አላስችል ብሏት ሳቀች። ሁልጊዜም አብረው ከሆኑ መነታረክ ስለሆነ፣ ሊስተር ዘርዓ የሁለቱን መጣቶች ከርዘር ከግራና ከቀኝ እያጓመጠች መሣቃቸው እንደ ዶሮ ጥል ያስታታል። እንድ ልባ ደግሞ አብረው እንዲሆኑ ይመኛል። የምስጢር ደጃት፣ ሰው ወዳድነትና ፍልቅልቅነት ደስ ይላታል። ለማን እንደምታደላም ርግጠኛ አይደለችም፣ ሲራክ ምስጢርን እንደሚወጻት እሷ ግን ለርሱ ምንም ሚድ እንደ ሌላት ስለምታውቅ ሳታወላውል ልባ ብዙ ጊዜ ወደ እርሱ ያዘነ በላል።

"ወይኔ ወይኔ ... ለምን ይመስልሻል ... እግዚሩም ሲፈጥረን ... ለመነዱ ሰት እድርገ ሲስጠው ... ለናንተ ሚጢጢ ጉበትና አነስ ያለች አንባል የገጠመላችሁ! ወኛ ይሄ ሳይንቲፊክ እውነት @ETBOOKSPDF ብላችሁ ነው እኮ እኩልነት ...

ንብርየሉ ... ምናምን የምትሉት"

"እዬ...ይ ሲራክ ... እንተም ካስር ዚሉ ድጥኝ እንድ ግራም ወርት እንደሚሻል የምትዘድ አይመስለኝም"

"ካንድ ግራም ጠጠር አስር ዚሉ ወርት እላለሁ ብለሽ ነው?" ብሉ ሲስቅ ፡

"ሲራክ ... የማታው አለቀተህም ... መይስ እስክ ባጭሩ ንገረኝ ... ምንድነው ነገብሀ?" አለች ፡ ከርክራቸው ለባውን እያጣ መጼትም የማያሄድ የታላት ጨዋታ ልለመንበት ።

"ነጥቡማ ... ሴት ከወንድ እኩል መሆኗን ለማሳየት ወይም ለማሳወት ከኳላው ኩስ ኩስ እያለች ... ወንድ ያደረገውን ሁሉ መኮረጅና መሞከር የለባትም ነው ... " ብሉ የምጸት ሳቁን ሳቅ ።

"እውነቱ ምን መሰለሀ? ... ወንድ ደግሞ ስራሱ የፈለገውን እያደረገ ሴት ልጅ ደስ ያላትን ስታደርግ ባህላችን ሃይማኖታችን ቅብርጥሶ እያለ መንጨርጨር አይገባውም ነው"

"ቀዩ አንቺ ሴት ልጅ ባደባባይ ሲጋራዋን እያቦንች ሰክራ ስትንገዳገድ ትከሰሻና ጨዋ የሴትነት ባህርይ ነው የምትይው?" አለ ነገሩ ስሜት የማይሰጥ መሆኑን ለማሳየት አፉን ጠምም አድርጎ የለበሳ ፈገግታውን እያሳየ ።

"አንተስ ወንድ ልጅ ሲጋራውን እያቦነን ሰክሮ ሲንገዳገድና እዚት ከኩስ ሲስት በኋላ ገብቶ ሲለፋደድና ቤተሰቡን ሲረብሽ ... ጨዋ የወንድ ባህርይ ነው የምትለው?"

"ቀዩ ለም"ን ለምጠይቅሽ ሞያቱ መልሱን አትስጪኝም ... ሞያቱ መልስ ሲሆን እኮ አይችልም ። "

"ስተንሻፈፈና ስተሳሳተ ሞያቱ ትክክለኛ መልስ የለውም ። ብቸኛው አማራጭ የማስተካከያ ሞያቱ ነው ። እኔ ኮ ያንተን ሞያቱ በማስተካከል እየረዳሁህ ነው"

"ሙይ ... ከጅማሪ ፈሚኒስት ጋር እኮ ማውራት መድረት ነው ... አዲስ ምእመት እጻጻሉ ባስ አሉ" በሁለም አትላሚ የምታመጣውን ነጥብ ማሸነፍ ባይችልም መሸነፉን መተበል ግን ለሲራክ አይሞክርም ።

"አርጌ ቮቪኒስቶች አስካሉ ድረስ አዳዲስ ፈሚኒስቶች መፈጠራቸው አይቀርም ። ቀይ አንተ ወንድ ከሴት ይበልጣል ስለዚህም ባጭሩ የተለየ መብትና የፈለገውን የማድረግ ለሴት የማይፈቀድ ነጻነት ይሰጠው ነው የምትለው አያይል?" ብላ ዓይን ዓይኑን ትኩር ብላ ስታየው ፡

"ኖ ... ኖ የት የት ... ችግሩ ... አንቺ ወንድና ሴት አንድ አይነት ስለሆኑ ወንድ ያደረገውን ሁሉ ... የማድረግ ችሎታውም መብቱም አላት አይደል የምትዪው? ቀይ ከወንዶች ከመኮረጅ የተለየ ምንም ኦሪጂናል ነገር የላችሁም ማለት ነው? ዘፓ እንደሱ ከሆነ እናንተ እኛን ስትኮርጁ እኛ ደግሞ አዳዲስ ነገሮችን እየፈጠርን ትንሽ ራትና

@OLDBOOOKSPDF

ላት ብለን መውየት ነው እንግዲህ ... ሴላ ምን አማራጭ አለን" ሲል ነገሩን ወደ ሹፈት በመቀየር ሃልቡን መናገሩ ስለገባት ፣

-ችግርህ እኮ ልትሸነፍ ስትል ነገሩን ቀልድ ታስመስለሃለህ ። ወንድና ሴት አንድ ሳይንት ናቸው የሚል ነገር አልወጣንም ። እንኳን ወንድና ሴት ... ሁለት ሴቶችም አንድ ሳይንት ሊሆኑ አይችሉም ። ልዩነት ግን መበላለጥና የመብት ልዩነት ሊፈጥር አይገባም ነው ነጥቡ ። በጾታ ብቻ ሳይሆን በቀለም ፣ በዘር ፣ በሃይማኖት እና በሌላም ስው ሊለያይ ይችላል ። ግን መለያየትን ለምን እንደ መበላለጫ መስያን የተጠለኑ ስዎችን ባለመብትና የለላው ን መብት ፈጭድና ከልካይ በማድረግ ፣ ሌላውን ደግሞ አሽከርና ጥገኛ አናደርጋለን ነው ጥያቄው ። ሴት ማዜሰም ሆነ መጠጣት የሌለባት የባህልና የሃይማኖት ዕቃ ስለሆነች ሳይሆን በሴትነቷ ወይም በሰውነቷ የማይጠቅማት ወይም የሚጎዳት መሆኑን ስላመነችበት ብቻ ነው ። ያንን የምትመስነው ደግሞ በዋናነት ራሷ መሆን አለባት" ስትል ፣ ከመቀመጫው ብድግ አለና ጎነበስ ብሎ እያጨበጨበ ፣

"እይ አም ሶ ኢምፕረስድ ...ማዳም ፈሚኒስት ... ለምን እዲሱን ማንፌስቶ አትጽፊም ታዲያ?" ሲል ፣ ሲሰተር ዘሊባ ምስጢር ያለችው ሁሉ ውስጥ ውስጡን አንጀቷን ቢያርሰውም ላለማዳላት ያህል ፣

"ብታችሁ ለዛሬ እስኪ ... የዘመናት ችግር እንግዲህ ባንድ ቀን በናንተ መጥት አያፈታ" ብላ የቀዘቀዘ ሻይዋን ቭሱ ቭሱ ጠጣች ። ትኩስ ነገር አቀዝቅዛ ነው የምትጠጣው ።

"ወደ ተነሳንበት ጉዳይ ስንመለስ ግን መጠየም ሆነ እጽን በተመለከተ ፣ የሴቶች ጉበትም ሆነ አንገል አለኮልን በመቋቋም ከወንድ ይልት አቅሙ ይነሳ ነው ። ሴቶች በማርገዝም ሆነ ሀጻናትን በመንከባከብ የበለጠ ሃላፊነትና ተጥቶኛ ተሳታፊነት እንዳላቸው አይካድም ። ይህም ሲሰከሩና በእጽ ሃደ ሲሆኑ ፣ ከወንድ ይልት ለበለጠ አነላዊና ወሲባዊ ጥቃትም መጋለጣቸው የታወቀ ነገር ነው ። አንቺ እንደምትዪው እንደ ወንድ ይጠጡ ይትበሉ ማለት ተገዚ እደመስለኝም ። የባህላችንና የሃይማኖቱ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ ..." ሲል ፣ ብሰጭት ብላ አጽረጠችውና ፣

"ሲራክ ግን የምርህን እንደዚህ ነው የምታስበው? በጣም ነው የምትገርመው" አለች ።

ትክሻውን ሰበቅ አድርጎ ፣ "ዋናው ነገር መግረም አለመግረሙ ሳይሆን እውነታው ምንድነው የሚለውን መረዳቱ ላይ ነው" አለ ።

"በመጀመሪያ የማንን እውነታ ነው የምናወራው ነው ጥያቄው ... በወንዶች ዓለም ወንዶች ስለፈጠራችሁት እውነታ ከሆነ የምታወራው ጊዜ ያለፈበት የድሮ ታሪክ ነው ። ቅድ ወሲባዊ ... አነላዊ ጥቃት የምትለው ማንው ወሲባዊና አነላዊ ጥቃት የሚያደርስው ... ትልልት ጉበትና ቋጥኝ ጡንቻላት አላቸው ያልካቸው ወንዶች እኮ ናቸው ። ለምን ታዲያ ሰክረው በሴቶች ላይ ጉልበታቸውንና እንስሳዊ ስሜታቸውን ከሚወጡ ታላላት አንገላቸውንና ጉበታቸውን ተጠቅመው እንደ ጨዋ ወንድ ለምን ራሳቸውን አይገዙም ።

@OLDBOOOKSPDF

"ልብ ያሴለው ወንድ በርሜል የሚያክል ጭንትላትና ከርሱን የሞላ ጉበት ተሸክሞ ቢዞር ምን ያጠቅማል። እርግዝና ልጅ ምናምን ላልከው ደግሞ እርግዝናውም ሆነ አናቱ የጎረቤት ብቻ ሃላፊነት ናቸው ያለው ማነው? ወንዱስ ቢራውን ሲጥልስ እሾሽ ቤተሰቡን በሰድብና በረሃብ ከሚጥላ ለምን እርጉዝ ሚስቱን አያግዝም ... እሾሽ ያልከውን ጭንትላቱን ተጠቅሞ፣ ለምን ለልጆቹ ጊዜ ሰጥቶ አንደ ፈጣሞ አባት እራገከባቸውም?" ስትለው ለወትሮ ሃላፊ የሚያልትበት ሲራክ ለትንሽ ጊዜ ዝም ብሎ ቀየና ዝት ብሎ ሳቀ።

ሰዓቱን አየት አድርጎ፣ "የት ነው ግን በናትሽ ይሄንን ሁሉ መጣት የተማርሽው? ዛሬ አልተቻልሽም። ለማንኛውም ወንድ መሆኑና ወንድ ያደረገውን ሁሉ እየኮረጁ ጥድረግ ትልት ሴት የሚያደርግ አይመስለኝም" አለ መናደዱ በውስጡ የሚያውቀውን ያክል እየፈጠረለት።

"በናትህ ... በደንብ ስማኝ ሲራክ ... አንድ ፅሆንና መኮረጅም የማልፈልገው ነገር ቢኖር ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ወንድ መሆን ነው። ጥሩ ሰው እሰከሆነ ድረስ ግን ወንድም ሴትም ለኔ አስተማሪዎቼ ናቸው። ወንድ ከሚባል ነገር ጋር ጥላቻም ፍትረም የለኝም። ወንድም በወንድነቱ ሴትም በሴትነታቸው ሰው ናቸው። ማንም የማንም ገዢ ሊሆን አልተፈጠረም። ማንም ከማንም የተለየ ወይም የበለጠ መብትም ሆነ የበላይነት ፈቃድ አልተሰጠውም።

"ትዳርም ቢሆን የኃላፊነት ልዩነት እንጂ፣ የእኩልነት ብልጫ ተፈጥሮበት እንዱ እሸከር ሌላው ገዢ የሚሆንበት አሰር ቤት አደደለም። ፍትርና መከባበር ሚዛን ይዞ ደስታንና ኃላፊነትን የምትካፋፈልበት የአረፍት ቦታ ነው እንጂ፣ ጾታ ዘመም የመገናኛ ክለብ ወይም ግደብ የለሽ ያንዱ ጾታ መፈንጫ ሊሆን አይገባም። ይሄ ደግሞ ወንዱን ብቻ ሳይሆን ሴቲንም በእኩል ይመለከታል። በኛ ባህል ግን ሚዛኑ ወደየት እንዳዘመመ የታወቀ ነው። ከዚያ ው-ጪ ግን ወንድና ሴት መሆን ላንዱ የተለየ የበላይነትና የገዢነት ፈቃድ ሲሰጥና ሊያበላልጣቸው አይችልም ነው የምልህ።

"እኔ የሚያስጠላኝ ሴትን በማክሰስ ትልት ለመሆን የሚንጠራራ ወንድ ነው። በሀይሙ ው-ስጥ በጣም ከምጠጸቸው፣ ከማደንቃቸው ሰዎች መካከል ከግማሽ በላይ ወንዶች ናቸው። ወንድ ስለሆኑ ሳይሆን ሰው ሆነው የሰው-ንም ክብር ከጾታ ጋር ሳያቀራኙ ስለሚያከብሩ። ራሳቸውን ሆነው ሌሎችም ራሳቸውን እንዲሆኑ ከልባቸው ስለሚያምኑና ስለሚሠሩ" ስትለው፣

"ይውንልሽ ... አገሩን በስነራምና ስርዓተ ቢስ ሴት መሉትና ያኔ ማጣፊያው ሲያጥራችሁ እናመራለን። አሁን መሄድ አለብኝ ... ከዶክተር ሴላ ጋር የግሩፕ ቴራፒ የምንያምርበት ሰዓት ደርሷል" ብሎ ሲነሣ፣

"ኦሲራዲ ... ስነራምና ስርዓተ አልባ ወንድ በሞላበት ዓለም እየኖርን ስለሆነ... የሴቶችን መቻል የሚያትሉን አይመስሰኝም" ብላ ተነስተው ወደ ቢሮ አመሩ።

"ሚስጥርዬ ... በናትም እንደዚህ አይነት ቲፍጋሪ መሆንሽን አላውቅም ነበር።

@OLDBOOOKSPDF

በጣም ብዙ ነገር ነው የተማርኩት" አለች ሲስተር ዘቢባ ሰዓቱ ሰለደረሰበት በችኮላ ተለይቷቸው ሲሄድ ።

"ብታወሪ ምን ይፈይዳል ብለሽ ነው ። ድንጋይ ላይ ውሃ ማፍሰስ ነው"

"አዪ ... እንዳይመስልሽ ... ትልቁን አለት የምትሰብረው የተደጋገመች የውሃ ጠብታ ናት ። የሱን ብትተይው እንኳን እኔ ምን ያህል እንደተ ግርኩ አታውቂም ። ጮሽ የኔ ልጅ ... በጣም ነው ያኮራሽኝ" ብላ አቀፈቻት ።

በሌላ በኩል እነዚህ ልጆች ተጋብተው እንድ ቤት ቢኖሩ ሊባሉ ወይ ሊጋደሉ ይችላሉ ብላ አሰበች ። ተጋብተው የማየት ህልሟ ግን እውንም ሊሞትላት አልቻለም ። የሲራክን ጭንቅላት እንደዚህ አስኪዛር ድረስ የምታውርና ታል የምታሳጣ ልጅ ትሆናለች ብላ ምስጢርን አስባትም አታውቅም ። ሁልጊዜም ተጫዋችና የላይ ላይ ሰው ነበር የምትመስላት ። በሴትነቷ አስባቸው የማታውታቸውን ጥያቄዎች ሁሉ ወደ ኋላ ድረስ ሄዳ እንድታስብ ነው ያደረገቻት ።

ሲራክ ከነሱ ተሰናብቶ የቡድን ምክር ከሚሰጥበት ሰፋ ያለ ክፍል ሲደርስ ብዙዎቹ በሰዓቱ ደርሰው ፣ በክብ በተደረደሩት ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ሲያወሩ ደረሰ ። ከማጣሪያው በትንሽ የገላስቲክ ስኒ ውሃ ቀዳና ደጅ ደጅን እያየ ከመስኮቱ አጠገብ ቆመ ። ወዲያው ሌላሙ ሲገባ ሁሉም ሰው ቦታ ቦታውን ያዘና ክፍለ ጊዜው ተጀመረ ።

የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ስለነበር የመግቢያውን ንግግርና ማብራሪያ ሌላሙ ጀመረ ።

"ኦኪይ ... በመጀመሪያ እንኳን ደህና መጣችሁ ። የዚህ ዓይነቱ የቡድን ምክክርና ህክምና በኛ ሃገር ብዙም የተለመደ አይደለም ። ባጠቃላይ ግን በተለምዶ እናቶቻችን ከሚያደርጉት የቡና መጠራራት ጋር የተቀራረበ ነው ። ስለዚህ ነው ቡና አፍልተን የጠበቅናችሁ ። ሁላችሁም ቡና ያዛችሁ?" ብሎ ሲስቅ ቤቱ ሁሉ በሳቅ ተሞላ ።

"አብዛኞቻችሁ በግል እኔን ነው የምታዩት መሰለኝ ... ጥቂት ይከተር ሲራክንና ሚስጥርንም የምታዩ ስምች እንዳላችሁ ሰምቻለሁ ። ከመተዋወቃችን በፊት ግን አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮችን መናገር እፈልጋለሁ ። በመጀመሪያ ደረጃ የምንገናኘው በየሳምንቱ አርብ ከሰአት በኋላ ዘጠኝ ሰአት ላይ ሲሆን ፣ ለአንድ ሰዓት እንቀያለን ። የምንሰበሰብበት ብቸኛ አላማ ፣ እናንተ በዋናነት ከምትቸገሩበት የሱስ ችግር አንጻር ከሱስ ለመላቀቅና ንጹ ሆኖ ለመቆየት የሚያስፈልጓችሁን ምክሮችና የሞራል ድጋፍ እንድታገኙ ነው ። በሰአቱ ስለምንጀምር በጊዜ መገኘት አስፈላጊ ነው ፣ ከሃያ ደቂቃ በላይ ያረፈደ ሰው መግባት አይችልም ።

"እዚህም ሆነ ከዚህ ስትወጡ የግል ጓደኝነት መመስረትና ከምንሰበሰብበት አላማ ውጪ የሆነ ነገር ማድረግ አይፈቀድም ። ከስርአት የወጣ ነገር የምታደርጉ ከሆነ ከቡድኑ ብሎም ከክሊኒኩ አገልግሎት ሊያስገልላችሁ ይችላል ። ሌላሙን አባል ማንቋሸሽ ፣ መሳደብ ፣ ለመደባደብ መሞከርና የማይገባ ነገር መናገር ከቡድኑ ያስገልላል ።

@OLDBOOOKSPDF

ከዚያ ውጭ ስርነት ባለው መንገድ መደጋገርና እንዱ ከሌላው መማሩ ተገቢና የምናደፋፍረው ጉዳይ ነው። እዚህ የምናወራው የአባላት ሚስጥር እዚህ የሚተር ነው።

"ሁላችሁም እንድትላተፉና ችግራችሁን ከፍት ሆናችሁ እንድታካፍሉ፣ የያቱ ከለ እንድትጠያቱ ትደፋፈራላችሁ። ዛሬ ትመጡትና አጠቃላይ መግቢያ ነገሮችን ነው የምናደርገው። "ገልጽ ነው? ... ጥያቱ ያለው ይኖራል?" ሲል ሁሉም ዝም አሉ። "ዶክተር ሲራክ አብሮኝ ቡድኑን ይመራል ... እንዳንድ ጊዜም ሌሎች ሰዎች እንዱ ሁኔታው ሲመቱና ሲመሩ ይችላሉ። በታቻለኝ አትም ግን እኔም ለመገኘት እሞክራለሁ። ዶክተር ሲራክ ሃሳብ አለህ?" ሲል እንደሰለው ሚንትላቱን በማነታነት ገለጸ።

"እሺ ጥያቱ ከሌለ ... ለምን ራሳችንን እናስተዋውቅም ... ያው እኔ ዶክተር ፊላሙነኝ ... የአእምሮ ሃኪም ነኝ፣ ዶክተር ሲራክም እንደሳው ነው። ከዚህ ጀምረን ወደ ቀኝ በተራ ራሳችሁን አስተዋውቁን ... ስም ... የምትቸገሩበት የሱስ አይነትና ለምን ወደዚህ የቡድን ምክር አገልግሎት እንዱ መጣችሁ ከነገራችሁን ይበቃል ለጊዜው" ብሎ ካጠገቡ የተቀመጠችውን ሴት እንድትጀምር ምልክት ሰጣት።

"እም ... ማረፊያ እባላለሁ ... የምቸገረው በአልከሆል ሱስ ነው ... የመጣሁበት ተስፋ ... እንዴት አድርጌ መጠጥ ማቆም ብቻ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ ሳልጠጣ መቆየት እንደምችል ምክርም ድጋፉም ለማግኘት ነው" ስትል፣ ካጠገቧ ያለው በሥላሳው እድሜ ክልል ያለ አይናፋር የሚመስል ሰው ብድግ ብሎ፣

"ስሜ ፍስሃ ነው ... የኔ ችግር ምናልባት ከብዙዎቻችሁ ይለያል ... የኔ ሱስ የወሲብ ፊልሞችና ምስሎችን መመልከት ሲሆን ... በዚህ ምክንያት ትዳሬን እየቻለውኝ። የምጠብቀው ከዚህ ከሄሲ ሱስ እንዴት እንደምላቀቅና አሸተንጥሬ እንደምጥለው መማርና ድጋፍ ማግኘት ነው" ብሎ ተቀመጠ።

"የኔ ስም ያሲን ነው። ትልቁ ችግሬ ሥጋት ሲሆን ከሱ ጋር ተያይዞ ያጠመደኝን የአንትልፍ ኪኒን ሱስ ለመላቀት ነው ህልሜ" አለ፣ ሰውነቱ ክስት ያለ እድሜው በአርባዎቹ ውስጥ የሚገመት ገልማሳ። ሁለት የላይኛ ጥርሶቹ ወልቀው ሌሎቹም በልዘው ከእይታ የጠፉ ጥርሶቹን በእጁ ሸፈኖ ነው የሚያወራው።

"የኔ ስም ... እም ... ረሺድ እባላለሁ። የሃሺሽና የሜት ሱስ ነው ችግሬ። በዚህም የተነሳ ከቢት ተባርሬ ቤት አልባ ሆኜ ሁለት ዓመት ኖሬያለሁ። ሱሴን አሸንፌ ትምህርቴን ጀምሬ እንደገና ሰው ለመሆን ነው ምሞቱ" አለ፣ ጸጉሩ ሜብርር ያለ ዕድሜው ከሃያ ሁለት የማይዘለለው ወጣት።

"በዚህ ዕድሜዬ ሱሰኛ ሆኜ ትዳር ቤተሰቤን ማጣትና ያለኝን ንብረት ሁሉ ሰቅማኛ አስረክበ መና መቅረት ጸጸቱ ብቻ ይገድላል። ስሜ ዕድሜዓለም ባህሩ ይባላል" ብሎ ተቀመጠ በርሜቸው ገላ ያለ ወፍራም ራስ በራ ጥቁር ሰው።

"የሚቸገሩበት ሱስ ምንድነው ሲባሉ ሲራቢ

"ውይ የኔ ነገር ሞት ያሪሳኝና ... ይሄን ከሃሲ ስሙን ቁስ ይጥራውና የታባቱ ... የኔ ሞነኛ ሰብ ቁማር ነው ... አሁን አሁን ደግሞ ብሰጭት ሲዘባ መጂ መ"ወጡም ተዛውሮብሻል" አሉ እጃቸውን እያወናጨፉ ። ሁሉም ሰው ፈገግ አለ ባነጋገራችው ።

አጠገብ ላጠገብ ተቀምጠው የነበሩ ሁለት ወጣት ሴቶች ደግሞ ሁለቱም ሴሳቸው ሲጋራና መጠጥ እንደሆነ ተናገረው ሲተመለሱ የቱሩት አራት ሰምንም የመጠጥ ፣ የሣት ፣ የወሲብ ፊልሞችና የሲጋራ ሱስ እንደሚያስጥሯራቸው ተናገረውና ራሳቸውን አስተዋውቀው ተመለሱ ።

"ያው እንግዲህ እንደ ሰማችሁት ... የአብዛኞቻችሁ የሱስ መንስኤ የተለያየ ቢመስልም ... ሁሉም የሱስ አይነት ግን ዘር ዘር በእንባላችን ላይ የሚፈጥሪው ተጽእኖ ተመሳሳይ ነው ። በርግጥ እንደ ሱሱ ዓይነትና የያንዳንዳችን የሰብእና አመታተር የሱሱ ጥንካሬና ባህርይ የተመሰነ ለውጥ ሊኖረው ይችላል ። ሱስ በእናና በግድን ፣ ሲያሻውም በደምስር ሊገባ ወይም ደግሞ እንደቁማር በገንዘብ ተመስሎ ሊያጠምደን ይችላል ። በእንባላችን ውስጥ ገብቶ የሚቀጣጠረውና ከጥቅም ውጪ የሚያደርገው ከናል ግን ከጥቂት ልዩነት በስተቀር ተመሳሳይ ነው ። ይህንን ችግር ለማከም ወይም ለመትረፍ አሁን በደረስንበት የህክምናና የሥነልቦና ዕውቀት መሰረት የምንጠቀመው የህክምናና የምክር መንገድ ለሁሉም ሱሶች ከሞላ ጮደል አንድ ነው ማለት ይቻላል ።

"እስኪ ወደ ዝርዝር ሳይንሱ ከመግባታችን በፊት መጂ ሱስ እንዴት እንደገባችሁ እንነጋገር ። ምክንያቱም አገባባችን እንዴት ልንወጣ እንደምንችል አንዳንዴ ጠቃሚ ፍንጭ ስለሚሰጠን" ብሎ ፣ ዙርያውን ታኝ ፈታይኛ የሚሆን ስው ካለ ለማየት ።

"እኔ ብቸኝነትና ሞንፀባትን ሽሽት ነው መጠጥ ውስጥ ሳላስበው የተነከርኩት ። ከባሌ ጋር በመረረ ፍቺ ውስጥ ካለፍን በኋላ ብቸኛ ዓይኛዬና መያዘቂያዬ ጠርሙሴ ነበር ። ተስ በተስ ግን እሱ ራሱ ልፈታው የማልችል ሴላ ከፉ ባል ሆኖ ቁጭ አለ" አለች ፣ መጀመሪያ ራሷን ያስተዋወቀችው ሴት ። ሌሎቹም ከሰዎች ጋር ለመመሳሰል ፣ በኅደኛ ገፊት ፣ ወሰጣቸው በተፈጠረ ጉጉት ነገሩን ለመርከርና ለመዝናናት በማለት ፣ ከሥራና ማኅበራዊ ሀያጠት ጋር በተያያዘ ጫና በገቡበት ሱስ መጠመዳቸውን ገለጹ ። ሌላሠው ንግግሩን በመቀጠል ሰዎች ሳያስቡ ሌሎች በሱስ የሚጠመዱባቸውን ምክንያቶች ጨመረ ።

"ባብዛኛው ማህበረሰብ በተለይ በኛ ሀብረተሰብ ውስጥ ሱስ በሽታ ተደርጎ አይታይም ... ስለዚህም ሱሰኞችን ከመርዳት ይልቅ መወንጀል ገልቶ ይታያል ። እናንተስ ሱስ በሽታ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምንድ ሲል ላቂር ጊዜ ሁሉም ጸጥ አሉ ። የቁማር ሱስ እንዳለባቸው የተናገሩት ሰውዬ ጉሮሯቸውን ጠረግረግ አደረጉና

"ግና ሲጀመምርህ እኮ ሱስ የሚባል ነገር የለም ... በዝህ ፈታይህ መተውና ማድረግ የምትችለው ነገር ነው ። ቀየት እያለ ግን ጣዙን ጠቅልሎ ሲሰናርብህ ... ህመም ብቻ ሳይሆን ልክፍትም ሲሆን ይችላል ። ችግሩ ብዙ ሰዎችን ስለምትገዳና ምክኖ የማትሰማ የሱሱ ባሪያ ስለምትሆን አንተም ሆነ ሌላው ቤተሰብ እንደ ህመም ሊቀበሉት ይቸገራሉ ። የጠባይ ግድፈት ያለብህ ከንቱ የማትረባ አደርገው ስለሚያደህ አንተን

@OLDBOOOKSPDF

ለራስሀ ከሳ የተለየ ገምት ሊኖርህ አይችልም" ሲሉ ፣ ሁሉም በመስማማት ራሳቸውን ነቀነቁ ።

"ልክ ነው አንዱ ችግር ሱስ የሳህርይና የሞራል ገድፈት ተናርነም ስለሚወስድ አለርም ብዙ ወንጀል ነክ ድርጊቶች ውስጥ ስለሚከት ... ህሙም ነው ብሉ ማሰብ በየትኖውም ህብረተሰብ ውስጥ ቢሆን አስቸጋሪ ነው ። ግን ደግሞ በሱሱ መጠመድ ሊመጣ በአንነላችንና በስውነታችን ላይ ያለሱሱ ለመኖር አንዳንችል የሚያደርጉ አካላዊና ስነልቦናዊ ለውጦች ስለሚከሰቱ ህመምንቱን መቀበል ከሱሱ ለመጠጣት አስፈላጊ ነው ። አንዳንድ ሰዎች በሰብእናቸው አመታተር፣ ከቤተሰብ በሚመጡት የዘር መወራረስ ለሱስ የበለጠ የተጋለጡ ይሆናሉ ። ለማንኛውም ለመጻን በሚደረገው ሂደት ውስጥ የመጀመሪያው፣ ቁልፉ ነገር ህመምንቱን መቀበልና ለመታከም ዝግጁ የሆነ ልቦናን መፍጠሩ ላይ ነው" አለ ሌላዋው ።

"እኔ ግን አንድ ጥያቄ አለኝ ... ቀድሙ የሱስ በሽታነት ... አንድ ሰው መጀመሪያውኑ እንነሱ ችግር ስላለበት ነው? ... መይስ ሱሱ ነው አንነሱን አዘላሽቶ ከጊዜ በኋላ በሽተኛ የሚያደርገው? ምክንያቱም አንዳንዱ እንደፈለገው እየተጠቀመም ያለ ችግር ይኖራል ..." አለ ያኪን አንዴ መደ ሲራክ አንዴ መደ ሌላዋው እያየ ። ሲራክ ፈጠን ብሎ ፣

"ሁለቱም ሊሆን ይችላል ። በሱስ ለመጠመድና ሱሰኛ ለመሆን ሁሉም ሰው እኩል የተጋለጠ አያደለም ። ልክ ሌሎች አካላዊ ህመሞች በቤተሰብ የመሄድ ዝንባሌ እንዳላቸው ... ለምሳሌ ስኳር ወደም ደም ግፊት ማለት ነው ። ልዩነቱ ሱስ ሊያሲዙ የሚችሉ ነገሮችን አስካልተጠቀመ ድረስ፣ ማንም ሰው ሱሰኛ ሊሆን መይም በሱስ ህመም ሊጠቃ አይችልም ። በተጨማሪም የሰብእናችን ሳይንትና አስተዳደጋችም የተወሰን ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል ። ባጠቃላይ ሱሰኛ ሆኖ የሚወለድ ሰው ባይኖርም ሱሰኛ ለመሆን የዘለቀ የተጋለጠ ማንነት ይዘን ልንወለድ ግን እንችላለን" ሲል ሌላዋውም ሞንቅላቱን በመነትነት መስማማቱን ገለጸ ።

"ታዲያ አንዴ በሱስ የተለከፈ ሰው ... የእድሜ ልክ በሽተኛ ነው መይስ ... ሙሉ ለሙሉ ሊድን ይችላል? ማለቱ የሀክምናውስ ዓላማ ምንድን ነው?" አለ ያኪን ፣ አውነም ጥያቄውን በመተከል ።

"ተለከፈ የሚለውን ታል መጠቀሙ ልክ መሆኑን እንኛ ... ግን አንድ ሰው ሱሰኛ ሲሆን በአንነሱ ውስጥ የሚፈጠሩ ለውጦች አሉ ። ይህም የሱስኝነትን ዝንባሌ ሙሉ ለሙሉ ለማስወገድ አስቸጋሪ ያደርገዋል ። ለምሳሌ የመጠጥ ሱሰኛ የሆነ ሰው ከታከመም በኋላ ከመጠጥ ካልራቀ አንድገና ወደ ጠጪንቱ በተላሉ መመለሱ አይቀርም ። ስለዚህ መጠጥን ሙሉ ለሙሉ ማቆም አማራጭ የለውም ። በአንድ ሱስ የተያዘ ሰው ከሌላ ሰው ይልቅ በሌሎችም ሱስ እም ጪ ነገሮች ለመጠመድ በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጠ ነው ። ባጠቃላይ ያለው ሙርህ ... "አንዴ ሱሰኛ የሆነ ሁሉም ሱሰኛ ነው" የሚልና "ያንድ ነገር ሱሰኛ የሆነ ሰው የሁሉም ነገር ሱሰኛ ነው" የሚል ነው ። ግልጽ ነው?" አለ ሌላዋው ሁሉንም እየቃኘ ። ሁሉም በአምንታ ዓይነት ፈገግ ሲሉ ከአጠገቡ የተቀመጠችው ሴት ካንበሳችበት ቀና እንደ ማለት ።

@OLDBOOOKSPDF

"እሱ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ሱሰኛ ሲት የመሆን ችግሩ ደግሞ ሱስህንም መያዟና የበለጠ ማህበረሰቡ የሚያሳይህን ንቀትና መገለል መቋቋም ይኖርብሃል። ይህን ለማድረግ ስትል ወይ ከሌሎች ሱሰኞች ጋር በመኖሮት ወይም በብቸኝነት የበለጠ ሱስ ሙሰጥ ለመግባት ትገደዳለህ" አለችና በረጅሙ አዛጋች።

ሲራክ በሷ ሃሳብ ላይ በመጨመር፣ "ከዛም በላይ በባህላችንና በሃያማኖቱ ሙሰጥ ስለ ሱስ ያለው ከሃጢያትና ከሞራል ነውርነቱ አንጻር ያለው የጉላ አመለካከት ሀመም ነው የሚለውን እይታ ደጋግደዋል። ሀጻናትን ሱስ ከሚያሲዙ ንግሮች አለመከላከል፣ አደንዛዥ እጽና መጠጥን ያላግባብ እንዳያሰራጩ ማድረግ አለመቻላችንም ገና በሌጋ እድሜ ብዙ ስዎች በሱስ እንዲጠመዱ በር ያከፍታል።

"የምዘርና የህዘምና አገልግሎቱም በበቂ አለመኖር ለሱስ የበለጠ መስፋፋትና ከሱስ ለመውጣት አለመቻል ያለው አስተዋጽኦ ተሳል አይደለም" ብሎ ሲላሙን እየት አድርጎ ትንፋሹን ሰብስቦ ንግግሩን በመቀጠል "እንድ ሰው በሱስ የመጠመዱ ምልክቶች ምንድናቸው? ምክንያቱም የጠጣ ሁሉ ለምሳሌ የመጠጥ ሱሰኛ አይባልም" ብሎ ለተካፋዮቹ ጥያቄ መረመረና ከፊቱ ያለውን ሙሃ አንስቶ ትንሽ ተንፈሷ።

ጸጥ ብሎ የቀየው ረሺድ የተንጨበረረ ጸጉሩን እያሻሸ "በቃ ... የሱስ እቃህን ለማግኘት የማትቀፍረው ጉድጓድ አይኖርም። የገባበት ገብተህ ነው የምታገኘው። የሚዘመው ለምገብ መብያ ብር ልታጣ ትችላለህ ... ለስስህ መፈጸሚያ ግን በፍጹም ሰው ሁሉ ደግ ነው የሚሆንልህ ... ከተሳሳትክ ይቅርታ አድርጉልኝ ግን እኔ ሳስበው የሱሰ አምላክ ያለ ይመስለኛል። እየለመድከው ስትመጣ ደግሞ እንደ ድሮ ዘትንሹ አያዘታህም ... ድንገት ከጠፋ ወይም ካላገኘህ ደግሞ ለምሳሌ እኔ ሜትና ሲጋራ ሆነው ... ፃራራውና ዱካዙ ሊገድልኝ ነው የሚያረስው ... ሳፋሽክ ነው የምሙለው። በቃ ሱስ ማለት ይሄው ነው ... መዘናኛህ ሳይሆን መዝናኛው ትሆናለህ" ሲል ሁሉም ሳቁ።

ጎን ለጎን ከተቀመጡት ሳይኖሞች አንዷ "እኔም ረሺድ ባለው እስማማለው ... በተጨማሪም ሱስ ብዙን ያደርግሃል። የሆነ አባዜ አለው ... ሱሰኛ ማለት እንደበዘ የሚሞት ... በቃ በቱመ እያለ... ሕያውቱ ሳይሞት የሞተችበት ... ቂም ንዘርና እውነት የራቀችው ... ራሱን ሳይሆን ሌላ ሰው ሆኖ የሚኖር ... የህብረተሰብ ጥገኛና ጥላ ሆኖ የሚኖር ምስኪን ሰው ይመስለኛል። ወሽትና ስርዮት ሱስ ማስፈጸሚያ መሰሪያዎችህ ናቸው ... ኢቫን ሌላ ከባድ ወንጀል እንኳ ለመስራት ያስገድድሃል። የሰውነት ክብርህንና ደረሻህን ያወርዱዋል። ሱስ ማለት የራሱ ድምጽና ፈቃድ ... ዕቅድና እጀገፋ ያለው ክፉ ጊታህ ነው። እንደፈለገው የሚያሽርህ ባንተ ቱር ውስጥ የሚኖር ሌላ ሰው ነው የሚመስለኝ" ስትል ሁሉም ራሳቸውን ነቀነቁ።

ሁሉም ጸጥ ሲሉ ሌላሙ ተበል አድርጎ፣ "ሁላችሁም ያላችሁት ሱስን በትክክል ነው የሚገልጸው። በየትኛውም መንገድ ይግባ፣ ምንም ንዘር ይሁን፣ ሱስ የሚፈጥሩ ንዘሮች ዘአንገላችን ውስጥ የሚፈጥሩት ተጽእኖ ተመሳሳይ ነው። ለህይወት እንቅስቃሴያችንና ለጉር ግኤታችን መነሳሳትንና ደስታን የሚሰጠንን የአንጎላችንን ማዕከል፣ ያላግባብና ካቅም በላይ በመቀስቀስ፣ ቅጽበታዊና ልክ የለሽ የሆነ ደስታ

@OLDBOOOKSPDF

ለመፍጠር ተብሎ የሚሰራ ስህተት ነው ።

"ይህ ያንገላችን ክፍል የድስታና የሽልማት ማዕከል ሪዋርድ ሲንተር ይባላል ። ሕክ ያስያዘን እጅም ሆነ ሴላ ነገር ከማእከሉ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ዶፓሚን የተባለ ጥንቅላታችንን በደስታና ልክ የለሽ በሆነ ጊዚያዊ መሩንዘንዝ የሚሞላ ንጥረ ነገር እንዲተጠብ ያደርገዋል ። ይህ ልክ የለሽ ትጽበታዊ ደስታ ሲያልት ደግሞ ፣ ያንን ተዚጸ ረስታ ፍለጋ የማይቀም ጥረት ውስጥ በማስገባት መጥመዲ ያጀምራል ።

"ሱስ ተፈጥሮአዊውን የደስታ ሃብት በአድራጭና ባልተፈተዩ ከፍተኛ መጠንና ፍጥነት ለማግኘት መሞከር ነው ። ኋላ ለእስፈላጊው የህይወት ግዴታና የንዮ ሃላፊነት ስንፈልገው የደስታ ኮሮጇችን ባዶ ስለሚሆን መነላሳት የሌለን የራሱ አሰሪዎችና የሱስ ቡሃ ያደርገናል ። ለዚህም ነው ሱስ ያለበት ሰው ከሱስ ንጻ የሆኑ ለሎች በሚያስቡበትና በሚዝናኑበት ነገር ላይ ስልቹ የሚሆነው ። በዚህም ምክንያት በሱስ ስንጠመድ ደስታንና ርካታን ለላምንና ሶራፍትን ፍለጋ በማያባራ አባዚ ውስጥ የምንገባው ።

"እንግዲህ የሱስ ህክምና ማለት ከዚህ አዙሪት ውስጥ ለመውጣት የሚደረግ የዚህን የአንገላችንን የደስታና የመነላሳት ማእከል መልሶ የማቋቋም ሥራ ነው ። ለዚህም በግል ብቻ ሳይሆን በማህበር ተጠያቂነትን በመፍጠር፣ አስፈላጊ በሆኑም ጊዚያት የግል ምክርንና መድሃኒቶች በመጠቀም መታከምን ብሎም መንፈሳዊ እገዛችን ማግኘትንም ይጠይቃል ። የቢተሰብም በዚህ ትግል ውስጥ አብሮ መቆም በጣም አስፈላጊ ነው" አለ ። የተነሱ ጥያቄዎችን እየመለሱ ሲወያዩ ቆይተው ስነቱ ሲያልት ለሚተዋለው ሳምንት ሲገናኙ ተተጣጥረው ተበተኑ ።

ሴላሙ ተሰናብቶት ከመጣ በኋላ ሲራክ አባው በተቀመጠበት ጥቂት ቆየ ። 'አባዚ' የምትለው ታል በአእምሮው እየደጋገመች መጨወሏን ተገነላለች ። 'ሰው ሁሉ በራሱ አባዚ የተሰነፈ አባዚያም ነው ። መጠጥ ባይሆን ሲጋራ፣ መሲብ ባይሆን ቁማር፣ ቡና ባያሆን ምግብ፣ እመትና ባይሆን ጉልበተኝነት፣ እጠቀት ባያሆን ገንዘብ ። ሰው ከሌላው ሰው በልዩና ተሻሎ የመገኘት አባዚ ...የንያል ጥማት ... ከፍ ብሎ የመታየት አባዚ የተጠናወተው ብኩን ፍጥረት ነው ። ' ሱስን የሚፈጥረው የሰው የንያልና የከፍተኛነት ጥማት መሰለው ።

"ሲጠላም ሆነ በመሲብ ሲሆዝ ...በእጽም ይሁን በገንዘብ ሲሰክር ... ሰው እቅመ ቢስነቱን ... የበታችነቱን ያረላል ... የበላይነት ይሰማዋል ። የሰው ዋልቱ ሱስ፣ ንያልን መራቡና ከፍ ያለ ስሜትን ፍለጋ መንከራተቱ ነው ። ሰው በሁሉ ነገር ውስዋ ትርጉምን የሚፈልግ ገስቲላ እንሰላ ... የሃይል ረሃብተኛ ደካማ ፍጥረት ስለሆነ ሳያስበው ትርጉምና ንያል በማይሰጡ አሚበርባሪ ትርጉም የለሽና ንያል አልባ ነገሮች ተጠምዶ ሲገኝ የሱስ ባሪያ ይሆናል ። ' ይህን እያሰበ ክፍሉን ዘግቶ ወደ ራሱ ቢሮ ገባና በሩን ቀላልፎ ወደ መኪናው ተጣደፈ ።

ከገቢው ሲወጣ ተደም ብሎ ከምስጢር ጋር ያደረጉትን ረጅም ከርከር አሰበ ። ንሱም ከርከሮን የማሸነፍ፣ የበላይ የመሆን አባዚ ... ያሌ ታውቀ ሱስ ሳይሆን አይቀርም' ብሎ በራሱ ለመሳቅ ተገደደ ። ሕይወት ከሱስ ከላይም በታች የመኖር ምርጫ ሆና

@OLDBOOKSPDF

ትናችው። 'እውነትን በሞራው የመፋጠጥ እትም የሌላቸው ... ዕለታዊ ጥቃትን ይስተዎትን ማጣጣም የማይችሉ ... ነሲጭች ተሸእኖና ሞላ ውጪ የመሩ ጥንካሬ የሌላቸው ብዎች በቀላሉ ተጠልፈው በሱስ መጸፍ ንብተው ይወድቃሉ። አቢት ሲያሳገት።'

ከጎሊና ጋር መኖ ተቃጠፍበት ቤት መስኮቱን ገራና ቀኝ ከፍት በተዘቃዥ ነፋስ የሞተ ፈቱን እያስመታ ነጻጹን ረገጥ አድርገ ከነረ። ለርሱ ያልተገለጠለትን የራሱን አባዜ ... እያባበለ ሊያስተኛ ... እያጣጣመ ሊረሳ ... ከቀጠሮው አንዳትም ደቂቃ ላለማርፈድ በረረ ... በቻለው ፍጥነት። ቀን ሲያንላጅጀው የዝረው እንቅልፍና ድካም የት እንደገባ ሊያውቅ አልቻለም። 'የሽልማት ማዕከሉ' በትዘበል ሥራውን እየሠራ ነው ብሎ አመነ። ማምሻውን ደግሞ ተጨማሪ 'ሽልማት' ሳይሰጠው አያቀርም።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 28 ፡

ሌላው በቅርብና በጥልቀት ለሚያጠናቸው የተወሰኑ ሰዎች የተለየ ማህደር አዘጋጅቶ ዝርዝር ነገሮችን እየመዘገበ ማስቀመጥ ይወዳል። በተለይ ያላቸው የሰብእና አወቃቀር፣ የሥነልቦና ውስብስነትና ችግሮቻቸው፣ በውስጡ ሲብላሉ ለነበሩ ጥያቄዎች መልስ ይሰጡኛል ብሎ ያሰባቸውን ጥቂት ሰዎች፣ ረዘም ላለ ጊዜ ማጥናት እንዳለበት ወስኗል።

ዛሬም በማለዳ ቢሮ ገብቶ በሳምንቱ ውስጥ ያገኛቸውን ሐሳቦች ሲጽፍና በስም በስማቸው በከፈተው ማህደር ውስጥ እየጠረዘ ሲያስቀምጥ አረፈደ። ከዚህም ውስጥ የምስጢር እናት፣ የምስጢር አድብቶ ተከታይ ማሰረሻ፣ ምስጢር ራሷና ሲራክ ይገኙበታል። ፋይሉን የሚያስቀምጠው ማንም እንዳይደርስበት ከመደበኛው የክሊኒኩ መዝገብ ክፍል ውጪ በራሱ ቢሮ በሚገኘው ተቀላፊ መሳቢያ ውስጥ ነው።

የማለዳዋ ፀሐይ ቢሮውን ድምቀትና ሙቀት ሞልታው ፍክት ብሏል። ሙሉ የየቱ በቀጠሮ የተሞላ ስለሆነ የሚደዋወላቸውን ስልኮች እየደዋወለና የሚፈራረሙ ወረቀቶችን እያገላበጠ አይቶ ቶሎ ጨራረሰ። በዚህ መሃል የገናናሽ እህት ደውላ የአባቷን መታመም ነገረችው።

"እባክህ ዶክተር አባባ ሰሞኑን ጤናም የለው። ዛሬ ሌሊት ደግሞ ብሶበት እንዲሁ ከላይ ከላይ ሲተነፍስ ነው ያደረው ... ውጋቱም ግራ ጎኔን ቀስርኖል ነው የሚለው ... ትኩሳቱማ አይጣል"

"ሃኪም ቤት መስዳችኋቸው ነበር?" አለ፣ ነገሩ የሳንባ ምች ሊሆን እንደሚችል እየጠረጠረ።

"እምን ... እዚህ ጤና ጣቢያ ወስደነው ... ማስታገሻ መርፌና የሆነ ኪኒና ሰዋተው ነበር ከትናንት ወዲያ ... ግን ባሰበት እንጂ ምንም አላሻለው" አለች ድምጿ በጭንቀት ተውጦ። የሀጻናቱ ወላጆች ልጆቻቸው ከጠና አልፎ ይሰግል።

@OLDBOOKSPDF

"በቃ ... እስኪ ከምላ በኋላ ብት ብዬ አያቸዋለሁ ። ካልሆነም የተሻለ ክሊኒክ ወይ ሆስፒታል እንዲታዘሙ እናደርጋለን ። ምግብስ ይበሉልሻል?" አለ፣ ወዲያውኑ መኪና ልኮ እንዲታዘሙ ለማድረግም አያሰበ ።

"እዎን ... ትንሽ ቁርስ ቀምሶ ነበር፣ ግማሹ ወጣ እንጂ ... የበላው ሁሉ አይረጋም" ስትል፣ ነገሩ አስቸኳይ ሊሆን እንደሚችል አሰበ ።

"በቃ አሁኑኑ መኪና እልክና ወደ ሆስፒታል ይወስዷቸዋል ። አንቺ ግን እትደናገጪ" ስልኩን ዘጋና ወዲያው የክሊኒኩን መኪና በሾፈር ላከላቸው ። ጥቂት ሀመምተኞችን አይቶ መልሶ ሲደውል ቤቲል ሆስፒታል ወስደዋቸው እንዲተኙ መወሰኑን ነገረችው ። ላንቾ ጋ ቢደውል ስልኩን ሰላላነሳለት ምስጢር ጋ ሞከረ ።

"ሰላም ሚስጥር ... ቢሮ ገብተሻል እንዴ?"

"እዎን ... ዛሬ ሙሉ ጠዋት ቀጠሮዎች አሉኝ ... ሰላም ነው?"

"ደህና ደህና ... ከዘንበወርቅ ጠዋት ላይ ደውለው ነበር ። የዝናሽ አባት ታመዋል ብለውኝ ... ሆስፒታል እንዲወስዷቸው ነግሬያቸው ቤቲል አስተኝተዋቸዋል ። ጊዜ ካለሽ ምላ አብረን በልተን በዛው ብናያቸው ብዬ ነበር"

"ውይ ... ምን ሆኑ? ... ለነገሩ እርጅናውም እኮ ቀላል አይደለም ። ችግር የለም እችላለሁ ... በጣም ቀየሁ እኮ ካየኋቸውም ። "

"እኔ እንሻ ... ኒሞኒያ ይመስላል ...ሳምባ ምች ነው የምትሉት ባማርኛ? እስኪ ላንቾም ከቻለ ንገሪው ... ሞክሬለት አያነሳም ስልኩን ... ምላ እኛ ቤት በልተን በዛው መሄድ እንችላለን ። "

"ጥሩ ... ስንት ... ስድስት ብለን እናስብ ከዚህ ለመውጣት?" አለች፣ ሰአቷን እየት እያደረገች ።

"ኦኬይ ... በቃ በኋላ እይሻለሁ" አለና ፣ ስልኩን ዘግቶ የሚቀጥለውን ሀመምተኛ ለማስገባት ተነሳ ። ለክትትል ከሚያያቸው ሀመምተኞች አንዱ ከሁለት ሳምንት በፊት ካባቱ ጋር በከፍተኛ የአምሮ መረበሽ ውስጥ ሆኖ የመጣው ኑረዲን ነው ። ስሜቱ ረገበና አእምሮው ተረጋግቶ ሌላ ሰው ይመስላል ። መድሃኒቱን በትክክል እየወሰደ መሆኑንና ወደ ሥራም ለመመለስ ማሰቡን ነገረው ። ከአንድ ሳምንት በኋላ ሁሉም ነገር ደህና ከሆነ፣ ወደ ሥራ መግባት እንደሚችል ተስማምተው ለወር ቀጠሮ ሰጠው ። ለጠየቁ የመጪረሻ ሕመምተኛውን ባንድ በኩል ልጃቸው በሌላ በኩል እርሱ ደግፏቸው እንደ ምንም ከረጅሙ ሶፋ ላይ አስቀመጧቸው ።

ለረጅም ጊዜ በዩኒቨርስቲ ያስተማሩ በኋላም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ በዲፕሎማትነት ብዙ ሃገሮች የሠሩ የታወቁ ሰው ናቸው ። ዕድሜያቸው ሰማኒያ ሶስት መሆኑንና ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ፣ ከርሷ ጋር እንደሚኖሩ ልጃቸው ነገረችው ። የጠየቃቸውን መሰረታዊ የማንነት ጥያቄዎችን እንኳን በትክክል መመለስ አልቻሉም ። ሁሉም ነገር ግራ ግብት ይላቸዋል ። የሆነ ያልሆነ ነገር ከድሮ ትዝታቸው

@OLDBOOOKSPDF

ጨምረው የሚጀምሩት ወሬ ማሰሪያ ያጣባቸዋል። ከአለባበሳቸውና ንጽህናቸው በጥሩ ሁኔታ የተያዙ ይመስላል።

አጠቃላይ ነገሮችን ከጠየቃት በኋላ ወደ እሳቸው ዘር ብሎ፣ "አቶ ገብረመድህን ... የዛሬን ቀን ይንግሩኛል? ቱኑን ወሩንና ዓመተ ምህረቱን?" ሲል ትኩር ብለው አየት።

"ምስክረም ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሰባት ..." አሉ፣ በጣታቸው ሰመቁጠር እየሞከሩ። ሌሎች ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን ቢጠይቃቸውም ከስማቸውና ከልደት ቀናቸው ውጪ፣ የቀረውን ሁሉ ሊያስታውሱ አልቻሉም።

"እሷ ምንዎ ናት?" ብሎ ወደ ልጃቸው ጠቀማቸው። እንደማያውቋት ትኩር አሉ አየዋትና፣

"እሷማ ባለቤቴ ... የልጆቼ እናት ናት ... ሌሊት እየጠፋች የት እንደምትሄድ አላውቅም። ከዛ ሽንካፋ ሰውዬ ጋር ይትርብሽ ብላትም አትሰማም። እኔ የተኛሁ ሊመስላት ሹልክ ብላ መሄድ ነው" አሉ፣ ቁጣ ብለው። ልጃቸው እገሪን ብላ፣

"አባባ እኔ እኮ ማህሌት ነኝ ... ማሚ እኮ ካረፈች አራት አመት ሆናት" ስትላቸው፣ ፊታቸውን አዞሩባት።

"ብዙ ጊዜ ሆነ ... ነገሩ ከጀመረ?" አለ፣ ረጋ ባለ ድምጽ ወደሷ እያየ።

"እህቴ ጋ ካናዳ ለህክምና የዛሬ ስድስት ዓመት ሄዶ ነበር ... ትንሽ መርሳትና አንዳንዴም እየነዳ መጥፋት የጀመረው ያኔ መሰለኝ። ከዛ በፊት ብዙ ቀዶ ህክምናዎችን አድርጎ ስለነበር ከዛ ጋር የተያያዘ መስሎን ነበር። ያኔ እናቴም በሕይወት ስለነበረች ብዙም ችግሩ አልታወቀንም ነበር። እሷ ዓይኑ ነበረች ማለት ትችላለህ። ከመሞቷ በፊት ሁለቴ ተሰያይቶው አያውቁም። ድንገት በደም ግፊቷ ቦሰ ሜንቅላቷ ውስጥ ደም ፈስሶ ስትሞት፣ በቃ በሚገርም በፍጥነት ባሰበት። ሃዘኑም በጣም ላይጎዳው አልቀረ። ከናዳ እንደገና ሲታይ አልዛይመር ነው ብለው የተወሰነ መድሃኒት ሰጡት። እህቴ ስላልቻለችው ነርሲንግ ሆም መግባት አለበት አሉ። እዚህ ትንሽ ከቤተሰብ ጋር ከተማከርን በኋላ፣ የሚያግዘን ሰው ቅጥረን ራሳችን እንንከባከበው ብለን የዛሬ ሁለት ዓመት አካባቢ ነው ያመጣነው" አለች፣ የሪጠቡ ዓይኖቿን እየጠራረገች። ድንገት ሲነሱ ሲሉ እንደ ምንም ብላ ይዛ መቀመጫቸው ላይ አቀየቻቸው።

"በዚህ ሁለት ዓመት ውስጥስ ብዙ ለውጥ አለ?" አለ፣ የሚንቀጠቀጡ እጆቻቸውንና ሜንቅላታቸውን እያጤነ።

"በቃ ያቺው የሚያቃትና የሚያስታውሳትም ነገር ሙሉ ለሙሉ ጠፍቶበታል። አሁን ማናችንንም አያውቁንም። ሁሉንም ነገር ሰው ነው የሚያደርግለት። ከዛ የሰጡት ሁለት መድሃኒቶች አሉ። ይሄ መንቀጥቀጡ የባሰው ሪስፔሪዶን የሚሉትን መድሃኒት ከጀመረ ወዲህ ነው። ማታም ምንም እንቅልፍ የለውም። ሲዖህ ሲጠራሮ ነው የሚያድረው። አፉ ብቻ ነው ያልተሽነፈው። በደህና ቀን ብታውቀው እንዴት አደነቅ ጨዋና ሊቅ ሰው ነበረ መሰለህ ዶክተር" አለችና ዓይኖቿ እንደገና በእንባ ተሞሉ።

@OLDBOOOKSPDF

"አይ አም ሶሪ ... አይዞሽ ... ምግብስ ይበሱልሻል? ሙላደብና ተናዶ ልግታ የማለት አይነት ባህሪስ ያሳያሉ?" አለ፣ ከፊቱ ያለውን ናፕኪን እያቀበላት። ሊያረግላቸው የሚቻለው ነገር የተወሰነ መሆኑን እንዴት እንደሚያስረዳት አሰበ።

"ምግብስ አልር አልር ቢቸገርም ይሀና ነው። ግን በታ ምን እንዳስቀጣው እንኳ ሳናውት ቱግ ይላል። ባለፈው ሁለት ወር ይገም እሹን እያመናጨረ ለብቻው ያወራል። በቀላሉ ንጭንጭ ያደርገሞል ... ወይ እሪ ብሎ ያለትሳል ድንገት። በዚህ ስቱጅ ዲፐረስድ ሊሆን ይችላል እንዴ ዶክተር?"

"እከቹሞሊ ... ድባቴ ብዙ ጊዜ ያጋጥማል ... ግን ብዙ ሰው በቀላሉ ሊያውቀው አይችልም። መንቀጥቀጡ የመድሃኒቱ የነን ጉዳትም ሊሆን ይችላል ... እሱን ግቶም ሊኖርብን ይችላል። ሽንትና እይነምድር ላይ ምንም ለውጥ የለም?"

"ሁልጊዜም ድርቀት አለው ... ሽንቱ ግን ሰሞኑን የተነሰ ይመስለኛል። ባለፈው ላምንትም ትንሽ ትኩላት ነገር ነበረው ... ግን በታ ትንፋን ነገር መስሎን ነበር።"

"ለማንኛውም የሽንት መተላለፊያ ወይም ሌላ ኢንፈክሽናች ሲናሩ ሁኔታውን የማባባስ ባህሪ ስላላቸው ... ሽንት ይምና ራጅ መርመራዎችን ማድረጉም አስፈላጊ ነው። በትርብ ወድቀው ወይም የሆነ ነገር ሞንትላታቸውን መታቸው ያውቃል?" አለ ተነስቶ ሞንትላታቸውን እያየና መሰረታዊ የሆኑ አካላዊ ምርመራዎችን እያደረገ።

"ኧረ ምንም ... እኔ እስከማውተው ድረስ ምንም የለም ... ግን ምን ይታወቃል ... ቢወድትም ... የሆነ ነገር ቢገጨውም አይነገርህ እሱ ..." አለች፣ ብድግ ብላ ትከሻቸውን እያሻሸች።

"ለሁሉም የሚሻለው ... ወደ ሆስፒታል ልከናቸው ምርመራውንም ብናደርግ ለጥቂት ቀን ይተኙ። ሌሎች ሜዲካል ችግሮችም ከተገኙባቸው እየታከሙ ቢያርፉ ጥሩ ይመስለኛል። ለቤተሰቡም ትንሽ እረፍት ሊሰጣችሁ ይችላል" አለ፣ እሺቸን እንደያዘ ቀሞ።

"ጥሩ ነው ..." አለች መልሰው ከሶፉው ላይ እያስቀመጧቸው። "እኔ ምለህ ዶክተር እንዲያው የዚህ ነገር ሂደቱና ፍጻሜው ምንድነው?" አለች ድክም እንላላት በሚያስታውት ድምፅ።

"ያው መጀመሪያ ላይ እንዳልነው ... ዕድሜያቸውም ገፋ ያለ ስለሆነ የሕመሙ አይነት አልዛይመርስ ዲሜንሽያ የምንለው ይመስላል። ያው በተለምዶ መጀመት ነው የሚባለው መስለኝ። ባብዛኛው በመርሳት ይጀምርና ሌሎች ከፍተኛ የሆኑ የአእምሮ ተግባራት ... እንደ ማተድ፣ ማስፈጸም፣ ስሜትን የመቀጣጠርና ማህበራዊ ችሎታዎች ሁሉ ቀስ በቀስ ይጠፋሉ። ዲሜንሽያ ስንል ግን ብዙ አይነት ሊሆን ይችላል። በየናንት የማስታወስንና የማመዛዘንን አቅም ከሌሎች የአእምሮ ተግባራት ጋር በሂደት የጣጥፋት ባህርይ ያለው የአርጅና ሕመም ነው። ለረጅም ጊዜ የመጠጥ ሱሰኛ የሆኑ ሰዎች፣ በአደጋ ምክንያት ሞንትላታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ወይም በተደጋጋሚ ሁኔታ የተነሱ

@OLDBOOOKSPDF

ልቦች ላይም ያለ እድሜ ሊከሰት ይችላል ። በተመሰን መጠንም በቤተሰብ የመሄድ ባህሪ አለው ።

"ባጠቃላይ ነገሩ እየባሰ እንጂ እየተሻለ አይሄድም ። ያሉት ሀክምናዎችም መሰባቡን በተመሰን መጠን ለማዘግየትና እስካሉ ድረስ የአንገልን ተግባር በተመሰን መጠን ለማገዝ ብቻ ነው የሚጠቅሙት ። ዘብካቤ ማደረጉ ለቤተሰብ በገንዘብም ሆነ በስነልቦና የሚያስከፍለው ዋጋ እጅግ ከባድ ስለሆነ መረዳዳት ያስፈልጋል ። በተለይ እንደ አገራችንና ድባቴ አይነት ሌሎች ሀመሞች ሲጨመሩ ችግሩን የበለጠ ያወሳስቡታል ። ሃመሙ ከታወቀ በኋላ ሌላ ችግር ከሌለ ከአምስት አስከ አስር አመት መኖር የተለመደ ስለሆነ፣ የረጅም ጊዜ እቅድ የግድ አስፈላጊ ነው ። እዚህ አገር ደግሞ ሥራው ሁሉ ቤተሰብ ላይ ስለሚወድቅ፣ እስካሁን ካላደረጋችሁ የቤተሰብ ስብሰባ አድርጋችሁ ዘላቂ የክብካቤ እቅድ ማውጣት አስፈላጊ ነው" ብሎ፣ ማስታወሻውን ካርዱ ላይ ጻፈና የሾኖ ደብዳቤ ወደ ሆስፒታል መጻፍ ጀመረ ።

"በደህናው ጊዜ እኮ ብታውቀው ... አውርተህ እትጠግበውም ። አባቴ ስለሆነ አይደለም ... በህይወቱ እንደሱ አይነት ሁለገብ ጥልቅ አሳቢ ሰው አይቼም አላውቅም ። አሁንእኮ ... ቀርውን ብቻነው ያስቀረልን ... ሀመሙ ፈጽሞ የማናውቀው ሌላ ሰው ነው ያደረገው ። ይሄ በሽታ አይደለም ... ለማንም አልመኘውም ..." ብላ ማልቀስ ስትጀምር ከጠረጴዛው ላይ ያለውን ናፕኪን እንደገና እያቀበላት፣

"እሞን ... አናውቀውም እንጂ ... ሰው ማለት እኮ የትዝታውና የትውስታው ድምር ነው ። ሕይወት የመርሳትና የማስታወስ ሚዛን ናት ። መርሳት ያለብንን መርሳት ሲያቅተንም ሕይወታችን ይመሳቀላል ... እሱም ሀመም ሊሆን ይችላል ። ደግሞ ማስታወስ ያለብንን የሕይወት ልምዶች፣ ጠቃሚ ሰዎችና ነገሮች ከረሳን ... የእኖነታችን መለያና የሰብእናችን ድንበር ይጠፋና እንዳልሽው ሌላ ሰው እንሆናለን ። አንባላችን አዳዲስ ነገሮችን በመማር፣ በማስታወስና እንዳስፈላጊነቱም በማመዛዘን የመምረጥና የመወሰን ችሎታችንን የያዘ ክፍል ነው ።

"ዲሜንሽያ የምንለው ሀመም እንግዲህ ይህን ተግባር የሚሰሩ የአንባላችን ክፍሎች መታወክ ነው ። ለማስታወስና ከፍተኛና ረቂቅ የአእምሮን ስራ ለማቀናበር አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን የሚያመነጩ ሴሎችን በማመናመን ቀስ በቀስ የሰውን ግንኙት ለውጦ ራስን ሳይቀር ወደ አለማወቅ የሚያመጣ ሀመም ነው ። ትዝታው ከሕመምተኛው ቢጠፋም ... ከቤተሰብና ከወዳጅ ስለማይጠፋ መደገፉ ነው መፍትሄው ። ሰባራ እግር ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ሰባራ አእምሮም የሚደግፈው አስካገኘ ድረስ፣ ሕይወት ፈተና ቢበዛባትም ትርጉም እንዳታጣ ማድረግ እንችላለን" ብሎ ገለጭ አለ ።

"ልክ ነህ ዶክተር ... ምንም ነገር ቢሆን ስለወደድነው ለዘላለም እንደነበረ ሳናቀየው አንችልም ። ከሁሉም ነገር ውስጥ ግን ትርጉምን ማግኘትና ተደጋግሮ በማለፍ ሕይወትን ችግር ሳይሆን ዕድል አድርጎ ማየት ይቻላል ። ገብቶኛል ... ግን ያው ሰው ነኝ ... የምትወደው ሰው በሕይወት እያለ ወደ አለመኖር ሲሔድና የምታውቀውን

@OLDBOOOKSPDF

ማንነቱን ሲያጣ ማየት ግን እንዴት ያማል መሰለህ ። ስለ ዶግ ምክርህና መስተንግዶህ በጣም ነው የማመሰግነው ። የክሊኒካችሁ ሠራተኞች በሙሉ ከጥበቃዎቹ ጀምሮ በጣም ነው የረዱኝ ። እመሰግንልኝ ...ጥሩ ሰዎች ናቸው ። እንተም ሁሉንም ነገር በሌላ መንገድ እንዳየው ነው ያደረከኝ" ብላ ምስጋናዋን አሸገደገደችው ።

የቀረውን ዝርዝር ዕቅድ ተነጋግረው በተኙበት ሊከታተላቸው ተሰማምተው ሸኛቸው ። ምስጢርና ሳጎቾ ደጅ ቀመው ሲጠብቁት ደረሰ ። በማርፈዱ ይቅርታ ጠይቀ፣ በምስጢር መኪና ተያይዘው ወጡ ። ከግቢ እንደወጡ እናቱ ጋ ደውሎ ለምላ እየመጡ እንደሆነ አስታወላቸው ።

"እያችሁት?"

"ምኑን?" እሱ ሁለቱም ዞር ዞር አያሉ ።

"አሁንማ አለፋችሁት ... ማስረሻን ነዋ ... ከበሩ ፊት ለፊት ካለው ሱቅ በር ላይ ፊቱን በጋዜጣ ሸፍኖ ስንወጣ ወዶ እኛ እያየ ነበር"

"ሪሲ ... እንቺ እንዴት አየሽው? አሁንም እዚህ መምጣቱን አላቀመም ማለት ነው?" አለ ሌላው ።

"እዩ ... ምን ያቀማል ብለህ ነው ... እኔማ እንዴት አላየው ... ምናልባት እኔን ስለሚከታተለኝ ከናንተ ይልቅ የኔ እንቴና ሁሌ እንደቀመ ስለሆነ ይሆናል ። የሚገርማችሁ ነገር እኮ ... እሱ ባካባቢው ሲኖር የሆነ የሚነግረኝ ነገር አለ ... ትከሻዩን ይከብደኖል ... ደግሞ የሚገርመው ሁል ጊዜም ዞር ዞር ካልኩኝ ... የሆነ ቦታ ተወሽቀ አየዋለሁ"

"እኔ ምልህ ዶክተር ሌላ ... ቀይ እሲን እንዲረሳ የሚያደርግ ምንም መድሃኒት የለም እንዴ... በቃ ስለሷ እንዳያስብ ... መኖሯን ከሚጎንቅላቱ የሚፍቅ ነገር ለምን አታገለትም...?"

"ውይ እንደሱ አይነትማ መድሃኒት ቢኖር እኔ ራሴ እከፍል ነበር የመድሃኒቱን ዋጋ ...የፈለገውን ያህል ውድ ቢሆንም"

"የሚያሳዝነው ነገር እኮ መርሳት ለማይፈልጉትና መርሳት ለሌለባቸው ሰዎች በሽታ ... ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ደግሞ የማይገኝ መድሃኒት መሆኑ ነው" ብሎ፣ መጪረሻ ላይ ስላያቸው ሀመምተኛ ነገራቸው ።

"እና የማስረሻ በሽታ አለመርሳት ነው ልንል እንችላለን?" ሲል ሳጎቾ፣

"አይ ... ሲረሱት አለማወቅም ሊሆን ይችላል ። ቢያንስ ስሙን መሆን ካልቻለ ቢያስተይረውና 'መንቻኪ' ወይ 'ኡሁ' ቢሉት ይሻል ነበር" አለች፣ ውስጧ እየደበ ላይ ላዩን እየሳቀች ።

"ሚስጥርዬ... ኧረ ረስቼው በናትሽ ...ጉድ እንዳልሆን ... ተመልሰን ቢሮ ስንገባ አደራ አስታውሺኝ ..." አለ ሳጎቾ የምሩን በሚመስል ድምፅ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ምኑን ..." አለች ደንገጥ ብላ

"ምንድን ነበር እንኳን በናትሽ ... እኔ እንጃ ልጄ አይገርምም አሁን ባሁን ራሱት መስለኝ ... እዩ ... 'መርሳትና ማስታወስ' እኔንም ያዙኝ መሰል ..."

"ለዛቢስ ... ቀይ ብቻ ..." አለች በመስተዋቱ ውስጥ እያየችው።

ቤት ደርሰው ምሳ እየበሉ ሲጫወቱ፣ "አታቲ ... የማስታወስ ችግር ይሻላል ይደለ የመርሳት ችግር?" አለ ሌላሠው ነገሩ እንደገና ትዝ ሲለው፣

"ምን አይነት ጥያቄ ነው ሌላዓለም ... ምንድነው ልዩነቱ?" አሉ የጠቀለሉትን ምንጉርሻ ለምስጢር እያገረሺት፣ "እስኪ ብዪ የኔ ቀንጆ ... ዝም ብሎ ሲያደርቃችሁ አየ ... አስኪ እሱን ትተህ ብላ ሳንችዬ ...እኔ እቀጻዋለሁ እሱን" አሉ ቁርጥ እንጀራውን ጠቅሰው እየዘርጋቱ።

"በጣም ቀንጆ ነው ... በጣም እየበላን ነው" አለ ሳንቾ ውሃውን ለሁሉም እያቀረበ።

"ልዩነቱማ ... አንዳንድ ሰው ምንም ነገር አይረሳም ክፉም ነገር ይሁን በጎ። ለላው ሰው ደግሞ ትንሹን ትልቁንም ... የሰው ስም ሳይቀር ... ዕቃ ያስቀመጠበትን ቦታ ... በቃ ሁሉን ይረሳል ... ልክ ሰው ሲጃጅ እንደሚሆነው ማለት ነው። እንደሱ ማለቴነው። የቱ ይሻላል?"

"ቀይ ... ምን እንድልህ ነው ልጄ ... ቀኝ ወይ ግራ እጅ ቢቀረጥ የቱ ይሻላል እንደማለት ነው እኮ። ነገር የሙጥኝ ብሎ መያዝና አለመርሳት እንደ አሲድ የሰው ልብ ሊመርገ ይችላል። ደግሞ ሁሉን ነገር መርሳትም ደግሞ ቀልበ ቢስና ከንቱ ሊያደርግህ ይችላል። መርሳትም ማስታወስም በደርሁ ካልሆነ ስንኩል የሚያደርግ ሽታ ነው" አጥንት ስማምጣት ሲነሱ ሁሉም ተያዩ። ከምላ በኋላ አንዳንድ ስኒ አቦል ፉና ጠጥተው፣ ሦስቱም የገና ሽን አባት ለማየት ወደ ቤቲል ሆስፒታል አቀኑ።

ኢንፈክሽኑ በደማቸው ተሰራጭቶ ኖሮ ከፍተኛ ህክምና ከሚለጥበት ክፍል አስገብተዋቸው መድሃኒት በደም ሰራቸው፣ አክሲጂን ባፍንጫቸው ተቀጣጥሎላቸው ደረሱ። ወሰድ መጣ እያደረጋቸው በከፊል አቅላቸውን ስለሳቱ ነቅተው ሊያናግሯቸው አልቻሉም። ከዚያ ወጥተው ሲሄዱ ምስጢርና ሳንቾ በማስረሻ ጉዳይ ሲከራከሩ ሌላሠው ደግሞ ባንድ ልቡ የነርሱን ሙግት እየሰማ፣ 'መርሳትና ማስታወስ' በሚለው ሐሳብ ውስጥ ገብቶ ለጥቂት ደቂቃዎች ዋኘ።

'ሕይወት መርሳትንና ማስታወስን ... በመሸለምና በመቅጣት ... አንዱን ስታነግስ ሌላውን ስታኮስስ ... የምትቀጥል የትዝታና የትውስታ ... የመርሳትና የመዘንጋት ... ግሀደር ናት። ለሰውሰ የሕይወቱና ድምር ቀሪ ነገሩ፣ ትዝታና ትውስታ እንጂ ሌላ ምን አለው? እንደ ባህር ከስፋው... በመርሳት ጨለማ ከተዋጠው ... ውስጠኛ በውር የአእምሮ ጓዳው ጀምሮ ... እስከ ውጭኛው ... ነገር በግልጥ እስከ ተደረደረበት የትውስታ ሳሎኑ ድረስ ... የማንነት ማሕደረትና ደሀልውናው መሰረት የሆነው ... የአዕዋ ትዝታና የህይወት ዘመኑ ትውስታ ተንሰራፍቶ ይገኛል። ጤንነት ማለትም

@OLDBOOKSPDF

እንዳገባብ እንዳግባቡ ግልጡን የመሰመርና ... ስውሩን የመግለጥ ጥበብና ችሎታ ነው። እንገል ሊታመክ ... ልቦና ሲባባ ... ትገታና ስውርታ ... ትውስታና ገንጋታ ... ሚዛን ያጡና ስውነት ለው ከመሆን ተራ ይወጣል። ስለዚህም ጥያቄው 'መሆን ወይ አለመሆን' ሳይሆን 'ማስታወስ ወይ መርሳት' ነው።'

@OLDBOOOKSPDF

29

ሌላው የቀረበለትን ቁርስ በግማሽ ልቡ ጐረስ ጐረስ እያደረገ፣ ጠረጴዛው ላይ የዘረጋውን ጋዜጣ በማይበላበት እጁ ያገላብጣል። ሁልጊዜም 'ጠዋት ላይ የተከሸነ ፍርፍር በሰባ ቡና ከደሀና ጋዜጣ ጋር ለቁርስ ከተገኘ ቀኑ አለቀለት' ይላል ሲቀልድ። "ገና ጠዋት አይደል እንዴ የምትበርረው ... ምነው ዛሬን እንኳ አረፍ ብትል ልጄ?" ለሱት እናቱ፣ የቀዱለትን ቡና በጃቸው እንዳየዙ ከፊት ለፊቱ ቀመው።

መልሱን እየጠበቁ መሰሉት ቀና ብሎ አያቸው። "አይ እታቲዬ ጥሩ ነበር ግረፉማ ... ግን ... በጣም ብዙ መጨረስ ያለብኝ ነገር አለ። ከመሄዴ በፊት የግድ ላያቸው የሚገባኝ፣ ለዛሬ የቀጠርኳቸው ሀመምተኞችም አሉኝ። የክሊኒኩን ሃላፊነትም ማስረከብና ማከፋፈል አለብኝ። ከቻልኩ ለምሳ ብቅ እላለሁ። ከቢሮ ልጆች ጋር ለእራት ቀጠሮ ስለያዝን፣ ሳላመሽ አልቀርም ..." አለ፣ ቡናውን በትኩሱ ፉት ፉት እያለ።

"ይሄ ሁሉ በዛሬዪቱ ቀን ነው የሚሆነው? ደግሞ ... ባክህ ቀስ ብለህ ንዳ። ልብህ እንዲህ ተሰቅሎ መንዳቱም እኮ ጥሩ አይደለም ... ሀገሩ ሁሉ ተንከዋክዎ ማለቁ ነው። ወይ ... ለዛሬ እንኳ ሹፈሩን ለምን አትጠቀምም?" አሉ፣ ላንድ ልጅ ምሣ የሚበቃ ንርሻ እያሰናዱ።

"ገዴለም እታስቢ አታቲዬ... ቀስ ብዬ እነዳለሁ። እ-ን-ዴ-ዬ ...የት ልትወስጂው ነው እሱን ደግሞ የምትጠቀልዪው ..." ብሎ፣ ጋዜጣውን ጠረጴዛው ላይ ጣል አድርጐ ሊነሣ ሲል፣ ባንድ እጃቸው ትከሻውን ወደ ታች ያገ አደረጉት።

"በሞቴ ...ልጄ... የናት ጉርሻ ...ጋሻ ነው ..." አሉት። አፉ ውስጥ በጠቀጠቁበት ንርሻ ተግስጉሶ አፉ ተለጕመመ። ተዘገጃጅቶ ሲጨርስ፣ ጋዜጣውን ጠቅልሎ ከሚይዛቸው ወረቀቶች ጋር ቦርሳው ውስጥ አጨቀና እየተጠዳደፈ ወጣ። ሳር ቤትን እንዳለፈ ንውሕ ደወለች። እያመነታ አነሣው።

@OLDBOOOKSPDF

ይዞ እንዲመጣላት ስለምትፈልጋቸው ነገሮች እያወሩ፣ የፖሊስ ፊሽካ ሰምቶ ዞር አለ። ለእርሱ መሆኑን ሲያውቅ፣ "እዪ ፍቅር ... ፖሊሱ ሊያቀመኝ ነው መሰለ ... እስኪ ልለምነው እሺ ካለ" አለና ስልኩን ዘጋው። ወዲ ጻር አቱም መስታዋቱን ወደ ታች አወረደ።

"ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ... እስኪ መንጃ ፈቃድ" አለ, ትራፊኩ ወታደራዊ ሰላምታውን ትቷም ባለ ፊት እያቀረበ። ረጅም ጠቅር ያለ ቦርሜም፣ ቢከፈል ሁለት መካከለኛ ወይም ሦስት ጀግሪ ፖሊሶች ሊወጣው ይችላል። አጸፋ ሰላምታውን ከመለሰ በኋላ መንጃ ፈቃዱን ሰጠው። ብዙ መጨቃጨቅ ስላልፈለገ ቲኬቱን ተቀብሎ መንገዱን ቀጠለ።

ክሊኒክ ሲደርስ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው አንድ አፍታ ቀም ብሎ ከጥበቃ ሰራተኛው ጋር ወሬ ጀመሩ። የያዘውን ቦርሳ ከፊት ወደ ኋላ ከቀኝ ወደ ግራ እያወዛወዘ ሲያወሩ ቀዩ። በብዙ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ዕውቀት ያካበቱና ብዙ ያንበቡ የቀድሞ ወታደር ናቸው። ሰበብ ፈልገ ከርሳቸው ጋር ማውራት ደስ ይለዋል። ጳውሎስ ሆስፒታል ሲሰራ፣ ልጃቸውን ሊያሳክሙ መጥተው ተግባብተው ነው፣ ክሊኒኩ ሲከፈት የቀጠራቸው።

ቢሮው ገብቶ የሰራ ጠረጴዛው ላይ ተዘበራርቀው የተከመሩ ወረቀቶችን ቦታ ቦታ ሲሰጣቸው ቀለል የሚል ስሜት ተሰማው። እያንጎራጎረ የመጻሕፍት መደርደሪያውንም አስተካከለ። የመሄጃው ቀን በቀረበ ቁጥር የጎጴሕና የልጆቹ ናፍቀት ብሶበታል። ሁልጊዜም ከሚቀመጥበት ሶፋ ላይ ቁጭ ብሎ ትንሽ አሰላሰለ። ከክሊኒኩ የአመራር ቡድን ጋር ሊወያይ ያለባቸውን ነጥቦች አይፓዱ ላይ ጫር ጫር አደረገና ከጮኑ ካለው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠው።

አሁንም ልቡ ሊረጋጋለት አልቻለም። ከጢያኖው ፊት ለፊት ጠቀመጠ። ከጎጴሕና ከልጆቹ ጋር የተነሳውን ፎቶ አንስቶ እየት አድርጎ እስቀመጠው። ያልቀሸሹ የጢያኖ ቁልፎቹን አንድ ባንድ አጸዳቸው። ከዚያም ረጋ ያለ ሙዚቃ እጹ እንጻመጣለት መጫወት ጀመረ። ሰማዩ ላይ በጠዋት በስሱ የተረጨውን ነጭ ደመና ሲያይ ውስው ትንሽ ረጋ አለለት።

የመጀመሪያ ህመምተኛውን የሚያይበት ሰዓት መድረሱን ሲያይ ድንገት ብድግ ብሎ ቀመ። ከፊት ለፊቱ ካለው ፎቶግራፍ ላይ ትክ ብለው የሚያዩትን ጎጴሕንና ልጆቹን በፈገግታ አያቸው። የተጫወተውን ሙዚቃ ለምተው ያጨበጨቡለት ያህል ሞቅታ ተሰማው። ፎቶዎቹን አንስቶ ሳም ሳም አደረገና አስተካክሎ አስቀመጣቸው።

ሰዕለቱ በዛ ያሉ ባለ ተጠሮዎች ስለነበሩት ጠዋቱ እንዴት እንደሄደ ሳይታወቀው አለፈ። ለምሳ ፒዛ አዝዘው፣ የማኔጅመንት ስብሰባቸውን እዛው ክሊኒኩ ካፈ ውስጥ አደረጉ። መደበኛና አዳዲስ ጉዳዮችን ከተዋያዩ በኋላ፣ ስለጉዞውና በማይኖርበት ጊዜ ሊፈጠሩ ስለሚችሉ አንዳንድ ክፍተቶችና የውክልና ሽፋን ባጭሩ ያስበውንነገራቸው።

@OLDBOOOKSPDF

"ከምስት ላምንት በላይ የመቀየት ሃላብ የለኝም። ዶክተር ሲራክ እኔን ወክሎ ይሸናናል። ሌላው ነገር እገዳለ ይቀጥላል። እስተዳደራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለስተርም ስላለች ብዙ የምትቸገሩ አይመስለኝም። እኔም እደጨላለው ...በኢሜይልም እገኝናለን። የትርፍ ጊዜ ሳይካትሪስቶቹ ስለሚገቡ ያለብዙ ችግር ያለውን ከሊኒካል ስራመቸልን የምትችሉ ይመስለኛል።

"እም...ም ሌላ ምን አለ? ... አንዳንድ ሀሙም ተሞች ... እኔን ግየት ስለ ለመዱ ወይም ገና አስራራችንን ስላግያውቁ፣ እኔን ብለው ካስቸገሩ እስከመለስ መጠበቅ ይችላሉ። የኔ ምርጫ ግን ሲራክ ወይም ሌሎቹ ሳይኪያትሪስቶች በተጠሯቸው መሰረት ቢሰየየቸው ነው። ግስረሻን ግን እኔ ስመጣ ነው የግየው፣ ያንን ለርሱም አስጠንቅቂ አነገረየለሁ። ኤኒ ቲንግ ኤልስ" አለ፣ ዙሪያ ገባውን እያየ።

ምስጢርና ሳንቾ ሲራክን መወከሉ ብዙም እንዳልጣማቸው አውቂል። የሌላው እትድ ደግሞ፣ ሲራክ በአመራር ኃላፊነት ብቃቱም እንዲያድግና ወደ ፊት እውልረጅም ጊዜ በግይናርበት ጊዜ ከሊኒኩን ሙሉ ለሙሉ መምራት እንዲችል ነው። ተስበቶስ ነገሩን መስመር ግስያዝ ስለፈለገ፣ ከሲስተር ጠሊባ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ነው ደወክለው የወሰነው። ስብሰባቸውን ሲጨርሱ፣ ግታ ለእራት የሚገናኝበትን ሰዓትና የታ መርጠው ተስያዩ።

ከሶላበኋላ ግስረሻን ረዘም ላለ ጊዜ አናገሮት፣ እሱ ከአሜሪካ ሲመለስ ሊያየው ተስግሙ። እስከዚያው ድረስ ከሊኒክ መምጣት እንደግያስፈልገው በግልጽ ነገረው። እስካሁን በመሰረታዊ ደረሻ የተሳቡ አስተሳሰቦቹ ላይ ነው ያተኮሩት። ከፍተኛ ፍጥጫ ሊፈናሩ በሚችሉ የውስጥ ግጭቶቹና ከምስጢር ጋር በተያያዘ ያሉትን ስር የስደዱና የተሳቡ እምነቶቹ ላይ ብዙም አልተጋፈጠውም።

በተቻለው አትም በእርሱ ላይ ያለውን መተግመን እንዲያጳብርና ጠንካራ የምክር ግንኙነት ድልድይ መስራቱ ላይ ነው ያተኮረው። ግስረሻ ደግሞ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው ስልኩን የሚያጠፋ መስሎ የነበራቸውን ውይይት ሁሉ ይቀጻል። ቤቱ ሊሄድ የቀጻውን ደጋግሞ እያሜወተ በምክሮቹ እያሾፌ ይስቃል።

የእራት ቀጠሮው ሲደርስ ቀለል ያለ ልብስ ቀይሮ ወደዚያው አቀና። ቀጠሮው ላንቲካ ስለነበር በወሉ ስፈር አቀራርቦ ለመሄድ ሞከረ። ቴራ ላይ በነበረው ሞንትጉት ምክንያት ለረጅም ደቂቃዎች ተሳስሮ ቀየ። ዋቂት ረፍዶበት ደረስ። ከሲራክ በስተቀር በሌናራው የደረስ አልነበረም። ካንድ ዋግ ላይ ሆኖ ዳገስ ያለ መጽሃፍ ይዞ በተመስዋኦ ውስጥ ስለነበር እጠገቡ ሲደርስ ደንገጥ ብሎ ቀና አለ። ሰላም ተባብለው እንደ ተቀመጡ መጽሃፉን ጠረጴዛ ላይ ደፍቶ ወዲያው የሞቀ ወሬ ውስጥ ገቡ። ከፊታቸው የተከመረውን መጽሃፍ ወደ ራሱ ጠጋ አድርጎ እገላብጦ አየውና

"ከየት አገኘሀው ይሄን መጽሃፍ ልጂ ...ሁለቱም ቮልዩም አንድ ላይ ነው የተጠረዘው?" አለ ተገርሞ።

"ኧ ... ሁለቱም ቅጽ በአንድ ላይ ነው ... ሦስተኛ እመት ሬዚደንሲ ስንጀምር ክሳርሃርድ ለአንድ ወር ልታሰቡበት የሚገባቸው አንድ አጀንዳ ላይኪያትሪስት ነበረች።

@OLDBOOKSPDF

ብዙ ጊዜ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እናወራ ነበር። ከመሄዱ በፊት 'ይሄንን መጽሐፍ ቢያገስ አንድ ጊዜ ከጫፍ እስከጫፍ ማንበብ ይኖርብሃል። ከመቶ አመት በፊት ስለ ተጻፈ ያለፈበት እንዳይመስልህ ... ፍልስፍናን ሳይኮሎጂንና ሕክምናን ከሰው አእምሮ አሰራር ጋር ግልጽና አስገራሚ በሆነ መንገድ የሚተነትንና በትክክል እንድታስብ የሚረዳ ብዙ የዚህ ዓይነት መጻሕፍት የሉም' ብላ ሰጠችኝ። ዛሬ ነገ ስል ሳልጀምረው ቀየሁ። አሁን ሶስት ሳምንት ሆነኝ ከጀመርኩት ... በጣም የሚገርም ነው ... እንዳለችውም በፍጹም የድሮ መጽሃፍ አይመስልም"

ሌላው አመጽሃፉን እያየ፣ "ትንሽ ቀየ እንጂ የተወሰነውን ክፍል አንብቤው ነበር ... የሚገርም ጭንቅላት ያለው ሰው ነው። ወንድሙ ሄንርይ እና እህቱ ... ማናት አሊስ ነው መሰለኝ ስሟ ... ባሜሪካ ፍልስፍናና ሥነጽሁፍ ላይ ትልቅ አሻራ ትተው ያለፉ ሰዎች ናቸው። ይሄ መጽሃፍ አሁን ብዙም ገበያ ላይ ያለ አልመሰለኝምና እዚህ ሳየው እኮ ገርሞኝ ነው" አለ፣ ማውጫውን በፍጥነት እየቃኘ።

"እኔንም እንዳነበው የበለጠ የገፋፋኝ ባለፈው 'ፖርትሬይት ኦፍ ኤ ሌዲ' የሚለውን የወንድሙን የሄንሪ ጄምስን መጽሃፍ ካነበብኩት በኋላ ነው"

"ኦህ እንብበሀዋል አሱንም? ... በጣም ከምወዳቸው ልቦለድ መጻሕፍት ውስጥ አንዱ አሱ ነው። አይ ቲንክ ... ዊሊያምም ሌላ ብዙ ጽፏል መሰለኝ ... ግን ሌሎች ስራዎቹን ብዙም ጊዜ አግኝቼ አላነበብኩትም። ፕራግማቲዝምና ፋንክሽናል ሳይኮሎጂን ከፈለሰፉ የመጀመሪያ ሰዎች ዋናው እሱ ነው" አለ፣ መጽሃፉን መልሶ ወደ ሲራክ እየገፋ።

"ታውቃለህ ...እኔ ይሄ ፕራግማቲዝም ... ኢምፔሪሲዝም ... ስትራክቸራሊዝም ... ፋንክሽናሊዝም ... ሮማንቲሲዝም ... እቦ ስንት ኢዝም እንዳለ ራሱ ግራ ይገባኛል። ነገሩን ገባ ብለህ ስታነበው እኮ እንደዚህ ፋንሲ የሆነ ስም ባይሰጡት፣ ሁላችንም የምናስበውና የምንኖረው ዕለታዊ የኑሮ ፍልስፍና ነው። እነሱ አይ ቲንክ ... ወራ እያጋነኑ መሸጥ ይወዳሉም፣ ይችላሉም። ... እኛ ደግሞ ማራገብ ብቻ። አሁን አሁን እያሰብኩ ያለሁት ትንሽ ከተረጋጋሁ በኋላ... ለክቶም ለደጉም ቢያንስ በማስተርስ ዶሪኛ ፍልስፍና መግር እንዳለብኝ ነው። አለበለዚያ የሆነ ነገር የጉደለኝ እየመሰለኝ ሚንትላቴን ሲጠዘጥዘኝ ነው የሚኖረው።" ሳቅ ብሎ ያልበላውን ራሱን እከክ እከክ አድርጉ፣ ጉፈሬ ጸጉሩን እንደገና አስተካከለ።

"ዩ ኖው ዋት ... እንዱ እኔ እንዱ እኔ ... ሁሉም ሳይኮሎጂስትና ሳይኪያትሪስት ቢያንስ መሰረታዊ የሆነ የፍልስፍና እውቀትና ትምህርት ያስፈልገዋል። በትክክል የማሰብ አቅምና ችሎታ ሳይኖርህ አስተሳሰባቸውና ማሰቢያቸው የታመመባቸውን ሰዎች ማከም የሚቻል አይመስለኝም። ... ሌላው ተርቶ ኢቭን ... ስለ መድሃኒትም ቢሆን እኮ ግልጽ የሆነ ፍልስፍና ያስፈልገሃል" ብሎ፣ ስልኩ ላይ የመጣውን የጽሁፍ መልእክት ሲያየው ምስጢር መንገድ ተዘጋግተባቸው እንዳረፈዱች የላከችው ነው።

"ቀይ ቀይ እንዲየውም ... ዶክተር ሌላ ... ጠዋት በጣም አስቸጋሪ ኪዝ አጋጥሞኝ ነበር። ብዙ ሰአት አብሬው ባጠፋም ... አይ ዶኖ ... ምን ብዬ ልረዳው

@OLDBOOOKSPDF

እንደምችል እርግጠኛ አልነበርኩም ... ዝም ብዬ ካንተ ጋር ካወራሁ በኋላ እንደገና ላየው ቀጥሬዋለሁ" አለ ፊቱን ጽጠር ፈታ እያደረገ ።

ሲራክና ሌላሠው በህመምተኛው ጉዳይ ላይ ሲያወሩ ሌሎቹም እየተንጠባጠቡ ደረሱ ። ምሽቱ ቀለል ያለና ጨዋታ የበዛበት ነበረ ። ለሌላሠው መልካም ጉዞ ተመኝተውለት ወደ ሦስት ተኩል ላይ ተለያዩ ።

ሕይወት ... መሄድ መምጣት ... መገናኘት መለያየት ... ማብሰል መብላት ... መታከም መዳን ... መወለድ መሞት ...ምልልሶሽ ናት ። በውስጧ ደግሞ ፍቅር ጓደኝነት ... ትናንት ነገ ... ሀልም ትዝታ ... ድካም እረፍት ... ምኞት ሽሽት ... ቁጥር የለሽ ልምምዶችን ይዛለች ። ሌላሠውም በማግስቱ ወደ አሜሪካ ተጓዘ ።

@OLDBOOOKSPDF

ክፍል ፫

ሌላ ሰው

@OLDBOOOKSPDF

• 30 •

ሌላው አሜሪካ ከገባ በኋላ የመጀመሪያውን ሳምንት ከቤት አልወጣም። ባረፈ ቁጥር ምን ያህል እንደ ደከመው ተረዳ። ልጆቹ ተመልሶ የሚሄድ እየመሰላቸው ከርሱ ጋር ተጣብቀዋል። ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ እንኳ በብዙ ልመናና ማባበል ነው። ንጹሕ ምን ያህል ሰውነቷ እንደተጐዳና ተለያይተው መቆየታቸው ያሳደረባትን ጫና ሲረዳ ጥልቅ ጸጸት ተሰማው። ፍልቅልቁና ደስተኛ ማንነቷ ጠፍቶ በቀላሉ የምትነጫነጭ ቶሎ ሆድ የሚብሳት ሆናለች። ቤተሰቡን እዚህ ውጥረት ውስጥ በመክተቱ፣ የጥፋተኝነት ስሜት ሲያሰቃየው ከረመ።

ጠዋት ላይ ልጆቹን ትምህርት ቤት አድርሰው ቡናቸውን ይዘው ሲያወሩ ይውላሉ። ወይ ደግሞ ወደ አልጋቸው ተመልሰው፣ በመካከላቸው የተፈጠረውን ገደል ለመሙላትና ናፍቆታቸውን ለመወጣት ይሞክራሉ። እዛው ኩሽና ውስጥ የሆነ ነገር ይሠሩና ምላ እየበሉ ሲያወሩ፣ ሳያውቁት የልጆቹ መምጫ ሰዓት ይደርሳል። እነርሱን እያጫወቱ ወይ ፓርክ ወይ ደግሞ መዋኛ ስፍራ ሄደው ያመሻሉ። በዚህ ሁኔታ ያሳለፉት ሁለት ሳምንት፣ ስሁሉም ውስጣቸው የተፈጠረውን የመራራቅ ሕመም አስታግሶላቸዋል።

ኦሰቲን ቲክሳስ በዚህ ወቅት ሞቅ ብትልም፣ ሁሉ ነገር አረንጓዴ ነው። ቀኑ ረጅም ስለሆነ፣ ሰው ሁሉ ደጅ ነው የሚያመሸው። ማለዳ ገና ስማቡ ፈገግ ሲል ተነስቶ ብስክሌቱን ይጋልባል። ከሰፈሩ ወጣ ብሎ ያለውን ጫካ እያቀራረጠ፣ ረዘም ላለ ሰዓት የጠዋቱን ለስለስ ያለ አየር እያጣጣመ፣ ጠዋት እንድ ሰዓት ከመሆኑ በፊት ወደ ቤት ይመለሳል። የአሜሪካ ሕይወቱን ከሚወድባቸው ነገሮች መካከል እንዱ ያለ ችግር ብስክሌት የሚያሳጋልቡ በከተማና በጫካ ውስጥ የተሰሩት የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ናቸው። ኢትዮጵያ የመመለሱ ነገር አሳስቦታል። ኑሮው በዚህ ከቀጠለ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሚስቱና ልጆቹን በቀላሉ ሊያጣ እንደሚችል አሰበ። ተስምቶት የማያውቅ ፍርሃት አጥንቱ ውስጥ ገባ።

@OLDBOOOKSPDF

ሃስተኛውን ሳምንት ወደ ካሊፎርኒያ ለመንዳት አትደዋል። ከዚያ በኋላ ባለው ሳምንት የንጹህ ቤተሰቦች ወደ ሚኖሩበት ሚኒያፖሊስ ስለሚሄዱ፣ እረፍቱ ላይ አንድ ሳምንት ለመጪመር ወስኗል። የልጆቹም ትምህርት ቤት ሲዘጋ፣ ንጹሕ አዘዘኛውን ጊዜ ሚኒያፖሊስ ለማሳለፍ አስባለች። ኢትዮጵያ አብረውት ሄደው እንዲቆዩ ቢለምናትም እሻፈረኝ አለች። ድንገት የማይሰማሙበት ሃሳብ በተነሳ ቁጥር የሚፈጠረውን ግሩትና ሜትሜቅ መፍራት ጀምሯል። በሚሆኑት አንዳንድ ነገሮች ውስው ቢያዝንበትም፣ የጥፋተኝነት ስሜቱ እያየለበት ብዙውን ነገር አይቶ እንዳላየ ማለቱን መረጠ።

ወደ ካሊፎርኒያ ከመሄዳቸው ሁለት ቀን በፊት ጓደኞቻቸውን ራት ጋብዘው ቤቱ ድምቅምት ብሎ አመሸ። ከስድስት ወር በፊት ሚስቱ በአደጋ ከሁለት ልጆቹ ጋር የሞተችበት ጓደኛቸውም የተረፈችውን እንዲት ልጁን ይዞ መጥቷል። ልጅቷ በእርዷማ እድሜ ስለሆነችና ንጹሕ እሷንም ሙዚቃ ስለምታስተምራት ቤተኛ ናቸው። ሌላሠው አሜሪካ በነበረ ጊዜ ደግሞ አብረው ብስክሌት መጋለብ፣ ገልፍ መዟወትና ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ራት ያሰ ቦታ ነድተው መዝናናት ያዘወትሩ ነበር።

ከሐዘኑ ከብደት የተነሳ በጣም ተገድቶ ስለነበር የንጹሕ ድጋፍ በብዙ ጠቅሞታል። ንጹሕም ብቻዋን ልጆቹንና ሥራዋን ማለኪድ ሲያቅታት የሚያግዛት እሱ ነው። እንግዶቹ ከሄዱ በኋላ ወደ ጎላ ቀርቶ ሲሄጠቱና ስለ ሌላሠው ሥራ እየጠየቀው ሲያወሩ አመሹ። ልጁ ከነርሱ ጋር ወደ ካሊፎርኒያ እንድትሄድ ስለፈቀደላት ልጆቹ ረንድቀዋል። ከሚስቱና ልጆቹ ሞት በኋላ ልጁን እምኖ ለሰው ሲሰጥ የመጀመሪያው ነው።

በማግስቱ በጠዋት ተንሥተው ሲንዱ ሙለው አመሻሹ ላይ በኒው ሜክሲኮ ግዛት ከምትገኘው አልባከርኪ ከተማ ገቡ። ደክሚቸው ስለነበር ክአራት በኋላ ሁሉም በጊዜ ተኙ። በጠዋት ተነስተው የሚክሲኮ ባህልን በሚያሳየው የከተማይቱ አሮጌው ክፍል ውስጥ በእግራቸው ወዲያ ወዲህ እያሉ ሲገበኙ ቀይተው፣ ለቁርስ ወደ እንድ ባህላዊ ቤት ገቡ። ማርፈጃውን በከተማው መሃል ሲቢቢሩ ቀዩ። ለልጆቹ የፈለጉትን አንዳንድ መጫወቻዎች ገዝተው፣ ቡናቸውን ይዘው ጉዞ ቀጠለ።

"አባቢ ... አባከርኪን አሎደውም ... አሁንስ የት ነው ምንሄደው?" አለች፣ ስትጫነጭ የቀየችው አርሲማ።

"ለምን የኔ ቀንጆ ..." አላት በመስታዋቱ ውስጥ ሊያያት እየሞከረ።

"በታ ምንም የልጅ መጫወቻ ኮ የለም ... ዲዝኒ አይደል እንሄዳለን ያልከው እንዴ ... ዲዝኒ ኮ ብዙ መጫወቻ አለው ..."

"ዲዝኒማ ገና አልደረስንም ... ወደዛ እየሄድን ነው ...ዲዝኒ ሩቅ ቦታ ነው ያለው ... አንቺ በመኪና መሄድ ትወጂ የለ?"

"ታዲያ ቀኑን በሞላ ነው እንዴ ... እንትልፈን አመጣብኝ እኮ ... ዛሬም ማታ ነው ዲዝኒ የምንሄደው እንጂ ሁሉ አልቀረም ቆይኪ ሰዎች።

"እይ በቀን ነው የምንደርስው። አልንገርኩሽም እንኳን ግራንድ ካንየን ያለበት ቦታ ... ብዙ ሜዳና አውራዎች ሁሉ አሉ ..." አለ፣ ሜዮር ባለው መንገድ ላይ ፍጥነቱን ጨምሮ እየነዳ። ሉሎቹ ልጆች ደክሟቸው ስለነበር ብዙም ሳይቀዩ በእንቅልፍ ተሸነፉ።

"ቀይ ... ታዲያ ዲዝኒስ መቼ ነው የምንሄደው? ... ምንድነው ጋንድ ካኒን ግንቦ ብላ፣ በጆሯ የያዘችውን አሻንጉሊት ጥላ ፊቷን ማሻሸት ጀመረች።

"ዲዝኒ ነገ እንደርሳለን ... ግራንድ ካኒየንማ ... አላሳየሁሽም ኮምፒዩተር ላይ ... ያ ትልቁ ገደል ነዋ ... በጣም የሚያምረው ..."

"እንዲዬ አባቢ ደግሞ ገደል ምን ያደርግልናል ... እሱ ኮ ያስፈራራኛል ... ውድቅ ብልስ ... ሩቁ ውስጥ ግብት አልልም እንዴ?"

" አይ መሄጃ መንገድ አለው ... ደግሞ እታች ገደሉ ውስጥም ይገባል ... እዛም የሚኖሩ ሰዎች አሉ" ብሎ፣ ወደ ንጹህ ሲያይ፣ ከአሀቷ ጋር የያዘችውን ስልክ አውጥ ተጥላለች።

"ታዲያ እኛም ገደሉ ውስጥ እንገባበታለን እንዴ? ... እንዴት ነው የሚገቡት ዝልል ብለው ነው?" አለች፣ የበለጠ ግራ እየገባትና ስጋት ባዘለ ፊት።

"አይ መንገድ አለ ... በአገር ተሄዶ ወይ ደግሞ በፈረስ ይገባል። ከፈለግንም በአውሮፕላን በርረን መግባት እንችላለን።"

"በናትህ ባቢ ... ባውሎፒላን አድርገን ውስጡ እንግባበት እኛም ..." አለችና እየተቅበጠበጠች "ማሚ ...ማሚ ... ሽንቴ መጣብኝ ... ማሚ ..." ብላ ጮኸች።

ንጹሕ ዞር ብላ የያዘችውን ስልክ ከጆሮዋ ላይ ፈቀቅ አድርጋ፣ "እር-ሲ ... ቅድም የለም አላልሽም ነበር ... ቀይ ነዳጅ ማደያ እካባቢ እንድረስ ... ቀይ እንዲያውም እዛ ጋ አለ ... ደርሰናል እሺ ... ላይሽ ላይ እንዳትሸኚ ዋ ..."

ሉላሠውም ቀበል አድርጎ፣ "እርሲ ትልቅ ልጅ አይደለሽ? ... በቃ ደርሰናል እሺ የኔ ገበዝ ልጅ ..." አለ፣ ዞር ብሎ እያያት። ራሲን እነቃንቃ ጉበዝ ልጅ መሆኗን አረጋገጠችለት።

ግራንድ ካንዬን ሲደርሱ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ሆኖ ነበር። ሆቴል ይዘው፣ ተጣጥበው ምሳቸውን ከበሉ በኋላ ከልጆቹ ጋር በሜካው ውስጥ እየተጫወቱ ሲሣቁ ቀዩ። ልጆቹን አስተኝተው፣ ጥላ በረድ ብሎ የፀሐይ መጥለቂያ እስኪደርስ እነርሱም ጋደም አሉ። በኮሎራዶና በአሪዞና መካከል ያለው ግራንድ ካንየን እንደ ስሙ ግርማ የተጐናጸፈ፣ ሰፋት፣ ርዝመቱና ጥልቀቱ ግዙፍ የሆነ ገደል ነው።

ሣሩ እስከ ሣሩ ለማየት አይቻልም ... እስከ አምስት መቶ ዚሉ ሜትር የሚደርሰው ርዝመቱ ... በውስጡ የሚያልፉት ታላላት ወንዞችንና ለረጅም ዘመን ቀደምት አሜሪካውያን ሲኖሩበት የነበረን ሰፋፊ ሚዳ የያዘ ገደልና ሸለቆ ነው። በተለይ በፀሐይ መጥለቂያና መውጪያ ሰዓት ላይ፣ በገደሉ ውስጥና በዙሪያው የሚፈጠረው ውበት ምትሃት ይመስላል። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ከጥቂት የኅለማችን ተፈጥሯዊ ድንቃድንቆች መደዳ የተመዘገበው።

@OLDBOOOKSPDF

ሶስቱ በመኖራቸው ሲሞላ ገዛም የምትለው ነገሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለነበር ያመጣችሙ በመብቱ ተገርማ የምትለው ጠፍቷታል። ልጆቹን እጆቻቸውን ይዘው ወደ ውጭ ወደህ ሊሉ በየመሙለከቻ ጣቢያምቹ እየቀሙ ከውስጥ እሰከ ባሻገር ሬሚስቱና ሊያደንቁ ቀደ። የልጆቹን ጥያቄዎች መመለስ ... መሄድ ሲያትታቸው ሚያቶ ... ቢያደክማቸውም የተሰማቸውን ደስታ ግን አልተነሰባቸውም።

"ሌላ ... ለብቻችን እንደገና መምጣት አለብን ... ታች ሁሉ መውረድ እፈልጋለው ... በኮሎራዶ በኩልም ይጉበኛል እንዴ?" አለች፣ ትከሻው ላይ ደገፍ ብላ"

"ብጣም ያምራል በዛም በኩል ... በክረምት በረዶ ስላለው የተለየ ውበት አለው። ደና የምትባል በጣም የምትገርም ትንሽና እጅግ ውብ የጥበብ ከተማ አለች። ሁለት ሰዓት ብቻ ነው ከዚህ። ከቻልን እስኪ በዛው እናልፋለን። በሚተጥለው ስመጣ ፕሬ ቲንከ ሰፊ ጊዜ መስደን መምጣት ይኖርብናል" አለ። "በሚተጥለው ስመጣ" የሚለው ነገር ተመልሶ የመሄዱን ነገር አስታውሷት ውስጧን ከፍት አለው።

"ምነው ደበረሽ እንዴ ... ፊትሽ እዝን አለ ..."

"አይ እንዲያው የሆነ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው ... ገዛም ብሎ ነገር ..." ብላ፣ ሌላ ፊደ ጨማምራ አረሳሳችው። ሁለቱም በመካከላቸው የተፈጠረው ገደል እየሰፋ እንደለ በደምሳሳው ቢሰማቸውም፣ ቃል ፈጥረው ለትና ስም ሰጥተው ሊያወሩት አልቻሉም። የገራንድ ካኒየኑ ገደለስ መች ባንድ ቀን እንዲህ ሰፍቶ ሁለት ግዛቶችን ግዙ ለማደ ከፈለ። ሁለቱም ይህ ድንት ገደል እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ መላ ምት ቦሰጠትና በመገረም ተመላለቱ። ማታ ላይ "አይ ማክስ" በተባለው በግዙፍ የምስል ሰዴ ላይ የሚታይ ጥናታዊ ፊልም አዩ። ፊልሙ ገደሉ የረጅም ጊዜ የተለያዩ ቴፈኖሮአዊ ኃይላትና ከስተ-ቶች ፍርርቅ ውጤት መሆኑን ይተርካል።

በሚተጥለው ቀን የአሪዞናንና የምእራብ ካሊፎርኒያን በረሃ አቋርጠው ሎስ አንጀለስ ሲገቡ ሌላ ሀገር የገቡ ያህል ተሰማቸው። ለሁለት ቀናት ልጆቹን ደፎ በዲዝኒና በሆሊውድ ሲዞሩና ሲያዝናኗቸው ከረሙ። ከመመለሳቸው በፊት የመጨረሻውን ቀን ሳንዲያጎ ታላት እህቱ ጋ አሳለፉ። ትልቁን የአራዊት መናኸሪያ ... የባሩን ውብ ጻርቻ ... የሚያምረውን መሀል ከተማ ... የባህር እንሰሳትን የሚያሳየውን ዎርልድ ሲጎበኙ ከረሙ። እህቱና ባሏ ልጆቻቸው ሁሉ አድገው ከቤት ስለወጡ የሚናሩት ለብቻቸው ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ሳምንት ሲቀረው ወደ ሚኒያፖሊስ ሄዱ። እርሷማና ዝየ የሚያሳድጓቸው የዝናሽ ልጆች ናፉም ተቀያረዋል። ትልቁ ሳምሶን ጎደናቆርና ከመተኛ ሆኗል። ታናሹ ሰምረት ደግሞ እንደሁል ጊዜዋ ተጫዋች ደማትና ትብጥብጥ ነት። ትንሿም ደግሞ በእግሯ ድክ ድክ ማለትና ሰው ላይ ልጥፍ ብላ መጫወት የምትወድ ተንጅዬ ልጅ ሆናለች። ከንጹሕ ልጆች ጋር ሲቀላቀሉ መያገ መቀሚያ ጠፍቷቸው ነረ። ንጹሕ በሚሲሲፒ ወንዝ አካያ ባሉ የእግረኛ መንገዶች ላይ እየተመላለሰች፣ ከርች ስር ባሉ የድንጋይ መቀመጫ ወንበሮች ላይ እየተቀመጠች።

ጠዋት ላይ በኩሽናው በኩል ያለውን ሰፊ በር ከፍተው ከበረንዳው ላይ የቁርስ ጠረጴዛውን ዘረጉ። ቁርስ እየበሉ የድሮ ወሬ ተነስቶ ሲሳሳቁ አረፋፈዱ። "ለምንልጆቹን እነማሚ ጋ ትተናቸው ማታ ላይ ለራት እንወጣም?" አለች አርሴማ። የሴላሙ ልደት አንድ ቀን ቢቀረውም ቀደም አድርገው ሊያከብሩለት ከንዋያና ከንጹሕ ጋር መነጋገራቸው እንዳይነታባቸው ነው ድንገት ያሰበችው ሐሳብ ያስመሰለችው።

"ልጆቹስ ከኛ ጋር ቢሄዱ?" ሲል ንዋያ፣

"ውይ ናቺዬ ... እነሱን እናገዳለን ወይስ እኛ ልናወራ ነው? ... እነሱም ሳይጫነቁ ይጫወቱ ... እነማሚም ቢሆኑ ስንቱ ያገኙዋቸዋል እንዲህ አንድላይ ..." አለች፣ ኮስተር ብላ። አርሴማ ሥራዋን የተወሰነ ሰዓት ከቤት እየሠራች፣ ሙሉ ጊዜዋን ከልጆቿ ጋር ነው የምታሳልፈው። የእናትነት ርካታዋና ደስታዋ ሁለንተናዋን ቀይሮታል። በተለይ ከሰምሪት ጋር ያላት ግንኙነት ለየት ያለ ነው። ሳምሶን ደግሞ አንጀቷን ስለሚበላው ከሁሉም ልቧ ይንሰፈሰፍለታል። ትንሿ ግን ያባቷ ልጅ ሆናለች።

"እሾን ... ውይ ኔዊዬ ... ትንሽ አረፍ ብንል ጥሩ አይመስልህም?" አለች፣ ንጹሕም እህቷን ደግፋ።

"ጥሩ ... ታዲያ ምን ይበላ ... ሴላ ያማረህ ነገር አለ ... ስቲክ ...ሱሺ ...ታይ" አለ፣ ንዋያ የሴላሙን ትከሻ እንደ ኮሌጅ ዘመናቸው እየነቀነቀና እየሣቀ።

"ምን ይሻላ...ል ... እምም ... ያማረህ ካለከኝ ... የሙሪያ ስቲክ ነው ባይኔ ላይ የሚሄደው ... እዲሳባ እኮ ቁርጥና ከትር እንጂ የሪባ ስቲክ አታገኝም። እኔ ምረየ ከተባልኩ ስቲክ ... ነው" ሲል፣ ሁሉም በርሱ ምርጫ ተስማሙ። ጠዋቱን ልጆቹን ሞል አሜሪካ መስደው እስኪደክማቸው ሲያሣሡቷቸው ውለው፣ ወደ ከሰዓት በኋላው ማለቂያ ላይ አያቶቻቸው ቤት መስደው ላኳቸው። ለሰስ ያለ ነፋሻ ቀን ስለነበር ወዲያ ወዲህ እያሉ እግራቸውን እያፍታቱ ቀዩ። አርሴማ ከሴላሙ፣ ንጹሕ ደግሞ ከንዋያ ጋር እያወሩ ረዘም ላለ ጊዜ በወንዙ ዳርቻ በቀስታ ተዛዙ።

ወደ አመሻሹ ላይ ወደ ምግብ ቤቱ ደረሱ። ሁሉም እንደ ምርጫው የተለያየ አይነት ስቲክ አዘዙ። በመሃል አርሴማ መታጠቢያ ቤት ደርሼ መጣሁ ብላ ወደ ውስጥ ሄደች። ከራት በኋላ ለሴላሙ የልደት መልካም ምኞት መግለጫ ኬክ እንዲያመጡለት አዝዛ ተመለሰች። እራታቸውን እየበሉ ወሬው ወደ ሴላሙና ንጹሕ ሥረ ንዋያ ትንሽ አመንታና ሲከነክነው የነበረውን ጥያቄ ጠየቀ።

"ቀይ እኔ የምለው ... ይሄ ካትላንቲክ ማሩ ለማሩ ... የሁለት ዓለም ... ተለያይቶ ኦሮ እስከመቼ ነው? ማለቴ ... ሴላ እንደዚሁ ልትመላለስ ነው ወይስ ... ምንድነው በላቂው ዕቅድ?"

የሁሉም ዓይን ወደ እርሱ መሆኑን አወቀ፣ "ለጊዜው ይሄ ነው ማለት የሚቻል ግልጽ ዕቅድ የለም ... ነገሮች ገና መልክ መያዝ መጀመራቸው ነው ... ማለቴ ከሊኒኩ ተያይዞ ያለው አገልግሎት እስኪጠናከር ..." ብሎ፣ ትከሻውን ንትንቶ ገሸ አለ።

"ግንኮ ልጆቹም ቢሆኑ፣ ካንቲ አላውቅምና፣ አሁን ባሉበት ደረጃ

@OLDBOOOKSPDF

ዕለታችሁንም የሚፈልጉ ይመስለኛል ። መሰናችሁ አንዱ ጋ አብራችሁ ካልሠናችሁ፣ ሩጉ እጅ እየሠሩ በሌላ እጅ ማፍረስ ሊሆን ይችላል ። ሁለታችሁም ብትሆኑ በጣም እየተጸናችሁ ይመስለኛል" አለች ፣ የቀረጠችውን ሰጋ ከተፈጨ ድንችና ዙሪጭ አስፓራገስ ጋር አድርጋ ለእህቷ እያቀረበች ።

"እኔ እንደሆነ እዛ ሀገር ኑሮ አይታየኝም ... ከሁለት ሳምንት በላይ መቀመጥ አልችልም ... ብሄድም ምንም የምሰራው ያለ አይመስለኝም ... ልጆቹም ቢሆን እዛ ሊያድጉ ማየት ይከብደኛል ..." አለች ፣ "ነጹሕ ደጋግማ ለሌላሙ የነገረችውን ነገር እያጸናች ።

"ሌላ ... ምን ያህል ጊዜ የሚወስድ ይመስልሃል ... ሥራው መልክ ይዞ ቢያንስ ያተገብሙ እዛ መሆን ወደ ማይፈልግበት ደረጃ ለመድረስ?" አለች ፣ አርሴማ ሊታርቅ የማይችለውን የሁለቱን ፍላጎት የምታቀራርብበት መንገድ ግራ እየገባት ።

"እንስትሲ ... አርሲዬ ... አላውቅም ። ሀገሩ ልትገምቺው ከምትችይው በላይ ተለየዋቲና ርግጠኝነት ሊሰጥሽ የማይችል ቦታ ነው ። ሰጪ ደግሞ እንደኔ ያሳዘናል መሰለሽ ... እንግዲህ እስኪ አሁን ተመልሼ ሄጄ ... ለሦስት ወር ሁኔታውን አይቼ ... ካልሆነ ጥሎ መምጣት ነዋ ..." አለ ፣ አቅመቢስነቱን ለመግለጥ ይመስል ፣ ሹካና ቢላ የያዘባቸውን እጆቹን ዘርፍ አድርጎ ። ሦስት ወር የሚለው ቃል በንጹሕ ውስጥ እንዳች ቱግንና የማታውቀውን የልብ መራቅ ሲፈጥርባት ታመታት ። ምንም መልስ መስጠት አልፈለገችም ። ው-ይይቱ እንደ ተድበሰበሰ አለቀና ወደ ሌላ ተሰል ያለ ወሬ ተሰወጠ ። ልዩቱ ተከብሮለት ው-ስጣቸው እንደከበደው ፣ ልጆቹን ይዘው ወደ ቤት ተመለሱ ።

ከዚያ በኋላ ፣ ከላይ ከላይ እያወሩ ቀይተው የመሄጃው ቀን ደረሰ ። በሁለቱም ልብ ውስጥ ትልቅ ቁጣና ቅያሜ አድሮ ነበር ። ከርሱ ይልቅ አሜሪካንና የግል ምኞቷን የምትወድ ራስ ወዳድ ሆና ስለታየችው ለርሷ የነበረው ከፍ ያለ ቦታና ፍቅር ተሸረሸረበት ። ከቤተሰቡና ከርሷ ይልቅ ለአባቱ አደራና የልጅነት ፍቅረኛውን ፈልጎ ግኝት በልጦበት ፣ በማይጠቅምና ምንም ፋይዳ በሌለው ከለኒክ ሰም የራሱን ፍላጎት ለመፈጸም የሚንከላወስ ራስ ወዳድ ሆኖ ታያት ። ለርሱ የነበራት ያማይነታንት ፍቅር መናድ ጀመረ ።

በመካከላቸው የወደቀው ያለመግባባት ጥላ አንጻቸውን በሌላቸው ዕድታ ሌላ ሌሎ አለመሰሉ ቀረጻቸው ። ይህም ለልባቸው የመሸፈትና የመሻከር ጉዞ እንዲጀምር ር ከፈተለት ። በሻከረ የስሚት ብሩሽቸው በሳሉት ሌላ ሰው እና በእውነተኛ ግኝታቸው መካከል የተፈጠረው ልዩነት ሊያስታርቁት ከሚችሉት በላይ እየሆነ መጣ ። ይህም የነበትን ጠንካራ የፍቅር አለት ሰንጣጥቆ ፣ በመካከላቸው ታላት የሰሚት ገደል መፍጠር ጀመረ ።

@OLDBOOOKSPDF

31

ሌላው ከአሜሪካ እስኪመለስ ድረስ የርሱን ቢሮ እንዲጠቀምበት ቁልፉን ለሲራክ ሰጥቶታል። እሱ ከሄደ ጆምሮ ሲራክ የራሱን ቢሮ ተጠቅሞ አያውቅም። ወደ ፊት የሌላው ዓይነት ቢሮ ሊኖረው እንደሚገባ መሰኛል። በጠዋት ገብቶ ቡናውን ያፈላል። ከመጻሕፍት መደርደሪያው አጠገብ ካለው ተወዛዋዥ ወንበር ላይ ይቀመጥና ከጠዋቷ ፀሐይ ጋር ትኩስ ቡናውን እያጣጠመ ያነባል።

በሰፈው ክፍል ውስጥ በተሰየሙት ምቹ ወንበሮች ላይ ሆኖ ሀመምተኞችን ማየቱ፣ ክርሱ ጠበብ ያለች ቢሮ ይልቅ ፈጠስ እንደሚያፈጥን አመነ። በአራቱም መስኮቶች ያለው ዕይታና ወደ ክፍሉ የሚገባው የብርሃን ስብጥር ራሱ የማከም ኃይል እንደሚኖረው አልተጠራጠረም። ማታ ከስራ በኋላ ደግሞ ችሎታው ባይኖረውም ከጥቂት ጊያኖ ፊት ተሰይሞ ለማንም የማያገባ ሙዚቃ ይቀራቱራል። ጊያኖ መማርን ዋነኛ እቅዱ አድርጎ ይዟል።

ትዳሚ ከሰዓት በኋላ የሚያየው ሀመምተኛ ባይኖረውም ገብቶ ለማንበብና ለጸጥታው ብሎ ወደ ቢሮ ሄደ። ሚሩግግ ያለ ተን ስለነበረ ደጁ ብዙም አይስብም። ሲደርስ ግቢው የተመረረ ይመስል ሬሞ ብሏል። ያኮረፈውን ሰማይ እንደ ቀብ ደፍተው በስፍራቸው በጸጥታ የቀመጡት ዛርች የፈጠሩት አሳዛኝ ድባብ ተቀበለው።

ቢሮ ገብቶ እጁን ለማሞቅ እያሻሸ የኤሌክትሪክ ማሞቂያውን ሰካና ወደ መንበሩ ጠጋ አድርጎ አስቀመጠው። ሁሉንም መብራቶች ሲያበራራቸው ቤቱ በብርሃን ሲሞላ፣ ውስጡም ፈክ ያለ መሰለው። ከውሃ ማጣሪያው የፈላ ውሃ ቀዳና የአረንጓዴ ሻይ ከረጢት ጨምሮ፣ ፊቱን ወደ መስኮቱ አዙሮ ፉት እያለ በራሱ ሃሳብ ወዲያ ወዲህ ሲል ቀየ።

ሌላው ከሄደ ብዙ ባይቀይም ጥቂት ከማይባሉ ሰዎች ጋር ያጋጠመው ግጭት ረብሾታል። ሁልጊዜም ለሌላው በደስታ የሚታዘዙት የክሊኒኩ ሰራተኞች ያደሙበት መስሎ ተሰማው። በተለይ ላንቾና ምስጢር የሚያሾፉበት ስለሚመስለው ውስጡ አቂሞባቸዋል። ምስጢር ሚስጥር መሆኑን ሳንቾ ነው ብሎ አምኗል።

@OLDBOOKSPDF

ለእርሱ ብቸኛ አጋዥና በስኬቱ የምትደሰት መጻጅ ሲስተር ዘቢባ መሆኗን ያምንማል። እኔ ሉላሠው መሆን አለብኝ እንዴ? እሱ ሉላ ... እኔ ሉላ ... ለሁሉም ያሄ ጥሩ አጋጣሚ ነው። የሁላችንም ማንነት የሚፈተሽበት ጊዜ አሁን ነው፡ አለ ለራሱ። ከመቀመጫው ተነስቶ ከመደርደሪያው ላይ ያለትን መጻሕፍት ባይኑ ከላይ ታች ቃኘ። ምናልባትም በንድ ሥራቱኛ ላይ ጠበት ያለ አርምጃ ብወስድ ማንነቱን ሊያወቁ ይችላሉ ... ያሄ ባጃጅ ራስ ሁሉ' ብሎ ተመልሶ ተቀመጠ።

ኪሱ ውስጥ ያለው ስልክ ሲጮህ እያመነታ አወጣጥ እየውና በፍጥነት "ሄይ ... የጠፋች ወፍ ... እንዴት በትዳሜው ተገኘሽ?" አለ፣ የድብርት ስሜቱ ባንዴ ብርሃን እንደበራበት ጨለማ ብን ብሎ እየጠፋ።

"ትንሹ ዶክተር ... አንተን ልጠይትህ እንጂ ... ያንተን ኩራት የሚያድን መድሃኒት ይጥፋ ... በቃ እኔ ካልደወልኩ ትዝም አልልህ አይደል?" አለች፣ ሉሲ በሚያምር ድምጿ ኩርፊያዋን ለመግለጽ እየሞከረች። ከጅርባዋ ብዙ ሚሌታ ስላለ በግድ ነው የሚሰማት።

"የት ሆነሽ ነው ... በመከራ ነው እየሰማሁሽ ያለሁት ... ደህና ነሽ?" አለ፣ ላያስበው ጮክ ብሎ።

"ደህና ደህና ... እዚህ ኤድና ሞል ... ሙቪ ልንገባ እየጠበቅን ነው። የት ነህ አንተ?"

"ቢሮ ... ትንሽ የምሠራቸው የወረቀት ሥራዎች አሉኝ።"

"በትዳሜ ምድር ተረኛ ነህ ወይስ ... ትጉህ ሰራተኛ ለመባል ነው? ... የምር ግን አትገኝም እንዴ?"

"ማታ ትችያለሽ?"

"ስንት ሰዓት?"

"አንድ ... ሁለት? ... ያለሽበት ልመጣ እችላለሁ"

"እንደዋወል ወይስ አሁኑኑ ቦታ እንቀጣጠር?"

"እዛው አካባቢ ከቀየሽ ... ጎሲፕ አንድ ሰአት?"

"ጥሩ በቃ ... እዛው እጠብቅሃለሁ።"

"ሉሲት ... አብረን አምሽተን ወደ ቤት መሄድ እንችላለን? ... በጣም ነው የናፈቅሽኝ ... የማወራሽም ነገር አለኝ?" አለ፣ እግሩን ጠረጴዛው ላይ አነባብሮ ከመቀመጫው ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ እየተቀመጠ።

"አቤት አቤት ... አልተረብሀም ... ሰው በደወለው ናፍቆት ...እሱ ጸባይህ ታዲቅ ማታ ይመሰናል ... ያማ ሉሲት ሆንኩኝ ... እንተ አያልቅብህም ... በል ልግባ እይሃለሁ በኋላ።"

@OLDBOOOKSPDF

"ሚስጥርነትሽን አልገልጥ ካልሽ ... ሉሲንቱ ይሻልሻል ብዬ ነዋ ... ሻርፐ አንድ ሰአት። አባይ የቻልኩትን ያህል ገዝቼም ይሁን ተውሼም እመጣለሁ ... የኔን ነልወደድሽው ..."

"እንስህ እንጂ ጠላሁት አላልኩም።"

"ብቀጥንም ጠጅ ነኝ።"

"ተረተኛ ... አያልቅብህ ተረት ... በል ቻው።"

ስልኩን ከዘጋ በኋላ አንዴ 'ሉሲን' ... ከዛ ሀሊናን ... ደግሞ በሉሲ ሶስ የተጣላችውን ውጸሴን እያፈራረቀ ሲያስብ ቆየ። 'የውጸሴ ሚንቅላት፣ የጎሊና የቁሀንትና የሉሲ ምስጢራዊነት' ተጨፍልቀ እንዲት ሴት ቢሠራበት ብሎ ተመኘ። ወዲያው የምስጢር ጉዳይ ትዝ አለው።

'ሚስጥርማ ... ሁሉንም ትበልጣቸዋለች ... ግን እንደዚህ የመሰለኝ ... ምናልባት እንደማትወደኝ ልቦናዬ ስላወቀም ሊሆን ይችላል። የአንድዮሽ ፍቅር ... ተፈታሪን ከሆነው በላይ የሚያገንን ... አፍታሪን እንደ ጥፋተኛ የሚያንበረክክ ዘፋ ምትሃት አለው። ጎሊናን እኔ እግር ስር ያንበረከካት ... እኔንም ሚስጥር እግር ላይ ሊደፋኝ የሚተናነቀኝ ... ፍቅር የሚሉት ያው አንድ አውራ ነው። እሁን ምኗ ነው እሷን ከሌሎቹ የሚያስበልጣት ... ድቡልቡል ነገር ...

'ያንዳንድ ሰዎች ልብ እንደ ጠንካራ ብረት ለመቅለጥ ከፍ ያለ የፍቅር ሙቀትና የጊዜ መሰዋዕትነት ይጠይቃል ... ምናልባት የሚስጥር ውበቷ ውስብስብ ስብእናዋ ነው ... ትልቅነቷ ያለው ... እኔን በቀላሉ ትንሽነት እንዲሰማኝ ማድረግ መቻሏ ላይ ይሆናል። ስለዚህ 'ፕሮጀክት ሚስጥር' ... ወይ አፋቅሮ እኩል ያደርገናል ... ወይም የእኔን ማንነት በትክክል አውቃ ... ትንሹ እኔ ሳልሆን እሷ መሆኗን በማይረሳ መንገድ ያስተምራታል። ለጊዜው ግን ... ከሚስጥር ፍቅር ይዘኖል፣ ብሎ ማመኑ ይበጀኖል መሰለኝ' አለና ራሱን በራሱ መከረ።

ከዴቪኩ ላይ ያሉ ወረቀቶችን ሲያስተካክል ከወረቀት መሃል ሁለት ቁልፎች እንደተያያዙ ተንሸራተው ወደቁ። አንሰቶ ሲያያቸው የዴስኩ መሳቢያ ቁልፍ ስለ መሰለት እያመነታ ሞከራቸው። የላይኛውን መሳቢያ ሁለተኛው ቁልፍ ከፈተለት። ስቦ ሙሉ ለሙሉ ሲከፍተው በስነስርአት የተሰደሩ የተለያዩ ፋይሎች በስም በስም ተደርድረዋል። የፋይሉን ስሞች እያነበበ እንድ ባንድ ሲያይ በሱም ስም እንድ ፋይል ተከፍቶ አገኘ።

ለማወቅ የተቀሰቀሰበት ፍላጎት የሚያደርገው ነገር ትክክል አለመሆኑን እስኪረሳ ድረስ ተቆጣጠረው። ወደ አስራ አምስት የሚሆኑ ፋይሎች ሲሆኑ የአንዳንዶቹን ስም አያውቃቸውም። የምስጢር፣ የእናቷ፣ የርሱ፣ የሲስተር ዘዚባንና የሳንቶን ፋይሎች ነጮሎ ከማወጣቱ በፊት ወረቀት አውጥቶ የተደረደሩበትን ቅደም ተከተል ጽፎ አስቀመጠ። ሉላሠው ለምን ከሠሙተኞችና ከሚያውቃቸው ሰዎች ጋር በስም ፋይል እንደከፈተለት እስኪያውቅ ጥበሰ።

@OLDBOOOKSPDF

በመጀመሪያ የራሱን ፋይል ከፍቶ ሲያየው በውስጡ መጂ አስር ገጽ ያህል በተለያየ ጊዜ ዶክ እየተጠቀሰ ስለርሱ የተጻፈ መሆኑን ተረዳ። እያንዳንዱን ገጽ በተመስጦና በፍጥነት አነበበው። ጉብዝናውንና ያለውን ሁለንተናዊ የእውቀት ደርዝ ያደንቅና ይፈራት ጀመሩ የእእምሮ ሀከምና ጠበብት ለመሆን ትልቅ አድል ካላቸው ወጣት ሳይኪያትሪስቶች አንዱ ሊሆን እንደሚችል ያትታል።

ሆኖም ግን ከፍተኛ የሆነ የሰብእና ችግሮች እንዳሉበት በተለይም ስለራሱ ያለው አፍቶና ግምት፣ ለሌሎች ያለው ደንታ ቢስነትና ንቀት፣ ከአስተዳደጉ የመነጣ በውስጡ እናና የያዘው የበታችነት ስሜትና የተበለጠ ሲመስለው የሚፈጠርበት አፍራሽ የውድድር ስሜትን ያብራራል። ከምስጢር ጋር ስላለው ፍቅርና እሷ ልትወደው የማትችል ቢሆንም እሱ ግን ሊፈነትለው የማይሞክረው ድንጋይ እንደሌለ ያትታል።

"ሁሉ የሱን ፍላጎት ለመፈጸም የተፈጠረ የሚመስለው ... በራሱ የተሞላ ... ማስተካከያን ለመተበል የሚፈራና ያለበትን ናርሲስስቲክ ጥልቅ የሰብእና መፋለስ ለማወቅም ሆነ ለመተበል ዝግጁ አይመስልም። በትልቅ አእምሮ ውስጥ ያለ እንግዳና ለስ የልጅ ሰብእና ይታይበታል። እንደሚያስበው ትልቅ መሆን ከፈለገ ብዙ ስራ ይጠብቀዋል" የሚለው አስተያየት ሊያነብ መረቀቱን ጨምድዶ ያዘው። ልቡ በንዴት ተንጨረጨረ።

ትንሽ ጋብ ሲልለት የምስጢርንና የእናቷን ዝርዝር ታሪክ በመገረም አነበበ። የሷን ምስጢሮች በመሉ በእጁ ማስገባቱ የሚሰጠውን የማሸነፍ ዕድል ሲያስብ ንዴቱ በረድ አለለት። "እጅሬ ለካ ... ከሊኒክ ከፈተኩ ብሎ የሱ መሞከሪያ አይጦች ... የየናት አሻንጉሊቶቹ አርጅናል። ካሁን በኋላ ማን አሻንጉሊት ማን ተመራማሪ መሆኑ ይታያል።"

ትንሽ ተንጐራደድና የሳንቾና የሲስተር ዘሪባን ፋይል ይዞ ከሶፋው ላይ ተቀመጠ። በሁለቱም ፋይል ውስጥ ብዙም የተጻፈ ነገር የለም። የሲስተር ዘሪባ ፋይል ውስጥ ሁለት ገጽ አጠቃላይ ነገሮችን ጽፎ "ያልታመመ ሰብእና ምሳሌ መሆን የምትችል ሚዛናዊ ሕይወት ያላት ስለራሷም ስለሌሎችም ቁናና ያልተወሰጋገደ አስተሳሰብ ያላት ሴት" ይላል። "እሀሀ ... የኛ ሰብእና ነዋ የታመመና የተወሰጋገደ ... ቀይ ዶክተር ሉላሙ ... እኔም ለርሶ ፋይል ከፍቼ ... የማደርገውን አውቃለሁ" ብሎ በልቡ ዛተ።

የሳንቾን ፋይል ሲከፍት እሱም ብዙ ነገር አልነበረውም። ዝርዝር የህይወቱን ውጣ ውረዶችና ያለፈበትን የከፋ ህይወት ባጭሩ ገልጾ "በጠቅላላው ከደረሰበት መከራና የልጅነት አበሳ፣ እንዲሁም ከተሸከመው ሃላፊነት አንጻር ራሱን ከህይወቱ ጋር አስተካክሎና አሳምሮ መኖር ችሏል። ሰብዕናው፣ ማህበራዊ ህይወቱና የሰሚት ብስሉሉ ሚዛኑን የጠበቀ ነው። ታሪኩ እንደ ሰው ምንም ዓይነት አስከፊ ነገር ቢደርስብንም፣ ሕይወት የደረሰብን ነገር ብቻ ሳትሆን፣ ለደረሱብን ነገሮች በሰጠነው ምላሽና ለመሄድ በመረጥነው መንገድ ላይ የምትወሰን መሆኗን ያሳያል" የሚለውን ሲያነብ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ... "ሚዛኑህ ይዋፋ ... ገጸኛ" ብሎ ቻርቱን ወረወረው።

@OLDBOOKSPDF

ድንገት እጁ ላይ የወደቀው ነገር ፈጽሞ ያልጠበቀው ተገኮ የሚያልት ሲላይ ሆኖ ታየው። እንዴ ሲበላጭ እንዴ ደግሞ እንዴት አድርጎ ሊጠቀምበት እንደሚችል ሲያስብ ጥቂት ቀየ። ከመቀመጫው ፈንጠር ብሎ ተነሳና የቀሩትን ፋይሎች አውጥቶ እያነበበ ራሱን እገናናባቸው። ብዙዎቹ የሚያውቃቸው ሰዎች ቢሆኑም ካሁን በፊት ከተነጋገሩት እንጻር ለምን በትርብ ሊያጠናቸው እንደወሰነ ሳይገባው አልተረፈም። ከሁሉም ያንገበገበው እሱም ከሕመምተኞች መሃል ተመድቦ እየተጠና መሆኑ ነው። አንድ ዳገስ ያለ ፋይል ጋ ሲደርስ አውጥቶ "ሆ...ሆ ይሄ በጣም የሰባ በሬ መሆን አለበት" ብሎ ሳቀና ከመጀመሪያ ጀምሮ ማንበብ ጀመረ። የማስረሻ ፋይል ነበር።

የምስጢር እድብቶ አሳዳጅና ለብዙ ዓመታት በሲ ፍትር ተጠምዶ ሲዝታቱላት የኖረ መሆኑን ሲያውቅ የበለጠ ፍላጎቱ ናረ። ፋይሉን ሁለተኛ እንደማያገኘው የፈተና ወረቀት ማስታወሻ እየጻፈ በጥንቃቄ ማንበብ ተጠለ። የታሪኩ ዝርዝር በድንብ ስለተጻፈ በመሃል ማስታወሻ መጻፉን ትቶ በተመስጦኦ ሲያነብ ቆይቶ ሲጨርስ በረጅሙ ተነፈሰ።

"ዎው... ስንት እብድ አለ ባካቹ... እቺ ልጅ ምንድነው ላዩጥ ላይ የተገጠመው ማግኔት" አለ ጮክ ብሎ። 'ለማንኛውም ማስረሻን በድንብ ማወቁ ሳይጠቅም አይቀርም። ማልማት ባይችል ሁኔኛ የጥፋት መሳሪያ የቅጣት በትር ሊሆንኝ ይችላል። አሁን ይሄንን ሁሉ ሚስጥር ባንድ ከስአት በኋላ ልግዛ ብል ፕንዘቡስ ከየት ያመጣል? አሁን የሚቀረው ዶክተር ሌላውን ፋይል ከፍቶ ማጥናት ነው።" ጥሩ ቀልድ እንደሰማ ያህል ከት ብሎ ኢያሳቀ ከፍሉ ውስጥ ተንገራደደ። ንደቱ እየለተተው ሰሄድ ጥሩ ምግብ እንደበላ ሰው ውስጡ ሲረካ ተሰማው።

ትንሽ አሰብ አደረገና ወደ ካርድ ክፍሉ በፍጥነት ሄደ የኮፒ ክፍሉ ክፍት መሆኑን አረጋገጠ። ሁሉንም ፋይሎች መስደ በጥንቃቄ እንድ ባንድ ኮፒ አደረጋቸው። ፋይሎቹን በነበሩበት ቅደም ተከተል ቦታቸው መልሶ ቁልፉን ደብቆ አስተመጠመ። የሌላውው መምጫ እስኪደርስ ማንም እንዲያገኘው አልፈለገም። ሠረቀቦቹን ከርሳው ውስጥ ባንድ የፋይል ማስሪያ አድርጎ አገራቹው። ስእቱን ሲያይ ለተጠቸው ሃያ ደቂቃ ብቻ ነው የቀረው። እንደ ብርጭቆ ውሃ በቱመ ፈጣሪ መብራቱን አጠፋፋና በጥድፊያ ወጣ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 32 ፡

ሲራክ ገሊፐ ካፈ ሲደርስ ለ·ሲ ተድማው· ኖሮ ስልክ ስታወራ ደረሰ ። ቡና እገዘ ለ·ነ ያልሆነው·ን ሲያወሩ ቆዩ ። ሁለት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ራት በልተው በቀጥታ ወደ ፅት ለመሄድ ወስኑ ።

"ምን መብላት ነው· ያሰኘሽ?" አለ ፣ በሩን ከፍቶ እንደ ያዘላት ።

"ምን ... ይበላ ... ፓስታ ወይም ፒዛ ... ኢዝ ዛት አኪ ላንተ?"

"አሪፍ ነው· ... የት ... አባ ጉበን ሳር ቤት ... ወደ መስቀል ፍላወር መንገድ ላይ _እንድ አሪፍ የጣልያን ቤት አለ ... ፒዛ ካልሽ ግን እርይም አለ መንገዳችን ላይ ..." አለ፣ ሞተሩን አስነስቶ ወደ ኋላ እየሄደ ።

"እንዴ ኧረ በቃ ... አባ ጉበን እንሂድ ካልራቀ ..." አለች ፣ የሹራቧን ቁልፎች እየዘጋች ። ለስለስ ያለ ሽቶዋ መኪና ው·ን የስሜት መ··ቀት በሚፈጥር መአዛ ሞላው ።

"ንፍስ የሆነ ሽቶ ነው· ... ደግሞ ከሳሽ ልበል ... ወይስ ጥቁር ስለለበስሽ ነው?" አለ፣ ዞር ብሎ እያያት ።

" አይ ያው· ነኝ ... ወይ ስለራበኝ ወይም ልብሴ ይሆናል ... ወይ ማን ያው·ቃል ... ከወፋፍራሞች ጋር ከርመህ ይሆናል ..." ብላ ስትስቅ ፣ ጎኗ ላይ ጎንተል አደረጋት ።

"ምን ለማለት ነው·...?"

"ከነ ጎሊና ... ከንሚስጥር ... ያቺኛዋ ደግሞ ማናት በጥፊ ያሥለችህ ... ታረቃችሁ·?" ብላ ፣ ከት ብላ ስትስቅ ፣

"ሆሆ ... እሳው· ሰይጣኑ ያጨላችና ... ከዛ ወዲህ አይቻትም አላው·ቅም ... ደግሞ ሚስጥር ያልሻት ማናት·?" አለ ፣ ከግምት በላይ እንደማታው·ት በማሰብና ፖስጢር የምትባል ልጅ እንደሌለች ማሳመን እንዳለበት በማሰብ ።

"እንት ንገረኝ እንጂ ... ትዝ ይልሃል ... 'ሚስጥር' ሁኚልኝ ያልከኝ እኮ ራስህ

@OLDBOOOKSPDF

ነበርክ ። ምናልባት ሚስጥሩን ማግኘት ሲያቅትህ በኔ ልትተካት የምነበርክ መስሎኝ ነበር ። በንፈራችን ላይ በጣም ብዙ ሰው አለ እንደዛ የሚያደርግ ... የኛ ሥራ የሚያሳየን የለም ። ባለፈው እንዳልኩህ ሌሊት ላይም እኔ ላይ ተለጥፈህ ስትተበጣጥር ነበር እኮ ። የእውነት ከሌለች ተወው ። ግን እውን ከነሊናና ከባለጥፊዋ ልጅ ሴላ እውነት ማንም የለም?" አለች ፊቷን በመኪናው መስታዋት ለማየት እየሞከረች ።

"ብናትሽ ጥፊ ጥፊ አትበይ ... እንደገና እያሳመመሽኝ እኮ ነው ። ስሚ ውዴ ነው ። ደግሞ ስለቢ ልጅ ባናወራም ደስ ይለኛል ። ሴላ ሰው የለም ወይ ላልሽው ... ልዋሽሽ አልችልም ሰሞነኛ መጪና ሂያጅች አሉ ። ጎሊና ብቻ ናት ጭሚ ተሰላፊ ... ኡፍ ... እቢን ልጅ ምን ማድረግ እንዳለብኝም አላወቅኩም ። አሁንማ ኮ በታ እናቴ ነው የምትመስለኝ ። ለኔ ከማሰብና ከመጨነቅ ሌላ እኮ ምንም ስራ የላትም ። ጡር የሚባል ነገር ካለ የቢ ልጅ ጡር ምን መቀመቅ ውስጥ እንደሚከተኝ አላወቅኩም" አለ ፣ ዓይኑን ጨፈን አድርገ ፊቱን ግራና ቀኝ እያወዛወዘ ።

"እና ... እኔም እስካሁን ሰሞነኛ ነው የምባለው ማለት ነው? ... ጭሚ ተሰላፊ ደረጃ ለመድረስ መመዘኛው ምንድነው?" ብላ ፣ የሸፈት ላቲን እየላቀች የመኪናውን ቁቡዮ ፈታች ። ደርሰው ስለነበር መኪናውን አቁመው ወደ ምግብ ቤቱ ገቡ ።

"ይሄ ቤት ሁሉ ነገሩ ጥሩ ነው ... ሠንበሩ ግን እንደ እሮሀ ተንጨባበር ሲዋጋ ያስፈሰፈ ይመስለኛል ። ጥቁር ስለሆነ ደግሞ አንዳንዴ በደንብ ላያታይሽ ይችላል ። እኔ ዊይስ ... ወደ ጠየቅሽኝ ጉዳይ ልመለስና ... አንቺ ጭሚ ተሰላፊም ነሽ ማለት አይቻልም ... ሰሞነኛም ነሽ ብሎ መደምደም ከባድ ነው ። ምን እንደሆነነሽ ለኔም ግልጽ አይደለሽም ። ሳስበው ሳስበው ሚስጥር የሚለው ስም ጥሩ ነበር መሰለኝ ... ግን ሉሲም ምንም አይልም ። ልብሽ ተቀፍሮ ማንነትሽ ከተገኘ ማለት ነው ። ያኔ የጭሚ ተሰላፊነት ማለያ ትለብሻለሽ"

"እንዳቀፋፍርህ ነው ..." ብላ እሱን ጠመም አድርጋ ሳቀች ። "እኔ ምለህ ላዛኛ ብበላ ደስ ይለኝ ነበር ... መይስ ፒዛቸው ይሻላል?" አለች ፣ የምገቡን ዝርዝር እያገላበጠች ።

"ካማረሽ ላዛኛውን ትመጂዋለሽ ... ፒዛው ም አሪፍ ነው ... ከኔ ላይ መቅመስ ትችያለሽ ።"

"እንጄት ነው የከሊኒኩ ስራ ... ተለመደ?"

"ተለመደ እንጂ ... ኮርፍ ሆኗል ሰዉ ... ከተማው ውስጥ ምንም የራሳ የአእምሮ ህዝምና የሚሰጥ ከሊኒክ የለም ። ሰሞኑን እንዳያውም ... አለታችን አሜሪካ ሄዶ የሱንም የኔንም ስለምሸፍን ... ተመጥፊ ልምት ነው" አለ ፣ ቀን ያየውን ፋይሎች አስታውሶ በልቡ "አለታ ምን እንደሆነ ይታያል" አያለ ።

"አንተ ልጄ ተመችቶሃል ... ሲያዩህ እንኳን ስራ የበዛብህ ፣ ስራ ያለህም አትመስልም" አለች ፣ በእጇ የያዘችውን ሻይ ደጋግማ ራት አያለች ። አራታቸውን በልተው ቢት ሲገቡ አራት ሰዓት አልፎ ነበር ። እንደገቡ ተሸተዳድማ

@OLDBOOKSAMDE

ሥራ ትጠቢያ ቤት ገባች ። እንደዮሙ ሣጓማውን በራፉ ላይ በቁሙ አውልቆ ፣ እንደ ሥሩው ከፍረጁ ውስጥ የተዘቀዘዘ ቢራውን አወጣና ተነፈሙን ከናፍቆ ከሶፋው ላይ ጋደም አለ ፣ ቦርሱን ቁምጣና ተሸርተት አድርጋ ተንደርድራ ላዩ ላይ ልትወድትበት ስትል ጮኾት ሲል ላቀችበት ። ካጠገቡ ተቀምጣ እንት አድርጋ ሳሙችው ።

"እስኪ ልብሴንም ልቀይር ሻወርም ብወስድ ጥሩ ነው ... መጣሁ" ብሎ ሲነሳ

ተሚያሽህ ትፈልጋለህ?" አለችው እጁን እንደያዘችው ።

"አይ በስሱ ለትለት ብዬ መውጣት ነው የፈለኩት ... እስክዛ ሻይ ምናምን ሂጓቸ እጠጣለሁ ። መጣሁ" ብሎ ፣ ሹራቡን አውልቆ በጁ እንደያዘ ወደ መኝታ ቤት ገባ ። ሊመጣ ሻይና ቶሎ አዘጋጅታ ስልክ ስታወራ ደረሰ ። አጠገቧ ቁጭ እንዲል አልፍ አለችለት ። እርሱ ላይ ተንተርሳ ፣ ሶፋው ላይ በጀርባዋ እግሯን ዘርግታ ተኛች ።

"በስሱ ይሄን ያህል ነወሰደብህ ... በመፍራመ ሲሆን ሰንት ሰዓት ነው የሞትየው?" ብላ ስትስት ፣ አገጯን በሌባ ጣቱ መታ እያደረገ ፣

"ወዲያው ጨርሼ ነበር እኮ ... ወንድሜ ደውሎ ከሱ ጋር ሳወራ ነው" አለ ።

"አባት-ወንድምህ ነው መደስ ሌላ ወንድም?" ስትለው ላቱን ለቀቀው ።

"እንዲያው እንቺ ልጅ ምን ይሆን የሚሻልሽ ...እሱ ነው ..."

"ታሪታችሁ እንደ ...ማለቱ ... ባለፈው ስትነግረኝ በጣም የምር ጥል መስሎኝ ነበር ... የገረድ ልጅነትህ ጉዳይስ ምን ደረስ?"

"ወይ ጉድ ... እሱማ ምን ይሆናል ... አለ ባለበት ... የወንድሜ ሚስት በጣም ደግ አስተዋይ ሰው ናት ። እነደሷ ዓይነት ሰዎች በዓለም ላይ በጠቅላላ ቢቀጠሩ መቶ የሚሞሉ አይመስለኝም ። ወንድሜ ከየት እንዳገኛትና ምኑን ወዳ እንዳገባችውም አይገባኝም ። ብቻ ለማሳጠር በርሷ ብርታት ከብዙ ድርድር በኋላ አባትነቱ ሳይነሳ ወንድማማች ሆነን በለመድነው ግንኙነት በመቀጠሉ ተመስን ። እንግዲህ ቀስ ቀስ እያለን ምንም አንል"

"የእናትህስ ጉዳይ ይታመታል?"

"ምንም የሚያጠራው ነገር የለም ... ሠላሳ አመት ሊሆነው ምን ቀረው ብለሽ ነው ... በሕይወት መኖሯንም አላውቅም ። እንዳንዴ ፈልጌ ማገኛት እንዳለብኝ እሰማለሁ ... ከዛ ደግሞ የት ብዬ እንደምጀምር ... ባገኛትስ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላማላውቅ ... እንደ ተንጠለጠለ የተረፈ የሕይወቱ ምእራፍ ነው ። አዛው እንደተሸገ ቢቀር ይሻላል መሰለኝ" ብሎ ላያስበው የሆነ ትካዜ ውስጥ ገባ ።

"ስማ ሲራክ ... እናት እናት ናት ... እንዴትም ሆና ብትገኛት ለውጥ የለውም ... በሕይወት ባትገኛት እንኳን ... የናትህ መቃብር ላይ ማልቀስ በራሱ ዘብር ነው"

"አይ ተንከ ስለኔ ብዙ አሠራሽኝ ... እንቺ ሣን እንደሆንሽ ... ምንም ነገር ሰላንቺ አላውቅም ... እውነተኛ ሰምሽን እንኳ እኮ አልነገርሽኝም ... እኔን ማናዘዙ

@OLDBOOKSPDF

እያበቃሽም" ብሎ ግንባሯ ላይ ሳም አደረጋት ። ዓይን ዓይኗን ሲያያት ፣ ዝም ብላ ቀየችና ... ድንገት እይኗ በእንባ ሞሞም አለ ። ፊቷን በጅቧ ሸፍና ብዙ ቀየች ።

"ሲራክ ... መጥፎ ስው ነህ ብዬ አላስብም ... ግን ደግሞ ... ራሴን ከፋፍቼ ላሳይህ እፈራለሁ ። ብዙ የተገፋው ሰው ስለሆንክ ... ሁሉም ነገራችን እንዲሁ እንደሳፈጠ ፣ የተጠለሙን ያህል ቀየሎ በራሱ ጊዜ ሲያልት ቢያልት እይሻልም?" ብላ ፣ እምባዋን ጠራርጋ ተነስታ ቁሙ አለች ።

"እንደ ... እኔ እኮ የልቤን ላንቺ የነገርኩትን ያህል ግማሹን የሚያውት ግንም ስው በምድር ላይ የለም ። ግን ደግሞ ዝግጁ ከሆንሽው በላይ መይም በፊት ... ምንም ነገር እንድትነግሪኝ አልፈልግም ... ይቅር ... ገደለም"

"አውታለሁ ... ግን እኮ ... አንተ ይዝተር ነህ ... በባ ላይ ወንድ ነህ ... ነገ የፈለከውን ማድረግና መሆን ትችላለህ ። እኔ ግን ታሪኳ የተበላሸባት ... ተመጥጣ የተጣለች አገዳ ... የተረገጠች ጽጌረዳ ነኝ ። እንደገና ተመጥሞ መተፋትና ተወርወሮ መረገጥ የሚችል አቅም የለኝም ... ይገባሃል?" ስትለው ፣ ዝም ብሎ ወደ ራሱ ሳብ አድርጎ አቀፋት ። ጸጉሯን ... ግንባሯን ... አንገቷን ... ሲስማት ... ልፃ እስኪፈነዳ ... አይኗቿ የሚፈርጡ እስኪመስሉ ድረስ አለቀሰች ። ትንሽ ጋብ ሲልላት ቀስ ብሎ ለቀቃትና ... ሌላ ትኩስ ሻይ ቀድቶ መጣ ። እሷም ወደ ጓዳ ሄዳ ፊቷን ታጥባ መጣች ።

"ታሪኬን ስለነገርኩህ ምንም የማደረግና የመሆን ሜዜና የለብህም ። ብዙ ታሪኮችን ስትሰማ እንደምትውል አውታለሁ ። ይሄንንም እንዳነዱ ብትቆጥረው አልተየሙህም ። ግን ቢያንስ ስለዓደኝነታችን ሲባል ታሪኬን ብነገርህ ጥሩ ነው ። ለነገሩ እኔም የዛ ታሪኬን ከሰማሁት ቀደቻለሁ ። አስኪ ላንተም ለኔም ባሬ እንደኛ ልንገረው" ብላ ፣ ሻዩን ደጋግማ ፉት አለች ። ቀየሎ የምትለውን በመጠበቅ ሞንትላቱን በእሺታ ነቀነቀ ።

"ትዝ ይልሃል መጀመሪያ ቀን የተዋኩልህ ማስታወሻ ላይ ኤስ ኤስ ብዬ ነበር ስሚን ። ብታምንም ባታምንም እውነተኛ ስሚ ... ሳቢላ ነው ... ያባቱ ስም ስጊዜው ይቅር ... እሱው ነው ስሜንም ያወጣልኝ ። እኔ የተወለድኩ ጊዜ ከመጽሐፏ ገጸባህርይ ሳቢላ ጋር ኦል-ሞ-ስ-ት ፍትር ይሆት ነበር አሉ ። ሃይ በናትህ ኧረ ቀይ ሳልንግርህ ደግሞ ...አውን ትዝ ስላለኝ ነው ። ባለፈው ዲቪ ስሞላ ምን ነዘቶኝ እንደሆን አላውትም ባሌ ብዬ ሞልቼሃለሁ ። ቢደርሰኝ ግን አብረኸኝ አትሄድም? ሳልንግርህ በማድረጌ ይቅርታ ... እንደዛ ማድረግ አልነበረብኝም አያደል?" ብላ ፣ ዓይኗን ሰበረች ።

"ተገኝቶ ነው ... ኢንፎርሜሽኔን ግን ከየት አገኘሽ ... ማለት የልደት ቀን ምናምንገ" አለ ፣ ጸጉሯን እያሻሸ ነገሩ ዝርሞት ።

"መንሻ ፊታድህ ላይ ነው ያየሁት ... እንጂ ያየሁትን ነገር አልረሳም ። ሌሎቹን ጥያቱዎች ባለፈው ካፈ ወስዋ ላሞር ጊዜ የተገናኘን ጊዜ በየመሃሉ ሰይቁህ ነበር"

"ትገርሚያለሽ ... ዕድል ኑነሳችን መገጠሙ ያታያላ እንግዲህ ። ስለተስወኝ የባልነት ማዕረግ ዝት ብዬ አመሰግናለሁ" ብሎ ግንበስ ሲል ፣ ጸጉሩን ይዛ ወዘወዝ አደረገችው ።

@OLDBOOOKSPDF

አለት ነበት ... አለተረብሀም ወት" ሰትለው፣

ናም" ቢቃ ከባራ ያ'ም'ር ... ሳማ ተሰላፈ ብያ ሳያሀን የቡድኑ አምበል ሶ"

"እሰፈለ'ም ... አሰልጣኝ መሆን ነው የምፈልገው" ብላ፣ የተዘቀዘ ሻይዋን ታወዛ አስቀሶጠችው።

"እሺ በራ ቶጥይልኝ ስለ ቡድኑ አምበል ...ስለ ሳቤላ ... ባያ ዘ ቂያ ... በጣም አናሽ ነው"

"ታንዝ ፍ ... እና ... እናቴና አባቴ አረፍ ትዳር ነበራቸው። እኔ ምስተኛና ምጨረሻ ልጅ ነኝ። ታላት ወንድምና እህት አሉኝ ... ሁለቱም ከናቴ ጋር ነው ያደኑ አሜሪካን አገር። እኔ ከሁሉም ልጆች ያልት በመልኬም ባህባዩም አባቴን ጅ የምስለመ ያላሉ። አባቴና እናቴ በጣም ቢዋደዱም እሱ አርር እንደማያቀሙሦ ሴው ሁዴም ያደረሳት ነበር። ገዘገዙን ለዘርዛሪዎች እንተጠሙና እንዴ የለችም ጭ ሊቀብጥ ሪራሳቸው አልጋ ላይ ካንዲ ጋር ተጋድሞ ያዘችው። በስንት አነክ ሀና እሱ የተነሉ ሽማግሌዎች ገብተው በብዙ እግዚኦተና ልመና ታረቁ። ከዛ ደቂቀመለሰ - እንዴ ድሮው ሊሆን አልቻሉም።

"ያኔ እኔ የሰባት አመት ልጅ ነበርኩ መስለኝ። እሱን ሰለምመስላት ያውን እንጂ የማቀው ምክንያት ጥምድ አድረጋ ያዘችኝ። ሳስበው እሱን በጣም ስለምወደው ያሁትን የሰግሁትን ሁሉ ለሱ ስለማሳብትም መስለኝ። ከእሁቸ ጋር ተማዘረው ባድ እሀቷ ምረቃ አሳበው ታላላቀቿን ብቻ ያዛ አሜሪካ ገባች። እዛ ከደረሰች በኋላ እንደንትመለስ ደውላ ነገረችው። እኔንም ጥላ ስለሄደች አትመለስም ብሎ ቂራሽ ከጨፈረረም ነበር። ብዙ ገሩ እንደፈጸመባት የጥገኝነት ማግልኪቶቿ ላይ ሳትሞላ አትቀርም ... ወይም ለደህንነቷም ያሰጋሻል ብላ ... አላውትም ብቻ እሱ ወደዛ እንደሄድ ልረጅም አመታት ቪዛ ከልከለው ነበር።

ለሁለት ዓመት ያህል የቤቱ ልዕልትና ንግሥት ሆኜ ቀየሁ። ዴላሞና ሰድሟ ጨፈረኝ እናቴ አለመኖር ብዙም አልረበሸኝም ነበር። ወንድምና እህቴ ግን ሁሉም ሳታላቅ ያሄዱ ነበር። ከሁለት ዓመት በኋላ መሰለኝ፣ ያቺን እናቴ አልጋ ላይ ከርሱ ጅ የያዛትን ሠላት ሰት ድል ባለ ሰርግ አገባት። እኔን ሁሣም ነበር የምትወደኝ። የሚያሳዝነኝ ነገር የማገኝገረኝ ሚስዮር አልነበረም። አስራ ሦስት አስራ አራት ሰመት ሲሆነኝ ግን መጋዜት ጀመርን። በተለይ አባቴ የማያውቀው ሲላ እኖውትም እንሰጣ ሰረዴ፣ ሳባቴ መቀርቀርና እገዴት አድርጌ እንደማጋልጣት ማልዘ ጀመርኩ ዝ ፈገግ ብደግ ብላ መኖ ጎጻ ሄጻ ለሁሉቱም የተዘቀዘ ቢራ ያዛ መጣች።

"ከግጽህ የምቱ መራ በቀዘቀዘ ቢራ ካልሆነ ኑ ያሮህን እንሳደቃዋለው ብዙ ነው ትባላቸ እንዴ ተገንዝታ መራዋን ቀጠለች።

"እሷ ግን ከኔ ያልት ብልጭ ሰልህራች በፊት የበለጠ ጎደናዊ አደረገችኝ። ያለነን ፍቅር ስለም ታውት በሆዴ ቢመጣም አገኛችሁልህ ብዙ

@OLDBOOKSPDF

የማላስባቸውን ዘፋኖችና ሙዚቀኞች አስተዋወቀችኝ። አንዳንድ ፓርቲዎች ላይ መስሩን እንደበፊትነቴውና እንድደነስ ይጠይቁኝና ሲያደንቁኝ ትንሿ ልዜ ሰማይ ነካች ። አልኮል በእዝህ ውሃ እየበረዝኩ እንድጠጣ ፈቀደችልኝ።

"አባቴ ለስራ ከከተማ ሲወጣ ደግሞ ጓደኞቿን ጠርቼ፣ እቤት ውስጥ እኔ ነኝ የተባለ ፓርቲ ማድረግ ሆነ ሥራዬ። ስለዚህ ሁሉታችንም ሃሞ ያተሞች ስለሆንን የበለጠ ተቀራረብን። ሲጋራ ... ከዚያ ሃሺሽ እያለች ... ተስ በተስ ብዙ ነገር አስተማረችኝ። ኮኬይን የሚባለውን ድረግ ያስጨሰችኝ ቀን ራሴን አላውቅም ነበር። ያኔ አስራ ስድስት እመት ሆኖኝ ነበር መሰል። በሱሱ በደንብ እንደተጠመድኩ ስታውቅ እጹን ከሚሸጥሏት ሰዎች ጋር አስተዋወቀችኝ።

"ለመጀመሪያ ጊዜ የማታ ፓርቲ ወሰድችኝ። መጠጡ ትላለህ ድረት ... ሙዚቃው ... ብቻ እብደት ነበር። እቅሌን በሳትኩበት ሰዓት እንዴ ይሆኝ እደረ። አንድ መሆኑንም እስካውን ድረስ እርግጠኛ አይደለሁም። እንዳላወቀ ሆና ጠዋት ፈልጋ ስታገኘኝ ለምን ከወንድ ጋር አደርሽ ... ምን ሰራሽ ... ትብርጥሴ ላባትሽ ነው የምናገረው ብላ ጀት ሆነች። ያገር ማል ከሰንት ጊዜ በኋላ ነው ያ ሁሉ የሷ ወጥመድ መሆኑ የሚገባኝ። ነፍሷን አይማርና እንደሷ አደነት ሽሩድ ሰው በሕይወቴ አይቼም አላውቅም" ብላ ሚንቅላቷን ስትነቀንቅ ሳያስበው፣

"ምተች...?" አለ፣ የቢራውን ጠርሙስ አፉ ጋ አድርሶ እየመለሰ።

"ሳታስበው ብዙ ድረግ መስጻ መስለኝ ... ብቻ አላውቅም ... ራሷን ለማጥፋት ብላም ይሆናል ... አይታወቅም ... አባቴ በሌለበት መኝታ ቤት ነው ሞታ ስራተኛዎ ያገኟት" አለችና ፊቷን በሁለት እጆቿ አሻሽታ ተንጠራራች።

"እኒ ቄያስ ... የመጠጥ የድረግና የፓርቲ ላያፈ ጣራ ላያ በወጣበት ሰዓት ... ካስሩ ጋር ስዛለል ... ማርገዜን ላውቅ ድንብርብሬ ወጣ። እንጻስወጣው እንደምትረዳኝ እርግጠኛ ነበርኩ። አስራ አንደኛ ክፍል ብደርስም ክላሰ የማልገባበት ቀን ይበልጥ ነበር። በፍጹም አለች ለኔ አሳቢ መስላ ... አንድ ነገር ብትሆኚ አባትሽን ምን ልለው ነው። ለሱ መንገር አለብን ብላ ሙጭጭ አለች። አንቺ ባትነግሪውም እኔ እነግረዋለሁ ብላ ስታስፈራራኝ እጅ ሰጠሁ። ውጤቱ ምን እንደሆነ አሳምሬ ታውቅ ነበር። አባቴ በመጀመሪያ ፉረኛ እገዴት ተደፍሬ ብሎ በራሩ አለ። እሱ በየሰርቻው እየተገበዘለለ ... ጎስራ ሴት ጋር በየቦታና ቤቱ ሲንጾባለል ከርሞ ደርሶ ጨዋ መሳይ ... ባህላችን ከብራችን ቅብርጥሴ እያለ ዘፈነ።

"ከዛ ደግሞ ... ምቼ እገኛለሁ ... ልጄ እያለሳም ... እኖ እናላድቦለን ... የግዜን ቁጣ ሊቅመፈብን ነው ምናምን ማለት ጀመረ። እግዜር ቢቀጣ የሚቀጣው ሚስቱን ይስቀምጦ ሳልጋዥ ላይ በብሶገው በሉ ነበር። መይም እሱን እገሩ ዕየ እናተሚወተችብት ከማንም ሃሺሻም ጋር በሉ ገንዘብ በምትላልግ በአዲሱ ሚኔቱ በነሱ ያልተቀጣ እግዜር በኔ ይቀጣል ማለቱ ራሱ አስቂኝ ሆነብኝ። ጽንሱን ሳስወገዱም እኔም ለዘዲሙ ከቤት ተባረርኩ። ንብቃ ያለተጸጸትኩኝ ሽማግሌውን ከየቀበቱ ፀሬ

@OLDBOOOKSPDF

ያለንባች መስላት" ስትል ፣ ስልኳ ሲጮህ ቦርሳዋን ከጠገቡ አቀበላት ። ስልኩን ከቦርሳዋ ፍስኖ አውጥታ አይታው አስክን አላቱው አጠፋችው ።

"አባቱ በዛ ሰማይና ምድሩ በጨለመብኝ ሰአት ፣ ከኔ ይልቅ ለክብሩና ስሚ ብዙ ለሚኮራበት ቀር ማንኑቱ ተጨንቆ እንደ እታ ሲወረው ረኝ ልቤ በበቀል ተሞላ ። ለክሌ የምከፍለው ገንዘብ ስለ ሌለኝ በየናይት ክለቡና መንገዱ ላይ እየቀምኩ መራራ እይወቱን ሳላስበው ጀመርኩ ። መጀመሪያ ላይ የማያውቁኝ የሱ ጓደኞችና ደንበኞች የሚገቡበት ቤት እገባና አብራያቸው ከወጣሁ በኋላ ገንዘባቸውን ኪሴ ከትቼ የማን ልጅ እንደሆንኩ ስነግራቸው የሚገቡበት ይጠፋቸዋል ። ወሬው እንዲደርሰው አደርጋለሁ ። ለለማ ሊያብድ ምንም አይቀረውም ። መጨረሻ ላይ እሱም ልጄ አይደለችም ብሎ ለከደኝ እኔም ከሱ ጋር ትግሌን ትቼ ወደ ራሴ ሕይወት ተመለስኩ ።

ዋሀሬ አምስት አመት ገደማ እንደ ምንም ብዬ ትምህርት ቤት ገባሁ ። ዩኒሰራበትም በነርሲንግ ዲፕሎማ ያገኙኝ ። አሁን ደግሞ ዲዛይኒንግ እየተማርኩ ነው ። አባቴን ስሙን ብንግርህ ታውቀዋለህ ... አገር አንቱ ያለው ቁጭር ነው ። እናቴም ቤቱት ካንሰር ባለፈው ዓመት ከመሞቷ በፊት እዚህ አገር መጥታ ነበር ። ይቅር ለግዜር ተባብለን ስለሞተች የህሊና እረፍት አገኘሁ ።

"ወንድምና እህቴ ግን ሴትኛ አዳሪ ስለ ሆንኩ አጠገቤም መድረስ አይፈልጉም ። እዚህም ትልት ቢዝነስ ጀምረዋል ። ካባቴ ጋር ታርቀው የሱን ቢዝነስ ማኔጅ ሚያደርጉት እነሱ ናቸው ። እኛም ይሄው ሲያገብን ጨካኝ አውሬውን ... ሲያገነልን ደግሞ ከንዳንተ አይነቱ ትብጥብጥ የልጅ ምሁር ጋር ወጣ ገባ እያልን አለን ። ሠላሳን ለመድፈን በትርብ ርቀት እንገላምጣታለን ። "

በጸጥታ ሲሰማት የቀየው ሲራክ ራሲን እያሻሸ ፣ "ይገርማል ... ዩ ኖው ... ሉሲ ሰምዶብኝ ... ሳቢላ ማለቱ ያገ ያደርጋል ... ሳቢ ልበል?" ሲል ፣ ቀና ብላ አየችውና ፣

"ደስ እንዳለህ ጥራኝ ... የሚሳብ ከተገኘ ..." ብላ ፣ ስትስቅ እሱም አብሯት ሳቀ ።

"ታውቃለህ እንኳን እንደኔ አይነቷ የቱጭር ንጋዴ ልጅ ቀርቶ ማንም የደሃ ልጅ ቢልጅታ ሴትኛ አዳሪ እሆናለሁ ብላ እንደማታስብ ። ይሄ ሁሉ መንገዱን ሞልቶትና ከከፍተኛ ባሮች እስከ ጉራንጉር መሸታ ቤቶች የሚያጣብቡ ሴቶችን አስበሃቸው ታውቃለህ? ሁሉም በተለያየ ምክንያት የህልማቸው ከንፍ ተሰብሮ መብረር የማይችሉ ኦሳት ናቸው" ብላ ተነሣች ። ብድግ ብሎ ተንጠራራ ። ምንም ሳይነጋገሩ እንደቀሙ ተቃቀፉ ።

ቀጣዩ ሳምንት ለሲራክ አስቸጋሪ ጊዜ ነበረ ። ብዙ ሀመምተኞች መጥተው ሌላው ስለሌለ ዶክተር ሲራክ ይያችሁ ሲባሉ አሻፈረኝ እሱ እስኪመጣ እንጠብቃለን እያሉ ቀጠሮ አስቀይረው መሄጻቸው የበለጠ አናዶታል ። ከካፌቴርያ ሠራተኛዋ ጀምሮ ሁሉም ለሌላው እንኳ ለጓደኛ ታታዘዝም ያሚሉት መስለው ። ዘበኛው በሩን ቶ አይከፍቱለትም ... ሁለት ሦስት ጊዜ ቡና እገዛ ከብዙ ወ-ትወታ በኋላ ቀይቶ

@OLDBOOKSPDF

ነው የሚመጣለት። ለማኔጅመንት ሳምንታዊ ስብሰባው ሲስተር ዘሪባ ብቻ ናት የመጣችው። ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰበ ድንገት በሩ ሲንኳኳ

"ይግቡ ..." አለ ሥጋ ብሎ።

ላንቾ በሩን ከፍቶ ገባ። "ፈልገገኝኝ ነበር ..." አለ፣ የያዘውን ጋዜጣ በጁ እየጠቀለለ ራቅ ብሎ እንደቆመ።

"ያ ... ትናንት ከለዓት ነበር ... እንድምፈልገህ ለጸሐፊዋ የነገርካት ... አልነገረችህም?" አለ፣ ቁጭ በልም ሳይለው።

"ትንሽ ሥራ ስለበዛብኝ ነው ... ምን ተገኘ?" አለው፣ ከማዶ ያለው ሶፋ ጠርዝ ላይ ደገፍ ብሎ።

"ችግር አለ? ... የማኔጅመንት ስብሳባ ላይ እንተም ሚስጥርም አልመጣችሁም። ደግሞ በዲስፕሊን ቅጣት ለሳምንት እንዳትገባ ያዘገሳትን የጽዳት ሰራተኛ መልሰህ አስገብተሃታል አሉ ..." አለ፣ የውስጥ ጌጡን እየተቆጣጠረ።

"በመጀመሪያ ሁሉም ነገር አሰራር አለው ... ይሄ ሱት አይደለም። አስተዳደርና የለው ኃይል አመራር ... ደግሞ የቅርብ አለቃ የሚባል ነገር አለ። ዝም ብለህ ታችና ላይ እያልክ ሰው ማባረርና መሾም አትችልም። ለሦስት ሳምንት የተሠጠህ ውክልና አስፈላጊ ቴክኒካል ጉዳዮችንና አስቸኳይ ውሳኔ የሚፈልጉ ነገሮችን ለማስፈጸም መሰለኝ። እንጂ እንደመሰለህ ብቻህን ፈላጭ ቆራጭ እንድትሆን አይደለም" አለ በተረጋጋ ድምጽ።

"እና አንተ የኔን ውሳኔ ለመቀልበስ ተወክለሃል ማለት ነው? ደግሞ የማኔጅመንት ስብሰባ ከቀራችው ቤትህ መጥቼ እንድነግርህ ነው? ለጊዜው ከሊኒኩን የምመራው እኔ መሆኔን አትርሳ" ብሎ የሚጮኸውን ሰልክ አንስቶ ወራ ጀመረ።

ሰልኩን እስኪዘጋ ጠበቀው። "ሲራክ ችግርህ ምን እንደሆን ታውቃለህ? በጣም ብዙ የምታውቅና ያላንተ ማንም ሰው ያለ አይመስልህም። እውነቱ ግን ገና ብዙ መብሰል የሚቀርህ ከትምህርት ቤት ውጪ ያለውን የሕይወት እውነታ ያልተገነዘብክ እንጭጭ ልጅ መሆንህ ነው። ሀይወት ባነበብካቸው መጻሕፍትና በእውት አለም መካከል በጣም የተለያየች ናት ...እሺ?"

ሲራክ ከት ብሎ ሳቀ። "በመጀመሪያ ደረጃ ያለነው ሥራ ላይ ነው። እኔ ባደናህ አይደለሁም ስለዚህ ዶክተር ሲራክ ብትል ደስ ይለኛል። ይሄን የሰፈር ፍልስፍናህን ደግሞ ሰራስህ ተጠቀምበት። ካሁን በኋላ ግን ጣልቃ እየገባህ ባትፈተፍት ደስ ይለኛል። ጨርሻለሁ" ብሎ፣ ራቁን እዙሮ ኮምፒዩተሩ ላይ አፈጠጠ።

"እንዴት እንዴት ነው የሚያቀናጥርህ ልጄ ... ዶክተር ሲራክ ... መከበር ከፈለግህ መንገዱ ሌሎችን ማክበር መሆኑን እወት። እኔ ብዙ ነገር መፈትፈት አላውቅበትም። ካሁን በኋላ ይሄንን ልት አፍህን ካልዘጋህ እኔ ራሴ ሁለተኛ እንዳትከፍተው አድርጌ ልዘጋልህ እችላለሁ ... ገባህ?" ብሎ፣ የጁን ቡጢ እያሳየው ጠጋ አለው።

@OLDBOOOKSPDF

ፎሬትም መውጫ እንደሌለው ያወቀው ሲራክ ውስጡ የተፈጠረውን ፍርሃት ያመቃኘር እየሞከረ፣ "እታካሮና ጥል አልፈልግም ... አሁን ቢሮውን ትለቅልኝ አ፣ በድምጹ ውስጥ ከፊል ልምምጥ እየታየ ።

"ባልስት ምን ታመጣለህ? ... ሁሉ ሰው እኮ ለዶክተር ሌላሠው በደስታ ሮታዘዘው ለምን እንደሆን ታው ታለህ? እሱ ሁሉንም ሰው ያከብራል፣ የሌላው ሰው ኦና ያክብ ይገባዋል ... ባሮሩ ሰው መሆን ስለሚያውቅበት ነው ። እንተ ኮ አፍሀና ተራህበዛ ... ሰው እንዴት ሦስት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ አገር ይበጠብጣል ። ምን አይነቱ የኛነው ባክቹ ይሄ ..."

"ስውዬ ልትሰድበኝማ አትችልም ... ካሁን በኋላ ሁሉንም እሱ ሲመጣ እነሂንገራለን"

"እኔ እንተን አልሰድብህም ... ካስፈለገም ... ታየዋለህ ይሄን ... ካሁን በኋላ እኛን ብትከፍት ..." ብሎ፣ ወደርሱ ተጠጋ ።

ስታልፍ ሞቅሞቃቸውን የሰማችው ምስጢር በሩን ከፍታ ስትገባ ተፋጠው ደረሰች ። "እንዴ ምንድነው ... ሰላም ነው?"

"ኧረ ...ምን ሰላም አለ? ... ካልተደባደብኩ ብሎ እየተገበዘ ኮ ነው ..." አለ፣ ለራክ ከመቀመጫው ተነስቶ ።

"ምን እሷ የምታስጥልህ መሰለህ ... አሁንም ከፈለኩ እንገትህን ቀልምሚ ነው የምደፋህ ..." ብሎ፣ ሲጠጋው ምስጢር ሮጣ ያዘችው ።

"እንዴ ... ሰኢዶ ምን ነካህ ... በቃ በቃ ... እንውጣ አሁን ማውራት የምትችሉ አይመስለኝም ። ይቅርታ ዶክተር ሲራክ ..."

ሳንቾን ይዛ ልትወጣ ስትገትተው፣ "ደግሞ ... ይሄን ብሎ ዶክተር ... ዶሮ ራት ..." ሲራክ ንዴቱን ጥርሱን ነክሶ ዋጠና ዝም አለ ። ሳንቾን ወደ ራሷ ቢሮ መስዳ ትነሽ አረጋጋችው ። ሲራክን እንድታናግረው ሲስተር ዘቢባ ቢሮ ሄዳ፣ ነገሩን ባጭሩ ከረቻት ። ሲስተር ዘቢባ ቢሮው ስትገባ፣ ሲራክ በንዴት ጦፎ ወዲያ ወዲህ ይላል ። ትነሽ ተቀምጣ ካረጋጋችው በኋላ ይዛው ወደ ውጪ ወጣች ። ካፈው አካባቢ ካለ ዛፍ ር ተቀምጠው ከግማሽ ሰዓት በላይ አዋራችው ። ክሊኒኩ ውስጥ እየተፈጠረ ያለውን አለመግባባት እንዴት መያዝ እንዳለበት አንዳንድ ምክሮችን ለጥታው፣ ስሜቱ ሞርገቡን ስታውቅ ወደ ቢሮ ተመለሱ ።

ቢሮው ከገባ በኋላ ሀመምተኛ ስላልነበረው ቴሌቭ ብሎ ሲያስብ ቆየ ። ሌላሠውም ... ምስጢርም ... ሳንቾም ... ሁሉም ከሲስተር ዘቢባ በስተቀር መሸነፍ ያለባቸው፣ ግስቱን ያላወቁ በእሳት የሚጫወቱ ቂሎች መሰለው ታዩት ። 'የራሳችሁ ምርጫ ነዉ ... ካሁን በኋላ እኔ ሲራክ አይደለሁም' ብሎ ዛተና መመጫወት ከማይችለው ፒያኖ ሪት ተቀመጠ ። ምን ማድረግ እንዳለበት አያስላስለ፣ ስሜትም ትርጉም የማይሰጥ ዝበርዝቅርቅ ያለ ነገር መጫወቱን ቀጠለ ። የፒያኖው ድምጽ ከምስጢር ቢሮ በደንብ ሰሚሰማ ምስጢርና ሳንቾ ተያይተው ... ውስጥ ይሰማል።

"አሁን ምናለ ... ሌላውን ለመሆን ከመሞከር ራሱን ቢሆን ..." ስትል ፣

"ሌላውን መሆን እንደማይችል ቶሎ ካልገባው ... ሲራክንም ስለማይሆን ሁለቱንም የማይመስል ሌላ ሰው መሆኑ እይተርለትም ። ይሄ ከምኑ የተጣላ የሚሉት ዓይነት ..." አለ ሳንቾ ፣ ለመሄድ እየተነሳ ።

ሲራክ በበኩሉ የጥበብ ችሎታውን ሳይሆን የንዬት ስሜቱን በፒያኖው ቁልፎች ላይ እያሳረፈ ... በውስጡ የተደበቀውን ... እስከዛሬ ለመውጣት ዕድል ያላገኘውን 'ሌላ ሰው' ታስሮ ከተደበቀበት የልቡ ዋሻ ሊለቀው ትግል ላይ ነበር ። 'የገረድ ልጅ ... ባጃጅ ራስ ሁላ ... ሙንቻ ባይኖረኝ ... ሁልሽንም ተራ በተራ የሚያንበረክክ እዚህ ውስጥ ያለውን ስታዪ ፣ ሲራክ ማን መሆኑን ታውቂያለሽ ...' አለና ሌባ ጣቱን ጆሮ ግንዱ ላይ ደግሞ ፈግግ ብሎ ተነሳ ።

@OLDBOOOKSPDF

33

"ኒስተር ... ሰውዬውን እኮ ብታውቂው ነገሩ ይገባሽ ነበር ... ዶክተር ሌላ ሥዩሉበት ... ከሱ በቀር እዚህ ከሊኒክ ማንንም ማየት እንደማይችልና ... እሱ እዚ ሆስፒታል እንደሌለበት በግልጽ አስረድቶታል። እሱ ከመምጣቱ በፊት ድንገተኛ ችግር ካጋጠመው፣ ወይ የመንግሥት ሆስፒታል አለበለዚያም ሌላ ቦታ ነዚሄድ በደንብ አስረድቶት ተስማምቷል" አለች ምስጢር፣ የማስረሻን መታየት ሀተታወች።

"ሚስጥርዬ ... ይገባኛል እኮ ... ግን ደግሞ ሰው ጎራሲን ላጠፋነው ... የምገድለው ሰው እሰ ... ገደል ገደል የሚለኝ ድምፅ እሰማለሁ' እያለ እዚህ አትታይም ብለን ማዘዝ አንችልም። በዚያ ላይ ሰውዬው የኛ ሀመምተኛ ነው። ካርድ ከፍሉን እኮ የገደለገሩ ነው ያቀመው። ቢያንስ እስኪ ዶክተር ሲራክ ባሜሩ ይየውና ችግሩ የምር ከሆነው ወደ አማኑኤል ሪፈር ያድርገው። አንቺ እኮ ምንም ማድረግ የለብሽም ... እሱ እስኪሄድ ድረስ ወይ ወጣ በዪና ተመለሺ። ጨንቆኝ እኮ ነው የኔ ቀንጮ ... እስከ ሚሄዱበት ድረስ የምታዪው ሰው አለሽ እንዴ?"

ሲራክ ይየው የሚለው ሐሳብ ደስ ባይላትም ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌለ ስታስብ። "አይ ቲንክ ለጊዚው ምንም አማራጭ ያለን አይመስለኝም ... እኔ እስከ ሚሄዱበት ድረስ ወጣ ብዬ እመለሳለሁ። ዶክተር ሌላ ሲመጣ ሁሉንም እንነጋገራለን። ዶክተር ሲራክ ገብቷል እንዴ?" ከኋላዋ ያለው መንበር ላይ ዘሞ ብላ ተቀምጣ ፊቷን ወደ ግራና ቀኝ ራዕን አወዛወዘች።

"አዩ አም ሶሪ ... የኔ ቀንጮ ... እስኪ ቀይ ልደውልለት ..." ብላ፣ ስልኩን ዘይዉል ወዲያው አነሣው።

"ሂይ ሲስተር ... ሰላም ነው ... ይቅርታ ቅድም እኮ ከበሽተኛ ጋር ሆኜ ማንሣት አትችልኩም። ልክ ልደወልልሽ ስል ነው።" ሁኔታውን አስረድታው ሕመምተኛውን እንዲያይላት በልመና አይነት ጠየቀችው።

@QUEBOOOKSPDF

"ማን ነው ስሙ? ቻርቱን ማየት እችላለሁ እንዴ ከማየቱ በፊት? ምክንያቱም ... ዶክተር ሌላ ያየው ከሆነ ... የሱን ፕላንና ሃሳብ ማወቁ ይጠቅመኛል።"

"ስሙ ... ማስረሻ ይባላል ...ዶክተር ሌላ ከሱ ውጪ ማንም እንዲያየው አይፈልግም። ያው ምንም አማራጭ ስለሌለንና የሱፍቲ ጉዳይ ስለሆነ ነው ..." አለች፣ ጭንቅ ባለው ድምፅ። ማን እንደሆነ ወዲያው አወቀው። የሚፈልገው የአደን ሚዳቋ አፍንጫው ሥር እንደመጣለት የራበው ነብር ውስጡ ቦረቀ።

"ልዘ ነው ይገባኛል ሲስተርዬ ... ካርዱን ማየት ከሌለብኝም ምንም ችግር የለም። ዋናው ... ደህንነቱን ማረጋገጥና ለራሱ ወይ ለሌሎች ስጋት የሚፈጥር ከሆነ ደግሞ ፖሊስ ጠርተን ወደ አማኑኤል እንልከዋለን" ሲል፣ ቀለል ብሏት ተንፈስ አለች።

"በቃ ... እሱን ነው የምልህ ... ቻርቱ ላይ ምንም ይሄ ነው የሚባል የተጻፈ ነገር የለም። ከእንቅልፍ ኪኒን በቀር ሌላ መድሃኒትም የተጻፈለት አይመስልኝም። እሱ የሚለው ... ራስህን አጥፋ ... ሰዎችን ግደል ግደል የሚል ድምጽ ምናምን ይሰማኛል ነው" ስትለው፣ 'ታሪኩንማ አስከ ጥግ አንብበነዋል' አለ በልቡ።

"ግዴለም በቃ እንግዲያውስ ... ቻርቱንም እሱንም ትልኪልኛለሽ?" አሏ ራሷ አብራው እንደምትወጣ ነግራው ስልኩን ዘጋችው። ሲስተር ዘቢባ ማስረሻን አስከትላ ወደ ሲራክ ቢሮ ስትገባ፣ ምስጢር ደግሞ መኪናዋን አስነስታ ከግቢው ወጣች።

"ሲስተር እኔ ከዶክተሩ ጋር ለብቻዬ ማውራት እችላለሁ?" አለ ማስረሻ፣ ሁሉም እንደዶፈረሱ ያሉትን ትንንሽ አይኖቹን እያጉረጠረጠ። አጠቃላይ ሁኔታውን ሲያየው ትንሽ ፍርሃት ቢያድርበትም፣ ሊያወራው የፈለገውን ጉዳዮች እሱም ለብቻው ማውራት ስለፈለገ፣ የርሱን መልስ የምትጠብቀውን ሲስተር ዘቢባን ረጋ ባለ ድምፅ፣

"ግዴለም ... ለብቻ ላውራው" ብሎ፣ ባይኑ ምልክት ሰጣት።

"እሺ ... ምንም ችግር የለም ... ዶክተር ከፈለክን እዚሁ ቅርብ ነን" ብላ፣ በራፍ ላይ መሆኗን በምልክት ነገረችው። ከወጣች በኋላ ድንገት ችግር ቢፈጠር በማለት፣ አትክልተኛውን አስጠርታ የቢሮው በር ላይ ተቀምጠው መጠበቅ ጀመሩ።

"ይቅርታ ዶክተር ስልክ እንዳይረብሽን ... ላጥፋት ..." ብሎ፣ እንደ ውልጊዜው ስልኩን አጥፍቶ የድምጽ መቅጃውን ከፈተና የዶረት ኪሱ ውስጥ አስቀመጠው።

"ጥሩ ነው ..." ከመጣበት ጉዳይ ጀምሮ ከሌላሠው ጋር ያወሩትን ነገሮች፣ ከምስጢር ጋር ስላላው ጥልቅ የፍቅር ስሜትና ሙሉ ታሪኩን ቀስ በቀስ አናዘዘው። ሲራክ ብዙ የፈጠራ ተመሳሳይ ታሪኮችን እየነገረው፣ ጽናቱና ትዕግስቱ ከሰው እንደት ሁሉንም ነገር ስራሱ ጥቅም ሊቀይራቸው እንደሚችል ልቡን ከፍ እያደረገ መከረው። ከሌላሠው ጋር ያለውን ከፍስ ጊዜ እንዲቀጥል፣ እሱን ማግኘት ከፈለገ ግን በሰልክ፣ ካስፈለገም በውጪ በአካል ሊያገኘው ፈቃደኛ እንደሆነ ነግሮት የግል ስልኩን ሰጠው።

@OLDBOOOKSPDF

ዶክተር ሲራክ ባንድ ቀን የህመሙ ሁሉ መድኃኒትና የሰቃዩ ፈውስ ሆኖ ታየው። ከዚህ በኋላ ከሲኒክ መጥቶ መረበሹና ሌላሠው እስኪመጣም ካልታየው ጫለቱ በምስጢርም ዘንድ የበለጠ እንድትሸሸውና እንድትፈራው የሚያደርግ ጉዳይ ስለሆነ፣ ለርሱም ባያደርገው እንደሚሻል መከረው። ዶክተር ሌላሠው እስኪመለስ ድረስ፣ ሁለተኛ ከሲኒኩ አካባቢ ድርሽ እንደማይል ምሎ ተገዝቶ ቃል ገባለት።

ከአርባ ደቂቃ በኋላ እየተሳሳቁ ተያይዘው ወጡ። እርሱንም ሲስተር ዘቢባንም አመስግኖና በሰላም ወደ ቤቱ ሄደ። ሲስተር ዘቢባን ጪምሮ የከሲኒኩ ሰራተኞች ሁሉ ያዩትን ማመን አልቻሉም። ሲስተር ዘቢባ ሲራክ ጮበዝና የተለየ ችሎታ ያለው ሳይኪያትሪስት ነው የሚለውን እምነቷን አጠናክረላት። ሲራክም በሠራው ሥራ ኮራ ብሎ፣ ለፅቅዱም ሁነኛ የሆነ መሳርያ እጁ ውስጥ እንደገባ እያሰበ፣ ቱቱን ሁሉ ውስጡ ለደንቅ ዋለ።

ሲስተር ዘቢባም ከሲራክ ቢሮ እንደወጣች ለምስጢር ስትደውል አታነሣም። ትንሽ ቆይታ መልሳ ደወለችላት። "ሲስተር ... ይቅርታ እየነዳሁ ነበር ... እንዴት ሆናችሁ?" አለች፣ ጉጉት ባዘለ ድምፅ።

"ሰላም ነው ... በጥሩ ሁኔታ ሀንድል አድርጉት ... ሆስፒታልም ሪፈር ማድረግ ላያስፈልገን ... ዶክተር ሌላሠው ከሦስት ቀን በኋላ እንደሚመጣ አስረድቶት ... ተረጋግቶ ወደ ቤቱ ሄደ"

"እሀ ጥሩ ነው ... ምን አወሩ ... አብረሻቸው ነበርሽ?"

"አይ ለብቻዬ ነው ዶክተሩን የማናግረው ስላለ ... ለብቻው ነው ያዋራው"

አንዳች ነገር ውስጧን ቅር አለው። "እሀ ... ብዙ ቀዩ ወይስ...?" አለች፣ ቅዝቅዝ ባለ ድምፅ።

"እም ...ም አዎ አንድ አርባ አምስት ሃምሳ ደቂቃ አልቀዩም ብለሽ ነው። ሲወሩ ብታዪ ... ያ አካኪ ዘራፍ ... ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል የነበረ አውሬ ... የተገራ ኮርማ ይመስል ... አንገብሶ እየተቅለሰለሰ ... አመስግኖ ነው የሄደው"

ነገሩ ለምስጢር ሊዋጥላት አልቻለም። ምን ብሎትና ስለምን አውርተው የማሸረሻን ልብ እንዳሸነፈው ጥርጣሬ ገባት። "የተባባሉትን ባውቅ ጥሩ ነበር ... ኢን አረ ኬዝ ... ዋናው ሰላም መፈጠሩ ነው" አለች፣ ሌላ ዘርገር ውስጥ ላለመግባት።

"ሚስጥርዬ ... ያው አንቺ ስለማይመስልሽ ነው እንጂ ኮ ... ዶክተር ሲራክ በጣም በጣም ጮበዝ ልጅ ነው። እኔ መቼም ዛሬ ደግሞ እንዴት ኢምፕረስ እንዳደረገኝ ~ቃላትም የለኝም"

"ይሁን ሲስተርዬ ... ጉብዝናው ስ ባልከፋ ነበር"

"ምኑ ነው የከፋው ታዲያ?" ውስጥ ለውስጥ ስለተዋወቁ እሷ ሳቀች። ከሰዓት በኋላ እንደምትገባ ነግራት አመስግናት ተሰናበቱ። ደጋግሞ ሲደውል ስለነበር ሳንቾ ጋ እመለሳለች። የሆነውንነገርና ከሲራክ ጋር ያወሩትን ሁሉ ዘርዝራ ነገረችው። የሲራክን በማስረሻ

ጉዳይ ውስጥ መግባት አልወደዱትም። ካለበት ቦታ ሩት ስላልነበረች ወደዚያው ሂጻ ቡና አዘው በጉዳዩ ላይ ሊነጋገሩ ቀዩ። በመሃል እናቷ ደወሉ።

"ማሚዬ ካሳንች ጋር ነን ... ለምሳ ቤት እንምጣ እንዴ?"

"ውይ ጥሩ ነበራ። ቀንጁ የትግራ ሽሮ አለ። ሳንችዬም ናፍቀኛል ... እጠብቃችኋለሁ" አሉ፣ ደስ ብሏቸው። ወይዘሮ ኤደን ሳንቾን እንደ ልጃቸው ነው የሚያዩት። ጨዋታና ቁም ነገሩን፣ ርጋታውንና ጠንካራ የስራ ሰው መሆኑ ደስ ይላቸዋል። ለምስጢር እድሜዋን ሙሉ ያጣችውን ወንድም ሆኖላታል ብለው ስለሚያምኑ ቤተኛ ሆኗል።

"ሳንችዬ ... ለምን እንዳንዴ ልጆቹን ይዘሃቸው አትመጣም? ... ይሄ ኮቤታቸው ነው ... መጥተው ይጫወቱ ... ዘመድ ይናፍቃቸዋል እኮ ... ቅዳሜና እሁድም መጥተው እዚህ ይከረሙ ... ቤቱ እንደሆነ አገር ነው" አሉ፣ የምላ ገበታው እየተነሳሳ።

"እሺ ትዬ ኤደን ... አሁን ፈተና ላይ ናቸው ብዬ ነው። ሲጨርሱ አመጣቸዋለሁ።" ምስጢር ሁለቱን ትታቸው ጓዳ ገብታ ስልክ ስታወራ ቀይታ፣ ልብሷን ቀያይራ ሌላ ሰው መስላ መጣች።

"የት ጠፋሽ ልጄ ትተሽን ... ከሰዓት ሥራ እገባለሁ ያልሽ መስሎኝ ..."

"አይ ስልክ ይገር ስለነበር ነው ... ምነው? ... ሥራ የማልገባ እመስላለሁ እንዴ?" አለች፣ ቀሚሷን ሳብ ሳብ እያደረገች።

"አይ ስብሰባ ወይም ለየት ያለ ፎርማል ነገር ያለብሽ ይመስላል አለባበስሽ" ብለው፣ ሳቅ አሉ።

"ልቀይረው እንዴ ... ቅድም የለበስኩት ቀሚሴ ቡና ተጠባጥቦበት እኮ ነው" ብላ፣ ተራ በተራ ስታያቸው ትንሽ ቀላልደውባት በዛው ጸናች።

ወደ ክሊኒክ እየተመለሱ፣ "ሰሊዶ ግን የዚህ ክሊኒክ ነገር ምን ይመስልሃል? ... ዶክተር ሌላስ ቢሆን ቤተሰቡን እዛ አድርገ እስክ መቼ ይዘልቃል? ንጹሕ እንደሆነ ወደዚህ አገር መምጣቱን አሻፈረኝ እንዳለች ነው። አልፈርድባትም፣ እኔም ብሆን የማደርገው አይመስለኝም። እሱ ከሌለ ደግሞ ... ይሄው ገና በሦስት ሳምንት ውስጥ ቤቱ ሲኦል ሲሆን ምንም አልቀረውም" አለች፣ ፊቷ ላይ ስጋትና ጥርጣሬ እያንጸባበቀ።

"እኔንኛ ሚስጥር ... ልጁ እንኳንስ ዶክተር ሌላን ተክቶ ሊሰራ ... አይገባኝም ... ዶክተር ሌላ ደግሞ ሰለርሱ በጣም የተጋነነ እመለካከት ነው ያለው ... ምን ብሎ እንዳሳመነው አላውቅም። እስኪ ለማንኛውም እሱም ይምጣና እናያለና። ለነገሩ ችግሩ ከእሁኑ መፈጠሩ መጥፎ ነገር አይደለም።"

"ታውቃለህ ... ሲስተር ራቢ እኮ ... ያለ ሲራክ ሰው ያለ አይመስላትም። ዛሬ ራሱ ... በቃ ... ሰውዬውን አስደስቶ በሰላም መሸኘቱ፣ ለሷ የሲራክ ችሎታ ማረጋገጫ ነው። እኔንጃ ... ነገሩ ብዙም አላማረኝም ... የሆነ ነገር ብሎትና የውሸት ተስፋ ሰጥቶት

@OLDBOOOKSPDF

ሥን አለበት። እንጂ ሰውዬው ... ባርባ ዶቂቃ አይደለም ... ባርባ አመትም የሚድን እንዳልሆነ የሚያውቅ ያቀዋል" ብላ፣ መሪውን ደጋግማ በቡጢ መታችው።

"ለጊዜው ምንም ብሎት ይሁን ... በሰላም ከዛ ቤት ወጥቷል። ዶክተር ሌላ ደሙ፣ ሁሉንም ነገር በግልጽ ተነጋግረን አንድ ነገር መደረግ አለበት። ከዶክተር ፅላጋር የገቡትን የሕክምና ስምምነት አፍርሶ ነው አይደል ቡራ ከረዩ ሲል የዋለው?" ይለኢክ ሊደርሱ ሳንቾ አስቸኳይ ሥራዎች ስለነበሩት፣ በቀጥታ ወደ ቢሮው ሄደ። እሷ ደግሞ ወደ ካርድ ክፍል ሄዳ፣ ያሏትን የምክር ባለቀጠሮዎች ቻርቶች ይዛ ወደ ቢሮዋ ፀታለፍ ከሲራክ ጋር ተገጣጠሙ።

"ሄይ ... ዶክተሩ ... ሲስተር ነገረችኝ ... ነገሩን በሰላምና በጤና ማኔጅ እንዳረከው። በጣም ታንክ ዩ ..." አለች፣ ካንገት በላይ በሆነ ፈገግታ።

ጠዋት ካያት ተቀያይራና አምራ ሲያያት ድንግርግር ብሎት፣ ምላሱን እያወናከፈው፣ "በጣም አምሮብሻል ... ምን ተገኘ እንደዚህ ዝነጣው ..." ሲል፣ ሳቅ አለችና፣

"ያን ያህል ... ቡና ስጠጣ ተደፋብኝና ቤት ለምሳ ሄጄ ስለነበር ... ከጸዶቁ አፅቀር ብዬ ነው።" ከሳንቾ ጋር እንዴ ነበሩ መኪናዋን ስታቆም በመስኮት አይቷታል። እሱ ከማስረሻ ጋር ሲታገል እነሱ ሲያሾፉበት ቀይተው የመጡ መሰለው።

"ያ ... ሰውዬውን አይቼው ነበር ... ግራ የገባው ነገር ይመስላል። እንዲረጋጋ ለማድረግ ትንሽ ጊዜ ወሰደብኝ። ዶክተር ሌላ እስኪመጣ እዚህ መምጣትም ሆነ ሞታየት እንደማይችል ያመነ ይመስላል። ራሴን አጠፋለሁ ምናምን የሚለው ያው አቲነሽን ለማግኘት ነው። ለማንኛውም አርባ ዶቂቃ ያህል እንዴ ሀዳን እሱን ሳባብል ቀይቼ መጨረሻ ላይ ቁናኝ መሰለኝ" አለ፣ ነገሩን ቀለል አድርጎ።

"በጣም ትልቅ ሥራ ነው የሠራኸው ... ታንክ ዩ ..." ብላ፣ ልትሄድ ስትዞር፣

"ሻይ ቡና ..." አለ፣ አብራው እንድትቀይና ተጨማሪ ሊያወራት ፈልጎ።

"ውይ አሁን ጠጣሁ ... ደግሞ አስራ አምስት ዶቂቃ ናት ያለችኝ ... ባይሆን ዐመሃል ጊዜ ከተገኘ ቢሮህ ብቅ እላለሁ። ታንክ ዩ በድጋሚ እሺ ..."

"ኮሩ ... ኧረ ምን አደረኩና ..." ብሎ፣ ወደ ዶክተር ሌላሠው ቢሮ ገባ።

ጥቂት ሕመምተኞች ሲያይ ቀየ። ብዙ ጊዜ መቅረት ወይ ማርፈድ የሚያዘወትር ሕመምተኛው ስላልመጣ፣ ከመጻሕፍቱ መደርደሪያ አጠገብ ካለው ተወዛዋዥ ወንበር ላይ ደገፍ ብሎ ተቀመጠ። ራሱን ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየናጠ ማሰብ ጀመረ። የሚስጥርን ንቀትና የውዳሴን ንዴት ... የጎሊናን ፍቅርና የሳቢላን ችግር ... የሳንቾን ንፅህትና የማስረሻን ስሜት፡ ተቃጣጥሮ፣ ሁሉንም የእቅዱ ማስፈጸሚያና የድሉ ማደምደሚያ ለማድረግ የሚጠብቀውን አስቸጋሪ ጎዳና አውጠነጠነ።

@OLDBOOOKSPDF

'ከሁሉም በላይ የኔ ስኬት በሌላው ወንድቱ ላይ ይመሰናል' ብሎ ደመደመ።
'አንድ ሰው ሳይወድቅ ሌላ ሰው እንደማይልቅ ... ሰማይም ምድርም ... ትናንትም ዛሬም ... ሀይወትም ሞትም ... ከጥንት ጀምሮ ምስክሮች ናቸው' ብሎ ከራሱ ጋር ሲስማማ የቢሮው በር ተንኳኳ። ምስጢር መሰላው ዘሎ ተነሣ። ልብሱን አስተካክሎ በትልቅ ፈገግታ በሩን ሲከፍተው፣ የዘወትር አርፋጅና አስቸጋሪ ሀመምተኛው አጸፋ ፈገግታውን አንቦግቡጎ ለሰላምታ እጁን ዘረጋለት።

@OLDBOOOKSPDF

34

ሌላው ከአሜሪካ ሲመለስ መንገድ ላይ የጀመረው ጉንፋን ጠንቶበት ሦስት ቀን ሙሉ ካልጋ አልወጣም ። ንጹሕ ጋ ደጋግሞ ቢደውልም ለሁለት ቀን ስልኩን አልመለሰችለትም ። ጥቂት እንዳወሩ ስልኩ ሲቋረጥ መልሳ አልደወለችም ፣ ሲደውልም ስልኩን አታነሳም ። በመካከላቸው ያለው የልብ መሻከር ከጉንፋኑ በላይ እያሰቃየው ነው ። ምናልባት ንዴቷ በረድ ሲልላት ይሻላል ብሎ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሊያወራት ወሰነ ። ትንሽ ቀለል ሲለው አልጋ ውስጥ ጋደም እንዳለ በመስኮት የሚገባውን ቀዝቀዝ ያለ የክለዓት በኋላ ንፋስ እያጣጣመ ለማንበብ ሞከረ ። ደረቱን እየፋቀ ካስቸገረው ደረቅ ሳል በቀር የህመሙ ስሜት ጋብ ብሎለታል ።

"ሌላዓለምዬ ... ነቅተሃል?" የሠሩስትን የቡላ እጥሚት በትልቅ ጋቢጣ ይዘውለት መጡ ።

"እዎን አታቲዬ ...ቀየሁ እኮ ... ትንሽ ቀለል ስላለኝ ማንበብም ቻልኩ ዛሬስ"

ትራሱን አቃንቶ ደገፍ ብሎ ተቀምጦ ሲያዩት ደስ አላቸው ። "ውይ እመቤቴ ... ምን ይሳናታል ... ጎሽ ... እስኪ ይቺን ደግሞ ጣል አድርግበት ... አቅም ትሆንሃለች ። " ለእጥሚት እምብዛም ግድ እንደሌለው ያውቃሉ ።

"አዩ ... የበላሁት ምሳ እኮ እንደተቀመጠ ነው ... እጥሚትስ ይቅርብኝ"

"እንዲህ እንዳይመስልህ ... ቡላ ነው ... ደረትህን የሚፍቅህ ላይ ሄዶ ነው ልክክ የሚለው ... እንካ ልጄ ትኩሰ ትኩሱን ፉት በልበት ። " እጃቸውን እየዘረጉና አልጋው ጫፍ ላይ እየተቀመጡ ሊያቀብሉት እጃቸውን ዘረጉ ። እንደማይቀርለት ስላወቀ ተቀብሎ የግዱን መቀማመስ ጀመረ ።

"ንጹሕ ወርቅ ደውላ ነበር? ... ልጆቹስ እንዴት ናቸው?" አሉ ፣ ነገሩን እንዴት እንደሚያነሱበት እየጨነቃቸው ።

"ትናንት ደውላ ነበር ... ደህና ናቸው ..." ተጨማሪ ጥያቄዎችን ላለመመለስ ይመስል አፉን በእጥሚቱ ለጎመ ።

@OLADBOOKS.PDF

"አሁን ትምህርት ቤት ሲዘጋ ... ለዝረምቱ አይመጡም እንዴ?" አሉ፣ ግንባራቸውን ወደ ላይ እየሸበሸቡ ።

"ንጹሕ የምትለው ... ልጆቹም የዝረምት ካምፕ መሄድ አለባቸው ... የተወሰነውን ጊዜ ደግሞ ከአያቶቻቸው ጋራ ማሳለፍ ይኖርባቸዋል ነው ። እሺም የምትወስደው ኮርስ ስላላት መምጣት አልችልም ብላለች ።" ፊቱን ሞምድድ አድርጎ ግማሽ የደረሰውን አጥሚት ይብቃኝ ብሎ ሰጣቸው ።

"እኔ የምለው ሌላለሜ ... ይሄ ነገር እንዴት ነው የሚሆነው? ... አንድ ቤተሰብ ተከፍሎ ሁለት ሀገር መኖር ይቻላል እንዴ? ለልጆቹስ ቢሆን ለናንተም ጥሩ አይደለም ... ነፋሰም እኮ በቀዳዳ ነው የሚገባው ።"

"ያው ብዙ ተነጋግረን ነበር ። ግን ምንም ልንግባባ አልቻልንም ። እሷ ፈጽሞ በምንም ዓይነት መንገድ ይሄንን ሀገር ልትወደው አልቻለችም ። እኔ እዚህ ለምሰራው ሥራም ያን ያህል ግድ የላትም ። ያለው ብቸኛ አማራጭ የኔ ወደዚያው መመለስ ነው ። በዚህ ሁኔታ ብመለስ ደስተኛ እንደማልሆን አውቀዋለሁ ። አልመለስም ካልኩ ደግሞ ቤተሰቤን ማጣቴ ነው ። ስለዚህ እስኪ ትንሽ ላስበው ብዬ ነው ... የመጣሁት ።" በተከታታይ ስላሳለው ከላይ ከላይ እየተነፈሰ ገዘም አለ ።

"እኔን እናትክን ... አይዞህ ... እስኪ ትንሽ አረፍ በልበት ። አይ ልጄ ሁሉ ቀሪ ነው ። ምንም ቢሆን ቤተሰብ እንደሁ ቤተሰብ ነው ። ሌላውን የትም ሆኖ ማድረግ ይቻላል ። የዚህ አገር ችግር እንደሁ አንተ ብትኖርም ባትኖርም እንደ ሞላሎ ተራራ ተኩፍሶ ይኖራል ። የትም ሀረሀ መቼም ብትመጣ የትም አይሄድብህ ። ደግሞስ አንተ ብቻ ነህ እንዴ ያለኸው? ሌላውም ሰው የድርሻውን ያድርግ ... ዕዳ የለብህ ከዚህ በላይ ... አንተ የምትችለውን ጥረኸል ። ደግሞ ለዚህ ምስጋና ቢስ ሕዝብ ..." የግዱን ፈገግ አለና ዓይናቹን ጨፍኖ ገዘም አለ ።

"ምነው አመመህ እንዴ ..." አሉ ፣ ፊቱን እያባበሱ ።

"አይ አታቲዬ ደህና ነኝ ... ያልሽውን እያሰብኩ ነው" አለ ፣ ፊቱ ላይ ያለውን እጃቸውን በእጁ ያዝ አድርጎ ።

"ታዲያ ምን አሰባችሁ? ይሄ ንፋስ ደግሞ ብርድ እንዳያስመታህ ..." ብለው፣ መስኮቱን ሊዘጉ ተነሡ ።

"አይ አይ አታቲ ተዪው ... በጣም ነው ደስ የሚለው" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ ። "በቃ እስኪ እንድ ሦስት ወር ቀይቼ ፣ ከቻልኩ ከሊኒኩንም መልክ መልክ አስይዤ ... ካልሆነም ዘግቼውም ቢሆን ለመመለስ ነው የማስበው ። አስፈላጊ ከሆነ ባመት እንዴ ላንድም ለሁለት ወርም ቢሆን እየመጣሁ የምችለውን አደርጋለሁ ። ልክ ነሽ ፣ ከቤተሰብ አይበልጥም ።" ፊቱ ላይ ያለው ቅሬታ ቢያላዝናቸውም በውሳኔው ተደሰቱ ። ወዲያው ስልክ ሲደወለለት ፣ የአጥሚት ስኒውን ይዘው ወደታች ወረዱ ። ሲስተር ዘቢባ ነበረች ።

መታመሙን ስላላወቁ [illegible] አንጎላቸው ውስጥ ገብቶ ነበር ። እንምጣ ብትለውም አሻፈረኝ አለ ። ካንድ ሁለት ቀን በኋላ ቢሮም እንደሚገባ ነገሯት በግድ ሃሳቢን

አስለመጣት ። እሱ ባልነበረበት ጊዜ ከሊኒኩ ውስጥ የተፈጠሩትን ችግሮች፣ ጥያቄና አስፈላጊ የመሰሏትን ነገሮች ሁሉ በዝርዝር አሳወቀችው ። የማስረሻን ጉዳይ በትነገረው ሲራክን ማየቱ ደስ ባይለውም ፣ ነገሩ በስላም በመርገቡ እመስገኗት ፣ በመለነችው ውሳኔ ሙሉ ለሙሉ እንደሚስማማ ገለጸላት ። የሳንቾ ጥል የከረረ መሆኑን ነገረችው ። አፍ አውጥተው ባያወሩትም ፣ ምስጢር የግጭቱ የውስጥ መንስኤ መሆኗ ለሁለቱም ገብቷቸዋል ።

ስልኩን ከዘጉ በኋላ ለረጅም ጊዜ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የሄደበትን መንገድ ሊያስላስል ቀየ ። ሲስተር ዘቢባ የነገረችውን ግጭትና ሌሎች ችግሮች ሲያስብ፣ የከሊኒኩ ጉዳይ ችግር እንኳ ጥቅም የሌላው ባዶ ህልም ሆኖ ታየው ። የህመሙ ስሜት ተጨምሮበት ድብርት ግዙን ሞኖ ጨፈረበት ። ከልጋው ሳይወጣ የጀመረውንም መጽሐፍ መራት እሽቀንጥሮ ጣለና በጀርባው ተጋድሞ ሲተክዝ ሲቀዝም አመሸ ። ወደ ሦስት ሰዓት ማታ ላይ ሲራክ ጋ ደውሎ ባሚሩ አውርተው ፣ በማግስቱ ለእራት ሊገናኙ ተቃጠሩ ። ከምስጢርና ከሳንቾ ጋር ከማውራቱ በፊት ፣ ሲራክን ማዋራቱ የተሻለ ያላብ መስሎ ታየው ።

ጠዋት ሲነሣ የበለጠ ቀለል አለው ። የሻወሩን ውሃ ሙቀት ጨምሮ ታጠበ ። የጠዋት ቡናውን ሲጠጣ የበለጠ ሰውነቱ ፈታ አለለት ። የምግብ ፍላጎቱ ተዘግቶ ፣ የሚወደውን ፍርፍር እንኳን ነካክቶ ተወው ። ንጹህ ከገባ ጆሮር አንዴ መደወሏ ብቻ ላይሆን እንጸመመው ብታውቅም እንዴት እንደሆነ አለመጠየቋ ቢያስቀይመውም እሱም ለመደወል አልፈለገም ። ምናልባትም ባወሩ ቁጥር ሞቅሞቅና ክርክሩ እታክቷት ሊሆን እንደሚችል አሰበ ። 'ኡፍፍፍ ... እንግዲህ ምን ይደረጋል ... የመጣው ይምጣ ... ብደውልም ... ብሄድም ያው ነው ..." ብሎ ፣ ነገሩን ለመርሳት ሞከረ ።

በማግስቱ ከሰአት በኋላ ሂልተን ሳውና ገብቶ ፣ ጉሪና ጉንፋን ሲያንገላታው የከረመውን የጳገለ ሰውነቱን ሲያፍታታ ዋለ ። የተጠሮው ሰዓት እስኪደርስ ሎቢው ውስጥ የጀበና ቡና እየጠጣ ፣ ከመንገድ ላይ የገዛቸውን ጋዜጦች እያገላበጠ አየት አየት አደረጋቸው ። ከሲራክ ጋር ሲገናኙ ፣ እራት እየበሉ ፣ የሆነ ያልሆነውን ሲያወሩ ቆዩ ።

የአሜሪካ ጉዞው እንዴት እንደነበር ጠየቀው ። "አሪፍ ነበር ... ጊዜው ቡማም አጠረ ... ልጆቹም በጣም ተላቀቁ ... የመመላለሱ ነገር በጣም እየከበደ ነው ለሁላችንም ።"

"አሆ ... እንዲያውም እናንተ በጣም ገበዝ ናችሁ ... አውን ለክረምት ይመጣሉ አይደል?"

"አዩ ... ቢሆን ጥሩ ነበር ... የሚችሉ አልመስለኝም ... ከጥቂት ወር በኋላ አኒው መሂድ ሳይኖርብኝ አይቀርም ። እንተስ እንዴት ነበር ሦስቱ ሳምንት?" አለ ፣ በጁ የያዘውን ጸቦ ቀርሶ ፊቱ ባለው አዋዜ ሚን አድርጎ እያጠቀሰ ።

"ምን ባክህ ... ድብልትልቁ ወጥቶ ነው የከረምነው ... ምን ያህል እንደነገሩህ አላውቅም ...ካሰብኩት በላይ ወጪ ሆኖብኛል ። ግን ብዙ ያልፈናው ፣ ምን ያህል እንደሰማ እርግጠኛ ስላልነበረ ።

@ወሊሞ ቤተ መጽሐፍት ebooksPDF

"አይ ... ማንም ምንም የነገረኝ ነገር የለም ። ትናንት ማታ ግን ከሊስተር ጋር ተደዋውለን እንዳንድ ግዜዮች እንደነበሩና አንድ ለቲራፒ ሳየው የነበረ ሀመም ተሻ አምባ ላሮ ፈጥሮ በጥሩ ሁኔታ እንደሸኘኝው ነው የነገረችኝ ... ሀት ኢዝ ኦል ..."

"የሚገርም እኮ ነው ... እንተ እያለህ ሥራቸውን ሰዮ ለዮ ብለው የሚሠሩ ዘታች እስከላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ ኮ ናቸው ያመጹብኝ ። መጀመሪያ ላይማ ለሦስት ሳምንት ተወከልኩ እንጂ መፈንቅለ መንግሥት ያደረኩ መስሏቸው ነው እንዴ ብዬ እኔ ራሴ ፓራኖይድ ሆኜ ነበር ። በርግጥ በኔና በሳጌቾ መካከል መግባባት እንዶሌለ ሰለሚያውቁ አድቫንቴጅ ለመምታት የሞከሩ ሰዎች እንዳሉም ይገባኛል ። ግን መፈጠራን የጠላሁበት ጊዜ ነበር" ሲለው ፣

"ሪሲ ... ያንን ያህል?" አለ ተገርሞ ።

"ምን መሰለህ ... እኔም አሁን ሳየው ሁሉንም ነገር ባለበት ማስኪድ ነበር መለለኝ የሚሻለው ። ምናልባት እንዳንድ ነገሮችንም አይቶ እንዳላየ ማለፍ ነበር መሰለኝ የተሻለው መንገድ ። ሳላስበው ከሁሉም ጋር ተጠላለፍኩኝ ። ከሳጌቾ ጋራ እንኳን የራሴ ጥፋት ነው ... ሥልጣኔን እንዲያውቅልኝ ላልፍጪረጪር አልቀረሁም ። እሱም ጡንቻውን ሊያሳይ ተገብዞ ነበር ። ግን በዋናነት የኔ ነው ጥፋቱ ... ይቅርታም ልጠይቀው እያሰብኩ ነው ። "

ከፊቱ ተቀምጦ የሚያወራው ሲራክ አልመስልህ ብሎት በመገረም እየው ። "ዋው ... ሲራክ ... በርግጥ በሦስት ሳምንት ውስጥ ብዙ ነገር ያሳለፍክ ይመስላል ። ኢሜይል እኮ ብታደርግልኝ መረዳት እንችል ነበር ... ቢያንስ በሃሳብ" ሲለው በልቡ 'አይ መረዳት ...ሞኝህን ፈልግ ... ስለኔ የምታስበውን እሳምሬ አውታለሁ' አለ ።

በሌላሠው ላይ የተፈጠረበት ጥላቻና የበቀል ሰሜት እንዳይታወቅበት የሚችለውን ሁሉ ማድረግ እንዳለበት ወሰነ ። "እዪ ... አሁንማ ላስበው ጥሩው ነገር እሱ ነበር ። በዛን ጊዜ የኔ ሐሳብ ... በሆነ ባልሆነው ነገር ... ካለችህ ሦስት ሳምንት ላይ እረፍትህን በኛ ባዶ ንትርክ ላለማበላሸት ነበር ። "

"አይ ያንን ያህልማ መጪነቅ አልነበረብህም ። ማስረሻስ ምንድነው የሚለው?"

'የሚለውንማ አንተ ንገረኝ እንጂ የኛ ተመራማሪ' በሚል የልብ እግዐ ተሞልቶ ፣ "እኔም ብዙ አልገባኝም ... አንተ ታየው ነበር መሰለኝ ። ቻርቱ ላይ ብዙም ነገር አላገኘሁም ። ከነገረኝና ከሁኔታው እንደገባኝ ሚስጥርን ይወዳት ነበር መሰለኝ ካምፓስ እያሉ ። በታ ዴሉሽናል ነገር ይመስላል ... ራሴን ካላጠፋሁ ... ሰው ግደል ግደል ይለኛል ምናምን ብሎ ነው መሰለኝ ከሊኒኩ ውስጥ አምባላሮ የፈጠረው ። ኤኒ ዌይስ ... ያው እሰኪበታው አዳምጨው ፣ አንተም በሦስት ቀን ውስጥ እንደምትመጣ ነገርኩት ። ለስሚትና ለብሶቱ ጆሮና ሃዘኔታዬን በሰፈው ስለሰጠሁት መሰለኝ ፣ ደሀና ሆኖ ሄደ ። ከዛ ወዲያ አልመጣምም አልደወለምም ።"

"በከፍተኛ ብስለትና ፕሮፌሽናል መንገድ ነው በጊዜው የተፈጠረውን ችግር የፈታኸው ። ሲስተር ዘቢባም በጣም እሚያሥደስታት የነገረችኝ" ሲለው ፣ ሲራክ

@OLDBOOKSPDF

ዕልው 'የማስረሻ ችግር የኔ ሳይሆን የሚስጥርና ያንተ ነው ... የኔ ችግሮች አንተና ሳንቾ ናችሁ' እያለ በውስጡ አሾፈበት ።

ራታቸውን በልተው ሲጨርሱ ፣ ያመጣለትን የምክርና የሳይኮቴራፒ መጎንጮችን በተመለከተ በቅርብ የታተመ ጥሩ መጽሐፍ ሰጠውና ሌሎች ነገሮችን ሲያወሩ ቀዩ ። በግማሽ ክሊኒክ እንተያያለን ተባብለው ሲለያዩ ፣ ሌላው በሲራክ ሥራና ነገሮችን ባየበት እይታ ተመስጦ ነበር ። ሲራክ የሆዱን በሆዱ ይዞ የሚፈልገውን መፈ ያለ ግድፈት በሌላው ልቦና ውስጥ ፣ ከእራቱ ጋር ሲጠቀጥቀው እንዳመሸ አምኖ ደስ ብሎት ወደ ቤቱ ሄደ ።

ሌላው በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ክሊኒኩ ውስጥ የተፈጠሩ ግጭቶችንና ዘፈቶችን በማስተካከል ሥራ ላይ ተጠመደ ። ላብዛኛው ግጭት ሲራክ በራሱ የላራነትን በመውሰድ ያለምንም ማንገራገር ሳንቾን ጨምሮ ሁሉንም በግልም በህብለባዎች ላይም ይቅርታ ጠየቀ ። ይህም ችግሮችን ከታሰበው በላይና በፈጠነ ሁኔታ ስለፈታቸው ነገሮች ወደ ነበሩበት ሁኔታ የተመለሱ መሰለ ። የሲራክ መለሳለስና ልበ ምሉሰ መሆን ፣ ሲስተር ዘቢባ በሲራክ ማንነት ላይ ያላትን እምነት አንድ ደረጃ እንዲጨምር አድርጓል ። በሳንቾና ምስጢር ውስጥ ግን አዲስ ጥርጣሬን መጫሩ አልቀረም ። ሌላው የሆነውን እንደሆነው ከመውሰድ ውጪ ፣ በውስጡ ስለ ማንም ያለውን እምነት አልቀየረም ።

ከምስጢርና ከሳንቾ ጋር በመጣ በስድስተኛው ቀን ቅዳሜ ለቁርስ ተገናኙ ። ከቁርስ በኋላ ለገናና ሽ አባትና እህት ከነንዋይ የተሳከላቸውን እቃዎች ለማድረስ አብረው ሄዱ ። የተከራዩላቸው ቤት ግቢ ያለውና በመጠኑም በጥራቱም ላካባቢው ጥሩ የሚባል ነው ። ግቢ ሲገቡ የገናና ሽ እህት ልጆች ተሯሩጠው ተቀበሏቸው ። ወደ ውስጥ ከገቡ በኋላ ሳሎኑ ውስጥ የተዘረጋ የሸቦ አልጋ ላይ የገናና ሽ አባት ጋቢያቸውን ተከናንበው ጋደም ብለው ሲጠብቋቸው ደረሱ ። ጉዝጓዝ ተነስንሶ ረከቦት ቀርቦ ሲቀላ ብረት ምጣድ ላይ ታጥቦ የተሰናዳው ቡና የአንሱን መድረስ ነበር የሚጠብቀው ።

የገናና ሽን ልጆች ፎቶዎችና ቪዲዮዎች ሲያዩ ፣ ሕፃናቱ ብቻ ሳይሆኑ ትልልቆቹም ልባቸው በአሜሪካ ፍቅር ተነደፈ ። ሁሉም እዛ የሚኖር ባለጠጋ ሰው መሰዶ 'ቢያሳድጋቸው' ከልባቸው ተመኙ ። ሕፃናቱ የተሳከላቸውን አዳዲስ ልብሶች ለብሰው ፣ የተሰጣቸውን ቸኮሌቶች ይዘው ፣ እነርሱም በተራቸው ጓደኞቻቸውን ለማስቀናት እየተሯሯጡ ከቤት ወጡ ። የገናና ሽ አባት ጉልበታቸውም ዓይናቸውም ደክሟል ።

ሰለ ገነትና እናቷ የሰሙት አዲስ ወሬ አለመኖሩን ፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ግን እያጣያየቁ እንደ ሆነ ለሌላው ነገሩት ። የጀመረው ክሊኒክም ሆነ የነበት የመግኘቷ ተስፋ ደብዘዘበት ። የአባቱ አደራና የልጅቱ ናፍቆት ፣ የገነት መጥፋት እንቅልሽና የጓኡሕ ፍቅር ፣ እየተፈራረቁ ውስጡን ከግራ ከቀኝ አላጉት ። ቤተሰቡን የማትረፉ ጉዳይ በውስጡ አይሎ ቢያሸንፍም ፣ የተፈጠረበትን የመሸነፍ ስሜት ግን ሊቀበለው አልቻለም ። ሳንቾ መኪኒላ አነባበቢ መቅረት ስለፈለገ እሱን እዚያ ጥለው ከምስጢር ጋር መኪናዋ ጋ ሊያደርሳት እየሄዱ ፣

@OLDBOOOKSPDF

"እዪ እውንስ ብዙም ተስፋ ያለው‌ም አይመስልም። ምናልባት ያኔው‌ኑ አገር ለቀው ሄደው ይሆናል እንጂ እስካሁን ቢኖሩ ይገኙ ነበር። አይ ሆፕ ... ባሉበት ሰፍራ ደህና እንደሚሆኑ ..." አለ፣ ተስፋ ሊቀርጥ በቀረበ ድምጽ።

"አይ ዶክተር ሌላ ... ምንም አይታወቅም ... ተስፋ መቁረጥ የለብህም። ይሄኔ ኮ እዛው ጎረቤት ወይም እንዱ ጋ ተወሽቀው ሊሆን ይችላል። ትገ ይልሃል ፎረስት ጋምብ ላይ ... 'ህይወት በማሸጊያ ካርቶኑ እንዳለ ቸኮሌት ናት ... የትኛዋ ቁራጭ እንደምትደርስህ አታውቅም ... ትል ነበር እናቴ' የሚለው ... ምናልባት የመጪረሻዋ የዕድል ቁራጭ እነሱ ይሆናሉ ... አይታወቅም"

"ማሸጊያ ካርቶኑ ባዶ ሆኖ ከሆነስ?"

"ኧረ ... ገና መቼ ተከፈተና፣ ይልቅ የሂልተን ሚሊርኒ አምሮኛል ... ጊዜ አለህ እንዴ?"

"እም ... አክቸዋሊ ... ከሰዓት በኋላውን ምንም ዕቅድ የለኝም" ብሎ ወደዚያው አመራ። ከገን በኩል ካሉችው ካፌ ተቀምጠው፣ የቀረውን ከሰዓት በኋላ አብረው አሳለፉ።

በሚቀጥሉት ሳምንታት ሁሉም ነገር ወደ ቦታው ተመልሶ ሰላም የሰፈነበት መሰለ። ከንጹሕ ጋርም እንደ በፊቱም ባይሆን የተሻለ ቶሎ ቶሎ እየተደዋወሉ ማውራት ጀምረዋል። ልጆቹን አያቶቻቸው ጋር ትታ እሷ በጀመረችው ትምህርትና የቢዝነስ ሃሳብ እዛው ኦስትን እንዳለች ነገረችው። በነገሩ ባይሰማም ምንም ማድረግ እንደማይችል ስላወቀ ዝምታን መረጠ። በየሁለት ሳምንቱ እየሄዴች ታያቸዋለች።

ባለቢቱ ከሞተችበት ጓደኞቸው ጋር በየቀኑ ስለሚገናኙ ቅርርባቸው ጨምሯል። ልጁም ለንጹሕ የተለየ ፍቅር ስላላት እሱ ከተማ ውስጥ በማይኖርበት ጊዜ እሷ ጋ ነው የሚተዋት። የረጅም ጊዜ የቢዝነስ ልምድ ስላለው ቢዝነስ እንድትጀምር ያደፋፈራትም ... በማድጋው ላይ እያገዛት ያለውም እሱው ነው። ምናልባትም እርሱን ችላ ማለት የጀመረችው ከዚሁ ከወዳጃቸው ጋር ያላቸው ቅርርብ በመሃል ገብቶ ይሆን ወይ የሚል ሐሳብ በሰው መጣበት። በንጹሕ ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበት ለልቡ ፊት ሊሰጠው አልፈቀደም።

ብቻ ከአእምሮው ሊያወጣ ያልቻለው ሐሳብ በውስጡ ሲመላለስ ዘረመ። 'መሬት ብቻ ሳትሆን የሰው ልብም ያለ ሰው መናኛ እዳሪ ነው። ከልብ የራቀ ኪይንም የራቀ ነው። ልብ የኔ ያለው ሰው ሲርቀው አጠገቡ ያገኘውን ሌላ ሰው የራሱ እድርጎ ያስተናግዳል። ልብ የፍቅር ማግኔት ነውና የመያዶው ቢርቀው በቀረበው መጠኑ አይቀርም። የኔ ያለው ሰው የራቀው ልብ ሙሉ አድሮ የሌላ ሰው የሆነውን የራሱ ለማደረግ ያቀበቁባል። የልብ እና መሬቻ ቋንቋ ስሜት ላይሆን መተራረብ ነውና፣ ቢሆንም ለጊዜው ምንም ማድረግ አልቻለም።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 35 ፡

ድንገት የቢሮው በር ብርግድ ብሎ ሲከፈት ደንገጥ ብሎ ቀና አለ ሌላው። ዕድሜው አምስት ወይም ስድስት አመት የሚሆነው ልጅ እየተንደረደረ ወደ ርሱ ሲሮጥ አይተ ፈገግ አለ።

"ታዲያስ ማሙሽዬ ... ማንን ፈልገህ ነው?" ሲለው፣ አጠገቡ ደርሶ ቀም ብሎ አተኩሮ አየውና በመጣበት አካሁዋን ተስፈንጥሮ ወደ በሩ ሮጠና ሊወጣ ሲል ምስጢርና እናቱ ተከታትለው ገቡ።

"ይቅርታ ዶክተርዬ ... አምልጦኝ ኮ ነው ... ከምኔው በርሮ እንደመጣ ..." አለች፣ እናቱ ሽምቅቅ ብላ።

"ኧረ ... ችግር የለም ... ልጅ አይደል እንዴ ..." ብሎ ከመቀመጫው ተነስቶ ሰላም አላቸው። "እዛች ሶፋዋ ላይ ይሻላል መሰለኝ ..." ብሎ ተከታትለው ሲሄዱ፣ ልኮም የሱን እጅ ይዞ የሆነ ያልሆነ ነገር እየቀበጣጠረና እየዘለለ ተከተላቸው።

ወዲያው ፒያኖውን ሲያይ እጁን መንጭቀ በሩጫ ሄዶ ቁልፎቹን እየነካካ፣ "ፕ ... አሪፍ ፒያኖ ነው ... ያንተ ነው እንዴ ዶክተር...? አንተ ዶክተር አደለህ እንዴ... ፒያኖ ምን ያድርግልሃል...? ባቢ የገዛልኝ የኔ ፒያኖ ኮ ሚጢጢዬ ናት ... ካልጋ ላይ ወድቃ ግታ ተሰበረች ... በዚህ ልጫወትልህ?" ብሎ ጥያቄውን ሲያዘንብበት፣ እየሳቀ ወደእርሱ ቀርቦ አጠገቡ ቆመ።

"እሰኪ ተጫወትልኝ ... ምን መዝሙቃ መጫወት ትችላለህ?" አለና ብድግ እድርግ ታቀፈውና መቀመጫው ላይ አስተመጠው። ባንዲት ጣቱ 'ኤ-ቢ-ሲ-ዲ ..." የሚለውን የረዳል መማሪያ መዝሙቃ ተጫወውቶ ቀና ሲል 'ሞው ... ገበዝ ነህ። ኤ-ቢ-ሲ-ዲ ነው ... አይደል?" አለው። ሞንትላቱን በአምንታ ሲነቀንቅ "ሃይ ፋይቭ ... ገበዝ ልጅ" ብሎ፣ እጁቸውን አጋጨ።

@OLDBOOOKSPDF

ወዲያው በፍጥነት መቀመጫው ላይ ቀመጥ ተንጠራርቶ የንጹሀንና የልጅቱን ርቶ ብድግ አድርጎ፤ "ማናቸው እነዚ?" አለ ወደ ልጅቱ እየጠቆመ።

"እነሱ ልጆቼ ናቸው።"

"ይቺስ?" ብሎ ንጹሀን ሊጠቁም ሲመዘር ፍሬሙ ከጁ አምልጦ ወደቀና መሬት ላይ ወድቆ መስተዋቱ ተከሰከሰ። እናቱ በድንጋጤ በመብረቅ ፍጥነት ዘላ መጥታ እጁን ይዛ ወደ ራሲ ሰባ መስደቻው። ሚኮ ስር ገብታ ስትመዘልገው በእራታ ቢርመጎ አደባለቀው። ሌላውና ምስጢር እንድትተወው ቢለምኗትም እጁን ይዛ እየገተተች ወደ ሶፋው መስደቻው። ገም እንዲል ብትቆጣውም አልሰማ ብሎ ፊኙቱን ቀጠለ። ሶፋው ላይ ተቀምጣ ታቅፋ ወደ ደረቷ አስጠግታ ስታባብለው ቀስ በቀስ ገም አለ። እነሱ ሲያወሩ በጨረፍታ እንዴ ሌላውን እንዴ ምስጢርን ማየት ጀመረ።

ከናቱ ላይ ወርዶ ለመሄድ ትግል ሲጀምር፤ እጁን ጉያው ሙሰዋ ስታስገባ ሚኮን ስብስብ አድርጎ ሲያለቅስ፤ "በታ አርፊሀ ተቀመጥ አለበለዛ ቴንጥጥ ነው ..." ስትለው ፊቷን አይቶ ማምረሯን ስላወቀ ለጊዜው ባለበት ቀየ። "ይሄው ልህ ዶክተር ... በታ ሲነጋ ጀምሮ እስኪመሽ ይሄው ነው። የቤቱን እቃ ሁሉ ጨርሶት፤ የብረት ድስትና የኒኬል ሳሃን ብቻ ነው የቀረው። እኔ ኮ ምን አይነት የማያልት ባትሪ ሙሰው እንዳስ አላወቅም ... ምግብ አይበላ ... ለሙነቱም ይሄው ሲባባ ነው። ግን በታ መሮጥ ነው ... ያገኘው ነገር ላይ መንጠላጠል ... ክልጆች ጋር ተስማምቶ አይጫወት ... እትሙን አያውቅ መደባደብ ነው። እየው ፊቱን ካገኘው ነገር ሲጋጭ ተፈነካክቶ አለቀ እኮ። እኔ ኮ ሶስት ልጆች ከሱ በፊት አሳድጌያለሁ ... ለሙ መንታ ልጅ ማሳደግ ከባድ ነው ይላል ይሄ የብቻው ነው ... ሙያ አምላኬ ..."

ሳታስበው ያመለጣትን እምባ በነጠላዋ ጫፍ ጠራርጋ ሚንትላቱን ማባበሏን ቀጠለች። አጠገቧ ያለችው ምስጢር፤ ከጠረጴዛው ላይ ናፕኪን አቀበላችትና ትክሻዋን መታ መታ አደረጋ ልታጽናናት ሞከረች። "አይዞሽ ... እንዳንድ ልጅ እንግዲህ ይከብዳል ... እቤት ነው የሚውሰው ወይስ ትምህርት ቤት ገብቷል?"

"ያልሞከርነው ነገር የለም ዶክተር። የምንኖረው ኮንዶሚንየም ሙሰዋ ስለሆነ አባቱ መጫወቻ ቦታ ጠቦት ይሆናል ባይ ነበር። ስለዚህ ምናልባት ትምህርት ቤት ቢገባ፤ ሲዛለል ሙሉ ጽክሞት ስለሚመጣ ትንሽ ረጋ ይላል ብለን አስበን ነበር። ደህሞት ሃያሉን ስለሚጨርስ ትንሽ ጋብ ይል ይሆን ብለን ሕፃናት መዋያ አስገባነው። ወረም አልዋየ ... ክልጆች እየተደባደበና ከፍል ሙሰዋም እርፎ አልተመኖ ሲላቸው ትንሽ ከፍ ይበል ብለው ከሠላት ቦታ አስወጡት። በዛ ላይ የምትለውን አይስማህም ... በታ ሚንትላቱ እንደ ፈጣን ማሽን ያለማቋረጥ ሲሽከረከር ነው የሚውለው። አነሰም በዛ ያቺው የእንቅልፍ ስአቱ ናት እፎይ የምንልባት ጊዜ" ብላ ገም አለች።

"በሀጓንቱ እንዴት ነበር አስተዳደጉ ... እርግዝናውስ ላይ ችግር ነበር?"

"ኧረ ልክ በዘጠኝ ወሩ በሰላም ነው የተወለደው። ሠሲቻል በኖርማል ምጥ ነው የተገላገልኩት። ከስድስት ወሩ ጀምሮ ግን ንጭናጫ ነበር ... ሁለት ጎመት

@OLDBOOOKSPDF

እስኪሞላው ድረስ ምንም ሴላ የተለየ ነገር አልነበረውም። በግሩ መሄድ ሲጀምር ነው ... ለትያዙኝ አትክልዝሉኝ ማለት የጀመረው። የሱ ታላት አሰራ ሦስት ጎመጅ ነው። እሱን ስወልደው አርባ ሦስት አመት አካባቢ ነበርኩ ... እንዳንዴ እድሜዬ ይሆን ብዬም አስባለሁ"

-አይ እንደሱ ለማለት... የተረጋገጠ ምንም ነገር የለም ... በእርግጥ ከእድሜ ጋር ያንዳንድ ጄኑቲክ ችግሮች ሪስክ ይጨምራል። በቤተሰብሽ እንደሱ ዓይነት ከሚገጣው በላይ የመቅበዋበዋ ወይም ትኩረት የማጣት ችግር ያለው ሰው አለ?"

-"እረ ምንም ... እኔ የማውቀው ሰው የለም ... አባቱ ግን ታናሽ ወንድሜ ከሱ የበለ አገር ያቃጠለ ነበር ... ሲያድግ ሁሉንም ነገር ትቶ ታል ይላል። የሱ ወንድም ለእኔ እሁንም ቢሆን መቅኖ ቢስ ነው። የጀመረውን እንኳ ባግባብ የማይጨርስ ... በቃ ዐሣትና በሲጋራ ኃይል ነው ያሰው።"

"ቤቪስ ውጪም ቤትም ባህሪው ያው ነው? እንዲያው ትንሽ ረጋ የሚያደርገውና ልቦናውን ገዝቶ ሰክን እንዲል ለረጅም ሰዓት የሚይዘው ነገር ... ልብ ያልሽው ነገር አለ" አለ፣ እናቱ ላይ ያሸለበውን ልጅ በፈገግታ እያየ።

"ስእል መሳል ይወዳል ... ሴላ ኳስ ነፍሱ ነው ... ኳስ ግጥሚያ ኖሮ ከተከፈተለት ... እርባ እምስት ደቂቃ መሉ ልውስ ሳይል ነው የሚቀመጠው ... የማያውቀው ተጫዋችና ቡድን የለም ... ያሻንጉሊት ፊልምም እንደሀው ... ከሀ ውጪ የትም ይሁን የት ያው ነው ... እቤት ወንድምና እህቶቹ ፈንጣው ነው የሚሉት። ሴላ ትዝ አለኝ ... ለልጅ ቡና እንደማይሰጥ አውቃለሁ፣ ይዝርምሃል በተለይ እቦል ቡና ከኔ ላይ ወስዶ የጠጣ ቀን ሰክን ይላል። እኔ ሳውት ቡና ያትበጠብጣል ... እሱ ላይ ግን ረጋ ነው የሚያደርገው። ካልያገኘው ከሰኒ ሰኒ እያገላበጠ መጨለጥ ሁሉ ይወዳል ... ያው ከሰር ከሸሬ ስለማይጠፉ" አለች፣ እንደማፈር ብላ።

"የሚገርም ነው። ባጠቃላይ ከንገርሽኝና ካየነው ባህርይው በህክምናው ኤዲኤች.ዲ የምንለው ችግር ያለበት ይመስላል። እርግጠኛ ነኝ ሰሙን እንደምታውቂው ... ያው የእንግሊዝኛው ምህጻረ ቃሉ ሲፈታ 'አቴንሽን ዴፊሲት ሃይፐርአክቲቭ ዲስኦርደር' ... ሲሆን 'የትኩረት ጉድለትና ከልክ ያለፈ ትብጥብጥነት' በምንነት የሚታይበት ሰነ ልቦናዊ ችግር እንደ ማለት ነው" ሲል ቀበል አድርጋ

"በቃ ራሱ እኮ ነው ... የሚሰማህም አይመስልም እኮ ... ትብጥብጥነት እሱን አይገልጸውም ..." አለች፣ የልጇ ችግር ሰም ያለው በሽታ መሆኑ በራሱ መፍትሔ የተገኘለት ያህል ደስ እያላት።

"እና ይሄ ችግር የሚታየው ብብዛኛው በህጻናት ላይ ሲሆን ብዙዎቹ ሲያድጉ መሉ ለመሉ ባያተውቸውም እንኳን ቢያንስ መቅበጥበጡ በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል። ከልጅነት ደግሞ ብዙውን ጊዜ ችግሩ ጎልቶ የሚታየው ወንዶቹ ላይ ነው። ትናቶች የሚሉት ... በእንባላችን ውስጥ አንደንድ ትኩረትንና እርጋታን የሚቀጣጠሩ ክሮሱት ላይ ዶፓሚን የሚባል ኬሚካል ያጥራቸዋል። ያው እንቸ ነርሰም ስለሆንሽ

@OLDBOOKSPDF

በዶንብ ይገባሻል ። የምንሰጣቸው መድሃኒቶች ዶግሞ ባብዛኛው ስቲሙላንት ወይም አነቃቂ ስለሆኑ ገብተው የዶፓሚኑን መጠን ነው የሚጨምሩላቸው ወይም የሚያስተካክሉት ።

"ቡና ፣ ሜትና ሲጋራ በመጠኑም ቢሆን ዶፓሚንን የመጨመር ባህሪይ ስላላቸው ነው ፣ ይሄ ችግር ባለባቸው ሰዎች ላይ ተቃራኒ ተጽእኖ የሚኖራቸው ። ሜትና ቡናን ብዙ ሰው ለጥናትና ለመሳሰለ ስራ የሚጠቀምባቸው በተመሳሳይ መንገድ የትኩረት እቅምን የመጨመር ባህርይ ስላላቸው ነው ። ቅድም ቡና ይወዳል ስትይኝ የገረመኝ ለዛ ነው ። ሆኖም ግን ሱሱ የባስ ችግር ውስጥ ስለሚከታቸው እሱን ህክምና አድርገ መውሰድ አይቻልም ... ግልጽ ነው?"

"በጣም ነው የገባኝ ... ይገርማል የተፈጥሮ ነገር ። እጅሬ ለካ ቡናዋን የምታጨልጠው ለዚህ ነው ። አሁን ወዴ ሜቱ ሳይሽጋገርብኝ ፣ ቶሎ የሆነ ነገር ማድረግ ይኖርብናል ዶክተርዬ" አለች ፣ ፈገግ ብላ የውስጥ እፎይታዋ እየጨመረ ።

"ምን መሰለሽ ... ህክምናው የበለጠ እንዲሰራ ከተፈለገ ... ሁለት ነገሮችን ማድረግ ይኖርብን ይሆናል ። እንደኛው በጥንቃቄ እየተከታተልነው የሚሰጥ የመድሃኒት ህክምና ሲሆን ... ሌላው ደግሞ የምክር አገላው ነው ። በምክር አገልግሎቱ ሚስጥር ታግዛችኋለች ። በተለይ ቤተሰብና በትምህርት ቤት ቢያንስ ዋና አስተማሪ ለሆኑት ሰዎች የተወሰነ እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል ። ምናልባት ችግር የሚሆነው መድሃኒቱ ውድ ባይሆንም ... እዚህ አገር ብዙ የሚገኝ አይመስለኝም ግን እስኪ ማዘዣው ልጻፍልሽና ሞክሩ ። "

"አረ ምንም ችግር የለም ... ሆስቴስ እህት አለችኝ ... ካለበት አስፈልገን እናስመጣለን ... ባለቤቴም እንግሊዝ አገር ብዙ ዘመዶች አሉት" አለች ።

"ጥሩ በቃ ከሚስጥርም ጋር ቀጠሮ ውሰዱ ... የሚቀሩ መጠይቆችን መሙላትና ... የምክር አገልግሎት እቅዳችሁን ከሷ ጋር ትሰራላችሁ ። እኔም መድሃኒቱን መውሰድ ከጀመረ በኋላ እስኪ አየዋለሁ ..." ብሎ ፣ አጠር ያለ የመጀመሪያ ማስታወሻውን ካርዱ ላይ ጻፍ ጻፍ አደረገ ።

ተሰናብተው ሲወጡ ሀጻኑ እንደ ተኛ ስለነበር ምስጢር አግዛት በጀርባዋ አዘለችው ። የተሰበረውን የርቶ መስታዋት ሰብስቦ ቀሻሻ መጣያ ውስጥ ጣለ ። እባራ የጠጣውን ርቶ ጠራረገና ፒያኖው ላይ በፊቱ ደፍቶ አስቀመጠው ። ሦስት አራት የፒያኖ ቁልፎችን እንደነገሩ ነካከቶ የሚቀጥለውን ህመምተኛ ለማስገባት ወደ መጠበቂያ ክፍሉ ሄደ ።

በማከታተል ሁለት ሕፃናትና አንድ አዳጊ ወጣት ልጆችን አየ ። በትርፍ ጊዜ የምትሠራላቸው የሕፃናትና አዳጊዎች ስፔሺያሊስት ለአንድ ወር ያህል በእረፍት ምክንያት አትገባም ። ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ አዋቂዎችን ቢያክምም ፣ ከሕፃናት ጋር መሰራቱንም አይጠላውም ። ከልጆች ጋር ሲሰሩ ትልቁ ችግርና ፈተና በያንዳንዱ ህጻን የአእምሮና ሥነልቦናዊ ችግር ፣ ከግማሽ በላይ ችግሩ ያለው ቤተሰቡ ላይ መሆኑ ነው ።

@OLDBOOOKSPDF

ቱፍሌሱ ደግሞ ትምህርት ቤትና ጓደኛ ተጨማሪ የችግሩ ክፍል ይሆናል።

ከያቸው ሀጻናት አንዱ የዘጠኝ አመት ልጅ ናት። ካሰባት ከፍተኛ የፍርሃት ችገር የተነሳ ትምህርት ቤት አልሄድ ብላ በማስቸገሯ ነው ያመጧት። ከቢተሰቧ ውጪ ከማንም አንግዳ ሰው ጋር ማወራትም ሆነ መተራረብ ስለምትፈራ ምንም ጓደኛ የላትም። ሱት እንኳ ተልካ ከገቢ ሳትወጣ የውጭ በሩ ስር ቁማ ስታሰትስ ነው ሆተገኘው። ለጥየታ የመጡ ዘመዶች ሰላም ሊሏት ያለችበት ክፍል ከመጡ፣ አልጋ ስር ገብታ እየሥገች እትወጣም።

ይሆንን ፍርሃቷን ህመም ነው ብለው ስመቀበል፣ ለቢተሰቡ ብዙ ጊዜ ፈጅተባቸዋል። በሆነው ባልሆነው ስትገረፍና የሚያደርጉት ሲያጡ ደግሞ እቢት ውስጥ ዘግተውባት ሲሄዱ ችግሩ ከቀን ወደ ቀን እየባሰ መጣ። ዓይነጥላ ነው ... የሰው ዓይን ነው እየተባለ ያልተወሰደችበት ቦታ አልነበረም። በመጨረሻ ምንም ማድረግ ወደማይችሉበት ደረጃ ስትደርስ፣ በሰው ገፊት ሃኪም ቤት ይዘዋት መጡ። እሷንም ከምስጢር ጋር አይተዋት ፍርሃቷን የሚያረግብ መድሃኒት በትንሽ መጠን ለዘዘላት። ተከታታይ የሆነ፣ ፍርሃቷን ቀስ በቀስ የሚያረግብ የምክር እገዛ እንድታገኝ በቀጠሮ ሸኟቸው።

እነርሱ ከመጡ በኋላ የአስራ ሦስት ዓመት ዕድሜ ያለው አዳጊ ወጣት ከእናቱ ጋር እየተቀራቀሱ ገቡ። ከርሷ ፈንጠር ብሎ ተቀመጠ። ከእናቱ ጋር እሳትና ሚድ ሆነው እነርሱን መጻኘቱ ራሱ አድካሚ ሥራ ሆነበት። እናቱ አርሱንና ሁለት ታላላቅ ወንድሞቹን ለማሳደግ በብዙ ችግር ማለፏን ነገረችው። ወንድሞቹ ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ ገና በልጅነታቸው ከፍተኛ ሱስ ውስጥ እንደገቡና አሁን አንዱ እስር ቤት መሆኑንእና ... ሌላው ያለበትም እንደማይታወቅ እያለቀሰች አሣወቀችው።

"ዶክተር ... እንደነገርኩህ ታላላቆቹ ... ከንቱ ... መና ሆነው ቀሩ ... እባታቸውም ... እዛ የፈረንጅ ... ይቅር ብቻ ... ተታጠልኩ እኮ ... እነርሱ ሰው ይሆኑልኛል ብዬ ለጅነቴን ሁሉ በከንቱ አባከኜ ... ዶክተርዬ ... እርዳኝ ባክህ። እስኪ ይሄን እንኳ ሰው ቢሆን አትርፍልኝ ... ምነው ፈጣሪ ልፋቴን ... እምባዬን ቃጥሮ ... ለሌላ ሰው ከሚያፈሰው በረከት ፍርፋሪውን እንኳ ነሳኝ ..." ብላ፣ ስትስት ብላ አለቀሰች።

"አቦ ...ምንድነው ...ዝም ብሎ የሚያስለቅስሽ ... ምን ነገር ታካብሻለሽ ..." አለ፣ ልጁ ጭንቅላቱን እያሻሸ። ከዘፍሱ ውስጥ ሮጦ ለመውጣት ያሰበ ይመስል በር በሩን ያያል።

"ተው እንጂ ... ችግር የለም እንዴ? ... እስኪ ባንተ የተነሣ ትምህርት ቤት ያልተጠራህበት ሳምንት አለ? የቤቱን እቃ ሸጠህ ጨረስከው ... ዞር ካልኩልህ ሁሉም ነገር ዞር ነው ... እም ... ሰፈር ውስጥ ባንተ ሴብነትና ተንኮል ያልተማረረ ሰው አለ? ስትፈልግ አምሽተህ ... ደስ ካለህ ደግሞ አድረህ ትመጣለህ። ሌላው ቀርቶ የግይነገሩትን የሰፈሩን ውሾችና ድመቶች እንቀህ ... ደብድበህ ትገድላለህ ... ምን ክው ችግር የሌለው አንተ ...? ይህ ሁሉ ሃሳብ ይንሸራሸርባቸው የነንት ዘመን ጥሩ ትሪቤቱን

... ቤታቸውን ጋዝ አርከፍክፎ ሊያቃጥል ሲል ሰውዬው ደጅ ጥሮው አይተውት ባይደርሱበት ኖሮ ቤተሰቡን በተኙበት ሊያጋያቸው ነበር ።

"እንዴ ... ወንድሞቹ እኮ በስንት ጣዕማቸው ...ሆሆ ... ባለፈው እንዲት ... አንድ ፍሪት የገረቤት ልጅ ቤት አስገብቶ ሊደፍር ሲል ደርሽ ያስጣልኩት እኔ ነኝ ... ውሸት ነው? ... አሁን ማወት የምፈልገው በሕክምና ሊረዳ የማይችል ወይም የማይፈልግ ከሆነ ...ማወት ነው ። ፖሊስ ጠርቼ ማስረከብ ነው ... ከዚህ በላይ አትም የለኝም ... አሁንማ ለራሴም ሕይወት ያስፈራኛል ። ገንዘብ አምጪ ነው ... የለኝም ካልኩ ... ጦርነት ነው ... ባለፈው በሩን እጄ ላይ ዘግቶብኝ ሲሄድ ይሄው ጣቴ ተቀረጠ ... " ብላ ፣ የተቀረጠ የግራ ሴባ ጣቷን አሳየችው ።

"እቦ በታ ምን የሆነ ያልሆነውን ትናዘዝያለሽ ... ከቤትሽ እመጣልሻለሁ ... ካንቺ ሞትሞት መገላገሉ ራሱ ረፍት ነው ። ዶክተር ብታይ ... አንተ የቧ ሞትሞትና ንትርክ አንድ ቀን ቢወርድብህ ጨርቅህን ጥለህ ታብዳለህ ... ደግሞ እኛ ውለዱን አላልናችሁ ... ምን እዚህ ... ትምህርት ቤትም አንዴ ከጠመዱህ በታ ...የማሪያም ጠላት ነው የምትመስላቸው ። እኔ ኮ ሁሉም ሰው ስለሚጠላኝ ... ምንም ብሆን ግድ የላቸውም ። ከዚህ እገር ብን ብዬ መጥፋት ነው የምፈልገው ... ሀክምና ምናምን ... እኔ ምንም በሽታ የለብኝም ... ሞንትላቷ ዞር ያለባት ... መታከም የሚያስፈልጋት እቧ ራሲ ናት " ሲል ፣ ተንደርድሮ ሄዳ በጥፊ ስታሟለው አንገት ላንገት ተናንቀው ተነሱ ።

ሌላሠው ሊያገላግላቸው ተነስቶ ሲደርስ እናትዬውን አሽቀንጥሮ ሲገፋት ሶፋው ስር ድፍት ብላ ወደቀች ። ዞር ብሎም ላያይ ከክፍሉ መሰጥ በሩን በርግዶ ሮጦ ወጣ ። ደግሮ ሲያነሳት የሶፋው ጠርዝ ስለመታት ግንባሯ ባንድ ጊዜ አበጠ ። መልሶ ቦታዋ ላይ እንድትቀመጥ ረድቷት ከፊት ለፊቷ ገንበስ ብሎ ያበጠ ግንባሯን አሻሸላት ።

"በጣም እገናለሁ ... ሌላ ቦታ የመታሽ ነገር አለ?" አለ ፣ የሚለው ጠፍቶት ። በእሱታ ሞንትላቷን እያወዛወዘች ስትስት ብላ ግልቀቧን ቀጠለች ። አጠገቧ ተቀመጠና እጁን ትከሻዋ ላይ አስቀምጦ በድንጋጤ እንደተዋጠ ዝም አለ ። ትንሽ ስትረጋጋ ወደ ፍሪጁ ሄደና በረዶ በንጹህ ጨርቅ ጠቅልሎ አምጥቶ ፣ጓን አድርጋ እንድትይዘበት ሰጣት ።

"አሁን እሱና አንቺ ብቻ ናቸሁ ... አብራችሁ የምትኖሩት?" እያመነታ ሲጠይቃት እንባዋን ጠራረገችና ግንባሯን እንደያዘች ጸጥ ብላ ቀየች ።

"አዎን ... ሰራተኛ ቢቀጠርም ቁም ስትላቸውን ያሳያቸዋል ... ወርም ሳይቀየ ይሄዳሉ ... ሰው እንዳይመስልህ ... አውሬ እኮ ነው"

"ለመሆኑ አባታቸው ወዴ ሙዚ ሀገር ሲሄድ እድሚያቸው ስንት ነበር? ከዛስ በኋላስ መጥቶ አይታቸው ያውቃል ወይ በስልክ ያዋራቸዋል?"

"እሱ ሲሄድ ... ይሄኛው አራት አመቱ ነበር ... በያራት አመት ልዩነት ነው የተወለዱት ። በሄዱ ስድስት ወሩ አካባቢ ጠፍቶ ጠፍቶ ደመለ ። ከዚያ ስአንድ አመት ያህል አልር አልር ይደውል ነበር ። ከዚያ ወዲህ ምንም ... ይውስም ... መጥቶም

@OLDBOOOKSPDF

ሮነኖ አድናቅላችው አያወቅም ይገጠ ዘጠኝ አመቱ። በሄዱ በሦስተኛ አመቴ
እናቴ መለለኝ የማደርገው አጥቼ ላለትሰባት አንድ እዛ ያለች ያክስቴ ልጅ አለች
ፈልፈልኝ አገኘችው። ካንዲት ፈረንጅ ጋር ተጋብቶ ኑሮ መጀመሩን ይረሰችበት።
እርሷን አውጥቼ ተጠኑት። እሱን የት ያውን ምን ያድርግ የማውቀው ነገር የለም።

"ብጣም ያሳዝናል ..." ብሎ ዝም አለ።

"ቀያ ዶክተር ... ምን አያነት ኃጢአት ብሰራ ነው ይሄ ሁሉ ርግማን
የሚወርድብኝ! ሰው እንዴት አንድ ልጅ እንኳን አይመጣለትም! አንዳንዴ ይሄ ሁሉ
ቢኖሩት ነው ብዬ ሴሊቱን ሙሉ ሳለቅስ አድራለሁ። ያልተሳልኩት ስእለት የለኝም
ምን ንድ ነው? እነሱን በእንጀራ እባት ላለማስታየት ... ስንት ... ምን የመሰለ ዕድል
እያዚ ብዬ ...አንጅቱን አሰራ እነሱን ማሳደጊ ..." ብላ፣ እንደገና ማልቀስ ጀመረች።

"የውልሽ ... ይሄ ያንቺ ጥፋት አይደለም። ነገሩ በጣም የተመሳሰበ ጉዳይ ነው።
እነቺ የምታውቂውንና የምትችይውን ሁሉ አድርገሻል። ራስሽን አትውቀሺ ...
ያንቺ ኃጢያት ወይም እንደ እናት ያለመብቃትሽ የፈጠሪው ነገር አይደለም። ለመሆኑ
እዛታቸው ከመሄዱ በፊት ከእርሱ ጋር እንዴት ነበር ግንኙነታቸው?" አለ፣ እንዴት
እደርጎ ሊረዳት እንደሚችል ግራ ግብት ብሎት።

"እንግዲህ እኔ እስከማውቀው ጥሩ ነበር። ስንጋባ እኔ ገና ሃይ ስኩል መጨረሴ
ነበር። በእድሜ ብዙ ይበልጠኛል ... ሃይ ስኩል ላይ ባዮሎጂ አስተምሮኛል። እኛ ግቢ
ተዘራይቶ ይኖር ስለነበር፣ በዛ ነው የተቀራረብነው። አዲሳባ ተቀያሮ ሲመጣ እናቱ
ፃጉትምህርትሽን ተማሪ ስትለኝ ...አሻፈረኝ ብዬ ... አብረን መጣንና ላመቱ ተጋባን።
ዮለተኛ ልጃችን ሲወለድ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መማገሱን እንደተወሰበት አንዳንድ
ነገሮች ነበሩኝ። ይሄን ትንሹን ከወለድኩ በኋላ አደብ የገዛ መስሎኝ ነበር።"

"ደጅ ደጅ ማለቱን ትቶ ወይ ከልጅቹ ጋር ይሟጠታል ... ወይ መጽሐፉ ላይ
ተጣብቆ ሲጋራውን እያንበለበለ ሲያነብ ያንጋል። የትዳር ግንኙነታችን ከሁለተኛው
ልጅ በኋላ ለስም እንጂ የደባል ኑሮ ሆነ። ድንገት ብድግ አለና የውጭ ዕድል
አገኘሁያለሁ ብሎ በሁለት ሳምንት ውስጥ ሄደ። ልጆቹ እንዴት እንደተላቀቁ ልንገርህ
አልችልም። ትንሹ በተለይ አባቴን ውለጂ እያለ ነጋ ጠባ ማልቀስ ሆነ ሥራው።
ደርገኖ ብሎ ጠፍቶ እንዳልኩህ በስድስት ወሩ ይመለ። እነሱ የሚመስላቸው በእኔ
ምረት አዝር ጥሎ የጠፋ ነው። እኔ ደግሞ እንዳጠፉት ሰለማልፈልግ ምንም ከቱ ነገር
ሀደሉ አልነገራቸውም" ብላ፣ በእምባዋ ርሰው የተዝመሩ ሶፍት ወረቀቶችን ስብስባ
ሀሪቱ ናገኒን ጠቀለለቻቸው።

"በዚህ ላይ ... እነርሱን ማሰቃየሩና የኑሮ ሸክሙ ሙሉ ለሙሉ የኔ ቀጋበር ሆነ።
ዩኤስኤ ተማርኩ ወይ ዘመድ የለኝ ... በምኔ ላስተላድራቸው? የነርሱን ከርስ ለመሙላት
እዛ እዚህ ስማሰን ... ሃይ የሚላቸው ጠፍቶ እንዳይገ ጠቶ። ትልቁማ ... ውይ ሰው
እንዳይመስልህ ...ከይሲ ዲያቢሎስ ራሱ ቀሞ የሚሄድ ነው የሚመስልህ። ሰው ቤት
ንብቶ ሲበረብር፣ ባለቤትዬው ነቅተው ተያይዘው ሲታገሉ ... ሕይወታቸው እኔ ላይ
ሚሳ። ይሄው አሁን የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባት ሁሉት ዓመቱ። መከከለኛውም

@OLDBOOKSPDF

ብን ብሎ ከጠፋ እመት አለፈው። ወደ ሱዳን ከጓደኞቹ ጋር ገብቷል ሲባል ሰማሁ ባለፈው ስሞን። በታ ወልዶ መና ..." አለች፣ ግንባሯ ላይ ያለውን በረዶ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ፣ ከፊቷ ከተቀመጠው ውሃ ላይ ፉት አለችና አፏን አረጣጠበች።

"ያንቺስ አስተዳደግ እንዴት ነበር?" አለ፣ እስከአሁን ስለ ራሷ ብዙም ስላልጠየቃት።

"እኔማ ምን አስተዳደግ አለኝ ብለህ ነው ዶክተር ... ስድስት ነበርን ... አራተኛ ነኝ ... ካንተ ባላው-ቅም ሞገደኛ እናትና ዳተኛ አባት ካሳደገህ ... ወይ አመጸኛ ... ወይ ጥገኛ ነው የምትሆነው። ... ከናቴ የባስኩ ሞገደኛ ነበርኩ ልጅ ሆኜ ... አሷ ነጭ ካለች እኔ ጥቁር ነበር የምለው። ያገሩን ዱላ እኔ ላይ ነበር የጨረሰችው ... የፎም ርግማን ነው መሰለኝ። የልጆቹ አባት ደግሞ አሁን ሳስበው የእኔ አባት ኮፒ ነበር ... ሁሉም ነገር የሚገባህ እያደር ነው ... ሰው አባቱን ያገባል?"

በሰጠችው ትንተና ተደንቆ፣ "ይገርማል ..." አለ።

"አሁን ኮ ትልቁ ፍርሃቴ ... ይሄ ልጅ በዚህ እያያዙ ... ወይ የሰው-ሰው አንድነገር አድርጎ መዘዙ ለኔም እንዳይተርፍ ነው። ቅድም እንዳልኩህ ባለፈው እቃ ረስቼ ከስራ ቦታ ተመልሼ ቤት ስገባ ... የሆነ የብልግና ቪዲዮ ከፍቶ ... አንዲት ከኛ ቤት የማትጠፋ የሰባት እመት የጮረቤት ልጅ አለች ... እጅና እግሯን ጠፍሮ ... እዛ ቪዲዮው ላይ የሚያየውን ነገር ሊያደርግ ይሁን አላው-ቅም ... አሷ ትጮሃለች ... ደርሼ አስጣልኳት ... መጠጥ ብትል ጫት ... ምንም አይቀረው-ም ... ምን ይሻለኛል?"

የምትነግረው ነገር ሁሉ አስደንጋጭ ሆኖበታል። "ይቅርታ አድርጊልኝና ... በዚች አጭር ጊዜ እንዳየሁትና ከምትነግሪኝም እንዳተረዳሁት ልጁ አስራ ሦስት ዓመቱ ቢሆንም ካንቺ አትም በላይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፈጽሞ አደገኛ ነው። ለህክምና እርዳታና ምክርም ቢሆን ፈቃደኛ የሚሆን አይመስለኝም። የግድ የህግ እገዛ ያስፈልግሻል። እንደምታው-ቂው እኛ ማስገደድ አንችልም። ፖሊስ ጣቢያ አመልክተሽ ... የኛንም ድጋፍ ከፈለግሽ እንጽፍልሻለን።

"ባይሆን እንቺን በምክርም ቢሆን እንረዳሻለን። አላው-ቅም እዚህ አገር ያለውን አሠራር ... ጸባይ ማረሚያ ነው የሚሉት? እዛም ካስገቡልሽ ከነሱ ባለሙያዎች ጋር ተባብረን ልንረዳው እንችላለን። ከዚያ ው-ጭ ግን ልጁ ላንቺም፣ ለራሱም ከፍ እያለ ሲሄድ ደግሞ ለሁሉም ሰው አደገኛ እየሆነ ነው የሚሄደው። በልጅነቱ አባቱን ማጣቱና መሰመር ያለው አስተዳደግ አለማደጉ ... በዛም ላይ የታላላቆቹም ተጽእኖ ተጨምሮ ... ባጠቃላይ መሪና ሞዴል የሚሆን አዋቂ የሆነ ወንድ ስላልነበረው ይመስላል፣ ሰብአናው ከፍተኛ ቀው-ስ ው-ስጥ ነው ያለው።

"አካሄዱ አደገኛ ወንጀለኞች የሚያሳዩትን የሰብአና ባህርይና ቅርጽ እየያዘ ስለሆነ የሚቻለው ሁሉ አሁን መደረግ አለበት። አንቺም ከምታስቢው በላይ ብዙ የተገዳሽና ውስጥሽ የተመረዘ ይመስለኛል። የምክር አገዛ ማግኘትሽ ለራስሽም ሆነ ለሌላውም ችግር መፍትሄ ከማግኘት አንጻር ቁልፍ ነገር ነው። ፈቃደኛ ከሆንሽ ለአንቺ

@OLDBOOOKSPDF

እዚሁ ከሲኒዝ የምበር ድጋፍ ልንሰጥሽ እንችላለን ። ልጁን ግን እንዳልኩሽ አድርጊ ፣ የምንፈልሽ ነገር ካለ "ንገሪን" አለ ፣ ከዚህ የተሰየ ሊያደርግ የሚችለው ምንም ነገር ስላልታየው ።

የግነባሯ እብጠትና የሰሜኒቷ ሙጥረት ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በከፊል ተንሰላት ከረቮው ወጣች ። የገዛ ልጇ ገፍትሮ ለመረመራት እናት ልቡ አዘነ ። እሷን ከሸኘ በኋላ ከክፍሙ ላይ ተመልሶ ተቀመጠና የራሱን ልጆች ማሰብ ጀመረ ። ብዙ ብቸኛ ወላጆች ... በተለይ እናቶች ... የሚያሳድጉዋቸው ልጆች የሚያልፉበት አስቸጋሪ የማንነት ቀውስና ጠመዝማዛና የተወሳጋገደ የሰብእና የእድገት ጉዞና ለመረዳት ሞከረ ።

"በግለም ላይ ያሉ አስር ቤቶችን ከሞሉና አሰታዊ ወንጀሎችንየፈጸሙ አስረኞች አብዛኞቹ የተዛባ ስብእናና የተበላሸ ልጅነትን ያሳለፉ ናቸው ። እያንዳንዱ ትልቅ ሰው በልጅ ውስጥ ይኖራልና ... በዛው ልጅ ውስጥ አድጎ የሰብእና የባህርይ ቅርጹን ይዞ የራሱ ሰው ይሆናል ።

"ወላጅ የልጁ መስተዋት ነው ... ሕፃኗ በመስተዋቱ ውስጥ ያየችውን አይነት ሰው ትሆናለች ። ሰባራ መስተዋት ሰባራ ስብእናን ... የተበላሸ መስተዋትም የተዛባ ስብእናን በልጆች ውስጥ ይፈጥራል ። የእናት መስተዋትነትና የአባት መስተዋትነት ደግሞ ለየቅል ነው ። ልጆች የሰብእና ገንባሌነና የመሆን እምቅ ችሎታን ይዘው ይወለዳሉ ። ከቤት ወላጅ ... ከደጅ ጓደኛ ... ትምህርት ቤት ... እና ሌሎች የማህበረሰብ ኃይላት ከሕጻናት ውስጥ የበለጸገ ወይም የጉደፈ የሰብእና ማንነትንና የባህርይ ቀለምን በመቀባት ትልቁን ሰው ይስሉታል ።

"እያንዳንዷ ሀጻን በውስጧ ... ገና ያላደገች ሌላ ሴት ተሸክማለች ... በትንሿ ሰውነት ውስጥ መገለጫዋን የምትጠባበቀው ትልቋ ሌላ ሴት ... የሰብእና ዝንባሌዋንና እምቅ ችሎታዋን እንደ ተቀረጸችበት መነገጃ ... ከፋ ወይም ደግ ... ትጉ ወይ ሰነፍ ... ገፈኛ ወይም ሩህሩህ ... ትሆናለች ። ወላጅ ልጅን ቢወልድም ... ልጅ ደግሞ ሌላ ወላጅን ይወልዳል ። ከልጅ ውስጥ አዲሱን ወላጅ ማሞለድ በሞናነት የመጀመሪያው ወላጅ ስራ ነው ።

"ከሕመሞች ሁሉ ትልቁ ሕመም ካንሰር ወይም ኤይድስ ሊመስለን ይችላል ። እውነቱ ግን ከሰብእና መዛባት የከፋ ሕመም የለም ። ወ-ጫጪ መልክ የሰው የገጽ ሽፋን ነው ። ሰብእና ግን የሰው እውነተኛ መልክ ነው ። በየእለቱ አብረን የምንኖረው ሰው ፣ እውነተኛና የሚያረጅ ዘላቂ ማንነታችን ሰብእናችን ነው ። በዓይናችን የማናየው እውነተኛ መልካችን ... በውስጥ ማንነታችን ውስጥ ተኮብሮ ያለው ሰብእናችን ነው ። የሰብእና ስንኩልነት ፣ ጠባሳዎችና መዛባቶች ቤት ያፈርሳሉ ፣ አገር ይንዳሉ ፣ ግንኙነትን ይመርዛሉ ። ለማከምና ለማዳን ብቻ ሳይሆን ለማየትና ሕመሙን ለመረዳትም አዳጋች ነው ።

"ሰብእና በልጅነት እንደ ተበከ ሲሚንቶ ፣ በአዋቂነት ደግሞ እንደ ደረቀ አርማታ ነው ። የብዙ ሰው ሰብእና እንዴ ተበኪ ሲሚንቶ ፣ በልጅነቱ በትክክል የሚቀርጸው ካላገኘ ተንሻፎና ተጣብቶ ያድጋል ። ፅድቄው ከገዱ ከኋላ ደርቆ ስለሚጠነክር ፣ ብዙ

@OLDBOOKSPDF

ጊዜ ለመነሸራ መዶሻና ለምክር መዋረዚያ አዳጋዮ አገር ያጠፋል ። የልጅ ውበቱ በቀላሉ መውራቱ ... ያዋቂ ከፍቱ ለመለወዋ አስቸጋሪ የሆነ ከፉ እውቀቱ ...ነው' በሚል አላቡ ውስዋ እሳው በተቀመጠበት ሲወጣ ሲመርድ ዋየ ። የናትና ልጅን ታሪክ ባጭሩ ጽፎ ካርዱን ከፊቱ ካለው ከብ ጠረጴዛ ላይ መርመር አደረገው ። በረጅመ ተንፍስ ለውነቱን ሲያንጠራራ ምን ያህል እንደ ደከመው ታመቀው ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 36 ፡

ከጠዋቱ አራት ሰዓት ተኩል ዕለተ ረቡዕ ነው። ቀኑ በብሩህ ፀሐይ ድምቅ ብሏል። ሲራክ በጠዋቱ አብዛኛዎቹን ህመምተኞቹን አይቶ ስለጨረሰ ስጊዜው የሚጠብተው ሌላ ሰው እንደሌለ ካርድ ክፍል ጠይቆ ተረዳ። ቁርስ ስላልበላ ራብ ብሎታል። ሲርበው ቡና ፣ ሲጠግብ ሲጋራ ይጠማዋል። ከካሮ መጻለው የክሊኒኩ ካፌ ሄዶ ያዘዘው ምግብ እስኪደርስ ቡናውን በትኩሱ ጨለጠ። ሳቢላ ደጋግማ ስትደውልለት ስለነበር መልሶ ደወለ።

"ትንሹ ዶክተር ምንድነው ነገሩ? ... ድንገተኛ ሊሆን ይችላል ብሎ ሰው ደንገጥ እንኳ አይልም ..." ስትለው ሳት ብሎ ፣

"ሳቢ-ሳቤላ ... ድንገተኛና አጣዳፊ ከሆነ ቁስት ... ብዬሽ የለ ... ምን ተገኘ በጠዋቱ?" አለ ፣ የቡና ስኒውን ማስቀመጫው ላይ እያሽከረከረ።

"ገሰ ዋት ... በጠዋት ... ወፍራም ዜና ... ዲቪ ክች አለ"

"እኔ አላምንም ... አር ዩ ሹር?" አለ ፣ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ።

"ዩ ኖው ቁጥሩ ራሱ የመጀመሪያ አካባቢ ነው ... እኔ ታይቶኛል እኮ ድሮም ... በል ቶሎ ሞልተን እንላከው ... ሰለብራሽንም ነገር ማታ? ... ዲረራ-ራ-ዲ-ዲ-ዲ-ን" አለች ፣ ደስታዋ ድምጿን እያሸነፈ።

ለእራት ተቀጣጠሩ። ሕይወቱ ሁሉ ባንዴ ሌላ አቅጣጫ ሲይዝ ታየው። በክሊኒኩ ፍርስራሽ ላይ እየተረማመደ አዲዮስ ኢትዮጵያ ብሎ አሜሪካ ሲገባ ታየው። "ባጃጅ ራስ ሁላ ... ማን ምን መሆኑ አሁን ይታያል" አለ ሥክ ብሎ። ሠስው እንደ ፈነደቀ ወደ ቢሮ ተመለሰ። ሰመኑን ሲመጥነው የነበረውን ሃሳብ እንዴት ወደ ተግባር እንደሚለወጠው ሲያስብ ሌላ ስልክ ሲጮህ ሰማ። "የስ ..." አለና ወዲያውኑ ወደ ሌላው ቢሮ ሄደ።

@OLDBOOKSPDF

የቢሮውን በር እንኳኩቶ ሰው መኖር አለመኖሩን ሲማየት አንገቱን አውልቶ ሲያይ "ሄይ ግባ ዶክተር ሲራክ ..." አለ ሶፋው ላይ ተቀምጦ የሕመምተኛ ቻርት እያገላበጠ። "አይገርምህም ... ፈልጌህ ልክ እያሰብኩህ ነው የመጣኸው ... እስኪ ቁጭ በል" ብሎ ከፊት ለፊቱ ወዳለው ሶፋ ጋበዘው። በስራና በኑሮ ሁሪያ የተለመዱ ነገሮችን ተጠያይቀው ሲጨርሱ "ትዝ ትልህ ይሆን ይህቺ ሀመምተኛ ... እኔ አሜሪካ እያለሁ አንዴ አይተሃት ነበር መሰለኝ ..." ብሎ፣ ቻርቷን አቀበለው።

"ኦ...ህ ... ትዝ አለችኝ ... እኔ ያየኋት ጊዜ ምንም አትሳገርም ነበር ... የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበረች መሰለኝ። ከጓደኛዋ ጋር ሐረር ከተማ ውስጥ አታ ሊጠ ወጥተው አፍንው መስደዋቸው ... በተደጋጋሚ የደፈሯቸው አይደለች? ... ጓደኛዋ በኋላ ሞተች መሰለኝ። ዘግናኝ ነገር ነው። በጊዜው ምንም ልታሳግረኝ አልቻለችም። እንዴ መሰለኝ ቢተሰቦቿም ማግኘት የፈለጉት አንተን ነው። ለእንትልፍ የሚያግዛትና ለዲፕረሽኑ አሚትሪፕትሊን ብቻ ነበር ያዘዝኩላት። ዶክተር ሌላው ሲመጣ እንመጣለን ... እሰከዛ ምንድነው እሱ የሚሉት ... የመሲብ ተጠቂዎች ምናምን የምነር አገልግሎት ... መሰለኝ እዛ እየሄዱች ነው ... ምናምን ብለው ነበር መሰለኝ። በዚህ ኤርያ ላይ ልምድም ስለሌለኝ ምን ላደርግላት እንደምችልም አርግጠኛ አልነበርኩም"

"ኖ ኖ ... ዩ ዲድ ጉድ ... በተለይ በዛ ደረጃ ላይ ነገሩ ለማንም አስቸጋሪ ነው። ተጥሎ ከማያቸው ሰዎች ውስጥ ናት ... ቻርቷ ላይ ያንተን ጽሁፍ ስላየሁ ነው። በጣም አሳዛኝ ነገር ነው ... እዚህም አገር እንደዚህ አይነት ነገር አለ ማለት ነው?" አለ፣ ፊቱን አዙሞያ።

"ወይ ጉድ ... ስለማያወራ ነው እንጂ ባይብስ ብለህ ነው። ጠለፋና ግርዛት ባለበት ሃገር ... ሌላው ነገር ምን ይከለክለዋል ብለህ ነው ... እንዳልይዝህ ቢቃ ..." ብሎ ለመሄድ ብድግ ካለ በኋላ "ኧረ ... የመጣሁበትን ጉዳይ ረስቼው ... ንጹሕ ኦስቲን ቲከሳስ ናት አይደል?" አለ፣ እየተንጠራራ።

"ያ ... ምነው ... ቲከሳስ ምን ተገኘ?"

"ባክህ አንድ ጴንቨር በትምህርት የቀየች የወንድሜ ባለቤት አህት ... ጥሩ ስራ አግኝታ ወደ ኦስቲን መ-ቭ ልታደርግ እያሰበች ነው ሰሞኑን ... እዛ ብዙም የምታውቀው ሰው ስለሌለ ብታገኛት ብዬ ነው"

"ኦህ አሪፍ ነዋ ... ንጹሕም በጣም ደስ ነው የሚላት ... ቀደ ..." ብሎ ከዚያ ወንበር የራሱን ቢዝነስ ካርድ አውጥቶ ኢሜይሏንና የጅ ስልኳን ጽሮ ሰጠውና "ሌላ እገዛም ከፈለገች ንገረኝ። ብዙ ጥሩ ወዳጆቻችን እዛ አሉ"

"ታንክ ዩ ... አያ ቲንክ እሰኪ እሷን ታግኛትና መጀመሪያ አውን ያላትንም ሥራ ለመልቀቅ እያመነታች ስለሆነ ... መጀመሪያ ሄዳ ከተማውን ማየት ነው የፈለገችው መሰለኝ ... ያው አዘኛ ለመጥ ጠላቱ አይደል ... እስኪ እንገረሃለው። በቃ አልያዝህ ... እኔም ከምሳ በፊት አንድ የማየው አዲስ ኬዝ አለኝ መሰለኝ። የልጅቷን ነገር እስኪ እያትና ... እንዴት እንደሆነችና ያንተን ሐሳብ ባወት ደስ ይለኛል።"

@OLDBOOOKSPDF

"ጥሩ ... እናመራለና ... ታንክ ዩ ..." ሲራክ ከቢሮው ሲወጣ፣ ሃሳቡን በእጁ ይዘው ቻርት ሙርያ ሰበሰበ። የመስዋ ስልኩ ሲሥሀ ወደ ጠረጴዛው ሄዶ ሲያነሳው ከካርድ ከፍል ነበር።

"ዶክተር ... አንድ ለክሰኦት ተጠሮ የነበራት ሀመምተኛ ነበርችህ ... ከናዝሬት ነው የመጡት። ቀድመው ደርሰው እዚህ ተቀምጠዋል ... ዛሬ መደዚያው ተመልሰው ሂያጆች ናቸው። ከምሳ በፊት ልታያቸው ከቻልክ ብዬ ነበር" ብላ፣ የሀመምተኛዋን ስም ነገረችው። ሲያያት እንደሚችል ነግሯት፣ ወደ ወረፋ መጠበቂያ ክፍሉ ሄደ። ስሟን ሲጠራ ወላጆቿ ከሚመስሉ ጥንዶች መሃል የተቀመጠች በሃያዎቹ መጀመሪያ እክሊኢ ያለችው ወጣት እሷ መሆኗን እርጋን ከፍ አድርጋ አረጋገጠች።

በለበሰችው ረጅም ጥቁር ስማያዊ ቀሚስና ትልቅ ባለ ኮፍያ ጃኬት፣ ከራቷ በቱር ሰውነቷ ሁሉ ተሸፍኗል። ከመሃል አድርገዋት ረጅሙ ሶፋ ላይ ተጠጋግተው ተቀመጡ። እባቷ እጃቸውን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርገዋል። እናቷ ደግሞ ግራ እጇን እያፈተለተሉ በስስት ዓይን ያዩዋታል።

ከዋቂት ጸጥታ በኋላ፣ "ካልተሳሳትኩ ወላጆቿ ናችሁ? ... እንዴት ነሽ? ጽጌረዳ ነው አይደል ስምሽ?" ሁሉም ልዘ መሆኑን ራሳቸውን በመነቅነቅ ገለጹለት። "ይቅርታ ለተወሰነ ጊዜ አልነበርኩም ... ዶክተር ሲራክ የዛሬ ሦስት ወር አካባቢ አይተሽ ነበር አይደል? እንዴት ነው ለውጥ አለ?"

እባቷ ፈጠን ብለው መልስ ሰጡ። " ልዘ ነው እንደ ወጣት ዶክተር እያታት ነበር ... ትንሽ ቸኮል ቸኮል ይላል እንጂ ጥሩ ነበር የረዳን። ብዙ መጻጅታችን እርሶ ጋ እንድንመጣ ስለመከሩን ነበር ልናይዎ የጓጓነው። ይመስገነው ... አሁን ትንሽ ለውጥ ያለ ይመስላል። የኔ አበባ ... አስኪ ንገሪው" ፊታቸውን ወደ ልጃቸው ሲያዘሩ መሬት መሬቱን እያየች ዝም አለች።

"በሆነው ነገር በጣም ነው ያዘንኩት ... የሚያሳፍር ሥራ ነው ያደረጉት። አሁን ነገሩ ከሆነ ስንት ጊዜ ሆነው ማለት ነው?"

"አራት ወር ያለፈው ትዳሜ" አሉ እናቷ፣ ትንሽ አሰብ አድርገው።

"የጓደኞሽንም መሞት ሰምቼ በጣም ነው ያዘንኩት። በርግጥ ዝርዝር ነገሩን አላውቅም፣ ግን ሁሉም ነገር በጣም የሚያስደንግጥና የሚዘገንን ነው።" ጽጌረዳ እንባዋ መፍሰስ ጀመረ። ጠረጴዛ ላይ ያለውን ናፕኪን ሲያስጠጋላት እናቷ እንባዋን ጠረጉላት።

"እናንተ ምን እደነት እገዛ ጠብታችሁ እንደመጣችሁ አላውቅም። የደረሰባት ነገር ከፍተኛ የሆነ ሥነልቦናዊ ጫናና የመስዋ ስሜት መታወስ ሊያስከትል ይችላል። ረዥም ያለ የመከርና አሰፈላጊ ከሆነም መድኃኒት መውሰድ ሊያስፈልጋት ይችላል። ከመሰናችን በፊት ግን የሆነውን ነገርና ነገሩ ከተከሰተ በኋላም ስላለችበት ሁኔታ ከናንተ መሰማት ይኖርብኛል" ብሎ፣ ተራ በተራ ሲያያቸው ራሳቸውን በመነቅነቅ መስማታቸውን ገለጡ።

@OLDBOOOKSPDF

ጽጌረዳ እየተረጋጋች ስትሄድ አልር አልር ቀና ማለት ጀመረች። "ከሞቀሽ ጓዜቱን ማውለቅ ትችያለሽ ጽጌረዳ ... ሻይ ቡና ይምጣላችሁ? ... ውሃም ይኖራል" ብሎ የበለጠ ዘና እንዲሉ ለማድረግ ሞከረ። አስከትሎም "ምናልባት ለብቻሽ ማውራት ከፈለግሽ ... ወላጆችሽ ውጪ ሊሆኑም ይችላሉ ... ዋናው እንቺ ነጻነት ተሰምቶሽ ማውራትም መጠየቅም መቻልሽ ነው።" ወላጆቿ ባንድነት ደጅ ሊጠብቁ እንደሚችሉ ተናገሩ።

"እሱ አይ ... ለዛሬ ምንም የተለየ እንርሱ የማያውቁትና እነሱ ፊት ማውራት የማልችለው ነገር የለም ... እዚሁ ይሁኑ" አለች። ከገባች ለመጀመሪያ ጊዜ ድምጿን መስማቱ ነበር።

"ጥሩ እንግዲህ ... በመጀመሪያ ... የት ነበር የምትማሪው ... ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ"

"ልክ ነው ... እኔም ሚቺ ዓይኖዬም ... ሁለታችንም አንድ ላይ እዛ ተመድበን አንድ ዶርም ነበር የምንኖረው። እሷ ኢኮኖሚክስ እኔ ደግሞ ሀግ ነበር የምናጠናው ... ሁለተኛ ዓመት ነበርን" ብላ ዝም አለች።

"ችግሩ የደረሰባችሁ ... ሐረር ከተማ ነው?"

"አዎ ... አንዳንዴ እዛ የተመሰኑ አታዎች ይረክሳሉ ስለሚባልና ከተማው ንም ለማየት ተማሪ በብዛት ከድሬዳዋ ይሄዳል። እኛም ሐረርን የማየት የረጅም ጊዜ እቅድ ነበረን። የሷ አገት መሞቶ ደህና ገንዘብ ሰጥታት ስለነበር፣ ልብስ ለመግዛትና በዛውም ከተማው ን ለማየት ነበር አካሄዳችን። ጠዋት ላይ ከተማው ን ዓይተን ምሳ ከበላን በኋላ እታ ለመግዛት እዛ ... ሐረር መጋላ ነው የሚባለው መሰለኝ ... እየጠየቅን ሄድን። በኋላ እንደ ገባኝ ከመጀመሪያ ጀምሮ ሲከታተሉን የነበሩ ሦስት ገረምሶች ነበሩ። እንዱ እንዲያውም ተባሮ የወጣ የገዢ ልጅ ነው።

"እታ የሚገዙ መስለው እኛ የገባንበት ሱቅ ገብተው ሰላም ብለው ን ... ምን እንደምንገዛ ጠይቀው ን ሰንገረቡው የሆነ ሱቅ ጠቅመውንና እየተሳሳቁ ዋለው ን ሂዱ። ምንም ሳንጠረጥር ያሳዩን ሱቅ ገብተን የምንፈልገው ን እታ መርጠን ለመለካት ወደ ውስጥ ገባን። ከየት እንደመጡ ሳናውቅ ግር ብለው ገብተው አፈጡን። በሆነ ጨርቅ አፍና አፍንጫችንን ሲያፍኑን ብዙም ሳልቆይ ራሴን ሳትኩኝ። ከዛ በኋላ ያለውን ነገር ምንም፣ የሆነው ንም ለተመሰን ጊዜ አላወቅሁም ነበር" ብላ፣ ቀስ ቀስ መተንፈስ ስትጀምር፣ ከውሃው አንድትጠጣ እናታ አቀበሏት።

"አይዞሽ ..." አለና ንግግሯን እስክትቀጥል ዝም ብሎ ጠበቃት።

"ስንነቃ እጅና እግራችንን በገመድ ጠፍረው ን ... አፋችንን በቀሻሻ ጨርቅ አሰረው ን ..." ብላ ራሷን በመጸየፍ አጨማደዳችው። "ብንጮህ እንኳ እንዳይሰማ የሆነ አስቀያሚ ሙዚቃ ለቀው ብን እየተሳሳቁ ወጡ። ተመልሰው ሲመጡ ስድስት ነበሩ። ልብሳችንን ሁሉ አወላቀው ... በቢላ እያስፈራሩ እየተፈራረቁ የፈለጉትን አደረጉብን። ለምን ያህል ጊዜ እንደሆን ትዝ አይለኝም። ረጅም የሰዓታ ጊዜ መሆኑ ..." ብላ፣ ማውራት አትታት ራሷን በጆቿ ሸፍና አነነበሰች። አባትዬው እንባቸውን

@OLDBOOOKSPDF

ሥላሜዋር አቅቷቸው እኛኮሙን አያመናጨቅና እየተንተባተቡ ቢሮጡን ሰቀመ
ሙ።

ከላይ ከላይ እየተነፈሰች ... ንግግሯ እየተቀራረጠ "እህ ...ህ ...ህ ... ራሳች...
ንን ስን...ስት ጥራሽ ላይ የሆነ እሮጌ ብርድ ልብስ ነገር ጣል አድርገሙብን ... እነሱ
ሣታቸውን እየቃሙ ሲያሾፉብን ... እንደሀልም እንደሀልም ትገ ይሰኖል" ብላ፣
ኗ አለች። እናቷ የሷን እጅ ይዘው ሲያስትሱ አሷ ደግሞ አልፎ አልፎ ሁልል እያለ
የሚወርድ እምባዋን እየጠረገች የሉላ ሰሙ ታሪክ እንደምታመራ የበዘሙ ዓይኖቿ
ሚገነዘቡ ላይ እንደተተክሱ ተጠለች።

"በጣም የሚገርመው ... ያ የግቢ ልጅ ነው ያልኑህ ... ጓደኛዬን ከጎዝፈት
ጀምሮ ያስቸገራት ነበር። በኋላ ከሉላ ልጅ ጋር ሰለነበረ የተዋት መስሏት ነበር። የዚህ
ውስ ጠንሳሽ እሱ እንደሆነ እመቃለሁ። በጣም ከመሽ በኋላ ይመስለኛል እንደገና
ተከተሱንና ጀለቢያ ነገር አልብሰውን የሆነ አፈር አፈር የሚል ሻይ በግድ ጋቱን።
ኗሀታችን ልዘ ሰላልነበረው ያሉንን ከማድረግ ውጪ አማራጭ አልነበረንም።
ጾየት ብሎ እኛን ያገኑን ሰው ጠስዋ ቱጭ ብሎ የነበረው ባለ ሰፉ ራሱ ሲመጣ ነገሩ
ገሸኝ። እሱም ፍራሹ ላይ ሜቱን ገዝትዘ ተቀመጠ። ወዲ እኔ እየጠቀመ ... እሷ የኔ ናት
አምልልኝ ሲል ንትተው አጠገቡ ጣሉኝ።

"ትም ሲመረትን ... "እሷን ከፈለጋችሁ የምትመስዱበት ጠሰጅት ... እኔ ማረኛ
እፈልጋለሁ" ብሎ ሥገባቸው። በዛ በጨለማ አይንና አፏን አፍነው የዘሞት ሲመጡ
ደንግጬ ስሥዘ ስፈር በማያስል እኛ በጥራ ሲለኝ ሰማያ ምድሩ ዞሮብኝ ተያፋሁ።
ቀዝቅዛ ጠዋ ላይ ላያ ራቱ ላይ ሲያፋብኝ ከገባሁበት ስመመን ነቃሁ። ወሰዋ ሰዘነቱን
በተሰማኝ ሠመም ማድረግ የፊለገሙን ሁሉ እንዳደረገ ገባኝ።

"ከዛ ግትጥ ከሞግ በኩል ካለችው ትንሽ ሻመር ከፍል ወሰዋ አስገብቶ ተዝቃዛ
ውሃ ለቀብኝ እንድታጠብ ሳመና መረመረልኝ ጠጣ። ትዝታዚው ቢያንዘረዝፈኝም
ምንሳፈሙን ከየት አንጀመጣሁት አላጠትም። ያንን ሁሉ ቀሽሽ ከላዩ ላይ ለማስለቀት
ይመስል ሰዘነቱን ባለ በሉለ ኃይሉ ፈተገዙት። አብዛኛው ቀሽሻ ወጪ ሰዘነቱ ላይ
አልነበረምና በሳመና ላስለትተው አልቻልኩም።" ሰዘነቷን ለመንካት የተጀየፈች
ይመስል እጅጀን ራት አድረጋ ተንዘፈዘፈች። ላያቋረጥ የሚፈስ እንባዋን እየጠረገች
አጉገባላ ቀረች። አያቢታም እንዴ በሚል ዓይነት እናቷ በቱጣ ሲገላምጡት፣ እንዳለየ
ሆኖ ተጥዬ በሚል ዓይነት አያያት ገም አለ።

"ከእኔ ላይ ከደረሰብኝ ሰቃይ በላይ ጓደኛዬ በዛች ትጽበት የት ትሆን ይሆን
የሚለው ጭንቀት ነበር ጠሰጨን ያላመመኝ። ያው አመራ ሰውዬ መጀመሪያ ቀን ሰቱ
አንገባ ... ምን የመሰለች አራት ዓመት የማይሞላት ሕፃን ሲያጣው ነበር" ብላ፣
እንየምንም ጥርሷን ነክሳ እንባዋን ተቆጣጠረች። "ከዛ ታኮቢ ስጨረስ ልብሱን
ወረወረልኝና ልበሺና ሻይ አፍዪ ... በሩ ቁልፍ ነው ... ለመውጣት ብትሞክሪም የጅብ
ረት ነው የምትሞኚው ወይም የዚህ የቢለዋ ብለ- ማንን ከታትፎ የነላበትን ትልቅ ቢለዋ
ሲያጠፋውብኝ ነፍሴ በፍርሃት ራደች።

@OLDBOOOKSPDF

"ትንሽ ቀይቶ ሻመር ገብቶ እያፏጨ ሲታጠብ እኔ ግሦን ጥጄ ስማስብ ትንሽ እርያታ አገኘሁ። አይኔ የሆነ የኒኒን ብልቃጥ ላይ አረፈ። ከፍቼ ሳየው- ሙሉ ነው። ሳነዘው የአንቅልፍ ዚኒን መሆኑን ተረዳሁ። "ምሽጉን ግዩ ወስዋ ምጀርኩት። ስነር በግ አድርጌ ቀድቼ አንድሰጠውና ለራሴም አንድጠጣ ነግሮኝ ጓደኞን ሠተረጣጠፍ ጀመረ።

"ብርዶት ስለነዘር መሰለኝ የቀጸሁለትን ሻይ ጥሎ ጥሎ ሲጠጣው ደስ አለኝ። እንድጨሥርለት እየተንተባተበ አዘዘኝና አሣው ከንብል ብሎ "ግንኮራፋት ጀመረ። ቁልፉን ከኪሱ አውጥቼ በሩን ስከፍተው ሰው የሰ ምን የለ አካባቢው ረጭ ብሏል። እንጣልሥሀ ሲለኞ እሣው ሰፈር ቢሆኑስ ብዬ ፈራሁ። በሩን እንደተከፈተ ትቼ እያንከሰከሱ በሩጫ ትንሽ እንድሄድኩ ፖሊሶች አያቼ ስሥሀ ተሯሩጠው መጡ።

"የሆነውን ነገር በምችለው መጠን እየተንተባተብኩ ነገርኳቸውና ቤቱን በሩቁ ስጠቁማቸው ደንግፈውኝ ያዘውኝ ሄዱ። ስውዬው ቢታስትሱት አደሰማ እያለማ። አምቡላንስ ተጠርቶ ውለታችንንም ያዘውን ሆስፒታል አደረሱን። እሱም እኔም እሣው ታየን። እሱን ስከፍተኖ ህዘሙና ወደ አያሲዩ አስገቡት። እኔን ከአምስት ደቂቃ ምርመራ በኋላ ሳንድ ምሽት አሳድረውኝ በማግስቱ ትውጣ ተባልኩ። የፖሊስ ምርመራ ስላለቀና ነገሩ እስኪጣራ እንድቀይ ተደረገ። እያለቀስኩና እየጮህኩ ለጓደኛዬ እንዲደርሱላት ብማጸንም፣ ማንም ከቁም ነገር የሚቀጥረኝ ጠፋ። ስውዬው ከልጅታ ምንም ልንረዳሽ አንችልም ብለው ጭራሽ ተጠርጣሪ እኔ ሆንኩ"

"ወይ... ወይ... የግፍ ሀገር..." ብለው አጨበጨቡና ደጋግመው በረጅሙ ተነፈሱ እናቷ። የቢሮው በር ተከፍቶ አባቷ ገቡ። ከሌላኛው ሶፋ ላይ ፈታቸውን በቮጋቸው ያግፈው እንዳቀረቀሩ ተቀመጡ። እናቷም አባቷም ልጃቸው ላይ የደረሰውን ነገር በዚህ ገዘገዝር ሲሰሙ የመጀመሪያቸው ነው።

"ከሦስተኛው ቀን የጓደኛዬን ፊላ ... በለሊት ሣህነ ውስደው ሲዮስ ሲሉ የተጠራጠረ ስው ፖሊስ ጠርቶ ሲያሲዙቸው ... ሁሉም ነገር ተጋለጠ። እኔም የቤተሰቦቿ ዕዳ ሆንኩ። አንድ ስሞን የሚዲያ ሞፈራና የፖለቲካ ዳንስ አደረጉን። ከዛ በኋላ አሰሯ የአፈር ሲሳይ ሆኖ ቀረች። በእ ይብታ እንኳን ብስሀ ታሪከሀን ልትናገር ስትል ልታዋርጂን ነው ... በኋላ ፈላጊ አታገኚም ... እያለ ጓደኛና ቤተሰብ ቁም ስትልሀን ያሳይሃል። ሁሉም ከነ ሀሙሚና የውስጥ ልብኩቱ ታፍኜ እንድሞት ነው የሚፈልጉት። ቅደ ... ከደረሰብኝ በላይ ምን ሊደርስብኝ ይችላል?"

ተገሰትሰታ ስታለቅስ ከተቀመጠበት ተነስቶ ከኀኗ ተቀምሞ በእንድ እጁ ጀርባሞን እያሻሸ፣ በሌላ እጁ እጇን ይዞ በተደጋጋሚ "አይዞሽ" እያለ ቀየ። ድንገት ከመካከላቸው ብድግ ብላ ተስፈንጥራ ተነስታ ወደ መስኩቱ ስትሄድ ሁሉም ደንግጠው ሊነሱ ሲሉ ወደ እነርሱ ዘራ፣

"ለምንሂ ለምን? ... ቢያንስ ለምን አያምኑኝም ነበር? ... አንዲት ሴት በእኩለ ሌሊት እየጮኸች ድረሱልኝ ስትል እንዴት እትታመንም? ... አምስት ደቂቃ በእንቅልፍ ልቡ ቀሚሴን ገልቦ ስላየ አንድ ሃዚም የደረሰብኝን ሲታይና መደፈር አለመደፈሬን እንዴት ሊጣራ ይችላል? የሚያሳፍሩ ሀኪጠት መጥረፍ ሲችል እነ

@OLDBOOOKSPDF

ሥን ስላልቻሉና ስላልፈለጉ ብቻ መሞት ነበረባት? ራሳዋን እንደቀሻሻ እስኪጣል ሥጠበት ነበረባችሁ? እኔ የማልታመነው ለምንድነው?

"ያ ነይሲ ልጅ ከሃይ ስኩል ጀምሮ እየተከታተለ አበሳዋን ሲያሳያት ... ለምን ልንጅ ... አስተማሪዎቹ ... አያምኗትም? ስለሚወድሽ ነው ... በፍትርሽ ተነድፎ ነው እየተባለ የሷ ስታይና መብት ሳይሆን የሱ ፍላጎት መከበር አለበት? ... ነጋ ጠባ ለተከሰሰው ... በየመንገዱ ... በየትምህርት ቤቱ እንደ መሲብ እታ እየታየን ... ልፅእናችንን ሲያዋርዱ ... የታሳት አተላቸውን ሲደፉብን ሊሳተላቸው ይገባል? ገና ከመጀመሪያው ... በታሳት ሲደፍሩን ... ሲገነትሱንና ሲለክፉን ... ዝም ባይባሉ ይሄ ሁሉ ይደርስብን ነበር? አገር ተደፈረ ... ድንበር ተመረረ ተብሎ ይጮከራል ፣ የሴት ልጅ የሰውነት ድንበሯ ሲደፈር ... ሰብአዊ ክብሯ ሲወረር ምነው የሚናገር ጠፋ?

"በየቤቱና በየትምህርት ቤቱ ... በየመሰሪያ ቤቱና በየሰፈሩ ... በየሚጸሙና በየጊያው ... በየታክሲውና ምግብ ቤቱ ውስጥ ... የሴት ሰው መሆንስ የሚከበረው ቦቹ ነው? በህግ ቢጻፍ ... በስብሰባ ቢለፈፍ ... በየሚጻፈው ቢለፈለፍ ... ምን ጥቅም አለው? የሃይማኖት ሩይጻው ... የጨፕ ህዝብነት ጉራው ... የሰው አዘባሪነት አንጀባው ምኑ ላይ ነው?

"ከሴት ተወልዶ ... ሴት አፍትሮ ... የሚያገባ ወንድ ... ወንድነቱ ... የሴትን ክብር በመግፈፍ ነው እንዴ? የሴት ክብርና ሰብእና ሲገፈፍ ዝም ብሎ ማየትና ግስተባበልስ አሞቲነቱ ምኑ ላይ ነው? የዴፋሪና የባሲጊ ወላጆች ናቸው ወይስ የተደፋሪና የተጠቂ ቤተሰቦች ማፈር ያለባቸው?"

አንዴ ቆማ ደግሞ ወዲያ ወዲህ እየተንገራደደች ... እጇን እያወናጨፈች ... ቢዘምት ራሷን ይዛ ... ለወራት በውስጧ የሞላውን ህመም ... የታመቀውን ጥያቄ ታፈሰው ጀመረ ። ዳሾና ተከላሽ ... ጠበቃና አቃቤ ህግ በሌለበት ። ጩኸቷን የሰሙ ቤተሰቧና አማካሪው ሴላሙ ብቻ ነበሩ ። ሌላው ሰው በራሱ እስኪደርስበት ከንፈሩን መጮ ... ዜናውን አዳንቆ ... በኑሮው ይጠመዳል ... ወደ አንቅልፉ የሚመልሰውን ሰበብና ምክንያት ተክናንቦ ይተኛል ። ተጠቂው ሌላ ሰው ... ጥፋተኛውም ሌላ ሰው ... ክለጉቱም የሌላ ሰው ነው ... በራስ ሰኪደርስ ። በራስ የደረሰ ቀን ግን ...

ድንገት ሁሉም ነገር የደከማት ይመስል ዝልፍልፍ አለችና ከወደ ጥግ ግድግዳውን ተደገፋ ወለሉ ላይ ተቀመጠች ። ተሯሩጠው ደጋግፈው ወደ ሶፋው አመጧትና እናቷ ጭን ላይ ጋደም አለች ። በውስጧ የታመቀውን ቁጣ ማውጣቷ ... ያሰፈችበትንና የሚሰማትን ነገር ሁሉ ለመግለጽ መቻሏ አስፈላጊ መሆኑንና ነገር ግን ረዘም ላለ ጊዜ የምዝር እገሳ እንደሚያስፈልጋት አስረዳቸው ።

እሱ ራሱ በየቀኑ ለተወሰነ ጊዜ እንደሚያያት ሲነግራቸው ተንፈስ አሉ ። ለሴላ ሕመምተኛ የማያደርገው ቢሆንም ... በጣም ስላሳዘኗቸውና ለመጻን ያላትን ተስፋ ስመረጽት ሳትጨነቅ በፈለገችበት ጊዜ እንድትደውልለት የራሱን የግል ተንቀሳቃሽ ሰልክ ቁጥር ሰጣት ። የተሻለ እንቅልፍ እንድትተኛና ለዕሚቷ መዋዠቅ የሚረጻትን መድኃኒት አዘዘላት ። በማግስቱ እንዲያያት ተጠቢ ከክርድ ዘፍል እንዲመለሱ ነግሮ አሰናበታቸው ።

@OLDBOOKSPDF

ሰኑቱን ሊያየው ስምንት ሊሆን ትንሽ ነበር የቀረው። ከሁለት ሰዓት በላይ መቆየታቸው አልታወቀውም ነበር። ወደ መታጠቢያ ቤትገብቶ ፊቱንና እጁን በቀዝቃዛ ውሃ ቢታጠብም ዘብድ እንዳለው ነበር። በመስኮቱ አንጻር ቆሞ ተከዘ። የሰማው ታሪክ ስሜቱን ዘፋኖ በጥብጦታል። ሌላው ጽጌረዳን ሲያይ ሲራክ ደግሞ ቢሮው ተቀምጦ ቲክሳስ እስኪንጋ ድረስ አላስችል ብሎት ሲንቀራጠጥ ቆየ። በቲክሳስ ሰዓት ማለዳ አስራ ሁለት ሰዓት ሳይሆን ንጹህ ጋ ደመለ። አንድ ሁለት ጊዜ እንደጠራ አነሳች።

ማንኑን ከነገራት በኋላ፣ "ያቅርታ ንጹሕ ... በጠዋት ደመልኩብሽ መስለኝ ... እንዴት ነሽ?" ሰላምታ ተለዋወጠው ትንሽ ካወሩ በኋላ እንዴት እንደ ደመለ ጠየቀችው።

"እኔ እንኳን ... ኢሚያል ላደርግልሽ ነበር ግሳቤ ... ግን የምንገርሽ ነገር ትንሽ ሲንሲቲቭ ነገር ስለሆነ ... ምናልባት ኢሚያሉን ከዶክተር ሴላ ጋር የምትገሩት ከሆነ ብዬ ነው መደወሉን የመረጥኩት" ሲል፣ ፊቷ ሁሉ ጆሮ ሆኖ ነገሩን ለመስማት አቁበዮበች።

"እሺ ... ተቸገርክ ግን ...እኔ ልደውልልህ ታዲያ?"

"አረ ምንም ችግር የለም"

"እሺ ታዲያ ምንድነው ጉዳዩ?" ሲራክን ከአዲስ አበባ ድረስ ያስደውለውን ነገር ለመስማት ጓጉታለች።

"ያሄንን ነገር እንድነገርሽ ያስገደደኝ ምክንያት ... አንድም ነገሩ ለኔ ከጠበቅሁት ጋራ ፈጽሞ የማያሄድና ያስደነገጠኝ ነገር ስለሆነ ነው ... ከዛም በላይ ባሞር ጊዜ ትውውቃችን ምን እያነት የሞሀና ትን ሰው መሆንሽን ስላየው ነው። ያክተርም እዚህ መሞኖ እንዲሠራና የሚቻላችሁን ሁሉ ለሀገርና ለወገን ለመስጠት የከፈልሽውን ዋጋ ስለማውቅ ነው። ነገሩ ተስፋ ያለው ከሆነም በጊዜ ማወቁ ስለሚበጅ ብዬ ነው" ትንሩሹን ሰዞ ዝም ሲል፣

"እሺ እየሰማሁ ነው ..." አለች፣ ረጋ ባለ ድምጽ።

"ባሁሩ ምን መሰለሽ! በተለያ መጨረሻ መሞተሽ ከሄድሽ ጊዜ ወዲህ ... በያክተር ሴላና በሚስዮር መካከል ያለው ግንኙነት መስመሩን እየለቀቀ መሆኑ በጣም ስለረበሸኝና ከሱ ፈጽሞ የማልጠብቀው ነገር ስለሆነ ነው። እሷ እንኳን ያው ልጅነቱም አለ ደግሞ በባህርይዋም አርፋ የምትቀመጥ ልጅ አይደለችም። እኔ ለነገሩ የከሊኒኩን ቦታ እንዲሠራበት ስትወትውተው ጀምሮ ነገሩ ብዙም አላማረኝም ነበር። መቦመድ እንደማያመጣ ገብቶኝ ነበር። አሁን በማየው ነገር ብዙ ደስተኛ ስላልሆንኩ በበኩሌ እዚህ ያለውን ሥራ በትርብ ሰመተውም እያሰብኩ ነው ... መጀመሪያ ላይ ብዙ ነበር ተስፋ ያደረኩት" ብሎ፣ ዝም አለ።

"የምትለው የኔም ፍርሃትና ጥርጣሬ ነበር ... ግን ምንድነው አንተን በርግጠኝነት ነገሩ እንደዚህ ነው እንድትል ያስባለህ። ስላላመንክህ ሳይሆን ... የተጨበጠ ነገር መያዙ ለኔ አስፈላጊ ስለሆነ ነው" አለች፣ በተገራ ስሜት አልባ ድምጽ።

@OLDBOOOKSPDF

"ያው የስ ቢር ነው የሚያመሽት ብዙ ቦን ...አንዳንዴ ማታ አስካምስት አስከ
ዳስት ስአት ። ማለቱ ሀመም ተኛም ሉላ ሠራተኛም በሉለበት ነው የምልሽ ። ብዙ ጊዜ
ሚ መጪና ነው የሚመላለስት ። ዘነበ ወርቅም የሆኑ የሥጋ ደዊ በሽተኞች አሉ መስለኝ
...ብቻ የትም ሲሄድ እሷን አንጠልጥሎ ነው የሚዘረው ። ብቻ አብረው ስታያቸው
...የሚገባሽ ነገር አለ ። ልክ ያልሆነ ነገር ለማወት እኮ ሁላችንም ልጅች አይደለንም ።
ያንም እያደረጉ ነውና ምንም ባይኔ ያየሁት ነገር የለም ። ነገሩ በዚህ ከተጠለ ፡ አንቺም
እዛ ሠርንሽና መራራታችሁ መፍትሄ ካላገኘ ግን አካሄዱ ወደ የት ሊሄድ እንደሚችል
ለማንም ግልፅ ነው" አለ ፡ መዘራት የሚፈልገውን ዘር ከዘራ በኋላ ነገሩን አያለበበ ።

"ዘማም አመሰግናለሁ ...አደራ አንደደወልክልኝ አይወት ...እኔም አልነግረውም
...አዲስ ነገር ካለ አሳወቀኝ ... ሉላ ኢሜል አድራሻ አለኝ ... ቲክስት አደርግልሃለሁ"
ብላው ፡ ትንሽ አውርተው ስልኩን ዘጉት ። በመስኮቱ አንጻር ቆሞ ፈገግ ብሎ አንቱን
ወደ ታችና ወደ ላይ ከዚያም በትክሻው ላይ እያዞረ መጣጥሮ አንቋቋው ። "እውነትም
ሉላሙ ... ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ በማም ሉ---ላ ሰ---ው ትሆናለህ" ብሎ ሳቀ ።

ወዲያው ስልኩን አወጣና ሉላሙ ጋ ደውሎ ስለ ጽጌረዳ ያለውን ሁኔታ
አወሩ ። "ያዝተር ሉላ ... ከስራ በኋላ ካልተያገኘ ... ራት በልተን በዛውም አዲስ የወጣ
ያማርኛ ኮሜዲ ፊልም አለ ... ለምን እሱን አልጋብዝህም?"

"በደስታ ... ከፈለግህም አንዱን መኪና እዚህ ትተን ባንድ መኪና መሄድ
እንችላለን" ብሎት ፡ አብረው ሊያመሽ ተስማሙ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 37 ፡

ያለፉት ሁለት ሦስት ሳምንታት ሴላሠው ግራ ገብቶት ተጨንቋል ። ንጹሕ ጋ ደጋግሞ ቢደውልም ቀይቹ እደወላለሁ የሚል የጽሑፍ መልእክት ትልካለች ... ወይ ደግሞ ስልኩን ከናካቴው አታነሳለትም ። ንዋይና አርሴማ ጋ ሲደውል ከነሱም ጋ እንደጠፋችባቸውና ስልካቸውን ብዙ እንደማትመልስ ነግረውታል ። ምናልባት መምጣቱ የተሻለ መሆኑን ስለነገሩት፣ የሚሄድበትን ጊዜ ለመወሰን እየታገለ ነው ። የክሊኒኩ ሥራ ካሰበው በላይ ችግር የበዛበት ሆኖ ስላገኘው ተስፋ እየቀረጠ ነው ። ጠቅልሎ መመለሱ ብቻ ነው የታየው የተሻለ አማራጭ ።

ቅዳሜ ጠዋት በማለዳ ተነስቶ፣ ለሩጫ መስቀል አደባባይ ቀይቶ ተመለሰ ። አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ነገሮችን ሲያወጣና ሲያወርድ ቀየ ። የጠዋቷ ዐሐይ በመስኮት ገብታ ክፍሉን አሙቃዋለች ። በቀስታ የሚነፍሰው ንፋስ ዛፎቹን ከወዲያ ወዲህ ያወረገረጋቸዋል ። በመስኮቱ ዘልቆ የሚሰማው የሽውሽውታ ድምጽ አንዳች ምስጢር በሹክሹክታ ሊነግረው የሚሞክር ይመስላል ። ላፕቶፕ ኮምፒዩተሩን ከፍቶ ኢንተርኔት ውስጥ ገብቶ ወዲያ ወዲህ እያለ የተለያዩ ዜናዎችን አነበበ ። ኢሜይሉ ውስጥ ከንጹህ የተላከ መልእክት ስላየ ገርሞት ቸኩሎ ከፈተው ። ኢሜይል መላክ ቀርቶ ማንበብም እንደማትወድ ያውቃል ።

ስልኩን ከመመለስ ይልቅ ለምን ኢሜይል መላክ እንደ ፈለገች ሲያስብ ከነከነው ። የዘፋቱ ደግሞ ኢንተርኔቱ በጣም ቀርፋፋ ሆኖ መልእክቱን ሳይከፍት ቀየ ። ርእሱ ላይ አስቸኳይ ይላል ። መልእክቱ ባሜሩ የተጻፈ ሲሆን፣ ለአስቸኳይና አስፈላጊ ጉዳይ ስለምትፈልገው በቻለው ፍጥነት ወደ አሜሪካ እንዲመጣ የሚያሳስብ ነው ። መዘግየቱ ትልቅ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ገልጻለች ። ነገሩ የከረረ መሆኑን ውስጡ ነገረው ። የጉዞ ወኪሉ ጋ ደወለ፣ ለዛን ለታው ማታ ቲኬት አስቀርጦ ለጉዞ መዘጋጀት ጀመረ ። ዋጋው በሌላው ጊዜ ሦስት ቲኬት የሚገዛ ቢሆንም አማራጭ አልነበረውም ።

ስልኩን አላነሳ ስላለችው በማታው በረራ ተነስቶ በነጋታው እንደሚገባ የጽሑፍ

@OLDBOOOKSPDF

ሞልለዘትና ኢሜይል አደረገላት። ድንገተኛ ጉዳይ አጋጥሞት ስለሚሄድ ሲስተር ዘቢባ የሱን ቦታ እንድትሸፍንና ዶክተር ሲራክ በሚዲካል ጻይሬክተርነቱ አብሯት እንዲሠራ ሌሎቹም በተቻላቸው አቅም እንዲያግዟቸው ስሁሉም ግልባጭ አድርጎ ኢሜይል አደረገላቸው። እናቱ መርካቶ አረፋፍደው ሲመጡ ነገሩን ሲነግራቸው ድንጋጤ ያዛቸው።

"ምንድነው ደህና አይደለችም እንዴ ንዪህወርቅ ...ልጆቹስ ደህና ናቸው? ..." እያሉ፣ በጥያቄ አጣደፉት።

"እታቲ ... ደህና ናቸው ... ያው ታውቂው የስ በኔ እዚህ መሆን ደስተኛ አይደለችም ... ከዛ ጋር የተያያዘ ነገር ነው የሚመስለኝ። ባለፈው የሄድኩ ጊዜ በመከከላችን ብዙ አለመግባባት ነበር። ወደዚህ ስመጣ በጣም እኩርፋ ነበር። ስለዚህ ቶሎ መሄድ አለብኝ" ብሎ፣ እጄን ፈታ ጨበጥ እያደረገ በረጅሙ ተነፈሰ። ውሰጣቸው ከልክ በላይ ተጨነቀ። ነገሩ ውሎ አድሮ እንደሚመጣ ያወቁት ጉዳይ ቢሆንም ድንጋጤያቸውን አልቀነሰውም።

ከሰዓት ላይ ሲስተር ዘቢባ ጋ ደውሎ ሁኔታውን በድፍኑ ነገራት። ኢሜይል ያደረገውን የክሊኒኩን ጉዳይ አስረዳትና በነገሩ ተስማማች። ምስጢርና ሳንቾ ማታ እብረው መጥተው ቦሌ ሊያደርሱት ተነጋገረዋል። ሲራክ ጋ ደወሎ ሁኔታውን ባጭሩ አስረዳው። ቦሌ ላድርሰሀ ሲለው እነ ምስጢር እንደሚያደርሱት ነገረው። ስልኩን ሲዘጉት በያንዳንዳቸው ስም በከፈተው ፋይል ውስጥ፣ ልክ ሌላሠው እንደሚጽፈው አድርጎ የእስቱን ክስተት በሌላሠው ፋይል ውስጥ እየሳቀ ጻፈ።

ሌላሠውን ቦሌ ከደረሱ በኋላ ጊዜው ም ስለመሸ ሳንቾን ቤቱ ጥላ በቀጥታ ወደ ቤት ሄደች። ስትገባ እናቷና የምትወዳት እክስቷ ወይዘሮ ዘምዘም ሳሎን ቤት ውስጥ ቶሎ እየቀረጣጠሙ ሲያወሩ ደረሰች። አንገቷ ላይ ያደረገችውን የማዳመጫ ሽቦ ጠቅልላ ኪሷ ውስጥ ጨመረችና ጃኬቷን አውልቃ ሶፋው ላይ ጣል አደረገችው። እንደ ልማዷ በቀመችበት ፈጣማዋን አውልቃ ወርወር ወርወር አደረገቻቸው።

እጆቿን ከፍታ ሁለቱንም አቅፋ ሳመቻቸው። "እንዴት ነው ዛሬ ... ፍቅር ቦኋል ... እስካሁን ስታወሩ እንዳይሆን ብቻ ... ምን ተገኘ ዘሚሻ?"

"ምን ጠፋ ብለሽ የኔ ማር ... ያው አንቺን እየጠበቅን ... የባጥ የቆሙን ስናወራ ነዋ ...አሮጊት እኮ የሚሰራ እንጂ የሚወራ አያጣም ..." በድጋሚ ቡና ተራልቶ ሲላላቁ ሊሄዱ ከሌሊቱ ሰባት ሰአት ላይ ወደ የመኝታቸው ሄዱ። ሁሉም ደክሟቸው ስለነበር ጠዋትም ከራፈደ ተነሱ። ምሳ ተቀርቦ ሲበላ ሲል ሁለት የቀዩ የእናቷ ጓደኞች መጡ። ከምሳ በኋላ አያት ከምትኖረው ጓደኛዋ ጋ ተጫዋረው ሰለነበር ሁሉንም ላመል ያህል ጉንጭ ጉንጫቸውን ተሰናበተቻቸው።

"አንቺ ልጅ ... ዋ ብያለሁ ይሄ መጥፋት ... ምን ተገኘ? ... መቼ ነው ደግሞ ቤት ሞጥተሽ የምታድሪው? ... ቤተሰቡን ሁሉ ይገረ መጥቼ ተታውሞ ሰልፍ እዚህ ግቢ ሳንሰለፍ ..." ብላ፣ ሳቀች አክስቷ።

@OLDBOOOKSPDF

"ዘሚዬ ሙች ... በሚቀጥለው ትዳሜ እንቺ ጋ ነኝ ... ጋሽዬን ... ልጆቼን ሁሉ እኔን እንደ ገመገሽኝ ግመጪልኝ እሺ ..." እጇን አመለብልባ መጣች ።

ምስጢርና ዓይኖዋ ለማውራት ጸዋ ያለ ቦታ ስለፈለጉ ካዛንቺስ ኢንተርኮንቲኔንታል ተቀላጠሩ ። ስለ ሥራ ... ስለ ዓይኖ ታሞው ... በትርብ ዴባይ ሄዳ በነበረ ጊዜ ስላየቻቸው ነገሮችና ... ከእሥኖዋ ጋር እየተካረረ ስለመጣው የተለመደ ግጭታቸው በሰፊው አጫወተቻት ። ሲመጋብት የቀራቸው ሦስት መር ቢሆንም ፣ አሁንም በብዙ ጉዳዮች ላይ ፈጽሞ እንደማይስማሙና የዜተሰበሰም ጣልታ ገብነት ካሁት ሚንትላቲ ላይ እየወጣ መሆኑን ነገረቻት ።

"ብታዩ ከዜተሰቦቹ ቤት ጓር እኔ ነኝ ያለ ቀንጅ ሁሉ የተሟላለት ቤት አላቸው ። እሱ እባ እንኑር ባይ ነው ። ገንዘብ ሲሽ ማድረግ ስለምንችል የራሳችንን ቤት ቶሱ ሰርተን እንወጣለን ባይ ነው ። እንደዬ እናቱ ማንም አይችላትም ... ውጣ ነው የምታኝከኝ ። ኮንዶሚኒየምም ቢሆን ተከራይተን ራት ብለን እንኑር ስለው ምንም ሊገባው አልቻለም ። በዛ ላይ እሱ መጽሐፉ ውስጥ ሊቀበር ... እኔ ልንገረገብለት" ብላ ተንሸገሸች ።

"ታዲያ ምን አሰብሽ አንቺ? "

"ስሞኑን ትንሽ ተኳርፈናል ... እኔ ሰርተ ይገፋ ባይ ነኝ"

"ካልሆነ ይሻላል ... ወንዶቹ እንደሆነ ካገቡሽ በኋላ ግድም የላቸው ። ሌላ ሰው ነው የሚሆኑት "

"ማግባት ራሱ ኮ ሌላ ሰው ነው የሚያደርገው ። እንኳን እናት ... ዘመድ ... ሌላ ኑተት ተጨምሮበት ። በናትሽ ሚሲ ... በቃ ሁሉ የኔ ችግር ብቻ ነው የሚመራው አይደል? በቃ ኮ ሳይኮሎጂስት ስትሆኚ ማንም የምትቸገሪ አይመስለውም አይደል ። በናትሽ የሰንት ሰው ችግር ስትሰሚ ነው የምትውዪው? ያንቺን ችግር የምትነግረው ሰው አለ?"

"ኧረ ... እንቺስ አለሽልኝ አይደል ... ድግሞስ ምን አለ ብለሽ ነው ለአትመ መሬ የደረሰ ነገር" ብላ ሳቀች ።

"ምንም አጸም ቢጤ አልመጣም? ... ያስ ስር ስርሽ ሲል የነበረው የማትወጂው ጨጨው የእብድ ዶክተሩ?" አለች ፣ በሹፈት ዓይነት ።

"ውይ ... ሲራክ? ... እሱማ ተንጋዥን አይደል እንጂ ... ስንቱ እናውራው ማርቲ?"

"ቀይ ግን እንጂ ብቻ ... ልጁ ኮ መልኩም ... ስታይሉም ... ምን ይመጣሃል? "በዛ ላይ ሂ ኢዝ ቨርይ ስማርት" ብላ ሳትጨርስ ፣

"እዪዪ ... ማርቲ... ያለተ ነገር ነው የሱ ጉዳይ ... ምንም ዕድል የለውም ። ይልቅስ ሌላኛው ልጅ ... ባለፈው ቡና አብሮን የጠጣው ትዝ ይልሻል? ስኢዶ ..." ስትል ፣

@OLDBOOOKSPDF

"ኧረ በናትሽ ... እሱ ለቦዲ ጋርድነት ... ወይም ለሾፈርነት ከሆነ እሺ ... ምኑ ነው እሱን እሱ ደስ ያለሽ ... በናትሽ እስኪ ከላስሽን ጠብቂ ..." አለች ፥ ቮሮዋን ግመን እቅፏ ሳያሲን እፍኖላ ።

"ችግሩ ኮ ያ ነው ። ምንም የማ ኑ ሙ ቲው ን ሰው በኪሱ መግመት ... ብር ወይም ፈገራ ያለ የተመለደ አለ እንዴ? ምን ጉደለው?" አለች ፥ በስጪት ብላ ።

"ምን እንደሚያንጨረጭርሽ ታው ቂያለሽ ሚሲ .... ልበናሽ ስለሚያው ቱው ነው እውነቱን ።"

"ምኑ ነው እው ነቱ ማርቲ ... ያሃ የልምድ ሳያኮሉጂስትነት ይትርብሽ አላልኩሽም ነበር?" ብላ ፥ እጇን ቱንቦዋ አደረገቻትና "ስሚኝ ... እኔ ደስ የሚለኝ ... እንደሱ አይነት ወንዳወንድ የሆነ ... ግን ሙንቻው የደግ ልቡ አሽከር የሆነ ... የኋላ ታሪኩ የፊት ዕድሉን እንዳጠለሸን የማያፈቅድ ...ከራሱ በላይ ሰው የሚወድና ኃላፊነት ለመሸከም የማያሸሽ ወንድ ነው ። ከጎዳና አዳሪነት እነ ነው ራሱን አስተምሮ እዚህ የደረሰው ...ከዚህ በላይ ምን ትፈልጊያለሽ?"

"ብይ በይ ... ለእኔ ... እንዴ ጎዳና ላይ የኖረ ... ሁሌም የጎዳና ልጅ ነው ... እንዳትታለዪ ። ሁሉም ያሁን እሺ ... እሱ መ ሰ ሊ ም አንቺ ከርስቲያን ... እናትሽ እሺ የሚሉ ይመስልሻል? ... ምንም የማያመስል ነገር አታ ወ ሪ ... በቃ ጥሩ ሰው ነው ... በስውነቱ ወ ደ ጂ ው ። ባል ግን ... አ...አ ... ብሪት መገዢያ የሚሆን ... ሙንቻው ላይሆን ዲግሪው ና ጭንትላቱ ደልደል ያለ ... ከላስ ያለው ሲሆን ነው የሚያምረው ። በናትሽ እደራ ...እንዳታጥርጪኝ" ብላ ፥ እጇን በመንገሽገሽ ወዲያ ወዲህ አደረገች ።

"ምንም ነገር የለም ኮ ... አዘሂች እንዴ ልጅቷ ... ስሜቱን ነው የነገርኩሽ ... በቃ ለመጀመሪያ ጊዜ ወ ሰጠ ው ድድ ያደረገው ሰው እሱ ነው ። እሱኮ ምንም የሚያው ቀው ነገር የለም ... ምንም ያለኝም ነገር የለም ... ማሚም እንዴ ልጂ ነው የምትወያው ።"

"ዘቃ ... እንደሱ ጥሩ ነው ... አየሽ ጨዋ ልጅ ነው ... ልኩን ያታል ... ልባድርገ ያላሰበውን እንዳታሳስቢው ተጠንቀቂ ... ፍትሪኛ አገኛለሁ ብለሽ ጥሩ ወንድምሽን እንዳታጪ ... 'ወንዶች ወንድም ሲሆኑና ፍትሪኛ ሲሆኑ ሁለት የተለያዩ እንሰሶች ናቸው' ... ያለችው ማን ነበረች? ... ዮዲት ጉዲት ነበረች?" ብላ ፥ ከት ብላ ስትስቅ ምስጢርም ሳትወድ በግዷ ላቀች ።

"ጉላባሽ ይመ ላና ... እንቺን ነበር በዮዲት ጉዲት ማስገረሩ" ስትል ፥ እንደገና እንደ ሞኝ ከት ከት ብለው ሳቁ ።

"ካልሽስ ዮዲት ጉዲት ብትኖርልኝ ... ያንን ጉደኛ ሰው ዬሽን ... ማነው ስሙ ... ግስረሳ ነው ... እሱን ነበር መስጀ የማስጠበጥበው ...ማስረሻውን ለራሱ አይጠቀምም እንጂ ... ለመሆኑ ሰሞኑን አይተሽው ታቂያለሽ?"

"ኧረ እኔንጃ ስሙን አትጥራብኝ ... የው ይከተር ሌላ በየላምንቱ ያየዋል መስለኝ ... ትንሽ ጋብ ብሉ ለታል አሁን ደግሞ ።

@OLDBOOOKSPDF

ከውጭ የመጡ ሌሎች ጓደኞቻቸውን ተቀላቅለው፣ ለአራት ግሪክ ከለላ ጥሩ ምሽት አሳለፉ። ከዚያ ሲወጡ መብራት ድርግም ብሎ ጠፍቶ ስለነበር ከተማው የተወረረ ይመስላል። ጓደኞቿን እድርሳ ቤት ስትገባ ከምሽቱ አራት ሰአት ተኩል ሆኗል። መብራቱ ስለጠፋ ብዙ ሻማዎች በየጠረጴዛውና ጥጋጥጉ ተስክሰው ሳሎን ቤቱ መትደስ መስሏል።

እናቷ ከሶፋው ላይ ኩርምት ብለው ጋደም ብለው ድምፅዋን ሲሰሙ "ሚሚዬ ... መጣሽ?" አሉ፣ ደከም ባለ ድምጽ።

"ይቅርታ ማሚዬ መሸ በጣም ... መብራቱ ደግሞ ከተማው ሁሉ ጠፍቶ ... ጨለማ የተደፋባት መስላለች። ምነው ደህና አይደለሽም እንዴ?"

ተነስተው ለመቀመጥ እየሞከሩ፣ "አይ ... ሻረ ... ደህና ነኝ ... ትንሽ ደክሞኝ ነው ... መብራቱ ሲጠፋ ደግሞ ተጫጫነኝ መሰለኝ" አሉና ጋቢያቸውን ሰበሰቡ። አጠገባቸው ተቀመጠችና አንገታቸው ስር ሸጥጥ ብላ ሳመቻቸው።

"ሰውነትሽ ደግሞ ግሏል ... ምነው አሞሻል እንዴ ... ሰሞኑን ምንም ደህና አልመሰልሽኝም ... ቅድም ሳይሽ ከላ ያለ መሰለኝ?"

"አይ ደህና ነኝ ... ሰሙኑን እንቅልፍም እምቢ ብሎኝ ነበር ... ትንሽ እንደ ሳልም ጠዋት ላይ ..."

ጋቢውን ተጋርታቸው እንዳቀፈቻቸው ባንድ እጇ ጆርባቸውን አሻሸቻቸው። "ታዲያ ለምን አትታዩም?"

"ቅዳሜ ጠዋት እዚህ ኮሪያ ሄጄ ነበር ኮ ... ልነግርሽ ሰል ቅዳሜም የዶክተር ሌላው መሄድ ... ማታም ዘሚ መጣችና ... ያው ዛሬም ይሄው ሳይታወት አለቀ" ብለው፣ ትንሽ አሳላቸው።

"እና ምናሉሽ ... መድሃኒት ሰጡሽ?"

"ብዙም ርግጠኛ አይደሉም ... እስኪ ለነገ ስፔሻያሊስቱ ያይሻል ብለዋል። ራጁና ሲቲ ስካኑ ላይ ግን የሚያሳይ ነገር አለ ... የዛሬ አምስት አመቱ ኦፕሬሽን ታሪክ ሰንገራት ... ትንሽ የፈራችው የጡቱ ካንሰር አገርሽቶ እንዳይሆን ነው። የሳምባ ምች ነገርም ሊሆን ይችላል ብላ የሚዋጥ መድሃኒትም ሰጥታኛለች"

"እማ ... ትዬ ዘሚን ይዛን ልትነግሪያት አንቺ ነሽ የጠራሻት እይደል?" ብላ አንገታቸውን እቅፉ አፋጠጠቻቸው። ዝም ሲሉ ድንገት እምባዋ አመለጣት።

"ኤዲያ ... ምን ትላለች ይቺ ... ምንድነው እንዲህ መሆን? ... ነገርኩሽ እኮ ምንም የለም ... ውጤቱ ገና ስፔሻያሊስት ሃኪሙ ሲያየኝ ነገ ነው የሚረጋገጠው ... ደግሞ መድሃኒቱን ከጀመርኩ በኋላ ደህና ነኝ" አሉና እምባቸው ሊያመልጣቸው ሲል ብድግ ብለው ወደ መታጠቢያ ቤት ሄዱ። ነገሩን እድበስብሰው አለፉና ሌሎች ነገሮችን

@OLDBOOOKSPDF

እያነሱ ሲጫወቱ አመሹ ። በማግስቱ አብረዋቸው ሆስፒታል ልትሄድ ተሰማምተው ወደ የመኝታቸው ሄዱ ። ሌሊቱን ሙሉ አንዴ ስለ ማስረሻ ... ደግሞ ስለ ሌላው ... ከዛ ለለሳንቾ ... ደግሞ ስእ ለናቷ ስታስብ ... በሚንቀት ስትነቃና ስትባንን ወደ አነጋጉ ላይ ትንሽ አሸለባት ።

@OLDBOOOKSPDF

• 38 •

የሉላሠው የአሜሪካ ጉዞ ጠመዝማዛና ረጅም ነበር ። በፍራንክፈርት አድርጎ ቺካጎ ቀይቶ በመንገድ ላይ ከሃያ ሰባት ሰአት በላይ ቆይቶ ኦስቲን ገባ ። እቤት ደርሶ ሻወር ወስዶ አልጋ ውስጥ እስኪገባ ተጣድፏል ። ልጆቹ ደግሞ ባይኑ ላይ እየሄዱበት ነው ። ከንጹሕ ጋር አስቸጋሪ ጊዜ እንደሚጠብቀው አውቋል ። አሁንም ምን እንዳሰበች ወይም አጣዳፊው ጉዳይ ምን እንደሆነ በትክክል ሊያውቅ ግን አልቻለም ። ቺካጎ ሆኖ ሲደውል ስልክ መመለስ የማትችልበት ሁኔታ ላይ እንዳለችና የኦስቲን አየር ማረፊያ እንደምትጠብቀው የጽሑፍ መልእክት ላከችለት ። ኦስትን እንዲገባ መድረሱንና ሻንጣ መረከቢያ ጋ እታውን እየጠበቀ መሆኑን የጽሑፍ መልእክት ሲልክላት ፣ በአስር ደቂቃ እንደምትደርስ መለሰችለት ።

ደጅ ወጥቶ ግራና ቀኝ እያየ ሲጠብቅ ቆየ ። ድንገት አጠገቡ የማያውቀው መኪና ሲቆም ደንገጥ ብሎ ሲያይ እሷ ናት ። ወርዳ ወዶ አርሱ ስትመጣ ሊስማት ጠጋ ሲል ልትጨብጠው እጇን ሰጠችው ። "ይቅርታ ... መንገድ ተዘጋግቶ አቀየኝ ... እንዴት ነበር ጉዞ ስትለው?" ነገሩ ሁሉ ከጠበቀው በላይ ድንግርግር ብሎት የሚለው ጠፍቶት ገረም አለ ። እታውን ከኋላ ካስገባ በኋላ ገብቶ ተቀመጠ ። ሁልጊዜም ልትገዛ የምትመኘውን ማርሴዲስ ኤም ክላስ መኪና ይዛለች ።

"ሰላም ነው?" አለ መኪናውን እያስነሳች ከአየር ማረፊያው ሲወጡ ።

"ደህና ... እንተ ድካሙ እንዴት ነው አለች?" ፊቷን ከፊት ለፊት ወዳለው መንገድ እንደተከለች ። ጥቁር ቱታና ስኒከር ጫማ ሲሆን ያደረገችው ጸጉሯ ላይ ሻሽ ጣል አድርጋለች ። ሁሉም ሉላሠው የማይወዳቸው አለባበሶች ናቸው ።

"ልጆቹስ...?" አለ ፣ እንዴት አብረዋት እንዳልመጡ ተገርሞ ።

"ትምህርት ሊጀመር ... ገና ላምንት ስለቀረው ... እዛው ሚኒሶታ ናቸው ... እንዳያስቸግሩ ብዬ መምጣትህንም አልነገርኳቸውም ። እነ አታቲ ደህና ናቸው?"

@OLDBOOOKSPDF

ውስጡ ሲጨስና መሽመጡ ቁርጥ ሲል ተሰማው ። ዞር ብሎ አይቷት ዝም አለ ። ከሆነ በኋላ ቤት እስኪደርሱ ድረስ ምንም አላወሩም ። ቤት ደርሰው ዕቃውን ይዞ ሲገቡ ሁሉም ነገር ቅይርይር ያለበት መስሰው ። ከፍራጁ ውሃ ተድቶ ተነጨና ሶፋው ላይ እንዘሙ ብሎ ተቀምጠ ። ግራና ቀኝ ሲያይ ሁለቱ ውሾች ድምጹን ሰምተው ላዩ ላይ ታንበሳጥለው ሲላፉት ለጥቂት ጊዜ ትኩረቱን መለዱት ።

"ራት ቀለል ያለ ነገር ሰርቻለሁ ... አውን መብላት አስኝቶሃል ወይስ ..." ስትለው የማያውቃቸው ሰዎች ቤት ያለ መስሎ ተሰማው ። ንጹህ አልመስል ብላው ትኩር ብሎ ሊያያት ቀየ ። ነገሩ ካሰበው በላይ ከባድ መሆኑ ገባው ። ብዙ ነገሮች እንደተበላሹና ተስፉ እንደሌላቸው መቁጠሩ ሊመጣ ላለው ነገር የተሻለ ሊያዘጋጀው እንደሚችል አሰበ ። ዙሪያ ገባውን ሲያይ የሱና የሷ ፎቶዎች በሙሉ ከስፍራቸው ተነስተዋል ። የቷት የልጆቹ ፎቶዎች ብቻ ናቸው የቀሩት ።

"በጣም ስለደከመኝና ሰውነቱም በጣም እየጨፈገገኝ ስለሆነ ... መጀመሪያ ልታጠብና ... ከዚያ ይደርሳል" ዕቃውን መደላይ ይዞ ሲወጣ ሰልክ ስለመጣባት በጭንቅላቷ እሺታዋን ገልጻለት መደ ስልኳ ዞረች ። መኝታ ቤቱ ሲገባ ሌላ መስሏል ። የመልበሻ ክመዲናውና ክፍሉን ሞልተውት የነበሩ የሷ እቃዎች ሁሉ በስፍራቸው ቦሉም ። ቁም ሳጥኑን ሲያየው የሱ ልብሶችና እቃዎች ብቻ ናቸው ያሉት ። አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ሲያስብ ሁሉም ነገር ሀሪበት ።

ነገሩ በየደቂቃው እየከረረ መሄዱ ከሚችለው በላይ ስለሆነበት ልቡ ወደ ሆዱ የሰመጠች መስሎ ተሰማው ። እንደምንም ተነስቶ የሚቀይረውን ልብስ ይዞ መታጠቢያ ክፍል ገባ ። ሲታጠብ የደከመ ሰውነቱ ትንሽ ተፍታታ ። ልቡ ሲገልጸው በማይችል ስቃይ ተይዞ ሞንትላቱ ደነዘዘበት ። ምን ማድረግ እንዳለበት አላወቀም ። ሁሉንም ነገር በዝምታ ለማየት ወሰኖ ወደ ታች መረደ ።

መደላሱን ሲደርስ ሰልኳን እንደያዘች ምግቡን አቀራርባ የራሷን እውጥታ የሱን ሰየን ካስቀመጠችለት ራቅ ብላ እየበላች ትስታለች ። አንድ ቁራሽ እንጀራ ዘርግቶ ትንሽ ሾሮ እድርጎ የመጀመሪያውን ጉርሻ እንደ ጮረሰ ሰውነቱ አልቀበል ስላለው በውሃ አመራርዶ ትቶት ተነሳ ። በደሀናው ጊዜ ለአንድ ቀን እንኳ ወጥተው ከመጡ ፣ ምግቡን ባንድ ሳህን ላይ አቀርበው ሲገራረሱና ሲላቆ ፣ ቤቱ ባንድ እግሩ ነበር የሚቀመው ።

የያዘችውን ሰልክ ስትጨርስ ፣ "ቤቱም መኝታ ቤቱም ተቀያይሯል ..." አላት ፣ ውሃ የጠጣበትን ብርጭቆ በጣቱ እያሽከረከረ ።

"ምን ይደረግ ... ሰው ሲቀየር ቤትም ይቀየራል ..." አሰች ፣ ሰልኳን ጠረጴዛው ላይ ጣል አድርጋ የበላችበትን እያነሳች ። "ብዙ የምንነጋገረው ነገር ይኖራል ... አሁን ግን ገላውም ስላደከመህ አረፍ ብትል ይሻላል ። እንዳየኸው ትልቁን መኝታ ቤት ላንተ አስተካክዬልሃለሁ ። እኔ የእንግዳ መኝታ ቤት ታች ሆኖሰሁ ። ብዙ መነጋገርና መጨረስ ያለብን ነገር ስላለ ነው ልጆቹ እዛው እንዲኖዩ ያፈለኩት ። አሁን አንድ የማገኘው ሰው ሰላሳ መሂድ አለብኝ ። በታ አረፍና ነጋ ወጥት እናወራለን"

@OLDBOOOKSPDF

ነገሩ ካትሙ በላይ ሆነበትና ብድግ ብሎ ፊቱን በእጅፅ አሻሸ ። "ገዱለም ... እኔ ሆቴል መቆየት ይሻለኛል ። የዛሬው መኪና ቁልፍ ካለ እሱን መጠቀም እችላለሁ ። የቤቱ ቁልፍ ስለማያስፈልገኝ ይሄዉልሽ ። ትንሽ ልረፍና ሰንቃ እደውልልሻለሁ ። እንዳልሽው በተረጋጋ አእምሮ መነጋገር እንችላለን ። ቸንሽን ማቱድ እንድትችዪ ወሞት አራት ሰአት ላይ ... ሠዉኒ መገናኘት እንችላለን ። ካልቻልሽ ቪዘበት አድርጊልኝ ። እምም ሌላ ምን አለ? በቃ ... እንዳይረፍድብሽ ... የሚያስፈልጉኝን መቀየሪያ ልብሶች ይዤ መጣሁ ..." ብሎ ፣ መልሺንም ሳይጠብቅ ወደ ላይ መጣ ። ጸጥ ብላ በቶመችበት ሆና ጠበቃችው ።

ከቁልፎቹ መሃል የመኪናዋን ቁልፍ ብቻ ለይቶ ጠለደ ። ምንም ሳይል የጋራጅ በሩን ከፍቶ ወጥቶ ሲሄድ በመስኮት ቀማ ስታየው ቆየች ። መኪናው ከአይና ሲሰወር ፣ ትልቁ ሶፋ ላይ ራሺን መረመረችና ስትስት ብላ አለቀሰች ። ካሳይዳት በላይ መልሶ አላዘናት ። እንደገና ደግሞ ይበልጥ አናደዳት ። "የራሱ ጉዳይ ነው ... ሞጋው ነው ..." ብላ ፣ ሶፋውን እጇን እሰኪያዝማት በዙሪ ነረቱችው ። ደግሞ ደግሞ መንዘላዘሉን አላቆም አላት ። ምንም ቀጠሮ ሰላልነበራት አሳው እንደ ተጋሪመች ለረጅም ሰአት ሳራው ላይ አፍጥጣ ቆየች ።

እሰ ደግሞ ልክ ከጋራጁ በር ሲወጣ ጅምሮ እምባውን መቆጣጠር አቅቶት ሲያለቅስ ... ሲሥሀ ... መሪውን በቡጢ ሲመታ ... በንዴል ሲተነፍስ ... በደመ ነፍሱ ወደ አንዱ ቅሌት አውራ ንፀና ገብቶ ሸመጠጠ ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሳን አንቶኒዮ የሚባል ከኦስቲን አንድ ሰአት ተኩል ርቀት ላይ ያለ ከተማ ሲገባ ነበር ወደ ልቡ የተመለሰው ። በአካባቢው ከገኘው ዋልግሪን ሱቅ ገብቶ የጉንፋንና የአንቅልፍ መድሃኒት ገዝቶ መጣ ። ከዛም አሳው አካባቢ መጀመሪያ ያገኘው ሆቴል ገብቶ አልጋ ያዘ ። ከፍሉ እንደ ገባ ከሁለቱም ጠርሙሶች ሙሰዋ ሳያቀዋር አጄ ላይ የተዘረገፉትን ኒኒኖች ቃመና ከነልብሱ አልጋ ሙሰዋ ገብቶ ተዘረጋ ። እፍታም ሳይቀይ ነበር እንቅልፍ የወሰደው ።

ንጹህ እንዳይ ስትነሳበዋ ነው ሴሰቱ የነጋላት ። ጠዋት ላይ ቀደም ብላ መጥታ ከጠበቃዋ ጋር አንዳንድ ነገሮችን ተነጋገረች ። እስከ አምስት ሰአት ስልኩን ብትጠብቅም አልደወለም ። ደጋግማ ብትሞክርም ስልኩ አይነሳም ። ምናልባት ደክሞት እንቅልፍ ዋስት ይሆናል ብላ በማሰብ እስከ አኩለ ቀን ድረስ ጠበቀችው ። አንዳንድ ነገሮችን እያደረገች ስልኳ በራሺ ቁጥር እሱ አለመሆኑን ሲታይ ሰጋች ናረ ። አደጋ ደርሶበት ይሆን ብላ አሰበች ። ደግሞ ሪሱን የሆነ ነገር አድርገ ቢሆንስ ብላ ውስጢን ፍርሃት ፍርሃት አለው ። በመሳሳ ደቂቃ ውስጥ ካልደወለ ለፖሊስ ለማመልከት ስታስብ ትንሽ ቀዩቶ ደመለ ።

ስልኩን ወዲያው አንስታ ፣ "በሰላም ነው ..." አለች ፣ ባለችበት ድርቅ ብላ ።

ጉንፋን የዘጋው ግና ከእንቅልፍ የነቃው ድምጹን እየሰራረገ "በጣም ይቅርታ ... ግታ ሞንትላቱ ቭ ከነል አልነበረም ... ከቢት ወጥቼ ወዴት አንደሄዉም ሳላውቅ ራሴን ሳን አንቶኒዮ ገብቼ አገኘሁት . . ጉንፋትም በእንቅልፋ ላይ ተደራርቦ ..." ብሎ ፣ ያዋረጠውን ሳል ሲሠሩ ...

@OLDBOOKSAMPLE ስለነበር ስንት እንደሆን ትገ

አያለኝም ናይኩዊል መስጂ ... ገና መንታቲ ነው ...ይትርታ ...ኡፍፍ ... ዚቻልኩት ቱነት እመጣለሁ ..." ብሎ ፣ እንደገና በተከታታይ አላለው ።

"አይ ... እንኳን ደህና ሆንክ ... ገዴለም ... እረፍና ሲሻልህ ይደርሳል ..." ውስቢ ከቂንቶት እርይ ቢልም ልባ እንደገና በንዴት ተሞላ ።

"እሺ ... በታ አውንም ራስ ምታቱና ... ኡፍ ... መደ በኋላ ልደውልልሽ"

"ብቻልከው ጊዜ ... ካልቻልከም ነገ ..." ብላ ስልኩን ዘጉት ። ጸጸቱና ለምን እቤት ና አላልኩትም የሚለው ሃሳብ ናላዋን አዞረው ። ምን ያህል እንዳሳዘናትና ልባ እንዴ ተሸበረ ስታይ ሰርሱ ያላት ያልሞተ ፍትር ከንዴቷና ቁጣዋ ሰር ተደብቆ እያደባ እንዳለ ተረዳች ። ስታስብባቸው የከረሙችውን ነገሮች ደጋግማ ለራሷ ነገረች ። ሊያላምናት የፈለገውን ምክንያትና ዘዴ ይዞ ቢመጣም ፣ የፍቺ እትዷን መተየር እንደሌለባት ጥርሷን ነክሳ መሰነች ።

የራስ ምታቱን መድሃኒት ውጦ ተመልሶ ለመተኛት ቢሞክርም አልቻለም ። በየቂት መራቶች ሙስዋ ነገሮች ምን ያህል እንደተለጠፉና ከቁጥጥር ውጪ እንደሆኑ አሰበ ። ምን ማድረግ እንዳለበት ግን ማወቅ አልቻለም ። በገጹሌ ቦታ ራሱን አደርገ ሲያስብ አንዳንድ ነገሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ገልጽ ይሆኑለት ጀመረ ። አላስችል ብሎት ልጅቱ ጋ ሲደወል ስልኩን ካነሳ በኋላ ተመው ። በተቻለው መጠን ንትርክ ሙስዋ ላለመግባት ጠነ ። ያስግግሙም አደስግግሙም ... የምትፈገውን ሁሉ እሺ ብሎ ሊያደረግ ቀረጠ ። ካንድ ሰአት በኋላ ተነስቶ ሙቅ ሻወር መስዶ መኖሪም ቡና ሲጠጣበት ቀሰል ብሎት ነቃ አለ ።

በመስኮቱ አንጻር ካለው መንበር ላይ ተቀምጦ ላፕ ቶፑን ከፍቶ ኢሚል ሲያይ ቀየ ። ቲከሯን ሲከፍተው የምግብ አሰራር ማቢያ ላይ ነበረ ። ሆዱ የሚበላ ጥየታ ይመስል መሥሀ ጀመረ ። ትዝ ሲለው ዚት ሲገባ ንጹሕ አትርባለት ከገረሳት ጉርሻ ሴላ ፣ ምንም ላያበላ ከሃያ አራት ሰአት በላይ ሆኖታል ። አናቱ ጋ ደውሎ በሰላም መግባቱንና ሁሉም ደህና መሆናቸውን ነገራቸው ። ብዙም የረባ ኢሚይል አልነበረውም ። በሰላም መግባቱን ሰዙሉም አንድ የጋራ ኢሚይል አደረገላቸው ። ኮምፒዩተሩን አጠፋፋና ትመለስ አሊጋው ላይ በጀርባው ጋደም ብሎ ማሰብ ጀመረ ።

በኢንተርኔት አሰትን የሚዮይበትን ሆቴል ያዘ ። ራሱን የመገተት ያህል ፍንጭቶ ተነሳ ። ትንሽ ቸቱ ብሎ ቆየ ። እታውን ቦርሳው ውስዋ ጨማምሮ ሂሳቡን ዘግቶ ወጣ ። ምግብ ናሊጋ መደ ዝተማው መሃል እግሩ እንደመራው አየነዳ ሄደ ። አንድ ትልት ሚዘሲካን ቤት ጋ ሲደርስ አቁሞ ገባ ። ውስው ደማቅና በብዙ ተሰተናጋጅች ኖልቶ ሚሞታው ጮፈል ። የዶሮ ካሳዲያ እገዘ አስኪመጣለት ድረስ ትኩስ ሻይ አገጪያመጡለት ነገራቸው ። ለማቀያ የመጣለትን ናቾ የሚሉትን የሚዘሲካን ድርቀሽ በሚያታኮል ማጣቀሻቸው አጠጀመ ።

አስቲን ንብዮ ዘፍሉን ከያዘ በኋላ አልጋው ላይ ጋደም አለ ። ንጹሀ ጋ አንድ ሁለቱ ቢየዉልም አላነሳችም ። ከፉ ቆይታ ይዳለ ቢመስልት ፎጠራ ለማዩ ላይ እንጻፈጠጠ

@OLDBOOKSPDF

እንቅልፉ ወሰድ መጣ እያደረገው ቀየ ። ትንሽ ቀይታ ስትደውል በትግል ነቃ ። "ይቅርታ ስልኬን መኪና ውስጥ ትቼው እኮ ... ተሻለህ?" ስትለው ፣ የሚያውታት ንጹሕ ድምጽ መሰለው ።

"ደህና ... በጣም ተሽሎኛል ... ይቅርታ ስለ ጠዋቱ ..." አለና ዝም አለ ። ምን ማለት እንዳለበት ርግጠኛ አልሆነም ።

"ኧረ ... ችግር የለም ... ምግብ ነገር አገኘህ?" አለች ። መጨነቋ ድምጿ ላይ ያስታውታል ።

"ቀማምሻለሁ ... አሁን እኮ ኦስቲን ገብቼ ... አልጋ ጸውን ታውን ዊስቲን ይገር ... ማታ መገናኘት ከቻልሽ ብዬ ነው ። ካልቻልሽም ነገም ቢሆን ይደርሳል ። " ዊስቲን ሆቴል የሚለው ልቧን በጠበጠው ። ወደዚህ ከተማ ለመኖር ገና እንደተጋቡ ሲመጡ ፣ ለሁለት ሳምንት ያረፉበት ቦታ ነው ። በያመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ ወጥተው እዛ የማደር ልማድ ነበራቸው ። እዛ ለማረፍ በመምረጡ ድብልትልት ስሜት ተፈጠረባት ። ቁጣዋ እየተነነ ሲመጣ ታውቂት ራሺን ፈራችው ።

"ከቤት ተባረርኩ ብለህ ዘመድ ቤት መነብለልህ ነው?" ስትል ሳቅ ብሎ ፣

"ኧረ እኔ እንደሱም አላሰብኩትም ... ዝም ብዬ በደመ ነፍስ ነው እግሬ መርቶኝ ..." ብሎ ሳይጨርስ ፣

"እንተ እንደምትለው ... ሳያውቁ የሚያደርጉት ... አውቆ ካደረጉት ይልቅ ያሳብታል ..." ብላ ስትስት ፣ አብሯት ሳቀና ትንሽ ዝምታ ሰፈነ ። ለምን ወደ ቤት እትመጣም ልትለው ካፏ ሊያመልጣት ሲል ያዘችው ። "አሁን ስንት ሰአት ነው? እ...ም ላንድ ሩብ ጉዳይ ... አንድ ተኩል ላማድሊን ... እንገናኝ?" ካለችው በኋላ እሺም ሳምንታዊ ቁርስ መብያቸው ቤት ለመገናኘት እንደተጠረችው አስተዋለች ። "ሌላ ቦታ ... ለማውራት ጸጥ ያለ ... መገናኘትም እንችላለን ..." አለች ፣ እያመነታች ።

ቀድሞ ደርሶ ሲጠብታት ስለነበር ስትደርስ ላመል ያህል ተታትፈው ሰላም ተባባሉና ተፋጠው ተቀመጡ ። ቀስ ቀስ እያለ የጋለ ወሬያቸው እንዴ ወደ ኮፈ ክርክር ተለወጠ ። ረገብ ብለው ለመወያየት ሲሞክሩ ቀዩና ፣

"ሌላ ይሄ ኮ ነው ... የፈለገ ያህል ብንወያይ የሚፈጠር ለውጥ የለም ። እኔ ጠበቃ አናግሬ ጨርሻለሁ ... ብቸኛው መፍትሄ ፍቺ ነው ። አንተም በነጻነት የፈለክውን ነገር ከቢጤህ ጋር ... እኔም ሳይመሽብኝ ቢጤዬን ፈልጌ ህልሜን መኖር መብቴ መሰለኝ ..." ብላ ፣ የያዘችውን ሹካ አስቀመጠች ።

"ፍቺ ላይ የሚያደርስ ነገር ላይ ደረስን?" አለ ፣ የጠበቀው ነገር ቢሆንም ትንሽ ተለሳልሳ ስለነበር ፣ የተሻለ አማራጭ ይገኝ ይሆን የሚለው ተስፋው እየጨለመ ።

"ቀየ ኮ ሌላ ... አንተ ኢትዮጵያ ነው መኖር የምትፈልገው ... እኔ ደግሞ በፍጹም አልፈልግም ። አንተ የምትፈጽመው ያባትህ አደራና የምትፈልጋት የልጅነት ጓደኛህ ያለችው እዛ ነው ። አንተ ለማመን ባትፈልግም ... ልብህ ግን ከኔ ከራቀ ቀይቷል ...

@OLDBOOOKSPDF

በታ ... ይሄንን ትዳር ትለዋለህ?" ስትል ሌላ ዙር ክርክር ውስጥ ላለመግባት ብሎ ዝም አለ። "እኔም የራሴን ... ፍላጎት መከተል አለብኝ ... ሁልጊዜም ግልጽና እውነተኛ ሃሳቡ ላንተ። ልደብቅህ አልችልም ... አሁን ልወደው የምችልና የጋራ የሕይወት አላማ ሊኖረን የሚችል ሌላ ሰው አግኝቼያለሁ ..." ስትል ፣ ሳያስበው ፊቱን በጥፊ እንዳሮሉት ሰው ደንግጦ ዝም አለ ።

"የምርሽን ነው?"

"ለምን እዋሽሃለሁ ... ከዚህ በኋላ ምንም ድብብቆሽ የለም ... እንተ መናገር ከለፈልግህ መብትህ ነው"

"ምኑን ነው የምነግርሽ?" ሲል ፣ ከት ብላ ሳቀች ።

"ሌላ ... የማታምንበትን ነገር አታድርግ ... አምነህ ያደረከውን ነገር አትደብቅ ። ተሳስተህ ካደረከው ደግሞ መፍትሄው ኑዛዜ እንጂ ድብብቆሽ አይደለም" አለችና በጽኑታ ዓይኑ ውስጥ አተኩራ አየችው ።

"እሺ ... ምንም ብል ምንም ባደርግ ሃሳብሽን የማስለውጥሽ አልመሰለኝም ። ስለዚህ ምን ማድረግ ነው የሚሻለው?" አለ ፣ ቅዝቅዝ ባላ ድምጽ ።

"አጭር ነው ... ፍቺ ..."

"ንጹሕ ... ፍቺ ኮ አንቺ እንደምትዪው አጭርም ቀላልም አይደለም ... ትንሽ ግልብ አያስፈልግም?"

"ውይ ሌላ ታሰበ ኮ ... ያንተን አላውቅም እኔ በጣም ብዙ ሌሊት በእንባ እየታጠብኩ ... ብዙ ማታ በብቸኝነት ጨለማ ውስጥ ሆኜ ... አስብኩ ። ከዚህ በኋላ የማልፈልገው አንድ ነገር ማሰብ ነው ። "

"ጥሩ ... ይሁን ... ግን እንዴት ነው ማድረግ ያለብሽው ... ጠበቃ አናግራያለሁ ስላልሽ?" አለ ፣ ወደኋላ ደገፍ ብሎ ።

"ትልቁ ጉዳይ የልጆቹ ነው ... የማሳደግ መብቱ አንተ ወደ እዚህ ለመኖር እስክልመጣህ ድረስ ሙሉ ለሙሉ የኔ ይሆናል ። በማንኛውም ጊዜ መደወልና በመጣህ ጊዜ ልታያቸው ትችላለህ ። ክረምት ላይ እነሱ እስከፈለጉ ድረስ ኢትዮጵያ ከሆነ የምትኖረው አንተ ጋ መሆን ይችላሉ ። ከዛ ውጪ ንብረት ምናምን መነጋገር እንችላለን ... እሱ ችግሬ አይደለም"

"እሺ ... የመጨረሻ ውሳኔሽ ከሆነ አንቺ ባልሽው እሄዳለሁ ። ግን የመጨረሻ ከር ... አሁን በዚህ ጥድፊያ ከሚሆን ... መለያየቱን እንለያይ ... ያን ከሆነ የምትፈልጊው ። ግን ነገሩን ከቤተሰብ ጋር እንምከርበት ... በደንብ እናስብበት ። ላላውቅ ምን ያህል እንደ ገዳሁሽ አሁን ነው የገባኝ ። በጣም ይቅርታ ... ይቅርታ በማለት የሚለወጥ እንዳልሆነ አውቃለሁ ። ውሳኔሽ ላይ እንድትደርሺ ያደረገሽ ነገር ሌላሠው ከሌላ ሴት ጋር መውጣት ብቻ ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ ስህተት ነው ።

@OLDBOOKSPDF

እንኳን ላደርገው ሀሳቡም የለኝም ። ግን ቢታ ትንሽ ረጋ ማለቱ ማንንም አያገዛም ሲል የሆነ ልሂ ወሰኖ ያስ ድምፅ እውነቱን ነው ያላት መሰላት ። ዝም አለች ።

በእግሯ መራቱን እየቀረቀረች ቀየችና ሲራክ የላከላት ፎቶዎች ፣ በራሱ በሌላው እጅ ጽሁፍ ስለ ምስጢር የተጻፈው ጽሁፍና ሌሎቹ ነገሮችንስ ብላ አሰበች ። ድንገት ይሄ ሁሉ ወሸት ከሆነስ? ሲራክ የነገረኝን ነገሮችና የላከልኝን ፎቶዎች ላሳየው አላሳየው ብላ ታገለች ። ምንም የሚለወጥ ነገር ላይኖር ምን ይጠቅማል ፣ ብላ መልሳ ተወችው ። ስታየው እንዴ የሚያወራው ሁሉ እውነት ደግሞ ቀየት ብሎ ሞላሜ ወሸታም እየመሰላት መወሰን ተቸገረች ። ከሌላ ዙር ሞትሞትና የጋለ ውይይት በኋላ ፣ በብዙ ትግል የፍቺ ሂደቱን ለማዘግየት ተስማሙ ።

በሚግስቱ እሱ ልጆቹ ጋ ወደ ሚኒሶታ በረረ ። ከንዋይና እሀቷ አርሴማ ጋር ብዙ ተመያዩበት ። ነገሩ ሊፈታም ሆነ ሊያግባቧቸው የሚይችል ሲሆንባቸው ባለበት ተውት ። ሁሉም በንጹሕ በኩል ሆነው የወገኑ ስለመሰለው ወሰኑ ተከፋ ። ከሁሉም ነገር ራት ማለት ስለፈለገ ልጆቹን ይዞ ለሞቂት ጊዜ ወደ ሳንዲያጎ እህቱ ጋ ሊቆይ ወሰነ ። መሄጂያው እስኪደርስ እላ መቆየቱ ለሁሉም የተሻለ ነው ብላ ስላሰበች ንጹሕሀም ሃሳቡን አልተቃወመችውም ። የልጆቹን መንገላታትና ጸባያቸው በፍጥነት ምን ያህል እንደተለወጠ ሲያይ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያሰው ፍላጎት እንደተነፈሰ ፊኛ ሚሸሽበት ።

·የሌላ ሰው ልጅ አተርፋለሁ ብዬ የራሴ ልጆች ሌላ ሰው ሆነው ጠበቁኝ ። የሌላ ሰው ትዳር አስተካክላለሁ ብዬ የኔ ትዳር ራሱ በሌላ ሰው ላይ የምጠላው አይነት ትዳር ሆኖ ቀየኝ ። ሌላ ሰው አዘግለሁ ብዬ ሄጄ እኔ ራሴ ሐኪም የሚያስፈልገኝ ሕመምተኛ ልሆን ነው ። በሌላ ሰው የማላብበው ችግር የለም ... ስለዚህ ከሌላ ሰው የምጠብቀው መፍትሔም አይኖርም ። ብዙ ለውጥ ማድረግ ይኖርብኛል ። እኔ እምቢ ብል እንኳን ለውጥ ራሱ እንደ ባህር ማዕበል ኑሮዬን ሊገለባብጥ ከቤቱ ገብቶ እያስገመገመ ነው ። የምችለውን አድርጌ የተረፈው ቢተርፍ የጠፋውም ቢጠፋ ጸጸቱ ብዙ አይሆንም ። ጊዜው የይሉኝታና የገምታ ሳይሆን የፍልሚያና የኮድፊያ ነው· በመወሰንና በማድረግ መካከል ድልድይ የሌለው ገደል አለ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 39 ፡

ሲራክ ስሞኑን ከሥራ ሰዓቱ ውጪ ከሳቤላ ጋር ሆኗል ውሎ አዳሩ ። ጎሊና ይጋግማብትደውልለትም ችላ ብሏታል ። እንዲያውም እንዴት አድርጎ ለመጨረሻ ጊዜ ከሕይወቱ እንደሚያስወጣት መላ እየፈለገ ነው ። ከሳቤላ ጋር ለማምሸት ተቀጣጥረው ስለነበር ወደዚያው ለመሄድ ካልጋው ላይ ተነስቶ እያንገራገረ ለባበሰ ። ብቻውን የሚጨነቀውን ቲቪ አጥፍቶ ጎሊና ያመጣችለት ቀሎ እየቀረጣጠመ፣ የነገሮችን አካሄድና የስሞኑን ትላልቅ ዕቅዶቹን በጥንቃቄ አውጠነጠነ ።

'የራሱ ጉዳይ ... እኔ ሲራክ ምን አገባኝ ...ሚስጥር ከተንበረከከች ሌላው እንደ ፍጥርጥሩ ... ሳቤላሞንም እንደምትሆን ማድረግ አያስቸግረኝም ። እምዬ አሜሪካ ትገላገለኛለች ... እሷን እዛ አድርሶ ላንዱ ዕድለኛ ማስረከብ አይከብድም ። ከዚያ ግሪን ካርዷን ቀቤክስ ካደረኩ በኋላ፣ ለመጨረሻው ሚሽን ተመልሶ ከች ማለት ይቻላል' አለና ለራሱ ፈገግ አለ ። አንገቱን በኮሌታው ሸፍኖ፣ ኮሌታውን እያስተካከለ ነጠር ነጠር እያለ ወጣ ።

ማታ ወደ አራት ሰአት ተኩል ላይ ቤት ሲገቡ ከመሰጥ በኩል በራፉ ላይ የወደቀ ፖስታ አይቶ ሲያነሳው ከጎሊና ነበር ። ሳቤላ ወደ መታጠቢያ ቤት ለመግባት እየተጣደፈች ስለነበር፣ ልብም አላለችውም ። በሩን ዘጋና ፖስታውን ቀድዶ የጻፈችውን እያነበበ ወደ ኩሽና ገባ ።

"ሲሩ ... ምነው እንደዚህ ዘጋኸኝ ... ያጠፋሁት ነገር አለ እንዴ? የቤቱን ቁልፍ እንደ ቀየርከው እንኳን ለምን አልነገርከኝም? ያን ያህል ከሰጠላሁህና ከኔ መራቅ ከፈለግህ እኮ በግልጽ ልትነግረኝ ትችላለህ ። ለማንኛውም ነገ ጠዋት ወደ ሥራ ከመግባቴ በፊት አንድ ሰአት ላይ ብቅ ብዬ ላገኝህ እምክራለሁ ። በጣም ነው የናፈቅከኝ ... ብዙ ጊዜ ላምኩህ"

ማስታወሻውን እንብቦ ሲጨርስ የሆነ ሃሳብ ብልጭ አለለትና ስልኩን አውጥቶ፣ "ሂሉዬ ... በጣም@KOLFBOOKS.COM ምሄድበት ቦታ ስላለ በጠዋት

መውጣቴ አይቀርም ..." ብሎ ነይም አትምጪም ሳይል የፅሑፍ መልእክት ላከላት። እንደምትመጣ እርግጠኛ ነበር። ሳቤላ ልብሷን ቀያይራ ወደ ሳሎኑ መጣች።

"የምን ፖስታ ነው ... የቤት ኪራይ ማስጠንቀቂያ ነው እንዴ?" ብላ ሳቀች። የቲቪውን ጣቢያ እየቀያየረች ሶፋው ላይ ጋደም አለች ። ያላየችው መሰሎት ነበር።

"ዝም ብሎ ኮተት ነው ባክሽ ... እኔ የምልሽ አሜሪካ ሲንሄድ ... ምን ማድረግ ነው የምትፈልጊው?" አለ፣ አፉ ላይ እንዳመጣለት።

"ዲዛይነር ስኩል ... የዓለም ምርጥ ዲዛይነር እንደምሆን እርግጠኛ ነኝ" አለችው ፊቷ በርቶ።

"እምንሻለሁ ... ደግሞም እተማመንብሻለሁ ... አሪፍ ቲስት አለሽ ..." አለ፣ ሳቅ ብሎ።

"አንተ እዛም ሄደህ የአብድ ሃኪም መሆን ነው የምትፈልገው ወይስ?" አለች፣ ተነስታ ሻይ ለመጣድ ወደ ኋላ እየገባች። ሃያ አራት ሰአት ሻይ ብትጠጣ አይሰለቻትም።

"እኔ እንጃ ... ሕክምናውን ብተወውም ደስ ይለኛል ... ግን እስኪ ኑሮ እንደፈቀደ ይሆናል ..."

"እግዜር እንደፈቀደ ነው የሚባለው" አለች ኮስተር ብላ።

"የኔ እግዜርና ጊታዬ ... ኑሮዬ ነው ..." አለ፣ በሹፈት ድምጽ።

"ተፈላሰፍ ... ምን ሆነሃል ደግሞ ... ደህና አልነበርክም እንዴ ... የሆነ ውስዋስ ውስጥ የገባህ ትመስላለህ?"

"የክሊኒኩ ነገር እየደበረኝ ነው ባክሽ ... ሰውዬውም የለም ... ቤቱ ራሱ እያስጠላኝ ነው" አለና አጠገቧ ሄዶ ተቀመጠ።

ራሱን እያሻሸችው፣ "ከደበረህ ተወዋ ... ሌላ ቦታ መስራት አትችልም እንዴ? ማለቴ ለነፍስህ አይደል ... ደግሞ ግፋ ቢል እኮ ጥቂት ወራት ነው። ከዚያ አዲዮስ ነው።"

"እስኪ ... ቀይ ትንሽ ...የረጋ ወተት ይሉ የለ ሰምቼ ... ድክም ብሎኛል ... ብንተኛስ?" አለ፣ ብድግ ብሎ እየተንጠራራ። ነገ ከማስረሻ ጋር ስለሚኖረው ቀጠሮና ጠዋት ጎሊና ስትመጣ ምን ማድረግ እንዳለበት በማሰብ ተጠምዷል። አልጋ ውስጥ ገብተው ብዙም ሳይቆዩ፣ እያወራችለት እንቅልፍ እንደያዘው ሆኖ ማንኮራፋት ጀመረ። እውነትም ደክሞታል ብላ የጀመረችውን መጽሐፍ ትንሽ አንብባ መብራቱን አጠፋፍታ ተኛች። እንቅልፍ ባይኑም ሳይዞር፣ እስከ ዘጠኝ ሰአት አካባቢ ድረስ ሲያውጠነጥን ቀየ። ያሰበውን ነገር ግብ ካላደረሰ ውስጡ አያርፍም።

ጠዋት ላይ በሩ ሲንኳኳ ሳቤላ ነቅታ ቀሰቀሰችውና፣ "ኧረ በሩ ይንኳኳል ... ማነው በዚህ ጠዋት?"

@OLDBOOOKSPDF

ከእንቅልፉ በከፊል እንደነቃ ሆኖ፣ "ጽዳት ሠራተኛዋ ይሆናሉ ... አንዳንዴ አለባቸው የሆነ ነገር በጠዋት የሚያንቀገርቅሽ ... በናትሽ ቀየት ብለው ኑ በያቸው" ብሎ፣ ተገላብጦ ትራሱን ጭንቅላቱ ላይ አድርጎ ተኛ። በስስ ፒጃማዋ ላይ ፎጣ ነገር ጣል አድርጋ በባዶ እግሯ ቀንጠር ቀንጠር እያለች ሄዳ፣ በሩን ስትከፍት እንዲት ወጣት ከነላጲ በሩ ላይ ቆማለች።

ደንገጥ ብላ አይኗን እያጨናበሰች፣ "አቤት ..." አለቻት።

ግራ መጋባትና ድንጋጤ በተቀላቀለበት ፊት፣ "ሲራክ የለም እንዴ?" አለችና ወደ ውስጥ ለማየት ሞከረች።

"ተኝቷል ... መልእክት አለሽ?"

ብልጭ አለባትና የያዘችውን እቃ አሽተንጥራ ገፈታትራት ወደ ውስጥ ተንደርድራ ገባች። ጎሊና ማለት እሷ ልትሆን እንደምትችል ገምታ ከው ብላ ቀረች። ከፈስታሉ ውስጥ የተበታተነውን ቲርሙዝና በሰሃን የታሰረ ቱርስ ስታይ የመጀመሪያ ቀን ከሲራክ ጋር የበሉት ፍትፍት ትዝ አላት። የምታደርገው ጠፍቷት ላሉን ሄዳ ቁጭ አለች። ወዲያው ልጅቷና ራቁቱን በቱምጣ ያለው ሲራክ ተከታትለው እየተዉዋዩ ወጡ።

"ስማ አንተ ሲራክ ሳትሆን ጭራቅ ነህ ... ሲያዩህ ሰው ትመስላለህ ... ጨካኝ ጥራቅነህ። አንተን ነበር አማኑኤል አስገብቶ መርፈ መጠትጠቅ ...በኔ እንደተጫወትክ የምትቀር መስሎሃል ..."

"ቀይ አስኪ ሂሉ ..." ብሎ፣ እጇን ሲይዛት መነጨቀችው።

"እዛ ሂሉህን ፈልግ ... ላንተ ሄለ ነው የሚገባህ ... ያቻት ሶፋህ ላይ ... ሄደህ ከሷ ጋር ተጓተት ...ሁለተኛ ..." በግልምጫ ሳቢላን ከመሬት ደባልቃት የተበታተነውን እቃ ተራምዳ እየተወናጨፈች ወጣች። በሩን ዘጋና ከሶፋው ጫፍ ላይ ጸጥ ብሎ እንገቱን አቀርቅሮ ተቀመጠ። ከትንሽ ጸጥታ በኋላ፣ "ሶሪ ... አይ አም ሶሪ ..." አለ።

"እንደምትመጣ ታውቅ ነበር አይደል? ... አስበህ የሰራሃት የራስህ የጅ ስራ ናት" አለችው፣ አይኗ እሳት እየተፋ።

"በሌላ መንገድ ልትተወኝ አትችልም ... ያለኝ አማራጭ ይሄ ብቻ ነው" ብሎ፣ ወደ ጓዳ ሲገባ ተከተለችው።

"በጣም ጨካኝ ነህ ... ሲራክ ሙት እኔም ጭራት ነገር መሰልከኝ አሁንስ። እንዴት እንደዚህ ታደርጋለህ። እታሳዝንህም ... ምስኪን ... ላንተ ቱርስ ሰርታ በዚህ በጠዋት ስትመጣ ... ምንም ርህራሄ የለህም። የኔ ነው ጥፋቱ" ብላ፣ ልብሷን መተያየር ጀመረች።

"ቢታ ድራማው ሰለቸኝ ... ከዚህ ውጪ ተስፋ ቮርጣ ልትተወኝ የምትችልበት መንገድ አልታየኝም። ደግሞ ሳራየስ የሆነ ነገር ነሰብን ... ሌላው ከተት መወገድ አለበት። መንገዱ አይደለም ዋናው ነገር ... የምትፈልጊውን አላማ

@GEDBOOKSPDF

ከስፈጸመ መጨከን አለብሽ። እንዳንዴ ደግነትና የምትፈልጊው ውጤት አብረው አይኖሩም። ሶሪ ..." ሲላት ፣

"ምኑን ነው ለኔ ብለህ ያደረከው አንተ?" አለች ፣ ባለችበት ቀጣ።

"እየው ሳቢ ... ያቺኛዋ በጥሬ አጨላኝ የሄደችው ባንቺ ምክንያት እንደሆነ ታውቂያለሽ። ጎሊና መምጣቷን ሳውቅ ዝም ያልኳት ... በታ ይለይላትና ትተወኝ ብዬ ነው። ለርሷም ቢሆን ዝም ብዬ ብተዋት ፣ እየነፈረቀች አብረን እንድንቀይ የማታደርገው ነገር አይኖርም። አሁን ግን በቃ... አለቀ። እኔ ሲኦል የሚገባኝ ... ባለጊ ጭራቅ ... ከሴት ጋር እጅ ከፍንጅ የተያዝኩ አታላይ ነኝ። ይሄ እሷን ተበዳይና ጻድቅ ሆና እንዲሰማት ስለሚያደርግ ፈውሷን ያፈጥንላታል። እግዜር ከጭራቅ መንጭቀ አወጣኝ ብላ ስታመሰግን ትኖራለች። ገባሽ ... ለራሴ ብቻ ሳይሆን ለሷም ከዚህ የተሻለ መንገድ ሊኖር አይችልም።" ትኩር ብላ ስታየው ቀይታ ፣ ዝም ብላ ወደ መኝታ ቤት ገባች። ልብሷን ቀያይራ ፣ ለራሷ የሆነ ነገር እያጉተመተመች ምንም ሳትለው በሩን ዘግታ ወጣች።

'አንቺም ያው ነሽ ... ደርሶ አሳኝ መላይ እንጓች ... አዲዮስ ... ባሻጅ ራስ ሁሉ" ብሎ ፣ አልጋው ላይ ተወርውሮ በጀርባው ተዘረረና የሆነውን ነገር ሁሉ እንዴ ገና ባይን ህሊናው ለማየት ሞከረ። በትክክል እንዳተደው ስለሆነ ምራቁን ዋጠ። የማታ ተጠርሙን ሲያስብ ባዲስ ኃይል ተሞላና ካልጋው ላይ ተስፈንጥሮ ተነሳ። ሳቤላ ጋ ደጋግም ቢደውልላትም ጠዋት ከተለያዩ በኋላ ሙሉ ቀን ስልኩን አልመለሰችለትም።

ከጠዋት ጀምሮ ከዘሊኒክ ሳይመጣ ብዙ ህመምተኞችን ሲያይ ዋለ። ውስጡ በድልና በነጻነት ስሜት ተሞልቶ ፣ ምሳውን ከምስጢርና ከሳንቾ ጋር እየተቃለደ አዘው ካፈ በላ። የጸባዩ መለወጥና ከሁሉም ሰው ጋር መግባባቱ ግራ ቢገባቸውም ፣ የዘሊኒክ ሠራተኞቹ ሁሉ በመልካም ነው ያዩለት። ሲራክ ተለወጠ ተባለለት። ሰው ሁሉ ከወጣ በኋላ ወደ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ፣ ማስረሻን ለአራት ወደ ተጠረበት መካኒሳ አርከባሲኖ በታጥቃ ሸመጠጠ።

ጸጥታውንና ብዙ የሚያውቁት ሰዎች የማያዘወትሩት ቦታ ስለሆነ ነው የመረጠው። መኪናውን አቁሞ ደረጃውን ወጥቶ ወደ ቀኝ ዞር ሲል ማስረሻን ጥቁር ዮብና መነጽር አድርጎ ከወዳጥ ተቀምጦ አየው። ሰላም ተባብለው ትንሽ የባጥ የቆጡን ሲያወሩ ቀዩ። የሚበሉትን አዘው ፣ እንደ ተለመደው የማስረሻን ብሶትና የሩትር እንጉርጉሮ ታግሶ ሲያዳምጥ ዋየ። በውጪ ተገናኝተው ሲያወሩ ይሄ ሦስተኛቸው ነው።

"ቀይ እኔ የምለው ያ ድሩንድሩ ታክሲ ነጂ ምኗ ነው? አውነማ ነ ቤተኛ ሆኗል" አለ ፣ በጋለ ስሜት።

"እኔም ብዙ አይገባኝም ... ልጁ ትንሽ ጥጋበኛ ነገር ይመስላል። የዕን ባላውቅም እሱ ግን ከሰሯ አይጠፋም። ወንድ ልጅ ከቀንጅ ስር ስር ካለ ምን ፈለገ ይመስልሃል?" ሲለው ፣ የበለጠ ሰሜቱ ጋለ።

@OLDBOOOKSPDF

"በሚገባው ቋንቋ ልነግረው ሞክሬ ነበር። ይሂንን ያበጠ ጡንቻውን እንዴ ጉማ ጣስተንፈስ ብቻ ነው ያለኝ አማራጭ።" በቀረበላቸው የመቀያ ዳቦ አጥቢውን ዝቅ ሊጮርሰው እይኑን ጨፈን አደረገ።

"ትንሽ መታገስ ጥሩ ነው። ቀይ ግን የሲ ምርጫ እሱ ቢሆንስ ምን ታደርጋለህ?" ከመቀመጫው ብድግ ብሎ፣ "ከመኖርና ከመሞት ምርጫ አሰጠዋለኋ..." ሲል፣ እንዲቀመጥ በጹ ምልክት አሳየው።

"እሱን በሆነ መንገድ ዞር ማድረግ ካልተቻለ ... አሲን የማግኘቱ ነገር በጣም የሰለለ እድል ያለው ይመስለኛል። እሱ ደግሞ እንደዚህ ቀላል ልጅ አይደለም"

"እሱን ለኔ ተወው ዶክተር ... ያኛው ዶክተር መቼ ነው የሚመጣው ለመሆኑ? እሱ ደግሞ መፈላሰፍ ያበዛል። የሰው ስሜት አይገባውም ... ሁሉ ነገር ሳይንስ ይመስለዋል። ግን በቃ ከሱ ጋር እያወሩ መገናኘት ይጥመኛል ስንገሩ። ሳይንሱን ወልቶታል ... ችግሩ አርቱ ግን በደረሰበትም አልደረሰም። ቀይ ወደ አንተ ጋ መቀየር አልችልም?" ሲል ሲራክ ከት ብሎ ሲስቅ "ምነው ተሳሳትኩ እንዴ...?" ሲለው፣

"አረምን ትሳሳታለህ ... በልተ ኸዋል እንጂ ... እሱ አሜሪካንን እዚህ ለመፍጠር የሚጥር ሀልመኛ ነው። ያበሻ ወኔ ... ያበሻ ሃሞት ... አይገባውም። ግን ከርሱ ጋር መቀየትህ ጥሩ ነው። ከኔ ጋር እንደዚህ በመጪም መገናኘት እንችላለን። ግን ማንም ግቤት የለበትም። ላንተ ብዬ ነው ... ያው ሳይኮሎጂስት ነህ አንተም ... ይገባሃል። አቲከሱ አይፈቅድም ..." ሲል፣ ደስ ብሎት ሳያስበው ትከሻውን ነቀነቀው።

"በደንብ ገብቶኛል ... እና ታዲያ ምን ትመክረኛለህ? ትግስቱ ነ እያለቀ ነው" ሲለው፣ ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ ከንፈሮቹን አጣብቆ ወደ ላይና ወደ ግን እያሽከረከረ ሲያስብ ቀየና፣

"ሁለት ነገር ... ለርሲ ያለህን ፍቅር ያለመታከትና በማያሻማ ሁኔታ መግለጽ ... ደግሞም ወሳኙ ነገር እሱን ከመንገድህ ላይ ዞር ማድረግ። ዝርዝሩን ላንተ አተወዋለሁ። ቀላል ልጅ እንዳይመስልህ ግን ... እንደምታየው አይደለም። እሱም ሊያስወግድህ ይችላል። ግልጽ ነው?" አለው።

ቅናጠን ብሎ፣ "በደንብ ... በደንብ ገብቶኛል። የተረዳውን ለኔ ተወልኝ። እኔም ከዛሬበኋላ አንተንም ብዙ አላስቸግርህም ... ፈጣሪ ካለ ከድል በኋላ ነው የምንገናኘው። በጣም ካልቸገረኝ ወይም አዲስ ነገር ካልተፈጠረ ... በስልክ ከተገናኘን ይበቃኛል።"

"አረ ምንም ችግር የለም። አንተ ደህና ሁን እንጂ ... ደግሞ ሁሉ ነገር እኩ ቦርከርና በመድሃኒት አያድንም ... ወሳኔን የግድ የሚሉ ነገሮች አሉ" ሲለው መሳጭነቱን ጠበቅ አድርጎ በመጨበጥ ገለጸለት። ሂሳባቸውን ከፍለው ሲወጡ "ማሰረሻ ስልኩን አወጥቶ የእለቱን ንግግራቸውን ወሳኔ" በሚል ርእስ ከደሚ ፋይሉ ወስዋ አስገባው።

@OLDBOOOKSPDF

ከማሰሪያ ጋር ከተለያዩ በኋላ ከጓደኞቹ ጋር አምሽቶ ወደ ቤት ሲገባ ሰውነቱ ውልትልት ብሎ ነበር ። በማግስቱ አርብ ከሰአት በኋላ ጀምሮ ከወንድሙ ቤተሰቦች ጋር ትዳሜና እሁዱን ለማሳለፍ ወደ ሀዋሳ ለመሄድ እቅዶዋል ። ክሊኒክ አስክ ሰኞ ስለማይገባ ለጥ ብሎ አረፈደ ። ሳቢላም እንደዘጋችው ነው ። ይውጣላት ብሎ ዝም ብሏታል ። ስልኩ ደጋግሞ ሲደወል እንደ ምንም ተንጠራርቶ ሲያየው ሲስተር ዘቢባ ናት ።

ደግማ ለሦስተኛ ጊዜ ስትደውል እነሳውና "ይቅርታ ሲስተር ማታ በጣም አምሽቼ ነበር የገባሁት ... ሞልጥ ያለ እንቅልፍ ውስጥ ነበርኩ ..." አለ ፣ ሙሉ ለሙሉ ያልነቃ በሚመስል ድምፅ ።

"ዶክተር ሲራክ ጉድ ሆንልህ ... እንዲያው አሁን ምን ይባላል ..." ብላ በተረበሸ ድምጽ መናገር እትፈት ስታለቅስ የማሰረሻ ፊት ድቅን አለበት ። 'ይሄ በቱፒድ ሰውዬ ምን አድርገ ይሆን' አለ በልቡ ። "ምንድነው? ... ሰላም ነው?" አለ ፣ ድካሙና እንቅልፉ ባንዴ ጠፍቶ ።

"ልጆቹ ተላለቁ ... ያ እብድ ልጅ መጥቶ ...ሚስጥርን ካልመጣሽ ብሎ ሲመታት ሲገበገ ... ከሳንቾ ጋር ተናንቀው ... ሽጥጥ ይዘ ነበር ... አሁን ፖሊሶቹ ሁሉ እዚህ ናቸው ... የት ነህ አንተ ... ከቻልክ አሁኑኑ ና ..."

"መጣሁ ... መጣሁ ..." አለ ፣ በድንጋጤ ። ስልኩን ዘግቶት ያገኘውን ልብስ አጥልቆ ወደዚያው ከነፈ ። መልሶ መላልሶ ደወለ ። ማንም ስልክ ስላላነሳለት የልብ ምቱ ጨመረ ። የአደጋ መብራቱን አብርቶ የቻለውን ያህል ፈጠነ ። በመኪናዎች መሃል እየተሹለከለከ ቢነጻም መንገዱ አልገፋ አለው ። ምስጢር ጮዳና ላይ በደም ተንከራ ተዘርራ ታይታው አይናቹን ጨፈነ ። ደግሞ ሳንቾ ሞንትላቱ ተቦድሶ ወድቀ ምስጢር እሱ ላይ ወድቃ ስትሮህ በሞኘትላቱ ሳለ ። ፖሊስ ማስረሻን የፊጢኝ አስሮ ሊወስደው ሲጎትተው ወደርሱ እየጠቆመ 'እሱ ነው እሱ ነው' ሲል ታየውና ዘግየት ብሎ ለመሄድ አሰበ ።

ክሊኒኩ ጋ ሲደርስ ሰው ተሰብስቦ ሁለት የፖሊስ መኪኖችና አንድ አምቡላንስ ቆመው ደረሰ ። ምስጢርን ሲስተር ዘቢባ ትከሻ ላይ ተደግፋ ሲያያት ትንሽ እርይ አለ ። እያለቀሰች አንድ መርማሪ ፖሊስ ሊያዋራት ይሞክራል ። አምቡላንሱ እያባራ ካካባቢው ነጎር ተፈተለከ ። ሌላኛው የፖሊስ መኪና ላይ በሁለት ፖሊሶች መሃል ሳንቾ በካቴና ታስሮ ተቀምጧል ። ከመኪናው እንደወረደ ፣ ሳንቾን የያዘችው መኪናም ካካባቢው ተሰወረች ። ሲራክ አጠገቧ ሲደርስ ወደ ፖሊሱ እያየች ፣

"መቶ አለቃ እሱ ዶክተር ሲራክ ይባላል ። የክሊኒኩ ሚዲካል ዳይሬክተር ነው ። ባሬ ቢሮ አልነበረም ... አሁን ደውዬለት ነው የመጣው" ስትል ፣ ተጨባብጠው ሰላምታ ተለዋወጡ ።

ሰዉ ዙሪያቸውን ከባቢው ሞንትንት ብሎ ስለነበረ "መቶ አለቃ ... ወደ ውስጥ መደ ቢሮ እንግባ ወይስ ..." አለ ሲራክ ፣ የመኮንኑን ማፅደግ ሲስተር ዘቢባ ስትጠራ ስለ ሰማ ።

@OLDBOOOKSPDF

መኮንኑ ሲራክ ያለውን እንዳልሰማ ሆኖ ወዲ ሰዉ ሀረና፣ "በቃ ... ምንድነው ዕሬ ... ወዴ የትዳያችሁ ሂዱ" ብሎ፣ አጠገቡ ወደ ቀሙት ፖሊሶች ሲያይ ሰዉን ለመበተን በትራቸውን መዘዙ። ሰዉም እያጉረመረመ ቀስ በቀስ ተበተነ።

"ያው ከሁላችሁም ቃል መቀበል ስላለብን ... አሁን ወደ ጣቢያ ብንሄድ ሳይሻል አይቀርም ... እነርሱ ከኛ ጋር ይሄዳሉ ... ለምን አንተ አትከተለንም?" አለው መኮ አለቃው ቁምጭጭ ባለ ድምፅ ወደ ሲራክ ዞሮ።

"እነርሱ ክኔ ጋራም ሊመጡ ይችላሉ ... ችግር አለው?"

"አስራር ነው ... ቃል ከመስጠታቸው በፊት ... ከሌላ ሰው ጋር እንዲያወሩ አይፈቀድም ... በሱ እንሂድ"

ወደ ጣቢያ አመሩ። ፖሊስ ጣቢያ ደርሰው ብዙም ሳይቀዩ የምስጢር እናትና አክስት፣ አቶ ሲራጅና የማስረሻ ቤተሰቦች ተራ በተራ ደረሱ። ጣቢያው በውጥረት ተሞላ። ሳንቾ በፖሊስ ቁጥጥር ሲር እንዲቀይ ተመሰነ። ከብዙ ድርድርና ሙትጭት በኋላ ምስጢርን በሞስ ወደ ቤቷ እንድትሄድ ፈቀዱላት። ማስረሻ ወዲያው ሀይወቱ ብታልፍም ራሳው ለምርመራ ተብሎ ወደ ምኒልክ ሆስፒታል ተወሰደ። ጨርሰው ከፖሊስ ጣቢያ ሲወጡ ከምሽቱ አንድ ሰአት ሲሆን ምንም አልቀረውም ነበር።

ከፖሊስ ጣቢያ ወጥተው ሁሉም ወደ እነ ምስጢር ቤት ተከታትለው ሄዱ። ሲራክ እነ ምስጢር ቤት ሲመጣ የመጀመሪያው ነው። የሆነውን ነገር ሁሉ ማመን አቅቷት እስካሁን ድርቅ እንዳለች ነው። እቤት ስትገባ እናቷ ላይ ተጠምጥማ ለቅሶዋን ለቀቀችው። ተባብረው እንደ ምንም ገዘ ቢያሰኟትም የሆነው ሁሉ አሁንም አሁንም ራቷ ላይ ድቅን እያለባት ብርግግ ትላለች። ሲራክ አጠገቧ ሆኖ ሊያረጋጋት የቻለውን ሁሉ ሲሞክር ቆየ።

ጊዜው ስለመሸ ሰዉ ሁሉ ባንድ ጊዜ ተሰናብቶ ወጣ። ከእናቷና ካክስቷ መሃል በድኗን ብታሰቀምጥም፣ ልቧ ግን ከሳንቾ ጋር ፖሊስ ጣቢያ ገብቶ ታስሮ ነበር። ሲደበድቡት ... ሲገርፉት ይታያታል። ደረቱ በደም ተበክሎ ወደ እርሷ እያየ ሲያንጸባርር የነበረው ማስረሻ ፊቷ ላይ ወጥቶ ድቅን ይላል። የተረበሸ ስሜቷን ይባስ እንዳያደፈርሱት ፈርተው ምንም ሊጠይቋት አልደፈሩም። በትዝታ የተሞላውን ሌሊት ከመካከላቸው ተኝታ አሳለፈች።

ሲራክ ወጥቶ ወደ ቤቱ እየነዳ ምንም የተሰማው የሀዘን ስሜት አልነበረም። ነገሮች ግን በዚህ መንገድና በፍጥነት ይሄዳሉ ብሎ አላሰበም። ሞር ያለ ቦታ ሄዶ በላይ በላዩ እያጨሰ ለብቻው ሲጠጣ አመሸ። ሰልኳን አላነሳ ብላ የዋለችው ላቤላ ደጋግማ በትዩዉል ስልኩን ዘግቶ ኪሱ ጨመረው።

ትናንት በዚህ ጊዜ ማስረሻ የሱን ምክር ሰምቶ ለመተግበር ተፍ ተፍ ሲል ባይኑ ላይ ሄደ። ሳንቾ ደግሞ በጠባብ ጨለማ ክፍል ውስጥ ታጉሮ የሻማ ተብሎ ሲጠፈጠፍ የማስረሻ ቤተሰቦች ደግሞ ለልጃቸው ደም ተበቅለው ሲያስጠበዋቡት ታየው።

@OLDBOOOKSPDF

'እትምን አለማወቅ ሙሉ ይሄው ነው ... ባጃጅ ራስ' ብሎ የተረችው'ን ቢራ ጨልሞ ሌላ እንድታመጣለት ላስተናጋጁ በጁ ምልክት ሰጣት ።

ድንገት 'እንተ ሲራክ ሳትሆን ሜራትህ ... የጅህን ታገኛታለህ' ያለችው የጎሊና ቃል ትዝ አለው'ና 'ያቺ ሜጪት ፊት ... ደግሞ ሰው ሜራት ትላለች' አለ ሥክ ብሎ ፣ ውስጡ ያለው'ን በድንጋጤ ግራ የተጋባ ስሜት ለማርገብ እየሞከረ ። አንድ ልቡ ደግሞ ጎሊና እንዳለችው ሲራክነቱ ተፈረካክሶ 'ሜራት' የሆነ ሌላ ሰው ከመ'ስጡ እየበቀለ መሆኑን ነገረው ። 'ሁሉም ሜራት ነው ... እድል ያጣ ሜራት ... ሜራትም ሰው ነው ... በሰው ግፍ የተመረረ ... በሰው ደም የሰከረ' አለ ፣ ሰራሱ ድምጹ'ን አውጥቶ ።

ቤቱ በጨለማ ተውጦ ፣ ከባሻገር በሚመጣው ደባች የሆነ መዚቃ ተሞልቷል ። ወደ አምስት ሰአት ገደማ ሁለት ጠበደል የሆኑ ሰዎች በጋለ ድምጽ እየተጨቃጨቁ ገብተው እሱ ከተቀመጠበት ሶፋ ገን ተቀመጡ ። አንደኛው ደጋግሞ ያየው መሰለው ። ሁኔታቸው ስለተፈፈው ሂሳቡን ከነጉርሻው አስቀምጦ በችኮላ ሲወጣ ከኋላው ተከተሉት ። መኪናውን አስነስቶ ወደ ወንድሙ ቤት አቅጣጫ ሸመጠጠ ። ከበራፉ ላይ ደርሶ መኪናውን ሲያቆም የተከተለው ማንም ሰው አልነበረም ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 40 ፡

ሴላሠው፡ ካሰበው፡ ቀድሞ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ። ከማሰረሻ ሞት ጋር በተያያዘ በክሊኒኩ ውስጥ በተፈጠረው ተውስ ሁሉም በድንጋጤ ተውጧል ። ይህም ከንጹሕ ጋር የጀመሩትን በጽፍ ያለውን ድርድር ፍርክስክሱን አወጣው ። ከሠሉ በላይ በድንገት መመለሱ ልጆቹ ላይ የፈጠረው ስተተን ሲረብሸው ነው የነረመው ። ከመጣ ጀምሮ ብዙ ጊዜውን ከቢሮ አይወጣም ። ማታም ከመሸ ለመኝታ ብቻ ነው ወደ ቤት የሚሄደው ።

የሳንቾን ጉዳይ የመከታተል ኃላፊነቱን ለምስጢርና ለሲስተር ዘቢባ ትቶታል ። እናቱሊያናግሩት ያልሞከሩት መንገድ የለም ። ከንጹሕ ጋር በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳልሆኑ ብቻ ነው የነገራቸው ። ችግሩን ለመፍታት በምንም መንገድ እንዳይሞክሩና በዚህ ጉዳይ ማንንም እንዳያናግሩ ስላስጠነቀቃቸው የሚያደርጉት ጠፍተባቸዋል ። ኃላት እህቱ ደጋግማ ከደወለች በኋላ ያደረጉት ንግግር ሜትሜት የተሞላው ነበር ። ምንም ስለማይነግራቸው፣ ቤተሰቡ ለጤናው እየሰጋ ነው ።

ከብዙ ዳር ዳር ማለት በኋላ፣ ምንም ነገር ላይደብት ነገሩን ከሥር ጀምሮ ለምስጢር ነገራት ። ከዚያ በኋላ ትንሽ ተለል ብሎት እንዳንድ ነገሮችን ለማስተካከል መንቀሳቀስ ጀመረ ። ክሊኒኩ መስጥ የተፈጠረውን ነገር ለመረዳት የራሱን ምርመራና ጥናት ጀምሯል ። ሠራተኞቹን ሁሉ አንድ በአንድ ቢሮው እየጠራ ቢያናግርም ያገኘው ፍንጭ የለም ።

የሲራክና የምስጢር በፍጥነት መቀራረብ መጥፎ መስሎ ባይታየውም ትንሽ ግር ብሎታል ። ብዙ ጊዜ አብራው በመሆን ምስጢሩን የምትካፈለውና የምታበረታታው እሷው ናት ። ሲራክ ሴላሠውን የመጨረሻ የሴራው ኢላማው አድርጐታል ። እንዴት እንዳይነሳ አድርጎ ከጥቅም ውጪ ሊያደርገው እንደሚችል እቅዱን በጥንቃቄ እየጠነሰሰ ነው ። የምስጢርን ልብ በሴላሠው ላይ በማሻከር፣ ሁለቱን ማራራት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ አምኗል ። ከሴላሠው ጋር ከሆነው በላይ ትርብ እንደሆነ ምስጢርን ለማላመን ይቻላቸው ያህል ጊዜ ከሴላሠው ጋር ለማጥፋት እየሞከረ ነው ። እንዳንድ ያወሯቸውን ነገሮች በጨዋታ አያድረግ ይነግራታል ።

@OLDBOOKSPDF

ሌላሠው ተመልሶ ከመጣ በኋላ የነበሩት ጥቂት ሳምንታት በብዙ መንገድ አስቸጋሪ ነበሩ ። ባለፉት ጥቂት ቀናት ነው ወጣ ወጣ ማለትም የጀመረው ። የትዳሚ ሩጫውንም በብዙ ትግል ነው እንደገና የጀመረው ። የሳንቾ አለመኖርና ሌሎች ብዙ ጠንካራ ትገታዎች እየረበሹት ብዙ መቀየት አልቻለም ። ለኛ በጠዋት ክሊኒክ ደርሶ ላንቾን ለማየት መደ አስር ቤት ሄደ ። ነነምስጢር ጋር ላጭር ጊዜ ካልሆነ ፣ አሰካሁን ለብቻው አላየውም ።

ተጠርቶለት ሲመጣ መዘሳቱን አይቶ አሳዘነው ። 'ሰው ባላጠፋው ... በሌለበት መከራውን ያያል?' አለ በልቡ ። ጉስቁልቁል ብሎ በተስታ ነበር የሚራመደው ። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ሁለቱም ተረብሸው ስለነበረ በመካከላቸው ጸጥታ ሰፍኖ ቀደ ። ላንቾም ቀስ ቀስ ዘና ሲል መቀለድና ስላጋጠሙት አንዳንድ ነገሮች እየነገረው መሳሳቅ ጀመሩ ። ስላከቡ ልጆች ይህንነት ... ስለክሊኒኩ ... ስለንጹሕ ... አንስተው እያወሩ ጥቂት ቀዩና ትንሽ ጸጥ አሉ ።

"እኔ የምልህ ላንች ... ቀይ ምንድነው የሆነው? ሚስጥር እኮ በትክክልም ልትነግረኝ አልቻለችም" አለ፣ ግራ መጋባቱን በሚያሳይ ፊት ።

"እ ...ም ... ምን ልበልህ ዶክተር ሌላ ... ከዚህ በፊት ቤቱ ድረስ መጥቶ መኪናዬን ያደረገውን ምናምን ስምተሃል አይደል?" ሲለው፣ በአምንታ ራሱን ነቀነቀ ።

"የዛን ለታ ከሚስጥር ጋር ለሻይ ሙጪ ወጥተን እየተመለስን ነበር ። በር እካባቢ የሆነ ጥግ ስር ተወሽቶ ነበር መስለኝ ። ድንገት ከኮን ነገር መጣና ... የሆነ መጥፎ ቃል ተጠቅሞ 'ስሚ እንቺ ... ነይ ... ምናምን' ... ሲል ፈርታ ወደ እኔ ተጠግታ ቀመች ። ተንደርድሮ መጥቶ 'ምን ይሄ ከውሻ የማያስጥል ታክሲ ነጂ ... ከእጄ ያድነኛል ብለሽ ነው ...' ብሎ ሲገትታት ክንዷን ሲይዛት ሞከረ ። ተው ብለው አልሰማ ስላለ፣ እጁን ጠምዝዤ ... የራሱን ኃይል ተጠቅሜ ላስተናግደው መሬት ላይ ተዘረረ ።

"ከዛ እንደገና ተንስቶ ከነኑ የሆነ ነገር ሊያወጣ እየሞከረ ተመልሶ ወደ እኔ መጣ ። ሚስጥር ቀድማ አይታው ኖሮ 'ሽጥጥ ...ሽጥጥ' እያለች ስትጮህ ሮጬ ልይዘው ሞከርኩ ። ኦልራዲ እውነቶት ስለነበር መቀነስ እንዳይችል እጁን ይገርው ስንታገል ... አይ ገስ ... ላስጥለው ስሞክር ባረቀ ። እንግዲህ መጥፎ ቦታ ደረቱ ላይ በግራ በኩል ሳይመታ አልቀረም መሰለኝ ። ሌላው ያው እንደ ስማኸው ነው ። የሚገርምህ እንደዛ እያጣጣረ እንኳን ሽጉጡን እጁ ለማስገባት ነበር የሚፍጨረጨረው ። እኔ ምን ማድረግ እንደ ነበረብኝም አላወቅሁም ። የመጀመሪያ እርዳታ ሲሰጠው የሚችል ወይም ሲረዳው የሚችል ሰው ቶሎም ስላልደረሰ ... እዛው እንደወደቀ ብዙም ላይቀይ ሕይወቱም አለፈች" ብሎ፣ በግሩ መራቱን ሲቀረቁር ፣

"በጣም ያሳዝናል ። ቀይ ግን ለምን ሽጉጥ ይዞ መጣ? ... ተዘጋጅቶበት የመጣ ወይም ያሰበበት ነገር መሆን አለበት ... እንለስ ... ሁልጊዜም ሽጉጥ ይዞ የሚሄር ከልሆነ"

"አላውቅም ... ከርሱ በላይ ደግሞ ቤተሰቦቹ ሊገቡኝ አልቻሉም ... እኔ ቤቱ ሄጄ የገደልኩት ለማስመሰል@XMLFB&@KSAPDE ገርል ፍሬንዱን ቀምቶት ...

ለሀዘንና በሄደበት ምናምን ... ፈጠራቸው ... ከፖሊሶቹና ከመርማሪዎቹም ጋር እጅና ጓንት ናቸው ...እዚህም እነ ላይፈን ሃርድ አድርገው-ብኖል ..." ብሎ ተከዘ።

"እይዘህ ... የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለን ... የተሻለ ጠበቃ መቅየር ከለብንም እሱንም እያሰብኩ ነው ..." ሁለቱም ዝም ብለው ጥቂት ቆዩ። ትንሽ እንጸወሩ ጊዜያቸው ስላለቀ ተሰነባበቱ። ከሳንቾ ጋር ተለያይቶ መኪናው ውስጥ ሲገባ ያልተመለሱ ጥሪዎችን ሲያይ የዝናሽ እህት ደጋግማ ደውላ እንደ ነበር አየ። ከመነሳቱ በፊት ደወለላት። ወዲያው ስላላነሳች ቅየት ብሎ ደግሞ ሲሞክር አነሣችው።

ትንፋሿ እየተቅራረጠ "ዶክተር ... እንዴት ከረምክ ... ደህና ነህ?" አለች ከላይ ከላይ እየተነፈሰች። ትንሽ ደንገጥ ብሎ ደህንነታቸውን ጠየቃት።

ደህና መሆናቸውን ነግራው፣ "ኧረ ... እመብርሃን ... እመቤቱ ... ሳትረጸን አይቀርም ... እማማ ተዋበችን ... ሰዎች አግኝተዋቸው ዛሬ ጠዋት ላይ መጥተው ነገረውኝ ... ላያቸው ሂጂ ኮ ገና መምጣቱ ነው። ገንት የምትባል ልጅ እንደ ነበራቸውም ነገረውኖል።" ጮሮውን ማመን አልቻለም። 'እንደ ነበራቸው' የሚለው ቃል ግን ልቡ ላይ የሆነ ቅሬታን ፈጠረ። ውስጡ በድንጋጤና ባለማመን ተደበላልቆ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ጠየቃት።

"ታዲያ ... አሁን ልምጣ? ... እናንተ ጋ ነው ያሉት?" አለ፣ ስሜቱን ለመቆጣጠር እየሞከረ።

"ጥሩ ነው ...ጥሩ ነው ... እጠብቅሃለሁ ... ከዚህ ብዙም አይርቁም ... አሁን ረፋዱ ላይ ነው የተከራዩበት ቤት ሂጂ ያየኋቸው። ስላንተ ምንም የነገርኳቸው ነገር የለም ... በጣም አርጅተዋል ..." ስትለው፣ ወደ እነርሱ ቤት እየመጣ ስለሆነ፣ እንድትጠብቀው ነገራት። አመስግኗት ስልኩን ዘጋና ምስጢር ጋ ደወለ።

"ገስ ... ዋት ... የማይታመን ... ያልተጠበቀ ነገር ... ፊፀሞ ያልተጠበቀ" ሲል ፣ድምጹ ላይ ደስታ ድንጋጤና ከፍ ያለ ስሜት በመስማቷ ገርሟት፣

"ምን ተገኘ ... ሳንች ተፈታ እንዳትለኝ ብቻ..." አለች፣ እርሷም ደንገጥ ብላ።

"እሱማ ቢሆን እቤት መጥተን ነበር ... ሰርፕራይዝ የምናደርግሽ።"

"እሺ እነ ንጹሕ ሊመጡ ነው...?"

"ቢሆንማ ኖሮ ... ኤርፖርት ነበርኩ ይሄኔ ..." ብሎ ሳቀ።

"ታዲያ ምን ... ሎተሪ ደረሰህ...?"

"ቢሆንማ ኖሮ ... ለምን እደጨላለሁ ..." ብሎ እሱም የበለጠ ሲስት አብራው ሳቀችና፣

"እሺ በቃ ... አይ ጊቭ አፕ ... ምን ... ምን ተገኘ?" የዝናሽ እህት የነገረችውን ነገር ነገራት። "እኔ በፍጹም አላምንም ... ይሄ የማይታመን ነገር ነው ... እስካያቸው ግመን የምችልም አይመስለኝም ... ያት ንህ እሁንም" አለች፣ ድምጿ ባንዴ ናረ።

@OLDBOOOKSPDF

"ሳንች ጋ እሄዳለሁ ብዬሽ አልነበረም ። እዛ ቀይቼ ስመጣ እኮ ነው የነገረችኝ ። ተለበት መንገድ መግቢያው አካባቢ ነኝ ..."

"በናትህ በዚሁ ናና ... አብረን እንሂድ ... ቦሌ ሚሄፍ ነኝ ... ፕሊስ ..."

አብረው ለመሄድ ተስማምተው ስልኩን ዘጉ ። በጎተራ - ቂራ አድርገው ወደ ዘንበ-ወርቅ እየነዱ ሄዱ ። ቤት ሲገቡ ቡና ተፈልቶ ... ምላ ተርቦ ይረሱ ። የገነት እናት የተባሉትን ሴት ለማየት ልባቸው ተንጠልጥሎ መቸመሞም አልፈለጉም ። ከአቦል ቡና ጋር ትንሽ ምላ በግድ ተግምሰው ከዝናሽ እህት ጋር ተያይዘው ወጡ ። የዝናሽ አባት ቤተክርስቲያን እንደሄዱ አልተመለሱም ። ወይዘሮ ተዋበች አሉ ወደ ተባሉበት ሰፈር ለመድረስ አስፋልቱን አቋረጠው ወደ ቀሽ በሚያስነደው መንገድ ቁልቁል ወረዱ ።

"ይሄ ሰፈር ምንድን ነበር የሚባለው?" አለች ምስጢር ፣ ባለፈው የነገሯት ስም ጠፍቶባት ።

"ዘውዴ ሚዳ ነው የሚሉት" አለች የዝናሽ እህት ። ወደ ቀሽ መግቢያው ጋ ሲደርሱ ትንሽ እስኪተራቸው ውስጥ ውስጡን የውሃ ቦዮችን እየዘለሉ ሄዱ ። ካንድ አፋፍ ላይ ካለ በእሾህ የታጠረ ግቢ ገቡ ። ውስጥ ውስጡን ጎንበስ ቀና እያሉ በማዳበርያ ጨርቅ ላይ የተሰሩ ድርቀቦችን በጥንቃቄ ተራምደው አለፉ ። በመደዳ ካሉ ያዘመሙ አሮጌ ቤቶች ጥግ ላይ ተጣብቃ የተሰራች የውሻ ቤት የምታክል ከፍል ሲደርሱ የዝናሽ እህት ጮንበስ ብላ ፣

"እማማ ተዋቡ ...አሉ?" እያለች በሩን የሸፈነውን የጆንያ መጋረጃ ገልጣ ወደ ውስጥ አሮሌቀች ። ከትንሽ ደቂቃ በኋላ አንዲት የደከሙ ሽበቶ አሮጊት በትር ተደግፈው እንደ ጮበጡ ሲወጡ "ይሄው ... ተመልሼ መጣሁ ... ዘመድ ይገኛልም ..." አለች በድል አድራጊነት ኮራ ብላ ወደነሱ እየመራቻቸው ። ምስጢርና ሌላሠው ያዩትን ነገር ማመን አቅቷቸው ለጥቂት ቅጽበት ባሉበት ደርቀው ቀሩ ። ሴትዮዋ አጠገባቸው ሲደርሱ የእንግዶቹን ማንነት ለመለየት ዓይናቸውን እያሻሹ ጨፈን ገለጥ አደረጉ ።

ሌላሠው በውስጡ የሚገላበጠውን ስሜት እንደምንም ለመቆጣጠር ሞከረ ። "ትዬ ተዋቡ ረስተውኛል ወይም ብዙ ተቀይፊያለሁ መሰለኝ ... ሌላሠው ነኝ ... የገነት ጓደኛ ..." የበለጠ ቀረብ ብለው ሊያዩት ሞከሩ ። ተንገዳግደው ሊወድቁ ሲሉ ደግፎ ያዛቸውና "አወቁኝ?" ብሎ ግንበስ አለ ።

ጉንጮቹን በሁለት እጆቸው ይዘው ጥቂት አጤኑት ። "እወይ ... እወይ ... እመቤቱ ... አንቺ አያልትብሽ ..." በድንጋጤ በትራቸው ከጃቸው ወደቀ ። አንስቶ አቀበላቸው ። "ልጄ ... እንዲያው ከየት መጣህ...?" አሉ በያመንፍስ ። የሆነው ነገር ሁሉ በሀልም ላይመሰላቸው አልቀረም ። በትራቸውን ወደ ሰማይ አትጉተው የሆነ ነገር እተተመተሙ ። እጆቸውንና ፊታቸውን ሀመሙ ተያይሮ ታል ። እርጅናው ተያምሮበት የሚያውተው መልካቸው ፈጽሞ ጠፍቷል ። ፍንጭት ጥርሳቸውና ያንገት ንቅሳታቸው ብቻ አልተቀየሩም ።

@OLDBOOOKSPDF

የአይናቸው ትንድብ ረግፎ ግለቱና ፊታቸው ላይ ያሉ ሙንቻዎች መድከም ፣ ሸፍት አልባ ሌላ ሰው አስመስሏቸዋል ። ቢያስትሱም ካይናቸው የሚወጣ እምባ አልዘረፈም ። ጣቶቻቸው በከፊል ተቆራርጠው የቀሩትም ተወሲጋግዶዋል ። እንደምንም ጉንፉን ይዘው አገላብጠው ሳመት ። ምስጢር ደንግጥ አለችና ሳታስበው ፈገፍ ብላ ቀመች ። ዓይንና ጆሯቸው ቢደክምም አእምሯቸው ብሩህ ነው ። ህመሙ የልፍጫቸውን የውስጥ ክፍል ከጥትም ውጪ ስላደረገው ፣ የሚነሩነፈው ድምጻቸው ከተበላሸ ቱፕ የሚወጣ ይመስላል ።

ዋናው ቤት ለሚኖሩት አከራዮቻቸው ነግረው ፣ ደጋግፈዋቸው ወደነገናሽ ቤት ይዘዋቸው ሄዱ ። ቤት ገብተው እየተጫወቱ ቀዩ ። ምስጢር ቀስ በቀስ እየለመዷቻቸው ስትመጣ ፣ ፍርሃቷ ረግቦ ሁኔታቸው እያሳዘናት መጣ ። የገነትን ጉዳይ ለመጠየቅ ፈርቶ ዳር ዳር ሲል ቀየ ። ወይዘሮ ተዋበች ደግሞ ምስጢርን አልር አልፍ ሰርት አድርገው ሊያዩዋት ነበር ።

"ይቺስ እመብርሃንን የመሰለች ቀንጆ ... ሚስትህ ናት?" አሉ ሲፈሩ ሲቸሩ ።

"እይ ... አብረን ነው የምሰራው ...የስራ ጓዶች ነን ... ሚስቱ እይደለችም"

በትራቸውን መርኩዝ ብለው ፣ "እስታሁን መቼም ላታገባ አትቀይ...?" አሉ ፊታቸውን ወደርሱ መለስ አድርገው ።

"እምን ... ኧረ ቀየሁ ... ሁለት ልጆችም አድርሻለሁ ... ሚስቱም ልጆቿም ያሉት ውጭ ሃገር ናቸው"

"እሰይ እሰይ ..." ብለው ፣ ተነገገ አሉ ።

"ትዬ ተዋቡ ... ገነትስ...?" አለ ፣ ሲፈራ ሲቸር ያለ የሌለ ኃይሉን አጠራቅሞ ።

"ምናባቴንስና አወቁ ልጄ ... ያኔ እንዶ ጠፋች ... ጠፋች ... በሃው ቀረች ..." አሉና ዋልት ትካዜ ውስጥ ገቡ ።

"ትገ ይልዎታል ... ያኔ ተመላልሼ ስመጣ ። ደብዳቤዋን ሰጥተውኝ ነበር መዉረሻ የተለያየነው ። አላስችል ብሎኝ በማግስቱ ስመጣ ቤቱ ተቆልፎ ማንም አልነበረም ። ተመላልሼ ብመጣም ምንም ፍንጭ ስላላገኘሁ ተስፋ እንዶ ቀረሞሁ ወደ ውጪ ሃገር ሄድኩ" አለ ፣ ትገ ይበላቸው አይበላቸው እርግጠኛ ባይሆንም ።

"እንዴት ረሳሞለሁ ... ልጄ ... ደብዳቤውን ላንተ ሰጥቼሀ በማግስቱ ሌሊት ወፍ ላይንጫጫ ብን ብላ ጠፋች ። እኔም እሷን ፍለጋ ተዛን ለት ጅምር ካገር አገር ስንከራተት ... መና ሆኜ ቀረሁ ። ተሁለት አመት በኋላ ህመሙ ዘፋኖ አገርሽቶብኝ ባደ እጇን ወዲሁ ተመለስሁ ። ይሄው ተያ ወዲህ ... ጤናም የለኝ ... ሰውም አልሆንኩ ። መቼም ወይ አውራ በልታት ወይ የማጅራት መቺ ሲሳይ ሆና ይሆናል እንጂ እስታሁን አትጨክንብኝም ነበር" ተቀብሮ የቀየ እምት ሐዘናቸው ተቀሰቀሰ ። የሚወጣ እምባ ባይኖራቸውም በቀስታ እዬዬ ብለው አለቀሱ ። የነርሱም ዓይን ረጠበ ። ሲያባብሷቸው ቢሞክሩም አልቻሉም ።

@OLDBOOOKSPDF

ለቅሏቸው ትንሽ ጋብ አለኪል ጠብቶ፣ ሲያብሰለስለው የኖረውን ጥያቄ አቀረበላቸው። "እማማ ተሞቡ ... እኔ ግን እስካሁን ሊገባኝ ያልቻለው ነገር ... ገነት ግን ምን አድርጊያት ነው እንደዛ የተቀየመችኝ ... ለምን እንደጠፋች የሚያውቁት ነገር አለ?"

ሲፈሩ ሲቸሩ ... ዙሪያ ጥምጥም ሲሄዱ ቆዩና አንዱ ምንም ጨክነው፣ "እናትህ ናቸው ... ያንተ እናት ናቸው ... ትስሚን ሰብረው ስዚህ ያበቁት..." አሉ ፊታቸው ላይ የማይነበብ ቲምና ቁጣ ከመስጣቸው እየገነፈለ። "አንተን ፍለጋ ብላ ቤታችሁ በመጣችበት ... 'አንቺ ደሀ ... የቀማጣ ልጅ ... የኔ ልጅ ላንቺ አንኳን ባል ጓደኛሽም ሊሆን አይችልም። ሁለተኛ እዚች ደጅ ድርሽ ብትይና ... ከልጄ አጠገብ ባይሽ ቅልጥምሽን ነው የምሰብረው' ብለው ... በሰው ፊት አዋርደውና ሰድበው አንዳባረሯት ነግራኝ ነበር። በዚያ የተነሳ ዓይኗ እስቲፈርጥ ስታለቅስ ከረመች። የቀን ተሌት ጭንቀቷ አንተ ነበርህ ... ኋላ ግን ምን እንደንካትም አላውቅ ... ለእኛም ምንም ላትንግረኝ ... እንዲት ፍንጭም ሳትሰጠኝ ብን ብላ ካገር ጠፋች ... ወይ ልጄን ... የኔ ገነት" አሉና አዲስ እዬዬ ጀመሩ።

የሚለው ጠፍቶት ገም አለ። በሕይወቱ ሰመጀመሪያ ጊዜ በእናቱ ላይ ክፉ ቂም ቋጠረ። ደግነታቸው ሁሉ ጠፍቶ ... ጨካኝና ክፉ ሴት መሰሉት።

የገነኖሽ እህት ከእነርሱ ጋር አንዲቀዩ ስለተስማማች፣ ቋሚ የሆነ መኖሪያ እስከያመቻቹላቸው እዛው ተጪኦቸው። እንዳንድ የሚያስፈልጋቸውን ነግሮች ለመግዛት ከምስጢር ጋር ተያይዘው ወደ መርካቶ ሄዱ። ከሠፈሩ እየወጡ፣ "ዶክተር ሌላ ... ይቅርታ ... ይሄ ነገር ግን በንክኪ ምናምን አይተላለፍም ... ርግጠኛ ነህ?" አለች ምስጢር፣ ከቦርሳዋ ውስጥ ፈሳሽ ማጽጃ እያወጣች። እጇን ደጋግማ እያሻሸች ፊቷ ላይ ጭንቀትና ስጋት አንጧበበ።

የገነትን እናት ላለመንካት ስታደርግ የነበረው ጥንቃቄ ትዝ ብሎት ፈገግ አለ። "በፍጹም ... በንክኪም በዘርም አይተላለፍም ..." ሳታስበው በግራ እጁ ጉንጯን ሲነካት ሽምቅቅ ብላ ፊቷን ደጋግማ ጠራረገች።

"እስኪ ሽረ በናትህ ... እንካ አንተም እጅህን በዚህ እሽት አድርገው እስኪ ..." ብላ ፈሳሹን እጁ ላይ ልታፈስ አቀረበችለት። "ቀይ ታዲያ በአየር ነው የሚተላለፈው ልትል ነው?" ፊቷን የበለጠ ጭምድድ አድርጋ ጉንጯን እንደገና በትዝሻዋ ጠራረገች።

"ልክ ነው ... በትንፋሽ ነው የሚተላለፈው ... አይገርምሽም?"

የቀልዱን ነው የመሰላት። "ሁላችንም መያዛችን ነው በለኛ ..." አለችና በርሷ በኩል ያለውን የመኪናውን መስኮት ከፋፍታ አየት አደረገችው።

"እውነቴን እኮ ነው ... መተላለፊያ መንገዱ ልክ እንደ ቲቢ ምናምን በትንፋሽ ነው። ባክቴሪያው ከሰውነት ውጪ መኖር የማይችል በጣም ደካማ ነው። ስለዚህም በህመሙ ለመያዝ ለረጅም ጊዜ በተፋፈነ ቤት ባክቴሪያው በብዛት ካለበት ሰው ጋር መኖር ይጠይቃል። በተጨማሪም የተለዩ ዓይነት የበሽታ ተከላካይ ሴሎችና ልዩ ንጥረ

@OLDBOOOKSPDF

ነበርች መሰለኝ ፣ ከታማሚው ሰው በኩል ይኖራል የሚል መላ ምት አለ ። መድሃኒቱም እኮ ልዘ እንደ ቲቢ ጸረ-ባክቴርያ አንቲ-ባዮቲክስ ነው ። ረዘም ላለ ጊዜ መውሰድ ይኖርበታል እንጂ ። ህመሙ ግን በትንሹ የሚተላለፍ ኢንፌክሽን ነው ። "

"እና ምን ያህል ጊዜ ይፈልጋል ከሰው ወደ ሰው እንዲተላለፍ?" አለች አሁንም ነገሩን ለማመን እየተቸገረች ።

"በጣም ረጅም ጊዜ ይፈልጋል ... ለዚያውም በተፋፈገና በቂ አየር በሌለው ሁኔታ ሲሆን ነው ... ለዚህ ነው የድሀ በሽታ የሆነው"

"እሺ ታዲያ ለምንድነው ሰውነታቸውን የሚቀራርጠውና ሬታቸውን የሚያበላሸው?" አለች በትንሹ ከመተላለፉና ከባክቴሪያው ደካማነት ጋር አልጌድልሽ ብሏት ።

"ባክቴርያው በህይወት ለመቀየትና ለመራባት ቀዝቃዛ ቦታ ስለሚያስፈልገው በጀርቦችና በአፍንጫ ስር ተወሽቀ ነው የሚኖረው ። ባክቴሪያው ሰውነታችን ውስጥ እየበዛ ሲመጣ ደግሞ የበሽታ ተከላካይ ህዋሶቻችን ተቀጥተው በሚረጩት ኬሚካል ቦሰ ብዙ ነርቦች ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ ። ነርቭ ከጥቅም ውጪ ሆነ ማለት ደግሞ ጡንቻዎቻችንና እንደ ህመም ፣ መሞቀትና ቅዝቃዜ የመሳሰሉ ስሜቶቻችንን የሚቀጣጠሩ ነርቦች ሁሉ ቀስ በቀስ ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ ። በዛ የተነሳ ደግሞ ብዙ የለውነት ክፍሎቻችን ቀስ በቀስ ተግባራቸውን እያጡ ቅርጻቸው ይጠፋል ። ነገሩ ከምታስቢው በላይ ውስብስብ ነገር ነው ። "

"አህ ማይ ጋድ ... በፍጹም እንደዚህ ነው ብዬ ገምቼም አላውቅም ። ሁሉም ሰው እኮ በዘር የሚተላለፍ ... ወይ ደግሞ በንክኪ የሚይዝህ አድርገ ነው የሚያስበው ። ወይ ደግሞ የፈጣሪ ርግማን ...ምናምን ... እቤት አለማወቅ ... " ብላ ራሷን ታዘበች ።

"ልክ ነው ... ትልቁ ህመም ባክቴሪያው ያመጣው ሳይሆን አለማወታችን የጫነብን ነው ። ድንቁርና ሲበዛ በዓይን የማይታይና ከባክቴሪያዎች ሁሉ ደካማ የሆነው ህዋስ እንኳ ... ምን ያህል ሰውን የሚያህል ፍጥረት ... ከጥቅም ውጪ አድርገ ... ከከተማ ጥራጊ እኩል እንደሚያዋርድ ። ኡፍፍፍ ... የገዛ እናቴ ያደረገችውን እዩ ... ምን የመሰለች ልጅ ... ያኔ እናቷን ብታውቂያቸው እኮ ... ምን የመሰሉ ደግና እዩ ... ምን የመሰለች ልጅ ... ያኔ እናቷን ብታውቂያቸው እኮ ... ምን የመሰሉ ደግና ደርባባ ሴት ነበሩ መሰሉሽ ... ባክቴርያው ሳይሆን የኔ እናት የድንቁርና ንግግር ያጠፋው ቤተሰብ ። ምን እንደማደርጋት አላቅም አታቂን ... ወሽመጤን ነው የበጠሰችው" ብሎ መሪውን በቡጢ መታውና በረጅመ ተነፈሰ ።

"እሳቸውማ ምን ያድርጉ ... ዶክተር ሌላ ... ላንተ ብለው ነው" ስትለው ፣

"ለኔ ብላ? ለራሷ ክብርና ስም ብላ ነው ። ለእኔ አይደለም ሚስዮር ... ደግሞ ይሄንን ሁሉ ዓመት እንደዚህ ስሰታደና መከራዬን ስበላ እያየች ... ዝም ትላለች ኡፍፍፍ" ብሎ ወሰው ተንገበገበ ።

@OLDBOOOKSPDF

"እሁን ሁሉም ነገር አልፏል ... ምን ማድረግ ትችላለህ? የገዛ እናትህ ናቸው ... ባያውቁት ነው እንጂ ለከፋት ብለው እነ አይደለም።" አለች ፊቱ ላይ ያለውን ቁጣ እዘል ስሜት ስታይ ትንሽ ተጨንቃ።

"የማያርገውን እኔ ነኝ የማውቀው። አለማወቅም ቢሆን ዋጋ ያስከፍላል። አለማወቅ የሰዎችን ክፋትና ጭካኔ የነፋ ሊያደርግ ይችላል ... መደበቂያ ዋሻ ግን ሊሆን አይችልም።"

"እስኪ ሁሉንም ነገር ጊዜ መስደህ በደንብ አስበው። እንደ እኔ ግን ምንም ባትላቸው ጥሩ ነው" አለች እንደዚህ ሲናደድ አይታው ስለማታውቅ።

የሚገዙትን ሰታ ገዝተው ተመለሱ። እንዱ ክፍል ውስጥ አልጋቸውን አሰናዱላቸው። በማግስቱ ተመልሶ እንደሚመጣ ነግሯቸው የተመለሰን ገንዘብ ለገናኘ እህት ሰጥቶ ወጡ። እሷን መኪናዋ ጋ አድርሶ ቤት ሲገባ፣ እናቱ ሰላልነበሩ ከፍሪጁ ተገዝታ አምቦ ውሃ ይዞ በቀጥታ ወደ መኝታ ቤቱ ገብቶ ጋደም አለ። ስለገነት ... ስለእናቷ ... ከዚያ ደግሞ የዚህ ሁሉ ችግር ፈጣሪ አድርጎ ያያቸውን የራሱን እናት በተራ በተራ አሰበ። በጀርባው እንደ ተንጋለለ ስሜቱን ተቆጣጥሮ እናቱን እንዴት እንደሚያናግራቸው እያሰበ ሲገላበጥ ቆየ።

በማግስቱ ጠዋት እናቱ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ሊያናግራቸው መሰነ። ወደ ሳሎን መሪያና ቡናውን ይዞ፣ ቢቢሲ ዜና እያየ ጠበቃቸው። ቁርስ ተበልቶ እየተጨዋወቱ፣ "እታቲ ... ገነት ትዝ ትልሻለች?" ሲላቸው

"ገነት? ገነት?" አሉ እሱ ያሰባት ገነት ፈጽሞ ትዝም አላለቻቸው።

"ገነት የኔ የልጅነት ጓደኛዬ?"

"ውይ በምን ትዝ አለችህ ልጄ ... ያቺ የዘነበ ወርቁ ልጅ?"

"አዎን ... እኔ ላንድ ቀንም ረስቼያት አላውቅም ... መጨረሻ ላይ ድንገት ነበር የጠፋችው እኔ ልሄድ ስል ... ትዝ ይልሻል?" አለ፣ ዓይን ዓይናቸውን እያየ። ነጠላቸውን አውልቀው ሶፋው ላይ ወርወር አደረጉና የጠጡበትን ስኒ ይዘው ተነሱ።

"እንሻ ልጄ ... አንተ ከሄድክም በኋላ ብትም ብላ አታውት። ጠፋች ጠፋች በዛው ... አንድ ሁለቴ መኖራቸውን እዩልኝ ብለኸኝ ልጆቹን ልኬያቸው ... እሷም እናቷም ሰፈር ሰቀው አልተመለሱም ነበር።" እንደቀሙ ስኒውን ለልጅቷ አቀበሏት።

የሚጠይቃቸውን ጥያቄ ሁሉ እያጣጣሉ ሲያልፉት ወይም ትዝ እንደማይላቸው ሲሆንበት ትንሽ በስጨት አለ። "ቆይ እታቲ ... አንቺና እቲቱ በዛ ፍጥነት ሃይ ስኩል እንሂን ሳልጨርስ ወደ አሜሪካ እንጠልጥላችሁ የላካችሁኝ ለምንድን ነበር?"

"ኧረ በገብርኤል ... ልጄ ምን ነበቶታል ዛሬ ... ታዲያ እንዳይን ስትጠፋ ዝም ብዬ ላይህ ኖሯል። እዚህ ብተውህማ ኖሮ ዛሬ የት ልትሆን እንደምትችል ራስህ ታውቃለህ?"

@OLDBOOOKSPDF

"እሱን ለጊዚው እንተወው ... ዋናው ምክንያት ግን እኔንና ዝትን ለማለያየት ነበር አይደል?" አለ ፊቱን ትሚም አድርጎ።

"ምነው እታለም ... እና እሱን ምን አድርጊ ነው የምትለኝ...?"

"ትናንትና ከብዙ ዓለጋ በኋላ እናታን ትዬ ተሞበችን አገኘኋቸው ..."

"ምን እንዲያደርጉልህ ነው የምትፈልጋቸው? ይልቅስ ሰንት ነገር አለ አይደል የሚፈለግ ... የሚስተካከል" አሉ፣ ብስጭት ብለው። አፈትልኮ የወጣ ቨበቶ ያነራቸውን ወደ ውስጥ ገፉ እደረጉና ሻሻቸውን ጠበት አድርገው አስረው ፈንጠር ብለው ተቀመጡ።

"እታቲ ... ባጭሩ ዝትን ሥጨረሻ ላይ ያልሻት ነገር ትዝ ይልሻል? የተናገርሻት አየንትን የሚሰብር ንግግርና ስድብ ነው ልጅታን ብን አድርን ያጠፋት። ምን ያህል እንደምንኖደድ እያወቅሽ እንዴት እንደዛ ትያለሽ" ሥጨረሻ ላይ እሱን ፈልጋ ሞኖታ፣ የውሂ በራችው ላይ እንደቀሙ በስው ፊት ስድበውና እመናጭቀው ሊያባርሯት የነበረው ሁኔታ ትዝ አላቸው።

ነገሩ የበለጠ አበሳጭቷቸው፣ "እና ... እኔ እታቲ ... አበሾሽ ልጄን አባልጊልኝ እንድላት ፈለገህ? በገዛ ቤቴ ከማንም ቀማጣ ጋር ስትጋዘላዘል ዝም ብዬ ላይህ ነበር? እዝን ብናስጠጋት ቤቴ መጥቶ ልጄን ስታባልግ አበሾሽ እንድላት ፈልገህ ኖሯል? ለንድም ላላስተር እውነት ... እውነቱን ነው የነገርኳት።"

ያርውን ማመን አትቶት አገጉብሶ ራሱን ያዘ። ንዴቱን እንደምንም ዋጥ አደረገና፣ "እታቲ ... አፀም እኔም እኮ ልጆች ነበርን ... እንዴት ነው እሷ እኔን የምታባልገኝ? ... ቀማጣ የቀማጣ ልጅ ስትዪስ እንዴት አታፍሪም? ለእናቷ ብቸኛ አንድ ልጅ ናት እኮ። ያንቺ ልጅ ብትሆንስ ...? ዛሬም እንኳ ምንም ጸጸት አይሰማሽም? ... ደግሞ በጣም ሲናደድ ሁሌም እንደሚያደርገው ራሱን እያሻሸና እጆቹን ጨበጥ ለቀት እያደረገ ገሙ አለ።

"ደግሞ ምን? ... እሳው በጠበላቸው ... ቢጨያቸውን ያፈልጉ ... እና ቀደ አሁን ምን አድርጊ ነው የምትለኝ?" ብለው፣ ቀንጠር ቀንጠር እያሉ ትተው-ት ሲሄዱ ተክቶ ተከተላቸው።

"እንቺስ ያገባሽው የኔ አባት የሚሰኛ ልጅ መኖጪ ድሀ አይደል እንዴ? ለሱ ብለሽ ከባላባት ቤተሰብሽ መውረሪጥሽ ትዝ አይልሽም? ደግሞ ዝት ምን ይመጣላታል ... የሰጋ ደኖ ታማሚ ልጅ መሆን ነውር ነው?"

"ምናልክ አንተ? አይ በታህ ... ስድብህን አቁም። የት ወዴት ... አባትህንማ ከማንም ቀማጣ ጋር አታወዳድረውም ... እሱ ከደሃ ይወለድ እንጂ ኩሩ ቀፍጣና ምሁር ነው።"

ከት ብሉ እያጨበጨበ ሳቀ። ንዴቱ ከቁጥጥሩ ውጪ እየሆነ፣ "አንቺ በመርዘኛ ቃል አሳንቷን ባትሰብሪያት ... ዝትም የት ልትደርስ የምትችል ልጅ እንደነበረች

@OLDBOOOKSPDF

ውስጥሽ ያውቀዋል አታቲ ... አሁን የምጠይትሽ አንድ ነገር ነው ..." ሲል፣ ዞር ብለው እፍጥጠው ሲያዩት፣ ለመናገር አድልም ሳይሰጣቸው፣ "እናቷን ይገርያቸው እዚህ እመጣለሁ ... ይቅርታ እንድትጠይቂያቸው አፈልጋለሁ ... እሷ ሞታም ይሆናል አላውቅም"

ጆሯቸውን ማመን እንዳልቻሉ ሁሉ "ምን አልክ አንተ? ጆሮ አይሰማው የለ ..." ብለው በረጅሙ ከት ብለው ሳቁና፣ "እሺ ባክህ ... ሌላስ ... በራድዮና በጋዜጣስ ልታውጅልኝ አላሰብክም ... አንተ ልጅ ግን ጭንትላትህ ጤነኛ ነው?" አሉ፣ የምርም ጤነኛነቱን እየተጠራጠሩ።

"የምፈልገው መልስ አጭር ... እሺ ወይም እምቢ ነው" አለ፣ እንደቀመ እጆቹን ወደ ላይ አንበቶ።

"ማነሽ አንቺ ልጅ እሱን ቡና አነሳሺው። ትሰማኛለህ የኔ ልጅ ... ይቺ ቤትዮ ... ቤቱ አይደለም እዚች ዳሻፍ ድርሽ ትልና በፖሊስ ነው ...ሆ ሆ ሆ ... ይቅርታ ጠይቂያት አልክ ... ለምኑ ነው ልጄ ይቅርታ የምጠይቀው? ብታውቀው ... ከማንም ቀማጣ ጋር በትግግጥ ሕይወትህን አትርፈ ሰው ያደረኩህ እኔ ነኝ። የው-ልህ ... ይልቀውን አንተ ጤናህን ተመርመር ... ምን እንደገባብህ ወይም ምን አዚም እንዳስነነኩህ አላውቅም። ደግሞ በቃ በዚህ ጉዳይ ከዚህ በላይ ማውራት አልፈልግም ... አሁን ተወኝ ... ሰይጣኔን አታምጣው።" ቁጣቸው እየትግለገለ ጥለውት ወደ ጓዳ ሲገቡ፣ ተመልሶ ላሉን ተቀመጠና ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያስብ ቀየ።

በማግስቱ በጠዋት ክሊኒክ ደውሎ ከርሱ ጋር ቀጠሮ ያላቸውን ሀመምተኞች ሰርዞ ቤት ፍለጋ ጀመረ። የሳንቾ አለመኖር ምን ያህል እንደጐዳው ታወቀው። ምስጢር ውሳኔውን እንዲቀይርና ነገሩን በርጋታ እንዲይዘው ልታሳምነው የቻለችውን ሁሉ ብትጥርም አልቻለችም። በሳምንት ጊዜ ውስጥ ቤቱን አስተካክሎ፣ የገነትን እናት ይዞ ለብቻው መኖር ጀመረ። በዚህ የተነሳ ከእናቱም ጋር ተኳርፎ መነጋገር አቁመዋል። የቤት ሰራተኛ አድርገ የቀጠራት ከሁለት ልጆቿ ጋር መግቢያ አጥታ ስትንከራተት አነ ሲስተር ዘቢባ ቤት ለጊዜው ያሳረፏት የሰራተኛቸው እህት ናት።

የምስጢር እናት ደግሞ ሀመማቸው እየባሰ ስለመጣ፣ ብዙ ጊዜዋን ከርሳቸው ጋር ነው የምታሳልፈው። ሁሉም ሰው በያቅጣጫው ተወጥሮ፣ የራሱን ችግር ለመፍታት ሲታገል የክሊኒኩ ሥራ መገረከረኩ አልቀረም። የማስረሻ ዘመዶች ደግሞ ከሳንቾ በተጨማሪ ሙሉ ክሊኒኩን በልጃቸው ሞት ስለከሰሱ ለሌላው የፍርድ ቤት መጥሪያ ደብዳቤ ደረሰው። የክሊኒኩ ሕመምተኛ ከመሆኑም ባሻገር ሕይወቱ የጠፋበት ምክንያት ከክሊኒኩ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው ባዮች ናቸው። ጉዳዩ እየተወሳሰበ ስለሄደ ዶክተር ሌላው ከሲስተር ዘቢባ ጋር ተማክረው፣ የተሻለ ልምድና አቅም ያለው አማካሪ ጠበቃ ለመቀየር ወሰነዋል።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 41 ፡

የሲስተር ዘሪባ ቢሮ ሁልጊዜም ደስ በሚል ለስላሳ ሙዚቃ የታወደ ነው። ከኮምፒዩተሯ ላይ በተለታ የሚሣመት ሙዚቃ መከረት ትወዳለች። በመሰኩቷ እንጻር ግራና ቀኝ ያሉት ተከሎችና በግድግዳ ላይ የተሰቀሉ መልከአ ምድራዊ ስእሎች ልቢው ተፈጥሯዊ ስሜትን ፈጥረውለታል። ሌላውም ሀገ ሴሎቹ ተደምት የከሊኒኩ ሰራተኞች ስራ ጋብ ካለላቸው ወደሷ ቢሮ መሄድ ይቀናቸዋል። ከእንግዳ መቀበያ ሶፋዎቹ መሃል ባለችው ዘብ ጠረጴዛ ላይ ያለችው ሙላይ ውስጥ ከረሜላ ወይ ቸኮሌት አያጠፉም። የቸኮሌቱን ገማሽ የምትጨርሰው ደግሞ ምስጢር ናት።

ሌላው ሥራው ስላልነበረው፣ ቢሮዋ ሄዶ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሲማክሩ የቱ። ያለበት ሁኔታ ሲያስጨንቃት ነው የከረመው። "ዶክተር ሌላው ያንተ ደህና መሆን እኮ ለክሊኒኩ ደህንነት ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው። ላይህ በጣም የደከመህና የታከተህ ትመስላለህ። ወይ ለምን ትንሽ ሙላ ብለህ አታርፍም። ለስንቱ ተጨንቀህ ትችለዋለህ! ለመሆኑ እነ ንጹሕ እንዴት ናቸው?"

በረጅሙ ተነፈሰና፣ "ትልቁ ጭንቀት እሱ ነው ... ከልጆቹ ጋር በሳምንት ቢያንስ አንድቀን ስለማወራ ለሰላምታ ያህል መገናኘታችን አይቀርም። ባለፈው እንደነገርኩሽ እዛ የሚኖር ባለቤቱ ከሁለት ልጆቻቸው ጋር በመኪና አደጋ የሞተችበት መጻሽችን አለ። ንጹሕ ከሱ ጋር መወዳጀቷን ትንሽ ጭምጭምታ ሰምቼያለው። ባይሆን ደስ ይለኝ ነበር። እሱ የሞተ ጉዳይ ያመስላል። የልጆቹ ጉዳይ ነው የሚያሳስበኝ አሁን።

"እኔም ትንሽ ሙላ ብዬ ባርፍ በወደድኩ ነበር። ግን በቃ ትንሽ ራት ካልኩ የሆነ ነገር እንዳይፈጠር መፍራትም ጀምሬያለው። ይሄ ከሊኒክ የቀን ትዝት እየሆነብኝ ነው። የሳንቾም ጉዳይ ረፍት ሊሰጠኝ አልቻለም ... ምን ማድረግ እንደሚቻል አላውቅም ... ለኔ በሚያውቀው ጉዳይ ጣላ ውስጥ ገብቶ። ይልቁን አሁን የተሻለ አትም ያለው ጠቃ መቅጠር አለብን። ለክሊኒኩ የላኩትን መጥሪያ አይተሽዋል አይደል?" ብሎ፣ ግቱን እያንቋቋ ቀየና ራቱን በእጁ ሸፍኖ በረጅሙ አዛን።

@OLDBOOOKSPDF

"እንዲያውም ሳልነግርህ ... ሲራጁ አንድ በጣም ጥሩ ወዳጁ ትልቅ የሕግ ቢሮ ነው ያለው። ብዙ ጊዜ የጤና ድርጅቶችንም ወክሎ ይሰራል። ለረጅም ጊዜ ዳኛም ሆኖ ሰርቷል መሰለኝ። ብዙ ገበዝ ጠበቆች በስሩ ያሰራል። እሱን እንሞክር ይሆን? ለምን ሲራጁን አታመራውም?"

"ጥሩ ነው ... እንግዲያውስ ጓላ ላይ ደውልለታለሁ ሊጋሽ ሲራጅ።"

"እኔ ምልህ ዶክተርዬ ... ከናትህስ ጋር ምንም አዲስ ነገር የለም?"

"ምን ባክሽ ሲስተርዬ ...ኡፍፍ ... ምን ላድርጋት? ... ግራሽ እኮ ከርሷ ብሶ ... እኔ ጤነኛ አልመስላትም።"

"ያው ዶክተርዬ ... ምን ታደርገዋለህ እንግዲህ? ያው ምንም ቢሆን እኮ እናት ናቸው። ለምን ነገሩን ችላ ብለህ ... ሄደህ አታናግራቸውም ... በሁሉም ነገር እኮ ልክ መሆን አይቻልም። ማወቅ ያለብህ ህብረተሰባችን እያሰበ ሳይሆን እያባበበ መኖር የሚወድ ነው። ለምን ራስህን በትንሽ ትልቁ ታታጥላለህ። በቃ ጭክን በልና ሄደህ አናግራቸው። ትንሽ በሩን ከከፈትክላቸው ... አሳቸውም እኮ ሳያስቡበት አይቀሩም። ለይቅርታውም በር ይከፍታል። ግድየለህም ሞክረው።"

"እሺ ... ጥሩ ምክር ነው ... እስኪ ላስበው። እኔም አለህ ውስጥ ሳልገባ አልተረሁም መሰለኝ።"

"ኧረ ... ዶግም የባች የሚስጥርም እናት እኮ እየባሰባቸው ነው መሰል ... ባንዴ ጣጣችን በዛ አሁንስ። እንዲያው እሷ ልጅ ... አንዴት እንደምታሳዝነኝ ... አግኝተሃት ታውታለህ?" ከኋላዋ ተንጠራርታ ሁለት የጠርሙስ ውሃ አወጣታ፣ አንዱን ለርሱም አቀበለችው።

"ሞቼ ነበር ባክሽ ... ከትናንት ወዲያ ቤታቸው ሄጄ ... እናቷንም ጠይቂያቸው ነበር። ዛሬ ጠዋት ላይም እሷን በስልክ አግኝቼያት ነበር። ምን ታደርጊዋለሽ እንግዲህ ... የመጣውን መቀበል ነው ... እም ...ም ... እናንተስ ... ቤተሰብ ሁሉ ሰላም ናችሁ?" አለ የሰጠችውን ውሃ እየከፈተ።

"ሁሉ ሰላም ነው ... ሁሉ ደህና ነው" አለች፣ ፊቷን ወደ ላይ ቀና አድርጋ። ፊቷ ላይ ያለው የመጨነቅ ስሜት እምብዛም ላይለቃት፣ "ዶክተር ሙት ... ግድ የለህም ... ትንሽ ከዚህ ሁሉ ውጥረት ላንድ አራት አምስት ቀን ወጣ ብትል ይሻልሃል ... ጉባይ ሄደህ ታውታለህ?"

"አይ ... ሁል ጊዜ ለመሄድ እያሰብኩ ያልሞላልኝ ቦታ ነው ... እንዲያውም ባለፈው የመጡ ጊዜ ከነንጹሕ ጋር ... ኦልሞስት ልንሄድ ተነስተን ... መጨረሻ ላይ ጊዜው ተወጣጠረና ሳንችል ቀረን።"

"አሁን እኮ ... አይ ቲንክ ... አየሩም ጥሩ ነው ... ግያለህም ... ትንሽ ዘና ብለህ ና ... እዚህ ያለው ችግር የት ይሄዳል ብለህ ነው? እኛ አለን አታስብ" አለች፣ አይን አይኑን እያየች።

@OLDBOOOKSPDF

"ልክ ነሽ ... ምናልባት ይሻላል መሰለኝ ... አሁንማ በትክክል ማሰብም እያቃተኝ ነው። ሞንትላቱም ሞላ መሰለኝ" ብሎ ፈገግ አለ። በቢሮዋ መስኮት አንጻር ትንሿ ካፌያቸው ሙሉ ለሙሉ ትታያለች። ሲራክና ምስጢር ለረጅም ሰአት ከካፈዋ በረንዳ ላይ ተቀምጠው እየተሳሳቁ ሲያወሩ አይቶ ፈገግ አለ።

"የወ/ልህ ዶክተር ... እንዲያውም ሰሞ ዓመት በአል አይደል ... አርብን ጨምረህ ብትሄድ ... አራት ቀን በቂ ጊዜ ነው ... ለምን ነገ ዝም ብለህ አትወጣም? ትኬቱን ... የኛ ደንበኛ አለች እሷን እኔ ላናግራት እችላለሁ።"

"ጥሩ ሲስተርዬ ... በቃ እስኪ አናግሪያትና ... ከቻልሽ ማታ ላይ ደውይልኝ ... አሁን ግን ልወጣ መሰለኝ።"

"በቃ ... እኔም ጨርሻለሁ ... ሙኒራም አጎቷ ቤት እየጠበቀችኝ ነው ... ገና አስኮ ድረስ መሄድ አለብኝ" ብላ፣ ዕቃዋን ሰበሰባ ተከታትለው ወጡ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 42 ፡

ሌላው ዱባይ አርብ ማታ ገብቶ፣ ቅዳሜ ጠዋት ላይ የምስጢር እናት ድንገት መተንፈስ አቅቷቸው ሆስፒታል ገቡ። የምትደውልበት ሰው ግራ ግብት ሲላት ሲራክ ጋ ደወለች። አልጋ ይዘው ሁሉ ነገር አስኪረጋጋ እያገዛት እስከ ምሽት ድረስ አብሯቸው ቀየ። ደጋግማ እንዲሄድ ብትለምነውም፣ አሻፈረኝ ብሎ ቀየ። ከመሸ በኋላ ከተረኛ ሃኪሞቹ ጋር ችግር ቢኖር እንዲያግዟት አስተዋውቋት ወጣ። እሁድ ጠዋትም ከተወሰነ ሰአት ውጪ አልተለያቸውም። ከሰዓት በኋላ ላይ እሷ እቤት ሄዳ አረፍ እንድትል ከአክስቷ ከወይዘሮ ዘምዘም ጋር በግድ አሳምነዋት ቤት አደረሳት። ብዙውን ጊዜ መኪናውን የሚሾፍረውና የሚያስፈልጉ ነገሮችን እየወጣገዝቶ የሚያመጣላቸው እሱ ነው።

አመሻሹ ላይ ምስጢር አዳሯን መጣች። ትንሽ ቆይተው የታዘዙ መድሃኒቶችንና አንዳንድ ነገሮችን ለመግዛት ከሲራክ ጋር ወጡ። እነርሱ ሲወጡ፣ እንዴት አይነት ጥሩ ትሁት ልጅ እንደሆነና ለምስጢር ያለውን ፍቅር እንስተው እያደነቁ ለአክስቷ አወሯት። ነገር ቀንቶ ሁለቱ ቢጋቡላቸው ምኞታቸው መሆኑን ከላይ ከላይ እየተነፈሱ ነገሯት። አክስቷ ግን ስታየው የሆነ ቀልቧ ያልተቀበለው ነገር እንዳለ ለማስረዳት ሞከረች። ነርሷ መጥታ መድሃኒት ሰጥታቸው የጉልኮስ ከረጢቱን ሰትቀይርላው ወራያቸው ተጽረጠ።

ሲራክና ምስጢር ስለክሊኒኩ ጉዳይ እያወሩ መንገዱ ከፍት ስለነበር ኦሊምፒያ አካባቢ ደረሱ። በወሬያቸው መሃል የሳንቾም ጉዳይ ተነሳ። "የሱ ልጅ ነገር በጣም ነው እያስጨነቀኝ ያለው ... የባ የርኩስ ቤተሰቦች እኮ ጥሩቱ የሳንቾ እንዳልሆነ ያውቃሉ እኮ። እሱን ያሳሰሩት የሆነ የሚበቀሉት ሰው ፍሊጋ እንደሆነ ግልጽ ነው ..." አለ ሲራክ። ከፊቱ ያለው ፒክ አፕ ላይ ክላክሱን አምባርቆ ሾር ብሎ እጁን አወናጭፎ አለፈው።

"ምን ታደርገዋለህ ጊዜው የጉልበተኛ ነው ... እነሱማ ቢችሉ ኖሮ እኔንም ለማሳሰር ያላደረጉት ጥረት አልነበረም ..." ብላ፣ በረጅሙ ተነፈሰች ሰዓቷን እያየች።

@OLDBOOOKSPDF

"ለዓቱ ሄደ አይዶል? በጣም ያዘንኩት ግን ... ምን ያህል ሚስእንደርስታንድ ያደረኩት ልጅ እንደሆነ አውን ሲገባኝ ነው። በታ ኮ ደረቱን ወጣጥሮ ሲሄድ ትዕቢተኛ በለሚመስለኝ በጣም ነበር የምጠላው። ለውን ግን ከውጭ አይተሽ በሚለማሽ ስሜት መገመት ትልቅ ወንጀል ነው። ታውቂያለሽ ሳስበው ... የማስረሻ ቤተሰቦች አውን ጠቅላላ ዘሊኩን በመከሰሳቸው ባንድ በኩል ደስ ብሎኛል ..."

"ለምን?" አለች ፣ ምን እስቦ እንደሆነ መገመት እያቃታት።

"ሁላችንንም ለልጃቸው መሞት ሃላፊ ያደርጉናላ ... ሁላችንም ተጠያቂ ከደረጉን ደግሞ እሱን ነጥለው ማጥቃት አይችሉም። ደግሞም የተሻለ ጠበቃና የመከራከሪያ ነጥብ ይዞ መቀም ይችላል። ምንም ቢሆን ከግለሰብ ድርጅት ይበረታል" አለ፣ ነጥቡን ለማስመዝገብ የሚችለውን ሁሉ እያደረገ።

"ሀም ...ም እንደሱ አላየሁትም ነበር ... እስኪ ይታያል እንግዲህ ..." አለች። ሲራዝ ከሰበችውና ከገመተችው በላይ ለሰው የሚጨነትና ጥሩ ልጅ ሆኖ ታያት። ስለርሱ የነበራት አስተሳሰብ ሁሉ የተዛነፈ ሆኖ በመሆኑ ተጸጸተች።

"እኔ የምልሽ ... ማዘር መታመማቸውን ዶክተር ሌላ ሰማ እንዴ?"

"ምን አውቃለሁ ... ኢሜይል አድርጊለት ነበር ትናንት ማታ ... ሳይጨነቅ ቢያርፍ ደስ ይለኝ ነበር ... ግን ደግሞ ...ላልነግረው እንድ ነገር ብትሆን" ብላ ፣ ማልቀስ ጀመረች።

"ሽረ በናትሽ ... ምንም አይሆኑም ... ኢንፈክሽኑ ነው ትንሽ ያደከማቸው ... እሱን በቱጥጥር ስር ካደረገት በታ ... ይሻላቸዋል። ዶክተር ሌላ ግን ምናልባት እንግዲህ ኢሜይል እክሰስ ባይኖረው ወይም ደከሞት ተኝቶ ኢሜይሉን ቼክም አላደረገው ይሆናል ... እንጂ ሰምጠለ ወይም ሰምጣቱ አይቀርም ... አይዞሽ" ብሎ፣ ጀርባዋን ባንድ እጁ እሻሸና ከመኪናው ላይ ናፕኪኑን አተበላት።

"ታንክ ዩ ... አይ አም ሹር ቢሰማማ ባይ ናው ወይ ይመጣል ... ቢያንስ ይደውል ነበር" አለች ፣ አይኖቿን እያደራረቀች።

"እባች ካልዲሲ ጋትነሽ እንቱም ...ማኪያቶምናምን ...በዛውም ትንሽ ተረጋጊ" ሲላት ፣ ትንሽ ነቃ ለማለት ማኪያቶ መጠጣቱንም ስለፈለገች ፣ ሙጪ ቮሎና መኪና ውስጥ እንዳሉ አዘዘ። መልሱን ካነበበው የሌላሠው ማስታወሻ ላይ ቢያወላውም ፣ ቀስ ቀስ እያለ አንዳንድ ጥያቄዎችን ስለ ራሷና ስለ ቤተሰቦቿ ጠየቃት። በናታም ባባታም ካሉ ዘመዶች ርቀው እንደሚኖሩና ወንድምም እህትም እንደሌላት ነገረችው። እናቷ ቢሞቱ ማንም እንደሌላት እየነገረችው ስታለቅስ ፣ አቅፎ ሊያባብላት ጥየና ትንሽ ጋብ ሲልላት ተጨማሪ ሶፍት ሰጣት።

"ታውቂያለሽ ሚስጥር ... ለረጅም ጊዜ በጣም ወንዶችን የምትጠዪ ... በወንዶች ስታይ የምትደሰች ጨካኝ ሰው አድርጌ ነበር የምስልሽ ..." ሲላት ፣ ዓይኑ ውስጥ እያየችው ፣

@OLDBOOOKSPDF

"እና አሁን ሃላብህን ምን አስተየረህ ታዳያ? ... ሳልትስ ስላየኸኝ ነው...?"

"ኖ ኖ ... እሱ አይደለም ... ሁልጊዜም ከዶክተር ሴላ ጋር የምንከራከርበት ጉዳይ እኮ ነው። በምንም መንገድ ሊያሳምነኝ አልቻለም ነበር። በትርብ ቀን ግን በቃ ስላስተዳደገሽ ... ካባትሽ ጋር ስለነበራችሁ ግንኙነትና ስላደረሱብሽ ነገሮች ምናምነ ሲነግረኝ ... ከጥላቻ ይልቅ ስላንቺ ጥልቅ ሃዘን ነበር የተሰማኝ ..." ፊቷ ልውጥውጥ ማለቱን ሲያይ፣ እንደ ደነገጠ ሆኖ እጅቹን ከፍ አድርጎ የሆነ ነገር ሊል መሰለ።

"ምንድነው የነገረህ ካባቴ ጋር ስላለኝ ግንኙነት...?" ውስጧ ቁጣ ቢልም እንደምንም ስሜቷን ለማርገብ ሞከረች።

ፊቷ ላይ ያለውን ለውጥ እንዳላየና እንዳልገባው ሆኖ፣ "ኦህ ... በጣም ይቅርታ ... ማለት የሌለብኝን ነገር ተናገርኩ መሰለኝ። እም ሶሪ ... በርግጥ እውቃለው ... እሱ እንዲህ አለኝ ምናምን ማለት እንደሌለብኝ። ግን ደግሞ ዝም ብዬ ነገሩን ብንግርሽም ማን ነገረህ ብለሽ መጠየቅሽ አይቀርም። ለማንኛውም የኔ ጥና አላማ ... እኔ ስላንቺ የነበረኝ የተሳሳተ አመለካከት እንዴት እንደተቀየረ ለመናዘዝ ብቻ ነበር። ምናልባት እሱም ለኔ ሊነግረኝ የተገደደው ... ለክፋት ብሎ ሳይሆን ... የተሳሳትኩ መሆኔን ለማስረዳት ሊሆን ይችላል ..."

"እሱን ለኔ ተወው ... ቶይ እስኪ ምን ነገረህ ... ሁሉንም ማወቅ አፈልጋለው" ብላ፣ አፈጠጠችበት።

አውንም ነገሩ ከጠበቀው መጪ የሆነበትና ግራ የተጋባ በሚመስል ፊት፣ "እይ ዶ ኖ ... በቃ ምን ያህል እየሰከሩ አንቺንም እናትሽንም አዚዞዝ ያደርጓችሁ እንደነበር ... በተለይ ደግሞ አንቺንም ለረጅም ጊዜ ... አይ ዶኖ ከአባት የማይጠበቅ ነገሮችን እንዳደረጉሽ ... ደግሞ ... ከነበሩሽ ቦይ ፍራንዶችም ጋር ... ያሉትን ችግሮች ምናምን ... ያ ሁሉ አውን ባለሽ ግንኙነቶችና ... እሰ አይደል ያሰውን ተጽእኖ..."

ሳታሰጨርሰው በንዴት እጇን እያመናጨቀች፣ "እሺ ... ገባኝ ... ገባኝ ... በቃ ታንኪዩ ... አውን ስለኔ ስለ ጥሪህ ቀና አመለካከት አመሰግናለው። ይጠብቁናል ... ሂሳቡን ከፍለን እንሂድ አውን ..." አለች፣ ሞጁን በሁለት እጆቿ ጥብቅ አድርጋ ይዛ። ከዚያም ጸጥሯን ብትነትን አድርጋ እንደገና ለማስተካከል ሞከረች።

"ሚስጥር ... በጣም ይቅርታ ... በዚህ ሰአት ይህን ሁሉ ማንሳት አልነበረኝብኝም ... እሱም ቢሆን ለክፋት አስቦ አይመስለኝም ... ያው ኮሊገች ስለሆንን ይመስለኛል ... ጥፋቱ የኔ ነው ... ሶሪ በናትሽ ..." እያለ፣ ይቅርታውን አሸንጉዶደው።

"አይ አም ሹር ...ሁላታችሁም ለክፋት ብላችሁ አይደለም ... ታላላት የክሊኒኩ ሲታውንት ... ኮሊገች ስለሆናቸው ነው ... በቃ እንተመው እሱን ... ቶሎ እንሂድና ለአክሰቱ ልተካላት... ትጠብቀኛለች" ብላ፣ የሚገዙትን ገዝተው በተጥታ ወደ ሆስፒታሉ ተመለሱ።

መንገዱን ሁሉ ባብሰው ጸጥ ብለው ነበር። ለሚጠይቃት ጥያቄ ባጭሩ እየመለሰችለት፣ በላይ በላዩ ትኩሰ ትኩሱን እየተነፈሰች ደረሱ። ብዙም ሳይቆይ

@OLDBOOOKSPDF

በማግስቱ ከከተማ ውጪ ስለሚውል ወደ ማታ ላይ እንደሚመጣና ደውሎ ያሉበትን ሁኔታ እንደሚጠይቅ ነግሯቸው ወጣ ።

ሲራክ ተስናብቷቸው ከሆስፒታል እንደ ወጣ ቀጠሮው ስለ ረፈደበት በቦሌ ሆምስ አሳብሮ ሄደ ። 'ወይ ሲራክ ... ወፍቼ ሁሉ እየዘለሉ ወጥመድህ ውስጥ ገቡ ። እንግዲህ ምን ቀረ? ... ትልቁ አሞራ ነው ... እሱም ከሊኒኩና ትዳሩ መቀመቅ ከወረደለት ... ይቺን የድሀ ሀገር ሰዋ ውልት ማለቱ አይቀርም ። ' ሚስጥር የሰጠችውን ቸኮሌት አፉ ውስጥ ከትቶ አጣጠመው ።

ምስጢር ደግሞ አክስቷ ከሄዱ በኋላ እናቷም ተኝተው ስለ ነበር ስትብሰለሰል አመሸች ። ሌሊቱን ሙሉ ስትንጨረጨር ... የረባ እንቅልፍም ባይኗ ሳይዞር ነበር የነጋው ። ለማንም ያልነገረችውን የግል ሚስጥሯ ብላ የነገረችውን ጉዳይ ለሲራክ እንደ ተራ ወሬ ከዝ አድርጎ በማውራቱ ሌላሠውን ከልቧ ተጸየፈችው ።

ሲራክ ቴሌ መድሃኒአለም አካባቢ ሲደርስ ሳቤላ ጋ ደጋግሞ ቢደውልም ለረጅም ጊዜ ስልኳ ጠፍቶ ስለነበረ የት እንዳለችም ሊያውቅ አልቻለም ። ነገሩ መጀመሪያ ስጋት ፈጠረበት ። እየቆየ ሲሄድ ብስጭቱ እያየለ መጣ ። ሰው ሲያረፍድበት መታገስ አይችልም ። እየቆየ ሲሄድ ደግሞ ልቡ በጥርጣሬ ተሞልቶ የት ልትሆን እንደምትችል የሆነ ያልሆነ ነገር እያሰበ ውስጡ በቅናት ተንጨረጨረ ። ወዲያው "ሲሩ ... ችግር ገጥሞኝ ነው ... አሁኑኑ ወደ ቤት ሄደህ ጠብቀኝ ... ወደባው እየመጣሁ ነው" የሚል የጽሁፍ መልእክት ደረሰው ። ቢደውል ስልኳ ዝግ ነው ። ብስጭትና ግራ መጋባት እየተፈራረቁበት መኪናውን እያከሰፈሰፈ ወደ ቤቱ አቀና ።

በሩን ለመክፈት ሲሞክር እምቢ አለው ። ምን እንደሚያደርግ ግራ ገባው ። ትንሽ ቀይዶ ከወስጥ በሩ ሲከፈት እያመነታ ገባ ። ቤቱ በሻማ ተንቀጥቅጦ የሚወደው ለስለስ ያለ ሙዚቃ ተቀበለው ። ድንጋጤው ሳይለቀው ሳቤላ ላዩ ላይ ተጠምጥማበት 'ሰርፕራይዝ ..." ስትል ደነገጠ ። 'ሃፒ በርገዳይ' ስትዘምርለት ንዴቱ ሁሉ ተኖ ጠፋ ። ያዘጋጀችውን ራት እየበሉ የባጥ የቆሙን ሲያወሩ መሸ ። በማግስቱ በጠዋት ተነስተው ላንጋኖ ውሎ ገብ ሄደው ተመለሱ ።

@OLDBOOOKSPDF

43

ሌላው የምስጢርን ኢሜይል ካገኘ ጀምሮ ደጋግሞ ቢደውልም ... የጽሑፍ መልእክት ቢልክላትም አልመለሰችለትም። በጠዋት ተንሰቶ እያሰበ ከሰዓት በኋላ አዲስ አበባ ሲገባ በቀጥታ ሆስፒታል እንደሚመጣ የሚገልጽ የሚያበረታታ የጽሑፍ መልእክት ላከላት። ጽሑፉ እንደደረሳት አጠፋችው። ማመሻሻው ላይ ሆስፒታል ሲደርስ ትንሽ አብራቸው ቀይታ ደክሞኛል ብላ ከእህስቷና ከናቷ ጋር ትታቸው ወደ ቤት ሄደች። የባህርይዋ መለዋወጥ የእናቷ መታመም የፈጠረባት ድንጋጤና ጫና ነው ብሎ አሰበ።

በየቀኑ ከስራ በኋላ እየተመላለሰ እናቷን ሲያጫውታቸውና ሲያበረታታቸው ከረመ። ምስጢር ግን ከፉም በጎም ላትናገረው ካንገት በላይ ነው የምታዋራው። እሱ ሲናር ሆስፒታል ላለመኖር ትመክራለች። ነገሩ ግራ ገብቶት እናቷን ቢጠይቃቸው ከታመመው ጀምሮ የሚሰራትን እንዳላጣትና ከማልቀስ ሌላ ሙያ እንደሌላት ነገሩት። ሆኖም በውስጡ አንድ ጥሩ ያልሆነ ነገር ተሰምቶታል። አርብ ማታ ወደ ቤት ለመሄድ ሲነሳ በማግስቱ ቅዳሜ የሚያማክሩት ብርቱ ጉዳይ ስላላቸው፣ ከቀኑ ስምንት ሰዓት እንዲመጣላቸው ጠየቁት።

ቅዳሜ ቀን ላይ ምላቸውን አብልታቸው ለብቻቸው ሲያወሩ "ሚስጥሬ ... ይሄ ሀመም እኮ አሁንስ አምርሮ ነው የመጣው መሰለኝ። ወስጤ እየታወቀው ነው ... ምናልባት ይሄ የመጨረሻ ሳይሆን አይቀርም። ልቤ እየባባብኝ ነው"

"ውይ ማሚዬ በናትሽ ... እኔ እንደሱ ማሰብ አልፈልግም። እግዚያብሔርን ለምኜዋለሁ ... ምንም አትሆኚም ... ያላንቺ እኮ ማንም የለኝም" ስትላቸው፣ ጸጉሯን እያሻሹ ትንሽ ዝም ብለው ቀዩና ራሳቸውን አበርታቱ።

"ሚሚዬ ... ለብዙ ጊዜ ተሸክሜው የኖርኩት የምነግርሽ አንድ ትልቅ ሚስጥር አለኝ። እኔ ካሁን በኋላ ምን ያህል እንደምቀይ አላውቀውም። ሳልነግርሽ ደግሞ መሞት አልችልም። ነግሬሽ ብቀይም ምንም ችግር የለውም ... ዛሬ ልነግርሽ ነው ያለብኩት ..." ሲሉ ልቧ በ[illegible]ላይ ተጠመጠመች።

"እማ ... ምንድነው ... ፈራሁ ..." ብላ፣ የበለጠ እንቅ አድርጋ ስታቅፋቸው ሁለቱም አፋፍላይ ያለ እምባቸውን ለቀቁት ..."ም ...ን...ድነው?" አለች፣ አንገታቸው ውስጥ እንደተቀበረች

"ልጄ ... ስላንቺ ነው ... ለኔ ከልጅም በላይ ልጅ ነሽ ... ግን ደግሞ እኔ ወላጅ እናትሽ አይደለሁም ... አባትሽ ..." ብለው፣ አቅም አንሷቸው ከላይ ከላይ መተንፈስ ጀመሩ።

እንደ መብረቅ ተስፈንጥራ ተነሳችና፣ "እኔ አላምንም ... እምቢ ... አልፈልግም ... እማ ... አንቺ ነሽ እናቴ ... ሌላ እናት አልፈልግም ... አባትሽ አትበይኝ አሱ ... አውሬ ነው ... አትንገሪኝ" ብላ፣ አልጋው ጫፍ ላይ ተቅምጣ ራሷን በእጆቿ ይዛ መንሰቅሰቅ ጀመረች።

አትማቸውን እንደምንም ሰብስበው እንደምንም ቀና ለማለት ሞከሩ። "ዘመዘም ...ዘመዘም ..." የሚለውን ቃል ገና ካፋቸው ሲያወጡ በሩን በርግዳ እያለቀሰች ከፍሉን ጥላ በሩጫ ወጣች። እየተደንዶረዶረች በዶረጃው ላይ በሩጫ ስትወርድ ሌላሠው ደግሞ በሊፍቱ ውስጥ ወደ ላይ እየወጣ ስለነበረ ተላለፉ። ግራና ቀኝ ሳትዞር እንባዋን በሹራቧ ጫፍ እየጠረገች ወደ መኪናዋ ሮጠች።

ሰው ሁሉ ዞር ዞር እያለ ቀም እያለ አያት። ሊያናግሯት የሞከሩ ሰዎችን ዞርም ብላ አላየቻቸውም። መኪናዋን በደመነፍስ አስነስታ ወደ ቤት ከነፈች። ከላከሱን ደጋግማ ስታጮኸው ዘበኛው ደንግጠው እየተርበተበቱ ከፈቱላት። መኪናውን እንደ ነፋሱ አቁማ የሩጫ ያህል እየተወናጨፈች በሳር በኩል ወደ ትልቁ ቤት ገባች።

የሳንቾ ያከሰት ልጆችና ሠራተኞቹ ተሯሩጠው ሲከተሏት ሳሎን ገብታ ተቀመጠች። ልጆቹን ላመችና እንደምንም ራሷን አረጋግታ "እማሚ ደህና ናት ... ሃይ ብላችኋለች ... እኔ በጣም ስለደከመኝ ማረፍ አፈለጋለሁ ... አባው ደጅ ተጫወቱ ... ራሴንም ትንሽ አሞኛል ..." አለች ራሷን ያዝ አድርጋ። ከሰራተኛዋ ጋር ትንሽ አወራችና ማረፍ እንደምትፈልግ ነግራት፣ ወደ መኝታ ቤቷ ገብታ አልጋዋ ጫፍ ላይ ተቀመጠች።

ራሷን በጆቿ ይዛ እንዳቀረቀረች፣ እንባዋ ምንጣፉ ላይ ዱብ ዱብ አለ። ሹራቧን አውልቃ ወለሉ ላይ ወረወረችና ወደ መታጠቢያ ቤት ገባች። በቀዝቃዛ ውሃ ፊቷን ታጥባ ያበጠ ፊቷን በመስተዋት ውስጥ ስታየው የሷ አልመስላትም።

አባቷ እቶ መዝገቡ አክስቱ ብላ ከምትወዳቸው ከወይዘሮ ዘምዘም የወለዱት መሰላት። "ያ ክፉ አውሬማ ... ከትዬ ዘምዘም ... የወለደኝ ዲቃላው ልሆን አልችልም ... አሁንስ በዛ ... በዛ ... እ-ሀ-ህህ" ብላ፣ የሻወሩ ግንዳ ላይ ተቀምጣ ስትስት ብላ አለቀሰች። የተለያዩ ነገሮች በፍጥነት ፊቷ ላይ መጡ። ከዚያም አክስቷ ወይዘሮ ዘምዘም በወጣትነቷ አርግዛት ሊሆን እንደሚችል አሰበች ... በፍጹም እናቷ ከወይዘሮ ኤደን በቀር ማንም ሊሆን እንደማይችል ወሰነች።

@OLDBOOKSPDF

ድግሞ... ሳንኮ ባልሰራው ወንጅል እስር ቤት ሆኖ እየተሰቃየ ፍርዱን ሲጠብቅ ... ትልት ነው ብላ ያመነችበት ሌላው ሚስጥሯን የትም እንዳ ብትል ሲያስጣው ... በፍቅር የምትንለፈለፍላቸው እናቷ ወይዘሮ ኤደን በሞት አፋፍ ላይ ሆነው ... እናቷ አለመሆናቸውን ሲናዘዙ ሲንገታገቱ ... ታያት ። ሰዉ ሁሉ ያልገመተችው ሌላ ሰው ... መኖር ራሱ ኪሳራ ብቻ የሆነ ድካም ሆኖ ተሰማት ... የምታምነው ሰው በሌለበት ጨካኝ ዓለም ውስጥ ቀዝቃዛ ብቸኝነት ተሰማት ።

ውስጢም ዙሪያዋም የተስፋ መቁረጥ ጨለማ ከደነው ። ሮላ የምታመልጠው አልመስልሽ አላት ። አዲስ ሌላ ማንነትን ለመተበልና ... ሌላ እናት ለማወቅ ወሰኗ እምቢ አለ ። 'እኔ ማነኝ?' የሚለው ጥያቄ እያጸፋት ... ጥልቅ የማንነት ቀውስ ወሰጥ ሰጠመች ። 'ከተምታታ ማንነት የሌለ ማንነት ይሻላል' የሚል ሐሳብ ብልጭ አለላት ። ተነስታ ክፍሏ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ተመላለሰች ። አልጋዋ ላይ በጀርባዋ ተንጋላ መሞት ምን ሊመስል እንደሚችል አወጠነጠነች ። አሟማቹ ስታይ ከሌለው ሞት እረፍትና ከዚህ ሁሉ ስታይ ብቸኛ ማምለጫና ማረፊያ ሆኖ ታያት ።

ድግሞ ሞታ ነፍሷ ስትወጣ ... ወደ ገሃነም እሳት ስትጣል ... ቦታ ደልጻይ ሰይጣኖች ከንዲን ይዘው እባታ ወዳሉበት ክፍል ሲወስዷት ... እንዲያሰቃዩዋት ለርሳቸው እንደገና ሲያስረክቧት ታያትና ቀፈፋት ። ጣሪጣራውን ስታይ ቀየችና ነፍሷ በየት በኩል ከዘፍሉ እንደምትወጣ መገመት አቃታት ። ብድግ ብላ የመድሃኒት ማስቀመጫ መሳቢያዋን ከፍታ ስታይ ጥቂት የራስ ምታት መድሃኒትና አንቲባዮቲክ ብቻ አገኘች ።

ወደ እናቷ መኝታ ቤት ተንደርድራ ገባች ። ከራስጊያቸው የተደረደሩትን ሰድስት ብልቃጦች አገላበጣ አየች ። የአንትልፍና የድባቴ መድሃኒቶቹን መረጠች ። እነርሱን ይዛ ወደ ክፍሏ ተመለሰች ። ከሞተች በኋላ ስለሚሆኑ ነገሮች ላለማሰብ ሞከረች ። እናቷ ነገሩን ሰምተው በድንጋጤ ሲሞቱና የተብር ተናቸው ባንድ ላይ ሲሆን ታይቷት 'አብረን መኖር ካልቻልን አብረን ብንሞት ይሻላል' ብላ አሰበችና በደረቁ ፈገግ አለች ።

ከራስጊዋ ማታ የጀመረችውን ውሃ አንስታ ተገነጨችለት ። ብልቃጦቹን ከፍታ ጥቂት አሰበች ። ፍርሃት ወረራት ። ሳልሞት ቢደርሱብኝስ ... ብተርፍስ ... የሚል ሃሳብ አሰጨነቃት ። ያሉትን ኪኒኖች ብዛት ስታይ እንደማትተርፍ አሰበች ። ማስታወሻ ጽፋ ልትተው አሰበች ። 'ለማን ... ለማን እጽፋለሁ?' ብላ ተመችው ።

ድንገት ብድግ አለችና ከሁለቱም ብልቃጦች ላትኮሮር ታመችና በውሃው አመራርጻ አልጋዋን ተደግፋ በርከክ አለች ። በሞቲት ደቂቃዎች ውስጥ ተዘለፍለፉ ጠለሉ ላይ ወደቀች ። ሁኔታዋ ያላማራት ስራተኛቸው ሻይና ጥቂት የሚቀመስ ነገር ይዛ መጥታ በሩን ብታንኳኳ መልስ የለም ። መክፈቻውን ሣጒን ስትለው ያለችግር ተከፈተላት ። ወለሉ ላይ ተከፍትው ከተበተኑት ጥቂት ኪኒኖች አጠገብ ዝንፍልፍል ብላ ወድቃ ስታያት ኡኡታዋን አስንካችው ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 44 ፡

ሊላሠው፡ ከሊፍቱ ወጥቶ ወደ መይዘር ኤደን ክፍል አንኳኩቶ ሲገባ አልጋቸው ጫፍ ላይ ደገፍ ብለው፡ ተቀምጠው ... እንባቸው እየፈሰሰ ከላይ ከላይ ይተንፍሳሉ። ትንሽ ካረጋጋቸው በኋላ ነርሶቹን ጠርቶ ... ኦክሲጅን ተተየለላቸው፡ ትራሱን ደገፍ ብለው፡ ሲተመጡ ትንሽ ተሰል አላቸው። እንደምንም ትንፋሻቸውን ስብስበው፡

"ዶክተርዬ ... ሚስዮራን እየሃት? ... አሁን አንተ ስትገባ ነበር እኮ የመጣችው" አሉ፣ አይናቸው እየተከራተተ።

"አይ ኧረ አላየኋትም ... ምነው ሰላም ነው?"

"ሰላ--ም ነው ... ሰ...ላ...ም ..." አሉ፡ ትንፋሻቸው እየተቆራረጠ ... ትንሽ ዝም ብለው፡ እንዲያርፉ ስለነገራቸው አንድ አስር ደቂቃ ጸጥ ብለው፡ ቆዩ። ትንሽ ጋብ ሲልላቸው፡ "የሆነ ነገር ... ልነግራት ... ስጅምር ነው፡ ተበሳጭታ ... ሮጣ የወጣችው ... ምን ላደርግ እኔ ... አድሜዬን ወሶሉ፡ ተሸክሜው ኖርኩ። አሁን እኔ ከሞትኩ ደግሞ ማንም እውነቱን ሊነግራት አይችልም። የቀረኸኝ ተስፋ አንተ ብቻ ነህ ዶክተር ..." ብለው፣ ተንጠራርተው፡ ነራስጊያቸው ቦርሳቸውን አወጡ። "ይሄው ... እስኪ ... እንካ ..." አሉ፣ ሁለት የታሸጉ ፖስታዎች እየሰጡት።

"ምንድነው፡ እሱ መይዘር ኤደን...?"

"እየው ... ተጽፎበታል ... እንዱ የሷ ነው ... አንዱ ላንተ ነው .... ይሄን ሳልነግራት ያንገት፡ ብሞት ብዬ ነው፡ ያዘጋጀውት ... ከዚህ በኋላ ያለሃት ተስፋ አንተ ብቻ ነህ ... አደራ ብዬሃለሁ ዶክተርዬ ... ማንም የላትም ... ልጄን ..." አሉ እምባቸው እየፈሰሰ። በመሃል ስልካቸው ሲጮህ ከራስጌ ከመዳጣው ላይ አንስቶ አተበላቸው። ሰራተኛቸው ናት።

"ምንድነው ... ይሁና አይደለሽም እንዴ ... ኧረ ምን ሆነሻል? ... ፍትራ?"

@OLDBOOOKSPDF

"እትዬ ጉድ ሆንልዎ ... ሚስጥር ... ሚስጥር ... ወይኔ እናቴ ..." ስትል፣ ዝልፍልፍ ብለው ወደቁ። በድንጋጤ ተስፈንጥሮ ተነሳና ደግፎ አስተመጣቸው።

የወደቀውን ሰልክ እንስቶ "ሃሎ ..." ሲል፣ የልቅሶና የጩኸት ድምጽ ነው የተሰማው። ድምጹን ከፍ አድርጎ፣ "ምንድነው እሱ?"

"ሚስጥር ሚስጥር ..." ብላ፣ ለትሶዋን ቀጠለች። እንደምንም ካረጋጋት በኋላ ምስጢር መኝታ ቤቷ ገብታ መድሃኒት ወስዳ ራሷን ስታ ወለሉ ላይ ተዘርራ እንዳገኘቻት ነገረችው።

ድንጋጤውን እንደምንም ለመቀጣጠር እየሞከረ፣ "ሄሎ ... እስኪ አንዴ ... ረጋ በይና ስሚኝ ... ትተነፍሳለች?" አለ፣ ወይዘሮ ኤደንን ባንድ እጁ እንደደገፈ።

"እንሻ ... እንሻ ... አይመስለኝም ... አዎ ...እስኪ ቀይ ..." ብላ፣ ለትሶዋን ቀጠለች።

"ትሰሚኛለሽ? ... እኔ አሁኑኑ መጣሁ ... በኃኗ እስተኚያት ... እስክመጣ ድረስ ፈጽሞ እንትልፍ እንዳይወስዳት ... የፈለገውን አድርገሽ ቀስቅሺያት... ፊቷ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ... በረዶ አሁኑኑ አፍስሺባት ... ደግሞ እንዳትታፈን ... በቂ አየር እንድታገኝ መስኮቱን ከፈቱት ... መጣሁ እኔም ... መኪና ያለው ሰው የለም ጎረቤት ... አንዳችሁ ያገኛችሁትን ሰው ጥሩ ከጮረቤት ... መርሁህ ካለባችሁም ጩሁ ...ሰልኩን እንዳትዘጊው ..." ብሎ፣ በጩኸት አፉ ላይ የመጣውን ሁሉ ተበጣጠረ።

ሰልኩን እንደያዘ ነርሶቹን በጩኸት ተጣርቶ የሆነውን ባጭሩ ነገራቸው። ወይዘሮ ኤደንን ለነርሱ አስረክቦ በሩጫ ወደ ድንገተኛ ክፍል ሮጠ። ሁኔታውን በፍጥነት አስረዳቸው። አምቡላንስና የህክምና ቡድን ይዘው ወደ ሻክሮስ ገሰገሱ። ከኮሪያ ሆስፒታል እነ ምስጢር ቤት ለመድረስ ጊዜው ዓመት ሆኖ ረዘመበት። ጎረቤቶች ተሰብስበው ምን መደረግ እንዳለበት ሲጨቃጨቁ ደረሱ።

ትንፋሺና የልብ ምቷ መኖሩን ሲያዩ ተሯሩጠው ወደ መታጠቢያ ቤት ወሰዷት። ከነመዲናዋ ላይ ከወሰዶች በኋላ የተረፉትን ኪኒኖች አገኟቸው። ምን መድሃኒት መሆናቸውን አወቁ። እንድታስታውክ አድርገው የተወሰነው እንዲጣላት አደረጉ። አንቡላንሱ ውስጥ የሚሰካካውን ነገር ሰካክተው፣ በፍጥነት ድንገተኛ ክፍል ደረሱ። ቀስ በቀስ በራሷ መተንፈስ እያቃታት መጣ። መተንፈሻ መሳሪያ ላይ አድርገው ወደ አይሲዩ አስገቧት። እናቷም ያሉበት ሁኔታ በጽኑ ስለነበር ወደዚሁ ክፍል ተሸጋግረዋል። ከርሷ ባሻገር ካለው የአይሲዩ አልጋ ላይ ተኝተዋል።

ሰዉ ሁሉ ቀስ በቀስ እየተሰናበተ ወደ ቤቱ ሄደ። ዶክተር ሌላው፣ ሲስተር ዘቢባና ባለቤቷ እንዲሁም አዘስቷ ወይዘሮ ዘምዘም ከባለቤቱ ጋር ብቻ ቀሩ። እኔ ልደር እኔ ልደር በሚለው ሲከራከሩ ቀዩና በመጨረሻ አዘስቷ በማደሯ ተወሰነ። ሌላው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነበር ወደ ቤት ለመሄድ ከሆስፒታል የወጣው። ከመወጣቱ በፊት ተረኛ ዶክተሩን አናገረው። ሁለቱም ያሉበት ሁኔታ የከፋ መሆኑን እና በዚህ ጊዜ ምንም ለማለት እንደማይቻል ነገረው። በተለይ ምስጢር በሕይወትና በሞት መካከል

@OLDBOOOKSPDF

ውጣ ገባ እያለች ነው ። ስፔሺያሊስት ሃኪሙ ሁኔታዋ አስጊ መሆኑንና ብዙ ተስፋ ማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን ነግሮታል ። ሐኪም መሆኑን ስለነገራቸው ያለውን ነገር ሁሉ ሳይደብቁና ሳይቀንሱ ነው የነገሩት ።

ወደ ቤቱ እየተመለሰ አድርጎት የማያውቀውን ቴሌ መድሐኒዓለም ደጅ ላይ ቀሞ ረዘም ያለ ጸሎት አድርሶ በውድቅት ሌሊት ቤት ገባ ። ቤት ደርሶ ዘበኛው ሲከፍትለት ሰው ሁሉ ተኝቶ ፣ ቅዝቅዝ ያለው ሳሎን ጠበቀው ። ከምገብ ጠረጴዛው ላይ ተከዳድኖ የተቀመጠውን ምግብ አየት አደረገና አንድ ብርጭቆ ሻይ ቀዳና በረጅሙ ተነፈሰ ። ጸኑቱን አውልቆ ወንበሩ እናት ላይ ሰቀለና ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደ ። ፊቱን በቀዝቃዛ ውሃ ሲታጠብ ቀለል አለው ።

ሻይ ከቴርሙሱ ቀዳና ሶፋው ላይ ተቀምጦ አንድ ሁለት ጊዜ ፉት አለ ። ወዲያው የምስጢር እናት የሰጡት ደብዳቤ ትዝ አለው ። ወደ ውጪ ወጣና ከመኪናው ወረቀት ማስቀመጫ ላጥን ውስጥ አውጥቶ ብርዱ ቀንጠጥ ስላደርገው ሮጥ ብሎ ወደ ቤት ገባ ። የምስጢር ሥም የተጻፈበትን ጻጋስ ያለ ደብዳቤ ጠረጴዛው ላይ ጣል አደረገና የራሱን ለመክፈት ትንሽ አመነታ ። ረዘም ያለውን የመኪናውን ቁልፍ ተጠቅሞ ፖስታውን ከሜፋ ላይ ቀደደው ። አንድ በእጅ የተጻፈ ደብዳቤና ሌላ አርጌ የታሸገ ፖስታ ነበር በፖስታው ውስጥ ።

ከውጪ ያለውን ደብዳቤ ነጣጥሎ አየት አደረገው ። ከበታቹ ኤደን ይላል ። ረጋ ብሎ ማንበብ ጀመረ ።

'ዶክተር ሌላሠው

መቼም ይህንን ደብዳቤ የምጽፈው፣ በልቤ ቀብሬ የኖርኩትን ሚስጥር ሳልገልጽልህ ማን ያውቃል ጊዜ አግኝተን ሳናወራ ድንገት አንድ ነገር ብሆንስ ብዬ ሰለሰጋሁ ነው ። ውስጤን እየበላው ያለው ይህ ካንሰር መቼ ቁጻሜዬን እንደሚወስነው አላውቅም ። የስንት አመት ጸሎትና እምባዬ የተመለሰችባትን ያቺን ምሽት ግን ፈጽሞ አልረሳትም ። በቲሲቪሽን መስኮት ቀርበህ ስምህን፣ በራህንና ታሪክህን ስትናገር ራሴን ስቼ ልወድቅ ነበር ። አሁን ይሄንን እውነት ነው ቢባል ማን ያምናል? በል እንግዲህ አሁን የምነግርህን ልብ ብለህ ስማኝ ።

ነገሩ ትንሽ ግራ አጋብቶት ቀና አለና አይኖቹን አሻሸት ማንበቡን ቀጠለ ። የልቡ ምት ግን የተወሰነ ጨምሯል ።

የዛሬ ሃያ ስድስት አመት ግድም ገንደር ታምማ በጣር ላይ ያለች የእናቴን ብቸኛ እህት ልንጠይቅ ሄደን ነበር ። በባህሪዋ ሰው መሰብሰብ ትወዳለች ። መኪና ተራው ላይ ካፈ ነበራት እህቴ ። አንዲት አይነግቡ ቀንጅዬ ልጅ ማረፊያ አጥታ ስትንከራተት አግኝታት ቤቷ አስጠግታት ነበር ። ገና ካዲሳባ መምጣቷ ስለነበር ግራ ግብት ብሏት ነበር ። ካቅሚ በላይ በሆነ ሃዘን የተመታች ልጅ ነበረች ።

@OLDBOOOKSPDF

ድንግሙ ይብዛኪውን ላያስበው ጨበጥ አድርጉ ያዘው "ሊሆን አይችልም ..." አለና አሮጌውን ፖስታ ሊከፍት ብሎ ፈራ። ተመልሶ ይብዛኪውን ለማንበብ ሲሞክር እጁ እየተንቀጠቀጠ ተቸገረ። በረጅሙ ተንፍሶ ከመቀመጫው ተነስቶ "ሊሆን አይችልም ..." ብሎ እንደገና ተቀመጠ ...

ቤት ውስጥ የሚረዳኝ ሰው እየፈለግሁ ስለነበርና በጣም ስላሳዘንችኝ አናገርኳት። መጠጊያ ካገኘች ምንም ሰራ ቢሆን ሰመስራት ፈቃደኛ መሆኗን ስትነግረኝ ወደ አስመራ ይዣያት ተመለስኩ። ታሪኳን ሁሉ ስታጫውተኝ ልጅ ባይኖረኝም ልጄ መሰለችኝ። ነፍሰ ጡር መሆኗንም አልሸሸገችኝም ነበር። ባለቤቱ በነገሩ በደስታ ሰለተሰማማ ከኛው ጋር እየኖረች የማታ ትምህርት ቤት ገባች። መቼም እንደሷ ያለ ገበዝና ፈጣን የሆነች ልጅ አይቼም አላውቅም።

ልጇን ከወለደች በኋላ ቤታችን የበለጠ በደስታ ተሞላ። ልጇ እንደ ልጃችን ሆነች። ሕፃኗ ሁለት ዓመት እንደ ሞላት ግን ነገሮች ተለዋወጡ። ከፉ የሆነ የላምባ ነቀርሳ ተጠናወታት። የምንችለውን ብናደርግላትም ሕይወቷን ግን ልናተርፈው አልቻልነውም። አብራ ከፖስታው ውስጥ የከተትኩለሆን ይብዛቤ የጻፈችለሀ እሷ ናት። 'እንድ ቀን ታገኘዋለሽ ... ስታገኘው ስጪልኝ' ብላኝ ነበር። ያ እምነቷ አሁን ይዣመኛል።

"ይሄ ሊታመን አይችልም ... ሚስጥር ... ነት ... እሀ ፈጣሪ ምን አደረኩሀ ... እምላኪ ..." እያለ ፣ ላሎት ውስጥ ተንቀራጠጠ። ወደ ሆስፒታል በዚያው ቅጽበት ሊሄድ ፈለገ ... ደግሞ ግራ ገብቶት ይብዛቤውን አፍዋሮ አየው። የታሸገውን ፖስታ ለመክፈት ግን ብርታት አልነበረውም።

የልጇን ሁለተኛ ዓመት ባከበርን በሳምንት በሞት ስትለየኝ ጥልቅ ሃዘን ውስጥ ገባን። ቢሆንም ጥሳልን የሄደችው ልጇ የሃዘናችን መረሻ ሆነችን። ስሟን ያወጣችላት ግን እናቷ ናት።

የሚለውን ሲያነብ "ያንተ ያለህ ... ገኒ ..." ብሎ ሶፋው ላይ ተቀምጦ ማልቀስ ጀመረ። የመጨረሻ ያያት ቀን የነበረው ፊቷ መጣበት። እንባው ወረቀቱ ላይ እየተንጠባጠበ የቀረውን ለማንበብ ሞከረ።

ስለመለያቻት እናቷ ሳልነግራት ብሞት ከኩነኔ የምንጻ አልመስልሽ አለኝ። ይሄው የኔም ሞት ደጅ ያንኳኳ ጀምሯል። ላንተም ይሄንን ነገር ልነግርህ አስብና አትም አላለሁ። ሁሉንም ነገር የሚበጠብጠው ይመስለኝና ሰፈራ ሰቸር ይሄው ጊዜው ነገደ። ለእኔም ያለችኝ ብቸኛ ልጄና ሕይወቱ እሷው ስለሆነች ራስ መዳድንቱም ሳይጠናብኝ አልቀረም። እሷን ካጣሁ አንድ ቀንም የማድር አይመስለኝም። ልጅቱ እንደ ስሟ ሚስጥር ናት። ልጄን ለመለጸት አባቷ ከማስረከብ በላይ ምን መልካም ነገር አለ።

ይዝተራ ሚስጥር የነንትም የኔም ልጅ ናት። መቼም እንደምታውቀው

@OLDBOOOKSPDF

መዝገቡ ጥሩ አባት አልነበረም። ብዙ ስቃይና ጠባሳ በህይወቷ ላይ አኑሯል። አንተ ግን ለርቢ ጥሩና የህመሟ ፈውስ የምትሆን አባት እንደምትሆን አውቃለሁ። እሷም ላንተ ያላት ጥልቅ ፍቅር አባቷ መሆንህን ስታውቅ ምን ሊሆን እንደሚችል አይቼ ብሞት ምኞቴ ነበር። የሷኑ እናት ፍለጋም እንደመጣህ ስትነግረኝ ... ሕይወት መልሷን እጅህ ውስጥ ሰውራ ጎዳና ለገዳና የምታንከራትት ጨካኝ ሚስጥር መሆኗን ነው የተረዳሁት። ዝንትም የጻፈችልህ ደብዳቤ እዚሁ ፖስታ ውስጥ አስቀምጬልሃለሁ። ሁለቱን ፎቶዎች ዝንት ላንተ እንዳደርስ በአደራ የሰጠችኝ ነው።"

የፎቶዎቹን ነገር ሲያስብ ተጣድፎ እሮጌውን ፖስታ ቀደደው። ከውስጡ ሁለት ፎቶዎች ወደቁ። ብድግ አድርጎ ሲያያቸው ዝንት የልጇን ሁለተኛ አመት ስታከብር የተነሱትና ከርሱ ጋር ለመጨረሻ የተነሱት ፎቶዎች ናቸው። ደብዳቤውን ሲያየው የሚያውቀው የዝንት እጅ ጽሁፍ ነው። 'ያንተው ገኒት' ይላል መጨረሻው። ስሜቱ ተደበላልቆበት ሊያነበው አልቻለም። ሰው በሌለበት እዬዬ ብሎ አለቀሰ። ፎቶዎቹን አገላብጦ ሳማቸው። የምስጢር ሕይወት በቀሚን ከር ላይ ተንጠልጥላ እንዳለች ትገ ሊለው "ያንተ ያለህ ... አባክህ ፈጣሪ ..." ብሎ ተንበረከከ። በሕይወት የሚያገኛትም አልመሰለውም። ስልኩን ሲያየው ባለመደወሉ ደስ አለው። ወዲያው ተነሳና ጃኬቱን ደርቦ እየተጣደፈ ወጣ። በሩን እንዲከፍትለት ዘበኛውን ሲቀሰቅሰው ደንግጦ አይኖቹን እያሻሸ ወጣ።

ጋቢውን ከትከሻው ወደ ራሱ ከፍ አድርጎ እየተከናነበ፣ "ምነው ዶክተር ... ችግር አለ እንዴ?" አለው።

"ደህና ደህና ... የታመመ ሰው ስላለ ሆስፒታል መሄድ አለብኝ። ባክህ ... ቶሎ ዘፈትልኝ ... አስቸኳይ ነው። ጠዋት ነው የምመለሰው ...እሺ ... ቤቱን በደንብ ነቃ ብለህ ጠብቅ ... ንገራቸው እሺ" ብሎት፣ መልሱንም ሳይጠብቅ መኪናው ውስጥ ገብቶ አስነሳው። በሩን እንደከፈተለት ወደ ሆስፒታል ተፈተለከ። ከሴሊቱ ስምንት ሰአት ከስላሳ ስምንት ደቂቃ ይላል የመኪናው ሠዓት ... ተገዘገዘ ሴሊት ... ያዲሳባ መንገዶች ጭር ብለው ከተማ ውስጥ ሰውም ያለ አይመስልም። መንገዱን ሁሉ እምባውን እያዘራና ለብቻው እያወራ በምን ፍጥነት እንደ ደረሰ ሳያውቀው መኪናውን እቁም እንደ 'እብድ' ወደ አይሲዩ ሮጠ።

@OLDBOOOKSPDF

45

'ያላጡት ነጻነት በነጻ የተገኘ ይመስላል። ሴላው ቀርቶ ልብ በፈቀደ ጊዜ እሪ ብሎ ለመጮህና ብድግ ብሎ ለመሮጥ እንኳ የሚቻለው ነጻነት ሲኖር ነው። እሺና እምቢ ማለት ትርጉምና ፋይዳ የሚኖረው ነጻነት ባለበት ብቻ ነው። የቀዘቀዘን ውሃ በዶረቀ ጉሮሮ ላይ ድርግም አድርገው ቢችልቡት ... ማለዳ ወፍ ሲንጫጫ ተነስቶ የፀሐይን አወጣጥ በአርምሞ ቢመለከቱ ...ውበትና ርካታው በነጻነት ሀልውና ውስጥ ነው። ወሀኒ የወረደና ታሞ ካልጋ የተቀራኘ ሰው የነጻነትን ጣእምና ዋጋ ከማንም በላይ ይረዳል። ሰውነት ያለ ጤና ... ነፍስ ያለ ነጻነት ... ዓይን ያለ ብርሃን እንደ ማለት ነው።' ይህ ሁሉ ለሳንቾ በጥልቅ የገባው ከታሰረ ወዲህ ነው።

ሕይወቱ በእውነት ከር ላይ ተንጠልጥላ፣ በይደር ቀጠሮ በትውዛወዝ ነጋ ጠባ ራሱን በተስፋ ለማቀየት ይታገላል። የምስጢርንና የእናቷን ሁኔታ ከሰማ በኋላ ደግሞ ነፍሱ በሀዘን ደቅቃለች። ያከሰቱ ልጆች ጉዳይ ቢጨንቀውም፣ የመኖር ምክንያቶቹ ሆነው ሊያበባቸው ይጽናናል። ከብዙ ትግልና ፈተና በኋላ፣ ቀና ሬቷን ያዞረችለት ሕይወት፣ ተመልሳ ያከረፈችው ... የከፋችበት መሰለው። በእስር ቤቱ ውስጥ ከሰው ሁሉ ራሱን አግልሎ መተከዝ ሆኗል ሥራው።

የሴላሠው ሕይወት ማቀሚያ የሌለው አዙሪት ሆኗል። እንደ ምንም ብሎ በሳምንት አንድ ጊዜም ቢሆን ከልጆቹ ጋር በስልክ ያወራል። ከንጹሕ ጋር ላይ ላዩን ቢሆንም ይነጋገራሉ። ሲራክ የሚሆነውን ሁሉ በራሱ ቅመም አጣፍጦ በስልክና በኢሜይል ስለሚነግራት፣ እየሆነ ካለው እንድም ያመለጣት ነገር የለም። ከሴላሠው ጋር ስታወራ ግን ምንም እንደማታውቅ ሆና ነው። ልጆቹ እንደ በራቱ ካልመጣህ እያሉ ስለማያለቅሱበት ከናፍቀቱ ውጪ ትንሽ ሩታ አግኝቷል።

ምስጢርና እናቷ ሆስፒታል ከገቡ አምስት ቀን ሆኖቸው። ምስጢር አውንም አቅሏን እንደሳተች በጥልቅ ኮማ ውስጥ ናት። የእናቷ ጉዳይ በየቀኑ እየባሰ ስለ መጣ፣ በማንኛውም ሰዓት ሊያርፉ እንደሚችሉ ሃኪሞቹ ለቤተሰብ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ

@OLDBOOOKSPDF

ሰናተዋል ። የኩላሊትና ጉበት ሁኔታቸው ሊመለስ ወደ ማይችልበት ዶረጃ ስለደረሰ ሁሉንም ነገር አወላስቦታል ። በላምባቸው ውስጥ ቶሎ ቶሎ የሚሞላውን ውሃ መቅዳቱ አሪታች ሆኗል ።

ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ወይዘሮ ዘምዘምና ሌላሠው ተራ ገብተው ቀንና ማታ ደሚ አስታማሚ ሆነዋል ። ሌላሠው በጽሚነት ማታውንና ሌሊቱን ሁሉ ሆስፒታል ነው የሚያሳልፈው ። ቀን ላይ በተለያዩ ጉዳዮች ተጠምዶ ስለሚውል ፣ ክሊኒክ መግባቱን ከናካቴው ባይባልም ትቶታል ። ነገር ዓለሙን ትቶ የምስጢርና የእናቷ የሙሉ ጊዜ አስታማሚ መሆን ለሁሉም ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ሆኗል ። በተለይ ለሲራክ ነገሩ እንቆቅልሽና እረፍት የነሳው ጉዳይ ሆኖበታል ።

ሌላሠው ረፋዱ ላይ ከሆስፒታሉ ካፌ ደጅ ትቀምጦ ቡናውን ፉት እያለ የሰሞኑን ጋዜጣ ሲያገላብጥ ቀየ ። አልፎ አልፎ ቀዝቀዝ ያለው ንፋስ ሽው ሲል በዐሐይዋ ያጋለውን ሰውነቱን በረድ ሲያደርግለት ደስ የሚል ስሜት ፈጥሮለታል ። ከዐሐይዋ ጨረር ራቅን ለመሸፈን ተከልሎ ስለነበር ፣ እጠገቡ መጥታ የቀመችውን ወጣት አላያትም ።

ጉሮሮዋን እንደመጠራረግ ብላ ፣ "ይቅርታ .... ዶክተር ሌላሠው ...?" ስትል ፣ ደንገጥ አለ ።

"ልክነው ... ይቅርታ ... አላየሁሽም ነበር እኮ ..." ግራ በገባው ፊት ፈገግ ብሎ ሽቅብ አያት ። ቀጥሎ የምትለውን እየጠበቀ ወንበሩን አስተካከለ ።

እጇን ለሰላምታ እየዘረጋች ፣ "ውዳሴ እባላለሁ ..." ብላ ለክሊኒካቸው ጥብቅና ከቀመላቸው ቢሮ እንደመጣችና የነሱን ኬዝ በዋናነት እንድትከታተል የተመደበችው ጠበቃ እሷ መሆኗን ነገረችው ። ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ሰላምታ ተለዋውጡና ወንበር አቅርቦላት ከፊቱ ተቀመጠች ። ካሰበው በላይ ወጣት ስለነበረች ፣ የነርሱን ክስ ለመከታተልና ለመወከል ብቃቷ አጠራጠረው ።

"ክሊኒክ እንድ ሁለት ጊዜ ሄጄ ነበር ... በጓላ ሲስተር ... ዘቢባ ነው ስሟ? ... እሷ ናት እዚህ ብመጣ ላገኝህ እንደምችልና እሷም እንደምትደውልልህ የነገረችኝ"

"ኦህ ... ልክ ነው ... እዚህ እንድ የክሊኒካችን ስታፍ የሆነች ልጅና እናቷ ... ሁለቱም በከፍተኛ ዶረጃ ታመው አይ ሲ ዩ ነው ያሉት ... ብዙ ጊዜ እዚህ እሆናለሁ ። ቢሮ መጥተሽ እንደ ነበር ... ሲስተር ነግራኝ ነበር ። ይቅርታ እዚህ ድረስ አደከምኩሽ ። " የምታወቀውንና የማታውቀውን ነገር እርግጠኛ ስላልሆነ ጥያቄው ከርሷው ይምጣ ብሎ አሰበ ።

"አይ ምንም አይደለም ... ይገባኛል ። እንዳልኩህ ውዳሴ እባላለሁ ። አዝናለሁ ከሲኒካችሁ ላይ ስለተፈጠረው ውጣ ውረድ" ብላ ፣ ራሷን ካስተዋወቀችው በጓላ በእስከ አሁኑ ምርመራና የፋይል ጥናት የደረሰችበትን ነገር ባጭሩ ነገረችው ። የምትሰራውን የምታውቅና ካሰበው በላይ ብስለትና መረጃት ያላት መስላ ታየችው ።

ቢሮው ውስጥ ብዙ ጊዜ ብዙ የማይታዩ ፣ የተዘበራረቁና የተወሳሰቡ ኬዞች ሲመጡ ፣ ባለቤቱ ስርሷ ይሰጡና ራሳቸው በቅርብ ይከታተላሉ ። እጇ ላይ ብዙ ክሶች

@OLDBOOOKSPDF

ስላሉ፣ ይሄኛው ክስ ለሌላ ጓደኛዋ ነበር የተሰጠው። እንድታገዘው ጠይቋት ፋይሉን እያየች ሲመካከሩ፣ የሊራክን ስምና እሱ የሚሰራበት ክሊኒክ መሆኑን በታውቅ ራሷ ወስዳ ልትሰራው ፈልጋ ነበር። ኬሆን የያዘው ልጅ በቤተሰብ ችግር ምክንያት ወደ ክፍለ ሀገር ሲሄድ ሙሉ ሃላፊነቱ ለርሷ ተሰጣት። ጓደኛዋ ሲመለስ ነገሩ ከትከሻው ላይ ወርዶ ስለጠበቀው ደስ ብሎት፣ 'ለበላተኛ በራ ጥድ ያገለታል' ብሎ ቀለደባት። የሆዷን በሆዷ ይዛ ሰቃ፣ ፋይሉን በደስታ ወሰዶችው።

የቀድሞ ፋይሉን ከላንቾ ጠበቀች ተረክበው ነገሩን ከሰሩ ለመመርመር እየሞከረች እንዳለች ነገረችው። "ሲስተር ዘቢባንና ሌሎች ማስረሻ በሞተ ቀን የነበሩ ሰዎችን ሁሉ እናግራ የምፈልገውን ብዙ መረጃዎች አግኝቻለሁ። በጊዜው እንዳልነበርክ እውቃለሁ ግን የምትነግረኝ ነገር ካለ ..." ብላ በደፈናው ጠየቀችው። በጊዜው ባለመኖሩም ስለ ክስተቱ ያለው እውቀት ውሱን መሆኑን ነገራት። የሰማቸውን ነገሮችና ስለ ማስረሻም የሚያውቀውን ያህል አስረዳት።

"ቀይ ዶክተር ... ማስረሻ ስለ ራሱም ሆነ ሌላ ላንተ የነገረህን ነገር ዝርዝር እንተ የነገረከው ሰው አለ?"

"ኖ ... ኖ ... በፍጹም እንደሱ እድርጌ አላውቅም " አለ ቁርጥ ባለ ድምፅ ርግጠኛ ሆኖ ።

"ከዶክተር ሲራክ ጋር ብዙ ጊዜ ይገናኙ ነበር?"

"ኖ ... እኔ እስከማውቅ ድረስ ... አንድ ጊዜ ብቻ ነው ... እሱም እኔ አሜሪካን አገር ስለነበርኩ ... ክሊኒኩን በጥብቦ ...ራሴን አጠፋለሁ ምንምን ሲል ነው እንዲያየው የተደረገው ... ሲስተር ሁሉንም ነገር ስለምታውቅና ሁልጊዜም ስላለች ከኔ ይልቅ እሷ ታውቃለች" አለ፣ ፊቱ ግራ እንደገባው።

"ጠይቂያት ... እሷም እንደዘመው ነው ያለችኝ ... ሌላስ ስለ ማስረሻ ዝርዝር የሚያውቅ ሰው አለ?" ከቦርሳዋ ውስጥ የጀመረችውን ወሃ እውጥታ ተገነጨች።

"እንግዲህ ... ምስጢር ናት ... የምታውቀውን ከነገረችም ለላንቾ ነው" ብሎ፣ ጋዜጣውን ጠቅሎ ጠረጴዛው ላይ ወርወር አደረገው።

"አቶ ሰኢድ ማለት ነው?" ስትል በአምንታ ራሱን ነቀነቀ። "ሲስተር ዘቢባም እንደሱ ነው ያለችኝ። አንተ ከዋናው ቻርት ተጨማሪ ለምትከታተላቸው ደንበኞችህ የምትይዘው ተጨማሪ የተለየ ፋይል አለህ?" ስትለው አሰብ አድርጎ፣

"በጣም ለተወሰኑት ... ከዛ ውስጥ ማስረሻም ይገኝበታል" አለ። አሁንም የጥያቄዋ አቅጣጫ ሊገባው አልቻለም።

"እሱን ማየት እችላለሁ? ... ካንተ ሌላ እንዘህን የግል ፋይሎች ማየት የሚችል ሰው አለ?"

"ያ ... ቢሮዬ ናቸው ያሉት። እስኪ የሚለጥር አዘዘት አሁን ትመጣለች ... እሷ ስትተካልኝ .... [illegible] ያቸው ትችያለሽ። ሁልጊዜ

ስለሚቀለፍባቸው ከኔ በቀር ማንም ሊያያቸው አይችልም" የሚሉኸውን ስልክ ከኪሱ አውጥቶ ሲያይ ወይዘሮ ዘምዘም ናት ። ይቅርታ ጠይቆ ሲያነሳው መድረሷን ነገረችው ። "እንዲየውም እሷ ናት ... መድረሷን ነው የነገረችኝ ... እንሂድ?" ወደ ሆስፒታሉ ውስጥ እያመሩ ገቡ ። "ዶክተር ሲራክንስ አገኘሽው?"

"ይችን ሶስት ቀን ረፍት ላይ ነው ብላናለች ሲስተር ..." አለችና ትንሽ እመንትታ "ከርሱ ጋር ያለፈ ግዴኝነት ስለነበረን ... እሱን ማናገሩን ... ባልደረባዬ ነው የሚከታተለው" አለች ።

"ኦህ ... ዓለም ጠባብ ናት ...ነው የሚሉት ። የምታውቂውን ሰው የት እንደትምታገኚው መገመት አትችይም" አለ ሳቅ ብሎ ። ከወይዘሮ ዘምዘም ጋር ትንሽ አውርተው ... የሚስጥር እናት ጉዳይ በጽፍ ስለሆነ ... ችግር ካለ ደውዪልኝ ብሏት ፣ ከውጻቤ ጋር ተያይዘው ወጡ ።

"ቤተሰብስ ... ባለቤትህም ልጆችህም አሜሪካን መሆናቸውን ሰማሁ ። ዐቢም በጣም ከባድ ነው ... ቤተሰብ እዛ ትቶ እዚህ ምኖር" አለች ፣ ጊዜውን ለመጠቀም ወደ እርሱ መኪና ገብተው ወደ ክሊኒኩ ሲያመሩ ።

"በጣም ከባድ ነው ... በጣም ... ግን ምን ታደርጊዋለሽ" ብሎ ትንሽ ጸጥ አሉ ። ቢሮ እስኪደርሱ ድረስ ስለ እርሱም ሆነ ስለቤተሰቡ ማወቅ ያለባትን ዋና ዋና ነገሮች ነገራት ። የሚጠጣ ነገር አገዘላት ፣ ተቀምጠው የቢሮውን ማማር እያደነቀች ትንሽ ተቀላለዱ ። ፋይሎቹን ሊያመጣላት ወደ ዴስኩ ሄደ ። ፋይሎቹን አውጥቶ አንድ ባንድ እያገላበጠ እያቸው ። የምስጢር ፋይል ጋ ሲደርስ ከፍቶ ገጾቹን እየገላለጠ ሲያይ አንድ ፎቶ ኮፒ የሆነ ገጽ ላይ ሲደርስ ቀም አለ ። ሌሎቹን ፋይሎች ሲያገላብጥ ምንም የተለየ ነገር አላገኘም ። የማስረሻን ፋይል ከፍቶ ሲያገላብጥ ሁለት ገጾች ተዟዙረው ተፈርጀዋል ።

የማስረሻን ፋይል እየለጣት "እንግዲህ ... ይሄ ነው የግል ፋይል ያልኩሽ ... እዚህ ውስጥ ብዙ በጣም ቢመጡ ሊገዱ የሚችሉ የርሱ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ሰዎችም ሚስጥሮች ስላሉ ... በዋናው ፋይል ላይ አልጽፋቸውም ። ከፈለግሽ ኮፒም እድርገን ልንሰጥሽ እንችላለን" ብሎ ከፊት ለፊቷ ተቀመጠ ።

"በጣም እስቸጋሪ ሥራ ነው ... ሚስጥርና ህመም የተቀላቀለበት ስራ ... ከኛ ጋር ይመላለሳል ... የኛ ደግሞ ወንጀልና ሚስጥር ሆነ እንጂ ..." ብላ ሳቅ ስትል አጠቃላይ ብስለቷና ነገሮችን የምትመለከትበት ደረጃ መተማመኑን ጨመረው ። 'ከሲራክ ጋር መቼና እንዴት ነው የምትተዋወቁት?' ሊላት አስቦ አስፈላጊ አለመሆኑን ተገንዝቦ ተወው ። "ግን ምን ያህል ርግጠኛ ነህ ... ይሄ ፋይል ካንተ በቀር ማንም እንዳላየው?" አለች የሆነ ገጽ ላይ ስትደርስ ቀም ብላ ።

"በጣም ርግጠኛ ነበርኩ ... ዩ ኖው ... አሁን ላንቺ ፋይሉን ላመጣልሽ ሳገላብጥ ... አንዳንድ ለውጦችን አየሁ ..." ሲል ካቆ ቀበል አድርጋ ፣

"እዚህኛውም ፋይል ላይ ተዛንፈው የተቀመጡ ገጾች አሉ" ስትለው የማጤን አትሚን አድንቆ ነገሩን እሱም እንደየዉ ነገራት ። በሌላኛው ፋይል ውስጥ

@OLDBOOOKSPDF

የተጨመረውን ፎቶ ኮፒ የተደረገ ገጽ አሳያት። ጉዳዩን በሰፊው ካወሩበት በኋላ የምትፈልጋቸውን ፋይሎች ኮፒ እድርገላት ወሰደች። እሷ ከሄደች በኋላ ፋይሎቹን ሁሉ እንደገና በጥንቃቄ አገላብጦ እያቸው። ቁልፎቹን አሜሪካ ሲሄድ ረስቶ ይሂድ እይሂድ ትዝ ሊለው አልቻለም። ነገሩን ጊዜ ወስዶ ባሰበው ቁጥር ሁሉም ነገር የተወሰነ ትርጉም እየሰጠው መጣ።

አንዳንድ ወረቀቶችን ሲፈራርምና ወደኋላ የቀሩ ነገሮችን ሲያስተካክል ቀየ። ለምሳ ከሲስተር ዘቢባ ወደ ካፈያቸው ሄደው እንደ ተቀመጡ፣ "ዶክተርዬ ... ምንድነው የመጣብን ጉድ ... ሁሉም ነገር እኮ እያየነው እየተፈረካከሰ ነው። አሁንማ ቀጥሎ ደግሞ ምን ሊሆን ነው ብዬ ቀንና ሌሊት በፍርሃት ተወጥሬ ልሞት ነው። እንዴት ናት ያቺ ሚስጥር?" ብላ፣ ጭንቅላቷን አወዛወዘች።

"እኔም ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ምንም ነገር አልቋረጠም ሲስተርዬ ... ያው ብዙም ለውጥ የላትም ... ሃኪሞቹም በዚህ ደረጃ ምን ልትሆን እንደምትችል መገመት አንችልም ነው የሚሉት። አሁን ትልቁ ስጋት ... እናቷ ኤኒ ታይም ሊሞቱ እንደሚችሉ ነው ጠዋት ዶክተሩ ያነገረኝ" ብሎ፣ ምግብ የቀማመሰበትን እጁን በናፕኪኑ እየጠራረገ ዝም አለ።

እሷም "እንዲያው ምኑን ዘራ ቀን አመጣባቸው ... የኔናት!" አለች። ቡናዋን እንድ ሁለቴ ፉት ብላ አይን ዓይኑን እያየች፣ "እዲሷን ጠበቃ አገኘሃት ... ትንሽ ልጅ መስላኝ ነበር። ግን የምትሰራውን በደንብ የምታውቅ መስለችኝ። ስትለው፣ ስሜቱን መጋራቷ ደስ አለው።

"እኔም እንደዛው ነበር የተሰማኝ። ሳናገራት ግን ገበዝ ልጅ ትመስላለች። እንዳለችኝ ከሆነ ሰዎቹ ከሊኒኩን ለመክሰስ ብዙ ጠንካራ ምክንያት አላቸው። የኛ ሀመም ተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ አደጋውም የደረሰው ከኛው ሰታፎች ጋር በተፈጠረ ግጭት ስለሆነ ጠንካራ መከላከያ ነጥብ ከሌለን ዘሱ ከባድ ነው የሚሆነው ባይ ናት።"

"ደግሞ የልጁም ዘመዶች የዋዛ አይደሉም ... ብዙ ንክኪ እስከ ላይ ድረስ አላቸው አሉ" አለች፣ ጣቷን ወደ ጣሪው እየጠቆመች።

"እኔ እውነት ከሁሉ ትበልጣለች ብዬ ነው የማምነው። ሌላ ጉልበት የለንም። እስከ አሁን ከሆነው የባሰ ሊሆን የሚችል ነገር የለም። እድሜ ይስጠን እናያለን።" ሰዓቱን ሲመለከት ሰምንት ሰአት ሊሆን ምንም አልቀረውም። ከካፌ ወጥተው ወደ ቢሮ እየሄዱ፣ ከሆስፒታል ወይዘሮ ዘምዘም ደወለች። የምስጢር እናት ማረፋቸውን እያለቀሰች ነገረችው። ነገሩን ለሲስተር ዘቢባ ነግሯት ተያይዘው ወደ እዛው አቀኑ።

@OLDBOOOKSPDF

፡46፡

ጊዜው እመሻሹ ላይ ሲሆን የምስጢር እናት ከተቀበሩ ሁለተኛ ቀናቸው ነው። ለላመው ሆስፒታል ነው የዋለው። ምስጢር ከተኛችበት ክፍል ፊት ለፊት ኮሪደሩ ላይ ወንበሩን አውጥቶ ተቀመጠ። ወጪ ወራጁን በትዝብት እያየ በየመሃሉ ወይዘሮ እደን የሰጡትን ደብዳቤ እንደ አዲስ ደጋግሞ ያነበዋል። ደግሞ ተነስቶ ወዲያ ወዲህ ይመላለስና በመስኮቱ አንጻር እያየ ይተክዛል። ለእንድሳምንት ያህል ያላየው ሲራክ ድንገት መጣ። ሙሉ ልብስ አድርጎ ዘንክትክት ብሎ ዘንጪል።

ሰላምታ ተለዋውጠው በመስኮቱ አንጻር ደጅ ደጁን እያዩ ቀሙ። የሰፈነውን ዝምታ ለመስበር "ከከተማ ውጪ ነበርኩ ... የሚስጥር እናት መሞታቸውን ሰምቼ ቤት ደርሼ መምጣቴ ነው" አለ ሲራክ።

"እኔም ሲስተርም ብዙ ሞክረን ነበር ... ስልክህ ሊገባልን አልቻለም" ብሎ፣ አተኩሮ እየው።

"አዎን ...ባጣም መጥፎ ጄት ወርክ ነበር ... አውንማ ካዲሳባ ወጣ ካልክ ኔት-ወርኩ ተቀይሮ ኖት ወርክ ነው አሉ ..." ብሎ ሳቅ አለ። ከዚህ በፊት የሰማው ቀልድ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ውስጡ ለሳቅ ምንም ፍላጎት ስላልነበረው ዝም አለ። የጸጥታው ክብደት ስለከብደው ለወሬው ያህል፣ "ሚስጥር ግን እንዴት ናት ... ምንም የመሻል ምልክት የለም?" አለ።

"ትንሽ አለ ይመስገነው ... ከጠዋት ጀምሮ በራሷ መተንፈስና ሀመም ሲሰማት በጣም በከፉሉ አይኖቿን መግለጥ ጀምራለች ... አሁም አንድ ተስፋ ነው" ብሎ ወደ ውስጥ ገብተው ምስጢርን አየት አደረጓት። ሌላ ወንበር ጨምረው ወጥተው ተቀመጡ። ጥቂት አወሩና ደግሞ ጸጥ ብለው ቀሩ።

"እኔ ግን ዶክተር ሌላ ... ብዙ የሚያላስቡኝና የሚያስጨንቁኝ ነገሮች አሉ። አንተ ምን እንደምታስብ አላውቅም። ላንቺ እስር ቤት እየማቀቀ ነው ... ሚስጥር

@OLDBOOKSPDF

እዚህ በሞትና በህይወት መካከል ተንገላድገዳስች ... እም ... ክሊኒኩም ባንድ በኩል ትልቅ ክስ ይጠብቀዋል ...ኦልሞስት ስራውም ቀሞ ሊዘጋ ነው። ሚዲያው ሁሉ ይወርድብናል። አንተ ደግሞ ቀንና ሌሊት እዚህ ሆስፒታል ሆኗል ኑሮህ። እኔ ካንተ ጋር መስራት ስመስን የነበረኝ እይታና አሁን የማየው ነገር ምንም አልተጣጣመልኝም። ምን እያሰብክ ነው?" ብሎ፣ መልሱን በመጠበቅ ፊት ለፊት አፈጠጠበት። የነገሩ እውነትነት በግልጽ ቢታየውም በሲራክ አጠያየቅ ተገርሞ ፈገግ ብሎ አየው። ነገሩ የንቀት ስለመሰለው ሲራክን አናዶታል።

"ልክነህ ዶክተር ሲራክ ...ሁሉም ነገር ከቁጥጥር ውጪ የወጣነው የሚመስለው። አንተ ያልከው ብቻ ሳይሆን የራሴ ቤተሰብም ከዚህ ባልተናነሰ ቀውስ ውስጥ መሆኑንም ሳታውቅ የምትቀር አይመስለኝም። አንተ ከምታስበውና ከምታወቀው በላይ ነው ውስጤን እያስቃየኝ ያለው። በእሁኑ ሰዓት ግን እውነቱን ንገረኝ ካልከኝ ... ለኔ አንደኛና ዋነኛ ነገር የተደረገው ሁሉ ተድርገ የምስጢርን ህይወት ማትረፍ ነው። ሌላው ሁሉ ይደርሳል ... ቢጠፋም ይተካል" ብሎ፣ አይን አይኑን ሲያየው የሲራክ ስሜት የበለጠ ጋለ።

"ለምን? ... ቀይ ሚስጥር ምንህ ናት? ይሄ የኔ ብቻ ሳይሆን እኮ የሁሉም የክሊኒኩ ሰራተኛ ጥያቄ ነው። ቀይ ከሊኒኩን የጀመርክበት ምክንያቱ ሚስጥር ናት ማለት ነው? ቤተሰብህ እዛ ተበትኖ ... ክሊኒኩ ሊወድቅ አንድ ሃምሳ ቀርቶት ... ቀይ ሚስጥር ሚስጥር ማለት ... ትርጉሙ ምንድነው? ...የማናውቀው ሚስጥር ካለ ደግሞ ንገረን። ሁሉም ሰው ግራ የሚያጋባ መቀራረብ እንደነበራችሁ ሁላችንም እናውቃለን ..." አለ፣ ከወንበሩ ተነስቶ። መስመሩን እንደለቀቀና የሐሳብ የበላይነቱን እንደተነጠቀ ዘግይቶ ገባው።

"ሲራክ የምታወራውን እያሰብክ ነው? ... አንድ ነገር ልንገርህ ... አንተ ሊገቡህ የማይችሉ ብዙ የሕይወት እውነታዎች አሉ ... በጣም ጎበዝና ትልቅ ቦታ መድረስ የምትችል ልጅ ነህ ... ገና ግን ረጅም መንገድ መሄድ አለብህ። አሁን ለእኔ የሚታዩኝ ነገሮች ከተወሰኑ አመታት በኋላ ላንተም ይታዩሃል ... አሁን ግን በእድሜም በጭንቅላትም ልጅ ነህ" ሲለው፣ እንደገና ስሜቱ ቱግ አለ። ቢችል ወንበሩን አንስቶ ቢጭንበት ደስ ባለው ነበር።

"ዶክተር ሌላ ... ችግርህ እኮ አንተ ራስህን ሰማይ ላይ መስቀልህ ነው። አንተ ከምታውቀው በላይ ስላንተና ስለትንሿ ክሊኒክህ ፕሮጀክት እውቃለሁ። ይሄንን ክሊኒክ ተብዬ ስንጀምር፣ አሁን ስላንተ የማውቀውን ያህል ባውቅ ኖሮ፣ እንኳን አብሬህ ልሰራና ይሄ ክሊኒክ ብለህ የከፈትከው ድራማ አይከፈትም ነበር። እስኪ ንገረኝ ... ምንድነው ላንተ የሚታይህ ... ለኛ ግን የማይታየን። እንዳንተ አይነት 'ዴሉድድ የሆነ ናርሲስቲክ ሚጋሎማኒክ' ሰው አይቼም አላውቅም ..." ብሎ፣ ለፍልሚያ የተዘጋጀ መስሎ ተጠጋው።

"ብዙ ነገር የምታውቅ እንደሚመስልህም አውቃለሁ ሲራክ ... አንድ ቀን ምን ያህል እንደማታውቅ ሲገባህ ... ያኔ እናወራለን። ምክንያቱም እስከዚያ ድረስ

@OLDBOOOKSPDF

ለማወቅ ያልተዘጋጀህ እንጭጭ ልጅ ስለሆንክ ምንም ማድረግ አይቻልም። ስልጅ ደግሞ ልትነግረው የምትችለው ስለትናንሽ አሻንጉሊቶችና ብስኩት ከረሜላ ካልሆነ ልትነግረው የምትችለው በጣም የተወሰነ ነገር ነው" አለው፣ እንደ ተቀመጠ የሲራክ ንግግሮች ብስጭት እያደረጉት ስለሆነ ውስጡ ያለው ንዴት ቢያልፍልኝ ብሎ።

"የፈለከውን ማለት ትችላለህ ... እኔ ግን እርግጠኛ ሆኜ የማውቀውን ልንገርህ ... ልክ እንደ በምህ አንት ሌላ ... ነኝ ብለህ የምታስበው ሌላ ... ሰዎችህ ብለው ከበው የሚያስቡት ማንነትህ ሌላ ... በታ ሌላ ለው ነህ ... የሚያሳገኙኝ እዛ መከራቸውን የሚያዩት ጉድን ያላየች ምስኪን ሚስትህና የዋህ አንድ ፍሬ ልጆችህ ናቸው ..." ሲል፣ ሊቆጣጠረው የማይችል ንዴት ከውስጡ ፈንቅሎ ገነፈለ። ከመቀመጫው ተስፈንጥሮ ተነሳና የሸሚዙን ኮሌታ ከነከረባቱ ጨምድዶ ብድግ አደርጎ ከመስኮቱ ጋር አጣብቆ አንጠለጠለው።

"ትሰማኛለህ? ... አሁን አንድ ቃል ሳይወጣህ ... ጸጥ ብለህ ከዚህ ውጣ። አለበለዚያ ግን በዚህ መስኮት ነው እንደ ወረቀት ነው ጨምድጄ የምጥልህ። ከልጅ ሙሣወት ድርም ይሄው ነው። ... ከዚህ ወጥተህ የፈለከውን ማለትና ማድረግ ትችላለህ ... ሰምተኸኛል አይደል?" ብሎ፣ ከግድግዳው ጋር ጥብቅ አድርጎ ከያዘው በኋላ ግራና ቀኝ ወዝውዞ ለቀቀው። አንዲት ቃል ሳይወጣው ከላይ ላይ እየተንፈሰ ተንገዳግዶ ቆመ። የተጨማደደ ልብሱን እያስተካከለ ትንፋሹን ከሰበሰበ በኋላ የበለጠ ወደ ኋላ አፈግፍገ የቻለውን ያህል ካጠገቡ ራቀ።

"ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሁላችንም ማንነት ይገለጣል ..." ብሎ፣ እየተመራጨና በንዴት እየተንቀጠቀጠ ጥሎት ሄደ። ይሄ ሁሉ ሲሆን በኮሪደሩ ላይ ማንም ሰላልነበረ ከሁለቱ አልፎ የወጣ ረብሻ አልተፈጠረም። በቀጥታ ወደ ቤቱ ሄዶ ፎቶ ኮፒ አድርጎ ያስቀመጣቸውን መረቃዎች እያገላበጠ ሲያስተካክል አመሸ። ከመሸ ደውሎ ከሲስተር ዘሪባ ጋር ስለጅም ሰዓት አውርቶ ሲጨርስ ጠዋት ላይ ቢሮ ተቃጠሩ።

ሲስተር ዘሪባ በማግስቱ ረፋዱ ላይ ሌላሙ ጋደው ላበተቻለ ፍጥነት ልታናግረው እንደምትፈልግ ነገረችው። ግንፍል ግንፍል ከሚለው ስሜቷ እንዲተረጻው ሲራክ የራሱን ታሪክ እንደሞላት አወቀ። ቀድሞውንም ስሲራክ ባላት ስስ ልብ አብዛኛውን ነገር ሳታምነው እንዳልቀረች ገምቷል። ሆስፒታል እንደሆነ ነግሯት እዛው ሊገናኙ ተስማሙ። ሲራክ በስልክ ካወራት በተጨማሪ ፎቶ ኮፒ ያደረገውን በተለያዩ ሰዎች ላይ የጀመረውን ጥናት አሳያት። ከሆነው በላይ ለጥቦ ሲነገራት ውስጧ በንዴት ጦፈ። የሌሎቹን ካስነበባት በኋላ በርሷ ፋይል ውስጥ የጻፈው ለማሰብም ስለሚቀፈው፣ ሲያሳያት ፈቃደኛ አለመሆኑን ነግሮ ወሽመጧን በጠሰው።

ሆስፒታል ስትደርስ ላመል ያህል ጪብጣው ጸጥ ያለ ቦታ ካፈው ውስጥ ፈላነው ተቀመጡ። ዋቂት ዝም ብለው ቆዩ። "ቀይ ግን ይሄንን ሁሉ ማድረግ ለምን አስፈለገህ...? ጸክተር ምን ያህል እንዳመንንህ እያወቅህ እንዴት እንደዚህ ታደርጋለህ? እስኪ እያው የሆነውን ... ምኑ ነው ላንተ አሁን ስኬት የምትለውና ደስታ የሚሰጥህ? ብላ፣ ትኩር ብላ አየችው።

@OLDBOOOKSPDF

"ሲራክ እናግሮሽ ነበር እይደል?" አላት፣ ረጋ ብሎ።

"ዶክተር ... ምን ለውጥ አለው ማንሰ ቢያናግረኝ ... እውነቱ እኮ ራሱ አፍጥጦ ይታያል? ሰለስታፉ በድብቅ በከፈትከው ፋይልህ የምትጽፈው ጉድ ... የገዛ ትዳርህ ቢሆን ይሄው ገደል ገብቶ ከሊኒኩን ሊዘጉት የፍርድ ቤት ቀጠሮ አፍጥጦ እየጠበቅን ነው። እሺ ምን ይባላል ... አንተ ከዚህ ሆስፒታል ቀንና ሌሊት አትጠፋም። የማይገባኝ ... ሚስጥር እኮ ለሁላችንም የምንወዳት ልጃችን ... የስራ ባልደረባችንና ት ... ያንተ ትንሽ የበዛ አልመሰለህም?" ብላ፣ ቃላት እንደጠፋው ሰው እጇን አወናጭፋ ዝም አለች። ዝም ብሎ ሲለማት ቀየና ሲራክ ምን ያህል እንደተላካለት አስቦ በልቡ አደነቀው።

በረጅሙ ተነፈሰና ከኪሱ ውስጥ የሆነ ወረቀት አውጥቶ ሰጣት። "ሲስተር ... ሁሉንም ነገር ለማስረዳት ይከብዳል። ግን እውነቱ አሁን ከምትዪው ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ምንም ከማውራቴ በፊት እዚህ ፖስታ ውስጥ ያለውን እዪው።" በምን ጪንቀኝ አይነት ተቀብላ ከፈተችው። ከውስጡ ሁለት ፎቶዎች ተንሸራተው ጠረጴዛው ላይ ወደቁ። አንስታ አይታ ብዙም ስላልገባት አስቀመጠቻቸው። ከሁለቱ ደብዳቤዎች መጪረሻው ላይ ኤደን የሚለውን የምስጢር እናት ለርሱ የጻፉለትን ማንበብ ስትጀምር ተመስጣ ቀረች።

ደብዳቤውን አንብባ ፎቶዎቹን በተራ በተራ አየች። ቀና ብላ አይታው እጇን በራቷ ሸፍና ጸጥ ብላ ቀረች። ከቦርሳዋ መሐረቧን አውጥታ እንባዋን ጠራርጋ ፎቶዎቹን እንደገና ትክ ብላ ማየት ጀመረች። ስለ ዝት ጫፍ ጫፍ የነገራት ትዝ አላት።

"ይቅርታ ... ይቅርታ አድርግልኝ" ብላ፣ አሁንም ፎቶዎቹ ላይ አፍጥጣ ጸጥ አለች። ከዛም ዝት ሰሌላው የጻፈችውን ደብዳቤ በየመሃሉ እምባዋን እየጠረገች አንብባ ስትጨርስ በጸጥታ ተንሰታ አቀፈችው። አንዴ ፎቶዎቹን አንዴ እሱን እያየች ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቀችው።

"ታዲያ ለምን ራሷን ልታጠፋ ፈለገች ... ይሄንን ሁሉ ታውቃለች ማለት ነው?"

"አልመሰለኝም ... እናቷ ብዙም ጊዜ አንደ ሌላቸው ሳታውቀው አልቀረም ... በዛ ላይ የሳንቾ ነገር ... የከሊኒኩ ሁኔታ ... ተጨማምሮ ... ያ ልጅ ምን እንደነገራት አላውቅም። እኔን ተቀይማኝ ዓይኔን ማየት ነበር ያስጠላት። ብቻ እንደመሰለኝ ገና ነገሩን ሊነግሯት ሲጀምሩ መሰለኝ ... ተስፈንጥራ ወደቤት ሄዳ መድሃኒቱን የወሰደችው። ምን ታድርጊዋለሽ ... የሄው ልሽ ... ለሷም የጻፉላት ደብዳቤ እንደታሸገ ነው። እሷ ሮጣ ስለሄደች እንድሰጥላቸው እየነገሩኝ እኮ ነው ከቤት ተደውሎ የሄድነው ..." ብሎ፣ የታሸገውን ፖስታ ከኪሱ አውጥቶ አሳያትና ዓይኑን የሞላውን እምባ ጠራረገ።

"ይህን ነገር ካንተ ሌላ የሚያውቅ ማንም የለም?" አለች፣ የራሷንም እምባ ለማስቆም ይመስል አፍጇን ሞምሳ እያደረገች።

@OLDBOOOKSPDF

"ወይዘሮ ዘምዘምን ታውቂያት ይሆን...? እሷ የናቷም የሚስጥርም ብቸኛ ጉርብ ዘመድና ሚስጥረኛ ናት። ያባቷ ታናሽ እህት ናት። እሷ ታውቃለች ሁሉንም ነገር። ሌላ ... ያልነገርኩሽ ... በቀደም ካናገርሽኝ በኋላ አታቲን ላገኛት ሞከራ ነበር። ኮሚስጥር እናት ቀብር በኋላ አፈልግሃለሁ ብላኝ ተገናኘን። ምን ታይቷት እንደሆነ አላውቅም። የነበትን እናት ይቅርታ መጠየቅ አፈልጋለሁ አለችኝ።

"እሷ ራሷ ቤት መጥታ ... አሁን ልነግርሽ አልችልም። እንደዚህ ዓይነት ነገር ለይቼ አላውቅም ... ሁለቱም ተያይዘው ተላቀሱ። እኔ ራሴ በእልከኝነቴ አፈርኩኝ። ይቅርታ ማለት ለካ እንደዚህ ኃይለኛ ነገር ነው። ከማንም ይልቅ ትልቅ ሰው፣ ይቅርታ የሚጠይቅ ሰው ነው። በተለይ የምር ሲሆን።

"ከዚያ በኋላ ይህንን ሁሉ ታሪክ ነገርኳት። እሷም አልትሳልትሞት ነበር። ድሮም ሚስጥርን እንደ ነፍሷ ነበር የምትወዳት። ለገነት እናት ግን ገና አልነገርኳቸውም። ሚስጥር አንድ ነገር ብትሆን፣ የሚከብዳቸው ስለመሰለኝ" አለ፣ ረጋ ብሎ።

"ውይ ... እንዴት ደስ የሚል ዜና ነው ዶክተርዬ ... ደግ አደረግህ ... ግን ደግሞ ትንሽ ሻል ካላት፣ እሳቸውም ታሪኩን አውቀው ቢያዩዋት ጥሩ ነው ... ምስኪን ... የኔ እናት ... እንዴት እንደሚያሳዝኑኝ እኮ። የስንት ዘመን ጸሎታቸውን ፈጣሪ ሩህሩህ ሰምቶ ... ይሄው ልጃቸውን ሰርቶ አበጅቶ መልሶ ሰጣቸው ..." አለችና ሰበበኛ እንባዋ ማቆሚያ እንደ ሌለው ጅረት እንደገና ይፈስስ ጀመረ።

"ኧረ በቃ ሲስተር ... እንዴ ...ባክሽ" አለ፣ ትከሻዋን እያባበሰ።

"ይሄ የደስታ ነው ...እስኪ ልያት የኔ ቀንጮ ... ዛሬ ግን እንዴት ናት?" አለች፣ ፈገግ ብላ።

"ትንሽ ይሻላል ... አይኗን አልፎ አልፎ ትገልጣለች ... አተነፋፈሷም ብዙ ለውጥ አለው። ያው ምግቡ በቲዩብ ነው ... የቀረው ነገር በሰው እገዛ ነው ... ገና ራሷን በደንብ አላወቀችም" ብሎ፣ እያወሩ ወደ ተኛችበት ክፍል አመሩ።

አጠገቧ ቁመው ሲያዩዋት ቀዩና ሲስተር ዘቢባ ጉንበስ ብላ ግንባሯ ላይ ሳም አደረገቻት። "የኔ ፎልፏላ ቀንጮ ..." ብላ፣ የተጠቀላለለ ጸጉሯን እያሻሸች ቀና አለች። "ሚስጥረ ሌላሠው ... እንዴት የምያምር ስም ነው ... እውነትም ሚስጥር ..." ብላ፣ ከንዱን መታ መታ አደረገችው። "ሚስጥረ ገነት ... ሚስጥረ ሌላሠው ..." አለና እሱም ጉንበስ ብሎ ግንባሯን ሳም አደረጋት።

ትንሽ አውርተው ከክፍሉ ሲወጡ፣ "ታዲያ ይሄንን ልጅ ምን ልታደርግ አሰብክ...?" አለች፣ የሲራክ ሁኔታ እያስጨነቃት። ብትወደውም እያደረገ ያለው ነገር ብዙ ጥፋት ሊያመጣ እየታያት አበሳጫት።

"ምንም ..." ሲላት፣ ደንገጥ ብላ፣

"እንዴት ምንም ዶክተር? ... ስለ ሰራተኞቹ ሁሉ የጻፈው ነገር አለ ... በኛ ላይ ጥናት እየሰራብን ነው። @OLሚወዱሆወወOሽSምኽ እንጻለው ደርሽበታለሁ እያለ

እንዴት ነው ምንም የማታደርገው? ከንጹሕም ጋር ይደዋወላል መስለኝ ... ትናንት እንደነገረኝ ከሆነ ..." ስትል ፣ የንጹሕን ስልክ የወሰደበት ቀን ትዝ ብሎት ነገሮችን ወደ ኋላ ማውጠንጠን ጀመረ ።

"ሲስተርዬ እውቃለሁ ... ግን ሲራክን እኔ ምንም አላደርገውም ። ዕድሜና ልምድ ያስተማረንን መራራ እውነታ ... ከዕድልና ከሌላ ሰው ቢማር ጥሩ ነበር ... ግን ለሁሉም የራሱ መማሪያ መንገድ አለው መሰለኝ ...እኔ ግን ሲራክን ምንም አላደርገውም" ሲላት ፣ የምሩን መሆኑን አይታ ገረማት ።

"ግን ቀይ እንድነገር ... ስለኔ ምን ብለህ ነው የጻፍከው ..." ብላ ሳቀች ። "ሲራክ ስመናገርም ያሳፍራል ነው ያለኝ ። ግን እንዲያው ምን ብታይብኝ ... ምንስ አይነት የጭንቅላት ጉድለት ቢኖርብኝ ነው?" ስትለው ፣ እሱም በረጅሙ ሳቀ ።

"እንደዛ አለሽ...? ... አይ ሲራክ እንዲያው ምን ይሻለው ይሆን? ለማንኛውም የራሱን ወይም የማስረሻን እንብቦ ያንቺ መስሎት ይሆናል ። ይሄው ቁልፉ ... መሳቢያ ውስጥ አሉልሽ ሁሉም ፋይሎች ... ኦሪጂናሎቹ ። የራስሽንም ... የሁሉንም እንብቢው ... ከዛ እናወራለን" ሲላት ፣ ቁልፉን እያመነታች ተቀበለችው ።

"ሰው ስለኛ የሚለው ግን ይሄንን ያህል ለምን ያስጨንቀናል?" አለች ፣ 'ስለርቢ የተጻፈው ነገር' ይሄንን ያህል ለምን እንጻብሰለሰላትና እንጻተከናት ገርሟትና ትንሽም ሀፍረት ነገር እየተሰማት ። እጹን ኪሱ ከትቶ ከፊት ለፊቷ እንደ ቀመ መሬት መሬቱን ሲያይ ቀየና ቀና አለ ።

"እኛን እኛ ያደረገን ሰዎች የሚሉን ብቻ ሳይሆን ሰዎች ይሉናል ብለን የምናስበውና የምናምነውም ስለሆነ ይሆናላ ። እያንዳንዱ ሰው በሌላ ሰው ጥላ ስር የሚኖር ፣ የሌላ ሰው አስተያየትና መላ ምት የእጅ ስራ ነው ። ራሳችን ከሆነውና ካደረገነው ይልቅ ሌላ ሰው ስለኛ ያለው ሆዳችንን ይበላናል ። ሰው ራሱ ስለራሱ ሊጽፈው የሚችለው ስንት ቁም ነገር እያለ ፣ ሌላ ሰው በጻፈው የግል አስተያየት መድበል ሕይወቱን ማስተዳደሩና ማሸርገዱ ሰው የመሆን መራራ እውነታ ነው" ብሎ ፣ ሲሰናበታት እጹን ዘረጋ ።

"ይሉኝታና ... አሉባልታ ... አገር ያጠፋውስ ለዚሁ አይደል" አለች ፣ ለርሱም ለራዕ.ም በሚመስል ወደ ውስጥም ወደ ውጪም በሚለማ ድምፅ ። የለጣትን ቁልፍ ቦርሳዋ ውስጥ ጨምራ የዘረጋውን እጹን ጨብጣ ሄደች ።

@OLDBOOOKSPDF

• 47 •

ሲራክና ሳቤላ የዲቪ ሂደቱ እያለቀላቸው ነው። የቪዛ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ኤምባሲ ከሳምንት በኋላ ለመግባት እየተዘጋጁ ነው። ብዙውን ጊዜ የሚያጠፋው ከሳቤላ ጋር ሆኗል። ጠቅልላ እሱው ቤት የመግባት ያህል ሆኗል ኑሮዋ። አልፎ አልፎ ስለመጋባት ስታነሳበት ነገሩን አድበስብሶ ወይም ቀልዶ ስለሚያልፈው ለጊዜው ነገሩን ብትተወውም ውስጥ ውስጡን ይከነክናት ጀምሯል። በርሱ በኩል ስለአሜሪካ ጉዞው ለወንድሙም ይሁን ለማንም ትንፍሽ አላለም።

ከሌላው ጋር ከተጋጨ ወዲህ አልፎ አልፎ ካልሆነ ከሊኒክ መግባቱን ትቶታል። ከመሄዱ በፊት እሱን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ክሊኒኩን የማስረሻን ሞት ከስ በመጠቀም እንጦሮጦስ ማውረድ ዋና እቅዱ ነው። ክሊኒኩን እንዲከሱ በተዘዋዋሪ ለማስረሻ ቤተሰቦች ሹክ ያላቸውም እሱ ነበር። ሲስተር ዘቢባ ከርሱ ጋር እንድትወግን የቻለውን ሁሉ አድርገ አልቀናውም። ንግግሯ ሁሉ ጥርጣሬ ያዘለ፣ ሁኔታዋም ከበፊቱ ቅዝቅዝ ያለበት ስለመሰለው ከሷ ጋር የሚያጠፋውን ጊዜ መቀነሱን መርጧል።

ሳንቾን ከታሰረ ጀምሮ ጠይቀትም እንደማያውቅ ትዝ ሲለው አንድ ከሰአት በኋላ ሄደ። ከዚህ በፊት ስለነበራቸው ግጭት የተሰማውን ትልቅ ጸጸት ያዘነ መስሎ ገለጸለት። እሱን ለመርዳት ማድረግ የሚችለውን ሁሉ እንደሚያደርግ ቃል ገባለት። ሳንቾ ሲራክን ድሮም እንደ ሰው ም አይቀጥረውም። አሁን ግን ሁሉም ነገር ስላታከተው ተስፋው ስለመነመነ ከፉም በጎም ሳይል አመስግኖት ተለያዩ።

የሌላው መረጋጋት ሲራክን ይረብሸዋል። ዛሬም የሚያደርገውን እንደማያውቅ ለማጅ ተማሪ የሚቀጥረው ስለሚመስለው ውስጡ ይቃጠላል። 'ለሱ ከምንም የማላውቅ የቤት ልጅ ነኝ ... 'እንድ ቀን ይገባሃል' ይለኛል እንዴ ... ቀይ ግን ምኑን ተማምኖ ነው? ... ይሄ ባጃጅ ራስ ...' ይላል ደጋግሞ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሌላው 'ባጃጅ ራስ' ሊባል የማይችል ይመስለውና ያለውን ርግጠኛነት ያጣል። የሚያደርገውንና የሚለውን አስቦ የሚያደርግ እንደሆነ

@OLDBOOOKSPDF

ስለሚያምን ሊያጠፋ ያልቻለው ፍርሃት ውስጡ ጉብ ብሎ ያስፈራራዋል። 'ምን ያመጣል ከዚህ በኋላ ... ከነክሊኒኩ ማጥ መስጥ ገብቶ ሲንፈራገጥ ... እኔ ሲራዘ ... ዴንቨር ሆኜ ... አንጀቴን ነው የማርሰው' ብሎ ራሱ በፈጠረው የድል በአል ላይ ሰራሱ ተደጋጋሚ ንግግር ያደርጋል።

ላለፈው ሁለት ሳምንት ብዙም ያላገኛት ንጹሕ ትገ አለችው። የሆነውንና እንዲሆን የሚፈልገውን አደበላልቆ የተቀመመ ኢሜይል ጽፎ ላከላት። ስለ ምስጢር ሲጽፍላት፣ 'በእውነት መትረፏን እጠራጠራለሁ ... ብትተርፍም ሞንቅላቷ ለምንም የማይጠቅም የቅቤ ቅል መሆኑ አይቀርም። እሱም ሆስፒታል የተሰፋ ይመስል ከስሯ አይለይም። በዚህም የተነሳ ከሲኒኩም በቅርብ ሳይዘጋ አይቀርም። ሁሉም ቀስ በቀስ የጁን እየተቀበለ ነው። የፍትህ ፀሐይ የጠለቀች ስትመስል፣ በተስፋ ለሚጠብቋት የሌሊቱ ቁር ለጊዜው ቢከፋባቸውም ... ማለዳ ላይ በሙሉ ግለቷ የወጣች ጊዜ ገለባውና ፍሬው ይለያል ...' ይላል።

ምስጢር ግን ቀስ በቀስ ከነበረችበት ጥልቅ ራስን ያለማወቅ እንቅልፍ (ኮማ) ቀስ በቀስ መንቃት ጀምራለች። አሁን ችግር የሆነው ውስጧ በማይታወቅ ምክንያት እየተረበሸ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለች ለያዥ ለከልካይ ማስቸገሯ ነው። ሞንቅላቷ ሙሉ ለሙሉ ስላልነቃና የንቃት ሁኔታዋ የተዘበራረቀ በመሆኑ በየዶቂቃው አብሯት የሚሆን ሰው ያስፈልጋል። አንዳንዴ ተነስቼ ካልሄድኩ ብላ ስለም ታስቸግር እጅና እግሯን ማሰርና የሚያረጋጋ መድሃኒትም መወጋት ያስፈልጋታል።

በተለይ ሌላሠውንና አክስቷን ወይዘሮ ዘምዘምን ስታይ ፍጥጥ ብላ ታያቸዋለች። ድንገት ዘልላ ልታንቃቸው ትሞክርና ሲያቅታት እሪ ብላ ትጮሃለች። ደጋግማ የናቷንና የሳንቾን ስም ትጠራለች። ሳንቾን ምን ያህል እንደምትወደውና ከሱ ሌላ ማንንም ማግባት እንደማትፈልግ እየተናገረች ታለቅሳለች።

ሃኪሞቹ በአንገቷ ላይ ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰና ከዚህ በኋላም ምን ያህል ሊሻላት እንደሚችል እርግጠኛ መሆን አልቻሉም። አሁን የምታሳያቸው ምልክቶች በተወሰነ መጠን የመሻል ምልክት እድርገው ነው የወሰዱት። ጊዜያዊና ዘላቂ የሚሆነውን የሞንቅላቷን የጉዳት ደረጃና ሁኔታ ግን ጊዜ ብቻ ነው የሚገልጠው ባዮች ናቸው። ጉበቷ ኩላሊቷና ሌሎች የውስጥ አካላቷ ሁሉ በትክክል እንደሚሰሩ ማወቁ ትልቅ የምስራች ነበር።

ከፍተኛ ሀዘንና ከትትል ከሚሰጥበት ክፍል እንድትወጣ ተወሰነ። ከጥግ አካባቢ ወጣለ ሰፊና ጸጥ ያለ የአንደኛ ማዕረግ ክፍል አዛወሯት። ቤተሰብ እየተፈራረቁና እየተረዳዱ ሊንከባከቧት ችለዋል። ለረጅም ጊዜ አብራቸው የኖረች የቤት ሠራተኛቸውና የሌላሠው እናት አብረዋት ሲሆኑ ትንሽ ረጋ ትላለች። ወደ ምስጢር ጋ ሊሄድ ከቤት ሲወጣ ሲስተር ዘቢባ ደወለችለት።

ሰላም ከተባባሉ በኋላ፣ "ዶክተር ... የሆኑ ሰዎች ሊያናግሩኝ መጥተው የፍርድ ቤት ማዘዣ አለን ባዮች ናቸው። ከጤና ቢሮም ይብጸቤ አምጥተናልና ክሊኒኩ

@OLDBOOOKSPDF

የተመሰረተበት ከሰ ታይቶ ውሳኔ ላይ እስኪደረስ መዘጋት አለበት ነው የሚሉት ..." አለች ።

ድንጋጤና ግራ መጋባት ሞልቶት፣ "ምን ... ደግሞ እንደዚህ ያለ ነገር አለ እንዴ? ... ተከሰስን እንጂ እኮ ጥፋተኛ አልተባለም ። እየሰራን ነው እንጂ የምንከራከረው ... ተዘግተን እንዴት ይሆናል? ከተዘጋ እኮ ጥፋተኛ ነን ማለት ነው ። ጠበቃችንን ማናገር ይኖርብናል ... ለሁንም እሱው ጋ ናቸው እንዴ?" ሲል

"አዎን ትንሽ ጊዜ እንዲሰጡኝ ለምኛቸው ... ካፌ ናቸው ... ምን እዚህ አገር እኮ ጉዳይ መሆንህ እስኪታወቅ በወንጀለኛነት የመሰለው ሁሉ ነው የሚቀጠቅጥህ" አለች፣ መጨነቋ ድምጿን ጎልቶ እየተነበበ ።

"እስኪ ቀዩኝ ... እንዴ ልደጪልላቸውና ጠበቆቹ የሚሉትን እንስማ ... እኔም እየመጣሁ ነው" ብሎ፣ ሆስፒታል የመሄድ ሃሳቡን ለውጦ ወደ ክሊኒኩ አመራ ። ነገሩን ለወይዘሮ ዘምዘም ነግሯት ሰው እስኪመጣላት እቢ ልትቀይ ተስማሙ ። ቀኑን ሙሉ የሚችሉትን ሁሉ ቢያደርጉም ከሊኒኩ እንዳይዘጋ ማድረግ ሳይችሉ ቀሩ ። በመጨረሻ ክሊኒኩ የወንጀሉ መፈጸሚያ ቦታ ሰላልሆነና የተለየ የሚበላሽ የወንጀል መረጃ ስለሌለው ስራውን ብቻ ማቀም እንጂ መታሸግ አያስፈልገውም በሚለው ተወሰነ ።

ጥናው የፍርድ ቤት ቀን ተጠሮ ከእስር ቀን በኋላ ስለሆነ ጠበቀቻቸው ያላቸውን ኃይል ሁሉ አሰባስበው እየሰሩ ነው ። ሩይሱን በዋና ጠበቃነት የያዘችው ውዳሴም ከጉዳዩ ጋር ቀጥ ታም የሩቅም ግንኙነት አላቸው ያሏቻቸውን ሰዎች ሁሉ እንጋግራለች ። ያልበረበረችው ቁጻዳና መረጃ የለም ። ምንም እንኳ ሲራዝ የነሳሽ ዋነኛ ምስክር ቢሆንም በሰበሰበቻቸው መረጃዎች መሰረት የመከላከያ ክርክሯን የጣባችውም በሱው ዙርያ ነው ። እንዳንዴ በበቀል ጉልበትም እየሰራች ይመስላታል ። ራሷን ትፈትሽና ግልጽ መልስ አታገኝም ። ምንም ይሁን ምን ድሮም መሸነፍ የማትወደው ውዳሴ ዛሬም ማሸነፍን ብቻ አማራጭ አድርጋ ነው እየሰራች ያለችው ።

ኤምባሲ የምትሰራ ጓደኛዋ ሲራዝ ዲቪ ደርሶት ካንዲት ልጅ ጋር ተጋብተው ለመሄድ ቪዛቸውን እንደ ወሰዱ ደውላ ነገረቻት ። ልጅቱን እንደማታውቃት ነገረቻት ። ፋይሷ ላይ ከለው ምስሏ ላይ በስልኳ ፎቶ አንስታ ላከችላት ። ውዳሴ ልጅቷ ማን መሆኗን ወዲያው አወቀቻት ። ይሄ ደግሞ በሌላ አዲስ የበቀል ማዕበል ልቧን ሲንጠው ተሰማት ። እየር መንገድ የሚሰሩ ጓደኞቿ ጋ ደውላ የሲራዝና የሳቤላን ሙሉ ስም ለጥታቸው የበረራ ቀናቸውን አረጋገጠች ። ነገሩ በሕግ እንደማይፈቀድ ብታውቅም የያዛት እልህ ውስጧን እየቆጠቆጠው ነው ።

የምስጢር የጤና ሁኔታ ደግሞ ዘቀን ወደ ቀን በፍጥነት ተሻሻለ ። በትክክል ሃሳቧን መግለጽ ብትቸገርም፣ ቀን የተሻለ ንቃት መጥልና ግታም በሰላም መተኛት ጀምራለች ። ምግብ በራሷ መመገብና በትንሽ እገዛ ለራሷ የሚያስፈልጓትን ነገሮች ለማድረግ ትምክራለች ። ሆስፒታል ልትገባ አካባቢና ከዚያ ወዲህ የሆኑ ነገሮችን ግስታወስ ግን አልጀመረችም ። ሰው ደግፏት በሆስፒታሉ ኮሪዶር ላይ ወዲያ ወዲህ ማለት ችላለች ። ለአየሩና ለምግብ ቀላለል ውስጧ በቀኑት ላስቲኮች

@OLDBOOKSARE

ምክንያት ጉርሮዋ ቀስሎና ደክሞ ስለነበር ድምጿ በቅጥም አይሰማም። ለረጅም ጊዜ ያልተጠቀመችባቸው ጡንቻዎቿም ፈዝዘው፣ መሄድና ሌላ ከበድ ያለ አቅም የሚጠይቁ ነገሮችን ማድረግ ስታይ ሆኖባታል። ለዚህም ልዩ የአካል እንቅስቃሴ እገዛ እየተደረገላት ነው።

ሃኪሞቹ በሌላ አንድ ሳምንት ውስጥ ወዴ ቤት ልትሄድ እንደምትችል ተስፋ ሰጥተዋቸዋል። ሙሉ ለሙሉ ነቅታ ወደ ቤት ሳትገባ መዶረግ ያለባቸውን ነገሮች ማቀድ ጀምረዋል። በተለይ የእናቷን መሞት እንዴት እንደሚነግሯት ሌላሠውና አክስቷ ገራ ገብቷቸዋል። ሌላሠው ነገሩን እቤት ከመሄዱ በፊት እዚሁ ሆስፒታል መንገሩን ነው የመረጠው። ደግሞ ገና የማንነቷና እውነተኛ ወላጆቿን የማሳወቅ ሌላ ከባድ ስራ ስላለ እሱም ሌላ ጭንቅ ሆኗል። መትረፍ መሞቷን አስፍስፈው ከሩቅ ሲጠብቁ የነበሩ የአባቷ ዘመዶች ድና ወደ ቤት መሄጃዋ ሲቀርብ አለን አለን ማለት ጀምረዋል። በደረሰባት የአእምሮ ጉዳት ራሷንና የቤተሰቡን ሃብት ልትንከባከብ ስለማትችል ሙሉ ሀጋዊ ሞግዚትነት ይሰጠን ብለው ለማመልከት ዳር ዳር ሲሉ በፍጥነት እየተሻላት መጣ።

ቅዳሜ ማረፋፋቹው ላይ ሊጠይቃት ብዙ ሰው ተሰብስቦ ነበር። ሲስተር ዘቢባ ከነቤተሰቦቿ፣ የሌላሠውና የገነት እናቶች፣ የሳንቾ አክስት ልጆች፣ ወይዘሮ ዘምዘምና ባሏ፣ ሁለት የምስጢር ጓደኞች። ከፍሉ ሰፊ ስለነበር እዛው ቡና ተፈልቶ ... ያመጡትን ምግብ ለምሳ ቀርቦ ሲላሳቁና ሲጫወቱ ቀዩ። ምስጢር ትንሽ ወዲያ ወዲህ ለማለት ብትፈልግም ብዙም እንድትንቀሳቀስ አልፈቀዱላትም። የእናቷ አለመኖር ቢከነክናትም ደፍራ ለመጠየቅ ግን ወኔው ጠፋት። ምናልባት ሞተው ይሆናል የሚለውን ፍርሀቷን ለመጋፈጥ አልፈለገችም።

ሰው ሁሉ ቀስ በቀስ ሄዶ ሲስተር ዘቢባ፣ ሌላሠውና ወይዘሮ ዘምዘም ቀሩ። ምስጢር ሰውነቷ ድክምክም ብሎ ጋደም ባለችበት እንቅልፍ ወሰዳት። ጋቢ ጣል አድርገውባት እነርሱ ሲጫወቱ ትንሽ ቀዩ። ሌላሠው በመቅየቱ ተወሰኖ ሌሎቹ ተሰናብተው ወጡ። ምስጢር ድንገት አቃሾፏት ብንን ብላ ስትነሳ ክፍሉ ጸጥ ብሏል። ቀና ብላ ስታይ ሶፋው ላይ እንደተደገፈ ሲያንኮራፉ ከነበረው ከሌላሠው በቀር ማንም የለም። ሽርተት ብላ ካልጋው ላይ ወርዳ አጠገቡ ቀማ ቁልቁል አየችው። የሆነ ነገሩ አሳዘናትና 'ለምንድን ነው ይሄን ሁሉ የሚያደርግልኝ?" ብላ አሰበች። ከዛ ደግሞ ሲራክ የነገራት ነገሮች ትዝ አሏትና ውስጧ መናደድ ጀመረ።

ጋቢውን ትከሻዋ ላይ እንደጣለች ወደ መስኮቱ ሄዳ ደጁን እያየች ደገፍ ብላ ቀመች። የሆነውን ነገር ወደ ኋላ ሄዳ ለማስታወስ ጣረች። የእናቷ የመጨረሻ ቃል ትዝ አላት። ወዲያው ከሆስፒታል ወጥታ ስትሮጥና ቤት ሄዳ የነበረው ሁኔታ በደብዛዛው ትዝ አላት። ቀኑን በትክክል ልታስታውሰው አልቻለችም። በጣም ረጅም ጊዜ መሰላት። ካመት ከሁለት አመት በላይ ሆኖ ተሰማት።

'ስለዚህ በወሰድኩት መድሃኒት ጦስ ነው እስካሁን እዚህ ሆስፒታል ያለሁት?' ብላ ጠየቀች። ዞር ብላ ስታይ ብዙ ካርዶች ከመዲኖቹን ሞልተው አይታ እያነሳች ማንበብ ጀመረች። እንደገና የእናቷን ጉዳይ የቻለችውን ያህል ለማሰብ ሞከረች።

@OLDBOOOKSPDF

"ሞታ መሆን አለበት እንጂ እንዴት እናቴ ... ካጠገቤ ትጠፋለች?" ብላ ደመደመች። መጨረሻ ላይ ስታያቸው የነበራቸው የተጨነቀና በሀመሙ ዘፋኝ የገረጣ ፊታቸው ትገ አላት። "እንኳን ተሻለሽ" ከሚሉ ካርዶች አንዱን እንደያዘች ወደ መስኩቱ ተመልሳ እምባዋ መፍሰስ ጀመረ።

ድንገት ነቅቶ ፊቱን ጠራርጎ ሲያይ ምስጢር በመስኩቱ እንጻር ቀማለች። ብድግ ብሎ ወደ እርሷ ጠጋ አለና "ሰላም ነው? ይቅርታ ቁሜ ባልኩበት እኮ ይሆኝ ሄደ።"

"ይሀና ..." ብላ ስትሀር ፊቷ በእምባ ታጥቧል።

"ምነው ... ምን ሆንሽ...?"

"እናቴ ... እናቴ የት ናት? ... ሞታለች አይደል? ባትሞትማ ኖሮ ከዚህ አትጠፋም ... ካጠገቤ አትላወስም ነበር። በናትህ ዶክተር ሌላ አትዋሸኝ ንገረኝ ... እውነቱን ነው ማወቅ የምፈልገው" ብላ፣ ቅርቧ ያለው መንበር ላይ ተቀምጣ ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች።

እንደ ደነገጠ አጠገቧ በርከክ ብሎ፣ "በጣም አዝናለሁ ... ሚስጥርዬ ... ልክ ነው። መጨረሻ ላይ ሆስፒታል ተኝተው ... ካንቺ ጋር አውርታችሁ ... ትዝ ይልሻል የሆነ ነገር ሊነግሩሽ ጀምረው ... አንቺም ነገሩ ካቅምሽ በላይ ስለነበረ ጥለሽ ሮጥሽ" የሚለው ነገር ዝብርቅርቅ ብሎበት ፊቱን ጠራረገ። "አንቺ ሮጠሽ ስትወጪ ... እኔ ደግሞ እየመጣሁ ነበር። እንዴት እንደሆን አላውቅም ተላለፈን። ስደርስ በጣም አሟቸው ነበር። እንደ ምንም አንዳንድ ነገሮችን ለኔ ሊነግሩኝ ሲሞክሩ ከቤት ስልክ ተደወለ።

"የሆነውን ነገር ሰራተኛዋ ልትነግራቸው ስትጀምር ... ነገሩ ከቅማቸው በላይ ሆነባቸው። እሳቸውን ለሃኪሞቹ ትቼ አምቡላንስ ይገር እቤት ስደርስ ራስሽን ስተሽ ነበር። እሳቸውም አንቺም ላንድ ሳምንት ያህል አይሲዩ ከፍል አብራችሁ ቀያችሁ። ያው ሁኔታቸው በካንሰሩ በከፍተኛ ደረጃ መሰራጨት የተነሳ ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ ምንም ማድረግ ሰላልተቻለ አረፉ" ሲል፣ ፊቷን በእጆቿ ሸፍና ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

ሊያባብላት የቻለውን ያህል አደረገ። ከተቀመጠችበት ተነስታ አልጋዋ ላይ በደረቷ ተዘረረች። ድምጿን ከፍ አድርጋ ለቅሶዋን ስታቀልጠው የሚያደርገው ጠፍቶት በቆመበት ቀረ። ትከሻዋን ነካ ነካ እያደረገ ሊያጽናናት ሞከረ። ተነስታ መታጠቢያ ቤት ገብታ በሩን ዘጋች። የሚያደርገው ጠፍቶት በሩ ላይ ቆመ። ዘለግ ላለ ጊዜ እዩዬ ብላ አለተሰች። ትንሽ ጋብ ሲልላት ከመታጠቢያ ቤት ፊቷን እየጠራረገች ወጣች። አልጋው ላይ ጸጥ ብላ ተተመጠች።

ሰፈራ ሲቸር፣ "ሚስጥርዬ ... ለምን ትንሽ ወደ ደጅ ወጥተን፣ ንፋስ ነገር አትተነፍስም?" ዘም እንዳለች ጋቢውን ላዩዋ ላይ ጣል አድርጋ ጫማዋን ጠለት ጠለት አድርጋ ተነሳች። እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ ከክፍሉ ወጡ። ብዙ ጥያቄዎች በጭንቅላቷ ውስጥ እየተተረማመሱ ነበር።

@OLDBOOOKSPDF

"ቀይ ግን ለምንድነው ይሄን ሁሉ ጊዜ ቀንና ሚታ አንተ እዚህ ከኔ ጋር አብረህ የሆንከው? ... ለምን?" አለችው ድንገት ፈንጠር ብላ በጥርጣሬ ዓይነት እያየችው።

"ታሪኩ በጣም ረጅም ነው ... ለጊዜው አሁን የሰማሽው ይበቃል። እሱም ከበቂ በላይ ነው። ባጭሩ ግን እናትሽ ናቸው... 'እንደኔ ሆነህ ... ካጠገቧ ስትለይ ... ሁሉም ነገር አልፎ ... ሁሉንም ነገር ተረድታ ... ደህና እስክትሆን ... አብረሃት ሁን ... እንዳትለያት' ብለው የአደራ ቃል ያስገቡኝ። ዝርዝሩን ወደፊት እነግርሻለሁ። ብዙ የማታውቂው ነገር አለ"

እዛው እንደቀመጡ ጋቢዋን ወደ ላይ ሰበሰበችና "ምኑን ... የትዬ ዘምዘም ልጅ መሆኔንና ማሚ የኔ እናት አለመሆኗን...?" ስትለው፣ ነገሩ ግራ ገባው።

"ማነው እንደሱ ያለሽ...? ግዴለም .... እሱን አሁን ተዪው ... አሁን አንቺና እናትሽ ወይዘሮ ኤደን ላይ ብናተኩር ይሻላል" አለ። ሃሳቡን ከየት እንዳመጣችው ሊያውቅ ስላልቻለ። በናቷ ሞትና የመጪረሻ ቀኖች ላይ ሲያወሩ ትንሽ ተረጋጋች።

ጮን ለጮን ከተቀመጡበት ውሃ ልክ ስር በትለው የደረቁ ሳሮችን አንድ ባንድ እየነቀለችና እየበጠሰች አጮንብሳ ቀየች። "ሰኢዶስ? ... ልጆቹስ?" ቀና ብላ እየችው።

"ሳንች ያው እስር ቤት ነው ... ነገሮች ተደራርበው ብዙ ገድተውታል። ልጆቹ ግን ደህና ናቸው ... ሙሉ ለሙሉ እናንተ ቤት ነው የሚኖሩት። የማስረሻ ቤተሰቦች ከሱን አስፍተው ... ሳንችን ብቻ ሳይሆን ከሲኒኩን ሁሉ ከስሰዋል። ጥናው የፍርድ ቤት ቀጠሯችን ሰሞኑን ነው።"

"ከሲኒኩ ደግሞ ምናደረገ ... ባከሙወ? እንደዚህ መሆኑ ለሰኢዶ ጥሩ ነው መጥፎ?" አለች፣ የማስረሻ ስም ሲጠራ እየቀፈፋት።

"ለሳንቾ በጣም ጥሩ ይመስለኛል። ቢያንስ እሱን ነጥለው የበቀል ኢላማ እንዳያደርጉት የሚረዳ ይመስለኛል። ጥፋቱ የከሲኒኩ ቢሆን ይሻለኛል ... ሳንቾን የሚረዳ ምንም ነገር ቢሆን ደስታዬ ነው። ነገሩ ግን በጣም እየተወሳሰበ ይመስላል" ድንገት ሲራክ የነገራት ነገሮች ትዝ አሏት። ልጠይቀው አልጠይቀው በሚል ትግል ውስጥ ቀየችና እንደምንም አመጣችው።

"ቀይ ግን ዶክተር ሴላ እኔ ሚስጥሬ ብዬ የነገርኩህን የግል ህይወቴን ጉዳይ ... እንዴት? ..." ብላ እንደገና ጸጥ አለች። "ለዛውም ለሲራክ ... ለምን መንገር አስፈለገህ? እውታለሁ ተገናኝታችሁ ብዙ እንደምታወሩ። ሁሉም ነገር ለእናንተ ኪዝና ተራ የህክምና የውይይት ርእስ ሊሆን ይችላል ... ግን..." ነገሩ መጀመሪያ ላይ ግራ ገባው። ሁሉንም ነገር ቀስ ብሎ ከስሩ አስረዳት። ታምማ ራሷን ስታ በነበረበት ጊዜያት የሆኑ ነገሮችን እየጠየቀችው ሲያወሩ አመሸ። ለአዳር ልትተኛው ወይዘሮ ዘምዘም ስትመጣ ተያይዘው ወዴ ዘፍሷ ሄዱ። ምስጢር ወደ መታጠቢያ ቤት ስትገባ፣ የእናቷን ሞት እንዳረዳት፣ ሌሎች ጉዳዮችን ግን እንዳላወሩ ቀስ ብሎ ነገራት።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 48 ፡

ሴላሠው ኢትዮጵያ ውስጥ ፍርድ ቤት ተገኝቶ አያውቅም ። ስርአቱና ሂደቱም ምን እንደሚመስል አያውቅም ። አሜሪካን ሀገርም ቢሆን በክፍተኛ ደረጃ የታመሙ የአእምሮ ህመምተኞችን ያለፈቃዳቸው እንዲታከሙ ህጋዊ ፈቃድ ለማግኘት ሲሄድ ካልሆነ ፍርድ ቤት ምን እንደሚመስል አያውቅም ። ጥሪ የደረሰው በምስክርነት ቢሆንም ልቡ ሲረበሽበት ነው የነጋው ። ልብሱን ለባብሶ ሲጨርስ ከቤት ከመውጣቱ በፊት ምስጢር ጋ ደወለ ። ደህና ማደሯን ጠይቀ ከፍርድ ቤት መልስ በቀጥታ ወደ እሷ እንደሚሄድ ነግሯት ወጣ ። ሲስተር ዘቢባ ጋ ሲደውል ቀድማ መድረሷን ነገረችው ።

ወደ ውስጥ ሲገባ፣ ሳንቾ እጁ በካቴና ታስሮ በሁለት ፖሊሶች ታጅቦ ሲገባ በዓይናቸው ሰላምታ ተለዋወጠው ተላለፉ ። ውዳሴ ጥቁር ካባዋ ውስጥ ወተት የመሰለ ነጭ ሸሚዝ አድርጋ ከቀይ ሃር የተሰራ ሻሽ ነገር አንገቷ ላይ ሸብ አድርጋለች ። በራስ መተማመኗ ከፊቷና አካሄዷ ይነበባል ። ሳንቾን ፈገግ ብላ ሰላም አለችውና ተቀምጣ ጥቂት ተነጋገሩ ።

ሲራክ ጥቁር ሱፍ በነጭ ሸሚዝና ቀይ ክረባት ተላብሶ፣ የሚያምር ጥቁር ሙሉ ቀሚስ ለብሳ፣ በቀይ ጫማና ቦርሳ ከተንቦጠቦጠች ቀንጅዬ ልጅ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው ገቡ ። እሷ ወደ ኋላ ፈንጠር ብላ ስትቀመጥ እርሱ ወደፊት ሄዶ የተመደበለትን ቦታ ያዘ ። ድንገት ከውዳሴ ጋር አይን ላይን ሲጋጩ ንቱት የተሞላ ፈገግታ አሳይቷት፣ ከቁብም እንዳልቆጠራት ፊቱን አዞረባት ።

ዳኞቹ ገብተው ስፍራቸውን ሲይዙ፣ ችሎቱ ተሰይሞ የፍርድ ቤቱ ሥርዓተ ደንብ ተፈጽሞ፣ የክሱ ሁኔታ ተነበበ ። ምስክሮቹም እውነቱንና እውነቱን ሁሉ እውነቱንም ብቻ ሲናገሩ እየማሉ ተራ በተራ የሚያውቁትን ተናዘው ሲጨርሱ፣ ከግራ ቀኝ በቀረበ መሰቀለኛ ጥያቄ ልባቸው ጠፉ ። የከሳሽና የተከሳሽ ወኪል የሕግ ባለሟሎች ችሎታቸውን አስመሰከሩ ።

@OLDBOOOKSPDF

ፍርድ ቤቱን ለማላመን የምስክሮችን ሀሲና እየፀረጠ፣ ያላቸውን ብልሃትና መረኛ እየወደሩ፣ እውነቱ ላይ ለመድረስ ላባቸውን ጠብ አደረጉ። ምስጢር ሆስፒታል በመሆኗ ለመምጣት ከለመቻሏ በተር ዶክተር ሌላሠው፣ ሲስተር ዘቢባ፣ ሳንቾ፣ የዘሊኒኩ ጥበቃና ባካባቢው የነበሩ ሰዎች ሁሉ የሚያውቁትን ላይደብቁ የማስታመስ ሃይላቸው እንዶቻለ ዘረገፉ።

የማስረሻ እናትና የረጅም ጊዜ ጓደኛም የልጁን ደግነት፣ ባለራእይነትና ባይሞት ናር ለወገንና ለሃገር ሊሰጥ ይችል የነበረውን ያልተበዘበዘ ጉትርና ድንት ችሎታ እያስረዱ እምባቸውን ረጩ። የመጨረሻው የአታቤ ሀገ ምስክር የዶክተር ሲራክ ተራ ደርሶ ከመቀመጫ ኮርጁ ውስጥ ገባ። ራሱን ከነሙያ ማዕረጉ አስተዋውቆና መሃላ ግዝቱን ፈጽሞ፣ የመጀመሪያ ጠያቂ በመሆን ተራ የወሰደው አታቤ ሀጉ ንበር።

"ዶክተር ሲራክ ሚችን ያውቁት ንበር?"

"እዎን ... በሙያ አጋጣሚ"

"የትና እንዴት እንደሚያውቁት ለፍርድ ቤቱ ቢያስረዱልን"

"ቀድሞም እንደተገለጸው የዘሊኒካችን ህመምተኛ ወይም ደንበኛ ሆኖ ዶክተር ሌላሠውን ያይ ነበር። ዶክተር ሌላሠው በሃገር ውስጥ በሌለበት ጊዜ ትንሽ ተረብሾ ወደ ዘሊኒኩ በመጣ ጊዜ ነበር ያየሁት። ራሱን ወይም ሌላ ሰው አጥፉ አጥፉ እንደሚለው ገልጾ ወዲያውኑ እንዲታይ ርዳታ ፈልጎ ነበር የመጣው። እታያለሁ አትታይም በሚል በተነሳው አታካሮ ጣልቃ ገብቼ አረጋጋሁት። ዶክተር ሌላሠው በሦስተኛ ቀኑ ስለሚመጣ እስከዛ ችግሩን የሚያረግብለት መፍትሄ ሰጠሁት። ከዛ ውጪ ግን የኔ ህመምተኛ ወይም ደምበኛ አይደለም" ብሎ ከረባቱን ላላ አደረገ።

"ከሱ ጋር አብረህ ባሳለፉት ጊዜና በካርዱ ላይ የተጻፈውን ስያዩ ... በርስዎ ሙያዊ ግምገማ ሚቹ አቶ ማስረሻ ምን ያህል አደገኛ ነው ይላሉ? በከፍተኛ የአእምሮ ህመም የተረበሸ ህመምተኛ ነው ብለው ያስባሉ?" ብሎ ቦር ቦር ብሎ እየና ወደ ሲራክ ተመለሰ።

"በመጀመሪያ ደረጃ ሌላ ሐኪም እንብቦ ሲረዳ የሚችለው ምንም አይነት ጠቃሚ መረጃ ቻርቱ ላይ አልነበረም። ያየሁትም ሃኪሙ ውሳኔ ነው። እኔ ባየሁት ጊዜና ሁኔታ ግን የምትነገረውን በትክክል የሚስማ ሰው ነው። ከተመለሱ ያለፈባቸው አስቸጋሪ የህይወት ገጠመኞች ከፈጠሩበት ሚንተትና በዘሊኒካችን ውስጥ የምትሰራ እንዲት ልጅ ላይ ካለው ጠንካራ የፍትር ስሜት ሙጢ ለኔ የተጋነነ ነገር አላየሁበትም። አደገኛ ቢሆን ናሮ የዛን ዕለትም ወደ ቤት ሳይሆን ወደ ሆስፒታል ንበር የምልከው። ዋናው ሐኪምም ሆስፒታል አስተኝቶት የሚያውት አይመስለኝም" አለና ዘና ማለት ሲጀምር ድምጹም በራስ መተማመኑን ያሳይ ነበር።

ሳንቾና ሲስተር ዘቢባ ጆሯቸውን ማመን አቅቷቸው ራሳቸውን ከግራ ወደ ቀኝ ያወዛውዛሉ። የማስረሻ ቤተሰቦች ደግሞ በያንዳንዱ መልሱ አንጀታቸው እየራሰ ሞንትላታቸውን ላይ ታች ይነቀንቃሉ። ሌሎች ጥያቄዎችንም ያለ ብዙ ማመንታትና

@OLDBOOOKSPDF

ግራ መጋባት ሲመልስ ቀይጮ አታቢ ሕጉ ተጨማሪ ጥያቄ እንደሌለው ተናገሮ፣ ዶክተሩን አመስግኖ ወደ ቦታው ተመለሰ። ከባሻገር ምልልሱን ስትከታተል የነበረችው ጆሮው ማመን አልቻለም። ሲራክን እንደ አንድ ገበዝ ቲያትረኛ አድንቶት በረጅሙ ተነፈሰ።

የመሃል ዳኛው ወደ ውዳሴ ዞር ብለው ምስክሩን ለመጠየቅ ዝግጁ መሆኗን ጠየቁ። ፈጠን ብላ ተነስታ ወደ ሲራክ የሚቻለውን ያህል ቀርባ ቀመች። ሁለቱም የለብሱት ልብስ መመሳሰሉ ተመካከረው ያደረጉት ይመስላል።

የምጸት ፈገትታዋን ብልጭ አድርጋ፣ "ዶክተር ሲራክ የሚገርም ነው ... ተመሳሳይ መልበሳችን ..." ስትል ትክሻውን ሰብቀ አጸፋውን የምጸት ፈገግታ መለሰላት። ላቢላ ጠበቃዋ ማን መሆኗን ስታውቅ የሆነ ደስ የማይል ስሜት ተሰማት።

"የክሊኒኩ ሜዲካል ዳይሬክተር እንደ መሆንዎ ... ባጠቃላይ የክሊንካችሁን ስራና ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት እንዴት ያዩታል ዶክተር?" ስትለው፣ ያልጠበቀው ጥያቄ ነበር።

"ጥሩ ነው ... ብዙ ሰው ደስተኛ ነው ... ብዙ ለመታየት መረፋ የሚጠብቁ ሰዎችም አሉ። ክፍያው ከብዙ ክሊኒኮች አንጻር በጣም ከፍ ያለ ቢሆንም አገልግሎቱም ላት ያለ ስለሆነ ... ጥሩ ነው ባይ ነኝ። ዶክተር ሌላው በተደጋጋሚ ቢተሰቡ ጋ አሜሪካን አገር መሄዱ የተመሰነ ጫና ቢኖረውም። ልክ የሚቹ የአቶ ማስረሻን ጉዳይ ዓይነት ..."

"ጥሩ ነው ... ዶክተር ... ያትርታ ወጣት ሃኪም ስለሆኑ ... አንተ ብዬ ብጠራዎ ቅር ይልዎታል ...?" አለች፣ ፈገግ ብላ ዓይን ዓይኑን እያየች።

"ችግር የለም ..." አለ ባጭሩ ወደ ማዶ እያየ።

"ከክሊንኩ ስታፎች ጋር ያለህን ግንኙነት እንዴት ታየዋለህ?" ስትል፣ አታቢ ሀጉ ሃሳቡ ዝምድና የሌለው ጉዳይ በመሆኑ ጥያቄው ውድት እንዲሆን ጣልቃ ሲገባ ዳኛው፣

"ዶክተር ጥያቄውን መመለስ ያስቸገርሃል?" አሉ ረጋ ባለ ገጢ ድምጽ።

"ምንም ችግር የለም ... እንዳንድ የስራ ላይ አለመግባባት ካልሆነ ... ምንም የተለየ ነገር የለም ... ጥሩ ግንኙነት እንደነበረን ነው የማውቀው።"

"ኦህ እንደነበራችሁ ... አሁን ችግር አለ...?"

"ባንዳንድ አሰራሮች ስላልተስማማን ... ከተወሰኑት ጋር እም ..." አለ፣ የሚቀጥለውን ጥያቄ መገመት እያታተው።

"ዛሬ በሀመም ምክንያት ልትገኝ ያልቻለችው ወይዘሪት ምስጢር ስተፈጠረው ችግር ዋነኛ ምክንያት ናት ብል ስህተት ነው ትላለህ?"

@OLDBOOOKSPDF

ትከሻውን ሰበቅ ከንፈሩን ጠመም አድርገ፣ "እንደሱ ማለት መቻሌን አላውቅም ... እስከማውቀው ግን የአቶ ማስረሻም አንዱ የውስጥ ትግል ሰሷ የነበረው ፍቅር ነው ... በስፍራው ባልኖርም የሞተ እለትም በስፍራው መኖሯንና የግሞቱ መንስኤ እንደነበረች ሰምቻለሁ" አለ ።

"ከወይዘሪት ሚስጥር ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን አይነት ነው?" ስትል የነገሩን አካሄድ አልወደደውም ። ምስጢር የሚለው ስም የሳቢላን ቀልብ ስቦት ጆሮዋ ቆመ ።

"ምንም የተለየ ግንኙነት የለንም ... በቃ ተማሪ ሆና ለልምምድ ስትመጣ ለጥቂት ሳምንታት በኔ ስር ሰርታ ነበር ። በኋላም የዚህ ክሊኒክ ጉዳይ አቀራርቦን አብረን ስለምንሠራ ... የሥራ ባልደረባነት ...ሌላ ...እም...ም እናቷ ታመው የተመለሰ ልረዳት ሞክሬ ነበር" ብሎ፣ እጁን ከፍ ዝቅ አድርጎ ዝም አለ ።

"ዶክተር አንተ ለሚስጥር የተለየ የፍቅር ስሜት የለህም ወይም በፍቅሯ አልተያዝክም?"

አቃቤ ህጉ ዘለሎ ተነሳ ። "ክቡር ፍርድ ቤት ... ይሄ ግምታዊ የሆነ አካሄድ ... ፍርድ ቤቱ ከያዘው ሞብጥ ጋር የማይያያዝና የምስክሩን ስሜት ለመረበሽ የሚደረግ ትርጉም የለሽ ጥያቄ ስለሆነ ተቃውሞ አለኝ ።" ዳኛው ጥያቄውን ውድቅ ሲያደርጉት ወደ ዴስኳ ተመልሳ የተመለሱ ወረቀቶችን ይዛ ተመለሰች ። ሲራክ ትንሽ የተረበሸ ይመስላል ። ሳቢላን ከሩቅ ሲያያት ረዘም ላለ ጊዜ አቀርቅሯ ስለነበር ጨነቀው ።

"ዶክተር ሲራክ ... በአንድ ወቅት ከአቶ ሰኢድ ጋር ጹላ ቀረሽ ጥል ተጣልታችሁ ነበር ... በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከዶክተር ሌላው ጋር ከፍተኛ ግጭት ላይ ናችሁ ... እውነት ነው?"

እንዴት እንደሚመልስ ሲያስብ ጠበቃው አሁንም ብድግ ብሎ፣ "ክቡር ዳኛ ... ይሄ ከሞብሙ የራቀና ከክሱ ጋር ያልተዛመደ የምስክሩን ስሜት የሚገዳና በግል ጉዳዩ ውስጥ የሚገባ ጥያቄ ነው ... የተከሳሽ ጠበቃ እያናገሩ ያሉት ፍርድ ቤቱ ለምስክርነት ከጠራቸው የሕክምና ባለሙያ ጋር እንጂ ከተከሳሽ ጋር አለመሆኑን ማስታወስ እፈልጋለሁ" አለ፣ እጁን እያወናጨፈ ።

ውዳሴ ፈጠን ብላ፣ "ክቡር ፍርድ ቤት ... አሁን በሚች ሞት ጉዳይ ተከሳሽ ሆኖ የቀረበው አቶ ሰኢድ ብቻ ሳይሆን ክሊኒኩም ነው ። የምስክሩ የዶክተር ሲራክ የክሊኒኩ ሜዲካል ዳይሬክተር ነው ። በተጨማሪም ምስክሩ ከክሊኒኩ ሰራተኞች ጋር ያለው ግንኙነት ከክሱ ሞብጥ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው ። ይህ የምስክርነት ቃል ሁሉ ሲታይ የሚገባው ከዚህ አንጻር ነው ። ከዚህም የበለጠ ለፍርድ ቤቱ ማሳየት የምፈልገው ጠቃሚ ነጥብ ስላለኝ ... ክቡር ፍርድ ቤቱ ምስክሩ ጥያቄውን እንዲመልስ እንዲፈቅድ በትህትና አጠይቃለሁ" አለች ።

ዳኛው ዶክተር ሲራክ እንዲመልስ ትእዛዝ ስለሰጡ አቃቤ ህጉ ዘሎ ብሎ ተቀመጠ ።

@OLDBOOOKSPDF

"ከአቶ ሰኢድ ጋር የተጣላነው በሥራ ላይ በተፈጠረ አለመግባባት ሲሆን ... ያንተታ ጠይቂው ችግራችንን አርግበን ሰላም ከወረደ ቀይቷል። ከዶክተር ሌላው ጋር የተጋጨነው ግን ራሱ በሚሰራቸው የሕክምና ኤቲክስንም ሆነ የክሊኩን የስራ ፖሊሶች በሚጻረሩ ድርጊቶች ምክንያት ነው" ሲል፣ ተበሳጭቶ የነበረው ጠበቃ ያረው ነቅቶ ማስታወሻ መጻፍ ጀመረ። ንግግሩን በመቀጠል "የተወሰኑ ስታፎችንና ህመምተኞችን የግል ጉዳይ እየተከታተለ እገሌ እንዲህ ነው እገሌ እንዲህ ናት የሚል ሪተቀበረ ሩይል መክፈቱን ደረስኩበት። በሠራተኞቹም ሆነ በስታፉ የጽሑፍና የቃል ፈታድ ሳያገኝ የሚያደርገው ጥናት ስህተት መሆኑን ስነግረው ለምን ተደፈርኩ ዓይነት ቡራ ከረዩ ካልተደባደብኩ አለ። ከሚያጠናቸው ሰዎች ውስጥ እኔ፣ ሚስጥርና ማቹም አቶ ማስረሻ ይገኙበታል" ሲል ፈጠን ብላ፣

"የሚገርም ነገር ነው ... ይህንን የሚስጥር ጥናት አንተ እንዴት ልትደርስበት ቻልክ ዶክተር?" አለች።

"መክሎኝ በሄደበት ጊዜ የሱን ቢሮ ስለነበር የምጠቀመው ... ቢሮው ውስጥ ከበሩ ሩይሎች ጋር ነው ያገኘሁት።"

"እሀ እነዚህን ሚስጥራዊ ሩይሎቹን አይቶልፍባቸውም ማለት ነው?" ብላ፣ አንዴ ወደ እርሱ አንዴ ወደ ዶክተር ሌላው፡ አየች።

"እሱን የማውቀው ነገር የለም" ብሎ፣ ወደ ኋላ ተደገፎ ዝም አለ።

"ምናልባት ካልተሳሳትኩ ... ሁሉም ሩይሎች በጥንቃቄ ተቀልፎባቸው የሚቀመጡ ናቸው። ዶክተር ሌላው በድንገት ተጠርቶ ወደ አሜሪካ ሲሄድ ቁልፉን በችኮላ ሆኖ በሌላ መሳቢያ ውስጥ ረሳው። ቁልፉ እጅህ ሲገባ ካገናውን በርብረህ ነው አይደል ሩይሎቹን ልታገኛቸው የቻልከው? ሩይሎቹን በኋላ እንዳየኋቸው ደግሞ የግል ማስታወሻዎች እንጂ የጥናት ዶኩመንቶች አይደሉም" ስትል፣ አታቢ ሀጉ ትእግስቱ አልቆ እጁን አወጣና፣

"እሁንም ወደማያስፈልግ ዝርዝርና ከክሱ ሜብጥ ጋር ወደማይያያዝ ጉዳይ እየተገባና ምስክሩን በማይገባ ነገር እያደከምናቸው ነው" ሲል፣ ዳኛው ምትእግስታቸው እያለቀ ኖሮ፣

"ይሄ ነገር ወዴት እንደሚሄድ እኔም ግራ እየገባኝ ነው። የተከሳሽ ጠበቃ ልታስረጂን ትችያለሽ ከመቀጠልሽ በፊት?" አሉ፣ ወደ ኋላ ደገፍ ብለው።

"ከቡር ፍርድ ቤት ... የተፈጠሩት ችግሮችና የአቶ ማስረሻ ሞት ከነዚህ ሩይሎች ጋር በቀጥታ ስለሚያያዝ ... ከቡር ፍርድ ቤቱ ከምስክሩ ጋር የጀመርኩትን ውይይት እንድቀጥል ጥቂት እንዲታገሰኝ በትህትና እጠይቃለሁ" ስትል፣ በሜንትላታቸው መስማማታቸውን ገለጹላት።

"ስለዚህ ዶክተር ሲራክ ... በክሊኒኩ ውስጥ ስላሉ ስታፎችና በከፍተኛ ጥንቃቄ ዶክተር ሌላው ስለሚከታተላቸው ህመምተኞች የጻፈው የግል ማስታወሻው ሁሉ ሳታስበው በጅህ ገባ ማለትኛው?

@OLDBOOOKSPDF

"ለኔ የተለየ የሚደንቅ ነገር የለውም" አለ ፣ የነገሩ እባዜድ ባያምረውም ራሱን ለማረጋጋት እየሞከረ ።

"ከቀደምት ምስክሮች እንደሰማነው አቶ ማስረሻ ፣ ከዶክተር ሌላው ጋር የነበረውን ስምምነት ጥሶ ከልታየው ብሎ ከፍተኛ ረብሻ ከሊኒኩ ውስጥ ፈጥሮ ነበር ። ሲስተር ዘሪባ እንድታየው ስትጠይቅህ ሳታንገራግር ነበር ያየኸው ። ለምን?" ስትለው ፣

"ምን ማለት ነው? እንደዛ የተረበሸና ራሴንና ሌላ ሰው አጠፋለሁ እያለ ዘራፍ የሚል ሀሙምተኛ ... ለዛውም የራሳችንን የክሊኒኩን ህመምተኛ መመለስ ተገቢ ነው የምትዪው?" ጥያቄዋ እንዳበሳጨው ሆኖ በጥያቄ መለሰላት ።

"እሺ ... ጥሩ ... አቶ ማስረሻን ልታየው ስትሰማማ ... ዶክተር ሌላው ስለሚሰጥና ስለእናቷ ... እንዲሁም ስለ አቶ ማስረሻ የጻፋቸውን ዝርዝር ማስታወሻዎች አይተሃቸው ነበር?"

"ትዝ አይለኝም ... ፋይሎቹን ያገኘኋቸው ከዛ በፊት ይሁን ከዛ በኋላ" አለ ፣ ነገሩ ብዙም ጠቃሚ በማይመስል አይነት ።

"በነገራችን ላይ ፋይሎቹን ሁሉ አይቻቸው ነበር ..." ብላ ለዳኛው ኮፒዎች እየሰጠች "ዶክተር ስላንተ የጻፈው ማስታወሻ በጣም ያስቀጣህ ይመስላል ..." ስትለው ፣ አፉን ጠመም አድርጎ ፣

"እሱ የራሱ የተዘበራረቀ አስተያየት ነው ..." ብሎ ፣ ትከሻውን ሰበቀ ።

"ይቅርታ ዶክተር ... ቅድም አቶ ማስረሻን አንድ ጊዜ ብቻ እንዳገኘኸው ነግረኸን ነበር ። መጀመሪያ ካገኘኸው በኋላ አላየኸው?"

"ዶክተር ሌላው ወዲያው ከአሜሪካ ስለተመለሰ እኔ ላየው አስፈላጊ አልነበረም"

"ከክሊኒክ ውጪም አግኝተኸው አታውቅም?" አለችው ፣ ፊት ለፊት እያየችው ።

"ዊል ... መንገድ ላይ ወይ ካፌ ውስጥ ... ባጋጣሚ ሊሆን ይችላል ። ክሊኒክ ውስጥ ግን አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያየሁት" ሲል ፣

ወደ ዴስኳ እየሄደች "ዶክተር የምትሰጠው ምስክርነት ሁሉ በቃለ መሃላ የታሰረ መሆኑን አትርሳ" ብላ የተተዳ ቴፕ ይዛ ወደ እርሱ ስትመጣ ነገሩ እየጠመመ የሄደ መሰለው ።

"የማስታውሰውን ሁሉ አየተናገርኩ ነው" አለ ፊሯ ተዛ እያለ ። የነገሩ እባዜድ ጓሮቹንም አታቤ ሀጉንም ሰጪን ተስፎ ስለ ያዛቸው ፍርድ ቤቱ ውስጥ መርፌ ብትወድቅ ይሰማል ። ዳኛው በባህርያቸው ወጣ ያለና የተለየ ነገር ሲያጋጥማቸው የነገሮችን ፍሰት ሳያቋርጡ ፣ አስፈላጊ ከሆነም በመሰቀለኛ ጥያቄዎች ውስጥ ራሳቸውም እየገቡ የመጣት ሂደቱን ማተላለፍ የሚወዱ አይነት ዳኛ ነበሩ ። ጥሎቱን የሚመሩት እሳቸው

@OLDBOOOKSPDF

መሆናቸውን ስታውቅ ወዳሴ ቀኑ ቀና እንደሚሆንላት ገምታ ነበር።

"ዶክተር ሲራክ ... መቼ ነበር አቶ ማስረሻን ለመጪረሻ ጊዜ ያየኸው?" ስትለው፣ የያዘችውን ቴፕ እያየ ምን ማለት እንዳለበት እርግጠኛ መሆን አቃተው።

"በትክክል ትዝ አይለኝም ..." ብሎ፣ ጣቱን እፉ ላይ እየጠበጠበ ለማስታወስ ይመስል ጣራ ጣራውን አየ።

"እህ ብዙ አትቸገር ... ልክ እሱ ከመሞቱ አንድ ቀን በፊት ማታ ላይ አርኪባሊና ለአራት ተቀጣጥራችሁ ... ብዙ ምክር እየሰጠኸው አብራችሁ ነው ያመሻችሁት"

"ትዝ አይለኝም ..." ሲል የሚያውቀውን የምጸት ሳቋን ሳቀች። ውስጡ ቱግ ሊልበት ሲል፣ ተስ ብሎ ወደ ውስጥና ወደ ውጪ በመተንፈስ ስሜቱን ሲቀጣጠር ጣረ።

"እንግዲህ ዶክተር ራስህ እንድትነግረን እድሉን ሰጥቼህ ነበር ... ካልሆነ ምን ይደረጋል?" ብላ ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች።

"የማውቀውን ሁሉ የተናገርኩ መሰለኝ" ብሎ፣ ጸጉሩን እሻሸ።

ከንፈሮቿን ራስ ራስ እድርጋ፣ ጉሮሮዋን ጠራረገችና የያዘችውን ቴፕ ወደ ፍርድ ቤቱ ከፍ አድርጋ አሳየች። "በነገራችን ላይ ሟቹ አቶ ማስረሻ፣ እንተም ሆንክ ዶክተር ሌላሠው የሰጣችሁትን ቴራፒ ወይም ምክር ሁሉንም በስልኩ ላይ ቀድቶ አስቀምጦታል። ስለቱንና ቦታውን ጨምሮ አሞር መግለጫ ራሱን እየቀዳ አብሮ አስቀምጧል። ይሄ የሞተ ቀን በፖሊስ እጅ ገብቶ በወንጀል ኤግዝቢት ተይዞ ከነበረው የርሱ ስልክ ላይ የተወሰደ ነው" ብላ ቴፑን ፊቱ አስቀመጠች። አቃቤ ህጉ በስልኩ ውስጥ ያለውን በማስረሻ ተቀድቶ የተቀመጠውን የስልክ ፋይል እጅግ ብዙ በመሆኑ በዝርዝር ስላላየው፣ ደንገጥ ብሎ ጆሮው እንደ አዲስ ቀመ።

"የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ውይይታችሁ እንደሚያሳየው ... በማስረሻ ኬዝ ላይ በደንብ የተዘጋጃህበትና ብዙ ነገር እንደምታውቅ ግልጽ ነው። በውጪ እየተገናኛችሁ እንደምትመካከሩና ልትረዳው እንደምትችል ታል ስለ ገባህለት ይመስላል ከሲኒኩን ማወኩን ትቶ በስላም ሊሄድላችሁ የቻለው። ከዛም በሂደት የነበራችሁ ምክክር እንደሚያሳየው ... አቶ ሰኢድን ዋነኛ ባላንጣውና ወይዘሪት ሚስጥርን የነጠቀው እሱ መሆኑንም አሳምነኸዋል። ለበቀል እንዲነሳሳ ያደረከው መከራ የተሳካ ይመስላል ... ግን ለምን?" ብላ፣ ፊት ለፊት አየችው።

የያዘችውን የተቀዳ ድምጽ ከነማጫወቻው ከፊቱ ስታነሳው ሜንትላቱን እየወዘወዘ ዝም አለ። ዳኛውን ካስፈቀደች በኋላ የተመሰነውን አጫወተችው። እንዴት ምስጢር ከሳንቾ ጋር ባትሆን በሂደት የሱን ፍትር ተረድታ ልትቀርበው እንደምትችል ሲነግረው ያለውን የዶክተር ሲራክን ድምጽ አሰምታ ስታጠፋው፣ ልቡ ጪጓራው ውስጥ የወደቀች ያህል ተሰማው። አቃቤ ሕጉም ይህንን የመሰለ ጠቃሚ መረጃ በፋይሉ ውስጥ ቢኖርም እንዱንም ባለመስማቱ ሀፍረት ተሰማው።

@OLDBOOOKSPDF

"ፋይሎቹ ላይ ያሉትን መረጃዎች በመጠቀም ... ለሚስጥርና ሰሲስተር ዘቢባም የነገርካቸው ነገሮች አሉ። ይህም ዶክተር ሌላው በነርሱ ላይ ያደረገው ሽሬትና የነርሱን ሚስጥር በያዶባዩ እየዘራ መሆኑን ነው። ግን ለምን?" ብላ፣ ጥቂት ጸጥ አለች። እንዶገና፣ ሳንቾ እስካለ ድረስ ሚስጥርን ሊያገኝ እንደማይችል የሚገልጽ የሲራክ ንግግርና የማስረሻን ቁጣ እዘል ዛቻ ሰፍርድ ቤቱ አስደመጠችና ንግግሯን ቀጠለች።

"ደግሞ ... ከዶክተር ሌላው ላይ ከወራት በፊት የባለቤቱን ሰልክ መውሰድህ ትዝ ይልሃል? እስክ ቅርብ ጊዜ ድረስም ከሲ ጋር ትደዋወላላችሁ አይደል? ለምን?" ስትለው፣ የማታውቱው ነገር የሌለ ስለመሰለው ውስጡ ሲናድ በጨረፍታ ወደ ሳቢላ ሲያይ አይኖቿ ፈጥጦ ወደ እርሱ ታያለች። እሷም 'ለምን?' የምትል መስለው።

"ለምን እንደሆነ እኔ ልንገርህ ... ሚስጥርን ትወዳታለህ ... እሷ ደግሞ ላንተ ብዙም ግድ የላትም ... ያንን መቀበል ፈጽሞ የማይዋጥልህ ሆነ። በመሀል ሚስጥርና ሳንቾ ያላቸው መቀራረብ ሲበዛ ቅናት አንዝገበህ ... በዚህ መሃል የዶክተር ሌላው የግል ሚስጥራዊ ፋይሎች እጅህ ላይ ገቡ። ዶክተር ሌላው ስላንተ የጻፈው ነገር ደግሞ ክፉኛ ሞራልህንና ስለራስህ ያለህን አመለካከት ስለገዳው በርሱ ላይም በቂጣ ተሞላህ። ከፋይሎቹ ባገኘኸው መረጃ ውስጥ ማስረሻን የመሰለ በራሱ ችግር የሚሰቃይ ግን ያንተን ዓላማ ሊያስፈጽም የሚችል ኃይል እጅህ እስገባህ።" ብላ ጸጥ ሰትል፣ የሁሉም ትንፋሽ ላፍታ የተያዘ ይመስል ክፍሉ ረሞ አለ። ንግግሯን በመቀጠል፣

"በተፈጠረው እደገኛ እምባነሮ ሳንቾም ማስረሻም ቢሞቱ ተጠቃሚ ልትሆን እንደምትችል ሳታስብ አልቀረህም። ሚስጥርም ልትሞት ትችል ነበር እኮ ... እሱን ወይ በደንብ አላሰብከውም ወይም ደግሞ ለኔ ካልሆነች ለማንም እትሆንም የሚል ራስ መጻድነትህ አሸንፎህ ይሆናል። እንዳልኩት ዶክተር ሌላው ስላንተ ያለው አመለካከት በትልቁ እንድትበቀለው ገፋቱህ። ስለዚህ በትዳሩ ላይ ጣልቃ ገባህ ..." ብላ፣ ወደ ርሱ በቅርብ ርቀት ተጠግታ አፈጠጠችበት።

ከማዶ ሳቢላ ችሎቱን ጥላ እያለቀሰች ስትወጣ አየ። ውስጡ ብው ብሎ ነደደ። መጪረሻ ሊለያዩ ያሙለችው ጥፊ ድጋሚ ፊቱን ክፉኛ ለበለበው። ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ከየት መጣ ሳይባል ተንደርድሮ ከምስክር ሳጥኑ ውስጥ ወጥቶ ባለ በሴለ ኃይሉ ውዳሴን በጥፊ ሲያጮላት ተንገዳግዳ የዳኛውን የችሎት ዴስክ ተደግፋ ባፍጢሟ ከመደፋት ተረፈች። ማንም ያልጠበቀው በብርሃን ፍጥነት የተፈጸመ አስደንጋጭ ትዕይንት ነበረ።

ሰጪ ሁሉ ሲንጫጫ ችሎቱ በተፈጠረው ትርምስ ገበያ መሰለ። ዳኛው በገርናና ድምጻቸው፣ "ሥርዓት ... ሥነ ሥርዓት" ብለው፣ ጠረጴዛውን ደጋግመው ሲመቱ ፖሊሶች ተሯሩጠው ጣልቃ ገቡ። ችሎቱን የበለጠ ለማረጋጋት፣ ዳኛው ችሎቱን ለአጭር ጊዜ አሳርፉ።

ውዳሴም እንዶምንም ራሷን አረጋግታ ደጋግማ ፊቷን እያሻሸችና እፏመድማቱን ለማረጋገጥ ይመስል በእጇ እየነካካች ቀየች። ረዳቷ ውኃ በብርጭቆ ለጥታት ትገሽ

@OLDBOOOKSPDF

ተቅመጠች ። ፍርድ ቤቱ ተረጋግቶ ሁሉም ነገር ጋብ ሲል ዳኛው ችሎቱን እንደገና አስጀመሩ ። የምትናገረው የመጨረሻ ነገር እንዳላት ለዳኛው ስላሳሰበች ፣ ሲፈቀድላት ድምጿን ከፍ አድርጋ

"ከዚህም በተጨማሪ ዶክተር ሲራክ ... ከእሱኛው ጋር ወደ አሜሪካ ለመብረር የዲቪ ቪዛውን ጨርሷል ። የአውሮፕላን ቲኬቱን ቀርጦ ዛሬ ማታ ለመብረር በዝግጅት ላይ መሆኑንም መረጃ ደርሶናል ። በመጀመሪያ በስህተት ያለ ጥፋታቸው የተከሰሱ ደምበኞቼ የቀረበባቸው ክስ ሙሉ ለሙሉ እንዲነሳላቸው በትህትና እጠይቃለሁ ። ዶክተር ሲራክ መ.ያውን አላግባብ ተጠቅሞ የፈጸመው አደገኛ ወንጀል በፖሊስ እስኪጣራ ድረስ አገር ጥሎ የመጥፋት እድሉ ከፍተኛ ስለሆነ ፣ የዋስ መብቱ ተነፍጎ በቁጥጥር ስር እንዲውል ፍርድ ቤቱ ማዘዣ እንዲሰጥ እጠይቃለሁ ። ጨርሻለሁ" ብላ አፏን እያሻሸች ወደ መቀመጫዋ ሄዳ ተቀመጠችና በብርጭቆ ያለውን ውኃ ተጎነጨች ።

አቃቤ ሕጉ ደግሞ ለጊዜው ለምስክሩ የሚቀርብ ተጨማሪ የመስቀለኛ ጥያቄ እንደሌለው ተናግሮ ፣ በምስክሩ ላይ የተረበው መረጃና በፍርድ ቤቱ የተፈጠረው ሁኔታ ተጨማሪ ምርመራ ስለሚያስፈልገው ፣ ፍርድ ቤቱ ከወሳኔ በፊት ሌላ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቀረበ ። ዳኛው ሲራክ የክቡር ፍርድ ቤቱን ስርዓት በመጣስ ባሳየው ድፍረትና የተከሳሽ ጠበቃን በጥፊ በመማታቱ እስርና የገንዘብ ቅጣት በየንበት ። ፍርድ ቤቱ የፍርድ ብይኑን ከመስጠቱ በፊት ተጨማሪ የፖሊስ ምርመራዎችንና መረጃዎችን ለማየት ወሰነ ። ዳኛው ተከታይ ቀነ ቀጠሮውን አሳውቀው ችሎቱ ሲያርፍ ዶክተር ሲራክ በፖሊሶች ግራና ቀኝ ታጅቦ ወጣ ። ሴላሠው ደግሞ ቁሜት ፣ ጸጸትና ንዴት በተቀላቀለበት ስሜት ተሞልቶ ማንንም ሳያናግር አንገቱን እንደደፋ ወደ መኪናው ቸኮለ ።

በሲራክ ሥሰጥ ያየው ልዩ ችሎታ በዚህ ሁኔታ ባጭር መቀጨቱና ተጨናግፎ መቅረቱ ውስጡን አሳረረው ። ሴላሠው ሁልጊዜም ለሲራክ ልዩ ስስ ነው ። በዚህች አገር ላይ ወጥና ጥልቅ ስራ ሊሰራ የሚችል ፣ ረጅም መንገድ የሚሄድ የተክነ የአእምሮ ሃኪም ሊሆን እንደሚችል ከልቡ አምኖ ነበር ።

የግል ማስታወሻ ፋይሉቹን በመጻፉ ራሱን ወነጀለ ። ከፍተኛ ጸጸት ተሰማው ። ተመልሶ ደግሞ በሲራክ ላይ ተናደደበት ። ጸጥ ያለ ቦታ ፈልጎ ጥቁር ቡና ያለ ስኳር እየጠጣ ከዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ ትርጉም ፈልጎ ሊያገኝ አልቻለም ። 'ሰው እንዴት እንዲህ የሚመር ቡና ገንዘቡን ከፍሎ ይጠጣል?' አለ በልቡ ። ከፊቱ የቀረበውን ቡና በትኩሱ ቶሎ ቶሎ ጠጣው ። 'ለነገሩ ... እንዲህ የሚመር ነገር ባይኖር ኖሮ ሴላሠን መራራ የሕይወት አጋጣሚ በምን መርሳት ይቻል ነበር?' ብሎ አሰበና ወደ ምስጢር ጋ ለመሄድ ተነሳ ።

@OLDBOOOKSPDF

፡ 49 ፡

ምስጢር ከሆስፒታል ወጥታ ወደ ቤት ከገባች ሦስት ቀን ሆናት ። ለረጅም ጊዜ አልጋ ላይ ስለቀየች ሰውነቷ ተገድቷል ። በየቀኑ ጠዋት ጠዋት የአካል እንቅስቃሴ ህክምና (ፊዚካል ቴራፒ) ለመውሰድ ሆስፒታል ትመላለሳለች ። ቤት ከገባች ጀምሮ አከሰቷ ወይዘሮ ዘምዘም አልተለየቻትም ። አሁንም የእናቷ የመጨረሻ ቃል ጆሮዋ ላይ ይደውላል ... 'ዘምዘም ... ዘምዘም' የሚለው ። እናቴ እሷ ትሆን? የሚለው ጥያቄ የተሸከመ ስሜት ልቧ ላይ ይንገዋለላል ።

የሳንቾ ያከሰት ልጆች እብረዋት መሆናቸው ጠቅሟታል ። በተለይ ሃሊማ ሁሌም ካጠገቧ ስለማትጠፋ የሃዘኗ መርሻ ሆናታለች ። የፍርድ ቤቱን ሂደትና የተፈጠረውን ነገር ከስማች በኋላ ሳንቾ በቅርብ ይፈታል የሚል ተስፋ ውስጧ አንሰራራ ። እስር ቤትም ቢሆን ሄዳ እስክታየው ድረስ ቸኩላለች ።

የሲራክ ሁኔታ ድብልቅ ስሜት ፈጥሮባታል ። መቼውንም ልትወደው እንደማትችል ገብቷታል ። ራስ ወዳድ ባህሪው ቢያበሽቃትም በሆነው ነገርና ሊደርስበት የሚችለውን ጠንካራ ቅጣት ስታስብ ደግሞ አሳዘናት ። ሲራክ እየጠሱ የሚወዱት ፣ እየሸሹ የሚናፍቁት አይነት ውስብስብ ሰው ነው ። ለብዙ አመታት እስር ቤት ቀይቶ ... ጉስቁልቁል ብሎና ሸብቶ ... ላዩ ላይ ያረጀ ልብስ ለብሶ ... መሄጃው ግራ የገባው ገፍጓፋ አዛውንት ሆኖ ... ባይነ ህሊናዋ ታያት ።

በረንዳው ላይ ተንጋልላ የሆነ ያልሆነውን ስታስብ ቆየች ። ላይዋ ላይ የተኛችውን ድንክዬ ውሻዋን ስታሻሽ ሠራተኛዋ ስልኳን አቀበለቻት ። "ስልክ ... ሚሚዬ ... ቁርስ ደርሷል ደግሞ ... እዚሁ ይምጣልሽ እንዴ" ስትላት ፣ ፊቷ ላይ ያረፈውን ፀሐይ በእጇ እየከለለች ማን መሆኑን ስታይ ሌላው ነው ።

ስልኩን ወደ ጆሮዋ እያስጠጋች "ቀዪኝ አንዴ ..." አለች ። ሌላው እየዶረሰ መሆኑንና እንድትዘጋጅ ነገራት ። "በቃ ዶክተር ሌላም እየመጣ ስለሆነ ፣ ቁርሱ ሳሎን ይቅረብ ። ትዬ ዘሚስ?" ውሻዋን እንደታቀፈች ብድግ አለች ።

@OLDBOOOKSPDF

"እሱ ... ጓዳ ናቸው ... ዛሬ ሆስፒታል ትሄጃለሽ እንዴ?"

"እይ ... ዛሬ የለኝም ግን ከዶክተር ሌላ ጋር ወጣ ለማለት አስበናል። ወዴ ግታ ላይ ተመልሰን እንመጣለን ... ውይ ... ታፍኜ ልሞት እኮ ነው"

የተገረከረከውን ጋቢ ሰብስባላት ተከታትለው ገቡ። "ይሻላል ሚሚዬ ... ኧረ ... እንዲያውም ወዴ ውጭ አገርም ቢሆን ... እንዶ ሰዒ ጣሊያን ወይ ፈረንሳይ ሄደሽ ለምን አረፍ አትይም? ... ለምኑ ነው ... ሲኖሩ ነው መኖር ..." ስትላት፣ ከት ብላ ሳቀች። "ምን ያስቅሻል? ... የውነቴን ነው እኮ ሚሚዬ ... እገዚያሀር ትረፊ ብሉሽ እንጂ ... የኔ ናት ... ዘና ዘና ማለት ነው ... ለየትኛው ሕይወት ነው? ከፉ ከፋውን መርሳት ነው" ብላ፣ በስስት ዓይን አየቻት።

ወዴ ጓዳ ገብታ ለጉዞ ስትዘገጃጅ ብዙም ሩቅ ስላልነበረ ሌላውም ደረሰ። ቁርሱ እየቀራረበ ሳሎን የተከፈተውን የሲኤንኤን ዜና እያየ ከወይዘሮ ዘምዘም ጋር ወሬ ጀመሩ። ሁሉንም ነገር ዛሬ ሊነግራት እንዳሰበ አሚወታት። ነገሩን እንዴት ሊነግራት እንዳሰበ ነገራትና እሷ እንዴት ልትወስደው እንድምትችል እርግጠኛ ስላልሆነ ሊጨነቅ ማደሩን ነገራት።

ተነሥታ መጋረጃዎቹን ሁሉ ከፋፈተችና፣ "ውይ እንደዚህ ፍንትው ሲል እንዴት ደስ ይላል ልጄ? ግዴለሀም ከዛሬ የተሻለ ቀን አይመጣም። እንተ አንዴ ከጀመርከላት ... ለኔም ይቀለኛል" አለች። ከጓዳ የምስጢርን ድምጽ ሲሰሙ ርዕሱን ቀይረው ስለ ዜናው ማውራት ጀመሩ። ተለል ያለ ጥቁር ቁምጣና አረንጓዴ ቲሸርት በጥቁር ሽራ ጫማ አድርጋ ብቅ ስትል በጨለማ ውስጥ ተደብቃ የምታብረቀርቅ ፈርጥ መሰለች። ብዙ ከብደት ስለቀነሰች ገና እያደገ ካለው አፍሮ ጸጉሯ ጋር ሽንትጥና ቅልል ብላ ትንሽ ልጅ መስላለች።

"ሚሚዬ ... እንዴት እንዳማረብሽ ...ውይ በቃ እኮ የነመልሀት እኩያ አንድ ፍሪት የሃይ ስኩል ተማሪ መሰልሽ እይደል እንዴ?" አለች፣ አቅፋ እየሳመቻት። መልሀት የሷ የመጨረሻ ልጅ ስትሆን ከምስጢር ጋር የተለየ ቅርበት አላቸው።

እሷም አጸፋውን ሳመቻትና፣ "ትዬ ዘሚዬ ... ነው ብለሽ ነው?" አለች፣ በጇ የያዘቻት ትንሽ አረንጓዴ የእጅ ቦርሳ ሶፋው ጠርዝ ላይ ጣል እያደረገች።

ሌላውን ሰላም ብላው ወደ ቁርስ ቀርበው ተቀመጡ። "እነ ሃሊማ ትምህርት ቤት ሄደው ነው?" አለ፣ ከመጣ ጅምሮ ስላላያቸው።

"አይ የፊልድ ጉብኝት አለን ብለው በጠዋት ነው የወጡት" አለች፣ ምስጢር እንዶ ልማዷ የተጠበሰው ዳቦ ላይ የሚቀባውን እየቀባባች። እትከልትና እንቁላሉን ጻቦው መሀል ከትታ የሰራችውን ሳንድዊች በትልቅ ስኒ በተቀዳላት የሙስኘ ሻይ እያወራረደች።

@OLDBOOOKSPDF

"እማማ ተዋቡ እንዴት ናቸው?" አለች ከሆስፒታል ከወጣች ስላላየቻቸው። መጀመሪያ ላይ ያስፈራት የነበረው በህመሙ የተጎዳ ፊታቸውና ሰውነታቸው፣ አሁን ለምዳው እይረብሻትም። ከውስጣቸው የተደበቀውን ደግና ሃዘን የሰበረውን ማንነታቸውን ማየት ጀምራለች።

"ደህና ናቸው... ያው እርጅናውም ... መጐዳቱም ተጨምሮ ድክም ይላቸዋል። እኔ ከሌለሁ ከመኝታ ቤታቸውም አይወጡም። አሁንም የልጃቸው ሃዘን ውስጣቸውን የሚበላው ይመስለኛል። ሁሉንም ነገር ይፈራሉ። እንዴ ቤታቸው እንዲሰማቸው ያላደረኩት ጥረት የለም። ግን ከዚህ ሁሉ የስታይና የልመና አመታት በኋላ በሰብእናቸው ላይ የተፈጠረውን ጠባሳና ጥልት ጉዳት ማዳን የሚቻል አይመስለኝም አለ፣ መብላቱን ትቶ ቡናውን ደጋግሞ ፉት እያለ።

"ዶክተር እስኪ ብላ ..." አለች፣ ወይዘሮ ዘምዘም ከፊቱ እንጆራ እያቀረበች። ወይዘሮ ተዋቡን እንደምታውታቸው መሆን አልፈለገችም።

"ባለፈው ሆስፒታል ከትዬ አታለም ጋር መጥተው ሳይ ...እንዴት እንጆቲን እንደበሉኝ። ቢልላቸው እኮ እሳቸውም ልጃቸው ባትጠፋና እስከ ዛሬ ኖራ ቢሆን እንዲህ አይሆኑም ነበር። ተምራ ትልት ቦታ ብትደርስላቸው የኩሩ እመቤት መሆን ይችሉ ነበር" አለች፣ የወይዘሮ ዘምዘምን መኖርና 'ታሪኩን አለማወቅ' ረስታው። ወዲያው ሰቀት ብላ "ማለቴ ... እሳቸውም ልጅ ኖሯቸው በጊዜ ታከመው ቢሆን ... ለማለት ነው" አለች። ወደ ሌላው በጨረፍታ አየት አድርጋ፣ ይትርታ እንደማለት ብላ ስታቀረቅር ሌላውና ወይዘሮ ዘምዘምም በአይን ተነጋገሩ።

"ትንሽም ፈታ ብለው የሚጫወቱትና ዘና የሚሉት ከአታቲ ጋር ሲሆኑ ነው ... ሲመቻት ወይ መጥታ ታጫውታቸዋለች ወይ ደግሞ እቤቷ ትወስዳቸዋለች" አለ። ቁርሱ እየተንሻሳ ተያይዘው ወጡ።

የቀለበት መንገዱን ጨርሰው ወደ ደብረዘይት መንገድ ሲደርሱ ጠዋት አራት ሰአት ተኩል ሆኖ ነበር። ፀሐይዋ ማታጠል ጀምራለች። መንገዱ በከባድና ቀላል ... ባሮጌና አዲስ መኪኖች ተጨናንቆ የኤሲ ጉዞ ሆኗል። የአየር ማቀዝቀዣ የሌለው መኪና የሚነዳ ሰው ወይ መሥኮቱን ወይ ደግሞ ሞስና አቧራውን ለመጠጣት እንዲመርጥ ይገደዳል።

"ውይ መታሰር እኮ ነው ...ሌላ መንገድ ካልተሰራ ይሄ ቦታ ..." አለች፣ ከሁለት ከባድ መኪኖች መሃል ሆነው ብዙ ሳይንቃነቁ ቀሩ።

"እኔ ሞራሹን ላለማሰብ ነው የምሞክረው ... ለዚህ ነው በተለይ ወደ አሞላ ላንጋኖ የምሄድ ከሆነ የቡታጅራውን መንገድ የምመርጠው" ብሎ፣ እንደምንም ተፈትልኮ ወጣና ለጥቂት ርቀት በነጻነት መንዳት ቻለ።

"ምን እንዳማረኝ ታውታለህ ... ሰፊ ውሃ ... ጸጥ ያለ ... እየተንበሻረቁ ወዘ ማድረግ ... ደብረዘይት እኮ ምንም የለም? ... ላንጋኖ ደርሰን ብንመጣ ይመሽብናል?"

@OLDBOOOKSPDF

ሰዓቱን እየት አድርጎ ፣ ‹‹ኖ ... ቢመሽም ያን ያህል አይመሽም ...ስንመለስ እችላለሁ ... ካልደከመሽ ...››

ሁለቱንም ከንፈሮቿን በጥርሶቿ መሃል አድርጋ ከወንበሯ እንደመቁነጥነጥ እንደ መንጠራራት አለች ። ‹‹እም ...ም ዋይ ኖት ... ጥሩ ነው ... ሳንቾን እየት አድርገው ብናልፍ ግን ይመሻል?›› አለች ፣ ነገሩ እንደማይሆን ታውቋት የግንባሯን ቀዳ ሽብሽባና እፏን ጠመም አድርጋ ። ሳት ብሎ በጎን ሲያያት ‹‹አይ ኖው ...አይ ኖው ... ያው በቃ በጣም ስለናፈቀኝ ነው ›› አለች ፣ በሁለት እጆቿ ጉንጮቿን ሟን ሟን እያደረገች ።

‹‹ነገ አሁድ አይደል ... ለሰኞ ጠዋት ማቀድ እንችላለን››

በመስማማት ሟንቅላቷን ወዘወዘችና ፣ ‹‹እኔ ምልህ ... ከዛ በኋላ ስለ ሲራክ ሰምተህ ታውቃለህ? በጣም ተሰማኝ ትናንት ሳስበው ...አይ ዶኖ ...›› ብላ ፣ ድንገት ትዝዝ ባለ ፊት ሰታየው ፣

‹‹እንድ ሁለቴ ሂጄ ... ላገኘው ሞክሬ ነና ከሩት ሲያየኝ ተሳድቦ ተመለሰ ። ታላቅ ወንድሙ ነው መሰለኝ ባለፈው ደውሎ የዛቻ መአት አውርዶ ተመነጫጨቀብኝ ። ያልገባው ነገር እኮ ... ሲራክ ራሱ በሠራው ወጥመድ ውስጥ ነው የገባው ... እኔ ምን ሳደርግ እችል ነበር ። የኛን ኪዝ ይዛ የነበረችው ጠበቃ ደግሞ የቀድሞ ገርል ፍሬንዱ ነበረች መሰለኝ ። ለነገሩ ልጅቷ ግን ብታያት የምትገርም ጂኒየስ ... ከሰማይ የወረደች ፈንጂ ናት ። እንደ እሷ አይነት ጠበቃ እዚህ አገር ይኖራል ብዬ አስቢም አላውቅም ።››

‹‹ኦህ ... ሪሊ ... የሲራክ ገርል ፍሬንድ? ... እና የለመደች ጦጣ ... ገርል ፍሬንዱ መስላው ነው ፍርድ ቤቱ ውስጥ በጥፊ የመታት? ... ሊመስለኝ ... ሊመስለኝ ... ደካማ ጎኑን ስለምታውት ... ሳትሰራለት አትቀርም ። ግን እሱ ልጅ ስንት ገርል ፍሬንድ ነው ያለው ... ልጹ እንደ ጠቢቡ ሰለሞንም ያደርገዋል እንዴ?›› ስትል ፣ ሁለቱም ሳቁ ።

‹‹ኤኒ ዌይስ ... የሚያሳገኘው ... የባከነ ችሎታ መሆኑ ነው ። እንደተወረሰ እቃ ታሽጎ ሊበሰብስ ነው ... አሁንም ማመን ነው የሚያቅተኝ ... እንዳንዴ ራሴን እወቅሳለሁ ...›› ብሎ ፣ መሪውን መታ አደረገ ።

‹‹ደግሞ ለምንድነው ራስህን የምትወቅሰው? ለኔ ግን ምንም የባከነ ችሎታ አይታየኝም ... በጊዜ የተቀጨ መርዘኛ አረም ነው ። እሱ ያሰበው ሁሉ ቢሆን ብለህ እስኪ አስበው ... የፈለገውን ሁሉ ብሎና አድርጎ ፣ ይሄንን ሁሉ ሰው እሳት ላይ ጥዶ እሱ ሚታ ወደ አሜሪካ ሊበር ነበር ። ... ኧረ በናትህ ...ተው እንጂ ዶዘተር ሌላ›› አለች ፣ ፊቷ ላይ ቁጣና መንገሽገሽ አይነት ስሜት እየታየ ። የሲራክን ጉዳይ ለማስወጣት ይመስል መስኮቱን በሷ በኩል ከፍታ በረጅሙ ተነፈሰች ። ምሾን አልፈው ስለ ነበር መንገዱም እየሩም ሞለል አለ ።

‹‹ቢሆንም ... ለኔ እሱን ለአስራ አምስትና ሃያ አመታት እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ማየት ማሰብ አልችልም ... የማስረሻ ቤተሰቦችም በቀላሉ የሚለቁት አይመስለኝም ።››

@OLDBOOOKSPDF

"እና ሳንቾ ያንን ያህል ዓመታት ባልሰራው ወንጀል እስር ቤት ውስጥ ይበስብስ? ... ማሰረሻ መሞቱን እትይ ... እኔ ወይም ሳንቾም እንሆን ነበር እኮ ሚቾቹ ... ሲራክ ወንጀለኝነቱ ባይዋጥልህ እንኳን አደገኛ ሰው መሆኑን ልትክድ የምትችል አይመስለኝም"

መከራከሪያ ነጥብ ስላልነበረው "ልክ ነሽ ... ልክ ነሽ ... በተበላሸ የሰብእና መዋቅር ውስጥ የተፈጠረ ድንት ሞንትላት ያለው ልጅ ነው" አለ።

"ለኔ ግን ሊሰራ በማይችል ሁኔታ ከተበላሸ ማርሴዲስ ቤንዝ በትክክል የሚሰራ ጋሪ ይሻለኛል።"

"ያስኬዳል ..." አለና አላብ ውስጥ ገባ።

"እሺ ... የሲራክ ችግሩ የተዘባ የሰብእና መዋቅርና አስተዳደግ ነው ሊሆን ይችላል። አሁን ግን ደንበኛ ሳይኮፓት የሆነ ናርሲሲስቲክ ሰብእና ያለው በራሱ የተሞላ አደገኛ ሰው ነው። ስርሱ የሚጠቅም የመሰለውን ማንኛውንም ነገር ከማድረግ አይመለስም። እንዲያውም ትልትነቱን በሰው ስቃይና በበላይ በሚያንበረክካቸው ሰዎች ብዛት የሚለካ ያልበረደ ቁጣ ይዞ የሚዘር የተረበሸ አብድ ነው የሚመስለኝ።

"እሺ እስር ቤት ባይገባ ኖሮ ... ችግር አለብኝ ብሎ አመነልህ እንበል ... ከዚያም ፈቃደኛ ሆኖ አብረኸው አምስት አስር አመት ብታየው ... የሚድን ነገር ያለው ይመስልሃል? ... አንተ እንደምትለው ሲራክ የሚባል ደግና ንፁህ የኢትዮጵያን የስነልቦና ገጸና ቲያሽና ፈር ቀዳጅ የአእምሮ መሀንዲስ ሊሆን ይችላል ብለህ ከልብህ ታምናለህ?" ብላ ዓይን ዓይትን ሰታየው፣

"ተስፋዬ እሱ ነበር ... አውንግን ... በጠቅላላ የሄደውን ርቀት ... ከሩት ለመቦራት ያለውን ችሎታና ፍላጎት ሳይ ... እውነቱን ለመናገር እኔ መስማት የምፈልገው እውነት ሴላ ቢሆንም ... በጣም ነበር ያስፈራኝ ... የሚቻል አይመስለኝም ... ስብእናው ሲስተካከል በማይችል ደረጃ ሳይበላሽ አልቀረም" ብሎ፣ ግምባሩን መታ መታ አደረገ።

"አይ አም ሶሪ ... ግን ደግሞ ከሱ የተሻለ ሴላ ሰው ይኖራል ... ሲራክ ብቻ አይደለም ያለው ... ምን አልባት ተስፋ ሳይቆርጡ ማየት ነው" አለች፣ ውስጡ ምን ያህል እንደ ተገዳ ስታይ የምትለው ጠፍቷት።

"ሴላ ሰው ሀ...ም ... መጠበት ነዋ ... ሴላ ሰው እስኪገኝ ... ችግሩ ኮ ሲራክም ሴላ ሰው ነበር የመሰለኝ ... ሰው ሁሉ ውጪው ሴላ ... ውስጡ ሴላ ሆኖ ተቸገርን። የሰውን እውነተኛ የውስጥ ማንነት የሚያሳይ መነጽር ቢኖር እንዴት ጥሩ ነበር ..."

"እኔስ እሱ ይቅርብኝ ... ሰው እንኳን ውስጡን አይተኸው ... ውጪውንም አውቀ መኖር ከባድ ነው። ውስጡን ስቲስ እንዳሉት ... ጊዜ ይግለጠው ... እግዜር ሽፍኖ የሰወረውን ... ሲገለጥ ይገለጥ እንጂ ... ማፍቀርም ... ሃጢያንም የምንችለው ... ጓደኝነትም ሁሉም ትርጉም ያለው ... በሥጋ የተለበጠውን ... በልብስ የተሸፋፈረውን ... ከውስጥ ያለውን ሴላ ሰው ... ስለማናውት ይመስለኛል ..." ስትል፣ ሞንትላትን በመስማማት ወዘወዘ። ለረጅም ደቂቃዎች በጸጥታ በየራሳቸው ዓለም እየዳከሩ ነዱ።

@OLDBOOOKSPDF

ዝሞይ ላይ ሲደርሱ ፣ "ውይ ውሃ እንዴት እንደጠማኝ" አለች ።

"አሀ ... ሶሪ ... ዝም ብዬ ... ኮ ... መቂ ላይ እንድንቀም አስቢ ነበር ...አሳብ ውስጥ ገብቼ ..." ብሎ ግራና ቀኝ እያዩ ትንሽ እንደነዱ ፣ ደሀና ከመሰላቸው አንድ ካፈ ዝ ። እሱ ቡና አሲ ደግሞ አምቦ ውሃ አዘው በረንዳው ላይ አረፍ አሉ ። ከዚያ ወጥተው ላንጋኖ ሳባና ሲደርሱ ሰባት ሰአት ተኩል ነበር ። ከምሳ በኋላ ታች ወደ ሐይቁ ወርደው ከንድ ፖንጥላ ስር ተቀምጠው አይስክሬም አዘዙ ።

ከባሻገር ለሰስ ያለ ንፋስ እየገረፈው ወደ እነርሱ የሚንደረደር የሚመስለው ሽጉማ የላንጋኖ ሃይቅ ፣ በአሸዋ ከተቀመጠለት መለን ላይ እየተላተመ ይመላለሳል ። ድንገት ብድግ አለችና ሜሪማሞን መለት መለት አድርጋ ወደ ሃይቁ ስትሮጥ ፈገግ ብሎ ቢይኑ ተከተላት ። ወደ ሃይቁ ዳርቻ ስትደርስ እየተንቦጫረቀች ... ወደ ባሻገር እያየች ... እየቦመች ... ደግሞ ባሸዋው ላይ እየሮጠች ... ርቃ ሄደች ። ዘራ ስታየው እጁን አውለበለበላት ።

ተመልሳ ስትመጣ ጥቂት ስለሮጠች ኢያለከለከች ነበር ። "ወይኔ ... አሁን ተርጠና ነው ... ምን ያህል አትመ ቢስ እንደ ሆንኩ ... አሰ...ር ኪ....ሎሜ...ትር ነበር... እኮ ባ...ንድ ትን...ሩሽ የም...ሮ...ጠው ..."

"እንዲየውም ገበዝ ነሽ ..." አለ ፣ ወደፊት አንድ ቀን በመስቀል አደባባይ ደረጃዎች ላይ እየተሽቀዳደሙ ሲሮጡ ባይን ህሊናው እየታየው ።

"እኔ ምልሽ ገነት ብትገኝ ... ምን ትያለሽ?"

"ኑ ኡ ብዬ ነው የምሮጠው ... ከነልብሴ ነው ውሃ ውስጥ የምገባው..."

ፈገግ ብሎ ሁለት ፎቶግራፎችን ሰጣትና ፣ "አንቺ አሞሽ ተኝተሽ በነበረ ጊዜ ተነሽች ..." አለ ።

ቀልዱን መሆኑን እርግጠኛ ሆና ፎቶውን እየተቀበለችው ፣ "እቤት ውሽት ..." አለች ። "እም ...ም ... የም'ር ... ማናቸው እነዚህ?" ብላ ፣ የሁለቱን ወጣቶች ፎቶ ወደርሱ አቦረቃቸው ።

"እሱ ማንን ይመስላል?"

"እቤት ውሽት ... እኔ ነኝ እንዳትል ... አያ ገፈራ ... ደግሞ እንዴት ቀጫጫ ነገር ነበርክ ... ይቺ ናት ገነት?"

"አስረኛ ክፍል ስንጨርስ ... ገነት አንደኛ እኔ ሁለተኛ ነበር የወጣነው ... ቀንጅ ናት?"

"እኔ ኮ አላምንህም ... ወይኔ ... እንዴት ታምራለች ... በጅሊነትም በጣም ትበልጥሃለች ... የም'ር በናትህ ልቤን አትስቀለው ... ገነት ናት?" ብላ ሌላውን ፎቶ እያየች "ው.ይይይ ... የኔ ጌብዬ ... ይቺስ የማናት ልጅ?"

@OLDBOOOKSPDF

"በደረሰኝ መረጃ መሰረት ... ገነት እንድም የጠፋችበት ምክንያት ... እናቴ በተናገረቻት ከፉ ቃልና እኔ በመሄዴ ምክንያት ብቻ ሳይሆን አርግዛ ነበር። ነገሩን ለኔ ብትነግረኝ የኔን ሀይወት መረበሽና ዕድሌን ማሰናከል ስለ መሰላት እንደዛ ማድረግ አልፈለገችም። ይቺ የምታያት ከዛ አርግዝና የተወለደችው ልጅ ናት ..." ሲላት፣ ነገሩ እውነት መሆኑን ወደ ማመን መጣች።

"ው-ይ-ኔ ... እንዴት አይነት ኪክ የሆነች ልጅ ናት ... ሁለታችሁንም የምትበልጥ እንደኛ ቀንጆ ልጅ ...ኡሁሁሁሁ ... በናትህ እንዴ እያየኋቸው ሙኪ ልምጣ ..." ብላ መልሱንም ሳትጠብቅ እየጮኸች ወደ ሃይቁ ሮጠች። ከዳርቻው ስትደርስ እንደነና ጉሮሮዋ እስኪዝል ጮኸች። ከዛ ደግሞ ዳርቻውን ይዛ ስትሮጥ ቀይታ እያለከለከች መጥታ ተቀመጠች።

"እንዴ ዶክተር ሌላ ... ዚስ ኢዝ ሶ ... እንብሊቨብል እኮ ... ታዲያ የት ናቸው እሁን ... እዚህ አገር አይደሉም? እገኘሃት ገነትን ... እዋራሃት?" እያለች፣ የጥያቄ መአት ስታዘንብበት ከኪሱ የታሸገ ፖስታ አወጣቶ ሰጣት።

"ብዙው ነገር እዚህ ውስዋ አለ ... እኔ ከምነግርሽ እጪው ..." ሲላት፣ የያዘውን የታሸገ ፖስታ የመንጠቅ ያህል ተቀበለችው።

"እንዴ ታሸጓል እኮ..."

"ከፈቺው ... ዛት ኢዝ ኦኪይ ..." አለና ወንበሩን ጠጋ አድርጎ አጠገቧ ተቀመጠ። ፖስታውን ስትከፍተው ለማገዝ አስመስሎ ተቀበላትና ውስጡ ከነበሩት አንዱን ደብዳቤና ፎቶዎች ሰጥቷት "መጀመሪያ ይሄንን እይው ... ከዛ ደግሞ ይሄንን ታዪዋለሽ ብሎ ከእናቷ ከወይዘሮ ኤደን የተጻፈውን ደብዳቤ ከፖስታው ጋር ያዘው። ፎቶዎቹን ስታያቸው የሌላሠውና የገነት አብረው የተነሱት ሌላ ፎቶና የሀጻኗ ፎቶ ለብቻዋ ዳዴ ስትል፣ አንደኛና ሁለተኛ አመት ልደቷ ሲከበርላት እንዲሁም ከእናቷ ከገነት ጋር የተነሡት ነው።

"እውይ ... እንዴት ታምራለች ... ይሄኔ ኮ ምን አዘላ ይሆን ...የትልቅነቷ ፎቶ የለህም?" አለችና፣ ቀና ብላ አየችው። ደብዳቤውን ካልወሰድኩ እያለ ከግራ ከቀኝ የሚንሸዋሸወውን ንፋስ ለመከላከል ጠበቅ አድርጋ ያዘችው።

"መጀመሪያ እሱን አንብቢውና ..." ሲላት፣ ጎንበስ ብላ ደብዳቤውን ማገበብ ጀመረች።

'ልጄ ሀይወቴ ... መጽናኛዬ ደስታዬ ... ማስታወሻዬ ሚስጥሬ ...
ልጄ

አሁን ትንሽ ልጅ ነሽ። ሁሉንም ነገር ብነግርሽም ምንም አይገባሽም። ሁሉም ያስቅሻል ሁሉም ነገር ላንቺ መጫወቻ ነው። ልክ እንዳባትሽ ልፊያ ጨዋታና ቡረቃ ትወጂያለሽ። ሳቅሽና ንጭጭትሽ እሱን ያስታውሱኖል። እኔና አንቺ የሄድንበት ገዳና ያሰፍንበትን መከራ እሱ አያውቅም። ግን አትታየሚው እኔ ስላልነገርኩት ነው እንጂ ቢያውቅ ኖሮ

@OLDBOOOKSPDF

እንደማይለየን እርግጠኛ ነኝ። አንቺን ማርገዜን ሳውቅ እሱ ደግሞ ሩቅ ሃገር መሄድ ነበረበት። የሁላችንም ዕድል ከሚሰናከል ብዬ እኔ አንቺን ሆዬ ውስጥ ድብቅ አድርጌሽ ከሱም ከእናቴም ብን ብዬ ጠፋሁ። ማንም ወደማያገኘኝ ማንም ወደማያውቀኝ አገር።

'ሁሉ ነገር በጨለመብኝ ጊዜ ታምሯ የማያልቅባት እመብርሃን ለኔም ላንቺም እናት ሰጠችን። እናትና አባት ሰጠችን ማለት እችላለሁ። እኔ ላድግ አባት ምን እንደሆን አላውቅም። እኔ የቤት ሠራተኛም ሆኜ ላሳድግሽ ነበር የቀረጥኩት። ግን ፈጣሪ ደግነውና ቤተሰብ ሰጠን። ምሞቴ ሁሉ አንድ ቀን አንቺም አድገሽ አባትሽን አግኝተነው ... እናቴም አብራን ሆና አንድ ትልቅ ደስተኛ ቤተሰብ እንድንሆን ነበር። ግን አሁን እንቺም ገና ሕፃን ላለሽ እኔን ላሸንፈው የማልችል ሀሙም ተጠናወተኝ። የሚደረገው ሁሉ ቢደረግልኝም ባሰብኝ እንጂ ሊሻለኝ አልቻለም። ካሁን በኋላ ብዙ የምኖር አልመሰለኝም።

'ገና ስትረገዢ ጀምሮ አንቺ የኔ ሚስጥር ነሽ። ስትወለጂም ሚስጥሬ አንቺ ነሽ። ከዚያም ሚስጥሬን ሁሉ የተሸከምሽ ሚስጥሬን ሁሉ የማካፍለሽ ጓደኛዬ ሆንሽ። የምንግርሽ ባይገባሽም እኔን የሚያስለቅሰኝ አንቺን ቢያስቅሽም በትንሿ እጅሽ አይኔን እያባበስሽ ታባብዪኝ ነበር። ግንባሬን ጎንጩን ሁለንተናዬን ስትስሚኝ፣ ሚስጥሬ የገባሽ ሀመሜ የተሰማሽ እየመሰለኝ የባሰ ሚስጥረኛዬ አደረኩሽ። ዛሬ አድገሽ ይሄንን ደብዳቤ ስታነቢው ሰንቱ የነገርኩሽ ሚስጥር ትገ ይልሽ ይሆን? ለዚህ ነው ስምሽንም ሚስጥሬ ያልኩሽ። ለጊዜው ሚስጥሬ መገገቡ። አንድ ቀን ግን አሱም ይቀየራል አባትሽን ያገኘሽው ቀን።" የሚለው ጋሰትደርስ ወረቀቱ ከእጇ ወደቀ

"እንዴ ... ም ...ን ... ምንድነው የሚለው? ... ማነው? ..." ብላ ብድግ አለች።

እንደ ምንም እጇን ይዞ፣ "ሚስጥርዬ ... ያቺ ልጅ ... ህጻኗ አንቺ ነሽ ... ሌላው ደግሞ እኔ ነኝ ... ይሄንን ደብዳቤ የሰጡኝና ነገሩን ሁሉ ..." ሲል፣ እጇን አስለቀቀችው። አይኖቿ ተገልጥለው የሚወጡ መሰሉ ... ቆመች ... ራሷን አዞራት። እንዳትወድቅ ጠረጴዛውን ተደገፈች ... ደግሞ አፍጥጣ አየችው። በደመ ነፍስ ፎቶዎቹን ከጠረጴዛው ላይ እንስታ ተራ በተራ አየቻቸው።

ደብዳቤውን አንስታ ለመሄድ ሬቷን አዞረች። በጹ የያዘውን ቀሪ ደብዳቤ "ይሄንንም እዪው ..." አላት። በጸጥታ ተቀብላው ወደ ሐይቁ ጸር ሄደች። አንድ ነገር እንዳትሆን ብሎ ስለፈራ ሊከተላት ፈለገ። ደግሞ ለብቻዋ መሆኗ አስፈላጊ መሆኑን ስላመነ ባይኑ እየተከተላት በተቀመጠበት ቀረ። የሆነው ነገር የስሜት ቋቁን እንደ ጎርፍ አጥለቅልቆት ሲያልፍ ሲያቀመው ያልቻለ እምባ ፊቱን አጠበው።

ከአይኑ እየራቀች ሄዳ ስትሰወርበት ስጋት ነገር ገባው። ተነስቶ ወደ ሄደችበት አትጣፋ አመራ። ከሩት ከጠረጴዛው ላይ ተጥለው የነበሩ ፎቶዎች ሄዶ ምን እንደሚያሞራት

@OLDBOOKSPDF

ወይም እንደሚያደርግ ግራ ገባው። እዛው ከሐይቁ ጸር መደ ማዶ እያየ በራሱ ሐሳብ ውስጥ ተዘፈቀ። ንውሕና ልጆቹ ትዝ አሉት።

ተመልሳ መጥታ ካጠገቡ በጸጥታ ቀመች። "ምን ማድረግ ወይም ማለት እንዳለብኝ አላውቅም" አለ፣ ሀዘን በሰበረው ድምጽ። መልስ አልሰጠችውም።

እምባ ባረጠበው ዓይኗ ሽትብ እያየችው፣ "መ-ቼ ነ-ው ...እን...ተ ... ግን ... ነገሩን ያመ...ትከው?" አለች። በእጁ የያዘውን ገንትና እናቷ ለርሱ የጻፉለትን ደብዳቤ ሰጣት። ከሌሎቹ ደብዳቤዎች ጋር ደርባ ያዘቻቸው። ሴላ የገሙታ ድባብ በመካከላቸው ነገሰ። እንደ ምንም ሐሳቡን ለመሰብሰብ ሞከረ። አይኖቹን በሐይቁ ማዶ ላይ እንደተከለ፣

"እናትሽ ላንቺ ነገሩን ሲነግሩሽ በነበረ ሰዓት እኔንም ሆስፒታል ባስቸኳይ እንድመጣ ነገረውኝ ነበር። እኔ ስደርስ፣ በዛው ሰዓት በነገሩሽ ነገር ተበሳጭተሽ ወይም አላውቅም ምን እንደሆነ፣ ስትወጪ ተሳለፍን። ደብዳቤዎቹን ሰጥተውኝ ገና ነገሩን ሲነግሩኝ ሲጀምሩ ከቤት ተደወለ። መድሃኒት ወስደሽ ራስሽን መሳትሽን ነገሩን። እሳቸውም ኦልራዲ ብዙ ተጎድተው ስለነበር ነገሩን ሲሰሙ በድንጋጤ ተገለፈለፉ። ሁሉታችሁም ባንድ ቀን እይ ሲ ዩ ገባችሁ። የዛን ለታ ማታ እስክ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት ከናንተው ጋር ቀይቼ ወደ ቤት ገብቼ ..." ብሎ፣ ሁሉም ነገር እንደገና ትዝ ብሎት ዓይኖቹ በእምባ ተሞሉ።

መናገር አትቶት ትንሽ ጸጥ ብሎ ቀየና " እሱን ደብዳቤ ከፍቼ ...ሳነ...በው ... ያኔ ነ...ው ..." ብሎ፣ መናገር አትቶት ሲያስቅስ ... የምታደርገውን አጣች። ትከሻው ላይ መታ መታ አደረገችው።

ለቅሶው ጋብ ሲልለት የሱን ደብዳቤዎች እየከፈተች "ማንበብ ይቻላል?" ስትለው ራሱን በአምንታ ነቅንቅ ዝም አለ። ደብዳቤዎቹን ሁሉ ይዛ ለብቻዋ ወደ ሐይቁ ወረደች። በየመሃሉ ለትሰጥ እያቋረጣት እንዴ ጮክ አንዴ ጸጥ ብላ ስታነብ ቀይታ ተመልሳ መጣች። ውሰጧ የሞላው ስሜት ስምና ልክ የሚሰጠው አልነበረም።

እናቷ ትዝ በሚላት የመጨረሻ ታላቸው 'ዘምዘም ... ዘምዘም' ያሉት ትዝ አላትና፣ "ትዬ ዘሚስ መቼ ነው ያወቀችው?" አለችው።

"እሷ የናትሽ ሚስጥረኛ ስለሆነች ... ለረጅም እመታት ሁሉንም ነገር ላታውት አትቀርም" ሲላት፣ ጸጥ ብላ ስታስብ ቀየች።

ድንገት ቀና ብላ፣ "ሉላስ ማን ያውታል?" ስትለው፣

"ካንቺ በቀር ዓለም ሁሉ ነው የሚያውቀው ... ወሮቹም" ብሎ ሳት አለ።

"የምር የምር ..."

"እም ... ም አታቲ ትዬ ተጥቡን ከለሷ ይቅርታ የጠየቀች ቀን ነዝኳት ... አልቅሳ ልትሞት። ደጎም ታውቲያለሽ እንዴት እንደምትወጅሽ"

@OLDBOOOKSPDF

"የኔ እናት ... እሺ ... ለእማማ ተዋቡስ ነገርካቸው? ... ወይኔ አሳቸውም እኮ አያቱ ናቸው ማለት ነው ... ወይኔ ... እኔ አላምንም ... በራሴ በጣም ነው የማፍረው ... መጀመሪያ ያገኘናቸው ቀን እንዳይነኩኝ የፈራሁት መፍራት ...ደገሀ አያቴን ... እንኳን የኔ ዘመድ ቀርቶ ..." ብላ አቷን ያዘች ።

"አሳቸው አንቺ ከመስማትሽ በፊት እንዲሰሙ አልፈለኩም ... ምክንያቱም የልጅቸውንም ሞት አብሮ ማርዳት ስለሚሆን ።"

"የኔን እናት?" አለች ፣ ታሉ አቷ ላይ እንገዳ እየሆነ ። ለወይዘሮ ኤደን ካንቺ ሌላ እናት የለኝም ... አልፈልግም' ያለቻቸው ትዝ አላት ። የተደበላለቀ ስሜት ውስጧን ሞላው ። አባቷ እቶ መዝገቡ ያደረጓት ሁሉ ባይሄ ላይ ለቅጽበት አለፈባት ። ንጹሕና የሌላው መንታ ልጆች ሲሯሯጡ ታያት ... 'እህትና ወንድም ሊኖረኝ ነው?" ... ማሰብ አታታት ። ሌላ ለው የሆነች ... ከሌላ ዓለም የመረደች ... ወይም በሌላ ፕላኔት ላይ ያለች አይነት ... መሰላት ። የምታውቀው ሁሉ የማታውቀው ሆነባት ። የማታውቀው ደግሞ ሁልጊዜም እንደምታውቀው አይነት አብሯት የነረመ ሆኖ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ውስጥ ገባች ። ምን እንደ ተሰማትና ምን እያሰበች እንደሆነ ለማወቅ ተቸገረች ።

"ላንቺስ?" አለች ድንገት ትዝ ብሏት ።

"ለሱ ነግሬው ... ዩ ዶንት ብሊቭ እንዴት ደስ እንዳለው ... ከእስር ቢፈታ እንኳን እንደሀ ደስ የሚለው አይመስልኝም"

"የኔ ናት ..." ያመሰላጣትን እምባ ጠራረገች ።

"ቀይ በናትህ ... ንኒ ... ልበል እናቱ ምን አይነት ሰው ነበረች?"

"ልዘ እንጸንቺ ... ትንሽ በቱንጅና ትብልጥላለች እንጂ ..."

"እምን በጣም ቱንጅዬ ኮ ናት ... ያንተ ፋንጋ ጂን ገብቶ ነው ያበላሸኝ"

"ፎቶዋን ስታዪና ደብዳቤዋን ስታነቢ ... አንቺ ምን አይነት ሰው ትመስልሻለች?"

"እኔንጃ ... ጥሩ ሰው ትመስለኛለች... በጣም ጥሩ ሰው ..." አለች ግራ በገባው ፊት ። አሁንም ሁሉም ነገር ህልም ... እንጂ በእውን አልመስል ብሏታል ። ደብዳቤውን ደጋግማ ታየዋለች ። የጥያቄ መዓት ውስቧ ይንጋጋባታል ። የቱን ጠይቃ የቱን መተው እንዳለባት ግራ ገብቷታል ። "አይ ቲንክ ብንሄድ ጥሩ ነው ። ቤት ገብቼ ... ትንሽ ለብቻዬ መሆን ላይኖርብኝ እይተርም ። አይ ዶኖ ... ይትር'ታ ... ሀልም ነው እውን ... ግድ የለሀም ... ብንሄድ ይሻላል ... ወደ ቤት እንሂድ?" ብላ ብድግ አለች ።

የሚያደርገው ጠፍቶት አሰብ አደረገና ፣ "ትንሽ በሐይቁ ዳር ወዘ እናድርግና እንሂድ ... ወይስ?" አለ ፣ ሊሣዛናት ስላልፈለገ ።

@OLDBOOOKSPDF

"እሺ ..." አለች ትከሻዋን በምን ችገረኝ አይነት ሰበቅ አድርጋ። ይብጸቢዎቹን ለርሱ ሰጠችውና ሚማዎቿን ይዛ እግሮቿን ሐይቁን በእግሯ እያንቦጫረቀች ጉን ለጉን ሆነው ተጓዙ። ተመልሰው መኪና ውስጥ ገብተው መንገድ እስኪጀምሩ አንድም ቃል አልወጣቸውም። ከግቢ ወጥተው ወደ ዋናው አስፋልት ሲገቡ ሲሉ መኪናውን ቆም አደረገና ከጆሮዋ ሥር አንገቷ ላይ ሳም አደረጋት። ዓይኖቿን ጨፈን አድርጋ ሞንቅላቷን በትከሻዋ ላይ እያስተሻሸች ለጥቂት ደቂቃዎች በገሞታ ቀየች።

@OLDBOOOKSPDF

ክፍል ፮

ማሳረጊያ

@OLDBOOOKSPDF

ከሳምንት በኋላ ...

ሐመሉስ ጠዋት ላይ ሳላ ያለ ንፋስ ሽው ይላል ። ሴሊኑን ሙሉ ሲረብብ ያደረውን ሙርሞ ንፋሱ በእየሩ ውስጥ ሲናኝ የሚፈጠረው ቅዝቃዜ አጥንት ይገባል ። የዕለቱ ተረኛ የማለዳ ፀሐይ ፣ ሰፋቱ ያለተባት ደማት የመንገድ መብራት ይመስል ነገሩን ከሩቅ ትታዘባለች ። ሴላሙው በጠዋት ተንስቶ ረጅም መንገድ በእግሩ ተጉዞ ተመለሰ ። የጠዋቱ ንፋስ ፊት ፊቱን ሲመታው ሰላም ያለው ንቃት ፈጠረለት ። ብርዱ ሽንቀጥ ሲያደርገው ሮጥ ሮጥ ብሎ ስውነቱ በሚፈጥረው መሞት ይሞቋመዋል ። ሙቅ ሻወር ውስጥ ተለታለተና ለባበሰ ወደ ሳሎን ወጣ ።

ሠራተኛዋ ሹፈሩ መምጣቱን ስትነግረው በቱሙ አንድ ስኒ ሻይ በቱራሚ ጸበ ማር ተብቶ በላ ። የሥራ ቦርሳውን ይዞ ፣ ጣደፍ ጠደፍ ብሎ ወደ መኪናው ውስጥ ገባ ። ዘበኛው ወደ ሱቅ ወጣ ብሎ ስለነበር በሩን ከፍታላቸው ወጡ ። ብዙም ሳይሄዱ የተጠሩት ሰዎች ስልክ ይመለው እንደማይገኙ ሲነግሩት ወደ ቤት ተመለሰ ።

በሚቀጥለው ቀን ወደ ደብረሊባኖስ ለሚያደርጉት ጉዞ መኪናዋን ሰርቪስ ለማስደረግ ሾፈሩ በደጅ መኪናውን ይዞ ተመለሰ ። ዘበኛውን ሰላም ብሎ ፣ በየጠዋቱ በረንዳ ላይ ተቀምጠው ፀሐይ እየሞቱ የንበሩትን ትዬ ተዋቡን ትንሽ አዋርቶ ወደ ውስጥ ገባ ። ሰራተኛዋ ከጓሮ ካለው ሰርቪስ ቤቱ ውስጥ የሚያስትስውን ሁለተኛ ልጇን እያባበለች ስለነበረ ፣ ተመልሶ መምጣቱንም አላየችም ።

የመኝታ ቤቱን መስኮት ከፋፍቶ አልጋው ላይ ጋደም አለ ። በራስጌው ኮመዲና ላይ ተጀምረው ሳያልቁ እንደተከፈቱ ካሉ መጻሕፍት አንዱን አንስቶ ማንበብ ጀመረ ። ሁሌም ቢያንስ ሦስትና አራት መጻሕፍት ጀምሮ እያፈራረቀ ማንበብ ይወዳል ። መኝታ ቤቱ ከበረንዳው የራቀ አይደለም ። ጆሮውን ጣል አድርጎ በዉኽት የምታወራውን ሠራተኛ ለመስማት ሞከረ ። የሰማውን ማመን ስላልቻለ ካልጋው ላይ ብድግ ብሎ ወደ ደጅ ወጣ ። የሳሎኑን በር ከፍቶ ሲወጣ ያልጠበቀችው ሰራተኛ በድንጋጤ ዘው አለች ።

ፊቱ የተቆጣ ንበር መስሎ ፣ "እንቺ ...! ምንድነው ያልሽው...?" ብሎ ሲጠይት ፣ ሽምቅት ብላ መራት መራት ማየት ጀመረች ።

@OLDBOOOKSPDF

"ግገሪኝ እንጂ ... ማንነው የማንም ቁማጣ ... ለካ አንቺ በር ቀልፈሽባቸው እያሞልሻቸው ነው ..." ብሎ ፣ ሰውነቱ ሲንቀጠቀጥ ቁጣውን እንደምንም ለመቆጣጠር እየሞከረ ፣ "በይ አሁኑኑ ... አሁኑኑ ... አታሽን ይዘሽ አይኔ እያየ ከዚህ ወዲ ምትሂጂበት ..." ሲል ፣ እምባዋ ተዘርግፎ እግሩ ስር ስትንጠፍ ትንሹ ልጁ ደግሞ የግራ ሱሪውን ይዞ ሽቅብ እያየ የናቱን ልመና ለመቀላቀል ይመስል ጪኸቱን ለቀቀው ።

ልጁን ለንሰቶ ለማባበል እየሞከረ ምን ማድረግ እንዳለበት ለጥቂት ጊዜ ግራ ገባው ። አትክልተኛውም ከባሻገር ቀም ብለው መኮትኮቻቸውን ባንድ እጃቸው እያሽከረከሩ የሚሆነውን ያያሉ ። "አሁን ከእግሬ ስር ተነሺ ... የኔ እናት ያንቺን ልጅ ምንካት ከሌለባትና ... በይ አሁን ከዚህ መሄድ አለብሽ ..."

"ሚጡ እኮ ትምህርት ቤት ናት ... የት እባቴንስ ነው የምሄደው ... የዛሬን ማሩኝ ዶክተር ..." ብላ ፣ እንደገና ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። ምንም ቢሆን በልጆቹ አይጨክንም ብላ ሳታስብ አልቀረችም ። ቅድም ውስጥ ሆኖ ትዬ ተዋቡን ቀሻሻ እንደነካው እቃ ስትሰድባቸው የነበረችው ሴት አልመሰል አለችው ። 'ሂጂ ... እዛ ከፍልሽ ግቢ ... ልጄን ሁለተኛ ብትነኪ ... እኔ ሰናፍትሽ አይደለሁም ... አስሬ ነው እዛ ከፍልሽ የምወረውርሽ ... ደግሞ ምን ቁም ነገር ይመስል ...ገና ለማኝ ሳያራ በረንዳው ላይ ወጥታ ጉብ ታላለች...' ያለችው ፣ በሜንትላቱ እንደገና እያቃጨለበት ።

"የማውቀው ነገር የለም ። አሁን እያየሁሽ እቃሽን ይዘሽ ... መሄድ አለብሽ ... በይ ...በይ በፍጥነት..." ብሎ ፣ ማመረራ ገባት ። ልጁን እመርዶ ወዶትዬ ተዋቡ ዘር ሲል ተላቀው የሚሉትና የሚያደርጉትን እጥተው ኩርምት ብለው እንዳተቀመጡ ግራና ቀኝ አይናቸው ይንከራተታል ።

ስራተኛዋ ልጇን ይዛ ወደ ጓዳ ስትገባ እትክልተኛው ሲፈሩ ሲቸሩ ጠጋ አሉና ፣ "እዱ ዶክተር ... ዛሬ እመ ብርሃን የኚህን ምስኪን እምባ አይታ እግር ጣልምት እንጂ ... እኔ እንኳን ባየሁት ...ሙይ ሙይ ... ኧረ ጡር ነው ...እንደ ልጅ እኮ ነው ስታመናሚቃቸው የምትውል ። ኧረግ ኧረግ ... ይሄ ያዘ እምባዋ እንዳያታልልዎ ... እኔ ኮ የርስዎ ዘመድ ስለምትመስለኝ እንጅ ... እኚህ ሁለት እጣናት ናቸው እንጂ ... ልቡን አይቶ እግር ነሳው አሉ ..." ሲሉ ፣ ወደ ትዬ ተዋቡ ዘር ብሎ ፣

"ትዬ ተዋቡ ይሄ ሁሉ ሲሆን ለምን አይነግሩኝም ነበር...?" ሲላቸው ፣

"አይ ልጄ ... ሰንቱ ተነግሮ ይቻላል ... ደግሞ የነዚህ የአምበቀቅላዎች ነገር ይዞኝ ነዋ ... እኔ አንዱ ለምጄዋለሁ ... ባክህ ልጄ ግዴለ ... የዛሬን ይቅር በላት" ሲሉ ይሄ ሁሉም ደርሶባቸው ነገሩን በዝምታ መቀበላቸው ምን ያህል ለራሳቸው ያላቸው አይታና ከብር መጨፍለቁን አይቶ አዘነ ። በሌላ በኩል ደግሞ ህይወትያላየቻቸው ብዙ ውጣ ውረዶችና የሰው ልጅ ጥልቅ የማይድን ክፋትና የበላይነት አባዜን ስለተረዱ ከሦስ ብሎ አሰበ ። በናታቸው ክፋት ሳቢያ ህጻናቱን እውጥቶ ገዳና ላይ መበተኑም አጸተው ። ትልቋ ልጇ ለርሱ ያላት ፍቅርና እንዲያስጠናት ደብተሯን ይዛ ማታ ማታ ወደርሱ ስትመጣ ታየው ። ትንሹ ልጇም የሱሪውን ጪርቅ ጨምድዶ የተማጸነው መሰለው ።

@OLDBOOOKSPDF

ውሳኔውን ላሰመቀየር ጥርሱን ነክሶ ወደ ውስጥ ገባ። የሶስት ወር ደሞዝ ሰዋቷት ልጇን እንጻዘለች ከግቢው ስትወጣ ጸጥ ብሎ ባይኑ ተከተላት። የሙሚ በሩን ከፍታ ልትወጣ ስትል ሀጻኑ ልጅ ዘር ብሎ እጹን ሲያውለበልብ በአጸፋው እጹን አውለብልበ ወደ ውስጥ ገባ። ነገሩ ለረጅም ሰአት ሲረብሸው ቀየ። ማባረሩ ነው ወይንስ በይቅርታ ማለፉ ነው ትክክል? ያደረገችው ነገር ጥፋት ነው ክፋት? የሕሃኑ እድል ነው የትዬ ተሳቦ ስብእዊ ክብር ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው? ሲላ ትኩሰ በኖ አፍልቶ ሁሰት ሲ ቀድዮ ወደ በረንዳው ተመለሰ።

ለምሳ ምስጢር ቤት ሂዱ። እናቱም እዛው ስለነበር ያደሩት ነገሩን አንስተው ሲነሪከሩ ቀየ። ሚስጥር ስልጆቹ ሲባል ይቅርታ ተደርገላት በማስጠንቀቂያ ልትታለፍ ይገባል ስትል እናቱ ደግሞ በክፋት የተሞላ ጨካኝ ሰው ቢይቅርታ አይተየርም። መከሪ ያልመከራትን ምክር አያርታትም ስለዚህ ልጆቹ ቢያሳዝኑም ምንም ማድረግ አይቻልም ብሰው የልጆቸውን ውሳኔ ደገፉ። ሰራተኛ በሌለበት ብቻቸውን ከሚኖሩ ወይ ወይኖቱ ቤት መመለስ ወይ ከምስጢር ጋር ቢኖሩ እንደሚሻል ሃሳቡ ተነሳ።

"እታቲዩ ... አባቢን እድሜውን ሙሉ ካንቺ ጋር እኮ ነው የኖረው። ከእኔ ጋር ገና ... ወርም አልሆነንም እኮ ... እነ አርሲ ሳይወስዱብኝ ... ስለዚህ ከኔ ጋር ነው መሆን ያለባቸው..." ብላ፣ ልመና አዘል ከርከሯን ስታቀርብ ተረቱ። በመጪረሻ ብቻቸውን መሆኑ እንዳያታከታቸው ትቤ ተሞቡ ከሲላሙው እናት ጋር ለተወሰነ ጊዜ እንዲቀየ ተስማሙ። በማግስቱ ደብረሊባኖስ ለሚያደርጉት ጉዞ ሲዘጋጁ ሁሉም እዛው ምስጢር ቤት ወሰጡ አደሩ። የምስጢር እናትና አባት አቶ መዝገቡና ወይዘሮ ኤደን የተቀበሩት በደብረሊባኖስ በሚገኘው የቤተሰቡ መካነ መቃብር ነው።

ንጉት ለምስጢር ከጻፈችው ደብዳቤ ጋር በላስቲክ ውሰጥ ለማስታወሻ ብላ ከጸጉሯ ቀርጣ አስቀምጣላት ነበር። የገነትንም መካነ መቃበር ከቤተሰቡ ጋር ለማድረግ ነው ያሰቡት። ለንዳያን ገዝዘር የሚያወጡትን ምገብ አዘጋጅተው ለማከፋፈል እንዲመቻቸው በፈለቃል ላስቲክ እንጆራ በወጡን ከጻቦ ጋር አድርገው አሰናድተዋል። ከጻሳባ መውጫ ላይ ያለውን አቀበት አልፈው ሚጻው ላይ ሲደርሱ አካባቢው በጠዋቷ ጸሃይ ደምቋል። ዝናሽ የሞተች ቀን እጹ እንደመራው ነድቶ የመጣው ቀን ትዝ ብሎት ነገራቸው። አልፎ አልፎ ያሉትን አነስተኛ ዝተሞች እያለፉ ወደ ደብረሊባኖስ ገዳም ማዘሪያ ሲደርሱ ረፋዱ አራት ሰአት አካባቢ ነበር።

ታጥፈው ትንሽ እንደነዱ በየሰፈሩ አካባቢ ቀም እያሉ ከያዙት ገዘር ሳይ ለችግረኞች ለመስጠት ሲሞክሩ ሰጪ ስብስብ ይልና ጉልበተኛው ደካማውን እያሸነፈ ይወስዳል። በጣም ደካሞቹ ወደ መኪናው መድረስ እንዳልቻሉ ሲያዩ ምስጢር ወርዳ ያሉበት እየሄደች በጅ በሻቸው መስጠት ጀመረች። መኪናውን ከበው አላስኪድ ያሏቸውን ገንዘብ እየሰጡ መሸኘት ጀመሩ። የሰዎቹ ቁጥር ጨምሮ መሄድ ሲያቅታቸው

"ሲላግለም ... ከቀምከ ምንም አያሳልፉህም። እዛው ቤተክርስቲያኑ ጋ ... ብዙ ችግረኞችና አቅመ ደካሞች ስላሉ ... ደግሞም የሚረዱን ሰዎች እናገሻለን ስለዚህ ዝም ብለህ ሂድ ... እስክትደርስ ድረስ አታቁም ..." ሲሉት ሊ ቀስ ብሎ ከግርግሩ

@OLDBOOOKSPDF

ወጣ ። ቤተክርስቲያኑ ደሻፍ ሲደርስ መኪናቸውን ከጥላ ስር አቁመው፣ ባላር በመከራ የያዙትን እከፋፍለው ጨረሱ ። ብዙ የሥጋ ደዌ ህመምተኛ የነበሩና በህመሙ ምክንያት ለውነታቸው ከፉኛ የተጎዱ ሰዎች መኖራቸውን አዩ ። የከበቡዋቸው ሰዎች በተለይ እትዬ ተዋቡን እንዴ ሴላ ሰው አፍጥጠው ያዩና ዞር ብለው እርስ በርስ የሆነ ነገር ያጉሸካሸካሉ ።

ተላልመው ወደ ውስጥ ከገቡ በኋላ በመቃብር ቤቱ በጎላፊነት የሚሰራውን ሰው አግኝተው ተያይዘው መረዱ ። በሚያምር ሁኔታ የተሰራው ዘመናዊ የመቃብር ቤት በቂ ብርሃን ያለውና በንጽህና የተያዘ ነው ። መያዳውን ያሉ የተለያየ ዘመን ኗሪና ሟቾች ቤቱን ሞልተውታል ። ከታች እስከላይ በረጅሙ ቤት ውስጥ ሲሄዱ ትልቅ ቤተ መዛግብት ወይም ውድ እቃዎች የሚቀመጡበት የባንክ ክፍል ይመስላል ። እርግጥም ብዙ የከበሩ መዛግብቶችና ሃብቶች ከአጸዶ ስጋ ወደ አጸደ ነፍስ የተሸጋገሩ ሰዎች ማኖሪያ ስፍራ ነው ። ከወዴ መሃል አካባቢ በሁለተኛው ረድፍ ላይ ነበር የነወይዘሮ ኤደን ክፍለ መቃብር ። በእባቷ ቀብርም ይሁን ከዛ በኋላ ስላልመጣች ምስጢርም እዚህ ስትመጣ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነው ።

ሁሉም ጸጥ ብለው ወዲያ ወዲህ እያሉ በመቃብሮቹ ላይ የተጻፉትን ሲያነቡ ቀዩ ። ወጣት ሀጻናትና አዛውንቶች ... ከተለያዩ የሕይወት ዘርፍ የመጡ ሰዎች በዚህ አርፈው በጸጥታ ይገኛሉ ። አንዱ ባንዱ ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ... አንዱ በሌላው ሞትም ሆነ አሟሟት አይቀናም ... ማንም ጎረቤቱ ይበልጠኛል ብሎ የበታችነት አይሰማውም ። ሞት ሁሉን እኩል አድራጊ ... ሞት ሁሉን ዝም አሰኚ ።

የሌላው አባት ኮሎኔል ዲንሳም የተቀበሩት እዚሁ ስለነሆነ፣ በሌላው በኩል ዞረው ጥቂት ከመቃብራቸው ፊት ለፊት ቀዩ ። በቦታቸው ላይ በማእረግና ሜዳሊያ የተንቀጠቀጠ ወታደራዊ ልብሳቸውን ለብሰው ከነሙሉ ግርማቸው ይታያሉ ። የሌላው እናት ሻማ ለኩሰው በባለቤታቸው መቃብር ደሻፍ ላይ እኖሩና የባለቤታቸውን ፎቶ እያዩ አለቀሱ ። ምስጢርም ብዙ የሰማችላቸውን የአያቷን መቃብር ስትነበኝ ድብልቅልቅ ስሜት ፈጠረባት ።

ሌላውና ምስጢር ደግፈዋቸው ወደ እነወይዘሮ ኤደን መቃብር ደሻፍ ተመለሱ ። ደሻፉ ተከፍቶ ስለነበር ገነት ለምስጢር በመቃብሪያነት የተወችላትን ጸጉር በትንሽ ሳጥን አድርገው ከእንድ ጥግ ላይ አስቀመጡት ። የመቃብሩ ደሻፍ ሲዘጋ የሁሉም እምባ ፈሰሰ ። ምስጢር ለማባበልና ለማጽናናት አስቸገረች ። ደሻፉ ከተሰሰነ በኋላ፣ ሻማ አብርተውና አበባ አስቀምጠው፣ ተደጋግፈው በቀስታ ወደ ደጅ ወጡ ። ፀሐይዋ በሙሉ ሃይሏ ያላትን መቀት ብትለግስም፣ በከፍታ ቦታ ላይ ሆኖ በዛፍ የተከበበው ገቢ ደሰ በሚል ቅዝቃዜ ተሞልቷል ። ወይዘሮ እታለምና እትዬ ተዋቡ ለጸሎት እዛው ቤተክርስቲያን ለመቆየት ወሰኑ ። ምስጢርና ሌላው ደግሞ አካባቢውን ለማየት ተያይዘው ወጡ ።

በመጀመሪያ ከቤተክርስቲያኑ ብዙም ሳይርቅ ያለውን የአእምሮ ህሙማን ማገገሚያና መንከባከቢያ አገልግሎት ጉብተው ገቡ ። በቤተክርስቲያኗና እዲሳባ

@OLDBOOOKSPDF

ባሉ ጥቂት የአእምሮ ሃኪሞች ትብብር የሚሰጥ አገልግሎት እንደሆነና መንፈሳዊውን አገልግሎትና በዘመናዊ ህክምና ያሉትን መድሃኒቶች አጣምሮ የሚሰጥ አገልግሎት ነው። ካላቸው አትምና አቅርበት እንጻር እየተሰጡ ያሉትን አገልግሎቶች ሁሉቱም አድንቀው አመሰገኑ። የተመሰነ ገንዘብ ለሥራው አበርክተው ተመልሰው ሊመጡና ሊገበኙ ቃል ገብተው ወጡ።

ወደ ሞናው መንገድ ወጥተው ዞር እንዳሉ ካለው መገናኛ ሱጅ ገብተው መኪናቸውን አቀሙ። ውስጡን እየት እየት አድርገው ደጃፉ ላይ ከባሻገር ያሉትን የተራሮችንብርብርና ሰፊ ጉድባ ከሚያሳዩባለድጋፍ አግዳሚዎች አንዱላይ ተቀመጡ።

ቡና ያመጣላቸው ልጅ፣ "ታች ወርዳችሁ ነበር?" ሲላቸው፣

"የት ታች?" አለ ሴላሠው ፈገግ ብሎ።

"በዚህች ... ያቺን ቀጭን መንገድ ይዛችሁ ብትሄዱ ... እ...ም እምስት ደቂቃ ቢሆን ነው። ከምስት መቶ እመት በፊት ፖርቱጋሎች በእንቱላልና በድንጋይ የሠሩት ድልድይ አለ። ከዛ ጋ ሆኖ አገሩን ሲያዩትም ... በጣም ነው የሚያምረው ..."

"በእግር ይገባል ... እያስቸግርም?" ስትል፣ ምስጢር ባደረገችው ስኒከር ሚጣ መራቱን መታ መታ አደረገች።

"ኧረ ... ምንም ... ልጆች ሁሉ ይሄዳሉ ..." ብሎ፣ ዞር ብሎ ሄደ ቡና ያመጣበትን ትሪ ይዞ።

ልጁ በጠቅማቸው ቀጭን መንገድ እየተጠማዘዙ ቁልቁለትና ዳገቱን ጨርሰው ከመግቢያ ሐሳብ መክፈያ ቦታው ደረሱ። የስፍራው ዙሪያ ገባ ውበትና ግርማ ቀልብን ይሰልባል። እየተቀላለዱ ተደጋግፈው ድልድዩ ላይ ወጡ። ድልድዩ የከረመ ውበት ጠግቦ፣ ዛሬ ... በጥንካሬ ሳይፈርስና ሳይደክም አለ። ሲሚንቶ ባልነበረበት ዘመን ከእንቱላል አስኳልና ኖራ ተቀላቅሎ የተሠራ ድልድይ ነው ይባላል።

ድልድዩን አልፈው ከበታች ካለው አነስተኛ ውብ ፏፏቴ አጠገብ ወረዱ። የዘመናት የውኃ መላትና ፍሰት ድንቅ አድርጎ በሸረሸረው አለት ላይ ቀመው ቅርብ ሩቁን አማተሩ። አሚሪካ ከንዱስና ከልጆቹ ጋር የነበኙት የግራንድ ካንየን ታላቁ ገደል ጋር ተመሳስለበት። የደብረሊባኖሱ ሽለቋማ ገደል ውበቱ ያልታየና ብዙም ያልተባለለት ምስጢራዊ ውበት ነው። ከገዳም እስከ ገደሉ ... በሚዳና ሽንተረሩ ... የተመልከች ያለህ የሚል ድንቅ ውበት በሰላም ተሞልቶ ተንሰራፍቷል። ወደ ገደሉ አፋፍና አናት ላይ ሲወጡ የበለጠ ሩቅና ስፋት ያለውን የገደሉን ግዝፈት ማድነቅ ቻሉ። ተመልሰው በድልድዩና በፏፏቴው መሃል ባለው ተፈጥሮ ያነጠፈችው አለት ላይ ከተደረደሩ ድንጋዮች ላይ አረፍ አሉ። ምንም ሳይነጋገሩ በፀጥታ ለጥቂት ጊዜ ቀዩ።

"ቀይ ይሄ ሁሉ ለመሻገር የማይቻል ወንዝ ነበር ማለት ነው .... ድልድዩ ያኔ ያስፈለጋቸው?" አለች ምስጢር፣ ከክፍለ ዘመናት በፊት የነሬው ገደል ያኔ ምን ሊመስል እንደሚችል ባይነ[illegible]።

"መሆኑ ነዋ ... ምናልባት ያኔ ይሄ ለመሻገር የማይቻል አስፈሪና በውኃ የተሞላ ወንዝ ሊሆን ይችላል ..." ብሎ ፣ የራሱን መላ ምት ሰጠ ።

"ያለ ድልድይ ... የገደል ሃይል ግን ... የሚገርም ነው ..."

"ምን ቅርብ ቢሆን ... ገደል የመለያየትና የመራራቅ ንጉሥ ነው ። ድልድይ ደግሞ ሁለት ነጥቦች ምን ቢራራቁ የመያያዝና የቅርበት ። ድልድይ የሌለው መንገድ የምሞት ነው ... በንት ወራት አብረን እየሠራን ...እየበላንና እየጠጣን ... የጠፋችውን ነትን ፍለጋ ስንከራተት ... አንቺም ስታፋልጊኝ ... ያለማወቅ ገደል ... አብረን ሆነን አለያይቶን ... ቅርብ ሳለን አራርቀን ... አይገርምም ... ሁሉም ነገር ያለ ድልድይ ... የቅርብ ሩቅ ነው ። "

"በመንገድ ሥራ ላይም እኮ ከፍተኛ ወጪና ረጅም ጊዜ የሚወስደው ... ድልድይ መሥራቱ መሰለኝ ..." አለች ። ገደሉ ሁሉ ወንዝ ሆኖ በውሃ ተሞልቶ አስበች ። መቶ ሜትር የማይሞላው በሁለቱ ጫፍ መካከል ያለው ገደል ድልድዩ ባይኖር ርቀቱ የወንዙን ርዝመት ያህል ሊሆን ለመጀመሪያ ጊዜ አሰበች ።

"አሁን ሲገባኝ ... የኔና የነንትም የጓደኝነት ... ሊቀራረቡ በማይችሉ ቤተሰቦች መካከል የነበረውን ገደል መዝጋት ነበር ዓላማው ... አንቺ በመኖርሽ አታቲና ትዬ ተዋቡ ዛሬ ባልንጀራ ሆነው በደጅ ሰላሙ ተገኙ ..." አለ ፣ ራሷን እያሻሻት ። እናቷ ነበሩ ራሷን የሚያሻሿት ። ቀስ ብሎ ከሚነፍሰው ንፋስ ጋር ተዋሀዶ ደስ የሚል ሰሜት ተሰማት ።

"እንዴት ነበር ... ድልድዩን ለመስራት የባጀቱ ጉዳይ?" ብላ ሰትሰት ፣

"አይ ድልድዩን ለመስራት የተጠቀምነው ማቴርያል ... ይሁን ... ወይም የገደሉ ጥልቀት ... አላወቅም ። የከፈልነው ዋጋ ካሰብነው በላይ ነው ... የነንትን ሕይወትና የነበረንን የፍቅር ሕይወት ..." ብሎ ጥልቅ ቁዘማ ውስጥ ገባ ።

"እንዴ ... ምነው አመረርክ እንዴ?" ብላ ፣ ተለደችና ተነሥታ ቀመች ።

"እ...እ ... ቢሆንም ደስ ብሎኛል ... ከሁሉም በላይ አንቺን አገኘሁ ... አገቺ በመኖርሽ ደግሞ አታቲና ትዬ ተዋቡ ተቀራርበው ... አብረው ሲጸልዩ ... አብረው ሲያለቅሱ ማየቱ ራሱ ... በቀሼና በቦሌ መካከል የተሰራ ድልድይ ..." ብሎ ፣ ፈገግ አለ ።

"ታዲያ በንጹሕና ባንተ መካከል ለተፈጠረው ገደልስ ድልድይ ሊሰራለት አይቻለም እንዴ" ስትለው ፣ እሱም እጇን ይዞ ተነሥቶ ቀመ ። ትከሻዋ ላይ እጁን ጣል አድርጎ በረጅሙ ተነፈሰ ።

"በሁሉም ገደሎች ላይ እኮ ድልድይ መሥራት አይቻልም ። አንዳንድ ገደል በቃ ገደል እንደሆነ ይቀራል ። ልሥራም ብትዪ ወይ አደጋው ይበዛል ወይም የልፋትሽን ያህል ...የሚገኝበት ነገር የለም" ብሎ ፣ ዝም አለ ።

@OLDBOOOKSPDF

"የምር የምር ግን ... ምን ታስባለህ?" ስትለው ፊቱ ልውጥውጥ ብሎ ራሱን ይዞ ካንድ ትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀመጠ ።

"አይ ዶኖ ... እኔንኛ ሚስጥርዬ ... ሳስበው ራሱ ሁለንተናዬን ያመኛል ።" እጆቹን ያዝ ጨበጥ አደረገና ተከሻውን እንደነገሩ ሰበተ ።

"የልጆቹስ ነገር? ... ያላባት ሊያድጉ ..." ስትለው ፣ ብድግ ብሎ ወደ ገደሉ አፋፍ ሄዶ ፊቱን እያሻሸ ቀመ ። እርቀ ከባሻገር ለማየት ሞከረ ። ካማዶ ገደሉ ውስጥ ብዙ ገጾዎች አሉ ። ገደሉ ቢወድቁ የማይተረፍበት ፣ ቀጥ ያለና ጥልቅ ነው ። ከአጠገቡ ጸጥ ብላ ቀመች ። "ይትር ታ ..." አለች ። ውስጡ ምን ያህል እንደተጉዳ ለመጀመሪያ ጊዜ ተረዳች ። እጁን በእጆቿ ይዛ ፣ ራሷን ትከሻው ላይ ዘምበል አድርጋ ቀመች ።

"አይገርምሽም ... እዛ ታች ድሪስ ሰምች ይኖራሉ?"

"ያለድልድይም ከገደሉ ማዶ መሻገር ... ከገደሉ ውስጥም መኖር ይቻላል ማለት ነው?" ስትለው ፣ ምን ለማለት እንደፈለገች ስለገባው ጸጥ አለ ። በነጋዱሕ ጉዳይ ላይ ስጊዚው ከዚህ በላይ ማውራቱ ስሜቱን የበለጠ መጉዳት ብቻ መሆኑን ተገነዘበች ። ሁለቱም ቃል ሳይወጣቸው ረዘም ላለ ጊዜ ማዶ ማዶ እያዩ ባሉበት ቀዩ ።

ከአፋፉ ላይ የዝንጆሮዎች በማህበር ግር ብለው መጥተው አፈጠጡባቸው ። ሌላሠው ልብም ያላቸው አይመስልም ። ምስጢር ጥቂት ድንጋዮችን በጇ ይዛ ፣ ወደ እነርሱ እንደምትሄድ ሆና ካንድ ድንጋይ ወደ ሌላው ስትዘል ወለም አላት ። ሥሃ ባለችበት እግሯን ይዛ ተቀመጠች ።

"ምነው ... የሆነ ነገር መታሽ?" አለ ፣ በፍጥነት ወደርሷ በድንጋጤ እየሮጠ ።

"አይ ... እ-ግ-ሬ ... ን ወለም አለኝ መሰለኝ ... በሁለት ድንጋዮች መሃል ገብቶብኝ" በህመሙ ስታለቅስ በቀስታ እግሯን ይዞ እያሻሸ ሊያባብላት ሞከረ ። ተንስታ ለመቀም ስትሞክር ህመሙ ስለባሰባት ፣ "እ ... ኣ ..." ብላ ፣ ተመልሳ ተቀመጠች ። እንገቷ ላይ ሽብ ያደረገችውን ስስ ሻሽ መሳይ ጨርቅ አወለቀና ሁለት ቦታ ቀዶደው ። ወለም ያላት ቦታ ላይ ጠምጥሞ አሰረላት ። ደግፏት ተነሳችና እንደ ምንም ልትረግጥበት ስትሞክር ህመሙ አስጮሃት ።

"አይ ቲንዝ ... ከልጅነት ያላወራረድኩት የማዘል እዳ ሳይኖርብኝ አይቀርም ... በይ ነይ ..." ብሎ ፣ በጀርባው ሊያዝላት ሲዞር የግዷን ሳቀች ።

"እንዴ ይሄንን ሁሉ ዳገት ... አትችለኝም ... ቀይ ትንሽ ልሞክር ..."

"ኧረ ... ግዴለም ... ግን የዛሬው በደብረሊባኖስ ገደል ለገደል ያዘልኩሽ ... ይሄ ለሶስት አመት በሕፃንነትሽ እንዳዘልኩሽ ይቀጠርልኝ ..." ብሎ አሳቃትና ቀስ ብሎ አዘላት ። ቀስ ብሎ ዳገቱን ከጨረሱ በኋላ ፣ በድልድዩ ላይ ወደ መጡበት ሲሻገሩ ዝንጆሮዎቹ የበለጠ እየጮሁ በቅርብ ርቀት ተከተሏቸው ። ከድልድዩ ባሻገር ያሉ ሰዎችም 'ወይ ቅብጠት ..." በሚል አይነት ፈገግ አሉ ። መጀመሪያ የተቀመጡባት

@OLDBOOOKSPDF

አግዳሚ ወንበር ላይ ሲደርሱ ቀስ ብሎ አስቀመጣትና በረጅሙ ተንፍሶ እያለከለከ ሜዳው ላይ ተቀመጠ ።

"ውይ ... ደክመሀ አይደል ... አይ አም ሶሪ ..." አለች ፣ ወንበሩ ላይ ደገፍ ብላ ።

ወለም ያለውን አግሯን ይዞ እያሻሸላት ፣ "ደህና ነኝ ... እንዴት ነሽ አሁን?" አለ ። እግሯ የበለጠ አብጧል ። ከመኪና ውስጥ የተሻለ ጪርቅ አምጥቶ ጠበቅ አድርጎ አሰረላት ። የህመም ማስታገሻም ስለነበረው እሱን ስትውጥበት ሻል አላት ።

"ቀይ ግን ... ከሲኒኩስ ... በታ? ... ሌላውስ ያሰብከው ሁሉ ነገር?"

"እንጂ ... አለሽ አሁን ... እኔ ደክሞኛል ። ልመልሳቸው የማልችላቸው ጥያቄዎችና ... ሞፍቻ ዝልፍቸው የጠፉብኝ ችግሮች ... አሉኝ ። ሲራክና ሳንቾ መታሰራቸው ... ቤተሰቤ ተበታትኖ ... እኔንጃ ..." ብሎ ከንፈሩን ነከሰ ።

"ግን ደግሞ የነካካቸውንና ... ሕይወታቸውን በበኮ ፈጽሞ የቀይርካቸውን ለዎች ሁሉ አስብ ... እኔን ... ትዬ ተዋቡን ... ማሚን ... የዝናሽን ልጆች ... አርሴማና ጎዊይን ... እንዴ ... አስበው እስኪ ... አባትህም ያሉት እኮ ... ሀንጻና መንገዱን ሳይሆን ... ለዎችን ይመስለኛል ... ሀገር ሰው ነው ... ሰው ሰው ሲሆን ሀገርም ሀገር ይሆናል ... በዚች አጭር ጊዜ ... ብዙ ነው የሰራኸው ... የሲራክና የሳንቾ ጉዳይም እውነትና ጊዜ የሚፈታው ነው እንጂ አንተ በአጸትህ ወይም ..." ብላ በሀዘኔታ አየችው ።

"እስኪ ... እንግዲህ ... ሌላውን ሰው ለመርዳት ራሴን ማወቅና መረዳቱ ሳያስፈልገኝ አይቀርም ... አሁን ብዙ ነገሮች ተደበላልቀውብኛል ። እውነቱን ንገረኝ ከልሽኝ ... ሌላው ማነው ብትዪኝ እንኳን ያ የማውቀው ርግጠኛ መልስ ግማሹም የለም በውስጤ ። አንቺን ባላገኝ ምን ልሆን እንደምችል አላወቅም ።

"ለጊዜው ... ከሲኒኩም ... ሁሉም ነገር አንቺ ነሽ ... ያ ማለቴ አንቺ ላይ ሸክምና ኃላፊነት በመሜን ሳይሆን ፣ አሁን የሕይወት ትርጉምና ዓላማዬ የተምታታብኝ ጊዜ ስለሆነ አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓሴ ነሽ ለማለት ነው ... ገባሽ ... ደግሞ ለኔ መጪነቅ የለብሽም እሺ ... ጊዜ ከፈጣሪ ጋር የማይፈታው ችግር የሚፈጠረው ፣ ለጊዜ ጊዜን መስጠት ሲሳነን ብቻ ነው ። እሱ ያውቃል" ብሎ ወደላይ ሲያይ ፣

"እንደዚህ ጠንካራ አማኝ መሆንህን አላውቅም ነበር" አለችው ።

"ለእኔ ጠንካራ አማኝ ማለት ምን አይነት ሰው እንደሆነ ታውቂያለሽ? እንደ ቶማስ ያለ ተጠራጣሪ ሰው ነው ። ጥርጥር የእምነት ምንጭ ነው ። ምክንያቱም የእምነታችን ጥንካሬ ታግለን የሸነፍነውን ጥርጣሬ አይበልጥም ። የድፍረታችንም ልክ ብርዘ አስይዞን ከረታነው ፍርሃታችን ስንገዘር አይዘልም ። የፈራነውን ነገር ላናሸንፍ እንዴት ደፋር መሆን እንችላለን?

"ራሴን ግን ... ጠንካራ አማኝ እንደሆንኩ አስቤ አላውቅም ። ዛሬም ከውስጥ ፍርሃቶቼና እምነቴን ከሚፈትኑ ጥርጣሬዎቼ ጋር ትግል ላይ ነኝ ። ደግነቱ እምነት በአማኙ ጥንካሬ ላይ ሳይሆን በሚታመነው ማንነት ላይ የሚመሰረት ነው ። የተፈተነ

@OLDBOOOKSPDF

እምነት ጥርጣሬን ወደ እርግጠኝነት ... አለመቻልን ደግሞ ወደ መቻል ... የሚያዘልል ድልድይ ነው" አለ ። ወዲያው ራሷን ለማጥፋት በሞከረችበት ዕለት በውድቅት ሌሊት ከቤተክርስቲያኑ ደጃፍ ላይ ያደረሰው ጸሎት ትዝ አለው ። እሷን ከፊቱ ተቀምጣ ሲያይ እምነት የሚፈጥር ብሩህ የተስፋ ፍንጣቂ ታየው ።

@OLDBOOOKSPDF

ከሰድስት ወር በኋላ ...

ሌላው ባለፉት ወራቶች ውስጥ በአሠርት አመታት ያህል ያረጀና ከሕይወት ትምህርት ቤት ካሰበው በላይ ተምሮ የወጣ ያህል ተሰማው። የጊዜ ፍጥነት በሕይወት ጉልበትና በሰው ውስብስብነት ላይ ያለው ኃይል ዛሬም እንደ አዲስ አስገረመው። ሳቅና እምባ ... ውድቀትና ስኬት ... ግርምትና ስልችት እንዴት ባንድ ሰው ሕይወት ላይ በዚህ ፍጥነት መፈራረቃቸው ገርሞታል። ዛሬም ሕይወት የማትሰለችና የማትለመድ ምስጢር ሆናበታለች።

ሥራ ያቅመውን ክሊኒክ እንዴት በተሻለ ሊጀመር እንደሚችል ማሰብ ጀምሯል። የፍርድ ቤቱ ሂደት ወደ መጠናቀቁ ደርሷል። ክሊኒኩ ለሚች ቤተሰብ መጠነኛ የካሳ ገንዘብ እንዲከፍል ተበይኖበት ለመክፈል ተስማምተዋል። ሳንቾ አትዶና አድብቶ ባይሆንም በደም ፍላትና ለጓደኛው ለምስጢር ተደርቦ ለማስረሻ ሕይወት መጥፋት አስተዋጽኦ አድርገኻል የሚል ብይን ተሰጥቶታል። ለዚህም ከተበየነበት የእስራት ቅጣት ሦስት ወር ብቻ ነው የቀረው።

ሲራክ ግን በወንጀሉ ዋነኛ ተጠያቂ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወስኗል። ወንጀል አልባ ቅደመ ታሪኩ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶለት በአስራ አምስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተፈርዶበት ዘብጥያ ወርዷል። በወንድሙ እርዳታ ይግባኝ ጠይቆ ፍርዱ እንደገና እንዲታይላቸው ላይ ታች እያሉ ነው። ነገሩ ያነድ ስሞን የዚና ማጻመቂያ ሆኖ ከረመ። አሁን ሁሉም ነገር ረግቦ ዕጻው የባለ ቤቶቹና የፍርድ ተጋሪዎቹ ብቻ ሆኗል።

አቶ በድሉ ለረጅም ጊዜ ካልጋ ሳይወርዱ ታመው ቀይተው ባለፈው ወር አረፉ። ሌላው የገናሽን እህት ለማጽናናት ዘንበወርቅ መለስ ቀለስ ሲል ነበር የከረመው። የገነት እናት ትዬ ተዋቡ ጠቅልለው ከእናቱ ጋር መኖር ጀምረዋል። ቀስ በቀስ ደስተኛ ሆነው የድሮው ማንነታቸው እየተመለሰ ነው። ቁሜ ብለው ሲጫወቱና ተያይዘው ሲሠሩ ላያቸው ተጠፋፍተው የተገናኙ እህትማማቾች ይመስላሉ። ሁለቱ የላንቾ ያከሰት ልጆች ደግሞ እርሱ ከታሰረ ጀምሮ ከምስጢር ጋ ጠቅለለው ገብተዋል።

@OLDBOOOKSPDF

ምስጢር ከአዲስ አበባ ሆና በስልክና በኢሜይል ከንጹሀና ከቤተሰቦቿ ጋር ለመነጋገር ያላደረገችው ጥረት አልነበረም ። በመጀመሪያ አርሴማን ከዚያም የወላጆቿን እምነት ካገኘች በኋላ ነበር ንጹሕ ለኢሜይሏ መልስ የሰጠቻት ። ከጥቂት የኢሜይል መለዋወጥ በኋላ በስልክ ልታወራት ተስማማች ።

"ቀይ ሚስጥር ... አሁን እኮ ምንም የምንፈጥረው ተአምር ወይም የምናመጣው ለውጥ የለም ። ሌላው የወሰነውን ውሳኔ ሁሉ የወሰነው እኮ አንቺ ልጁ መሆንሽን አውቀ ወይም ገምቶ አይደለም ... ስለዚህ ያንቺ ልጁ መሆን ምን ልዩነት ያመጣል? ... ይቅርታ እንደዚህ በማለቴ" አለች ፣ ድምጿን ዝርር አድርጋ ።

"ልክነሽ ንጹሕ ... እኔ አንቺን ብሆን ካንቺ የተለየ ወይም የተሻለ ነገር አደርጋለሁ ማለቴም አይደለም ። ግን እኔ አሁን አባቴ መሆኑን ስላወቅሁ ወይም ስለሆነ አይደለም ። ምን ያህል እንደሚወድሽና አሁንም ያንቺ ነገር ሲነሣ ውስጡ እንደሚረበሽ ስለማውቅ ነው ። ውስጡ ያለው ጸጸት ምን ያህል እየበላው እንደሚኖር ብታዪ ... እኔ ስለማውቅ ነው ... ምን ያህል ጨዋ ሰው እንደሆነ ..." ብላ ፣ መቀጠል አቅቷት ስታለቅስ ጸጥ ብለው ቀዩ ።

"ሚስጥር ይገባኛል ... አንቺ በሱ በኩል ያለውን ነው የምታውቂው ... እኔ ያሳለፍኩትን አንድ ቀን አብረሽኝ ብትሆኚ ... ወይም እኔን ወይም የኔ ልጅ ብትሆኚስ ... ምንድን ነበር የምታስቢው?" አለች ፣ ከውስጧ ጠንካራ ለመሆን እየሞከረች ።

"እኔንጃ ... ምናልባት ልክ ነሽ ... ስለማይገባኝ ይሆናል ... ግን የሱን ያህል ባላውቅሽም ካየሁሽ ጀምሮ አንቺንም ከልቤ ነው የወደድኩሽ ... ልጆቹን ላስብ ደግሞ ... እኔ አባቴ ባልሆን ሰው እጅ ብዙ ነገር አይቼ ስላደግሁ ይሆናል ..." ብላ ዝም ስትል ትንሿ አርሴማ ላይ የምታያቸውን ባህሪዎችና መሞዳቶች አሰበች ።

"ኧሺ ... ሚስጥር እኔን ምን አድርጊ ነው የምትይኝ? አሁን ምን ላደርግ እችላለሁ?"

"ምንም አልልሽም ተነናኍና ሁሉንም ነገር እንደገና አውሩ ... ምን ታውቂያለሽ?" ስትላት ፣

"እዩ ... ሚስጥር ... አንቺ ምንም የገባሽ አልመሰለኝም ... አሁን ሁሉም ነገር ተቀይሯል ... እኔ እኮ ከሌላ ሰው ጋር ነኝ ..." ስትላት ነገሩን ብታውቅም ወሸመጢ ብጥስ አለና ዝም አለች ። "አሁን መሄድ አለብኝ ... ይቅርታ የኔ ቀንጆ ... ኡይ አምሶሪይ እሺ ..." አለች እገዘን ባለ ድምጽ ።

ስልኩን ዘግተውት ከተለያዩ በኋላ ፣ ምስጢር ተስፋዋና የተነሳሳ ሰሜቷ ሁሉ አሽቀልቁሎ ተደብራ ከረመች ። ለሳምንት ያህል ከቤት ብዙም ሳትወጣ ሁሉም ነገር አስጠልቷት ከረመች ። የንጹሕ እህት አርሴማ ደዉላላት ሲያወሩ ተስፋዋ እንደገና ትንሽ አንሰራራ ። ንጹሕ አብራው ካለችው ሰው ጋር በጥሩ ሁኔታ ላይ አለመሆኗን ነገረቻት ። ባለፈው ሳምንት ከምስጢር ጋር ከተደዋወሱ በኋላ ከበፊቱ ይልቅ ስለእርሷም ሆነ ስለሌላው ብዙ ስታወራ እንዳሰማቻት አውራቻት ። በመጨረሻም የተቻለውን

@OLDBOOKSPDF

ሁሉ ለማድረግ የምስጢር ወደ አሜሪካ መምጣት የተሻለ እንደሚሆን ተስማሙ። እርሴማ ተቀብላ ልታስተናግዳትና ንጹሕን አብረው ሲያገኟት አወሩ።

የሁለት አመት የአሜሪካ ኒሳዋ ሲቃጠል አንድ ወር ብቻ ስለቀረው፣ እሱን ለማሳደስ ብዙም ችግር አልሆነባትም። የሚቀጥለውን ሳምንት ጉዞዋን ስታቅድና ነገሮችን ስታስተካክል ከረመች። ከሴላሠው ጋር ለምሳ አያቷ ወይዘሮ እታለም ቤት ተቀጣጥረዋል። ወደ አሜሪካ እንደምትሄድ እስካሁን አልነገረቻቸውም። ግቢ ገብታ መኪናዋን አቁማ ከኋላ ወንበር የገዛቻቸውን ጋዜጦች ይዛ ወረደች። እቤት ስትገባ ምላቀርቦ ሲጠብቋት ደረሰች። እንደቀመች ይቅርታ ጠይቃ የያዘችውን ጋዜጣ አንድ አንድ ስጠቻቸውና፣

"ገጽ ስምንት ላይ አውጡ ..." ስትላቸው ሁሉም በመገረምና በጉጉት ጋዜጣውን ግንኩሻኩሽ ጀመሩ።

አከስቷ ወይዘሮ ዘምዘም ነገሩን ብታውቅም እንደማታውቅ ሆና፣ "አንቺ ልጅ ደግሞ ምን ተገኘ?" ስትል ተያይተው ተሳሳቁ።

"ስድስተኛው አምድ ውስጥ ... አንብቡ ..." ስትል፣

"ምስጢረ ሴላሠው ዲንሳ" አለ ሴላሠው ፊቱ ሁሉ ብርትርት ብሎ። ተንሥቶ እቅፍ ላግት። አያቷ ደግሞ አልልታቸውን አቀለጡት። ምላ ቀርቦ እየተሳሳቁ በሉ። ገበታ ተነስቶ ቡና ሲቀራርብ፣

"ሴላ ማስታወቂያ ... እሱ ጋዜጣው ላይ የለም። ነገ ወደ አሜሪካ ልሄድ ነው።" ስትላቸው ሁሉም የቀልድ ነበር የመሰላቸው። ነገሩን ባጭሩ ስታስረዳቸው ከሴላሠው በስተቀር ሁሉም ጉዞዋን ደገፉ። ሀሳቡን ባይጠላውም ነገሩ ባይሳካ እንዳትጐዳ ተጨነቀል።

* * *

አሜሪካ እንደደረሰች እርሴማ ተቀበለቻት። ወዲያው ጥሩ ወዳጆች ሆኑ። ሙሉ ለሙሉ በአሜሪካ ባህል ውስጥ ሰርገው የተለወጡት የገናና ልጆችም የግይጠግቧት አዲስ ዘመድ ሆናላቸዋለች። ሁሉም አድገዋል። ስምረት ምንም ነገር ሳትረሳ ስላስታወሰቻት ገረማት። የነንጹሕ ወላጆችም ደጋግመው አማኝተዋት እንደ ልጃቸው መስላቸው ወደዋታል። ከተወሰኑ የስልክ ወሬዎች በኋላ የንጹሕን መለሳለስም ልብ ብላለች። ለሳምንቱ መጨረሻ ልጆቼን ይዛ ስለምትመጣ በናፍቀትና ጊዜው አልሄድ ብሏት እየጠበቀች ነው። ወንድምና እህቷን ለማገኘት።

ንጹሕ ከመጣች ጀመሮ ከምስጢርና ከአርሴማ ጋር ብዙ አወሩ፣ በነገሮች ላይ ተከራከሩ። በሚቀጥለው ቀን ወደ ኦስቲን ከመመለሷ በፊት ከምስጢር ጋር ለብቻቸው ለግዑራት ለቡና ወጡ። ካንድ [illegible] ብዙ አወሩ።

"እስኪ እዪው ... እንቺም እሱም የከፈላችሁት ዋጋና ያሳለፋችሁት ስቃይ እኮ ያለዋጋ አልቀረም ... እኔን እዪኝ ... የት ነበርኩ ... እናቴ ስትሞት ሟች ነበርኩ። ብኖርም ኦሮ አትበዪው። አሁን አባቴን ብቻ ሳይሆን ራሴንም ነው ያገኘሁት። አህትሽን እያት እስኪ ... ልጆቹንም። ደስተኛ እናት ሆና ስታያት ... አስቢው ይሄስ ይሆን ነበር። የገነትን እናት ትዪ ተዋቡን ስታያቸው ደግሞ ... አስቢው ይሄ ጫፉ ነው ... ያባቢ መምጣት እኮ ... በጣም የብዙ ሰዎችን ሕይወት እኮ ነው የለወጠው ..." ስትል፣

"በፍጹም እንደሱ አስቢውም ... አይቼውም አላውቅም። ሁልጊዜም በራሱ ፍላጎትና ሀልሜ በሚለው ነገር የሚነዳ ነበር የሚመስለኝ ... ኦህ ማይ ጋድ ... በጣም ልከ ነሽ ..." ብላ ጸጥ አለች። የምስጢር ሴላሠውን 'አባቢ' ማለት ራሱ የሆነ ልትገልጸው የማትችለው ስሜትን ፈጠረባት።

"እሺ ... አሁን አብረሽው ካለሽው ሰው ጋር ደስተኛ ናችሁ?" ስትላት ጸጥ ብላ ቀየችና ራሷን ነቀነቀች።

"ግን ... ደግሞ ከሱ ጋር ደስተኛ ስላልሆንኩ ወይም ከርሱ ጋር መሆን ስለማልችል ከሴላ ጋር መታረቅ አለብኝ ብዬ አላምንም ... ለሃውም ... አስቢው እስኪ ... ሰውም ቢሆን ፈይር አይደለም ..." አለችና ፊቷን ሞምትርትር አደረገችው።

"እሱን ተዪው ... እኔ የምለው ... በቃ አንድ ጊዜ ተገናኙና ... የሆነውን ሁሉ እንደገና አውሩት ...ምናልባት እኮ ሁለታችሁም የሄዳችሁበት መንገድ ብዙ ነገር አስተምሯችሁዋል። ምን ያህል እንደተለወጠ የሱን አውቃለሁ። ምንም ነገር ሳትወስኚ በቃ ዝም ብለሽ ሳሞር ጊዜ ... ልጆቹም እሱንም አያታቸውንም ይዩ ... እታቲ እኮ እንዴት እንደምትንሰፈሰፍልሽ ..." ስትላት እምባዋ አመለጣት። እጇን እያሻሸች ጸጥ ብላ ጠበቀቻት። ምንም እፍ ያወጣ ውሳኔ ባታደርግም ንጹሕ ወደ ኢትዮጵያ ላሞር ጊዜ ለመሄድ ልቧ ፈቃደኛ እንደሆነ ተረድታለች። የቀረውን ነገር ከእርሴማ ጋር አውርተው አንዳንድ እትዮችን አወጡ። እሺም በዚያው የአያታቸውን ለቅሶ ለመድረስ፣ ልጆቹን ይዛ አብራቸው ለመሄድ ወሰነች።

ምስጢር ወደ አሜሪካ ከሄዶች በኋላ ከንጹሕ ጋር ያለው ግንኙነት በፍጥነት እየተሻሻለ መምጣቱን ሴላሠውም ልብ ብሏል። በራሱ በኩል ያለፉት ወራቶች በህይወቱ ላይ ያሳደሩትን ጫናና ተውሰ ለማርገብ እየሞከረ ነው። ለረጅም ጊዜ የተለያቸውን ያባቱን ዘመዶች ሲጠይቅ ነው የከረመው። የጸጥታና የጥሞና ጊዜ ወስዶ ቀለል ያሉ ነገሮችን እያነበበ ጊዜ ያሳልፋል። ተወት አድርጎት የነበረውን ዋናና ሩጫም ጀምሯል። በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ ላንች ጋ ሄዶ ይጠይቀዋል። ሲራዘን ሲያገኘው ደጋግሞ ቢሞክርም አሻፈረኝ እንዳለ ነው።

ቅጽሜ ከጠዋት ሩጫው ሲመለስ ቁርሱን እንደነገሩ ቀማምሶ መንገዱ ሳይጨናነቅ ብሎ ቶሎ ወጣ። የጠዋት ዋና እትዱ ላንች ጋ ለመሄድ ነው። አልፎ አልፎ እንደሚያደርገው ፈቃደኛ ከሆነ ሲራዘንም ሊያገኘው አስቧል። መኪናውን ከቀመ በኋላ፣ ለሚጠብቁት ልጆች አደራ ብሎ ባካባቢው የተገጠገጡትን ሱቶች እያለፈ

@OLDBOOOKSPDF

ሄደ ። ሁልጊዜም ያንጹ መከራ የሴላው ሥራ መሆኑ ይገርመዋል ... ሆስፒታልም እስር ቤትም ። ሆስፒታል ተረኛ ሆኖ ሥራ በዝቶበት ሲደክመው ፣ 'ህመምተኛ ለመሆንም እኮ ተረኛ መሆን አለ' ብሎ ራሱን ራሱን ከማማረር ያቅባል ።

እንዶ ሁልጊዜውም ሲሞክር ሲራክ ፈታደኛ ሆኖ መጣ ። ወዶ እርሱ ሲመጣ ሲያይ ደስታና አለማመን ተፈራረቀበት ። ጠጋ ብሎ ሲያየው የሚያውቀው ሲራክ አልመሰለውም ። ራሱን ተላጭቶ ጢሙን አሳድገታል ። የበለጠ የከሳ ይመስላል ። ቁጣ ይለዋል ። ከስቶ በለበሰው ልብስ ውስጥ ሲጠፋ የደረሰ ይመስላል ። ድንጋጤና ደስታ ተቀላቅሎበት ሰላም ሊለው ሲል ፣

"ቀይ እሺ ... ዶግሞ ... አሁን ምን ቀረህ ... ተወኝ ሲሉህ አይገባህም እንዴ እንተ ። ስማ ለምን ራስህን እንዶ ጻድቅ ማየትህን አታቀምም ። ወንጀለኞችን ለመጠየቅ በየሳምንቱ ከምትመላለስ ... ለምን የራስህን ወንጀል ለማየት አትሞክርም ። ታውቃለህ አይደል ... አንተ እዚህ አገር ባትመጣ ኖሮ ... እኛም እዚህ የተረገመ ቦታ እንደማንመጣ ። አሁን ምን ቀረህ እሺ?" ብሎ በቁጣ እጁን እያወናጨፈ ወረደበት ።

ትንፋሹን ለመሰብሰብ ጋብ ሲል ፣ "እንዴት ነህ?" አለው ረጋ ባለ ድምጽ ።

"ምናገባህ ... እንዴት ነህ ይለኛል እንዴ? ... እንዴት አንዶ ሆንኩ ለማወቅ ትፈልጋለህ ... በዛኛው በር ዞረህ ግባና እዚህ ሦስት ቀን እደር ... ደግሞ ስምቼልሃለሁ ... ልትጠብሳት ያሰብካት ቺክ ... ልጅህ ሆና ተገኘች አሉ ። እሱ እንኳን አያሳፍርህም? አቦ ሴላው ሲሉህ ተሳስተዋል ... አንተን ሴላው ከሚሉህ ... ሴላ ዩር ቢሉህ ነበር የሚሻለው ። ወይኔ ... ሲራክሻ ... አስራ አምስት አመት ... ኡ ኡ ..." አለና ፣ ራሱን ይዞ ተቀመጠ ። ሊያናገረው ቢፈልግም እንደገና ጩኸቱን እንዳይጀምረው ፈራ ። እሱ እየጮኸ ሲለፈልፍ ባካባቢው ሰጥየቃ የመጣው ሰው ሁሉ ዞር ዞር እያለ መረበሹን በሚያሳይ ግልምጫ ገረፋቸው ።

"ስማ ... ሴላው ... እይ ... አሁን እዚህ ልብስ ውስጥ የምታየው አንተ የምታውቀውን ሲራክን እንዳይመስልህ ። ኮምፕሊትሊይ ሴላ ሰው ነው ... እንኳን አንተ እኔም አላውቀውም ። አንተም ያኔ የመሰልከኝ ጉብዙና ላገር አሳቢው ዳያስፖራው አይደለህም ። እሱ እዚህ የማየው አውሬ ጭምብል ነው ። በገዛ ጽሑፍህ ስለኔ ምን እንደምታስብና ባንተ አናሲሲስ ላንተ ምን እንደሆንኩ ተናግረኻል እኮ ።

"አንተ ... የዛሬ አስራ አምስት አመት ... አካባቢ ሽሜ ነገር መሆንህ አይቀርም ። እኔ ደግሞ የአርባ አምስት አመት ጎልማሳ ። እኔ ከዚህ ሳልወጣ ... ወይ እግዜር ወይ ካንሰር ካልገደለህ ... አንተንና ያቺን ባጃጅ ራስ ጠበቃ ... እንዶ ጭዳ ዶሮ እንቁ ... እኔ ራሴ ነኝ ባንድ መቃብር ውስጥ ገን ለገን የምቀብራችሁ ። ... ቀልዴን እንዳይመስልህ ... ዶግሞ ከልብህ እንደምትፈራኝ አውቃለው " ብሎ ፣ ረዘም ላለ ደቂቃ አፈጠጠበት ። ምራቁን ወደርሱ አትጣጫ ተፍቶ ከት ብሎ ሲስቅ ጠባቂዎች ይዘውት ሄዱ ።

'እውነትም ሴላ ሰው ... ሲራክም ሴላ ሰው ሆኗል ... ወይ እስር ቤት' አለ በውስጡ ። ትንሽ አረፍ ብሎ ባንቻን አስጠርቶ ከርሱ ጋር ረጋ ብለው ሲያወሩ ቀዩ ።

@OLDBOOOKSPDF

ከሲራክ ጋር የተለያየ ክፍል ሰላሉ እንደማይገናኙ ነገረው። ውጪ ሰላሉ ነገሮች የጠየቀውን ሲመልስለት ቀየ። "ሚስጥርም ከሰሞኑ እመጣለሁ እያለች ነው ... ምን ጥቂት ቀን ብላ እኮ ወር ሊሆናት ነው"

"ዶክተር ሌላ ... እነ ንጹሕም ይመጣሉ ነው ያልከኝ?"

"አዎን ... የዝናሽ ልጆችም ይመጣሉ ..."

"እንዴት ነው ከንጹሕ ጋር ... ምንም ተስፋ የለም?"

"ብዙ ነገር ተበላሽቷል ... እስኪ እንግዲህ እናያለን"

"ልቤ ሁሉም ሰላም ይሆናል ነው የሚለኝ። ኧረ ... ባለፈው የነገርኩህ ነገር ድግሞ... እየከረረ ነው። ትናንትም መጥታ ነበር ሰሚር ... ቤተሰብም አውቋል ነው የምትለኝ። ማመን ነው ያልቻልኩት። ሰው ውጪ ሆኖ ያልሆነለት ነገር ... እሰር ቤት ድረስ ሰተት ብሎ ይመጣል። ቤተሰቦቿ እንተን ማውራት ይፈልጋሉ መሰለኝ ግን ..."

"ምን ችግር አለ ይምጡ ... ሽማግሌም መሆን ካስፈለገ አለን ... አሁን እኮ ቤታ አለቀ ... ሶስት ወርም አይሞላም እኮ የቀረህ ልትወጣ" አለ፣ ደስታው እየፈነቀለው።

"እምን የማያልቅ የለም አለቀ ... ካለፈ በኋላ ደሰ ይላል። ይገርምሃል ... ተስፋ ውስጥህ ሲፈጠር ሁሉም ነገር ትርጉም ያገኛል። አሁን ኮሌጅ ያለሁ እንጂ እሰር ቤት ያለሁ አይመስለኝም። መጀመሪያ ላይ ዓለም ላዬ ላይ የተደፋችና ... የሆነ በትንሽ ብልታጥ ውስጥ ዘግተውብኝ ሰው የማይደርስበት በረሃ ውስጥ የጣሉኝ ሆኖ ነበር የተሰማኝ። ወደዚህ ቦታ ስገባና ጪርሼ ስወጣ ሌላ ሰው ነኝ። የሚገርምህ ነገር እኮ በህልሜም በውኔም እሷ የኔ ትሆናለች ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። የሰው ምኞቱ የሚፈጸምበትን መንገድ አንድ አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው። አሁን የኔ የፍቅር ህልም እሰር ቤት ውስጥ ይሞላል ብዬ እንዴት ላስብ እችላለሁ?" አለ፣ ፊቱ እንደጠዋት ፀሐይ እየፈካ።

ሲሳላቱና ሌሎች ጉዳዮችን ሲያወሩ ቀዩ። ከርሱ ተለይቶ እየራቀ ሲሄድ ድብትልት ባለ ስሜት ተዋጠ። በሲራክ ላይ ያየው የፍርሃት ቅዠትና የላንቾ የስኬት ህልም የፈጠረበት ድንጋራ ስሜት። ሁለቱንም መጀመሪያ ሲያገኛቸው የነበረው ሁኔታ ትዝ አለው። አሁን ሁለቱም ሌላ ሰው ሆነዋል። እሱ ራሱ እነሱን ሲያገኛቸው ከነበረው ፍጹም ሌላ ሰው ሆኗል። እናቱ ቤት ሲደርስ እነ ምስጢርን ለመቀበል ሽር ጉዱ ቤቱን አድምቀታል።

የመግጫ ሰዓታቸው ሲደርስ እየር ማረፊያ ቀደም ብለው ተገኙ። እቃቸውን ተረክበው ከውስጥ ሲወጡ መጪዎቹ ከተቀባዮቹ በቁጥር እያንሱም ነበር። በሰላምታና በመሳሳም ... በመላቀስና በመተቃቀፍ አካባቢውን አደመቁት። ምስጢር ወይዘሮ ዘምዘምን፣ ሲስተር ዘቢባን፣ አያቶቿንና የላንቾን ያክስት ልጆች እያቀፈች ሰላም ስትል ሌላውን ነገር ረስታው ነበር። እርሷማና ዲንሳ አባታቸውን ሲያገኙ ደስ ቢላቸውም የእንግድነት ግራ መጋባትና ገታ ያለ ስሜት ሲያላቸው ውስጡን ቀረቀረው።

@OLDBOOOKSPDF

የገናናሽን ልጆች እናታቸው አርሴማ ላይ ተለጥፈው ሲያዩ የሌላሠው እናት ልጆቹን በጉዲፈቻ ለመውሰድ ሲወስኑ የነበረው የቤተሰብ ስብሰባ ትዝ ብሏቸው ጸጸት በሚት በውስጧ ያልፍ ነበር። ከሌላሠው ጋር ስላም ሲባባሱ ሁለቱም የተደበላለቀ ስሜት ነበራቸው። እንደኛው አንዱን እንዴት እንደሚቀበል እርግጠኛ አለመሆን፣ የግንኙነታቸው በም የለሽነትና በመሃል የተፈጠረው ተስፋ ተቀላቅሎ በደመነፍስ ተቃቅፈው ያለ ቃል ሰላምታ ተሰጣጡ። ደህንታቸውን ተጠያይቀው ራሳቸውን በለጪ ግርግርና ጫጫታ መሃል ይብቅው ስሜታቸውን ማረጋጋት ቻሉ።

ምሳ ተበልቶ ሁሉም አረፍ አረፍ ማለት ጀመረ። አርሴማና ምስጢር ተመካክረው ንጹሕ ከለዓት በኃላውን ደክሚት ሰለነበር ተኝታ አሳሰፈች። ከሌላሠው ጋር ለብቻቸው ራት እንዲወጡ ሼራተን ደውለው ቦታ ያዙላቸው። ምሰጢር ደግሞ ከአርሴማ ጋር ወደ ማታ ላይ ልጆቹን ሁሉ ይዘው ወደቢ ቤት ወሰደዋቸው ሲጫወቱ አመሹ።

ለእራት ወደ ምግብ ቤቱ ከመግባታቸው በፊት በላውንጁ ውስጥ ቁጭ ብለው ወሬ ጀመሩ። ሰለራሳቸው እንዴት እንደሚያወሩ ተቸግረው ጸር ጸር ሲሉ የተወሰኑ ደቂቃዎች አለፉ። ሌላሠው ሀሳቡን ሰብስቦ፣

"እንዴት እንደምነግርሽ አላውቅም። ምናልባት ሚስጥር ነግራኻለች ብዙውን ነገር። ባለፉት ወራት በከባድ ሁኔታ ውስጥ ነበር ያለፍኩት። አንቺም ብዙ ነገር እንዳለፍሽና ብዙ ሰቃይ እንዳየሽ አውቃለሁ። በጣም አዝናለሁ። ሰሆነው ነገር ሁሉ ጥፋተኛው እኔ ነኝ። በራሴ ሀሳብ ተውጬ ... ላንቺ ሰሚትና ፍላጎት ዓይኔን በመጨፈኔ ይቅርታ። አውቃለሁ አውን ለሁሉም ነገር ጊዚው አልፏል ... ግን ..." ብሎ ዝም ሲል፣ ጸጥ ብላ እያየችው ጣቷን ማፍተልተሏን ቀጠለች።

ንግግሩን ቀጥሎ "መጀመሪያ አብረን ስንሆን ...ከዚያም ለመጋባት ስንወስን የጠየቅሽኝ አንድ ነገር ብቻ ነው ... የተረጋጋና የማይለያይ ቤተሰብ እንደምትፈልጊና ... እንደ ወላጆችሽ ካገር አገር መንከራተትና ቤተሰብሽን በዚያ ውስጥ ማላለፍ እንደማትፈልጊ ... ቃል ገብቼልሽ ነበር ... ግን ያንን ማድረግ አልቻልኩም ..." ብሎ፣ እንደገና ዝም አለ። ጸጥ ብላ ትሰማዋለች ... ሌላሠው አልመስልሽ አላት ወይም የድሮው ሌላሠው ሆነባት።

"እኔ ዊይስ ... ከዚህ በኋላ ... አንቺ የፈለግሽውን ብትወስኚ ጥፋቱ ያንቺ ላይሆን የእኔ ነው። ግን ቢያንስ ከልጆቹ መራቅ አልፈልግም። እዚህ ያለውን ነገር ሁሉ እነርሱ አድገው ራሳቸውን እስኪችሉ ለማቀም ወስኛለሁ። ለመኖር የምትወስኚበት አካባቢ መሆን እችላለሁ" ሲል፣ ፊቷ በሀዘንና በርህራሄ ስሜት ታጠበ። ለማውራት ብትፈልግም አልቻለችም።

"እኔም ሳበብ ነበር ... በተለይ ምስጢር ከመጣች በኋላ። ብዙ ያላየሁዋቸውን ነገሮች አሳየችኝ። እኔ ያልኩት ይሁን በሚለቱ እንጂ ... ቤትህ ከምትወደው ሰው ጋር የጋራ ህልምን የምትኖርበት ሁኔታ ነው እንጂ ቦታ ወይም ሀገር አደደለም። ወራ

@OLDBOOOKSPDF

በመስማት ባላደረከውና ባልሆነ ነገር ስለጠረጠርኩህ ይትርታ አድርግልኝ። ብቸኝነቱና የሰማሁት ወሬ ደግሞ ማድረግ የማልፈልገውንና የሌለብኝ ነገር ውስጥ እንድገባ አደረገኝ። በራሴ በጣም ነው ... የማ...ፍ...ሬ" ብላ፣ ግልቱስ ስትጀምር እጆቿን ያዛቸው። "እይ እም ሶ ሶሪ ..." ብላ፣ እንዳቀረቀረች በረጅሙ ተነፈሰች።

"እዚህ ሁሉ ውስጥ እንድትገቢ ፈተና ውስጥ የጨመርኩሽ እኔ ነኝ ..." ሲል፣

"ከዚህ የተሻለ ማሰብ ነበረብኝ ..." አለች፣ ገዘግ ባለ ድምጽ።

በጓሮው በር ወጥተው በውሃ ፏፏቴው አጠገብ ተቀምጠው ብዙ አወሩ። ያለፋባቸውን ነገሮች ያለምንም መደባበቅ አንዳቸው ለሌላቸው ሲናዘዙ ረጅም ሰዓት ወሰደባቸው። ወደ ምግብ ቤቱ ሲሄዱ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሆኖ ነበር። ምግቡን እዘው ቀለል ያለ ወሬ ሲያወሩ ቀዩ። ወደ ቤት ሲሄዱ ቀጥሎ ምን እንደሚሆን በግልጽ ባይነጋገሩም አቅጣጫው ግን ግልጽ ነበር።

ከሦስት ቀን በኋላ ነበር ያለ የሌላ አቅሙን ሰብስቦ "ንጺ ... አንድ እድል ብትሰጪኝ ... ሁሉንም ነገር ትቼ መጀመሪያ የገባሁልሽን ቃል ለመፈጸም የምር ... ማድረግ እችላለሁ ... እዚህ ያለውን ነገር ትቼ መሄድ ... ምንም ነገር ..." አለ፣ እጆቿን ይዞ።

"አውን ... ሁሉም ነገር ገብቶኛል ... ሀገር ሰው ነው ... ቤት ፍቅር ነው ... ምቾት ለሴላው መኖር ነው። ሁላችንም እዚሁ መኖር እንችላለን። የጀመርከቸው ሥራዎች የትኛውም አይጽረጥም። እኔም ከነንህ ነኝ" ስትለው ጆሮውን ማመን አቅቶት አተኩሮ አያት። "የምራን እኮ ነው ሌላ ... በቃ ... በሚስጥር ውስጥ ሁሉንም ነገር እይቼየለሁ ... ገነትን ... የጋሽ ዲንሳን እደራ ... ሁሉንም ... የሰው ሕይወቱ በምችው ላይ ሳይሆን በሀልሙ ላይ ሲመሰረት ነው ... ትርጉም ጥቅም የሚኖረው" ብላ፣ አቀፈችው።

ከሁለት ሳምንት በኋላ አርብ ቤተሰቡ ሁሉ ተሰብስቦ እነ ሚስጢር ቤት አደረ። ማታ ሲጫወቱ ብዙ ስላመሹ ሰዉ ሁሉ በእንቅልፍ መዳፍ ስር ወድቆ ተረፍርፏል። አስራ አንድ ሰአት ተኩል ማለዳ ሲሆን ሴላሠው ካልጋው ውስጥ ቀስ ብሎ ወጣ። ንጹህ የሰላም እንቅልፍ ውስጥ ገብታ ትዋኛለች። እንደ ለመዷቸው በደረቷ ነው የተኛችው ትራሱን አቅፋ። እግሮቿ ተገልጠው ስለነበር ቀስ ብሎ ባቷ ላይ ሳም አደረጋትና አለበሳት። የስፖርት ቱታውን አጥልቶ ቀስ ብሎ የመኝታ ቤቱን በር ዘግቶ ወጣ። ሚስጢር ቀድማው ወጥታ መኪናዋን አሥነስታ እየጠበቀችው ነበር።

መስቀል አደባባይ ሲደርሱ መኪናቸውን አቁመው ወደ ደረሻዎቹ ላይ ወጡ። ለምስጢር የመጀመሪያዋ ... ለርሱ ግን ብዙ መቶኛ ጊዜው። ፀሐይ ባትወጣም ያነጋት ፈገግታ አካባቢውን ደስ የሚል ብርሃን አርከፍክፎበታል። ድምፅም ጸጥታም አለ። ቅዝቅዝ ያለ ሰስ ንፋስ ቢኖርም ንጹሑ የጠዋት አየር በሳምባ ውስጥ እንደ ንጹሕ ማር ጣፍጦ ይገባል። ነን ለነን ሆነው፣ ዱብ ዱብ እያሉ መሮጥ ሲጀምሩ ሲገልጸው የማይችል ደስታ በውስጡ ናኘ።

@OLDBOOOKSPDF

"ልጅ ሆኜ ካባቴ ጋር ... ቅዳሜ ቅዳሜ እዚህ እንቀርም ነበር ... ልክ እንደዚህ እንሮጥ ነበር ..." አለ፣ ትከሻዋን በትከሻው ላመል ያህል ገፋ እያደረገ።

"ማን ነበር ቀድሞ የሚደክመው?"

"ብረት ነበር እሱ ... ሮጦም ዋኝቶም አይደክመውም ..."

"ከኔና ካንተስ ማን ቀድሞ ይደክማል?"

"እኔም እንዳባቴ ከብረት የተሰራሁ ብረት ነኝ?"

"እስኪ አያ ብረቶ የብረት ልጅ ይታያሉ ..." አለችና፣ ፈጠን ብላ ስትሮጥ በሏው ፍጥነት ተከተላት። ትንፋሿም ሆነ ፍጥነቷ ከገመተው በላይ ነው። ቀድሞ ደክሞት በረጅሙ ተንፍሶ እጆቹን በጉልበቱ ላይ አደረገና ላቡን እያንጠፈጠፈ ከላይ ሲተነፍስ፣

"ብረት በሽክላ ተሸነፈ ..." ብላ፣ ትንፋሿ እየተቀራረጠ ስትስቅ፣ እጁን አንስቶ መሸነፉን አመነ።

ትንሽ ካረፉ በኋላ ፈጠን ባለ ርምጃ እየሄዱ፣ "የሰው ሀልም የሚፈጸምበት መንገድ ሁሌም ይገርመኛል ..."

"እንዴት?" አለችው ቀና ብላ።

"አርሲና ዲንሱ አድገው ... ልክ በልጅነቴ እኔ ከአባቴ ጋር እንደምናደርገው የሚሮጡበት ቀን ይናፍቀኝ ነበር። እነርሱ ሲያድጉ እኔ እንዳላረጅ ነበር ፍርሃቴ።"

"አሁን ላለማርጀትህ እርግጠኛ ነህ?"

"ቢያንስ ብትር ምርኩዝ አያስፈልገኝም።" ቀስ በቀስ ደረጃዎቹን ጨርሰው ወደ ታች ወረዱ። አረፍ ለማለት ብለው ደረጃዎቹ ጫፍ ላይ ደገፍ ብለው ተቀመጡ። ፀሐይዋ ድምቀትና መሞቂያ እየጨመረ ነው።

"ከሳንቾም ጋር እዚሁ ለሩጫ መጥቼ ነበር የተገናኘነው። ትናንት ይመስላል የጊዚው አፈጣጠን ..." አለ፣ ፊቱ ላይ የትዝታ ጉዞ እየተነበበ።

"አንድ ቀን ሦስታችንም እየሳቅን እዚሁ እንደምንሮጥ ይታየኛል። ሁለት ወር አይደል የቀረው...?" አለች፣ ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ፊቱ እየቆመች።

"አዎን ... አይ ሆፕ ..." አለ፣ ሁለት እጃቸውን እያጋጨ።

"አንድ ነገር ብጠይቅሽ ..." ብሎ ሲያንገራግር፣

"የፈለከውን ... ምን?" አለች ልቧ በቅል ብሎ።

"ያኔ የታመምሽ ጊዜ ... ሙሉ ለሙሉ ከመንታትሽ በፊት ለሳንች ስላለሽ ስጦት አልፎ አልፎ ታመሪ ነበር ..." ሲላት እንደማፈር ብላ፣

"ምን አልኩ ... ምን አልኩ?" አለች።

@OLDBOOOKSPDF

"እሱን እኔ ከምነግርሽ ... አንቺ ስለርሱ የምታስቢው ምንድነው?" ሲላት ፣ ከፊት ለፊቱ መራቱ ላይ በጆሯ ወደ ኋላ ተደግፋ ተቀመጠችና ሰማይ ሰማዩን ማየት ጀመረች ።

"መጀመሪያ ያልኩትን ንገረኝና"

"ባጭሩ ማግባት የምትፈልጊው እሱን መሆኑን ... እንደዛ አይነት ነገር ..."

"አቤት አቤት ... አልመሣሳኝም ..."

"እሺ ንገሪኝ ...አንቺ ምንድነው የምታስቢው?"

"አይ ቲንክ ... ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ ፍቅር የያዘኝ ከሳንች ይመስለኛል ። እሱ ግን ምን እንደሚያስብም አላውቅም ። አይ ዶኖ ..."

"ሚስጥርዬ ... ሳንቾ ላንቺ አይሆንሽም ። "

ፍንጥር ብላ ከተቀመጠችበት ተነሳችና ፣ "ለምን...? ለምን...?" አለች ።

"እመኚኝ ላንቾ ጥሩ ጓደኛሽ ... ጥሩ ወንድምሽ ብቻነው ሊሆንሽየሚችለው ። "

የበለጠ ጠጋ ብላ ዓይን ዓይኑን እያየች ፣ "ምን ያንሰዋል እሱ? ለምንድነው የማይሆነኝ ... ስለርሱ እንደዚህ እንደምታስብ አላውቅም ነበር" አለች ፣ ሳንቾ ላንቺ ያንስሻል ... ወይም ላንቺ አይስማማሽም እንዳለ ተረድታው ።

"ሚስጥርዬ ... እንድትነጂብኝ አልፈልግም ... የምነግርሽ ነገር እኔ ስለ ሳንቾ ካለኝ አመለካከት የመነጨ አይደለም ። "

የያዘውን እጇን አስለቀቀችውና ፣ "ታዲያ ምንድነው? ... ለኔ ከሱ ሌላ የተሻለ ሌላ ሰው በዚህ ዓለም ላይ የለም ። ጠንካራ ፣ ጨዋ ደግና የሕይወትን ብዙ ገጽ በልጅነቱ ያየ ልጅ ነው ። ደግሞ ትንሽ ጊዜ ከሰጠሁት አሁን እንኳን ስሜቱ ባይኖረው በጊዜ ውስጥ ሊወደኝ እንደሚችል አውቃለሁ" አለች ፣ ቁርጥ ባለ ድምጽ ።

"አንቺ እንደምትወጂው አውቃለሁ ... እሱ ግን በዛ መንገድ አይደለም የሚወድሽ ። "

"አላምንም ... አላምንም ... የፈለገ ቢሆን ... ራሴ እናገረዋለሁ ። " ለግልቱስ ጸጸት ፣ ከንፈሮቿ ተንቀጠቀጡ ።

"አይሆንም ቢልስ?"

"አይልም ... ከምታምነው በላይ ሳንችን አውቀዋለሁ" ብላ ፣ የረጠቡ ዓይኖቿን ስትጠራርግ ብታሳዝነውም እውነቱን ሊነግራት ወሰነ ።

"እሺ ... እውነቱን ልንገርሽ ... ሳንቾ የሚወዳት ሌላ ልጅ አለች ። ሃይ ስኩል ሆና በየተኑ ታክሲ የሚያመላልሳት የሲሴ ተማሪ ነበረች ። ከፈረንሳይ አገር ሆና ብዙ ትደውልለት ነበር ። አልፎ አልፎም እየመጣች ትጠይቀው ነበር ። ባለፈው ወር ነው ከእስር ቤት ሲወጣ ሊጋቡ የወሰኑት ። ቤተሰብም ኦልሬዲ አውጀዋል ። "

@OLDBOOOKSPDF

"አላምንም ... ተስፋ እንድቀርጥልህ ነው። ደግሞ... የፈለገው ቢሆን እኔ ለሱ ያለኝን ስሜት እነግረዋለሁ። ውሳኔው የራሱ ነው፣ ... ሕይወቴን ሙሉ ሊቀጪኝ አልኖርም ..." ብላ አኮረፈች። ልታለቅስ ፈለገች። ልታምነው ግን አልፈለገችም። የላይኮሎጂ ጪዋታ መስሎ ታያት ፣ ቢሆንም ተመኘች።

"ስለዚህ ማስረሻና ሲራክ ታዲያ ምንድን ነበር ጥፋታቸው?" አላት ፣ ኮስተር ብሎ።

"ምን ለማለት ነው...?" አለች ፣ ቀጣም ደንገጥም ብላ።

"ሚስጥርዬ ...ፍቅር ... በልመና ... በማስፈራራት ... በማጭበርበር ... በአንዱ ሰው ጠንካራ ስሜትና ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ ሊፈጠር አይችልም። ፍቅር በሁለት ሰዎች በጎ ፈቃድ ብቻ የሚፈጠር የሁለትዮሽ መንገድ ነው።"

"እምቢየው ... አልፈልግም" ብላ ፣ ፈንጠር ብላ ተቀመጠች። እምባዋ እንደገና አፋፍ ላይ ደርሷል። አሁንም ውስጪ ነገሩን ሊቀበለው አልቻለም። በማታውቃት ልጅ ላይ ቀናችባት። ተስፋ ብትቀርጥ ልቧ ስራ የሚያቆም መስላት። "እሺ ለምንድነው ... ይሆናል ብዬ የማስበው ደህና ነገር ሁሉ የሚበለሻሸው ... ይሄኔ የማንም ሉዘር ቢሆን ኖሮ ... ቅይ እሺ ታዲያ ለኔ የሚሆን ሰው ማነው?" አለች ፣ እንዳመጣላት ውስጪ ያለውን ህመም ለማስታገስ።

ወደ እርሷ ጠጋ ብሎ ተቀምጦ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ ጥቂት ጸጥ ብሎ ቆየ። "ያንቺ የሚሆነው ሰው-ማ...?" ሲል ፣ መልሱን ንገረኝበሚል ዓይነት ቀና አለች።

"ሌላ ... ሰው"

"እሺ ... ታዲያ የት ነው ይሄ ሌላ ሰው ያለው?"

"ሌላ ቦታ" ሲል እየተለደባት እንደሆነ ገባት።

"ኧረ ባኮት ... ታዲያ ጪቹ ነው ይሄ ሌላ ሰው እኔ ጋ የሚመጣው?"

ጉንጪን ቀንጠጥ አደረጋትና ፣ "ሌላጊዜ ..." ሲል መሳቅ ጀመረች።

"እሺ ሌላስ ... የቀረ ሌላ ነገር የለህም?" አለችና ትከሻው ላይ ተደገፈች። ጸጉሯን እያሻሸ ግምባሯ ላይ ሳም አደረጋት።

"የቀረ ነገር? ... ህም...ም ... የቀረችው እንዲት ነገርት ናት ... እሷን ልነግርሽ አልችልም ... የሌላ ሰው ሚስጥር ናት።"

"ሚስጥረ ሌላሠው?" አንገቱን እትፋው ጸጥ አለች።

"አምን የኔ ልጅ... አንቺ!" እንደገና ከግንባሯ ከፍ ብሎ ራሷን ከነአጉሯ ሳም አደረጋት።

@OLDBOOOKSPDF